# የቃሉ ሃይማኖታዊ ክበራዎችና ፋይዳዎቹ፡ በጉጂ ኦሮሞ

በ

ዘላለም አበበ

ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪዎች

ፍቃዱ አዱኛ (ዶ/ር)

ታደሰ በሪሶ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

ነሐሴ /2008 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

አማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹ፡ በጉጂ ኦሮሞ

ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ዘላለም አበበ

ነሐሴ /2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## በሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹ፡ በጉጂ ኦሮሞ

በ

ዘላለም አበበ

ነሐሴ /2008 ዓ.ም.

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

የአማካሪዎች ስም ፊርማ

1. ተፈራ ቦሬ (ዶ/ር) [illegible]
2. [illegible] (ዶ/ር) [illegible]

የውጭ ፈታኝ ስም ፊርማ

[illegible] (ዶ/ር) [illegible]

የውስጥ ፈታኝ ስም ፊርማ

[illegible] (ዶ/ር) [illegible]

## ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን ጥናት ለማማከር ሙሉ ፍቃደኝነታቸውን በማሳየት ጊዜያቸውንና ዕውቀታቸውን ለቸሩኝ፤ እንዲሁም ለስራዬ መሳካት በማሰብ ስለጉጂ ቃሉና ገዳ ከበራ ከእኔ ይበልጥ ዶ/ር ታደሰ በሪሶ ያውቃሉ በማለት እሳቸውን በማግባባት አብረው ለማማከር በማመቻቸት ለስራዬ መሳከት ከፍተኛ ጥረት ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ፍቃዱ አዱኛ ያለኝ አድናቆትና አክብሮት ከፍተኛ ነው።

በመቀጠል በወቅቱ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ወቅት በነበረባቸው የስራ ጫና ሳይታክቱ ከዶ/ር ፍቃዱ የቀረበላቸውን ጥያቄ በመቀበል ለጥናቱ ወሳኝ የሆኑ ምንጮችን በመጠቆምና በማዋስ፣ እንዲሁም በፍጥነት አንብበው ገንቢ አስተያየት በመስጠትና አንድም እንደ አማካሪ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደመረጃ አቀባዬ በመሆን የነበሩብኝን ክፍተቶች በመሙላት ለስራዬ መሳካት ክፍተኛ ድርሻ ለነበራቸው አማካሪዬ ዶ/ር ታደሰ በሪሶ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ሌላው በትልመ-ጥናቱም ሆነ በደረጃ ማበልጸጊያው ወቅት የስራዬን ጥረት በመረዳት የነበሩኝን ጉድለቶች አብጠርጥረው በማውጣት፣ ሊከተል የሚገቡኝን የአማራጭ መንገዶችን በመጠቆም፣ እንደፈታኝ ብቻ ሳይሆኑ፤ እንደአማካሪም ዕውቀታቸውንና ልምዳቸው ላካፈሉኝ ዶ/ር ዘላለም ተፈራ ውስጣዊ አክብሮቴና ምስጋናዬ ይድረሶት እላለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ ለአባቃሉ አጋ ሳቆ፣ እንዲሁም በ75 ዓመታቸው የአያታቸውንና የአባታቸውን የማምለክያ ቅዱሳን ስፍራዎች ከተራራ ተራራ በመውጣት ያለመሰልቸት ሙሉ ጊዜያቸውን በመረጃ ማቀበል ላገለገሉኝ የአባቃሉ አጋ ሳቆ አጎትና የቅርብ አማካሪ ለሆኑት ለአቶ ሞኮና ናጋኦ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመቀጠል አባገዳ ዋቆ ዱቤ የኡራጋ ገዳ የነበሩ፣ አባገዳ ዳንቦባ አጋ የማቲ ገዳ የነበሩ፣ አባገዳ ጋንቤላ በርሶ የሆኩ ገዳ የነበሩ እና ለአሁኑ የኡራጋ አባገዳ ጂሎ ማንዶ (Maandhoo) እንዲሁም ለሀሎ አባገዳ ደንቦባ ጉሚና የዌስቱ አባገዳ ሀልቻዬ ዳራ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመቀጠል ለአባያ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኞችና በወረዳ ውስጥ በተለያዩ ቀበሌዎች ለሚገኙ መረጃ አቀባዮቼና በሚኤ ቦኩ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ የጉጂ ዩባዎች፣ ሀዩዎችና የሀገር ሽማግሌዎች በሙሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ጠቃሚ ሀሳቦችን በማንሸራሸር ለጥናቴ አስተዋጽኦ የነበራቸው ጓደኞቼ ለዶ/ር በጅጋ ተካ እና ለአቶ ተመስጌን ምንዋጋው ምስጋና አቀርባለሁ።
በመጨረሻም በስራዬም ሆነ የቤቱን ኃላፊነት በመወጣት ከጎኔ ላልተለየችኝ ለውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ንግስት አዳነ እና አንዳንድ ጽሑፎችን በማገዝ ለረዳኝ ለልጄ አያልቅበት ዘላለም ያለኝን አክብሮትና ምስጋና በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ።

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ..................... i
ማውጫ ..................... ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ..................... v
የምስል ማውጫ ..................... v
የፎቶ ማውጫ ..................... vi
ሙዳዬ ቃላት ..................... vii
አጠቃሎ ..................... x
ምዕራፍ አንድ ..................... 1
መግቢያ ..................... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ..................... 2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ..................... 4
1.3. የምርምሩ ጥያቄዎች ..................... 5
1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ..................... 5
1.4.1. ዓቢይ ዓላማ ..................... 5
1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች ..................... 6
1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ..................... 6
1.6. የጥናቱ ወሰን ..................... 7
1.7. የጥናቱ ውስንነትና የተወሰዱ መፍትሔዎች ..................... 8
ምዕራፍ-ሁለት ..................... 10
ክለሳ ድርሳናት ..................... 10
2.1. ፅንሰ-ሀሳባዊ ፅሁፎች ..................... 10
2.1.1. ፎክሎርና ሃይማኖት ..................... 10
2.1.2. የሃይማኖት ፅንስ ሀሳብ ..................... 12
2.1.2.1. የሃይማኖት ምንነት ..................... 12
2.1.2.2. የሃይማኖት ባህሪያት ..................... 13
2.1.3. የከበራ ፅንስ ሃሳብ ..................... 14
2.1.3.1. የከበራ ምንነት ..................... 14
2.1.3.2. የከበራ ዓይነቶች ..................... 16
2.1.3.3. የከበራ ባህሪያት ..................... 18
2.1.3.4. የከበራ ፋይዳዎች ..................... 19
2.1.4. ሚት ..................... 20
2.1.5. ቁሳዊ ባህል ..................... 21
2.1.6. ስነ-ፍችና አውድ ..................... 23
2.1.6.1. ስነ-ፍች ..................... 23
2.1.6.2. አውድ ..................... 25

2.2. የንድፈ-ሀሳብ ቅኝት ....................26
2.2.1. የማህበራዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ ....................27
2.2.2. ተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ ....................28
2.2.3. አውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ....................31
2.2.4. ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ....................32
2.2.5. ክልላዊ ንድፈ-ሀሳብ ....................34
2.3. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ....................36
ምዕራፍ ሦስት ....................46
የአጠናን ዘዴ ....................46
3.1. የጥናቱ ዓይነት ....................46
3.1.1. የጥናቱ ስነ-ዘዴ ....................50
3.1.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ....................52
3.1.2.1. ምልከታ ....................52
3.1.2.2. ቃለ-መጠይቅ ....................53
3.1.2.3. የቡድን ውይይት ....................54
3.1.2.4. ንጥል ጥናት ....................55
3.1.3. የናሙና መረጣ ሂደት ....................56
3.2. የመረጃ ምንጮች ....................57
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መቼት ....................57
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ....................57
3.5. መረጃዎችን መሰብሰቢያ አንጻሮች ....................58
3.6. የተሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች ....................59
3.6.1. ትራንስክሪፕሽን ....................60
3.6.2. አተረጓገም ....................60
3.7. ከመስክ ውሎ የተገኘ ልምድ ....................60
3.8. የምርምር ሥራ ሥነ-ምግባር ....................62
ምዕራፍ አራት ....................63
የጉጂ ኦሮሞ ማሕበረ-ባሕላዊ ዳራ ....................63
4.1. የጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ፣ አካባቢያዊና ታሪካዊ ዳሰሳ ....................63
4.1.1. የጉጂ ኦሮሞ መገኛ ....................63
4.1.2. የጉጂ ኦሮሞ ዘር ሐረግ ....................68
4.1.3. ሃይማኖት ....................72
4.1.4. ቋንቋ ....................73
4.1.5. መተዳደሪያ ....................74
ምዕራፍ-አምስት ....................75
ቃሉና የቃሉ ተቋም ....................75
5.1. ቃሉ ....................75

5.1.1. የቃሉ አመጣጥ ሚት ....................................................................77
5.1.2. የቃሉ ስያሜና መስፈርቶቹ.................................................................79
5.1.3. የቃሉ መማክርት አባላትና ተግባራቸው...................................................84
5.1.3.1. የቃሉ ተግባራት ............................................................................84
5.1.3.2. የገዳ ተግባራት ..............................................................................91
5.1.3.3. የኮከብ ቆጣሪዎች ተግባራት.............................................................100
5.1.3.4. የካሎዎች ተግባራት.........................................................................103
5.1.3.5. የሞራ አንባቢዎች ተግባራት ..............................................................105
5.1.3.6. የሀገር ሽማግሌዎች ተግባራት ..............................................................107
5.1.3.7. የሀዳ አንባ ተግባራት ........................................................................108
5.2. የቃሉ ከበራዎች መቼቶች.........................................................................110
ምዕራፍ-ስድስት...........................................................................................127
የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ትንተናና ገለጻ....................................................127
6.1. የገዳዎች ስልጣን ማጽደቂያ ከበራ .............................................................127
6.2. የጎንዶሮ ከበራ .......................................................................................154
6.2.1. የግጭት አፈታት ሂደቶች......................................................................155
6.2.2. የጎንዶሮ ዓይነቶች...............................................................................156
6.2.2.1. የግጭት ማሳረጊያ ጎንዶሮ ..................................................................158
6.2.2.2. የምልጃ ማሳረጊያ ጎንዶሮ..................................................................182
6.3. የሁሉቃ ከበራ .........................................................................................183
6.4. የፋጭ ከበራ............................................................................................190
6.5. የቃሉ ስያሜ ከበራ....................................................................................200
6.5.1. የቃሉ ጋብቻ ከበራ ................................................................................201
6.5.2. የቃሉ ስያሜ ከበራ ሂደት .........................................................................207
6.5.3. ለቃሉ የሚሰጡ ስጦታዎች.......................................................................210
ምዕራፍ-ሰባት ..............................................................................................212
የቃሉ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት ................................................................212
7.1. የገዳዎች ስልጣን ማጽደቂያ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት ....................................223
7.2. የጎንዶሮ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት ............................................................232
7.3. የሁሉቃና የፋጭ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት .............................................235
7.4. የቃሉ ስያሜ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት ........................................................237
ምዕራፍ-ስምንት ...........................................................................................239
ማጠቃለያና ይሁንታ .....................................................................................239
8.1. ማጠቃለያ .............................................................................................239
8.2. ይሁንታ.................................................................................................247
ዋቢዎች.......................................................................................................

## የሠንጠረዥ ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| ሠንጠረዥ፡- 1. የጉጂ ኦሮሞ ገዳ ደረጃዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ | 93 |
| ሠንጠረዥ፡- 2. የቃሉና ቃሊቻ/ቃሊቲ አንድነትና ልዩነት | 125 |
| ሠንጠረዥ፡- 3. የፋጭን ቅደመ-ተከተላዊ ሂደት የሚያሳይ | 197 |


## የምስሎች ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| ምስል፡-1. የኦሮሚ ዞኖች መገኛ የሚያሳይ ካርታ | 64 |
| ምስል፡-2. በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር፣ የቦረናና ጉጂ ዞኖች የሚያሳይ ካርታ | 65 |
| ምስል፡-3. የጉጂ ኮንፌድረሺኖች መገኛ የሚያሳይካርታ | 67 |
| ምስል፡-4. የኮንቶማና ዳሪሙ አከፋፈልን የሚያሳይ ቻርት | 71 |
| ምስል፡-5. የኮንቶማና ዳሪሙ አሰፋፈር የሚያሳይ ምስል | 72 |
| ምስል፡-6. የሰባቱ ከዋክብት ስሞችና ምስል | 103 |
| ምስል፡-7. የጉጂ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች ተስተላልፎ አቅጣጫ የሚያመለክት | 142 |
| ምስል፡-8. የጉጂ ገዳ መደቦች የስልጣን ሽግግር ዑደት የሚያሳይ ምስል | 143 |
| ምስል፡-9. የዋቄፋታ፣ ገዳ፣ ቃሉና ዋቃ ግንኙነትና ከበራዎች ፋይዳ የሚያሳይ ሞዴል | 240 |

## የፎቶ ግራፍ ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ፎቶ፡- 1. 16ኛ አባቃሉ አጋ ሳቆ በገልማ ውስጥ ሆነው ....76

ፎቶ፡- 2 አባ ቃሉ አጋ፣ አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ገዳ ሀልቻዬና ሌሎች የመማክርት አባላት ....91

ፎቶ፡- 3 የጃልዳባ አባላትን የሚያሳይ ፎቶ ....96

ፎቶ፡- 4 ሲቄ፣ ሆሮሮ፣ የዋንዛ እንጨት እና ቦኩ የሚያሳይ ፎቶ ....98

ፎቶ፡- 5 መረጃ ሰጪዎች በሚኤ ቦኮ....98

ፎቶ፡- 6 እና 7 ሞራ አንባቢዎች ስተነቢዩ የሚያሳዩ ፎቶዎች ....106

ፎቶ፡- 8 የቂሊጦ ጋራ የሚያሳይ ፎቶ....113

ፎቶ፡-9 የቃሉ ቤተ-አምልኮ እና ሂሮ የሚያሳይ ፎቶ ....114

ፎቶ፡-10 እና 11. በሚኤ ቦኮ የተሰሩት ጊዚያዊ ማረፊያ (ቃቻ) በከፊል የሚያሳዩ ፎቶ....129

ፎቶ፡-12. የቀድሞ የኡራጋ ገዳ አጋ ጤንጣኖና የመማክርት አባላቱን የሚያሳይ ፎቶ....132

ፎቶ፡-13 እና 14. ስልጣን ተረካቢ ገዳዎችና የመደቡ አባላት ለርክክብ ሲሄዱ የሚያሳዩ ፎቶዎች ....147

ፎቶ፡-15. የከብት ሁሉቃ መቼት ....187

ፎቶ፡-16. የቃሉ እህት፣ የቃሉ አጎት፣ ገዳ ሀልቻዬና ሌሎችም ከስጦታዎቹ ጋር ሙሽሪትን ለማምጣት ሲሄዱ ....205

# ሙዳዬ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሀዳ አንባ (haadha ambaa) | የቃሉ ሚስት |
| ሀዳ ቦላ (haadha bollaa) | የገዳ ሚስት |
| ሀሪራቴ (Harirate) | ለመስዋዕት የሚቀርበውን ከብት ጀርባ በእጅ ወይም በበትር በመዳሰስ እግዚኣብሔር መለማመን ነው |
| ሁሉቃ (hulluuqaa) | በቋሚ እንጨቶች ላይ ሀረግ በማሰር የሚዘጋጅ መሹለኪያ ስፍራ ሲሆን ለጦስ ማውጫ የሚያገለግል ነው |
| ሂሮ (hirroo) | ከአባዩ(abbayyii) እንጨት እንደ ዳመራ የሚዘጋጅ ስፍራ ነው፡፡ |
| ሆዳ (hooda) | ማንኛውንም ችግር እንደ እግዚሃብሔር ፍቃድ ይሁን ብሎ በፀጋ መቀበል |
| ላላባ (lallaba) | ዐዋጅ ነገራ |
| ላዱ (laduu) | የቃሉ አንባር (የስልጣን ምልክት) |
| ላጉ (laguu) | በባህላዊ ህግጋት ክልክል (የማይፈቀዱ) ነገሮች ወይም ክዋኔዎች |
| መቼት | የክዋኔ ጊዜና ቦታ |
| ሙዳ (muuda) | በቃሉ ለስልጣን ይሁንታ ወይም ምርቃት መስጠት |
| ሜዲቻ (meedhicha) | ለከበራ ከታረደው በሬ ቆዳ በቀጭኑ ተተለተትሎ የሚወጣና በእጅ የሚጠለቅ (የባለቤትነት መታወቂያ) |
| ሳፉ(safuu) | ህገ-ልቦና |
| ሩፋ (ruufa ) | ረጅም ፀጉር፣ የቃሉ ፀጉር እንዲሁም የሃይማኖት አባቶች በእራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት ፎጣ መሰል ጥምጣም |
| ቁብሱማ (qubsuma) | የገዳ አባላት የሚሰፍሩበት ቦታ |
| ቁቶ (quttoo) | የልጃገረድነት ምልክት ሲሆን፤ ልክ እንደ አንቴና የሚቆም፣ በቀጭን ቆዳ ላይ ጨሌ በመሰካት ተሰርቶ በጸጉራቸው ላይ የሚያስሩት ጌጥ |
| ቁንቢ (qunbii) | ከርቤ (እጣ መሰል) ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል |
| ቃሉ (qaalluu) | የኦሮሞ ሀገረሳባዊ ሃይማኖት መሪ ነው፡፡ |
| ቡና ቃላ (buna qalaa) | ድፍኑን ቡና ቆልቶ፣ በለጋ ቅቤ፣ በማርና በትኩስ ወተት ተቀላቅሎ የሚዘጋጅ ባህላዊ የምግብ ዓይነት ነው፡፡ |
| ባቤ (baabbee) | ሙሉ ዘንግ (ለሽንኮራ፣ ለጥንቅሽ፣ ለቀርከሃ...) |
| ቦኩ (bokkuu) | የቃሉና የገዳ በትር (የኦሮሞ ህዝብ ከፍተኛ የሥልጣን ምልክት) |
| ቦኩ (bokuu) | ከማህበረ-ባህላዊ አገልግሎቶች ላይ ማዕቀብ ማድረግ |
| ቦካ (booka) | ከማር ብቻ የሚጣል የጠጅ ዓይነት |
| አውድ | አንድ ፎክሎራዊ ቅንጣት የሚከወንበት መቼትና አጠቃላይ ድባብ |
| አያንቱ (ayyaantuu) | የእግዚሃብሔር መንፈስ ያደረባቸውና ትንቢት የሚናገሩ ሰዎች |

| | |
|---|---|
| ኡሉፋ (ulfaa) | መንፈሳዊና ባህላዊ ቁስ |
| እችማ (ichima) | አስቴ |
| ካላቻ (kallachaa) | ቃሉና ገዳ በግንባራቸው ላይ የሚያደርጉት መንፈሳዊ ምልክት ሲሆን፤ ከነሀስ ወይም ከእንጨት በወንድ ብልት ቅርጽ የሚሰራ |
| ካሎ (kalloo) | የቃሉ አገልጋዮች (ባለካላቻ) |
| ወዲዳ (wadiida) | ፍም እሳት |
| ዋቃ (waaqaa) | እግዚሃብሔር /ፈጣሪ/ |
| ዋቄፋታ (Waaqeefataa) | በዋቃ የሚያመልኩ/የሚያምኑ ምዕመን |
| የጉቱ ጉዞ | ገዳዎችና የመማክርት አባላቱ ወደቃሉ የሚያደርጉት የስልጣነ ሚመት ማጽደቂያ መንፈሳዊ ጉዞ |
| ዲባሱ (dhibaasuu) | ፈጣሪን መስዋዕት (ወተት ወይም ቦካ) አቅርቦ መለማመን |
| ዲኪቻ (dikichaa) | በቆላ የሚገኝ የሀረግ ዓይነት |
| ዳሪሙና ኮንቶማ | የጉጂ ጎሳዎች ለሁለት ተከፍለው ያላቸው አሰፋፈር ሁኔታ መጠሪያ |
| ዳኑ (danuu) | ባጋጣሚ ወይም ሳይታሰብ የሚፈጠር ክስተት |
| ጂላ (jila) | የቃሉ/የገዳ ከበራ |
| ገልማ (galma) | የቃሉ ቤተ-አምልኮና መኖሪያ እንዲሁም የተቋሙም መጠሪያ ስም ነው። |
| ገዳ/አባገዳ (gadaa) | የገዳ ስርዓት መሪ |
| ጉማ (gumaa) | ለደም ካሳ የሚሰጥ ከብት ወይም ገንዘብ፣ የስርዓቱም መጠሪያ ስም ነው። |
| ጎንዶሮ (gondooroo) | የችግሩ ወይም የሀዘኑ ዳርቻ ያድረገው |
| ጬቡ (cubbuu) | ሀጢያት |
| ፋጭ (faacii) | ንስሃ መግባት |

## ለእንግሊዚኛ ቃላት የተሰጡ ፍችዎች

| | |
|---|---|
| Accommodation | ማስማማት |
| Acculturation | መቀየር/ማዋሃድ |
| Adaptation | መላመድ |
| Case study | ንጥል-ጥናት |
| Disappearance | መጥፋት |
| Hemispheric theory | ክልላዊ ንድፈ ሀሳብ |
| Recession | መዘንጋት/ትዝታዊ |
| Retention | መቋቋም |
| Revitalization | ማንሰራራት |
| Ritual | ከበራ |
| Social Construction theory | የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ |
| Symbolic Interpretations theory | ተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ |
| Syncretism | ማጣመድ/ማጣመር |

## ምህፃረ-ቃላት

| | |
|---|---|
| ቀ/ገ/ማ | ቀበሌ ገበሬ ማህበር |
| ት/ቤት | ትምህርት ቤት |
| አ.አ.ዩ. | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ |
| ጽ/ቤት | ጽሕፈት ቤት |
| ዓ.ም. | ዓመተ ምህረት |
| የኢ. ፌ. ዴ. ሪ. | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |
| CSA | Central Statistical Agency |
| GTAGO | Gumii tokkummaa abbooti gadaa Oromoo) |
| WAWA | Waldaa Amantii Waaqeffannaa Addunyaa |
| A.L.I. | Akka Laakkofsa Itiyoophaatti |

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹ ትንተናና ገለጻ ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ ርዕስ ዙሪያ በቀጥታ ግንኙነት ያለው ሰፋ ያለ ጥናት አይታይም። በተዘዋዋሪ መንገድ የተካሄዱት ጥናቶችም አብዛኛዎቹ ከገዳ ስልጣን ሽግግርና ከጎንዶሮ ከበራዎች ጋር ያላቸውን ሂደቶች ከማሳየቱ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ሌሎች ደግሞ በቃሉ ተቋም ላይ የተካሄዱትን ጥናቶች የተመለከትን እንደሆነ አብዛኛዎቹ በይዘታቸውም ሆነ በፅንሰ-ሀሳባቸው ሰፊ ልዩነቶች ይታይባቸዋል። ይህ ደግሞ ስለሀገረሰባዊ ሃይማኖቱና ዕውቀቱ ላይ ስላለው ግንዛቤ ክፍተቶች እንዲፈጠሩ ምክንያቶች ሆነዋል። ይኸውም፦ ቃሉን ከ‹‹ቃልቻ›› ለይቶ አለመግለጽ፣ እንዲሁም ግብራቸውንና ተግባራቸውን ቀላቅሎ የመግለጽ ሁኔታዎች ይታያሉ። ስለዚህ ይህን መነሻ በማድረግ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዓላማ፦ የቃሉን ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በመተንተን፤ ያላቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳዎችን ማሳየት ነው። ይህንንም ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የምርምር ጥያቄዎችን በማንሳት ማለትም፦ በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምን ምንድናቸው?፣ ለምን ይከወናሉ?፣ መቼቶች ምን ይመሳላሉ?፣ ለሚሉትና ሌሎችም ጥያቀዎች በጥናቱ መልስ ተሰጥቶባቸዋል። በጥናቱም ማህበረሰቡ ይህን ዕውቀት እንዴት እንዳዋቀሩ ኢፒስቲሞሎጂያዊ አተያይን መሰረት በማድረግ ለማት ተችሏል። መረጃዎችንም ኢትኖግራፊያዊ ስነ-ዘዴን መሰረት በማድረግ፦ በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅና በቡድን ውይይት ተሰባስበዋል። ከዚያም ንጥል ጥናቶችን በመጠቀም በዋናነት በማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያንና በተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳቦች የተተነተኑ ሲሆን፣ በአጋዥነት በአውዳዊ፣ በፋይዳዊና በክልላዊ ንድፈ-ሀሳቦች በመተንተን ተገልጸዋል። በትንተናውም በቃሉ ከበራዎች ማህበረሰቡ በሚከወኑት ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች በመጠቀም፤ በሰዎችና ከብቶች በሽታ፣ በድርቅ፣ በግለሰቦችና በአጎራባች ማህበረሰቦች መካከል በሚፈጠሩ ግጭቶች የተነሳ ሰላማቸውን በማጣት የነበረባቸውን ስነ-ልቦናዊ ጭንቀቶች በማረጋጋት፣ በግጭቶቹም ምክንያት ተበላሽቶ የነበረውን ማህበራዊ ግንኙነት በመጠገን፣ የገዳን ስርዓት ዴሞክራሲዊ ሂደት በማስከበርና አንድነታቸውን ጠብቀው መቆየታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። በመጨረሻም በጥናቱ መሰረት በማንሰራራት ላይ ያሉ ከበራዎች እንዳሉ ሁሉ፤ አንዳንድ ቢስተካከሉ ተብሎ የቀረቡ የይሁንታ ሀሳቦች በሚመለከተው አካል ትኩረት ቢደረግባቸው ይህን ዘርፈ-ብዙ የሆነውን የቃሉና የገዳ ተቋማትን ጠቀሜታዎች ማስቀጠል ይቻላል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የጉጂ ኦሮሞ እንደማንኛውም የኦሮሞ ማህበረሰብ የሚያመልኩት የራሳቸው የሆነ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት አላቸው፡፡ የሃይማኖቱም መጠሪያ «ዋቄፋና» ይባላል፡፡ የዋቄፋናን ሃይማኖት በበላይነት የሚመራው ደግሞ ቃሉ ይባላል፡፡ በቃሉ አማካይነት በተለያዩ ወቅቶችና ክስተቶች የሚከናወኑ ሃይማኖታዊ ከበራዎች አሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት «በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹ ትንተና» በሚል ርዕስ ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. በከፊል ማሟያ የቀረበ ነው፡፡ ከርዕሱ ለመረዳት እንደሚቻለው ጥናቱ በዋናነት የሚያጠነጥነው እነዚህን ከበራዎች በመተንተን ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳዎች መግለጽ ነው፡፡ ይኸውም፡- ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ በምን ዓይነት መንገዶች እንደሚከሰቱና ፋይዳዎቹንም ለይቶ ለማውጣት እንደተሞከረ በትንተናው ወቅት ተዳሰዋል፡፡ ለዚህም እንዲረዳኝ እነዚህ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምን ምንድናቸው?፣ ከበራዎቹ ለምን ይከወናሉ? የሚሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በማንሳት መረጃዎችን በዋናነት ከቃሉና ከገዳ ተቋማት በቀዳማይ ምንጭነት ተሰብስቧል፡፡ ለጥናቱ ማስተንተኛ የዋሉትን ፅንሰ-ሀሳቦችና ንድፈ-ሀሳቦችን ደግሞ ከካልኣይ ምንጮች በማጠናቀር አግባብነት ባለው መልኩ ተተንትነው፣ በገለጻ ዘዴ በማቀናበር በስምንት ምዕራፎች ተከፍለው ቀርበዋል፡፡

ይኸውም፡- የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ሲሆን፤ በስሩ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱን ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰንናውስንነት ያካተተ ነው፡፡

ምዕራፍ ሁለት ደግሞ ለጥናቱም እንደማስተንተኛ ያገለገሉ ጽንሰ-ሀሳቦችና ንድፈ-ሀሳቦች የቀረቡበትና ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት አላቸው የተባሉ ቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ የተደረገበት ክፍል ነው፡፡

የአጠናን ዘዴው ከኢፕስትሞሎጂና ኦንቶሎጂ አተያይ ምን እንደሚመስል፣ የጥናቱ ስነ-ዘዴ (methodology)፣ ዘዴዎች(methods)፣ ናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የተሰበሰበው የመረጃ ዓይነቶችና የመሳሰሉት ደግሞ በዝርዝር በምዕራፍ ሦስት ስር ቀርበዋል፡፡

የጉጂ ኦሮሞ ማሕበረ-ባሕላዊ ዳራ ማለትም፡- የጉጂ ኦሮሞ መገኛ፣ የጉጂ ኦሮሞ ማንነት፣ ሃይማኖቱ፣ ቋንቋውና መተዳደሪያው ተጠናቅረው በምዕራፍ አራት ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል፡፡
ምዕራፍ አምስት ቃሉና የቃሉ ተቋምን በተመለከተ ከመስክ በተሰበሰቡትና ከካልኣይ ምንጮች በተገኙ መረጃዎች ስለቃሉ ማንነት፣ የቃሉ መማክርት አባላትና ተግባራቸው፣ የቃሉን ስልጣነ-ሢመትና የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እንዲሁም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ መቼቶች በዝርዝር ታይተዋል፡፡

ስለ ከበራዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለይቶ በማውጣት፤ ከቀረቡት ተያያዥ ጽንሰ-ሀሳቦችና ንድፈ-ሀሳቦች አንጻር በንጥል ጥናቶች (Case Studies) በመጠቀም ለማሳያነት ትንታኔና ገለጻ በተመለከተ በምዕራፍ ስድስት ስር በሰፊው ቀርበዋል፡፡
ምዕራፍ ሰባትን የተመለከትን እንደሆነ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት አስመልክቶ የተቃኘበት ሲሆን፣ ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች አሁን ያሉበትን ደረጃም ተዳሰዋል፡፡

በመጨረሻም በምዕራፍ ስምንት ስር የጥናታዊ ጽሑፉ ማጠቃለያ ሀሳብና አጥኚው በጥናቱ ወቅት ያያቸውን፣ የታዘባቸውንና ይህ ቢሆን በማለት ያቀረባቸው የይሁንታን ክፍል አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የኦሮሞ ማህበረሰብ በገዳ ስርዓት ተደራጅቶ እራሱን በራሱ የማስተዳደር ባህል የረጅም ጊዜ ተግባርና ልምድ ውጤት ነው፡፡ ይህ የማህበረሰብ ዕውቀት ዴሞክራሲያዊ መሰረት እንዳለው ብዙ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር አጥኚዎች አረጋግጠዋል፡፡ ለዚህ የገዳ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ ገጽታዎች መሰረት የቃሉ ተቋም አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ በዚህ ጥናት ውስጥ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በቃሉ ተቋም ውስብስብ ተግባራትን ማለትም፡- ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይከወናሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የገዳ ስልጣነ-ሢመት ማጽደቂያ ከበራ፣ የጎንደሮ ከበራ፣ የፋጭ ከበራ፣ የሁሉቃ ከበራና የቃሉ ስያሜ ከበራ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህን ከበራዎች የጉጂ ኦሮሞ ከተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ለመውጣትና ለተለያዩ ጉዳዮች ይገለገሉባቸው ነበር፤ እየተገለገሉበትም ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የማህበረሰብ

ዕውቀቶች በግለሰቦችና በማህበረሰቡ እንዴት እንዳወቁትና አንቶሎጂዎቹም በጥናቱ ውስጥ ተዳሰዋል፡፡

የሃይማኖታዊ ከበራን የተመለከትን እንደሆነ ከፎክሎር ዘውጎች ውስጥ በዋናነት በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ይመደባል፡፡ ይሁን እንጂ የቃሉ ከበራ ከዚህ በቀር ሌሎችን የፎክሎር ዘውጎችን ባህሪያት አይጋራም ለማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በክዋኔው ላይ የሚዜሙት ዜማዎች፣ የሚነገሩት ሚቶች፣ እንዲሁም ምርቃትና እርግማን ከተመለከትን ከስነ-ቃል ዘውግ የሚጋራው ባህሪያት እንዳሉት ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በከበራዎቹ ላይ የሚለበሱ አልባሳት፣ የሚቀርቡት ምግቦችና መጠጦች ደግሞ ቁሳዊ ባህሉን ያመላክታል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያመለክተው የፎክሎር ዘርፎች እርስ በርስ ተሳስረው እንደሚገኙ ነው፡፡ ይህንን ማወቅ የሚቻለው በከበራዎቹ፣ በሚቶቹና በቁሳዊ ባህሎቹ ላይ ጥልቅ ምርምር በማካሄድ ነው፡፡ ይኸውም፡- እነዚህ ማህበረሰባዊ ዕውቀት እንዴት እንደተዋቀሩና ለማህበረሰቡ ተመልሰው እንደመተዳደሪያ ህግ፣ እንደ ባህል ማስቀጠያና እራሳቸውን ከሌሎች ማህበረሰብ ለየት የሚያረጋቸውን ማንነት እንዲይዙ እንዳደረጉ በጥልቀት ተዳሰዋል፡፡ በመሰረቱ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ሲከወኑ፡- የሚከወነው ቴክስት፣ የአነጋገር ለዛ፣ የሚከወንበት አውድ፣ ቁሳዊ ባህሉና በዚህ ዙሪያ የሚባሉ ተረኮችን በውስጣቸው ያጠቃልላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ተዳምረው ሲተነተኑ ሃይማኖታዊ ከበራው ፍች ያገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ተተንትነዋል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው በተለያዩ የትምህርት መስኮች ላይ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ነገር ግን አብዛኛዎቹ የቃሉ ተቋም ግጭትን ከመፍታትና ከማስወገድ አኳያ ያለውን ሚና የሚያትቱ ሲሆን፤ የተወሰኑት ደግሞ በገዳ ስርዓት ውስጥ ቃሉ ያለውን ሚና የገለጽበትን ሁኔታ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ነገር ግን አብዛኛዎቹ የቃሉ ተቋምና ከበራ ብለው ያነሱት፤ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ከሚከወነው ሃይማኖታዊ ከበራ ጋር በብዙ መልኩ ያለመመሳሰል ይታይባቸዋል፤ በጥልቀት ለተመራመረም ከገዳ ስርዓት ጋር ያላቸው ተዛምዶም ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ናቸው፡፡

ይህንኑ የቃሉና የቃሊቻ ከበራን በተመለከተ ያለውን ብዥታ በኦሮሞ ተወላጆችም ሆኑ፤ በሌላው ብሔር ተወላጆች ላይ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ከዚህም የተነሳ እንደ አጠቃላይ ኦሮሚያ ይህ ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያለውን ተቋም በውስጡ የሚከወኑ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በሎሎች ሃይማኖት ተከታዮች (በክርስትናና በእስልምና) ዘንድ አልባሌ ስም በመስጠት፤ ያለ ግብሩ

እየተነቀፈ ይገኛል። ስለዚህ የቃሉን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምንነት፣ መከዋኛ መቼቶቹን፣ የሚከወኑበትን ዓላማና ከገዳ ስርዓት ጋር ያላቸውን ጥብቅ ግንኙነት በመረጃ በማስደገፍና ትንታኔዎችንም በመስጠት ያለውን የመረጃ ክፍተቶች ለማሳየትና መሙላት ተችሏል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

የዚህ ጥናት አቅራቢ የአካባቢው ተወላጅ በመሆኔ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ በተወሰነ ደረጃ ታድሜያለሁ። ይኸውም፡- በዓመት ከአንዴም ሁለቴ በቃሉና በገዳ ተቋማት በጋራም ሆነ በተናጥል ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ያካሄዳሉ። ማህበረሰቡም ለቃሉ ተቋም ያላቸው አመለካከት ጥብቅ ነው። ይህን የሚያስረዱ የተለያዩ የፎክሎር ዓይነቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ሲንፀባረቁ ይስተዋላል።

ለአብነት ያህል ልጆች እንቆቅልሽ በሚጫወቱበት ወቅት ለተጠየቁት እንቆቅልሽ ምላሻ ካጡ፤ በጫወታው ህግ መሰረት ሀገር ይሰጡና፤ እንዳይሰደቡ(arrabsoo) ፍራቻ ቶሎ ብለው «ቃሉ ቤት ገባሁ (mana Qaalluu seene.)።» ወይም «ከቃሉ ቤት ጥልቅ (caca'u mana Qaalluu.)» ይላሉ። ቃሉ በኦሮሞ ባህልም ሆነ በዋቄፋና ሃይማኖት የተከበረ ስለሆነ፤ የሱ የሆኑ ሁሉ ይከበራሉ። ስለዚህ ስድቡ ይቀርና መልሱን ብቻ እንዲመልሱ ይደረጋል። ሌላው በደቦ ስራ ላይም ሆነ በተለያዩ ጭፈራዎች (Qeexala) ወቅት ቃሉን የሚያሞግሱ ዘፈኖች ይደመጣሉ። አንዳንዴም ሴቶች እራሳቸውን ከወሲባዊ ጥቃት፣ ከተለያዩ የዱር አራዊት በቃሉ ስም በማውገዝ ከጥቃቱ እንደሚታደጉ ይነገራል።

ከዚህ በተጨማሪ ምስክር ላለው፣ ምስክር ለሌለውና በህግ ፊት የተካዱ ወንጀሎች በቃሉ ተቋም አምኖ ለይቅርታ መዘጋጀት ወይም የበደሉትን ክሰው ለመታረቅ ያለው ሂደት የጠበቀ ነው። በግለሰቦች፣ በአጎራባች ጎሳዎችና በገዳዎች መካከል ግጭቶች ሲፈጠሩ የመፍታትና የማስቀም ስልጣን እንዳለውም ይታመናል። ሌላው በቃሉ መማክርት የሚወጡ ህጎችንና ደንቦችን የማክበር ሁኔታዎች ይታያሉ። ታዲያ እነዚህንና የመሳሰሉ ተግባራት የማስፈጸም አቅም እንዴት ሊኖረው ቻለ? የቃሉ ተቋም ከበራዎች ለማህበረሰቡ ምንድናቸው? የሚሉትንና ሌሎችንም ፋይዳዎች በጥልቀት የማወቅ ጉጉት ለዚህ ጥናት አንደኛው አነሳሽ ምክንያት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ለሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ በከፊል የማሟያ ጥናት «Sirna Gaa'ilaafi Moggaasa Qaalluu Oromoo Gujii.» በሚል በቃሉ የጋብቻና ስያሜ አሰጣጥ ከበራ ላይ በአ.አ.ዩ. ለአፋን ኦሮሞ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ጥናት አካሂጀ ነበር። በወቅቱ

ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ስራዎች ዙሪያ የተደረጉ የዳሰሳ ንባብ ለአሁኑ ርዕሰ-ጉዳይ መነሻ ሀሳብ ሆነውኛል፡፡ ይኸውም፡- በተለያዩ የቃሉ ተቋማት ተብለው የቀረቡት የሃይማኖታዊ ከበራዎች ጥናት ከይዘታቸውና ከፅንሰ ሀሳባቸው አኳያ የጎላ ልዩነቶች የታየባቸው ነበሩ፡፡ ይኸውም፡- ከይዘታቸው አኳያ አብዛኛዎቹ ያነሱት ከገዳ ስልጣነ-ሢመት ጋር ያለውን ግንኙነትና ከግጭት መፍታትና ማስወገድ ጋር ያሉትን ፋይዳዎች ናቸው፡፡ ሌላው ከፅንሰ-ሀሳብ አኳያ በአብዛኛው አካባቢ በተካሄዱት ጥናቶች ውስጥ ቃሉ (Qaalluu) እና ቃልቻ/ቃሊቲን (qaallichaa/qaallittii) እንዲሁም የሙገሳ ዘፈን (weedduu) እና ወዳጃን (wadaajaa) አንድ እንደሆኑ በመቁጠር ሲጠቀሙበት ይታያሉ፡፡ የዚህ ማብራሪያ በ 2.3. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ስር በስፋት ተገልጿል፡፡

ስለዚህ እኔ ሊሰራ የፈለኩት ቃሉ ምንድነው?፣ ምግባሮቹስ ምን ምንድናቸው? የማህበረሰቡ ዕውቀትስ ምን ይመስላሉ? ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ለማህበረሰቡስ ምን ምን ፋይዳዎች አሉት? የሚሉትን ከጉጂ ቃሉ አኳያ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና ተንትኖ በመግለጽ የነበረውን የዕውቀት ክፍተት ለመሙላት በማሰብ ነው፡፡

## 1.3. የምርምሩ ጥያቄዎች

- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምን ምንድናቸው?
- የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለምን ይከወናሉ?
- የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ መቼቶች ምን ይመስላሉ?
- በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ የሚቀርቡ ተምሳሌቶች ምን ይመስላሉ?
- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት ምን ይመስላሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በጥናቱ ምላሽ ይሻሉ፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ዓቢይና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

### 1.4.1. ዓቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በመተንተን ያላቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳዎችን ማሳየት ነው፡፡

### 1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ለይቶ መግለጽ፣
- የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች መቼቶችን መግለጽ፣
- የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን መተንተን፣
- በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ የሚቀርቡ ተምሳሌቶችን በመተንተን መግለጽ፣
- በቃሉ ተቋም ውስጥ የታዩ ለውጦችና ቀጣይነታቸውን ማሳየት የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ በቀጥታ የተሰሩ ጥናቶች ባይኖሩም፤ በገዳ ስርዓት ውስጥ ስለቃሉ በታሪክ፣ በስነ-ሰብ፣ በህግ፣ በፊሎሎጂና በፍልስፍና የትምህርት መስኮች ስር በተደረጉ ጥናቶች የተነሱ ሀሳቦች አሉ፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ የተካሄደው ከፎክሎር የጥናት መስክ አኳያ ነው፡፡ ጥናቱም የታየው ከበራውን ከተከወነበት አውድ አኳያ በመተንተን፤ እያንዳንዱን ሃይማኖታዊ ከበራዎች በስፋትና በጥልቀት ያየ በመሆኑ የሚከተሉት ነጥቦች ተፈላጊ ያደርጉታል ተብሎ ይገመታል፡፡ እነሱም፡-

- በክለሳ ድርሳናት ውስጥ እንደታየው በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራና ፋይዳ ዙሪያ በይዘትና በፅንሰ-ሀሳብ ደረጃ የተፈጠረውን የዕውቀት ክፍተት ይሞላል ተብሎ ይገመታል፡፡
- የቃሉ ተቋም በማህበረሰቡ ዘንድ ካለው ተሰሚነትና ተዋረዳዊ መዋቅር ላይ በመመርኮዝ በህዝቡና አካባቢው ላይ ተመስርተው ለሚወጡ ፖሊሲዎችና መርሃ-ግብሮች አቅጣጫ እንደ ግብአትነት ሊያገለግል ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል በጤናው መስክ፡- በስነ-ተዋልዶ፣ በኤች.አይ.ቭ ኤድስና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ በሰፊው መስራት ይቻላል፡፡
- ለቋንቋ መምህራን፣ ለመጽሐፍ አዘጋጆች፣ ለኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች እንደ መረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡
- ስለቃሉ ተቋምና ስለሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ማወቅ ለሚፈልጉ የጋራ ግንዛቤ ይፈጥራል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የጉጂ ኦሮሞ በአሁን ወቅት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ አስራ ዘጠኝ ዞኖቹ ውስጥ ባብዛኛው በቦረናና ጉጂ ዞኖች ውስጥ ሰፍረው ይገኛሉ።[1]የቃሉ ተቋም ደግሞ ከአዲስ አበባ በስተ-ደቡብ ወደ ሞያሌ-ኬንያ በሚወስደው አስፓልት መንገድ በ375 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ይህ ተቋም ቀደም ሲል በጉጂ ኦሮሞ የአላብዱ ጎሳ ወሰን ውስጥ ነበር። ነገር ግን በጉጂና ጌዴኦ የድንበር ይገባኛል ጥያቄ በቀድሞው የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት የድንበር ማካለል ሂደት ከተወሰኑ መንፈሳዊ ስፍራዎች ጋር ወደ ደ/ብ/ብ/ክ/መ፣ ጌዴኦ ዞን፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀበሌ ልዩ መጠሪያው ካራ ሶዲቲ ተከልሏል (Asebe, 2007) እና (ዘላለም፣ 2000)።

ስለዚህ አንደኛ ከዞኑ የመሬት አቀማመጥና ስፋት የተነሳ ሁሉንም ማዳረስ ባለመቻሉ፣ ሁለተኛ ጥናቱ የሚያጠነጥነው በቃሉ ተቋም ዙሪያ በመሆኑ ከቦታ አኳያ የቃሉ ተቋም በዋናነት ትኩረት ተሰጥቶታል። ከዚህ በተጨማሪ በቦረና ዞን፣ አባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀበሌ የሀሎ ገዳ ተቋም እና በጉጂ ዞን የሚገኘው የገዳዎች ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ማዕከል፤ ሚኤ ቦኮንም ያማከለ ነው። ምክንያቱም በሁለቱም ዞኖች ውስጥ ያሉት ሶስቱም የጉጂ ኮንፌድረሲ ገዳዎች የስልጣን ርክክብ የሚፈጽሙበት መንፈሳዊ ስፍራ በመሆኑ ነው።

ሌላው የጉጂ ኦሮሞ ሁለት ዓይነት የገዳ ስልጣን ሽግግር ይከተላሉ። ይኸውም በዘር ከአባት ወደ ልጅ የሚሸጋገር እና በየስምንት ዓመት ልዩነት የሚካሄድ የስልጣን ሽግግር ነው። ዝርዝሩን በ4.1.1. ስር ተገልጿል። ከእነዚህ የስልጣን ሽግግር ውስጥ የመጀመሪያውን የተወሰነ ገለጻ ብቻ በመስጠት፤ በሁለተኛው ዓይነት ማለትም በየስምንት ዓመቱ የሚካሄደው የስልጣን ሽግግር ላይ በጥልቀት ትንተና ተደርጓል።

የጥናቱም መረጃዎች የተሰበሰቡት በተለይም ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች ከአባቃሉና ከመማክርት አባላቱ ላይ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪያ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በአውዱ ላይ በመገኘት በምልከታና በቃለ-መጠይቅ ስልጣኑን ከሚረከቡትና ከሚያስረክቡ አባገዳዎች፣ ከዩባዎች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከሴቶችና የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮችን በማሳተፍ ቃለ-መጠይቆችና የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል።

---

[1]. ይህ ጥናት በተካሄደበት ወቅት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር አስራ ዘጠኝ ዞኖቹ ነበሩ። አሁን ግን የበደሌ ቡኖና የምዕራብ ጉጂ ዞኖች ተጨምረው ተቋቁመዋል።

የጥናቱም ትኩረት በአካባቢውና በህዝቡ ከሚከወኑ ከበራዎች ውስጥ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ ሲሆን፤ ይህም በአውዳዊ ክዋኔዎቹና ፋይዳቸው ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በባህላዊ ከበራዎቹ ወቅት የማህበረሰቡ ዕውቀት፣ ጎልተው የወጡ ስነቃሎችን፣ ቁሳዊ ባህሎችንና ተምሳሌቶቹን እንዴት እንደሚመሰርቱ የመመዝገብ፣ የመተንተንና የመግለፅ ስራን ያካተተ ነው፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውስንነትና የተወሰዱ መፍትሔዎች

አጥኚው የአካባቢው ተወላጅ በመሆኑ ቋንቋውንና ባህሉን ያውቃል፡፡ ነገር ግን ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በአብዛኛው የሚገኙት በቃሉና በገዳ ተቋማት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ በግልጽና በስውር የሚከወኑ ስርዓቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህ በስውር የሚከወኑትን በተመለከተ መረጃዎችን በምልከታም ሆነ በቃለ-መጠይቅ ለማሰባሰብ ፍቃደኛ ያለመሆን ክፍተቶች ተከስቶ ነበር፡፡

እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከየካቲት 6-13/2008 ዓ.ም. በጉጂ ዞን ሚኤ ቦኮ ላይ በተደረገው የገዳ ስልጣን ሽግግር የመከታተሉ አጋጣሚው ተፈጥሮ ነበር፡፡ በሂደቱም በመጨረሻው መርሃ-ግብር ወደ ቃሉ ተቋም ስልጣነ-ሢመታቸውን ለማጽደቅና ቃለ-መሃላ ለመፈጸም ይደረግ የነበረው የጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ ሳይካሄድ ቀርቷል፡፡ ምክንያቱም በውስጣዊ ተግዳሮቶች እንደሆነ በዝርዝር በ7.1.1. ስር ተገልጿል፡፡ ከዚህም የተነሳ የገዳ ስልጣነ-ሢመት ሃይማኖታዊ ከበራ በቃሉ ተቋም ከአውዱ ላይ በምልከታ ሊሰበሰብ ታቅዶ የነበረው መረጃ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሚኤ ቦኮ በተደረገው የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ ላይ ከነበረው የሰው ብዛትና ግፊያ፣ እንዲሁም ከጋዜጠኞች በቀር አብዛኛዎችን ለቀረጻ ከመከልከላቸው የተነሳ፣ የተወሰኑ መረጃዎችን ለመከታተል አልታደልኩም ነበር፡፡

ሌላው በአሁኑ ጊዜ ባለው የኑሮ ውድነትና ለጥናቱ ተብሎ ከዩኒቨርሲቲው የሚመደበው ገንዘብ ስለማይበቃ የበጀት እጥረት ተከስቶ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ጥናቱን በወጣው ዕቅድ መሰረት ለማካሄድ የጊዜ እጥረትም ተፈጥሮ ነበር፡፡
ይሁን እንጂ እነዚህን ችግሮች ለማቃለል፣ የበጀትና የጊዜ እጥረቱን አስመልክቶ ከትምህርት ክፍሉ ጋር በመነጋገር የመፍትሄ አቅጣጫ ተሰጥቶበታል፡፡ የመረጃ ክፍተት እንዳይፈጠር ደግሞ በተቻለ መጠን ባህሉንና እምነቱን በማይጋፋ መልኩ በማግባባት በተወሰነ መልኩ በቃለ መጠይቅና የተወሰኑ መረጃዎችንም ከቀረጹ አካላት በማግባባት ወስጄ ክፍተቶቹን ለመሙላ

ጥሪያለሁ፡፡ ያልተከናወነው የጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ በተመለከተ በቃለ-መጠይቅ በተወሰነ ደረጃ መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡

ሌላው በመስክ ቆይታዬ ወቅት መረጃ አቀባዮቼ በቀጠሮ ዕለት ያለመገኘት፣ በመብራት መቆራረጥ ምክንያት የካሜራ ባትሪ በማለቁ የተነሳ የተሟላ ክዋኔ ያለመቅረጽ ክፍተቶች ተፈጥረው ነበር፡፡ እነዚህን ክፍተቶች ተለዋጭ ቀጠሮ በማድረግና የተቋረጡ ክዋኔዎችን በተቻለ መጠን በማስታወሻ በማስቀረት ክፍተቱን ለመሸፈን ተችሏል፡፡

በመጨረሻም በሚኤ ቦኮ መንፈሳዊ ስፍራ በአንድ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች፤ የተለያዩ እርከን ውስጥ ያሉ የገዳ መደብ አባላት የተለያዩ ክዋኔዎችን ይከውኑ ስለነበር እነዚህን ተሯሩጦ ለመመልከት አስቸጋር ነበር፡፡ እንደመፍትሔ የተጠቀምኩት ባጋጣሚ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ጓደኞቼን አንዱ ክዋኔ ላይ እንዲከታተሉልኝና ክዋኔውን እንዲቀርጹልኝ በማድረግ፤ የተቀረጸውን ቪዲዮ ተመልክቼ፣ ያልገባኝንና ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን ለይቼ በማውጣት፤ የሚመለከታቸውን አካላት በማፈላለግ በቃለ መጠይቅ የነበረውን የመረጃ ክፍተት ለማሟላት ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ስር በርዕሰ-ጉዳዩ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ፅንሰ-ሀሳባዊ ፅሁፎች፣ የጥናቱን መረጃዎች ማስተንተኛ ንደፈ-ሀሳባዊ ፅሁፎችና የተጠኑ ተዛማጅ ስራዎች ተዳሰው ቀርበዋል።

### 2.1. ፅንሰ-ሀሳባዊ ፅሁፎች

በዚህ ርዕስ ስር ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ ፅንሰ-ሀሳቦች የቀረቡበት ክፍል ነው። ይኸውም፡- ስለፎክሎር፣ ስለሃይማኖት፣ ስለክበራዎች፣ ስለሚት፣ ስለቁሳዊ ባህል፣ ስለአውድና ከነሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፅንሰ-ሀሳቦችና የእያንዳንዱን ተግባር በተመለከተ ተዳሰዋል። ምክንያቱም የተሰበሰቡት መረጃዎች የተተነተኑት ከንደፈ-ሀሳባዊ ፅሁፎች በተጨማሪ በነዚህ ጽንሰ-ሀሳቦች አጋዥነት ነው።

#### 2.1.1. ፎክሎርና ሃይማኖት

ፎክሎር የአንድ ማህበረሰብን ልማዶች፣ ወጎች፣ እምነቶችና ህዝባዊ ጥበቦችን ያካተተ ሰፊ የባህል ጥናት ዘርፍ ነው። Bauman, (1972) የAlan Dundes'ን ሀሳብ በመጥቀስ ፎክሎርን ሲበይን ከሁለት ቃላት የተመሰረተና ቃላቱም የቆሙለትን እሳቤ፡- ፎክ (folk) የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቢያንስ አንድ የጋራ የሆነ ጠባይ ያላቸው ማንኛውም ቡድንን የሚገልጽ ነው። ይህ ቡድን ምናልባትም የጋራ ቋንቋ፣ ስራ፣ እምነት ያላቸው ሲሆኑ፤ ይሄነው የሚባል የራሳቸው የሆነ ትውፊት (tradition) ይኖራቸዋል። በቲዮሪ ደረጃ ቡድን የሚባለው ቢያንስ ሁለት ሰው ያለበት ነው። ትውፊቱ ደግሞ ቡድኑን የራሱ ቡድናዊ ስሜት (sense of group identity) እንዲኖረው ያደርጋል። ለምሳሌ፡- የእንጨት ፈላጭ ቡድን ካለ፤ ፎክሎሩ የሚሆነው የእንጨት ፈላጭ ነው። ወታደሮችና የኮሌጅ ተማሪዎች እንኳን ፎክ ናቸው በማለት ይገልጻል። ሎር(lore) ደግሞ ጥበብ ነው፤ ቡድናዊ ጥበብ ማለት ነው። ስለዚህ የአንድ ሃይማኖት ተከታዮችን የተመለከትን እንደሆነ እራሳቸውን የቻሉ ፎክ ናቸው። ምክንያቱም እነዚህ የእምነቱ ተከታዮች የጋራ የሆነ የአምልኮት ስርዓት፣ የጋራ የሆነ የማምለኪያ ስፍራ፣ የጋራ የሆነ አንድ ስያሜ ያለው ሃይማኖትና የሚከተሏቸው የጋራ የሆነ ሃይማኖታዊ ክበራዎች ያላቸው በመሆኑ ነው።

ፎክሎርን ለማጥናት በድንበር ቀንብቦ መመልከቱ ተገቢነት ያለው ነው። ምክንያቱም ከላይ እንደተገለጸው ዘርፈ-ብዙ የጥናት መስክ ነው። የተለያዩ ምሁራን ፎክሎርን በተለያዩ ዘርፎች ይከፍሏቸዋል። ከነዚህም ውስጥ Wilson, (1986:228) እና Schoemaker, (1990፡3) ፎክሎርን በሦስት ምድቦች ይከፍላሉ:: እነዚህም:- ሰዎች በቃላቸው የሚያስተላልፉት (verbal lore)፣ በእጃቸው የሚሰሩት (material lore) እና በተግባር የሚተገብሩት (customary lore) ናቸው:: በሌላ በኩል በሙያ ዙሪያው በስፋት የሚጠቀሰው አቀራረብ በ Dorsen (1972:3-4) የተከፈለው አመዳደብ ነው። ይኸውም:- ፎክሎር በዋናነት ስነ-ቃልን፣ ቁሳዊ ባህልን፣ ሀገረሰባዊ ልማድንና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን ያካትታል። እነዚህ የፎክሎር ዘርፎች ለየብቻቸው የቆሙ ሳይሆኑ፤ በመካከላቸው ግንኙነት፣ መስተጋብርና ተደጋግፎ አላቸው። በሌላ በኩል እያንዳንዱ የጥናት ዘርፍ በውስጡ የተለያዩ ዘውጎች ይኖሩታል።

ለአብነት ያህል ሀገረሰባዊ ልማድ በስር እንደፌስቲቫሎች፣ ክብረ በዓላት፣ መዝናኛዎች፣ ጨዋታዎች፣ ሀገረሰባዊ መድኃኒቶች፣ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቶችና ሌሎችንም እንደሚያካትት Dorson'ን በመጥቀስ ፈቃደ (1991፡13) ይገልጻል።
የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ በዋናነት ከሀገረሰባዊ ልማድ የፎክሎር ዘውግ ስር ይመደባል። ከዚህ በተጨማሪ የሌሎችን የፎክሎር ዘውጎች ባህሪያትንም በተወሰነ ደረጃ እንደሚጋራ በመግቢያው ላይ ለማየት ተችሏል።

ሌላው የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራን ፎክሎር ሊያስብለው የሚችለው የጉጂ ኦሮሞ የዋቄፋና ሃይማኖት ተከታዮችን እንደ አንድ እራሳቸውን የቻሉ ፎክ ልናያቸው ስለሚያስችለን ነው። ምክንያቱም የጋራ ጉዳያቸው የዋቄፋና ሃይማኖትና በስሩ የሚከናወነው የቃሉ ከበራዎች፣ ለከበራዎቹ ማጀቢያ የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ ምግቦቹና መጠጦቹ፣ ባህላዊ ጭፈራው፣ ከስርዓቱ ጋር አብረው የሚከወንባቸው ማንኛውም ቁሳዊ ባህሎች ሁሉ የዚህ ፎክ ቡድን ጥበብ ውጤትና የጋራ መገለጫዎች መሆናቸው ነው። ይህን እውቀት ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በትውልድ እየተዋቀረ ወይም በአምሳያው (ሞዴል ተደርጎ) የተፈጠረ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ይህ የጋራ እውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃልና በድርጊት ሲተላለፍ ማህበረሳባዊ ተቋም ሆኖ ማገልገሉ አይቀርም። የቃሉና የገዳን ተቋማት የተመለከትን እንደሆን የዚህ እውቀት ጥምረት ይመስላሉ። ከዚህም የተነሳ ይመስላል የጉጂ ኦሮሞ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለየ እንዲታወቅና እንዲጠራ ያስደረገው። ስለዚህ ይህ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ከፎክሎሩ ጋር ያለውን ጥምረትና ፎክሎራዊ ገፅታዎቹን በሚገባ ለመመልከት ያስችላል።

### 2.1.2. የሃይማኖት ፅንሰ ሀሳብ

በዚህንዑስ ርዕስ ስር ስለ ሃይማኖት ምንነት፤ በተለይም ስለ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ወደ ሆነው የኦሮሞ ዋቄፋና ሃይማኖት የሚያንደረድሩንን ፅንሰ-ሀሳቦች በመዳሰስ ወደ ዋናው ርዕሰ-ጉዳይ የሆነው የቃሉ ሃይማኖት ከበራዎች ምንነት እንሸጋገራለን፡፡

#### 2.1.2.1. የሃይማኖት ምንነት

ስለ ሃይማኖት ምንነት የተለያዩ ጸሐፍት በተለያየ መልኩ፣ ነገር ግን ተቀራራቢ ይዘት ባላቸው አገላለጽ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡ ለአብነት ያህል O'Neil, (2009) ሃይማኖት ማለት ሰዎች ዘወትር በልዕለ-ተፈጥሮ (supernatural being) ኃያልነት የማመን ስርዓት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ Schoemaker,(1990:238) ደግሞ የሃይማኖት ቢያኔ መታየት ያለበት ከመንፈሳዊ ልምዶች አንጻር እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ይኸውም እነዚህን በሚመስሉ የሕይወት ልምዶች ስርዓት የተደራጀ ሲሆን፣ ሃይማኖቶች በቅርጻቸውና በይዘታቸው ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ሃይማኖት የእምነት ስርዓት ሆኖ በሃይማኖቱ ተከታዮች እንደ ፈጣሪያቸው ከሚያምኑት ጋር በማስገባት አብሮ የሚከወኑ ከበራዎች አሉ፡፡ እነ Peoples, J. and Bailey, G. (1991:293). ይህንኑ ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *The three components of all religions, then are (1) belifes about the existence and nature of supernatural powers, (2) mythologies about the historical deeds of these powers, and (3) rituals intended to influence these powers to intervene favorably on behalf of the performances.*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሃይማኖት በውስጡ እምነቶች (belifes)፣ ሚቶች (mythologies) እና ከበራዎች (rituals) እርስ በርስ የሚደጋገፉ ጽንሰ ሀሰቦችን እንደሚያካትት ነው፡፡

ጠቅለል ባለ አገላለጽ ሃይማኖት ዓለምን በፈጠረና ተፈጥሮን በበላይነት ይቆጣጠራል ተብሎ በሚያምኑት ልዕለተፈጥሮ (supernatural being) ልዩ ኃይል በእምነት መቀበል፣ ስለልዕለተፈጥሮው እውነትነትና ሀያልነት የሚያስረግጡ ሚቶች ያለውና ሃይማኖታዊ ድርጊቶቹ የተሸከሟቸውን ጉዳዮች የሚገልጹ ከበራዎች ውጤት እንደሆነ ከተለያዩ ቢያኔዎች ለመረዳት እንችላለን፡፡

በአለማችን ላይ የተለያዩ ዓይነት ሃይማኖቶች አሉ። ለምሳሌ የክርስትና፣ የእስልምና፣ ህንዱዝም፣ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ወ.ዘ.ተ. መጥቀስ ይቻላል (Jonathan, 1996)። ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ሰዎች በቡድን የሚያከናውኗቸው ተግባራት ናቸው። በዚህ ቡድናዊ ክዋኔ ውስጥ ሃይማኖት የሚያካሂዳቸው ከበራዎች አሉ ፊቃደ፣ (1991፡14)። የጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ከዋቄፋና ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ የተወሰኑት ናቸው።
ሃይማኖትና ከበራ የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸው የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ። ከበራና ሃይማኖት ፈጽሞ ተነጣጥለው የማይቆሙና መነሻቸውም ወይም ምንጫቸውም ሚት ነው (Rappaport, 1999፡158)።

ስለዚህ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ለማጥናት በይበልጥ ትኩረት የተደረገው የሃይማኖታዊ ከበራዎችን፣ ሚቶችንና ቁሳዊ ባህሉን በጥልቀት በመመርመር፤ ሃይማኖታዊ ከበራውና ቁሳዊ ባህሉ ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳና የማህበረሰቡን እውቀት ማለትም ስለማንነቱ ያቆየውን አሻራ መግለጽ ላይ ነው።

### 2.1.2.2. የሃይማኖት ባህሪያት

ሃይማኖት የብዙ ባህሪያት ባለቤት ነው። ከነዚህም ውስጥ ትራዲሽን፣ ሚቶችና ተምሳሌቶች፣ የመዳን ፅንሰ-ሀሳቦች (concepts of salvation)፣ የተቀደሱ ቦታዎችና ቁሶች፣ ከበራዎች፣ መንፈሳዊ ጹሑፎችና መልዕክቶቻቸው፣ የተቀደሱ ማህበረሰብና ቅዱሳዊ ልምድ የተወሰኑት ናቸው (Schoemaker, 1990፣60-61)። እነዚህ የተለያዩ ባህሪያት በአንድ ተጣምረው ለሃይማኖቱ እንደ አንድ መገለጫ ባህሪ ሆነው ያገለግላሉ።

ከእነዚህ ሃይማኖታዊ ባህሪያት ውስጥ የዋቄፋና ሃይማኖት ከመንፈሳዊ ጹሑፎችና መልዕክቶቻቸው ባህሪያት በቀር ሌሎቹን ያሟላል። እነዚህን ባህሪያት መሰረት በማድረግ በተናጠልና እንደየሁኔታው በአንድ ላይ በፎክሎራዊ የጥናት መስክ ማጥናት ይቻላል። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ውስጥ በአጥኚው በዋናነት የተተኮረው በሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ላይ ነው። እነዚህን ባህሪያት በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ ምን ይመስላሉ? የሚለውን ከአውዳዊ ክዋኔው አኳያ ከተመረመረ በኋላ ያለውን ፋይዳ በጥልቀት ተንትኖ ለመግለጽ ረድተዋል።

ይኸውም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ትራዲሽን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው በቃልና በድርጊት ነው። ስለቃሉ አመጣጥ፣ ስለቃሉ ተቋምና ሌሎችም ክዋኔዎች

አጀማመርና እውነተኛነቱን ለማረጋገጥ የሚጣረው ደግሞ በሚቶቹ ነው፡፡ የመዳን ፅንሰ-ሀሳብን በተመለከተ ከዋቄፋና ሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞች የዓለም አተያይ አኳያ የእግዚአብሔርን አምስቱን አእማድ ህግጋት ማለትም፡- ማምለክ፣ እቀባ፣ ሳፉ፣ ቅዱስና ክቡር እና በፀጋ መቀበል የጠበቀ ከሀጢያት ነጻ ነው ተብሎ ይታመናል፤ ከዚህ በተቃራኒ ከፈፀመ ደግሞ ሀጢያተኛ ነው ይባላል፡፡ እነዚህ ህግጋት በ5.1.3. ስር በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ አንድ ሰው ሲያውቅ በድፍረት፤ ሳያውቅ ደግሞ በስህተት ሀጢያትን ከፈፀመ በሃይማኖቱ መሰረት ፋጭ ወይም የንስሀ ከበራ ይፈጸምለትና ከሀጢያቱ እንዲነጻ ይደረጋል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን ከበራዎች የሚከወኑት ደግሞ ማህበረሰቡ አምኖ የተቀበላቸው የተቀደሱ ቦታዎችና ቁሶች አሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሃይማኖታዊውን ከበራ በዋናነት የሚመሩ የተቀደሱ መሪዎችና ማህበረሰብ እንዲሁም ቅዱሳዊ ልምድ አሉበት፡፡ ታዲያ እነዚህን ማህበረሰባዊ እውቀት በራሱ አዋቅሮ፤ለራሱ እየተገለገለበት እንደሆነ በተለያዩ ንድፈ-ሀሳቦች በመታገዝ ተተንትነው ተገልጸዋል፡፡

## 2.1.3. የከበራ ፅንሰ ሃሳብ

ማንኛውንም ሃይማኖት የተመለከትን እንደሆነ የራሱ የሆነ የሚያካሂዳቸው ከበራዎች አሉት፡፡ ስለዚህ ከበራን በተመለከተ አንዳንድ ፅንሰ ሃሳቦችን ማብራራቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ስለከበራ ምንነት፣ ዓይነቱ፣ ባህርያቱና ፋይዳው በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

### 2.1.3.1. የከበራ ምንነት

የከበራን ምንነት ወይም ብያኔ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጸውታል፡፡ «ritual» የሚለው የእንግሊዘኛው ቃል ከላቲን «ritus» ከሚባል ቃል የመጣ እንደሆነና የሚወክለውም ለአንዳች ሃይማኖታዊ ነገር ተብሎ የሚከወንን ዝግጅት እንደሚያሳይ Robert, (2006:199) ይገልጻል፡፡

ይህን «ritual» ለሚለው የእንግሊዘኛው ቃል በተለያዩ የአማርኛ ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ ከበራ፣ ስነ-ስርዓት፣ ሪችዋልና የመሳሰሉትን በማለት እንደሚጠቀሙበት ለማየት ተችሏል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት ውስጥ ከበራ የሚለውን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ምክንያቱም ካሉት የተሻለና በብዙዎቹም ዘንድ እየተለመደ የመጣ በመሆኑ ነው፡፡

ብያኔውን በተመለከተ በተለያዩ ጽሁፎች ውስጥ ይዘቱን ባልቀየረ መልኩ፤ በተለያየ መንገድ ሲገልጹ ይታያል፡፡ በአብዛኞቹ ጽሁፎች ውስጥ ከሚገኙት ብያኔዎች ውስጥ የሚታዩ የጋራ

ነጥቦች አሉ፡፡ እነሱም እንደ መዋቅራዊነት፣ ቅደም ተከተላዊነት፣ ታዳሚ፣ ውጤት፣ ቅዱሳዊነት፣ ቡድናዊነት፣ ተደጋጋሚነት፣ ቋሚነት፣ ጎን ለጎንም ተለዋጭነት፣ ውስን መዋቅርና የጊዜና የቦታ ጽንሰ ሀሳብ ያካትታል (Salamone, 2004፡321)፡፡

ከበራ ቃላዊ ያልሆነ፤ ነገር ግን ልክ እንደ ስነ-ልሳናዊ ጉዳዮች በርከት ያሉ ትእምርቶች ያሉበትና እያንዳንዱ ትእምርት ደግሞ ትርጓሜ የሚያገኘው በበቀለበት ባህል ባለው የምግባርና የትውፊት ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ከበራ የአንድን ቡድን የተለመዱ ጽንሰ ሀሳባዊና ቅደም ተከተላዊ ሂደቶችን የሚገልጽ ጉዳይ ነው (Bell, 1997፡44)፡፡

ከበራ የሰዎች ሃይማኖታዊ የሆኑ እምነቶች፣ ትእምርታዊ የሆኑ መግባቢያዎች፣ ማህበረሰባዊ የሆኑትን ንድፈ-ሃሳቦችና ሌሎችንም ማህበራዊ ትርጓሜዎች የሚያስተላልፍ የመግባቢያ መንገድ ነው (Myrvold, 2008፡21)፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝ በስነ-ሰብዓዊያን ብያኔ መሰረትም ከበራ አውዳዊ የሆነና ሐቲታዊ ጽንሰ ሀሳብ እንጂ የሰዎች ድርጊት ዋናው ጉዳይ ምንድን ነው? ወደሚለው የሚወስድ እንዳልሆነ በመገንዘብ፤ በአንጻሩ ይህ ጉዳይ የሰዎቹ አስተሳሰብ (እይታ)ና የሚሰጠው ትርጓሜ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከበራ ማለት ሃይማኖታዊ ድርጊቶች የተሸከሟቸውን ጉዳዮች የመግለፅ ከበራ ሲሆን፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ወይም ከዘመን ዘመን የሚዘልቅ እንደሆነ Mazama and Asante, (2009፡ 575) ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ከበራ በራሱ አንድ ፎክሎራዊ ክዋኔ ነው፡፡ እያንዳንዱ ከበራ ደግሞ የሚቀርብበት የራሱ የሆነ አውድ ይፈልጋል፡፡ አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ከሚያከናውናቸው ሰፊ ከበራ ውስጥ በርካታ ከበራዎች ተጨምረው ይቀርባሉ፡፡ ከበራ ደስታን፣ ሀዘንን፣ ጭንቀትን፣ ብሶትንና ሌሎች ስነ-ልቦናዊ ስሜቶችን በመግለጽ እረፍት ለማግኘት ይከወናል፡፡ በመሆኑም ሰው እስካለ ድረስ ከበራ አለ፡፡ ስለዚህ ታዳሚዎች በኑሯቸው የሚጠቀሙባቸውንና የሚመሩባቸውን እሴቶችና ተምሳሌቶች መግለጫ አድርገው ይጠቀሙባቸዋል (Bell, 1997፡171-172)፡፡

በአሁን ወቅት የስነ-ሰብና የባህል ተመራማሪዎች ትኩረታቸውን በከበራ ምንነት መግለጽና መተርጎም ላይ አድርገዋል፡፡ ለዚህም-እንደ ምክንያት የሚያነሱት በርካታ አዳዲስ ንድፈ ሀሳቦች ምንጫቸው ማህበረሰቡ የሚያከብራቸው ከበራዎች ናቸው የሚል ነው፡፡ ንድፈ ሀሳቡን

ለመረዳት ከበራውን የሚያከናውኑ ሰዎች ለከበራውና ለማህበራዊ ደንብ ያላቸው አመለካከት፣ እንዲሁም ክዋኔው የሚፈልጋቸው ህጎች ሁሉ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች እንደሆኑ McCormick & White (2011፡1105) ይገልጻሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የአንድ ማህበረሰብ ከበራ ማህበረሰቡ ህይወቱን፣ኑሮውን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የግድ አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር፤ የተሳታፊዎችን ስሜታዊና ስነ-ልቦናዊ ጥንካሬ የሚያዳብር መሆኑን Mazama and Asante, (2009፡575) ያስረዳሉ፡፡
ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣እምነት፣የሚያስደስታቸውንና የሚያሳዝናቸውን ነገሮች ለመለየትና ስሜታቸውን የሚገልጽበትን መንገድ ለመረዳት ብሎም ማንነታቸውን ለማወቅ በህይወት ዘመናቸው የሚያከብሯቸውን ከበራዎች ማጥናት ተገቢ ነው፡፡ ይኸውም ከበራው በማን፣ መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደሚከበር በማጥናት የሚኖሩበትን ዓለምና ማንነታቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

በዚሁ መሰረት የቃሉን ከበራዎች በመመልከትና በመተንተን ስለጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ እውቀት፣ የአብሮነት አኗኗር ዘይቤ፣ ተቻችለውና እሴታቸውን ጠብቀው የኖሩበትን መንገድ መግለጽ ተችሏል፡፡

## 2.1.3.2. የከበራ ዓይነቶች

ከበራዎችን የተለያዩ ምሁራን ከተለያዩ አቅጣጫ እንደሚከተለው ከፋፍለው ያዩታል፡፡ Van Van, Gennep, (1960) ከበራዎችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይመድባቸዋል፡፡ እነሱም፡- አንደኛው አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ማህበራዊ ደረጃ በሚሸጋገርበት ጊዜ የሚከወን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በወቅቶች መቀያየር ምክንያት የሚከሰቱ ለውጦች፣ የአዲስዓመት፣ የአዲስ ወቅታዊ ክስተቶች ምክንያት በማድረግ የሚከወኑ ከበራዎችን የያዘ ነው፡፡ ሌላው Bell, (1997:93) Durkheim'ን በመጥቀስ ከበራን መንፈሳዊና ዓለማዊ በማለት በሁለት እንደሚከፈሉ ትገልጻለች፡፡ መንፈሳዊ ከበራ ለማንኛውም ቡድን የመንፈሳዊና የልዕለ ተፈጥሮ ዓለም ወይም ክስተቶች ከእምነቶች ጋር ተያያዥነት እንዳላቸው Sims,M. & M. Stephens, (2005:102) ይገልጻሉ፡፡ በመንፈሳዊና ዓለማዊ ከበራዎች መካከል ልዩነቶች አሉ (Salamone, 2004:xi)፡፡

Turner, (1977) ደግሞ ከበራን በተለየ መልኩ በሁለት ይከፍላቸዋል፡፡ እነሱም፡- አንደኛው በሕይወት ላይ ለሚደርሱ ውድቀቶች የሚከወኑ ከበራዎች (Life Crisis ritual) ማለትም

በአንድ ሰው የህይወት ዘመን የሚያጋጥሙ እክሎች፣ ለምሳሌ በሞትና በፍቺ ሰበብ የትዳር ጓደኛ ማጣት ከመሳሰሉት ውጥረቶች ለመዳን የሚከወኑ ከበራዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ሁለተኛው ደግሞ በስነ-ልቦናዊና አካላዊ ከሚደርሱ መከራዎችና ችግሮች ለመውጣት የሚከወኑ ከበራዎች (Rituals of affliction) በማለት ይከፍላቸዋል።

በሌላ በኩል ከአውዳዊ ገጽታው አኳያ ደግሞ ከበራን በሁለት ሲከፍሉት ይታያል። እነሱም ባለዝቅተኛ አውድ ከበራና ባለከፍተኛ አውድ ከበራ ናቸው። ባለዝቅተኛ አውድ ከበራ የሚባለው በትክክለኛ መንገድ ዲዛይን ያልተደረገና በተለመደ መልኩ ያላስተዋወቁት ወይም በጥንቃቄ ያልታቀደበትን ነው። በተቃራኒው ባለከፍተኛ አውድ ከበራ የሚባለው ደግሞ በአግባቡ ዲዛይን የተደረገና በተለመደው መንገድ ያስተዋወቁት ወይም በጥንቃቄ የታቀደበት ነው። ይኸውም ተሳታፊዎቹ ለክዋኔው ሆን ተብሎ የተዘጋጁ አልባሳትና ጌጣጌጥ ይጠቀማሉ። ምናልባትም በዚህ ዓይነቱ አውድ ውስጥ የዚያ ፎክ ወይም ቡድን መሪ የተለየ አለባበስ ሊጠቀም ይችላል። ይህ ደግሞ ማን ምን እንደሆነ በአለባበሳቸው እንድንለያቸው ያስችለናል (Sims & Stephens, 2005:98-99)። የ Salamone, (2004) አከፋፈል የተመለከትን እንደሆነ ወደ አስራ ስምንት የተለያዩ የከበራ ዓይነቶች እንዳሉ በዝርዝር ያስረዳል።

በሌላ በኩል Bell, (1997) የ Ronald Grimmis አከፋፈል ማለትም፡- ከበራን በአስራ ስድስት ዓይነቶች መክፈሉን በመግለጽ፤ በራሷ መንገድ ደግሞ እንደሚከተለው በስድስት ዓይነቶች መድባ ለማየት ችላለች። እነሱም፡-

1ኛ. የሕይወት ዑደት (rites of passage)፣

2ኛ. ዓመታዊና የመታሰቢያ ከበራ (calendrical and commemorative rites)

3ኛ. ማህበረሰቡ ከፈጣሪያቸው ጋር ላላቸው ቀረቤታ (ለሚነት) ና ላደረገላቸው መልካም ነገር የሚያደርጉት ምላሾች(rites of exchange and communion) የሚመለከት የከበራ ዓይነት፣

4ኛ. በስነ-ልቦናና አካላዊ ከሚደርሱ መከራዎችና ችግሮች ለመውጣት የሚከወኑ ከበራዎች (rites of affliction)፣

5ኛ. የድግስ፣ የአፅዺማትና የክብረ-በዓል ከበራ (rites of feasting, fasting, & festivals)ና

6ኛ. ፖለቲካዊ ከበራ (political rituals) ናቸው ።

ይሁን እንጂ እነዚህ የዣኔሮች ዝርዝር የተሟሉ ናቸው ለማለት አይቻልም፤ ብዙ ተቀባይነት ያላቸው ሌሎችም ከበራዎች በሌላ ምድብ ሊደለደሉ ይችላሉ፡፡ ሌላው ደግሞ ካለው እውነታ ተመርኩዞን ስንገምት ከበራ ከአንድ ቦታ በላይ ሊመደብ እንደሚችል Bell በማከል ታስረዳለች፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የከበራ ዓይነቶች ውስጥ ይህ ጥናት Bell ከከፈለቻቸው ምድቦች በ3ኛ እና 4ኛ ተራ ቁጥር ስር ባሉት ውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡ ምክንያቱም በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ውስጥ አንዱና ዋንኛው ክዋኔ የጉጂ ማህበረሰብ ከፈጣሪው (waaqa) ጋር ያለው ግንኙነትና ለፈጣሪውም የሚያቀርበው ምስጋናና ውዳሴ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቡ ላይ ከሚደርሱና ከደረሱ ስነ-ልቦናዊና አካላዊ ችግሮች፤ ማለትም ከሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ለመውጣት የሚከወኑ ከበራዎች ስላሉ ነው፡፡ ስለዚህ በነዚህ የከበራ ዓይነቶች ላይ በዋናነት በማተኮር ሌሎችንም፡-ማለትም ቃሉ ከመንፈሳዊ ድርጊት ተነስቶ ወደ ዓለማዊ ከበራዎች ሊያመራ ስለሚችል፣ በሌላ በኩል ከአውዱ አኳያ ባለዝቅተኛ አውድ ከበራና ባለከፍተኛ አውድ ከበራን የተመለከትኩበት ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡

## 2.1.3.3. የከበራ ባህሪያት

የከበራ ባህሪያት ናቸው ተብለው በተለያዩ ምሁራን የተገለጹ መገለጫዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ክዋኔው ድግግሞሽ ያለው፣ መዋቅራዊ የሆነና በተከታታይ የሚቀርብ ድርጊታዊ ዝግጅት ሲሆን፤ በውስጡም ተምሳሌቶች፣ ድርጊቶች፣ የድግግሞሽ ባህሪያት ያለውና የከበራው መክፈቻና መዝጊያ ስርዓት የተበጀላቸው እንደሆኑ Myerhoff (1977)'ን በመጥቀስ Sims and Stephens, (2005:95-97) ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል የከበራ ድርጊቶች ቅደም ተከተልን የጠበቁና ቡድናዊ ገፅታ ያላቸው ናቸው (ዝኒ ከማሁ)፡፡

Bell በበኩሏ የከበራን ባህሪያት ስትገልጽ ስርዓት ያለው፣ ባህላዊነት፣ አንዱን ከሌላው የሚለይበት ገደብ የሌለው፣ በህግ የሚመራ፣ ቅዱስ ተምሳሌነት፣ ክዋኔ የሚታይበት እንደሆነ ትገልጻለች (Bell,1997:139-160)::

ከላይ ከተሰነዘሩት አጠቃላይ ባህሪያት እንደምንመለከተው ከበራ የመዋቅራዊነት፣ ቅደም ተከተላዊነት፣ ተደጋጋሚነት፣ ታዳሚ፣ ውጤትና ቅዱሳዊነት ይንፀባረቅበታል፡፡ ስለዚህ እነኚህ ባህሪያት የከበራ መገለጫዎች ናቸው፡፡ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራን የተመለከትን እንደሆነ እነዚህ ባህሪያት ሙሉ ለሙሉ በጥናቱ ውስጥ ታይተዋል፡፡

## 2.1.3.4. የከበራ ፋይዳዎች

አንድ ከበራ በዋል ፈሰስ አይከወንም፤ የራሱ የሆነ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ከበራ ያለው ፋይዳ ማህበራዊ ወይም ግለሰባዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ የሚያሳየው ማህበራዊ የሆነውን ከበራ ግለሰቦች የሚፈጽሙት ለራሳቸው ግለሰባዊ ፋይዳ ሊሆን መቻሉን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እኛም ሆነን ሌሎች የሚያውቁትና የሚረዱት ከበራን እየከወንን መሆናችንን ነው (Myrvold, 2008፡19)፡፡ ስለዚህ ከበራዎች ሲጠኑ የሚከወኑበትን ማህበረሰብ ማንነት እና የሚጠናውን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት እንዲቻል የከዋኞቹን ማንነትና የክዋኔውን ምክንያት መረዳት ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ከበራውን ከነአውዱ በጥልቀት በማጥናት የሚመጣ ይሆናል፡፡

ህዝቦች ደጋግመው የሚከውኑዋቸው የእምነትና የባህላዊ እሴቶች ከበራዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ከበራዎች ደግሞ ውስጣዊ ልምዶችን ወይም ወጎችን ለባህሉ ባለቤትም ሆነ ለውጭው ታዳሚ ገዝፈው እንዲታዩና እንዲለመዱ ያደርጋሉ (Sims & Stephens, 2005:94)፡፡
Bell, (1997:37) የ Van ’ን ሀሳብ በመጥቀስ የከበራ ተግባር ቡድኖች የሚተዳደሩበት ስርዓት ወይም የሚያራምዱት አመለካከት፣ የሚመሩባቸውን ህግጋት እንዲያከብሩና እንዲጠብቁ የማነሳሻና ማደራጃ ዘዴዎች እንደሆኑ ትገልጻለች፡፡
ከበራዎች ሁልጊዜ የሚከወኑት ታዳሚዎቹን ለማሳመን ነው፡፡ ባጠቃላይ ከበራዎች መንፈሳዊ ፍላጎትን ያረካሉ፡፡ የከዋኞቹን ማህበራዊ ግንኙነት እንዲሁም የቡድኖችን የማንነት ስሜትና የእርስ በርስ ግንኙነት ያጠናክራሉ፡፡ ከበራዎች ግጭቶችን ይፈታሉ፡፡ እንዲሁም ወጎችንና እሴቶችን ለመግለፅ ያግዛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለነገሮች ወሰን እንዲበጅ፣ የአብሮነት ስሜት እንዲራመድ ያደርጋሉ (ዝኒ ከማሁ: 24-25)፡፡ ከዚህ በመነሳት የማንነት ፖለቲካም ያራምዱበታል፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች፣ ከተለያዩ አካባቢዎች ተሰባስበው በአንድ ላይ የሚያከብሩት፡፡

ከዚህ ጋር በማያያዝ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ፋይዳዎችን በተመለከተ ከቀረቡት ፅንሰ ሀሳቦች አንጻር የታዩ ሲሆን፣ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በተመረጡት የመተንተኛ ዘዴዎች በተወሰነ ደረጃ ተፈትሸዋል፡፡

ሌላው ስለ ሃይማኖታዊ ከበራ ሲነሳ በዋናነት ከሃይማኖት ጋር ቁርኝት ስላለው ሚትን ማንሳት የግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም ስለ ፍጥረታትና ፈጣሪ ምንነት የሚተርክ ሚት በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ለግንዛቤ ይረዳን ዘንድ ባጭሩ ስለሚት ምንነት እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 2.1.4. ሚት (Myth)

ቃላዊ ዝርው ተረኮች በመባል በዋናነት የሚታወቁት የፎክሎር ቅርጾች ሦስት ዓይነቶች ናቸው፡፡ እነሱም *ሚት*፣ አፈ-ታሪክና ተረት ናቸው (Bascom, 1965፡5)፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሚት ስለ አማልክትና ስለ ነገሮች አፈጣጠር የሚተርክ፣ በአማኞቹ ዘንድ የተቀደሰ ተብሎ የሚታመንበት ሰነድ ነው (ዝኒ ከማሁ፡ 4)፡፡

ይህንኑ ጉዳይ Oring, (1986፡124) ሲያጠናክረው *ሚት* እውነትነቱ መረጋገጥ የማይችል፣ ዓለምን ማን ፈጠረው ለሚለው ምላሽ የሚሰጥ፣ የተቀደሰ፣ ስለ ፍጥረታትና ፈጣሪ የሚያወጋ፣ ገጸባህሪያቱ ልዕለሰብ የሆኑ፣ ፍጹም መንፈሳዊነት የሚንጸባረቅበት፣ የሚታመን፣ የመክፈቻና የመዝጊያ ስርዓት የሌለው ወይም ያልተወሰነ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

እንደ ቴዎድሮስ (2001:xii) ገለጻ ደግሞ "*ሚት* የሰው ልጅ የነገረ ፍጥረትና የነገረ ህላዌ እንቆቅልሾችን ለመመለስ የሞከረበት፣ እየተመሰቃቀለ ለሚያስቸግረው ዓለም ህልው ሥርዓት ለማበጀት የባተለበት እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው፡፡ *ሚት* የማኅበረሰቡ የእሴት ስርዓትም ነው" ይላል፡፡
ከጥቅሶቹ ለመረዳት እንደሚቻለው *ሚት* የአማልክትና አምላክ አከል የሆኑ ልዕለ ተፈጥሮ ኃይላትን የያዘ፣ ስለ ፍጥረት አመጣጥና ስለ ተፈጥሯዊ ልዩ ልዩ ክስተቶች የሚያትት የሰው ልጅ ህልውና የተመሰረተበት እንደሆነ ነው፡፡

ሌላው ስለ*ሚት* መነሳት ያለበት፤ ሚት ከድሮ ጀምሮ ያለ መንፈሳዊ ተረክ (sacred narrative) ነው፡፡ ፎክሎረኛ ባልሆኑ ሰዎች ዘንድ ሚት ማለት ልክ እንደ ሞኝነት ወይም ውሸት ነገር እንደሆነ ይረዱታል፡፡ ነገር ግን ፎክሎረኞች የዚህን ቃል ትርጉም የሚረዱት በዚህ መልኩ አይደለም፡፡ ሚት ሰዎች ስለነገሮች አመጣጥ (አጀማመር) የሚናገሩት የፎክሎር ዘውግ ነው፡፡ ዘወትር ከሰዎች ሃይማኖት ጋር ይያያዛል፣ ከከበራና ዝግጅት (ሰሪሞን) ጋር ይጣመራል፡፡ ስለ መሬትና አጠቃላይ ነገሮች አፈጣጠር ያስረዳናል፡፡ ነገሮች ለምን ባሉበት መንገድ ሆኑ ለሚለው ማብራሪያ ይሰጣል (Schoemaker,1990፡237)፡፡

በሌላ በኩል በሚተረኩ ሚቶች ላይ ተንተርሰን የዚያን ቡድን ፖለቲካዊ ፍላጎት ማጥናት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ስለቃሉ ስርዓትና ሃይማኖታዊ ከበራዎች መረጃ ማግኘት የሚቻለው ከማህበረሰቡ ሚት ስለሆነ፤ የጉጂ ኦሮሞ ሚቶች በተወሰነ ደረጃ ተዳሷል፡፡ ምክንቱም ለተሰበሰበው መረጃዎችም ሆነ ለሚተነተኑበት ዘዴዎች አቅጣጫ የሚያመላክት በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው ስለሃይማኖታዊ ከበራዎች ጥናት የሚያካሂድ ተመራማሪ በከበራዎች ላይ ከሚተረኩ ሚቶች በተጨማሪ የሚከወኑባቸውን ቁሳዊ ባህሎች ሳያማክል ትንታኔ ማካሄድ አይታሰብም፤ ቢሞክርም እንኳን ትንታኔውን የተሟላ አያደርገውም፡፡ ስለዚህ በከበራዎቹ ላይ የቀርቡትን ቁሳዊ ባህሎች ምንነትና ተምሳሌትነታቸውን መመልከት ሰላስፈለገ ፅንሰ-ሀሳቦቹን እንደሚከተለው ለማየት ተችሏል፡፡

### 2.1.5. ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል ማለት ከአራቱ የፎክሎር ጥናት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ፈቃደ፣ (1991፡15) Dorson'ን በመጥቀስ በዚህ ዘርፍ ስር ሀገረሰባዊ እጅስራ፣ ሀገረሰባዊ ስዕል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰባዊ ልብስና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራርን የመሳሰሉ እንደሚጠኑ ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ቁሳዊ ባህል ሲባል ሰዎች በአካባቢያቸው ለማህበራዊ ግልጋሎት የሚጠቀሙበት፣ ለማህበረሰቡ ተምሳሌታዊ ፍች ያላቸው ዕቃዎች ናቸው (Woodword, 2007፡3)፡፡ ስለዚህ በቁሳዊ ባህል አማካኝነት የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ልናጠና እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ቁሳዊ ባህል በአንድ በተወሰነ ጊዜ የነበረን ማህበረሰብ እምነት፣ እሴት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብና እውቀትን ከእደ ጥበባቸው አንጻር የሚያጠና በመሆኑ ነው (Prown, 1982፡1)፡፡ ስለዚህ ባህላዊ ቁሶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያስተላልፉት መልእክት አሏቸው (Danesi, 2004፣33)፡፡

በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ በሃይማኖቱ መሪዎቹም ሆነ፣ በታዳሚዎቹ የሚለበሱ ሀገረሰባዊ አልባሳት፣ በዝግጅቱ ላይ የሚቀርቡ ባህላዊ ምግቦችና የመሳሰሉት ከተመለከትን ቁሳዊ ባህሉን እንድንቃኝ ያስገድዱናል፡፡ ምክንያቱም በከበራው ላይ የሚቀርቡት አልባሳትም ሆኑ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች ከወትሮው ዕለት የተለዩና የማህበረሰቡ የማንነት መገለጫ ስለሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን የፎክሎር ዘርፎች ከከበራው ለይቶ ማውጣት ያስቸግራል፡፡

ሃይማኖታዊ ተቋማትና ተያያዥነት ያላቸው ቁሳዊ ባህሎች ሲጠኑ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው በ Oring, (1986፡44) ውስጥ Danielson እንደሚለው፡- በቅድሚያ ቁሶቹን የሃይማኖቱ ባለቤት

ምን ይላቸዋል? እንዴትስ ይገለገልባቸዋል? የሚሉትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር ወደ ፎክሎራዊ ገጽታቸው መምጣቱ የተሻለ መሆኑን ይገልጻል።

ሌላው ቁሶችን ከሃይማኖታዊ ከበራው ጋር ለማጥናት የተፈለገበት ምክንያት ቁሶቹ ለማህበረሰቡ ከዕለት ተዕለት ግልጋሎታቸው ባሻገር ሰፊ ትርጉም አላቸው። ይኸውም ቁሶችን የዚያን ማህበረሰብ እሴቶች፣ አመለካከቶችና ፍላጎቶች እንዲሁም የዘመኑን መንፈስና የማህበረሰቡን የህይወት ልምድ ያንጸባርቃሉ (Jones, 2000፡9)። Glassie, (1999፡143) ይህንን ጉዳይ በምሳሌ ሲያስረዳ የእርሻ መሳሪያዎችን በማጥናት ስለ አራሾቹ፣ የአደን መሳሪያዎቹን በመመርመር ስለ አዳኞቹ ወይም የእምነት ተቋማትን በመመርመር የአማኞቹን የህይወት አተያይና እሴቶች መረዳት እንደሚያስችል ይገልጻል።

አንድ ሃይማኖታዊ ከበራ በሚከወንበት ወቅት እንደየእምነቱና ባህሉ ለየከበራው ማስፈጸሚያ፣ አሊያም ማጀቢያ የሚውሉ የተለያዩ ቁሳ ቁሶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ምግቦችና መጠጦች፣ አልባሳትና የመገልገያ ቁሳቁስ በዋናነት ይጠቀሳሉ። አብዛኛውን ጊዜ የነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ስያሜና አገልግሎቱ ከወትሮው በተለየ መልኩ ነው። ለአብነት ያህል ብንመለከት አንድ በቤታችን የምንጠቀመው ውሃ እና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ከበራ የሚጠቀሙት ጠበል (holy water) የተለያዩ ናቸው። ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ ጠበሉ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የተቀደሰ ነው ብለው ስለሚያምኑ ከተለያዩ ደዌዎች የመፈወስ ኃይል አለው ተብሎ ይታመናል። በሌላ በኩል ለእምነቱም ከበራ እንደመገለጫነትም ያገለግላል። ባጠቃላይ ለተለያዩ ግልጋሎት የሚውሉ ቁሳዊ ባህሎች ከመገልገያነታቸው ባለፈ የተጠቃሚውን ማንነትም የመግለጽ አቅም እንዳላቸው Danesi, (2004፡182) ያስረዳል። ስለዚህ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ የሚታዩ ከአባቃሉና የመማክር አባላቱ አልባሳት፣ በከበራው ላይ የሚቀርቡ ምግቦች፣ የከበራ ማስፈጸሚያ ቁሶችና የመሳሰሉት ሁሉ የየራሳቸው ተምሳሌትና ትርጉም አላቸው። ምክንያቱም ተምሳሌት አንድን ቁሳዊ አካል ሞራላዊና መንፈሳዊ እውነትን ወክሎ እንዲቆም በማድረጉ ነው (Ballenger,1998፡769)።

ስለዚህ የአንድን ሃይማኖታዊ ከበራ ምንነትና ፋይዳ መርምሮ ለመግለፅ የሚቻለው የክዋኔውንም ሆነ የቁሳዊ ባህሉን ትርጉም (ፍች) ስናገኝ ነው። ፍቹን ለማግኘት ደግሞ የቀረበው ቴክስት ምንድነው?፣ የቀረበበት አውድስ ምን ይመስላል? የሚሉትንና በክዋኔው ላይ

የቀረበው የቴክስቱ አገላለጽ ለዛ ምን ይመስላል? የሚሉትን በመተንተን የሚገኝ ነው፡፡ ስለዚህ የነዚህን ፅንሰ-ሀሳቦች ምንነት እንደሚከተለው ማየት ያስፈልጋል፡፡

## 2.1.6. ስነ-ፍችና አውድ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የአንድን ፎክሎር መልዕክት ለመረዳት የቀረበውን ቴክስት፣ በምን ዓይነት የአነጋገር ለዛ እንደተገለጸና በምን ዓይነት አውድ ላይ እንደተከወነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የነዚህን ፅንሰ-ሀሳቦች ምንነትና ባህሪያቸውን ማወቁ የመጀመሪያ ጉዳይ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ርዕስ ስር እያንዳንዱን ጉዳዮች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 2.1.6.1. ስነ-ፍች

ስነ-ፍች (semantics) ማለት በቋንቋ ውስጥ የፍቾች ፍልስፍናዊ ወይም ስነ-ልሳናዊ ጥናት ነው፡፡ የማንኛውም አገላለጽ በስነ-ፍች አስተሳሰብ ፍቾቹ ከቅርጻቸው ተቃራኒ እንደሆኑ Baldick (2001፡232) ይገልጻል፡፡

የፎክሎርን ትርጉም የተሟላ ለማድረግ ሦስት የትንተና ዓይነቶች (ደረጃዎችን) እንዳሉ፣ እነሱም፡- ቴክስት (Text)፣ አውድ (context) እና የአቀራረብ ለዛ (Texture) እንደሆኑ Dundas, (1980) ይገልጻል፡፡ አንድን የፎክሎር ዓይነት ወይም ዘውግ (gener) በእነዚህ በሦስቱ ላይ ትንተና በማድረግ ለፎክሎሩ የተሟላ ትርጉም መስጠት ይቻላል፡፡

በአብዛኛው የፎከሎር ዘውጎች በተለይም በቃላዊ የፎከሎር ዓይነቶች ውስጥ የአቀራረብ ለዛ (Texture) ቋንቋ ነክ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የድምጽ (phoneme) እና የምዕላድ (morpheme) ጉዳይ ትኩረት ስለሚያገኝ ነው፡፡ በቃላዊ ፎክሎር ውስጥ ያለው ለዛ የሚከወነው ቴክስት ውበትን እንዲጎናጸፍ የሚያደርግ ነው ማለት ይቻላል፡፡

Schoemaker, (1990፣37) እነካቲሪንግ እና ጀኒፈርን በመጥቀስ በንግግር ወቅት በአንድ ጊዜ በሦስት ደረጃዎች በመታገዝ እንደምንግባባ ይገልጻል፡፡ ይኸውም፡- ስነ-ልሳን (lingustic) ማለትም፡- ቃላትን፣ ንበትንና ሰዋሰውን ሲያካትት፣ ፓራሊንጉስቲክ (paralingustic) ደግሞ የድምጽ አወጣጥ ቅላጼያችን፣ የድምጽ ከፍና ዝቅ ማድረግና የንግግራችንን ፍጥነት ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ ካይነስክስ (kinesics) ሲሆን፡- የፊት ገፅታ መቀያየርና ምልክቶችን (በአካላዊ እንቅስቃሴዎች) በመታገዝ መልዕክት ማስተላለፍ ናቸው፡፡

ይህንን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ እነ Sims M. & Stephens M., 2005,134). ሲገልጹ፡-

> *Folklorists pay attention to the performed act of expressive, artistic communication, the when, where, with whom, how, and why people communicate with each other. In addition to actual content, words, or actions (texts), folklorists consider literary, linguistic or physical nuances of those texts (texture); and they study these elements within specific groups and settings (contexts).*

በማለት እንደ አንድ ፎክሎርኛ ትኩረት መስጠት ያለበትን በንግግር ወቅት ከማን ጋር፣ ምን አይነት ርእሰ ጉዳይ፣ መቼ፣ እንዴት፣ ለምን ሰዎች እርስ በርስ ይግባባሉ? በማለት የንግግራችንን ዘዴ የምናቀናጀው ከሁኔታዎች ጋር ነው፡፡ በተለያዩ አውዶችና መቼቶች የተሳካ ንግግር ለማድረግ እንደየሁነቱ የተለያየ የንግግር ዘዴዎችን እንጠቀማለን፡፡ በተጨማሪ በቋንቋችን በትክክል ለመጠቀም በቋንቋው ውስጥ ያሉትን ቃላት በበቂ ሁኔታ መረዳትና ሰዋሰዋዊ ህጎችን ጠንቅቀን ማወቅና መጠቀም ይጠበቅብናል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአቀራረብ ለዛ (Texture) ሙሉ በሙሉ ከቋንቋ ጋር የተያያዘ ብቻሳይሆን በሰውነት እንቅስቃሴም ታግዞ የሚከወነው ቴክስት ውብት ባለው ሁኔታ መልዕክቱን እንዲያስተላልፍ ማድረግ ነው፡፡

ስለዚህ አንድ በቃል፣ በምልክት ወይም በድርጊት ያለ የፎክሎር ዘውግ ቴክስት ይባላል፡፡ በውስጡ ያዘለውን ስሜት፣ ጥበብ፣ መልዕክትና የመሳሰሉትን ደግሞ የአነጋገርለዛ (texture) ይባላሉ፡፡ ከዚያ በአንድ የተወሰነ አውድ (context) ሲተረክ ወይም ሲከወን በጥምረት የሚያስተላልፉት መልዕክት ደግሞ ፍች ይባላል፡፡ ይህም መልዕክት ወይም ፍች አንድም ቀጥተኛ ፍች፣ አሊያም ተጓዳኝ ፍችን ይመለከታል፡፡

በመሰረቱ ፍች ማለት በመዝገበ-ቃላት ፍችው ቃል ወይም ቃላት ስለአንድ ነገር፣ ድርጊት፣ ስሜት፣ ሀሳብ፣ ወዘተ… በመወከል የሚያስተላልፉት መልዕክት ነው (Shovel, 2007፡933)፡፡ ፍችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መድበን ማየት እንችላለን፡፡ አንደኛው እማሬያዊ ፍች (literal meaning) ሲሆን፣ ቃሉ ወይም ቃላቱ የያዙት መሰረታዊው ቀጥተኛ ፍችን ይመለከታል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ፍካሬያዊ ፍች (contextual meaning) ማለትም ቃሉ ወይም ቃላቱ የያዙት ቀጥተኛ ፍች ሳይሆን አውዳዊ ፍች ነው።

ሌላው ስለ ፍች ስናነሳ ቃላት ከአገባባቸው አኳያ የተለያየ ፍች ይኖራቸዋል። እነሱም:- አቻ ፍች፣ ሆሞኒየም (Homonymy)፣ ተቃራኒ ፍች፣ የጥምረት ፍች (Hyponymy)፣ ፍች-ብዙነት (polysemy)፣ ተዛማጅ ፍች (metonymy)፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች (idioms) እና ዘይቤያዊ አነጋገሮች (metaphor) እንደሆኑ Danesi, (2004:66፣118) ይገልጻል። ስለዚህ እነዚህን አውቀን ትርጉሙን ለመረዳት የማህበረሰቡን ቋንቋና ባህል ማወቁ ግድ ይላል።

ፎክሎረኞች በትንተና ሂደት በፎክሎር ቴክስት፣ ክዋኔና አውድ መካከልና በጋራ ያላቸውን ግንኙነት ለመረዳት እንደሚችሉ Sims & Stephens, (2005:28) ያስረዳሉ። ይህ ማለት አንድ የፎክሎር ቅንጣት ወይም ቴክስት ሲከወን አንድም በቃል ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በድርጊት ነው። ክዋኔ ካለ የሚከወንበት አውድ አይቀሬ ነው። ታዲያ በዚህ ሂደት ውስጥ የአነጋገር ለዛው የትርጉም ለውጥ ሊያመጣ ይችላል።

### 2.1.6.2. አውድ

ለአውድ በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ተሰጥተዋል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ Dundes (1994) አውድን አንድ ድርጊት የሚከወንበት ጊዜና ቦታ እንደሆነ በአጭሩ የገለጸው ይገኛል። ስለዚህ የአንድ ፎክ ቡድን አባላት ፎክሎርን የሚጋሩበት አካላዊ መቼቶችና ማህበራዊ ሁነቶች እንዲሁም የታዳሚዎችና ከዋኞች ግንኙነት አውድን ይመሰርታሉ። በመሆኑም አውድ የሚያመለክተው በቴክስትና ክዋኔ ዙሪያ የሚገኙ ማንኛውንም ክዋኔ፣ እውነታ፣ ቁሳቁስ፣ ሁነቶችና ክስተቶችን ጭምር ነው (Sims & Stephens, 2005:138)። የተለያዩ የአውድ ዓይነቶች አሉ። እነዚህን ለይቶ ማወቁ ለሚካሄደው ፎክሎራዊ ትንታኔ ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል። ስለዚህ የአውድ ዓይነቶች መመልከቱ አስፈላጊ ነው።

የአውድ ዓይነቶች በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም ሁኔታዊና ባህላዊ አውዶች ይባላሉ። ሁኔታዊ አውድ የሚባለው የሚከወነው ጉዳይ የሚቀርብበትን ማህበራዊ ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ባህላዊ አውድ ደግሞ በውስጡ የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚቀርብበት ሰፊ ገጽታ ሲሆን፤ ክዋኔው በውስጡ የሚወክላቸውን ነገሮች፣ የሚከወነው ጉዳይ፣ የሚመራበት ማህበራዊ ደንብ፣ የተሳታፊዎች የእምነት ስርዓት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና የንግግር ስልት፣ የከዋኙ የታሪክ ዕውቀትና የስነ-ምግባር ህግጋትን ሁሉ ያጠቃልላል (Ben-Amos, 1993:216)።

ከስነ-ዘዴ አኳያ የፎክሎር ቅርጾችን በአውዳዊ ትንተና ዘዴ ለመተንተን የተለያዩ ዕቅዶች አሉ፡፡ አንድ ፎክሎረኛ ከመስክ የሚያገኘውን መረጃ ሲያደራጅ አውድን በተመለከተ ሊያተኩርባቸው የሚገባ ስድስት ነጥቦች እንዳሉ Bauman ያስረዳል፡፡ እነሱም፡- ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድና ሁኔታዊ አውድ ይባላሉ (Bauman, 1983፡367)፡፡ እነዚህን የአውድ ክፍሎች እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው በዝርዝር እንመልከት፡፡ እነሱም፡-

i. **ፍቻዊ አውድ**፡- የዚህ አውድ ትኩረት የሚያጠነጥነው ፎክሎራዊ ጉዳዩ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? የሚለውን ጥያቄ ከመመለስ ላይ ነው፡፡

ii. **ተቋማዊ አውድ**፡- ይህ ደግሞ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው፡፡

iii. **የተግባቦት ሂደት አውድ**፡- የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ቅርጽ ምንነት፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድናና አንዱ ከሌላው ለመለየት ማህበረሰቡ የሚጠቀሙበት ዘዴንም ያካትታል፡፡

iv. **ማህበራዊ መሰረት**፡- የፎክሎር ማህበራዊ መሰረት በመካከላቸው ዝምድና ባላቸው ቡድኖች መካከል የሚታይ ዋነኛው የአውድ መገለጫ ገጽታ ነው፡፡

v. **ግለሰባዊ አውድ**፡- ፎክሎር ግለሰቦችም ስሜታቸውንና ሀሳባቸውን የሚገልጹበት ጥበብ ነው፡፡

vi. **ሁኔታዊ አውድ**፡- ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዩን የሚከውነው በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? ሁኔታዊ አውድ ሲባል በባህሉ የተወሰነ የአንድ ባህሪ ወይም ገጠመኝ መግለጫ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት የሚከናወንበት አውድ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በእነዚህ የአውድ ዓይነቶች በመታገዝ የቃሉ ከበራዎች ከአውድ አኳያ ያላቸውን ፍች ተተንትነውበታል፡፡

## 2.1. የንድፈ-ሀሳብ ቅኝት

በፎክሎር ጥናት መረጃዎችን ከመሰብሰብ እስከ መጨረሻው የጥናቱ ውጤት ማጠናቀሪያ ድረስ በተለያዩ ሂደቶች ውስጥ ያልፋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ በፎክሎር የመስክ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች በሁለት ደረጃዎች ይገለጻሉ፡፡ ይኸውም፡- መረጃዎችን መለየትና መተርጎም እንደሆኑ Dundes, (1980:211) ይገልጻል::

ስለዚህ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ዙሪያ ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመጀመሪያ ደረጃ ካላቸው የድርጊቶች የእርስ በርስ ቅርበትና ቅደም ተከተላዊ ሂደታቸው ላይ በመመስረት ተለይተዋል፡፡ ከዚያ በመቀጠል ለእያንዳንዳቸው ትንታኔ ለመስጠት አመቺ ናቸው ተብለው የተመረጡና በስራ ላይ የዋሉ ንድፈ-ሀሳቦች ተለይተው ተገልጸዋል፡፡ እነሱም፡- የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን (Social Construction) እና ተምሳሌታዊ አተረጓገም (symbolic Interpretive) ንድፈ-ሀሳቦችን በዋናነት የጥናቱ ማቀንቀኛ ሲሆኑ፤ አውዳዊ፣ ፋይዳዊና ክልላዊ (hemispheric)[2] ንድፈ-ሀሳቦች ደግሞ እንደ አጋዥ ማስተንተኛ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በጥናቱ ውስጥ የእያንዳንዱ ንድፈ-ሀሳብ ሚና ምን ምን እንደሆነ ከዚህ በታች በዝርዝር ለማየት ተችሏል፡፡

### 2.1.1. የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ

አንድ ማህበረሰብ በሚኖርበት ዓለም ያሉትን ነገሮች የሚያውቅበትና ትርጉም የሚሰጥበት፣ ከዚያም አልፈው ተቋማትን መስርተው በእነሱ ተመልሰው የሚተዳደሩበት ህግና ደንብን ይመሰርታሉ፤ ይገዙለታልም፡፡ ይህ ዕውቀት ከየት መነጨ ሲባል ምሁራን የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የዕውቀት አዋቃሪያን አንደኛው ነው፡፡ በዕውቀት አዋቃሪን ስር የሚነሳው ንድፈ-ሀሳብ የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ነው፡፡ይህ ንድፈ ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ገኖ የወጣው እ.አ.አ. በ1966 በእነ *Berger,P. & Luckman T.* ካሳተሙት *"The Social Construction of Reality"* ከሚል መጽሐፋቸው በኋላ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

የዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ ማህበረሰቡ ከሚያከናውናቸው የዕለት ተዕለት ተግባራት በሂደት ልማድን እየፈጠሩ፤ በመቀጠል ተቋማትን እየገነቡ ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ ለተቋማቱ ቅደም ተከተላዊ ተግባራትን በመጀመሪያ ደረጃ ያዋቅራሉ የሚል እሳቤ አላቸው፡፡ ይህ የጋራ ዕውቀትም እያንዳንዱ ሰው በተናጠል ካለው ዕውቀት ተጠራቅሞ የተገነባ እንደሆነ Berger & Luckman, (1966:83) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> The primary knowledge about the institutional order is knowledge on the pretheoretical level. It is the sum total 'what everybody knows' about a social world, an assemblage of maxims, morals, proverbial nuggets of wisdom, values & beliefs', myth, and so forth....

[2]የእነዚህ ንድፈ-ሀሳቦች አቻ ትርጉም በትምህርት ክፍሉ የተለመዱና ቀደም ካሉ የፒ.ኤች.ዲ ድሰርቴሽን የተገኙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ከዚህ ንድፈ-ሀሳብ አተያይ ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማህበራዊ ውቅር ነው። ንድፈ-ሀሳቡ ማህበረሰቡ በጋራ ያዋቀሩት ዕውቀት በግለሰብ ደረጃም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ በእኩል የሚሰራ ድንጋጌ እንደሆነ ይገልጻሉ። ግለሰቦች ማህበረሰቡ ባኖሯቸው ድንጋጌዎች ይገለገላሉ፤ ይመራሉ፤ ይቀጣሉ። ንድፈ-ሀሳቡ ዕውቀቱ በሂደት ባዋቀሯቸው የጋራ ጉዳዮች ውስጥ በግለሰብ ደረጃና በማህበረሰብ ደረጃ ትርጉም አዘል ሆኖ ሊሰራ እንደሚችል ያወሳል። ሆኖም በግለሰብ ደረጃ ያለው ዕውቀት ከግለሰብ ግለሰብ ሲለያይ፤ ተቋማትም ባላቸው ሚናና አግባብነት ያለው የግንኙነት ህግ የተነሳ በየደረጃው ይለያያሉ (ibid)።

ብዙን ጊዜ ሰዎች በዓይናቸው ፊት ለፊት ስላላዩትም ሆነ በቀጥታ ልምዱ ስለሌላቸው ነገሮች ሲናገሩ ይደመጣሉ። በዚህ በኩል ቋንቋ ነገሩ በምን ዓይነት መጠን ፍችና ልምድ እንዳለ በወቅቱ የመግለጽና ለተተኪው ትውልድም የማስተላለፍ አቅም አለው (ibid፡ 52)። በተለይም ስለቃሉ አመጣጥና ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ሁኔታ የጉጂ ኦሮሞ በሚቶቻቸው በዚሁ መልክ ሲገልጹ ኖረዋል፤ እየገለጹበትም ነው። የማህበረሰብ ዕውቀት በማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ እያደገ የሚሄድ፣ የሚተላለፍና ማስተካከያ ሊደረግበት የሚችል ነው (Berger and Luckmann;1966:15)።

የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ፋይዳዎች በምናይበት ወቅት መቅደም የሚገባው ይህንን ማህበረሰባዊ ዕውቀት እንዴት አወቁት? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል። ይህን ጥያቄ ለመመለስ ቀደም ሲል አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ዕውቀት እንዴት ሊያውቁ እንደሚችሉ በ3.1. ውስጥ ስናነሳ አንደኛው በዕውቀት አዋቃሪያን መንገድ እንደሆነ ለማየት ችለናል። ስለዚህ ይህ የማህበረሰብ የዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ በመጠቀም የጉጂ ኦሮሞ ቃሉን፣ የቃሉ ተቋምን፣ የቃሉ መማክርት እነማን መሆን እንዳለባቸው፣ ተግባራቸውም ምን ምን መሆን እዳለበት፣ ሃይማኖታዊ ህጎቹ ምን ምን እንደሆኑና በህጉም እንዴት እንደሚመሩበት ያዋቀሩትንና ለህጉም እንደሚገዙና እንዴት እየተገበሩ እንደሆነ ተተንትኖበታል።

## 2.1.2. ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳብ (symbolic Interpretive)

ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳብ ጠንሳሽ George Mead ሲሆን በመቀጠል በ Herbert Blumer የዳበር የንድፈ-ሀሳብ አካል እንደሆነና ጥናትም በእነሱ ስራ እንደጀመረ ይነገራል።

*‹‹ Symbolic interactionism emphasises the construction of the social world and meaning through the human use of symbols in communication, most importantly language.››* (Burr, 2003:205).

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ይህ ንድፈ-ሀሳብ አጽንኦት የሚሰጠው ሰዎች ስለማህበረሰባዊ ዓለምና ፍችያቸው በተግባቦት ወቅት ተምሳሌቶችን፣ በአብዛኛው ቋንቋን በመጠቀም እንደሚያዋቅሩ ነው።

ተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ በቀጥታ የሚያወሳቸው ጉዳዩች እንደ ቋንቋ፣ ተግባቦትና በመካከላቸው ያሉ ግንኙነቶችንና ማህበረሰቡን ነው (Crotty, 1998:7-8)።
ተምሳሌት ደግሞ በወካይና በተወካይ መካከል ያለውን ዝምድና ለመግለጽ ያገለግላል። መገለጫውም በቋንቋ፣ በቁሳቁስና በክዋኔ ሆኖ በውስጡም በርካታ ትርጉሞችን ይይዛል። ተምሳሌት እንደየባህሉ የተለያዩ ትርጓሜዎችን ሊይዝ ይችላል። ለአንድ ማህበረሰብ ተምሳሌት የሆነው ለሌላው ላይሆን እንደሚችል Dundes, (1989:112-114) ያስረዳል። እንደ Bronner, (2007:63)። ገለጻ የአንድ ባህል ተምሳሌታዊነት የሚገለጸው ፎክሎሩ በተገለጸበት በዚያው ባህል ውስጥ ነው።

መንፈሳዊ ተምሳሌትን የተመለከተን እንደሆነ ከሌሎች ለየት የሚያደርገው የራሱ የሆነ ባህሪይ አለው። እነ Sosis, R., የ Douglas (1966) ሀሳብ በመጥቀስ ስለመንፈሳዊ ተምሳሌት ሲያስረዱ፡- መንፈሳዊ ተምሳሌት የተለየ እእምሯዊ የአቀባበል ሂደት ያለው ነው፤ ነገር ግን አንድ ሰው የቅዱስነቱን ፍች የሚያገኘው በሚታየው ስሜት ውስጥ እንደሆነ ያስረዳሉ። ሃይማኖታዊ ተምሳሌቶች የሚፈጠሩት ከረቂቅ ነገሮች ሲሆን፤ እነዚህን ቁሶች የሚቀርቡት በአክብሮትና በመንቀጥቀጥ ስሜት ("awe")፣ ንጽህናን ("purity") እና አደገኛነትን ("danger") በማላበስ ይሆናል። እነዚህ በማንኛውም ሃይማኖታዊ ክበራ ላይ የሚታዩ ወሳኝ ገጽታቸው ናቸው (Sosis, R., and C. S. Alcorta, 2005:332)።
ከዚህ በተጨማሪ Turner, (1967:19) በመስክ ቆይታው ከተገነዘባቸው ውስጥ በዓይነታቸው ቁሶች፣ ክዋኔዎች፣ የማህበራዊ ግንኙነቶች፣ ክስተቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችና የከበራ ስፍራዎች ተምሳሌታዊ ፋይዳ እንዳላቸው እንደሚከተለው ይገልጻል። *‹‹The symbols I observed in the field were, empirically, objects, activities, relationships, events, gestures, and spatial units in a ritual situation. ››*

ሌላው ተምሳሌት በቀለማት፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ፣ በቁሶች፣ በተለያዩ የፊት ገጽታዎችና የመሳሰሉት እንደሚገኙ Danesi, (2004:4) ይገልጻል።

በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ የሚቀርቡ ቁሳዊ ባህሎች፣ ክዋኔዎች፣ አከዋወናቸው፣ የማህበራዊ ግንኙነቶች ደረጃዎችና የመሳሰሉት የሚያስተላልፉት መልዕክት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚወክሉት ነገሮች አሏቸው። ታዲያ እነዚህንና የመሳሰሉት ተምሳሌቶች ፍች በሦስት መንገድ ማግኘት ይቻላል። ይኸውም፡- 1) የከበራ ተሳታፊ መረጃ አቀባዮችን በመጠየቅ፣ 2) የከበራው ድርጊት ሲከወን በመመልከት በተምሳሌቱ የሚገለፀውን ድርጊት በመተንተን ፍችውን ማወቅ እና 3) ከሌሎች ተምሳሌቶች ጋር ባለው ግንኙነት የተደበቀ ፍችውን ማግኘት ናቸው (Turner, 1967:50-52)

ከዚህ በተጨማሪ Conner, (1996:8) የተምሳሌት ዓይነቶችን በስምንት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ እንደሚቻል ያስረዳል። እነሱም፡- ‹‹(1) Symbolic Objects (Human, Man made, Mineral, Objects in the Sky, Superhuman Objects, Vegetable), (2) Creatures, (3) Actions, (4) Numbers, (5) Names, (6) Colors, (7) Directions & (8) Places›› ተብለው ይጠራሉ)። እነዚህ ቀደም ሲል የተዘረዘሩት እያንዳንዳቸው በውስጣቸው ብዛት ያላቸውን ተምሳሌቶች አቅፈዋል።

በመሰረቱ ተምሳሌታዊ አተረጓገም እንደሰዎች ስለእኛ እና በመካከላችን የሚኖረውን ማንነቶች የምንገነባው በዕለት ተዕለት በምናደርገው ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ነው። በግለሰብም ሆነ ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ ያለው የዕውቀት ስርጭቱ እንዲጣጣም፣ ሽግግርም እንዲኖረው ቋንቋና ተምሳሌቶች ያሏቸው ድርሻ ትልቅ ነው። ሁለቱ እርስ በርስ ያላቸውም ትስስር ጥብቅ ነው። ይህን አስመልክቶ እነ Berger & Luckman, (1966:55) እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> *Language is capable not only of constructing symbols that are highly abstracted from everyday life experience, but also of 'bringing back' these symbols and presenting them as objectively real elements in everyday life.*

በእነርሱ አገላለጽ ተምሳሌት በቋንቋ ይፈጠራሉ፤ ይገለፃሉም። እነዚያ የተፈጠሩት ተምሳሌቶችም ከትውልድ ወደ ትውልድ ከሚሸጋገሩበት መንገድ አንዱ በቋንቋ እንደሆነ ነው።

ተምሳሌታዊ ሚና አለው ወይም አገኘ ማለት ፍች አዘል እንደማለት ነው። ይህ ፍች የተባለው በተምሳሌታዊ ነገሩ ውስጥ የታቀፈውና ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጠው ዕውቀት ነው። ከዚህም በላይ በተምሳሌታዊነቱና በፍችው ዝምድና ላይ አንዳች የሚቀርብ ምክንያት መኖሩ ስለማይቀር ያለውን ዕውቀት ተጨባጭ ያደርገዋል።

ስለዚህ የቃሉ ከበራን አስመልክቶ ከተሰበሰቡ መረጃዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ተምሳሌነትና የሚሰጡትን ግልጋሎት በዚህ ንድፈ-ሀሳብ ተቃኝተዋል። ለአብነት ያህል በጎንደሮ ከበራ ላይ ስለሚታረደው በግ መልክ፣ ስለሚጋረደው ነጠላ፣ የደሙ፣ የጠጁና የውሃው ተምሳሌታዊ ፍች፣ ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች ማለትም፡- ገዳዩ በጎንደሮ ከበራ ለመጀመሪያ ጊዜ ጀርባውን ዞሮ መሄድና የመሳሰሉት በዚህ ንድፈ-ሀሳብ ትንታኔ ተደርጎባቸዋል። ባጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቀሪያን ንድፈ-ሀሳብ በተጨማሪ ተምሳሌታዊ አተናተን በዋናነት መተንተኛ ሆኖ ቀርቧል።

### 2.1.3. አውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ

በዘመናዊ አጠቃቀም አውድ ማለት በስፋት ሲታይ ስለ አንድ ድርጊት ክንውን የሚገልጽ ሲሆን፤ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ደግሞ ንድፈ-ሀሳቦችንና ዘዴዎችን ይመለከታል (Ben Amos, 2006)። ከመስክ የሚገኘውን መረጃ የሚተነትንበት መንገድ በዋናነት አውዳዊ የትንተና ዘዴ ነው። ከተፈጥሯዊ መቼት የተሰበሰበ ክዋኔን ማዕከል ያደረጉ መረጃዎች የሚተነተንበት አተያይ ነው። በሌላ በኩል አካላዊ ነገሮች ማለትም በክዋኔ ወቅት እንደ የአካል እንቅስቃሴ፣ የፊት ገፅታ መለዋወጥ፣ የድምፅ መቀያየርና ዜማን የመሳሰሉት በራሳቸው የአውድ ክፍል ናቸው (Sims & Stephens,2005:138)።

አውዳዊ ትንታኔ የቡድኑን አባላት እይታ በፎክሎር ትንታኔ አቅጣጫ የሚታይበት ነው። ምክንያቱም የባህል ትርጉም የሚገኘው አውድን መሰረት ባደረገ መልኩ ትንታኔ ሲካሄድ በመሆኑ ነው (ibid: 26)። ከዚህ በተጨማሪ በቃሉ ተቋም የሚከወነው ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለታዳሚው የሚያስተላልፉት መልዕክት አላቸው። ስለዚህ አውዳዊ ትንተና በመጠቀም መረጃዎቹን በመተንተን መልዕክቱን መረዳት ያስችላል።

በአጠቃላይ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የአውድ ግንዛቤ ያለውንና የታየውን መረጃ መግለጽ ብቻ ሳይሆን ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን አካቶ መተርጎምንና መተንተንን የሚያካትት መሆኑን

Ben-Amos, (1993፡210-211) ያስረዳል፡፡ ስለዚህ በ 2.1.6.2. ስር የተዘረዘሩት የ Bauman የአውድ ዓይነቶች እንደ መረጃው ዓይነት በስራ ላይ ውለዋል፡፡ ይኸውም በጎንደሮ ከበራ ውስጥ የሚከወኑት እያንዳንዱ ድርጊት ምን ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ በፍቻዊ አውድ፣ የገዳ ስልጣኑ-ሢመት በቃሉ ተቋም ውስጥ መከወኑ የሚያስገኘውን ተቋማዊ ፋይዳ ለመመርመር ደግሞ በተቋማዊ አውድ፣ በጎንደሮ ከበራ ለመስዋዕት የቀረበውን ስርዓት መሳካቱንና ያለመሳካቱን፣ ምርቃትና እርግማን የሚከወነው በየትኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሆነ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉት አባላት በጾታ፣ በዕድሜ፣ በሙያ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በሃይማኖትና በመሳሰሉ ቡድኖች በመከፈል ለመለየት የማህበራዊ መሰረት አውድ በስራ ላይ ውለዋል፡፡

## 2.1.4. ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ

የፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ መነሻ የአዝግሞተ ለውጥ ንድፈ-ሀሳብ ሲሆን በተወሰነ መልኩ የራሱ ወደ ሆነው ስነ-ሰብዓዊ አመለካከት የመጣው በ Derkheim ተፅዕኖ ፈጣሪነትነው፡፡ የንድፈ-ሀሳቡ እሳቤ እየጎለበተ የመጣውግን Malinowski እና Radcliffe-Brown በተባሉ ተመራማሪዎችና በተከታዮቻቸው ስራዎች አማካይነትነው (Finnegan, 1977:44)፡፡ ይህ ንድፈ-ሀሳብ የሚያጠነጥነው አንድ የፎክሎር ቅንጣት ለማህበረሰቡ ትርጉምና አገልግሎት አለው በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ላይ እንደሆነ Okpewho, (1992:172-174) ያስረዳል፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ በግለሰቦች መካከል፤ እንዲሁም በማህበራዊ ተቋማትና በግለሰቦች መካከል ባሉ ግንኙነቶች ላይ ያተኩራል፡፡

በተጨማሪ የግለሰብ እርካታም፤ ፍላጎቶችን በባህላዊና ማህበራዊ ማዕቀፍ ውስጥ ያያል፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ አንድ የፎክሎር ቅንጣት ለቡድኑ ምን ማለት እንደሆነና ሰዎች ፎክሎርን የሚከውኑት በምክንያት መሆኑን ለመገንዘብ ያግዛል፡፡ ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማስተላለፍ፣ የማዝናናት እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው (Bascom, 1954፡344-346) ያስረዳሉ፡፡ ከዚያም በላይ የፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ እሳቤን ማወቅ አንድ ቡድን በአንድ ውስን ሁነትና ውስን ክዋኔ ውስጥ ምን እየሰሩ እንደሆነ ለመረዳት ያግዘናል፡፡

ይሁን እንጂ የዚህ ንድፈ-ሀሳብ ችግር የአንድ ክዋኔ ተግባር የማይቀየር ከሆነ ቡድኑ አይቀየርም የሚለው እሳቤ ነው፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ ሁሉም የቡድን አባላት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ይሰራሉ ብሎ ማመን ብቻ ሳይሆን ቡድኖች በዘመናት ሂደት ውስጥ ተመሳሳይ ሆነው ይቆያሉ ይላል፡፡ ይህም ማህበረሰብ አይለወጥም ወደሚለው ሃሳብ ያመጣናል፡፡ የፋይዳዊ አጠናን ዘዴ

ወግ አጥባቂና የማይለወጥ፣ ተግባራቱም ወግ አጥባቂ መሆናቸውን ያሳየናል። ይህ ደግሞ የዚህ ንድፈ-ሀሳብ ሌላው ድክመት ነው። ሌላኛው እንደ ድክመት የሚነሳበት ታሪክን እንደ አውድ አለመጠቀሙ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ፖለቲካዊ ተፅዕኖዎችን ያለፈ ሲሆን፤ ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ግን ፖለቲካን ከግምት አለማስገባቱ ነው።

ሌላው ከፋይዳዊያን ንድፈ ሀሳብ ቀጥሎ ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበረው ኒዮ-ፋንክሽናሊስት አቀራረብ ነው። የዚህ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች J. C. Alexander, Luhmann, and P. Colomy ሲሆኑ ከበራ የማህበረሰቡን ወይም የግለሰቦችን ሕይወት የጠቀመበትን የተለያየ መንገድ መፈተሽ ላይ ማተኮር እንጂ፤ የከበራ ፋይዳዎች መዘርዘርና መግለጽ ምን ያደርጋል ባይ ናቸው። ይህ አዲስ አስተሳሰብ ፋይዳን በ Radcliffe-Brownወይም በ Malinowski ፋይዳዊ አስተሳሰብ ቀንብቦ ማስቀመጥ ተገቢ አይደለም፤ በአንጻሩ የተለያዩ ባህላዊ ከበራዎች ግንኙነትን በማዋሃድ ስለሚፈጠረው ሁኔታ መግለጽ ላይ ያተኮረ ቢሆን ይመረጣል የሚለውንለማጽናት የሚሞክሩት ናቸው። ቢሆንም የቀደሙትን የፋንክሽናሊዝም ንድፈ ሃሳብ አንዳንድ እሳቤዎች በከፊልም ቢሆን ሲጠቀሙ እናያለን።

ኒዮ-ፋንክሽናሊስቶች ሊሰመርባቸው የሚገቡ ሁለት አስተሳሰቦች አሏቸው። የመጀመሪያው የሰው ልጅ ባህሪ በማህበራዊ ሁኔታዎች ብቻ የሚወሰን አይደለም። በተወሰነም ደረጃ ቢሆን የተለያዩ ሁኔታዎች ማለትም የኢኮሎጂያዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ዝርያዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ተለዋውጦዎች በሰው ልጅ ባህሪ ልዩነት ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ። በሌላ አገላለጽ ሁሉም ባህሪዎች የተለመዱና ሊለመዱ የሚችሉ ላይሆኑ ይችላሉ የሚሉ ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ እነዚህ ንድፈ-ሀሳባዊያን ነጠላ መገኛዎችን በማጥናት አለማቀፋዊ የሆነ የከበራ እንቅስቃሴ ተግባራት ሁኔታ ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ነው።

ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት ጉድለቶች ቢኖሩትም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ፋይዳዎችን በተወሰነ ደረጃ ለመግለጽ በመቻሉ ለዚህ ጥናት እንደ አጋዥ ማስተንተኛ በስራ ላይ ውሏል። የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች የገዳን ዴሞክራሲ ገጽታ ከመገንባት፣ የማህበረሰቡን ህልውና ከማስጠበቅ አኳያ፤ ባጠቃላይ ኒዮ-ፋንክሽናሊስቶች እንደሚሉት ከበራ የማህበረሰቡን ወይም የግለሰቦችን ሕይወት የጠቀመበትን የተለያየ መንገድ መፈተሽ ላይ በማተኮር ከባህል፣ ከፖለቲካ፣ ከማህበራዊና ከስነ-ልቦና አኳያ ያሉትን ፋይዳዎች ተተንትነው ቀርበዋል።

ከዚህ በተጨማሪ እንደ አጋዥ ማስተንተኛ በመሆን ክልላዊ ንድፈ-ሀሳብም በስራ ላይ ውሏል።

### 2.1.5. ክልላዊ (hemispheric) ንድፈ-ሀሳብ

ክልላዊ ንድፈ-ሀሳብ እንደሚያመለክተው አንድ ማህበረሰብ ከሰፈረበት ቦታ ሲንቀሳቀስ ወይም ሌላው ሲመጣበት በሚከሰቱ መስተጋብሮች የተነሳ ቀድሞ የነበረው የማህበረሰቡ ዕውቀት በሌላው አካል ለውጥ ሊካሄድበት ይችላል፡፡ ንድፈ ሀሳቡ በለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚዳቀሉ፣ የሚዋዋጡ፣ የሚዘነጉ፣ የሚጠፉ፣ አሊያም ያን ተፅዕኖ ተቋቁመውና አንሰራርቶ ሊቀጥል የሚችሉ የማህበረሰብ ባህሎችን የሚመለከት ነው፡፡ ታሪካዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ነባር ልማዶችን ለመለወጥ አቅሙ ስላላቸው እነዚህ ጉዳዮች በፎክሎርስቱ ሊጤኑ ይገባል፡፡ ስለዚህ እንደ አጥኚው በመስተጋብሮች የተነሳ የሚፈጠሩትን ለውጦች ለመመርመር መላመድ (adaptation)፣ ማስማማት (accomodation)፣ ማጣመር (syncroticism)፣ መጥፋት/መረሳት (disappearanc)፣ ትዝታዊ (recession)፣ ማዋሃድ/መቀየር (acculturation)፣ መቋቋም (retention) እና ማንሰራራት (revitalization) እንደ መመዘኛ ተጠቅሞ መመርመር እንዳለበት Dorson, (1972:44) ያስረዳል፡፡ እነዚህን መስፈርቶች እያንዳንዳቸው ካላቸው ቀረቤታ በመነሳት በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም፡- መላመድ፣ ማስማማት እና ማጣመር ባንድ ወገን፣ ቀጥሎ መረሳት፣ ትዝታዊ እና መቀየር እንዲሁም መቋቋም እና ማንሰራራት ደግሞ በሌላኛው ክፍል በማስቀመጥ መመልከት ይቻላል ጥላሁን (2007) ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

#### i.መላመድ፣ ማስማማትና ማጣመር

የተለያዩ ማህበረሰብ በታሪካዊና አካባቢያዊ ግንኙነት የተነሳ ሁለትም ሆነ ከዚያ በላይ የማህበረሰብ እውቀቶች እርስ በርስ መላመድ ጀምረው በሂደት እየተስማሙ፣ ተጣምረው እስከ መከወን ደረጃ ያለውን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

#### ii.መርሣት፣ ትዝታዊ እና መቀየር

በተለያዩ ማህበረሰብ መካከል በሚካሄድ መስተጋብር ውስጥ በሚፈጠሩ አጋጣሚዎች፤ በተግባር ይፈፀሙ የነበሩ ነገሮች እየደበዘዙ፣ በትዝታ (Memory culture) እየሆኑ፣ እየተረሱ፣ በስተመጨረሻም ነባሩ እውቀትና ልማድ በሌላኛው እየተተካ፣ አዲሱ ደግሞ በነባሩ ላይ ገኖ በመውጣት በሂደት የማህበረሰቡን እውቀት መተካቱን የሚመለከት ነው፡፡

iii.መቋቋምና ማንሰራራት

ይህ ደግሞ የአንድ ማህበረሰብ ባህል በአዲሱ ሳይገፋ በማህበረሰቡ ጥንካሬና በሌሎች አጋጣሚዎች ተቋቁሞ መቆየትና በሌላ መልኩ ደግሞ በጊዜ ሂደት ውስጥ በነባሩ ላይ በመመስረት በተለያዩ መልኮች በማንሰራራት ወደ ተግባራዊ ክዋኔ ለመመለስ የሚያደርገውን ሂደት ይመለከታሉ፡፡

በአጭሩ የክልላዊ ንድፈ-ሀሳብ ዋና ትኩረት እያንዳንዱ ማህበረሰብ ፎክሎራዊ ሀብቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት እንደሚያስተላልፍ፣ እንዴት ጠብቆ እንደሚያቆያቸው እና መልሶ ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንደሚያውላቸውም የሚታይበት ሲሆን፤ አዳዲሶቹን ደግሞ እንዴት ተለማምዷቸው የራሱ እንደሚያደርጋቸው የሚመለከት ንድፈ-ሀሳብ ነው Dorson, (1972:44)፡፡ለዚህ እንደማሳያ የሚያገለግለው በ Turner (1967:2) ስራ ውስጥ የአውሮፓውያን መስፋፋት ጋር ተያይዞ አፍሪካን በቅኝ ግዛት በመያዝ በነባሩ ባህልና ሃይማኖት ላይ ለውጦች እንደተከሰቱ ይገልጻል፡፡ ለምሳሌ የዛምቢያ ማህበረሰብ ነባር ሃይማኖታዊ ተቋማትና ከበራዎቹ በውጫዊ ሃይማኖት መዋጡን የዚህ ዓይነት ተፅዕኖ ውጤት እንደሆነ ይገልጻል፡፡

በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ ልክ እንደሌሎቹ ባህላዊና መንፈሳዊ ተቋማት በታሪካዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች አንዳንድ ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች ተከስተውበታል፡፡ በእነዚህም ምክንያት በተወሰነ ደረጃ የተፈጠሩ ለውጦች አሉ፡፡ በተለይም በገዳ ስልጣነ-ሢመት ላይ የነበረው ለውጥና ቀጣይነት በሀገራችን ከነበረው ታሪካዊ ጉዳዮች ማለትም፡- ካለፉት ሪዕዮተ-ዓለም የመንግስታት አገዛዝ ተፅዕኖዎች ጋር ያሳለፉትን ተግዳሮቶችና ውጤታቸውን በዚህ ንድፈ-ሀሳብ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ባጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ አግባብነት አላቸው የተባሉና በድጋፍ ሰጪነት ለማስተንተኛነት ይረዳሉ የተባሉ ንድፈ-ሀሳቦች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ይኸውም፡- በማህበረሰቡ ውስጥ የተቋቋሙት ሃይማኖታዊ ተቋማት፣ በውስጣቸው የሚከወኑ ተግባራት፣ የማከናወኛ ህጎቹና ደንቦቹ በዚሁ ማህበረሰብ የተዋቀሩ ዕውቀቶች መሆናቸውን በማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን (Social Constructio) ንድፈ-ሀሳብ የተተነተነ ሲሆን፣ በሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ውስጥ በተምሳሌታዊ አነጋገር፣ ክዋኔዎችና ቁሶች የመግባባቱንና የመከወኑን ፍች ደግሞ ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳብን በዋናነት በመተንተን ተገልጾዋል፡፡ በሌላ በኩል እንዳንዱ ሃይማኖታዊ ከበራዎች

የተተነተነ ሲሆን፣ ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ለማህበረሰቡ የነበራቸው ፋይዳዎች ደግሞ የተፈተሸበት በፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ነው። በመጨረሻም የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ አካላት በደረሰባቸው ተግዳሮቶች ምክንያት የደረሰባቸውን ለውጦችና ከእነዚያ ተፅዕኖዎች በመቋቋም የመቀጠልና የማንሰራራት ሂደቶችን በክልላዊ (hemispheric) ንድፈ-ሀሳብ አስፈላጊው ትንተናና ገለጻ ተደርጎበታል።

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ዙሪያ በተደረገው ቅድመ-ዳሰሳ ንባብ ወቅት ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለውን ጥናታዊ ስራ ለማግኘት አልቻልኩም። ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ተያያዥነት ያላቸውን፤ በተለይም በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች የተሰሩ ጥናታዊ ስራዎች ለማየት ችያለሁ። እነዚህን ስራዎች ካላቸው የይዘት ቀረቤታ በመነሳት በሁለት ተከፍለው ታይተዋል። ይኸውም:-የመጀመሪያዎቹ ቡድን ጥናታዊ ስራዎች የጉጂ ኦሮሞን ጨምሮ በሌሎች የኦሮሚያ አካባቢዎች በገዳ ስርዓት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው። ይኸውም በውስጣቸው ባነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችና ፅንሰ-ሀሳቦች የቃሉን ተግባራት በተወሰነ ደረጃ የዳሰሱ ናቸው። እነሱም:- (Hinnant, 1977,1981; Tedecha, 1988 & Al-Amin, 1998) ያካሄዱት ጥናቶች በጉጂ ኦሮሞ የገዳ ስርዓት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። እነ (Van de Loo, 1991; Zalaalam, 2000 & Asebe, 2007) ደግሞ በተለያየ ርዕሰ-ጉዳዮች ያጠነጠኑ ቢሆንም ስለጉጂ ቃሉ ተቋምና ተግባራት በስፋት የሚሉት አላቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ (Asmerom, 1973; Dejene, 2011; Dinsa, 1975; Israel, 2011; Emana, 2015 and Fille, 2015) እንዲሁም (ታቦር፣ 2006፣ አለማየሁና ሌሎች፣ 1998,1999, 2000) በቃሉ ተቋም ውስጥ የገዳ ስልጣነ ሢመትንና በግጭት አፈታት ዙሪያ ያለውን ሚና በዝርዝር አቅርበዋል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ስራዎች ከዋናው ጥናት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመረዳት ያስችል ዘንድ ከዚህ በታች በተወሰነ ደረጃ ከዋና ዋና ነጥቦች አኳያ ተያያዥነታቸውን ለመፈተሽ ተችሏል። ይኸውም:- አንዱ በ Hinnant, (1977)"The Gada System of the Guji of Southern Ethiopia" በሚል በቺካጎ ዩኒቨርሲቲ ለፒ.ኤች.ዲ ዲስርቴሽን የቀረበ ጥናት ነው። በውስጡም በስፋት ስለገዳ ስርዓት የሚያወሳ ቢሆንም፤ የቃሉና ገዳ ስርዓት አንዱ ለሌላው የሚጫወተውን ሚና ያስረዳል። ስለዚህ ስለጉጂ ቃሉና አባገዳዎች ግንኙነትና ተግባራቸው፣ ስለፈጣሪና ፍጡር ያለውን ሚት፣ በተለይም ስለዋቃና የዋቃ መንፈስ ምን እንደሚመስል በዝርዝር ተመልክቷል።

እነዚህ ሀሳቦች በአዲሱ ጥናት ውስጥም ስለሚነሱ በተወሰነ ደረጃ ለዚህ ጥናት ያለውን ጠቀሜታ ያሳያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ (Hinnant, 1981) "Guji Affinity & Case of A Conflictful Marriage." በሚል ርዕስ በማንችስተር ዩኒቨርሲቲ በ ‹Oromo kinship & Marriage› ኮንፍረንስ ላይ ባቀረበው ስራው ውስጥ ስለ ጉጂ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በስፋት አንስቷል፡፡ በጥናቱ ውስጥ በተለይም ስለቃሉ ሃይማኖታዊ መሪነትና አመጣጡን በዝርዝር የገለጸ ሲሆን በተጨማሪም፡- ከገዳ ስልጣን ሢመት ጋር ያለው ሂደትም ተገልጿል፡፡ ከዚህ ሀሳብ በአዲሱ ጥናት ውስጥ የተጠቀምኳቸው አሉ፡፡ ነገር ግን ከእኔ ጥናት የሚለየው ከቃሉ ከበራዎች ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ሰለገዳ ስልጣን ሢመት ከበራ ብቻ በማንሳቱ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልክ Tedecha, (1988) "The Politico-Legal System of the Guji Oromo." በሚል ርዕስ፤ በአ.አ.ዩ. ለህግ ት/ት ክፍል የቀረበ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የቃሉ ተቋምና በገዳ ስርዓት ውስጥ የገዳ መደቦች ክፍፍልና የሰራ ድርሻ፣ የገዳ የስራ አመራሩ ፓርላመንታዊ ይዘት ምን እንደሚመስል፣ የጉሚ ቦኮ ህገ-ጉባኤውና በስርዓቱ ያለውን የማህበረ-ፖለቲካ ለውጥን ጭምር የተነተነ ነው፡፡ ነገር ግን ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ በተናጥልና በጥልቀት ከቀረበበት አውድ አኳያ አላነሳም፡፡ ስለዚህ አዲሱ ጥናት ይህንን ክፍተት በምክንያት፣ በቦታ፣ በጊዜና ሂደቱንም ጭምር የዳሰሰ በመሆኑ እነዚህ የተፈጠሩ ክፍተቶችን የመሙላት ስራ ስለሚታይበት ለየት ያደርገዋል፡፡

የ Al-Amin, (1998) "Gada System: Nature, Operations and Constraints, with the Reference of the Experience of Guji Oromo." በሚል ለፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል፣ የቀረበ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ ይህ ሥራ በይበልጥ ስለገዳ ስርዓት ተፈጥሮ፣ ተግባራቱና በመጨረሻም ውስንነቱ ምን ምን እንደነበሩ የሚያትት ነው፡፡ ይኸውም በጉጂ ኦሮሞ የገዳ ስርዓት፣ የማህበረሰቡን ፖለቲካና የአፈጻጸም ስርዓቱን መመርመርና በጉጂ አካባቢ ቀድሞ የነበረውን የማስፈጸም አቅም እንዲያጣ፣ እየተዳከመ እንዲሄድ ያደረጉትን ተግዳሮቶች ለይቶ ማውጣት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጋር በማያያዝ ከቃሉ ሃይማኖታዊ ተግባራት ውስጥ ለገዳ ስልጣነ-ሢመት ወሳኝ እንደሆነ ለማስረዳት ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ስለሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ያለው ነገር የለም፡፡

ሌላዉ በ Asmerom, (1973) እና Dinsa, (1975) የተሰሩ ጥናቶች ሲሆኑ፤ የሁለቱም ጥናቶች ባብዛኛው በገዳ ስርዓት ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለትካዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ላይ ያተኮሩ ናቸው። የAsmerom'ን የተመለከትን እንደሆነ "Gada: Three Approaches to The Study of African Society." በሚል ለሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ለፒ.ኤች.ዲ ዲሰርቴሽን የቀረበ ነው። በጥናቱም ስለ ቦረና ገዳ ስርዓት፣ የገዳ ደረጃዎች፣ የገዳ ስልጣን ዑደትና የሚከናወኑትን የገዳ ክበራዎች በጥልቀት ያተተ ሲሆን፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለቦረና ቃሉና የቃሉ ተቋም በገዳ ስርዓት ውስጥ ያለውን ሚና ይገልጻል። ይኸውም፡- የቃሉንና የገዳ ስርዓት እርስ በርስ የሚደጋገፉ እንደሆኑ ለማስረዳት ችሏል።

ሌላው እሱ ባጠናበት ወቅት በገዳ የስልጣን ሽግግር ማለትም የሙዳ ስርዓት በየስንምት ዓመት አንዴ የሚካሄደው ታላቅ ክበራ በደቡባዊ የኦሮሞ አካባቢ፤ ማለትም በአርሲ፣ በባሌና በቦረና አካባቢዎች በሚካሄድበት ወቅት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች ለመንፈሳዊ ጉዞ ከሰሜን እንደ ወሎ፣ ከምዕራብ ደግሞ ከወለጋና ጂማ ድረስ በመምጣት ይሳተፉ እንደነበር ያወሳል፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች እየተዳከመ እንደሄደና እስካሁን ይህ ስርዓት ተጠብቆ ያለው በጉጂና በቦረና አካባቢ እንደሆነ ገልጿል። ከዚህ ጋር በማያያዝ በወሎና በሜጫ ኦሮሞ እየተከወነ ያለው የቃሉ ተግባር ከእነዚህ በተለየ መልኩ እንደሆነም ይገልጻል። ነገር ግን በአንዳንድ ሁነቶች ላይ የተመለከትን እንደሆነ በጉጂና በቦረና ቃሉ መካከል የተወሰኑ ልዩነቶች ይታያሉ። ይኸውም ለምሳሌ ያህል በጉጂና በቦረና ኦሮሞ የቃሉ የጫቁላ ስርዓቱ፣ ቃሉ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የስልጣን መተካት ክበራው፣ እንዲሁም በቁጥር የጉጂ ቃሉ አንድ ሲሆን የቦረና ደግሞ ሁለት መሆናቸውና በመሳሰሉት ሂደቶች ላይ ሰፊ ልዩነቶች አሉ። ይሁን እንጂ በተዘዋዋሪ መንገድ በአብዛኛው የመቀራረብ ሁኔታዎች ይታያል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ጥናት በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ክበራዎች ላይ በጥልቀት በመመርመር ትንተና ያደረገ በመሆኑ ከእሱ ጥናት ለየት ያደርገዋል።

በ Dinsa, (1975) "The Gada System of Government" በሚል ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሕግ ትምህርት ክፍል የቀረበ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ ሌላኛው ተቀራራቢ ስራ ነው።ጥናቱም በዋናነት የሚያተኩረው በገዳ ስርዓት ስልጣንና የስልጣን ሂደቱንና ባህሪያቱን በጥልቀት የሚያስረዳ ሲሆን፤ በውስጡ ስለቃሉ አመጣጥ፣ የቃሉ ስልጣን በትውልድ የሚተላለፍ መሆኑንና ወደ ስልጣን የሚመጣ ቃሉ ምን ምን መስፈርቶችን ማሟላት እንዳለበት፣ በኦሮሞ ጉባኤ (ጫፌ) ውስጥ የቃሉን ቦታ በሚገባ ያሳየ ነው። ስለዚህ እነዚህ

ንዑስ ርዕሶች የተወሰኑት በአዲሱ ጥናት ውስጥም በተለያየ መልክ ተዳሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ በእሱ ጥናት ውስጥ ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በተናጥል፣ በጥልቀትና ከቀረቡበት አውድ አኳያ አልተነሳም፡፡ ስለዚህ አዲሱ ጥናት ይህንን ክፍተት የመሙላት ስራ ያካተተ ነው፡፡

ሌላው በ Van de Loo, (1991) «Guji Oromo Culture in Southern Ethiopia. Religious Capabilities in Rituals & Songs.» በሚል ጥናቱ ውስጥ ከበራዎችና መዝሙሮች ሃይማኖትን የመግለጽ ኃይላቸውን በገዳ ስርዓትና በስርዓቱ ወቅት የሚዜሙ ዜማዎችን ጥበብ በመተንተን ያሳየ ሲሆን፣ በከበራዎቹና መዝሙሮቹ ከዝምድና፣ ከጋብቻ፣ ከልደት፣ ከቀብርና የመሳሰሉት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ እንደሚንጸባረቅ ያሳየ ነው፡፡ ይኸውም፡- ከህዝቡ አሰፋፈር፣ ከከብት እርባታ፣ ከመጠጥ አዘገጃጀት፣ ከእህል ማምረት፣ ምግብ አዘገጃጀትና ከመሳሰሉት ጋር ያለውን ግንኙነት እንደሚያሳዩ በሰፊው ገልጿል፡፡ በተለይም ስለገዳ የስልጣን ሽግግርና መንፈሳዊ ጉዞውን በስፋትና በጥልቀት ያሳየ ነበር፡፡ ስለዚህ ይህ ስራ ከአዲሱ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ የሚጋሩት ነጥቦች አሉት፡፡ ይሁን እንጂ የቃሉን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ከሚከወኑበት አውድ አኳያ በጥልቀት ያልተዳሰሰ በመሆኑ እነዚህን ክፍተቶች በአዲሱ ጥናት የሚሞሉ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ከዚህ በተጨሪማሪበ Zalaalam, (2000) የቀረበው ጥናት ደግሞ ‹‹Sirna Gaa'laafi Moggaasa Qaalluu Oromoo Gujii.›› በሚል ለአፋን ኦሮሞ ቋንቋና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ፣ በአ.አ.ዩ. የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱም በዋናነት ስለቃሉ ስልጣን አሰያየምና የጋብቻ ከበራው ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በማያያዝም ሰለቃሉ ተቋም አመጣጥ፣ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች መኖራቸውን፣ የተወሰኑት ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለግንዛቤ ማስጨበጫ ያህል ሳይተነተኑ ተገልጸዋል፡፡ አዲሱ ጥናት ግን ዓላማ ያደረገው እነዚህን ጽንሰ-ሀሳቦች በቃሉ ስርዓት ውስጥ መኖራቸውን ከመጠቆም ባለፈ በየከበራዎች ውስጥ የሚታዩትን ሁሉ የዳሰሰ ነው፡፡ ይኸውም፡-የማህበረሰቡ ዕውቀት የሆኑትን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ክዋኔ፣ ከዋኙ፣ መከወኛው ቁሳቁስ፣ በአውዱ የሚታዩ ትዕምርቶችና የእነሱን ትርጉም፣ የክዋኔው ማህበራዊ ደንቦችን ጭምር በመመርመር ለማህበረሰቡ ያለውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ ተንትኖ ያቀረበ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሌላውበ Asebe, (2007) “Ethnicity & Ethnic Relation; The Ethiopian Experiment and The Case of Guji and Gedeo.” የሚለው ጥናት በብሔር ብሔረሰቦች ላይ የተመሰረተ

አከላለልና የብሔረሰቦች እርስ በርስ ግንኙነት፡ ኢትዮጵያ ከተገበረችው አዲስ የአገር አወቃቀር ሀሳብ፤ ከጉጂና ጌዴኦ ብሔረሰቦች አኳያ ለሀገር በቀል ዕውቀት ፍልስፍና ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ፣ በቶርምሶ ዩኒቨርሲቲ የተደረገ ጥናት ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በብሔር ብሔረሰቦች መካከል በሚፈጠረው ግንኙነት የመንግስት ጣልቃ ገብነት ያለውን ተፅዕኖ በጉጂና ጌዴኦ ግጭት ማሳያነት ያቀረበውና የጎንዶሮ ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓትን ያሳየ ነው። በጥናቱ ውስጥ የቃሉ ተቋም በዚህ የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ ግጭትን ለማስወገድ ያለውን ሚና ገልጿል። ይህ ስራ ከአዲሱ ጥናት የሚለየው፤ ከቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ አንዱን ብቻ የተመለከተ ሲሆን፤ አዲሱ ጥናት ግን ሌሎችንም የጎንዶሮ ዓይነቶችና የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ያካተተ መሆኑና የእያንዳንዱን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ፋይዳዎችን ጭምር የዳሰሰ በመሆኑ ነው።

Emana, (2015) ‹‹Historical Documentation and Thematic Analysis of Waqeffannaa Religion and Song Among Tuulamaa Oromo.›› በሚል በአ.አ.ዩ. ለስነ-ልሳንና ፊሎሎጂ ትምህርት ክፍል ለፒ.ኤች.ዲ. ዲሰርቴሽን የቀረበ ጥናት ነው። የጥናቱ ትኩረት "በቱለማ ኦሮሞ የዋቄፈና እምነት ክብረ-በዓላት ልማዳዊ ድርጊቶችና መዝሙሮች ታሪካዊ አመለካከት" ከፎክሎር አኳያ የሚመለከት ሲሆን ጥናቱ ኢትኖግራፊክ የሆነ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው። ከዋቄፈና ጋር ተያይዞ በተከበሩ እሬቻ፣ ጉማ ሥርዓት፣ ቃሉ ሥርዓት፣ አቴቴ እና ወዳጃ ክብረ-በዓላት ላይ በመገኘት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሥነቃል ዓይነቶች ከነተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው ጋር ተሰብስበው ተተንትነዋል። የዋቄፈና እምነት ልማዳዊ ድርጊቶችና መዝሙሮች በቱለማ ኦሮሞና ሌሎችም የኦሮሞ ጎሳዎች የየዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ሠላምና ደህንነትን አስተማማኝ በማድረግ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን በማጠናከር፣ አንድነትንና የጋራ መግባባትን በመፍጠር እንዲሁም ተከባብረውና ተቻችለው መኖርን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። ከእኔ ጥናት ጋር የጉማው ስርዓት በከፊል ከጎንዶሮ ከበራ ጋር ከመመሳሰሉ በቀር ሌሎቹን በእሱ ጥናት ውስጥ ተነስተው በእኔ ውስጥ የሌሉ እንደአቴቴ፣ እሬቻ እና ወዳጃ ክብረ-በዓላት ሲኖሩ፤ የቃሉ ሥርዓትም ቢሆን በክዋኔውም ሆነ በምግባሩ ከጉጂ ቃሉ ጋር የማይገናኝ ነው። እንዲሁም በእኔ ጥናት ውስጥ የተነሱት የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች አብዛኛዎቹ በእሱ ውስጥ አልተነሱም። ይህ እንዳለ ሆኖ ሌላው ይህ አዲሱ ጥናት ከኢማና ለየት የሚያደርገው ዋንኛው ምክንያት ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች የማህበረሰቡን ዕውቀት በማሕበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ

መተንተኑና በከበራዎቹ ይደረግ የነበረው ተግባቦት ማለትም፡- በቋንቋው፣ በክዋኔውና በመከወኛ ቁሶቹ ተምሳሌታዊነቱን ያሳየና ትርጉሙን/ፍች የሰጠ በመሆኑ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Fille, (2015) ‹‹Documentation of Folk Law & Description of Grammatical sketch of the Macca Oromo.›› በሚል ርዕስ በአ.አ.ዩ. ለስነ-ልሳንና ፊሎሎጂ ትምህርት ክፍል ለፒ.ኤች.ዲ ዲሰርቴሽን የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት በሜጫ ኦሮሞ ከሚገኙት ውስጥ ከምዕራብ ሸዋ በኩታዬ ሊበንና ከምስራቅ ወለጋ ደግሞ ሊሙ ጃዊ ጎሳ ውስጥ ሀገረሰባዊ ህግ ከማውጣትና ህጉንም በማስፈጸም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በጥናቱም ውስጥ የሀገረሰባዊ ህግ አወጣጥና አተገባበር ሂደትና የህጋዊ ተምሳሌቶች (legal symbol) አጠቃቀምን የመሰነድ ነው:: የጥናቱ ዓላማ የሜጫ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ህጎችን መሰነድና ሰዋስዋዊ ንድፉን መግለጽ ነው፡፡ የፊሌ ጥናት ከእኔ ጋር የሚያዛምደው በሀገረሰባዊ ህግ (folk Law) በኩል ሲሆን ባህላዊ የግጭት አፈታትና ዘዴዎቹ በሚለው ንዑስ-ርዕስ ስር ሽማግሌዎች፣ ሻኔ (shanee) እና የቃሉ ተቋም በማለት ይዘረዝራቸዋል፡፡ ነገር ግን በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሰው የቃሉ ተቋም ከላይ ከተጠቀሰው የኢማና ስራ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ከእኔ ጥናት ጋር በአውድም ሆነ በተግባሩ አለመገናኘቱ ለየት ያደርገዋል፡፡

ሌላው በባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ ከሚለው ስብስብ ጥናታዊ ስራዎች ውስጥ በ Dejenee, (2011) «The Customary Courts of the Waliso Oromo.» የሚለው ጥናት አንዱ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የቃሉ ተቋም ከገዳ ስርዓት በተጓዳኝ የሚገኝ ሃይማኖታዊ ተቋም እንደሆነና የቃሉ ችሎት ከግጭት መፍቻ ስርዓቶች መዋቅር ውስጥ አንዱ መሆኑን ያስረዳል፡፡ የቃሉ ተቋም የገዳ ስልጣንን ከማጽደቅ ባሻገር የተለያዩ የግጭት ዓይነቶችንና የተለያዩ ማህበረ-ፖለቲካዊ ችግሮችን የመፍታት ሚና እንዳለው ለማሳየት ችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው የቃሉ ተቋም ግን ከገዳ ስርዓት ጋር ተያያዥነት እንደሌለውም አመልክቷል፡፡ ስለዚህ አዲሱ ጥናት ከዚህ የሚለየው በመጀመሪያ ደረጃ በጥናቱ የተዳሰሰው የቃሉ ተቋም ከገዳ ስርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና እርስ በርስም ያላቸውን ተደጋግፎ በግልፅ ያሳየ መሆኑ ላይ ነው፡፡ ይኸውም፡- በቃሉ ተቋም ግጭቶችን ከመፍታት ባሻገር ያሉትን የገዳ ስልጣነ ሢመት ማጽደቅ ጨምሮ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ያካተተ በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው በ Israel, (2011) «The Quest for the Survival of Gada System's Role in Conflict Resolution.» በባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ ከሚለው ስብስብ

ውስጥ ሌላኛው ጥናታዊ ስራ ነው። በጥናቱም የገዳ ስርዓት ግጭቶችን በመፍታትና ሰላምን በማስፈን በኩል ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን አሳይቷል። ጥናቱ በገዳ ስርዓት የነበሩትን ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁመው በአሁን ወቅት በስራ ላይ ባሉት የቦረና፣ የጉጂና ምዕራባዊ አርሲ ዞኖች ላይ እንደሆነ ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ የግጭት መፍቻ ስርዓት መዋቅሮቹን፣ የግጭት አፈታት ሂደቶቹንና በሂደቶቹ ውስጥ የነበሩ ተግዳሮቶችን በሚገባ ገልጿል። ይህ ጥናት ከአዲሱ የሚለየው ልክ ከላይ እንደተገለጸው ጥናት ትኩረቱ በግጭት አፈታቱ ሂደት ላይ ብቻ በመሆኑ ነው። አዲሱ ጥናት ግን የግጭት አፈታቱን ከመግለጽ ባሻገር ከበራውንም የመተንተንና የመግለጽ ሂደቶች ተከናውነዋል። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችንም ያካተተ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የእነ (Knutsson, 1967; Lewis, 1970; Bartels, 1983; እና Meseret, 1995) ለማየት እንደተሞከረው ጥናታቸውን ያካሄዱት በቃሉ ተቋም ላይ ነው። በጥናታቸው ውስጥ የቀረቡት ሃይማኖታዊ አውዶች፣ የሃይማኖቱ መሪዎቹና ተግባራቸው፣ እንዲሁም በተቋማቱ ውስጥ የሚከወኑት ከበራዎች ጭምር ከአዲሱ ጥናት ጋር ያለመመሳሰል ይታይባቸዋል።

ይኸውም፡- የ Bartels, (1983) «Oromo Religion Myths and Rites of the Western Oromo of Ethiopia.» የሚለውን ያየን እንደሆነ፤ በኦሮሞ ሃይማኖታዊ ሚቶችና ከበራዎቹ በሚል ዙሪያ ያካሄደው ጥናት ሲሆን፤ በጥናቱም ስለ ኦሮሞ ሃይማኖትና ከበራ ያሉትን ሚቶችና የመንፈሳዊ ጉዞ ከበራው ጠቀሜታ በሰፊው አስረድቷል። በሌላ በኩል የሃይማኖታዊ ተምሳሌቶችንም ጥቅም ለመግለጽ ችሏል። ይሁን እንጂ ስለቃሉ ተግባራት በሚገልጽበት ወቅት የቃሉና የቃሊቻ ተግባራት የሚመስሉ ተቀላቅለው የመታየት ሁኔታዎች አሉ። ይህ ሀሳብ ደግሞ ከአዲሱ የጥናት ትኩረት በተወሰነ ደረጃ የተለየ ያደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ከእሱ የጥናት ወቅት አንጻር የነበሩትን ለውጦችና አሁን ያለበትን ሁኔታም ያካተተ በመሆነ የተለየ ያደርገዋል።

በ Knutsson, (1967) «Authoity and Change: The Study of the Kalu Institution.» በሚል የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን፤ በውስጡ ስለቃሉ ጥንተ-አመጣጥ፣ ስለተቋም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ሚናና ውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ በተወሳሰበ መንገድና በዓላትን በማማከል እንዴት አገልግሎት እንደሚሰጥ በሰፊው ገልጿል።

ነገር ግን በተወሰነ ደረጃ ልክ እንደ Bartels ጥናታዊ ስራ የቃሉና የቃሊቻን ምግባር ባደባለቀ መልኩ የቀረበበት ሁኔታ አለ፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት በሜጫ ኦሮሞ ያለው ቃሉ ከገዳ ስርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው ነው (Dejenee, 2011፡254)፡፡ ነገር ግን በአዲሱ ጥናት የታቀፈው የጉጂ ቃሉ ግን ከገዳ ስርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና አሁንም እያገለገለ መሆኑ በጥናቱ መገለጹ ለየት ያደርገዋል፡፡

ሌላው Lewis, (1970) «Kud'arfan: A Multi-Functional Institution Among the Western Galla.» በማለት ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ ጥናቱ ስለቃሉ አመጣጥና ተግባር፣እንዲሁም ባለዘርፈ-ብዙ ፋይዳ ተቋም እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በውስጡ በአብዛኛው የተዘረዘሩት ልክ እንደቀደሙት ጥናቶች ሁሉ አብዛኛውን የቃሊቻን ተግባር የሚመስሉ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት አሁን ከቀረበው ጥናት አውድና ተግባራት ጋር የሰፋ ልዩነት አለው፡፡

በመጨረሻ Meseret, (1995) ‹‹Qaallu as a Dispute Setting Institution.›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሕግ ትምህርት ክፍል ያቀረበችው ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ለማየት ተችሏል፡፡ በጥናቷም ውስጥ ስለ ቃሉ በተለይም በግጭት አፈታት ስርዓት ያለውን ተግባር በጥልቀት ዳሳለች፡፡ ነገር ግን ልክ እንደላይኛዎቹ ጥናቶች፤ አዲሱ ጥናት የቀረበበት አውድና የቃሉ ተግባር ጋር ሰፊ ልዩነት አለው፡፡

በኦሮሞ ታሪክና በጥንቱ የገዳ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ «ቃሉ» (መንፈሳዊ መሪ) ከፍተኛ ታሪክና ትልቅ ስፍራ ያለው ነው፡፡ ዳሩ ግን ከ19ኛው መቶ ክ/ዘ  በኋላ በታዩት ለውጦች ምክንያት በሰሜን አካባቢ ባሉት የኦሮሞ ጎሳዎች ዘንድ ከገዳ ስርዓት ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንደተቋረጠ ምሁራኖች ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው «ቃሉ» ከገዳ አስተዳደር ስርዓት ጋር የተያያዘ ኃላፊነት ያላቸው አለመሆናቸውን አለማየሁና ሌሎች (2000፡108) በስፋት ገልጸዋል፡፡

ባጠቃላይ የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ በእነ (Knutsson,1967; Lewis,1970; Bartels,1983; & Meseret 1995) እና ሌሎችም ጥናት ውስጥ እንደሚሉቱ "ቃሉ" በሚባለው የሃይማኖቱ መሪ ላይ የሚወርድበት ለየት ያለ መንፈስ ያለው ሳይሆን፤ እንደመረጃ አቀባዮቹ ገለጻና አጥኚው በምልከታ ወቅት እንደተገነዘበው የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበትና የተረጋጋ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏ፡፡ በሌላ በኩል እጣን እያጨሰ፣ ድቤ እየመታ፣ አፍንጫውን እየጎረጎረና እያጓራ ስለግለሰቦች ዕጣ-ፈንታ የሚገልጽ አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሳ የከበራውም ሆነ፣ የክዋኔው

አውድ ያለመመሳሰል ይታይባቸዋል። በተዘዋዋርም መንገድ ግንኙነት አላቸው ከሚባሉት ጥናቶች ውስጥ የተወሰኑት ጥናቱ ከተካሄደበት አካባቢ መመሳሰል፣ በገዳ ስርዓት ውስጥ አንዳንድ ሀሳቦችን በማንሳታቸውና በስርዓቱም ውስጥ የቃሉ ሚና ምን እንደሚመስል ከማሳየት ረገድ ቀረቤታቸው የጎላ ነው። ነገር ግን ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በተደራጀና በጥልቀት ያዩት ነገር እንደሌለ ለማየት ተችሏል። ሌላው ይህ ጥናታዊ ስራ በተበታተነ መልክ የተነሱትን ሀሳቦች በአንድ ላይ በማካተት፣ ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን በማከል፣ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ዙሪያ በማተኮርና ከተከወኑበት አውድ አኳያ ተንትኖ በመግለጽ፣ የቃሉን ተቋም ለውጥና ቀጣይነት ምን እንደሚመስልና በመጨረሻም የተጠቀሱት የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱትን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎች የገለጸ ነው። ስለዚህ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱ ክፍተቶች መሙላቱና እራሱን ችሎ በቃሉ ተቋሙ የሚከናወኑ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በአንድ አካቶ በጥልቀት ማየቱ ከሌሎቹ የተለየ ያደርገዋል።

ሌላው ስለቃሉ ታሪካዊ አመጣጥና ከጉጂ ቃሉ ጋር ተቀራራቢ ፅንሰ-ሀሳቦችን በዝርዝር የያዘ በ አለማየሁና ሌሎች፣ (1999) የገዳ ስርዓት፡ የቱላማ ኦሮሞ ፖለቲካ በሚል የቀረበ ስራ ነው። ጽሑፉ በአብዛኛው ስለቱለማ የገዳ ስርዓትና ያለፈባቸውን በርካታ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ውጣ ውረዶችን የሚያስጨብጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የገዳ ስርዓቱ አሁን ያለበት ደረጃ የሚገልጽ ቢሆንም የተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎችንም ለመዳሰስ የሞከረ ነው። በጽሁፉ ውስጥ በኦሮሞ የገዳና የቃሉ ስርዓቶች የማይነጣጠሉ እንደሆኑ፣ ስለቃሉ አመጣጥና ትክክለኛው ቃሉ የቱ እንደሆነ፣ በተለይም ከ19ኛው ክ/ዘ በኋላ ወደሰሜኑ የኦሮሞ አካባቢ ያሉት የቃሉ ስርዓት ከገዳ ስርዓት ጋር ተያያዥነት እንደሌላቸው በምክንያት አስደግፎ አመልክቷል። በተቃራኒውም የቦረናና ጉጂ ቃሉዎች የመጀመሪያው የቃሉ አካል፡- ማለትም ከማዳ ወላቡ የነበረው ዝርያ የመጡ እንደሆኑ ያስረዳል።

ከዚህ በተጨማሪ ስለቃሉ ምንነትና ከየት ተነስቶ ወዴት እንዳመራና በምን ተፅዕኖ ከቀድሞ ቦታ እንደተሰደደ፣ በተለይም በየስምንት ዓመቱ በሚካሄደው የገዳ ስልጣን ማጽደቅያ ወቅት የሚካሄደውን ስርዓትና በከበራው ወቅት የሚቀርቡትን ቁሳዊ ባህሎች በመጥቀስ የያዙትንም ፍች ለማስረዳት ሞክሯል። እነዚህ ሀሳቦች በአብዛኛው በአዲሱ ጥናት ውስጥም የሚነሱ በመሆኑ ለእኔ ጥናት በተወሰነ ደረጃ እንደመረጃ ምንጭነት አገልግሏል። ይሁን እንጂ በጽሁፉ ውስጥ ከቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ የገዳ ስልጣን ሽግግር ወቅት የሚካሄደውን ስርዓት

በሰፊው ቢገለጽም፤ የስርዓቱን ክዋኔና አውዳዊ ትንተና ያልተደረገበት ነው። በሌላ በኩል ለሎችንም ሃይማኖታዊ ክበራዎች አለማካተቱ፣ ቁሳዊ ባህሎቹንና ተምሳሌትነታቸው ጭምር በጥልቀት አለመመልከቱ የተለየ ያደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ስለቃሉ የአገልግሎት ዘመን እስከ ዕለተ-ሞቱ ድረስ እንደሆነ በመግለጽ፤ ከዕልፈተ ሕይወቱ በኋላ የቃሉ ባለቤት ተተክታ «ቃሊት» ተብላ ተቋሙን እንደምታስተዳድር ገልጿል። አንዳንድ ቦታ ደግሞ የቃሉ የመጀመሪያ ልጅ በቦታው እንደሚተካም ያስረዳል። በአዲሱ ጥናት ውስጥ የቀረበው ቃሉ ግን ከዚህ የተለየ አካሄድ ያለውና ከቃሉ አመጣጥ ሚት ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ለየት ያደርገዋል።

በመጨረሻም በታቦር (2006) «የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች» በሚል የቀረበ መጽሐፍ ለመዳሰስ ተሞክሯል። በጽሑፉ ውስጥ የኦሮሞ እውነተኛ ታሪክ የቱ እንደሆነና የውገና ድርሰት በማለት በተለያዩ በሀገር ውስጥና በውጭ ፀሐፍቶች የቀረቡ፡- ስለኦሮሞ ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነት፣ ከየት-መጣነቱንና የመሳሰሉትን በመረጃ በማስደገፍ ያለውን እውነታ በሰፊው አትቷል። ከዚህ በተጨማሪ ስለዋቄፋና ከቀደምት ሃይማኖቶች አንዱ እንደሆነ፤ የሃይማኖቱ መሪ ደግሞ ቃሉ እንደሚባል፤ የቃሉ የስራ ድርሻና የማያከናውናቸውን ተግባራት ጭምር በግልጽ አሳይቷል። ነገር ግን ስለቃሉ ወይም «ቃሊቲ» ጽንስ ሀሳብ ሲገልጽ «ቃሊቲ» (የሃይማኖቱ መሪ) ሆና ከዘርዋ በተዋረድ ባገኘችው የቃሉን ተቋም እስከ ዕድሜ ልኳዋ ድረስ መምራት እንደምትችል ይገልጻል። ይህ ጉዳይ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የተመለከትን እንደሆነ፡- «ቃሊቲ» የምትባል፤ እንደተባለው የቃሉን ተቋም የምትመራ አለመኖሯና ተግባሩንም የማትከውን ስለሆነች ከአዲሱ ርዕሰ-ጉዳይ ጋር ተመሳስሎ የለውም። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የኦሮሞ አካባቢዎች በተሰሩ ጥናታዊ ስራዎች ውስጥ የተመለከትን እንደሆነ ስለቃሉ እንጂ ስለ «ቃሊቲ» አመጣጥ የሚነገሩ ሚቶች ለማግኘት አልቻልኩም።

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች እንደ ዕውቀት ዘርፍ፤ እንደ ዕውቀት ምርት (production) የኦሮሞ ህዝብ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ይህንን ዕውቀት እንዴት እንደፈጠሩት የሚለውን ኢፒስቲሞሎጂያዊ የዕውቀት አረዳድ ስለሚመለከት፤ የተከተለው የአጠናን ዘዴ ማህበረሰቡ የማህበረ-ባህላዊ ሁኔታዎችን እንዴት አወቁት? የሚለውን ኢፒስቲሞሎጂያዊ የዕውቀት አረዳድ ከተለያዩ ማዕዘን የተመለከተ ሲሆን፤ ከቲዮሪያዊ አተያይ ደግሞ በዋናነት ተምሳሌታዊ አተረጓገም (Symbolic Interpretive) እና የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን (Social Construction) መሰረት ያደረገ ነው። ጥናቱ አብዛኛውን ተፈጥሯዊ አውድን ተንተርሶ መረጃዎችን በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ በቡድን ውይይትና በንጥል-ጥናት ዘዴዎች የተለያዩ የናሙና አመራረጦችን መሰረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ በመግባትና አብሮ በመቆየት የኢትኖግራፊያዊ ስነ-ዘዴን (methodology) በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል። በተፈጥሯዊ መቼት ያልተሳኩትን አርቴፊሻል መቼት በማዘጋጀት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተሞክሯል። ከዚህ በመቀጠል የማህበረሰቡ ዕውቀት ኦንቶሎጂያዊ ግምቶችን በዚህ ስር ተነስተዋል። ኦንቶሎጂያዊ ግምቶችን እነ Guba and Lincolin'ን በመጥቀስ Crotty ሲገልጽ፦ ‹በምናውቃቸው ነገሮች ዙሪያ ያለው እውነታ ምንድነው?› ወይም ‹የአኗኗር ዘይቤያቸው ተፈጥሯዊ ሁኔታ ምንድነው?› ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ እንደሆነ Crotty, (1998:2) ያስረዳል። ስለዚህ የማህበረሰቡ ዕውቀት እውነታ ምንድነው? ለምሳሌ፦ የትኛው ቃሉ እውነት ነው? ከማለት የተለያዩ እውነቶች /multiple truths/ ተፈጠሩ የሚለው ላይ ያተኩራል።

ስለማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያንና ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳቦች በ2.1. ስር ከሌሎች አጋዥ ቲዮሪዎች ጋር በስፋት ተዳሷል። ነገር ግን የተቀሩትን የአጠናን ዘዴ ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን።

### 3.1. የጥናቱ ዓይነት

ቀደም ሲል በሶሻል ሳይንስ የጥናት መስክ ባብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) የአጠናን ዘዴን በመምረጥ በተቃራኒዊ ወገን ደግሞ አሃዛዊ (quantitative) ዘዴ እንዳለ ይገመት ነበር። አሁን

ግን እንደ Crotty, (1998:14) ገለጻ  በዓይነታዊ እና አሃዛዊ የአጠናን ዘዴ መካከል ያለው ልዩነት በዘዴዎች (methods) ደረጃ ብቻ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ልዩነቱ በኢፒስቲሞሎጂው ወይም በቲዮሪያዊ አተያዩ ደረጃ ላይ አይታይም፡፡

ኢፒስቲሞሎጂ የዕውቀት ንድፈ-ሀሳብ ሲሆን ስለአንድ ነገር ወይም ሁነት ያወቅነው ፍች እንዴት እንዳወቅነው የሚገልጽ ነው፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉት ዕውቀቶች እንዴት ተረዱት ለሚለው በስሩ ሦስት ዓይነት መንገዶችን ያነሳል፡፡ እነሱም፡- ኦብጀክቲቭዚም፣ የዕውቀት አዋቃሪያንና ሳብጀክቲቭዚም ናቸው፡፡ ስለዚህ ኦብጀክቲቭዚም/ፖዘቲቭዚም ጥናት በአንድ በኩል ልክ እንደ አሃዛዊ የአጠናን ዘዴ፣ የዕውቀት አዋቃሪያን/ ሳብጀክቲቭዚምን ደግሞ በሌላ ወገን እንደ ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴ አድርጎ፤ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ማየት እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ሁለቱ የሚለያዩበት ዕውቀት ምንድነው? እንዴትስ ይመረታል? በሚለው ነው፡፡ ኦብጀክቲቭዚም እውነተ ማለት ነባራዊ እውነት፤ ልክ እንደ ነባራዊ ቁሶች የማይለወጥ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ የዕውቀት አዋቃሪያን ደግሞ ዕውቀት ወይም እውነት በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ስለሚመረቱ፤ ከሁኔታዎች መቀያየር ጋር አብሮ እንደሚቀያየር ይገልጻሉ (ዝኒ ከማሁ)፡፡

ከዚህ እሳቤ በመነሳት ይህ ጥናት በዋናነት የዕውቀት አዋቃሪያንና ሳብጀክቲቭስት ኢፒስቲሞሎጂን የተከተለ ነው፡፡ ምክንያቱም እውነት ወይም ፍች ከምንኖርበት ዓለም እውነታ ስናመጣው ከእኛ መደበኛ ስምምነት ውስጥ ወይም ውጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ፍችዎች (meaning) የነባራው ወይም የሁነቶች ግላው ባህሪያቸው አይደሉም፤ ውቅር ናቸው፡፡ ይህን አስመልክቶ Crotty ሲገልጽ፡-

> *There is not objective truth waiting for us to discover it. There is no meaning without mind. Meaning is not discovered, but constructed. In this understanding of knowledge, it is clear that different people may construct meaning in different way, even in relation to the same phenomenon* (ibdi).

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው እንደ ኦብጀክቲቭስት ኢፒስቲሞሎጂ ማለትም፡- የአንድ ነገር ፍች ፍጹም እውነት (absolute truth) እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ነገር ግን ከላይ ለማየት እንደተቻለው የዕውቀት አዋቃሪያን ኢፒስቲሞሎጂስት ደግሞ ይህን ሀሳብ በመቃረን ፍች ይህ ነው መሆን ያለበት ተብሎ የተቀመጠ ግኝት ሳይሆን የተዋቀረ ነው ይላሉ፡፡ ይኸውም፡- ያለ አእምሮ ፍች

(ትርጉም) ሊኖር እንደማይችልና ፍች አዲስ ግኝት ሳይሆን ውቅር (constructed) ነው። በዚህ የዕውቀት አረዳድ፤ በተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ፍችዎች፤ በተለያዩ መንገዶች ሊዋቀሩ ይችላሉ የሚል እሳቤ አላቸው። ሦስተኛው የኢፒስቲሞሎጂ መንገድ ደግሞ ሳብጀክቲቭዚም ሲሆን፤ ከመዋቅራዊያን፣ ከድህረ-መዋቅራዊያንና ከድህረ-ዘመናዊያን በመምራት የመጣ አስተሳሰብ ነው። በሌላ በኩል የዕውቀት አዋቃሪያን ፍችን ከነባራዊነት በመነሳት የሚዋቀር እንደሆነ ያነሱት አገላለጽ በነበረበት ወቅት የተፈጠረ አስተሳሰብ ነው።

በሌላ በኩል ስለኢፒስቲሞሎጂ ስናነሳ አይቀሬው ጉዳይ ኦንቶሎጂ ነው። ኦንቶሎጂ የስነ-ፍጥረት ጥናት ነው። የሚያጠነጥነውም ተፈጥሮ የያዘችውን እውነት ይዛ እንድትቆይ ያደረገው ምንድነው? ለሚለው ምላሽ የምንሻበት መንገድ እንደሆነ Crotty እንደሚከተለው ይገልጻል። "Ontology is the study of being. It is concerned with 'what is', with the nature of existence, with the structure of reality as such" (Crotty, 1998:10).

ቀደም ሲል ስለአንድ ነገር ወይም ሁነት ያወቅነው ፍች እንዴት እንዳወቅነው ከሦስቱም የኢፒስቲሞሎጂስት መንገዶች ለማየት ተሞክሯል። ባጠቃላይ ጥናቱ የተከተለው ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴ ነው።

ሌላው ደግሞ ነገሩ ወይም ሁነቱ ምንድነው? የሚለውን ደግሞ ከኦንቶሎጂያዊ አገላለጽ በመነሳት ያን የማህበረሰቡን ዕውቀት ምን ይሉታል። ለእነሱ ምንድነው የሚለውን የምናይበት መንገድ ነው።

ለአብነት ያህል ለዚህ ጥናት መረጃ ለማሰባሰብ የ2008 ዓ.ም. የገዳን ስልጣን ርክክብ ከበራ በጉጂ ዞን ሚኤ ቦኮ ቅዱስ ስፍራ የሚባለው ላይ ታድሜ ነበር። ከተለያዩ አካባቢዎችና የተለያየ ሃይማኖት ተከታዮችንም ለማነጋገር ሞክሬያለሁ። የመጀመሪያዎቹ በእነ ሀጂ መሀመድ ጅብሪል ከምስራቅ ሀረርጌ የመጡት ነበር። ይህን ከበራ ለእርሶ ምንድነው? እንዴት ተመለከታችሁት? የሚል ጥያቄ ሲያቀርብላቸው የእሳቸው መልስ «ይህ የቆዬ ባህላችን ነው። ነገር ግን ከወደ ሀረርጌ ካለው ስርዓት ጋር ከሞላ ጎደል የመመሳሰል ሂደቶች ይታያሉ። ስለእውነት ከተናገርን የጥንቱን ይዘት ይዞ ያለው ይህ የጉጂ ገዳ ነው» (ሀጂ መሀመድ ጅብሪል፣ በ8/6/2008)።

በተመሳሳይ መልክ ለአቶ አዱላ ዋታ፤ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የሆኑት ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡-

*እኛ እንደ ኦሮሞነታችን የጋራ የሆነ ባህል አለን፤ ያደግነውም በዚሁ ባህል ውስጥ ነው፡፡ አሁንም በውስጣችን አለ፡፡ በዚህ ምክንያት ከእነሱም ጋር እንገናኛለን፡፡ የገዳ ስርዓትማ ከጥንት ወላጆቻችን ያቆዩትና እኛም ለልጅ ልጃችን የምናስተላልፈው ባህላችን ነው፡፡ ነገር ግን ከእምነት አኳያ የምንለያይበት ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ያን ልዩነታችንን አውቀን ተከባብረን እየኖርን ነው፡፡ ሙሉ ለሙሉ ክርስቲያን ነህ ወይ? ብለህ ከጠየከኝ እንደእኔ መልሴ አይደለሁም እልሃለሁ፡፡ ምክንያቱም እኛ ቤተሰብ ውስጥ የሁለቱም ሃይማኖት ቅልቅል ነን፡፡ ለምሳሌ አባቴ ቤት ሲሄድ በጠዋት ቡና ሲቀርብ በዋቄፋና የጸሎት አካሄድ*

| | |
|---|---|
| *‹Ee waaqa dhugoo,* | *የዱጎ አምላክ፣* |
| *waaqa qaaluu,* | *የቃሉ አምላክ፣* |
| *waaqa gadaa,* | *የገዳ አምላክ፣* |
| *kan nagaan nu bulchite,* | *በሰላም ያሳደርከን፣* |
| *nagaan nu oolchi!* | *በሰላም አውለን፡፡* |
| *Kan qoonqootti kawwannu* | *የምንመገበውን ባርክልን!* |
| *nuu sifeessi!* | *በማለት ይለማመናል፤* |
| | *እኛም በምላሹ፡-* |
| *nagaan nu oolchi!* | *በሰላም አውለን፡፡* |
| *nuuf sifeessi* | *ባርክልን! እንላለን፡፡» የሚል* |

ነበር (አዱላ ዋታ፣ በ11/6/2008፣ ቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ)

በ12/6/2008 ዓ.ም. በስፍራው ሰብሰብ ያሉ ወጣቶች ደግሞ ስለገዳ ዴሞክራሲያዊ ሂደት እየተወያዩ፤ «ዴሞክራሲን መንግስት እራሱ ከገዳ ስርዓት መማር አለበት፡፡ እሱ ስልጣን ላይ እያለ የጉጂ ኦሮሞ ስንቴ ስልጣን አስረከበ፡፡» በማለት በማነጻጸር ሁኔታ ያወሩ ነበር፡፡ ሌሎች በአራተኛ ደረጃ ነባሩን ማህበረሰብ የሚወክሉ ወይም የባህሉን ማህበረሰብ ሊወክሉ ይችላሉ ያልኳቸውን አዛውንቶች ውስጥ ደግሞ ባሊ ጃርሶ እና ሞና ጎዳና በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን ከበራ እንዴት ተመለከታችሁት? የሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው፡፡ እነሱም ሲመልሱ «ለእኛ ይህ ከበራ ከእግዚአብሔር ጋር የምንታረቅበት ነው፡፡ የተጣላ የምታረቅበት ነው፡፡ በማህበረሰባችን ውስጥ ያለው የልጃገረድና ጎረምሳ ልጅ ጉዳይ ስርዓት የሚበጅለት ነው፡፡ ስለዚህ ገዳ ሁሉ ነገራችን ነው ማለቱ ይቀላል፡፡» (ባሊ ጃርሶ፣ 10/6/2008፣ የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ) በመቀጠል ሌላኛው «ይህ ከበራ በውስጡ ሁለት መልዕክት ያለው ነው፡፡ አንደኛው የቀድሞው ገዳ ቀደም ሲል ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ስልጣን የሚያስረክብበት (haaganaa kan galchuu) እና

አዲሱ ደግሞ በተራው ከእግዚአብሔር ስልጣን የሚረከብበት ሂደት ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ የቀድሞው ገዳ ስልጣኑን ለአዲሱ ገዳ የሚያስረክብበት ሂደት ናቸው። ታዲያ በአንድ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ወቅትም ነው፤ በሌላ በኩል ከተለያየ ቦታ ያለን የጉጂ ማህበረሰብ የምንገናኝበትና ስለጉዳዮቻችን የምንወያይበት ወቅት ነው። ስለዚህ ይህ ከበራ ለእኛ ሁሉ ነገራችን ነው።» (ሞና ጎዳና፣ 10/6/2008፣ የዋደራ ወረዳ ነዋሪ)

ከነዚህ መረጃ አቀባዮቼ የተረዳሁት ነገር በአንድነት የታደሙትን የገዳ ስልጣን ርክክብ ክዋኔ የመጀመሪያውና ሁለተኛዎቹ መረጃ አቀባዮች ከባህል እይታ ፍች ሲሰጡ፣ በመቀጠል መረጃ የሰጡት ደግሞ ከፖለቲካ አኳያ የገዳን ስርዓት ዴሞክራሲያዊነትን ከኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት ጋር በማነፃፀር የገለጹበት ሁኔታ ነበር። በመጨረሻ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡት ደግሞ ከባህላዊና ሃይማኖታዊ እሳቤ በመነሳት ነበር። ይህ የሚያመለክተው ማህበረሰቡ ምንድነው? ብለን ስንጠይቀው ከማህበረ-ባህላዊ ሁኔታዊ በመነሳት የሚመልሱልን የዕውቀት ውቅር በመነሳት ነው። ስለዚህ አንቶሎጂያው አገላለጻቸውን ካየን ከተለያየ ማዕዘን የተመለከቱት እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል።

ለዚህም ይመስላል Abdelhamid እንደማጠቃለያ ሀሳቡን ሲገልጽ፡- በዚህ ዓለም አጥኚዎች እንደሚሉት ባጠኑት ዓለም ውስጥ የራሳቸው የሆኑ አስተሳሰቦች (thoughts)፣ አገላለጽ (interpretations)ና ፍችዎች (meanings) ባላቸው ሰዎች እንደተሞላች አድርገው ይገምታሉ Abdelhamid, (2008:2) ይላል።

### 3.1.1. የጥናቱ ስነ-ዘዴ (methodology)

ጥናቱ የተከተለው የኢትኖግራፊያዊ ስነ-ዘዴን ነው። ኢትኖግራፊ የአጠናን ዘዴ ማህበራዊ መስተጋብርን የሚያጠና ሲሆን አመጣጡ ከስነሰብ የትምህርት መስክ መሆኑን በመጥቀስ የአጠናን ስልቱ ተፈላጊነት እየጎላ የመጣው ከ1900ዎች ወዲህ ታዋቂ ተመራማሪዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይተው መረጃዎችን የመሰነድ ስልት ተግባራዊ ማድረግ ሲጀምሩ መሆኑን እነ Reeves እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> *Ethnography is the study of social interactions, behaviours, and perceptions that occur within groups, teams, organizations, and communities. Its roots can be traced back to anthropological studies of small, rural (and often remote) societies that were undertaken in*

*the early 1900s, when researchers such as Bronislaw Malinowski and Alfred Radcliffe-Brown participated in these societies over long periods and documented their social arrangements and belief systems (Reeves,S. & et al, 2008፡512).*

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደተሞከረው የኢትኖግራፊ አጠናን ስልት በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ እነ Malinowski እና Radcliffe በማህበረሰቡ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይተው መረጃዎችን መሰነድ በጀመሩበት ወቅት የተገኘ የማህበራዊ አጠናን ስልት ነው። በመሆኑም ኢትኖግራፍ በማህበረሰቡ ውስጥ እየተኖረ የሚጠናውን ማህበረሰብ ባህላዊ ጉዳዮችን በጥልቀት ለማወቅ እየተሳተፉ መረጃዎች የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው።

ይህ የጥናት መስክ ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች ያሉት ሲሆን እነሱም 1ኛ.የሚጠናውን ሕዝብ ወግና ልማዳዊ ድርጊቶችን መግለጽ 2ኛ.እነዚህን ወጎችና ልማዶች እንዴት እንደሚከውኑ መግለጽና 3ኛ. የሕዝቡን ባህላዊ አስተሳሰቦችና ስሜቶችን መዝግቦ በግልጽ ማሳየት መሆኑን የMalinowski, (1946) ሀሳብ በማንሳት O'reilly, (2005:8) ያብራራል።
በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን ስነ-ዘዴ በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎችን ለማጥናትና ለማወቅ፤ እንዲሁም በፎክሎር መስክ በጥናቱና በግኝቱም ገለጻ አጥኚዎቹ ሀሳብ የሚካፈሉበት እንደሆነ እነ Sims እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> Ethnography is the process of studying and learning about groups of people, as well as the written description and analysis of those observations. It is through ethnographic research and the written descriptions of their findings in the field that folklorists share their ideas (Sims &Stephens, 2005:202).

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የኢትኖግራፊያዊ ጥናት በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎችን ለማጥናትና ለማወቅ፤ ከዚህ በተጨማሪ በመስክ የተመለከተውን የመግለጽና የመተንተን ሂደት በውስጡ እንደሚያካትት ነው። ስለዚህ በዚህ ስነ-ዘዴ በመጠቀም በማህበረሰቡ ውስጥ በመቆት የተለያዩ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚያጋጥማቸው ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች እንዴት፣ መቼ፣ ለምን ምክንያት፣ በማን አማካይነት እንደሚከወኑና ፋይዳቸውስ ምንድነው? የሚለው ለማየት ተሞክሯል።

ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከስነ-ዘዴው ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ የተለያዩ ዘዴዎች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ እነሱም፡- ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን ውይይትና ንጥል-ጥናት ናቸው፡፡

### 3.1.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች (methods)

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በመረጃ ማሰባሰቢያነት ያገለገሉት ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን ውይይትና የንጥል-ጥናት ዘዴዎች ናቸው፡፡

#### 3.1.2.1. ምልከታ

ምልከታ አንዱና ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከናወን ተመራማሪው በአካል ተገኝቶ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው፡፡ ምልከታ የሚለው ቃል ፍቺ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን ሁሉንም የስሜት ህዋሳት በማሳተፍ ነገሮችን መረዳትንም ያጠቃልላል፡፡ ማለትም የሚካሄደውን ክዋኔ በዓይናችን ከማየት ባሻገር በትኩረት በማዳመጥ፣ በማሽተትና በመቅመስ የክዋኔውን አጠቃላይ ድርጊቶችን መረዳትና መተርጎም እንደሆነ Goldstein, (1964፡77) ያስረዳል፡፡ የምልከታ ቴክኒኮቹም ተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ስለምልከታ ዘዴ (Goldestein, 1964) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡ ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ አጥኚው በባህላዊ ክዋኔ ሳይሳተፍ መረጃ የሚሰበስብበት ቴክኒክ ሲሆን፤ የተሳትፏዊ ምልከታ ደግሞ አጥኚው በማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ በመሳተፍ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የተወሰኑ የከበራ መረጃዎችን ባጋጣሚና በታላሚ ናሙና ላይ ተመስርቼ በምልከታ ዘዴ ስብስቢያለሁ፡፡ ይኸውም፡- የሚያጠናውን ማህበረሰብ ቋንቋ፣ ባህልና ሃይማኖት በሚገባ ስለማውቅ ከቃሉ ተቋም በውሎ ገብ ለመጀመሪያ ሁለት ሳምንታት ማለትም ከ29/11/2006- 12/12/2006 ዓ.ም. ድረስ ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት አንስቶ እስከ ቀኑ 11፡00 ድረስ ከቃሉና ከአማካሪው አቶ ሞኮና ጋር በዋናነት በማሳለፍ፣ ባጋጣሚ የሚከሰቱ ሁነቶችንም በካሜራና በመቅረጸ ድምፄ እያስቀረሁ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ችያለሁ፡፡ በመቀጠል በ21/2/2007 ከዩኒቨርሲቲው የትብብር ደብዳቤ ከተጻፈልኝ ጊዜ አንስቶ በተለያዩ ቀናት እስከ 14/12/2007 ዓ.ም. ለ20 ቀናት በመመላለስ በየዕለቱ የሚያጋጥሙኝን ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ስርዓታቸውን በማየትና በመጠየቅ መረጃዎችን አሰባስቤያለሁ፡፡

በመጨረሻም በ2008 ዓ.ም.በሚኦ ቦኮ የተካሄደውን የገዳ ስልጣን ርክክብ ከበራ በቦታዉ ቀደም ብዬ በ5/6/2008 ዓ.ም. በመገኘት ከ6/6/2008-13/6/2008 ዓ.ም. የነበሩትን የተለያዩ ከበራዎች በተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ አሰባስቤያለሁ፡፡ በዚህ ዘዴ ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ በሚከወኑባቸው ማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ የቀረበው ክዋኔ በማን፣ ለማን፣ መቼ፣ የትና እንዴት እንደተከወነ ተገልጿል፡፡ ይኸውም፡- በምልከታ ሽምግልናን፣ የጎንዶሮ ከበራን፣ የፋጭ ከበራንና የቃሉ ጋብቻ ከበራዎች በተወሰኑ ደረጃ በተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

አንድ ኢትኖግራፊያዊ ጥናት ከምልከታ በተጨማሪ ሌሎች ዘዴዎችንም ሊጠቀም ይችላል፡፡ ስለዚህ ከምልከታ የሾለኩና በቂ መረጃ ያልተገኘባቸውን በቃለመጠይቅ ዘዴ ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡

### 3.1.2.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ አንድ አጥኚ ከመረጃ አቀባዩ ጋር ፊት ለፊት ተገናኝተው ስለሚያጠናው ነገር ያለውን መረጃ በጥያቄና መልስ መልክ የሚያሰባስብበት ዘዴ ነው (Julia, 2008: 208)፡፡ ቃለ መጠይቅ የመረጃ ሰጪዎችን የግል ታሪክ፣ የሚያቀርቡትን ጥበብ፣ የዕውቀታቸውንና የስሜታቸውን ፍች፣ የፎክሎራዊ ጉዳዩን ተስተላልፎ፣ እንዲሁም በምልከታ ስላልተገኙ ከበራዎች ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል (Goldstein, 1964፡104-108)፡፡

ስለዚህ ይህን ዘዴ በመጠቀም ማህበረሰቡ ስለቃሉ ተቋም አመጣጥ፣ ስለ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምንነትና ዓይነት፣ ስለ ከዋኞቹ ማንነትና አከዋወናቸው፣ እንዲሁም ስለ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ፋይዳዎች ለመረዳት ቃለመጠይቅ በማዘጋጀት ስራ ላይ ውሏል፡፡ በዚሁ መሰረት ከሀገር ሽማግሌዎች በተጨማሪ ከተተኳሪ መረጃ ሰጭዎች፡- በታላሚ ናሙናና በጥቁም ናሙና፣ እንዲሁም ያጋጣሚ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ማለትም፡- ከቃሉ አጎት (አቶ ሞኮና ናጋኦ)፣ ከአባገዳ ደንቦባ፣ አባገዳ ሀልቻዬና በተቋሙ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ የቀድሞው ቃሉ ዘመዶች ስለቃሉ አመጣጥ፣ ስለቃሉ ስያሜና የጋብቻ ሃይማኖታዊ ከበራ፣ ስለጉጂ ኦሮሞ አመጣጥና ስለቃሉ ተቋም አጀማመር የሚነገሩ ሚቶችን እንዲሁም ስለ ሁሉቃ ሃይማኖታዊ ከበራዎች፣ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ የሚጨፈሩ ቄጣላዎች ማለትም፡- ማልጊቾ (Malggichoo)፣ ሳማጤ (Samaxee)፣ ቃሉ ቢፊ (Qaaluu biifi) የሚሉትንና አንዳንድ ጸሎቶችን፣ ምርቃቶችንና በቃሉ ተቋም ላይ የነበሩ ተግዳሮቶችን ለመሰብሰብ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በምልከታ ወቅት የተፈጠረውን የመረጃዎች ክፍተት ከማስታወሻዬ በማቅረብ ምላሽ ተገኝቶበታል፡፡

### 3.1.2.3. የቡድን ውይይት

በመጨረሻም በምልከታና በቃለመጠይቅ ያልተብራሩ ሀሳቦችን የበለጠ ለማብራራት፤ እንዲሁም በሁለቱ ዘዴዎች የተገኘውን መረጃ ተዓማኒነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችለን ዘዴ የቡድን ውይይት ነው፡፡ ቡድን ተኮር ውይይት የሚካሄደው በርዕሰ-ጉዳዩ ዙሪያ በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ሰዎችን በመምረጥ፤ በተለያዩ ዘዴዎች ምላሽ ያጣንበትን በቡድን በመሆን እየተወያዩ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡ በቡድን ተኮር ውይይት ላይ የተሳታፊ አባላትን ብዛት በሚመለከት እነ Marshal & Rossman, (2006:114) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡ ‹‹The groups are generally composed of 7 to 10 people (although groups range from as small as 4 to as large as 12 who are unfamiliar with one another and have been selected because they share certain characteristics relevant to the study's questions.››

ይህ ማለት የቡድን ውይይቱ አባላት ከ7 እስከ 10 ሊሆኑ እንደሚችሉና አነስተኛው የቡድኑ አባላት ቁጥር አነስተኛው ከ4 የማያንሱ፤ ከፍተኛው ደግሞ ከ12 እንደማይበልጡና በጣም የማይቀራረቡ ሆነው ሀሳብ ለሀሳብ መቀያየር የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል የቡድን ውይይት በምልከታ ወቅት የተፈጠሩና በቃለ-መጠይቅ ዘዴም ተፈትሸው በቂ ማብራሪያ ያልተገኘላቸው መረጃዎች ላይ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች በቡድን ሆነው በርዕሰ-ጉዳዩ ዙሪያ ስላላቸው ዕውቀት በመወያየት ልዩነቶቹ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአብላጫው ወገን ምን ያመላክታል የሚሉትን መረጃዎች የሚሰበሰብበት መንገድ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በተለያዩ ጊዜያት ከአምስት እስከ ሰባት ከሆኑ አባላት ጋር ማለትም፡- ከአባገዳ፣ የቃሉ አማካሪ ከነበሩትና የሀገር ሽማግሌዎች ጋር በታላሚ ናሙና መረጣ አምስት አባላት ባለው ቡድን፣ በሌላ በኩል የሀገር ሽማግሌዎችና ሴቶችንም ባሳተፈ መልኩ በጥቁም የናሙና ዘዴ በመምረጥ ሁለት ሴቶችና አምስት ወንዶች ካሳተፈ ቡድን ጋር ውይይት በማድረግ አስፈላጊ መረጃዎችን በቪዲዮና በማስታዎሻ ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ የሴቶችን ቁጥር ያሳነስኩበት ምክንያት ሴቶች ብዙን ጊዜ ለቃለመጠይቅ ፈቃደኛ ያለመሆንና ሁሉንም ጉዳይ ወንዶቹ

ይነግሯችኋል የሚል አስተሳሰብ እንዳላቸው ከመስክ ቆይታዬ ተረድቻለሁ፡፡ ስለዚህ በነዚህ የቡድን አባላት ጋር የቃሉ መማክርት አባላት ተግባራት ምን ምን እንደሆነ፣ ስለቃሉ ተቋም ተግዳሮቶችና እንደምክንያት የሚያነሷቸው ጉዳዮችንና በካልኣይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች የማረጋገጥ ስራ በውይይቱ ላይ ተካተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሚኬ ቦኮ የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ ላይ ከተሳተፉ ውስጥ ስምንት አባላት የነበሩት ከዶሪዎች፣ ከገዳዎችና ከባቱዎች እርከን ያካተተ ተተኳሪ የቡድን ውይይት በ8/6/2008 ዓ.ም. እና በ10/6/2008 ዓ.ም. ለሁለት ጊዜ በማካሄድ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ሌላው ሴቶችን ለብቻ ያሳተፈ 5 አባላት ያለው አንድ ቡድን በማዋቀር በ26/8/2007 ዓ.ም. በቃሉና በገዳ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ ሴቶች ያላቸውን ሚና መረጃ ተሰብስቧል፡፡

### 3.1.2.4. **ንጥል ጥናት** (case study)

ንጥል ጥናት ልክ እንደ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ ሁሉ የጥናት ዘዴ ስር እንደሚመደብ Crotty, (1998:5) ያስረዳል፡፡ ንጥል ጥናት የሚባለው አንድ በተወሰነ ድርጅት፣ ፕሮግራም ወይም ሂደት ላይ የሚደረግ የጥናት ሪፖርት እንደሆነ Yim'ን በመጥቀስ እነ *Peoples,J. and Bailey,G., (1991:156)* እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡ ‹‹*Report of research on a specific organization, program, or process (or some set of these) are often called Case Studies (Yim, 2003). Case Studies rely on historical and document analysis, interviewing, and typically, some forms of observation for data collection.*››

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ውስን ምክንያታዊ ጥናቶች የሚመሰረቱት በታሪካዊና ሰነድ ትንተና፣ቃለመጠይቅ በማድረግና በምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ወካይ በሆኑትና የተቀረውን ውጤት ሊያመላክቱ በሚችሉ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል እነ Best and Jems V., (1993:19) ንጥል ጥናትን ሲበይኑ፡- <<...case study is a way of organizing social data for the purpose of viewing social reality. It examines a social unit as a whole. The unit may be a person, a family, a social group, a social institution, or a community.>>

ከጥቅስ ለመረዳት እንደተቻለው ንጥል ጥናት ለማህበራዊ እውነታ አተያይ አገልግሎት የሚውሉ ማህበራዊ መረጃዎችን ማደራጃ መንገድ ነው፡፡ የተወሰነ የማህበረሰብ አካልን

በመውሰድ እንደ አጠቃላይ የሚመረምር ነው፡፡ ያ የማህበረሰብ አካል ምናልባትም ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰባዊ ቡድን፣ ማህበረሰባዊ ተቋም ወይም ማህበረሰብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ዘዴ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ ግለሰቦች በግልም ይሆን በተወሰኑ ቡድን ሆነው ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክዋኔ ሲፈጽሙ መሠረታዊ መመሪያቸው በጋራ ያዋቀሩት እውቀት ይሆናል፡፡ ይህን ለማረጋገጥና ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ በተወሰኑት ከበራዎች ላይ የተደረጉና የቀረቡ ንጥል ጥናቶች በተግባር የተፈተኑ ውጤቶች ስለሆኑ ድርጊቶቹ የተከናወኑ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በቃሉ ጋብቻ ከበራ አንድ፣በጎንደሮ ከበራ ሁለት፣በፋጭ ከበራ ሁለት፣ በሁሉቃ አንድ ንጥል ጥናቶችን በማካሄድ በተወሰነ ደረጃ የዚህን ጥናት ዓላማ ለማሳካት ተችሏል፡፡

### 3.1.3. የናሙና መረጣ ሂደት

በዚህ ጥናት በመረጃ አቀባይነት የታቀፉት በከበራዎች ላይ ካላቸው ንቁ ተሳትፎና በውስን ጥቁም ናሙና (snowball sampling)፣ ታላሚ ናሙና (purposive sampiling) እና ያጋጣሚ ናሙናን በማቀናጀት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በፎክሎር ውስጥ የከዋኞቹና የታዳሚውን ስሜት ለማጤን፣ የዕድሜና ፆታ ተዋፅኦ ለማካተት በተገኘ ናሙና (Available Random Sampling) አመራረጥ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የጥናቱ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት ለባህሉ ካላቸው ቅርበትና ዕውቀት አንፃር ከተመረጡት ቦታዎች ማለትም፡- ከቃሉ ተቋምና ከሚኤ ቦኮ በተጨማሪ ከአባያ ወረዳ፡- ከከላልቱ፣ ሳማሮ፣ ቡናታና ዳባቃ ቀበሌዎች ለቃለ-መጠይቅና ለቡድን ውይይት ወደ 60 ሰዎች የተመረጡ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ሴት 8 ሲሆኑ፣ 52 ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት አንደኛ ለሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ቅርበት አላቸው፣ ስለጉዳዩ ያውቃሉ የተባሉትን በጥቁም ናሙና (snowball sampling) መረጣ የተመለመሉ ሲሆን፤ እንደ ቃሉ፣ የቃሉ አማካሪና ገዳዎችን ደግሞ በታላሚ ናሙና (purposive sampiling) አመራረጥ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ በተገኘ ናሙና (Available Random Sampling) የተወሰዱ ናቸው፡፡ በዚህ የመረጃ አቀባዮች መረጣ ላይ የሴቶች ቁጥር ሊያንስ የቻለበት ምክንያት በባህሉ ሴቶች ቢያውቁም ከወንዱ እኔ አውቃለሁ ብለው እንደመናገር ይቆጠርብናል በማለት ስለማይሳተፉ ነው፡፡

### 3.2. የመረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን በመስክ ቆይታ ከቃሉ ተቋም፣ ከሚኤ ቦኮና ሌሎች መንፈሳዊ ስፍራዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት አማካኝነት የተሰበሰቡ ሲሆኑ፤ ይኸውም፡- ከአባገዳዎች፣ ከዶሪዎች፣ ከዩባዎች፣ ከቀድሞ ሀዳ አንባ፣ ከሀገር ሽማግሎዎችና ከማምለኪያ ስፍራዎች በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶ ግራፍ፣ በቪዲዮና በማስታወሻ ተሰባስበው፣ ከተቀናበሩ በኋላ የተተነተኑ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስለከበራዎች፣ ስለቁሳዊ ባህል፣ ስለሚቶችና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የሚገኙባቸው ዶክመንቶችን ከቤተ-መጻህፍት፣ የድረ-ገጽ መረጃዎች፣ ተዛማጅ ጥናታዊ ስራዎች፣ ዶክሜንተሪ ፊልሞች ላይ በጥናቱ ዙሪያና ከጥናቱ አካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንድፈ ሀሳቦችና ዳራዊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መቼት

መቼት ማለት አንድ ፎክሎራዊ ቅንጣት የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ነው፡፡ መቼት ከሚከወንባቸው ሁኔታ በሦስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡- ተፈጥሯዊ መቼት፣ አርቲፊሻል መቼትና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት በመባል ይጠራሉ፡፡ ተፈጥሯዊ መቼት የሚባለው ባህሉ የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ነው፡፡ አርቲፊሻል መቼት ደግሞ ከአውዱ ውጭ ማንኛውም መረጃ አቀባይ በተገኘበት ጊዜና ቦታ ተመራማሪው የሚሰበስብበት መቼት ነው፡፡ ሌላው ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት የሚባለው ሲሆን፤ ተፈጥሯዊ የሚመስል መቼት በማዘጋጀት፣ በማደራጀትና በማቀናበር ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ለማሰባሰብ የሚያስችለን የመቼት ዓይነት ነው (ፈቃደ፣ 2002፡122-124)፡፡

የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች የሚከወኑት ወቅት ጠብቀው መሆኑና በክዋኔው ወቅትም ዝርዝር ጉዳዮች ሾልከው ሊያመልጡ ስለሚችሉ፤ የተጓደሉትን አሟልቶ ለመሰብሰብ ሦስቱም በጥምረት መጠቀም ይመከራል (ዝኒ ከማሁ)፡፡ ይህም ጥናት የተወሰኑ መረጃዎችን ማለትም፡- የቃሉ ጋብቻ ከበራ፣ የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ፣ የተወሰነ የጎንዶሮ ከበራዎችን ከተፈጥሯዊ መቼት ላይ የተሰበሰቡ ሲሆን፣ ሌሎችን መረጃዎች ደግሞ እንደ ፋጭ ከበራና የሁሉቃ ከበራ ከአርቲፊሻል መቼት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡

### 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ይህንን ጥናት ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የፎክሎር ዘውጎችን ለመቅረፅ የሚያስችሉ መሣሪያዎችን መጠቀም የግድ በመሆኑ፤ ይኸው ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ከእነሱም ውስጥቪዲዮ

ካሜራ አንዱ ሲሆን አውዱ እስከፈቀደ ድረስ ለሁሉም የፎክሎር ዘውጎች መቅረጫነት ለመጠቀም የተሞከረ ቢሆንም በሙሉ ሳይሆን በከፊል ለመጠቀም ተችሏል፡፡ ነገር ግን በሚኤቦኮ በተካሄደው የክዋኔ ቀረጻ ላይ ግፊያ፣ በስርዓት አስከባሪዎች የቀረጻ ክልከላ ስለነበር የተወሰኑ ቀረፃዎች ብዥታ ሲኖራቸው፤ የተዘለሉም ነበሩ፡፡ በተሳትፏዊ ምልከታ ወቅት ደግሞ በረዳት የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያ አማካይነት የተካሄዱ ቀረጻዎችም አሉ፡፡

ቃላዊ የሆኑ የፎክሎር መረጃዎችን ከአውዱ ለመሰብሰብ እና ለቃለመጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያነት ደግሞ መቅረጸ ድምጽን ተጠቂሚያለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፎቶ ካሜራ የቃሉን ተቋም፣ መንፈሳዊ ስፍራዎችን፣ ቁሳዊ ባህሎችን የሚያመላክቱ ተምሳሌትነት ያላቸውን መረጃዎች ለመቅረጽ በተግባር ላይ ውሏል፡፡

## 3.5. መረጃዎችን መሰብሰቢያ አንጻሮች

አንድ የፎክሎር ተመራማሪ መረጃዎችን ሲያሰባስብ ከሁለት አንጻሮች ሊሆን ይችላል፡፡ እነሱም ውስጣዊና ውጫዊ አንጻሮች (emic & etic perspective) ይባላሉ፡፡ እነሱም፡-

### 3.5.1. ውስጣዊ አንጻር

ይህ አንጻር ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ከመስክ መሰብሰብ ያለበት የባህሉ ባለቤት የራሱን ባህል በሚገልጽበት መንገድ መሆን አለበት፡፡ ይኸውም አጥኚው በመስክ ቆይታው ወቅት ከማህበረሰቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥሮ፣ ማህበረሰቡን በወጉ ተረድቶ ዝርዝር ጉዳዮችን መሰብሰብና ለሌላው ማሳየትን ይፈልጋል (O'reilly, 2005:84):: በዚህ መሰረት በኢትኖግራፊ ስነ-ዘዴን በመጠቀም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለምን እንደሚከወኑ፣ እንዴት እንደሚከወኑና ለማህበረሰቡ ምን ምን ፋይዳዎች አሏቸው የሚሉትን ለማየት ተችሏል፡፡

### 3.5.2. ውጫዊ አንጻር

ውጫዊ አንጻር የሚባለው ደግሞ የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻሩ ለባህላዊ ጥናቱ አስፈላጊ የሆነ አመለካከት ነው፡፡ ይኸውም፡- ከባህሉ ውጭ የሆነው ተመራማሪ በሚያጠናው ባህላዊ ጉዳይ ላይ ያለውን አመለካከት የሚያንፀባርቅበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ የተመራማሪው አመለካከት በአሉታዊ ዓይን የሚታይ አይደለም፡፡ ሳይንሳዊ አመለካከት ነው፡፡ ለውስጣዊ አመለካከት ትርጓሜ መስጠትን ይመለከታል፡፡ በዚህ አካሄድ የተመራማሪው ተግባር የውስጣዊ አመለካከትን፣

ትርጓሜን ማካተት ብቻ ሳይሆን ከባህሉ ውጭ ላለውም ተደራሲ ግልፅ ሊሆን በሚችል መንገድ ማሳየት መቻል ነው፡፡ የውስጣዊና የውጫዊ አመለካከትን ሚዛን መጠበቅ ከአጥኚው ይጠበቃል፡፡ ይህ ሚዛን የተዛባ ከሆነ ነው አሉታዊ ገፅታ የሚኖረው፡፡ አጥኚው የሚያጠናውን ህዝብ (ቡድን) እንቅስቃሴና እምነት ገለልተኛ ሆኖ ማየትና መልሶ ማሳየት እንጂ የራሱን ሃሳብ ሊጭንበት አይገባም፡፡ ባህሉን በደንብ ተገንዝቦ ለማያውቀው ውጫዊ ተመልካች ሳያዛባ ማሳወቅ አለበት (Fetterman, 2010)፡፡ ስለዚህ አጥኚው የአካባቢ ተወላጅ በመሆኔ የውስጣዊ አንጻር እንዳያመዝንብኝ ሁለቱንም በማጣጣም ለመስራት ጥረት አድሪጊያለሁ፡፡

## 3.6. የተሰበሰቡት የመረጃ ዓይነቶች

ለዚህ ጥናት ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምንነትና ፋይዳዎቹን ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህም የተሰበሰቡት የመረጃ ዓይነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በተያዩ መልኮች የሚገኑ ናቸው፡፡ ይኸውም፡- በቃላዊ ግጥሞች መልክ ያሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ጭፈራዎች (qeexalaa) ሲሆን እነሱም፡- ማልጊቾ (Malggichoo)፣ ሳማጤ (Samaxee)፣ ቃሉ ቢፊ (Qaaluu biifi) የሚሉትንና አንዳንድ ጸሎቶችን፣ ምርቃትና እርግማንን፣ በሚቶች መልክ ደግሞ ስለቃሉ አመጣጥ (Dhuftee Qaalluu)፣ ስለቃሉ ስያሜና ጋብቻ (Dhuftee Moggaasaafi Gaa'ila Qaalluu)፣ ስለጉጂ ኦሮሞ አመጣጥ (Dhuftee Gujii Oromoo)፣ ስለቃሉ ተቋም አመጣጥ (Dhuftee Galma Qaalluu)፣ ስለገዳና ስልጣነ ሢመቱ አመጣጥ (Dhuftee sirna muudafi gadaa)፣ ስለገፀ-በረከት/ስጦታ/ አሰጣጥ አመጣጥ (Dhuftee Gumaacha kennuufi fudhachuu) የተሰበሰቡ ሲሆኑ፤ ሌላው ከቁሳዊ ባህሎች ደግሞ ባህላዊ ምግቦች (Nyaata aadaa) ማለትም እንደ ጠጅ/ቦካ (booka)፣ ቡና ቃላ (buna qalaa)፣ ማር (damma)፣ ቅቤ (dhadhaa)፣ ገብስ (garbuu)፣ ወተት (aannan) እና የመሳሰሉትን፤ ከሃይማኖታዊ ቁሶች (Meeshaale amantaa) ውስጥ ደግሞ እንደ ከርቤ (qunbii)፣ ቦኩ (bokkuu)፣ ካላቻ (kallacha) እና የመሳሰሉትን፤ ሌላው ሃይማታዊ ከበራዎች፡- የገዳዎች ስልጣን የማጽደቅ ሃይማኖታዊ ከበራ፣ የጎንዶሮ፣ የሁሉቃ፣ የፋጭ እና የቃሉ ጋብቻ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በግጭት ማስወገጃ መዋቅሮች ስር (ግለ-ወቀሳ፣ ሽምግልና (በቤተሰብ፣ በንዑስ-ጎሳና በጎሳ ደረጃ)፣ በገዳና ቃሉ ተቋማት)፣ በገዳና ቃሉ ተቋማት ላይ ስለነበሩ ተግዳሮቶች፣ ስለ ቃሉና ቃሊቻ አንድነትና ልዩነት፣ ከካልኣይና ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች በታላሚ ናሙና፣ በጥቁም ናሙና እና ያጋጣሚ ናሙና ዘዴዎችን በመጠቀም ከመረጃ አቀባዮቹ ተሰብስቦ በተግባር ላይ ውለዋል፡፡

### 3.6.1. ትራንስክሪፕሽን

ከማህበረሰቡ የተገኙትን መረጃዎች ከመተርጎሙ በፊት እንደ ወረደ በአፋን ኦሮሞ ወደ ፅሁፍ ተቀይሯል፡፡ ይህም ከመቅረጸ ድምፅና ከቪዲዮው መላልሶ በማዳመጥ ቃል አቀባዩ በትክክል የተጠቀሙባቸውን አገላለፆች ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ ከድምፅ ጀምሮ ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን ቃላትና ቅደም ተከተላዊነት የአነጋገራቸውን ለዛ ባለቀቀ መልኩ ለማስፈር ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡ በአውድ ላይ በመመስረት ለማስፈር ተሞክሯል፡፡

### 3.6.2. አተረጓጎም

ይህ ጥናት የተካሄደው በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ተቋምና አካባቢው ላይ ሲሆን መግባቢያ ቋንቋቸው ደግሞ አፋን ኦሮሞ ነው፡፡ ስለዚህ ለጥናቱ የሚያስፈልጉት መረጃዎች የተሰበሰቡት በምንጩ ቋንቋ (በአፋን ኦሮሞ) ሲሆን፤ በመቅረጸ ድምፅና በቪዲዮ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመጀመሪያ በመሰክረብ፣ በማስታወሻ የተያዙትን ጭምር ቃል በቃል (ቀጥተኛ ትርጉም)፣ አቻ ትርጉምና አውዳዊ ትርጉምን በመጠቀም ወደ ታላሚው ቋንቋ (ወደ አማርኛ) ለመተርጎም ተሞክሯል፡፡ በመረጃ ትርጉም ወቅት በተቻለ መጠን በምንጩ ቋንቋ ለማስተላለፍ የታሰበውን መልዕክትና ለዛ እንዳያጣ ጥረት ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ታላሚው ቋንቋ ሲተረጎም በአማርኛ ቋንቋ መልዕክቱ ሳይዛባ ለዛውን በጠበቀ መልኩ ለመተርጎም ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ቃላትም ሆኑ ሀረጋት በአማርኛ ቀጥተኛም ሆነ አቻ ትርጉም ሲታጣላቸው በምንጩ ቋንቋ በማስቀመጥ ስለጉዳዩ ማብራሪያ በመስጠት የተገለጸበት ሁኔታም አለ፡፡

## 3.7. ከመስክ ውሎ የተገኘ ልምድ

በመጀመሪያ ደረጃ ከካልኣይ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን መልክ በማስያዝ፤ ከትምህርት ክፍሉ የሚሰጠውን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ፤ ከአባያ ወረዳ አስተዳደር እና የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤቶች ከሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመተዋወቅ፣ ስለ ጥናቱ ዓላማና የአጠናን ሁኔታ በመግለፅ የትብብር ደብዳቤ ከወረዳው መስተዳድር አካል በመውሰድ ወደ መስክ ወጣሁ፡፡ የመጀመሪያ ጉዞዬን ወደ ቃሉ ተቋም ነበር፡፡ በወቅቱ ከአባቃሉ አጋ ሳቆ ጋር በመተዋወቅ የተሰጠኝንም የትብብር ደብዳቤ በማሳየት ስለሄደኩበት ጉዳይም አስረዳሁ፡፡ በደብዳቤው ብቻ ከማመን፤ «ከአስተዳዳሪው ስልክ ሊደወልልኝ ይገባል» አሉኝ፡፡ እዚያው ሁኜ ወደ አስተዳዳሪው ስልክ ብንሞክርም በወቅቱ መስመሩን ማግኘት አልቻልንም፡፡ በቀጣይ ጊዜ ቀደም ሲል ለሁለተኛ ዲግሪዬ ማሟያ የሰራሁትን ጥናትና አንዳንድ መረጃዎችን በመያዝ

አሳይቼ፤ ስለ ሁኔታውም በመግለጽ፣ በቀጣይ ደግሞ የተሻለ ስራ ለመስራት መዘጋጀቴን በጥሞና ለማስረዳት ሞከርኩ፡፡ በተወሰነ ደረጃ እያቅማሙ ለሀሉና ዌሲቱ ገዳዎችና ካሎዎቼ መልዕክት አስተላልፋለሁ ሳምንት ተመለስ ተብዬ ተለያየን፡፡ በሳምንቱ ረዳት የካሜራ ባለሙያ በመያዝ ስሄድ መልዕክት እንዳላስተላለፉና የመማክርት አባላቱም እንደማይመጡ ተነገረኝ፡፡ በወቅቱ ለጊዜውም ቢሆን ፊቴን ወደሌላ አቅጣጫ እንዲያዞር ተገደድኩ፡፡ ከዚያ በወቅቱ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ የነበሩት አቶ ደሳለኝ ሆርዶፋን ስለሁኔታው አማከርኳቸው፡፡ እሳቸውም ቃሉን በተመለከተ አቶ ሞኮና ናጋኦ (የቃሉ አጎትና የቅርብ አማካሪ) ብታገኛቸው ሁሉንም ነገር ያቀሉልሃል አሉኝ፡፡ የቃሉ አንቢታ እንደሚመስለኝ ከሆነ ከአስተዳደር በኩል ያስተላለፉላቸው መመሪያ ያለ ይመስለኛል፡፡ ይሁን እንጂ እውነትም ከአቶ ሞኮና ናጋኦ ጋር በመተዋወቅ ለስራው አስረድቼ በቀጠሮ ተለያየን፡፡ ከአቶ ሞኮና ጋር በቀጠሮው ዕለት የቃሉን ገልማና የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይፈጸምባቸዋል በሚባሉ ቦታዎች በመዟዟር ስለሃይማኖታዊ መቼቱና የነበራቸውን አገልግሎትና አሁን ያሉበትን ሁኔታ በመጠየቅ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን የመሰብሰብ ሥራ አከናወንኩ፡፡

በሁለተኛው ዙር ስምሪት ደግሞ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን በአቶ ሞኮናና በሌሎች የሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት በማፈላለግ፣ ስለጥናቱ አሳውቆ አብሮ ለመስራት በማስማማት በኩልም የአቶ ሞኮና ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለባህሉና ሃይማኖቱ ያውቃሉ የሚባሉ ሽማግሌዎችን አንዳንዴ ጠጅ ቤት እንደሚገኙ ሲጠቁሙኝ፤ እዚያው ድረስ በመሄድ በመጋበዝና እኔም አብሬ እየጠጣሁ እዚያው የሚከወነውን ምርቃት፣ በስርዓት እየተቀባበሉ ቀጠሮ ሲያስዙኝ በራሱ ፎክሎር ነበር፡፡

በተለይ የሀሉው አባገዳ ከአካባቢያቸው ብዙም ርቀው ስለማይሄዱ እዚያው እስከ አምስት የሚደርሱ የሀገር ሽማግሌዎችን አዘጋጅተው እንዲጠብቁኝ በማድረግ ለመረጃ አቀባዮቹ ተረጋግተው መረጃ ለመስጠት እንዲያመቼኝ ከከተማ ምግብና ጠጅ በጀሪካን በመያዝ ከረዳት የካሜራ ባለሞያው ጋር በመሆን በሞተር ሄደን መረጃ ለማሰባሰብ ችለናል፡፡ በዚህም ስኬታማ ሆኜ ተመልሻለሁ፡፡ ምክንያቱም የገዳው ተቋም ወጣ ያለ ስለነበር፤ ለምሳና ውሃ ፍለጋ ሰበብ ተሰላችተው እንዳይበታተኑብኝ ረድቶኛል፡፡

በመጨረሻም በጉጂ ዞን በሚኤ ቦኮ ያጋጠሙኝ ችግሮች ደግሞ በዋናነት በገዳ ስርዓት ውስጥ በገዳ የስልጣን ሽግግሩ ላይ የሚሳተፉት ከኡራጋ፣ ከሆኩና ከማቲ ገዳዎች ውስጥ ሦስት ሦስት

ቡድኖች ነበሩ። እነሱም፡- ራባ፣ ዶሪና ገዳ ናቸው። እነዚህ ሦስቱም ቡድኖች ያረፉበት ቦታ የተለያየና በመጠኑም ቢሆን የተራራቁ ስለነበሩ፤ ከዚህ ጋር ተያይዘው እያንዳንዳቸው ደግሞ የየራሳቸው ውይይትና ዝግጅቶች ስለነበሯቸው መረጃ ለማሰባሰብ ከወዲያ ወዲህ መሯሯጥ ነበረበረኝ። ስለዚህ መረጃዎችም እንዳያመልጡኝ በማሰብ፤ እንዳጋጣሚ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ጓደኞቼን በተወሰነ አቅጣጫ በመመደብ በአትክሮት እንዲቀርጹልኝ በማድረግ የተፈጠረውን ክፍተተ ለመቅረፍ ተሞክሯል።

በመጨረሻም በእነ አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ አቶ አባባ ቶተ፣ጎበና ቶተ እና ወ/ሮ ረጋቱ በሪሶ (የቃሉ ቤተሰቦች) አማካይነት ቃሉን በማግባባት መረጃ እንዲሰጡና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንም በማማከር በቪዲዮ እና ፎቶ ግራፍ በማንሳት መረጃዎቼን ለማጠናቀር ችያለሁ።

## 3.8. የምርምር ሥራ ሥነ-ምግባር

አንድ ተመራማሪ ወደ መስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በሚሰማራበት ወቅት ሊያጋጥሙት የሚችሉትን ችግሮችን ቀድሞ መገመትና የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ እንዳለበት ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል። ይኸውም የጥናቱ አውድ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እንደመሆኑ መጠን፤ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እንዲህ በቀላሉ ይገኛል ማለት ዘበት ነው። ይሁን እንጂ ያለነሱ መልካም ፍቃድ የተቋሙን ህልውና፣ የመረጃ ሰጪዎችን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ መረጃ ለማግኘት መጣር ከምርምር ስራ ስነ-ምግባር አኳያ አግባብነት የለውም። ስለዚህ አጥኚው ይህን ከግንዛቤ በማስገባት በመጀመሪያ የተጠኚውን ህዝብና የመረጃ አቀባዩን ባህልና እምነት ማክበርና ከስነ-ምግባሩ ውስጥ አንዱ በመሆኑ ባህሉና ሃይማኖቱ በሚፈቅደው መሰረት ሰላምታ በመጠየቅ፤ አቀራረቤን ከመግቢያው ለማሰተካከል ጥሪያለሁ። ከዚያም ለመረጃ አቀባዩቼ ስለምርምሩ ዓላማና ውጤት በሚገባ በማስረዳት፣ መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆናቸውን በመጠየቅ፣ መረጃውን በመስጠታቸው ለችግር እንዳይጋለጡ ግላዊ መብታቸውን በመጠቀምና በመወያየት አላስፈላጊ የምስልና የድምፅ ጥበቃ፣ ስም አለመጥቀስ ተደርጓል፣ ስለሃይማኖታዊ ተቋሙ ሚስጥሬነውያሉትንለመጠበቅ በመስማማት፣ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማያሳድር መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ተችሏል።

በሌላ በኩል መረጃ አቀባዮች ለዚህ ስራ ሲሉ ከአንዱ ሃይማኖታዊ መቼት ወደ ሌላው ሲንቀሳቀሱ የትራንስፖርት፣ የምሳና የመጠጥ ወጪያቸውን በመሸፈን፣ በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ምግብና መጠጥ በማዘጋጀት እዚያው እየተወያየንና አብሮ በመቋደስ በቤተሰባዊ ስሜት በመግባባት መረጃዎችን ያለአንዳች ስጋት ለመለዋወጥ ተችሏል።

# ምዕራፍ አራት

## የጉጂ ኦሮሞ ማሕበረ-ባሕላዊ ዳራ

### 4.1. የጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ፣ አካባቢያዊና ታሪካዊ ዳራ ዳሰሳ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ስለጉጂ ኦሮሞ መገኛ አካባቢ፣ ስለዘር ሀረጋቸው፣ የመግባቢያ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ መተዳደሪያና ሌሎችም በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

#### 4.1.1. የጉጂ ኦሮሞ መገኛ

የጉጂ ኦሮሞ በአሁን ወቅት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ አስራ ዘጠኝ ዞኖቹ ውስጥ ባብዛኛው በቦረናና ጉጂ ዞኖች ውስጥ ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ከክልሉ ውጭ ደግሞ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ፡- በሲዳማ ዞን፣ በወንዶ ገነት አካባቢ ከሚኖሩት ውስጥ ወደ 8 ቀበሌዎች በሪፈረንደም እራሳቸውን ችለው በሼሎና ኡቱ ገዳ ተደራጅተው ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በብላቴ፣ በነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክና በአርባ ምንጭ ከተማ አቅራቢያ ለዘመናት ሰፍረው እንዳሉ (Tadesse, 2004፡13; አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ አባገዳ ሀልቻዬ፣ አባገዳ ደንቦባ) ያስረዳሉ፡፡

የጉጂ ኦሮሞ ከጥንት ጀምሮ በደቡብ ከቦረናና ከጋሪ ጋር፣ በሰሜን ከጌዴኦ፣ ከሲዳማና ከወላይታ ጋር፣ በደቡብ-ምዕራብ ከቡርጂ፣ ከኮይራ (ኮሬ) እና ከጋሞ፣ በምስራቅ ደግሞ ከአርሲ ኦሮሞ ጋር በዋናነት ይዋሰናሉ:: የጉጂ ኦሮሞን አንዳንድ አጎራባቾቻቸው ጃምጃም ወይም ጃምጃሚቱ ብለው ይጠሯቸዋል (Tadesse, 2004፡13)፡፡ ከነዚህ አጎራባቾቻቸው ጋር በተለያዩ ምክንያቶች ይጋጩ እንደነበር Tadesse, (1994:312) & Asebe, (2007፡53) ያስረዳሉ፡፡ በተለይም የጋራ የሆነ የመግባቢያ ቋንቋ፣ ባህልና ወግ ያላቸው፤ ሦስቱ ባላንጣዎች (siddi-saddin) በመባል የሚታወቁት ጉጂ፣ ቦረናና አርሲ አንዱ ከሌላኛው ጋር መዋጋታቸውን እንደ ጀብድም ይቆጥራሉ (ዝኒ ከማሁ)::

በአብዛኛው ጥናታዊ ስራዎች ውስጥ የጉጂ ኦሮሞ በሦስት ኮንፌድሬሽን (ኡራጋ፣ ማቲና ሆኩ) እንደሚከፈሉ (Van de Loo,1991; Haberland,1963; Hinnant,1977; Tedecha,1988; Al-Amin,1998; & Tadesse,2004 ያወሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንደ አራተኛ ኮንፌድሬሲ የሚታወቁ አላብዱ የሚባሉ ጎሳዎች አሉ፡፡እያንዳንዳቸው ኮንፌድሬሽን የየራሳቸው ገዳ፣ የአሰፋፈር ቦታና ወሰን ያላቸው ሲሆን፤ የአላብዱው ገዳዎች ማለትም፡- የሀሎና ዌሲቱ ገዳዎች ግን በቃሉ ስር

ያሉና ከቃሉ ጋር በቅርበት የሚሰሩ መሆናቸው ለየት ያደርጋቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የገዳ ስልጣን ሽግግራቸውም የዘር ሀረግ ተከትሎ ከአባት ወደ ልጅ መሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያ ሦስቱ ገዳዎች ግን ከቃሉ ጋር የሚገናኙበት ጉዳዮችና ጊዜያት የተወሰኑ ናቸው፡፡ በማህበራዊ ግንኙነታቸው ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የደም/የስጋ ዝምድና ስላላቸው ከአጎራባች ጎሳዎች ጋር ግጭቶች ሲፈጠሩ አንዱ ለሌላው የመድረስና የመረዳዳት ባህል አላቸው፡፡ ለግጦሽና ለሌላ ጉዳይ አንዱ ወደ ሌላው በመጎዳኘት ያሳልፋሉ፡፡ እነዚህም ጎሳዎች አንዱ ከሌላው ጋር መጋባት ይችላሉ፡፡



ምስል፡-1 የኦሮሚያ ዞኖች መገኛ የሚያሳይ ካርታ (ምንጭ፡- CSA,2007)




ምስል፡-2 በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር፣ የቦረናና ጉጂ ዞኖች የሚያሳይ ካርታ (ምንጭ፡- CSA,2007)

ስለጉጂ ኦሮሞ ኮንፌድሬሽን ክፍፍልና የእርስ በርስ ግንኙነት በተመለከተ Abiyot, *(2005:310)* በተመሳሳይ መልኩ እንደሚከተለው ያስረዳል፡፡

> *Guji is a confederation of four independent, but by no means exclusive, subgroups known as Uraga, Mati, Hoku and Alabdu. The latter is in turn a confederacy of two interdependent groups called Halo and Woyestu. Despite their autonomy in their respective territories and right of exercising Gada system under their own leaders, each of these components of the confederation is mutually interdependent. They allied together in times of warfare, help each other during natural calamities and economic crisis, and more importantly conduct Gada rituals together.*

በሌላ መልኩ የጉጂ ኦሮሞ ሦስቱ እራሳቸውን የቻሉ ጎሳዎች ገዳዎች እንዳሉና አንድ የሉባ ፖለቲካዊ መሪዎች የሌላቸው ጎሳ እንዳሉ (Tedecha, 1988:17) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> *The only unique case is that of the Alladu group of which territorial unit is appeared as cradle of life and not that of authority as independent part. As a matter of fact Alladu dose not have the right to yield the leaders of the luba political office. From this follows, therefore, that the Guji people is a confederation of three independent tribes and one neutral group.*

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የአላብዱ ጎሳ የራሳቸው የሆነ የሉባ ፖለቲካዊ መሪዎች ተቋም መመስረት አይችሉም፡፡ ይህ ማለት በስሩ ያሉት ገዳዎች እንደ ሌሎቹ ሦስቱ ገዳዎች በየስምንት ዓመቱ የስልጣን ሽግግር የሚያደርጉ ሳይሆን፤ ልክ እንደቃሉ፤ የነበረው አባገዳ ከዚህ ዓለም ሕይወቱ ሲያልፍ ከልጆቹ መካከል የመተካት አካሄድ ስለሚከናወን ነው፡፡

እንደ አለማየሁና ሌሎች (1998፡200) ገለጻ የሀሎ እና የዌስቱ ጎሳዎች አሰፋፈርና መስፋፋት ወደ ሰሜን አቅጣጫ ያደረጉበትን ምክንያት በተመለከተ የተለያዩ ሀሳቦች እንዳሉ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> *አንደኛ የአላብዱ ጎሳ መጀመሪያ ላይ የኡራጋ ጎሳ አካል ነበሩ፡፡ ከዘመናት በኋላ የጎሳው ቁጥር እጅግ በመበራከቱ ተለይቶ እራሱን የቻለ ጎሳ ሊሆን ችሏል፡፡ ሁለተኛው የአላብዱ ጎሳ አሰፋፈርና መስፋፋት የሰሜን አቅጣጫ የያዘው አንድ የሀሎ ጎሳ አባል ሌላ ጉጂ ሰው በመግደል እርቅ ሳይፈጽም በምስራቅ አባያ ወደሚገኝ አካባቢ ሸሽቶ በመስፈሩ ነው ይባላል፡፡ በዚህ ጥናት ሂደት በተሰበሰበ ትውፊት ደግሞ የተለየ ምክንያት ይቀርባል፡፡ ይኸውም በጉጂ የቃሉ ልጅ በአንድ የደቡብ ጉጂ ጎሳ አባል በመገደሉ ቃሉ ቅሬታ አድሮበት የአላብዱ ጎሳ ግዛት ወደሚገኝ የአሁኑ ማዕከል እንደተንቀሳቀሰና ከዚያን ወቅት ጀምሮ የጉጂ ቃሉ ከአቢቱ ሀረግ በሚወለዱ ጉጂዎች ሊያዝ ችሏል፡፡*

ከሌሎች በተሻለ መልኩ Haberland (1963:781) የጉጂ ኦሮሞ አሰፋፈርና አደረጃጀት ሲገልጽ፡ በመጀመሪያ በሁለት የሰሜናዊ ጉጂ ወይም አላብዱና የደቡባዊ ጉጂ ኮንፌድሬሺኖች በማለት

ይከፍላቸዋል። የደቡባዊ ጉጂ ኮንፌድሬሺኖች የሚባሉት ኡራጋ፣ ማቲና ሆኩ ሲሆኑ የሰሜናዊ ጉጂ ወይም አላብዱ ኮንፌድሬሺኖች ደግሞ ከዌስቱና ሀሎ በተጨማሪ ኡቱና ሼሎ እንዳሉ ያስረዳል።

> They may be divided into two smallest confederations differing markedly in culture: the northern Guji or Alabdu and the southern Guji, consisting of the Uraga, Mati and Hoku. The Alabdu originally inhabited what is now western and northern Sidamo, where we still find two minor Alabdu groups, the Out and Shelo.

በተመሳሳይ መልኩ የአላብዱን ጉጂ ኮንፌደረሺን ሀሎ፣ ዌሲቱ፣ ኡቱና ሼሎን እንደሚያካትትና ከመጨረሻ ያሉት ሁለቱ በሲዳማ ዞን ውስጥ ተነጥለው እንደሚገኙ Brehanu, (1993:24) ያስረዳል።




**ምስል፡-3 የጉጂ ኮንፌድረሺኖች መገኛዎችን የሚያሳይ ካርታ (ምንጭ-አለማየሁና ሌሎች፣1998፡193)**

እነዚህ ሁለቱም በሲዳማ ህዝብ መሀል ሰፍረው የሚገኙ ሲሆን፤ ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን «የወንዶ ጉጂ» በማለት ይጠራሉ። እነዚህ ጎሳዎች በሰፈራ አካባቢያቸው ከሌሎች የጉጂ ኦሮሞ የተለዩ ቢሆኑም በገዳና በሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ወቅት ተወካዮቻቸውን እየላኩ ሲሳተፉ

የቆዩ መሆናቸው ይነገራል (አለማየሁና ሌሎች፣ 1998፡200)። ከመንፈሳዊ ጉዞው በኋላም በአንድነት ያርፋሉ፣ ለቀጣይ ጊዜያት የሚመሩበትን ህግም አብረው ያወጣሉ።

ሌላው መላ ምት ደግሞ ከቃሉ አመጣጥና የማዕከል ለውጥ ያደረጉበትን ምክንያት Hinnant, (1977፣54) ከተነገረው ሚት መሰረት አድርጎ የሚገልጸው ቃሉ ወደ መሬት በወረደበት ወቅት፣ በአርሲ፣ በቦረና፣ በጉጂና በሲዳሞ መካከል ጦሪነት እየተካሄደ ስለ ነበር እሱን ወደ አላብዱ እንደወሰዱት ያስረዳል።

የጉጂ ኦሮሞ ከተጠቀሱት ዞኖች ውጭ ያሉትን ለማካተት ቢያስቸግርም በ2007 በተደረገ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት በቦረናና ጉጂ ዞኖች ከሚኖሩት 2,352,289 አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት ውስጥ ወደ 1,946,477 ኦሮሞዎች እንደሆኑ ያሳያል (CSA,2007፡ 11-12)።[3]

### 4.1.2. የጉጂ ኦሮሞ ዘር ሐረግ

ስለ ጉጂ ኦሮሞ አመጣጥ የተለያዩ ሚቶች ይነገራሉ። ከነዚህም ውስጥ በ Tadesse, (1994) ስለጉጂ ኦሮሞ የቀረበውና እንዲሁም ስለጌዴኦ ህዝብ አመጣጥ በጥላሁን፣ (1982) ጥናት ውስጥ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ይኸውም፡- እንደ ሁለቱም አገላለጽ ጉጆ፣ ዳራሶና ቦሮ የሚባሉ የአንድ አባት ልጆች ነበሩ። በቀረበው ሚት ገለጻ ጉጆ አሁን ጉጂ ለተባሉት ቀደምት አባት ነው። ዳራሶ ደግሞ አሁን ጌዴኦ ለሚባሉት ቀደምት አባት ሲሆን ቦሮ ደግሞ አሁን ቦረና ይባሉ ለነበሩት ቀደምት አባት ነው በማለት ስለሦስቱ የዘር ሐረግ ትስስር ይተርካል። ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩ ዳራሶ ታላቅ፣ ጉጆ ደግሞ ታናሽ ወንድም እንደሆነና ይህንኑ ሚት አሁንም ጠብቀው እንደሚገኙ፤ ማለትም በተለያዩ ከበራዎች ላይ ለምሳሌ፡- በምርቃት ከበራ ላይ የሚቀርብ ሙሉ ነገር (mijuu) ይኸውም እንደ ወተት፣ ቦካ (ጠጅ) ያሉትን በመጀመሪያ የጌዴኦ ሽማግሌ ሳይቀምስ የጉጂው እንደማይቀምስ ያስረዳሉ።
ከላይ ከተገለጹት በተለየ መልክ ይህን የጉጂና ጌዴኦ የጋራ የዘር ሀረግ አመጣጥ ታሪክ፡- ጌዴኦዎች ለግዛት መስፋፋት እንደመከላከያ ዘዴ የተጠቀሙበት እንደሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአቢሲኒያኖች የተለያዩ ቡድኖችን በአንድ ላይ አድርጎ ለማስተዳደር ሲሉ የፈበረኩት የጉድፈቻ አፈ-ታሪክ ሊሆን እንደሚችል ካገኘው መረጃ በማጣቀስ Asebe, (2007፡57) እንደሚከተለው ይገልጻል።

---

[3].የ2007 ዓ.ም.CSA በቦረናና ጉጂ ዞኖቹ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ብዛትን በመደመር የተገኘ ውጤት ነው።(በአጥኚው)

*Coming back to the myth, the views from Guji and some non-Guji informants provide us a different version. They see it as Gedeo's need for protection, as a mechanism constructed by the Gedeo as atool for expansion and as an extension of the myth of Deresso's adoption to the family of Guji. It is also argued that the myth of brotherhood was possibly fabricated by the Abyssinians from the myth of adoption as an administrative strategy so as to conglomerate the groups together).*

በሌላ በኩል ደግሞ የጉጂ ሚት እንደሚያስረዳው የጉጂ ኦሮሞ መጀመሪያ የተገኘው በአሁኑ የምስራቅ ጉጂ ዞን፣ አዶላ በሚባል ቦታ ውስጥ እንደሆነ ያስረዳል። ከዚህ ቦታ በመጀመሪያ የተገኙት ወደ ጊርጃ የሚባል ቦታ፤ ማለትም ከአዶላ ከተማ በስተሰሜናዊ- ምስራቅና ከገናሌ ወንዝ አጠገብ ወደምትገኘው ቦታ ተንቀሳቀሱ የሚሉ አሉ። ሌሎች ደግሞ የጉጂ መገኛ ስፍራ እራሱ ጊርጃ እንደሆነና እራሳቸውንም «ጉጂ ጊርጃ» ብለው እንደሚጠሩ Tedecha, (1988) ይገልጻል። ይህንኑ ሀሳብ አለማየሁና ሌሎች፣ (1998፡195) እንደሚከተለው ያጠናክራሉ፡-

*ብዙዎቹ ጸሐፊዎች ጉጂ ከጊርጃ መጣ በማለት የሚገልጹት መዳወላቡ ላይ የነበረው የኦሮሞ ገዳ ማዕከል ተበታትኖ በምትኩ እያንዳንዱ የኦሮሞ አብይ ጎሳ የየራሱን የገዳ ማዕከል ከመሰረተበት ወቅት ጋር የሚገጣጠም ይመስላል። ይህ ክስተት የተፈፀመው በ16ኛው መቶክ/ዘ ማብቂያበ (1594) አካባቢ መሆኑን ከገዳ የዘመን አቆጣጠር ስሌት የተገኘ ማስረጃ ያመለክታል። ቀደም ሲል እንደተገለፀው ወደ ጊርጃ ከመምጣታቸው በፊት በአዶላ አካባቢ የቆዩ በመሆናቸው የጉጂ ኦሮሞዎች በተጠቀሰው የአዶላ አካባቢ ከ16ኛው መቶ ክ/ዘ በፊት የነበሩ መሆናቸውን ያመለክታል።*

ነገር ግን እንደ አለማየሁና ሌሎች አገላለጽ ከ16ኛው መቶ ክ/ዘ በፊት በአዶላ አካባቢ ያነበሩ መሆናቸውን ይግለጽ እንጂ በሌላ በኩል የጉጂ ጎሳ ቀደም ሲል የጂሌ ኦሮሞ አካል እንደነበሩ፤ ከዚያም አሁን ወዳሉበት አካባቢ ተገንጥለው በመሄድ እንደሰፈሩ የሚገልጹ እንዳሉም ያስረዳል። በሌላ በኩል የጉጂ ኦሮሞችን ቀደም ሲል በ15ኛ ክ/ዘ ውስጥ በላንጋኖ ሀይቅ አካባቢ ሰፍረው ከነበሩበት ዘረ ያዕቆብ (1434-1468) ወደ ደቡብ እንዲያፈገፍጉ እንዳደረጋቸው Alamaayyoofi kan biroo,(1999፡ 275) ይገልጻሉ።

እንደ Berhanu ገለጻ ደግሞ ሲዳማዎች ቀደም ሲል አሁን ካሉበት ግዛት (territory) በስተ-ምስራቅ በሚገኘው የገራንባ ፐላቶዋማ አካባቢ ነበሩ፡፡ ከዚያም ጉጂዎች ከዚህ ግዛት በስተ-ምዕራባዊና ደቡባዊ ክፍል ሰፈሩ፡፡ ሲዳማዎች ባጋጠማቸው የሕዝብ ብዛት ችግር ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እንዲስፋፉ አስገደዳቸው፡፡ ይህ የመስፋፋት እንቅስቃሴ የጉጂ ኦሮሞን ከሁለት እንደከፈለውና የተወሰነው ወደ ብላቴ ወንዝ አቅጣጫ እንዳፈገፈጉ፣ ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ ርቀው ከአባያ ሀይቅ በስተ-ምስራቅ እንደሰፈሩና ሰሜናዊ የጉጂ ኮንፈደሬሽንን እንደመሰረቱ፤ ሌላኛው ቡድን ደግሞ በሰተ-ደቡባዊ አቅጣጫ በማፈግፈግ ወደ ገናሌ ወንዝና የጌዴኦ ግዛት ከአባያ ሀይቅ ምስራቃዊ የባህር ዳሪቻ ካለው ሰንሰለታማ ተራራዎች ማለትም አሁን ያሉበት አካባቢ የሰፈሩት ደግሞ ደቡባዊ የጉጂ ኮንፈደሬሽንን እንደመሰረቱ Berhanu, (1993:24-25) ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ የጉጂ ኦሮሞን በትክክል ከዚህ መጣ ብሎ ለማስቀመጥ በጣም ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ ምሁራን ካገኙት መረጃዎች እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችም ሀሳቦችን ሰንዝረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከነዚህ ጭብጦች ተነስቶ እንዲህ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ይህ ጉዳይ በራሱ ጥልቅ ጥናት እንደሚያስፈልገው የአጥኚው እምነት ነው፡፡

የጉጂ ኦሮሞ ሦስት ጎሳዎች ማለትም፡- ኡራጋ፣ ማቲና ሆኩ እያንዳንዳቸው በስራቸው ንዑሳን ጎሳዎች አሏቸው፡፡ ይኸውም፡- በኡራጋ ስር ሰባት (ገላልቻ፣ ዋጂቱ፣ ሳርቦርቱ፣ አጋንቱ፣ ደራርቱ፣ ጉላና ሀሎ) ሲሆኑ፤ በሆኩም ስር ሰባት ንዑሳን ጎሳዎች (ገላልቻ፣ ኦቦራ፣ ሚቺሌ፣ ሔራ፣ ቡንዲቱ፣ ኪኖና ባላ) ይገኛሉ፡፡ በማቲ ስር ደግሞሦስት ንዑሳን ጎሳዎች (ኢንሳለ፣ ሐንዶሃና ሂሪቃርቱ) ይገኛሉ፡፡

ማቲ ቀደም ሲል እንደነኡራጋ ሰባት ንዑሳን ጎሳዎች እንደነበራቸውና አራቱ ንዑሳን ጎሳዎች ከአርሲ ኦሮሞ ጋር በነበረው ጦርነት እንደተደመሰሱ ታደሰ በሪሶን በመጥቀስ አለማየሁና ሌሎች፣ (1998፡199) ያሰረዳል፡፡ በሌላ በኩል መረጃ አቀባዮችን በመጥቀስ ደግሞ እነዚህ አራቱ የማቲ ንዑሳን ጎሳዎች ያለቁበት ከአርሲ ኦሮሞ ጋር በነበረው ጦርነት ሳይሆን ከሲዳማ ህዝብ ጋር በተደረገ ጦርነት እንደሆነና ጦርነቱም በገናሌ ወንዝ አካባቢ ለረጅም ዓመታት የዘለቀ መሆኑን፤ ቦታውንም ሐዶ ባሌሳ የሚል መጠሪያ እንደተሰጠው ይገልጻሉ፤ ትርጉሙም «የሰው ዘር ያለቀበት ወይም ጥፋት የደረሰበት ስፍራ ማለት ነው፡፡»

በመጨረሻም እነዚህን ሚቶች እንደ ታሪክነት አምኖ ለመቀበል የሚያዳግት መሆኑን በምክንያታዊነት የሚጠቅሱት ቀደም ሲል በህዝቦች መካከል የተደረጉ ጦርነቶች እጂግ በበዛ ከሰፈራ አካባቢ ከመንቀል ወይም ከመግፋት ባሻገር እንዲህ ጎሳዎችን ነጥሎ እስከማጥፋት ደረጃ አለማድረሱን አለማየሁና ሌሎች፣ (1998፡199) ያስረዳሉ።

እነዚህ ሦስቱ የጉጂ ኮንፌድረሲዎች በሁለት ትላልቅ እርስ በርስ መጋባት በሚችሉ ቡድኖች ማለትም፡- ኮንቶማና ዳሪሙ በሚባሉ ማህበራዊ አደረጃጀት የተከፈሉ ናቸው። አከፋፈሉም በኮንቶማ ስር ከኡራጋ አራት (ዋጂቱ፣ ሳርቦርቱ፣ ጉላና ሀሎ)፣ ከሆኩ ሦስት (ገላልቻ፣ አቦራና ባላ)፣ ከማቲ ደግሞ ሁለት (ኢንሳለና ሂሪቃርቱ) ባንድ ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በዳሪሙ ስር ደግሞ ከኡራጋ ሦስት (ገላልቻ፣ አጋንቱና ደራርቱ)፣ ከሆኩ አራት (ሚቺሌ፣ ሔራ፣ ቡንዲቱና ኪኖ) እንዲሁም ከማቲ ደግሞ አንድ (ሐንዶዛ) ይገኛሉ። በእነዚህ ቡድኖች ስር ደግሞ አንድ ዓይነት ጎሳ ያልሆኑ (non-totemic) እና እርስ በርስ መጋባት የሚችሉ (exogamous) ጎሳዎች ሲኖሩ ከዚያም አንዱን ጎሳ የመሰረቱ (segments) ነገር ግን፤ የተለያዩ የዘር ሀረግ ያላቸውን ደግሞ በ ‹ቤት› (mana) በማለት እንደሚከፈሉ Tadesse, (2004፡14) ያስረዳል። ከዚህ በተጨማሪ ጉጂ በዘጠኝ ሀገና (ጉባኤ) እና በአስራ ሰባት ባልባላ (balbalaa) ወይም ቁዬዎች እንደሚከፋፈሉ መረጃ አቀባዮችን ዋቢ አድርጎ አለማየሁና ሌሎች፣ (1999፡197) ያሰረዳሉ።




ምስል፡-4 የኮንቶማና ዳሪሙ አከፋፈለን የሚያሳይ ቻርት (ምንጭ፡-ከአለማየሁና ሌሎች፣ 1999፡ 190) ተሻሽሎ የተወሰደ።

ከዚህ በተጨማሪ የአላብዱ ጉጂዎችን ያየን እንደሆነ በሀሎ ስር ሰባት (ኦቢቱ፣ ሜሪቱ፣ ዳንቱ፣ ማሲንቱ፣ ሐንጌቱ፣ አኖልቱና ባላ) የሚባሉ ንዑሳን ጎሳዎች ሲኖሩ፣ በዌስቱ ደግሞ አራት ንዑሳን ጎሳዎች (ቢቄ፣ ወንቲቱ፣ ሀርጋጋና ዳሪሙ) ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ሌላ ሁለቱ በወንዶ የሚገኙት ዐቢይ ጎሳዎች ስር ደግሞ በሸሎ ሰባት፣ በኡቱ ሁለት ንዑስ ጎሳዎች እንደሚገኙ አለማየሁና ሌሎች ያስረዳሉ (ዝኒ ከማሁ፡191-192)፡፡




ምስል፡-5 የኮንቶማና ዳሪሙ አሰፋፈር የሚያሳይ ምስል (ምንጭ፡- Haberland, 1963)፡፡

### 4.1.3.ሃይማኖት

በታሪክ እንደሚታወቀው የኦሮሞ ህዝብ ከጊዜ በኋላ ከመጡ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች በፊት የሚያመልኩት ሀገረሰባዊ ሃይማኖት "ዋቄፋና" ይባላል፡፡ "ዋቄፋና" የሃይማኖቱ መጠሪያ ሲሆን፤ ትርጉሙም በአንድ እግዚሐብሔር (waaqa) የሚያምኑ ማለት ነው (Kuntsson, 1967፡47-48)፡፡ በዚህ ሃይማኖት ስር ቃሉ (kallu) ቀዳሚውን የመሪነት ቦታ ይይዛል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ቃሉ በሰው ልጆችና በፈጣሪ መካከል በመሆን የሚያገናኝ፤ ከፈጣሪ የተሰጣቸው ስጦታ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በቃሉ ተቋም (galma qaalluu) የተለያዩ ሃይማኖታዊ ክበራዎቹ ይከናወናሉ፡፡ ቃሉ በስሩ ካሉት የመማክርት አባላት ጋር በመሆን ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ክበራዎችን ያከናውናል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ለአብነት ያህል የአካባቢው ነዋሪዎች በአየር መዛባት፣ በጠላት ወረራ እንዲሁም በወረርሽኝ በሽታ ምክንያት እንዳይጠቁ፤ እግዚሐብሔር በምህረቱ እንዲታደጋቸው የተለያዩ የመለማመን፣ የማማለድና የምስጋና ክበራዎችን እንደሚፈጽምላቸው ያምናሉ፡፡ በጉጂ ኦሮሞ የሃይማኖታዊ ስብጥርን የተመለከትን እንደሆነ እንደ CSA, (2007፡ 359-360) መረጃ በጉጂና ቦረና ዞኖች ውስጥ ከሚኖሩት አጠቃላይ ህዝብ ወደ 52.5% ፕሮቴስታንት፣ 21% የሀገረሰባዊ ሃይማኖት ተከታይ፣ 12.7% እስላም፣ 6.65% ኦርቶዶክስ፣ 1.8% ካቶሊክ ሲሆኑ 5.35% ደግሞ የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች እንደሆኑ ያሳል፡፡[4]

የሃይማኖት ስብጥሩ ይህን ይምሰል እንጂ በእነዚህ የሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞዎች መካከል ትክክለኛ የእምነት ድንበር አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ክበራዎችን አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ሲከውኑ ይስተዋላሉ፡፡ አንዳንድ በአምልኮአቸው ውስጥ የነበሩትን ክበራዎች በአዲሶቹ ሃይማኖቶች ውስጥም መቀላቀል ይታያል፡፡ እንዲሁም ለቃሉ ከፍተኛ አክብሮት የሚቸሩና የቃሉዎችን ገልማ ለአምልኮ የሚቃኙም አሉ (Bartels, 1983:14) እና ከአጥኚው የመስክ ምልከታ ከተገኘ)፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በጉጂ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በዋቄፋና ሃይማኖት ወይም በቃሉ ሃይማኖታዊ ክበራዎች ውስጥ በአንዱ ወይም በሌላው የመሳተፍ ዕድላቸው የሰፋ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ በገዳ የስልጣነ-ሢመት ማጽደቅ ክበራ ይህን ክስተት ሊያሳዩ የሚችሉ በምዕራፍ ሦስት ስር በተወሰነ ደረጃ ለማየት ተችሏል፡፡

### 4.1.4. ቋንቋ

የአካባቢው የመግባቢያና የስራ ቋንቋ ኦሮሚኛ (Afaan Oromo) ይባላል፡፡ አፋን ኦሮሞ ከምሥራቅ የኩሽ ቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል (Tadesse, 2004፡13)፡፡ አፋን ኦሮሞ በአፍሪካ ከሚነገሩ ቋንቋዎች ውስጥ ከአረብኛና ሀውሳ ቋንቋዎች ቀጥሎ በተናጋሪ ብዛት በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል (Gadaa, 1988፡15)፡፡ በጉጂ ኦሮሞ አካባቢ ሌሎች ቋንቋዎች አይነገሩም ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች መገኛ እንደመሆኗ መጠን፤ የጉጂ ኦሮሞ ከሰፈሩበት መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ፣ ከንግድ፣ ከማህበራዊና ፖለቲካዊ ትስስር፣

[4].የ2007 ዓ.ም.CSA በቦረናና ጉጂ ዞኖቹ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች ላይ የሃይማኖት ስርጭቱን በመደመርና ወደ ፐርሰንት በመቀየር የተገኘ ውጤት ነው፡፡(በአጥኚው የተዘጋጀ)

እንዲሁም በአካባቢው በተለያየ ምክንያቶች በመጡ ነዋሪዎች እንደ ጌዴኦኛ፣ አማርኛ፣ ቡርጂኛ፣ ኮንስኛና የመሳሰሉ ቋንቋዎች ይነገራሉ።

### 4.1.5. መተዳደሪያ

የጉጂ ኦሮሞዎች የሰፈሩባቸው አካባቢዎች የአየር ንብረት ቆላ፣ ደጋና ወይና ደጋ ናቸው። የተወሰኑት በቆላማው አካባቢ ያሉት አርብቶ አደሮች ሲሆኑ፣ የቀንድ ከብቶችና የጋማ ከብቶችን በማርባት ይታወቃሉ። በተለይም የአላብዱ ጉጂ እስከ 20ኛው ክ/ዘ አጋማሽ ድረስ መተዳደሪያቸው በከብት እርባታ ነበር። በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ከበሬታ የሚለካውም ባለው የከብቶች ብዛት ነው (Asebe, 2007:41)። ከብቶች በጉጂ ዘንድ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ ማህበራዊና ከከበራ አኳያ ፋይዳቸው የጎላ ነው (Tadesse, 1994:311)። ይኸውም፡- አንድ ለአቅመ-አዳም የደረሰ ልጅ ጋብቻ ለመፈፀም ያለው የከብት ብዛት እንደ መመዘኛ መስፈርት ይታይ ነበር። በሌላ በኩል አንዳንድ ወንጀል ከተፈፀመ ለተከሰተው ጥፋት ማካካሻ የሚሰጠውም ከብት ነው። በቃሉም ሆነ በገዳ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ ለመስዋዕት የሚቀርበው ከብት ነው። ስለዚህ ከብት ሁሉ ነገራቸው እንደሆነ ይቆጥራሉ። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እንደሌሎቹ የጉጂ ጎሳዎች ከአርብቶ አደርነት ወደ ከፊል አርብቶ አደርነት ተቀይረዋል። በአካባቢው በዋናነት ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ እንሰትና ማሽላ ያመርታሉ (Tadesse, 2004: 14)። ከዚህ በተጨማሪ የተወሰኑ ወረዳዎች በቡና ምርታቸው ከሀገሪቷ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን አግኝተውበታል። በማዕድን ክምችት ከወርቅ አንስቶ እስከ ታንታለምና ራዲዮ አክቲቭ ማዕድን ድረስ ወደ ሃያ አምስት የማዕድን ዓይነቶች ባለቤት ናቸው። ታዋቂው የሻኪሶ ላጋ ዳንቢ ወርቅ ማዕድን የሚገኘው በጉጂ ውስጥ ነው (Danbalaa, 2000)።

# ምዕራፍ አምስት

## ቃሉና የቃሉ ተቋም

በዚህ ምዕራፍ ስር ስለቃሉ ምንነት፣ አመጣጥ፣ የስያሜ አሰጣጥ ሂደቱን፣ የመማክርት አባላት ማንነትና ተግባራቸውንና የቃሉ ተቋም አመጣጥ ታሪክና ሌሎች መቼቶችን ከቀዳማይና ካልኣይ መረጃ ምንጮች የተገኙትን በዝርዝር ለማቅረብ ተችሏል።

### 5.1. ቃሉ

በዚህ ጥናታዊ ስራ ውስጥ "ቃሉ" የሚለው ቃል ሲነበብ "ሉ" ትጠብቃለች።ቃሉ (qaalluu) የኦሮሞ ዋቄፋና ሃይማኖት መሪ መጠሪያ ስም ነው። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች አባሙዳ፣ ኢሬሳ ገዳ እና ጂላ ማሊማ በመባል ይታወቃል (ታቦር፣ 2006፣198)። እያንዳንዱ መጠሪያ የራሱ የሆነ አመጣጥ እንዳለው የተለያዩ ጸሐፍቶች ያስረዳሉ።

ለአብነት ያህል አባሙዳ የሚለው ስያሜ የመጣው በየስምንት ዓመቱ ከሚካሄደው መንፈሳዊ ጉዞና በቃሉ ተቋም በሚካሄደው የመቀባት (የመባረክ) ሃይማኖታዊ ከበራ የተወሰደ መጠሪያ ነው። ቃሉ የሚለው መጠሪያ ስም ደግሞ የተወሰደው "ቃሉ" የሚለው ሲነበብ "ሉ"ን በማላላት ቃሉ (qalu) ከሚለው የኦሮሚኛ ግስ የረባ ሲሆን ትርጉሙም መሰዋት ነው። ይኸውም የሚቀርበውን መስዋዕት ለሃይማኖታዊ ከበራው በቃሉ አማካይነት እንደሚከወንና ከዚህ ድርጊት (መሰዋት) እንደተወሰደ ያስረዳል (Mohammed,1994)።

በሌላ አገላለጽ ቃሉ ልክ እንደ ክርስትና እምነት ጳጳስ፣ አለያሚ ልክ እንደ እስልምና እምነት ኢማም ሊመሰል ይችላል (Gada, 1988:24)።

በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ግን በአብዛኛው የሚታወቀው ቃሉ፣ አባቃሉ፣ ሞቲ (mootii) በሚሉት መጠሪያዎቹ ነው። በባህሉ መሰረት አንድ የተከበረን፣ በዕድሜ የበቃን ሰው በነጠላ ስሙ አይጠራም። ወንድ ከሆነ «አባ» (abba):- ትርጉሙም አባት ማለት ነው። ሴት ከሆነች ደግሞ «ሀዳ» (haadha):- ትርጉሙም እናት ማለት ነው። ይህን የስም ገላጭ ከመጠሪያ ስሙ በፊት በማስገባት ይጠቀሙበታል። ሞቲ የሚለው ግን ታሪካዊ አመጣጡ ከፊውዳሉ ስርዓት ጋር የተያያዘና በዚያን ወቅት የተሰጠ ተጨማሪ ስም ሲሆን ትርጉሙም "ገዥ" ወይም "ንጉስ" እንደማለት ነው። ቃሉም ከኦሮሚኛ ‹moye› ከሚለው ግስ የረባ መጠሪያ ስም ሳይሆን

አይቀርም፡፡ ምክንያቱም ‹moye› ለሚለው የኦሮሚኛ ግስ ሲሆን፤ አቻ ትርጉም /አሸነፈ/ የሚለው ይይዛል፡፡



ፎቶ፡-1 16ኛ የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ አጋ ሳቆ በገልማ ውስጥ እያሉ የሚያሳይ

ስለቃሉ ሲነሳ የትኛው ቃሉ ነው? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ለዚህ አለማየሁና ሌሎች፣ (2000፡108) በጽሑፋቸው ውስጥ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ ይኸውም፡- «ከተለያዩ የታሪክ ሰነዶች መረዳት እንደተቻለው የቦረናና የጉጂ ኦሮሞዎች «ቃሉ» ከጥንቱ የኦሮሞ «ቃሉ» ስርዓት የነበረውና መቀመጫውም መዳወላቡ ከሆነው የ«ቃሉ» ተቋም በእጅጉ የተሳሰረ እንደሆነ ነው»፡፡

ቃሉ በተለያየ መጠሪያ ቢጠራም በዚህ ጥናት ውስጥ ቃሉና አባቃሉ የሚሉትን መጠሪያዎች ተጠቅሚያለሁ፡፡ ምክንያቱም የህገረሰባዊ ሃይማኖቱ ተቋም በስሙ «ገልማ ቃሉ» በማለት ስለሚጠራበት ነው፡፡

### 5.1.1. የቃሉ አመጣጥ ሚት

ቀደም ሲል ስለቃሉ ምንነት በስፋት አይተናል፡፡ ነገር ግን ቃሉ ማን ነው? ከየትስ መጣ? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ለዚህ መልስ ከተለያዩ መረጃዎች የተገኙትን እንደሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በመጀመሪያ መረጃ አቀባዮቹ የአካባቢውን ሚት በመጥቀስ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *ቃሉ ከዕለታት አንድ ቀን ፕላስቲክ በመሠለ ከረጢት (ሩፋ) ተጠቅልሎ ከሠማይ ወረደ፡፡ የወረደውም ልክ እንደማሪያም መቀነት (ቀስተ-ደመና) ጥቅሉ ከላይ እየተፈታ እሱን መሬት አደረሰ፤ ከዚያም ጥቅሉ ወደሰማይ ተጠቅልሎ ተመለሰ፡፡ ይህ ክስተት የተፈፀመው በጉጂ ዞን፣ በአዶላ ወረዳ፣ ኦባ (ኦቢቲ) በሚባል ቦታ ነው፡፡ ቃሉ ፕላስቲክ በመሠለ ከረጢት (ሩፋ) ውስጥ እንዳለ፤ ከሱ አጠገብ ከርቤ (qunbii) እና ‹ካላቻ› አብሮት ተጠቅልሎ ነበር፡፡ ቀድመው ያዩት የዋጂቱ ጎሳ አባላቶች ነበሩ፡፡ አጠገቡ ደርሰው ለመንካት ስለፈሩ ወደመንደሩ በመሄድ የተፈጠረውን ተናገሩ፡፡የአካባቢው ሰዎችም ሊያናግሩት ቢሞክሩም ምንም መልስ አልሰጣቸውም ነበር፡፡ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በማገናኘት ለማዋራት ቢሞክሩም ውጤት ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም ከገለልቻ ጎሳ ወገን የሆነች ልጃገረድ ስትመጣ ፈገግታ አሳያት፡፡ ከዚያ ወደቤት እንዲሄዱ ጠየቀችው፡፡ እሱ ግን እኔ የሰው ቤት አልገባም፤ አደራሽ (ገልማ) ስሩልኝ አላቸው፡፡ ሰዎቹም ከእግዚአብሔር የመጣ መልዕክተኛ ነውና ትዕዛዙን እንፈጽም በማለት ተሰራለት፡፡ ከዚያም ወደገልማው ተወሰደ፡፡ ቁርበትም ተነጠፈለት፡፡ ወተት በቅል አምጥተው ሲሰጡት አልቀበልም አላቸው፡፡ ከኋላ ግን በማለቢያ (Okolee) በስጦታ መልክ (gumaacha) ነው ሊሰጠኝ የሚገባ አላቸው፡፡ እነሱም እንዳላቸው አደረጉ፡፡ ሰዎቹም ያችን ከገለልቻ ጎሳ ወገን የነበረችውን ልጅ እዚያው ትተዋት ወደ ቄዬቸው ሄዱ፡፡ ከዚያ ሁለቱም አብረው መኖር ጀመሩ፡፡ ልጆችም አፈሩ፡፡* (ሞኮና ናጋዎ፣1/12/2006 ዓ.ም. አባያ ወረዳ፣ ከላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

በይዘቱ ብዙም ልዩነት ባይኖረውም Hinnant,(1977፤54) ደግሞ ከመረጃ አቀባዮቹ እንዳገኘሁት በማለት ስለቃሉ አመጣጥ ሲገልጽ፡-

አንዲት ልጃገረድ ከአረንጓደ መስክ ላይ ጥጆች ትጠብቅ ነበር። ጥጆቹ በድንገት ሳር ከሚግጡበት ወደ አንድ ቦታ ፍዝዝ ብለው ይመለከቱ ጀመር። በዚያ ቦታ የሆነ ልጅ ተጋድሟል (ትክክለኛ እድገቱን ጠብቆ የተወለደ ሰው፣ ነገር ግን ህጻን ልጅ የሚመስል።) ጥጆቹ ወደ ህጻን መሳዩ ሰውዬ ተጠጉ፣ ነገር ግን ወደ እሱ በቀጥታ መመልከት አልቻሉም። ከዚያ ወደኋላ ተመልሰው እንደገና ሳር መጋጥ ጀመሩ። ልጃገረዷ በርቀት ቆማ ስለነበር ምን እንደተከሰተ አላወቀችም ነበር። ጥጆቹ ይመለከቱት ወደ ነበረው ነገር ለማየት ተጠጋች። በጥጆቹ መሀከል በተለያዩ ከለር መስመር፣ መስመር ያለው ልብስ (ruufa) ተመለከተች። ምን እንደሆነ የምታውቀው ነገር የለም፣ ከዚያ ለወላጆቿ ለመንገር ሮጠች፣ያየችውንም ነገረቻቸው። እነሱም ወደቦታው በመምጣት ተመለከቱ። ሌሎችም በአካባቢው የነበሩ በመምጣት ሜዳውን ሞሉት። ቃሉ ከጨርቁ ውስጥ ለመውጣት ሞከረ፣ ነገር ግን አካሉ ሙሉ ለሙሉ ተሸፍኗል። በዚህ ምክንያት የተሰበሰበው ህዝብ ምን እንደሆነ ለመለየት አልቻሉም ነበር። አንድ ሰውዬ ጨርቁን ከመሀል በኩል ቢቀደድ የሚል ሀሳብ አቀረበ፣ በሀሳቡ ተስማምተው ሲቀደድ እራሱ መንቀሳቀስ ጀመረ። ይህ በባህል አዋቂ አማካይነት ከፊት-ለፊት በእራሱ መካከል ቢቀድ ጥሩ እንደሚሆን ሀዩ (hayyuu) ተናገረ፣ እናም የሱ ቃል ተቃባይነት አገኘ። ወዲያውኑ ሀዩው የህጻን መሳይ ሰውዬውን ፊት አየ፣ አይኑም ታወረ። ሁሉም የሚገርም ነበር። ህጻን መሳይ ሰውዬው በሀዩው ላይ ምራቁን እንትፍ አለበት፣ የሀዩውም ብርሃን ወዲያው በራለት። እስከዚያን ጊዜ ድረስ ህጻን መሳዩ ሰውዬ አይናገርም ነበር። ሰዎች ሲያናግሩት፣ እሱ ግን ምላሽ አይሰጥም።

በመጨረሻም መጀመሪያ ያገኘችውን ልጃገረድ አመጡለት። እሱም ተመለከታት፣ ከዚያም ፈገግታ አሳያት። ቃሉም ለህዝቡ እግዚአብሔር (ዋቃ) እሱን ወደታች እንዳወረደው ነገራቸው። በቀኝ እጁ የቡና ፍሬዎች፣ በግራ እጁ ደግሞ ከርቤ (Qunbii) ይዞ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ ከብረት የተሰራ በርጩማ፣ገባሰም አብሮት ነበር።በሩፋው ጨርቅ ላይ እባብ ነበር፣የተለየ ዓይነት እባብ /ኮብራ/ (buuti) የሚባል ነው። ለህዝቡም ሄደው ከወንዝ በወንፊት ውሃ ቀድተው እንዲያመጡ፣ በልብሳቸው ደግሞ እሳት ይዘው እንዲያመጡ ነገራቸው። ወንፊቱ ውሃውን ሊይዝላቸው አልቻለም፣ ልብሱም ተቃጠለባቸው። እሱ በማንኛውም መንገድ ሁለቱንም በራሱ የማድረግ

*ችሎታ ነበረው። ነገር ግን እሱ ወደ መሬት በወረደበት ወቅት፣ በአርሲ፣ በቦረና፣ በጉጂና በሲዳሞ መካከል ጦሪነት እየተካሄደ ነበር። እሱን ወደ አላብዱ (Alaaddu) የተወሰደው በዚህ ምክንያት ነበር* በማለት አትቷል።

ከነዚህ *ሚቶች* የምንረዳው የመጀመሪያው ቃሉ የመጣው ወይም የወረደው ከሰማይ እንደሆነና በኋላም ከዚያች የገለልቻ ጎሳ ልጃገረድ ጋር አብረው እንደኖሩ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በቃሉ ተቋም ከቃሉ መቀመጫ ስር ወይም ምሶሶ ስር ጉድጓድ ውስጥ የሚቀመጡ እባቦች አሉ። እነዚህ እባቦች ሀጢያት ሰርቶ፣ በውስጡ ተንኮል ይዞ የሚመጣን ሰው ይናደፋሉ ተብሎ ይታመናል።

በተመሳሳይ መልኩ በተለያዩ የኦሮሞ አካባቢዎች ስለቃሉ አመጣጥ የሚነገሩት *ሚቶች* በተለያየ አገላልጽ ቢሆንም መሰረቱ ከሰማይ እንደሆነ (Kuntsson, 1967;  and Mohammed, 1994) በስፋት ያስረዳሉ። «ቃሉ» በኦሮሞ ባህል መሰረት ታላቅና ክቡር ከመሆኑ የተነሳ ሰዎች ሊተዳደሩበት የሚገባቸውን ህግጋት ሁሉ ያውቁ ዘንድ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ቅዱስ ሰው ነው ተብሎ ይታመናል።

## 5.1.2. የቃሉ ስያሜና መስፈርቶቹ

በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የቃሉ ስልጣነ ሢመት ሂደትን የቃሉ ስያሜ አሰጣጥ (sirna moggaasa qaalluu) በመባል ይታወቃል። ይህ የስያሜ ከበራ የሚጀምረው ከመጀመሪያው የቃሉ አመጣጥ *ሚት* ጋር ትስስር ያለው ሂደት በመሆኑ ነው። ይኸውም፡- ቃሉ ከሰማይ ሲወርድ እንዴት ወረደ? ከዚያ የት ወረደ? ከማን ጋር ተገናኘ የሚሉት *ሚቶች* ለአሁኑ ተሰያሚ ቃሉ እንደ መሰረታዊ መመልመያ መስፈርቶች ተቀምጠው እናገኛለን።

አንድ በማገልገል ላይ ያለ ቃሉ በሕይወት ዘመኑ ሙሉ ያገለግላል። ነገር ግን የነበረው ቃሉ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ፤ እሱ ላይ የነበረው መንፈስ አይሞትም ተብሎ ስለሚታመን ስልጣነ መለኮቱ ይቀጥላል። ይህም የሚሆነው ከልጆቹ ውስጥ ማህበረሰቡ ባዋቀረውና ባስቀመጠው ሃይማኖታዊና ባህላዊ መስፈርቶችን የሚያሟላው ተፈልጎ ይሰየማል። ከቃሉ ስያሜ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ አንዱ ቀጣዩ አባቃሉ የሚሆነው ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች በማህበረ-ባህላዊ ዕውቀት ተዋቅረው የተቀመጡ አሉ። እነዚህ መስፈርቶች ምን ምንድናቸው? የሚሉትን ቀጥሎ እንመለከታለን።

የጉጂ ኦሮሞ የቀድሞው ቃሉ ሕይወቱ እንዳለፈች ስለእሱ መሞት ከመደናገጥ ይልቅ፤ ቀጣዩ ቃሉ ማን ይሆናል? የሚለው ነው የሚያሳስባቸው። ስለዚህ አስከሬኑ እዚያው እንዳለ መስፈርቱን የሚያሟላ ይመረጣል። ይኸውም፦

1. ከቃሉ የተወለደ መሆን አለበት፣

እንደጉጂ ኦሮሞ የመጀመሪያው ቃሉ የዘር ሀረግ ተከትሎ ስልጣኑ-ሢመቱን መተካት ያለበት ከቃሉና ከሀዳ አንባ የተወለደ መሆን አለበት። በቦረና ኦሮሞ ዘንድ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው። ይኸውም አንድ የቦረና ቃሉ ሊሆን የሚችለው ከቃሊቲ የሚወለድ ልጅ ነው። እንደ ቦረናዎች ቃሊቲ ማለትም፦ ከቃሉ ባለቤቶች ውስጥ አንዷ ስትሆን፤ ከቃሉ ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንደማትፈጽም ይታመናል። በእሱ ፈንታ አንድ በስም የማይታወቅ ሰው፤ ነገር ግን ልክ እንደወዳጅ እንዲሆናት የተፈቀደለት ሰው ጋር በውስጠ ታዋቂነት ግንኙነት እንድትፈጽም ይደረጋል። ከዚህ በመነሳት የምወለደውን ልጅ ‹‹የቦረና ልጅ›› ይሉታል። የቃሉ እናት የመሆን መብት ያላትም እሷ ነች። ለዚህም እንደምክንያት የሚቀርበው ልክ በብዙዎች ባህል ውስጥ እንደሚደረገው ሁሉ አንድ መሪ ወደ ስልጣን ሲመጣ ከመጣበት ማህበረሰብ የዘር ሀረግ ጋር የማያያዝ ችግሮች እንዳይፈጠር ሊሆን እንደሚችል Asmarom, (1973:46) ይገልጻል። ይህ በራሱ አንድ እራሱን የቻለ ፍልስፍና ነው።

2. የሚሰየመው ልጅ ከገለልቻ ጎሳ ከሆነችው ሚስት የተወለደ መሆን አለበት፣

የመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጋብቻ የዘር ሀረግ መከተሉን የሚያመላክት ነው። ይኸውም የመጀመሪያው ቃሉ ከሰማይ እንደወረደ የተዋወቃትና በኋላም የትዳር አጋሩ የሆነችው የገለልቻ ልጃገረድ እንደነበረች ከቀረበው ሚት ለመረዳት ችለናል። ስለዚህ ያንኑ ፈለግ ተከትሎ የሚከናወን በመሆኑ ይህን መስፈርት ማሟላት ይጠበቅበታል። በቦረና ኦሮሞ ግን በተ.ቁ. አንድ ላይ እንደተመለከትነው ቃሉ ሊሆን የሚችለው ከመጀመሪያው ቃሉ ሚስቶች ውስጥ ከቃሊቲዋ ሲሆን የቃሉ የአብራኩ ክፋይ አይደለም።

3. ዓይኑ ሸውራራ ያልሆነ፣
4. አካሉ ሙሉ የሆነ፣
5. ግራኝ እጅ ያልሆነ፣
6. በተለምዶ ‹‹ማሪያም የሳመው›› የማይባል፣
7. ጠባሳ የሌለው፣አካሉና ተክለ-ቁመናው የተስተካከለ፣
8. ስስ ላስቲክ በሚመስል (ruufa) ነገር ተሸፍኖ የተወለደ፣

የመጀመሪያው ቃሉ ከሰማይ በሩፋ ውስጥ ተሸፍኖ ከመውረዱ ጋር የተያያዘ ሚት ስላለ አሁንም ያንኑ አካሄድ የሚያመላክት መስፈርት ይመስላል፡፡ *(አቶ አባባ ቶቱ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቶቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ18/11/2007 ዓ.ም.)*

9. በሌላ በኩል ደግሞ እውነት የሚናገር፣ ወደ እግዚኣብሔር መንገድ ሰውን የሚመራ፣ በስሩ የሚኖሩትን ማህበረሰብ ያለ አንዳች መድሎ በአንድ ዓይን የሚያይና የመሳሰሉት የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

የእግዚኣብሔር መልዕክተኛ የሚሰራው የእግዚኣብሔርን ስራ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ እነዚህንና ሌሎችንም መልካም ምግባር ያለው መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ነገር ግን አንዳንዴ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሁለት ውድማማቾች ሲኖሩና አባታቸው (ቃሉ) መሞታቸውን ሲያውቁ ከሁለቱ የተሻለ ባህሪይና ችሎታ አለው ብለው የሚያምኑትን አንደኛውን በመምረጥ እንዲዘጋጅና ስለስራዉም አንዳንዱ ምክር እንደሚለግሱ ከመረጃ አቀባዩ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

ከዚያም እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ተመርጦ ለስያሜ የሚያበቃውን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይፈጸማሉ፡፡

ሌላው ቃሉዎች በአገልግሎት ዘመናቸው ደግሞ ከተወሰኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና ሥራዎች የተገደቡ ናቸው፡፡ ይኸውም፡-

- በተሰበረ ወይም በተሰነጠቀ ወንበር ላይ አይቀመጡም፣
- ፀጉራቸውን አይላጩም፣
- አያርሱም፣ አይቆፍሩም፣
- ከሰው ጋር ዘወትር አይገናኙም፣
- ከገዳ መሪዎች ጋር መንገድ አይተላለፍፉም፣
- በበዓላት ቀን ካልሆነ በስተቀር አያርዱም፣
- ገዳን ይመርቃሉ፣ የተጣሉትን ያስታርቃሉ፣
- የበዓላት ቀን፣ የሙዳ ቀን፣ የጸሎት ቀን፣ የምርቃት ቀን፣ ከለቻ በግንባራቸው ላይ ያደርጋሉ፣ ጫጩ ያጠልቃሉ፣ ሩፋ ይጠመጥማሉ (ታቦር፣ 2006፣198-199)፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የቃሉ ስያሜ ሲባል በሁለት መልክ ይከናወናል። ይኸውም፡- መጀመሪያ እንደ ማንኛውም የጉጂ ኦሮሞ ልጅ ከተወለደ በኋላ የመጠሪያ ስም ይሰየምለታል። ይኸውም፡- አንድ ልጅ ከተወለደ ወንድ ከሆነ ከአራተኛው ቀን በኋላ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ከሶስተኛው ቀን በኋላ፤ በሀገሬው ባህልና ወግ ላይ ተመስርተው የተወለደበትን ጊዜ፣ ቀን፣ ወርና ቦታ ላይ ተንተርሰው ይሰይማሉ።

ሁለተኛው ስያሜ ደግሞ ቃሉ የሚሆነው ልጅ የአባቱን ቦታ ተክቶ እንዲሰራ የተቀመጠለትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ስልጣነ ሢመቱን ሲፈጽም የሚሰጠው ሰያሜ ሲሆን፤ ከዚያም አባቃሉ ሊባል ይችላል።

እንደ መረጃ አቀባዩ አገላለጽ የቀድሞው ቃሉ ከዚህ ዓለም ሕይወቱ ካለፈች (yoo hancufa liqiimse) ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርርቶች የሚያሟላ ወንድ ልጅ ካለ የአስር ዓመት ልጅም ቢሆን የስያሜ ከበራ ይፈጸምለታል። ምክንያቱም ስያሜው የሚካሄደው ከመጀመሪያ የጋብቻ ስርዓት ጋር በመሆኑ ነው። ነገር ግን ልጅ እግር ከሌለ ከትላልቆች ውስጥ ሊመረጥ ይችላል። አንዳንዴም መስፈርቶቹን የሚያሟላ የደረሰ የቃሉ ልጅ ከሌለ፤ ከሟቹ ቃሉ ወንድሞች ውስጥ መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሊሰየም ይችላል።

በሌላ በኩል ከቀድሞው ቃሉ ልጆች ውስጥ የሚሰየም ሰው ከታጣ፤ ትዳር ከመሰረቱት ውስጥ ሊሰየም ይችላል። ስለዚህ ይህ የሚሰየመው ሰው ቀድሞ የፈጸመው ጋብቻ የተለያየ የጋብቻ ዓይነት ሊሆን ይችላል። ያገባትም ሴት ከጉጂ ኦሮሞ የተለያዩ ጎሳዎች ወይም ከሌላም ብሔር ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ለቃሉ ስያሜ የሚያስፈልገው ትልቁ መስፈርት ጋብቻ መፈጸም ይጠበቅበታል። ይህ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ደግሞ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል የጋብቻ ስነ-ስርዓት የተለየ ክንዋኔዎችን የያዘ ነው፤ ብዙ ልዩነቶችም አሉት።

እንደሚታውቀው በኦሮሞዎች ዘንድ የተለያዩ ዓይነት የጋብቻ ስርዓቶች አሉ። ለምሳሌ ማጨት (kadhaa)፣ ጠለፋ (buta)፣ ወዶገባ (addibaanaa)፣ ማባበል (awadii)፣ የውርስ ጋብቻ (dhaaluu) እና ሲጋባ (sigabaa) ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ለቃሉ ስያሜ የሚፈጸመው የጋብቻ ስርዓት በልመና ወይም በማጨት የሚከናወነው ነው። ለቃሉ ስያሜ የምታስፈልገውን ልጃገረድ ከማጨቱ አንስቶ እስከ ጋብቻው ዕለት ድረስ ያለዉን የጋብቻውን ሂደት በስፋት በ 6.5 ስር ተተንትኖ ቀርቧል።

እስካሁን ባለው መረጃ 16ኛው አባቃሉ ተሰይመዋል፡፡ እነሱም ከመረጃ አቀባዮቼ ባገኘሁት መረጃ መሰረት በቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው ያስቀምጧቸዋል፡፡

1ኛ. አባ ቃሉ ቁሉቤ ሉኮ
2ኛ. አባ ቃሉ ጋዶዬ ቁሉቤ
3ኛ. አባ ቃሉ ዳንቢ ጋዶዬ
4ኛ. አባ ቃሉ አጋ ዳንቢ
5ኛ. አባ ቃሉ ጋላኒ አጋ
6ኛ. አባ ቃሉ ቦሩ ጋላኒ
7ኛ. አባ ቃሉ አዳዮ ቦሩ
8ኛ. አባ ቃሉ ሳቆ አዳዮ
9ኛ. አባ ቃሉ ኮዮ ሳቆ
10ኛ. አባ ቃሉ በሪሶ ኮዮ
11ኛ. አባ ቃሉ ኤሉ በሪሶ
12ኛ. አባ ቃሉ ሀርባዬ ኤሉ
13ኛ. አባ ቃሉ ቶቴ ሀርባዬ
14ኛ. አባ ቃሉ ናጋኦ ቶቴ
15ኛ. አባ ቃሉ ሳቆ ናጋኦ
16ኛ. አባ ቃሉ አጋ ሳቆ ናቸው፡፡

ከነዚህ ውስጥ አባቃሉ ሂርባዬ ለየት ያለ ታሪክ እንዳላቸው ይነገርላቸዋል፡፡ ይኸውም አባቃሉ ሂርባዬ ብዙ ዓመት ካስቆጠሩ ቃሉዎች አንዱ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም የሶስት ትውልድ ዕድሜ ኖረው በአራተኛው ሰው ዕድሜ የሞተ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ስለ አሟሟታቸውም ሲያስረዱ፡-

> ብዙ በመቆየታቸው ፈጣሪያቸውን እንዲያሳርፋቸው በመጠየቅ ነው፡፡ ምክንያቱም የኖሩት በግምት ከ300 ዓመት በላይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚያም ሰባት የከብት ኮርማ፣ ሰባት ትላልቅ እንስራ ጠጅ (Duloo torba) አዘጋጅተው፣ ፈጣሪውን እንዲህ ብሎ ለመነ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ! ይሄው የሦስት ትውልድ ጓደኞቼን እድሜ ኖሬ አራተኛው ላይ ነኝ፤ ስለዚህ ውሰደኝ፡፡›› ብሎ ለፈጣሪው ነገረ፡፡ ሳይታመም፣ አንድ ነገር ሳይሆን፣ ህመም ሳያየው እግዚአብሔር ባለው ጊዜ ወሰደው፤ ይህንን አውቃለሁ፡፡ በዚያን ዘመን ወደ 300 ዓመት ያህል ኖረ፡፡ ልክ እንደ ማቱሳላ እንደሚባለው ነው፡፡ ሌላም እንዲሁ ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ አባቃሉ ኤሉ ወደ 200 ዓመት ኖሯል፡፡ የቀብሩም ቦታ ዶኬኖ የሚባል ቦታ ነው፤ አስከሬኑ ያረፈው እዚያ ነው፡፡ በባንቆ ቀበሌ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ በዚያን ዘመን የሰው ልጅ ዕድሜ በጣም ረጅም ነበር፤ እንዳሁኑ ሰው ዕድሜው አጭር አልነበረም፡፡ (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ 13/12/2007 ዓ.ም.፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

በዚህ ላይ በማከል አቶ ጎበና ጉጆ፡- ስለቃሉ ሲያብራሩ፡-

ጎሳቸው ትልቅ ነው፤ ዕድሜያቸውም ረጅም ነው፤ መርቀውም ያደርሳሉ። ከረገሙም ይደርሳል። የነሱ የሆነ ሁሉ ጥሩ ነው። ጥሩ ኑሮ ይኖራሉ፤ በዕድሜያቸውም ብዙ ይቆያሉ። የእሱ አባት እያሉ ወደ አቶ ሞኮና ናጋአ እያመለከቱ (አባ ቃሉ ናጋአ ቶቴ) እራሱ በጣም ቆያቷል። ወደ 150 አመት አይሆንም?፤ አዎ ይሆናል። እንዲህ ቆይተዋል፤ የእሱ አባት እንኳን። የሰው ልጅ 150 አመት የሚኖር አለ? የለም። በማለት ገልጸዋል። (አቶ ጎበና ጉጀ፣ 13/12/2007 ዓ.ም.፣ ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

ከነዚህ መረጃዎች የምንረዳው አንዳንድ ቃሉዎች ረጅም ዓመት እንደኖሩና የስልጣን ሽግግሩም ከአባት ወደ ልጅ መሆኑን በቅደም ተከተል ያሳየናል።

## 5.1.3. የቃሉ መማክርት አባላትና ተግባራቸው

በመጀመሪያ ደረጃ ቃሉ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን የሚከውነው ከተለያዩ የመማክርት አባላቱ ጋር በጋራም ሆነ በተናጥል በመሆን ነው። የቃሉ መማክርት አባላት ቃሉ ጨምሮ የገዳ አባቶች፣ ኮከብ ቆጣሪዎች፣ ካሎዎች፣ ሞራ አንባቢዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ሀዳ አንባ ናቸው። ለቃሉ ሀዳ አንባ እንደሆነችው ሁሉ፤ ለገዳም አዳ ቦላ ትሳተፋለች። በመማክርቱ ውስጥ ቃሉ የመሪነቱን ቦታ ይይዛል። በመቀጠል አባገዳዎች የሁለተኛውን ቦታ ሲይዙ፤ በራሳቸው ተቋም ደግሞ የመሪነቱን ቦታ ይይዛሉ። ሌሎቹ አባላት በአጋርነት የሚያገለግሉ ናቸው።

እያንዳንዱ የቃሉ መማክርት አባላት በሃይማኖታዊ ከበራዎች ወቅት የእነሱ መረጃዎች ተዳምሮ ያለፈው ወቅት ምን ይመስል ነበር? ወይም እንዴት አለፈ?፣ አሁንስ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንገኛለን? ለወደፊት ምን ይጠብቀናል? ለሚሉት ጉዳዮች ሁሉ ፍንጭ አመላካቾች ናቸው። ቃሉ ደግሞ በነዚህ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ለየትኛው ክስተት ምን ዓይነት ከብት ለመስዋዕት እንደሚቀርብ፣ በየትኛው የአምልኮ ስፍራ እንደሚከወን ያሳውቃል። ገዳዎችና ሽማግሌዎች ህብረተሰቡን የማስተባበሩን ኃላፊነት ይወጣሉ። ይህንና የመሳሰሉትን ተግባራት በእያንዳንዱ የመማክርት አባላት ምንና እንዴት እንደሚከወኑ በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### 5.1.3.1. የቃሉ ተግባራት

የቃሉ ተቋም ለጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰብ ያለውን የጎላ ባህላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች በስፋት ለማየት ችለናል። እንደ ሃገረሰባዊ ሃይማኖቱ ተከታዮች እምነት ቃሉ በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ምድር ያወረደው የሰው ልጅ በምድር ሲኖር

እንዴት መኖር እንዳለበት ከፈጣሪ የተሰጠውን ህግጋት ለማስተማርና ህግጋቶቹንም ለማስከበር ነው። ቃሉ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚያደርገው በመንፈስ (ayyaana) በኩል ነው።

እንደሚታወቀው የዋቄፋና ሀገረሰባዊ ሃይማኖት በጽሑፍ የሰፈረ የእምነቱ ህግ (ዶግማ) የለውም። እግዚሐብሄር የእምነቱን ህግጋትን ለምዕመኑ እንዲያስተምርና እንዲያስጠብቅ የሰጠው፤ በሰው ልጆችና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ እንዲያገለግል፤ ከሰማይ ያወረደው ቃሉን እንደሆነ አብዛኛው በጉዳዩ ላይ ጥናት ያካሄዱ አጥኚዎችና የጉጂ አዛውንቶችም ይገልጻሉ። ስለዚህ የቃሉ ተቋምና የቃሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ለሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ማዕከል ናቸው (Mohammed, 1994:6-9)። ምክንያቱም ቃሉ ለሰው ልጆች መተዳደሪያና ሊከበሩ የሚገቧቸውን ህግጋት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠውና እነሱንም የሚያስተምርና የሚያስከብ እንደሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታመናል።

ታቦር (2006) የብሩ ፀጋዬን ሀሳብ በመጥቀስ ዋቃ ለቃሉዎችና ለአያንቱዎች ነቢያትና ሐዋርያት የገለጹላቸውና እንዲከበሩ ያስተምሩ ዘንድ ያዘዛቸው ምሰሶ (አእማድ) ሕግጋት እንደሚከተለው ይዘረዝራል። እነሱም፡-

1. ***ማምለክ (Waaqeeffachu)፡-*** *ዋቃን የማምለክ ትዕዛዝ፤ እያንዳንዱ ግለሰብ፣ ቤተሰብና የአካባቢ ነዋሪ በግልና በጋራ የሚያከናውነው የዕለታዊና ወቅታዊ ስርዓተ ጸሎትና ምስጋና እንዲሁም፣ የስርዓተ መስዋዕት እንዲሁም፣ የስርዓተ ቀብር ትግበራዎች ያሉት ነው።*
2. ***እቀባ (Laguu)፡-*** *የእቀባ ትዕዛዝ መደረግ የሌለበትንና መበላት የሌለበትን ማናቸውንም ነገር ያካተተ ነው። በዋቄፋና ሃይማኖት መደረግ የሌለባቸውና ክልክል "ላጉ" የሆኑት የሰው ነፍስ ማጥፋትን፣ ስርቆሽን፣...ያካትታል።*
3. ***ሳፉ (Safuu)፡-*** *በዋቄፋና ሃይማኖት ልጆች ወላጆቻቸውን፣ ታናናሾች ታላላቆቻቸውን፣ ወጣቶችና ጎልማሶች አረጋዊያንን፣ እያንዳንዱ ዋቄፋታ ቃሉዎችንና አያንቱዎችን ማክበርና ቀድሞ ወንዝ ከመሻገር፣ ቀድሞ ከመመረቅ፣ እንደተቀመጠ ሰላምታ ከመስጠትና በነጠላ ስም ከመጥራት መታቀብ ይጠበቅበታል። ዋቃ ቀኑን ለሰዎችና ለቤት እንስሳት፣ ሌሊቱን ለዱር አራዊት የፈቀደ በመሆኑ ይህ መሻር እንደሌለበትና የደኖች ልምላሜና የወንዞች ንጽህና መጠበቅ እንዳለበት የሚያዝ ሕግ ነው። ፈረሃ-እግዚሐብሔርን፣ ወግና ባህልን መጠበቅ እንደማለት ነው።*

4. **ቅዱስና ክቡር (Ulfaa)፦** ወንዞች፣ መልካዎች፣ ተራሮችና ኮረብቶች፣ ኦዳ፣ በኩ፣ ጫጩ (ዛጎል) እና ከለቻ፣ ሲቄ፣ ቀነፋና የጫጩና ከለቻ መጎናጠፊያዎችና የገዳ ጉዞ፣ ባንዲራዎች (Faajjii) ክቡረ ክቡራን ናቸው።

5. **በፀጋ መቀበል (Hooda)፦** እንደ አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እህትና ልጅ ያሉ የቅርብ ስጋዎች እንኳን ሲሞቱ ከቀብራቸው በኋላ እንደ ዋቃ ፈቃድ በፀጋ ተቀብሎ፤ በዚህ በቃ ይል ዘንድ "ሆዳኔ" ይባላል እንጂ፣ ሀዘኑ ለምን ደረሰብኝ በሚል ዋቃን አያማርሩትም በማለት ያስረዳል።

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ሳፉ (safuu) የምንለው የባህላዊና ተፈጥሯዊ ሕጎች ጥምረት ነው። በኦሮሞ ዘንድ ባህላዊ ሕጎች የምንላቸው ታናሽ ታላቁን የማክበር፣ ልጆች ወላጆቻቸውንና አዛውንቶችን የማክበርና የመሳሰሉትን ያካትታል። ተፈጥሯዊ ሕጎች የሚባሉት ደግሞ ጋብቻ በተመለከተ በተቃራኒ ጾታዎች መካከል ካልሆነ አይፈቀድም፣ እንዲሁም ከእንስሳት ውስጥ የሚበሉና የማይበሉ አሉ። ባጠቃላይ ሳፉ ፈርሃ-እግዚሐብሔርን፣ ወግንና ባህልን መጠበቅ እንደማለት ነው።

እነዚህን የዋቄፋና እምነት ህግጋቶች ከእግዚሐብሄር ወደ ቃሉ፣ ከቃሉ ደግሞ ወደ ምዕመኑ፤ እንዲሁም ከምዕመኑ ወደ ምዕመኑ እየተላለፈ እዚህ የደረሰው በስነቃልና በድርጊት አማካይነት ነው። ይህ ባህሪይ ደግሞ የማንኛውም ሀገረሰባዊ ሃይማኖት መተላለፊያ መንገድ ናቸው።

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን የእግዚሐብሄር ህግጋት በዋናነት የሚያስከብረው ደግሞ ቃሉ እንደሆነ Alemayehufi kan biroo, (1999፡115) ያስረዳል።

እግዚኣብሔርን ማመን የሚያመለክተው እግዚኣብሔር በዓለም ላይ ለሚኖሩ ሁሉ ምንጭና መገኛው እሱ እንደሆነ የሚያሳይ መሰረታዊ እምነት ነው (Van de Loo, 1991፡284)። የጉጂ ኦሮሞ እግዚኣብሔር ብሎ የሚጠራው ፈጣሪውንና ሰማዩን ባንድ ላይ ነው። አንዳንዴ ሰማዩን ወይም ህዋውን ላይ (gubbaa) በማለት ከላይ ያለው እግዚኣብሔር በማለት የሚጠሩበት ጊዜም አለ። በሁለቱም አቅጣጫ እግዚኣብሔርን ሲጠሩ ፈጣሪና ማደሪያዉን/ መኖሪያውን ጭምር ነው። ለዚህ ጥሩ መገለጫው አንዳንድ የጉጂ ሽማግሌዎች በምርቃንና በእርግማን፤ እንዲሁም በምልጃ ፀሎት ወቅት ወደላይ በማንጋጠጥና እግዚኣብሔርን ከመገኛው በመለማመን ነው።
ሌላው የጉጂ ኦሮሞ እግዚኣብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ (uuma) እንደሆነና በሰማይና በምድር መካከል ከሱ የተሰወረ ነገር እንደሌለ ያምናሉ። ከዚህም የተነሳ በሰው ዘንድ ለተሰሩ

ጥሩ ስራ (waan gaarii) እና ኩነኔ (cubbuu) ሲሆኑ፤ ለእግዚኣብሔር ማስረጃዎቹ ደግሞ ሰማይና ምድር እንደሆኑ ያምናሉ።

አንዳንዴ ይህ ሁሉ ልመናና መስዋዕት ቀርቦ ነገሮች እንደቀድሞው በሰላማዊ መንገድ ላይቀጥል ይችላል። ይኸውም ልጅ ያልወለደች ሴት መሀን ሆና ትቀራለች፣ ሰዎች ይታመማሉ፣ ከብቶች ይሞታሉ። የጉጂ ህዝብ በሌሎች እጅ ወድቀው ሊጨቆኑ ይችላሉ። በመጨረሻም ይህ ሁሉ የሚሆነው በእግዚኣብሔር ፍቃድ እንደሆነ እግዚኣብሔር ያችን ሴት በዚህ መልኩ እንዲትኖር ፈጥሯታል ወይም "እግዚኣብሔር ከእኛ ዘንድ ርቋል" በማለት ይገልጻሉ (Van de Loo, 1991:284)። እንደ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ይህ ከእግዚኣብሔር ህግጋት ውስጥ የእግዚኣብሔር ስራ ነው ብሎ በፀጋ መቀበልን ያሳያል።

በተመሳሳይ መልኩ በኦሮሞ አተያይ ይህ ዓለም ሦስት ነገሮችን ይዟል። እነሱም፡- “አያና”፣ ”ኡማ” እና, ”ሳፉ” ናቸው። “አያና” ቀደም ሲል እንደተገለፀው መንፈስ እንደማለት ሲሆን፤ የዋቃ አንዱ መከሰቻ ነው። ”ኡማ” የሚለው ቃል ደግሞ ድርብ ፍች አለው። አንዱ ፈጣሪ የሚል ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ፍጡር ማለት ነው። ይህ ድርብ ፍች ዋቃና እርሱ የፈጠረውን እንደ እንስሳዊ፣ ዕፅዋቱ፣ ማዕድናቱ እና መንፈሳዊ፤ ባጠቃላይ ይህን ዓለም ይመለከታል። ”ሳፉ” ደግሞ የሰው ልጆች እንቅስቃሴዎች የሚመዘኑበት የሥነ-ምግባር መርሆች ናቸው። ስለዚህ በኦሮሞ አተያይ ይህ ዓለም የነዚህ ሦስት ነገሮች መስተጋብር ውጤት ነው። ለተለያዩ ነባር ባህላዊ ክዋኔዎች መቀጠልም አስተዋጽኦ ያበረከቱት የነዚሁ ጽንሰ ሃሳቦች ቀጥሎ መገኘት ነው (*Gemechu, 2005:70-71*)።

እነዚህ የኦሮሞ የዓለም አተያይ መግለጫዎች የተባሉት ጽንሰ ሀሳቦች የደስታና ሀዘን፣ የሀጢያትና የጽድቅ መግለጫ ክዋኔዎች መጠበቂያ ከበራዎች ማራመጃም ስለሆኑ በከበራዎች ውስጥ በመምጣታቸው እንደ አገባባቸው ተተንትነዋል።

እንደ መረጃ አቀባዮቹ ገለጻ በቃሉና በእግዚኣብሔር መካከል የሚያገናኘው የእግዚኣብሔር መንፈስ የሆነ፣ መንፈሱም የተቀደሰ፣ የተረጋጋና ለቃሉ፣ ለገዳ፣ ለሀገር ሽማግሌዎች በተለያዩ ድርጊቶችና መልኮች የሚገለጽ፤ ይኸውም፡- በህልም፣ በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶች መልክ የሚገለጹ እንደሆነ ያስረዳሉ። እነዚህ ክስተቶች እንደየቅለታቸውና ክብደታቸው በየደረጃው የሚፈቱ ናቸው። ስለዚህ በአካባቢው ጦርነት፣ ድርቅ፣ የሰውና የከብት በሽታ ቀድሞ እንዳይከሰት፤ ባጋጣሚ ከተከሰተ ደግሞ ባለበት ሁኔታ እንዲያበቃና ዳግም እንዳይከሰት ቃሉ

ለፈጣሪው መስዋዕት በማቅረብ ይለማመናል፤ ህዝቡም ከፈጣሪ ጋር ያማልደናል ብለው ያምናሉ።

የጉጂን አካባቢና ህዝቡን የሚጠብቀው በሰማይ የሚኖረው እግዚኣብሔር ነው። እግዚኣብሔር የጉጂ ቄዬዎችን፣ ከብቶቻቸውንና የከብቶቻቸውን በረት ይጠብቃል። እሱም ከአድማስ እስከ አድማስ በጉም የተሸፈነ ነው። እንደ ጉጂ ኦሮሞ የዓለም አተያይ እግዚኣብሔር ሁሉም ነገር በተትረፈረፈበት ዓለም ውስጥ የሚኖር እንደሆነና ከሰው ልጅ በመስዋዕት መልክ የሚቀርብለትን ይቀበላል ብለው እንደሚያምኑ Hinnant, (1977፡35) ያስረዳል። ታዲያ ይህንን ለእግዚኣብሔር መስዋዕት ማቅረብና የምህረት ልመናን በዋናነት የሚያከናውነው ቃሉ ነው።

ሌላው የቃሉ ተግባር በዋናነት ለገዳ ስልጣን በየስምንት ዓመቱ ያለምንም ደም መፋሰስ የስልጣን ሽግግር እንዲያደርጉ፣ ህዝቡንም በቅንነትና ያለአንዳች መድሎ እንዲያስተዳድሩ ቃለመሀላ በማስፈጸምና ስልጣነ ሢመቱን የማጽደቅና የመባረክ ተግባራትን ሲፈጽም፣ ከዚህ በተጨማሪ በተዘዋዋሪ መንገድ ለገዳነት የሚቀርቡ ዕጩዎችን ምርጫ ጭምር አስተያየት በመስጠትም ይሳተፋል። ባጠቃላይ በገዳ ስርዓት ፖለቲካ ውስጥ ቃሉ በስልጣን ሽግግር ላይ ከፍተኛ ሚና አለው (Alemayehufi kan biroo, 1999፡110)።

የጉጂ ቃሉ የጌዴኦ ብሔረሰብም ቃሉ ነበር፤ የጌዴኦ አባገዳም ልክ እንደ ሀሎና ዌስቱ ገዳዎች ለቃሉ ስጦታዎችን ይዞ በመምጣት ምርቃትና ከርቤ (qunbii) ይቀበል ነበር። ነገር ግን በአሁን ወቅት ይህን ሂደት እንደማያከናውኑና እዚያው በራሳቸው በጉሳ ሀለቃ አማካይነት ይፈጽማሉ (አባገዳ ደንቦባ ጉሚ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ እና አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ8/9/2007 ዓ.ም.)። ይህ ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ በምዕራፍ ሰባት ስር በዝርዝር ታይቷል።

ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ግጭቶችን ማስወገድና መፍታት እንዲሁም ለግጭቱ የመጨረሻ እልባት መስጠት ከቃሉ ተግባራት ውስጥ አንዱ ነው። በተለይም ምክንያቶች በግለሰቦች፣ በቡድኖችና በአጎራባች ብሔርና ብሔረሰቦች መካከል ለሚፈጠሩ ግጭቶችና በግጭቱም ምክንያት የሰው ነፍስ ከጠፋ በጎንዶሮ ከበራ ለግጭቱ የመጨረሻ ገደብ የሚበጀው በቃሉ ነው። ታቦር፣ (2006፣199) ይህንኑ ሀሳብ አጠር ባለ መልኩ ቃሉዎች ካሉባቸው ኃላፊነቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ በማለት እንደሚከተለው ያስረዳል። እነሱም፡-

- ✓ ምርጫ ላይ ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ መስጠት፣
- ✓ ለተመረጡ የገዳ ባለስልጣኖች ምርቃትና እውቅና መስጠት፣

- ✓ ሕግና ልማዶች እንዲከበሩ ማስተባበር፣
- ✓ የተፈጥሮ ሕጎች (ሳፉ) እንዳይጣሱ መጠበቅ፣
- ✓ የፈውስ ጸሎት ማድረግ፣ የበደሉ ክሰው፣ የተበደሉ ተክሰው እንዲታረቁ ማድረግ፣
- ✓ የፈጣሪን ሕግጋት ማስተማር፣
- ✓ በአካባቢያቸው በሚካሄዱ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ላይ መሪዎችን ማበረታታትና እውቅና መስጠት ናቸው፡፡

ነገር ግን የጉጂ ቃሉ እነዚህን ተግባራት ሲያካትት የኃመቺሳን ስርዓት ግን በቃሉ ተቋም ውስጥ አይከወንም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ ተግባር ምንድነው በማለት አቶ ሞኮናን ለጠየኳቸሁ፤ እሳቸውም ሲመልሱልኝ፡-

> *አንድ ሰው በማንኛውም ሰው ላይ ይሁን በራሱም ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡ አንድ ሰው እንዲጋጣሚ ሰው ሊገድል ይችላል፡፡ ወደ አባ ቃሉ ተቋም ("ገልማ") ከሸሸ የገዳዩ ቤተሰብና ንብረት ላይ የሟች ቤተሰብ ጥቃት እንዳያደርስ ይታደጋል፡፡ አባ ቃሉ ከተቋሙ ድረስ እንዲመጡ ወይም ጫን ያለ እንደሆነ ከመማክርትአባላቱ ጋር ችግር የተፈጠረበት አካባቢ በመሄድ ጉዳዩን ይፈታል፡፡ በአብዛኛው የመማክርትአባላቱ የቃሉ የሰላም መልክተኛ በመሆን በተላኩበት ሁሉ በመሄድ በተቻላቸው መጠን ለመፍታት ይጥራሉ፡፡ ከአቅማቸው በላይ ከሆነ ጉዳዩን ወደ ተቋሙ በማምጣት ለቃሉ ያቀርባሉ፡፡ ከዚያም ለአባቃሉ የነበረውን ሂደት በማስረዳት ያስተላልፋሉ፡፡ አባ ቃሉም ያለው እውነት ላይ ተመስርቶ ይወስናል፡፡ የአባ ቃሉ ውሳኔ ውሎ ያድራል እንጂ ይፈፀማል፡፡ 'አሞራ በራ፣ በራ ሞቷ ከመሬት ነው (allaattiin martee, martee duuti ishii lafa.) ይባል የለ?' "አሉኝ፡፡* (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ 13/12/2007 ዓ.ም.)

ሌላው በቃሉ መማክርት አባላት የተላለፉ የውሳኔ ሀሳቦች አልተገበርም የሚል ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ካለ በስተመጨረሻ ላይ ቃሉ የማህበረ-ፖለቲካ ማዕቀብ (bokuu) ያስተላልፋል፡፡ ይህን ማዕቀብ ማህበረሰቡም እንዲተገብሩት በተዋረድ ይተላለፍና በተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ የቃሉና የገዳ ተቋማት አንዱ ከአንዱ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና አንዱ ውስጥ ሌላኛው እንዳለ Hinnant, (1977) እንደሚከተለው ይገልጻል፡-

*The issue of dispute settlement is intertwined both in Gada and spiritual institutions. Guji believe in supernatural power called"Waqa", which literally means both "Sky" and "God". But it is the second meaning that is attached to their belief. They assume that Waqa lives far above the earth and sent Qallu for the people with Gada, law of peace and ways of life. Therefore, it is believed that disobeying any Gada laws and principles of peace (nagaa) would create misfortunes upon the person(s) or group(s)...*

*...If disputes could not be resolved at jarsa biyya level, the offices of Abba Gada and his advisors were the highest court of appeal in traditional Guji legal system.*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በጉጂ ኦሮሞ ህገረሰባዊ ሃይማኖትና የባህላዊ ህጉ ስርዓት በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ጠቦች ወይም ግጭቶች ቢከሰቱ ቀድሞ በሀገር ሽማግሌ የሚታይ ሲሆን፣ ከእነሱ አቅም በላይ የሆነው ወደቃሉና አባገዳ ተቋም በማድረስ እንደሚፈታ ነው፡፡ በመቀጠል Hinnant በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የእግዚሐብሄር፣ የቃሉ፣ የገዳና የማህበረሰቡን ትስስር ያስረዳናል፡፡ ይኸውም፡- ጉጂዎች በእግዚሐብሄር እንደሚያምኑና እግዚሐብሄርም ከምድር ርቆ በሰማይ እንደሚኖርና ለህዝቡም ቃሉንና የገዳን የሰላምና የምዕመኑ የሕይወት መንገድ ማሳያ ህግጋት ጋር እንደተሰጣቸው ያምናሉ፡፡ ለዚህ መመሪያዎችና ህግጋት አለመገዛት ወይም አለመታዘዝ ደግሞ ድርጊቱን አሻፈረኝ ባለው/ባሉት በግለሰቡ፣ በግለሰቦቹ ወይም በቡድኖቹ ላይ መጥፎ ክስተት እንደሚያስከትልባቸው ያምናሉ፡፡

የጉጂ ኦሮሞ ስለቃሉ ተግባር ሲገልጹ፡- ‹‹እኛ ቃሉን የምንፈልገው በጎሳው በሽታ እንዳይኖር፣ ጎሳው ሰላም እንዲሆን፣ ከብቶቻችን ጤናማ እንዲሆኑ፣ ከዚያም ኮርማው ለስሪያ እንዲነሳሳ (korma gaanaf kaasi)፣ አዱኛችንን መልስልን፣ ረድኤተ-በረከቱን አምጣልን እያለ ስለምጸልይና ስለሚያሳካልን ነው፡፡ እንዲህ እያለ ካልጸለየ ችግር ይፈጠራል፡፡›› ብለው ያምናሉ፡፡ (ወ/ሮ ዲኮ ሚጁ፣ አባያ ወረዳ፣ የካላልቱ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ፣ 13/12/2007 ዓ.ም.)




ፎቶ፡-2 አባ ቃሉ አጋ፣ አቶ ሞኮና (የቃሉ አጎት)፣ አባገዳ ሀልቻዬ እና ሌሎች የመማክርት አባላቱን የሚያሳይ

### 5.1.3.2. የገዳ ተግባራት

ወደ ገዳ ተግባራት ከመግባታችን በፊት ስለ ገዳ ምንነትና አንዳንድ ተያያዥ ጉዳዮችን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ገዳ የተወሰነ ዑደት ያለው ሆኖ በየስንምት ዓመቱ ከአንዱ የገዳ እርከን ወደሚቀጥለው እርከን የሚሸጋገሩበትና ስልጣን በሰላማዊ መንገድ የሚሸጋገርበት ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርዓት ነው፡፡ በአንዳንድ አካባቢ በስድስተኛ የገዳ እርከን ላይ የሚገኘውንና በስልጣን ላይ ያለውን ገዳ ብለው ይጠራሉ፡፡

አባ ገዳ ደግሞ በገዳ ስርዓት ህግ ለስምንት ዓመታት እንዲያገለግሉ በህዝብ ተመርጠው ስልጣን ላይ የሚወጡ ባለስልጣኖች ወይም የአስተዳደር አባላት ቁንጮ ነው፡፡ አባ ገዳ በቤተሰቡ ውስጥ ታላቅ የሆነና አክብሮት ያገኘ፣ የእሱ ጎሳ የሆኑት ሁሉ ምንም ዓይነት ግፍ ያልዋሉና የገዳን ስርዓትና ደንብ የሚያከብሩ፣ ባለትዳር፣ ጤናማና ትዳር መስርቶ ልጆች ያፈራ፣ የማይዋሽ፣ ብልህ፣ የንግግርና የአመራር ችሎታ ያለው ሰው መሆን አለበት (ታቦር፣ 2006፡ 218)፡፡ ከዚህ መስፈርት ውስጥ በሰው ልጅ ዘንድ አንድ ሰው ከተለያዩ ሀጢያትና ግፍ እራሱን ጠብቆ ሊኖር

ይችል ይሆናል። ነገር ግን የእሱ ጎሳ የሆኑት ሁሉ ከዚህ ዓይነት እንከን ነጻ መሆን ትንሽ የሚከብድ ሁኔታ ይመስለኛል። ያም ሆን ይህ የዕጩው ስብዕና ግን ወሳኝ ነው።

ከላይ እንዳየነው በገዳ ስርዓት አንድ አባገዳ በስልጣን ላይ የሚቆየው ለስምንት ዓመታት ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ማለትም፡- በስደት፣ በመጥፎ አደጋ ሰዎች ከስፍራቸው ሲፈናቀሉ፣ ከብቶቻቸው በተለያዩ ችግሮች ካለቁባቸው፣ ረሃብ ባገሩ ከገባ፣ ሀገሩ በጦርነት ከታመሰ፣ መረጋጋት ከጠፋና ይህን የሚመስሉ አስቸጋር ክስተቶች ከተፈጠሩ የአባገዳዎች የስልጣን ሽግግር ሂደቱ ሊተላለፉ ይችላሉ። ስምንት ዓመት የሞላው አባገዳ ለተወሰኑ ተጨማሪ ጊዜያት ሊያስተዳድር ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች እልባት በሚያገኙበት ወቅት ስልጣኑን ለቀጣዮቹ የገዳ አባላት በደረጃው ያላንዳች ችግር እንዲተላለፍ ይደረጋል። ይህን የስልጣን ሽግግር ለቀጣዩ የገዳ አባላት ያለማስተላለፍ ማለት የእግዚኣብሔር ህግ እንደተጣሰ ይቆጠራል። ከዚህ በተጨማሪ የገዳ ስልጣን ዑደቱን ማዛባት እንደ ሀጢያት (cubbuu) ስለሚቆጠር ለችግሩ ምክንያት በሆኑት አካላት ላይ ጫን ያለ ቅጣት ያስከትላል (Alemayehufi kan biroo, 1999፡169)። ተተኪው የገዳ እርከንም በባህሉና እምነቱ መሰረት ህጉ ስለሚፈቅድለት ስልጣኑን ያላንዳች ችግር አስገድዶ እስከመውሰድ ይደርሳሉ።
በማህበረ-ባህላዊ መሰረት ቦታውን ለሚለቀው አባገዳ ለመጦሪያው የሚሆነው ከብቶች ይሰጠዋል።ከብቶቹም በጃልዳባ አማካይነት ለማዋጣት ፍቃደኛ ከሆኑ ቤተሰቦች ላይ ይሰበሰባል። ነገር ግን ስርዓቱን አዛብቶ ወይም በጫና ቦታውን ለለቀቀ አባገዳ ግን ምንም እንደማይደረግለት ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ።

የጉጂ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በ 2008 ዓ.ም. ባሳተመው ልዩ እትም ላይ የካቲት/2008 ዓ.ም. የተካሄደውን የገዳ ስልጣን ርክክብ 74ኛው እንደሆነ ይገልጻሉ። እያንዳንዱን የስልጣን ሽግግር ያላንዳች የጊዜ መዛነፍ በየ8 ዓመት ልዩነት እንደተከናወነም ተገልጿል። ይሁን እንጂ ከመስክ የተገኘው መረጃ ግን የሚያሳየው ከዚህ የተለየ ነው። ምክንያቱም እንደነ አባገዳ አጋ ጤንጣኖ ያሉ ማህበረ-ባህሉ ከሚፈቅድላቸው ጊዜ ያሳለፉ እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህን በተመለከተ በምዕራፍ ሰባት ስር ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ተተንትኖ ቀርቧል።

በመግቢያው ውስጥ እንደተጠቀሰው በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ሁለት ዓይነት የገዳ ስልጣን አያያዞች አሉ። እነሱም፡- አንደኛው ከላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በየስምት ዓመቱ የሚመረጥና ሁለተኛው ደግሞ በዘር የሚተላለፍ ማለትም ከአባት ወደ ልጅ የሚሸጋገር ናቸው። የሁለተኛው

ዓይነት የሚገኘው በአሳብዱ ጎሳዎች ውስጥ ነው፡፡ ከነዚህ የገዳ ዓይነቶች ውስጥ በቅርበት የቃሉ መማክርት አባላት ሆነው የሚያገለግሉት የሁለተኛው ዓይነት ገዳዎች ናቸው፡፡ እነሱም፡- አሁን ያሉት የሀሎ አባገዳ (ገዳ ደንበባ) እና የዌስቱ አባገዳ (ገዳ ሀልቻዬ) ናቸው፡፡

### i. የገዳ እርከን ደረጃዎች

በዕድሜ አደረጃጀት (አወቃቀር) መሰረት የገዳ ስርዓት እርከኖች አሉት፡፡ እነሱም፡- በገዳ ስርዓቱ ውስጥ ካላቸው ማህበረ-ፖለቲካዊ ተሳትፎ አንጻር የንቁ-ተሳታፊ ገዳ አባላትና የኢ-ንቁ ተሳታፊ ገዳ አባላት ናቸው፡፡ ይኸውም፡- በንቁ ገዳ አባላት ስር የሚዘረዘሩት ጋሜ፣ ደበሌ፣ ኩሳ (ፎሌ)፣ ራባ፣ ዶሪ እና ሉባ (ገዳ) ናቸው፡፡ በኢ-ንቁ ገዳ አባላት ስር የሚገኙት ደግሞ ዕድሜያቸው ከ48 ዓመት በላይ የሆኑ ማለትም፡-1ኛ ጉላ/ዩባ፣ 2ኛ ዩባ፣ 3ኛ ዩባ እና ሽማግሌ (ጃርሳ/ቁሉሉ) ይባላሉ (Alemayehufi kan biroo, 1999፡145)፡፡ ይህ እርከን የገዳ ስልጣን ካስረከቡት ደረጃ በላይ ያሉትን ያካትታል፡፡ እነዚህ እርከኖች የቱለማ ኦሮሞ ያማከሉ ናቸው (ዝኒ ከማሁ፡,2000፡69)፡፡

የጉጂ ኦሮሞን የገዳ አደረጃጀት የተመለከትን እንደሆነ በዋናነት የልጅነት ደረጃ የጎልማሳነት ደረጃ የአዛውንትነት ደረጃ እና የሽምግልና ደረጃ የተከፋፈሉ ሲሆን፤ በስራቸው እነማንን እንደሚያቅፉ የሚከተለው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | የገዳ ደረጃ | ዕድሜ | ተ.ቁ | የገዳ ደረጃ | ዕድሜ |
|---|---|---|---|---|---|
| I. | የልጅነት ደረጃ | | III. | የአዛውንትነት ደረጃ | |
| 1 | ጉዱሩ፣ ዳባሌ | 0-8 | 7 | ባቱ | 49-56 |
| 2 | ቃሬ | 9-24 | 8 | ዩባ | 57-72 |
| | የመጀመሪ ቃሬ | 9-16 | | ዝቅተኛ ዩባ | 57-64 |
| | የኋለኛ ቃሬ | 17-24 | | ከፍተኛ ዩባ | 65-72 |
| 3 | ኩሳ | 25-28 | IV. | የሽምግልና ደረጃ | |
| II. | የጎልማሳነት ደረጃ | | 9 | ጃርሳ ጉዱሩ | 73-80 |
| 4 | ራባ | 26-39 | 10 | ጃርሳ ቁሉሉ | 81-88 |
| 5 | ዶሪ | 37-40 | 11 | ጃርሳ ራቀያ | 89-96 |
| 6 | ገዳ | 41-48 | 12 | ጃርሳ ጊኛ | ከ97 በላይ |

ሠንጠረዥ፡-1 **የጉጂ ኦሮሞ ገዳ ደረጃዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ** (ምንጭ፡- ከ Dirribii Damusee (2009) ላይ ተሻሽሎ የቀረበ)፡፡

ይሁን እንጂ ከመስክ ምልከታ እንደተረዳሁት አንድ የገዳ አባል በራባ ደረጃ እያለ ትዳር መስርቶ ልጅ መውለድ ይጠበቅበታል። ታዲያ በዚህ ወቅት የተወለደ ልጅ በዶሪ እርከን ውስጥ ከጉዱሩ ደረጃ ወደ ዳባሌ የማሸጋገር ስርዓት ይከወንለታል። ይህ ሳይሆን ዘግይቶ ከተወለደ የዳባሌ እርከን አመለጠው ይባላል። ከዚህም የተነሳ በዕድሜ ላይ መሰረት ያደረገ ምደባ የሚፋለስበት ወቅት አለ።

ከላይ በሠንጠረዥ ውስጥ ለማየት እንደተቻለው በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የገዳን ደረጃ በአራት ዐቢይ ክፍሎች ተመድበው እናገኛለን። ከእነዚህ ከልጅነት ደረጃ ውስጥ ኩሳን፣ እንዲሁም ከጎልማሳነት ደረጃ ውስጥ ደግሞ የዶሪን እርከን በጥልቀት ለማየት ወስኛለሁ። ምክንያቱም ከሌሎች በይበልጥ ለገዳ ስርዓት መሰረታዊ የሆኑ ማህበረሰባዊ ዕውቀት የሚያዋቅሩበትና የተለያዩ ተምሳሌታዊ ክዋኔዎችን የሚከውኑበት ደረጃ ስለሆነ ነው።

### ሀ. የኩሳ ደረጃ

ለገዳ ስርዓት እያንዳንዱ እርከን የራሱ የሆነ ሚና ቢኖረውም በኩሳ (ከ25-28 ዕድሜ ውስጥ ያሉ) ወደፊት ኃላፊነት ለመረከብ የሚዘጋጁበት ወቅት ያሉ ስለሆነ በንቃት የሚሳተፉበት እርከን ነው። ይኸውም፡- የዚህ ደረጃ መጨረሻ ላይ ይህን የገዳ እርከን የሚመራና ከ20 ዓመት በኋላ በ48ተኛ ዓመቱ ደግሞ ገዳ ሆኖ ህዝቡን የሚያስተዳድር የሚመረጥበትና የተለያዩ ልምምዶችና ዝግጅቶች የሚደረግበትበት ደረጃ ነው። ስለዚህ የቡድኑ አባላት በተለያዩ ፕሮግራሞች እየተገናኙ የእርስ በርስ ትውውቅ (waldhaggii) ያደርጋሉ። በመቀጠል የቡድኑን አባላት የማብላት ፕሮግራሞች (nyaachisa) ይካሄዳል። ይኸውም፡- የነዚህ ልጆች አባቶች የሆኑት ዩባዎች እያንዳንዳቸው ኮርማ በማረድ ያበላሉ (gubbisa gaggeessuu)። በዚህ ጊዜ የኩሳዎች ሚና እርስ በርስ በአግባቡ መተዋወቅ፣ መብላት፣ መጠጣት፣ መጨፈርና መዝናናት ነው።

ሌላው ኩሳዎች ከገዳ ቡድን (yaa'a gadaa) ጋር አብረው ይጓዛሉ። በዚህ ጉዞ ላይ አብዛኛውን የጉልበት ስራ በተመለከተ የሚያከናውኑት ኩሳዎች ናቸው። ይኸውም፡- ወደ ሚኤ ቦኮ የሚጎዳኙ ከብቶችን ማጎዳኘት፣ ለተጓዦቹ ከፊት ፊት ጥርጊያ መንገዱን መመንጠር፣ ባህላዊ ዕቃዎችን፣ የተለያዩ ምግቦችንና ቁሳቁሶችን ማጓጓዝ፣ የቡድኑን ማረፊያ (qachaa yaa'a) መስራትና የመሳሰሉትን ድጋፍ በመስጠት ከአባገዳዎች ስር ስር እያሉ የሚከውኑትን በመመልከትና በማዳመጥ ትምህርት ይቀስማሉ። እንዲህ እያሉ ወደ ፖለቲካዊ አመለካከትና ተግባር መሳተፉ ይጀምራሉ።

በዚህ እርከን መጨረሻ ላይ ይህን ቡድን ሊመሩ ይችላሉ የሚባሉ የማስተዳደር ችሎታ፣ መልካም ስነ-ምግባር፣ መልካም ዕጣ-ፈንታ ያላቸው የሚባሉትንና የተስተካከለ ቁመና ያላቸውን፤ የጉጂ ሰባት ቤት እንዲወክሉ ተደርጎ በጥንቃቄ ስምንት ሰዎች ይመረጣሉ። እነዚህ የተመረጡት አባላት ወደፊት ከሃያ ዓመታት በኋላ የገዳን ስልጣን እስከሚረከቡ ድረስ ቡድኑን የሚመሩ ናቸው። ስለዚህ ከወዲሁ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ሂደቱም ስልጠና መግባት (Fooqa/ agaallaa Seenuu) ይባላል። እነዚህ ስምንቱ ሰዎች የየራሳቸው የስልጣን መጠሪያና የስራ ድርሻ አላቸው። መጠሪያቸውም 1ኛ. ፋጋ (ሁለት ሰዎች ይመረጣሉ)፣ 2ኛ. አባ ሙርቲ 3ኛ. ጃልካያ/እርኪሳ አባገዳ፣ 4ኛ. ሀዩ፣ 5ኛ. ጃልዳባ፣ 6ኛ. ዋሙራ እና 7ኛ. ቶርቢ ይባላሉ። እነዚህ አሁኑ አባሙርቲ የሆነው ስልጣን ሲረከብ የገዳ መማክርት አባላት ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው። የስራ ድርሻቸውም፡-

1. **ጃልኬያ** (Jalkeya)

ጃልኬያ በገዳ ስርዓት ውስጥ አንዱ የመማክርት አባል ሲሆን አንዳንዴ እንደ ምክትል (irkisaa abbaa yaa'aa) ተብሎ ይጠራል።

2. **ፋጋ** (Faga)

ፋጋ የሚመረጡ ከገላልቻ ጎሳ ሲሆኑ አብዛኛው ስራቸው ሃይማኖታዊ ትንበያዎችን ነው። ምክንያቱም ገላልቻዎች ወዩ ናቸው ይባላሉ።

3. **ዋሙራ** (Waamura)

ዋሙራ የጉጂ ኦሮሞ ሰባት ቤት የሚወክሉ ሰባት ሰዎች ከጉባኤ ውስጥ የሚመረጡ ሲሆኑ፤ አብዛኛውን ጊዜ ስራቸው ጉባኤውን የመምራትና ድጋፍ መስጠት ነው።

4. **ቶርቢ** (Torbii)

ቶርቢ ከጉጂ ሰባት ቤት የሚወክሉ ሰባት ሰዎች በጉባኤው የሚመረጡ ሲሆኑ፤ እነሱም የሚተላለፉ ደንቦችንና ውሳኔዎችን በማዳመጥ በስራ ላይ የሚያውሉ አካላት ናቸው።

5. **ጃልዳባ** (Jaldhaaba)

ጃልዳባ ከጉጂ ሰባት ቤት የሚወክሉ ሰባት የሚመረጡ ሲሆኑ፤ እነሱን የሚመራና የመማክርት አባል የሚሆነው ማካላ (Makkala) ይባላል። እነሱ አባዛኛውን ጊዜ ስርዓት የማስከበር ስራዎችን ያከናውናሉ።




ፎቶ፡-3 የጃልዳባ አባላትን የሚያሳይ ፎቶ በሚኤ ቦኮ

6. ሀዩ (Hayyuu)

ሀዩ የሚባሉት ቀደም ሲል በገዳ የመማክርት አባልነት ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ለብዙ ዓመታት ያገለገሉና የካበተ ዕውቀት ያላቸው ሆነው በአዲሱ መዋቅር ውስጥ የሚመረጡና በማህበረ-ፖለቲካው እና ማህበረ-ባህላዊ ጉዳዮች ዙሪያ በማማከር የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

እነዚህ የተመረጡት አባላትና የእርከኑን ቡድን አባላት ሁሉም ለአንድ ወር ያለማቋረጥ በተዘጋጀላቸው የስልጠና ማዕከል በመግባት ይሰለጥናሉ፡፡ የስልጠናው ቦታ ከሰዎች መኖሪያ ራቅ ያለና ፀጥታ ያለው ቦታ ይመረጣል፡፡ በዚያ ስልጠና ቦታ መሀሉ ይታጠርና እነዚያ የተመረጡ ስምንቱ አባላት በስልጠናው ወቅት መሀል ሆነው ሲሰለጥኑ፤ የተቀሩት የመደቡ ቡድን አባላት ደግሞ አጥሩን ከበው በመንቀሳቀስ ስልጠናውን ይካፈላሉ፡፡ ስልጠናው የሚሰጠው በተሳታፊዎቹ አባቶች፤ በዩባ ደረጃ ባሉትና በቂ ልምድና ችሎታ ባካባቱት ነው፡፡ ይህ ሂደት የጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ ዕውቀት ሽግግር ያመላክታል፡፡

የስልጠናው ርዕሰ-ጉዳዮች በገዳ ስርዓት አስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ፣ በባህል ዙሪያ፣ የስራ ድርሻቸውንና ህጎች፣ ስነ-ምግባርን በተመለከተ፣ ስለውጊያ ስልቶችና ህጎች፣ ስለተለያዩ ሃይማኖታዊ ክበራዎች፣ ስለቅዱሳን (Woyyuu) እና የመሳሰሉትን ሌት ተቀን ያለ አንዳች እረፍት ጠበቅ ያለ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ ስልጠናው በፍጹም ጸጥታና መልካም ስነ-ምግባር

የሚከታተሉበት ነው፡፡ እነዚያ ለአንድ ወር ስልጠናዉን የተከታተሉት ስልጠናው እንዳበቃ በቡድን በቡድን በማደራጀት ወደ ማህበረሰቡ ውስጥ በመግባት የሰለጠኑትን ወደ ተግባር ይለውጡታል፡፡ በእንቅስቃሴያቸው ወቅት ከስልጠናውና የቀድሞ ልምዶቻቸው ያካበቱትን ህጎች፣ ባህል፣ ስነ-ምግባርና የመሳሰሉትን በመጠበቅ ይጨፍራሉ፣ እየተደገሰ ይበላሉ፣ የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች ይወጣሉ፡፡ በዚህን ጊዜ አሰልጣኞቻቸውም ከጎናቸው በመሆን ድጋፍ ይሰጧቸዋል፡፡

የዚህ እርከን መጨረሻና ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለመሸጋገር ከሚከወን ስርዓት ውስጥ አንዱ የባንቲ መላጨት (bantii haadataa/ yoosittii/ gonaadittii) ነው፡፡ ይህን በማከናወን ወደ ቀጣዩ ራባ እርከን ይሸጋገራሉ፡፡ (ሞና ጎዳና 9/6/2008 ዓ.ም.፣ የዋደራ ወረዳ ነዋሪ)
ይህ የባንቲ መላጨት የሚያመለክተው ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላኛው ደረጃ የሚያደርጉትን የሽግግር ከበራ ነው፡፡

### ለ. ዶሪ

ዶሪ በገዳ ስርዓት እርከን ውስጥ አምስተኛው ደረጃ ላይ የሚገኙ አባላት ናቸው፡፡ የቆይታ ጊዜያቸውም አራት ዓመታት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ያለ እረፍት የተለያዩ ከበራዎችን በማከናወን ይጠመዳሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ቃጅማና ወዴሳ ቆረጣ፣ የደበሌዎችን የእርከን ሽግግር ከበራ መፈፀም፣ ሁሉቃና ድባዩ (dhibaayuu) ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ የመሸጋገር ከበራዎቹም ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች ናቸው፡፡ እነሱም፡-

#### i. ቃጅማ ቆረጣ

በዚህ እርከን ውስጥ ያሉ ሴቶች የራሳቸውን የመጀመሪያቸውን ሲቄ (siiqqee) ቆርጠው የሚገቡበት ስርዓት ነው፡፡ የቃጅማ ቆረጣ የተባለበት ምክንያት ሲቄ የሚቆረጠው ቃጅማ ከሚባል የቆላ እንጨት ላይ ስለሆነ ነው፡፡

#### ii. ወዴሳ ቆረጣ

ወዴሳ (weddeessa) የዋንዛ እንጨት ነው፡፡ መረጃ አቀባዮቼ እንደገለጹልኝ፡-ከእንጨቶች ውስጥ ለዚህ ከበራ ተብሎ የሚመረጠው ዋንዛ ነው፡፡ ምክንያቱንም ሲገልጹ ዋንዛ ለሰው ልጅ ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡ ፍሬው ይበላል፣ እንጨቱ የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን ለመስሪያነት

ተፈላጊና ተመራጭ በመሆኑ ነው፡፡ (በሪሶ ጃልዴሳ፣የዱግዳ ዳዋ ወረዳ ነዋሪ፣ በ8/6/2008 ዓ.ም. እና አባ ገዳ ሀልቻዬ ዳራ፣ አባያ ወረዳ፣ ደበቃ ደቦቤሳ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣በ 26/7/2008 ዓ.ም.)

ስለዚህ ወደ ዶሪ እርከን የተሸጋገሩ አባላት ከራባ ወደ ዶሪ እርከን መሸጋገራቸውን አመላካች ከዋንዛ እንጨት ላይ ሙካ ወዴሳ የሚባለውን መካከለኛ ቁመት ያለውና ወፈር የሚል ዱላ መሰል ተጠርቦ ይዘጋጃል፡፡

እንጨቱን ከመቁረጣቸው በፊት በስሩ እርጎና ከገብስ የተዘጋጀ ገንፎ በመጨመር (dhibaasanii) እግዚአብሔርን ይለማመናሉ፡፡የወዴሳውን እንጨት የሚቆርጡት ዝግ ባለድምፅ (shookkisanii) "Weddeessi woddeessa nageyaati!" ወዴሳ የሰላም ወዴሳ ነው! እያሉ በማዜም ነው፡፡[5]






ፎቶ፡-4 ከታች ወደ ላይ ሲቁ፣ ሆሮሮ፣ የዋንዛ እንጨት፣ ከላይ ያሉት ሦስቱም የቦኩ ዓይነቶች ናቸው፡፡

ፎቶ፡-5 መረጃ ሰጪዎች በሚኤ ቦኮ

ባቱዎች ደግሞ ያን የቀረውን እርጎና ገንፎ በመያዝ ዶሪዎቹን "Dooriin doorii nageyaati! Doorometee gadoomii addee an geye tana geyi!" "ዶሪው የሰላም ዶሪ ነው፡፡ ዶሪ ሆናችሁ፤ ገዳ ሁኑ፤ እኔ የደረስኩበት ድረሱ" እያሉ በመመረቅ ያቀምሷቸዋል፡፡ ከዚያ የዶሪ አባላት ወዴሳውን ቢቆርጡም እንደገና "Addee ati geetteen na geyi!" "አንተ ከደረስክበት እኔንም ያድርሰኝ" በማለት እየተለማመኑ ወዴሳውን ይጠርባል፡፡ ከዚያ ያን የወዴሳ እንጨት አምጥቶ ለባለቤቱ ይሰጣታል፡፡ እሷም ከቤታቸው ጓሮ አስቀምጣ እንድትንከባከበው ወይፈን

[5] ሙካ ወዴሳ ጨምሮ ሌሎችን ቁሳዊ ባህል በተመለከተ ከሚከተለው ገጽ ላይ ምስሉን መመልከት ይቻላል፡፡

ይሸልማታል፡፡ የወይፈኑም ስም ከዚያን ዕለት ጀምሮ ዎዴሌ (woddeelle) ተብሎ ይሰየማል፡፡ እሷም የራሷን ሲቄ በጭስ እንዲያብረቀርቅ በማድረግ የባሏንም አደራ በአግባቡ ትጠብቃለች፡፡ ይህ ከአንድ ደረጃ ወደሌላ መሸጋገሪያ ከበራ ሲሆን እርጎው ስልጣናቸው ይርጋ (ይረጋገጥ) ወዴሳው ደግሞ ለሁሉም የሚጠቅሙ፣ የሚያገለግሉ መሆናቸው የሚያመላክት ተምሳሌት ነው፡፡ ገንፎውን የተመለከትን እንደሆነ ዝም ብሎ ገንፎ ሳይሆን የገብስ ገንፎ ነው፡፡ ገብስ ደግሞ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ልክ እንደ ቡና እግዚኣብሔር ከሚለማመኑበት የእህል ዓይነቶች ውስጥ ተቀዳሚ ያደርገዋል፡፡ ገብስ ለብዙ ዓይነት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ከመዋሉና ከጥንት ጀምሮ የሚታረስ የእህል ዓይነትነቱ ጋር ያያይዛሉ፡፡

iii. **የደበሌዎችን እርከን ሽግግር ከበራ መፈፀም**

በዚህ በዶሪ እርከን ውስጥ ከሚከወኑ ከበራዎች ውስጥ ሦስተኛው ደግሞ ልጆቻቸውን ከጉዱሩ ደረጃ ወደ ዳባሌ የማሸጋገር ስርዓት ነው፡፡ የዶሪዎች አባላት ልጆቻቸውን እራሳቸው ወደሚቀጥለው ደረጃ እንደተሸጋገሩ ያረጋግጡላቸዋል፡፡ በዚህ ወቅት የልጆቹ እናቶች የሚሉት አባባል አለ፡፡ ይኸውም፡- “Dur dhoksee guddisaa, hardha qoffee mudhisa...” ማለትም፡- “ቀደም ሲል ደብቄ አሳድገው ነበር፣ አሁን ግን አንገቱ ቀና አድርጌል፡፡...” እያሉ ይዘፍናሉ፡፡ ይህ የደረጃ ሽግግር በገዳ ስርዓት ውስጥ የመጀመሪያው በመሆኑ የሁሉም ወገን ደስታ የላቀ ነው፡፡ ይህ ሂደት አንድ የገዳ ደረጃ ወደ ሌላኛው እርከን የሚያደርገውን ሽግግር የሚያሳይ ከበራ ነው፡፡

iv. **ሁሉቃና ድባዩ**

ሌላው ከበራ የዶሪና የገዳ አባለት የስልጣን ርክክብ ከማድረጋቸው በፊት ዶሪዎች መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ (kaayoofi faroo hamtuu) ተከትሏቸው የወደፊት ስራቸውን እንዳያደናቅፍ በማሰብ፣ ስልጣን ላይ የቆዩት ገዳዎች ደግሞ ምናልባትም በስልጣን ዘመናቸው ወቅት አብሯቸው የነበረ መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ አሁንም እንዳይከተላቸው በሚል የሚፈጽሙት የጦስ ማውጣት ሃይማኖታዊ ከበራ ነው፡፡

በመጨረሻ የአሁኖቹ የዶሪ አባላት መጭውን የገዳ አስተዳደር የሚረከቡትና የሚያስተዳደሩት እነሱ ስለሆኑ ዘመኑ የጥጋብና የፍስሀ (kan quufaa gabbinnaa,kan misaafi mirgaa) እንዲሆንላቸው እርጎ በቅል እንዲሁም ቅቤ በጭጮ ሞልተው በመያዝ ድባዩ (ምስጋና) በሚካሄድበት እንጨት ስር እና በሚጎዳኙበት ወቅት ደግሞ መልካ (ወንዞች) ላይ ትኩስ ወተት

በመጨመር እግዚኣብሔርን የሚለማመኑበት ሃይማኖታዊ ከበራ ነው። እነዚህ የሁሉቃና ድባዩ ከበራ ትንተና በተመለከተ በ6.3. ስር በስፋት ቀርቧል።

ከዚህ በመቀጠል ወደ ገዳ እርከን ይሻጋገራሉ። ይህን በተመለከት ደግሞ በ6.1. ስር በዝርዝር ቀርቧል። ታዲያ በቃሉ የመማክርት አባልነት ውስጥ የአባገዳዎች ተግባር በስራቸው ያሉትን የየራሳቸውንየጎሳ አባላትን በባህላዊና ሃይማኖታዊ መንገድ ከማስተዳደርና በውስጣቸው የሚከሰቱ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳዮችን በራሳቸው የሃይማኖታዊ ከበራ መቼቶች ላይ ተመስርተው ለህዝባቸው እግዚኣብሔርን ይለማመናሉ። ከአቅማቸው በላይ የሆኑ ክስተቶች ሲያጋጥማቸው ጉዳዩን ወደ ቃሉ ተቋም በማምጣት በጋራ የሚፈቱበት ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ።

## 5.1.3.3. የኮከብ ቆጣሪዎች ተግባራት

ኮከብ ቆጣሪዎች ከቃሉ መማክርት አባላት አንዱ ሲሆኑ፤ በምሽት በመውጣት ከሰማዩ ላይ ያሉትን ከዋክብት ከአቀማመጣቸው፣ ከወጡበት አቅጣጫና በወቅቱ ከሚኖራቸው ከለር በመመርኮዝ ምን ዓይነት ክስተቶች ሊፈጠር እንደሚችል የመግለጽ ተስጦ ያላቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል። ከከዋክብቶቹ ውስጥ ስለማህበረሰቡ እምነትና ባህል መልካሙንና መጥፎውን የሚያመላክቱ አሉ ብለው ያምናሉ። እነሱም፡- ከዋክብት (ቡሳ ዋቃ፣ ሶስት ተከታትለው የሚወጡ ኮኮቦች)፣ ፀሐይና ጨረቃ የመሳሰሉ ናቸው። እነዚህን ከዋክብት አይተው ስለወቅቱ ዝናብ፣ በሽታ፣ ጦርነትና የመሳሰሉ ክስተቶች ለጉጂ ኦሮሞ ያለውን ጥሩነትና ጥፋት ለይተው የመተንበይ ተሰጦ እንዳላቸው ይገልጻሉ። ይኸውም፡- ሰባት ከዋክብቶች አንድ ላይ ተያይዘው የሚወጡ አሉ። እነዚህን ከዋክብት ቡሳ ዋቃ (buusaa waaqa) ይሏቸዋል። እነዚህ ሰባቱ ከዋክብት ወደ ሰማዩ መሀል ክፍል ከተጠጉ ክረምት መግባቱን ማብሰራቸው እንደሆነ ተረድተው ለህብረተሰቡ የእርሻ መሬታቸውን እንዲያዘጋጁ የሚያሳስቡበት እንደሆነ ይገልጻሉ። ነገር ግን እነዚህ ክዋክብቶች ወደ ምዕራብ አቅጣጭ ካዘቀዘቁና ከቆዩ፤ አውሎንፋስ የቀላቀለ ዝናብ ይዘንባልና በእረኝነትም ወቅት ሆነ በሌሎች እንቅስቃሴዎች ላይ ተጠንቀቁ ብለው ይናገራሉ። (ባሊ. ጃርሶ፣ የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ፣ 12/6/2008 ዓ.ም. በሚኤ ቦኮ)

ሌላው ፀሐይዋን የተመለከትን እንደሆነ በተለመደው መንገድ በሰላም ወጥታ የምትጠልቅ አለች። በዚያ መልኩ ከተካሄደ ሰላም ነው፤ነገር ግን ደም ለብሳ ከጠለቀች ችግር አለ ብለው ያምናሉ፤ ለዚያም ችግር ማሳለፊያ መስዋዕት ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ፤ ልመና ይከናወናል። ጨረቃዋም ከወትሮዋ ከለሯ ለየት ካለ የምታመላክተው ነገር እንዳላት ያምናሉ። ይኸውም፡- ጨረቃዋ ሙሉ ለሙሉ ደም ለብሳ፤ ቀልታ የወጣች እንደሆነ ጦርነት ይከሰታል፣ አሊያም ወረርሽኝ በሽታ ሊከሰት ይችላል፣ ከዚያም ሞት ይበዛል ተብሎ ይታመናል።

ከእነዚህ በተጨማሪ ሶስት ተከታትለው የሚወጡ ከዋክብቶች አሉ። እነዚያ ከዋክብቶች አወጣጣቸው ከቀድሞ ስርዓታቸው በተለየ መልኩ ከሆነ የተለያየ መልዕክት እንዳላቸው ይተነብያሉ። ይኸውም፡- ኮኮቦቹ ወደ ቀኝ ቀና ካሉ ሰላም ነው ይላሉ። ኮኮቦቹ ወደ ግራ ቀና ካሉ ደግሞ ችግር እንዳለ ይገመታል።

ከዚያ ቀጣዩ ስራ የሚሆነው የሰላም ከሆነ ተመስጌን ተብሎ በተገኘው መልካም አጋጣሚ እንዲጠቀሙበት መልዕክት ይተላለፋል። ነገር ግን የትንበያው ውጤት ችግር እንዳለ የሚያመላክት ከሆነ በቅድሚያ ስለ ክስተቱ ማጣራት ይኬዳል (qortii dhaqan)። ይኸውም ወደ አባገዳ በመሄድ ችግሩን በማስረዳትና ይህን ዓይነት ችግር ከምን ሊመጣብን ቻለ? ከዚያ ለጉዳዩ ማስታገሻ ሊሆን የሚገባ መስዋዕት ያስፈልጋል ማለት ነው፤ ፀሎት ይከናወናል። ከብት ታርዶ ሞራና አንጀቱ እንዲታይ ይደረግና፤ እግዚኣብሔር በዚህ ያሳልፍልን! በማለት ወደ መስዋዕት ማቅረብና እግዚኣብሔርን መለማመኑ ሂደት ይገባል።

በድሮ ጊዜ ኦሮሞ ታሞ ወደ ሐኪም ቤት አይሄድም ነበር፤ ከበሽታው የሚፈወሰው ወይም ከእግዚኣብሔር ምህረትን የሚጠይቀው በፋጭ፣ በሁሉቃ እና መስዋዕት በማቅረብ ነበር (ኡዴሳ ዲራሞ፣ የአባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ12/12/2007 ዓ.ም.)።

የአጥቢያ ኮከብ (bakkalcha) አቅጣጫዋን ጠብቃ ከወጣችና ለሊቱ ሊነጋጋ ሲል፤ ጎህ ሲቀድ ቃሉ ከመኝታው ተነስቶ ለህዝቡ እግዚኣብሔርን እንዲህ እያለ ይለማመናል፡-

| | |
|---|---|
| Borulle nage'i | የወጣሽው ጎህ ሰላም ላንች ይሁን፣ |
| Guji nage'i, | ጉጂ ሰላም ለናንተ ይሁን፣ |
| Ardaa nage'i. | ምድሯም ሰላም ሁኚ። በማለት ይፀልያል። |

ጠቅለል ባለ መልኩ የኮከብ ቆጣሪዎችን ተግባር ስንመለከት የለሊቱን ከዋክብት ተከታትሎ በመመልከት ስለወቅቱም ሆነ ስለቀጣዩ ጊዜያት መልካምነትና አለመሆን፣ ስለጉጂ ኦሮሞ ዕጣ-

ፈንታና ስለተለያዩ የሚከሰቱ ክስተቶችና ውጤታቸውም ምን ሲሆን እንደሚችል የሚያመላክቱ ከመማክርት አባላቶች ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡

ስለ ኮከብ ቆጣሪዎች Dirribii, (2009:141) እንደሚከተለው ሲያስረዳ፡- የኦሮሞ አያንቱዎች ዓርብ ለሊት በቡድን ሆነው ተራራ ላይ ወጥተው ኮከብ እየቆጠሩ ያድሩ ነበር፡፡ በወቅቱም የሚበሉት ቆሎና ቡና ቃላ ሲሆን የከዋክብቶቹን ልዩነት በአንድ ወይም በሁለት ወራት ውስጥ ምን እንደሚመስል ተረድተው ያስረዱ እንደነበር ይገልጻል፡፡ ከከዋክብት ዓይነቶች ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶባቸው የሚቆጠሩና የሚተነበይባቸው ሰባት ናቸው፡፡ እነሱም፡- ላሚ (Triangulum)፣ ቡሳን (Pleiades)፣ ባካልቻ (Aldebaran)፣ አልጋጂማ (Bellatrix)፣ አርባ ጋዱ (Centeral Orion)፣ ኡረጂ ዋላ (Saiph) እና ባሳ (Sirius) ይባላሉ፡፡

> *Ayyaantuu Oromoo Jimaata halkan koreedhaan gaaratti bahuudhaan urjii laakka'aa bula ture. worri urjii lakkaa'u kuni waa hedduu lagata. Guyyaa sana akaayii fi buna qalaa malee midhaan (nyaata) biroo hin nyaatan. Halkaan guutuu manatti hin galani. Alatti ibidda bobeessanii taa'uudhaan akkaata taa'umsa urjii ilaalu, adda addummaa isaan ji'a tokko ykn lama kessatti mul'isan hubatanii wal hubachiisaa turan. Hubannoon isaanii kuni immoo dhahaa Oromoo qopheessuuf isaan qarqaare* (Dirribii, 2009:141).

| Borana Terms | Technical Terms |
|---|---|
| Lamii | Triangulum |
| Busan | Pleiades |
| Bakkalcha | Aldebaran |
| Algajima(Alqajima) | Bellatrix |
| Arba Gaadduu | Centeral Orion |
| Urjii Walla | Saiph |
| Basa | Sirius |




ምስል፡-6 የሰባቱ ከዋክብት ስሞችና ምስል (ምንጭ፡- Asmarom,1973:181)

## 5.1.3.4. የካሎዎች ተግባራት

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ካሎ ማለት ባለከለቻዎች የሚጠሩበት ስያሜ እንደሆነ ተመልክተናል። እነሱም በቃሉ የሚወከሉ ሲሆኑ ተግባራቸውም እንደሚከተለው ይሆናል። እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለጻ ካሎዎች ወደ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ አምስት ሰዎች በግንባራቸው ላይ ካላቻ አስረው የሚላላኩት ናቸው። በቃሉ ተቋም ውስጥ የተለያዩ ስጦታዎችንም ሆነ ቅጣቶች ካሉ የሚቀበሉት እነሱ ናቸው። ዳንቢ፣ ሚኤሳ እና ዲኪቻ ቆርጠው (ሁለቱ የዛፍ ዓይቶች ሲሆኑ፤ ዲኪቻ ደግሞ ሀረግ ነው) የሀገሬውን ባህል ያሟላሉ። ቃሉ ያለ እነሱ መስዋዕት ማቅረብ አይችልም፤ ሃይማኖታዊ ከበራዎች (tolcha) ማከናወን፣ ከዋንዛ የሚዘጋጅ እንጨት መያዝም አይችልም።

ካሎዎች ማለት በሌላ አገላለጽ እንደ ቃሉ ባለቤት (ibidda isaa) ይመሰላሉ። እንደቃሉ አስቴ (ichima) ይቆጠራሉ። ለመስዋዕት የቀረበውን ከብት ጭንቅላት በገልማ ከሆነ ባለቤቱ፤ በተለያዩ መንፈሳዊ ተራራ ላይ ከሆነ ደግሞ እነሱ ካልያዙት በቀር እርዱ አይከናወንም። ለመስዋዕት በስጦታ ያበረከተው አካል ከብቱን ለማስረከብ እነሱን ይፈልጋል፤ ከዚያም የተረከቡትን ከብት ወደተራራው ይዘው የሚወጡትም እነሱ ናቸው።

የመስዋዕት ከብት ተይዞ ከተራራው ሲከሄድ አባቃሉን፡- አባገዳዎች፣ ሽማግሌዎችና የአካባቢው ነዋሪዎችና አጎራባቾች ከወጣት እስከ አዛውንት አጅቦት እየተጨፈረ (qeexalee) ይሄዳሉ። ከመስዋቱ ቦታ እንደደረሱ ወጣቶቹ አስቴውን እንዲሰብቁት (ichima akka buusu) ይደረጋል። ከዚያም ያንን አስቴ እየተቀባበሉ ሲሰብቁ ይጨስና ከኂላ እሳት ይወጣዋል። በዚያ ጊዜ ከተራራው ጥግ ጥግ ሳር በመንጨት እሳቱ ላይ ይጣላል፤ ወይራ (ejersa) ተተክሎ ተራራውን ሦስት ጊዜ እየተጨፈረ ይዞራል። በመጨረሻም ማልጊቻ (malgichcha) የሚባለውን መንፈሳዊ ጭፈራ ተጨፍሮ መስዋዕት የቀረበበት ጉዳይ መሳካት፤ አለመሳካቱን እዚያው ሊታወቅ ይችላል፤ አሊያም በሂደት ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

Malgichcha! Malgichcha koyyaa,
hujiin waaqaa meerree?
Hoo hoo!

ትርጉሙም፡- የጥንቱ/ቀደምቱ ጉጂ፣ የእግዚአብሔር ስራ/ተዓምር የታል? ሆ ሆ! እንደማለት ነው። በዚህ ከበራ ላይ የሚከወኑት እያንዳንዱ ድርጊት ምክንያታዊ ነው። ይኸውም፡- አስቴውን እንዲሰብቁት (ichima akka buusu) የሚደረገው ለከበራዎቹ የሚያገለግል እሳት ከግለሰብ ቤት ስለማይወሰድ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ቃሉ ባለቤትም ሆነች ማንኛውም ሴት ወደ ተራራው መስዋዕት ማቅረቢያ ስፍራ ስለማይወጡ ይህን ተግባር ባብዛኛው የሚሸፍኑት ካሎዎች ይሆናሉ። ለዚህም ነው ማህበረሰቡ ካሎዎችን በቃሉ ባለቤት ምትክ ስለሚከውኑ ልክ እንደሚስቱ የሚቆጥሩት። በመጨረሻም «ማልጊቻ ኮያ» የሚለውን መንፈሳዊ ጭፈራ ቃሉ የሚያወጣው በዜማ እግዚአብሔርን የመጡበትን ጉዳይ ልክ ለድሮዎቹ ጉጂ ያደርግላቸው እንደነበረው፤ ለእኛም አድርግልን፤ ተዓምራትህን አሳየን በማለት የሚጠይቁበት ስልት ነው። እንደ ጉጂ አዛውንቶች ገለጻ በዕለቱ ከእግዚሃብሔር የሆነ ምልክት እንደሚያዩ ይናገራሉ። ይህም ሊሆን የሚችለው አንድም በተግባር ወዲያው ለምሳሌ የዝናብ እጦት ከሆነ በዝናብ፤ አሊያም ለመስዋዕት በቀረበው ከብት ሞራ ሊገለጽ እንደሚችል ይገልጻሉ። በተለይም ይህንን ጉዳይ የሚያረጋግጡት ከመማክርት አባላቱ ውስጥ ሞራ አንባቢዎቹ ስለሚሆኑ ከዚህ ቀጥሎ የእነሱን ተግባራት የምናይ ይሆናል።

## 5.1.3.5. የሞራ አንባቢዎች ተግባራት

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ሞራ አንባቢዎች በተለያዩ አውዶች ላይ ለመስዋዕት የቀረበውን ፍየል ወይም በግ ከሆኑ ሞራቸው በስርዓት ይወጣና በገበቴ ላይ ተደርጎ ይቀርብላቸዋል፡፡ ለመስዋዕት የቀረበው ከብት ከሆነ ደግሞ አንጀቱን እዚያው የታረደበት ቦታ በመሄድ ያዩታል፡፡ የዘርፉ አዋቂዎች ያን አንጀቱን ከነሞራው በመመልከት ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ፀጋ በውስጡ ያሉትን የተለያዩ መስመሮች፣ በመስመሮቹ ከሚታዩ የተለያዩ ክስተቶች ተነስተው ከታያቸው (ካነበቡት) መረጃ ተመርኩዘው የቀረበው መስዋዕት ተሳክቷል፤ አሊያም ችግር አለው በማለት የመግለጽ ተሰጦ እንዳላቸው ይታመናሉ፡፡

ስለሞራ ማንበብ አጀማመር በተመለከተ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሰው ልጅ እንዲተዳደርበት ህግጋትንና ደንቦችን የሰጠው በመጽሐፍ መልክ ነበር፡፡ ከዚያም ከዕለታት አንድ ቀን ያ ለሰው ልጅ የተሰጠው የህግ መጽሀፍ አንዲት ላም ትበላዋለች፡፡ ሰዎቹም ተናደው ላሟን ያርዷታል፡፡ በመቀጠል ሆዷን ሰንጥቀው መጽሀፉን ቢፈልጉ ሊያገኙት አልቻሉም፡፡ ነገር ግን በላሟ ሞራና አንጀት ላይ የተለየ ክስተት ተመለከቱ፡፡ እሱንም እያገጣጠሙ ትርጉም ይሰጡት ጀመር፡፡ ከዚያም በሌላ ጊዜ እንዲሁ ከብት አርደው አንጀቱን ሲያዩ በሚያገኟቸው ምልክቶች ተንተርሰው ስለሰላም፣ ስለጦርነት፣ ስለበሽታ፣ ስለዘንድሮ፣ ስለመጭው መተንበይ ጀመሩ፡፡ ለዚህ ነው አሁንም እግዚአብሔር ይህንን ተሰጦ ያደላቸው አዋቂዎች በማንበብ እግዚአብሔር ያመላከታቸውን የሚገልጹበት በማለት ያስረዳሉ፡፡

ስለዚህ በቃሉ የቀረበው የመስዋዕት ከብት አንጀት ሲታይ ችግር እንዳለ ካመላከተ ሌላ ተመሳሳይ ከብት እንደገና ከዚያው ተራራ ሳይወርዱ፤ ካለበት ባሳቸኳይ ወጣቱ ተሯሩጦ እንዲመጣ ይደረጋል፡፡ በመቀጠል ቃሉ እግዚአብሔርን ተለማምኖ ወዲያው ሳይውል ሳያድር ከብቱ ይታረዳል፡፡ ሞራና አንጀቱን ሞራ አንባቢዎቹ ይመለከታሉ፤ ሰላም ከሆን እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ፤ ደስታቸውንም በጭፈራ ይገልጻሉ፡፡ ያ የታረደው ከብት ስጋ አንድም ሳይቀር እዚያው ይበላል፡፡ አጥንቱንና የማይበሉ የከብቱ አካላት ደግሞ ተሰባስበው ይቃጠላሉ፡፡




ምስል፡-6 ሞራ ሲያነቡ



ምስል፡-7 ከብት ታርዶ እዚያው ሞራውን ሲያነቡ (ምንጭ፡- Haberland, 1963)

እንደ መረጃ አቀባዮቹ በዚያን ወቅት ችግሩ ሀይለኛ ዝናብ እየዘነበ አስቸግሮ ከሆነ ወዲያውኑ ወቅቱንና መጠኑን የጠበቀ ዝናብ መዝነብ ይጀምራል፡፡ ወቅቱን ጠብቆ መዝነብ ሲገባው ካልዘነበ ደግሞ በዚያን ዕለት ዝናቡ ከየት መጣ ሳይባል ያወርደዋል፡፡ የጠላት ጦር እየመጣ ከሆነ እዚያው ይቆማል፤ አሊያም የእነሱ ጦር ተንቀሳቅሶ ድል በድል ሆኖ ይመለሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

በሌላ በኩል አንድ አባወራ ከታመመ ቤተሰቡ ተሰባስቦ ከብት ይታረዳል፡፡ እንደ ጉጂ አዛውንቶች ገለጻ የከብቱ ሞራ ስለሰውዬው ጤንነት ይገልጻል፡፡ ለምሳሌ ወንድማችሁን ሞራው ገሎታል፤ ስለዚህ ሌላ ከብት እረዱ ይባላል፡፡ እንቢ ካሉ ሰውየው ይሞታል፤ሚስቱን ሌላ እንደሚወርሳት፡፡ በሌላ በኩል አባወራውም ሆነ እማወራዋ ሂያጅ (የሚማግጡ) ከሆነ ያ ሞራ ይናገራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ችግሩ ከእሷ በኩል ከሆነ ችግር ተፈጥሯል፤ ባለቤትህን አረጋጋት፤ ደም ርጭባት ተብሎ ይነገረዋል፡፡ ችግሩ ከእሱ በኩል ካለ ደግሞ በዚሁ መልክ ይነገረዋል፡፡

> ሞራና አንጀቱን በማየት ስለፋልፋላ (falfalaa)፣ ስለሀብት፣ ስለቤተሰብ ችግር፡- ሆድ ለሆድ ተግባብተው መኖራቸውን፣ ሆድና ጀርባ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ ለአብነት ያህል ሞራው ከወደ አናቱ ጫፍ አበጥ ብሎ ነጣ ካለ፤ በዚያ ሰው ላይ ሟርት (ፋልፋላ) እንደተደረገበት ያመለክታል፡፡ በዚህ ጊዜ ያን ድርጊት ማርከሻ ሌላ ከብት እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰውዬው ልጆች ካሉት

ሁሉም ልጆች ማር እንዲገዙ ይደረጋል፡፡ ጠጅ ይዘጋጃል፡፡ ከዚያም የተነገረው መልክ ከብት ታርዶ፣ ጠጁ ተዘጋጅቶ፣ ዩባዎች ይጠሩና እግዚአብርን በመለማመን ሰውዬውን ይመርቁታል፡፡ ከዚያም እንዲህ ያለ መልክ ከብት እረድ፣ በዚህ አቅጣጫ ተጎዳኝ፣ ከዚያ ቦታ ስፈር፣ በዚህ ላይ ውለድና ክበድ በማለት ይመርቃሉ፤ የወደፊት ኑሮውን ያመላክቱታል፡፡ ይህ ድርጊት የሚከውኑት በአብዛኛው ዩባዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ዩባዎች በተግባርና በማየት (dhaggaafi dhageettiin) ለምድና ዕውቀት ያካበቱ ስለሆኑ ለማህበረሰቡ ስለ ዕጣ-ፈንታና ዕድል (faroofi kaayoo) የመተንበይ፣ ሞራና አንጀት የማንበብ፣ በቡና ቃላ እና በቦካ (ጠጅ) መተንበይ ስለሚችሉ ነው፡፡ (ባለ. ጃርሶ፣ ዕድሜ 74፣ ቡሌ ሆራ ነዋሪ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም.)

## 5.1.3.6. የሀገር ሽማግሌዎች ተግባራት

ለቃሉ በመማክርት አባልነት የሚሰየሙት የሀገር ሽማግሌዎች እነማን እንደሆኑ ቀደም ብሎ ተጠቅሷል፡፡ የነዚህ የሀገር ሽማግሌዎች በመማክርት አባላቱ ውስጥ ያላቸው ተግባር ባብዛኛው በተቋም ውስጥ በመገኘትና አንዳንዴም በቃሉ ትዕዛዝ መሰረት በመላክ ጭምር በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ አነስተኛ ማህበራዊ ችግሮችን በቃሉ ስም ይፈታሉ፡፡ ጉዳዩ ከመግባባት አልደርስ ብሎ ካስቸገራቸው የደረሱበትን ውሳኔና እንቢተኛው ማን እንደሆነ ለቃሉ ተቋም ሪፖርት በማቅረብ ያስተላልፋሉ፡፡

አንዳንድ በሳል የሀገር ሽማግሌዎች ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ ለሚቀርቡ ችግሮች ጠጠር ያሉ ሀሳቦችን በማቅረብ ነገሮችን ሳይንዛዙ እንዲፈቱ የሚያደርጉ አሉ፡፡ ሌላው አባቃሉንም ከገዳዎች ጋር በመሆን በማማከር የሚያገለግሉም እንዳሉ በመስክ ቆይታዩ ወቅት ለማየት ችያለሁ፡፡ ከመማክርት አባላቱ ውጭ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትም ይህንኑ ፈለግ ተከትለው አብዛኛውን ማህበራዊ ጉዳዮች በመፍታትና መጭው ትውልድ የማንነቱ መገለጫ የሆነውን ትውፊትና ስነ-ምግባር እሴቶች ይዞ እንዲያድግ የበኩላቸውን እየተወጡ ያሉት እነሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሀገር ሽማግሌዎች ተግባር ቀላል ግጭቶችን ከመፍታት አንስቶ በቃሉ መማክርት ውስጥ አባል በመሆን ትላልቅ ችግሮችን አብረው ይፈታሉ፡፡ በዋናነት ደግሞ ትውልድን ከስር ይቀርጻሉ፤ መልካም ስብዕና እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡

### 5.1.3.7. የሀዳ አንባ ተግባራት

የቃሉን ባለቤት በአላብዱ ጉጂ ዘንድ ሀዳ አንባ ትባላለች። ትርጉሙም የህዝብ እናት እንደማለት ነው። ነገር ግን ጉጂዎች የቃሉን ባለቤት «ቃሊት» ብለው አይጠሩም። እንደእነሱ ገለጻ «ቃሊት» የጥንቁልና ተግባር የምትፈጽም እንስት ናት። ሀዳ አንባ ግን የቃሉን ተግባራት ልትከውን ይቅርና ቃሉ መስዋዕት ለማቅረብ ወደ ተራራዎቹ ሲወጣ እንኳን እንደማንኛውም ሴቶች በቦታው አትገኝም።

"እንደሚታወቀው በእኛ ባህል ሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ እናቶችም ይመርቃሉ።" (ረጋቱ በሪሶ (የቃሉ እናት)፣ በወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ *በ18/11/2007 ዓ.ም.)* ለምሳሌ የተመለከትን እንደሆነ የቀድሞው አባቃሉ ባለቤት የሆኑት (የአንባ እናት) ይገለገሉበት የነበረውን የሃይማኖታዊ ቁሶች ለተተኪዋ የቃሉ ባለቤት መርቃ ታስረክባለች። ይኸውም ደረቅ ድፍን ቡናና ገብስ የእሳት ፍም ውስጥ በመጣል "ዳንቢ" (danbii) ከሚባል ከቆላ እንጨት በተሰራ መቁያ (qajimaa) በመነካካት ጭሱን በአደራሹ በማሽተት፣ የቡናውንና ገብሱን ጭስ ጎሳዎቹን ያጥኑታል። ይህ የምርቃት ሂደት ያፋቅራል፤ አንድ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ በመቁያው ቆስቆስ በማድረግ አካባቢውን ታውደዋለች። በመጨረሻ በዚያ በጋለ ፍም ላይ የቆየውን መቁያ በተዘጋጀው ቅቤ እየቀባች ሰላምና ምህረትን ከፈጣሪ እንዲያድለን በማለት እንደሚከተለው ትመርቃለች፤ ትለማመናለች።

| <u>ሀዳ አንባ</u> | <u>ታዳሚዎቹ</u> |
|---|---|
| አቤቱ ፈጣሪ ሰላሙን አምጣልን። | አምጣልን። |
| ለሰው ሰላሙን አምጣ። | አምጣ። |
| ለከብቶቻችን ሰላሙን አምጣ። | አምጣ። |
| መጥፎ በሽታን አርቅልን። | አርቅልን። |
| አማን አድርግልን። | አሜን አድርግልን። |
| መንደሩንም ዓለሙንም ሰላም አድርግልን። | አሜን አድርግልን። |

እየተባለ እሷ የጋለውን መቁያ በቅቤ እያቀዘቀዘች በሽታውን፣ ጦርነቱን፣ ረሀቡን እንዲቀዘቅዝ እግዚአብሔርን ስትለማመን፤ ታደሚዎቹ ደግሞ ከስር ከስር የመጨረሻዋን ቃል በመድገም ይሁንታቸውን ይገልጻሉ።

ታዲያ ታዳሚዎቹ የምርቃቱ ስርዓት ሲካሄድ ሁለቱን እጃቸውን ዘርግተው ምርቃቱ የምህረተና የሰላም ሲሆን ይሁን፣ አሜን ይላሉ። ክፉውን አርቅልን ሲባል፣ ትንሿን ጣታቸውን ቀስረው ወደ ግራ አቅጣጫ በማወራጨት በህብረት እየቀሰሩ፣ አርቅልን ይላሉ።" በማለት ቃላቱን ከድርጊቱ ጋር በማዛመድ ገልጸውልኛል።

የቀድሞዋ የሀዳ አንባ ስልጣን ማሸጋገር፣ መመረቅ፣ ከአዲሷ ሀዳ አንባ አጠገቧ ሆና ልምድ ማካፈልና ማማከር፣ እቤት ያሉትን ስራዎች በማስተባበር ተተኪዎችን ማሰልጠን የእሷ ተግባራት ናቸው።

ከእነዚህ በተጨማሪ በቃሉ ስር ሆነው የተለያዩ መንፈሳዊ ተግባራትን የሚከውኑ ወዩ (woyyuu)፣ ሀዩ (hayyuu)ና ጪዴሳ (cidheessa) የሚባሉ አሉ። ወዩ (woyyuu) ቅዱስ ማለት ነው:: ቅዱስነት በሁለት መልክ ይገኛል። አንደኛው ከእግዚኣብሔር በሚሰጠው ፀጋ ሲሆን፣ ይኸውም እንደቃሉ ዓይነቱ ቅድስናው ከእግዚኣብሔር የተሰጣቸው አሉ። ሌላኛው ደግሞ የቅዱሳን ማደሪያ በመሆን፣ ቅዱስ ከበራዎች የሚፈጸምበት በመሆኑ ቅዱስ ስፍራ ተብለው ይሰየማል። እንዲህ ዓይነቱ ቦታዎች በቃሉዎችና በገዳዎች ተቋማት አማካይነት በአዋጅ መልክ በመንገር ይቀደሳሉ። ለምሳሌ ሚኤ ቦኮ በአዋጅ በመነገር የተቀደሰ ስፍራ ነው። በገዳ አዋጅ ነገራ ወቅት «Me'ee bokkuu woyyuu, muka irraa hinmuramu beekkadhu!...» ማለትም ሚኤ ቦኩ ቅዱስ ስፍራ ነው፣ እንጨት ከውስጡ አይቆረጥም ተጠንቀቅ። እያሉ ቅዱስነቱንም ያረጋግጣሉ። ሀዩ (hayyuu) ደግሞ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዕውቀት ያለው ሰው ነው። ይህ ሰው በዕድሜና ልምድ ስለማህበረሰቡ፣ ስለአካባቢው፣ ስለማህበረሰባዊ ኑሮው፣ ስለነበረውና ስለሚመጣው መናገር የሚችል ሰው ነው።ሌላው ጪዴሳ (cidheessa) የሚባለው ደግሞ ባህላዊ መድኃኒት አዋቂ ነው። በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ሻቦላ (shaaboola) የሚባሉ ቤተሰብ እና ዳላጫ (dallaacaa) የሚባሉ ጎሳዎች አሉ። የእነዚህ ቤተሰብ አባላት ከፈጣሪ ልዩ ችሎታ የተሰጣቸው ቅዱሳን (woyyuu) ናቸው። እርግማናቸውም ሆነ ምርቃታቸው ይደርሳል ተብሎ ይፈራሉ። ሻቦላዎች መብረቅን የመቆጣጠር ተሰጦ አላቸው ብለው ስለሚያምኑ የእነሱ የሆነውን ነገር አይነኩም። ደላጫዎች ደግሞ የሆድ ውስጥ ህመም ይፈጥራሉ ተብለው ይፈራሉ። በእነዚህ ሰዎች አማካይነት የግለሰቦች ምርት ጥበቃ ይደረግላቸዋል። ይኸውም:- ጣሬ የሚባል በአዝመራው መካከል በእንጨት ይተክላሉ። ያን አዝመራ የእነሱ የሆነ ሰው መጥቶ ታሬውን ነቅሎ ካልመረቀው በስተቀር ያን አዝመራ ማንኛውም ግለሰብ ቢነካው:- ሻቦላዎች በዚያ በነካው ቤተሰብ ላይ መብረቅ በማስጣል አደጋ

ያደርሳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ዳላጫዎች ደግሞ ከዚያ አዝመራ ላይ የወሰደውን ሰው ሆድ በመንፋት እስከሞት ያደርሳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ነገር ግን እንደ መረጃ አቀባዮቹ ገለጻ ይህን ዓይነት ስህተት ፈጽሞ ችግር የደረሰበት ግለሰብ ወይም ቤተሰቡ ችግሩን ለማስቆምና ከአደጋውም ለማምለጥ ሲሉ ወደነዚህ ወዩዎች በመሄድ ያጠፉትን ነግረው፣ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ላጠፉት ጥፋት የሚቀጡትን ተቀጥተው ይመረቁና ይድናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በሚኤ ቦኮ አዋጅ ነገራ ላይ እነዚህን ወዩዎች ማክበርና የእነሱ የሆነውን መነካት እንደሌለበት ተገልጿል፡፡ (ገዳ ጋምቤላ ባርሶ፣ በ9/6/2008 ዓ.ም.፣ በሚኤ ቦኮ ቅዱስ ስፍራ በመገኘት)

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን የቃሉ መማክርት አባላትና ሌሎች በስሩ መንፈሳዊ ክዋኔ የሚከውኑ እያንዳንዳቸው በተናጥል ያላቸውን ተግባራት ለማየት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የነዚህ መማክርት አባላት በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ የእያንዳንዱ የጋራ ውጤት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 5.2. የቃሉ ከበራ መቼቶቹ

በቃሉ ተቋም ስር የተለያዩ የከበራ መቼቶች አሉ፡፡ መቼት ማለት አንድ ፎክሎራዊ ቅንጣት የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ነው (ፈቃደ፣ 2002)፡፡ የቃሉ ከበራዎች ገልማውን ጨምሮ የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቦታዎች ላይ ይከወናሉ፡፡ ከጊዜም አኳያ ቀናት፣ ወራትንና ዓመታትን ከክስተቶች ጋር በማያያዝ ባካበቱት ማህበረሰባዊ ዕውቀት በመጠቀም ምን ዓይነት ከበራን መቼ ይከወን ለሚለው ምላሽ የሰጡበት ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡
ስለዚህ እነዚህን መቼቶች ማህበረሰቡ ምን ይላቸዋል? ለምን ዓይነት ግልጋሎቶችስ ይውላሉ? በመቼቶቹ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነታቸው ምን ይመስላል? የሚሉትንና ሌሎችንም ጥቄዎች በሚመልስ መልክ ከመረጃ አቀባዮቹ ባገኘሁት መረጃ መሰረት እንደሚከተለው ተቀናብረው ቀርበዋል፡፡

### i. ተፈጥሯዊ መቼት

ተፈጥሯዊ መቼት የሚባለው ማህበረሰቡ ለሃይማኖታዊ ከበራው ይበጃል፣ ይሆናል ብለው ያመኑበትና የሰየሟቸው ስፍራዎች ናቸው፡፡ እነዚህም ስፍራዎች በቃሉ ጠቋሚነት ህዝቡ ምስጋና እንደሚያቀርቡበት ይነገራል (አለማየሁና ሌሎች፣ 2000፡80)፡፡

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ከተፈጥሯዊ መቼቶች ውስጥ ሀሮ ወላቡ ተጠቃሽ ነው፡፡ «...የጉጂ ጎሳ ቃሉ በሀሮ ወላቡ የሚገኘውን የኦብቱ ወገን «ቃሉ»ን እና ቀየውን በተለየ መልኩ የሃይማኖት ማዕከሉ እንዳደረገ ይነገራል» (ibid: 107-108)፡፡

በኦሮሞዎች ዘንድ መንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ ጉዳዮቻቸውን የሚፈቱት በየደረጃው ባሉት ባህላዊና ሃይማኖታዊ መዋቅሮቻቸው አማካኝነት ነው፡፡ እነዚህ መዋቅሮች እንደየአካባቢ የተለያየ ስያሜ ይኑራቸው እንጂ አገልግሎታቸው ተመሳሳይ ነው፤ ይኸውም የባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ማዕከሎች ሆነው ማገልገላቸው ነው፡፡ የማዕከሉ መጠሪያ በጉጂና በቦረና ኦሮሞ ዘንድ ጉሚ (Gumii) ሲባል፣ በሌላው የኦሮሚያ አካባቢ ደግሞ ጫፌ (Caffee) በመባል ይታወቃሉ፡፡

ጉሚ ማለት በአባገዳዎችና በኦሮሞ የባህል አዋቂዎች (hayyoota Oromoo) የሚካሄድ ከፍተኛ ጉባኤ (yaa'ii) ነው፡፡ በጉጂ ኦሮሞ አካባቢ ጉሚ ሚኤ ቦኮ፣ ጉሚ ዳራርቱና ጉሚ ዳሪቱ (Gumii Dharritoo) የሚባሉ ታዋቂዎቹ ናቸው (Alamaayyoofi kan biroo, 1999፡147)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደ ኦዳ ዶላ (Odaa Doolaa)፣ ፉቶ (Fuutoo) የቀድሞው የገዳ አባቶቹ የስልጣን ርክክብ የሚፈጽሙበት ቦታዎችም ይገኛሉ (Van de Loo, 1991፡42)፡፡

በአሁኑ ወቅት የጉጂ ኦሮሞ ገዳዎች በየስንምት ዓመታት ልዩነት የስልጣን ሽግግር ከበራዎችን የሚፈጽሙት በሚኤ ቦኮ (Me'ee Bokkoo) ተፈጥሯዊ መቼት ነው፡፡ በዚህ መንፈሳዊ ቦታ በአንድ ወቅት ሁለት ዓይነት የሽግግር ከበራዎችን ይፈጸማሉ፡፡ እነሱም፡- አንደኛው በከራባ ወደ ዶሪ፤ በዶሪ ደረጃ ያሉ አባላት ወደ ገዳ ደረጃ የሚሸጋገሩበት እና እንዲሁም በገዳ ደረጃ የነበሩት ደግሞ ወደ ቀጣዩ ዩባ ደረጃ የሚሸጋገሩበት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለስምንት ዓመታት ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መሪነቱን የሚያስፈጽም አባ ገዳ የሚመረጥበት፣ የሚጸድቅበት፣ ያለፈውን ህግና የአባገዳን የስራ አፈጻጸም የሚገመገምበት፣ ህግ የሚያወጡበትና የሚያውጁበት ቦታ እንደሆነ የሀገር ሽማግሌዎች ያስረዳሉ፤ በአጥኚው ምልከታ ወቅትም የታዩ ክዋኔዎች ናቸው፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም ሃይማኖታዊ መቼቶች ያየን እንደሆነ ቅድስናውን የሚያገኙት በሁለት መልክ ነው፡፡ ይኸውም፡- አንደኛው በተፈጥሮ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ተዓምራትን የሰራባቸው ቦታዎች ናቸው ተብለው የሚታመኑ ሲሆኑ፤ ለምሳሌ ቃሉ መጀመሪያ ወረደ የሚባለው ቦታ በአዶላ ወረዳ፣ ኦባ (ኦቢቲ) ቅዱስ ስፍራ ነው፡፡ ሁለተኛው መቼት ደግሞ በአዋጅ ቅድስናውን ይላበሳል (lallabaan ni woyyoomsu)፡፡ ለምሳሌ እንደ ሚኤ ቦኮ ያሉ

ቅዱስ ስፍራዎች ስያሜውን በአዋጅ ያገኛሉ፡፡ (ዋቆ ዱቤ፣ የኡራጋ አባገዳ የነበሩ፣ ጋንቤላ በሪሶ፣ የሆኩ አባገዳ የነበሩና ሞና ጎዳና በዩባ ደረጃ ያሉ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም. በሚኤ ቦኮ በመገኘት)

የቃሉ ከበራዎች ተፈጥሯዊ መቼቶችን ስናይ አብዛኛዎቹ ተራሮች ናቸው፡፡ በተራራ ላይ መስዋዕት ማቅረብ ጥንተ-መጥ እንደነበርና በስፍራውም የሚመለከውም ይሁን፤ የሚመሰገነው አንድ እግዚአብሔር እንደሆነ ታቦር፣ (2006፣211-212) እንደሚከተለው ያስረዳል፡፡

> ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር አብርሃምን በመጥራት ‹የምትወደውን ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ከፍ ወዳለችው ተራራ (የሞሪያ ተራራ) ሂድ፡፡ እኔም ከምነግርህ ከተራሮች ወደ አንዷት ተራራ አውጣውና መስዋዕት አቅርብልኝ፡፡ … በተጨማሪም ንጉሥ ሰለሞን በአባቱ በዳዊት ሥርዓት ስለሄደ እግዚአብሔር ይወደው ነበር፡፡ እርሱም መስዋዕት ለማቅረብ ገባኦን ወደ ተባለው ተራራ ሄደ፡፡ አንድ ሺህ የሚቃጠል መስዋዕት አቀረበ፡፡… ተራራዎች፣ ወንዞችና ዛፎች ለዋቃ ቶኮቻ (ለአንድ ፈጣሪ) መስዋዕት ማቅረቢያ ቦታዎች ናቸው፤ እንጂ የሚመለኩ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ኦሮሞ በተራራ፣ በወንዝና በዛፍ አያመልክም፤ አምልኮም አያውቅም፡፡

ቃሉ ለእግዚአብሔር መስዋዕት የሚያቀርብበትና የምልጃ ጸሎት የሚያካሂድበት ተፈጥሯዊ ቦታዎችን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ ይኸውም፡- የቀድሞውና ያሁኑ ይባላሉ፡፡ የቀድሞው የሚባሉት የወንዶ ወንድር፣ ሲሶ ቁሉሉ፣ ዳማ ዳንቼ፣ ቱቱ ፋላ፣ ሜዴዶ ኮባዎች (ጋራዎች) ሲሆኑ፣ ያሁኖቹ ደግሞ የሾምቦ፣ የጎላ፣ የቂሊጦ፣ የሚኤሳ፣ የኤጀርሳ እና የግምባ ጋራዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ስፍራዎች የሚቀርቡት የመስዋዕት ከብት ዓይነት እንደየሚከወነው ሁነቶች የተለያዩ እንደሆኑ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ይኸውም፡-

| መስዋዕት የሚያቀርብበት ስፍራ | ለመስዋዕት የሚቀርቡት የከብት ዓይነት |
|---|---|
| 1.የሾምቦ/ሙጥቻ ጋራ (ሀሴ ጎላ) | -ጥቁር ቦቃ ሰንጋ |
| 2. የጎላ ጋራ (ሀሴ ጎላ) | -ቀይ የፍየል ሙኩት |
| 3. የቅልጦ ጋራ (ቆቲ) | -ቀይ የፍየል ሙኩት |
| 4. የሚኤሳ ጋራ (ቆቲ) | -ቀይ የፍየል ሙኩት |

5. የኤጀርሳ ጋራ (ቆቲ) -ቀይ የፍየል ሙኩት

6. የግምባ ጋራ (ቆቲ) -ቀይ የፍየል ሙኩት ናቸው።

በእነዚህ ስፍራዎች ላይ ቃሉ ለሰላም፣ የሰውና የከብቶችን በሽታ ለመከላከል፣ የተዘራው እንዲበቅል፣ የተወለደው እንዲያድግ፣ ከብቶች በኮርማ እንዲጠቁ፣ ጥገቶች እንዲያግቱ ወዘተ ለእግዚኣብሔር መስዋዕት በማቅረብ ፈጣሪውን ይለማመናል።›› (አቶ ሞኮና ናጋዎ፣ በ10/12/2006)




ፎቶ፡-8 ከተፈጥሯዊ መቼት ውስጥ የቂሊጦ ጋራ (kooba Qilixoo) የሚያሳይ ፎቶ

## ii. ሰው ሰራሽ መቼት

ሁለተኛው የቃሉ ከበራ የመቼት ዓይነት ሰው ሰራሽ ናቸው። እነሱም፡- ገልማና ሂሮ ይባላሉ። ገልማ የሚሰራበት ቁሶችና የአሰራር ዲዛይኑ እንደየዘመኑ የተለያዩ ናቸው። ቀደሞ ባሉት ዘመናት ከሳር እንደሚሰራና ቅርጹም ክብ እንደነበር የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ። አሁን ደግሞ በቆርቆሮ ከዳን ሆኖ ቅርጽም እንደመኖሪያ ቤት ዛንጋባ አሰራርን የተከተለ ነው። ገልማ ከሃማኖታዊና ባህላዊ ክዋኔዎችን መከወን ባሻገር እንደቃሉ መኖሪያ ቤትነትም ያገለግላል። (አባቃሉ አጋ ሳቆ፣17/3/2008 ዓ.ም.)

ገልማ ቃሉ እንደ ቃሉ ተቋምነትም ይቆጠራል። ገልማ ባብዛኛው የሚመሰረቱት በተራራ ጫፍ፣ በተራራ ጥግ ወይም በትላልቅ ዛፎች በተከበቡ ቦታዎች ላይ ነው (Gada, 1988:25)። የጉጂ ኦሮሞ ስለቃሉ ተቋም (ገልማ) አመሰራረት የሚያነሱት ከቃሉ አመጣጥ ሚት ጋር በማያያዝ ነው። በ 5.1.1. ውስጥ እንደተገለጸው ቃሉን ያገኘችው ልጃገረድ ወደቤት እንሂድ ስትለው፤ ቃሉ መለስላት የሚባለው ሚት እንደሚገልጸው «እኔ የሰው ቤት አልገባም፤ ስለዚህ ገልማ ስሩልኝ።» እንዳላት ነው። ከዚያም በቦታው የተሰበሰቡ ሰዎች ይህ ከእግዚኣብሔር የመጣ ስለሆነ ያለውን እናድርግለት በማለት ገልማውን እንደሰሩለት ይተረካል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቃሉ የመጀመሪያው ማምለኪያውም ሆነ መኖሪያው ገልማ እንደሆነ ይገልጻሉ።




ፎቶ፡-9 የቃሉ ቤተ-አምልኮ (ገልማ) እና ሂሮ (ዳመራ መሳይ) የሚያሳይ ፎቶ

ሂሮ ደግሞ ከገልማው ፊት ለፊት በግምት አስር ሜትር ላይ የሚዘጋጅ ሰው ሰራሽ መንፈሳዊ ስፍራ ነው። ሂሮ ማለት ኣባቃሉ በተቋሙ (ገልማ) አካባቢ መስዋዕት የሚያቀርብበት አባይ (abbayyii) ከሚባል እንጨት እንደልምጭ ዓይነቶች ተቆርጠውና እንደዳመራ ተተክለው፣ ዙሪያው በሀረግ ታስሮ የሚዘጋጅ መንፈሳዊ ስፍራ ነው። ይህ እንጨት በየአመቱ እዚያው ላይ እየተጨመረ ይታሰራል። የቀድሞዎቹ እየደረቁ፤ እዚያው ረግፈው ይበሰብሳል፤ ደግሞ በላዩ ሌላ ይታሰራል። ይህ ድርጊት የሚከናወነው ቃሉ በሂሮ ስር መስዋዕት በሚያቀርብበት ወቅት ነው። ሂሮ ተቆርጦ የሚታሰረው በካሎዎች አማካይነት ነው። ሀዳ አንባ በገልማው ሳሎን ውስጥ ባለው ስፍራ እሳት አቀጣጥላ፣ በፍሙ ውስጥ ድፍን ቡናዎችን፣ የገብስ ፍሬ

በመጨመር በደጋን መሰል እንጨት (ቃጂማ) ወዲያና ወዲህ እየቆላችው ከሚወጣው ጭስ እያስከተለች ህዝቡን፣ አካባቢውን፣ ከብቶቹን ወዘተ ትባርካለች፤ ትመርቃለች። በዚህ ጊዜ ቃሉ ካላቻውን አድርጎ ሙኩት በመያዝ በዚያ ስፍራ ይሰዋል። ከዚያም ደሙን በገቡቴ ይጠራቀምና ከዳንቢ እንጨት ልጥ ተተልትሎ እንደጭራ የተዘጋጀውን በመንከር ግራና ቀኙን እየረጨ፤ እየመረቀ ይገባል። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Galma anaa naga'l | ገልማውን ሰላም አድርግልኝ! |
| Mi'ee bokkoo anaa naga'l | ሚኤ ቦኮን ሰላም አድርግልኝ! |
| Galma anaa naga'l | ቦረና ዳዋን ሰላም አድርግልኝ! |
| Bitaafi mirga anaa naga'l | ግራ ቀኙን ሰላም አድርግልኝ! |
| Ardaa anaa naga'l | ህዝቡን ሰላም አድርግልኝ! |
| Biyya anaa naga'l | ሀገሩን ሰላም አድርግልኝ!፣ |
| Horii anaa naga'l | ከብቶቹን ሰላም አድርግልኝ!.. |

በማለት ከሂሮ ስር ጀምሮ እየመረቀ፤ እየተለማመነ ወደ ገልማው ውስጥ ይገባል። ከዚያ ያን ገቡቴ ሀዳ አንባ (የቃሉ ባለቤት) ተቀብላ ታስቀምጣለች። አንዳንዴም ከማህበረሰቡ ውስጥ ወይፈን ወይም ኮርማ አምጥተው እንዲለማመንላቸው የሚያደርጉም ወቅት አለ። ከዚያ ከታረደው ኮርማ ቆዳ ተተልትሎ እንደጌጥ ይወጣና (eenjicha) በቃሉ እጁ ላይ ያደርጉለታል። ከታረደው ከብት ስጋ ውስጥም ከጎድኑ (Cinaacha) ላይ በማውጣት እንዲቀምስ (dhadhaama) ይደረጋል። ከዚያ በሀገሩ ላይ፣ በህዝቡ ላይ፣ በከብቶች ላይ የሚመጣውን መልካም ዕድልም ሆነ መጥፎ ነገር ለመረዳት ሞራ አንባቢዎቹ ቁጭ ብለው ሞራውን ያያሉ። (አቶ አባባ ቶቴ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ እና አባገዳ ሀልቻዬ ዳራ፣ አባያ ወረዳ፣ ደበቃ ደቦቤሳ ቀ/ገ/ማ፣ በ13/7/2008)

የዳንቢ እንጨት ለከበራው የተመረጠበት ምክንያት፤ የዳንቢ እንጨት ክረምት ከበጋ አይደርቅም፣ ውስጡ ወተት አለው፣ ተቆርጦ ቢተከል ይፀድቃል፣ ከሌሎች እንጨቶች ጋር ተጣብቆ ቢበቅል በመጨረሻ ሌሎችን በማጥፋት ቦታውን የሚሸፍነው እሱ ነው። ስለዚህ ለማህበረሰቡ መልካም ተምሳሌት ስለሚሆን፤ ከእንጨትም ውስጥ ለከበራ የሚውል እንጨቶች አሉ የሚባለው ለዚህ ነው። «ከእንጨት መርጦ ለታቦት፣ ከሰው መርጦ ለሹመት» ይባል የለ። በተራራና በገልማ (ሂሮ ስር) የሚደረገው ከበራ ልዩነት አላቸው። በሂሮ ስር የሚደረገው ከበራ የቃሉ ነው፤ ለመስዋዕት የሚሆነውን ከብት የሚያቀርበው ቃሉ ነው። ይኸውም በዘመን

መለወጫ ማለትም መስከረም (birraa) ላይ ከክረምቱ፤ ከጨለማዋ በሰላም ላወጣኸን አምላክ ምስጋና ይግባህ ለማለትና ቀጣዩ ጊዜ ደግሞ ከበሽታ፣ ከጦርነት፣ ከረሃብ፣ ከድርቅ፣ ህዝቡን፣ ከብቶቹንና እርሻውን እግዚአብሔር እንዲጠብቅ አደራ የሚሰጥበት ከበራ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር አንዳንዴ የእግዚአብሔር መንፈስ (ayyanni) እንዳመላከተው ሊከወን ይችላል፡፡ ይኸውም ኮኮብ ቆጣሪዎች፣ ሞራ አንባቢዎች እንዲሁም በባህሉና ሃይማኖቱ የበቁ አዛውንቶች (woyyuu) አማካይነት እግዚአብሔር በመንፈሱ ያመላከታቸው እንደሆነ ቃሉን እንዲህ ዓይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል፤ እንዲህ ታይቶናል ካሉ በመሀከሉም የሚያከብርበት ወቅት አለ፡፡ ከብቱንም በፍላጎት የሚያቀርብም ሊኖር ይችላል፡፡

በተለያዩ ተራራዎች ወይም መንፈሳው ስፍራዎች ላይ የሚካሄደው ከበራ ደግሞ የጎሳው ነው ይባላል፡፡ ምክንያቱም ቃሉ በነዚህ ስፍራ መስዋዕት አቅርቦ እግዚአብሔርን እንዲለማመን ሲፈለግ፤ ጎሳው ለመስዋዕት የሚሆነውን ከብት የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚያም ቃሉን በካሎዎች አማካይነት ወደተራራው እንዲወጣ («Qaalluu kooba nuuf ba'i.») በማለት ከብቱን ይዘው መጥተው ይጠይቃሉ፡፡ ለዚህም ነው በተራራ ላይ የሚደረገው ከበራ የጎሳው ነው የሚባለው፡፡ ያ ለመስዋዕት የቀረበው ከብት ከታረደ በኋላ ከከብቱ ላይ ከአፍንጫው ጀምሮ፣ የግንባሩን ቆዳ ከቀንዱ ጋር እንደተያያዘ፣ ሽንጡን ተከትሎ በቁመት ከነጭራው በመግፈፍ ይቀመጣል፡፡ በመጨረሻም ከበራው እንዳበቃ ያን ቆዳ ቃሉን ከጭንቅላቱ አንስቶ ጀርባው ድረስ በማልበስ፣ እየተጨፈረ ወደ ገልማው ይመለሳሉ፡፡ ከዚያም ለዚህ የመስዋዕቱ ምላሽ ማስቀመጫ ወደተዘጋጀ በስተቀኝ ካለው ኳዳ (Karba) ውስጥ ባለው ባለባላ እንጨት ላይ ይሰቀላል፡፡

| | |
|---|---|
| Kallacha ati dhaga'I | ካላቻ አንተ ስማ! |
| Hirroo ati dhaga'I | ሂሮ አንተ ስማ! |
| Galma kan ati dhaga'I | አንተ ገልማ ስማ! .... እያለ አስገብቶ |

ይሰቅላል፡፡ (ሀዳ ኦዳ ረጋቱ በሪሶ፣ ዕድሜ 40፣ ወናጎ ወረዳ፣ የቃሉ እናት (የቀድሞዋ ሀዳ አንባ) በ13/7/2008)

ከዚህ በተጨማሪ ለምሳሌ ይህ ከገልማው ፊት ለፊት የሚታየው ሂሮ ከአያት ቅድመ-አያታችን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣ እየሰማን አድገናል፡፡ ከዚያም አባታችን እዚሁ ላይ እየደመረ ያከብር ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ወደ ልጁ ተላልፏል፡፡ ስለዚህ በየወቅቱ ይሄ እያረጀ ሲሄድ መስዋዕት በሚቀርብበት ወቅት አዲስ ተቆርጦ በዚያው ላይ እየተጨመረ ይታሰራል፡፡ ከዚህ

ጋር አብሮ የሚነሳው ለመሰዋዕት የቀረበው ከብት ሞራ ስታይ ችግር ካለው በሉ ይህን ዓይነት ከብት ይታረድ፤ ሞራው እንዲህ አመላክቷል፤ በማለት የዳለቻ ቦቃ ከብት ሊታረድ ይችላል። ፍዬል ወይም በግ አሊያ ከብት ሊሆንም ይችላል። ከዚያ ሞራው አምሯል፤ ጥሩ ነገር አመላክቷል፤ ለቃሉ መልካም ጊዜ ነው፣ ለህዝቡም፣ ለከብቱም፣ ለሀገሩም ሰላም ነው ካሉ በዚያው ያበቃል።

የመማክርቱ አባላትና የሀገር ሽማግሌዎቹም በተራቸው ይመርቃሉ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Qaalluun nu'uu naga'a | ቃሉዋችን ሰላም ነው፣ |
| Gadaan nu'uu naga'a | ገዳችን ሰላም ነው፣ |
| mangudoon nu'uu naga'a | አዛውንቶቻችን ሰላም ናቸው፣ |
| biyyi nu'uu naga'a | ሀገራችን ሰላም ነው፣ |
| ilmi nu'uu naga'a | ወንዶች ልጆቻችን ሰላም ናቸው፣ |
| durbi nu'uu naga'a | ሴቶች ልጆቻችን ሰላም ናቸው፣ |
| Ee! nu'uu nageessi | አዎ! ሰላም አድርግልን። በማለት |

ይመርቃሉ።

በመቀጠል የከበራውን ማብቃት በሚገልጽና የእግዚአብሔርን ተዓምር አሳየን በሚል መልክ ቃሉ ‹‹Malgicha kooyyaa›› የሚለውን መንፈሳዊ ዘፈን በማውጣት ይጨፈራል። በመጨረሻው ቃሉ ለእኛ አማረልን፣ እኛን አኮራን እያሉ የታደሙት ሰዎች እየጨፈሩ ገልማውን ለቀው ይሄዳሉ። (አቶ አባባ ቶቴ፣ ዕድሜ 55፣ ወናጎ ወረዳ ቆቲ ቀ/ገ/ማ፣ የቃሉ ቶቴ ልጅ በ13/7/2008)

ባጠቃላይ ከላይ ለመመልከት እንደተሞከረው የቃሉና የገዳ ከበራዎች የሚከወኑባቸው መቼቶች አንድም ተፈጥሯዊ ሲሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሰው ሰራሽም እንዳሉ አይተናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጉዳይ ደግሞ መቼ ነው የሚከወነው ለሚለው የጊዜን ጥያቄ ለመመለስ የጉጂ ኦሮሞ ያዋቀረውን ማህበረሰባዊ ዕውቀት ማየት ያስፈልጋል። ስለዚህ ይህን በተመለከተ እንደሚከተለው ተቃኝቷል።

### iii. የቀናት ሃይማኖታዊ እሳቤዎች

መቼት የቦታ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የጊዜም ጉዳይ እንደሆነ ቀደም ሲል ለመግለጽ ተሞክሯል። ጊዜ ስንል እያንዳንዱ ሃይማኖታዊ ከበራ በዘፈቀደ የሚከወን ሳይሆን በዓመት ስንት ጊዜ

ይከወናሉ፣ በየትኛ ወርና ዕለት የሚሉት በማህበረሰቡ ዕውቀት ተዋቅሮና ተቀምረው የተቀመጡ ናቸው፡፡

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰብ እያንዳንዱ ወር የራሱ የሆነ ዕድል አለው፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ቀናት የየራሳቸው የሆነ መልካም ወይም መጥፎ ዕድል (kayo) አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ለሚከወኑ ከበራዎችና በዓላት መቼ መከወን እንዳለባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ አንድ ሰው የሞተበት ወይም የተወለደበት ቀን በራሱ ስለዚያ ሰው፣ ስለቤተሰቡ ወይም ስለማህበረሰቡ የሚከሰተውን ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር ያመላክታል ተብሎ እንደሚታመን *(Elfineh, 1994:62)* .እንደሚከተለው ያስረዳል፡፡

> *According to the society, each day of the month has specific significance. Different days have good and bad kayo, roughly, "fortune". Therefore, serious attention is paid to dates to practice ritual activities or to hold ceremonies. Birth or death on a given day is prognosticative of either the peace or trouble to happen to a person, family or the society at large.*

ምንም እንኳን ስም ከተሰያሚ ጋር የባሕርይ ግንኙነት ባይኖረውም፤ የጉጂ ኦሮሞ በወራቶች ውስጥ ያሉት ቀናት ለማህበረሰቡ ነበራቸው ወይም አላቸው ብለው ባመኑት መሰረት ከሃይማኖታዊ ጠቀሜታቸው አኳያ ለቀናቱ ከተሰጡት ስያሜ ውስጥ የተወሰኑትን በመውሰድ ያላቸውን ማህበረሰባዊ ፋይዳዎች እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

ለአብነት ያህል ዱሬቲ (Dureetti) የመጀመሪያዋ ቀን ስትሆን ትርጉሙ ሀብታሟ ማለት ነው፤ ከሀብት ጋር ተያያዥ ለሆኑ ጉዳዮች ከበራ የሚፈጸምበት ዕለት ነው፡፡ ለአብነት ያህል ከብቶች ይመረቃሉ፤ ነገር ግን በዚህ ዕለት ከብት አይታረድም፡፡

በመቀጠል ዱላቲ (Dullatti) አሮጌዋ የሚል ትርጉም አላት፡፡ በሌላ መልኩ የአረጋዊያን ቀን በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ ዕለት አዛውንቶች ለራሳቸውና በአካባቢያቸው ላሉ ሁሉ መልካም ነገር እንዲገጥማቸው የሚጸልዩበት ዕለት ነው፡፡ ሦስተኛዋ ቀን ሻልባና ዴቲ (shalbana deettii) ስትሆን፤ ይህች ዕለት ዕድለ-ቢስ ቀን ይሏታል፡፡ በዚች ቀን ውጤታማ አይኮንም ተብሎ ስለሚታመን ምንም ነገር አይከወንም፡፡

አራተኛዋን ቀን ሻልባና ብድርሳ (Shalbaana bidirsa) በማለት ይጠሯታል፡፡ ይቺን ቀን የንቦች ቀን፤ ንቦች የሚናደፉበት ዕለት ይሏታል፡፡ ተምሳሌነቱም የማጥቃት እንቅስቃሴ፣ በሙሉ አቅም የመናርና ለመከላከል ብቃት ያለው የሚል ነው፡፡ በዚህ ዕለት የሚወለድ ልጅ እነኚህን ብቃቶች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡ የእሱም ምርቃትና እርግማን ትልቅ ተፅዕኖ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ስድስተኛዋን ቀን ደግሞ ጋርዳዱማ (Gardaaduma) የምርቃት ቀን ትባላለች፡፡ መልካም ምኞት አላት ተብላ ስለሚታመን ማንኛውንም ዓይነት ከበራ መፈጸም የሚቻልበት ዕለት ናት፡፡
ከሰባተኛው እስከ ዘጠነኛው ቀናት ድረስ ባጠቃላይ ቡሳዋ (Busawa) የአራዊት ቀን በመባል ይታወቃሉ፡፡ ቡሳዋ ሦስት ዓይነት ናቸው፡፡ እነሱም፡- የመጀመሪያዋ ቡሳዋ (Busowaa qara) ጅብን የሚወክል ሲሆን፣ መካከለኛዋ ቡሳዋ (Busowaa gidduu) ነብርን ይወክላል፣ የመጨረሻዋ ቡሳዋ (Busowaa eegee) ደግሞ አንበሳን ይወክላል፡፡ በቡሳዋ ከበራ ለመፈጸም ጥሩ እንዳልሆነ ይነገራል፡፡

አስረኛዋ ቀን ጊዳዳ (Gidaadaa) የውርስ ቀን በመባል ትታወቃለች፡፡ በዚህ ዕለት አንድ ወንድሙ የሞተበት ሰው የወንድሙን ሚስት የውርስ ጋብቻ የሚፈጽምበትና በንብረቱም የሚወስንበት ዕለት ነው፡፡ በዚህ ዕለት የሚወለድ ልጅ አሟሟቱ ከሁሉም ወንድሞቹ በኋላ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው በዚህ ቀን ከሞተ በሚቀጥለው ከቤተሰቡ አባል ወይም አባላት ውስጥ መሞቱ/መሞታቸው የማይቀር መሆኑን አመላካች እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

አስራ አንደኛዋ ቀን ሩዳ (Ruuda) የከብት ቀን ትባላለች፡፡ ከብቶችን በተመለከተ ለሚደረጉ ከበራዎች ጥሩ ቀን እንደሆነ ይታመናል፡፡ በጉጂ ዘንድ በዚህ ዕለት ጋብቻ አይፈጸምም፡፡ ምክንያቱም በጋብቻ ስነስርዓቱ ላይ ልጃገረዷ ከቤቷ ወተት ተሸክማ መሄድ ይጠበቅባታል፡፡ ይህ ደግሞ ለእሷ ቤተሰቦች ከቤታቸው ወተት ከወጣ እንደ መጥፎ ዕጣ-ፈንታ ይታያል፡፡
አስራ ሁለተኛዋና አስራ ሦስተኛዋ ቀናት አሬሪ (Areerii) ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነኚህ ቀናት በገዳ ስርዓት ስያሜ ላላገኙ ሰዎች በዚያ ዙሪያ ከበራ የሚከናወንላቸው ቀናት እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ ቀናት ጋብቻ አይከናወንም፡፡ የከበራ እንቅስቃሴዎች ግን ይከናወናሉ፡፡ ሁለት ዓይነት አሬሪዎች አሉ፡፡ እነሱም፡- የመጀመሪያዋ አሬሪ (Areerii qara/garbittii) እና የመጨረሻዋ አሬሪ (Areerii eegee/badhoo) ይባላሉ፡፡ በተወሰነ ደረጃ ሁለቱም ተመሳሳይ ጠቀሜታ አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡

አስራ አራተኛዋና አስራ አምስተኛዋ ቀናት ደግሞ አዱላ (Adulaa) ተብለው ይጠራሉ። በእነዚህ ቀናት ሁሉም ባህላዊ ከበራዎችን ማካሄድ ይቻላል። ይኸውም እንደ የጋብቻ ስርዓት፣ የምርቃን ስርዓት፣ የስም ማውጣት ስርዓትና ሌሎችም ስርዓቶችን ሊያካትት ይችላል። ሁለቱም ቀናት የተለያየ ቅጥያ መጠሪያ አላቸው። እነሱም:- የመጀመሪያዋ አዱላ (Adulaa qara ) እና የመጨረሻዋ አዱላ (Adulaa eegee) ይባላሉ።
ሃያ አምስተኛዋን ቀን ባላ-ሆላ (Balla-holla) በመባል ትጠራለች። እንደ መረጃ አቀባዮቹ ገለጻ ይህች ዕለት የቃሉ ቀን በመባል ትታወቃለች።

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው በየወራቶቹ ውስጥ ካሉት ቀናት መካከል ለማሳያነት የተወሰዱ ሲሆን ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለማከናወንም ሆነ ላለማከናወን በማህበረሰቡ የተዋቀሩ ዕውቀቶች ሲሆኑ ተመልሰው ማህበረሰቡን እንደህግና ደንብ ሆነው ሲገለግሉ ይታያሉ።

ከዚህ በመቀጠል ለጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ከበራ ከጊዜ ውስጥ ወራትን ለይተው እንደሚከወኑ የሃይማኖት መሪዎችና የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ያስረዳሉ። ገዳዎች ወደ አባቃሉ ተቋም ለመባረክና ስልጣነ-ሢመታቸውን ለማጽደቅ ስጦታቸውን ይዘው ሲመጡ፤ በቅድሚያ የሚጠይቁት መቼ፣ የት ቦታና ከበራዎቹን አሳውቅ በማለት እንደሚከተለው ይማጸኑታል። ይኸውም:- ዓመቱን እወቅልን፣ ወራቱን እወቅልን፣ ሃይማኖታዊ ከበራችንን እወቅልን፣ የምናመልክበትን ተራራ እወቅልን በማለት እንደነበርና መባልም እንዳለበት ያስረዳሉ። (አቶ ሞኮና ናጋአ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ፣ በ14/12/2007 ዓ.ም.)

ይህ ማለት እያንዳንዱ ክስተት የራሱ የሆነ መቼት እንዳለውና ያንንም መቼት ቃሉ ለየገዳዎቹ አንተ ይሁነኝ ያልከው ይሁንህ! በታየህ ወር፣ ዕለትና ቦታ አምልክ በማለት ስለመቼቱ ይባርኳቸዋል ይባላል።

ስለዚህ ካሉት አስራ ሁለቱ ወራቶች ውስጥ ሃይማኖታዊ ከበራዎቹን ሊከወንባቸው ይቻላል የሚሉትን ልክ እንደ ቀናቱ ሁሉ ወራቱንም ማህበረሰቡ ለይተው እንደሚከውኑበት *Elfineh,* (*1994*:,65) እንደሚከተለው ይገልጻል።

> Nowadays, the Guji calendar has a year made up of twelve months or 360 days. There is no allowance for a leap year or intercalation. The twelve months are hageyya, birra, onkoleessa, sadaasa,

arfaasaa, qaamuu, badheessa, bisdottessa, caamsaa, ella, wocabajjii, and adoolessa.

Four important Months. Jia ilma orma, “the month of a stranger's son”. Among the twelve months arfasa, badheessa, camsa and adolesa are of extra-ordinary importance. The society believe that, if ritual activities or ceremonies like cultural naming, weddings and so on are held in these months, wishes will be fulfilled, plans will be successful. These months are the best ones for all activities. The phrase ji'a ilma orma is coined after a wedding ceremony- the most important deed, that assures the continuity of the society.

እንደ አስራ ሦስተኛ ወር ኦሪቶ ወይም ጮጮጷ ሀጌያ (orito ykn cocopha hageyya) ትቆጠራለች። እንደ Elfineh (*1994*:,65) አገላለጽ ለዚህም እንደምክንያት የሚቀርበው፡-

rains are expected to begin as soon as the month of hageya sets on. But once upon a time the Guji felt that there was a gap of some days b/n adoolessa- the last month of the previous year and hageyya- the first month of the new year.

ይቺን ወር ለብዙ ሞቶች መከሰቻ፤ ልክ እንደ መጥፎ ዕድል አምጪና በጠላት ብዙ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ከነበሩት ክስተቶች እያመኑ እንደመጡ ይገልጻል።

ነገር ግን በተለያዩ የጉጂ ኦሮሞ ኮንፌድረስዎች ዘንድ የጊዜ ስሌት ልዩነቶች ይታያሉ። ይህ ዓይነት ክስተት ሊፈጠር የቻለው የጉጂ ቀን መቁጠሪያ መሰረት ያደረገበት የተለያዩ ተፈጥሯዊ ሁነቶችና የአየር ሁኔታ ክስተቶች እንዳሉና የነዚህ ክስተቶች በተለያዩ ቦታዎች ተለዋውጠው በመፈጠራቸው ምክንያት እንደሆነ Elfineh እንደሚከተለው በማከል ያስረዳል።

*There are some variations among the three tribal divisions of the Guji-the uraga, the matti and the hokku in time calculation. This is due to the dependence of the Guji calendar on the variable natural environment and weather condition. The early or late coming rains appearance or dis- appearance of busan a group of seven stars,*

*getting or losing sight of the moon have great influence on the time reckoning (ibid, 66).*

ባጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ስር ቃሉ ማነው? ለሚለው የእግዚአብሔር መልዕክተኛ እንደሆነና አመጣጡም ከሰማይ መሆኑን በሚቶቻቸው ያስረግጣሉ፡፡ የቀድሞው ቃሉ ሲሞት ደግሞ ከአብራኩ ክፋይ ውስጥ ማህበረሰቡ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት መሰየም እንደሚቻል ከቀረበው ሚት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ቃሉ እያንዳንዱን ከበራ ሲከውን አብረውት የሚያከናውኑ የተለያዩ ተግባራት ያላቸው የመማክርት አባላቶች አሉት፡፡ አነሱም ግለሰባዊ ዕውቀትና ቡድናዊ ዕውቀታቸውን በማቀናጀት እንደ ቃሉ ተቋም ለማህበረሰቡ ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡ ይህንንም ክዋኔ የሚያስፈጽሙበት ጊዜና ስፍራ መቼት ይባላል፡፡ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች መቼቶች ከላይ እንደተመለከትነው እያንዳንዱ ከበራ በተመለከተ የት ይከወናል?፣ መቼ ይከወናል? የሚሉትን ከተሰበሰቡት መረጃዎች የተገኙትን ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ይኸውም፡- የት ይከወናል? ለሚለው በማህበረሰቡ ዕውቀት የተዋቀሩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ መቼቶችን በመጠቀም ነው፡፡ ከበራዎቹ መቼ ይከወናል? ለሚለው አንደ ጉጂ ኦሮሞ የዓለም አተያይ እያንዳንዱ ቀን፣ ወር፣ ወቅትና ዓመት የራሱ የሆነ መልካም ወይም መጥፎ ዕድል አላቸው ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ከበራው ማን እንደሚከውን፣ ለምን እንደሚከወንና ከሃይማኖታዊ ከበራዎች ጋር ያላቸውን ትስስር የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ እነዚህ የማህበረሰብ ዕውቀቶች ሃይማኖታዊ ተምሳሌትን በማላበስ ሲግባቡበት ኖረዋል፤ እየተግባቡበትም ይገኛሉ፡፡

ቀደም ሲል በ 2.3. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ስር በቃሉ እና ቃሊቻ/ቃሊቲ መካከል ያለውን የፅንሰ ሀሳብ ልዩነት ባላገናዘበ መልኩ በመተካካት በስራቸው ውስጥ ሲገለገሉበት ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ ልዩነት ደግሞ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ከዋኞቹ (ቃሉ ወይም ቃሊቻ) በተቀየሩ ቁጥር፣ ክዋኔውም ይለያል፡፡ በሌላ በኩል መከወኛው መቼትም ይለያያል፡፡ ከዚህ በመነሳት በቃሉና ቃልቻ መካከል ያለውን ልዩነቶች ከቀዳማይና ካልኣይ መረጃዎች የተገኘውን ከራሴ ልምድ ጋር በማቀናበር ስለ ሁለቱ አንድነትና ልዩነት እንደማጠቃለያ ለማሳየት ችያለሁ፡፡

ይኸውም፡- ስለቃሉና ቃሊቻ/ቃሊቲ አንድነትና ልዩነት ለማውጣት እንደማነጻጸሪያ የተጠቀምኩት የክዋኔውን አውድና ተግባራቸውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ከአውድ አኳያ ስናይ አውድ

በውስጡ መቼት፣ ከዋኝ፣ ክዋኔ፣ ታዳሚዎች፣ ቁሶችና የመሳሰሉትን ያካትታል። ስለዚህ ከእነዚህን ነጥቦች አኳያ በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ በዝርዝር ተገልጿል።

| ተ.ቁ. | ቃሉ | ቃሊቻ/ቃሊቲ |
|---|---|---|
| 1 | የቤተ-አምልኮው መጠሪያ "ገልማ" ይባላል። | በተመሳሳይ "ገልማ " ይባላል። |
| 2 | "ገልማ "የሚሰራው ከፍታ ቦታ ላይ ነው። | እዚህም ተመሳሳይነት አለው። |
| 3 | "ገልማ " ከባህላዊ ቁሶች በቀር በሌሎች ባዕድ ነገር አያሸበርቅም። | "ገልማ " በጃኖ ጨርቅ፣ በባንዲራ፣ በግምጃ ያሸበርቃል። |
| 4 | የቃሉ ገልማ ዕጣን፣ ሰንደል፣ ድኚ አይጨስም፤ ድቤም አይመታም። | ድቤ እየተመታ፣ ዕጣን፣ ሰንደል፣ ድኚ ይጨሳል። |
| 5 | ባህላዊ ዘፈኖች ያወጣሉ (weedduu baasu) | ይዘየራል፣ ወዳጃ ይወጣል። |
| 6 | ከመማክርት አባላቱ ጋር ይሰራል። | ከካዳሚዎቹ ጋር ይሰራል። |
| 7 | የሚቀመጠው ሳሎን በግልጽ ቦታ ነው። | የሚቀመጡት በመጋረጃ በተጋረደ ክፍል ውስጥ ተከልለው ነው። |
| 8 | መንፈሳዊ ጉዞ "የሙዳ" ከበራ ያከናውናል። | "የሙዳ" ከበራ አያከናውንም። |
| 9 | እንደቦኩ፣ ካላቻ፣ ሩፋና የመሳሰሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ቁሶችን ይገለገላል። | እንደ ቦኩና ካላቻ ያሉትን የመገልገል ስልጣን የለውም፤ አንካሴ፣ ባለባላ በትር ይይዛል። |
| 10 | በማህበረሰቡ ውስጥና ከአጎራባች ጎሳዎች ጋር ግጭቶች ሲከሰቱ የማስማማት/ ግጭቱን የመፍታት አቅም አለው። | የግለሰቦች ግጭት መፍታት፣ አንዳንዴም ጠላትህ እገሌ ነው በማለት ሊያጋጭም ይችላል። |
| 11 | የጎንዶሮን ከበራ ይፈጽማል። | የጎንዶሮን ከበራ አይፈጽምም። |
| 12 | ከገልማ ውጭ በመንፈሳዊ ተራራዎች ላይ ሃይማኖታዊ ከበራ ይፈጽማል። | አብዛኛዎቹ ከበራዎቹ በ"ገልማ " ውስጥ ብቻ ነው። |
| 13 | የመሪነቱን ቦታ ከአባት ወደ ልጅ ሲሸጋገር ልጅ ሊያሟላ የሚገባው ቅድመ-ሁኔታዎች አሉ። | ከአባት/ከእናት ወደ ልጆች (ሴት/ወንድ) ሊተላለፍ ይችላል። |
| 14 | የመሪነቱን ቦታ የሚይዘው ከመጀመሪያዋ (ከገለልቻ ጎሳ) የተወለደው መሆን አለበት፣ | ከ1ኛዋ፣2ኛዋ ወይም ሌላኛዋ ሚስት የተወለደው ሊሆን ይችላል። |
| 15 | በገልማና በመንፈሳዊ ተራራዎች ላይ ስለማህበረሰቡ መልካም አጋጣሚዎች ለማመስገን፣ ለደረሰባቸውና ሊደርስባቸው ይችላል ከተባለው ችግሮች እንዲታደጋቸው እግዚኣብሔርን ለመማጸን ዓመታዊ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በጋራ ይፈጽማል። | ተቸገርኩ ብሎ ስለሚመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች እዚያዊ በ"ገልማ " ውስጥ መላ ይላል እንጂ ስለማህበረሰብ ባጠቃላይ ደንታ የለውም። |
| 16 | ምርቃት የሚያከናውነው በሚጁ (ቦካ፣ | በቡና፣ በጫት፣በዕጣን..ይመርቃል። |

| | | |
|---|---|---|
| | ወተት፣ቡና ቃሳ) ነው | |
| 17 | የወር አበባም ሆነ፣ሴት ልጅ ወልዳ 40/80 ቀናት ሳይሞላት፣ "ገልማ " ውስጥ ለመግባት አያግዱም፡፡ | ሴት ልጅ ወልዳ 40/80 ቀናት ሳይሞላት፣ የወር አበባ ታይቷት ሳትፀዳ ወደ "ገልማ " ውስጥ መግባት አትችልም፡፡ |
| 18 | ሰው ሞቶ የቀብር ስርዓት ላይ መሳተፍ "ገልማ " ከመግባት አያግድም፡፡ | ሰው ሞቶ የቀብሩን ስርዓት ላይ የተሳተፉ የሟቹ 40ው ሳይወጣ ወደ "ገልማ " ውስጥ መግባት አይችሉም፡፡ |
| 19 | የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም "ገልማ " ከመግባት አያግድም፡፡ | የግብረ-ስጋ ግንኙነት የፈጸመ ሰው በዕለቱ ወደ "ገልማ " ውስጥ መግባት አይችልም፡፡ |
| 20 | በላዩ ላይ የሚወርድበት/ የሚሰፍርበት አውሊያ/ ውቃቢ/ዛር የለም፡፡ የተረጋጋ፣ ቅዱስ መንፈስ ነው የሚቀርበው፡፡ | አውሊያ/ውቃቢ/ዛር በላዩ የሚወርድ/ የሚሰፍርበትና በእሱ ላይ አድሮ የሚናገር መንፈስ አለ፡፡ |
| 21 | የገዳዎችን ስልጣነ ሢመት ያፀድቃል፡፡ ነገር ግን ዛር፣ ውቃቢና አጋንንት በመለየት ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት የለውም፡፡ | ዛር፣ ውቃቢና አጋንንትን በመለየት ውሳኔ ይሰጡበታል ይባላል፡፡ ነገር ግን የገዳዎችን ስልጣነ ሢመት የማጽደቅ ተሰጥኦም ሆነ፣ ስልጣኑ የለውም፡፡ |
| 22 | የ"ሀማቺሳ" ስርዓት አያከናውንም፡፡ | የ"ሀማቺሳ" ስርዓት ያከናውናል፡፡ |
| 23 | -የተለያዩ ከበራዎች የተወሰኑ መቼት ቢኖራቸውም፣ ባለጉዳዮችን ዘወትር ከማስተናገድ የሚያግደው ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም ቀናትን ለይቶ የሚቆም ዛር/ውቃቢ የለውም፡፡ | -ከተወሰኑ ቀናት ውጭ ባለጉዳዮችን ማስተናገድ አይችልም፡፡ ላስተናግድ ቢል እንኳን በባህሉ መሰረት የመሸምገል እንጂ እንደቀድሞው መከወን አይችልም፣ ምክንያቱም መንፈሱ ሲወርድበትና መንፈሱ ትቶት ሲሄድ የተለየ ባህሪይ ስለሚላበሱ ነው፣ |
| 24 | በስጦታ መልክ እንደ ብር፣ ከብቶች፣ እርጎ፣ ጨኮ፣ ቡና፣ ገብስና...የመሳሰሉትን ይበረከትለታል፡፡ | በስጦታ መልክ እንደ ብር፣ ሀረቄ፣ እጣን፣ ሰንደል፣ ዶሮ፣ ግምጃ፣ ጃኖ፣ መርፌ፣ ሻማ፣ ሽቶ፣ ቡናና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ |
| 25 | የተለያዩ ስጦታዎችን ከማህበረሰቡ በገዳ አስተባባሪነት የሚበረከትለት፡- በሠርጉ ዕለት፣ በሙዳ ከበራ ወቅት፣ የዓመት ጉርሱን በማሳረስና ሃይማኖቱንና ባህሉን በከፋ ሁኔታ ከጣሱ አካላት እንደካሳ ከሚሰጡት ነው፡፡ | ስጦታ የሚበረከትለት ግለሰቦች ከችግራቸው አኪያ ተሳካልን ወይም እንዲሳካልን በማለት ከሚያቀርቡት ውጭ፣ በገዳ አባቶችና በአብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል የሚሰጠውና የሚጎበኝ |

| | | |
|---|---|---|
| | | አይደለም፡፡ |
| 26 | በቃሉ ስር የሚገኙ የመማክርት አባላት በየሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ የራሳቸው አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ | በስሩ የሚገኙት የመማክርት አባላት ሳይሆኑ፤ ካዳሚዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን የተወሰኑ ሽማግሌዎች አንዳንድ ጉዳዮችን የማከናወን ሁኔታ ይታያል፡፡ |
| 27 | የውሳኔ አሰጣጥ ሂደታቸው ይለያያል፡፡ ያኸውም፡- ቃሉ እያንዳንዱን ጉዳዮች ከስረኛው መዋቅር እንዴት አልፎ እንደመጣ ያጣራል፣ እንደ ጉዳዩ ቅለትና ክብደት በተዋረድ እንዲታይ ያደርጋል፡፡ | ቃሊቻ ግን በመንፈሱ አማካይነት ደረሰኩበት ባለው መረጃ መሰረት ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡ ማንኛውንም ጉዳይ ከእሱ ገልማ ከደረሰ እዚያው በመሰለው መሰረት ይጨርሳል፡፡ አንዳንዴም ለሽማግሌዎች የሚያስተላልፍበት ሁኔታዎች አሉ፡፡ |
| 28 | ያገልማው አሰራር በአብዛኛው ይመሳሰላል፡፡ | ተመሳሳይ ነው፡፡ |
| 29 | ለተቋሙ ህግና ደንብ አልገዛ ያለውን የሚቀጣው በደረጃ ነው፡፡ የመጨረሻው ቅጣት ቦካ (boka) ማለትም ከማህበራዊ ግልጋሎቶች የማግለል ሁኔታ እንዳለ ይገልጻሉ፡፡ | ከተቋሙ የሚተላለፈውን የጥሪና የውሳኔ ሀሳብ አልቀበልም ካለ፣ በመንፈሱ ባለቤቱን አሊያም ከቤተሰቡ አባል ማሳበድ ወይም መግደል እንደሚችል ያስፈራራል፡፡ ተሰሚነቱ ያነሰ ቢሆንም ማህበረሰቡ እንዲያገለው መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ |
| 30 | ቃሉ በስሩ ገዳን ጨምሮ አብሯቸው የሚሰራ የመማክርት አባላት አሉት፡፡ | እዚህ ግን ሁሉም ነገር የሚከወነው በቃሊቻው ብቻ ሲሆን፤ የተወሰኑ የመላላክና ወዳጃውን የማሞቅ ስራዎች በካዳሚዎቹ ይፈጸማል፡፡ |
| 31 | የቃሉ ባለቤት ሀዳ አንባ ስትባል፤ ቃሉን ተክታም ሆነ፤ እራሷን ችላ ተቋሙን የመምራት ስልጣኑ የላትም፡፡ ባሏ ሲሞትም ተክታ አትሰራም፡፡ | የቃሉ ባለቤት ቃሊት ይሏቸዋል፡፡ ባሏ ሲሞት ተቋሙን እስከ ሕልፈተ-ሕይዎታ እንደምትመራ ይነገራል፡፡ ነገር ግን አንዷት ሴት ዛር ከሰፈረባት ቃሊት ተብላ ተቋሟን መምራት ትችላለች፡፡ |
| 32 | የከበራ ቀናትና ወራት የተወሰኑት ባላቸው ዕጣ-ፈንታ ላይ ተንተርሶ የተደለደሉ ሲሆን፤ ተቋሙ የተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካው ጉዳዮችን በማንኛውም ቀናት ለማስተናገድ ክፍት ነው፡፡ | የከበራ ቀናት አብዛኛውን ጊዜ ረዕቡ እና ዓርብን ይመርጣሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቅዱሳንን (የሚካኤል፣ የጊዮርጊስ፣ የማሪያምና የመሳሰሉትን) ክብረ-በዓላት ተንተርሶ ሲከውኑ ይታያል፡፡ |

ሠንጠረዥ-2 የቃሉና ቃሊቻ/ቃሊቲ አንድነትና ልዩነት (በአጥኚው የተዘጋጀ)

ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ እንደተመለከትነው በቃሉና ቃሊቻ/ቃሊቲ መካከል ያለው ተመሳስሎ በጣም ውስንና ያውም ከቅርጽ ላይ ሲሆን፤ ይዘታቸውንና ተግባራቸውን ያየን እንደሆነ ሰፊ ልዩነቶች የታዩባቸው ነው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ትንተናና ገለጻ

በቃሉ ተቋም ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይከወናሉ። ከነዚህም ውስጥ የገዳዎችን ስልጣነ-ሢመት ማጽደቅ፣ የግጭት መፍቻና ማስወገጃ ጎንዶሮ፣ የፋጭ፣ የሁሉቃ (ጦስ ማውጣት) እና የቃሉ ስያሜ ከበራዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ከበራዎች የማህበረሰቡ ዕውቀት ውጤቶች ሲሆኑ፣ እያንዳንዱ ከበራ የራሱ የሆነ መቼት፣ የራሱ የሆነ ፍችና ተግባር ወይም ፋይዳ አለው። እነዚህን ከበራዎች በንጥል ጥናት ዘዴ በመጠቀም ከኢፒስቲሞሎጂና ኦንቶሎጂ አተያይ ምን ይመስላሉ? እንዲሁም ከማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብና ተምሳሌታዊ አተረጓጎም አንጻርስ የሚሉትንና ከአውዳዊና ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ተተንትነው በዝርዝር ቀርበዋል።

## 6.1. የገዳ ስልጣን ማጽደቂያ ከበራ

የገዳ ስልጣነ ማጽደቂያ ከበራ የሚባለው በየስምንት ዓመት አንዴ በሚካሄደው የስልጣን ሽግግር ወቅት የሚከናወኑ ባህላዊ፣ መንፈሳዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ክዋኔዎችን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው። እነኚህ ክዋኔዎች ደግሞ የሚፈፀሙት የተለያዩ ሂደቶችን ደረጃ በደረጃ በማከናወን ነው። ስለዚህ በየደረጃው የሚከናወነው ምንድነው?፣ በሂደቶቹ ውስጥ ማን ምን ዓይነት ሚና አለው?፣ ሂደቶቹ የሚከወኑበት መቼት ምን ይመስላል? የሚሉትና ሌሎች ተዛማጅ ጥያቄዎችን በማንሳትና ለእነዚህ ጥያቄዎች ከቀዳማይና ካልኣይ የመረጃ ምንጮች የተገኙትን መረጃዎች በወጉ በማቀናበር፤ አግባብነት ይኖራቸዋል በተባሉ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች በመጠቀም ተተንትነዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ የሃይማኖታዊ ከበራው በገዳ የስልጣን ሽግግር ወቅት ያለውን ባህላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች ለመግለጽ ተችሏል።

በገዳ ስርዓት ውስጥ የቃሉ ተቋም ሚና ከፍተኛ ነው። ይህን በተመለከተ በ 5.1.3.1. በስፋት ተገልጿል። ከነዚህ ተግባራት ውስጥ አንዱ የገዳዎች ስልጣን በማጽደቅ ወቅት የሚከወነው ሃይማኖታዊ ከበራ ነው።

ቃሉ የገዳ መሪዎችን በመምረጥና ከበራዎችን በማከናወን፣ የገዳ ስርዓት ሕጋዊ መሰረት እንዲይዝና በገዳ መሪዎች መካከል የተካሄደውን የስልጣን ሽግግር የማጽደቅ ከበራዎች ጭምር

ያከናውናል። ነገር ግን የገዳ መሪዎችን በመምረጥ ሂደት ላይ ይሳተፋል ሲባል ቀጥተኛ ተሳትፎ አያደርግም፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ለገዳነት በሚቀርቡ ዕጩዎች ላይ ችግሮች ካሉ በህዝብ ተወካዮች አማካይነት በሚቀርብለት ጥቆማ መሰረት አስተያየት በመስጠት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ያደርጋል። ያን ካልፈጸመ በመጨረሻው ሂደት ላይ አለአግባብ ስልጣን ይዞ ቢመጣም ቃሉ የማጽደቅ ከበራውን አይፈጽምለትም። ይህ ከበራ ካልተፈጸመለት ደግሞ አንደኛ መንፈሳዊ ኃይል አልተጎናጸፈም እንደ ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ተኣማንነትና ተቀባይነት አይኖረውም። ስለዚህ እንደነዚህ ዓይነት ተፅዕኖ በማሳደር የገዳን ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት ያስጠብቃል።

አዲሱን የገዳ የአስተዳደር ጊዜያት የሚመሩ ገዳዎች የስልጣን ርክክብ የሚያከናውኑት በየራሳቸው መንፈሳዊ አረዳ (araddaa jilaa) ላይ ነው። ለምሳሌ የቀድሞው የሆኩ አባገዳ በሀሩ ጎባ (Harru Gobba)፣ የማቲ አባገዳ ደግሞ በድባ (Dibba) ሲሆን የኡራጋው አባገዳ ደግሞ በገደብ (Gadabi) እንደነበር Van de Loo, (1991፡41) ያስረዳል። ይህ የገዳ የስልጣን ሽግግር እራሱን የቻለ ሃይማኖታዊ ከበራዎች አሉት። ነገር ግን የአጥኚው ትኩረት በቃሉ ተቋም ላይ ስለሚያጠነጥን ከገዳዎች ስልጣን ሽግግር በኋላ በቃሉ ስለሚከናወነው የስልጣን ማጽደቁ ሃይማኖታዊ ከበራና ፋይዳው ላይ በጥልቀት ተፈትሿል። ስለዚህ ስለገዳ የስልጣን ሽግግር ሂደቶችን በየራሳቸው መንፈሳዊ አረዳ የሚያደርጉት በዝርዝር አልተመለከትኩም። ምክንያቱም ከጥናቱ ትኩረት አኳያ በዋናነት የሚመለከተው በሚኤ ቦኮ የሚደረገውንና በቃሉ ተቋም የሚከናወነውን የማጽደቅ ከበራ ስለሆነ ነው።

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ሁለት ዓይነት የገዳ ስልጣን እንዳሉ በ4.1.1. ስር ተገልጿል። ይኸውም፡- በአሳብዱ ኮንፌድረሲ ስር የሚገኙ የሀሎና ዌስቱ ገዳ የስልጣን ሽግግራቸው የዘር ሀረግን ተከትሎ ከአባት ወደ ልጅ ሲሆን፣ አባትዬው እስከ እልፈተ-ሕይወቱ በስልጣኑ ያገለግላል። ከዚያን በኋላ ከልጆቹ ውስጥ ተመርጦ ይሾምና ጎሳው ስጦታዎችን በመያዝና ወደቃሉ በመውሰድ ስልጣኑ እንዲጸድቅ ያስደርጋሉ።

ቀደም ሲል በጥናቱ ወሰን ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጥናት በዝርዝር የተመለከተው በየስምንት ዓመቱ በዴሞክራሲያው መንገድ የስልጣን ሽግግር በሚያደርጉት የኡራጋ፣ የሆኩና የማቲ ኮንፌድረሲዎች ላይ ነው። እነዚህ ገዳዎች ከየተቋሚቸው በመነሳት ለብዙ ወራት ከመማክርት አባላቶቻቸውና ታዳሚዎች ጋር በመሆን ወደ ሚኤ ቦኮ ጉዞ ያደርጋሉ። ሚኤ ቦኮ

(Me'ee Bokkoo) በጉጂ አካባቢ ከሚገኙ ባህላዊና ፖለቲካዊ ክበራዎች ከሚካሄዱባቸው ቦታዎች አንዱ ነው። ከጉጂ ኦሮሞ ገዳ መደብ ውስጥ ራባ (Raaba)፣ ዶሪ (Doorii) እና ገዳ (Gadaa) እርከን ላይ የሚገኙት በየስንምት ዓመቱ የገዳ ስልጣን የሚረካከቡበት መንፈሳዊ ቦታ ነው። ታዲያ እዚህ ቦታ ከመድረሳቸው በፊት እድምተኞቹ በመስመራቸው ላይ በሚገኙ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ክበራዎች በሚከናወኑባቸው ቦታዎች እርድ እየፈፀሙ፣ መስዋዕት እያቀረቡ፣ እግዚኣብሔርን እየተለማመኑ፣ ህዝባቸውን፣ ከብቶቻቸውንና ምድሯን እየመረቁ ይጓዛሉ። በጉዞው መስመር ላይ የሚገኙ ምዕመኑም በየቦታው ለታዳሚዎቹ የሚሆን ምግብና የሚጠጡትን ወተት ከየቤታቸው በማምጣት፣ ለመስዋዕት የሚሆኑ ከብቶችንም በማዘጋጀት ይጠባበቃሉ። እዚያም ሲደርሱ ያስተናግዷቸዋል። ሚኤ ቦኮ እንደደረሱ የአካባቢው ማህበረሰብ ለእድምተኞቹ ማረፊያ ‹ቃቻ› ይሰራሉ። በዚህ ቦታ የእግዚኣብሔር ትዕዛዛት ይፈጸምባቸዋል ተብሎ የሚያምኑባቸው "ሚኤ" የሚባሉ ዛፎች (Muka woyyuu) ስር ይገናኛሉ።




ፎቶ፡- 10 እና 11 በሚኤ ቦኮ የተሰሩት ጊዜያዊ ማረፊያ (ቃቻ) በከፊል የሚያሳዩ

በመቀጠል ከነዚህ የገዳ መደቦች ሰባት ሰባት ሰዎች ይወከላሉ። ይኸውም፡- ከኡራጋ ገዳ መደብ ውስጥ ከራባ ሰባት፣ ከዶሪ ሰባት እንዲሁም ከገዳ መደብ ሰባት በድምሩ ሃያ አንድ ተወካዮች ይዘጋጃሉ። ከተቀሩትም ሁለቱ ገዳዎች ውስጥ እንዲሁ ሃያ አንድ፣ ሃያ አንድ ተወካዮች በድምሩ ወደ ስልሳ ሦስት የሚሆኑ ተወካዮች ለጉዞው ይዘጋጃሉ። የተቀሩት በሚኤ ቦኮ ከትመው ይጠባበቃሉ። ከአዲሶቹ ገዳዎች ጋር በአባቃሉ ስልጣናቸውን ለማጽደቅ፣ ምርቃትና ክርቤ (qunbii) ለመቀበል፤ ስጦታዎችን ይዘው ቃሉ ወደሚኖርበት ስፍራ (galma qaalluu)፤

ወደ ቆቲ መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋሉ። ይህ ጉዞ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የጉቱ (guttuu) ጉዞ ተብሎ ይታወቃል። ተምሳሌትነቱም የመሞላት ጉዞ፤ የመባረክ ጉዞ መሆኑን ነው። (ጎባና ቶቴ፣ አባያ ወረዳ፣ ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ ገዳ ዋቆ ዱቤ፣ 9/6/2008 ዓ.ም. የኡራጋ አባገዳ የነበሩ)

ይህን መንፈሳዊ ጉዞ ቀደም ሲል በማቲ፣ ሆኩና ኡራጋ ገዳዎች ቡድን እንዴት እንደነበር Van de Loo, (1991፡53-54) ባጭሩ ሲያስረዳ፡- እነዚህ ከተለያየ አቅጣጫ የተነሱት የገዳዎች ቡድን የተለያዩ ሀገራትን አቋርጠው፤ በመጨረሻ በሀራ ቃሎ (Hara qalloo) አካባቢ በሚገኙ መስኮች ላይ ይገናኛሉ። ከሀራ ቃሎ ሦስቱም ቡድን ወደ ድባ (Dibba)፣ ቦሬ ጎሮ፣ ሀሮ ጋርቤ (ጋርቢቾ)፣ ዳማ፣ ብርብርሳ፣ እያሉ ዲላ ይደርሳሉ። ከዚያ ወደ ወናጎ፣ በመጨረሻም ወደ ቆቲ፤ የአላብዱ ቃሉ ገልማ ጉዞ ያደርጋሉ።

ይህን ወደ ቃሉ ተቋም የሚደረገውን የጉቱ ጉዞ በሌሎች የኦሮሞ አካባቢዎች የሙዳ ጉዞ በመባል ይታወቃል። ቃሉን አባ ሙዳ ይሉታል። ከበራውን ደግሞ የሙዳ ከበራ (sirna muuda) ይባላል። አባገዳ ከተመረጡ በኋላ ወደ አባሙዳ ወይም ቃሉ ዘንድ ገፀ-በረከት ይዘው ይሄዳሉ።

ይህ መንፈሳዊ ጉዞ የሚታቀደው በየስምንት ዓመቱ አንዴ ወደ መጨረሻው አካባቢ ነው። በመጨረሻም ጉዞው የሚያበቃውና አዲሶቹ ገዳዎች ስራቸውን የሚጀምሩት ደግሞ ወደ እራሳቸው ተቋም ከተመለሱ በሁለት ወራት አካባቢ እንደሚሆን መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ።

የጉጂ ማህበረሰብ ይህን መንፈሳዊ ጉዞ በዋናነት እንደ ማህበረሰባዊ ግንኙነት ማጠናከሪያ፣ ስለእራሳቸውና ስለአለም አፈጣጠር የሚረዱበት፣ እንደ ሃይማኖታዊ ከበራ የሚያዩበት፣ ቡራኬ (ምርቃት) ለመቀበል እና ህብረት ለመፍጠር እንደሚገለገሉበት ይገልጻሉ።

የጉጂ ኦሮሞ አባገዳዎች ቡራኬ ለማግኘትና ስልጣናቸውን ለማጸደቅ ወደ ቃሉ ገልማ የሚያደርጉት የጉቱ ጉዞን ጥንተ-መጥነቱን በሚታቸው ውስጥ ሲያረጋግጡም ይታያሉ። ይኸውም፡-

> የቃሉ ቅምቅም አያት ከሰማይ ወረደ። ድሮ አንድ የጉጂ ሰው ነበር። አንድ በጣም ግዙፍ የሆነ ሰው አየ። ያ ሰው ሰውነቱ በረጃጅም ጸጉር የተሸፈነ ነበር። ይህ ሰው ዙሪያውን ቸል ብሎ ይመለከት ጀመር። እንዲረዱትም ጠየቀ። ቀደም

ብሎ ያየው ሰው ምንም ሊረዳው አልቻለም። ከዚያም ወደ ባህል አዋቂ (cidheessa) ሄደ። ያም የባህል አዋቂ ሰውዬም አሰብ አድርጎ ሰውነቱን ሸፍኖት የነበረውን ጸጉር ላጨለት። በመቀጠል ትንሽ ልብስ ብጤ አምጥቶ አለበሰው። ከዚያም ያን የባህል አዋቂ ሰው ባረከው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ የተመረቀው ሰው የጉጂ የመጀመሪያ አባገዳ ሆነ። የሚል ነው

ከዚህ ሚት የምንረዳው የመጀመሪያው ቃሉ ከሰማይ መውረዱንና በወቅቱ መላ ሰውነቱ በጸጉር የተሸፈነ ስለነበር ሃይማኖታዊና ባህላዊ ዕውቀት ያለው ሰው እንደረዳውና በምላሹም እሱን እንደባረከው ነው። በመጨረሻም ይህ የተባረከው ሰው የጉጂ የመጀመሪያ አባገዳ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው። ይህን ከማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ስናየው ቃሉ ሰው እንደሆነና ነገር ግን በተክለሰውነቱ ደግሞ ከሰው ገዘፍ የሚልና መላ ሰውነቱ በጸጉር የተሸፈነ አድርጎ መሳላቸው ከተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ ሀሳብ አኳያ ሰው ሆኖ ነገር ግን ከሰው ለየት ያለ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ምግባሩንም በተመለከተ በፊት የተወሰነ ባህላዊ ዕውቀት ያለውን ሰው በመመረቅ የተሻለ መንፈሳዊና የማስተዳደር ኃይል እንዳላበሰው ያሳየናል። ይኸውም መጀመሪያ በማህበረሰቡ ውስጥ በተወሰን ደረጃ የነበረውን አቅም ወደ ጎሳን የመምራትና ማስተዳደር ማለትም ገዳ ደረጃ እንዳሳደገው ነው።

ሌላው ከዚህ ሚት የምንረዳው ቃሉ ገዳዎችን መመረቅና መንፈሳዊ ኃይል እንደሚያላብስና ገዳ ደግሞ ይህን ጸጋ ለማግኘት ለቃሉ ስጦታ በማቅረብ መባረክ እንዳለበት አመላካች ነው። በመሆኑም አባገዳዎች ከቃሉ ገልማ (ቆቲ) የሚሄዱት ቡራኬ (ምርቃት) ለመቀበልና ለስልጣናቸውም እውቅና እንዲሰጣቸው በማሰብ ነው። ይህ ምርቃት ደግሞ አባገዳዎቹ ከፖለቲካዊ የአስተዳደር ስልጣን በተጨማሪ ሃይማኖታዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ መንፈሳዊ ኃይል ያላብሳቸዋል ተብሎ ስለምታመንም ጭምር ነው። ስለዚህ የአባገዳና የአስተዳዳሪዎቹ ጉባኤ መደብ ላይ ያሉትን ቡድኖች ፀጋ እንዲላበሱ የሚደረገው የገዳ ስልጣን በሚጸድቅበት ወቅት በቃሉ አማካይነት ከርቤ (ቁንቢ) በማስነከስ እንደሆነ ይታመናል።



ፎቶ፡-12 የቀድሞ የኡራጋ ገዳ የነበሩ አጋ ጤንጣኖና የመማክርት አባላትን የሚያሳይ ፎቶ

ከርቤ (ቁንቢ) ከዋቂፋና ሃይማኖት አኳያ የተቀደሰ ቁስ ነው፤ እውነት ያናግራል ተብሎ ይታመናል። እንደእምነቱ ከአባሙዳ ከርቤ ተቀብሎ የበላ ሰው፤ የእግዚኣብሔር ህግ፣ የጥንቱን የኦሮሞ ስርዓት ማዛመም፣ ሀጢያት መስራት፣ ውሸት መናገር የለበትም። ህብረተሰቡንም በእውነተኛ ህግ እንዲያስተዳድር በቃሉ ምክር ይለገሳል። በሌላ መልኩ ይህ የአባ ሙዳ ምክር ደግሞ አባቃሉ በኦሮሞ ፖለቲካ ውስጥ ያለውን ድርሻ የሚያመላክት ነው።

ከዚህ የተነሳ ገዳዎች ቡራኬ ለመቀበል ከነመማክርት አባላቶቻቸው ጋር ሆነው ለቃሉ የሚሆኑ ብዙ ከብቶችን በስጦታ መልክ ይወስዱ ነበር። እንደ Van de Loo (1991) ገለጻ ከሆነ በሚቀጥለው ቀን ዘጠና ዘጠኝ ኮርማዎችና ጊደሮች (kormaafi raada) እንዲሁም ዘጠና ዘጠኝ የበግ ጠቦቶች (korbeessaafi goromtii) ለቃሉ ይሰጡታል። የበግ ወጠጤዎቹንና ኮርማዎቹን በቀጭኑ በተተለተለ ቆዳ በዛጎል አስውቦ እንደታሰሩ እንደሚሰጡ ያስረዳል። ከዚያም በቅድሚያ ካሉዎቹ ከብቶቹን ይቀበላቸዋል። በመቀጠል ወደ ሰፊ መስክ እንዲሰማሩ ያደርጋሉ። ነገር ግን በወቅቱ ውክልናቸውን (ኃላፊነታቸውን) የመወጣት ልምምድ፤ ድንገተኛ የማጥቃትና መከላከል ተምሳሌት የሆነውን ክዋኔ በቃሉ ገልማ አካባቢ ያካሂዳሉ። ይኸውም፡- የእነሱን ስኬታማነት ለማረጋገጥ ከአላብዱ ጉጂ ወገን የሆኑት በአንድ ወገን ሆነው አንድ ላም ለመውሰድ ይጣጣራሉ። እነሱ ደግሞ እንዳይወስድባቸው በጦር ለማጥቃት ሲነሱ፤ የአላብዱ ጉጂዎች ደግሞ ይከላከላሉ። ከዚያ በዚህ ሂደት ውስጥ የተወሰኑ ሰዎች ይቆስላሉ። በዚህን ጊዜ ሁለቱም

ወገን ደንገጥ ይላሉ፤ ከዚያ ግጭቱን ቀስ ብለው ያረግባሉ። በመቀጠል ሁለቱም ወገን አንድ በግ በማንሳት ከአጥሩ ላይ ከፍ አድርገው ወደ ውስጥ ይወረውራሉ። ይህም ክዋኔ በላምቱ ምክንያት የተደረገው ግጭት ተምሳሌትነቱ እዚያ የተሳተፉት አካላት የኦሮሞን ህዝብ የጋራ መነሻ (Origin)፣ እርስ በርሳቸው በሰላም የሚኖሩ፣ በክብት የተነሳ የሚያደርጉትን ግጭትና ክርክር መርሳታቸውን የሚያመላክት እንደሆነ ያስረዳል።

ነገር ግን ከመረጃ አቀባዮቼ እንደተረዳሁት ከሆነ የከብቶቹም ብዛት ሆነ ክዋኔው ከዚህ በተወሰነ ደረጃ የተለየ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ይኸውም፡- የኡራጋው ገዳ ሰላሳ ሦስት ከብቶች፣ የማቲና የሆኩም እንዲሁ ሰላሳ ሦስት፣ ሰላሳ ሦስት በድምሩ ዘጠና ዘጠኝ ኮርማዎችና ጊደሮች (kormaafi raada) እና አንድ በግ አዳማ የሚባልበት ቦታ ላይ ይሰባሰባል። ከበጉ ጋር መቶ ይሆናሉ። ከዚህም የተነሳ የቦታው መጠሪያ አዳማ ድባ (adaamma dhibbaa) ይባላል። ከዚያን በኋላ እነዚያን ዘጠና ዘጠኝ ከብቶችና አንድ የስጦታውን ይሁንታ መግለጫ በግ (hoolaa batalaa) በቀጭኑ የተተለተሉ ቆዳዎች በዛጎል አጊጤው የበጉን መላ ሰውነቱን አስውበው በመንዳት ወደ ገልማው ይጓዛሉ። የአላብዱ ህዝብ በቃሉ ተቋም ተሰባስበው ለምርቃትና ስልጣኑ-ሢመታቸውን ለማጽደቅ የመጡት አባገዳዎች ካመጡት የስጦታ ከብቶች ምንም አይወስዱም። ነገር ግን ወደ ቃሉ የከብቶች ማቆያ መስክ ቀድሞ ለማስገባት የሚያደረጉት ፉክክር ማለትም የኔ ይቅደም፤ የእኔ ይቀደም ሲሉ፣ አላብዱዎች ደግሞ የሁሉንም ወደ ኋላ በመመለስ ሂደት የሚፈጠር ቀለል ያለ ግጭት እንደሆነ ይገልጻሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ያን ድርጊት የሚያከናውኑት ረጃጅም ልምጮች (baabbe) በመቁረጥ በፀሐይ ላይ ያሞቁታል። በሌላ በኩል የገዳዎቹም ወገን እንዲሁ ይዘጋጃሉ። ከዚህ ባለፈ ጦር ይዘው ግጭት አይፈጥሩም። ለዚህም እንደምክንያት የሚያስቀምጡት በቃሉ ተቋም የሰው ደም መፍሰስ እንደሌለበት ያስረዳሉ። በዚህ ክዋኔ መካከል ላይ ከቃሉ መማክርት አባላት ሄደው ያንን በዛጎል ያጌጠውን በግ ይይዛሉ። የገዳዎቹም ቡድን ‹‹የቃሉ ወገን ማርኮናል።›› (worri Qaalluu boji'eera.) በማለት አሸናፊነታቸውን ያረጋግጡላቸውና ጊዜያዊ ግጭቱ እልባት ያገኛል። ከዚያን በኋላ ገዳዎቹም ከነስጦታቸው ወደ ግቢው እንዲዘልቁ ይደረጋል። ወዲያውኑ አባ ገዳዎቹም በጋሮ በኩል ዞረው ዘጠኝ ጊዜ ደጋግመው አባቃሉን እጅ ይነሳሉ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Abba Qalluu Yooyyaa! (9x) | ጤና ይስጥልኝ አባቃሉ (9x) |
| Haadhabola Yooyyaa!! | ጤና ይስጥልኝ የእኛ እናት |

worri kun worra maaliiti? እዚህ ቤቶች፤ ምን የሆኑ ሰዎች ናቸው?

(gidduutti jedhu) (በየጣልቃው)

bultanee namaa kan hin qabne; ለሰው ሰላምታ ምላሽ የማይሰጡ።

nama jalaan kan hin owwaatne. ሲጠሯቸው አቤት የማይሉ። እያሉ በተደጋጋሚ ዘጠኝ ጊዜ ብለው በአስረኛው ላይ አባቃሉ ጤና ይስጥልኝ (Yooyyaa!) በሚሉበት ጊዜ ቃሉም ጤና ይስጥልኝ (Yooyyaa!) በማለት ምላሽ ይሰጣሉ። በመቀጠል የአባ ገዳዎቹ ቡድን፦

Ee! Qaalluu keenya nuuf jiraadhu, አዎ! የእኛ አባቃሉ ኑርልን፣

Qaalluu keenya nuuf naga'l, የእኛ አባቃሉ ሰላም ሁንልን፣

Qaalluu keenya gabadhu. የእኛ አባቃሉ ይመችህ። በማለት ለሰላምታቸው ምላሽ በመስጠቱ ደስታቸውንና መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ።

ከዚያም በፊት ለፊት ዞረው ያመጡትን ስጦታ ማለትም፦ ዘጠና ዘጠኝ ኮርማዎችና ጊደሮች፣ እንዲሁም ለቡና ቃላ የሚሆን ድፍን ደረቅ ቡና፣ ማርና በዛጎል ያጌጠውን በግ ይሰጣሉ። አባቃሉ ያንን በግ ወዲያውኑ ያርደዋል። (አባገዳ ጋምቤላ በርሶ፣ የሆኩ አባገዳ የነበሩ፣ በ8/6/2008፣ ሚኤ ቦኮ ላይ)

ገዳዎቹ እኚህን ስጦታዎች ይዘው፤ እነሱ በጓሮ በኩል አልፈው ሰላምታ መጠየቃቸው፣ እንዲሁም ከአንዴም፤ ዘጠኝ ጊዜ «ዮያ አባቃሉ» ሲሉ ዝም ብሎ በአስረኛው ምላሹን «ዮያ» ማለቱ ከፍቻዊ አውድ አኳያ የቃሉን ክቡርነት አግዝፎ ማሳያ ናቸው። በሌላ በኩል ካየነው ከተቋማዊ አውድ አኳያ ደግሞ በባህሉ መሰረት የሰው ቤት የሄደ ሰው ሰላምታ የሚያቀርበው ከፊት ለፊት በኩል ነው። ነገር ግን ከኋላ በኩል ማለፋቸው ለተቋሙና ለተቋሙ መሪ ካላቸው አክብሮት፣ ያለእሱ ፍቃድ ከፊቱ መቆም አለመቻላቸውን የሚገልጹበት ክዋኔ መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ማህበራዊ መሰረቱን የተመለከትን እንደሆነ እነሱ ከቃሉ ቁንቢ በመቀበል፤ ተመርቀው ስልጣናቸው የሚጸድቅላቸው አካላት ሲሆኑ፤ ቃሉ ደግሞ የማጽደቅና ቡራኬ የመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑን ያሳያል።

በሌላ በኩል ዘጠኝ ጊዜ ዮያ «Abba Qalluu Yooyyaa!» ማለታቸውን አረጋግጦ በአስረኛው ምላሽ መስጠቱ ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ የሦስቱም አባገዳዎች ሦስት፣ ሦስት የገዳ ክፍሎች ማለትም የገዳ፣ የዶሪና የራባ አባላት ተሟልተው ዘጠኙም መምጣታቸውን ማረጋገጫ ሲሆንና የመጨረሻዋ ዮያ ደግሞ በአንድነት ሰላም ማለቱን ያመላክታል።

ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ ምላሽ መስጠት (ዮያ ማለት) እንደ እሺታ ስለሚቆጠር ከፊት ለፊት አልፈው ስጦታቸውን ያበረክታሉ። በዚያን ጊዜ ቃሉ በዛጎል አጊጦ የመጣውን በግ ወዲያ ከገልማው ፊት ለፊት ያርደዋል። ይህን ድርጊት ከግለሰባዊ አውድ አኳያ ቃሉ ስጦታዎቹን በፀጋ ለመቀበሉ እንደማሳያነት ያገለግላል።

ነገር ግን ከመጡት እጩ ገዳዎች (አባ ሙርቲዎች) ውስጥ ያለህዝቡ ፍላጎት የተመረጠና ቀደም ብሎ ለቃሉ ችግሩ ተገልጾለት እያለ እንዲያስተካክሉ ተነግሯቸው በምንቸገረኝነት የመጣ ካለ፤ ቃሉ በአስረኛው ጊዜም «ዮያ» በማለት ሰላምታውን ምላሽ አይሰጥም። ሰላምታውን ካልመለሰ ደግሞ ስጦታቸውን አይቀበልም ማለት ነው። ስጦታውን ተቀብሎ፤ ያን የይሁንታ መግለጫ በግ (hoola batalaa) አያርድም። ሁሉም ክዋኔ እዚህ ላይ ይቆማል። ይህን ስርዓት ካልፈጸሙ ደግሞ ወደ ጎሳቸው ሲወርዱ ተቀባይነት አያገኙም። ስለዚህ ቀድሞውኑ ተዘጋጅተውና አሟልተው ይሄዳሉ። በዚህ መልኩ የቃሉ ተቋም የገዳን ስልጣን ሽግግር ዴሞክራሲያዊ አካሄዱን ያስጠብቃል። ይህ ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ የቃሉን የገዳ ስልጣን ማጽደቅ ፖለቲካዊ ፋይዳን ያሳየናል።

በሌላ መልኩ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ጎዶሎ ቁጥሮች የመጥፎ ዕድል እና የመጥፎ ክስተቶች ተምሳሌት እንደሆኑ ይታመናሉ። በተለይም ዘጠኝ ቁጥርን ከጣረሞት (ghost)፣ ሕመም (illness) እና ሞት (death) ከመሳሰሉ አስጊ ክስተቶች ጋር ያያይዙታል (Taddesse, 2013፡65)።

ለዚህም እንደ መገለጫ የሚያገለግሉ የተለያዩ የፎክሎር ቅንጣቶች እንዳሉ ተገልጸዋል። ከነዚህም ውስጥ ስለዘጠኝ ቁጥር የሚነገር እንቆቅልሽ አንዱ ነው። ይኸውም፡- ልጆች ቁጥር ነክ የሆነውን «Tokko maali?» የሚለውን እንቆቅልሽ በሚጫወቱበት ወቅት እራሱን የቻለ የአጠያየቅና አመላለስ ስርዓት አለው። በጫወታው ህግ መሰረት አንድ ቁጥር በሚጠየቅበት ጊዜ ከዚያ ቁጥር ጋር ቀደም ሲል ከሚታወቁ ነገሮች፣ ክስተቶችና ሁነቶች ጋር በማያያዝ «ይሄማ እንትን ነው» በሚል ስሜት ይመልሳሉ። ለምሳሌ

| ጠያቂው | መላሹ |
|---|---|
| Tokko maali? | Tokko quboolee. |
| አንድ ምንድነው? | አንድማ ጣት ናት። |
| Lamma maali? | Lamma mucha re'ee, tokko quboolee. |
| ሁለት ምንድነው? | ሁለትማ የፍዬል ጡት፣ አንድ ጣት ናት። |
| Sadi maali? | Sadi sunsuma aayya, Lamma mucha re'ee, tokko quboolee... |

| | |
|---|---|
| ሦስት ምንድነው? | ሦስትማ የማዬ ጉልቻ፣ ሁለት የፍዬል ጡት፣አንድ ጣት ናት።… |
| Jahaa maali? | Jahaa jabbii qaraxaa… |
| ስድስት ምንድነው? | ስድስትማ የጥሎሽ/ ስጦታ ጥጆች… |
| Sagali maali? | Sagali lakkofsa ekeraa… (Taddessee, 2013:58-59) |
| ዘጠኝ ምንድነው? | ዘጠኝማ የጣረሞት ቁጥር… በማለት እስከ መቶ ቁጥሮች |

ለሚጠየቁት ከባህሉ፣ ከተፈጥሮው፣ ከተለያዩ ክስተቶችና ሁነቶች ጋር በማዛመድ በእንቆቅልሽ ብዙ ነገሮችን እንደሚማሩ ለመረዳት ችያለሁ። ነገር ግን ዋናው ሀሳብ በዚህ እንቆቅልሽ ውስጥ የዘጠኝ ቁጥር ከጣረሞት ጋር መያያዙ ምናልባትም ቃሉ ዘጠኝ ጊዜ አባቃሉ ጤና ይስጥልኝ (Yooyyaa!) ሲባሉ ዝምታቸው ከዚህ የመነጨ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም የቀደምት አባቶች ጣረሞት ከአከባቢው እንደማይርቅ ስለሚታመን ምናልባትም ይህ ጥሪ የገዳዎቹ ነው ወይም የጣረሞቱ ነው በማለት በማጣራት በአስረኛው ጤና ይስጥልኝ በማለት የሚመልሰው።

ዘጠኝ ቁጥር በሌላ በኩል ከዘጠነኛ ልጅ እርግዝናና ወልድ ጋር ተያይዞ በቤተሰብ ደረጃ ይዞ ይመጣል ተብሎ የሚታመን መጥፎ ዕድልና ስጋት፤ እንዲሁም ይህን ስጋት ለመቀነስና ለማስቀረት የሚደረገውን ከበራም ተገልጿል (ዝኒ ከማሁ: 60)።

ከዚህ በተጨማሪ «Gaalli Sagali bule, Kudhan bulu hindadhabu.» የሚል ምሳሌያዊ አነጋገርም አለ። ትርጉሙም:- «ዘጠኝ ቀን ያደረ ግመል፣ አስረኛው ማደር አያቅተውም።» እንደማለት ነው። ከትንተናው ለመረዳት እንደተቻለው፤ አንድ ግመል ዘጠኝ ቀን ሙሉ ያለውሃ ካደረ፤ አስረኛውንም ሊያድር እንደሚችል ነው። ይኸውም:- ዘጠኝ ጎዶሎ ነው፤ የመጥፎ ዕድል፣ የሞት ተምሳሌት ነው። ስለዚህ ያን መጥፎ ቀን ካለፈ ምንም አይሆንም እንደማለት ነው። በተምሳሌትነቱ ለማስተላለፍ የተፈለገው የትዕግስትን አስፈላጊነት ለማስረዳት ነው።
ሌላው ከዘጠኝ ቁጥር ጋር ተያይዞ የሚነገር ምሳሌያዊ አነጋገር «Haluun dhiira wagaaa sagalti bati.» የሚል ነው። ትርጉሙም:- «ወንድ ልጅ ቂሙን በዘጠኝ ዓመትም ይወጣል።» እንደማለት ነው። ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር አንድ ዘመዱ በጠላት የተገደለበት ሰው፤ የሟቹን ደም ዘጠኝ ዓመት ቢሞላውም እንኳን እንደሚበቀል የሚገልጽ ነው ((ዝኒ ከማሁ)።

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተገለጹትና ሌሎችም ከዘጠኝ ቁጥር ጋር በመጥፎ ዕድልነት የተያያዙት ተምሳሌታዊ መገለጫዎች ባንድ ላይ ተዳምረው ቃሉን ምናልባትም እስከ ዘጠነኛው ጥሪ ዝም ብለው በአስረኛው ላይ አባቃሉ ‹ዮያ› በሚሉበት ጊዜ ቃሉም ‹ዮያ› በማለት ምላሽ እንዲሰጡ ምክንያት ሊሆናቸው ይችላል።

በመጨረሻም ይህ ክዋኔ በአግባቡ ከተከናወነ በኋላ በቃሉ ገልማ ቀድሞ ከተጣለው ጠጅ ካሎዎቹ በቅል (duloo) እየቀዱ ያቀርባሉ። ገዳ እንኩ፣ ዩባ እንኩ፣ እያሉ በየደረጃቸው ያን ጠጅ ይሰጧቸዋል። ገዳዎቹ ያንን ጠጅ እየተጎነጩ እንትፍታ (biifee) እያሉ:-

| | |
|---|---|
| Qaalluun nu'uu naga'i | ቃሉ ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| Gadaan nu'uu naga'i | ገዳ ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| mangudoon nu'uu naga'i | አዛውንቶቻችን ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| biyyi nu'uu naga'i | ሀገራችን ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| ilmi nu'uu naga'i | ወንዶች ልጆቻችን ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| durbi nu'uu naga'i | ሴቶች ልጆቻችን ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| Galmi nu'uu naga'i | ገልማው ለእኛ ሰላም ይሁን በማለት ይመርቃሉ። |

ከዚያም አባቃሉ አንተም ጠጣና ለእኛም ፍቀድልን በማለት ይጠይቃሉ። ቃሉ ከቦካው ሲቀምስ ወዲያውኑ ያን በቅል እየተሞላ የተሰጣቸውን ጠጅ እየጠጡና እየጨፈሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ማረፊያቸው ይሄዳሉ። በማግስቱ አባቃሉ ደግሞ ለአባገዳዎቹ በየስማቸው የሰቡ ሰንጋዎችን ነድቶ ይሰጣቸዋል። እነኛን ሰንጋዎች በየቦታው ያርዱና ስጋውን ብቻ በመለየት ይቀቅላሉ፤ ከዚያም ቀኑን ሙሉ ይመገቡታል። በመጨረሻም ባህላዊ ጭፈራ ይጨፈራል። (ገዳ ጋምቤላ በርሶ፣ በ9/6/2008 ዓ.ም. ሚኤ ቦኮ፤አቶ አባባ ቶቴ፣ 22/7/2008 ዓ.ም. በወናጎ ወረዳ፣ የቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

በመቀጠል ከአባቃሉ ቁንቢ ለመቀበል ከማረፊያ ቦታቸው ወደገልማው ሲመጡ አባገዳዎቹ በጋራ ቃሉን የሚጠይቁት (የሚለምኑት) ነገር አለ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| bara nuu beeki, | ዓመቱን እወቅልን፣ |
| ji'a nuu beeki, | ወራቱን እወቅልን፣ |
| jila nuu beeki, | የሃይማኖታዊ ክበራዎችን እወቅልን፣ |
| kooba nuu beeki, | የመስዋዕት ማቅረቢያ ተራራውን እወቅልን |

በማለት ይጠይቃሉ። (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ የሆኑት፣ በ25/6/2008 ዓ.ም.)

ከዚያም አባቃሉ ስጦታውን በመረከብ ይመርቃል፤ የሚቀጥለውን ፀሎትም ያደርሳል።

| | |
|---|---|
| Naga'e abbaa Gadoo | ሰላም ሁን አባገዳ፣ |
| Ee dhugaa jilaa hin wollaaliin, | አዎ! የሃይማኖታዊ ክበራውን መሰረቱን አትርሳ፣ |
| ji'a hin wollaaliin, | ወራቱን አትርሳ፣ |
| ayyaan hin wollaaliin, | የእግዚአብሔርን መንፈስ አትርሳ፣ |

| | |
|---|---|
| bantittiin kan bantichaati, | ልጃገረድ ላላገባው ነች፣ |
| ardaan Gujii micciirraa hin qabu, | የጉጂ ህዝብ ተንኮል የለውም፣ |
| ilmi Gujii micciirraa hin qabu, | የጉጂ ልጅ ተንኮል የለበትም፣ |
| bantittiin micciirraa hin qabud, | ልጃገረድ(ድንግል) ተንኮል የለባትም፣ |
| Gujiin Gujii, Gujiin wal-hin ajjeessuu, | ጉጂ ጉጂ ነው፤ ጉጂ እርስ በርሱ አይገዳደልም፣ |
| Wal-hin ajjeessinaa, | እርስ በርስ አትገዳደሉ፣ |
| Oboleettii teessan hin fuudhinaa, | የራሳችሁን እህት አታግቡ፣ |
| Dhugaan waan duri jirati, | እውነት ጥንትም ያለ ነው፣ |
| danuu danuu beeka, | ያጋጣሚ ክስተት ያጋጣሚ ነው እወቁ፣ |
| isii wonni Gujii, | ይህ ነው የጉጂ ወግ፣ |
| ifii dhiigaan baddani, | እጃችሁ በደም ይበላሻል፣ |
| Gujiin wal hin ajjeessitn, | ጉጂ እርስ በርስ አይገዳደልም፣ |
| danuu gaafa wal-ajjeesse, | ባጋጣሚ ከተገዳደለ፣ |
| dhugaa sani dhaggi...... | ያንን እውነት አጣራ(በአግባቡ እየው) |
| Jedhee gorsa Gadaa, | በማለት ገዳ ይመክራል፣ |
| Jedhee gorsa Qaalluun, | በማለት ቃሉ ይመክራል፣ |
| Jedhee qooda, | በማለት ይከፋፍላል፣ |
| Qooda Gadaa gorsasaan qooda, | የገዳን የስራ ድርሻ በምክር ይከፍላል፣ |
| Raabaatti hima, | ለራባ ይነግራል፣ |
| Jadhaabaatti hima, | ለጃልዳባ ይነግራል፣ |
| Waamuratti hima, | ለሙራ ይነግራል፣ |
| Murtiitti hima, | ለሙርቲ ይነግራል |
| Akkana jedhee gorsa. | እንዲህ ብሎ ይመክራል። (አቶ ሞኮና |

ናጋኦ፣ በቆቲ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ የተወሰደ)

ይህ በምርቃት መልክ የሚተላለፈው ማህበረሰባዊ ዕውቀት ቀድሞ በሚት መልክ በሳብጀክትቭዚም ኢፒስቲሞሎጂ አተያይ ያደራጁት ነው። ይኸውም ጉጂ ጉጂን አይገድልም፤ ነገር ግን በስህተት ከተከሰተ ደግሞ ምን ይደረግ ለሚለው፤ የጎንዶሮ ከበራን ማህበረሰባዊ

ዕውቀት በማዋቀርና ወደቃሉ ተቋም ከገባ በኋላ ልክ እንደ ህግ፣ ልማድና ባህል ሆኖ መልሶ በቃሉና ገዳ አማካይነት ማህበረሰቡ እንዴት መተዳደር እንዳለባቸው ተመልሶ ወደታችኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሚወርድ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ለገዳዎቹም በምን ላስተዳድር፣ ከእነማን ጋር ላስተዳድር የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ ከማህበረሰቡ በፈለቁና በቃሉ ተቋም አማካይነት ተመልሰው ለማህበረሰቡ በምርቃትና ምክር መልክ እንደ ህግ፣ ደንብና ልማድ የሚያገለግሉ ዕውቀቶች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ሌላው ከማህበረሰቡ በኩል ደግሞ እንዴት ተጠባብቀው፣ ተከባብረውና ተደማምጠው መኖር እንዳለባቸውም ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ይህን ሂደት በሌላ በኩል ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ ሃይማኖታዊ ከበራው ያለውን ማህበረሰባዊ ፋይዳ ያሳያል፡፡

ሌላው በማግስቱ እንደታላቅነትና ተከታይነታቸው በቅድሚያ የኡራጋ ገዳ ከመማክርት አባላቱ ጋር፣ ቀጥሎ የማቲ ገዳና እንዲሁም በስተመጨረሻ የሆኩ ገዳ ተራ በተራ ከገልማው ፊት ለፊት ካለው ሂሮ መነሻ በማድረግ እስከ ገልማ ውስጥ አንድ በአንድ ተቀምጠው በመንፏቀቅ ይሄዱና ከቃሉ እጅ በአፋቸው ከርቤ (qumbii) ይቀበላሉ፡፡ ይህ ስርዓት ከተጀመረበት ሰዓት አንስቶ ለእያንዳንዱ እስከሚዳረስ ድረስ መተኛት አይቻልም፡፡ ከርቤውን የቀመሱትም ምንም ነገር አይናገሩም፤ በተቀመጡበት እስኪነጋ ይጠባበቃሉ፡፡ አባቃሉም ከርቤውን በአንድ እጁ እያቀመሳቸው፣ ከታረደው ከብት በገቦቱ የቀረበውን ደሙ እየነከረ በላያቸው ላይ ግራና ቀኝ እየረጨ፣ ከጠጁ እያቀመሳቸው ይመርቃቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ህዝባቸውን በባህሉና በሃይማኖቱ መሰረት እንዲመሩ፣ ያለአድሎ እንዲያስተዳድሩ ቃለ-መሀላ ያስፈጽማል፡፡

ከርቤውን በአፋቸው ሲቀበሉ ገዳዎቹ በእጃቸው ጋርደው በመውሰድ የተወሰነውን በማስቀረት ሌላውን በተጎነጬት ጠጅ ያወራርዱታል፡፡ አባገዳ ከርቤ (qumbii) ከቀመሰ በኋላ ውሃ እንኳን በራሱ እጅ አይጠጣም፤ ሰው ነው የሚያጠጣው፡፡ ሀዩ የሆነ ሰው ከአጠገቡ ከሌለ በግራ እጁ ወስዶ ይጠጣል፡፡ ማር እንኳን ከቀፎ ውስጥ ሲያወጣ በግራ እጁ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀኝ እጁ ወዩ ነው፡፡ በእጁ ሰው አይመታም፡፡ አይረግምም፡፡ የከፋ ነገር እንኳን ቢገጥመው ቡሉኮውን ያራግፋል፤ ያ እንደ እርግማን ይቆጠራል (ገዳ ጋምቤላ በርሶ፣ 9/6/2008 ዓ.ም. የሆኩ አባገዳ የነበሩት፣ ሚኤ ቦኮ ላይ)፡፡

ከርቤው (qumbii) ቀደም ሲል እንደተገለጸው መራር መንፈሳዊ ቁስ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ በቃሉ ተቋም ከሂሮ ስር ጀምሮ በእንፉቅቅ በመሄድ ከቃሉ እጅ ከርቤ መቀበልን ያየን እንደሆነ

ማህበረሰቡ ቀደም ብሎ ያዋቀረው ዕውቀት ነው። ምክንያቱም ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማህበራዊ ውቅር ነው። ይህን ዕውቀት ወደ ቃሉ ተቋም በማስገባት ለቃሉ፣ ለተቋሙና ለቁሳዊ ባህሉ ክበሬታና ተቀባይነት እንዲኖረው ተደርጓል። ቃሉ በወንበሩ ላይ ተቀምጦ ሳለ ገዳዎቹ እየተንፏቀቁ መሄዳቸው ቃሉን ማክበር እንዳለባቸውና የአክብሮታቸው መገለጫ አድርገው ያዋቀሩት ዕውቀት ውጤት መሆኑን ያሳያል። ይኸውም በሌላ በኩል ቃሉን የእግዚአብሔር መልዕክተኛ አድርገው ስለሚያምኑት፣ ለቃሉ ክበሬታ አሳዩ ማለት በተዘዋዋሪ መንገድ የላከውንም እግዚአብሔርን እንደማክበር ስለሚቆጠር ነው።

በሌላ በኩል ከሚከወንበት አውድ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ ይህ ክበራ የሚከወነው ከተቋማዊ አውድ አኳያ በቃሉ ተቋም ሲሆን፤ ከግለሰባዊ አውድ አኳያ ደግሞ መከወን ያለበት በቃሉ እጅ ብቻ ነው። ነገር ግን በምዕራፍ ሰባት ስር እንዳየነው የቦታና የከዋኝ ለውጥ ተደርጓል።

በሌላ በኩል የከርቤ መራርነት ለእውነት ተምሳሌት ሆኖ ቀርቧል። እውነት መናገር ከራስ ጋር ያጣላል፤ እውነት መናገር ከቤተሰብ ጋር ያጋጫል፤ እውነት መናገር በጎሳ ደረጃም ጥላቻን ሊያመጣ ይችላል። እንዲሁም በእውነት መስራት ከመንግስት ጋርም ሊያጋጭ ይችላል። ስለዚህ እነዚህ ጫናዎች ተቋቁሞ ማህበረሰቡን በእውነት ማስተዳደር ምንኛ እንደሚከብድና መጨረሻው ደግሞ ያማረ መሆኑን ደግሞ በጠጁ ሲያወራርዱት የሚያሳየው ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው። በመጨረሻም ይህን ተምሳሌታዊ ክዋኔ ከፈጸሙ በኋላ ስለተቀደሱ ወዩ (woyyuu) ይሆናሉ።

ሌላው ክዋኔ ቃሉ ለመስዋዕት ከታረደው ከብት በገበቴ የቀረበውን ደም እየነከረ በላያቸው ላይ ግራና ቀኝ እየረጨ፣ ከጠጁ እያቀመሳቸው መመረቁ ነው። እንደ ኦሮሞ የዓለም አተያይ መስዋዕት በሚቀርብበት ወቅት ደሙን ወደ ላይ ሲረጭ ለእግዚአብሔር እንደመስዋዕት ማቅረብ ይቆጠራል፤ በተቃራኒው ደግሞ ደሙ ከተረጨበት ወደታች ሲወርድ እንደእግዚአብሔር ምርቃት ስለሚቆጠር ነው (Hinnant, 1972)። ይህ ተምሳሌታዊ ክዋኔ ከተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ስንመለከተው ተመራቂዎቹ በቃሉ ብቻ ሳይሆን፤ በቃሉ አማካይነት በደሙ በእግዚአብሔርም እንደሚመረቁና ምርቃቱንም ወደውስጣቸው የሚያስርጉት በከርቤውና በጠጁ እያወራረዱ መሆኑን ነው።

የመጨረሻውን መስዋዕት ተከትሎ ቃሉ አባገዳዎችንና ህዝቡን ወደሚመለከታቸው የሃይማኖታዊ ከበራ (jila) ቦታ ወይም ወደ ራሳቸው የገዳ ስርዓት የሚከውኑበት ይሸኛቸዋል፡፡ በሽኝቱም ሲመርቃቸው፡-

| | |
|---|---|
| Gadaa murtii nageessi, | የገዳ ውሳኔን ሰላም ያድርገው፣ |
| ardaa nageessi, | ቀዬውን ሰላም ያድርገው፣ |
| Kolbaa nageessi, | ህዝቡን ሰላም ያድርገው፣ |
| Hulaa nageessi, | ደጃፋችንን ሰላም ያድርገው፣ |
| afaan nu beessisi, | አፍ ለአፋ እንድንጣጣም ያድርገን፣ (እንድንግባባ አድርገን) |
| Ardaa nu teessis, | በቀዬው አኑረን፣ |
| ilmee nuu bulchi, | ልጆችን አኑርልን፣ |
| abbaa nuu bulchi, | አባቶችን አኑርልን፣ |
| intala nuu bulchi, | ሴት ልጆችንም አኑርልን፣ |
| sa'a namaan bulchi, | ሰውን ከከብቱ አኑረው |
| biyya teenya nagaa nuu godhi. | ሀገራችንን ሰላም አድርግልን፡፡ በማለት |

እንደሚባርካቸዋል፤ እንደሚመርቃቸዋል ተገልጿል፡፡ (አቶ ሞኮና ናጋኦና አቶ አባባ ቶቴ በ15/7/2007 ዓ.ም. በወናጎ ወረዳ የቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ የሆኑ)

ከዚያም የፕሮግራሙ መጨረሻ ይሆናል፡፡ ታዳሚዎቹም በመጨረሻ የምስጋናና መልካም ምኞት መግለጫ የሆነውን ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው ይጨፍራሉ፤ ደስታቸውን ይገላጻሉ፡፡ ከዚያ ወደ ሚኤ ቦኮ ይመለሳሉ፡፡ ይህ የጉቱ ጉዞ ከተከናወነ በኋላ የገዳ አባቶቹ የስልጣን ርክክብ ለመፈፀም ወደ ሚኤ ቦኮ በመመለስ ይዘጋጃሉ፡፡ ይህ ከፍተኛው ጉባኤ ሲሆን አባገዳዎቹ ጎሳዎቻቸውን የሚያስተዳድሩበት ህጎች የሚታወጅበት (itti lallabuunu) እና የህዝቡን የተለያዩ ችግሮች የሚፈቱበት ጉባኤ (gumii) ነው፡፡

በመጨረሻም የቀደሙት አባገዳዎች በስልጣን ዘመናቸው አቅደው ያከናወኑትን መልካም ስራዎች በማሳወቅ፤ ጀምረው ከግብ ያላደረሱትን ሂደቶች ቀጣዮቹ ተረካቢዎች እንዲያስፈጽሙ ያሳስቧቸዋል፡፡ አዳዲሶቹ የገዳ አባቶች ደግሞ ስልጣኑን ከተረከቡ በኋላ የመተዳደሪያ ህጋቸው ሊሆን የሚገቡትን እዚያው ይታወጃል፡፡ አዋጁም አጠቃላይነት ባለው መልክ ስለህግ፣ ስለባህል፣ ስለአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲሁም ስለወዩነት ይታወጃል፡፡ አዋጁ የሚነገረው በዩባዎች

አማካይነት እንደሆነ በሚኤ ቦኮ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ከዚያም ዝርዝር ህጎችና ባህል ነክ ጉዳዮችና ወዩን በተመለከተ የሚከናወነው ከሚኤ ቦኮ በመነሳት በየጎሳዎቻቸው ውስጥ በመዝለቅና ወደ የራሳቸው የገዳ ማዕከል በሚጓዙበት ወቅት ይሆናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ስናየው ማህበረሰቡ የገዳን ስርዓት ሲያዋቅሩ ጋሜ →ዳባሌ →ኩሳ →ራባ →ዶሪ →ገዳ → ዩባ... እያለ በዕድሜ እርከን ካስቀመጡ በኂላ፣ በእያንዳንዱ ደረጃ ምን መከወን እንዳለባቸውና የደረጃ ሽግግር በምን ዓይነት ህግና ደንብ እንደሚያከናውኑ ተዋቅሯል፡፡ ከዚያም ይህን ዕውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ አንድም በከበራ መልክ፣ በሚትና በመሳሰሉት ሽግግር ሲያደርጉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ልክ እንደባቱና ዩባዎች ያሉት ደግሞ በልምድ ያዳበሩትን ዕውቀት ማለትም፡- እንደ ጋሜ ያደጉበትን፣ እንደዳባሌ ያለፉበትን፣ እንደኩሳና ራባ ደግሞ የተማሩትን፣ እንዲሁም እንደገዳ ከቃሉ ያገኙትን ዕውቀቶች (የእግዚኣብሔርን ህግጋት)፣ እንዲሁም ማህበረሰቡን ባስተዳደሩበት ወቅት ያጋጠማቸውን ልምድ ጥርቅም ዕውቀት በአዋጅ ነገራ መልክ ለተተኪው ትውልድ ያሸጋግራሉ፡፡ የዕውቀት ተስተላልፎውን የተመለከትን እንደሆነ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እንዲሁም ተመልሶ ወደ ዝርዝር መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም በእያንዳንዱ የእርከን ደረጃዎች ያሉት ዕውቀቶች ከስር ወደ ላይ ተዳምረው፣ በነዚህ ደረጃው ውስጥ ሲያልፉ በልምድ ያካበቷቸውን ጨምሮ ጥቅል የሆነ ስለባህል፣ ስለወዩና ስለህግ ዕውቀቶቹ በይበልጥ ያሉት በባቱዎችና በዩባዎች እጅ ነው፡፡ ስለዚህ ከዩባዎች ተመልሶ ወደታች ላሉት ሁሉ በአዋጅ (lallabaa) መልክ ይተላለፋል፡፡




ምስል፡-8 የጉጂ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች ተስተላልፎ አቅጣጫ የሚያመለክት(ምንጭ፡- በአጥኚው የቀረበ)

### i. የጉጂ ገዳ የስልጣን ሽግግር ዙር

የጉጂ ኦሮሞ ገዳ ስልጣን በአምስት መደቦች ተከፋፍሎ የተደራጀ ነው፡፡ እነሱም፡-ሙዳና (Muudana)፣ ሀልቺሳ (Halchiisa)፣ ዳላና (Dhallana)፣ ሀርሙፋ (Harmuufa) እና ሮባሌ (Roobalee) ይባላሉ፡፡ እነዚህ እያንዳንዱ መደብ በስሩ በሺዎች የሚቆጠሩ አባላቶች ይኖሩታል፡፡ ታዲያ እያንዳንዱ መደብ በየስምንት ዓመቱ በሚደረገው የስልጣን ሽግግር ህዝቡን በዙር ያስተዳድራሉ፡፡ አንድ የገዳ መደብ፤ ለምሳሌ ሙዳና ስልጣን ቢይዙ ለስምንት ዓመታት በማገልገል ስልጣኑን ለሚቀጥለው ማለትም ለሀልቺሳ ያስረክባሉ፡፡ ሙዳና ለቀጣይ ወደ ስልጣን መጥቶ ለማስተዳደር 40 ዓመታትን ይፈጅባቸዋል፡፡ ይህ ማለት ስልጣን ካስረከበ በኋላ ተመልሶ ወደ አምስተኛው ዙር እስኪደርሱ የሚፈጅባቸው ጊዜ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የሚከተለውን ምስል ይመልከቱ፡፡




ምስል፡-9 የጉጂ ገዳ መደብዎች የስልጣን ሽግግር ዑደት የሚያሳይ ምስል (ምንጭ፡ አጥኚው በንባብ ካዳበረው ተሻሽሎ የቀረበ)

በእነዚህ አምስቱ መደቦች ውስጥ የሦስቱም ኮንፈዲረሲ አባላት ተመሳሳይ ስያሜ ባለው አደረጃጀት ተዋቅረው እንዳሉ ለማየት ተችሏል፡፡ ይኸውም፡- በሙዳና መደብ ስር የኡራጋ ሙዳና፣ የማቲ ሙዳና እና የሆኮ ሙዳና መደቦች አሉ፡፡ ስለዚህ የሙዳና መደብ ወደ ስልጣን በሚመጣበት ወቅት የሦስቱም ኮንፈዲረሲ ሙዳናዎች ገዳ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በየስምንት ዓመቱ ለሌሎችም ስልጣኑን ያስተላልፋሉ፡፡

ii. **የገዳ ስልጣን ማስረከብ ሂደቶች**

የገዳዎች ከስምንት ዓመት የስልጣን ቆይታ በኂላ ያለአንዳች ማቅማማት በዴሞክራሲያዊ አካሄድ ስልጣናቸውን ለማስረከብ የሚከተሉትን ቅደም ተከተላዊ ክዋኔዎችን ይፈጽማሉ፡፡ ይኸውም፡-

***ሀ. ሀጋና ማስገባት/መመለስ*** (Haaganaa Galchuu)

እንደ ጉጂ ማህበረሰባዊ ዕውቀት አወቃቀር አንድ ገዳ ወደ ስልጣን ሲመጣ ሁለት ዓይነት ስልጣን እንደሚጎናጸፍ ይነገራል፡፡ ይኸውም፡- አንደኛው ከቀድሞው አባገዳ የሚረከበው ፖለቲካዊና ባህላዊ አስተዳደር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከእግዚኣብሔር የሚረከበው መንፈሳው የማስተዳደር ኃይልና ተሰጥኦ እንዳለ ይታመናል፡፡ ታዲያ አንድ ገዳ የስምንት ዓመቱ የስልጣን ጊዜው ሲያበቃ ከቀድሞው ገዳ ላይ የወሰደውን አስተዳደራዊ ስልጣን ለተተኪው አባገዳ ሲያስረክብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከእግዚኣብሔር የወሰደውን መንፈሳዊ ኃይል ደግሞ ለእግዚኣብሔር ይመልሳል ይባላል፡፡ ይህ ሂደት ደግሞ ሀጋና መመለስ ተብሎ ይጠራል፡፡ አባገዳ የፖለቲካዊ ስልጣኑን ከማስረከቡ በፊት ወደ ገናሌ፡- ካዶ (kaadho) ወይም ሀሮ ሱታሜ (haroo sutamee) የሚባልበት ቅዱስ ስፍራ በመሄድ ሀጋናውን ያስገባል፡፡

ገዳ ሀጋና ለማስገባት ሲሄድ ከገዳ መማክርት አባላት ውስጥ ማካላ፣ፋጋ፣ሀዩና የእሱ አባላቶች እንዲሁም የጉጂን ሰባት ቤት የሚወክሉ በአንድነት በመሆን ነው፡፡ በጉዞው ወቅት ማካላው ጋሻ፣ ጦር፣ እስቴ (ichima)ና ሁለት ረጃጅም የቀርከሃ ልምጮች በመያዝ ነው፡፡ እዚያ ሀጋናው የሚቀመጥበት ኦዳ ዛፍ አጠገብ እንደደረሱ፤ ፋጋው የግራር እንጨት (Muka waaccuu) ስር “ተቀመጡ” (“taa’aa”) በማለት አባታዊ መንፈስ ይላበሳል (abbooma). ከዚያን በኂላ አባገዳው ለዝግጅቱ የሚያገለግል እሳት አስቴውን በመስበቅ ያቀጣጥል፡፡ ከዚያም ኮርማ በማረድ በከለቻው ላይ ደም ይቀባል፡፡ በመቀጠል ፋጋው ግንባሬን አጠንክርልኝ በማለት በከለቻው ላይ ደሙን ይቀባል፡፡ “adda na jabeessi, jadhu’uu na baasi!” በመቀጠል በኂላ እዚያ የታደሙት እንደየቅደም ተከተላቸው ግንባራቸውን ደሙን ይቀባሉ፡፡ በመቀጠል ሞራና አንጀቱን

ከተመለከቱ በኋላ እየመረቁ ሞራውን በአባገዳው አንገት ላይ ያደርጉታል፡፡ ከዚያ ባላ ተቆርጦ፣ ስጋውን ዘልዝሎ (babanii) በመጥበስ በአካባቢው ከሚገኙ ማህበረሰብ ጋር በመሆን ወዲያውኑ በልተው ይጨርሱታል፡፡ ቆዳውን እየተተለተለ (injicha baasanii) ሁሉም ሰው በቅደም ተከተል "Nageyi!, nageyi!, nageyaan gadoomtee nageyaan baatomi!, akka gadaa nageyaa teete baatuu nageyaa te'i!" ማለትም፡- ሰላም ሁን!፣ ሰላም ሁን!፣ በሰላም ገዳ እንደሆንክ፤ በሰላም ባቱ ሁን፤ የሰላም ገዳ እንደሆንክ፤ የሰላም ባቱ ሁን! በማለት እርስ በርስ እየተመራረቁ፣ እየተለማመኑ በየእጃቸው ላይ "ኤንጂቻውን" ያደርጋሉ፡፡

ይህ በሀሮ ሱታሜ ላይ የታረደውን ኮርማ ደም ገዳውና ፋጋው በከለቻቸው ላይ፣ ሌሎችን ደግሞ ግንባራቸው ላይ ደም የመቀባቱ ተምሳሌታዊ ክዋኔ ሀገና ካስገቡ በኋላ እርኩስ መንፈስ እንዳይጠናወታቸውና መልካም የባቱነት ዘመንን ለማሳለፍ ያላቸውን ምኞት መግለጫ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመቀጠል በዚያ ከበራ ላይ የተሳተፉት ሁሉ ጥሩ የገዳ ጊዜ እንዳሳለፍክ፤ ጥሩ ባቱ ያድርግህ በማለት እግዚአብሔርን እየተለማመኑና እርስ በርስ እየተመራረቁ የኮርማውን ቆዳ በመተልተል (injicha) እያወጡ በእጆቻቸው ላይ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ክዋኔ የሚያመለክተው ገዳውና አባላቱ ወደ ቀጣዩ ደረጃ መሸጋገራቸውን ማመላከቻና አምነው ለመቀበላቸውም በመረጃነት የሚያገለግል ተምሳሌት ነው፡፡

ከዚያ ቁጠላ ይጨፍራሉ፤ቁጠላውን የሚያወጣው አባገዳውና ማካላው ሲሆኑ ሌሎቹ ይቀበላሉ፡፡ ቁጠላውም፡-

| | |
|---|---|
| "Ilma abbaan bobbaasee!, | አባት ልጁን አሰማራ! |
| dhageettaa hobbaasee!, | ማዳመጡን አበቃ! |
| Gadabitti qajeelee!, | ወደ ገደብ አቀና! |
| Baatomuu kajeelee!" | ባቱ ለመሆን ከጀለ፡፡ |

ከቁጠላው (ጭፈራው) የምንረዳውም የቀድሞው አባገዳ ስልጣኑን ለማስረከብ እንዳሰበና፣ ወደ ቀጣዩ ደረጃ (ባቱ) ሊሸጋገር መሆኑን ማብሰሩ ነው፡፡ ከዚያም ስልጣኑን በሰላማዊ መንገድ ለማስረከብና ወደቀጣዩ እርከን ለመሸጋገር እንደሚፈልግ ያበስርበታል፡፡

በመቀጠል ከየትም ተብሎ እባብ ተገድሎ ይመጣል፡፡ ከዚያም ሀጋና የማስገባት ከበራውን ለመከወን ከግራሩ ስር ተነስተው በጸጥታ ወደ ኦዳው እንጨት ይሄዳሉ፡፡ ኦዳው አጠገብ እንደደረሱ ማካላው በእጁ በያዘው ልምጭ ኦዳውን ነካ ነካ በማድረግ "kaan ulfaataa mare massee, kaan gabalaa kiyyaa mare massee." ማለትም «የተከበረውን ጠቅልዬ

አስቀመጥኩ፣ የእኔን ድንበር ጠቅልዬ አስቀመጥኩ፡፡» በማለት በእጁ የያዘውን (የተቃጠለውን እባብ አመዱ ጠቅልሎ) አስቀምጦ ወደ ሚኤ ቦኮ መልስ ይሆናል፡፡ በዚህ መልኩ አንድ የስልጣን ዘመኑን የጨረሰ ገዳ ቀድሞ በፋጋው አማካይነት ያን መንፈሳው ስልጣን (ሀጋና) የማስገባት ከበራ ይፈጽማል፡፡

በሌላ በኩል ወደ ስልጣን የመጣው ገዳ ደግሞ እዚያው ቦታ በመሄድ ሀጋና ይወስዳል፡፡ ይኸውም፡- ሀሮ ሱታሜ በመሄድ እባብ በመግደል ያቃጥልና አመዱን በማሸት ከለቻው ላይ ይቀባል፡፡ እንደገናም ያን መርዛማ አመድ ሀዳ (hadhaa) የሚባለውን በጣታቸው ነክተው ምላሳቸውን ያስነኩታል፡፡ ምክንያቱም አዲሱን ገዳ መንፈሳዊ ኃይል በማላበስ እሱ የመረቀውም ሆነ የረገመው ከመሬት ጠብ አይልም ይባላል፡፡ ስለዚህ የገዳን ህግ የጣሰን ቢራገም ያደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

እባቡ የአደገኛነት ተምሳሌት ነው፡፡ እባብ መርዙን ይዞ የምንቀሳቀሰው በአፉ ውስጥ ነው፡፡ በተለይም ውሃ ሊጠጣ ሲል ድንጋይ ላይ አስቀምጦ ነው፡፡ የጉጂ ኦሮሞ እባብ ቅንና ንጹህ ልብ ያለውን አይተናኮልም ብለው ያምናሉ፡፡ ለዚህም እንደማስረጃ የሚያቀርቡት እባብ ሕጻናትን አይተናኮልም፡፡ ሕጻናት በእጃቸው ይዘውት ወደ አፋቸው ሲወስዱት እንኳን ለሃጫቸውን ይልሳል እንጂ አይነድፋቸውም፡፡ ነገር ግን አዋቂዎች ሲያገኙት ሊገድሉትና ሊያጠፉት ስለሚያስቡ ይነድፋቸዋል ይላሉ፡፡ ስለዚህ ገዳም ለሰላማዊ ሰው ሰላማዊ ተግባራትን የሚከውን ሲሆን፣ ለጠላቶቹ ደግሞ ኃይለኛ እንደሆነ በተምሳሌታዊ ክዋኔ ይገልጻሉ፡፡ የአበው አባባልም «እንደ እባብ ብልህ፣ እንደ እርግብ የዋህ ሁን፡፡» አይደል፡፡

**ለ. የገዳ ስልጣን ርክክብ** (Baallii kennuufi fuudhuu)

የሦስቱም ጎሳዎች በዶሪ እርከን ላይ የሚገኙት በሚኤ ቦኮ በተዘጋጀላቸው ቦታ ሰፍረው የርክክቡ ዕለት እስክደርስ በአዋጅ ነገራው ላይ ከገዳዎች ቡድን ቀጥለው በመቀመጥ ለወደፊት መተዳደሪያቸውና ማስተዳደሪያ የሚሆናቸውን ዩባዎቹ የሚያስተላልፉትና አጠቃላይነት ይዘት ያለውን ህግጋትና ደንቦችን (seera gooroo) ያዳምጣሉ፤ አካሄዱን ይማሩበታል፡፡ በመጨረሻም በነጋታው ስልጣን በሚረከቡበት ዕለት መንገዱ እንዳያስቸግራቸው ማታውን አባገዳዎቹ ወደሰፈሩበት ቦታ መሄጃውን መንገድ ይመነጥራሉ፡፡ በምሽት የሚመነጥሩበት ምክንያት የገዳዎቹ ጠባቂዎች (Jadhaaboota) የገዳ ማረፊያ ስፍራ ቅዱስ (woyyuu) ስለሆነ መመንጠር የለበትም በማለት ስለሚጠብቁና ስለሚጋረፉ ነው፡፡ እነዚህ ያሁኖቹ ዶሪ በነጋታው ስልጣኑን

ከተረከቡ በኋላ ፈረስ ላይ ወጥተው የሚፎክሩበትና የሚሸልሉበት መንገድ አመቻችተው ያድራሉ።




ፎቶ፡-13 እና 14 **ስልጣን ተረካቢ ገዳዎችና የመደቡ አባላት ለርክክብ ሲሄዱ የሚያሳዩ ፎቶዎች**

በማግስቱ የሦስቱም ጎሳዎች የዶሪ እርከን አባላት ሁሉም ወደ ገዳዎቹ ማረፊያ (qachaa) ታጅበው ይሄዳሉ። እንደተቃረቡም ሦስቱ ዕጩዎች (አባሙርቲዎች) እና የጉጂ ኦሮሞ ሰባት ቤት ተወካዮች የሆኑት አማካሪዎች ጋር በመሆን ወደ ገዳዎቹ ማረፊያ ሲዘልቁ፤ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ታዳሚዎች ወደ ማረፊያው ቀረብ ብለው መንገድ ላይ ይጠባበቃሉ። አባሙርቲዎቹ ወደ ገዳዎቹ ማረፊያ ሲዘልቁ በባዶ እግራቸው ነው። ከዚያም ከደጃፉ እንደደረሱ ገዳዎቹን በነጠላ ስማቸው ይጠራሉ።

ለአብነት ያህል የኡራጋውን አባገዳ እንደ ንጥል-ጥናት ብንመለከት፡- መጀመሪያ ከደጃፍ ቆሞ አባገዳውን ይጠራዋል። ይኸውም፡-

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** የኡራጋ አባገዳ የነበሩትን ገዳ ዋቆ ዱቤን በነጠላ ስማቸው ሦስቴ ‹‹ዋቆ! ዋቆ! ዋቆ!›› ብሎ ሲጠራው ምላሽ አይሰጠውም፤ በአራተኛው ‹‹ዋቆ!›› ሲለው፤

**ገዳ ዋቆ፡-** ‹‹አቤት! (yaa!)›› ይለዋል።

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** በመቀጠል ‹‹ገዳው ያንተ ነው፤ የኔ?›› (“gadaan tiyya moo, teeti?”) በማለት ገዳ ዋቆን ይጠይቃል።

**ገዳ ዋቆ፡-** «gadaan teeti, gaarri tiyya» ማለትም፡- «ገዳው ያንተ ነው፡፡ ጋሪ (ዕድሉ) ግን የኔ ነው፡፡» በማለት ይመልሳሉ፡፡

ከዚያን በኋላ ፋጋው ወደ ገዳው ማረፊያ ቀድሞ ዘልቆ ይገባል፡፡ በተሰጠው መቀመጫ ከገዳው በስተግራ በኩል ይቀመጣል፡፡ ከዚያ በመቀጠል ለሌቹም ወደ ውስጥ ይዘልቁና ይቀመጣሉ፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-** ባለቤታቸውን (haadha bollaa) «ወተት አምጭ» በማለት ትኩስ ወተት ተቀብለዋት፣ ለአባሙርቲ ጂሎ ማንዶ « እንካ የኔን ገዳ ትኩስ ወተት» («hoo'o Mi'ii gadaa tiyyaa!») ሲሉ፣

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-**«በኔ ገዳ ጣፍጥ» («gadaa tiyya mi'aayi!») በማለት ተቀብሎ ይቀምስና አብረውት ለመጡት ያቀብላል፡፡ እነሱም ይቀምሳሉ፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-**አሁንም እርጎ ወተት ከባለቤታቸውን ተቀብሎ «እንካ የኔን ገዳ እርጎ» («hoo'o Itittuu gadaa tiyyaa!») ሲሉ፣

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** «በኔም ገዳ ከሰዎችና ከብቶችህ ጭምር ሰላም ይስፈንልህ» («gadaa tiyyallee namaa, sa'aan ititi!») በማለት ተቀብሎ ይቀምሳል፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-** አሬራ ተቀብሎ «እንካ የኔን ገዳ አሬራ» («hoo'o Areera gadaa tiyyaa!») ሲሉ፣

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** «በኔም ገዳ ኮረማው ይባረክልህ» («gadaa tiyyallee Kormi sii areeru!») በማለት ተቀብሎ ይቀምሳል፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-** ጠጅ ተቀብሎ «እንካ የኔን ገዳ አበባ» («hoo'o Daraaraa gadaa tiyyaa!») ሲሉ፣

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** «በኔም ገዳ በሰውና በከብትህ አብብ» («gadaa tiyyallee namaa, sa'aan daraari!») በማለት ተቀብሎ ይቀምሳል፡፡ ከዚያም ለሌሎቹም በማስተላለፍ እንዲህ እያሉ ይመራረቃሉ፡፡

ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አንጻር አባሙርቲው (አዲስ ገዳ የሚሆነው ሰው) ቀድሞውኑ አባገዳን በነጠላ ስም መጥራቱ የራሱ ማህበራዊ ፋይዳ አለው፡፡ በመሰረቱ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ አንድ በገዳነት የመራን ሰው ይቅርና አንድን ተራ አባወራ በነጠላ ስም የመጥራቱ ልምዱ የለም፡፡ ሁለተኛ በሚኤ ቦኮ መንፈሳዊ አረዳ ውስጥም እንዲህ ዓይነት ንቀት መሰል ሲህተትም ሊፈጸም እንደማይቻል ሁሉም ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ይህን የስልጣን ርክክብ ከበራ ስርዓት ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አኳያ በምናይበት ወቅት ማህበረሰቡ ስልጣን ሲሰጠው ገዳ በመሆኑ ከሌላው የገዳ መደብ እርከን መሪ መሆኑን የሚያሳይ፣ ማህበረሰቡ

ደግሞ ስልጣኑን እንዲያስረክብ በሚያደርግበት ወቅት ደግሞ እንደማንኛውም ዩባ እንደሚሆን አመላካች ክዋኔዎችን በመፍጠር፤ ያንኑ ክዋኔ በመከወን ስልጣኑን የሚያስረክበውም ሆነ የሚረከበውን ማንነት ይለዩበታል፡፡

በሌላ በኩል ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ስንመለከተው በዚያ አወድ ላይ የቀድሞውን አባገዳ በነጠላ ስሙን ሲጠራው ከዚያን ቀን ጀምሩ የቀድሞውና አዲሱ ገዳ ማህበራዊ መሰረታቸው የት እንደሆ አመላካች ነው፡፡

ከተምሳሌታዊ አተረጓገም አተያይ በክዋኔው ውስጥ የቀረበው ትኩስ ወተት ገዳው በንቃት የሚሰራበት ወቅት፤ ትኩስ ኃይል እንደሆነ ሲያመላክት፣ እርጎ ደግሞ ሰከን ብሎ ማህበረሰቡን የሚመክርበትና የሚያስተምርበት ጊዜ ተምሳሌት ነው፡፡ ሌላው አሬራውን የተመለከትን እንደሆነ መጀመሪያ እርጎ ነበር፤ ተንጦ አሬራና ቅቤ ወጣው፡፡ አሬራው የመጨረሻ ውጤት ይመስላል፡፡ ነገር ግን አይብ፣ አጓት አሁንም በውስጡ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ያ እርጎው ጊዜው ደርሶ በሚናጥበት ወቅት ቅቤና አሬራው ተለይቶ እንደሚወጣው ሁሉ አዲሱ ገዳም በቅቤው ይመሰላል፡፡ ምክንያቱም አዲሱ ገዳ ከስረኛው የገዳ ደረጃ እርከን አንስቶ እየሰለጠነ፣ እየበሰለ የመጣው በቀድሞው ገዳ ውስጥ ነው፡፡ ቅቤውም ቀድሞ በትኩሱ ወተት ውስጥ ነበር፤ በኋላም በእርጎው ውስጥ ነበር፤ በመጨረሻ ተንጦ ከዚያው ወተት ውስጥ መውጣቱ ሂደቱም ተምሳሌታዊ ያደርገዋል፡፡

ከዚያም የቀድሞው ገዳ የመሪነት አገልግሎት በስተመጨረሻ ማብቃቱንና የገዳነት ሚና እንደሌለው በአሬራው ይመሰላል፡፡ ነገር ግን በገዳነት ማገልገል ባይችልም፤ አዲስ ስልጣኑን የተረከበው ገዳ የእሱ ውጤት መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ለዚህም ተምሳሌት ጠጁን ከተመለከትን፦ ጠጅ የሚጣለው ከማር ነው፤ ማሩ ደግሞ የአበባ ውጤት ስለሆነ ተምሳሌነቱ በገዳነቱ ወቅት እሱ የመረቀው፣ በእሱ ስር የተማረውና የተደራጀው ቡድን እንደሚያብብና ፍሬ እንደሚያፈራ አመላካች መሆኑን ያሳያል፡፡

በመጨረሻ ያን የተሰጣቸውን ወተትና ጠጅ ከጠጡ በኋላ ፋጋው ቀስ ብሎ ከአባገዳው እራስ ላይ ከግራ በኩል ያለውን የሰጎን ላባ (baarguda ykn baallee guchii) በመንቀል በአዲሱ አባገዳ እራስ ላይ ይሸጠዋል፡፡ የሰጎን ላባው ልክ እንደዘውድ ከቀድሞው አባገዳ በማንሳት በአዲሱ መደረጉ የስልጣን ሽግግሩን አመላካች ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው፡፡ ከዚያች ክዋኔያዊ ቅጽበት በኋላ ሙሉ አባገዳ ይሆናል፡፡ ከዚያም አባገዳ ጂሎ ማንደ ስልጣን ከተረከቡ በኋላ ወደ

ውጭ በመውጣት በተዘጋጀላቸው ፈረስ በመውጣት (odolcha koranii) ገዳ! ገዳ! ገዳ! እያሉ እያቅራሩና እየሸለሉ ሲሄዱ ታዳሚዎቹም ተቀብለው እየተከተሉት ገዳ! ገዳ! ገዳ! እያሉ እውቅና ይሰጣሉ፡፡ ከዚያም ከሚጠባበቋቸው የቡድኑ አባላት ጋር በመቀላቀል፤ ቡድኑም ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ገዳ! ገዳ! ገዳ! እያሉ ወደ ማረፊያቸው አረዳ ይመለሳሉ፡፡ ከዚያም ቀጣዩን ስምንት አመት የኡራጋን ጎሳ የሚያስተዳድረው ይህ ገዳ ይሆናል፡፡

ይህ የገዳ አስተዳደር ስርዓት መማክርት አባላት የሚመረጡት ቀደም ብሎ በኦዳ ስር አዳር ከበራ (jila Odaa buliinsa/ gaafa yaa'l Odaa bulu) በአዋቂዎች ጉባኤ ይወከላሉ፡፡ እነሱም፦ አባገዳ (abbaa Gadaa)፣ ጃልኬያ (Jalkeya)፣ ፋጋ (Faga)፣ ሀዩ (Hayyuu)፣ ጃልዳባ (Jaldhaaba)፣ ዋሙራ (Waamura) እና ቶርቢ (Torbii) ይባላሉ፡፡ እነዚህ የመማክርት አባላት እያንዳንዳቸው በገዳ የአስተዳደር ስርዓትና የስልጣን ሽግግር ወቅት በሚካሄዱት ከበራዎች ላይ የየራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ ምርጫቸው የሚከናወነው በኩሳ ደረጃ እያሉ ለስልጠና በገቡበት (fooqa seenane) ወቅት ነው፡፡ የዚህ ዝርዝር ሀሳብ በ5.1.3.2. ስር ተካቷል፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ በዚህ ምዕራፍ ስር የምናየው ገዳን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡

i. አባገዳ (abbaa Gadaa)

አባገዳ የገዳ አስተዳደራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርዓቱን በበላይነት የሚመራ ሰው ነው፡፡ አመራረጡም አጠቃላይ ጉባኤው ኦዳ ስር በሚያድሩበት ዕለት ለሊት በአዋቂዎች ጉባኤ ከታጬ በኋላ ለጉባኤው እንደሚያሳውቁ ቀደም ብለን አይተናል፡፡ ለጉባኤው ዕጬዎቹን ሲያስተዋውቁ የቀድሞው አባገዳው ውይይቱን ወይም ጉባኤውን ከሚመራበት ትቶ ጉባኤው መካከል ይቀመጣል፡፡ ጉባኤውን የሚመራው ታላቅዬው ፋጋ ይሆናል፡፡ ዕጬዎቹን ለጉባኤው በሚያስተዋውቁበት ወቅት የመለመሉበትን መስፈርቶች፣ የዝምድናና የዘር ሀረጉ ሁሉ ይገልጻሉ፡፡

ይህን ስልጣን ስገለጽና ቃለ-መሃላ የሚፈጽሙት (ከርቤ የሚሰጡት) እንደየቀደም ተከተላቸው ይሆናል፡፡ ከርቤ በመስጠት ቃለ-መሃላ የሚያስፈጽመውም ፋጋ እንደሆነ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

አባሙርቲ ወይም ገዳ በጉባኤው ከማጽደቃቸው በፊት ጃልዳባዎች ቁጣሌ እያሉ አጅበው ከጉባኤው ፊት በማስቀመጥ ከርቤ ያበሉትና ካለቻ ያስሩበታል (haagana itti gambisan/

kallacha itti hidhan)። ከዚያን በኋላ የዶሪ አባሙርቲ ወይም አባገዳ በመሆን ህዝቡን ያስተዳድራል ወይም የገዳውን መደብ ይመራል።

ከከርቤው የማይቀምሰው ፋጋው ብቻ ነው። ምክንያቱም እሱ በመጀመሪያውኑ ከእግዚኣብሔር የተሰጠው ፀጋ አለው (hadhaa qaba/woyyuu)፤ ስለዚህ ዳግም እንዴት ይሰጠዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ለሌሎችን ፋጋው ከርቤ ስያበላቸው፡-

| | |
|---|---|
| Dhugaa afaan sikaaye! | እውነትን በአፍህ ውስጥ አስቀመጥኩ! |
| Dhara afaanii sifuudhe! | ሀሰትን ከአፍህ ውስጥ አውጣሁ! |
| Daba hin qorini! | በደባ አታጣራ! |
| Qorii mooqaan hin qoriin! | ገቡቴ በሞቃ(ማንኪያ መሰል) አትቧጥ! |
| Buna bulluqaan hin qoriin! | ቡና በሙቅ (የማይመስል ነገር) አታጣራ! |
| Haqa hariyaan hin qoriin! | በቀረቤታና በጓደኝነት አታጣራ! |
| Fira worraan hin qoriin! | በዘመድ አዝማድ አታጣራ! |
| Dhugaa waaqaa lafaa qori! | የምድር የሰማይ እውነትን አጣራ! |
| Yoo daba qorte afaan dabi! | አጣመህ ከሰራህ አፊህ ይጣመም! |

በማለት ቁንቢውን ካበላው በኋላ ለህዝብ አገልግሎት ዝግጁ ይሆናሉ ማለት ነው።

ይህ አካሄድ ቀደም ሲል ከቃሉ ገልማ የጉቱ ጉዞ በማድረግ፣ ስጦታዎችን በመስጠት ቁንቢ ይወሰዱ የነበረውን በተለያዩ ምክንያቶች ለተወሰኑ ጊዜያት በማቋረጥ በሌላ ከበራ ተክተውታል። ምክንያቶቹም በምዕራፍ ሰባት ስር በዝርዝር ቀርበዋል።

ነገር ግን ፋጋው ቀደም ሲል በአባቃሉ ሳቆ አዶዮ (8ኛው አባቃሉ) ጋ በመሄድ መቶ ከብት በስጦታ መልክ በመስጠት ስልጣኑን አጸድቆ የወሰደውን ቁንቢ ይዞ በመምጣትና ሌሎችን በማብላት ስርዓቱን እያስፈጸመ እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ያስረዳሉ። ይህ ሂደት ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ያየን እንደሆነ በተለያየ ምክንያቶች በቃሉ ገልማ የተቋረጠውን የገዳ ስልጣን ማጽደቅ ከበራ አሁን ካለው ሁነቶች (situation) ጋር በማጣጣም ያዋቀሩት ዕውቀት መሆኑን ያሳያል።

ለዚህ ማረጋገጫ ሊሆነን የሚችለው በሚኤ ቦኮ ጉባኤ ላይ በ8/6/2008 ዓ.ም. ከተነገረው አዋጅ አንዱ ስለቃሉ ነበር። የአዋጅ ነገራው አካሄድ አፋዊ ሲሆን የራሱ የሆነ የአነጋገር ስርዓቶች አሉት። ይኸውም፡- በመጀመሪያ ደረጃ የሚኤ ቦኮን ጉባኤ የኡራጋው አባገዳ በምርቃት

ይከፍቱና እንዲቀጥሉ ፍቃድ ይሰጣሉ። ይኸውም፡-የኡራጋው ገዳ ከኡራጋ ዩባዎች አንዱን በስሙ ጠርተው «Ani asiin dura gumii teessisee hin beekuu kunoo gumii hardha teessisee seera jiru, aadaafi woyyuu naa lallabi.» ማለትም፡- «እኔ ከዚህ በፊት ጉባኤ አስቀምጬ አላውቅም፤ይሄው ዛሬ አስቀመጥኩ ያለውን ህግ፣ ባህልና ወዩ ለእኔ አውጅልኝ።» በማለት ይጋብዙታል። በባህሉ መሰረት ይህንኑ ሀሳብ መልሶ ለሌሎች ዩባዎች ያቀርብና እንዲህ ተባለ ምን እናድርግ ተባብለው፤ ያው ስለጉጂ ህግና ደንብ፣ ስለባህሉና ስለወዩ ማንኛውም ህብረተሰብ እንዲያውቀውና እንዲያከብረው፤ እንዲሁም እንዲያስከብረው አዋጅ ነገራው ይቀጥላል። አዋጅ ነገራውን የሚያካሂዱ ዩባዎች ናቸው። በመቀጠል ለመናገር የፈለገ ሰው በስርዓቱ መሰረት ቆጲሴ (qophise)፣ ተናግሮ ሲጨርስ ደግሞ ቶጊሴ (toggise) ይላሉ። እንዲሁም ቀድሞ የተናገረውን ሰው የሀሳብ ስህተት ካለበት ምክንያታዊ የሆነ ማስተካከያ ለመናገር ደግሞ ቆጢሴ (qoxxise) በማለት ዕድሉ እንዲሰጠው በመጠየቅ አዋጅ ነገራውን ያካሂዳሉ። አዋጅ ነገራው በአንድ ቀን የሚያልቅ አይደለም። ቀደም ሲል ከ28 ቀናት እስከ አንድ ወር ይፈጅ የነበረውን አሁን ደግሞ ከተለያዩ ችግሮች ማለት፡- በከበራው ላይ የሚሳተፉ እድምተኞች ቁጥራቸው መብዛት፣ ከዚህ በተጨማሪ ለወር ያህል የሚቆይ ከሆነ፣ ለተለያዩ ከበራዎች እርድ ስለሚያስፈልግና ለእነዚህ የሚሆን ወጭዎችም በመብዛቱና የመሳሰሉት ችግሮች የተነሳ ለሳምንት የሚካሄድ መሆኑን ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። ስለዚህ የዕለቱን አዋጅ ነገራ ሲያበቁ አሁንም የኡራጋው አባገዳ ለጃልዳባ ጉባኤውን እንዲበትን በስነቃል እንደሚከተለው በማለት ያዛሉ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| hojjataan hujii yaadee, | ሰራተኛው ስራውን አሰታወሰ፣ |
| hafuuraan qorii yaadee, | ውስጣችንም ምግብ አሰታወሰ፣ |
| hinaafaan niitii yaadee, | ቀናተኛውም ሚስቱን አስታወሰ፣ |
| araadaan tamboo yaadee. | ሱሰኛውም ትንባሆውን አስታወሰ፣ |
| Jadhaaba gumii kaasi. | ስለዚህ ጃልዳባ ጉባኤውን በትን። በማለት |

ትዕዛዝ ይተላለፋል።

ከዚያም ከኡራጋ አባገዳ ትዕዛዙን የተቀበለው የኡራጋ ጃልዳባ ቀበል አድርጎ፡-

| | |
|---|---|
| hojjataan hujii yaadee, | ሰራተኛው ስራውን አሰታወሰ፣ |
| hafuuraan qorii yaadee, | ውስጣችንም ምግብ አሰታወሰ፣ |
| hinaafaan niitii yaadee, | ቀናተኛውም ሚስቱን አስታወሰ፣ |
| araadaan tamboo yaadee. | ሱሰኛውም ትንባሆውን አስታወሰ፣ |

gumiin galti geette. ጉባኤው መግቢያው ጊዜ ደርሰ። በማለት ያስተጋባል።

በመቀጠል አባገዳው የጉባኤውን መቀመጫ ስፍራ አጥረው የሚጠብቁትን የዶሪ ጃልዳባ «Jadhaaba karra bani!» ማለትም ያጠርከውን ክፈትና አሳልፍ እንደማለት ትዕዛዝ ይሰጣሉ። ከዚያም በመጡበት መልክ ተመልሰው ወደ ማረፊያቸው ይሄዳሉ።

ከአዋጅ ነገራው ውስጥ በ8/6/2008 ዓ.ም. የጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ መቅረቱ አግባብ አለመሆኑንና ከአሁን በኋላ መከናወን እንዳለበት እንደሚከተለው ሲነገር ለማዳመጥ ችያለሁ።ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Gujiin qaalluu qaba aadaa, | ጉጂ ቃሉ አለው ባህል ነው! |
| Qaalluun Obituu abbaayyaa jira aadaa, | የኦቢቱ ቃሉ አባያ አለ ባህል ነው! |
| Yaa'aan dhaquun aadaa, | በቡድን ይኬዳል ባህል ነው! |
| Jabbii guttuu fo'anee qaalluu lolan aadaa, | የጉቱ ጥጃዎች ተይዞ በመሄድ መጣላት ባህል ነው! |
| Jabbiin sun karaan hafuun aadimalee, | እነዚያ ጥጃዎች መቅረታቸው የእኛ ባህል አይደለም! |
| Gadaan seera ittiin kennane karaatti hinkutu aadimalee, | ገዳ የሰጡትን ደንብ ከመንገድ አያስቀርም የእኛ ባህል አይደለም! |
| Karaan gaha aadaa,... | ከቦታው ድረሱ ባህል ነው.... በማለት |

መታወጁ ያለፈው ስህተት ነው፤ ከአሁን በኋላ ሂደቱ መሰረቱን ሳይለቅ እንዲከናወን ማሳሰባቸው ነው፤ ማሳሰብም ብቻ ሳይሆን ይህ የታወጁት አዋጆች በተቻለ መጠን መፈጸም ስላለባቸው ለቀጣይ እንደሚከወን ከገዳዎቹ አንደበትም ለማረጋገጥ ችያለሁ።

በሌላ በኩል ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርግ አካሄድ የሚመስል የገዳ አባቶች ሸማግሌዎችን በመምረጥ ወደቃሉ ተቋም እንደተላኩና የባለፈውን በይቅርታ ታልፎ፤ ለቀጣዮቹ በስርዓቱ ለመመለስ ቅድመ ውይይት እንዳደረጉ በአባቃሉ አጋ ሳቆ ገልጻ ተገኝቼ ለማረጋገጥ ችያለሁ።

## 6.2. የጎንዶሮ ከበራ

ጎንዶሮ ማለት ይህ ክስተት ዳግም እንዳይመለስ ወይም እንዳይከሰትብህ/ሽ እንደ ማለት ነው፡፡ የጎንዶሮ ከበራ ከሚከወንባቸው ጉዳዮች አንዱና ዋንኛው ምክንያት ለተለያዩ ግጭቶች ዘላቂ መፍትኤ ስለሚያስገኝ ነው፡፡ ግጭቶች በባህሪያቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ ጠቅለል አድርገን ስናያቸው ሰው ሰራሽም ሆነ፣ ተፈጥሯዊ ችግሮች ከሚያደርሱት ጉዳት አንጻር ግጭቶችን ቀላልና ከባድ በማለት ልንከፍላቸው እንችላለን፡፡ ይኸውም፡-

### i. ቀላል ግጭቶች

ቀላል ግጭቶች የሚባሉት የባልና የሚስት ፀብ፣ የጓደኛሞች ግጭቶች፣ የቤተሰብ ግጭቶች፣ የጎረቤታሞች ግጭቶች ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ግጭቶች በተበዳዩ ላይ ቀለል ያሉ ጉዳቶች ያደረሱ ከሆነ፣ የሚፈቱት በቤተሰብ ደረጃ አለያም በአካባቢው ሽማግሌዎች ደረጃ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ መልክ የተነሱ ግጭቶች አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ሳይፈቱ ቀርተው ወደ ከባድ ግጭቶች የሚያመሩበትና ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱበት ሁኔታዎች ሊከሰት ይችላሉ፡፡

### ii. ከባድ ግጭቶች

ከባድ ግጭት ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው ከባድ ለሆነ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና አኮኖሚያዊ ቀውስ ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ነው፡፡ በዚህ የግጭቶች ዓይነት ስር ምናልባት በገዳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ካሉ፣ በግለሰቦች መካከል በተፈጠረ ግጭት መንስኤ የነብስ መጥፋት ካጋጠመ፣ የጎሳ ለጎሳ ግጭቶችና የብሄር ግጭቶች ሳቢያ የነብስ መጥፋት ከተከሰቱና የመሳሰሉት በዚህ ስር ይመደባሉ፡፡

እነዚህ ግጭቶች በበዳዩ ወገንም ሆነ በተበዳይ ወገን የሚያደርሱት ጉዳት በጣም የከፋ ስለሚሆን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በመፈጸም እርቀ ሰላም ማውረድ ግድ ይላቸዋል፡፡ እርቀ ሰላም ወርዶ ወደ ቀድሞ የሰላማዊ አኗኗር ዘይቤ ውስጥ ካልገቡ በቂም በቀል ወደ ከፋ ደም መፋሰስ ያመራሉ፡፡ በመጨረሻም በሁለቱም ወገን አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ግንኙነታቸው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ስለዚህ ማህበረሰቡ ከእንደነዚህ ዓይነት ችግሮች ለመውጣት ካዋቀረው ማህበረሰባዊ ዕውቀት ውስጥ አንዱና ዋንኛው የጎንዶሮ ከበራ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ለሁሉም የግጭት ዓይነቶች የጎንዶሮ ከበራ ይከወናል ማለት አይደለም፡፡ ሌላው እያንዳንዱ የግጭት ዓይነቶች እንደየደረጃቸው የሚፈቱበት የራሳቸው የሆነ ሂደቶች አሏቸው፡፡

### 6.2.1. የግጭት አፈታት ሂደቶች

አንድ ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ያን ችግር ለመፍታት በተሰየመው አካል የሚከናወኑ ሂደቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- የግጭቱን ምክንያት ማወቅ፣ የግጭቱን ምክንያት ማዳመጥ፣ መረጃዎቹን ማረጋገጥ፣ ውሳኔ መስጠት፣ የማስማማት ከበራና በመጨረሻም ውሳኔውን ማስከበር ናቸው፡፡ እነዚህን ሂደቶች ምን እንደሚመስሉ ባጭሩ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

#### i. የግጭቱን ምክንያት ማወቅ

ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት በቅድሚያ በምን ምክንያት እንደተጋጩ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፡- በግጦሽ መሬት (የጉጂና የቦረና)፣ በድንበር ይገባኛል ጥያቄ (የጉጂና የጌደኦ፣ የጉጂና የኮይራ)፣ ውል ወይም እምነት ማፍረስ (በእምነት የተሰጠን ነገር መካድ፣ ቃል ገብቶ ቃል ማፍረስ....)፣ ድንገተኛ ክስተቶች (በስካር፣ አውሬ መስሎት በስህተት ሰውን መግደልና የመሳሰሉት) እንዲሁም የመልሶ ማጥቃት ሂደቶች (አንድ ቡድን ከብቶቻቸውን ቢዘረፉ፤ እነሱም በተመሳሳይ ሁኔታ ለማስመለስ ሲጥሩ የሚፈጠሩ ግጭቶች....) እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በየትኛው ምክንያት ግጭቱ እንደተቀሰቀሰ ማወቅ ወይም መለየት የግጭት አፈታቱ የመጀመሪያ ሂደት ነው፡፡

#### ii. የግጭቱን ምክንያት ማዳመጥ

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ግጭቱን ለመፍታት የተሰየሙት አካላት፤ በዚህ የሂደት ደረጃ በመጀመሪያ እግዚኣብሔር እርቁን በሰላም እንዲያስፈጽምላቸው ይለማመናሉ፡፡ በመቀጠል አካሄዱን የሚመሩ ሁለት ግለሰቦች በባህሉ፣ በሃይማኖቱና በጎሳ ደረጃ ካላቸው ቦታ ታይተው ይመረጡና ይሰየማሉ፡፡ ከዚያ ከተበደልኩ ባዩ የግጭቱን ምክንያት እንዲያስረዳ ይጠየቃል፡፡ በዚህ መሰረት የግጭቱን ምክንያት ከስረ መሰረቱ ያዳምጣሉ፡፡

#### iii. የግጭቱን ምክንያት መረጃዎች ማረጋገጥ

በዋቄፋና እምነት መዋሸት በራሱ ጨቡ ነው፤ እውነት የእግዚኣብሔር ልጅ ናት ("dhugaan ilmoo waaqati.") ይላሉ፡፡ ስለዚህ በተቻለ መጠን እራሳቸው እውነቱን እንዲያወጡ ወይም እንዲያረጋግጡ ለሁለተኛ ጊዜ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህም ካልተሳካ ደግሞ በሰው፣ በሰነድ ማስረጃ እንዲያረጋግጡ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ሌላው አማራጭ ወኪሎቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው ስለግጭቱ ምክንያት የሚያውቁት ነገር ካለ እንድገልጹ ይጠየቃሉ፡፡ በእነዚህ

ሁሉ ምላሽ ከጠፋ፤ ሽማግሌዎቹ በሁለቱም ወገን ከአነጋገራቸው ውስጥ ከታዘቡት ጉዳይ ተነስተው በተረትና በምሳሌያዊ ንግግሮች ወደ እውነቱ መንገድ እንዲመጡ ምክር አዘል ንግግር ጣል ያደርጋሉ። በእንደዚህ ዓይነት ሂደት መሰረት ተደርጎ ከተረጋገጠ በኋላ ወደ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ይገባል።

iv. ውሳኔ መስጠት

ይህ የውሳኔ መስጠት ሂደት የተበዳይን በደል የሚያካክስ፣ አንዳንዴም ደግሞ የበዳይን አቅምና ለይቅርታው ምን ያህል እንደተፀፀተ ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ተበዳይን በመለመን የማግባባት ስራ የሚሰራበት ሁኔታም እንዳለ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ።

v. የማስማማት ከበራ

ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዳዩ የተወሰነበትን ነገር እንድፈጽም ይደረግና ሁለቱንም ግለሰቦች ወይም ቡድኖች አቀራርቦ እንዲጨባበጡ፣ ዳኤ እንዲባባሉ ይደረጋል። በዚህ ጊዜ እንደስልጣንና ዕድሜ ደረጃ ጎንበስ ብሎ ይቅርታ መጠየቅም የሚካሄድበት የሂደት ደረጃ ነው።

vi. ውሳኔውን ማስከበር

የጉጂ ኦሮሞ በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠሩ ግጭቶችን በእርቅ ከፈቱ በኋላ ያ ችግር ዳግም እንዳይመለስ በመጀመሪያ ደረጃ የታረቁትን አካላት እየመረቁ፤ በምርቃቱ ውስጥ ዳግም በዚያ ድርጊት እንዳይመለሱ በማውገዝ ውሳኔው እንዲፀና ይደረጋል። ሌላው በቃሉና ገዳ ተቋማት በኩል ከሆነ የጎንዶሮ ከበራና ቦኩ (boku) ማለትም ማዕቀብ በመጣል ውስኔዎችን ማስከበር እንደሚቻል ይገልጻሉ።

### 6.2.2. የጎንዶሮ ዓይነቶች

በዋናነት ሁለት የጎንዶሮ ዓይነቶች አሉ። እነሱም የግጭት ማሳረጊያና የምልጃ ማሳረጊያ ጎንዶሮ ይባላሉ። የነዚህን ልዩነትና አንድነት ከተሰበሰበው መረጃ አኳያ ለማየት ተችሏል። ስለዚህ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ለማየት እንችላለን።

#### 6.2.2.1. የግጭት ማሳረጊያ ጎንዶሮ

ቀደም ሲል እንዳየነው ከባድ ግጭት በግለሰብ ደረጃ፣ በቤተሰብ አባላት ውስጥ ወይም በተለያዩ ቤተሰብ ውስጥ ካሉ ግለሰቦች፣ ጎሳዎች ወይም ከአጎራባች ብሔሮችና ብሔረሰቦች ጋር ሊፈጠር ይችላል። የግጭቱም ምክንያቶች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

በጉጂ አካባቢ ከሚነሱ ግጭቶች ውስጥ አንድ መንስኤው ይህ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ከፊል-አርብቶ አደርነታቸው ከአጎራባች ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ጋር አልፎ አልፎ ግጭቶች ይከሰታሉ፡፡ እነዚህ ግጭቶች ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርሱበት ጊዜም አለ፡፡
የገዳ ስርዓት ግጭቶችን በመፍታትና ሰላምን በማስፈን በኩል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው (Israel, 2011፡300)፡፡ ለዚህ ስኬት ደግሞ የቃሉ ተቋም ያለው አስተዋጽኦ የጎላ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ ተቋም በራሱ ከፍተኛ ግጭቶችን የመፍታት አቅምና ችሎታውም እንዳለው ማህበረሰቡ ያምኑበታል፡፡

ይህ የጎንዶሮ ከበራ እያለም አልፎ አልፎ በአጎራባች ህዝቦች መካከል በተለያየ ወቅት ግጭቶች ይነሳሉ፤ ብዙ ደም መፋሰስ ደረጃም ይደርሳሉ፡፡ ለዚህ የሚስማማ አንድ የጉጂ ኦሮሞ ምሳሌያው አባባል አለ፡፡ ይኸውም፡-
“kaleessa hin kakannee?” jennaan “edana hin bullee.” Jedhe
አቻ ትርጉሙም “ትላንትና አልማልክም ነበር?” ቢባል “ምነው ትላንት አድረን የሌ፡፡” አለ ይባላል፡፡
ከዚህ አባባል የምንረዳው በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም፡- በግጦሽ መሬት ይገባኛል፣ ከህዝብ ቁጥር መብዛት የተነሳ፤ የእርሻና የግጦሽ መሬት ፍለጋና በመሳሰሉ ምክንያቶች ዳግም የሚያገረሽበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡ በሌላ በኩል የገዳዎች ቁርጠኝነት ማጣት እንደሚታይና የጎሳዎቻቸው ክፍተት የመሸፋፈን ሁኔታዎች እንዳሉና ለዳግም ግጭት እንደሚዳርጋቸው መረጃ አቀባዮቼ ይገልጻሉ፡፡ ይህ በዝርዝር በ7.2. ስር ተገልጿል፡፡

## I. በጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ ውስጥ የቃሉ ሚና

ቀደም ሲል እንደተገለጸት የቃሉ ከበራዎች፡- የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች እንዳይከሰቱ ቅድመ-መከላከል፣ አሊያም ችግሮቹ ከተከሰቱ በኋላ እንዳይስፋፉ፣ ጉዳታቸው እንዳይበዛና ከናካተው እንዲያበቃ የሚከወኑ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶችና አካላት የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት የሚፈጸም የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

የቃሉና የገዳ ስርዓት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ የገዳ ስርዓት እርስ በርስ የተሳሰሩ ሶስት አካላት አሉት፡፡ እነሱም፡- ሃይማኖታዊ ተቋም (የቃሉ ተቋም)፣ ጠቅላላ ጉባኤ

(gumii) እና ገዳ ማለትም የስርዓቱ ፖለቲካዊ አመራር እንደሆኑ Asmarom, (2000:100) ያስረዳል።

ከነዚህ ሶስቱ አካላት ውስጥ በጣም ብዛት ያለው ሰው የሚሳተፍበት ጠቅላላ ጉባኤ (gumii) ነው። ምክንያቱም ይህ ጉባኤ አዲስ ሕግ የሚወጣበት፣ በነባሩ ሕግ ውስጥ ያረጁ፣ ያፈጁ ሕግጋት የሚታደሱበት፣ ማለትም ከወቅቱ ጋር የማይሄዱ ከውስጡ የሚወገዱበት፣ ምናልባትም አዳዲስ ሕግጋት የሚታከልበት ቦታ ስለሆነ፤ እዚህ ቦታ ላይ ደግሞ ስለ ባህሉና እምነቱ ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትና የኦሮሞ አዋቂዎች (hayyuu) የሚሳተፉበት መሆኑን Asmarom በማከል እንደሚከተለው ያስረዳል።

> Gumi means 'the multitude' because it is a very large assembly made up of many councilors (hayyu) and assemblies (ya'a) drawn from different section of the gada institution as well as ordinary citizens who have the ability to express their thoughts on matters of national concern (Ibid:97).

ይሁን እንጂ ለነዚህ ሶስቱ አካላት ትስስር ውሉ የቃሉ ተቋም ነው። ምክንያቱም የገዳ ስርዓት መሰረቱን ሳይለቅ በየስምንት ዓመቱ የሚያደርጉት የስልጣን ሽግግር እንዲቀጥል የሚያደርግ ማዕከላዊ ተቋም በመሆኑ ነው። ሌላው ጠቅላላ ጉባኤውንም የተመለከትን እንደሆነ ከዚሁ ሂደት ጋር አብሮ የሚነሳና ከገዳ ስልጣን ሽግግር በኋላ አሮጌው ሕግ የሚከለስበት ጉባኤ ነው። ስለዚህ የነዚህ ከበራዎች መጀመሪያውም ሆነ መጨረሻውም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በመሆኑ ነው።

ቃሉ በገዳ ስርዓት ውስጥ በሀገረሰባዊ ሃይማኖት ዙሪያ ለሚካሄዱት ከበራዎች ኃላፊነት ያለው አካል ነው።

ከዚህም ባሻገር የቃሉ ተቋም በዋናነት በገዳዎች መካከል ግጭቶች ቢፈጠሩ፣ እንዲሁም በጎሳዎች መካከል ግጭቶች ቢከሰቱ፣ ከአጎራባች ብሔሮችና ብሔረሰቦች ጋር ግጭት ቢፈጠር እነዚህንና የመሳሰሉት ግጭቶች ከመፍታትና የመጨረሻ መቋጫ ከማበጀት አኳያ ያለውን ሂደት የማስፈጸም ድርሻ ከፍተኛ ነው።

ይህ ሲባል የገዳ ተቋማት ሚና የላቸውም ማለት አይደለም። የገዳ ተቋማት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነሱ ግጭቶችን ከመፍታትና ለማህበረሰቡም ያለው ቅርበትና ተደራሽነቱም ሰፊ ነው። እንደመረጃ አቀባዮቹ ገለጻም ገዳዎች የእርስ በርስ ችግራቸውንም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን የመፍታትና ዘላቂ መፍትሔ ከማስገኘት በኩልም ከፍተኛ ሚና አለው። ነገር ግን ከነሱ በላይ የሆነውን ጉዳይ ሊፈታ የሚችለው ግን የቃሉ ተቋም ነው።

## II. የግጭት አፈታት መዋቅሮች

በጉጂ ኦሮሞ አካባቢ የተለያዩ ማህበራዊ ግጭቶችና ክርክሮች ሲከሰቱ የሚፈቱባቸው የተለያዩ መዋቅሮች አሉ። እነሱም፡- ግለ-ወቀሳ (si himadhaara)፣ ሽምግልና (Jaarsummaa) እና የቃሉ መማክርት (gumii qaalluu) ናቸው። ከእነዚህን መዋቅሮች ውስጥ የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን የተወሰነ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ገለጻ በማቅረብ የሚታለፉ ሲሆኑ፤ ሶስተኛው መዋቅር ግን ከጥናቱ ትኩረት አንዱ ስለሆነ በጥልቀት ትንተና ተካሂዶበታል። ስለዚህ ከዚህ እይታ አኳያ እንደሚከተለው አንድ በአንድ እንመለከታለን።

### 1. ግለ-ወቀሳ (si himadhaara)

ግለ-ወቀሳ ማለት ሁለት ግለሰቦች በተለያዩ ነገሮች ላይ ያለመግባባትና ተበዲያለሁ ባይነት ስሜት ሲሰማቸው አንዱ ሌላውን የእንወቃቀስ ፍቃድ ጠይቆ እርስ በርስ የሚተራረሙበት የመጀመሪያው መዋቅር ነው።

እንደ ጉጂ ኦሮሞ የግጭት አፈታት መዋቅር በግለሰቦች መካከል ካለ ቀረቤታ፣ ከሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ፣ እንዲሁም ከወግና ባህሉ ተነስቶ ከአንድ ሰው የሚጠበቅበት ስነ-ምግባሮች አሉ። ለምሳሌ፡- እንደዋቄፋና እምነት እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት ምዕመኑ እንዲያከብራቸው ያስተምር ዘንድ ካዘዛቸው ሕግጋት ውስጥ አንዱ ስለ ሳፉ (Safuu) እንደሆነ በ4.2.5. ስር ተመልክተናል።ይኸውም፡- በዋቄፋና ሃይማኖት ልጆች ወላጆቻቸውን፣ታናናሾች ታላላቆቻቸውን፣ ጎልማሶችና አረጋዊያንን፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ዋቄፋታ ቃሉዎችንና አያንቱዎችን ማክበርና ቀድሞ ወንዝ ከመሻገር፣ ቀድሞ ከመመረቅ፣ እንደተቀመጠ ሰላምታ ከመስጠትና በነጠላ ስም ከመጥራት መታቀብ ይጠበቅበታል። ዋቃ ቀኑን ለሰዎችና ለቤት እንስሳት፣ ሌሊቱን ለዱር አራዊት የፈቀደ በመሆኑ ይህ መሻር እንደሌለበትና የደኖች ልምላሜና የወንዞች ንጽህና መጠበቅ እንዳለበት የሚያዝ ሕግ ነው። እነዚህ ትዕዛዛት ደግሞ ፈረሃ-እግዚሐብሔርን፣ ወግና ባህልን መጠበቅ እንደሚያስፈልግ የሚያስጠነቅቁ ናቸው (Bartels,1983 & Dejene, 2007)።

ይህ ከላይ የተመለከትነው የዋቄፋና እምነት ህግጋቶች ከእግዚኣብሔር ወደ ቃሉ፣ ከቃሉ ደግሞ ወደ ምዕመኑ፤ እንዲሁም ከምዕመኑ ወደ ምዕመኑ እየተላለፈ እዚህ የደረሰው በስነቃልና በድርጊት አማካይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ነው። ይህ ባህሪይ ደግሞ የማንኛውም ህገረሰባዊ ሃይማኖት መተላለፊያ መንገድ ነው።

እንደ መረጃ አቀባዮቹ ታላቅን ማክበር (በሰላምታ፣ ወንዝ ሲሻገሩ ቅድሚያ በመስጠት፣ ተራ ጠብቆ አነጋገር፣ ምርቃት....)፣ እንግዳ መቀበል (እግር አጥቦ፣ በቅቤ አሽቶ፣ አብልቶ፣ አጠጥቶ ማሳደርና መሸኘት...)፣ የታመመን መጠየቅ፣ የሞተ መቅበር... ማህበረሰቡ ከባህላዊ አኗኗሩና ከእምነታቸው ያካበቱት እሴቶች እንደሆኑ ይገልጻሉ። በሌላ በኩል መፋቀር፣ እውነት መናገር፣ በሰላም መኖር፣ ለሰው ልጅ ክብር መቆርቆርም በባህላቸው ውስጥ እንደሚታይ ይገልጻሉ።

ለምሳሌ፡- ልጅ ለአባቱ መታዘዝና አባቱን ማክበር እንዳለበት እየታወቀ፤ ኀረመስኩ ብሎ አባቱን ቢንቅ ወይም ቢያንጓጥጥ ቤተ-ዘመዱም ሆነ ኀረቤቱ ዝም ብሎ አይመለከትም። ምክንያቱ በአንድ በኩል የቃሉ አስተምሮትም ተጥሷል። በሌላ በኩል እንዲህ ዓይነቱ ጋጠ-ወጥ ልጅ ነገ ለሌሎች የዕድሜ እኩዮቹ የሚያስተምረው መጥፎ አርኣያ በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳይሰራጭ ከማሰብ ነው። ስለዚህ ቀድመው ይመክሩታ። በዚህ የማይመለስ ከሆነ ቤተሰብ ተሰብስቦ የአካል ቅጣት ይፈጽሙበታል።

ሌላው የቃሉን ግለሰባዊ ልዕልና የተመለከትን እንደሆነ በመጀመሪያ ደረጃ በማህበረሰባዊ እሴቶች የተገነባ፤ ከዚያ ባለፈ ለቀሪው ማህበረሰብም ተምሳሌት በመሆን የሚያገለግልና በተቋሙም ውስጥ የካደ እውነቱን የሚያወጣበ ወይም የሚናገርበት፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ የበደለ የሚካስበት፣ ባህልና ወጉን የጣሰ ተወቅሶ የሚታረምበት፣ ታላቅን ካላከበረና የባህል ጥሰት ከፈፀመ፤ ይህን ጥሰት የፈፀመ መውቀሻ/ቅሬታ ማሰሚያ መንገድም አለ። ይኸውም፡- ቅሬታ አለኝ፤ ልወቅስህ ነው (Quuxxee qaba, Si himadhaa.) የሚል ቅሬታ ማቅረቢያ ባህላዊ አውድ ነው።

ታዲያ ተበደልኩ ባዩ ግለሰብ ከላይ የተጠቀሰውን ግሉ-ወቀሳ በሚልበት ወቅት፤ በዳዩ በባህሉ መሰረት ጥፋቱን ተረድቶ ቶሎ ብሎ "አትውቀሰኝ በድየሃለውኝ፤ ባጠፋሁት እቀጣልሃለሁ።" በማለት በሁለቱ ስምምነት ሊፈታ ይችላል። በዚህን ጊዜ ስህተቱን በምን ምክንያት ሊፈጽም እንደቻለ በማስረዳት ይቅር እንድለው ይማጸነዋል። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Balleesan kiyya. | ጥፋቱ የኔ ነው። |
| Yaadoo ta'e tokko keessa ta'ee | የሆነ ሀሳብ ውስጥ ሆኜ |
| si hin argin, | አላየሁም፣ |
| Kanaaf malee, akkamiin si | ይህ ባይሆን ኖሮ! ሰላም ሳልልህ |
| hin yooyyifatin darba? | እንዴት አልፋለሁ? |
| Kanaafuu,hattoo naan jedhe. | ስለዚህ ይቅር በለኝ። በማለት |

ይቅርታውን ይጠይቀዋል። ከዚያ ያም የወቀሰው እምነቱ፣ ባህሉና ወጉ እንዳይሸረሸር ለመቆጣጠሪያነት ያህል ተቆርቁሮ መሆኑን በማስረዳት የተጠየቀውን ይቅርታ ተቀብሎ በሰላማው መንገድ እንደዱሮዋቸው መኖር ይጀምራሉ።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ አጥፊው መስሎት ያደረገው ነገር ከሆነ "ውቀሰኝ፤ ሽማግሌ ይየው።" በማለት ሽማግሌዎች እዚያው ይሰየሙና በባህሉ መሰረት ጉዳዩን እንዲጣራ ይደረጋል፤ ውሳኔ ይሰጥበታል። ውሳኔውም እንደሁኔታዊ ተፈጻሚ ይሆናል።

መቼቱ ድርጊቱ በተፈፀመበት ቦታና ዕለት (መጠጥ ቤት፣ ገበያ...) አካባቢ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ወቀሳውን እንዲካሄድና እንዳይካሄድ የሚወስኑ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ።

ለአብነት ያህል ጊዜው ምሽት ከሆነ ተወቃሹ፤«ጀንበር አዘቅዝቃለች፤ በዚህ ሰዓት ሽምግልና አይታይም።» (lafti oliifi gadi, hayyuu gaafachuu hindande'amu.)፣ በሌላ በኩል «እኔ አባት አለኝ» (ani abbaa qaba.) በማለት ይከራከራል። ምክንያቱም በባህሉ መሰረት አባት ያለው ልጅ፤ አባቱ እያለ እሱ አይወቀስም። ስለዚህ አባትህን አቅርብ ይባላል። በዚያን ጊዜ ደግሞ «አባቴ መንገድ ሄዷል» (abbaan kiyya Karaa deeme jira.) የሚሉትንና የመሳሰሉትን የማምለጫ ሀሳቦች እየሰነዘረ ጉዳዩን በይደር እንዲታለፍ የሚደረግበትም ሁኔታዎች እንዳሉ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ።

ተወቃሹ ይህን የሚያደርገው ላለመካድ፣ ላለመዋሸትና ሳጠፋው ጥፋት የሚክሰው ነገር ከሌለው ባህልና ወጉን ላለመጣስ፤ ከባሰበት ባህሉ ያስቀመጣቸው የማምለጫ ዘዴዎች መጠቀሙን ያሳያል። ስለዚህ ቀጠሮ ይያዛል። ይኸውም፦ የተወቃሹ ጥያቄ የጊዜ ጉዳይ ከሆነ በማግስቱ ጠዋት ይታያል። አባቱ መንገድ ሄዷል ካለ መመለሻው ተጠይቆ በዚያን ዕለት ይዞት እዲቀርብ ይነገረውና በዚያን ወቅት ጉዳዩ ይፈታል። ስለዚህ በዚህ ምክንያት ነገሩን ሊያሳድሩት ይችላሉ። ነገር ግን ተወቃሹ እንዲህ መወትወቱ በራሱ በውስጠ ታዋቂነት በጉዳዩ እንዳመነና ከቅጣት

ለመሸሽ መጣጣሩ ይታወቃል፡፡ ለማንኛውም የማህበረሰባዊ እሴቶች መጣስ እንደሌለባቸውና ከተጣሰ ደግሞ ወደ መስመሩ የመመለሻ ስርዓት እንዳለ ያሳየናል፡፡ ከዚህ ውጭ ከሆነ ያ ሰው እንደባለጌ፣ ወሮበላ...ይታያል፡፡

ስለዚህ እነዚህ እሴቶች የእያንዳንዱ ግለሰባዊ ልዕልና በማህበረሰባዊና አለማቀፋዊ እሴቶች እንደተገነባ ያመላክታሉ፡፡
ይህ ሳይሆን ሲቀር ቀላል ግጭቶች ሲፈጠሩ ደግሞ ወደሚቀጥለው የሽምግልና የግጭት መፍቻ መዋቅር ይተላለፋል፡፡

1. ሽምግልና (Jaarsummaa)

ከስያሜውን ብንነሳ "ሽምግልና" (jaarsummaa) የሚለው ስም የመጣው ጉዳዩን ከሚመለከተው ሽማግሌ (jaarsa) ከሚለው ስም እንደሆነ የሀገር ሽማግሌዎች (መረጃ አቀባዮቹ) ይናገራሉ፡፡ ይኸውም የበዳይንና የተበዳይን ጉዳይ በሽማግሌዎች አማካይነት አቀራርቦ መረጃዎቹን አያችሁ፣ ሰማችሁ በማለት ይፈቱታል፡፡ ስለዚህ የዚህ ችግር መፍቻ ባህላዊ ተቋም ስያሜም ሽምግልና ተባለ፡፡ በአፋን ኦሮሞ የግስ ርባታ ሂደት የተመለከትን እንደሆነ "jaarsa" ስም ሲሆን "jaarsummaa" ሂደት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የሽምግልና ሂደት ስያሜ የመጣው በሽማግሌ አማካይነት ጉዳዮቹ ስለሚታዩ (ስለሚዳኙ) ነው፡፡ በመሆኑም የጉጂ ማህበረሰብ ይህን ስያሜ የሰጠው ከዚህ አኳያ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

እንደጉጂ ኦሮሞ የሽምግልና ደረጃዎች አሉ፡፡ ይኸውም፡- ማንኛውም ችግር በተቻለ መጠን በታችኛው መዋቅር እንዲፈቱ የመከራል፡፡ በተለይም ጥቃቅን ነገሮችን ወደ ላይኛው ደረጃ ማምጣት አይጠበቅም፡፡ ይኸውም በቤተሰብ ደረጃ፣ ቀጥሎ በዘመድ ደረጃ፣ በጎረበት ደረጃ፣ በመጨረሻም በጎሳ ደረጃ ሊታይ ይችላል፡፡ እነኝህን መዋቅሮች ጥሶ የሚሄድ ጉዳይ ካጋጠመ በገዳና ቃሉ ደረጃ ይታዩና ይፈታሉ፡፡

ለዚህም የሚረዳ የጉጂ ኦሮሞ ምሳሌያው አነጋገር አለ፡፡ ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| «dubbii worra gowwaa olla gahaa, | የሞኝ ቤተሰብ ጉዳይ ከጎረቤት ይደርሳል፣ |
| dubbii ollaa gowwaa fira gahaa, | የሞኝ ጎረቤት ጉዳይ ከዘመድ ይደርሳል፣ |
| dubbii fira gowwaa gadaa gahaa. | የሞኝ ዘመድ ጉዳይ ከገዳ ይደርሳል ይባላል፡፡ |

ከላይ ካየነው ምሳሌያዊ አነጋገር የምንረዳው አንድ የተወሰነ ግጭትም ሆነ ችግር በቤተሰብ ውስጥ ከተከሰተ እርስ በርስ የመደማመጡና የመከባበሩ ባህል ስላለ በዚያው ቤተሰብ ደረጃ ይፈታል የሚል እምነት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሳያውቁበት ዕድሉን ካልተጠቀሙ የጎረቤት ሽማግሌዎች ጣልቃ ይገቡና ይፈቱታል፡፡ ይህም ሳይሆን ቀርቶ ከዘመዶቻቸው በቤተሰብ ጉባኤ አማካይነት የተከበሩና ተሰሚነት ያላቸውን በማስጠራት ለመፍታት ጥረት ይደረጋል፡፡ ከዚህ ደረጃ በላይ ከሆነ ጉዳዩንና ባለጉዳዮቹን በመያዝ ወደ ገዳ ተቋም ያቀርቡታል፡፡ በሚኤ ቦኮ የአዋጅ ነገራ ወቅትም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት የባልና ሚስት ጉዳይ ይዘው ወደ ፖሊስ ጣቢያና ፍርድ ቤት መሄድ ባህላቸው እንዳልሆነና በእነዚህ ባህላዊ የግጭት መፍቻ መዋቅሮች መፍታት እንዳለባቸው ይደነግጋሉ፡፡

በሽምግልና ወቅት ቀድመው ፈጣሪ (ዋቃ) በሰላም ስላገናኛቸው ያመሰግኑታል፡፡ በመቀጠል እርቁን እርቅ ሰላም እንዲያደርግና በመካከላቸው ተገኝቶ ጉዳዩን እንዲፈታላቸው እግዚአብሔርን ይለማመናሉ፡፡

የሽምግልና ስርዓት በባህላዊ አካሄድ ተበደልኩ ባይ ባቀረበው የጉዳዩን እዩልኝ ጥያቄ መሰረት ሽማግሌ ከመንደሩ ነዋሪዎች በማህበራዊ መዋቅሩ መሰረት የዘር ሀረጉ ይታያል፣ በዕድሜ፣ በንግግር ችሎታ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ባለቸው ተቀባይነት ተመርጠው የሚሰየሙ ናቸው፡፡
የሽምግልናውን ይዘት ስንመለከት በመጀመሪያ ከግራ፣ ቀኙ ወገን መረጃ ይሰበሳባል፡፡ ከቀረበው ምልልስ ከጭብጡ በመነሳት፤ በምን ምክንያት ሊበድል እንደቻለ ማለትም፡- ሆን ብሎ ነው ወይስ በድንገት የተከሰተ ነው? የሚሉት ይታያሉ፡፡ ከዚያ ለበዳዩ አውቆ አድርጎት ከሆነ "የቀን ነገር ነው፤ፍርጃ ነው፡፡ በማለት ተበዳዮ ቂም እንዳይዝ በማስተባበል፤ ለተበዳዩ ደግሞ አውቆ ባይሆንም «ይህ ሰው ተጉድቷል፤ ሊካስ ይገባዋል፡፡» በማለት ሰላምን የማውረድ ሀሳብ እንዳለው ከመረጃ ሰጪዎቼ ገለፃ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

የሚከውኑት (የምናገሩት) ሽማግሌዎችና በሽምግልናው ውስጥ ደግሞ ምልልስና ክዋኔዎችም አሉ፡፡ እንደመረጃ አቀባዬ ገለፃ በሽምግልና ሂደት ወቅት የሽማግሌዎች የእርስ በርስ ምልልስ ከተመለከትን፤የመጀመሪያው ጠያቂ ሽማግሌ የሚሰየመው ካሉት ሽማግሌዎች ውስጥ ማህበረሰቡ ባስቀመጠው ተዋረዳዊ መዋቅር መሰረት በተሻለ ቦታ ላይ ነው ብለው የሚሉትን ነው፡፡ ይኸውም ጎሳው፣ሃይማኖታዊና ባህላዊ ዕውቀት ደረጃው ይታያል፡፡ በዚህ መልኩ ሁለት ሽማግሌዎች ይመረጡና እናንተ እዩ ይባላሉ፡፡ ሌሎች የተበዳዩን፣ የበዳዩን፤ እንዲሁም የሽማግሌዎቹን አጠያየቅ በጥንቃቄ ያዳምጣሉ፡፡ ከዚያ አንዳንድ ነገሮች ፈር ከሳቱ "የትንባሆ

መያዥህን ልሰርልህ" (coraa siif hidhuu) በማለት ይቅርታ ጠይቆ ተራ በመወሰድ የተሰማውን ስሜት ይናገርና ሀሳቡን እንደጨረሰ መልሶ ለቀድሞዎቹ ሽማግሌዎች ይሰጣል። ይህ እንግዲህ "አፍህን በማር..." ተብሎ ጣልቃ እንደመግባት ማለት ነው።

አንዳንዴ ጉዳዮች ይካረሩና በአካባቢ ሽምግሌዎች ሊፈታ ካልቻለ ወደ ጎሳ መሪዎች ማለትም ወደ አባገዳዎች ወይም አባቃሉ ደረጃ የሚደርሱበት አጋጣሚዎችም ይፈጠራሉ። ለምሳሌ ከግለሰቦች በተነሳ ግጭት የሰው ነፍስ መጥፋትና የንብረት ውድመትን ካስከተለ፤ ፀቡ ከግለሰባዊ ባህሪይ ወደ አካባቢያው መልክ ሊይዝ ይችላል። በተለይም የእርስ በርስ ግድያን በተመለከተ፣ የንብረት ውድመትን በተመለከተ ከአካባቢው ሽማግሌዎች አቅም በላይ ስለሆነ ከላይ በተጠቀሱት ትላልቅ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ተቋማት ዘንድ እንደሚታዩ ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ችያለሁ።

በሽምግልና ወቅት የሚነገረው በዋናነት ለበዳይና ተበዳይ ነው። ቀጥሎ በቦታው ለተገኙት የሀገር ሽማግሌዎችና የበዳይና የተበዳይ ወገን ነው። ከአጥኚው የቀድሞ ተሞክሮና ከተሰበሰው መረጃ፣ ለመገንዘብ እንደተቻለው፣ በቦታው የተገኙ ታዳሚዎች ከሽማግሌዎቹ ተግሳጽና ምሳሌያዊ ንግግሮች ከሚሰሙት መልዕክት ተነስተው እራሳቸውን ወደሚፈለገው አቅጣጫ እያስተካከሉ ይሄዳሉ። ከቀረበው ጭብጥ ተነስተው ነገሮች እንዲፈቱ ሁሉም የራሳቸውን ጥረት ያደርጋሉ። የሽማግሌዎችን ቃል አልቀበልም ባለው ላይ በዝምድናና በታላቅነት ጫና ለመፍጠር ይጥራሉ። በተለይም የበዳይና ተበዳይ ዘመዶች፤ ሽማግሌዎቹ ያዩትን ጠንካራና ደካማ ጐን በማንሳት ምን መሆን እንዳለበት ለመወያየት አስፈቅድው ዞር ብለው ይወያየሉ። በአካሄዱም "እስቲ ሽንተን እንመለስ"(fincoofnee haadeebinu) በማለት ፍቃድ ይጠይቃሉ። አሊያም ሽማግሌዎቹ እራሳቸው (mee finco'aa kootta) በማለት ተማክረው የመፍትሔ ሀሳብ ይዘው እንዲመጡ ይደረጋሉ። ይህ አባባል በኦሮሞዎች ዘንድ ከሚጠቀሙት ፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ አንዱ ሲሆን አቻ ትርጉሙም በቅደም ተከተል ተማክረን እንመለስ የሚልና ተማክራችሁ ኑ እንደማለት ነው።

የዚህ ሂደት ጠቀሜታ በዳዩም ይሁን ተበዳዩ ያልተረዳውን ነገር በማስረዳት እሺ ወይም እንቢ እንዲሉ ቤተሰባዊ ጫና መፍጠሪያ መንገድ ነው። ከዚያ ሲመለሱ "ሽንታችሁ መጣችሁ?» በማለት ሽማግሌዎች ይጠይቃሉ። "አዎ! መተናል"። በማለት የደረሱበትን ሀሳብ ያስረዳሉ።

በዚያም ጉዳዩ እንደ ሁኔታው ይፈታል። አሊያም በይደር ይተላለፍና ጉዳዩ በቀጠሮው ቀን ይታያል።

የሽምግልናውን አውድ በተመለከተ ማህበረሰቡ ለሽምግልና በዋናነት የሚጠቀምበት ቦታ “ኦዳ” ስር ነው። “ኦዳ” የዋርካ እንጨት ሲሆን የጉጂ ኦሮሞ እንደ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ማዕከል አድርጎ ይጠቀምበታል። ማህበረሰቡ አንድ ማህበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ወይም ሃይማኖታዊ ጉደዩችን ተሰባስቦ የሚፈታበት ስፍራ ነው። ስለዚህ እንደ መረጃ አቀባዬ ገለፃ እንደተረዳሁት የተበዳዩም ሆነ የበዳዩ ቤት ተፈላጊ አይታይም። ምክንያቱም ጉዳዩ ሳይታይ ማን እንደበደለ፤ ማን ደግሞ እንደተበደለ ሳይታወቅ አንዱን ከፍ አንድን ደግሞ ዝቅ አርጐ ማየት ስለሚመስል ነው። ስለዚህ ለሁሉም አማካይ በሆነ ቦታ ተመርጦ የሚካሄድ ሂደት ነው። አሊያም አማካይ ቦታ ላይ በጠዋት ይከናወናል። የባልና ሚስት ጉዳይ ከሆነ ደግሞ በራሳቸው ቤት ወይም ተበዳይዋ ከተከለለችበት ቤት ውስጥ ሊሆን ይችላል።

የሽማግሌዎቹ አቀማመጥ እርስ በርስ እየተያዩ ለመነጋገር እንዲያመቻቸው ተብሎ ክብ ሰርተው ይቀመጣሉ። በዳይና ተበዳይ ደግሞ ጐን ለጐን አይቀመጡም። ምክንያቱም ጉዳዩ እስካልተፈታ ፀበኛ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው።

ሽምግልና ብዙውን ጊዜ የሚከናወነው በጠዋት ነው። ስለዚህ ሁሉም ሽማግሌዎች ቡሉኮዋቸውን ተከናንበው ሜዳው ላይ ቁጭ ብለው የዕለቱን ጉዳይ ይፈታሉ። ጊዜው በጠዋት የተመረጠበት ምክንያት፡- ታዳሚው ባዶ አፉን ማለትም መጠጥ ሳይጠጣ በትክክለኛ አእምሮው ለመወያየት እንዲያመች ሲሆን፣ ሌላው በጠዋቱ ጉዳዩን ከፈቱ በኋላ ወደየግል ስራቸው ለመሰማራት እንዲያመቻቸውም ጭምር እንደሆነ የአጥኚውም የቆየ ግንዛቤ ነው።

በመጨረሻ በዳይ ለተበዳይ እንደጥፋቱ መጠን ባህሉ ባስቀመጠው ህግ መሰረት እንድክስ ተደርጎ የማስማማት ሂደቱ ይፈጸማል። በዚህ ወቅት አንዳንድ ተበዳዮች የተካሱትን ከወሰዱ በኋላ እኔ በእናንተ (በሽማግሌዎች) አማካይነት እውነትን አግኝቻለሁ፤ ነገር ግን ከወንድሜ/እህቴ ላይ ካሳ አልበላም በማለት የሚመልሱም እንዳሉ ካገኘሁት መረጃ ለመረዳት ችያለሁ።

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የግጭጥት አፈታት መዋቅሮች እንደየችግሩ ወይም ጥፋቱ መጠን በሂደት ከስር ወደላይ የሚመጡ ናቸው። በቃሉና ገዳ ተቋም ደረጃ ትናንሽ ችግሮችን

ይዘው መሄድ አይፈቀድም፤ ቢኬድም እንደገና ወደሚመለከተው ክፍል ሄደው ጉዳያቸውን እንዲፈቱ ይደረጋል።

2. **የቃሉ መማክርት** (gumii qaalluu)

በቃሉ አማካይነት ከሚፈቱ የግጭት ማስወገጃ ከበራዎች ውስጥ የጎንዶሮ ከበራ አንዱና ዋንኛው ነው። ይህ ከበራ የሚካሄደው ደግሞ በቃሉ መማክርት አባላት በኩል ነው። ስለዚህ ይህን ሂደት እንዴት እንደሚያስፈጽሙና በምን ዓይነት መንገድ እንደሚቋጩት ከዚህ በመቀጠል በዝርዝር ለማየት እንችላለን።

I. **የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ ሂደት**

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ጎንዶሮ ማለት ይህ ክስተት ዳግም (ሁለተኛ) በእኔ/በእኛ እንዳይመለስ ወይም እንዳይከሰትብን እንደማለት ነው። ለምሳሌ ከዱር አራዊቶች ውስጥ ጅብ ወይም አንበሳ ሊሆን ይችላል፤ በተደጋጋሚ እየመጡ ከብቶች ከመስክም ሆነ ከበረት የሚያጠቁ ከሆነ፤ ይህ ነገር ጥሩ አይደለም፤ የጎንዶሮ ከበራ መፈጸም አለብኝ በማለት ያከናውናል። ይኸውም ከበራውን ሀብት ያለው በግ ወይም ከብት በማረድ ያካሂዳል። የሚያርደው የሌለው ደግሞ በምትኩ ውሃ በማዞር፣ እንቧይ በማረድ ይህን ችግር ዳግም እንዳይከሰትበት ክዋኔውን ይፈጽማል።

በማንኛውም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ወቅት የሚከናወን እርድ ሞራው ይታያል። ከዚያም ስለተከወነው ሁኔታ ከሞራው በማየት የሚሉት አላቸው። ስለክዋኔው መሳካቱን አሊያም አለመሳካቱን ይናገራሉ። ካልተሳካ ሌላ እንዲታረድ ይደረግና ሞራው እንደገና ይታያል። ለዚህ ክዋኔ ከጉረኖው ውስጥ ሲወጡ ቀልቡ ያረፈበትን እንጂ እንዳገኘ ወስዶ አያርድም። እንደነሱ አባባል ‹‹እኔን እረደኝ ብላ (kan fariste) የምትለውን›› ነው የሚያርደው።

ሌላው ግለሰብ ከግለሰብ ጋር አሊያም ከአጎራባች ክልል ህዝብ ጋር በሚፈጠሩ ግጭቶች ደም መፋሰስ ሊከሰት ይችላል። በዚህ ወቅት ግጭቱ እንዲያበቃ፣ ለወደፊት ደግሞ በሰላም እንዲኖር የጎንዶሮ ከበራ ይፈጸማል። በዚህ ደረጃ የሚፈጸመው ጎንዶሮ በአባቃሉና በመማክርት አባላቱ አማካይነት የሚከወን ነው። ይህንኑ ሀሳብ Asebe እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

> The leaders of the qaalluu institution were the only legitimate and respected officials in prayers, blessings and conflict mediation processes together with gadaa leaders (Asebe, 2012፣16).

ሌላው እንደ መረጃ አቀባዮቼ ገለጻ አንድ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም፡- በጊዜያዊ ግጭት ወይም በመጠጥ መንፈስ አሊያም ሳያስበው አውሬ መስሎትና እንዲህ ባሉ ክስተቶች እገላለሁ ብሎ ሳያስብ በእጁ የሰው ነፍስ ሊጠፋ ይችላል፡፡ይህ ክስተት ደግሞ በማንኛውም የሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከሰት ነው፡፡ ነገር ግን ጉጂነታቸው እንደሚያገናኛቸው ያምናሉ፡፡ እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለጻና ከአጥኚውም የቀደመ ዕውቀት ወንጀል ፈፃሚው በዚህ ጊዜ በራሱም ሆነ በቤተሰቦቹ ላይ የበቀል ጥቃት ሊሰነዘር እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል ባደረገው ነገር ተፀፅቶ ለቤተሰቦቹ በፍጥነት መልዕክት እየተቀባበሉ ካስተላለፉ በኋላ እግሬ አውጭኝ እያሉ ወደ አባቃሉ ተቋም ይሸሻሉ፡፡ አሊያም ወደገዳ ማዕከል ይሸሻሉ፡፡ ይህ ማድረገረ ካልተቻለው በአቅራቢያ ተቀባይነት ወዳላቸው የባህል ሰዎች ዘንድ በመጠለል ለገዳ ወይም ለቃሉ እንዲያሳውቁላቸው ያደርጋሉ፡፡ ከዚያም የተፈጠረውን ክስተት ለአባቃሉ ያስረዳሉ፡፡ አባቃሉም በአስቸኳይ ወደስፍራው አባገዳንና ሽማግሌዎችን፣ አሊያም ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችን መርጦ ወደተበዳዮቹ ቤተሰብ ጎንዶሮ እንዲሉ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ መልዕክቱም «የሞተውም የእኔ ነው፤ የገደለውም የእኔ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ እምነታችን፣ እንደ ባህላችን ጎንዶሮ በሉ» በማለት መልዕክቱን ይዘው ይላካሉ፡፡ እነዚያም የተባሉበት ቦታ በመሄድ በአካባቢው የሚገኙ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችን መርጠው፤ ጉዳዩን በማጣራት የበደለ ክሶ እንዲታረቁና የጎንዶሮ ክዋኔ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

ይህ የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ በተለይ በጉጂና በጌዴኦ መካከል ለዘመናት ተጠብቆና ተከብሮ ያለና የሚኖር ነው፡፡ በተለይም በግጭት ማስወገድ ሂደት ላይ ጎንዶሮ ከተከወነ በኋላ ዳግም ወደዚያ ጉዳይ መግባት እንደመቅሰፍት ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም ይህን ቃል ያፈረሰ አካለ ጎዶሎ ይሆናል፣ ይቆመጣል፣ ሕይወቱ የተመሰቃቀለ ይሆናል፤ አሊያም ይሞታል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ስለዚህ በክዋኔው በስተመጨረሻ ላይ ከዛሬ በኋላ በእንዲህ ዓይነት ስህተት ውስጥ አንገባም፤ ስለተከሰተውም ሁኔታ ዳግም አናስታውሰውም በማለት ቃለ-መሃላ ይፈጽማሉ፡፡ ይህን የጣሰ ደግሞ ያ የእርግማን ቃል ሊደርስበት ይችላል ብለው ያምናሉ፡፡

የጎንዶሮ ክዋኔ የሚካሄደው በስተ-መጨረሻው ላይ ውሳኔውን በዘላቅነት ለማስከበር ነው። ይህን በዋናነት ማስከበር የሚችለው ደግሞ ቃሉ ነው። ቃሉ በስተመጨረሻው ሁለቱም ወገን እሺ ብሎ እርቁን በመፈጸማቸው፤ በመጀመሪያ ይህን ጉዳይ ያስፈጸመውን ፈጣሪን ያመሰግናል። በመቀጠል ሁለቱን ወገኖች ተሯርጠው ለዚህ ያበቁትን የካውንስሉን አባላት ይመርቃል። ከዚያ ተበዳዮቹ የዕለቱን ግጭት ሳይሆን፤ የድሮ ወዳጅነትንና በሰላም አብሮ መኖራቸውን በማስታወስ ይቅር በማለታቸው ሰላም ከቤታቸው፣ ሰላም ከቄያቸው፣ ሰላም ከጎሳቸው፣ ሰላም ካገራቸው እንዲገባ፣ ዳግም እንዲህ ዓይነት አደጋ አይግጠማችሁ በማለት ይመርቃል። በመቀጠል በዳዮቹንም ቢሆን ካሁን በኋላ ከእንዲህ ዓይነት አደጋ ይሰውራችሁ፤ ዳግም አይግጠማችሁ በማለት ይመርቃል። በመጨረሻም አባቃሉ ይህን የሰላም ውል በተለያየ መንገድ በማስታወስ እንዳያገረሽና ዳግም እንዲህ ዓይነት ግጭት ውስጥ እንዳይገቡ ይረግማል፤ ታዳሚዎቹም እርግማኑን ከአባቃሉ በኋላ ደግመው በማለት ያረጋግጣሉ፤ ይህም ድርጊት እንደ ቃለ-መሃላ ይቆጠራል። ታዲያ ይህን ቃለ-መሃላ የጣሰ ደግሞ ያ የእርግማን ቃል ሊደርስበት ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ሁሉም በፍርሃት እንደሚያከብሩት ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። ይህንኑ ሀሳብ Asebe በሚያጠናክር መልኩ ሲገልጸው፡-

> Finally, the *Abba* Qallu concludes the ceremony by blessing the peace to be durable and at the same time cursing any attempt of retaliation/ avenge (Asebe, 2007:67).

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አባቃሉ በስተመጨረሻ ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራው ላይ በመመረቅ፤ ዳግም ለበቀል እንዳይነሳሱ ደግሞ በዚህ ድርጊት ውስጥ እንዳይሳተፉ የሚያስጠነቅቅ እርግማን ይፈጽማል።

ጎንዶሮ በሀገር ሽማግሌዎች፣ በአባገዳና እንዲሁም በቃሉ ደረጃ ይከወናል። ይህ እንግዲህ ከከዋኞቹ አኳያ ሲሆን፤ ጎንዶሮ ሊፈጸምለት ከሚገባው ክስተቶች አኳያ ደግሞ ያየን እንደሆነ በጉጂ ኦሮሞ ጎሳዎች መካከል የእርስ በርስ ግጭት የተፈጠረ ከሆነ እንደ ችግሩ ስፋትና ክብደት፤ ማለትም የጉጂ ኦሮሞ ከቦረናና ከአርሲ ኦሮሞ ጋር እንዲሁም ከሲዳማ፣ ከኮይራና ከጌዴኦ ብሄር ብሄረሰቦች በተለያየ ወቅት፤ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶች የሚፈቱት በቃሉ፣ በአባገዳዎች፣ ሀዩዎች (የባህልና ሃይማኖት አዋቂዎች)ና የሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት ነው።

እንደ መረጃ አቀባዮቼ ገለጻ ከተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ጋር የተከሰተን ግጭት እርቅ ለማውረድ የፈለገው ወይም እርቅ እንዲወርድ የሚፈልገው አካል አባገዳዎች፣ ሀዩዎችና የሀገር ሽማግሌዎች በአንድ ላይ ይሆኑና በየራሳቸው ጎሳ ውስጥ ሆነው ሰላሙን እንዲያወርድላቸው ለአምላካቸው ጸሎት ያደርሳሉ። ጦርነቱ እንዲቆም ከህዝቡ ጋር ይለምናሉ።

ለምሳሌ ግጭቱ በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ብሄር መካከል የተከሰተ እንደሆነ፤ በሁለቱም ህዝቦች የእርስ በእርስ ጦርነት ያስከተለ ከሆነ፤ ከጌዴኦ ብሄር በኩል ወደ ጉጂ ኦሮሞ አሊያም ከጉጂ ኦሮሞ በኩል ወደ ጌዴኦ ወገን አምስት ሴቶችን በመምረጥ ጦርነቱ በሚካሄድበት ድንበር አካባቢ ይላካሉ። እነዚያ አሮጊቶችም ጩኸት እያሰሙ ይሄዳሉ። ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት በኦሮሞም ሆነ በአጎራባች ብሄር ብሄረሰቦች ባህል ሴቶችን መግደል የተወገዘ በመሆኑ ማንም ስለማይገድላቸው ነው። ስለዚህ ለግጭቱ መንስኤ የሆነው አካል ወኪል ሴቶቹ የእግዚሐብሄር ሰላምታ በመጠየቅ፣ ከጉጂ ኦሮሞ ወይም ከጌዴኦ የተላኩትን የሰላም መልዕክት ይዘው እንደመጡና እነሱ በራሳቸው በተለይም፡- በጉጂ ኦሮሞ «እኛ ሰላም ነን፤ እኛ መልዕክት ነን፤ ተቀበሉን» («nuuti nagaadha; nuuti ergaadha; nurraan fuudha.») ይላሉ። የተቃራኒው ወገን ደግሞ ሴቶቹ ይህን ዓይነት መልዕክት ይዘው ሲመጡ አንደኛ የሰላም ተምሳሌት በመሆናቸው፣ ሁለተኛ ሴቶች በመሆናቸው፣ ሦስተኛ ከሩቅ አካባቢ ተጉዘው ስለመጡ፤ ጩኸቱን ሰምተው የተሰበሰቡት የሀገር ሽማግሌዎች «ጥሩ ነው፤ ለማንኛውም አረፍ በሉ።» በማለት ማልደው ስለወጡ ውሃ፣ ወተትና ምግብ ጋብዘው፤ እንዲህ ዓይነት ችግሮች ድሮም እንዳሉና፤ አሁንም የሚከሰት መሆኑን በማስረዳት የተሰበሰቡት ሽማግሌዎች በአባገዳ መሪነት እሽታውን ይገልጹና ሴቶቹን ይሸኛሉ። ሴቶቹም ተሰናብተው ምላሹን ይዘው ወደ ላካቸው ወገን ይመለሳሉ። የላከውም አካል መምጣታቸውን በጉጉት እየጠበቀ ስለሚቆይ ሰመጡ እንኳን በደህና መጣችሁ በማለት ምላሻቸውን ይጠይቃሉ። እነሱም ያኛው ወገን ለእርቅ ዝግጁ ከሆነ የሁለቱም ወገን አባገዳዎችና የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የተጋጩ ቤተሰቦች በተገኙበት እርቁ ይከናወናል።

በእርቁ ወቅትም የጉጂ ኦሮሞ ከብት ያቀርባል። የጌዴኦ ብሄር ደግሞ ቦካ (የማር ጠጅ) ያቀርባል። ለጎንዶሮ የቀረበውን ከብት የሚያርደው ከሁለቱም ወገን ያልሆነ ሰው ይደረጋል። ምክንያቱም ጎንዶሮ በራሱ ይህ ግጭት በዚህ ይብቃ፤ ዳግም አያምጣው፤ የሚል ሀሳብ ያለው ስለሆነ ያን ጦስ ይዞ ወደ ማህበረሰቡ እንደመመለስ ስለሚቆጠር ነው።

በቃሉ የሚከወን የጎንዶሮ ከበራ በከባድ ግጭጦች መፍታት ላይ ያለው ሚና ከሌሎች በበለጠ ወሳኝ ነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው የ Asebe, (2007) ጥናታዊ ስራ ውስጥ በጉጂና ጌዴኦ መካከል ከተከሰቱት ግጭቶች ውስጥ በመንግስት መከላከያ ሰራዊት ጣልቃ ገብነት የተካሄደው የግጭት አፈታትና በቃሉ ከበራ የተፈታው የሁለቱ ህዝቦች ግጭት ዘለቄታ የነበረው ሁለተኛው እንደነበር እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

> *The 1995 conflict for example, ended up by the military intervention. Without resolving the fundamental question of the groups by the time - fair and free territorial rearrangement - the government opted for process of 'peace formation', which the Guji in Wonago district reject as illegitimate both from the practical means used and intended goals desired. They argue that no peace formation would be legitimate unless the root causes of the conflict are resolved. Practically, they saw it as violation of the principles of gondoro tradition as the practice would only be conducted by Guji Abba Qallu in cooperation with the two Abba Gadas. Coming back to the post 1998 period, informants are divided in their views. There is a common understanding that the 1998 conflict ended by intervention of elders. Unlike the 1995 case, government authorities also recognised the role of traditional methods of conflict resolution through the gondoro practice. The Guji Abba Qallu was brought from the jail to perform the blessing on the ceremony and taken back to prison up on completion of the ceremony (Asebe,2007:8)*

ከዚህ በተጨማሪ ስለጎንዶሮ ጥቅም ሲገልጹ በዚህ መንገድ የተፈታ ግጭት ዘላቂ ሰላምን ያመጣል። ነገር ግን በዘመናዊ ህግ መሰረት በፍርድ ቤት ቀርቦ የተፈረደበት ወንጀለኛ ቅጣቱን ጨርሶ ከማረሚያ ቤት ሲውጣ ከሟች ቤተሰብ ውስጥ ለበቀል የሚነሳ አይጠፋም፤ የሟች ቤተሰብ እንዲህ ዓይነቱን ባያስብም ያ የህግ ታራምው በራሱ በስጋት ይኖራል። ነገር ግን በጎንዶሮ ከበራ የተፈታ ከሆነ ሁለቱም ወገን ለቃለ-መሃላቸው ተገዥ ስለሚሆኑ ስጋት አይፈጠርም።

ስለቃሉና አባገዳ ተቋማት ክብር ሲገልጽ በአጎራባች ክልሎች አካባቢ የፈለገ ግጭቶች ቢከሰት ሌላውን አከባቢ ቢዳፈሩም፤ የቃሉና የገዳ ተቋም ወሰን ጥሶ የሚጋጭ አይኖርም፤ ያከበራል፡፡ ለዚህ ማሳያ እንደመረጃ አቀባዬ በ1987 ዓ.ም. በጉጂና በጌዴኦ መካከል በነበረው ግጭት የአባቃሉ ተቋም አካባቢም ሆነ በአባገዳ ደንቦባ ወሰን ከውስጥ ባሉ የጌዴኦ ህዝብ ላይም ሆነ፤ በጌዴኦ ክልል ውስጥ ባሉ የጉጂ ኦሮሞ ህዝብ ላይ ጥቃት እንዳልተሰነዘረ ይገልጻሉ፡፡ በወቅቱ አባገዳ ደንቦባ የሁለቱ ድንበር በሆነው (የጨጩ ወንዝ) ላይ በመሄድ ባንድራ እንደተከሉና ከሁለቱም ወገን ያን ጥሶ ጥቃት እንዳላደረሱ መረጃ አቀባዮቹ ገልጸውልኛል፡፡

ይሁን እንጂ የቃሉ ወሰን የተቋሙ መገኛ ብቻ ሳይሆን በስሩ ያሉ ጎሳዎች ወሰን እንደሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል የገዳዎች ወሰንም እንዲሁ የተቋማቸው ዙሪያ ብቻ ሳይሆን በስራቸው የሚያስተዳድሩት ቦታና ህዝብ ማካተት አለባቸው፡፡ ስለዚህ የቃሉንም ሆነ የገዳን ወሰን ማክበር ካለባቸው ይህን ሁሉ ማካተት ነበረባቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል የጎንዶሮን ሙሉ ክዋኔ  በንጥል-ጥናት ከነትንተናው እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

### የጎንዶሮ ንጥል ጥናት-1

በጉጂ ኦሮሞዎች ዘንድ እርስ በርስ የሚፈጠር የግዲያ ወንጀል ግጭትን የማስወገድና የጎንዶሮ ከበራ ክዋኔ፡፡

> የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ (2001 ዓ.ም.) አንዱ የአጎታችንን ልጅ የሆነውን መሳሪያ ባርቆበት ባጋጣሚ ገደለው፡፡ እኛ ታዲያ ከነዚያ ሰዎች ጋር ተቀያይመን እያለን እነሱ ቶሎ ብለው ወደ አባቃሉ ገልማ ሄደው የተፈጠረውን አስረዱ፡፡ ጉጂ ደግሞ ጎንዶሮ ማለት ስላለበት ቃሉ ለእኛ(የሟች ቤተሰብ) በሽማግሌዎች «የሞተውም የእኔ፤ የገደለውም የእኔ ነው፡፡ ስለዚህ በሽማግሌዎቹ አማካይነት ጉዳዩን በመያዝ ጎንዶሮ በሉ» በማለት ደብዳቤ ጽፎ ላከ፡፡ እኛ አሁን ጎንዶሮውን ፈጽመናል፡፡ ነገር ግን የታረደውን ከብት ስጋ አላየንም፡፡ የጦስ መጣያ ገደል (bowwaa bitaa) የሚባል አለ፤ ምንድነው ይሄ ፉርፉርሳ የሚባልበት ቦታ፣ ከለዶ ቀበሌ ወዲያ የጦስ መጣያ ገደል፣ ለጦስ ማውጫ የታረደውን ከብት

የሚጣልበት ቦታ፣ ወደዚያ ወስዶ ነው የተጣለው። የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ተምሳሌተ ክዋኔ በቃሉ ተቋም (ገልማ) ውስጥ አይፈጸምም፤ ጎንዶሮ የራሱ የሆነ ቦታ አለው። ለዚህ ነው የፉርፉርሳ ጦስ መጣያ ገደል ላይ የተፈጸመው።

ከእኛ ወገን የሆኑት በሽማግሌዎች እየተመራን ወደ ጎንዶረሮው ቦታ አመራን። የገዳይ ወገን እንደዚሁ መጡና ማዶ ለማዶ አስቀምጠውን በመካከላችን ደግሞ ውሃ አለ። ከዚያ ሽማግሌዎች ከመሀል ሆነው፣ ነጭ መጋረጃ ጋርደው (ነጠላ ጋቢ) ከመሀል ተደርጎ፣ ጥቁር በግ መጣ። ጠጅ (ቦካ) መጣ። በጉን የሚያርድ ከሌላ ወገን የሆነ ሰው መጣ። ያን በግ አርደው፣ አንጀቱን አውጥተው እዚያ የተገኙትን ቤተሰብ ባጠቃላይ በእሱ ይተበተብና የታሰራል። ያ ቀድሞ የተጋረደውን መጋረጃ የሃይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎቹ ከቀረበው ጠጅ ላይ እንትፍትፍ (biifuu) እያሉ ይገልጡትና ቀድም ጀርባ ለጀርባ ቆመን የነበርነውን ወገኖች፤ ፍታቸውን አዙረው እንዲገናኙና እንዲሳሳሙ ተደረገ። ያን የታረደውን ከብትም አልተበላም፤ ያ ለጎንዶሮው የቀረበውን በግ ያረደው ሰው ነው ስጋውን ይዞት የሄደው። ምክንያቱም ጦስ የወጣበት አይደል? (mulqaa mitii?) ስለዚህ ያንን ጠጅ ብቻ እዚያው ጠጥተው፤ ጎንዶሮ ብለው ተለያየን። እነዚያ ሰዎች ለብዙ ዓመት ተሸክመውት የነበረውን ጭንቅ አውርደው ወደ እኛ ቤተሰብ በመምታት፤ በልተው፣ ጠጥተው ሄዱ። ከዚያ በኋ እኛም ተጠርተን እነስ ቤተሰብ ጋ በመሄድ እንደዚያው በልተን፣ጠጥተን ተመለስን። ከዚያ በኋላ እንደቀድሞው ሰላም ወርዶ አብሮ መኖር ተጀመረ። (6/7/2007 ዓ.ም. ኡዴሳ ዲራሞ ዱካሌ፣ ዕድሜ 36፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

### የጎንዶሮ ንጥል ጥናት-2

ሌላው አንድ የጉጂ ኦሮሞ ተወላጅ ሆን ብሎ፣ አስቦበት የራሱን ወገን አይገድልም። ነገር ግን ባጋጣሚ በተፈጠረ ጠብ፣ መሳሪያ ባርቆበት፣ ወይም አውሬ መስሎት በርቀት ተኩሶ ወይም በጦር ወግቶ ሊገለው ይችላል። በዚህ ጊዜ በመግደሉ በወኔ፣ በጀግንነት ስሜት አያቅራራም። በተከሰተው ጉዳይ በመደናገጥ እንደሚገልጽና ጉዳዩ ወደ አባቃሉ ወይም አባገዳ ደርሶ እንዴት የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራው እንደሚከናወን መረጃ አቀባዮቹ እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

አንድ ወቅት ማለትም ወደ 1978 ዓ.ም. ገደማ ነው። አቶ አዱላ ጫራቃ የሚባል ሰውዬ ነበር። በእጁ ጦር ይዞ ወደ ዳንጎ ቀ/ገ/ማ ጫካ ለጫካ እያቆራረጠ ከቢዮ ተነስቶ ይሄድ ነበር። የሆነ ሀሳብ ውስጥ ሆኖ ሲጓዝ በድንገት ገጫካው

ውስጥ የኮሽታ ድምጽ ይሰማና ደንገጥ ብሎ ይመለከት ጀመር፡፡ አሁንም ሲንኮሻኮሸበት ድምጹን በሰማበት አቀወጣጫ ጦሩን ይሰደዋል፡፡ ከዚያም የሚያቃስት ሰው ድምጽ ይሰማል፡፡ ከዚያም በስህተት ሰው እንደወጋ ተረዳ፡፡ ገዳዩ ጭንቅላቱን ይዞ፣ ጦሩን ጥሎ፣ ‹ጉድ ሆንኩ!፣ ወይኔ ጠፋሁ!፣ ኡ!-ኡ!- (nan bade! Uu..arrii..)› እያለ ይጮህ ጀመር፡፡ ከዚያ ያንን ጩኸት ሰምተን በአቅራቢያው የነበርነው ሁሉ ወደዚያ ሰው እንሮጥ ጀመር፤ ከዚያም እደደረስን ገዳዩን ይዘን እንዲረጋጋ አደረግነው፡፡ ያ የተወጋው ሰውዬ ድንገት የመትረፍ ዕድል ካለው ብለን የተወሰኑት ሄደው እንዲያዩት ተደረገ፡፡ ነገር ግን ተስፋ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ ገዳዩን ዞር እንዲል አደረግነው፡፡ ምክንያቱም በድንገተኛ ክስተቱ አንዳንድ መታገስ የማይችል የሟቹ ቤተሰብ ሊበቀል ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ደም መቃባቱን ያባብሰዋል፡፡

ስለዚህ ያ ሰው ጉማ ከፍሎ፤ ጎንዶሮ እስከሚባልና እስከሚታረቁ ድረስ እራሱን ይሸሸጋል፡፡ ከማንም ጋር ግንኙነት አይፈጥርም፤ እራሱን አግልሎ ይኖር ነበር፡፡ ከባለቤቱም ጋር አብሮ አይተኛም፡፡ ጸጉሩን፣ ጺሙንና ጥፍሩን አይቆረጥም፡፡ የቀን ልብሱንም አይለውጥም፡፡ በዚህ መልክ በጉዳዩ ማዘኑን ይገልጻል፡፡ በጣም ይሰቃያል፡፡ ስለዚህ ችግሩ እንደተከሰተ ይህን ጉዳይ ቶሎ ብለው ወደ አባቃሉ አደረሱ፡፡ ቃሉም ወደ ሟች ቤተሰብ ሽማግሌዎችን ለእርቅ ተያዙልኝ/ እሺ በሉኝ (naaf qabamaa) በማለት ይልካል፡፡ ሽማግሌዎቹም መልዕቱን በመያዝ አባቃሉ እንዲህ ብሏል በማለት ያቀርባሉ፡፡

የሟች ቤተሰብም የቃሉን መልዕክት እንቢ፣ አሻፈረኝ እንደማይባል፤ በባህሉም ሆነ በእምነቱ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ መልካም ነው፤ እሺ እንያዛለን (ለውይይት እንቀርባለን)፤ ነገር ግን ይህ የቤተሰብ ጉዳይ ነው፤ የጎሳ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ተማክረን መልሱን እንመልሳለን በማለት ይገልጻሉ፡፡ የተላኩትም ሽማግሌዎች ቀጠሮ በመያዝ ይመለሱና ለቃሉ የዋሉበትን ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

በቀጠሮው ዕለት በህዝብ በዓል ማክበሪያ ስፍራ (araddaa jilaa) ለመገናኘት ተቀጣጠሩ፡፡ ከዚያ የሟች ቤተ-ዘመድ ቀድመው በሀገር ሽማግሌዎች እየተመሩ ከቦታው ደረሱ፡፡ በመቀጠል የገዳይ ቤተ-ዘመድ እንዲሁ በተቃራኒ በኩል በሀገር ሽማግሌዎች እየተመሩ ከተዘጋጀላቸው ቦታ አስቀመጧቸው፡፡

ከዚያን በኋላ በቅድሚያ በባህሉ መሰረት ጸሎት ተደረገ፡፡ በመቀጠል ስለአሟሟቱ በደንቡ መሰረት ቅድመ ማጣራት ያደርጉ ገቡ፡፡ በመጀመሪያ አባገዳ ከሽማግሌዎቹ ጋር በመሆን ከሟች ቤተሰብ ‹እንዴት ነው የገደለው? ቂም፣ ጠብ ብጤ ነበራችሁ?› በማለት ያጣሩ ገቡ፡፡ የሟች ቤተሰብም ከዚህ በፊት ቂም ብጤ እንዳልነበራቸውና እንደጣሩትም ለዚህ የሚያደርስ ግጭት እንደነበሩ መለሱ፡፡ በማከል እንደ እኛ አስተሳሰብ ይህን ማለት የምንችለው፡፡ ነገር ግን ከእሱ ጋር ምን እንዳላቸው የምናውቀው ነገር የለም› አሉ፡፡ ከገዳይ ቤተሰብም ተጠየቁ፡፡ ገዳዩም በተናጥል ጠጠየቀ፡፡ እሱም የአጋጣሚ እንደሆነ ገለጸ፡፡ በሂደቱም ቀደም ሲል የነበራቸውን መልካም ግንኙነት፤ ተከባብረው እንደኖሩ ከሦስቱም ወገን ምላሽ ተደመጠ፡፡

የሟችም ቤተሰብ «እኛ እንኳን ምንም ዓይነት ችግር የለብንም፤ ስንገናኝ ሰላምታ ተጠያይቀን፣ ካለን ተገባብዘን ነው የምንለያየው፡፡» በማለት በተለያየ መልኩ ጠብ እንደሌለባቸው አስረዱ፡፡ ከዚያን በኋላ ለአባገዳም ሆነ ለሌሎች ታዳሚዎች ስለጉዳዩ ውይይት ለመጀመር መንገድ መክፈቻ አካሄድ ነው፡፡

አደጋውን ያደረሰው አንድ ሰው ቢሆንም ጦሱ (መዘዙ) የሁላቸውም እንደሆነ የገዳይ ቤተ-ዘመድ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ለግለሰቡ ሰላም መውረዱ፤ ለሁላቸውም እንደሆነ ስለሚረዱና በጎሳ ውስጥ አንድ ችግር ከደረሰ የመረዳዳት የቆየ ባህልም ስላለ፤ ለጉማ (የደም ካሳ) የሚሰጡትን ከብቶች በማዋጣት እየነዱ ይመጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለጎንዶሮው ከበራ ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ጥቁር በግ፣ ቦካ (የማር ጠጅ) እና ውሃ አቀረቡ፡፡

በመቀጠል ገዳዩ ቀደም ሲል ከቤተ-ዘመዶቹ ጋር አብሮ አልመጣም ነበር፡፡ ከበስተኋላ በሌሎች ሽማግሌዎች ተከልሎ እሱ የኋልዮሽ ዞሮ ወደ ጎንዶሮው ስፍራ አመጡት፡፡

አጠቃላይ አካሄዱን ስንመለከት፡- በመጀመሪያ አባገዳ ከመማክርት አባላቱ ጋር ስለግድያው ሁኔታ ካጣሩ በኋላ፤ ‹ለነገሩ ጉጂ ጉጂን አይገድልም፡፡ ነገር ግን ያጋጣሚ ነገር ሆኖ ይህ ከተከሰተ፤ «ዳኑ» ነው፡፡ ሁለቱም ወገን አንድ ዘር፤

አንድ ጎሳ ናቸው እኮ!፡፡ ስለዚህ መቼም ደም ፈሷል፡፡ ገዳዩም የእኔ፤ ሟቹም የእኔ ነው፡፡ ስለዚህ ጎንዶሮ ሊባል ይገባል› አሉ፡፡

ከዚያም በቦታ ላይ ከብቶቹን ማምጣታቸው ቢታዩም ለደንቡ ያህል፤ አምጥተው እንደሆነ ተጠየቁ፡፡ የገዳይም ቤተሰብ ብድግ ብሎ ‹‹አዎ! ይቅር በሉን! ከብቶቹም ቀርበዋል፤ ተቀበሉን›› አሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም ‹‹እግዚኣብሔር ይሁንላችሁ!›› አሉ፡፡ ሽማግሌዎቹ በመቀጠል የሟችን ቤተሰብ ደግሞ ‹‹በሉ በባህላችን መሰረት የበደለ ይክሳል፡፡ ስለዚህ ከብቶቹን ተቀበሉን›› በማለት ጠየቁ፡፡ የሟችም ቤተሰብ እርስ በእርስ ‹‹ሰማችሁ አይደል?›› በማለት የማረጋገጥ ያህል ተጠያየቁ፤ ሌሎችም በተራ ‹‹አዎ! ሰምተናል፡፡›› አሉ፡፡ በመጨረሻም ለሽማግለዎቹ ‹እናንተ ካላችሁ፤ መቼስ ምን ይደረጋል፡፡› በማለት የቀረበውን ሀሳቡ መቀበላቸውን ገለጹ፡፡

ቀጥሎ የገዳዩን ጸጉርና ጺሙን በመላጨት፤ ጥፍሮቹን በመቁረጥ፤ በላዩ ላይ የከረሙትን አልባሳት አውልቆ በመጣል፤ ወደ ጎንዶሮው መቼት ይወሰዳል፡፡ ከዚያም ለጎንዶሮው ክዋኔ የመጣውን ጥቁር በግ፣ ቦካና ውሃ ተይዞ ይኬዳል፡፡ በጉን በገዳዩ ጭንቅላት ላይ ለሁለት ሰዎች በማንጠልጠል ይታረዳል፡፡ በግ ያረደው ከጉጂ ኦሮሞ ውስጥ ያልሆነ ሰው ነው፡፡ ምክንያቱም ጎንዶሮ በራሱ ይህ ግጭት በዚህ ይብቃ፤ ዳግም አያምጣው የሚል ሀሳብ ያለው ስለሆነ፤ በጉም የጦስ ማውጫ በግ በመሆኑ፤ ያን ንኪኪ ከዚያው ለማስቀረት ከማሰብ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ከዚያም በላዩ ላይ በፈሰሰው የበግ ደም ይታጠባል፡፡ በመቀጠል በቦካው (ጠጁ) ደሙን ያስለቀቁታል፡፡ በወቅቱም ቃሉ ከአባገዳውና ሽማግሌዎቹ ጋር በመቀባበል ‹እንደዚህ ማር ሽተት!፣ ዳግም እደዚህ ዓይነት ክስተት አይግጠምህ፣ እንደዚህ ማር ጣፍጥ፣ ከወገንህ ያስማማህ!› እያሉ ይመርቃሉ፡፡ በመጨረሻም በንጹህ ውሃ ያንን ሰውነቱን ያፀዱታል፡፡ ከዚያን በስተመጨረሻ ላይ የተዘጋጀለትን ንጹህ ልብስ በማልበስ ሁለቱን ወገን ወደ ማቀራረቡ ምዕራፍ ይታለፋል፡፡

እስከዚህ ደረጃ ድረስ የማችና ገዳይ ቤተሰብ ፊት ለፊት አልተገናኙም፡፡ ስለዚህ ሁለቱንም ወገን ለማቀራረብ በመጀመሪያ፡-ሽማግሌዎች ነጭ ነጠላ ጋርደው

የሚችን ወገን በአንደኛው አቅጣጫ፣ የገዳይን ወገን ደግሞ በተቃራኒው አቅጣጫ አቆሙ። በመቀጠል ገዳዩን ሽማግሌዎች ከልለው ከእሱ ወገን ተርታ አስገብተው አቆሙት። ከዚያም በእሱ ትይዩ በስተጀርባ የሚቹን የቅርብ ዘመድ አቆሙ። በመቀጠል ቅድም ከታረደው የጎንዶሮ በግ ስጋ ውስጥ አንድ የጎድን አጥንት በማውጣት በእሳት ተጠብሶ መጣ። ከዚያም ያን አጥንት በቅድሚያ ለገዳዩ ተሰጠው። እሱም አጥንቱን በጥርሱ እየነከሰና ወደመሬት እንትፍ እያለ፤ በእሱ ትይዩ ከኋላ ላለው የሚች ዘመድ ስሙን እየጠራ «ከኋላዬ የለህም» በማለት ያንን አጥንት ከነጠላው በላይ በኩል እጁን በመዘርጋት ይሰጠዋል። ያኛውም ሰው በተራው «ከኋላህ አለሁ» በማለት የጎድኑን አጥንት ነክሶ፤ ወደ መሬት በመትፋት መልሶ ይሰጠዋል፤ እንዲህ እየተባባሉ ለሦስት ጊዜ ሳይተያዩ ተቀባበሉ። በመቀጠል ሽማግሌዎቹ ከመሀል እንደቆሙ፤ የሁለቱም ወገን ቀኝ እጆቻቸውን የኂሊት በመዘርጋት ለሽማግሌዎቹ አሲያዙ፣ ከዚያም ሽማግሌዎቹ በመካከላቸው ተጋርዶ የነበረውን ነጠላ በማንሳ፣ ተቃራኒዎቹን እጅ ለእጅ አያያዙ። ከዚያም ዞረው እንዲተቃቀፉና እንዲሳሳሙ ተደርጎ፤ እርቁ ወረደ። (አቶ አዱላ ዋሬ፣ አባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ ጉሚ 5/3/2006 ዓ.ም.)

የታረደው በግና የታረደበትም ብላዋ ወደ ጦስ ማውጫ ገደል (bowwaa bitaa) ይጣላሉ። ለዚህ ከበራ እርዱን ለፈጸመው ሰው ደግሞ ገንዘብ እንደሚሰጠው ለመረዳት ችያለሁ። እንደ Salamone, (2004፡141) ገለጻ ይህ የሚያመለክተው ለከበራ የሚዘጋጁ ምግቦች በዝግጅቱ ማንን እንደሚያሳትፍና ማንን ደግሞ እንደማያሳትፍ፣ እንዲሁም የትኛው የምግብ ዓይነት ለማን እንደሚሰጥና እንዴት እንደሚሰጥ ነው።

በሌላ በኩል ከሁኔታዊ አውድ አኳያ የተመለከትነው እንደሆነ ማህበረሰቡ ይህን የጎንዶሮ ከበራ የሚከውነው በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? የሚለውን ይመልስልናል። ይኸውም፡- ማህበረሰቡ በባህሉ የተወሰነ የአንድ ባህሪ ወይም ገጠመኝ መግለጫ የሆነ፤ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት የሚከናወንበት አውድ ሲለሆነ ነው፤ እሱም የጎንዶሮ ከበራ። በዚህ ውስጥ መቼቱ፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ ክዋኔውን የሚገዙት የተለያዩ ህግጋት፣ በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ተግባቦት፣ የክዋኔው አተረጓገም የሚከናወንበት መርህና የመሳሰሉት ይካተታሉ።

ይህን የጎንዶሮ ከበራ ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አተያይ ስንመለከተው የሰው ልጅ በማህበራዊ ተራክቦ ውስጥ በሚያደርገው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ውስጥ ግጭት ሊኖር እንደሚችል፣ ግጭቶቹ ደግሞ ከቀላል እስከ ከባድ ማለትም፡- የሰው ነፍስ ማጥፋትና የንብረት ውድመት ሊስከት መቻሉን፣ ከዚያም አጥፊው የጥፋተኝነት ስሜት አድሮበት መሰደዱን፣ ተበዳዩ ደግሞ ቂም ቋጥሮ የመበቀል አዝማሚያ መፍጠሩን በማሰብ፣ በመጨረሻም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጎጂው የጉጂ ኦሮሞው መሆኑን ተገንዝበው የጎንዶሮ ከበራን እንዳዋቀሩ ያሳየናል፡፡ ይህ ሀገረሰባዊ ዕውቀት በዋናነት በቃሉ ሲገለጹ ይታያሉ፡፡ ይኸውም፡- ቃሉ የገዳና ስልጣን ስያጸድቅ በምርቃት መልክ ምክር አዘል መልዕክቶቹ ውስጥ ይንጸባረቃሉ፡፡ ይኸውም፡- «...ጉጂ ጉጂን አይገድልም፣ ሳያቅ ከገደለ (danuu)፣ ያን አለማወቁን (danuu sana) ተረዱለት...» የሚሉ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል ከላይ ከተመለከትነው የጎንዶሮ ክዋኔ፣ ቃሉም ሆነ ገዳ ወደ ሚች ቤት ሽማግሌዎችን እርቅ ለማስጀመር ሲልኩ «ሚቹም የእኔ፣ ገዳዩም የእኔ ነው፡፡» በማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ልክ

«ሀዘንሽ ቅጥ አጣ፣ ከቤትሽ አልወጣ፣
የገደለው ባልሽ፣ የሞተው ወንድምሽ፡፡» እንዲሉ ማለት ነው፡፡

ምክንያቱም ሁለቱም ወገን የጉጂ ናቸው፤ በሌላ አባባል ሁለቱም ወገን የቃሉና የገዳ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቃሉም ሆነ ገዳ ለሁለቱም አንድ መሆኑንና እነሱንም በማስማማት አንድ ለማድረግ የተጠቀሙባቸው አገላለጽ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ለክዋኔዎቹ ማስፈጸሚያ ስነ-ልቦናዊ እርካታን በሚፈጥር መልኩ ለባህላዊ ቁሶቹ ተምሳሌታዊ በማድረግ በገዳይ፣ በሚች ቤተሰብ፣ ለጎንዶሮ ከበራ በቀረቡ መከወኛዎችና ድርጊቱን በሚከውኑት መካከል ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች እንዲከወኑ ተደርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከበራ ቃላዊ ያልሆነ፤ ነገር ግን ልክ እንደ ስነ-ልሳናዊ ጉዳዮች በርከት ያሉ ትእምርቶች ያሉበትና እያንዳንዱ ትእምርት ደግሞ ትርጓሜ የሚያገኘው በበቀለበት ባህል ባለው የምግባርና የትውፊት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ Bell, (1997፡44) ትገልጻለች፡፡

ስለዚህ እነዚህን ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም አተያይ ብንመለከት፡- በመጀመሪያ ደረጃ የክዋኔው ማጀቢያና ማስፈጸሚያ ቁሳዊ ባህሎችን በኦሮሞ ዘንድ ጥቁር የጥሩ ነገር ተምሳሌት ነው፡፡

ይህ ማለት በጉጂ ኦሮሞ የዓለም አተያይ ‹ዋቃ ጉራቻ›፣ ጉጂ ‹ጉራቻ›፣ ‹ቢሻን ጉራቻ› በማለት ንጹህነትን ወይም ጥርት ያለ ያለ የሚለውን ፍች እንዲይዝ አድርገው ሲጠቀሙበት እናያለን፡፡

ለአብነት ያህል፡- አንድ የጉጂ ኦሮሞ ‹‹እኔ ጉጂ ‹ጉራቻ› ነኝ፡፡›› ካለ የቀለሙ ተምሳሌትነት እራሱን ንጽህ ጉጂ (typical) ነኝ ለማለት የተጠቀመበት አባባል ነው፡፡ የበጉ መልክ ጥቅር የሆነበት ጥቁር ጥሩ ተስፋን፣ ለደስታ ማብሰሪያነት እንደሚወክል ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከበራ የሚያመለክተው ሰውነቱ በደም መቆሸሹን (የሰው ነፍስ በእጁ መጥፋቱን) ሲሆን፤ ይህ የሰው ደም ደግሞ የሚጠራው፤ በበጉ ደም መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንደ ኦሮሞ አተያይ ደም አንድም መጥፎ ዕድልን ማሳለፊያ ተደርጎ ይታመናል፡፡ ሌላው መስዋዕት በሚቀርብበት ወቅት ደሙን ወደ ላይ ሲረጭ ለእግዚአብሔር እንደመስዋዕት ይቆጠራል፤ ለሰው ደግሞ ደሙ ተመልሶ ሲወርድ እንደምርቃት ወይም በረከት ይቆጥሩታል፡፡

ስለዚህ ለገዳዩ ተስፋንና ጥሩ ስሜትን ያጎናጽፈዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመቀጠል በቦካው ያንን ደም የሚያጸዱት ተምሳሌታዊ ክዋኔ ደግሞ ቦካ በጉጂዎች ዘንድ አበባን (daraara)፣ ጣፋጭነትን (Mi'aa) ፣ መልካም መዓዛን (hurgaa) ይወክላል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል ነፍስ በማጥፋቱ መልካም ስሙ፣ ምግባሩ፣ ጉጂነቱ ሁሉ ጠፍቶ ነበር፡፡ ከማህበረሰቡም ተገልሎ ነበር፡፡ ታዲያ በዚያ ቦካ ሲያጥቡት በቃሉ ወይም በአባገዳና ሽማግሌዎቹ በመቀባበል እንደዚህ ማር ሽተት!፣ ዳግም እደዚህ ዓይነት ክስተት አይግጠምህ፣ እንደዚህ ማር ጣፍጥ፣ ከወገንህ ያስማማህ ወ.ዘ.ተ. እያሉ ይመርቁታል፡፡ ከዚያን በኋላ ይህ ክዋኔ የቀድሞውን መልካም ስምና ምግባር የማስመለስ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመጨረሻ በውሃ እንዲታጠብ የሚደረገው ተምሳሌታዊ ክዋኔ ደግሞ በጉጂ ኦሮሞ አተያይ ውሃ የንጽህነት ወይም የምርጥነት ገላጭ ነው፡፡ ንጹህ ውሃ ለማለት ጥቁር ውሃ (bishaan gurraacha) ይላሉ፡፡ ባጠቃላይ ውሃ ከፈጣሪ የተሰጠ፤ ንጹህ ነገር እንደሆነ በጉጂዎች ይታመናል፡፡ ስለዚህ በስተመጨረሻ በውሃ መታጠቡ ገዳዩ ከአሁን በኋላ ከሀጢያትህ ነጽተሃል እነደማለት ነው፡፡ እነዚህ ከበራዎች የማንጻት ክዋኔዎች ናቸው፡፡ ከዚያ አዲስ ልብሶቹን ለብሶ ወደሚቀጥለው ክዋኔያዊ አውድ ይሸጋገራል፡፡

በሚቀጥለው ክዋኔ የተገለጸው ተጋርዶ የነበረው ነጭ ነጠላ ደግሞ በመካከላቸው ችግር ተከስቶ መለያየታቸውን የሚያመላክት ነው፡፡ ምክንያቱም በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የቀለሙ ተምሳሌት የሚመሰለው በአመድ፣ በዱቄት፣ በረሃብና እርዛት ነው፡፡ ባጠቃላይ የመጥፎ ነገር መገለጫ ተምሳሌት እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ከግዲያው ዕለት አንስቶ በሁለቱም ወገን መካከል ሰፍኖ የነበረውን የሀዘን ድባብ፤ በዚያ ነጭ ነጠላ ይመሰላል፡፡ ነገር ግን ይህ ተምሳሌትነት አንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢ እንደ ጥሩ ነገር የሚታይበት ሁኔታም አለ፡፡ ይኸውም፡- በምርቃት መካከል <<adii nyaadhu, adii uffadhu!>> ቢባል፤ አቻ ትርጉሙ ‹‹ነጭ ልበስ፣ ነጭ ብላ!›› እንደማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ነጭ ልበስ ሲባል ለጋቢ፣ ለእጀ ጠባብና የመሳሰሉ ከጥጥ የሚሰሩ

ባህላዊ አልባሳትን ሲሆን፤ ነጭ ብላ የሚለው ደግሞ ደግሞ ለጮማ፣ ነጭ ጤፍና የመሳሰሉትን ይወክላል።

ሌላው ከክዋኔያዊ ተምሰሌት አኳያ ያየን እንደሆነ ገዳዩን ወደ አርዳ ጅላ ሲያመጡት ከለለውት፤ ጀርባውን አዙሮ ነው። ይህ የሚያመለክትው በሰራው ሀጢያት የተነሳ ከቤቱ፣ ከቤተሰቦቹና ከማህበረሰቡ ተገልየ ነው ያለሁት፤ በዚህም ምክንያት ተጎሳቁያለሁ፤ ውስጤም በጣም ተጎድቷል የሚል ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው። ይህም በጀርባው ሲመጣ እሱ ሳይሆን ሁሉም ሰው በእሱ ላይ ጀርባውን እንዳዞሩበት የሚያመላክት ነው። ምክንያቱም ጉጂ ጉጂን አይገድልም። ነገር ግን ባጋጣሚ ከገደለ የጎንዶሮ ከበራ ካልተፈጸመ በቀር ገዳዩ እንደረከሰ ሰው ይቆጠራል። ይኸውም የሰውን ደም የሚያስፈስስ እርኩስ መንፈስ ጋር አብሮ እንዳለ ይታመናል። ይሁን እንጂ በቃሉ ሃይማኖታዊ አስተምሮት አንጻር ባጋጣሚ የተፈጠረ ክስተት (danuu) መሆኑ ከታወቀ በጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ ሊፈታ ግድ ይላል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የሁለቱን ወገን አቋቋም ደግሞ ጀርባ ለጀርባ ተሰጣጥተው መቆማቸው፤ በመካከላቸው አለመግባባት እንዳለ አመላካች ይህን ሀሳብ ከሚያጠናክሩ የጉጂ ኦሮሞ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ውስጥ አንዱ «ጀርባውን ሰጠኝ።» (dudda natti gale.) የሚለውን ከተመለከትን ተቀይሞኛል/ፊት እየነሳኝ ነው የሚል ፍች ይኖረዋል። ስለዚህ ያ ችግሩ እስከሚፈታ ድረስ እንደደመኛ ስለሚተያዩና በሟች ቤተሰብ ውስጥ የእልህና ቁጭት መንፈስ ሰላለ አንዳንድ ግጭቶች እንዳይጫሩ፣ የሟች ቤተሰብ ልጃቸውን አስታውሰው ሆድ ሲብሳቸው፤ የሞተው ሰው ነውና በክፉ ዓይን እንዳይተያዩ በማሰብ ነው፡ ፡ ከዚያ ጀርባ ለጀርባ እንደተሰጣጡና ነጠላው (ችግሩ መካከላቸው) እያለ ያን የተጠበሰ የጎድን ስጋ፤ ከተምሳሌታዊ አተረጓገም አተያይ ስጋ ዝምድናን ይወክላል። የመጠበሱ ወይም እንዲበስል የመደረጉ ተምሳሌት ደግሞ ጉዳዩ ወይም የዕርቁ ሂደት መስመሩን መያዙን፣ ወደ መቋጫ ደረጃ መድረሱን አመላካች ነው። የጉጂ ኦሮሞ ‹‹Dubbiin dheedhii.›› ካለ ቀጥተኛ ትርጉሙ ‹‹ነገሩ ጥሬ ነው።›› እንደ ማለት ነው። ይኸውም፡- ነገሩ ምንም ፈር አልያዘም ለማለት ያገለግላል። በሌላ በኩል የጎድኑ አጥንት የሚወክለው አንድ ወገን ለመሆናቸው ነው። ባጠቃላይ የክዋኔው ተምሳሌት በመካከላቸው የተፈጠረው ክስተት በዘመዳሞች መካከል በመሆኑ አቅልለው ማየት እንዳለባቸውና ወደ ስምምነት ደረጃ መቃረባቸውን አመላካች ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አጥንቱን በመንከስ እንትፍ የማለቱ ክዋኔ ደግሞ ሰው እንዴት ስጋውን (ዘመዱን) ይነክሳል (ይገላል)፤ እርም ነው የሚለውንና ከአሁን በኋላ አለመፈላለጋቸውን ማሳረጊያ ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው። ገዳዩ ስሙን

እየጠራ ሶስቴ ‹‹የለህም፡፡›› እያለ አጥንቱን ሲሰጠው የሟች ወገን ‹‹አለሁ›› እያለ መቀበሉ ደግሞ አደጋው ከተከሰተበት ዕለት አንስቶ ተቃራኒ የነበሩ ወገኖች፤ ከአሁን በኋላ አንዱ አንዱን ሲጠራው፤ማለትም ለችግሩ እንዲደርስለት ሲፈልገው ቂም ይዞ ችላ እንደማይለውና የድሮ ትብብራቸውንና መደጋገፋቸውን ማስቀጠያና ማረጋገጫ ከበራ ነው፡፡ የከበራ ግብም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠርን ግጭት ማረጋጋት እንደሆነ (Myrvold, 2007,19) ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አንጻር የተመለከትን እንደሆነ በተፈጠረው ግጭት አጋጣሚ ተበለሻሽቶ የነበረውን ማህበሪዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነታቸውን በዚህ ከበራ ያድሱበታል፡፡

ከዚያም ያን የመጥፎ ክስተት ትእምርት የሆነውን ነጠላ ከመካከላቸው ተገልጦ መነሳቱና እጅ ለእጅ እንዲጨባበጡ መደረጉ፣ እርስ በርስ ዞረው እንዲሳሳሙ የሚደረገው ተምሳሌታዊ ክዋኔ የሚያመለክተው ችግሩ ከመካከላቸው ተወግዶ፣ እንደድሯቸው ሆድ ለሆድ ተገናኝተውና ተያይዘው ለመቀጠል ቃል መግባታቸውን ማሳያ ነው፡፡

በመጨረሻም ይህንኑ ሀሳብ ለማጠናከሪያነት ቃሉ ወይም ገዳና ሽማግሌዎቹ በቦካው እንደማሩ ጣፍጡ፣ እንደ አበባው ሽተቱ እያሉ በቦካው እንትፍትፍ (biifee) እያሉ ሁለቱንም ወገን እያቀመሱ ይመርቃሉ፡፡ ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Waaqa qaalluu, Waaqa gadaa, | የቃሉ አምላክ፣የገዳ አምላክ፣ |
| Ee Waaqa me'ee bokkoo, | የሚኤ ቦኮ አምላክ፣ |
| Ati nu nageessi! Ardaa nageessi! | አንተ ሰላም አርገን! |
| Araddaa nageessi! | ህዝቡን ሰላም አርግልን! |
| Balaa akkasii lammuu isinitti hin deebi'in, | እንዲህ ዓይነቱ አደጋ ዳግም አይግጠማችሁ! |
| Jaarsaatti hin deebisin, | በሽማግሌው አይመልሰው! |
| Jaartiitti hin deebisin, | በአሮጊቷ አይመልሰው! |
| Kaa'imaatti hin deebisin, | በወጣቱ አይመልሰው! |
| Araddaatti hin deebisin, | በህዝቡ አይመልሰው! |
| Akka nuuf toltane isiniif haa tolu, | ለእኛ እንደተመቻችሁ ለናንተም ይመቻችሁ! |
| Bishaaniifi Marga ta'aa! | ውሃና ሳር ሁኑ!፣ |
| Aannaniifi Damma ta'aa! | ወተትና ማር ሁን!፣ |

Kan wal-jaallattan, kan wal-fuutan ta'aa! የምትዋደዱ፣ የምትጋቡ ያድርጋች!
Wal-fuutanii kan hortanu ta'aa! ተጋብታች የምትረቡ ሁኑ! ብዙ ሁኑ!...

እያሉ ይመርቃሉ፡፡ ሁለቱም ወገን አሜን እያሉ ምርቃቱን ይቀበላሉ፡፡ (አባገዳ ሀልቻዬ፣ አቶሞኮና ናጋኦ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ በ25/11/2007 ዓ.ም. እና አቶ ብርሃኑ ንጉሴ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም. ጉጂ ዞን፣ ቦሬ ከተማ ነዋሪ)

ይህ ከበራ የሁለቱን አንድነት ከማጠናከር አኳያ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ይኸውም በዚህ ክዋኔ ላይ በመጀመሪያ ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አንጻር አውዱን የተመለከትን እንደሆነ ይህ የጎንዶሮ ከበራ የሚፈጸምበት ተቋማዊ ትርጉሙ ግጭትን ለአንዴና መጨረሻ ጊዜ መፍቻ ቦታ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ ክዋኔ ውስጥ የአባቃሉና አባገዳ ማህበራዊ መዋቅራቸውን ያየን እንደሆነ በባህሉም ሆነ በሃይማኖቱ ያላቸው ደረጃና ተሰሚነት፤ ምን ያህል ተፅዕኖ ፈጣሪ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የማሳረጊያው ምርቃት ሰላም ያድርጋችሁ!፣ ይህን ዓይነት ክስተት ዳግም አይመልሰው!፣...ሁለቱን ወገን አንድ እንዲያደርጋቸውና እንዲያስማማቸው ደግሞ ውሃና ሳር ሁኑ! ወተትና ማር ሁኑ!፣ የምትዋደዱ፣ የምትጋቡ ያድርጋች!፣ተጋብታች የምትረቡ ሁኑ! ብዙ ሁኑ!... የሚሉትን ስንመለከት ተምሳሌታዊ ይዘት አላቸው፡፡ ይኸውም፡- ያንዱ መኖር ለሌላኛው መኖር እንደሚያስፈል፣ተጋብተውና ተዋልደው አንዱ ከሌላው ጋር በደም፣ በስጋ/ በዝምድና የሚተሳሰሩ ያድርጋችሁ የሚለው ዝምድናቸውን እንዲያጠናክሩና ከአሁን በኋላ መልካም መልካሙን እንዲያስቡ የሚያደርግ ነው፡፡

በመጨረሻም ወደየመጡበት አቅጣጫ ተሰነባብተው ይሄዳሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል በፕሮግራም የገዳይ ቤተሰብ ድግስ ብጤ አዘጋጅቶ የሟቾቹን ቤተሰብ ይጋብዛሉ፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ የሟች ቤተሰብ ደግሶ የገዳይን ቤተሰብ ይጠራሉ፡፡ በዚህ መልኩ ሰላማቸውን ወደ ቀድሞው ደረጃ ያሸጋግሩታል፡፡ ይህ ደግሞ ከከበራ የማህበራዊ ትስስር ማጠናከሪያ ፋይዳ ውስጥ አንዱና ዋንኛው ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ገዳዩም ሆነ የእሱ ቤተሰቦች ከሟቹ ቤተሰብ የበቀል እርምጃ ይደርስብናል የሚል ስጋት አይገባቸውም፡፡ ነገር ግን ይህን ጉዳይ በዘመናዊ የህግ መዋቅር ቢፈታ ኖሮ ገዳዩ ከሟች ቤተሰብ የሚበቀለው ሰው ባይኖርም ገና ለገና ይበቀሉኛ ይሆን የሚል በእሱና በቤተሰቡ ውስጥ ስጋት ያድርባቸዋል፡፡ በጎንዶሮ ስርዓት የተከናወነው ግን እንዲህ ያለ ጭንቀትን የሚያቃልል መሆኑ የጎንዶሮ ከበራን ስነ-ልቦናዊ ፋይዳን ያመላክታል፡፡

### 6.2.2.2. የምልጃ ማሳረጊያ ጎንዶሮ

ሌላው የጎንዶሮ ዓይነት የምልጃ ማሳረጊያ የጎንዶሮ ከበራ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው የግልቢያ (የኮርቻ) ፈረሱ እየሞተ ሊያስቸግረው ይችላል። ለዚህም የጎንዶሮ ከበራ ይከወናል። ሌላው አንድ ሴት ልጅ እየወለደች፤ የተወለደው ልጅ የማያድግላት ከሆነ፤ ልጅ ወልዳ እንዲያድግላት ሲፈልጉ ለመስዋዕት የሚሆን ከብት በማዘጋጀት፣ ሃይማኖቱና ባህሉ በሚፈቅድላቸው መንገድ ወዩ (Woyyuu) በመጥራት ተለማምነው ዲባሴ (ni dhibaafatu) ያደርጋሉ። እንደ መረጃ አቀባዬ ጠጅ (በካ) በመጣል፣ ታዋቂ ሽማግሎዎችን ጠርቶ፤ ከብት አርደው፤ እነዚያን ባልና ሚስት እንዲመረቁ ይደረጋል። ይህ ሰው የአብራኩን ክፋይ አጥቷል። ስለዚህ የአብራኩን ክፋይ (ልጅ) እንዲያገኝ ይመረቃል፤ ወዲያው ደግሞ እንደዚያ ዓይነት አስደንጋጭ ክስተት ካሁን በኋላ እንዳያጋጥመው የጎንዶሮ ከበራ ይፈጸማል።

ድሮ ሰዎች ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ማለትም፡- ድርቅ ሲከፋ፣ የከብቶች በሽታ ከመጣ ወንዝ ወርደው/ይዘው/ (malkaa qabatan) እግዚኣብሔርን እንደሚለማመኑ ከመረጃ አቀባዬ ለመረዳት ችያለሁ። ይኸውም ወደ ወንዝ ሲሄዱ ቡናና ቅቤ ተይዞ ነው። ከዚያ ወንዝ ወርደው እግዚኣብሔር በመለማመን ዝናብ እንዲዘንብ የማድረግ ተሰጥኦ እንደነበራቸው ይገልጻሉ። ጉጂሚ ወንዝ ወርዶ እግዚኣብሔርን ይለማመናል? የእኔ ጥያቄ ነበር። እሳቸውም «አዎ! ጉጂሚ ወንዝ ወርዶ ይለማመናል። ከዚህ በተጨማሪ በመንቲያ መንገድ ሳይም (woldeena irratti) ወጥቶ ይለማመናል።» በዚህ መልክ በድርጊት እየተቀባበሉ እዚህ እንዳደረሱና በአሁኑ ትውልድ ችላ ባይነት የተነሳ ወደፊት የመቀጠሉን ስጋት እንደገባቸው ገልጸውልኛል። (አቶ ብርሃኑ ንጉሴ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም. ጉጂ ዞን ቦሬ ከተማ ነዋሪ)

በክዋኔው ወቅት ስለጉዳዩ በጥልቀት የማጣራት (qortuma) ሂደት ይከናወናል። በጉጂ ኦሮሞ አራዊቶች የራሳቸው ክልል አላቸው። አለአግባብ አይገደሉም። እንደ ጉጂ ኦሮሞ እነሱ የአራዊቶቹንና የአዕዋፋትን ድምጾቻቸውንየመረዳት፣ በሌላ በኩል አራዊቶቹና አዕዋፋቱ ደግሞ የእነሱን ቋንቋ ይረዱናል የሚል እምነት አላቸው። ስለዚህ አንዱ አንዱን ሳያጠቃ ተስማምተው የመኖር ልምድ አላቸው። ነገር ግን ችግሮች ሊፈጠሩ የሚችሉት ይህን የተፈጥሮ ስምምነት ሲጣስባቸው እንደሆነም ያምናሉ። ስለዚህ ከቤተሰቡ ውስጥ ወይም ከማህበረሰቡ ውስጥ ጥሰት የፈፀመ ካለ ይጣራል። በሂደቱም በማወቅም ይሁን ያለማወቅ የተፈጠረውን ስህተት ከታወቀ በኋላ ለጎንዶሮው ክዋኔ የሚያስፈልጉ ነገሮች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

ለምሳሌ ከላይ እንደተገለጸው አንድ አውሬ ማለትም ጅብ ወይም አንበሳ ለብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ እየመጣ ከብቶቹን ከበረትም ሆነ ከጉረኖ የሚያጠቃበት ከሆነ፤በመጀመሪያ ስለጉዳዩ በጥልቀት የማጣራት (qortuma) ሂደት ይከናወናል። እነሱን ያለ አግባብ ተተኗክለው ከሆነ፣ አለአግባብ ከመኖሪያቸውን አፈናቅሏቸው ከሆነና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ያጣራሉ። በመጨረሻም ይህ ክስተት እንዳይደገም፣ አውሬውም ወደ መኖሪያው እንዲመለስ፣ ዳግም አንደርስብህም፤ አንተም አትድረስብን ተብሎ የጎንዶሮ ከበራ እንደሚያከናውኑ ገልጸውልኛል።

በማንኛውም ከበራ ወቅት የሚከናወን እርድ ሞራው ይታያል። ከዚያም ስለተከወነው ሁኔታ ሞራ አንባቢዎቹ ከሞራው በማየት የሚሉት አላቸው። ይኸውም መስዋዕቱ መሳካቱን፤ አሊያም አለመሳካቱን በመተንበይ ተሰጦኣቸው ይናገራሉ። ካልተሳካ ሌላ እንዲታረድ ይደረግና እንደገና ይታያል።

## 6.3. የሁሉቃ ከበራ

ሁሉቃ (hulluuqa) ከቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ አንድ ክዋኔ ነው። የክዋኔውም ሆነ የመከወኛ ቁሳዊ ባህሉ መጠሪያ ስም ሁሉቃ ይባላሉ። ሁሉቃ በጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ ዕውቀት የተዋቀረ የከበራ መቸት ነው። አዘገጃጀቱም በዋናነት በቃሉና በገዳ ተቋማት አቅራቢያ ባሉ ቦታዎች፣ግራና ቀኝ በቆሙ እንጨቶች፣ በሀረግ ከአንዱ አቅጣጫ ወደሌላው ተሻግሮ የታሰረ ነው።ለሰው መጠኑ ከፍታው ረጅም የሚባል ሰው ሊያሻግር የሚችል፣ወደጎን ደግሞ ብዙ ሰው በአንድ ላይ ሊያሳልፍ በሚችል መልኩ የሚዘጋጅ ሲሆን፤ለከብቶች ደግሞ ከፍታው ከብቶቹን በማይነካ መልኩ ከፍ ተደርጎ፣ ወደጎን ደግሞ ብዙ ከብቶች ሊያሳልፍ የሚችል መሆን እንዳለበት ለማየት ተችሏል። ወደ ጎን የሚታሰረው የዲኪቻ ሀረግ ወይም ቀርከሃ ሊሆን እንደሚችል ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ።

በአላብዱ ጎሳ አካባቢ ዲክቻ (dikicha) የሚባል ሀረግ አለ። ይህ ሀረግ ተቆርጦ፣ ግራና ቀኝ በቆሙ እንጨቶች ላይ በማሰር የሚዘጋጅ ሃይማኖታዊ መቼት ነው። ከዚያ በስሩ በመሽሎክ እርኩስ መንፈስንና በሽታን የማስወገድ ከበራ ሁሉቃ በመባል ይታወቃል። ያነጋገርኳቸሁ የሀገር ሽማግሌዎች እንደሚሉት ይህን ከበራ የሚያካሂዱት ለቅድመ-በሽታ መከላከል እንደሆነ ነው። ወደ ኡራጋ አካባቢ ደግሞ ቀርከሃ በመሰንጠቅና ግራና ቀኝ በቆሙ ጉዱባ የሚባል የሚመር እንጨት ላይ በማሰር እንደሚሾልኩ መረጃ አቀባዩ ይገልጻል። በሚሾልኩበት ወቅት ከእንደዚህ ዓይነት መጥፎና መራር ወቅት ውስጥ አውጣን በማለት እንደሆነ ያስረዳሉ።

እንጨትም ተይዞ በማሹለክ ያንን እንጨት በገዳዎች አማካይነት በግራ አቅጣጫ የሚጥሉትም (bita gatanu) የሁሉቃ ዓይነት አለ። የዚህ ዓይነቱ ሁሉቃ ይህ ነገር (መጥፎ ዓመትና በሽታ) ዳግም እንዳይመለስብን ተብሎ ወደ ገደል ወስዶ በመጣል የሚከወን እንደሆነ ይገልጻሉ።
በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ በዋናነት ሁለት የሁሉቃ ከበራ ዓይነቶች አሉ። እነሱም፡- የሰውና የከብት ሁሉቃ በመባል ይታወቃሉ። (አቶ ብርሃኑ ንጉሴ፣በ7/6/2008 ዓ.ም.፣ጉጂ ዞን፣ቦሬ ከተማ ነዋሪ)

### 6.3.1. የሰው ሁሉቃ ከበራ

ሁሉቃ ለሰው ልጆችጤንነት መታወክ፣ ሰላም ማጣት፣ ለምርት ማነስ፣ ለትውልድ አለመቀጠል፣ ለክፉ ዘመን፣ ለጦርነትና የመሳሰሉት ሰበብ ወይም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ የሚሉትን እርኩስ መንፈስ ማንጫ ከበራ አድርገው እንደሚጠቀሙበት ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። (ገዳ ደንበባ ጉሚ፣ አባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)
ሁሉቃ በቃሉ፣በገዳና በማህበረሰቡ ደረጃም ይከወናል። ሁሉቃ በግለሰብ ደረጃ አባት ለልጆቹ፣ እናት ለልጆቿ ታከናውናለች። አባት ወይም እናት ልጆቻቸውን ለሆነ ጉዳይ ከቀዬው ርቀው ሲሄድ፣ ሲታመሙ፣ ስለነሱ መጥፎ ህልም ካዩ፤ ግራ እጃቸውን በልጆቹ እራስ ላይ ሦስት ጊዜ በማዞር፤ አሊያም እንጨት ቢጤ ቆርጠው በማዞር፤ ወይም ልጆቻቸውን ከብብቷ/ቱ ስር በማሾለክ እንዲሁም በእግሮቻቸው ስር በማሽሎክ ጭምር ክፉ መንፈስ እንዳያያቸው ወይም እንዳይነካቸው እግዚሐብሄርን በመለማመን ያን እንጨት ወደ ውጪ ይጥሉታል። በእጃቸው፣ በእግሮቻቸው ስር እና በብብታቸው ስር ሲከውኑ ደግሞ ያ ጦስ ከእናንተ ይልቅ ለእኛ ያድርገው እንደማለት ነው።

በተለይ በቃሉ ተቋም የሁሉቃ ከበራ የሚካሄደው በጥቅምት ወር ነው። መቼቱም የሁሉቃ መግቢያ (karra hulluuqa) የሚባል አለ። ከዚያ አካባቢ ባሉ ትላልቅ የብሳና እንጨቶች ላይ በታሰረው ሀረግ በመጀመሪያ ቃሉ፣ በመቀጠል የመማክርት አባላቱ፣ ከዚያ እንደየጎሳውና ዕድሜ በቅደም ተከተል ይሾልካሉ። ቃሉ በመጀመሪያው ላይ እየመረቀ ይሾልካል። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Aara hamaa nu hulluuqsis, | ከመጥፎ ጭስ አሽሉከን፣ |
| ibidda hamaa nu hulluuqsis, | ከመጥፎ ንዳድ አሽሉከን፣ |
| dhibee hamaa nu hulluuqsis, | ከመጥፎ በሽታ አሽሉከን፣ |
| kan namaan dhufte nu hulluuqsis, | በሰው ላይ ከመጣው አሽሉከን፣ |
| kan guddaan dhufte nu hulluuqsis, | በአዛውንቱ ላይ ከመጣው አሽሉከን፣ |

kan xiqqaan dhufte nu hulluuqsis. በትናንሾቹ ላይ ከመጣው አሽሉከን፣ በማለት ይመርቃል፤ እግዚአብሔርን ይማጸናል።

በገዳ የደረጃ እርከን ስር ካሉት ውስጥ የዶሪና የገዳ አባለት የስልጣን ርክክብ ከማድረጋቸው በፊት የሁሉቃ ከበራ ይፈጽማሉ። ምክንያቱም ዶሪዎች መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ (kaayoo fi faro hamtuu) ተከትሏቸው በመምጣት የወደፊት ስራቸውን እንዳያደነቃቅፍ በማሰብ ሲሆን፣ ስልጣን ላይ የቆዩት ገዳዎች ደግሞ ምናልባትም በስልጣን ዘመናቸው ወቅት አብሯቸው የነበረ መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ አሁንም እንዳይከተላቸው በሚል የሚፈጽሙት የጦስ ማውጣት ከበራዎች ናቸው።

ሴቶች ወጠባ (ባህላዊ ጭፈራ) ሲጫወቱ በቦታው የታደሙትን ህዝብ በእጃቸው ገብስ (የተቆላ) በመያዝ፣ህዝቡን ወደ መሃል በመተው (ልክ ልጆች «መሀረቤን ያያችሁ» እያሉ እንደሚጫወቱት ዓይነት) ለአራት ሆነው ሶስት ጊዜ እልል እያሉ ይዞራሉ። ከዚያም በእጃቸው ይዘውት የዞሩትን እህል የሁሉቃው እንጨት (ብሳና) ስር ያስቀምጣሉ። በዚያ በገብስ አዙረው እንደጦስ መጣላቸው ነው።እንደ ጉጂ አዛውንቶቹ አባባል ልክ አባት ወይም እናት ልጆቻቸውን በራሳቸው እንደሚያሾልኩ ሁሉ ሴቶቹም በእራሳቸው ተጠቅመው ህዝቡን ማሾለካቸውን ያስረዳሉ። ይህ ደግሞ በገዳ ስርዓት ውስጥ የሴቶችን ሚና ያሳያል።

ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ የሁሉቃ መቼት የሰውን ልጅ መልካም እንዳይገጥመው የሚተናኮሉ መጥፎ መናፍስት በላዩ ላይ ካሉ አስሮ መያዣ አውዱ እንደሆነ ነው። ከተምሳሌታዊ አተረጓገም አንጻር ሀረጉ፣ ገብሱ፣ እንጨቱ የጦስ ማውጫ ተምሳሌት ሲሆን ሀረጉ በሁለት እንጨት መሀል መታሰሩ ደግሞ ያ ይኖራል ተብሎ የሚታመነው መንፈስ ማስቀሪያ አመላካች ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው። ከፋይዳዊ ንደፈ-ሀሳብ አኳያ ደግሞ በቦታው ተገኝተው የሾለኩ ምዕመናን ከዚያን ጊዜ በኋላ እስከ አመቱ መጨረሻ መጥፎ ነገር እንደማይገጥማቸው አድርገው ስለሚያስቡ ስነ-ልቦናዊ እርካታ ያገኛሉ። ይህ ደግሞ ከከበራ ፋይዳዎች ውስጥ አንዱ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በገዳ ስልጣን ሽግግር ወቅት የሚያስረክቡት የገዳ አባላት ቀድመው ሾልከው እራሳቸውን ስላነጹ፤ ለሚያስረክቡት የዶሪ እርከን ላይ ላሉት ጥሩ ዕድልና ዕጣ-ፈንታን እንደሚያስረክቡ ሲያስቡ ውስጣቸው በደስታ ይሞላል። በዶሪ ደረጃ ላይ ያሉትም የሁሉቃን ከበራ ፈጽመው ስልጣኑን መረከባቸው የአገልግሎት ዘመናቸው ውጤታማ እንደሚሆን

ስለሚያስቡ በውስጣቸው መልካም ተስፋን ሰንቀው እንዲሰሩ ያነሳሳቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የመንፈስ ጥንካሬን ይፈጥርላቸዋል፡፡ Bell የከበራን ተግባር ስታስረዳ ቡድኖች የሚተዳደሩበት ስርዓት ወይም የሚያራምዱት አመለካከት የሚመሩባቸውን ህግጋት እንዲያከብሩና እንዲጠብቁ የማነሳሻና ማደራጃ ዘዴዎች እንደሆኑ ትገልጻለች (Bell, 1997:37)፡፡ ስለዚህ የሰው ሁሉቃ ተግባር የሰውን ልጅ ለቀጣይ ዘመኑ ተነቃቅቶና እራሱን በሞራል ገንብቶ እንዲነሳ ማድረግ ነው፡፡

## 6.3.2. የከብት ሁሉቃ ከበራ

የከብቶች ሁሉቃ ልክ እንደሰው ሁሉቃ በቃሉ፣ በገዳና በግለሰብ ደረጃ ይከወናል፡፡ በቃሉና በገዳ ተቋማት በተዘጋጁ የሁሉቃ መቼት ላይ ሲያከናውኑ፤ አርብቶ አደሩ ግን ከብቶቹን በብትሩ ስር እንዲሾልኩ በማድረግ ከበራውን ይፈጽማል፡፡

መቼቱም በቃሉና በገዳ ተቋም አካባቢ ለሚደረጉ የሰውና የከብት ሁሉቃ ክዋኔዎች ጎን ለጎን ይፈጸማሉ፡፡ የሚዘጋጀውም ከአንድ ዓይነት ቁሶች ሲሆን፤ ልዩነታቸው ለከብቶች የሚዘጋጀው ጎኑና ቁመቱ ላይ ነው፡፡ይኸውም የከብቶች ሁሉቃ ጎኑ ሰፋ ማለት አለበት፡፡ ለሰዎች የሚዘጋጀው ግን ከአምስት እስከ አስር ሰዎችን ጎን ለጎን ሊያሾልክ በሚችል ሁኔታ የሚዘጋጅ ነው፡፡

ይህ የሁሉቃ ከበራ የሚካሄደው በአመት አንድ ጊዜ ሲሆን እሱም መስከረም ሲጠባ ነው፡፡ ምክንያቱም በዘመን መለወጫ ማለትም መስከረም (birraa) ላይ ከክረምቱ፤ ከጨለማዋ በሰላም ላወጣኸን አምላክ ምስጋና ይግባህ ለማለትና ቀጣዩ ጊዜ መልካም እንዲያደርግላቸው የሚከውኑት ነው፡፡

ሁሉቃ የማህበረሰባዊ ውቅር ዕውቀት ነው፡፡ አዘገጃጀቱም ለዚህ ተግባር ተብሎ በተመረጠው ቦታ ማለትም ሜዳማ ሆኖ ከግራና ቀኝ በተፈለገው ስፋት የቆሙ ሶስት ወይም አራት ዛፍ እንጨቶች ይመረጣሉ፡፡ ከዚያም በስተቀኝ በኩል የሰው ሁሉቃ፣ በስተግራ በኩል ደግሞ የከብት ሁሉቃ ይዘጋጃል፡፡ ይኸውም፦ዲክቻ የሚባለውን ሀረግ ተቆርጦ ይመጣል፣ ከዚያም በተመረጡት እንጨቶች ላይ ለሰውም ሆነ ለከብት በሚያሾልክ ቁመት ከግራና ከቀኝ ይታሰራል፡፡ ቋሚው ከስሩ የበቀለ እንጨት ቢሆን ይመረጣል፡፡ ያ የሁሉቃ እንጨት ምን ጊዜም ቢሆን አይቆረጥም፤ አይመለመልም፡፡ ምክንያቱም መጥፎው በሰዎችና በከብቶች ላይ ነበር ተብሎ የሚታመነው መንፈስ በእሱ ላይ ቀርቷል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ቦታውም

የተከበረና ጥብቅ ነው፡፡ እንደመረጃ አቀባዬ ገለጻ የበቀለ ወጥ ዛፍ ከሌለ ዘለግ ያሉ እንጨቶች ተቆርጠው ይተከሉና ሀረጉን በእነሱ ላይ በማሰር ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ (አቶ አባባ ቶቴ፣ 23/2/2007 ዓ.ም.፣ በወናጎ ወረዳ የቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

የከብት ሁሉቃ ክዋኔ የሚከወነው ይህን ዓመት ከመጥፎ የከብቶች በሽታ ያሾለከን አምላክ ምስጋና ይግባህ፣ለቀጣዩም ከክፉ በሽታ ሰውረን፣ አውጣን፣ አሹልከን፣ መጥፎ በሽታን አሁንም ያዝልን፣ የግጦሹን ሳር አሳምርልን ወዘተ...በማለት እግዚሐብሄርን የሚያመሰግኑበት፣ የሚማፀኑበትና ከብቶቹን ከመጥፎ ነገሮች የሚያነጹበት ከበራ ነው፡፡ ይንንም ተግባር ቃሉ ወይም አባገዳ ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ከሁሉቃው እንጨት ጎን ቆመው፣ በእርጥብ የእንጨት ዝንጣፊ ከብቶቹን ቸብ ቸብ እያደረጉ፤ በሁሉቃው ስር ተራ በተራ ያሾልካሉ፡፡ ከብቶቹ በብትር አይመቱም፡፡ በዚህ ጊዜ ያን የእንጨት ዝንጣፊ ቅጠሉ እንዳይበጣጠስና ሁሉንም በአንድ ዓይነት ሁኔታ ለማሾለክ ከማሰብ የተነሳ በቀስታ ቸብ ቸብ እንደሚደረግ ይናገራሉ፡፡




ፎቶ፤-15 የከብት ሁሉቃ መቼት

የምርቃቱም ሂደት እንደሚከተለው ይከወናል፡፡ ይኸውም፡- ቃሉ ወይም አባገዳው

ከብቶቹን ሰላም አድርግልኝ!

ላሞቹ ያግቱ!

ኮርማው ለስሪያ ይነሳሳ!

ጥጆቹ በመስክ ላይ ይቦርቁ!

ጋንዲ (የከብት በሽታ) አጥፋልን! (አቶ ብርሃኑ ንጉሴ፣ጉጂ ዞን፣ ቦሬ ከተማ ነዋሪ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም.)

ቃሉ የሁሉቃ ከበራ ላከናውን ነው ብሎ መልዕክት ካስተላለፈ፤ የቅርቡም ሆነ በርቀት ያሉት ከብቶቻቸውን ነድተው ይመጣሉ፡፡ በመጀመሪያ በቃሉ ተቋም ዙሪያ ያሉት ከብቶች እንዲሾልኩ ይደረጋሉ፡፡ ከዚያም እንደየአመጣጣቸው ከርቀት የመጡትንም ያስተናግዳሉ፡፡ ከብቶች የምሾልኩት ከእረኞቻቸው ጋር ነው፡፡ በዚያን ቀን በደረቅ ዱላ አይመቱም፤ ልምጭ ይዘው ለአመል ያህል እየመቱ አብረው ይሾልካሉ፡፡ በሁሉቃ ወቅት በእጁ ጦርም ሆነ መሳሪያ የያዘ ሰው ካለ ከነጦሩ አይሾልክም፡፡ ሰውዬው ከስር ስሾልክ፤ ጦሩን ወይም መሳሪያውን ከላይ አሳልፎ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን ሲቄ፣ ቦኩ፣ የወተት ማለቢያ ጭጮውንና ማስሪያ ጋዱን በመያዝ ከብቶቻቸውን እየነዱ በስርዓቱ ላይ ይታደማሉ፡፡

ቀደም ሲል እንዳየነው ጦር፣ የጦር መሳሪያ ተምሳሌነታቸው የጦርነት በመሆኑ በሁሉቃ ስር አያልፉም፡፡ ነገር ግን ሲቄና ቦኩ ቅዱስ ቁሳዊ ባህሎች በመሆናቸው እነሱም ለቀጣዩ ዘመን መንጻት ስላለባቸው ከሰውና ከብቱ ጋር ይሾልካሉ፡፡ የወተት ማለቢያ ጭጮ (Okolee) እና ጋድ (gaadii) ያየን እንደሆነ ከከብቶቻቸውና ከከብቶቹ ውጤት ጋር ተያያዥነት ስላላቸው እነሱም መንጻት አለባቸው፡፡ ስለዚህ በላያቸው ላይ እርኩስ መንፈስ አርፎ ወተቱንና ከብቱን ለበሽታና ምርት መቀነስ ምክንያት እንዳይሆን የሁሉቃ ተምሳሌታዊ ክዋኔ በማድረግ እንዲነጹ ይደረጋሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ አርብቶ አደሩ ከብቶቹን በብትሩ ስር እያሾለከ የሚመርቅበት ሁኔታ አለ፡፡ምርቃቱ ያው ከመጀመሪያዎቹ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይኸውም፡- ከብቶቹን ከመጥፎ በሽታ፣ ከድርቅ፣ ከውሃ እጦት አውጣቸው፡፡ በማለት ስለነሱ መልካም መልካሙን እየተመኘ ማሾለክ ነው፡፡(አቶ ታደሰ ደንበባ፣አባያ ወረዳ፣ቡናታ ቀበሌ ነዋሪ)

በመጨረሻም ታድመው የነበሩ እናቶች፣ወጣቶችና እረኞች ከብቶቻቸውን እየነዱ በደስታና በጭፈራ ወደ ቂያቸው ሲመለሱ፤ገዳዎች፣ወዩዎችና አዛውንቶች ቃሉን አጅበው እጨፈሩ ወደ ገልማው ይሄዳሉ፡፡ በአቅራቢያ ያሉ እናቶች ከቤታቸው ጠጅ ያመጣሉ፡፡ ቡና ቃላ ይዘጋጅል፡፡ ከዚያ በመጀመሪያ ቃሉ ቡና ቃላውን እግዚአብሔርን ተለማምኖ ይቀምስና ባለቤቱንም ያቀምሳል፡፡ በመቀጠል እንደ ስልጣን ቅደም ተከተላቸውና እንደ ጎሳ ታላቅነትና ታናሽነት እየተቀባበሉ ይበላሉ፡፡ ከጠጅም ለቃሉ በራሱ መጠጫ (duloo)፣ ለጎሳውም በሌላ መጠጫ

(duloo) ተቀድቶ ይሰጣል። ጎሳው ያን ቡና ቃላ እየበላ፣ ከጠጁም ጎንጨት እያደረጉ ቃሉን ይመርቃሉ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Nu'uu buli ati, | አንተ ከእኛ ኑር፣ |
| nu keessa buli, | እኛ ውስጥ ኑር፣ |
| nu keessa ool, | እኛ ውስጥ ዋል፣ |
| nu'uf jiraadhu, | ኑርልን፣ |
| jireenni kee nagaa ta'u, | ሕይወትህ ሙሉ ሰላም ይሁን። እያሉ በእንትፍትፍ |
| (biifee) | ምርቃቱን ያጸድቃሉ። |

በመቀጠል ቃሉም እነሱን በመመረቅ ያሰናብታቸዋል። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Isinille bulaa, | እናንተም ኑሩ፣ |
| ardaa nagaa ta'aa, | ሰላማዊ መንደር ሁኑ፣ |
| Gujii nagaa ta'a, | ሰላም የሰፈነበት ጉጂ ሁኑ፣ |
| Gujii gabbinnaa ta'a, | ኑሮዋችሁ ያማረ ጉጂ ሁኑ፣ |
| Qayeen isin nagaa haata'u, | መንደራችሁ ሰላም ይሁን፣ |
| Nagaan gala. | በሰላም ግቡ ይላል። |

የከብት ሁሉቃ በሚካሄድበት ወቅት በከብቶቹ ላይ ምናልባትም በሽታ አምጭ፣ ኮርማዎቹ እንዳይሰሩ የሚያፈዝና ላሞቹም እንዳይግቱና ወተት እንዳይሰጡ የሚያደርግ እርኩስ ሰፍሮባቸው ከሆነ እንዲነሳ፤ አልሰፈረባቸው እንደሆነ እንዳይተናኮላቸው እግዚአብሔር እንዲጠብቅላቸው የሚለማመኑበት ሂደት ነው። ከሁሉቃው ከበራ በኋላ እያንዳንዱ ግለሰብ ለከብቶቹ ደህንነት መድህን እንደገባላቸው ይቆጥራል። መንፈሳዊ እርካታም ይሰማዋል። ይህ ደግሞ የከበራ ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ነው። በሌላ በኩል ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ የሁሉቃው መቼት ከብቶችን የሚተናኮሉ መጥፎ መናፍስትን ማስቀሪያና ማሰሪያ በመሆን ለከብቶቹ ደግሞ መንጽያ አውድ እንደሆነ ይቆጠራል።

ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም አንጻር ከብቶቹ ሁሉቁ ሲሉ በእርጥብ ቅጠል ቸብ ቸብ የሚደረገው፡- እርጥቡ ቅጠል የልምላሜ፣ የምርታማነት ተምሳሌት በመሆኑ ከብቶቹ ማህጸናቸው እርጥብ

እንዲሆን፣ ከወለዱም በኋላ ወተታማ እንዲሆኑ፣ ከርማዎቹ ለስሪያ ንቁ እንዲሆኑ ምኞት መግለጫ ነው።

## 6.4. የፋጬ ከበራ

እንደ ዋቄፋና ሃይማኖት ተከታዮች እምነት እግዚኣብሔር (ዋቃ) ለቃሉዎች የገለጹላቸውና ሰዎች እንዲያከብራቸው ያስተምሩ ዘንድ ያዘዛቸው ዋና ዋናዎቹ ሕግጋቶች አሉ። እነዚህን ሕግጋት በሰው ልጆች ዘንድ ተምረውና አውቀው በስራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው ይታመናል። ነገር ግን ሰዎች አንድም በማወቅ፤ አሊያም በስህተት ወይም ባለማወቅ ከእነዚህ ሕግጋት ውስጥ የተወሰኑትን ሊጥሱ ይችላሉ። እንደ ዋቄፋና ሃይማኖት እነዚህ ጥሰቶች እንደ ሀጢያት (cubbuu) እንደተሰራ ይታመናል።

በሌላ አባባል እንደ ጉጂ ኦሮሞ ሀጢያት ማለት የእግዚኣብሔር ቀደምት እውነቶችን (dhugaa ganamaa) በመጣስ በተፈጥሮ ላይ የሚደርስ ጉዳትና እግዚኣብሔርን ማሳዘን እንደሆነ ያምናሉ። እነዚህም እውነት ሳለ መዋሸት (በሀሰት መመስከር፣ የሰውን ሀቅ መካድ፣ አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት መሞከር)፣ ነፍስ ማጥፋት፣ የሰውን መመኘት፣ ሌብነትና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ባጠቃላይ እነዚህን እግዚኣብሔር የማይፈቅደውን ስራዎች መፈጸም ሀጢያት እንደሆነ ያምናሉ።

ሌላው ጉጂ እግዚኣብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ (uuma) እንደሆነና በሰማይና በምድር መካከል ከሱ የተሰወረ ነገር እንደሌለ ያምናሉ። ከዚህም የተነሳ በሰው ዘንድ ለተሰሩ ጥሩ ስራ (waan gaarii)ና ሀጢያትን (cubbuu) ምን ምን እንደሆኑ እግዚኣብሔር ለቃሉ ህግጋቱን ለህዝቡ እንዲያስተምር ተገልጾለታል በማለት የሚያከብሯቸው እንዳሉ አይተናል። እንደ ጉጂ ኦሮሞ ጥሩ ስራም ሆነ ሀጢያት በሰው ልጅ ቢሰራ ለእግዚኣብሔር ማስረጃዎቹ ሰማይና ምድር እንደሆኑ ያምናሉ። እንደመረጃ አቀባዮቼ አገላለጽ አንዳንድ ሰዎች የሰው ማስረጃ ኖረም፤ አልኖረም ስላደረጉት ድርጊት ለሌላኛው ወገን ሲያረጋግጡ፡- በጣታቸው ወደ ሰማይና ምድር እያመለከቱ «ይኸው! ሰማይና ምድር በሚያውቀው» «Kunoo! Waaqiifi lafti tun kan beektu» በማለት እንደሆነ ያስረዳሉ። ኦሮሞ እግዚሐብሄርና ሰማዩን በአንድነት ዋቃ (Waaqa)

ብሎ እንደሚጠራ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ከዚህ የምንረዳው በአፋን ኦሮሞ ዋቃ (Waaqa) የሚለው ስም አውዳዊ ፍች አለው ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡-1. Qaalluun Waaqaafi nama gidduuti ta'ee seera waaqaa barsiisa.

ቀጥተኛ ትርጉሙ፡- ቃሉ በእግዚሐብሄርና ሰው መካከል ሆኖ የእግዚሐብሄርን ህግ ያስተምራል የሚል ነው፡፡

2. Xiyyaarri waaqarra ka'e; balalaʼe.

ቀጥተኛ ትርጉሙ፡- አውሮፕላኑ በሰማይ ላይ ተነስቶ በረረ የሚል ነው፡፡

ከነዚህ ምሳሌዎቹ የምንረዳው ዋቃ (Waaqa) የሚለው በአንደኛው ዐ.ነገር ውስጥ ያለው ፍች «እግዚሐብሄር» የሚለውን የሚገልጽ ሲሆን፣ በሁለተኛው ዐ.ነገር ውስጥ ያለው ፍች ደግሞ «ሰማይ» የሚለውን እንደሚገልጽ ያሳየናል፡፡ ስለዚህ የዋቃ (Waaqa) አውዳዊ ፍች የሚገኘው ከገባበት አውድ አኳያ መሆኑን ለማየት ችለናል፡፡

አንድ ሰው ሀጢያት ቢሰራ ምን ይሆናል? ለምለው ጥያቄ መረጃ አቀባዮቹ ሲመልሱ፡- ሀጢያት የሰራ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተለያዩ ችግሮች ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይኸውም፡- በቀጥታ በራሱ ሕይወትና በንብረቱ ላይ አነስተኛ ጉዳት እንደ ማስጠንቀቂያ ደወል ይደርስበታል፣ ሌላው ባጠፋው ጥፋት መጠንና ዓይነት ሊደርስበት ይችላል፣ አሊያም ከዚያ የከፋ ችግር ሊደርስበት ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ሀጢያት የሰራ እንደሆነ ያ ግፍ በራሱ ሳይሆን በልጆቹ ወይም በልጅ ልጆቹ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ «Guji are not interested in eschatology, a purely spiritual development of the person, or life after death» (Van de Loo, 1991:286). ከዚህ ጥቅስና ከአጥኚው የካበተ ልምድ እንደጉጂ ኦሮሞ አተያይ የሰው ልጅ ሀጢያት ሰርቶ ከሞተ ገሀነብ፣ ጽድቅ ሰርቶ ከሞተ ገነት ይገባል የሚል አስተምሮት የለም፡፡ ሀጢያት የሠራ፣ ለክፉ ሥራው በምድር እያለ ቅጣቱን ያገኛል (Hussein, 2002:66)፡፡

### i. የሀጢያት መገለጫ ወይም አመላካች ችግሮቹ

የሀጢያት መገለጫ ወይም አመላካች ችግሮቹ የሚባሉት አንድ ሰው በራሱ ላይ፣ በንብረቱ ላይ፣ በቤተሰቡ ላይ ያልተለመዱ ክስተቶች ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች እንደ አጋጣሚያቸውና

ድግግሞሻቸው ይለያያሉ፡፡ ጉጂዎች እንዲህ ዓይነቱ ችግር ሲያጋጥማቸው በምን ምክንያት መጣብኝ ወይም መጡብኝ በማለት እራሳቸውን እንዲጠይቁ ስለሚቀስቅሳቸው እንደ ሀጢያት መገለጫ ይቆጥሩታል፡፡
ያም ሆነ ይህ የሀጢያት መገለጫው እንደታየ ከችግሩን መውጫ መንገድ ፋጭ (ንስሀ) እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

**ፋጭ** (faacii) ደግሞ አንድም እንደ ሀገር፣ አንድም እንደጎሳ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ቤተሰብና እንደ ግለሰብ ሊከወንላቸው ይቻላል፡፡ ይኸውም፡- ከእግዚአብሔር ቁጣ የተነሳ፤ የችግሩ ተፅዕኖ የደረሰው እንደ ሀገር ከሆነ፡ ቃሉና ገዳ በመሆኑ ማህበረሰቡ ምን ቢሰራ/ ምን ጥሰት ቢፈጽሙ ነው/ ይህ ሊከሰት የቻለው በማለት የሚከውኑት የማጣራትና የንስሀ ከበራ ሲሆን፣ ሌሎቹም በየደረጃቸው ምን ቢያጠፉ ነው የምለውን በማጣራት የሚከውን ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በሰራው ሀጢያት ተፀፅቶ፤ ከበደለው አካል ይቅርታን በማግኘት፣ ይቅር ለእግዚአብሔር ለመባባልና ከፈጣሪውም ምህረት እንዲደረግለት የሚከወን የንስሀ ከበራ ነው፡፡ ይህ ከበራ የሚፈጸመው አብዛኛውን ጊዜ አንድም አንድ ሰው በራሱ ላይ፣ አሊያም በቤተሰቡ ላይ ወይም በንብረቱ ላይ ያልተለመዱ ክስተቶች ከተፈጠሩ፤ እንደነዚያ ዓይነት ችግር ዳግም እንዳይከሰት ለመከላከል የሚደረግ ሃይማኖታዊ ከበራ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

ሌላው ደግሞ ቀደም ሲል በምን ይመጣብኛል ትዕቢት ወይም ንዴት ውስጥ ሆኖ ሀጢያትን ይሰራና በኋላ ላይ መፀፀት ይመጣል፡፡ በዚያን ጊዜ ጥፋቱን በመግለጽ መፀፀቱን ያስረዳና በራሱ ላይ ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት አስቀድሞ የሚከወን የፋጭ ዓይነትም እንዳለም መረጃ አቀባዮቼ ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ በጥፋቱ ምክንያት የሀጢያት መገለጫ ወይም አመላካች ችግሮች ከተፈጠሩ፤ ይህ ችግር ከምን መጣብኝ? ከደረሰው ችግር እንዴት ሊወጣ ችላለሁ? አሊያም እንዴትስ ነው ችግሩ ሊያበቃ የሚችለው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኘው በፋጭ ሃይማኖታዊ ከበራ መሰረት እንደሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታመናል፡፡

ከዚያን በኋላ ችግሩ የተከሰተበት ሰው የሀገር ሽማግሌዎችን በመሰብሰብ ችግሩን ይነግራል፣ አንዳንዴም ችግሩ በተፈጠረበት ወቅት የነበሩ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ያዩታል፣ እንደሁኔታው ቅለትና ክብደት ችግሩ የቃሉ ተቋም ሊደርስ ይችላል፡፡

በዚህ መሰረት ፋጭ አንድን ሰው በፈፀመው ስህተት እንዳይፀፀትና ዳግም ወደ ስህተት ውስጥ እንዳይመለስ ለማድረግ የሚከወን ሃይማኖታዊ ከበራ ነው። ይህ ከበራ የማህበረሰቡ ውቅር ዕውቀት ነው። ይኸውም እንደ ጉጂ ኦሮሞ በፋጭ ከበራ ማንኛውም ሀጢያት ይቅር ሊባል እንደሚችል፤ ይቅርታውም አንድም ከተበደለው ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ከእግዚኣብሔርም ይቅርታ እንደሚያገኝ ያምናሉ።

በጉጂዎች ዘንድ በፋጭ ሂደት ውስጥ ሰውን በመፍራትም ሆነ፤ ምን ይሉኛል ተብሎ የሚሸሸግ ሚስጥር የለም። ምክንያቱም አንድ ሰው ጥፋቱን በፍርሃትም ሆነ በማንአለብኝነት ቢደብቅ፤ የሰውን ልጅ ዋሽቶ ከሰው ዘንድ ይቅርታን ሊያገኝ ይችላል። ነገር ግን እውነተኛውን ይቅርታ፤ ከእግዚኣብሔር የሚገኘውን ይቅርታ እንደማያገኝ ያምናሉ። ስለዚህ ችግሩ ይቀጥላል፤ ከዘር ወደ ዘር ይተላለፋል ተብሎ ስለሚታመን እውነቱን አውጥተው መናገር እንዳለባቸው ይታመናል።

በዚህ የፋጭ ሂደት ውስጥ እንዳጋጣሚ በደል የደረሰበት አካል በወቅቱ ቢኖር፣ አሊያም በወሬ ወሬ ቢሰማ እንኳን ቂም መያዝ እንደሌለበት በባህሉም ሆነ በእምነቱ ውግዝ እንደሆነ የጉጂ የሀገር ሽማግሌዎች ይገልጻሉ። ስለዚህ በፋጭ ጊዜ በድያለሁ የሚለው አካል ሀጢያቱን ያለአንዳች ፍርሃትና ስጋት ይናዘዛል።

ለአብነት ያህል በጉጂ ኦሮሞ አንድ ሰው በድንገት በመኪና አደጋ ከሞተ ዝም ተብሎ አይቀበርም፤ እንዲሁም የደም ካሳ አይወሰድም፤ ተቻኩሎም ለክስ አይሮጥም። አስከሬኑን አስቀምጠው ይህ አደጋ ከእኛ ቤተሰብ ውስጥ እንዴት ሊከሰት ቻለ? ብለው ቀድመው ያጣራሉ። በዚህ የማጣራት ሂደት ወቅት ከዚህ በፊት በማወቅም ይሁን፤ ባለማወቅ በተመሳሳይ አደጋ የደም ካሳ የወሰደ ሰው ካለ አደጋውን ይደግማል ተብሎ ስለሚታመን ይህም ጉዳይ ተነስቶ ይጣራል። ምክንያቱም እንደ ጉጂ ኦሮሞ አተያይ ባለመኪናው ከቤቱ ሲወጣ እገሌን በመኪናዬ ገጫለሁ፤ ገድለዋለሁ ብሎ አልወጣም ብለው ያምናሉ። እንዲሁም ሟቹም ከቤቱ ሲወጣ ሞታለሁ ብሎ አልወጣም። ስለዚህ ይህ ክስተት ፍርጃ ነው፤ የእግዚሐብሄር ትዕዛዝ ነው ብለው ያምናሉ። ታዲያ አንዳንድ የቤተስቡ አባል «በምን ይመጣብኛል» አስተሳሰብ አደራዳሪ መስለው በመቅረብ፣ ለቀብር ማስፈፀሚያ ብቻ የተባለው ላይ ጨምሮ በመወሰድ የቀድሞውን ስርዓት የሚጠሱ ስለማይጠፉ እነዚህ ሁሉ በንስሀ ከበራው ሂደት ላይ ይጣራሉ። እንዲህ እንዲህ እየተባለ የማጣራቱ ሂደት ይቀጥላል።

የፋጭ ሂደት በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ ደረጃ እንዲሁም በአባገዳዎችና በአባቃሉ ደረጃም ሊከወኑ ይችላሉ። ስለዚህ በአንድ የጉጂ ጎሳ ውስጥ የተለያዩ ችግሮች ቢከሰቱ ለነዚያ ችግሮች መንስኤው ምናልባትም ከላይኛው ደረጃ ላይ ባሉት በተፈጠረ የእግዚኣብሔር ህግጋት ጥሰት ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ እግዚኣብሔርም ቅጣቱን እንደ ህዝብ ወይም በጎሳው ላይ ሊያወርድ እንደሚችል ይታመናል። እነዚህን ችግሮች ሲከሰቱ ሁሉም በየደረጃው እራሱን መፈተሽና የንስሀ ክዋኔ መፈጸም እንዳለበትም ይታመናል።

እንደ Van De Loo አገላለጽ አንዳንዴ ይህ ሁሉ ንስሀ፣ ልመናና መስዋዕት ቀርቦ ነገሮች እንደቀድሞው በሰላማዊ መንገድ ላይቀጥል ይችላሉ። ይኸውም አንድ ሴት መሀን ሆና ልትቀር ትችላለች፣ ሰዎች ይታመማሉ፣ ከብቶች ይሞታሉ። የጉጂ ህዝብ በሌሎች እጅ ወድቀው ሊጨቆኑ ይችላሉ። በዚህ ወቅት ይህ ሁሉ የሚሆነው በእግዚኣብሔር ፍቃድ እንደሆነ ያምናሉ። አሊያም «እግዚኣብሔር ከእኛ ዘንድ ርቋል» እንደሚሉ (Van De Loo,1991፣284) ይገልጻል።

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አንዳንድ ጊዜ ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ የፋጭ ሃይማኖታዊ ከበራ ተካሂዶ፣ ለእግዚኣብሔር መስዋዕት ቀርቦና ተለማምኖ እንኳን ነገሮች ወደቀድሟቸው ቦታ ላይመለሱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ማህበረሰቡ እግዚኣብሔርን ከማማረር ይልቅ ከአምስቱ የዋቄፋና ህግጋት ውስጥ አንዱ የሆነውን፡- የመጣውን ችግር የእግዚኣብሔር ስራ ነው ብሎ በፀጋ መቀበልን ያሳያል። አሊያም «እግዚኣብሔር ከእኛ ዘንድ ርቋል» የሚሉት ደግሞ ከሀጢያታቸው ብዛት የእግዚኣብሔር ጥበቃ እንደተለያቸው በማመልከት ለችግሩ ኃላፍነቱን መውሰዳቸውን ያሳያል።

በሌላ መልኩ በአንድ የማህበረሰቡ አባል ወይም በማህበረሰቡ ጥፋት ወይም አባገዳዎች፣ አባቃሉ እንዲሁም የመማክርት አባላቶቻቸው ከተሰጠጣቸው ደንብና መመሪያ ውጭ ሲሆኑ ሀጢያትን እንደፈጸሙ ይቆጠራል። ለምሳሌየገዳ ስልጣን ዑደቱን ማዛባት እንደ ሀጢያት (cubbuu) ስለሚቆጠር ለችግሩ ምክንያት በሆኑት አካላት ላይ ጫን ያለ ቅጣት ይወሰዳል (Alemayehufi kan biroo, 1999፡169)። ታዲያ እግዚኣብሔርም በዚህ ድርጊታቸው ያዝናል። አዝኖም ዝም አይልም። የቅጣት ጅራፉን ይሰነዝራል። ይኸውም፡- በድርቅ፣ የዝናቡን መጠን

በመጨመር ወይም በመቀነስና ወቅቱንም በማዛባትና የመሳሰሉትን በማድረግ ህዝቡን ሊቀጣ እንደሚች ያምናሉ።

ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ እንደጎሳ ከተከሰተ፡- ከስር ጀምሮ ህዝቡ ውስጥ ምን ሀጢያት ቢፈፀም ነው እንዲህ ዓይነቱ የእግዚኣብሔር ቁጣ የመጣብን በማለት ያጣራሉ። በመቀጠል አባገዳውና የመማክርት አባላቶቹ አካባቢስ ምን ምን ክፍተቶች አሉ?፣ እያለ ወደ አባቃሉና የመማክርት አባላቱም ጋ እየተጣራ ይመጣል። ካለመስልቸት በየደረጃው ፋጭ እየተባለ፤ መስዋዕት በማቅረብ እግዚኣብሔርን በመለማመን ሊፈታ እንደሚችል ይታመናል።

### ii. የፋጭ ከበራ ሂደት

ቀደም ሲል እንዳየነው የፋጭ ከበራ ሂደትን በቅድመ-ፋጭ፣ ፋጭና ድህረ-ፋጭ ደረጃ መመልከት ይቻላል። እነዚህን ሂደቶች ለመተንተን የሚከተለውን የፋጭ ንጥል ጥናት እንመልከት።

### የፋጭ ንጥል ጥናት-1

አንድ በምዕራብ ጉጂ ዞን፣ በአባያ ወረዳ፣ የፎጌ ቀበሌ ነዋሪ የሆነ አቶ ዋቆ ኦቶሮ የሚባል ሰው ነበር። ይህ ሰው ከዕለታት አንድ ቀን በጠና ይታመማል። በሽታውም እየጠናበት ሄዶ ነፍስ ውጭ፣ ነፍስ ግቢ፤ ሲቃይ ሆነ። ከዛሬ ነገ ይሞታል እየተባለ ሲጠበቅ ዝም ብሎ እንደታረደ በሬ ያንኮራፋ ጀመር። ቤተሰቦቹና የአካባቢው ሽማግሌዎች ተመካክሩ፤ ይህ ሰው እኮ ተሰቃዩ፤ እንዲሻለው ወይም ከስቃዩ እንዲገላግለው ለምን ፋጭ አይደረግለትም አሉ። በሀሳቡ ተስማምተው በማግስቱ ከአካባቢው የባህልና ሃይማኖት አዋቂዎች (Woyyuu)ና ሽማግሌዎች ተነግሯቸው በጠዋቱ መጡ። ከዚያም በባህሉ መሰረት ተጠያይቀው ሽማግሌዎች ተሰየሙ። ቀድሞ እግዚኣብሔር መለመን ያለበት ሰው በመጀመሪያ ጸሎት አደረሰ። ተራ በተራ ሶስት ሽማግለዎች ጸሎት አደረሱ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Ee Waaqa! | አቤቱ እግዚኣብሔር፣ |
| Ee Waaqa Qaalluu, | አቤቱ የቃሉ አምላክ፣ |
| Ee Waaqa Gadaa, | አቤቱ የገዳ አምላክ፣ |
| Kan nagaan nu bulchite, | በሰላም ያሳደርከን፤ በሰላምአውለን! |
| nagaan nu oolchi, | |

| | |
|---|---|
| Afaaniifi arraba nuu bani, | የምንናገርበትን አንደበታችንን ክፈትልን! |
| Ee Waaqa faacii nama kanaa, | አቤቱ እግዚአብሔር የዚህን ሰውን ስህ ተቀበል! |
| nuu dhage. | ይቅርም በለው። በማለት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ |

ሦስቱም ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን ከተለማመኑ በኋላ የመጡበትን ጉዳይ ብያውቁትም፤ ለምን እንደተጠሩና እዚህ እንደተሰበሰቡ ይጠያየቃሉ። ከዚያም ችግሩ ከደረሰበት ቤተሰብ አባላት መካከል አንድ ሰው (ባለቤቱ፣ ወንድሙ፣...) ተነስቶ ለሽማግሌዎቹ ይሄ ወንድማችን/እህታችን ወይም ልጃችን አልጋ ከያዘ ቆዬ። ከዛሬ ነገ ይሻለዋል ስንል ባሰበት፤ የተለያዩ ባህላዊ መድኃኒቶችንም ሞከርንለት። ነገር ግን ከበሽታው ሊድን አልቻለም፤ እረፍትም ነሳው። ስለዚህ ከእሱም ሆነ ከእኛ ጥፋት አይታጣምና ለፋጭ ነው የጠራናችሁ ይላል።

ከዚያ ሽማግሌዎቹ በባህላዊ የአነጋገር ስልት ለሁለት በመከፈል፤ ግራና ቀኝ በመቀባበል ውይይቱን (hayyuu gaafachuu) ጀመሩ።

ይህንን የፋጭ ክዋኔ ሂደት በውይይቱ ላይ በተካሄደው ቅደም ተከተላዊ ሂደት እንደሚከተለው በቀጣዩ ሠንጠረዥ ውስጥ ቀርቧል።

| 1ኛው ሽማግሌ (Jaarsa 1ffaa) | 2ኛው ሽማግሌ (Jaarsa 2ffaa) | ተጠያቂው/ወኪሉ (kan faaci'atu) | በጋራ የሚባለው |
|---|---|---|---|
| 1. ጃል! (abboo!) | 2. እሺ ጃል (abbatto!) | | |
| 3. ይህ ሰው ታሞ እያጣጣረ ነው። (nami kun baay'ee dhukkubsatee jira.) | 4. አዎ!በሞትና በሕይወት መካከል ነው። (lubbuun ba'uuf jedha jirt.) | | |
| 5.ታዲያ ይህ ነገር ከምን መጣባችሁ አንልም? (wanti kun maal irraan isnitti dhufe hinjennuure?) | 6.አልን ይሄው። አቦ! እየሰማህ ነው? (jenne. Abboo dhageettee?) | 7. አባቶች! እኔ በሕይወቴ ብዙ ሀጢያቶችን ሰርቻለሁ። የቱን ተናዝዤ፤ የቱንስ እተዋለሁ? ስለዚህ አንድም ንስህ አልገባም በማለት መለሰ፣ (abbooti kiyya! Ani cubbuu hedduu hojjadheera. Kami faaci'adhee, kami ba'a. kanaafuu tokkolle hin faaci'adhu.) | |
| 8. ጃል! (abboo) | 9. እሺ ጃል (abbatto) | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10. ያለውን ሰማህ? ?(waan deebifate dhageettee) | 11. አዎ! «ምንም ፋጭ አልልም፡፡» ነው ያለው፡፡ (Ee dhaga'e;« tokkolle hin faaci'adhu» jedhe. | | |
| 12.ፋጭ ትላንትም ያለ ነው፣ ከእግዚአብሔር የምንታረቅበት መንገድ ነው፡፡( faaciin waan kale jiru;karaa Waaqaan ittiin araaramnu.) | 13. ፋጭ አልልም ማለት ነበረበት? (hin faaci'adhu jechuu qabaa? | | |
| 14.አልነበረበትም፡፡ ለምን አልክ አንለውም? (hin qabu ture. Maaf jette hin jennuure?) | 15.ይሄው አልነው፡፡ (kunoo jenne.) | 16. አባቶች! እኔ ፋጭ አልልም ያልኩበት ምክንያት ከንቀት መንፈስ ሳይሆን፤ ከሀጢያቴ ብዛት የተነሳ ነው፡፡ያላሳዘንኩት ሰው የለም፡፡ (abbooti kiyya! Ani hin faaci'adhu kan jedhe; marroo cubbuu hedduu hojjadheef;nama ani hinboochisne hinjiru. Kanaaf jedheeti.) | |
| 17. ቢሆንም እንዲህ ማለት ነበረበት? (waan fedhe yoo ta'e akkas jechuu qaba?) | 18. አልነበረበትም፡፡ (Hinqabu.) | | |
| 19. ለምን አለ? (maaf jedheree?) | 20. አልአግባብ ነው፡፡ (Uddi maleedha.) | | |
| 21. ለእግዚአብሔርስ? (Waaqaaf hoo?) | 22. እውነት አለው፡፡ ፈጣሪ ሆይ ታረቀን፡፡ (dhogaa; nu araaram waaqa.) | | 23. ሁሉም በአንድ ላይ እጃቸውን በመዘርጋት «አቤቱ ታረቀን» ይላሉ፡፡(Nu araaram ya Waaqa.Jedhan ) |

ሠንጠረዥ፡-3 የፋጭን ቅደመ-ተከተላዊ ሂደት የሚያሳይ

ከዚህ በኋላ ቡና ቃላ ተዘጋጀ፣ ቦካም (ጠጅም) መጣ፣ ሽማግለዎቹ ተራ በተራ እየተቀባበሉ እግዚአብሔር ይቅርታውን ወይም ፋጭውን እንዲቀበለው፣ ምህረቱንም እንዲያወርድለት እየተለማመኑ በቦካው ግራና ቀኝ እንትፍትፍ (biifee) እያሉ ይመርቁ ጀመር። ቡና ቀላውም በኦሮሞ ዘንድ እንደ ሙሉ (Mijuu) ስለሚቆጠር እሱንም በዙር በመቅመስ እየመረቁ ያስቀምሳሉ። በመጨረሻም ሰውዬው ትንፋሹ መለስ ብሎለት ቀና እንዳለና እንደተሻለው ከሰሙት ታሪክ ገለጸውልኛል። (አለማየሁ አድማሱ፣የሀሩ ቀበሌ ነዋሪ፣ዕድሜ 45፣14/5/2007)

ከዚህ የፋጭ ከበራ የተገነዘብኩት ለፋጭ ክዋኔ መኖር፤ ማህበረሰቡ ከእምነቱ አኳያ ጨቡ ናቸው የሚሏቸውን የማይጣሱ ትዕዛዛት ወይም ህግጋቶች መጣሳቸው እንደሆነ ነው። ስለዚህ በፋጭ ከበራ አካሄድ መሰረት እንደሚከተለው መከወኑን ያሳየናል። ይኸውም፡-

**በቅድመ-ፋጭው፡-** በዚህ የሂደት ደረጃ የሚከወነው የፋጭው ቅድመ-ክዋኔ ሂደት ሲሆን ነው። ይኸውም፡- በመጀመሪያ ደረጃ ፋጭውን የሚከውኑ፡- ወዩዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችን (የሚመለከተውን አካል) መርጦ መሰየም፣ የሚመለከታቸው የተባለበት ምክንያት፡- እንደ ችግሩ ቅለትና ክብደት በአባቃሉ፣ በአባገዳ፣ በሀዩ ወይም ሀገር ሽማግሌዎች የሚያዙ ጉዳዮች ስላሉ ነው። ከዚያ ሽማግሌዎቹ በተሰራው ጨቡ ምክንያት በቀጥታ ችግር ላይ የወደቀውን አካል የመለየት(የማወቅ)ና በተሰየሙት ሽማግሌዎች አማካይነት እግዚሐብሄርን በመጀመሪያ ለዚህ ስላበቃሄን ምስጋናችን ይድረሰህ፣ አሁን ደግሞ ለበደልንህ ንስሀችንን ተቀበለን፤ ይቅርም በለን፣ አንደበታችንን ክፈትልን፣ እውነትን አናግረን በማለት የመክፈቻ ጸሎት እየተቀባበሉ የሚያደርሱበት ሂደቶችን ያካትታል። ከዚያም ወደሚቀጥለው የፋጭ ደረጃ ይሸጋገራሉ።

**ፋጭ፡-** በፋጭ የሂደት ደረጃ ሽማግሌዎቹ ለፋጭ የተዘጋጀውን ሰው በስም በመጥራት ምን ተቸግሮ እንደጠራቸው ይጠይቁታል። ተጠያቂውም በመጀመሪያ ይቅር በሉኝ በማለት ለመናገር ፍቃድ ይጠብቃል። ከዓይን ትረፍ (mucuca'i/hobba'i) ቀጥል ይሉታል። ከዚያ በቤታቸው ውስጥ ልጅ አላድግ ብሏቸው ይሆናል፤ አለያም ድርስ ላም፣ ፈረስ እየሞተባቸው ተቸግረው ይሆናል፣ የመኪና አደጋና ከመሳሰሉት ውስጥ አንዱን በተደጋጋሚ እንደደረሰበት ያስረዳል። በመቀጠል «የሆነ ጨቡ ስለሰራሁ እንጂ እግዚሐብሄር እንዲህ አድርጎ የሚቀጣኝ» በማለት ይገልጻል። ሽማግሌዎቹም ችግሩን በጽሞና ካዳመጡ በኋላ እየተቀባበሉ ጉዳዩን ያጣራሉ። ይኸውም ከእግዚሐብሄር ህግጋት ውስጥ የቱን በመጣስ ነው ጨቡ የተሰራው?፣ ጨቡውን በማወቅ ነው ባለማወቅ የተሰራው?፣ ለፋጭ የተነሳሳው በሰራው ጨቡ በወቅቱ ተፀፅቶ ነው?

ወይስ ችግሮቹ በመደጋገማቸው ፈርቶ ነው? የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጥያቄዎች አንዱ የረሳውን ሌላው እያነሳ ያጣራሉ። ለዚህም እንደምክንያት የሚያቀርቡት እግዚሐብሄር የእውነት አምላክ ነው። ስለዚህ እውነቱን ከስር አጣርተን በአግባቡ ስንለምነው ይታረቀናል ብለው እንደሚያምኑ መረጃ አቀባዮቼ ይገልጻሉ።

ከዚያ ሽማግሌዎቹ ጉጂ ሳፉ ያውቃል። ላገ ያውቃል። አንተ ግን ይህን ጣስኩ አልከን። አንደኛው ሽማግሌ ‹‹ትሰሙ የለም?›› ይላል።

ሌሎቹ ሽማግሌዎች ደግሞ ‹‹አዎ! ሰማን፤ ለምን ይጥሳል?››

አንደኛው ሽማግሌ ቀበል አድርጎ ‹‹አግባብ አይደለም።›› ሲል

ሌሎቹ ሽማግሌዎች ደግሞ ‹‹ለዋቃስ?›› ይሉና ሁሉም በአንድነት ‹‹እውነት አለው። ፈጣሪ ሆይ ታረቀን።›› ይላሉ። በዚህ መልኩ አንድ በአንድ ፋጭውን ያካሂዳሉ።

እግዚኣብሔር በመጀመሪያ ይህን አድርጉ፤ ይህን ደግሞ አታድርጉ ብሎ በቃሉ አማካይነት ለምዕመኑ ትምህርት ተሰጥቷል። ስለዚህ አታድርጉ ያለውን ማድረግ ጩቡ ነው። ከዚህ በመነሳት የዋቃ ቅጣት አግባብ ነው፤ነገር ግን መሐሪ ነውና ይቅር ይበለን እያሉ በዳዩንና ተበዳዩን ያስማማሉ። በዚህ አውድ ተበዳዩ እግዚኣብሔር ነው። ስለዚህ እግዚሐብሄር ሆይ ታረቀው፤ ይቅር በለው። በማለት ሽማግሌዎቹ በመቀባበል የፋጭውን ሂደት ያስፈጽማሉ። ጩቡ የተሰራው በተደጋጋሚ ከሆነ ለእያንዳንዱ ጩቡ ከላይ ባየነው መሰረት የፋጭ ከበራ ተራ በተራ መከወን እንዳለበት ይገልጻሉ። በመጨረሻም ወደ ድህረ-ፋጭ ሂደት ይሸጋገራሉ።

**ድህረ-ፋጭ:-** እንደየጩቡው ዓይነትና መጠን ቦካ፣ ቡና ቃላና ቅቤ እንዲሁም የመስዋዕት ኮርማ ተዘጋጅቶ የዚህ ዓይነቱ አደጋ ከዚህ ሰው፣ ከዚህ ቤት፣ ከዚህ ቤተሰብ ራቅ (ati hanqadhu), ዳግም አይመልስህ (lammuu si hindeebisin) በማለት በጎንዶሮ ከበራ የሚያሳርጉ አሉ።

ባጠቃላይ እንደጉጂ ኦሮሞ ልምላሜ፣ ጤንነት፣ ጥጋብ ሊኖር የሚችለው የእግዚሐብሄር ህግጋት ሲከበር እንደሆነ ያምናሉ። ነገር ግን ህግጋቶቹ ተጥሰው፣ ነገሮች በተሳሳተ መንገድ ከተከናወኑ እነኚ የተጠቀሱት ጥጋብ፣ ሰላም፣ ልምላሜና የመሳሰሉት ሁሉ አይኖሩም ተብሎ ይታመናል። የዚህ ዓይነት ክስተት ሲፈጸም በቅድሚያ ምክንያቱን የማጣራት ሂደት ያከናውናሉ። ይኸውም ጉጂ ኦሮሞ በመጀመሪያ ለዚህ ችግር ምን ሀጢያት ብንሰራ ነው ይህ የሀጢያት መገለጫ ሊከሰትብን የቻለው በማለት ያጣራሉ። ችግሩ ሰውን መበደል፣ መስረቅ፣ ሳፉ ያለማክበር፣ ቀድሞ ይከወን የነበረ ከበራን ወደ ጎን መተውና ከመሳሰሉቱ ውስጥ አንዱን

ወይም ከዚያ በላይ ተፈጽሞ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያን በኋላ ለዚያ ጉዳይ ኃላፊነት የሚወስድ አካል ተፈልጎ ግለሰብ/ቡድን የፋጭ ከበራ ይካሄዳል፡፡ ብዙን ጊዜ የፋጭ ከበራ የሚካሄደው ሰዎች ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ሲገቡ ነው፡፡ ይኸውም፡- በግለሰቦች ደረጃ በጣም ታመው ሲያጣጥሩ፣ በወልድ ወቅት ምጥ ጠንቶባት ነፍስ ውጭ፤ ነፍስ ግቢ ሲሆን፣ በሚወዱት ነገር ላይ ተደጋጋሚ አደጋ ሲደርስና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እንደ ቡድን ወይም ማህበረሰብ ደግሞ ከብቶቻቸው ባልታወቀ በሽታ ሲጠቁ፣ የእርባታው መጠን እየቀነሰ ሲሄድ፣ የግጦሽ ሳር እጦት፣ የተዘራው እህል ምርት ማነስ፣ የሰዎች ባልታወቁ በሽታዎች መሞትና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመቀጠል ያን የበደሉት ነገር በፋጭ የሚስተካከልበትን መንገድ በማሳየት ቀጣዩ ጊዜ እንደቀድሞው እንደሚሆንላቸው ያምናሉ፤ያም ካልሆነ ችግር የእግዚሐብሄር ስራ ነው ብሎ በፀጋ ይቀበላሉ፡፡ አሊያም«እግዚሃብሄር ከእኛ ዘንድ ርቋል» በማለት በራሳቸው ስራ በመፀፀት በጸሎትና መስዋዕት በማቅረብ የእግዚሐብሄርን ምህረት ይጠባበቃሉ፡፡

ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ከመስኩ ልምላሜ፣የጥጆችና ሕጻነቱ ፋፍተወ መቦረቅ፣ የጎተራ በእህል መሙላትና የመሳሰሉት እግዚኣብሔር ከእነሱ ጋር እንዳለ አመለካች ነው፡፡ በተቃራኒው አካባቢው በድረቅ ተመቶ፣ ጥጆችና ልጆች በመቦረቅ ፈንታ ኩስምን ካሉ፣ጎተራው ከሳሳባቸውና የመሳሰሉ ክስተቶችን ደግሞ ከሚያዩት ነገር ተነስተው እግዚኣብሔር እንደተቀየማቸው፤ ፊቱንም ከእነሱ ላይ እንዳዞረ አድርገው ያምናሉ፡፡

ባጠቃላይ ይህ የፋጭን ከበራ ያየን እንደሆነ የጉጂ ኦሮሞ ከደረሰበትና ከሚደርስበት ችግሮች መውጫና ከፈጣሪው ጋር የሚገናኝበት ማህበረሰባዊ ዕውቀት ነው፡፡ ለዚህም ክዋኔ ደንብና ስርዓት አበጅተውለት በዚያ ስርዓትና ደንብ በመመራት ይከውናሉ፡፡ ይህን ዕውቀት ከኦበጀክቲቭዝም ኢፒስቲሞሎጂ አተያይ ስንመለከተው በአቅራቢያቸው የማይታያቸውን እግዚኣብሔር፣ በሚታዩ ምድራዊ ክስተቶች መገለጫነት ተግባቦት መፍጠር ችለዋል፡፡ ከነዚህ የተግባቦት መንገድ አንዱ ደግሞ የፋጭ ከበራ ነው፡፡

## 6.5. የቃሉ ስያሜ ከበራ

ቀደም ሲል እንዳየነው ስለቃሉ ስያሜ አሰጣጥ በተነሳበት ወቅት አንድ ወደ ስልጣነ-ሢመት የሚመጣ የቀድሞው ቃሉ ልጅ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ካለ የስያሜ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይፈጸሙለታል፡፡ ስለዚህ ከመረጃ አቀባዮቼ ባገኘሁት መረጃዎችና የ16ኛው አባቃሉ

አጋ ሳቆ ጋብቻና ስያሜ ከበራዎች እንደ ንጥል-ጥናት በመመርመር ከዚህ በታች ለመተንተንና መግለጽ ችያለሁ።

### 6.5.1. የቃሉ ጋብቻ ከበራ

ቃሉ እንደማንኛውም ኦሮሞ ከባህላዊ ጋብቻዎች ውስጥ በማጨት (kadhaan /naqataan) ስርዓት የሚከናወነውን ጋብቻ ይፈጽማል። ነገር ግን የስነ-ስርዓቱ ሂደት ለሌላው የማህበረሰብ ክፍል ከሚደረገው የተለየ ነው። ለዚህ እንደማሳያ የ16ኛውን ቃሉ የጋብቻ ሂደትና ሃይማኖታዊ እሴቱን ከዚህ በታች እናያለን።

የአባቃሉ አጋ ሳቆ ለጋብቻና የስልጣነ-ሢመት ሃይማኖታዊ ከበራ የመጀመሪያው ምክንያት የእሱ አባት የነበሩት 15ኛው አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ነው። ጉጂዎች አንድ ቃሉ ከዚህ ዓለም በሞት ስለይ «ሞተ» አይሉም፤ «ምራቁን ዋጠ» (hancufa liqimse) ይላሉ። የአሁኑ አባቃሉ አጋ ሳቆ የተመረጠው ታዲያ ቀደም ሲል ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ የመጀመሪያ የሆነውን ከእናቱ ከገለልቻ ጎሳ ካገቧት ባለቤታቸው የተወለደ መሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሌለሎችንም መስፈርቶች ስላሟላ ነበር።

በሌላ በኩል ለቃሉ የወደፊት የትዳር አጋሩ እንድትሆን የምትመረጠው ልጃገረድ ከጉጂ ኦሮሞ ጎሳዎች ውስጥ የገለልቻ ጎሳ ልጃገረድ መሆን አለባት። ምክንያቱም ቃሉ ከሰማይ ወረደ በተባለ ወቅት በተለያዩ ሰዎች ለማነጋገር ተሞክሮ ነበር። ነገር ግን ለማንም ምላሽ አልሰጠም ነበር። በመጨረሻም ከገለልቻ ጎሳ ወገን የሆነች ልጃገረድ ስትመጣ ፈገግታ እንዳሳያትና በመጨረሻም ሁለቱም አብረው መኖር እንደጀመሩ፣ ልጆችም እንዳፈሩ በምዕራፍ አምስት ስር በቀረበው ሚት ውስጥ ለማየት ችለናል። ታዲያ ይህ የገለልቻን ልጃገረድ መረጣ ከዚህ ሚት ተከትሎ የመጣ ነው።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የቃሉ ጋብቻ ሃይማኖታዊ ከበራን የምንመለከተው በመተጫጨት ላይ በተመሰረተው ባህላዊ የጋብቻ ዓይነት ላይ ነው። ይህ የመተጫጨት ሂደት እስከ ጋብቻው ዕለት ድረስ የተለያዩ ስርዓቶችን ተከትሎ የሚፈፀም ነው። ይኸውም፡- በመጀመሪያ ለትዳር አጋር የምትሆነውን ልጃገረድ መረጣ ይካሄዳል፣ በመቀጠል ማጨት፣ ከዚያም የሴቷ ቤተሰብ ምክክር ያደርጋል፤ በመጨረሻም እሽታውን ተከትሎ ጋብቻው ይፈፀማል::እነዚህን ሂደቶች ምን እንደሚመስሉ ከዚህ በመቀጠል አንድ በአንድ እንመለከታለን።

ከላይ እንደተገለጸው በማጬት ሂደት የሚከናወነው ባህላዊ ጋብቻ በስሩ የተለያዩ ክዋኔዎችን በቅደም ተከተል ይታለፋሉ። እነሱም፡-

### i. ልጃገረድ መረጣ

ልጃገረድ መረጣ ሲባል ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አንድ ለአቅመ-አዳም የደረሰ ልጅ በባህሉ መሰረት የወደፊት የትዳር አጋር ልትሆነው የምትችል ልጃገረድ መምረጥ የወንዱ ቤተሰብ መብት ነው። ለቃሉ የምትሆነውን ልጃገረድ ግን የሚመርጠው እራሱ ወይም የእሱ ቤተሰብ ሳይሆን፤ ህዝብ (kolbaa) ነው። ከማህበረሰቡ ውስጥ እንዲሁም ከገለልቻ ጎሳ ልጃገረዶች ውስጥ የትኛዋ ብትሆን ትሻላለች ብለው፤ በባህሉ መሰረት የሚመርጡት አባገዳዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ካሎዎችና የጎሳ አባላት ናቸው። እነዚህ ከቃሉ ጋር በመገናኘት መረጃዎችን ይለዋወጣሉ። ከዚያም እኔ ከገለልቻ ጎሳ ወገን የሆነች መልካም ልጃገረድ አግኝቻለሁ ከሚለው ሰው መረጃ ይደመጣል። ከዚያ ለጊዜው በምርጫው ከተስማሙ ዕጣ-ፈንታ (faroo) ታይቶ፣ እግዚሐብሄርን ተለማምነውና ጠይቀው፣ ስለጉዳዩ የታዩ ህልሞች ተፈተው፣ ከሰሙትና እግዚሐብሄር ካመላከታቸው ላይ ተመርኩዘው ይመርጣሉ።

ለቃሉ ባለቤትነት የምትታጬው ልጃገረድ ማሟላት ያለባት መስፈርቶች አሉ። ይኸውም፡- ከገለልቻ ጎሳ ከመሆኗ በተጨማሪ ከነክብረ-ንጽህነዋ የቆየች (quttoo kan qabdu)፣ መልካም ፀባይ ያላት፣ ባህልና እምነቷን ጠብቃ የኖረችና ጨዋ የጨዋ ቤተሰብ ልጅ መሆኗንና የመሳሰሉት ሁሉ ይታያሉ። በመጨረሻም የእገሌ ልጅ ትሆናለች ተብሎ ከተስማሙ በኋላ ልጅቷን ለማጬት የሚሄዱበትን ዕለት ወስነው ይለያያሉ።

### ii. ማጬት

በጉጂዎች ዘንድ በባህላዊ ጋብቻ ውስጥ የሴቷ ወገን ለልጃቸው የትዳር አጋር እንዲሆናት ከወንዱ ወገን ጥያቄ ሲቀርብላቸው በቀጥታ የሚገቡት ስለማንነቱ ከማወቁ ላይ ነው። ይኸውም፡- ጎሳው፣ መተዳደሪያውን፣ እምነቱንና የመሳሰሉትን በመጠየቅ ለዝምድና የቀረበላቸውን ጥያቄ የመቀበል፤ አሊያም ውድቅ የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ። ነገር ግን በቃሉ በኩል ለመጡ ሽማግሌዎች እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች አይቀርቡም። ምክንያቱም በጎሳ በኩል ለሚነሳው ጥያቄ ከቃሉ ቤተሰብ የበለጠ እንደሌለ ይናገራሉ። በንብረትም በኩል ከሆነ የእሱ ንብረትና ለእሱ በስጦታ መልክ የሚበረከትለት ተቆጥሮ መዝለቅ እንደማይቻል ያውቃሉ። ስለዚህ ለአባቃሉ የወደፊት ባለቤት የሚያጬት፡- የቃሉ አጎት፣ አባገዳዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ካሎዎች ፈጣሪያቸውን ተለማምነው፣ የታያቸውን ህልም ፈተው፣ ዕጣ-

ፈንታቸውን (faroo) እያዩ ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ጉዞ ያደርጋሉ። ከዚያም እንደደረሱ በኦሮሞ ባህል መሰረት የልጅቷን ቤተሰብ ሰላምታ በመጠየቅ የመጡበትን ጉዳይ ይገልጻሉ። የልጅቷም ቤተሰብ ከቃሉ ወገን የቀረበላቸውን ጥያቄ በታላቅ ክብር ይመለከቱታል። እንደባህሉ ልጃቸውን ለመከልከል ያልሆኑ ምክንያቶችን መደርደር የለባቸውም። ይሁን እንጂ እንዲያው ለወጉ ተብሎ «ከዘመድ ተማክረን፣ ዕጣ-ፈንታ አይተን መልስ እንሰጣለን»በማለት በቀጠሮ ይለያያሉ።

### iii. የቤተሰብ ምክክር

እንደ ጉጂ ኦሮሞ አንድ ሰው ልጃችሁን ለልጄ ብሎ ከጠየቀ፤አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎችን በመጠየቅ ዝምድናውን የሚከለክል ጉዳይ ከሌለ ወላጆቿዋ ጋብቻው ለብቻቸው እሺ አይሉም። ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ያሉ ዘመድ አዝማድ ተጠርቶ በጉዳዩ ይመክሩበታል። ሲተርቱም“worri marii qabu jibicha qalate, kan marii hinqabne immoo, raada qalate.” ይላሉ። ይህም «ተማክረው የፈሉት...» እንደማለት ነው። ታዲያ የልጂቷ ቤተሰብ ቀደም ብሎ ይጠራራና ልጅቱን እንስጥ ወይም አንስጥ በሚሉት ሀሳቦች ላይ ሳይሆን የሚመካከሩት፡- «ሀላፊነቷን በአግባቡ ትወጣለች?» የምል ሀሳብ ላይ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

በቀጠሮው ዕለት ከቃሉ ወገን ሽማግሌዎች ይሄዳሉ። በአዳራቸውም ሆነ በመንገዳቸው ላይ የታያቸውን ዕጣ-ፈንታ እያጤኑና እየፈቱት ይጓዛሉ። እዚያም እንደደረሱ እንደተለመደው የእግዚሐብሄር ሰላምታ በመስጠት «እኛ መልካም መልካሙን እያየን ነው የመጣነው። እናንተስ ምን ታያችሁ?» በማለት ይጠይቃሉ። የልጅቷም ቤተሰብ «እኛም ያየነው መልካም ነው፤ ነገር ግን ልጃችን የሀዳ አንባነቱን ኃላፊነት እንዴት ልትወጣው ትችላለች የሚል ስጋት ፈጥሮብናል።» በማለት ቅር የተሰኙበትን ነገር ያቀርባሉ።

የቃሉ አጎት «ይህን ክፍተት የመሙላቱን ጉዳይ እኔ እወጠዋለሁ። የቀደሞዋ የአንባ እናት ታስተምራታለች፤ አስተምራታለሁ።» በማለት አደራውን ለመረከብ ቃል ገቡ።
ከዚያ በኋላ የልጅቷ ቤተሰብ ለዝምድና የቀረበላቸውን ጥያቄ መቀበላቸውን ገለጹ። በመቀጠል ለሽማግሌዎቹ የተዘጋጀ ሙሉ መጠጥ (Mijuu) ቀረበ። ሁለቱም ወገን ደስታቸውን በጭብጨባ ገለጹ። ባህላዊ ጭፈራም ይጨፍሩ ገቡ።

በመጨረሻም የጋብቻውን ዕለት መወሰን ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ የሚሆነው ከቃሉ ወገን በመጡት ሽማግሌዎች አማካይነት ነው። ይኸውም የጋብቻውን ዕለት ሞራ አንባቢዎች፣ ኮከብ ቆጣሪዎችና ሽማግሌዎቹ አብረው ተቀምጠው ቀኑን፣ ወሩንና ዓመቱን መቸ መሆን እንዳለበት

ፈጣሪያቸውን በመጠየቅ የሚወሰን ይሆናል። ከዚያም ለልጅቷ ቤተሰብ ወቅቱ እንደደረሰ እንደሚነገራቸው ተገልጾ በቀጠሮ ይለያያሉ።

iv. የጋብቻ ስነ-ስርዓት

በቃሉ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ላይ አግቢው ከአጃቢዎቹ ጋር አብሮ በመታደም ወደ ልጅቷ ቤት አይሄድም። ቃሉ በጉጂ ማህበረሰብ ዘንድ በሀገረሰባዊ ሃይማኖቱም ሆነ በባህሉ በኩል ከፍተኛ ከበሬታ አለው። ስለዚህ ቃሉ ልጃገረድ ከመምረጥ አንስቶ እስከ ጋብቻው ስነ-ስርዓት ድረስ ያለው ሂደት ላይ አይሳተፍም፤ ከቤተ-አምልኮው (galma) አይንቀሳቀስም። ከአባቃሉ አጋ ሳቆ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ላይ ለማየት እንደተቻለው፡- የቃሉ አጎት፣ የቃሉ እህት፣ አባገዳዎች፣ ካሎዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የቅርብ ዝምድና ያላቸው በአንድ ላይ ሆነው ከሙሽራዋ ቤተሰብ ዘንድ በመሄድ ሙሽሪትን ይዘው፣ እየጨፈሩ ይመጣሉ።

በዚያን ዕለት አባገዳዎች፣ ካሎዎችና የሀገር ሽማግሌዎቹ ጎንፋ (gonfaa) እና ቡሉኮ መሳይ (ejja) የሚባሉ ባህላዊ አልባሳታቸውን ለብሰው፣ አባገዳዎችና ካሎዎች በተጨማሪ በግንባራቸው ላይ ካላቻ አስረው፣ቦኩ (bokku) ይዘው፣ የቃሉ እህት ደግሞ የጉጂ ልጃገረድ ባህላዊ ልብስ የሆነውን ቆሎና ቆሜ (Qoloofi qomee) ለብሳ፣ ጸጉሯን ባህላዊ ሹሩባዋ ተሰርታ፣በላዩ ላይ ልክ እንደ አንቴና የሚቆም የልጃገረድነት ምልክት የሆነውን ቁቶ (quttoo) አድርጋ ከእነሱ ጋር ትሳተፋለች። ለሙሽሪቷ የሚሰጥ ቡሉኮ (ejja) በመያዝ፣ ሌሎቹ ደግሞ ለልጅቷ ቤተሰብ የሚሰጥ ስድስት ጥጃዎች በመንዳት ይወሰዳል። ከባህሉም አኳያ መኬድ የነበረበት በእግር ሲሆን፤ ከቦታው ርቀት የተነሳ በመኪና እንዲጓዙ ተደርገው፤ ወደ ሙሽሪት ቤት ሲቃረቡ በስርዓቱ መሰረት እየተጨፈረ ከደጃቸው ሲደርሱ የእሷ ቤተሰብ በገበቴ ቦካ (ጠጅ) ሞልተው ጠጋ ብለው ይቀበሏቸዋል። ይህ ክዋኔ ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም አኳያ ስንመለከተው የመጡበት ጉዳይ እንደተሳካና መልካም ምኞት መግለጫ ተደርጎ ይቆጠራል። ከቃሉ ወገን ለሄዱት ደግሞ የሄዱበት ጉዳይ መሳካቱን አመላካች እንደሆነ ይቆጠራል። ከዚያ ሽማግሌዎቹ ደግሞ ቃሉን የሚያሞግሱ ጭፈራዎችን እየጨፈሩ ይጠጋሉ። ከዚያም ያንን ሙሉ ጠጅ ከአማቻቸው እጅ በመቀበል ይዘዋቸው በመጡት ጥጆች ጀርባ ላይ እንትፍትፍ (biifee) እያሉ፤ እርቡ! በረት ሙሉ! በማለት ይመርቋቸዋል።




ፎቶ፡-16 ከመሀል የቃሉ እህት፣ ከበስተቀኟ ሁለተኛው የቃሉ አጎት፣ ከበስተግራ ገዳ ሀልቻዬና ሌሎችም ስጦታዎቹን ይዘው ሙሽሪትን ለማምጣት ሲሄዱ፡፡

የልጅቷም ቤተሰብ የመጡትን እንግዶች በአክብሮት ወደ ውስጥ እንዲዘልቁ በማድረግ ይጋብዟቸዋል፡፡ ሙሽሪትን ከጓዳ ይዛት የምታወጣት የቃሉ እህት ናት፡፡ ምክንያቱም ከጋብቻው ቀን ቀደም ብሎ የቃሉ አጎት መጥቶ ቁንቢ ስላሰቀመሳት ሌላ ሰው ሊይዛት አይችልም፡፡ ስለዚህ የቃሉ እህት ይዛ የመጣችውን ቡሉኮ የሙሽራዋ ትከሻ ላይ ጣል አድርጋ ይዛት ትወጣለች፡፡

ሙሽሪትን ቤተ-ዘመዷና የአካባቢው ሴቶች ቅቤ አምጥተው እየመረቋት ይቀቧታል፡፡ የቅቤው ተምሳሌት እርጥበትን አመላካች ነው፡፡ መሀጸኗ እርጥብ እንዲሆኖ፤ልጆች እንድታፈራ መልካም ምኞት መግለጫ ነው፡፡ የልጅቷ እናት ደግሞ ሲቄ፣ ቦራቲ፣ በቅል እርጎ፣ የፊት ቅቤ፣ ቡና ቃላና እርጥብ ሳር ታስዛታለች፡፡ የሲቄው ተምሳሌት ከልጃገረድነት ወደ ሴትነት መቀየር እየሄደች እንደሆነና ከጋብቻ በኋላ የምትይዘው መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ቅቤው፣ ቡና ቃላውና እርጥቡ ሳር ደግሞ የሙሉነትና ልምላሜ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በመቀጠል አጃቢ ሽማግሌዎቹ ሸኙን ይላሉ፡፡ የልጅቷም ቤተሰብ በሰላም ግቡ በማለት ያሰናብታሉ፡፡ ሙሽሪትም ባህላዊ አልባሳቷን ለብሳ፣ የቃሉ እህት ቀኝ እጇን ይዛ፣ አጃቢዎቹ እነሱን መሃል አርገው ቃሉን እያወደሱ በመጨፈር ወደ ቃሉ ተቋም ጉዞ ይጀምራሉ፡፡

በመጨረሻ ወደ ቃሉ ተቋም ሲቃረቡ ከተለያዩ ቦታ በዝግጅቱ ለመታደም የመጡ አዛውንቶች፣ ሴቶችና ወጣቶች አካባቢውን በማጥለቅለቅ እንደየደረጃ እኩዮቻቸው በቡድን በቡድን እየሆኑ በባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎች መንደሩን እያቀለጡ ይጠብቃሉ፡፡ ቃሉ ደግሞ በቤተ-አምልኮው ውስጥ በመጋረጃ በተጋረደ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ ይጠባበቃል፡፡ ከዚያም የእነሱን መምጣት እንዳወቀ ወደ ደጃፉ ጠጋ ብሎ ይቆማል፡፡ በመቀጠል አጃቢዎቹ ቃሉ እንትፍትፍ በልብን (Qaalluu biifi)፣መርቀን (Qaalluu eebbis) እያሉ በመጨፈር ሙሽሪትን ወደ ገልማው ያስጠጋሉ፡፡ ለሙሽሪቷ የተዘጋጀችውን ጊደር ይሰጧትና የዚያች ጊደር ጭራ ይዛ፣ ከቤተሰቦቿ የተሰጣትን ስጦታዎች እንደያዘች የቃሉ እህት ቀኝ እጇን ይዛ ለቃሉ ታስዘውና ተያይዘው ወደ ውስጥ ይገባሉ፡፡ የዚያችን ጊደር ጭራ ይዛ ወደ ውስጥ እንድትዘልቅ የሚደረገው ተምሳሌታዊ ትርጉም አንደኛው ይቺ ጊደር የዚያ ቤት የመጀመሪያዋ ስጦታ መሆኗን አመላካች ናት፡፡ በሌላ በኩል በባህሪያቸው በማመሳሰል የልጃገረድነቷ መገለጫም አድርገው ያዩታል፡፡ በመቀጠል የጫቁላ ስነ-ስርዓቱ (quttoo kaasuu) ይፈፀማል፡፡

በመቀጠል ሙሽሪትን ከጋብቻው በፊት በቃሉ አኅት አማካይነት ቁንቢ እንድትቀምስ የሚደረግበት ምክንያት እሷም ከጋብቻዋ ዕለት አንስቶ ከቃሉ ጋር ስትኖር ውሸት ላለመናገርና ከኀኑ ሆና አብራው ለመስራት ቃል የማስገባት ስርዓት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በከበራ ውስጥ አንድ ሰው በፊት ከነበረበት ደረጃ ወደ ሌላው የሚያደርገው ሽግግር ነው፡፡ ይኸውም ሙሽሪቷ ቁንቢውን ከቀመሰችበት ዕለት አንስቶ ከተራ ምዕመንነት ወደ ቅዱስ ሰውነት ተሸጋግራለች ማለት ነው፡፡

የጉጂ ቃሉን የጫቁላ ስነ-ስርዓቱ (quttoo kaasuu) ከተመለከትን ከቦረና ቃሉ ለየት እንደሚያደርገው በምዕራፍ አምስት ስር ተመልክተናል፡፡ የጉጂ ቃሉ የሙሽሪቷን ክብረ-ንጽህና የሚወስደው እራሱ ነው፡፡ የነገው አባቃሉ የሚወለደውም ከዚች ሴት እንደሆነ ከቃሉ አመጣጥ ሚት እንረዳለን፡፡ እንደ ጉጂ ኦሮሞ አተያይ ቃሉ በባህሪው ከሌላ ሰው ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ከፈጸመች ሴት ጋር ግንኙነት አይፈጽምም፡፡ በኦሮሚያ «Qaalluun dubartii namni biraa tarkanfate, hintarkanfatu.» ማለትም የጉጂ ቃሉ ሌላ ሰው የተገናኛትን ሴት አይገናኛትም ለማለት ነው፡፡

የቃሉን ስልጣን በዘር ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ነው ካልን የጉጂው ቃሉ የመጀመሪያ ሚስቱን የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማድረጉ፣ ስልጣኑን ከእሱ ወደ ልጁ እንዲተላለፍ ማስቀጠያው መንገድ መሆኑን እንረዳለን።

## 6.5.2. የቃሉ ስያሜ ክበራ ሂደት

ለቃሉ ስም የምሰየምለት ሁለት ጊዜ ነው። ይኸውም፡- አንደኛው እንደተወለደ እንደ አንድ የጉጂ ወንድ ልጅ በአራተኛው ቀን የተፀኦ ስም ይሰየምለታል። ሁለተኛው ደግሞ ስልጣኑ-መለኮቱን ሲያጸድቁለት የሚኖረው ስያሜ ነው። ከቀድሞው ቃሉ ሞት በኋላ ለተተኪው ልጅ ቃሉ ለመሆኑ የማጽደቅ ክዋኔ አለ። አዲስ ቃሉ የሚሆነው ልጅ ቀደም ሲል ያየናቸውን መንፈሳዊና ሰዋዊ መስፈርቶችን ካሟላ በኋላ የመጨረሻ ጋብቻ መፈጸም አለበት። የጋብቻውን ሁኔታ በ 6.5.1. ስር በዝርዝር ተገልጿል። ከዚያ በመቀጠል የአዲሱ ቃሉ አጎት በጋብቻው ማግስት ከተሰያሚው ጎን በመቀመጥ እንደ ባህላቸውና እምነታቸው መሰረት ለታዳምዎቹ ጥያቄ ያቀርባል። ከአደራሹ የሚገኙት ታዳሚዎችም በተራቸው በማጽደቅ መንፈስ ምላሽ ይሰጣሉ። ክዋኔውም ከቃሉ አጋ ሳቆ ስያሜ ከአውዱ ላይ ለመመልከት እንደተቻለው የሚከተለውን ይመስላል።

| <u>Abbaan (wasiilli ykn abuyyaan)</u> | <u>Jamaan</u> |
|---|---|
| Ani ilmaaf maqaa baafadhaara anaa-dhaga'aa. | Ilmi si'iif guddatu;guddatee si'ii uddo'u. |
| Ani ilmaaf maqaa Aagaa baafadhaara-anaa dhaga'aa. | Aagaan si'iif guddatu; guddatee si'ii uddo'u. |
| Ammalle intalaaf maqaa baafadhaara-anaa dhaga'aa. | Intalti si'iif guddattu;guddattee si'iif uddoottu. |

ሲተረጎም፡-

| <u>ስያሚው (አጎቱ)</u> | <u>ታዳሚው</u> |
|---|---|
| እኔ ለወንድ ልጅ ስም ላወጣ ነውና-አድምጡኝ። | ልጁ ይደግልህ፣ አድጎ ላንተ ጥሩ ይሁንልህ። |
| እኔ ለወንድ ልጂ አጋ ብየ ስም ላወጣ ነውና አድምጡኝ። | አጋ ይደግልህ፣ አድጎ መልካም ይሁንልህ። |
| አሁንም ለሴት ልጁ ስም ላወጣ- ነውና አድምጡኝ። | ልጅቷ ትደግልህ፣ አድጋ መልካም ትሁንልህ። |

በማለት እሱን በቃሉነት፣ እሷን ደግሞ በሀዳ አንባነት ስያሜው ይጸድቃል። ከዚያን ዕለት አንስቶ ይህ ስም ለሕዝቡ ይለፈፋል። ከዚያን ዕለት አንስቶ ማህበረሰቡ በዚያ ስም አባ ቃሉ አጋ ብለው ይጠሩታል።

### i. እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ልጅ ከሌለ ምን ይደረጋል?

አቶ ሞኮና ይህ የተጠቀሰውን መስፈርቶች የሚያሟላ ልጅ ካለ የአስር ዓመት ልጅም ቢሆን ይሰየማል፡፡ ነገር ግን ልጅ እግር ከሌለ ከትላልቆች ውስጥ ሊመረጥ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም፡-

> እንደ ምሳሌ አድርገን የአባቃሉ ሳቆ ናጋኦን ጋብቻ እንመልከት›› አሉኝ አቶ ሞኮና፡፡ *ከአባቃሉ ኢጋ ሳቆ በፊት የነበረው የሱ አባት፣ የኔ ደግሞ ወንድሜ የነበረው አባቃሉ ሳቆን ናጋኦ ይባላል፡፡ ከአባቃሉ ናጋኦ ቶቴ ነው የተወለደው፡፡ የተወለደ ቀን ከነክረጥት ተሸፍኖ ነበር የተወለደው፡፡ የተቀሩትንም መስፈርቶች ያሟላ ነበር፡፡ ነገር ግን፣አባቃሉ ናጋኦ ቶቴ በሕይወት እንዳሉ እሱ ለአቅመ አዳም ደረሰ፡፡ እንደባህላችን ተዳረ፡፡ ከዚያም የራሱን ሕይወት ይኖር ጀመረ፡፡ ከጉጂ ብሔር በተጨማሪ ከሌላም ብሔር ሚስት አግብቷል፡፡ ታዲያ እኝህ 14ኛው አባቃሉ ሲያርፉ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ካላገቡት መካከል መስፈርቶቹን የማሟላው እኔ ነበርኩ፡፡ አባታችን ጠርቶኝ እጄን ይዞ መረቀኝ፡፡ ህብረተሰቡንም እንዳስተዳድር ወከለኝ፡፡ እኔ ግን ይህ ኃላፊነት እሳት ነው፤ያቃጥላል፡፡ እውነት መናገር ይጠበቅብሃል፡፡ ሌላ ‹ሰው የተራመዳትን ሴት መራመድ› የለብህም፡፡ ስለዚህ በብዙ በኩል ካንተ የሚጠበቁትን ማሟላቱ ትንሽ ከብዶ ስለታየኝ እንቢ አልኩ፡፡ ስለዚህ በባህላችን ቀደም ሲል እንደሚደረገው ሁሉ ከልጆች ውስጥ ሲታጣ ከትላልቆቹ መስፈርቱን የሚያሟላ ይሰየማል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቀድሞዉኑ እሱን ስለመረጠና ስላዘጋጀው ነው፡፡ አሉኝ ከዚያ በኋላ ቃሉ የሚሆን ሰው ማንነቱ ከታወቀ በኋላ ለስያሜ ስርዓት ዝግጅት ይጀመራል፡፡ ቀደም ስል እንደነገርኩህ ባለ ሙሉ ስልጣን ለመሆን ሁለት ነገር ይቀረው ነበር፡፡ አንደኛው እንደ ጉጂ ባህልና እምነት ከገለልቻ ጎሳ ወገን ከሆነች ልጃገረድ ጋር ጋብቻ መፈፀም አለበት፡፡ ምክንያቱም ነጌ የአንባ እናት ተብላ የምትሰየመው እሷ በመሆኗና ከሱ ጎን ሆና መስዋት ስለምታቀርብ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የሱ ስያሜ ስርዓት መፈፀም ነበረበት፡፡ ስለዚህ ስርዓቱን ለማሟላት ከገለልቻ ጎሳ ወገን ከሆነች ልጃገረድ ጋር ጋብቻ እንዲፈጽም ከተደረገ በኋላ ቀድሞም እንደሚደረገው በሁለተኛው ቀን ስያሜው ተከናወነ፡፡ ከዚያ ስርዓቱን እንዳሟላ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ 15ኛው አባቃሉ ሆኖ ሲያገለግል ነበር፡፡አሁን ያለው አባቃሉ 16ኛው አባቃሉ ኢጋ ሳቆ ይባላል፡፡ ከቀድሞው አባቃሉ ሚስቶች ውስጥ የአንባ እናት ከሆነችው የተወለደና የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ስለሚያሟላ ተመርጦ የተሰየሜ ነው፡፡ (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ቆቲ* ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ በ12/11/2007 ዓ.ም.)

ከዚህ መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው ለቃሉ መሰየም ሁለት ዓይነት መስፈርቶች ናቸው፡፡ አንደኛው መንፈሳዊ ሲሆን፣ይኸውም፡- ከቃሉ አመጣጥ ሚት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ቃሉ ከሰማይ በፕላስቲክ መሰል ነገር ውስጥ ተሸፍኖ ከከበሩ ቁሶች ጋር እንደወረ ይነገራል፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጋር በሚያያዝ መልኩ አንድ ልጅ ከቃሉ ቤት ሲወለድ በስስ ሞራ መሰል ነገር ተሸፍኖ

የተወለደ ከሆነ ነው ቃሉ መሆን የሚችለው። ይህ ተምሳሌት ከሚቱ ጋር የተያዘ ነው። ከዚህም በመነሳት እግዚአብሔር ቃሉ የሚሆነውን ቀድሞ በዚህ ዓይነት ስለሚፈጥረው የመጀመሪያው መንፈሳዊ መስፈር ሆኖ ያገለግላል። ሁለተኛው መስፈርት ደግሞ ሰዋው ተክለሰውነቱንና ባህሪያቱን ያካተተ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን አኳያ እነዚህን መስፈርቶች ተዋቅረው፤ በነዚህ መስፈርት መሰረት በመምረጥ፣ በመጨረሻ ቃሉ ብሎ በመሰየም መሪያቸው አድርገው ይገለገሉበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉን መልሰው ሰው እንደሆነና ገልማውም ቤት እንደሆነ የሚያሳይ ፎክሎራዊ አገላለጾችን ሲጠቀሙ ይታያል። ከነዚህም ውስጥ ቃሉን እያወደሱ በውስጡ ሰዋው ባህሪውን በጭፈራ (qeexala) እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

| | |
|---|---|
| Samaxee yoo hoo | hayaa hayaa |
| ሳማጤ ዮሆ ዮሆ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |
| ሳማጤ | ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን |
| Qaalluu waaqa seyee | hayaa hayaa |
| ቃሉ እግዚአብሔር መስሎኝ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |
| ሳማጤ | ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን |
| Biraa geenyaan nama abboo | hayaa hayaa |
| አጠገቡ ስደር ሰው ነው ለካ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |
| ሳማጤ | ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን |
| Galmaan tulluu seyee | hayaa hayaa |
| ገልማ ጋራ መስሎኝ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |
| ሳማጤ | ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን |
| Biraa geenyaan mana abboo | hayaa hayaa |
| አጠገቡ ስደር ቤት ነው ለካ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |

ሳማጤ                                   ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን በማለት

ይጨፍራሉ፡፡

ከዚህ ዘፈን ግጥም የምንረዳው ቃሉ ቅዱስ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ወይም ፈጣሪ አይደለም፤ እንደኛውን ሰው ነው የሚል አንድምታ ሲኖረው፤ ገልማም መንፈሳዊ ስራ ይሰራበት እንጂ ያው ቤት ነው የሚል መልዕክት የያዘ ነው፡፡

## 6.5.3. ለቃሉ የሚሰጡ ስጦታዎች

እንደ ጉጂ ኦሮሞ በጋብቻ ወቅት ለተጋቢዎቹ ጎጆ መውጫ ተብሎ ስጦታ ማበርከት የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን ለቃሉ የሚሰጡ ስጦታዎች ከሌላው ማህበረሰብ ለየት ይላል፡፡ ይኸውም፡- ምዕመኑ ለቃሉ ከጋብቻው በፊት፣ በጋብቻው ዕለትና ከጋብቻው በኋላ የተለያዩ ስጦታዎችን (gumaacha) ያበረክታሉ፡፡ እነዚህም ስጦታዎች በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡ እነሱም የጋብቻ ወቅትና የሃይማኖታዊከበራዎች ወቅት ስጦታዎች ይባላሉ፡፡

የቃሉን ጋብቻ ለየት ከሚያደርጉት ጉዳዮች ውስጥ ሌላኛው ባህሪይ ድግሱ የሚደገሰውና ወጭውም የሚሸፈነው በማህበረሰቡ መሆኑ ነው፡፡ ይኸውም፡- ለእርድ የሚውሉ ሰንጋዎች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ጤፍ፣ ቅቤ፣ ማር፣ እርጎ፣ ጨኮና የመሳሰሉ ማንኛውንም ነገር በፍላጎት ላይ ተመስርቶ ማህበረሰቡ ያቀርባሉ፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የወጪ ክፍተቶችን ለመሸፈኛ የሚውል በጥሬ ገንዘብ በአባገዳዎች አማካይነት ተሰባስቦ ለቃሉ ይሰጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለወደፊት በሕይወት ዘመኑ ሊጠቀምበት የሚያስችለውን በመቶዎቹ የሚቆጠሩ ጊደሮችና ወይፈኖች እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠር በጥሬ ገንዘብ በአባገዳዎች አማካይነት በስጦታ መልክ ይበረከትለታል፡፡ቃሉ ደግሞ በምላሹ ስጦታውን ያበረከቱትንም ሆነ ጎሳውን ባጠቃላይ ይመርቃል፡፡ ህዝቡንና ምድሪቷን ጭምር ሰላም እንዲሆኑ፣ ከብቶቻቸውም እንዲረቡ፤ እንዲበዙ ይመርቃል፡፡ እነዚያ በስጦታ የተበረከቱትን ከብቶች ተመልሶ ማህበረሰቡ እንዲጠብቃቸው ተከፋፍሎ ይሰጣሉ፡፡ እንደመረጃ አቀባዩ ገለጻ እነዚያ ከብቶቹ የተሰጣቸው ሰዎች ከብቶቹ ደርሰው ሲወልዱ፤ ከወተቱና ከቅቤው እየያዙ ለቃሉ እንደሚያመጡና እነሱም የተረፈውን ለራሳቸው ይጠቀማሉ (Zalaalam, 2000; አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ጊዴኦ ዞን፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ27/6/2008 ዓ.ም.)፡፡

ሌላው በሃይማኖታዊ ከበራ ወቅት የሚሰጡትን ስጦታዎች በተመለከተ በምዕራፍ አምስት ስር ለመጥቀስ እንደተሞከረው በሂሮ ስር ለሚከወነው መስዋዕት የሚያስፈልገውን ብቻ በቃሉ

የሚዘጋጅ ሲሆን በሌሎች የከበራ መቼቶች ላይ ለሚከወነው የሚያዘጋጀው ህዝቡ ነው፡፡ ይኸውም አንዳንዴ ግለሰቦች በፍላጎታቸው በረከት ለማግኘት ከመፈለጋቸው የተነሳ የሚፈለገውን ከብት ያቀርባሉ፡፡ ነገር ግን ባብዛኛው የሚደረገው በጳልዳባዎች አማካይነት ከምዕመኑ ላይ ገንዘብ ተሰባስቦ የሚፈለገው ዓይነት ከብት ይገዛል፡፡ ሌላው ሴቶች ትኩስና እርጎ ወተት፣ ቡና ቃላና ወንደሮ (ጨከ) በስጦታ መልክ ያቀርባሉ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## የቃሉ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት

በዚህ ምዕራፍ ስር ስለጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ቀጣይነትና ለተከሰቱ ለውጦች በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ አስተዋጽኦ የነበራቸውን ዓለማቀፋዊ፣ ሀገራዊና ማህበረሰባዊ ክስተቶችን እንደ መግቢያነት ተዳስሰዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዱን የቃሉ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት ከክልላዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ተተንትነው በገለጻ መልክ ቀርበዋል፡፡ የጉጂ ኦሮሞ ቀደም ባሉት ጊዜያት ማለትም ከምኒልክ ወረራ በፊት ልክ እንደሰሜኑ የኦሮሚያ አካባቢ ይህ ነው የሚባል የጎላ ጫና በማንኛውም ወገን አልደረሰበትም ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እንደ አለማየሁና ሌሎች ገለጻ በ15ኛ ክ/ዘ ውስጥ የክርስቲያኑ መንግስት እያየለ በመጣበት ወቅት በዘረ ያዕቆብ (1434-1468) በላንጋኖ ሀይቅ አካባቢ ሰፍረው የነበሩትን የጉጂ ኦሮሞዎች ወደ ደቡብ እንዲያፈገፍጉ ተደርገዋል (Alemayehufi kan biroo, 1999፡275)፡፡

ጉጂዎች አሁን ላሉበት የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችም ሆነ ሌሎች ተያያዥነት ላላቸው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያና ባህላዊ የይዘትም ሆነ የቅርጽ ለውጦች፤ ከምኒልክ መንግስት አንስቶ አሁን እስካለንበት የኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት አገዛዞች የየራሳቸውን አሻራ አስቀምጠዋል፡፡ በተለይም በገዳና የቃሉ ተቋማትና ተግባራቸውን ከማዳከም አንስቶ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለማጥፋት እስከመሞከር ደረጃዎች መድረሳቸውን ታሪክ ያወሳዋል፡፡

እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለጻ ስለነዚህ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ተቋማት መዳከም እያንዳንዱ የአገዛዝ ስርዓት በመጠንና ዓይነት ተፅዕኖ ያደርሱና እያደረሱ ያሉበት መንገድ ይለያይ እንጂ የሁሉም አስተዋጽኦ ነበረበት፡፡ ይህ ደግሞ ለቃሉም ሆነ ገዳ ከበራዎች መዳከምና ለውጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን መረጃ አቀባዮቼ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *ከድሮው ብነሳልህ የጉጂ ኦሮሞ ከውጭ ኃይሎች ተፅዕኖ ነፃ የነበረና ራሱን በራሱ በቃሉ ተቋምና በገዳ የሚያስተዳደር ህዝብ ነበር፡፡ ከዚያ በታች የተለያዩ የቃሉም ሆነ የገዳ መዋቅሮች አሉ፡፡ እነሱ በእራሳቸው አብዛኛውን የማህበረሰቡን ችግሮች ይፈቱ ነበር፡፡ ባይገርምህ ያኔ የህዝብ ብዛቱም እንዲህ አልነበረም፡፡ የከብቶቻችን ብዛትም በቁጥር መግለጽ እስከሚያቅትህ ድረስ በሰፊ መስክ ላይ*

*ይሰማሩ ነበር። ነገር ግን ከብቶቹ እርስ በርስ ይተዋወቃሉ። ባንድ ላይ ውለው ባንድ ላይ ወደ በረታቸው ይገባሉ። እረኛ የሚያስፈልገው ከብቶቹን ከዱር አራዊት ለመከላከል ያህል ነው። መሬቱም የሰጡትን በእጥፍ ድርብ ይመልስ ነበር። እግዜሩም ቅርብ ነበር፤ የጠየከውን ወዲያው ይመልስልሃል። ነፍጠኛ መሬታችንን ከረገጠ ወዲህ ብዙ ለውጦች ተከሰቱ። ፖሊስ ብትል ከእነሱ ጋር መጣ። ዳኛና መካሰስ አናውቅም ነበር። አዝመራው ስያምር ሲሶ አስገቡ እንባላለን። ከብቶቻችንን ካዩ ለልጁ ሰርግ፣ ለክርስትና፣ ዝክር አለብኝ እያሉ የተለያዩ ሰበቦች እየፈጠሩ ከስር ከስር ይለቅሙብን ጀመር፤ እንዴት እንደግ፤ አቀጨጩን። ከዚህ የተነሳ ይሆን አላውቅም ከጉጂውም ውስጥ ስልጣን ፍለጋ አንዱ የሌላውን «እገሌ ምን የመሰለ ሙኩት አለው።» እያሉ ይጠቁሙ ጀመር። ውሸት የማያውቁት የነፍጠኛ ጫና ሲበዛበት መዋሸት ሁሉ ተጀመረ። አሁን ግን ሽማግሌው እውነትን ትቶ ላለው ሲያደላ ታያለህ። ገዳና ቃሉ ከገልማቸው ወጥተው ሆቴል የምታይበት ሁኔታዎች አሉ። ቃሉ የሚመገበው ምግብም ሆነ መጠጦች የተወሰኑ ናቸው። አሁን ግን ምርቃቱ በቢራ ሆኗል። ጋብቻው በመኪና ሆኗል። እንደድሮ ቢሆን ቃሉም ሆነ ገዳ ወገንተኝነታቸው ለህዝብ ነበር። አሁን ግን ከመንግስት ጋር በመተባበር እንቨስተር እያሉ ብዙ ሰዎችን እያፈናቀሉ የእርሻ መሬት ለአንድ ሰው በመስጠት፣ ከብቶቻችንን የምናሰማራበት እስኪጠበንና ከብቶቻችን ገደል እየገቡ እስከሚሞቱ ድረስ አንድ ሀገር መሬት ሲሰጥ አብሮ በመሄድ ይመርቃሉ። ቃሉም ሆነ ገዳ ክብር አላቸው። ከገልማቸው መውጣት የለባቸውም፤ ሲወጡም የሚወጡበት ምክንያት ውስን ነው፤ ርቀቱም ውስን ነበር። ያሁኖቹን ካየህ ከዚህ የተለዩ ናቸው። ከዚህም የተነሳ እግዚኣብሔርን ብንለምነው አልሰማ አለን (አቶ አየለ ጎዳና፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ በ16/6 2007 ዓ.ም.)*

ከዚህ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ወ/ሮ ሮዱ የቃሉንና የገዳን ከበራዎች በአግባቡ ይከውኑ እንደነበርና የህዝብ ወገንተኝነትታቸውም የላቀ እንደነበር በማስታወስ፤ አሁን ግን ያ ክዋኔ በተወሰነ ደረጃ እየተሸረሸረ መሆኑን በቁጭት እያስታወሱ፤ አሁኑ ያሉበትን ደረጃ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡-

*ቃሉ በኮባው ወጥቶ መስዋዕት አያቀርብም፤ ገዳዎቹም እንደዚያው ሆኑ። እግዜሩም ፊቱን አዞረብን መሰል፤ ከብቱ ደም የለውም (horiinu suga hinqabu; suga dhabe)፣ ሳሩ የበረከት ሳር አይደለም። ኮርማው እንደ ድሮው አያጠቃም። መሬቱም ማዳበሪያ የሚሉትን ነገር ለመደ መሰለኝ አንድ ዓመት ከሰጠ ሌላኛው ዓመት ላይ የለም። በረከት ጠፋ። ድሮ አባቶቻችን እንደሚነግሩንና እኛም እንደደረስንበት፡- የእኛን ከብቶች ከብዛታቸው የተነሳ በየቀኑ የሚወልዱትን ከብቶች መለየት ያቅተን ነበር። እኛ ሴቶች እንኳን የቷን አልበን፤ የቷን እንደምንተው ግራ ሲገባን ዝም ብለን ነካ ነካ እያደረግን እንተው ነበር። ያ ደግሞ እረኞቹም ሆኑ፤ ጥጆቹ እንደልባቸው ጠብተው እንዲፋፉ ያደርግ ነበር። ሰውም ከብቱም ወዝ ነበረው። ይህ ሁሉ በረከትና ሞገስ ከእግዚአብሔር ያገነው፡- ከቃሉና ገዳ እውነት አጣን፤ እግዜርም ፊቱን አዞረብን። (ወ/ሮ ሮዱ ሚጁ፣ አባያ ወረዳ፣ ካሳልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ16/6/2007 ዓ.ም )*

ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ የተመለከትን እንደሆነ ቀደም ሲል የነበረው የጉጂ ኦሮሞ አኗኗርና የቃሉና ገዳ ከህዝብ ጎን ሆነው ለህዝቡ እንዴት እንደሚያገለግሉን በወቅቱ ጥሩ ኑሮ እየኖሩ እንደነበር የሚያሳይ ነው። ነገር ግን የገዥው መደብ ስልጣኑን ወደ አካባቢው ተደረሻ ባደረገበት ጊዜ የተፈጠረውን ጭቆናና የመብት መጋፋት፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የቃሉና ገዳ ተግባራት መሸርሸሩንና የማስፈጸም አቅም እየላላ መምጣቱን ያመላክታሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ጉዳይ ቀደም ሲል በአካባቢው ሰፍሮ የነበረው የህዝብ ብዛት አነስተኛ መሆኑና በግለሰቦች ተይዞ የነበሩ መሬቶች በጣም ሰፋፊ የነበሩና የከብቱም ቁጥር በነጠላ ሳይሆን፤ በበረት የሚቆጠርበት ወቅት ነበር። ነገር ግን የተወሰኑ መረጃ አቀባዮች ደግሞ ከጊዜ በኋላ በስም የማያውቋቸው የከብት በሽታ እንደ አባሳንጋና የደስታ በሽታዎች እንደተከሰቱና ከዚህ ተዳምረው በተለያዩ ወቅቶች በተከሰቱ የአየር መዛባት ምክንያት ከብቶቻቸው በድርቅ እንደተጎዱባቸው ያስረዳሉ።

የለውጥና ቀጣይነቱን ሂደት በይበልጥ በሚያብራራ መልክ በድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ አካሄድ ከምኒልክ ወረራ አንስቶ እስከ ኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት የነበሩትን ውጣ ውረዶችና በጉጂ ኦሮሞ የራስ መተማመን ላይ የነበራቸውን ተፅዕኖዎች Taddese, (2004) በዝርዝር ገልጿል።

የምኒልክ ጦር በ1890ዎቹ አካባቢ የጉጂ ኦሮሞን ለመውረር ችሏል። የእነሱ ወታደራዊ አገዛዝ እና በኢትዮጵያ ግዛት ስር እንዲተዳደሩ መደረጋቸው በጉጂ ኦሮሞ አኗኗር ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል። ጉጂ ኦሮሞ ከውጭ ኃይሎች ተፅዕኖ ነፃ የነበረውና ራሱን በራሱ የሚያስተዳደር ህዝብነቱ እያከተመለት መጣ፤ ሀገረሰባዊ የመሬት አያያዝ ስርዓቱ ተለወጠ፤ የከተሜነት ፍላጎት እየተለመደ መምጣት፤ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የባህል ለውጥም ተፈጠረ። እነዚህ ለውጦች በጉጂ ኦሮሞ ማህበረ-ባህላዊ ሕይወትና በራስ መተማመናቸው (self-esteem) ላይ ለነበረው ተፅዕኖ ዋነኛ ምክንቶች ነበሩ። ከወረራው በፊት የጉጂ ኦሮሞ ነፃ ህዝብ የሆኑና የራሳቸውን ማህበረ-ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ያለ ውጫዊ ኃይል ጣልቃ ገብነት በራሳቸው ይመሩ ነበር። የወራሪው ተከታዮች የሀገሬውን ከብቶች ማሰማሪያ፤ በጣም ሰፊ መስኮችን እንደግል መሬታቸው አድርገው ወስደው ነበር። ቀስ በቀስ በጣም ሰፋፊ መሬቶች በመንግስት እጅ፣ በአብያተ-ክርስቲያን፣ በአስተዳደሮች፣ ወታደሮች እና ከሰሜኑ ክፍል ለመጡ ሌሎች ሰፋሪዎች በመስጠትና የነፍጠኛ ገባር ስርዓት ተቋቋመ። በዚህ ስርዓት ስር ነፍጠኛው በብዙ ገባሮች ይታገዙ ነበር። ይኸውም፡- ገባሮቹ ከሚያመርቱት እህል፣ ከሚያረቡት ከብት በመስጠት፣ እንዲሁም በጉልበታቸውም በማረስና የቤት ውስጥ ማንኛውንም ስራዎች ለነፍጠኞቹ ያሰሯቸው ነበር።

ነፍጠኛው በነባሩ የጉጂ ኦሮሞ የቅኝ አገዛዝ ያህል ግንኙነት መሰረተ፣ መሬታቸውን በመውሰድና በእነሱ ላይ ህግ አወጡባቸው። በተጨማሪ ከእያንዳንዱ አካባቢ ታክስ ይሰበሰባል፤ የተወሰነው ወደ ምኒልክ ማዕከላዊ ተቋም ይላክ ነበር። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለሀገሬው ተወላጆች በነፍጠኛው የበላይነት፤ ለበታቾቹ በደረጃ ስልጣን በመስጠት የጉጂ ባላባት፣ ባላንባራስ፣ ቆሮና ጭቃ ሹም በማለት ከእነሱ ጋር በመተባበር ታክስ (ግብር) መሰብሰብ፣ ሰላምን ማስከበርና በአስተዳደር የተወሰነላቸውን አካባቢ የማስተዳደር ኃላፊነት ተሰጧቸው ነበር።

ሌላው በምኒልክ የመስፋፋት ፖሊሲ መሰረት፤ በወረራቸው አካባቢዎች አቅራቢያ ላይ የራሱ ፖሊሶች የሚኖሩበትን ከተማ ያቋቁም ነበር። ይህን የሚያደርገው የወደፊት መስፋፋትን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፤ ከዚያም ክልሉን ለመቆጣጠር በማሰብ ነበር። ይኸውም ግብር ሰብሳቢውንና ሹማምንቱ ላይ ችግር እንዳይደርስ ለመከላከል ጭምር ነበር።

ከምኒልክ አገዛዝ በኋላ ወደ ስልጣን የመጣው የንጉሰ ነገስት ኃይለስላሴ መንግስት (ከ1930-1936 እና 1941-1974) ወቅት ነበር። ንጉሱም በጉጂ ኦሮሞ ላይ በምኒልክ ወቅት የነበረውን

አካሄድ ያስቀጠሉበት ሁኔታ ነበር። የጉጂ መሬት ከውጭ ሆነው በሹማምንቶቻቸው በኩል በመቆጣጠር ሲሶና እርቦ እንዲሁም ግብር እያሉ ያሰበስቡ እንደነበር ከታሪክ መረዳት ይቻላል። ሌላው የነበረው የታሪክ አጋጣሚ ከ1937-1940 ኢጣሊያ በሀገራችን በቆዬችበት ወቅት ጉጂን ጨምሮ በደቡባዊ ክፍል ትልቅ መነቃቃት ተፈጥሮ ነበር። ይኸውም «የጠላቴ ጠላት፣...» እንዲሉ በጉጂ ኦሮሞ ጫንቃ ላይ ተጭኖ የቆየውን የባርነት ቀንበር አሽቀንጥሮ የጣሉበትና የነፍጠኛውን ገባር ስርዓት ያስቀረበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛውን በደቡብ የሚገኙ ብሔረሰቦች፣ የጉጂ ኦሮሞን ጨምሮ ከምኒልክ ወረራ በኋላ የነፍጠኛው ስርዓት ላደረሱት አስከፊ አስተዳደር ምላሽ የተሰጠበት ሁኔታ ነበር። ለዚህ እንደጥሩ ምሳሌ የሚነሳ የጉጂ ዘፈን አለ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Hidhee nu hiika Axaalan | አስሮ ይፈታናል አጣለ (የጉጂ ባላባት)፣ |
| Hidhee nu dhaana habashaan | አስሮ ይመታናል ሐበሻ (አማራ)፣ |
| Haluun sun baate barana | ያን እልህ ተወጣን ዘንድሮ። |

ማለትም፡- በወቅቱ እንደፈለገ አስሮ ይፈታ የነበረው ባላባት፤ እንደፈለግ አሰሮ ይገርፍ የነበረው ነፍጠኛ ጊዜው ተለውጦ ያን እልህ መወጣታቸውን የሚያመለክት ዘፈን ነው።
በኢጣሊያ አገዛዝ ዞግ የተገኘው ለውጥ ለረጅም ጊዜ መዝለቅ አልቻለም። በመጨረሻም የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ መጨረሻ ጭቆናውና ግፉ እየበዛ በመሄዱ ኦሮሞዎቹም የእነሱን አገዛዝ እየጠሉ እንደሄዱ ተገልጿል። ንጉስ ኃይለ ስላሴ በብሪታኒያ ጦር በመታገዝ ተመልሶ መጣ። የተወሰኑ የጉጂ ኦሮሞ ተዋጊዎች ከኢጣሊያ ጎን በመሰለፍ የነፍጠኛው ኃይል ወደ ቀድሞው ቦታ እንዳይመለስ ትግል አድርገው ነበር። ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ተመልሶ በቀድሞው አገዛዝ ስር ለመውደቅ ችለዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ያላቸውን ሃይል በመጠቀም የተያዙ ሰዎችን ሆን ተብሎና በዘዴ ማንነታቸውን ለመቀየር የማዋሃድ (assimilation) ፖሊሲ አካሂደዋል። የዚህ ፖሊሲ ዋናው ኢላማ የነበረው የብሔር ድንበር ምልክቶችን፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የአለባበስ ስታየልና ማህበረ-ፖለቲካዊ ተቋማትን ማጥፋት ነበር (Taddese, 2004)።

በወቅቱ ለጉጂ ኦሮሞ የነበራቸው አመለካከት አነስተኛ ነበር። ይኸውም፡- ጉጂን እንደኋለቀር፣ እርባና ቢስ ባህልና ወግ አራማጅ የመመልከት ችግር እንደነበረባቸው Clay and Holcomb,

(1986:15) ይገልጻሉ። ከዘህ የሚንረዳው የሌላው ባህልና ሃይማኖት በማጥላላት የገዥውን አማራና ባህሉን የበላይነት ማረጋገጥ እንደነበር ነው።

በመጨረሻ በኃይል የማዋሃድ ፖሊሲው እስከ መጨረሻው አልተሳካላቸውም። ምክንያቱም በተለያዩ የኦሮሞ አካባቢዎችን ጨምሮ በወራሪው ኃይል ስር በነበሩት ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞና ትግል በጭቆና ስር ለነበሩት ህዝብ ክብርና በራስ መተማመን ተፈጥሯል። ለዚህም የባሌ ገበሬዎች አመጽ እንደምሳሌ ተጠቃሽ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በእነ ዋለልኝ መኮንን በ1969 ዓ.ም. መሪነት የተቀሰቀሰው የኢትዮጵያ ተማሪዎች አመጽ እና መሰል አመጾች ጋር ተዳምሮ የኃይለ ስላሴን አገዛዝ በኃይል በመገርሰስ ወታደራዊ የደርግ አገዛዝ በ1974 ስልጣኑን ጨበጠ። በ1975 የመሬት ፖሊሲውን በመቀየር መሬት ላራሹ መታወጁ በተለይም በጭቆና ቀንበር ስር ወድቀው ለነበሩት የጉጂ ኦሮሞ ታላቅ ድል ነበር። ሌላው ለእያንዳንዱ ብሔር እና ብሔረሰብ የራሱን ቋንቋና ባህል ማሳደግ እንደሚችል አስታውቆ ነበር። ይህ ደግሞ ካለፈው አገዛዝ በኃይል ከማዋሃድ ፖሊሲ የተለየ ነበር። ይህ አስተሳሰብ በወቅቱ የየማህበረሰቡን ማንነትና ማህበረ-ባህላዊ ልነቶችን በመደበኛነት የተቀበለና የሚደግፍ ነበር። ማዕከላዊ መንግስትን አንድ ዓይነት ህዝብ እንዲኖረው የታቀደ አልነበረም። ነገር ግን የደርግ አገዛዝ ኃይሉን ቀስ በቀስ አጠናክሮ «የብሔራዊ ጥያቄ» ዐዋጆችን በመሻር እና የተጠየቁትን ማንኛውንም የብሔራዊ መብቶችን በመመደብ እንደ "ጠባብ ብሔራዊ ስሜት" "narrow nationalism" ማየት ጀመረ። ይህ የደርግን ብሔርን የማስማማት ፖሊሲ ወደ ብሔርን የማዋሃድ ፖሊሲ ቀየረው (Taddese, 2004:21)።

ከዚህ በመቀጠል በ1983 ኢ.ህ.አ.ድ.ግ የደርግን አገዛዝ በመገርሰስ ኢትዩጵያን እንደተቆጣጠረ ወዲያኑ የኢትዩጵያ ሽግግር መንግስት አቋቋመ። በ1994 የሀገሪቷ መተዳደሪያ የሆነው ሕገ-መንግስት ተዘጋጀ። በሕገ-መንግስቱም የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች «የራስን እድል በራስ የመወሰን፣ እስከ መገንጠል» በማካተት ጸድቋል። ሕገ-መንግስቱ አጽንኦት የሰጠው «የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን» ማንነት ያከበረና የራሳቸውን ጉዳይ ለራሳቸው እንዲፈቱ መብት የሰጠ ነው።

ለአብነት ያህል፡- በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 39 ንዑስ ቁጥር 2 "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ህዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባሕሉን የመግለጽ፣

የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው" (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1987፡26) የሚለው በዋናነት ተጠቃሽ ነው፡፡

በሀገራችን ውስጥ ቀደም ብለን ካየናቸው መንግስታት የኢ.ፌ. ዴ. ሪ. መንግስት በአንጻራዊነት ይህንን እና ሌሎችንም በበጎነታቸው የሚታዩ ለውጦች የታየበት ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ነፃነት ወደታች ወረድ ተብሎ በሚታይበት ወቅት፤ መንግስት ለራሱ የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ ከሚለው በቀር ተፈጻሚነቱ ላይ እምብዛም አይደለም፡፡ ለዚህ እንደማሳያ የሃይማኖት ተቋማት መሪዎችን በተለያዩ መደለያዎች በመያዝ የራሳቸውን ዓላማ ሲያራምድባቸው ይስተዋላል፡፡ የመንግስት ሚዲያዎችም የተለያዩ ሃይማኖቶች ዐብይ በዓላት በሚከበርበት ወቅት የሃይማኖት አባቶች ስለበዓሉ አመጣጥና ምንነት በመንፈሳዊ ቋንቋ ከመግለጽ ይልቅ፤ ይህን እናወግዛለን!፣ እነዚህን ከውስጣችን በማጋለጥ ለህግ እናቀርባቸዋለን! የሚሉትንና የመሳሰሉት ሲያስተጋቡ ማድመጥ የተለመደ ሆኗል፡፡ ከዚህም የተነሳ ምዕመኑ በሃይማኖት መሪዎቻቸው ያላቸው እምነትና ለእነሱ ያላቸው ከበሬታ እየቀነሰ መሄዱን ከመረጃ አቀባዮቼ ያገኘሁት አስተያየት ይህን ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል አንዳንድ የመንግስት መዋቅር በቃሉና ገዳ የግጭት አፈታት ከበራዎች ላይ ጣልቃ ሲገቡሙ ይታያሉ፡፡ ለአብነት ያህል፡- የአስተዳደር አካላት፣ ፖሊስ እና ፍ/ቤት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት በል ሲላቸው የሀገረሰባዊ ግጭት አፈታት ሂደቱን የማድነቅና ውሳኔያቸውንም እንደሚያከብሩ ከተገኙት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
እንደ ጉጂ ኦሮሞ ቃሉና ገዳ ተቋማት ያየን እንደሆነ ቀደም ባሉት መንግስታት ለመሪዎቹ የባላባትነትና የባላንበራስነት ማዕረግ በመስጠት ተከታዩቻቸውን ያለምንም ደም መፋሰስ እንዲያስገብሩ ለማድረግ በመሳሪያነት እንደተጠቀሙባቸው አይተናል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በ1986 ዓ.ም የጉጂ ኦሮሞ በተለይም በደ/ብ/ብ/ክ/መ፣ የጌዴኦ ዞን አጎራባች የነበሩት የኦሮሞ ተወላጆች፤ በጌዴኦ ዞን እንዲተዳደር ሲካለልና በጌዴኢኛ ቋንቋ እንዲማሩ ሲደረግ፣ በጌዴኦ አመራሮች ሲመሩ ለምን እንዲህ ይሆናል? በሚል አብዛኛው የጉጂ ኦሮሞ ኮሚቴ አዋቅረው ለመንግስትን የመብት ጥያቄ ማቅረብ ጀመሩ፡፡ ይህን በተመለከተ Asebe, (2007) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> Those who were included into Gedeo Zone were bureaucratically forced to conform to the realities in the zone. For instance, if at all

> they had to go to school Guji children had to learn in Gedeo language (Gede'uffa) because that was the only language taught in the Gedeo Zone. For Guji civil servants, lack of language skill in Gede'uffa was presented as an excuse for inequitable job opportunity between the Gedeo and Guji.»

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በጉጂና ጌዴኦ መካከል አብረው በሚኖሩበት ወቅት በኦሮሞዎቹ ላይ የተፈጠረው በማያውቁት ቋንቋ እንዲማሩ መደረግና የተማሩትም የመንግስት ስራ ለማግኘትም የአከባቢውን ቋንቋ ባለማወቃቸው ምክንየት በጌደኦና በጉጂ መካከል ፍትኣዊ የስራ ዕድል ማግኘት አለመቻሉን ነው፡፡

እንደ መረጃ አቀባዬ ገለጻ ከላይ ለተነሱት ጥያቄያቸው አግባብነት ያለውን መልስ ከመስጠት መንግስት የወሰደው እርምጃ በጋራ ኑሩ፤ ማህበረሰቡንም በጋራ አስተዳድሩ በማለት ከዞን እስከ ቀበሌ በጥምር አስተዳደር አዋቀረ፡፡ የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ከጌዴኦ ብሔር ሲሆን በምክትል አስተዳዳሪነት ማዕረግ የጉጂ ኦሮሞን እንዲወክሉ የተደረጉት አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ ነበሩ፡፡ ህዝቡም ማጉረምረሙን ቀጠለ፡፡ ‹‹ቃሉ ከገልማ መውጣት የለበትም፤ ቃሉ በገልማህ ተመለስ፡፡›› ቢባሉም፤ እምቢ በማለት የመንግስት ተቀጣሪ ሆነው ማገልገል ጀመሩ፡፡ በሚገርም ሁኔታ ከሦስቱም የጉጂ ኮንፌደሬሲዎች ሽማግሌዎች ተመርጠው ስጦታና ገንዘብ ይዘውላቸው በመምጣት ወደገልማው እንዲመለሱ ቢጠየቁም እንቢታቸውን ገለጹ፤ ስጦታውንም አልተቀበሉም ነበር፡፡ በመጨረሻም የጉጂ ኦሮሞ በተለይም በአላብዱና ኡራጋ በኩል አዋሳኝ የነበሩት መንግስት ሰጥቶ የነበረውንና ነገር ግን እነሱ ግን የተነፈጉትን መብት ለማስከበር ጥቂያቸውን ቀጠሉበት፡፡ አባቃሉ ሳቆ ባሉበት የተለያዩ ስብሰባዎችም ተደርጎ ነበር፡፡ ቋንቋውን፣ ባህሉንና ማንነቱን የተነፈገ ህዝብ መሪው ከፊት ለፊቱ ቆሞ እረፍ ቢለውም በውስጡ የማያሳርፍ ጥያቄ ይዟል፡፡ ስለዚህ አባቃሉን «ከዓይን ትረፍ!» «Ilarraa hafi!; mucuca!» በለን በማለት አስፈቀዱ፤ አባቃሉም «mucuca!» «ከዓይን ያትርፋችሁ» በማለት ሲፈቅዱላቸው ጥቄዎችን ያቀርቡላቸው ነበር፡፡ ይኸውም፡- በሚያሳምን ንግግር ‹ወደ ገልማ መመለስ አለቦት፡፡ ስለዘመናዊ ፖለቲካ ብዙ የማያውቁት ነገሮች አሉ፡፡ እርሶን ከፊት ለፊታችን አቁመው እኛ ብዙ ነገሮችን እያጣን ነው፡፡› በማለት ተቃውሟቸውን ይገልጹ ነበር፡፡ እሳቸው ግን ሌሎች ይሉት የነበረውን አባባል መልሰው ይሉ ነበር፡፡ ይኸውም፡- «ይህ የኦነግ አመለካከት ነው፡፡

ስለዚህ መንግስት ባዋቀረው መልኩ መብታችንን እናስጠብቃለን።» እንዳሉ ከመረጃ አቀባዬ ለመረዳት ችያለሁ።

ከዚያም ይህ አካሄድ የትም ሊያደርስ እንደማይችል በመግለጽ፤ በየቦታው የተለያዩ ተቃውሞዎች ይቀሰቀሱ ጀመር። የተቃውሞ ሰልፎችም እየተበራከቱ መጡ። ‹‹ሕገ-መንግስታዊ መብታችን ይከበር!፣ በቋንቋችን እንድንማር ይደረግ!›› የሚሉና የመሳሰሉትን መፈክሮች ይስተጋቡ ነበር። ጥያቄዎቹ በሰላማዊና ሕገ-መንግስቱ በሚያዘው መሰረት እየተካሄደ እያለ፤ ከሰላማዊ ሰልፉ ሲመለሱ በአንድ ግለሰብ አማካይነት በተፈጠረ ስህተት የተነሳ ወደ ሁለቱ ህዝብ ግጭት አመራ። ጦርነትም ተቀሰቀሰ። በጦርነቱ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች ሞቱ፣ ብዙ ንብረቶች ወደሙ። እንዲሁም ግጭቱን ለማስቆም ከመጡት የመከላከያ ሰራዊት አባላትም ጭምር የሞቱ ነበሩ።

በመቀጠል ይህ ጥያቄ የህዝብ ሳይሆን የግለሰቦች፤ ያውም የስልጣን ጥመኞች ነው በማለት በጦርነቱ ላይ ጉልህ ሚና ነበራቸው የተባሉ ተጠርጣሪዎች እየታደኑ ወደ ወህኒ ቤት ተወረወሩ። ከእነዚህም ውስጥ አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ አንዱ ነበሩ። የእሳቸውም ክስ ጦሪነቱን ለማብረድ ከነበራቸው ሚና ይልቅ አባብሰዋል። ለዚህም እንደምክንያት የቀረበው፦ ‹‹የጉጂ ኦሮሞ ከእርሶ ቃል አይወጣም። ስለዚህ ከልቦ አቁሙ ብትሉ፤ ይችሉ ነበር›› የሚል ነው። ያም ሆኖ አባቃሉ ሳቆ ሳይፈረድባቸውም በዚያው ወህኒ ቤት እንዳሉ ሕይወታቸው አለፈ።
ከነዚህ ተግዳሮቶች እንዳየነው የጉጂ ኦሮሞዎች በተለይም በቦረና ዞን፣ በገላናና አባያ ወረዳዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩት በቋንቋቸው የመማርና የመዳኘት መብታቸውን እንዳሳጣቸው መረዳት ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የማንነታቸው መገለጫ የሆነውን ቋንቋ ካልተጠቀሙበት፤ በባህላቸውንና ሀገረሰባዊ ሃይማኖታቸውን እንደልብ መከወኑ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው። ቀደም ሲል በገልማ ተገናኝተው ይወያዩ የነበረው ባህል እየተቀዛቀዘ መጣ። ምክንያቱም አባቃሉ በጠዋት ተነስተው ወደ አስተዳደር ጽ/ቤታቸው ይሄዳሉ። የተወሰኑ የሀገር ሽማግሌዎችም ወደገልማው በመሄድ ከቃሉ ጋር ውይይት ለማድረግ ጥረት ባደረጉ ወቅት ልክ እንደ ‹‹ኦነግ›› በመቁጠር ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂዎች እንደደረሰባቸውና ይህ ደግሞ በወቅቱ በውስጣቸው ፍራቻ እንዳሳደረባቸው ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል የአባገዳ አጋ ጣንጣኖ የስልጣን ዘመን ታሪክ ያየን እንደሆነ ስለገዳ ስርዓት ማንሰራራት ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። በሀገረሰባዊ ዕውቀት የጠለቀ ግንዛቤ ያላቸውና

አንደበተ-ርቱኡ ገዳም ነበሩ፡፡ የገዳ ስርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲታወቅ በተለያዩ ጊዜያት ለሚዲያ በሰጡትና በሚሰጡት ገለጻዎች የበኩላቸውን የተወጡና እየተወጡም ያሉ ናቸው፡፡ ስለገዳና ቃሉ ከበራዎችና ስርዓቶች አስፈላጊ መረጃዎችን ለተመራማሪዎች በመስጠት ያገለገሉና እያገለገሉ ያሉ ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክተሬት ተሰጥቷቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ እንደ መረጃ አቀባዮቼ ገለጻ በተወሰነ ደረጃ ህዝቡን በማማከል፤ ለማህበረሰቡ መንፈሳዊም ሆነ አስተዳደራዊ አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ፤ የመንግስት ቀኝ እጅ በመሆን በተለያዩ ስብሰባዎችና የሚመረቁ መሰረተ ልማቶች ላይ በመገኘት ምርቃት ሲያካሂዱና ስለመንግስት መልካም መልካሙን በመስበክና እንከን የለሽነቱን በማወደስ ያሳልፉ ነበር፡፡ ለዚህም ከመንግስትን በተለያዩ መልክ ጥቅማጥቅሞች ይደረግላቸው እንደነበር ማለትም፡- በአበል መልክ የገንዘብ ስጦታ፣ የማጓጓዣ መኪና በማዘዝና ጥሩ ሆቴሎች ምግብና መኝታ እየተዘጋጀላቸው እንደነበር ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ከዚህም የተነሳ ማህበረሰቡ የነበረበትን ማህበረ-ፖለቲካም ሆነ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ለመፍታት ወደ ገልማቸው ሲሄዱ እንደማያገኟቸውና በመንግስታዊ አካላት በሚቀርብላቸው የይገኙልን ጥሪዎች ተጠምደው እንደሚያሳልፉ ያነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮች ያስረዳሉ፡፡ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እስኪመስሉ ብዙ ስራዎችን ማስፈጸማቸውንና መንግስትም በቦታው እንዲቀጥሉ እጁን በተዘዋዋሪ መንገድ ማስገባቱን Israel, (2011:315) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> *During the 2005 national election in Ethiopia, the then Abba gada elect was suspected of supporting dissident political groups that the regional government did not like him to ascend to power on the next traditional power transfer...Abba Gada Aga Tentano, delayed the traditional power transfer for almost a year and finally rejected the new Abba Gada and transferred power to somebody else in whom the people have no trust and whom the traditional screening process did not support.*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አንደኛው አንድ አባገዳ ከመንግስት በተቃራኒ ያለን የፖለቲካ ድርጅት ይደግፋል የሚል ጥርጣሬ ካሳደረበት ተለያየ መንገድ ጫና ለመፍጠር እንደሚሞክር ያሳየናል፡፡ የገዳ ስልጣን ቆይታ ጊዜ ስምንት ዓመት ሆኖ ሳለ በማን አለብኝነት ጊዜውን ማራዘሙን፣

ሁለተኛው ደግሞ በገዳ ስርዓት የዕድሜ እርከን ውስጥ ከኩሳ ደረጃ ጀምሮ የተመረጠና በተለያዩ የማህበረሰብ ዕውቀት እየተገነባና እየተደራጀ የመጣውንና ማህበረሰቡም ይሆናል ብሎ የሚጠብቀውን መሪ ወደ ጎን በመተው፤ በባህላዊውና ሃይማኖታዊ መንገድ ላልተመረጠውና የህዝብ እምነት ላልተጣለበት ሰው ስልጣን መሰጠቱ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ሊኖር እንደሚችል ጥርጣሬ መፍጠሩ አይቀሬ ነው፡፡

ከላይ በዝርዝር እንዳየነው ኢትዮጵያን ከምኒልክ ጀምሮ በተለያዩ ወቅቶች ካስተዳደሯቸው መንግስታት እንደ ጉጂ ኦሮሞ የቃሉና የገዳ ተቋማት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማዳከም የማህበረሰቡ ማንነትና ነፃነታቸውን ሲፈታተኑ እንደነበር መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸውም፡- የሃይማኖቱ መሪዎችንና የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪዎችን ከተቻለ በኃይል በማዳከም፤ አሊያም በአፄዎቹ ዘመን የባላባትነትና ባላንበራስነት ማዕረግ በመስጠትና ክርስትና በማንሳት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ እንዲሆኑ በማድረግ፤ እንዲሁም በደርግ ደግሞ እንደጊላ ቀር ባህል በመቁጠር በኃይል ሲያዳክሙ እንደነበር አይተናል፡፡ በመጨረሻም በኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት ደግሞ በገዳዎች ስልጣነ-ሢመት ሂደት ውስጥ ጣልቃ እስከመግባትና ከተመረጡም በኋላ በተለያዩ መደለያዎች በመያዝ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እንዳደረጓቸውና በተቃራኒው ደግሞ ገዳዎቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ተዓማኒነትና ከበሬታን እንዲያጡ በማድረግ ያሳደሩት ተፅዕኖ ይህ ነው የሚባል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በጎሳዎች መካከል፣ በአጎራባች ህዝቦች መካከል ለሚፈጠሩ ችግሮች መንግስት ብቻውን ለመፍታት ስለሚያዳግተው የእነዚህ ተቋማት መኖሪን ይፈልጋል፡፡ ከዚህም በመነሳት የተለያዩ ከበራዎችን እንዲያስፈጽሙ ድጋፍ የሚያደርግበት ወቅቶች አሉ፡፡ በሌላ በኩል ተደጋጋሚ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ያስደርጋል፡፡

እነዚህ በጉጂ ኦሮሞ ላይ በተለያዩ ወቅቶች፣ በተለያዩ አካላት የተፈጸሙት ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ጫናዎች በነባሩ ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ የማንነት ችግር ውስጥ ጥሏቸው ነበር፡፡ ስለዚህ እንደ ክልላዊ (hemispheric) ንድፈ-ሀሳብ በተለያዩ ምክንያቶች አንድ ማህበረሰብ ከሚኖርበት አካባቢ ሲንቀሳቀስ ወይም ሌላው ሲመጣበት፣ ወይም በሚከሰቱ ሌሎች መስተጋብሮች የተነሳ የማህበረሰቡ ዕውቀት የመዋዋስ፣ የመዋሃድ፣ የመዋዋጥ፣ የመጠናከር፣ እንዲሁም የመዘንጋት ክስተቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ በምዕራፍ ሁለት ስር አይተናል፡፡

ባጠቃላይ ከታሪክ እንደምንረዳው ከ16ኛው መቶ ክ/ዘ መጨረሻ እስከ 19ኛ መቶ ክ/ዘ ድረስ የኦሮሞ ህዝብ ቀደም ሲል እንደነበረው በማዕከላዊነት ደረጃ ሳይሆን በየጎሳው አባ ገዳ አስተዳዳሪነትና በአባ ሙዳ ሃይማኖት መሪነት ያለምንም የውጪ ኃይል ጣልቃ ገብነት እራሱን ሲያስተዳድር ቆይቷል (ታቦር፣ 2006፡106)። ነገር ግን በአንዳንድ ውጫዊ ተግዳሮቶች የተነሳ ይሄን የማስፈጸም አቅም እያጡ እንደመጡ መረጃ አቀባዮቹና የተለያዩ ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ስለዚህ የቃሉን ሃይማኖታዊ ክበራዎች በእነዚህ የታሪክና አካባቢያዊ መስተጋብሮች ውስጥ በውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች የተነሳ የተለዋወጡ የዕውቀት መልኮችን፣ ተቋቁመው የተሻገሩና ያንሰራሩበት ሁኔታዎችን መመርመር ይጠበቃል። በዚሁ መሰረት ከተለየዩ ንድፈ ሀሳቦች አኳያ እንደሚከተለው ትንተናና ገለጻ ተደርጓል።

## 7.1. የገዳ ስልጣን ማጽደቅ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት

የቃሉ ተቋም ከሚያከናውናቸው ከበራዎች ውስጥ አንዱና ዋንኛው የገዳ ስልጣን ማጽደቅ ከበራ እንደሆነ በ 6.1. ስር በስፋት ተመልክተናል። ይህ ተቋም ከነበረበት ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁመው በአሁን ወቅት በስራ ላይ ካሉት ውስጥ የጉጂ ኦሮሞ አንዱ ነው። ስለዚህ የገዳ ስልጣነ-ሚመት ማጽደቅ ከበራ በተመለከተ ከማስማማት፣ መላመድ፣ ማጣመር፣ መዘንጋት፣ መረሣት፣ መቀየር፣ መቋቋምና ማንሰራራት አኳያ ምን ይመስል እንደነበር እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ተከናወኑ ከተባሉት የገዳ ስልጣን ሽግግሮች ዙሮች ውስጥ ለ 69 ጊዜ ብቻ ነው የቀድሞውን ማህበረ-ባህላዊ ደንቡን ጠብቀው የተከናወኑት። ይህ ማለት ገዳዎቹ የስልጣን ሽግግር ካደረጉ በኋላ ለቃሉ ስጦታዎችን በመያዝ ከቃሉ ገልማው ቀርበው ስልጣናቸውን ያጸድቃሉ። ነገር ግን ይህ ሂደት የተቋረጠው ከ70ኛ አባገዳ አዶላ አጋ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ተገልጿል።

ይህ ሲባል እነዚህን ሁሉ ጊዜያት ያለምንም ተግዳሮቶች እዚህ ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይኸውም ከምኒልክ ጀምሮ እስካሁን ባሉት መንግስታት እየተደረጉ የነበሩትን ተፅዕኖዎች በጥቅል ለማየት ችለናል። ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዘርዘር አድርገን ለማየት ሞክረናል።

በምኒልክ አገዛዝ በወረራቸው አካባቢዎች አቅራቢያ ላይ ፖሊስ ጣቢያዎች መቋቋማቸውን ተከትሉ የፓሊስ ጣቢያዎች እየተለመዱ ከገዳ ማዕከል ጋር በጥምረት የመስራት ሁኔታዎች

ብቅ ማለት ጀምረዋል። ይኸውም መጤው ሰፋሪ በነባሩ ነዋሪ የሚከሰሰውና የሚዳኘው በነዚህ ተቋማት እየሆነ መጣ። በመቀጠልም በሂደት በአስገባሪዎቹ የተቋቋሙት ከተሞች የህዝብ ቁጥር ከሰሜኑና ከአጎራባች አካባቢዎች ካሉት በመፍለስ እየጨመረ እንደሄድ አይተናል። በአካባቢዉ ት/ቤቶች፣ የጤና ተቋማትና መንገዶች አልነበሩም። ከዚህ ጋር በተያያዘ የክርስትናሃይማኖትና የአማርኛ ቋንቋን የማስራጨት ፖሊሲ ነበረው። ለዚህ ዓላማ ማሳኪያ ይሆን ዘንድ በጦር ጀነራሎቹም ጭምር ሳይቀር በወረሯቸው አካባቢ አብያተ-ክርስቲያናትን ያስገነቡ እንደነበር ከታሪክ ለመረዳት ተችሏል። ከዚያም ሀገረሰባዊ እምነት ተከታዩን ማህበረሰብ በማስጠመቅና የአማራውን ባህል እንዲከተሉም ተደርጓል (Taddese, 2004)። ማህበረሰቡም በወራሪው ክንድ ስር ከወደቁበት ጊዜያት ጀምረው አንድም በጫና፤ አሊያም በስብከት አዲስ እምነትና ባህል ከተላመዱ በኋላ ከሀገረሰባዊ እምነትና ባህል ጋር በማጣመር ይከውኑ ነበር። የንጉሳዊ አገዛዙ የማዋሀድ ፖሊስ (assimilative policy) በጉጂ ኦሮሞ ሀገረሰባዊና ባህላዊ ልምዶችን እንደባዕድ አምልኮና ህገ-ወጥ ድርጊት አስመስሎ ለማጥላላትና ለማጥፋት እንደተነሱ Hinnant, (1977: 25,217-220) በጥናቱ ውስጥ ያስረዳል።

በቀድሞ ነገስታት ተፅዕኖ የተነሳ ሲባል፦ ለምሳሌ በአጼ ኃ/ስላሴ ዘመን ቀደሞ የነበረውን ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ስያሜ በማጥፋት አባቃሉ በሚለው ስም ምትክ የባላባትነት ማዕረግ በመስጠት ንጉስ (ሞቲ) በማለት፣ እንዲሁም አባገዳን ደግሞ ባላንበራስ በማለት ስማቸውንና ተግባራቸውን የመሸርሸር ሁኔታ ተከስቶ ነበር። ለአብነት ያህል እነ አባ ቃሉ ቶቴ ህርባዬ፣ ናጋኦ ቶቴ፣ ሳቆ ናጋኦ እና አጋ ሳቆ ከአባቃሉ እና ከቃሉ መጠሪያ በተጨማሪ ሞቲ በሚለው መጠሪያ ይጠሩ እንደነበር ለማውቅ ተችሏል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሀሎና ዌሲቱ ገዳዎችም በባላንበራ ማዕረግ የጠሩ ነበር። ለምሳሌ፦ አባገዳ ጉሚ ባላንበራስ ጉሚ ተብለው ይጠሩ ነበር። ልጃቸውም ገዳ ደንቦባ አንዳንዴ ነሸጥ ሲያደርጋቸው ‹‹እኔ የባላንበራስ ጉሚ ልጅ ነኝ፤ ባላንበራስ ከእነ ልዕልት ተናኜ ወርቅ ጋር ቀረቤታ ነበረው።›› በማለት በጫወታቸው መካከል ጣልቃ እያስገቡ ሲያወጉኝ ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በማግባባትና በመደለል የሃይማኖት ለውጥ እንዲያደርጉ ሆነዋል። የሌላውን ሃይማኖት የመከተል ተፅዕኖ በአሁኖቹም የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ መሪዎችና የቅርብ ዘመዶቻቸው ላይ ይታያል። ለአብነት ያህል በቃለ መጠይቅና በምልከታ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተሞከረው፦ አባቃሉ አጋ ሳቆ፣ አቶ ሞኮና ናጋኦ (የቃሉ አጎት)፣ አባገዳ ደንቦባ ጉሚ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች እንደሆኑና፤ የቃሉ ገልማ ውስጥም ጎልተው የሚታዩ የመላእክት ምስሎች ለመመልከት

ተችሏል፡፡ አልፎ አልፎም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ መንፈሳዊ መዝሙሮችንም እንደሚያዳምጡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ሃይማኖታቸውን በመቀየራቸው ምክንያት የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱን ማህበረ-ባህላዊ ክዋኔና ፋይዳ ላይ ያደረሰው ተፅዕኖም እንብዛም ነበር፡፡ ምክንያቱም በቃሉ ተቋምም ሆነ በገዳዎች ማዕከላት ከሞላ ጎደል የሚከናወኑት ምርቃቶች፣ የእግዚአብሔር ልመናና ምልጃ ሂደቶችም ሆኑ ለሂደቱ የሚቀርቡት ቁሳዊ ባህሎች አይጓደሉም ነበር፡፡ በተለይም በቃሉ ተቋም የመጤው ሃይማኖቶች ተፅዕኖ በሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ላይ የፈጠሩት ጫና ሙሉ በሙሉ የቃሉንና የገዳ ተቋማትን አለመቀየሩንና አሁንም በተቻለ መጠን እንዲንቀሳቀሱ ያደረገ ለመሆኑ አንዳንድ መረጃዎች በግልጽ ያሳያሉ፡፡ ይሄውም አባቃሉ አጋ ሳቆ፣ አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ አባገዳ ደንቦባ ጉሚ በተለያዩ ገጠመኞች ላይ በተገናኘንበት ወቅት ውይይታችንም ሆነ፣ በሌሎች ጉባኤዎች ላይ ምርቃት ሲያካሂዱ በዋቄፋና ሃይማኖታዊ ስርዓት እንደሆነ በምልከታ ከተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ የሚያሳየው የመጤውን ሃይማኖትና ነባሩን ባህል በማጣመርና በማጣጣም ያስተናግዱ እንደነበር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጉጂ ኦሮሞ አካባቢ በክርስትናው እምነት በኩል በአብዛኛው የፕሮቴስታንት እምነት መስፋፋትና የእስላም ሃይማኖትም መጀመሩ በማህበረ-ባህላዊ (socio-cultural) እና በፖለቲካ ስርዓቱ ላይ ጣልቃ በመግባትና ከፍተኛ መሰናክል እየፈጠሩ እንደሆነ (Tadesse, 2004:3) በስፋት ያስረዳል፡፡

ሌላው ስለ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ በህዝቡ ውስጥ የሚሰብክ እራሱን የቻለ አካል አለመኖሩ፣ መደበኛ በሆነ መልኩ መሰበክ አለመቻሉ፣ ህዝቡም በሳምንት፣ አሊያም በወር የመገናኘት አጋጣሚዎቹ የሉትም፤ ቢኖሩም ስለተከሰቱ ወቅታዊ ጉዳዩች ከመወያየት ባሻገር አዳዲስ አባላትን የመስበክና የመመለስ ስራ ላይ በትኩረት የሚሰራ አካል የለም፡፡ በተቃራኒው ግን በመጤው ሃይማኖቶች እንደ ባዕድ አምልኮ፣ በተራራና በወንዝ እንደሚመለክ መሰበኩ፤ የሰባኪዎቹ በመንፈሳዊ ትምህርት የማስተማር ስነ-ዘዴ መሰልጠንና በሚደረግላቸው የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ጭምር ስለሚደረግላቸው፤ የዋቄፋታ ሃይማኖት ተከታዮችን ከመስበክ ባለፈ በተለያዩ ጥቅማጥቅም እየደለሉ ሃይማኖታቸውን ለመቀየር አመቺ ሁኔታዎችን እንደፈጠረላቸው መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ይህም ሆኖ (Bartels,1983) እንዳለው በእነዚህ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞዎች መካከል ትክክለኛ የእምነት ድንበር አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ከበራዎችን አውቀውም ይሁን ሳያውቅ ሲከውኑ ይስተዋላሉ፡፡ አንዳንድ በአምልኮአቸው ውስጥ የነበሩትን ከበራዎች በአዲሶቹ

ሃይማኖቶች ውስጥም መቀላቀል ይታያል፡፡ እንዲሁም ለቃሉ ከፍተኛ አክብሮት የሚቸሩና የቃሉዎችን ገልማ ለአምልኮ የሚቃኙም አሉ (ከአጥኚው የመስክ ምልከታ ከተገኘ)፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በጉጂ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በዋቄፋና ሃይማኖት ወይም በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ በአንዱ ወይም በሌላው የመሳተፍ ዕድላቸው የሰፋ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ በገዳ የስልጣን-ሢመት ማጽደቅ ከበራ ይህን ክስተት ሊያሳዩ የሚችሉ በምዕራፍ ሦስት ስር በተወሰነ ደረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቱን ከደረሰበት ጫና ማምለጥና መቋቋም ባይችልም፣ የመጤውን ሃይማኖት በመላመድና ከሀገረሰባዊው ጋር በማጣመር እየከወኑት መሆኑን ያመላክታል፡፡

ሌላው ለለውጥና ቀጣይነት እንደምክንያት እየተነሳ ያለው ችግር ድሮ ቃሉ ወገናዊነቱ ለህዝብ ነበር፡፡ አሁን ለራሱ ከተመቸው ስለህዝቡ ደንታ ያለው አይመስልም ተብለው ይታማሉ፡፡ ምክንያቱም ቃሉ የህዝቡን ጥቅምና ግዴታውን ወደጎን በመተው የመንግስትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲባል በመንግስታዊ የአስተዳደር ማዕቀፍ ውስጥ በማስገባት አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ በጌዴኦ ዞን የምክትል አስተዳዳሪነት ቦታ በመስጠት የቃሉነቱንና የአስተዳዳሪነቱን ስልጣን በማጣጣም ለማስኬድ ያደረጉት ጥረት ነበር፡፡ ነገር ግን ማህበረሰቡ ማንነታችንን እያጣን ነው፡፡ «መንግስት በአንቀጽ 39፣ ንዑስ አንቀጽ-2 ላይ የደነገገውን መብታችን ይከበር» በማለት ጉዳዩ ከጦርነት አልፎ በመንግስት ጣልቃ ገብነት በተወሰነ ደረጃ በሪፈረንደም መፍትሔ ተበጅቶለታል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ብዙ ስህተቶች ነበሩ፡፡ ይኸውም፡- የቃሉ ተቋም በሌላ ክልል ውስጥ መሆኑ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ብሄረሰብ መካከል በነበረው የድንበር ይገባኛል ግጭት የተነሳ የቃሉ ተቋም በሪፈረንደም ወደ ጌዴኦ ዞን መካተቱ ተገልጿል፡፡ ይህ ደግሞ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ቅሬታን ፈጥሯል፡፡ በመስክ ቆይታዬ ወቅት ባሰባሰብኩት መረጃ መሰረት የጉጂ ኦሮሞ የማንነታችን መገለጫ የሆነውን የቃሉ ተቋምና የተለያዩ ማምለኪያ ተራራዎች (Kooba) ለሪፈረንደም መቅረቡ በራሱ አግባብነት እንዳሌለውም ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ክስተት በራሱ ለቃሉ ተቋም መዳከም እንደ አንድ ዋንኛ የውጫዊ ተግዳሮት ሊቆጠር ይችላል፡፡ ይህ ክስተት ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ የማምለኪያ ቦታዎች የአከላለል ለውጥ መደረግ፣ ለምሳሌ፡- የቃሉ ተቋም፣ ገደብ የሚገኝ መንፈሳዊ ቦታና ለሌችም በሪፈረንደም ወደ ጌዴኦ ዞን መጠቃለላቸውና

የቦታዎቹ ስያሜና አገልግሎት መቀየርን ያሳያል። ለምሳሌ የቂሊጦ ተራራ ቀደም ሲል የቃሉ መንፈሳዊ ቦታ የነበረው፤ በአሁኑ ወቅት ወደ መለስ ፓርክነት ተለውጧል።

ሌላው ቀደም ሲል እንዳየነው የገዳዎች ቃሉ ተቋም ሄደው ቁንቢ መውሰድና ስልጣናቸውን ማጸደቅ ያቆሙት ከ70ኛ አባገዳ አዱላ አጋ (1976) ጀምሮ እንደሆነ ይገልጻሉ። በወቅቱ የነበሩት አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ ነበሩ። በዚያን ወቅት አባቃሉ በመንግስት መዋቅር ውስጥ በማስገባት የጌዴኦ ዞን ም/አስተዳዳሪ ሆነው ሲያገለግሉ ከወደ ኡራጋ ለእሳቸው የሚሆን ስጦታ በማምጣት ወደገልማ ተመለስልን በማለት ጠይቀው እንደነበር ከላይ ተጠቅሷል። ነገር ግን እሳቸው አሻፈር ሲሉ ለገዳዎቹ የቃሉ ገልማ እንዳይሄዱ ክፍተት ፈጥሯል። ከዚህ በተጨማሪ ለቃሉ ተይዞ የሚኬደውን ከብቶችና ሌሎች ስጦታዎችን ማህበረሰቡ ማዋጣት አለመፈለጋቸውና ገዳዎችም ይህንኑ የማሰባሰብ አቅም ማጣታቸው ተዳምሮ እንደ ውስጣዊ ተግዳሮቶች በመሆን ለጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ መስተጓጎል ምክንያት እንደሆኑ መረጃውን የሰጡኝ አባገዳዎቹ ይገልጻሉ። በምትኩም ያለውን የመዋቅርና የከበራ ክፍተቶች በፋጋ አማካይነት ቁንቢ በመስጠት እስከ 74ኛው ገዳ ስልጣነ-ሢመት መድረሳቸውን በ 6.1. ስር በስፋት ተነስቷል። ይህን ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ የቁንቢ አሰጣጥ ከበራ ሂደቱን፣ መቼቱንና ከዋኙ ላይም ለውጥ እንደተደረገ እናያለን። ከማህበረሰብ ዕውቀት አኳያ የተመለከትን እንደሆነ ይህ አሰራር ከተፈጠሩት ሁነቶች ጋር ሂደቱን ለማጣጣም ያዋቀሩት ማህበረሰባዊ ዕውቀት መሆኑ ያሳያል። ነገር ግን በደቡብ የኦሮሚያ አካባቢ ማለትም (በአርሲና በቦረና) በየስምንት ዓመት አንዴ በሚካሄድ ከፍተኛ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ ለመገኘትና ለመሳተፍ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ፦ ከሰሜን እንደ ወሎ እና ከምዕራብ እንደ ወለጋና ጂማ ኦሮሞዎች ወደዚያ ይጓዙ ነበር። ነገር ግን ይህ ሂደት ቀስ በቀስ በተለያዩ ምክንያቶች ማለት፡ በኢትዮጵያ ንጉሳዊ መንግስታት ጫናና የክርስትና ሃይማኖት መጀመር የተነሳ እየተዳከመ መሄዱን Asmerom, (2000:102-103) ይገልጻል። ይህ ሂደት ከለውጥና ቀጣይነት አንጻር ስንመለከተው እየተዘነጋና እየተረሳ ሄዶ በከበራው ላይ መሳተፉ መቅረቱን ያሳየናል።

ይሁን እንጂ እንደ ጉጂ ኦሮሞ የተመለከትን እንደሆነ በገዳ ስልጣነ-ሢመት ከበራ ክዋኔዎች ውስጥ የተረሱ የሚመስሉ አሉ። ለአብነት ያህል በስጦታ መልክ ድፍን ቡና፣ ከብቶች፣ ወተት፣ ቅቤ፣ ማር፣ ገንዘብና የመሳሰሉትን ለቃሉ ያበረክቱ ነበር። ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ እንዲህ ዓይነቱ የመተሳሰብና ለባህሉና ለሃይማኖቱ የመታዘዝ ሂደት እየተሸራረፈና እየቀዘቀዘ

መጥቷል። (ዲኮ ሚጁ ካላልቱ ቀበሌ ነዋሪ እና ሄሌሎ ሞኮና፣ ካላልቱ ቀበሌ ነዋሪ፣ በ30/3/2007 ዓ.ም.)

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ከማህበረሰቡ ለገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ ድፍን ቡና፣ ከብቶችና ወተት ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው ይታወቀል። የከበራ ጊዜ እርዝማኔ ከወራት በላይ ስለሚወስድ፣ በከበራው ላይ የሚታደሙ ሰዎች ብዛት በሺዎቹ ስለሚቆጠሩና ከብቶች በየከበራዎቹ የሚታረዱ ከብቶች፤ ያን ብዛት ያለውን ህዝብ ለማቆየት የሚወጣው ወጪ መብዛት፣ ከዚህ በተጨማሪ ቦታውን ለሚለቀው አባገዳ ለመጦሪያው የሚሰጡ ከብቶች መኖር፣ እነዚህ ከብቶች ደግሞ በጃልዳባዎች አማካይነት ለማዋጣት ፍቃደኛ ከሆኑ ቤተሰቦች ላይ ይሰበሰብ ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ጃልዳባዎች ይንን ጉዳ ለማስፈጸም ፍላጎቱ እንደሌላቸውና እናስፈጽምም ቢሉ ተቀባይነታቸው እንደቀድሞው እንዳልሆነ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ። ይህንን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ Hinnant, (1977:218-219) ይገልጻል። ስለዚህ ይህ ሂደት ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ የጃልዳባዎችን የማዘዝ አቅም ያሳጣና አካሄዱንም እንደተቀየረ ያመላክታል።

> አባቃሉ ከማንኛውም የጉልበት ሥራ ነፃ መሆን አለበት። እርሻውን የሚያርሱት የአካባቢዊ ህዝብ ነበር፤ አሁን ግን በራሱ ያሳርሳል፤ ከዕለት ጉርሱ እስከ ዓመት ቀለቡ በስጦታ መልክ ይበረከትለት ነበር። ሌላው መስዋዕት ለማቅረብ ወደ ተራራው ሲወጣ ህዝቡ የመስዋዕቱን ከብት በማዘገጀት አጅበውት እየጨፈሩ ይሄዳሉ፤ ባረፈበት ቦታም ገንዘብ በስጦታ መልክ በቡሉኮው ላይ ይጥሉለታል፤ እሱም በምትኩ ህዝቡን፣ ሀገሩን፣ ከብቶቹን ይመርቃል፤ ይባርክም ነበር። ይሁን እንጂ በአሁን ወቅት እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር በጣም በተወሰነ መልኩ እንጂ እንደወትሮው አይደለም።

በማለት በትዝብት መልክ (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ በ3/11/2007 ዓ.ም.) ገልጸውልኛል። ይህ ሂደት ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ስንመለከተው ለቃሉ ይደረግ የነበረው ከበሬታና ታዛዥነት ድርጊት በተወሰነ ደረጃ እየተዘነጋ መሄድ ያሳያል።

ስለዚህ አባቃሉ ኑሮውን ለማሸነፍ ሲል ንግድ ቢጤ እንደ ጀመሩ ለመረዳት ችያለሁ። ይኸውም ወናጎ ከሚባልበት ከተማ ከብት በመግዛትና በማስቀለብ፤መልሶ አትርፎ በመሸጥ ላይ እንደተሰማሩ መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ። ይህ የቃሉ ከገልማው ወጥቶ በየገበያው መሄድ፤ ቃሉ ከገልማው ሆኖ ለማህበረሰቡ ከማገልገል ይልቅ ኑሮዉን ለማሸነፍ እንዲሯሯጥ አስገድዶታል። ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል ልጆች በገዳ የተለያዩ የደረጃ እርከኖች ውስጥ ለመሆናቸው አመላካች የነበሩ የጸጉር አቆራረጦች ነበራቸው፤ አለባበሳቸውም እንዲሁ። አሁን ግን በመስክ ቆይታ እንደተመለከትኩትና ከመረጃ አቀባዮቼ እንደተረዳሁት ከግሎባላይዜሽን ጋር በተያያዘ፡

የዘመናዊ ሃይማኖቶች መስፋፋት፣ የት/ቤቶች በየአቅራቢቸው መከፈት፣ ቀደም ሲል ከተሜዎቹ ለጉጂ ሕዝብ የነበራቸው ዝቅተኛ አመለካከት በውስጣቸው ካሳደረው የስነ-ልቦና ተፅዕኖ ጋር ተዳምሮ፤ በተለያዩ ከበራዎች ላይ አብዛኛው ልጆቻቸው እንደማይቆረጡና አለባበሳቸው ዘመን ያፈራውን እንደሆነ ለማየት ችያለሁ፡፡ በከበራው ላይ የመሳተፉም ሁኔታ አሁን እየተሸሻለ መምጣቱን በመግለጽ፤ ቀደም ሲል በዘመናዊ ሃይማኖቶች አማካይነት በሚሰበኩ የማጥላላት ዘመቻ እየተሸበሩ በባህላቸው ላይ ባይተዋር ሆነው እንደነበር ያስረዳሉ፡፡

በመጨረሻም ከዚህ የገዳ ስልጣነ-ሢመት ከበራ ጋር የሚነሳው፡- ቀደም ሲል በምዕራፍ ስድስት ስር እንደተገለጸው የጌዴኦ አባገዳም ለቃሉ ስጦታዎችን ይዞ በመምጣት ምርቃትና ቁንቢ ይቀበል እንደነበር ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በአሁን ወቅት ይህ አካሄድ ተቀይሮ በራሳቸው ማከናወን ጀምረዋል፡፡ ይህ ከለውጥና ቀጣይነት አንጻር ሲታይ የመቼትና የተግባር ለውጥ ተካሂዷል፡፡

ይሁን እንጂ የጉጂ ቃሉ ተቋምና የገዳ ስርዓት እነዚህንና የመሳሰሉትን ጫናዎች በመቋቋምና በማንሰራራት አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡ ይህንን ሂደት ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ በምን መልኩ ተቋቋመ? እንዲሁም እንዴትስ ማንሰራራት ቻለ? የሚሉትን በመተንተን እንደሚከተለው ለማየት ተችሏል፡፡

በአሁኑ ወቅት በዋናነት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት ለህገረሰባዊ ባህል ማንሰራራት (revitalizátion) በፈጠረው ምቹ ሁኔታ የቃሉና ገዳ ተቋማትና ከበራዎቻቸው የማንሰራራት አዝማሚያ በማሳየት ላይ ይገኛሉ፡፡

ለአብነት ያህል እንደ ኦሮሚያ በማዕከል ደረጃ የኦሮሚያ አባገዳዎች አንድነት ጉባኤ (Gumii tokkummaa abbooti gadaa Oromoo) መቋቋሙ በራሱ ቀደም ሲል በተለያዩ ተፅዕኖዎች የተዳከሙና የጠፉ ገዳዎችን በተሃድሶ ስርዓቱ እንዲመለሱ ለማድረግ ያለውን አጋጣሚ እያሰፋ በመሆኑ፤ በቀጣይ ስለአባቃሉ (አባሙዳ) መንፈሳዊ ጉዞም እንዲያስቡበት የሚያደርግና ስርዓቱም እያንሰራራ መሆኑን አመላካቾች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ዓለም አቀፍ የዋቄፋና ሃይማኖት ማህበር (Waldaa Amantii Waaqeffannaa Addunyaa) መቋቋሙ በራሱ ሃይማኖቱ እንዲያንሰራራና ሃይማኖቱን በባለቤትነት ለማስተማርና ለማስፋፋት ባለቤት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ ይህ ማህበር ከተቋቋመበት ዓላማ

አንዱ በአካባቢው የሚከወኑ የሃይማኖቱን ስርዓቶች በማቀናጀት ሃይማኖቱ ማዕከላዊነት እንዲኖረው ማድረግ እንደሆነ ይገልጻሉ (WAWA, 2006)፡፡ ስለዚህ እንደ ጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ተቋም ያሉትን በእነዚህ ማህበራት ስር የመታቀፍና የመጠበቃቸው እድል ሰፊ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሬዲዮና ቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን የተመለከትን እንደሆነ የየብሔረሰቡን ቱባ ባህል አውጥቶ በማሳየት፡ የማህበረሰቡን የአመጋገብ ስርዓትን፣ አለባበሱን፣ በተለያዩ ወቅት የሚጠቀሙባቸውን ባህላዊ ጌጣ ጌጦችን ከተለያዩ ከበራዎች ጋር በማያያዝ ለታዳሚዎች ተደራሽ እንዲሁንና እንዲታወቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ለአብነት ያህል በአብዛኛው የኦሮሚያ ክልል ውስጥ የተደረጉ የገዳ ተሃድሶ ስርዓት (haaromsa sirna gadaa) ያየን እንደሆነ፤ ስለገዳ ስርዓት ማንሰራራት አመላካች ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ በሐረርጌ የኦዳ ቡልቱም ገዳ፣ በቦረና የጉሚ ጋዮ ጉባኤና እንዲሁም በየካቲት 2008 ዓ.ም. በጉጂ ዞን፣ ሚኤ ቦኮ ላይ የተደረገውና ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያገኘው የጉጂ አባገዳዎች ስልጣን ሽግግር ከበራዎች ማንሰራራት የተወሰነ ድርሻ አላቸው፡፡

ሌላው በአሁኑ ወቅት የሚቀርቡ ዶክመንተሪ ፊልሞችና ባህላዊ ዘፈኖችን ያየን እንደሆነ የባህሉንና የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ መዳከምና መረሳት ያሳስባቸው የነበሩ አዛውንቶችንም ጭምር ተስፋቸውን እያለመለመ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ወጣቱንም ክፍል በማንነቱ እንዲኮራና እራሱንም እንዲመለከት እንደ ማንቂያ ደወል እያገለገሉ እንደሆነም መረጃ አቀባዮቼ ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም፡- በየት/ቤቱ፣ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ የተቋቋሙት የባህል ማዕከላት አዲሱን ትውልድ ከመቅረጽ አኳያ ያላቸው ሚና ሰፊ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላት ሲከበር ባህላዊ አልባሳትን ለብሶ መታደምና በባህላዊ ዘፈኖች ማጀብ በሰፊው እየተስተዋለ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ ቀደም ሲል ወደ መዘንጋትና መረሳት ደረጃ የደረሱ ቁሳዊ ባህሎችንና ቃላዊ ግጥሞችን የመጠቀሙ ሁኔታ እያንሰራራ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል ዩባ ሞና ጎዳና ገለጻ የገዳ ስልጣን መያዝ ያለበት በዋቄፋና ሃይማኖት ተከታይ ነበር፡፡ ነገር ግን በአንድ ወቅት በሆኩ ገዳ ስር አባገዳ ጊርጃ ሶዱ የሚባሉ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የነበሩ በሚኤ ቦኮ ስልጣኑን ከተረከቡ በኋላ የገዳ ስርዓት የሚያዘውን ከበራዎች መከወን ተው፡፡ ይኸውም፡-

ተራራ ላይ ወጥቶ ለመስዋዕት ኮርማ ማረድ እንቢ አሉ፡፡ በቦካ (ደራራ) ህዝቡን አልመርቅም አሉ፡፡ ‹ይህ ሀራም ነው፡፡ ካፊር የሚሰራው ስራ ነው፡፡› በማለታቸው የተነሳ እሱእንዲህ ከናቀን የእኛ የሆነውን ከእሱ መውሰድ አለብን በማለት በዩባዎች አማካይነት ስብሰባ ተጠራን፡፡ ከዚያም ከአንደበቱ እንቢታውን መስማት ስለነበረብን፤ ዳግመኛ በባህሉ መሰረት ሊከውን እንደሚገባው ጠየቅነው፡፡ እሱም እንቢታውን ቀጠለበት፡፡ እኛም ከለቻውን ከእሱ ላይ በመውሰድ ይሰራልናል ብለን ላመነው፤ ለአባገዳ ጋምቤላ በሪሶ ከለቻውን ተደረገለት፡፡ አባገዳ ጋምቤላ ባህሉና ሃይማኖቱ በሚፈቅደው መሰረት በጥሩ ሁኔታ ከ2000-2007 ዓ.ም. በማገልገል ይሄው ለአሁን አባገዳ ሊያስረክብ በዝግጅት ላይ ነው፡፡ (ሞና ጎዳና፣ በ7/6/2008 ዓ.ም. ሚኤ ቦኮ ላይ)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው የገዳ ስልጣን ሽግግር ላይ የነበረውን የመጤ ሃይማኖት ጫና ተቋቁመው ወደ ቀድሞው ስርዓትና የዋቄፋና ሃይማኖት መመለስን ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ባህላዊ ዘፈኖች እራሳቸውን ችለው፤ በሌላ በኩል ባህላዊ ዘፈኑን በዘመናዊ መልክ በማቀናበር ባህሉ እንዲያንሰራራ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በአርቲስት አቡሽ ዘለቀ የተሰራው ሙዴ (Muudee) የሚለው ኪሊፕ የጉጂ ኦሮሞን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ለዛ ባለው ዜማና ክዋኔ የሚያሳይ ነው፡፡ ተደራሽነቱንም ያየን እንደሆነ ከጉጂ ኦሮሞ ባሻገር በተለያዩ ክልሎች፣ ከገጠር እስከ ከተማ የሸፈነ ነው፡፡ እነዚህና መሰል የኪነ-ጥበብ ዘርፎች ለባህሉና ሃይማኖታዊ ከበራው ማንሰራራት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ያመላክታል፡፡

በሌላ በኩል ዓለም አቀፍ የዋቄፋና ሃይማኖት ማህበር (Waldaa Amantii Waaqeffa- nnaa Addunyaa) ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ በአካባቢው የሚከወኑ የሃይማኖቱ ስርዓቶች በማቀናጀት ሃይማኖቱ ማዕከላዊነት እንዲኖረው ማድረግ እንደሆነ ይገልጻሉ (WAWA, 2006)፡፡ ስለዚህ እንደ ጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ተቋም ያሉትን በእነዚህ ማህበራት ስር የመታቀፍ እድላቸው ሰፊ በመሆኑ ለወደፊት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቀጠልና አገልግሎቱን ለማስፋፋት ዕድሉ የሰፋ ይሆናል የሚል የአጥኚው እምነት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም በባህልና ቱሪዝም ቢሮ አማካይነት በገዳ ስርዓት ላይ የተደረጉና እየተደረጉ ያሉት ጥናትና ምርምሮች አሉ፡፡ እነዚህ

ጥናቶች የስርዓቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በማመላከት በሚቀርቡት ይሁንታ አማካይነት እውቅና እንዲያገኝና እንዲያንሰራራ የማድረግ አጋጣሚያቸው የሰፋ ነው፡፡

በምዕራፍ ስድስት በ6.1 ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው በየስምንት ዓመቱ መጨረሻ ላይ በሚደረገው የገዳ ማሻሻያ አዋጅ ነገራ (lallaba) ላይ የጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ መቅረቱ አግባብነት እንደሌለውና ይህን ሂዴት ከመንገድ ማስቀረቱ ባህላቸው እንዳልሆነ ተገልጾ፤ ለቀጣይ መከወን እንዳለበት ቃል የተገባበት መልዕክት ተላልፏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አዲስ የተመረጡት ገዳዎች ወደቃሉ ተቋም ሂደቱን በሚያስቀጥሉበት ሁኔታ ላይ ምክክር እንደጀመሩ ከአባቃሉ አጋ ላይ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ታዲያ እነዚህ ሁኔታዎች የቃሉን ተቋም እንቅስቃሴ እንዲያንሰራራ ከሚያፋጥኑ ሁነቶች ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በገዳ ስልጣነ-ሢመት ከበራ ላይ ዋንኛው ተዋናይ ገዳዎቹ በመሆናቸው ነው፡፡

በመጨረሻ በሚኤ ቦኮ በ2008 ዓ.ም. የተደረገው የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራን የተመለከተን እንደሆነ ቀደም ሲሉ ከተከበሩት ለየት የሚያደርገው ገጽታ እንደነበረው ከመረጃ አቀበዮቼ ገለጻና በቦታው ተገኝቼ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ይኸውም፡- በከበራው ላይ የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ፕረዝዳንትና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፕረዝዳንት ጨምሮ፤ የተለያዩ ባለስልጣናትም በስፍራው በመገኘት በከበራው ላይ ታድመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሩቅ የኦሮሚያ አካባቢ ለምሳሌ ከሐረርጌ አካባቢ በስርዓቱ ለመታደም እንደተገኙ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ የህዝብ ብዛቱም ቢሆን ቀደም ሲል፤ ማለትም ከደርግ መንግስት ወዲህ ባሉት ጊዜያት ውስጥ እንደዚህ ያለ ቁጥር ያለው ህዝብ እንዳልተሳተፈ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

## 7.2. የጎንዶሮ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት

በምዕራፍ ስድስት ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው የጎንዶሮ ከበራዎች ለተለያዩ ምክንያቶችና በተለያዩ አካላት ሲከወኑ ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን ጎንዶሮ በተወሰነ ደረጃ የቀድሞውን ያህል ግልጋሎት እንዳይሰጥ ያደረጉት ተግዳሮቶች ተፈጥረዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የዘመናዊ የህግ ስርዓት ጣልቃ ገብነትም እንደ አንድ ውጫዊ ተፅዕኖ ሊታይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ወይም ቤተሰብ ወደ ቃሉ ተቋም በመሄድ የተወሰነባቸውን ውሳኔ መቀበል ግድ ይላቸዋል፡፡ የቃሉን ውሳኔ አልቀበልም ካሉ ከማንኛውም ማህበራዊ አገልግሎቶች ማዕቀብ (bokuu) ይተላለፍባቸዋል፡፡ ታዲይ ይህን ማዕቀብ በሚያስፈጽሙበት ወቅት አድማ ተደረገብን በማለት ለፖሊስ፣ ፍ/ቤትና አስተዳደር ክስ እንደሚሄዱና አንዳንዴም ማዕቀቡን ያስተላለፉ የቃሉ

ተወካዮች እስከመታሰር ደረጃ እንደደረሱ ከመረጃ አቀባቼ ለመረዳት ችያለሁ። ይሁን እንጂ ይህ አሰራር ቀድሞም የነበረ በመሆኑ የቃሉ መልዕክተኞችና የአስተዳደር አካል በመስማማት በጋራ ወደ መፍትሔው ሀሳብ የሄዱበት ወቅት እንደነበረ ለማወቅ ችያለሁ። ይህ ታዲያ ዘመናዊ የህግ ስርዓቱን ከህገሪሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ጋር በማጣመር ማካሄዳቸው አንዱ የለውጥና ቀጣይነት መገለጫ ሆኗል።

ሌላው በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ የመጨረሻው እርቁ እንዲሰምር፣ ልመናው እንዲያርግ የሚከወኑበት ቦታዎችና ቁሳዊ ባህሎች የተለዩ ነበር። አሁን ግን ከወቅቱ ጋር የተቀየሩ ወይም እንደ አማራጭ የሚጠቀሟቸው እንዳሉ ለማየት ችያለሁ። ለምሳሌ ከአንዳንድ ሽምግልናና የተለያዩ ከበራዎች በኋላ ላይ የሚመረቀው በጠጅ ወይም ቦካ ሆኖ ሳለ በቢራ የመመረቁ ሁኔታ እየተለመደ መጥቷል።

ሌላው የምልጃ ማሳረጊያ የጎንዶሮ የተመለከትን እንደሆነ ከዘመናዊ ሃይማኖት መምጣት ጋር ተያይዞ በተከታታይ ለሚከሰቱ ችግሮች የጎንዶሮን ከበራ ከመከወን ይልቅ ‹‹ስለ ጉዳዩ ማጸለይ›› በሚለው አብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንደሚያጸልዩ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ።

በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ አካላት፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለምሳሌ በመንግስት የቃሉንና የገዳና ተቋማት እራሳቸውን ችለው እንዳይቆሙ የሚያደርግባቸውን ጣልቃ ገብነት እንዳሉ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ መንግስት አንዳንዴም ሊጠቀምባቸው ሲፈልግ ከፍ ከፍ በማድረግ የጎላ ሽፋን ይሰጣቸዋል። ከነዚህም ውስጥ አንዳንድ የጎሳና የብሔሮች ግጭት በሚከሰትበት ጊዜ በእራሱ ብቻ ለመፍታት በሚያዳግተው ጉዳዮች በጋራና ተቋማቱ በራሳቸው እንዲፈቱ ያደርጋል፤ በሌላ ወቅት ደግሞ ቁብ እንደማይሰጣቸው መረጃ አቀባዮቼ ይገልጻሉ። ይኸውም፡- ተቀባይነታቸው እየጨመረ ማህበረሰቡ በእነሱ መገልገል ሲጀምር ደግሞ ተቀባይነታቸውን ለመሸርሸር የሚጠቀማቸው ሁኔታዎች አሉ። ለዚህም እንደ አስረጂ በመጀመሪያ በ1987 ዓ.ም. በጉጂና ጌዴኦ መካከል የተፈጠረውን የእርስ በርስ ግጭት በፌዴራል ፖሊስ ኃይል እንደተቆጣጠረውና ወቅታዊ መረጋጋትን ፈጥሮ ነበር። ነገር ግን በ1990 ዓ.ም. በድጋሚ የተካሄደው የሁለቱ ወገን ደም አፋሳሽ ጦርነት ተከሰተ። ጦርነቱን የፌዴራል ፖሊስ ኃይል እንደ በፊቱ ሊያስቆሙ አልቻሉም። የሁለቱም ወገን የሀገር ሽማግሌዎችን ጨምሮ በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

መሀል ገብተው ለመፍታት ሙከራ ጀመሩ፡፡ በመጨረሻም መንግስትም የቃሉን ሀገረሰባዊ ተቋም በመቀበል ችግሩ እንዲፈታ ተደረገ፡፡ ለሂደቱም የቃሉ መኖር ግድ ስለነበር አባቃሉ ሳቆ ናጋኦን ከታሰረበት ከሀዋሳ ወህኒ ቤት በማውጣት የጎንዶሮ ከበራ ተከወነ፡፡ በመጨረሻም ከከበራው መልስ ወደ ወህኒ ቤት ተመልሰው እንደታሰሩና በዚው ሕይወታቸው እንዳለፈ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ በዝርዝር ተገልጿል፡፡

ባጠቃላይ እነዚህ የቃሉ ከበራዎች ስለቃሉና ገዳ ተቋማት ህልውና ምን ደረጃ ላይ እንዳሉና ወዴት እየሄዱ እንደሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አመላካች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በተቋማቱ ላይ የነበሩትና ያሉባቸውን የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት፣ የዘመናዊ ሃይማኖቶች መስፋፋትና የዓለምአቀፋዊነት (globalization) ተዳምረው፤ ተቋማቱ እነዚህን ተፅዕኖዎች ተቋቁመው የመዝለቅና የማንሰራራት ዕድላቸውን ከጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ዓለማቀፋዊ የአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በአካባቢዉና አጎራባች ክልሎች እየተቀሰቀሰ ያለው ድርቅና ወረርሽኝ በሽታዎች ለበርካታ ሰዎች መጎዳትና በብዛት ለሚቆጠሩ የቤትና የዱር እንስሳት ሞት ምክንያት ሆነዋል፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከት የመንግስት አካላት ከተፈጠረው የአየር ንብረት ጋር በማያያዝ ችግሩ ዓለማቀፋዊ፣ ከዚያም አህጉራዊ ብሎም ሀገራዊ እንደሆነ በሳይንሳዊ መረጃ በማስደገፍ በመግለጽ፤ ከክልሉ መንግስት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል የሃይማኖት አባቶች ደግሞ ይህ ክስተት የተፈጠረው ከእግዚኣብሔር ቁጣ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይኸውም፡- በገዳ ስርዓት ደኖች የራሳቸው ህግ አላቸው፡፡ የሃይማኖት አባቶችም ሆነ የሀገር ሽማግሌዎች የእግዚኣብሔርን እውነት (dhugaa waaqaafi lafaa) መናገር፣ መመስከር፣ መጠበቅና ማስከበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ግጭቶች ሲቀሰቀሱ ጥፋተኛው ተጣርቶ፤ የበደለ ክሶ፤ ዳግም ወደዚያ ስህተት እንዳይመለሱና ጎንዶሮ ተብሎ ይቋጭ ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህ እውነቶች በአሁን ጊዜ በተለያዩ አካላት በሚደረጉ የመደለያ ቁሶች፤ ገንዘብን ጨምሮ እየተሸራረፉ እንዳሉ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ በማከልም ለእነዚህን ጥሰቶች ደግሞ የእግዚኣብሔር ምላሹ ቅጣት ነው፤ ቅጣቱም ደግሞ በድርቅ፣ በበሽታና የመሳሰሉት ሁኔታዎች እንደሚሆን ይገልጻሉ፡፡

ለአብነት ያህል በቦረና ዞን፣ ያቤሎ ከተማ በአጎራባች ወረዳዎችና ዞኖች መካከል ለሚነሱ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሔ ለማስገኘት በተደረገ ውይይት ላይ የተሳተፉ አንድ አባት የነገሩኝ ትዝ አለኝ። እሳቸው እንዳሉት፡-

*‹‹በውይይቱ ወቅት በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩ ግጭቶች ከተፈቱ በኋላ ዳግም ለምን ይቀሰቀሳሉ? የሚል ጥያቄ ከአወያዮቹ ቀርቦ ነበር። ከተሳታፊዎች የተለያዩ አስተያየቶች ቢቀርቡም እኔን የሳበኝ አንድ የፖሊስ አባል አለ የተባለው ነው። ይኸውም፡- በመጀመሪያ የገዳ አባቶችን ይቅርታ <(na hofkolchaa?) ‹ይቅር በሉኝ› በማለት ጠየቀ። እነሱም ‹ይቅር ይበልህ› (hofkol) በማለት ዕድሉ ታሰጠው። ከዚያም ‹በእውነቱ! በጉጂና ቦረና፣ በቦረናና ገብራ እንዲሁም ከሌሎች ጋር የተለያዩ ግጭቶች ተካሂደዋል። እነዚህን ግጭቶች የሚመለከታቸው አካላት ባሉበት ተፈቶ፤ ከብት ታርዶ፤ ጎንደሮ ከተባለ በኋላ ግጥጭቶቹ ተመልሰው ያገረሻሉ። በዚያን ጊዜ የማንኛውም ወገን አባገዳ ይህ ትክክል አይደለም ከማለት ይልቅ ለራሱ ጎሳ ወገናዊነት ያሳያል። ስለዚህ እውነት ተናጋሪ በሌለበት እንዴት ተደርጎ እውነተኛ ሰላም ሊሰፍን ይችላል።› አለ።›› (አቶ ቦሩ ኢፋ፣ ዕድሜ 45)*

ከዚህ መረጃና ሌሎችም እንደተረዳሁት ቀደም ሲል ለቃሉና ገዳዎች በማህበረሰቡ በገንዘብም ሆነ በተለያዩ ቁሳቁሶችና የጉልበት ስራ ይደረግላቸው የነበሩ ስጦታዎች በአሁኑ ወቅት ወጥነት የላቸውም። ከዚህም የተነሳ በሃይማኖታዊና ባህላዊ ተቋማቱ ላይ ብቻ ተወስነው አገልግሎት ለመስጠት ያላቸው ፍላጎት እያተቀዛቀዘ መጥቷል። በሚትኩ የተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ፣ ለተለያዩ መሰረተ ልማቶች የመሰረት ድንጋይ ሲጣል አብሮ በመገኘትና የተሰሩም ካሉ መርቆ በመክፈት፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚከፈላቸው አበልና በሚደረግላቸው ለየት ያለ እንክብካቤ እየተሳቡ እየሄዱ እንደሆነ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በገዳና የመማክርት አባላት ምርጫ ውስጥም መንግስት እጁን ሊያስገባ እንደሚችል ከመረጃ አቀባዮቼ ጥርጣሬ ለመረዳት ችያለሁ።

### 7.3. የሁሉቃና የፋጭ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት

እንደ ሀገሪቷ ከግሎባላይዜሽን ጋር ተያይዞ፣ የዘመናዊ ሃይማኖት፣ ትምህርትና የህክምና ተቋማት መስፋፋት፣ እንዲሁም ተደራሽነታቸውም በቀበሌ ደረጃ መውረዱና የማህበረሰቡም በእነሱ መጠቀም ልምዱ እየዳበረ መጥቷል። ከዚህም የተነሳ የተለያዩ ወረርሽኝ በሽታ ሲከሰቱ፤

ቀደም ሲል ለቃሉና ለገዳዎች ሪፖርት በማድረግ፤ በምላሹ ቃሉና ገዳዎቹ መስዋዕት በማቅረብ እግዚኣብሔርን ይለማመኑ ነበር። ሁሉቃና ፋጭ ይደረግ ነበር። አሁን ግን ችግር ሲከሰት የቀበሌው መዋቅር ለወረዳው ሪፖርት ያደርጋል። ከበላይ አካል አጥኚ ቡድን በመሄድና ችግሩን ከለየ በኂላ በዘመናዊ የህክምና ዘዴ የመከላከል ስራ ያከናውናሉ።

ይሁን እንጂ የሁሉቃና ፋጭ ከበራዎች ከነአካቴው ቀርተዋል ለማለት አይቻልም። ምክንያቱም የፋጭን ከበራ ያየን እንደሆነ በቤተሰብ ደረጃ ተደጋጋሚ ችግሮች ሲከሰቱ የሀገር ሽማግሌዎችና ወዩዎች በማስጠራት የፋጭ ከበራ እንደሚከወን ካነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። ሌላው በቃሉና ገዳ ተቋማት ደግሞ የሰውም ሆነ የከብቶች ወረርሽኝ በሽታ፤ እንዲሁም ተከታታይ ድርቅ፣ ከመጠን ያለፈና በረዶ የቀላቀለ ዝናብ ከተከሰተ፤ እንደ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ተከታዮች እምነት ይህ ክስተት ከመደበኛው ለየት ያለና በእግዚኣብሔር ቁጣ የመጣ መአት ነው ተብለው ይታመናል። ስለዚህ የፋጭ ከበራ ማካሄድ እንዳለባቸው ያስረዳሉ። ስለዚህ እንደ ቀድሞው ጊዜያት ሙሉ በሙሉ ይህን ከበራ የመከወኑ ሁኔታ እምብዛም አይታይ እንጂ አልፎ አልፎ እንደሚከወኑ ለማወቅ ችያለሁ።

ይኸውም፡- ሁሉቃን በተመለከተ እንደ መረጃ አቀባዮቼ በግለሰቦች ደረጃ በቤተሰቦቻቸው ችግር እንዳይደርስባቸው እንደሚከውኑ ይገልጻሉ።ከመከሰቻ አጋጣሚዎቹ ውስጥ ወላጆች ልጆቻቸውን ለትምህርት ወደ ከተማ ሲልኳቸው፤ ከዘመኑ መጥፎ በሽታ ያሽሉካችሁ!፣ ከሚወራው መጥፎ ወሬ ያውጣችሁ!፣ ክፉውን መንፈስ ያስቀርላችሁ በማለት በብብታቸው ስር፣ አንዳንዴም በእግሮቻቸው መካከል፣ አሊያም አጭር እንጨት ቆርጠው በጭንቅላታቸው ላይ በማዞር የጦስ ማውጫ ገደል (bowwaa bita) ይጥላሉ። እነዚህን ከበራዎች ከዘመናው ህክምናና ከመጡ ሃይማኖቶች ጸሎት ጋር በማጣጣም እየተከወኑ ይገኛሉ። መረጃ አቀባዮቼ እንዳስረዱኝ ከሆነ አንድ ሰው ከታመመ በመጀመሪያ በሀገረሰባዊ መድኃኒቶች የሞከርለታል። ከዚያ ልተሽለው እንደሆነ ወደ ህክምና ማዕከል ይወሰዳል። ነገር ግን ወደዚያ ከመሄዱ በፊት፤ በተለይም እናቶች እጃቸውን ወይም አጠር ያለች ልምጭ ቢጤ ከታማሚው አናት ላይ በማዞር ‹‹ጦስህን ይውጣ›› በማለት የበሽታው አምጭ እርኩስ መንፈስ እንዳይከተለው ወደ አቅራቢያቸው ገደል የመጣል ሁኔታ አሁንም እንዳለ ለመረዳት ችያለሁ።

በሌላ በኩል በየስምንት ዓመቱ በሚካሄደው የገዳዎች የስልጣን ሽግግር ወቅት ከገዳ የደረጃ እርከኖች ውስጥ በዶሪ ደረጃ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን እንደሚከናወኑ አይተናል።

ከነዚህም ውስጥ ሁሉቃ አንዱ ነው። የዶሪና የገዳ አባላት የስልጣን ርክክብ ከማድረጋቸው በፊት ዶሪዎች መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ (kaayoofi faro hamtuu) ተከትሏቸው የወደፊት ስራቸውን እንዳያደነቃቅፍባቸው በማሰብ፤ እንዲሁም ስልጣን ላይ የቆዩት ገዳዎች ደግሞ ምናልባትም በስልጣን ዘመናቸው ወቅት አብሯቸው የነበረ መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ አሁንም እንዳይከተላቸው በሚል የሚፈጽምት የጦስ ማውጣት (ሁሉቃ) ሃይማኖታዊ ከበራዎች ናቸው። እነዚህ ሂደቶች ያለማቋረጥ በየስምንት ዓመቱ የሚከወኑ በመሆናቸው ከለውጥና ቀጣይነት አተያይ የነበሩትን ጫናዎች ተቋቁሞ መዝለቁን ያመላከተ ነው።

## 7.4. የቃሉ ስያሜ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት

የቃሉ ጋብቻ ከበራ ከቃሉ ስልጣነ-ሢመት ጋር ተያያዥነት ያለው ከበራ እንደሆነና ሂደቱም ምን እንደሚመስል በ5.5. ስር በስፋት ተገልጿል። ይሁን እንጂ ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ምን እንደሚመስል ከዚህ ቀጥሎ ተገልጿል።

የቃሉ ተቋም እስካለ ድረስ የቃሉ ስያሜ ከበራ መኖሩ ግድ ይላል። ምክንቱም የቀድሞው አባቃሉ ሲሞት ለተተኪው የስያሜ ከበራ ይፈጸምለታል። ለአብነት ያህል የቃሉ አጋ ሳቆን የስያሜ ከበራ ከንጥል ጥናቱ ለማየት ችለናል።
ይኸውም፡- በአባቃሉ ሳቆ ናጋኦ እልፈተ-ሕይወት ምክንያት ከልጆቻቸው መካከል መስፈርቱን የሚያሟላ መተካት ነበረበት። ስለዚህ አባገዳዎችና የወረዳው የመስተዳድር አካላትን ጨምሮ በህዝቡ ውስጥ የቀድሞውን ያህል ንቅናቄ በመፍጠር የአባቃሉ አጋ ሳቆን ጋብቻና ስልጣነ ሢመት እንዲከናወን ተደርጓል። ከበራውንም በኦሮሚያ ቴሌቭዥን ሰፊ ሽፋን በመስጠት ተላልፎ ነበር። የከበራውን ሂደት በተመለከተ በምዕራፍ አምስት 5.5. ስር መመልከት ይቻላል።

ከቃሉ ስያሜ ከበራ ጋር አብረው የሚነስና አንዳንድ ለውጦች ቢኖሩም ቀጣይነታቸውን ያስመሰክሩ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህሎች አሉ። ከቁሳዊ ባህሎቹ ውስጥ ቀደም ሲል ከቆዳ በቀጥታ ለፍቶና አለስልሶ ይሰሩ የነበሩ አልባሳትና ጌጣጌጦች በዘመናዊ ሌዜርና ሴንቴቲክ እየተቀየሩ መጥተዋል። ይሁን እንጂ በሃይማኖት መሪዎቹም ሆነ፣ በታዳሚዎቹ የሚለበሱ ሀገረሰባዊ አልባሳት፣ በዝግጅቱ ላይ የሚቀርቡ ባህላዊ ምግቦችና የመሳሰሉት ከተመለከትን ቁሳዊ ባህሎች ከስያሜ ከበራው ጋር አብረው የመሻገር ዕድላቸውን አስፍቶታል። ከዚህ በተጨማሪ ከቃሉ

ስያሜ ከበራ ጋር ባህላዊ የጋብቻ ስርዓቱ፣ ባህላዊ ጭፈራዎች የነበረውንና ያለውን የተለያዩ ችግሮች ተቋቁመው እንዲያንሰራሩ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት እንደ ኦሮሞ የገዳ ስርዓት በዩኔስኮ የመመዝገብ አጋጣሚው ሰፊ በመሆኑ የተቋማቱ ተጠብቀው መቀጠል እድላቸውን ያሰፋዋል። በሌላ በኩል የተለያዩ እምነት ተከታዮችም የገዳን ስርዓት እንደማንነታቸው መገለጫ ስለሚቆጥሩት በከበራዎቹ ላይ ኦሮሞዎችን ጨምሮ የሌሎች ብሔርና ብሔረሰቦች፤ እንዲሁም የተለያየ እምነት ተከታዮች በከበራዉ ላይ ተገኝተው ማክበራቸው ለቀጣይነቱ ፍንጭ አመላካች ናቸው።

# ምዕራፍ ስምንት
# ማጠቃለያና ይሁንታ

## 8.1. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት የጉጂ ኦሮሞን የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹን መተንተን ያስፈለገበት ዐቢይ ዓላማ ከበራዎቹ ያሏቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳዎችን ለማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ ያሉትን የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በመለየት፣ ከበራዎቹ መቼና የት እንደሚከወኑ ለመተንተንና ለመግለጽ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሱት በከበራዎቹ ውስጥ የሚቀርቡ ቁሳዊ ባህሎችና ተምሳሌቶቹ ያላቸውን ተግባርና ፍች በመግለጽ፣ እንዲሁም በቃሉ ተቋም የታዩትን ለውጦችና ቀጣይነታቸውንም ለማሳየት ተችሏል፡፡

የጉጂ ኦሮሞ የዋቄፋታ ሃይማኖት ተከታዮች በቃሉና ገዳ ተቋማት አማካይነት ከፈጣሪያቸው ጋር መስተጋብር እንደሚፈጥሩ ይገልጻሉ፡፡ አብዛኛውን መስተጋብር የሚያካሂዱቱ በከበራዎች አማካይነት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቃሉ ከበራዎች የገዳ ስልጣነ-ሢመት፣ የጎንደሮና የመሳሰሉትን ከበራዎች ያካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህም ከበራዎች እያንዳንዳቸው የየራሳቸው የሆነ መቼት፣ ማህበራዊ ዓላማ፣ ክዋኔና መከወኛ ቁሳዊ ባህሎች አሏቸው፡፡ እንደ ማህበረሰቡ እምነት ከበራዎቹ በዋናነት የሚከወኑት የእግዚአብሔር ህግጋት ናቸው የሚሉትን እንዲከበሩ፣ ህግጋቱንም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከተጣሱ ደግሞ በከበራዎች አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅና ምህረትንም ለማግኘት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይህም ሲባል እግዚአብሔር ዝናቡን ዝናበ ምህረት፣ አዝመራው ጎምርቶ ጎተራ እንዲሞላ፣ ከብቶቻቸው እንዲረቡና ምርቶቻቸውም እንዲያምር፤ እንዲሁም ከበሽታ ነፃ እንዲሆኑላቸው፣ ሰውንም ከበሽታ፣ ከጦርነት፣ ካላስፈላጊ እስርና እንግልት እንዲታደጋቸው የሚለማመኑበትና በተጓዳኝም እግዚአብሔር ላደረገላቸው መልካም ስራ ምስጋና የሚያቀርቡበት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በከበራዎቹ የጉጂ ኦሮሞ ማንነታቸውን አጠናክረውና የገዳን ስልጣን ሽግግር ዲሞክራሲያዊ ሂደት ማቆየታቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ባጠቃላይ እነዚህን ከበራዎች በማህበረሰቡና በፈጣሪያቸው፣ በቃሉና ገዳ መካከል ያሉትን መስተጋብሮች እርስ በርሳቸው ምን እንደሚመስሉ በተወሰነ ደረጃ ከሚከተለው ሞዴል ለማየት ይቻላል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በሞዴሉ ውስጥ የወከሉት ከለሮች ከጉጂ ኦሮሞ የዓለም አተያይ እሳቤ ላይ በመንተራስ የቀረቡና ከዚያ ጋር ቀረቤታ ያላቸውን ያካተቱ ናቸው፡፡ ይኸውም፡- ጥቁሩን ከፈጣሪያቸውና ከማንነታቸው ጋር ያያይዙታል ስለዚህ ዋቃን እንዲወክል ተደርጓል፣ ቃሉ ደግሞ የጥቁር ግራጫ ከለር እንዲወክለው የተደረገው መንፈሳዊ ኃይሉ ከዋቃ ያገኘው ስለሆነ ከዋቃ መለስተኛ ለመሆኑ ለማሳያነት ነው፣ ግራጫው ደግሞ ገዳን እንዲወከወል የተደረገው በመንፈሳዊ ኃይሉ ከቃሉ ሰለሚያንስ ነው፣ አረንጓዴ ደግሞ የጉጂን ማህበረሰብና አካባቢውን ይወከወላል፣ ነጭ የሚወክለው አመድ፣ ድርቅንና ኮቴ ደረቅነት ነው፣ እንዲሁም ቀይ ደግሞ ከደም ጋር ይያያዛል፡፡ ደም ደግሞ ለእግዝኣብሔር መስዋዕትና ልመና ማቅረቢያ እንደሆነና በምትኩ ከእግዚኣብሔር በረከትን ማውረጃ እንደሆነ ስለሚታመን ነው፡፡




ምስል፡-10 የዋቄፋታ፣ ገዳ፣ ቃሉና ዋቃ መንፈሳዊ ግንኙነትና ከበራዎች የሚያሳይ ሞዴል
(ምንጭ፡- የጥናቱ አቅራቢ)

ስዕላዊ መግለጫ

- **ጥቁሩ ክብ ቀለም፡-** እግዚኣብሔርን (ዋቃን) ይወክላል፡፡ እንደ ኦሮሞ የዓለም አተያይ ጥቁር ከሰማይ፣ከንጹህ ውሃ ጋር በማያያዝ የጥሩ ነገሮች ተምሳሌት ሲሆን፤ነጩ ደግሞ የረሃብ፣ የእርዛት፣ የድርቅና የመሳሰሉት ተምሳሌት ነው፡፡ የጥቁሩ ክብ ቀለም ተምሳሌትነት እግዚኣብሔርን ለማመልከት ነው፡፡ ክብነቱ ደግሞ ሁሉም ፍጥረታትና ዓለም በእግዚኣብሐር እቅፍ ውስጥ መሆናቸውን አመላካች ነው፡፡ ከጥቁሩ ክብ እየፈነጠቁ ወደ ውስጥ የሚያመለክቱት ጥቋቁር ቀስቶች የእግዚኣብሔርን ህግጋት፣ ፀጋና በረከትን ወካይ ናቸው፡፡ ነጩ ጠመዝማዛ መብረቅ መሰሉ ደግሞ እግዚኣብሔር ህግጋቱ ሲጣሱ ቁጣና መከራን ማውረዱን የሚያመላክት ነው፡፡ ዝግዛጉ ቀስት ደግሞ የእግዚኣብሔር ቁጣ በቀጥታ ሀጢያት በሰራው ላይ ብቻ እንደማይደርስና ምናልባትም በልጆቹ፣ በንብረቱ፣ አሊያም በቅርብ ዘመዶቹና በመሳሰሉት ላይ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

- **የጥቁር ግራጫ ክብ፡-** አባቃሉን ይወክላል፡፡ የከለሩ ተምሳሌት አባቃሉ አመጣጡ ከሰማይ (ከእግዚኣብሔር) እንደሆነ ስለሚታመን፤ ከፊል መንፈሳዊ ባህሪይን ከእግዚኣብሔር ይዞ መምጣቱንና ከፊሉ ደግሞ ሰዋው ባህሪውን የሚወክል ነው፡፡ ከጥቁር ግራጫ ክብ (ከቃሉ) ውስጥ ወደ ዋቃ የሚያመለክተውቀስት የቃሉን ምልጃና ጸሎት ሲሆኑ፤ በተቃሪኒው ረጅሙ አረንጓዴ ቀስት ወደ ውስጥ የሚያመለክተው ደግሞ የምልጃውና የጸሎቱ መልካም ምላሽ ያተረፈውን ልምላሜንና ብልጽግናን በምርቃትና ቡራኬ መልክ ለምዕመኑ ሲያስተላልፍ የሚያመላክት ነው፣ በመጨረሻም የጥቁር ግራጫው ቀስት ወደ ግራጫው ክብ የሚያመላክተው ደግሞ ቃሉ ለገዳ ከርቤ (qunbii) በማስነከስና በመባረክ መንፈሳዊ ባህሪን ማላበሱን ለመግለጽ ነው፡፡

- **ግራጫ ክብ፡-** ገዳን ይወክላል፡፡ ከለሩ ግራጫ የሆነበት መንፈሳዊ ኃይሉ ከቃሉ ያነሰ ነገር ግን ከተራው ምዕመን ለቃሉም ሆነ ለእግዚኣብሔር ቀረቤታ እንዳለው ለማመላከት ነው፡፡ ከግራጫው ክብ (ገዳ) ውስጥ ወደ ቃሉና ዋቃ አቅጣጫ የሚያመለክቱት የገዳን ምልጃና ጸሎት ሲሆኑ፤ በተቃሪኒው አረንጓዴ ቀስት ወደ

ውስጥ የሚያመለክተው ደግሞ ከእግዚኣብሔር የምልጃውና የጸሎቱ መልካም ምላሽ ያተረፈውን ልምላሜንና ብልጽግናን በምርቃቱ መልክ ለምዕመኑ ማስተላለፉን ነው።

- **አረንጓዴ ክብ፡-** ዋቄፋታን ይወክላል። አረንጓደው ከለር የዋቄፋታውን መልካምድርና መተዳደሪያውን የሚወክል ሲሆን፣ የከለሩ ተምሳሌት ልምላሜን፣ ጥጋብን፣ ሰላምን ይወክላል። ከውስጡ ወደ ውጪ የሚያመለክቱት ቀስቶች ደግሞ ዋቄፋታዊ የገዳ አምላክ፣ የቃሉ አምላክ፣ የፈጠርከን ጥቁር እግዚኣብሔር ሆይ! እያለ ሦስቱንም እርከን ጠብቆ መጸለያቸውን አመላካች ናቸው።

- **ነጩ ቀስት፡-** ከዋቄፋታው መነሻ አድርጎ ወደ ውጪ የሚወጣው ነጭ ቀስት ሀጢያትን (Cubbuu) የሚወክል ነው። የከለሩ ተምሳሌት እንደ ኦሮሞ የዓለም አተያይ ነጪ የረሃብ፣ የእርዛት፣ የድርቅና የመሳሰሉት ተምሳሌት ነው። ስለዚህ ዋቄፋታ ሀጢያት ከሰራ ከዋቃ ህግ ውጭ ሆኗል ማለት ነው። ከዚህም የተነሳ ከለምለሙ ሕይወት፣ ከሰላማዊ ኑሮው ሊወጣና መከራን ሊቀበል እንደሚችል አመላካች ነው።
- **ቀዩ ግማሽ ክብ ቀስት፡-** የቃሉን ከበራዎችና ፋይዳዎቹን አመላካች ነው። የቀስቱ መነሻ የሚያመለክተው የቃሉ ከበራዎች ማህበረሰባዊ ዕውቀት እንደመሆናቸው መጠን ከዋቄፋታው ውስጥ የወጡ መሆናቸውን ሲያመለክት፣ የቀስቱ ጫፉ ደግሞ ወደ ውስጥ የሚያመለክተው አንድ ሀጢያት የሰራ ግለሰብ በሚከወኑ ከበራዎች አማካይነት ወደ ማህበረሰቡ ሰላማዊ ሕይወት ሊመለስ መቻሉንና የከበራውም ፋይዳ ያ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ከለሩ ቀይ የሆነበት ምክንያት አብዛኛው ከበራዎች የሚከወኑት ለእግዚኣብሔር መስዋዕት በማቅረብ ስለሆነ የመስዋዕቱን ደም እንዲወክል ነው።

- **ነጩ ክብ መስመር፡-** በአረንጓደው ክብ ላይ ዙሪያውን ከቦት ያለው ነጭ መስመር ዋቄፋታ በተለያዩ አካላት ይደርስበት የነበረውንና እየደረሰበት ያለውን ተግዳሮቶች አመላካች ነው።

በምዕራፍ አምስት ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው በቦረናና ጉጂ ዞኖች ከሚኖሩት ህዝብ የዋቄፋታ ሃይማኖት ተከታዮች የተወሰኑ ናቸው። ይሁን እንጂ አብዛኛው የሌላ እምነት ተከታዮች በገዳና በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ እንደሚሳተፉ ለማረጋገጥ ተችሏል። ለአብነት ያህል በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ አንደ የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ሰው ባጋጣሚ የሰው ነፍስ በእጁ ቢጠፋ፤ እንደ ዋንኛ አማራጭ የሚጠቀመው ወደ ገዳ ወይም ቃሉ ተቋም እጅ በመስጠት ወይም በመጠለል ለዘለቄታ በጎንዶሮ ሃማኖታዊ ከበራ ችግሩን መፍታት ላይ ነው። አሊያም ወደ ፖሊስ ጣቢያ እጁን በመስጠት በፍርድ ቤት በኩል የሚሰጠውን ውሳኔ መቀበል ነው። ስለዚህ አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል በጎንዶሮ ከበራ መፈጸሙን እንደሚስማሙበት ከመረጃ አቀባዮቹ ለመረዳት ችያለሁ። ምክንያቱም የፍርድ ሂደቱንም ቢጨርስና ነፃ ቢለቀቅ፤ ህሊናው ሁሌም ነፃ እንዳልሆነ እንደሚሰማው ተደርጎ ይታመናል። ስለዚህ ለጥፋቱም ሆነ ለህሊናው እረፍት የሚሰማው በጎንዶሮ ከበራ ሂደት ሲያከናውን እንደሆነ አብዛኛዎቹ የሚስማሙበት መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ። ስለዚህ ከዚህ ሂደት የምንረዳው የማንኛውንም ሃይማኖት ተከታይ በቃሉና ገዳ ከበራዎች ከመሳተፍ እምብዛም እንደማያግደው ነው።

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ሃይማኖታዊ ከበራዎቹና ሂደቶቹ የማህበረሰቡ ውቅር ዕውቀቶች ናቸው። ይኸውም፡- እንደ ማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ካጋጠማቸው ችግሮች የተነሳ፣ አሊያም ሊያጋጥመን ይችላል ከሚሉት ስጋት በመነሳት ማህበረ-ባህላዊ አደረጃጀታቸውን ጠብቀው ለማቆየት፣ ከፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ስጋት ለመታደግ ሲሉ የተፈጠረና በልማድ እየዳበረ የመጣ እንደሆነ ያመላክታል። ይህ ዕውቀት በግለሰቦችና ቡድኖች ተዋቅረው፤ ከዚያም ወደ ተቋማት በመግባት ለዚህ ማህበረሰብ እንደመተዳደሪያ ህግና ደንብ ሆኖ ሲያገለግሉ ይታያሉ።

ከበራዎችን ያየን እንደሆነ ከቃሉ አንስቶ እስከ ሀገር ሽማግሌዎች ባሉ ደረጃዎች የሚከወኑ ሲሆን፤ አስተምሮቱ ግን የቃሉ እንደሆነ ከሚቱ ላይ ለመረዳት ይቻላል። ከበራዎቹ በቃሉና በመማክርት አባላቶቹ አማካይነት በየራሳቸው መቼት ላይ ይከወናሉ። የሚከወኑበትም ምክንያቶችና መከወኛ ቁሳዊ ባህሎቹ የተለያዩ ናቸው። ቀደም ስል እንዳየነው በዚህ ክዋኔ ላይ የቃሉ መማክርት አባላት የየራሳቸው የስራ ድርሻ አላቸው። ለምሳሌ በከበራው ላይ የቀረበው መስዋዕት መሳካት አለመሳካቱን የሚገልጹት ሞራ አንባቢዎቹ ናቸው። በዚህ መልክ በየዘርፉ

የእያንዳንዱ እይታ ምን ይመስላል? የሚለው ተዳምሮ ስለዚያ ከበራ መሳካት ይገለጻል፤ ይፈጸማል፡፡

በከበራ ውስጥ የቃሉን ተግባር የተመለከትን እንደሆነ እንደ አብዛኞዎቹ ተመራማሪዎች ገለጻ ሃይማኖታዊ ፋይዳ እንዳለው ብቻ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት ለማየት እንደተቻለው ከዚህ በተጨማሪ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተግባራትም አለው፡፡ እነዚህ ተግባራት በግልጽ የሚታዩት ደግሞ በይበልጥ በገዳ ስልጣን ሢመት ከበራ ላይ ነው፡፡ ይኸውም ወደ አባ ሙዳው ቀዬ የሚደረገው ታላቅ መንፈሳዊ ጉዞ የተለያዩ ዓላማዎች አሉት፡፡ አንደኛው እያንዳንዱ የገዳ መሪዎች ከአባ ሙዳው ምርቃትና ይሁንታ ማግኘት ስላለባቸው ነው፡፡ ሌላውና ዋነኛው ደግሞ የጉጂ ኦሮሞ ጎሳዎች እያንዳንዳቸው በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ኩኔቶች ላይ ተገናኝተው ይወያያሉ፤ በተያያዘ መልኩ አንድነታቸውንም ጠብቀው እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የኦሮሞ ሃይማኖት ተቋም በኦሮሞ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በሌላ በኩል የገዳን ስልጣን በማጽደቅ ሂደት ውስጥ በአግባቡ ተመርጦ ያልመጣውን ገዳ ቁንቢ በመስጠት እንደማያጸድቅና በተዘዋዋሪ መንገድ ዴሞክራሲያዊ አካሄዱን እንደሚያስጠብቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የቃሉና ገዳ ተቋማት የተለያዩ ግጭቶችን በመፍታትና ዘላቂ ሰላምን በመመስረት የአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ሲያከናውን ይታያሉ፤ ቀድሞ የነበረውን ሰላማዊ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ከመመለስ አኳያ ያለው ፋይዳም ተጠቃሽ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በእያንዳንዱ ከበራዎች በተደረገው ንጥል-ጥናት መሰረት ተተንትነው ያላቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳቸውን ለመግለጽ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡- ቃሉ የውስጥ ግጭቶችን (ገዳ ከገዳ፣ ግለሰብ ከግለሰብ፣ ግለሰብ ከማህበረሰብ ጋር) እንዲሁም የውጭ ግጭቶችን (ጉጂ ከአጎራባች ብሄርና ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጋር) በመፍታት (በጎንዶሮ) ሰላምን ከማስፈንና ማስጠበቅ አኳያ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቀድሞ የነበረውን ማህበራዊ ህይወት ከመገንባትና ወደ ቀድሞ ሰላማዊ ኑሮ ከመመለስ አኳያ ያለውን ድርሻ ለማየት ተችሏል፡፡ ስለዚህ እንደ Bell አገላለጽ ከበራዎቹን ታዳሚዎች በኑሯቸው የሚጠቀሙባቸውንና የሚመሩባቸውን እሴቶችና ተምሳሌቶች መግለጫ አድርገው ይጠቀሙባቸዋል (Bell, 1997)፡፡

የቃሉ ተቋም ዘርፈ-ብዙ ተግባራት ያለው ቢሆንም በተለያዩ ጊዜያት በተነሱ መንግስታት፣ ዘመናዊ በሚባሉ ሃይማኖቶችና ግሎባላይዜሽን ሳቢያ አውንታዊም ይሁን አሉታዊ ለውጦችና ቀጣይነት የታዩባቸውም እንዳሉ ለማየት ተችሏል። አሉታዊ ለውጦችን የተመለከትን እንደሆነ በቃሉና ገዳ ስርዓትና ተቋማት ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በአጼዎቹ አገዛዝ፣ በደርግና በኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስታት በመጠንና በዓይነት ከመለያየቱ በቀር ተፅዕኖዎች ነበሩ፤ አሉም። የደርግ አገዛዝን የተመለከትን እንደሆነ የገዳን ስርዓት በኃይል ለማጥፋት መሞከሩና የቃሉን ተቋም ደግሞ እንደኋላ ቀር አስተሳሰብና ባህል በመቁጠር የማዳከም ሁኔታዎች ይታዩ ነበር። የአጼዎቹንና የኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት ደግሞ የሚያመሳስላቸው ቃሉና ገዳዎችን በመደለያ የመያዝ ስትራቴጂ በመጠቀም የእነሱ አስፈጻሚዎች ማድረጋቸው ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት አዲስ የአከላለል ስትራቴጂ የተነሳ የጉጂ ኦሮሞ መገለጫ ከሆኑት ውስጥ የቃሉ ተቋም፣ የተለያዩ የቃሉ መንፈሳዊ ቦታዎችና በገደብ የሚገኘው የገዳ መንፈሳዊ ቦታ ወደ ጌዴኦ ዞን በመካለሉና ለተለያዩ ግልጋሎቶች እንዲውሉ በመደረጉ እንዲረሱ፣ ሲያሜያቸውም እንዲዛቡ ከማድረግ አንፃር እንደውጫዊ ተፅዕኖ አድራሽ ሊቆጠሩ ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህ ሃማኖታዊና ባህላዊ ተቋማት እነዚህንና የመሳሰሉትን ጫናዎች በመቋቋምና በማንሰራራት አሁን ላሉበት ደረጃ ደርሰዋል። ለዚህም በተወሰነ ደረጃ ከአጼዎቹ አገዛዝ፣ የደርግ የተሻለ ነበር። ከደርግ ደግሞ የኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት ለባህልና ቋንቋ ከሰጠው መብት አንጻር የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም በሀገሪቱ ስራ ላይ ያለው ሕገ-መንግስት አጽንኦት የሰጠው «የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን»ማንነት ያከበረና የራሳቸውን ጉዳይ ለራሳቸው እንዲፈቱ መብት የሰጠ ነው።

በሌላ በኩል ቀደም ሲሉ ከተከበሩት ከበራዎች፤ ማለትም ከደርግ የስልጣን ዘመን አንስቶ ከተከበሩት የተለየ የሚያደርጉት ብዙ ነገሮች እንዳሉት ከመረጃ አቀባዮች ለመረዳት ተችሏል። ይኸውም፦ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ለከበራው መንግስት ክብር በመስጠት የኢ.ፌ.ድ.ሪ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ ሌሎችም ከፍተኛ ባለስልጣኖች ታድመዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በሚኤ ቦኮ በሚካሄደው ከበራ ላይ የፀጥታ ክፍሉን የሚቆጣጠሩት ጃልዳባዎች ብቻ ሲሆኑ፤የሚጠብቁትም በልምጭ ብቻ ነበር።ለዚህም እንደምክንያት የሚያቀርቡት ታደሚዎቹም ባህሉንና ስርዓቱን ስለሚያውቁና ስለሚያከብሩ ብዙ ያፈነገጡ የፀጥታ ችግሮች እንደማይከሰቱና ለስርዓቱም ተገዥ በመሆናቸው ነው። አሁን ግን ከበላይ አካል ከሚመጡትና ከዘመኑም ጋር

አንዳንድ የፀጥታውን ሁኔታ ሊያውኩ የሚችሉ አካላቶች ሊኖሩ ይችላሉ ከሚል ስጋት የተነሳ ከቀበሌ ታጣቂ እስከ ፌደራል ፖሊስና ልዩ ጥበቃዎች ሊሳተፉ ችለዋል፡፡
ከዚህ በተጨማሪ ከዘመኑ ጋር አብረው የመጡ ለውጦችን ስንመለከት ቀደም ሲል ሀጋና ለማስገባት ከሚኤ ቦኮ ወደ ሱታኤ የሚኬደው በእግር ሲሆን አሁን የመንግስት አካላት ለመስዋዕት የሚቀርበውን ከብት ጭምር በመግዛትና በመኪና እዚያ ድረስ ማድረሳቸውን ለማየት ችያለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በጥናቱ ለማየት የተቻለው በ2008 ዓ.ም. በሚኤ ቦኮ ላይ በተደረገው የጉጂ የገዳ ስልጣን ሽግግር ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተቋርጦ ለነበረው የጉቱ ገዞ የተፈጠሩትን ስህተቶች አምነው ለቀጣይ ወደ ቃሉ ተቋም ስጦታ በመያዝና በመጓዝ የገዳን ስልጣን-ሢመት ለማከናወንም ቃል የተገባበት ከበራ ነበር፡፡

ባጠቃላይ ይህ ጥናት በውስጡ በዓላማው ስር ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ የሰጠ ነው፡፡ ይኸውም፡- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ከበራዎች የገዳ ስልጣን-ሢመት ማጽደቅ፣ የጎንዶሮ፣ የፋጭ፣ የሁሉቃና የቃሉ ጋብቻ ከበራ እንደሆኑ በዝርዝር ታይተዋል፡፡ እነዚህ ከበራዎች የማህበረሰቡ ውቅር እውቀት እንደሆኑና እሱንም እንዴት አወቁት የሚለውን ደግሞ በማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያንና በኢፒስቲሞሎጂ ንድፈ-ሀሳቦች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ከበራዎች የሚከወኑትም ለማህበረሰቡ ካላቸው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳዎች ነው፡፡ ይህም ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ተተንትነው ተገልጸዋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ እነኚህ ከላይ የተዘረዘሩት ከበራዎች የሚከወኑት በዋናነት በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሯዊ መቼቶች ላይ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የጊዜ ጉዳይ ነው፡፡ የቃሉ ከበራዎች ማህበረ-ባህሉ ባስቀመጠው ጊዜና ቦታ የሚከወኑ ናቸው፡፡ በከበራው ላይ የሚቀርቡ ቁሳዊ ባህሎችም ሆኑ ክዋኔዎቹ ከባህሉ አኳያ የራሳቸው ተምሳሌቶች አሏቸው፡፡ ታዲያ እነዚህን ተምሳሌቶች በተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ተተንትነው ያላቸውን ፍች በዝርዝር ለማየት ተችሏል፡፡

## 8.2. ይሁንታ

ስለቃሉ ከበራ ስናነሳ፣ የቃሉን ተቋም ክዋኔዎችና ፋይዳዎቹ ማለታችን ነው፡፡ ቃሉ ደግሞ የዋቄፋና ሃይማኖት መሪ ነው፡፡ ስለዚህ የእሱ ተግባራትና ሃይማኖታዊ ስነ-ምግባሩ፣ እንዲሁም የቃሉን ተቋም ውስጣዊና ውጫዊ አደረጃጀት በተወሰነ ደረጃ የቀድሞውን ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ሌሎች የመጤ ሃይማኖቶች ተፅዕኖ አሻራዎች በቃሉ ተቋም ውስጥ ሰርገው በመግባት ህገረሰባዊነቱ ላይ ጠባሳ እንደፈጠሩ ለማየት ተችሏል፡፡

ለአብነት ያህል፡- በምዕራፍ ሰባት ስር እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አባቃሉንና የተወሰኑ አባገዳዎችን ክርስትና በማስነሳት፣ እምነቱንም እንዲቀበሉ በማድረግና ሌሎችንም ስርዓቶች እንዲከተሉ የማድረግ ሁኔታዎች ታይተዋል፤ ይታያሉም፡፡ ከነዚህም ውስጥ አዕጿማትን ማክበር፣ በአንገታቸው ላይ ማዕተብ ማሰር፣ የመላዕክት ምስሎችን በገልማው ውስጥ የመስቀልና መንፈሳዊ መዝሙሮችን ማስደመጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን ይህም ሆኖ ሳለ በቃሉ ተቋም ውስጥ የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱን ተግባራትና ፋይዳቸውን በመቃወም ክዋኔዎቹን ማስቆም የቻለ አካል አልነበረም፤ እየተከወነም ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ባዕድ ስርዓቶችና ሃይማኖታዊ ቁሶች የዋቄፋና ሀገረሰባዊ ሃይማኖት መገለጫዎች ስላልሆኑ ከሃይማኖት መሪዎቹም ሆነ ከተቋሙ ውስጥ ማስቀረት የሚቻልበትን መንገድ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/በት ከቃሉ መማክርት አባላት ጋር በመመካከር የመፍትሔ አቅጣጫ ቢፈለግ፤ ይኸውም፡- አሁን የኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት ለሀገረሰባዊ ሃይማኖቶችና ባህል ማንሰራራት በፈጠረው ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም፤ የቃሉ ተቋም ወደ ቀድሞው ሁኔታ ማንሰራራቱን እንደጀመረ ሁሉ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮቹ ተፈተው ወጥነት ያለው ተቋም ማድረግ ቢቻል፡-

- ሌላው በአሁን ወቅት በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች የገዳ ተሃድሶ ስርዓቶች እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለገዳ ስርዓት ማንሰራራት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህ እንደ አብነት በ2007 ዓ.ም. በሀረርጌ የተካሄደውን የ«ኦዳ ቡሉቱም» የገዳ ከበራ ተጠቃሽ ነው፡፡ በምርቃት ስርዓቱም ሆነ ምርቃቱን በመቀበል የተሳተፉ ብዛት ያላቸው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እንደነበሩ ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያመለክተው የገዳ ስርዓት ለኦሮሞዎች ሁሉ እንደ አንድ መገለጫ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ እምነታቸው ሳይገድባቸው በስርዓቱ ላይ መታደማቸው ደግሞ የማንነታቸው መገለጫ በመሆኑ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ተቋም መኖሩ ለባህሉም ሆነ ለህገረሰባዊ ሃይማኖቱ ወሳኝ በመሆኑ ማህበረሰቡ በቃሉና ገዳ ስርዓት የማንሰራራት ሂደት ውስጥ ተደጋጋፊነታቸው በግልጽ ማሳየትና ትኩረቱንም በሁሉም አቅጣጫ ቢያደርጉ፡-

- ከዚህ ጋር በተያያዘ አሁን በአዲስ መልክ ተዋቅሮ ያለው የኦሮሚያ አባገዳዎች አንድነት ጉባኤ (Gumii tokkummaa abbooti gadaa Oromoo) መዋቀሩ እንደ ኦሮሚያ የገዳ ስርዓቱ አንድ ዓይነት አካሄድ እንዲፈጠር እንደሚያደርግ ጥርጥር የለውም። ነገር ግን በዚህ ጉባኤ ውስጥ ለቃሉ ቦታ ሊሰጠው እንደሚገባ የአጥኚው እምነት ነው። ምክንያቱም አንዳንዴ አፈንጋጭነት ማለትም፡- ቀደም ሲል በምዕራፍ ሰባት ስር እንዳየነው አንዳንድ አባገዳዎች ከተፈቀደላቸው የስልጣን ጊዜ በተጨማሪ የማገልገል ፍላጎት ሊያሳዩ ይችላሉ። በሌላ በኩል የመንግስት አካላትም በስልጣን ላይ ያለው ገዳ ለእነሱ አሰራር የተመቻቸው ከሆነ የማስቀጠል ሁኔታም ይታይ እንደነበር ተገልጿል። ስለዚህ ይህን ዓይነት ክፍተት ቀደም ሲል በባህሉና በሃይማኖቱ ይቆጣጠሩበት የነበረው በዋናነት በቃሉ ተቋም አማካይነት ነው። ታዲያ ይህ ባህልና ወግ ሳይሸረሸር መተላለፍ ስላለበት ከአባገዳዎቹ ጉባኤ መዋቅር በተጓዳኝ በአሁኑ ወቅት ስርዓቱን ጠብቆ ያለውን የጉጂ ቃሉ ቦታ ቢኖረው ስርዓቱን ምሉዕ ሊያደርግ ስለሚችል የሚመለከተው አካል ቢያሰብበት፡-

- ሌላው ስለቃሉ ተቋም በሪፈረንደም ወደ ጌዴኦ ዞን፣ ወናጎ ወረዳ መካተቱ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ቅሬታ እንዳሳደረባቸው ተገልጿል (Asebe, 2007)። ከዚህ በተጨማሪ በመስክ ቆይታዬ ወቅት ባሰባሰብኩት መረጃ የማንነታችን መገለጫ የሆነውን ‹‹የቃሉ ተቋም›› ለሪፈረንደም መቅረቡ በራሱ አግባብነት እንዳሌለው ቅሬታ ባዘለ አነጋገር መግለጻቸውን ለማረጋጥ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ «ገልማ ቃሉ» ከቦታነቱ ባሻገር ለጉጂ ኦሮሞ ያለውን ፋይዳ የጉጂ ኦሮሞዎች ከተለያየ ቦታ መጥተው የሚገናኙበትና የተለያዩ መረጃዎችንም የሚለዋወጡበት ማዕከል እንደሆነና አሁን ግን እንደበፊቱ ለመሄድ ብዙም ምቾት እንደማይሰማቸው ካደረጉት ገለጻ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህ ጋር ተያይዘው የማምለኪያ ስፍራዎቹም ወደ ወናጎ ወረዳ የተካተቱ እንዳሉና በአሁኑ ወቅት ከመንፈሳዊ ግልጋሎታቸው ይልቅ ለሌላ አገልግሎቶች እየዋሉ እንደሆነ በመስክ ቆይታው ወቅት ለመረዳት ተችሏል። ለአብነት ያህል የቂሊጦ ተራራን (kooba qilixoo) ትክል ድንጋይ አምጥቶ በመትከል ጥንታዊ ይዘቱንም ቀይረው የመለስ ፓርክ ተብሎ መሰየሙ እጅግ

እንዳስከፋቸው ይገልጻሉ። ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊና ሃይማኖታዊ አሻራዎችን ጥያቄ ውስጥ ከሚያስገቡ ድርጊቶች ተቆጥበው ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመወያየት ለወደፊት በሰላማው መንገድ ለጉዳዮቹ የመፍትሔ አቅጣጫ ቢቀመጥላቸው፡-

- ከመንግስት በኩል በቃሉና ገዳ ተቋማት ላይ ነባሩን ባህላዊ፣ መንፈሳዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተግባራት በሚጥስ መልኩ፤ ቀጥተኛ የፖለቲካ ተሿም እስኪመስሉና የፖለቲካዊ አስተዳደር ቦታ በመስጠት በተቋሙና በተቋሙ መሪዎች እጅ የማስገባቱ ሁኔታ የታየበት ወቅት እንደነበርና አሁንም በተወሰነ ደረጃ እየታየ እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ ለማየት ተችሏል። ስለዚህ ይህ ዓይነት አካሄድ የተቋማቱ ህልውና ነጻነት ስለሚያሳጣውና ተዓማኒነታቸውንም ስለሚቀንስ የመንግስት ከእንዲህ ዓይነቱ ጣልቃ ገብነት የሚታቀብበት መንገድ ቢፈጠር፡-

- በቃሉና በገዳ የከበራ መቼቶች ላይ ያለው ገጽታ የተሻለ ሁኔታዎች እንዳሉ ያሳያሉ። ለምሳሌ፡- የሚኤ ቦኮን መንፈሳዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስፍራ ያየን እንደሆነ በተወሰነ ደረጃ ጥብቅ ነው። ነገር ግን የቃሉ ማምለኪያ ተራሮችን የተመለከትን እንደሆነ ከበፊቱ ለምነቱን የማጣት፣ ቦታዎቹም በግለሰቦች እየተገፉ መወሰድና የመሳሰሉ ችግሮች እንዳሉ በምልከታ ወቅት ለመረዳት ተችሏል። ስለዚህ እነዚህ የከበራ ስፍራዎች በመንግስት በኩል የህግ ጥበቃና እንክብካቤ ቢደረግላቸው፡-

- እንደ ጉጂ ኦሮሞ ዋንኛው የገዳ ስልጣን መረካከቢያ ስፍራ ሚኤ ቦኮ ነው። በሚኤ ቦኮ የገዳ ማዕከል ሊሰራ እንደታቀደ ለማወቅ ችያለሁ። ነገር ግን ከዚህ ጋር ተያይዞ የቃሉ ገልማ በዘመናዊ መንገድ የጉጂን ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች በሚገልጽ መልክ ወረዳው ማህበረሰቡን በማስተባበር ቢሰራ፤ ከባህላዊና ሃይማኖታዊ ተቋምነቱ ባለፈ እንደ ቱሪዝም መስዕብነት ሊያገለግልም ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡-

- በመጨረሻም ገዳን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እየተደረገ ያለው ጥረት ቢሳካ እነዚህ በጥናቱ ውስጥ የተነሱት ከበራዎችና ባህሉን ለማስጠበቅ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠሩ ጥርጥር የለውም የሚሉትን የይሁንታ ሀሳቦች አቀርባለሁ።

## ዋቢ.ዎች

### 1. በእንግሊዝኛ የተጻፉ

#### 1.1. Books


Asmerom Legesse. (1973). *Gada, the Three Approaches to the Study of African Society.* New York. The free Press of A division of Macmillan Publishing. Co. Inc.

______________. (2000). *Oromo Democracy.* An Indigenous African Political System. Lawrence Eville, NJ: The Red Sea Press.

Baldick C. (2nd ed.).(2001). *The Concise Oxford Dictionary of Literary Terms.* Oxford University Press.

Ballenger, E.W. (1998). *Figures of Speech Used in Bible; Explained & Illustrated.* Michigan; Baker Books house Grand Rapids.

Barnard A. & Jonathan S..(2002). *Encyclopedia Of Social & Cultural Anthropology.* London & New York.

Bartels, L. (1983) *Oromo Religion Myths and Rites of the Western Oromo of Ethiopia*-An Attempt to Understand Berlin: Dietrich Reimer Verlag.

Bauman, R. (1983). *The Field Study of Folklore in Context.* In Handbook of American Folklore, Richard Dorson, Bloomington: Indian University Press, PP 362-368.

Bell, C. (1997). *Ritual:Perspective and Dimensions.* Oxford: Oxford University.

Ben-Amos, Dan. (1993). *"Context in Context."* Western Folklore, vol, 52, no 214, PP 209-226.

Berger and Luckman. (1966). *The Social Construction of Reality.* United States of America.

Best Jhon, & Jems V. (7th ed.). (1993). *Research in Education.* New Delhi: Printice Hall of India Private Limited Press.

--------------. (2006). *Folklore in Context.* Nordic journal of African studies. New Delhi:Vol.15,No.3,South Asia Publishers.

Bronner, Simon J. ( 2007). **The Meaning of Folklore:** *The analytical essays of Alan Dandes.* Utah: Utah State University Press

Burr, V. (2nded.).(2003). *Social Constructionism.*Taylor & Francis Routledge

Campbell, Joseph.(1970). *The Hero With A Thousand Faces.* Princeton University Press.

Central Statistical Agency.*The 2007 Ethiopian Population and Housing Census: results for the Oromiya Region*. Volume II, Analytical Report.CSA. A. A..

Creswell, J.W. (2nd ed.).(2007). *Qualitative Inquiry Research Design:* Choosing Among Five Approaches. Thousand Oaks, London, New Delhi: Sage Publications, Inc.

Crotty, Michael. (1998). *The Foundations of Social Research*: Meaning & Perspective in the Research Process. Sage Publications.

Danesi M. (3rd ed.) (2004). *Messages, Signs, and Meanings*: A Basic Text book in Semiotics and Communication, Studies in Linguistic & Cultural Anthropology. University of Toronto, Canadian Scholars' Press Inc. Vol.1.

Dejene Gemachu. (2011).*The customary courts of the waliso oroimo*.Gebre & et al.(ed.).Customary Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia. P.p. 251-277. The Ethiopia arbitration and conciliation Center.A.A.

Dorson, Richard M. (1972). *Folklore and Folk life: An Introduction*. Chicago, the University of Chicago Press.

Dundes, A. (1980). *Interpreting Folklore*. Bloomington: Indian University Press.

Flick, Uwi. (2007). *An Introduction To Ultimate Research*. London: Sage Publication Ltd.

Finnegan, R. (1970). *Oral Literature in Africa*. Oxford University Press, Oxford.

Gadaa Melbaa. (1988).*Oromia: An Introduction*. Khartoum, Sudan.

Georges, A. & Michael, Jones. (1995). *Folkloristics; An Introduction*. Bloomington and Indiana polis; Indiana University Press.

Goldstein, Kenneth S. (1964). *A Guide for Field Works in Folklore*. Pennsylvania, Folklore Associates Inc.

Glassie, Henry. (1999). *Material Culture*.Bloomington; Indiana University Press.

Gray. E. David. (2004). *Doing research In The Real world*, Sage Publications, London: Thousand oaks', New Delhi,

Green. Thomas, A. (1997). *Folklorean Encyclopedia of Beliefs Customs, Tales, Music and Art*, Santa Barbara, California.

Geertz, Clifford.(1973). *The Interpretation of Cultures*. New York: Basic Books.

Haberland, E, (1963). *Galla Sud-Ethiopiens Stuttgart:* W. Kohl hammer Verlag.

Israel, Itansa.(2011). *The Quest for the survival of gada system's role in conflict resolution.*Gebre & et al. (ed.). Customary Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia. P.p. 299-320. The Ethiopia arbitration & conciliation Center. A.A.

Jonathan Z. Smith. (1996). *A Matter of Class: Taxonomies of Religion.* The University of Chicago,

Jones, M. Owen (ed.). (2000). *Putting Folklore to use.* The University of Kentucky.

Julia Riemer, Frances. (2008). *Ethnography Research*, Lapan.

Knutsson, K.E. (1967).*Authority and Change: The Study of the Kalu Institution Among the Macha Galla of Ethiopia.* Gothenburg.

Marshal, C. & Rossman,G. (4th Ed.). (2006). *Designing Qualitative Research.* United States of America: Saga Publication Inc.

Matthews, Bob. & Liz Ross.(2010). *Research Methods: A Practical guide for the Social Sciences.*University of Birmingham.

Mazama, Ama & Molefi Kete Asante.(eds.).(2009). *Encyclopedia of African Religion.* Sage Publications.Inc.

McCormick, C. T. and White, K. K. (eds.). (2011). *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.*

Mohammed Hassen. (1994).*The Oromo of Ethiopia.* A History, (1570-1860), Trenton, NJ: The Red Sea Press,

Myrvold, Kristina.(2007). *Inside the Gurus Gate Ritual Uses Text Among the Skins inVaranasi.* Sweden: University Lund.

Okpewho, Isidore (1992). *African Oral Literature.* USA: Indiana University Press.

O'Neil Dennis. (2009). *Anthropology of Religion:* Overview of Religion.

Oring, Elliott. (1986). *Folk Groups and Folklore Genres*; An Introduction. Logan; Utah State University Press

O'Reilly, Karen. (2005). *Ethnographic Methods*, London. Rout ledge,

Peoples, J. and Bailey, G. (2nd ed.).(1991). *Humanity:* An Introduction to Cultural Anthropology. West Publishing Company.

Population Census Commision (Dec 2008). *Summary and Statistical Report of 2007 Population and Housing Census.* Addis Ababa: United Nations Population Fund (UNDF).

Rappaport, Roy A. (1999). *Ritual and Religion in the Marking of Humanity.* Cambridge University press.

Robert, A. Segal (ed.). (2006). *The Black Well Companion to the Study of Religion.* United Kingdom: Black Well Publishing.ltd.

Reeves,S. & et al, (2008). *Qualitative Research Methodology Ethnography.*

Salamone, Frank A. (Editor). (2004). *Encyclopedia of Rites,Rituals and Festivals.* London:Rout ledge New York

Schoemaker H. George (ed.) (1990). *The Emergence of Folklore in Everyday life: A Field guide & Source Book.* Trickster press.Bloomington; Indiana: Trickster Press.

Shipley, J.T. (1970). *A Dictionary of World Literary Terms.* Aston, The Writers' Inc. Publisher,

Shovel M..(2nd ed.).(2007). *Macmillan English Dictionary: For Advanced Learners.* New edition Free online access. International Student edition. Macmillan Publishers Lim.

Sims, C. Martha & Stephen Martin. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition.* Lagon: Utah State University Press.

Turner, Victor (1977). *The Ritual Process structure and Anti- Structure.* New York: Cornell University Press.

Van. Gennep, A. (1960). *The Rites of Passage.* Translated by M.B. Vizedom and G.L. Caffee. London Rout ledge and Keg an Paul.

Van de Loo, Joseph. (1991). *Guji Oromo Culture in Southern Ethiopia.*Religious Capabilities in Rituals and Songs.Berlin: Dietrich Reiner Verlag.

Wilson, William A.(1986*)."Documenting Folklore" In Folklore Groups & Folklore Genres An introduction.* ed. Utah State University Press.

Woodword, Ian. (2007). *Understanding Material Culture.* London; Sage publ. Ltd.

## 1.1. Articles and Theses


Abiyot Negera. (2005) "Guji-Gedeo Relation from 1880s to 1974". BA thesis. Dilla College of Teachers Education

Al-Amin Sheyto. (1998). "Gada System: Nature, Operations and Constraints, with the reference to the experience of Guji Oromo." (Unpublished). A.A.U. BA Thesis in Pol. Science and Inter. Relation ship.

Asebe Regassa.(2007). "Ethnicity & Inter-Ethnic Relations: The 'Ethiopian Experiment & The case of GUji and Gedeo." Thesis Submitted for the Degree of Master of Philosophy in indigenous study, University of Toromso.

Bascom, W..(1965). "The Forms of Folklore Prose Narratives."The Journal of American Folklore. Vol. 78, No. 302, pp. 3-20.

Clay, J W and B K Holcomb.(1986). Politics and the Ethiopian Famine 1984-1985 Cultural Survival Report 20 Cambridge.

Dinsa Lepisa. (1975)."The Gada System of Government" Addis Ababa University: LLB Thesis.

Dorson, M. Richard. (1963). "Current Folklore Theories", in Current Anthropology. Vol.4, No.1.Accessed 17/02/2008,11:12

Elfineh Udessa. (1994)."The Guji Calendar. "Proceedings of the 11th International Confernce of Ethiopian Studies. ,P.P. 61-70. Institution of Ethiopian Studies, A.A..

Emana Beyene. (2015). ‹‹Historical Documentation & Thematic Analysis of Waqeffannaa Religion & Song Among Tuulamaa Oromo.›› PhD Dissertation, University of A.A.U.

Fetterman, M. David (2010). **Ethnography Step- by- step (3rd ed.)** Los Angeles: Applied Social Research Methods Series, Volume 17 SAGE.

Fille Jalleta. (2015).‹‹Documentation of Folk Law & Description of Grammatical sketch of the Macca Oromo.›› PhD Dissertation, University of A.A.U.

Garada Rabindra. (2015)."Dynamics of Macro-Sociological Theories: A Critical Reflection in Indian Context." IOSR Journal Of Humanities & Social Science (IOSR-JHSS) Volume 20, Issue 4,PP 61-70.

Hinnant, John.(1977). "The Gada System of the Guji of Southern Ethiopia" PhD Dissertation, University of Chicago.

__________.(1981). "Guji Affinity & Case of A Conflictful Marriage." Presented at the ‹Oromo kinship & Marriage› Conference, Manchester University, England, Spring,

Hussein, Bedru. (2002.). «Contextualization of the Gospel» Among the Oromo Tribe of the Estern Wollegga Region: The Mesrete kristos Church Experience Mission Focus: Annual Review, Volume10.

Lewis,Herbert.(1970). "Kud'arfan: A multi-functional Institution Among the western Galla" In proceedings of the 3rd International conference of Ethiopian Studies.AA.I.E.S.

Meseret Abaye.(1995). "Qaallu as a dispute setting institution." Among Oromo with Specific Reference to Macca Tuulama.(Un pub.) A.A.U. BA. Thesis in Low.

Paul,C.(1986)."Recent Developments in the Functionalist Approach to Change." The University of Akron.Vol.15 No. 5.

Prown, J. David.(1982). "Mind in Matter; An Introduction to Material Culture Theory and Method."Winterthur Portfolio. Vol,17 No. 1. pp. 1-19

Song, Sarah. (2007). "The subject of Multiculturalism: Culture, Religion, Language, Ethnicity, and Race?." Law and Political Science. University of California.Berkeley Draft for Presentation at the Stanford Political Theory Workshop.

Sosis, R., & C. S. Alcorta. (2005). «Ritual, Emotion, and Sacred Symbols: The Evolution of Religion as an Adaptive Complex.»Vol.16, No.4, pp. 323-359.

Tadesse Berisso.(1994). "Warfare Among the Guji- Oromo of Southern Ethiopia." Proceeding of 11th International Conference of Ethiopian Studies. A.A. IES, Vol. II Page 309-323.

______________.(2004).«The Pride of the Guji-Oromo: An Essay on Cultural Contact and Self-Esteem.» JOS.Vol.11, No-1 and 2,

_____________.(2013).«The Riddles of the Number Ninein Guji-Oromo Culture» George F. McLean(ed.).Cultural Heritage & Contemporary Change Series II. Africa, Volume 15, P.p. 53-68. The Council for Research in Values & Philosophy.U.S.A.

Tedecha Gololcha. (1988). "The politico-Legal system of the Guji Oromo." BA Thesis in Law.School of Law A.A.U.

Tita Mekonin.(2003). "Erecha፡ Its Meaning and Significance in the Traditional Oromo Religion." (Unpublished). A.A.U. BA Thesis in Sociology and Social administration.

## 2. በአማርኛ የተጻፉ

### 2.1 መጻሕፍትና መጣጥፎች

ታቦር ዋሚ፡፡ 2006፡፡ *የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች*፡፡ አ.አ.፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ 2001፡፡ *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ-ጽሑፍ ንባብ*። አዲስ አበባ፣ አ.አ.ዩ. ፕሬስ፡፡

አለማየሁ ኃይሌና ሌሎች፡፡1998፡፡ *የኦሮሞ ታሪክ እስከ አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን*፡ ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤ አ.አ.፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

------------------፡፡ (2000)፡፡ **በገዳ ስርዓት፡ የቱለማ ኦሮሞ ፖለቲካ**፡፡ ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ **የሥነቃል መምሪያ**፤አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

### *2.2 የመመረቂያ ጽሑፎች*

ጥላሁን ኢቢዶ፡፡ (1982)፡፡ "የጌደኦ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ ዲማጽ፣ አ.አ.ዩ. (ያልታተመ)፡፡

ጥላሁን ተሊላ፡፡ (2007)፡፡ "የቱለማ ኦሮሞ "መርሣ" ወቅቶች ፎክሎር አውዳዊ ጥናት" ለአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ.. ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አ.አ.ዩ.

በኢ..ፌ..ዲ..ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ፡፡ *የኢ..ፌ..ዲ..ሪ. ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ*፡፡ ነሐሰ 15/ 1987 ዓ.ም. አንደኛ ዓመት፣ ቁጥር-1፣ አዲስ አበባ፡፡

## 3.በአፋን ኦሮሞ የተጻፉ

### 3.1. መጻሕፍትና መጣጥፎች

Alamaayyoo fi Kan biroo. (1999). **Sirna Gadaa: Siyaasaa Oromoo Tuulamaa.** Biiroo Aadaafi Tuuriizimii Oromiyaa, Mana Maxxansa Biraaninna.

Addunyaa Barkeessaa. (2011). **Akkamtaa: Yaadrimee Qorannoo Hujoo**. Finfinnee, Oromiyaa.

Danbalaa Elemaa. (2000). **Odeeffanoo Bu'uuraa kan Naannowwan oromoo Gujii.** Chamber Printing House.

Dirribii Damusee. (2009).**Ilaalcha Oromoo; Barroo Amantaa,Sirna Bulciisaa fi Seenaa Oromo.** D.G. Printing & Publishing Enterprise. Finfinnee.

Waajjira Aadaafi Turizimii Godina Gujii፡ **Baallii 74ffaa**. Maxxansa addaa, Gurr./ 2008.

WAWA, (2006). **Waaqeffannaa Barsiisa: Amantii Durjireessaa.** Jildii I,lakk.1.

### 3.2. የመመረቂያ ጽሑፎች

Imaanaa Bayyanaa. (2007). "Qaaccessa Qabiyyee Faaruu Amantii Duudhaa Oromoo Naannoo Shawaa." Afaan Oromoofi Ogbarruun. Waraqaa Eebbaa MA. (kan hin maxxanfamne). Yuniversiitii Addisaabaa.

Zlaaalam Abbabaa. (2000). "Sirna Gaa'laafi Moggaasa Qaalluu Oromoo Gujii." Afaan Oromoofi Ogbarruun.Waraqaa Eebbaa MA., (kan hin maxxanfamne). Yuniversiitii Addisaabaa.

# አባሪዎች

## አባሪ-አንድ

### ዋና ዋና የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ. ቁ | ሙሉ ስም | ፆ ታ | ዕ ድ ሜ | አድራሻ | ሥራና የት/ደረጃ | በጥናቱ ውስጥ ያላቸው ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሄሌሎ ሞኮና | ሴ | 54 | አባያ ወረዳ፣ ካላልቱ ቀበሌ | የቤት እመቤት፣ አልተማሩም | በቃሉ ተቋም የሴቶችን ድርሻ በመግለጽና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 2 | ሀጂ መሀመድ ጅብሪል | ወ | 80 | ም/ሀረርጌ (ድሬዳዋ) | የሃይማኖት አባት፣ 10ኛ ክፍል | ስለባህላዊ ዳኝነትና ገዳ ስርዓት ከታዘቡት ተነስተው መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ አንድ ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 3 | መሀመድ አማን | ወ | 52 | ም/ሀረርጌ (ድሬዳዋ) | 8ኛ ክፍል | ስለገዳ ስርዓት ከታዘቡት ተነስተው በማነጻጸር መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ አንድ ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 4 | መሀመድ አሊማያ | ወ | 75 | ም/ሀረርጌ (ድሬዳዋ) | 6ኛ ክፍል | ስለባህላዊ ዳኝነትና ገዳ ስርዓት ከታዘቡት ተነስተው መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ አንድ ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 5 | ሚጁ ባካሩ | ሴ | 59 | ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | የቀድሞ ሀዳ አምባ፣ አልተማሩም | ስለቃሉ ሚስት ተግባራት መረጃ የሰጡ |
| 6 | ሞና ጎዳና | ወ | 66 | ዋደራ ወረዳ ነዋሪ | በአሁን ደረጃ በዩባ እርከን ላይ የሚገኙ | ስለገዳ ስልጣን ሽግግር፣ ስለ አዋጅ ነገራ፣ ስለኮንቶማና ዳሪሙ አከፋፈል በበቂ ሁኔታ መረጃ የሰጡ |
| 7 | ሞኮና ናጋአ | ወ | 75 | ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | ገበሬ፣ መሰረተ ትምህርት | የቃሉ አጎትና የቅርብ አማካሪ ሲሆኑ፣ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ነበሩ፡፡ ባጠቃላይ ስለቃሉና |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የተከታተሉ | በተቋሙ የሚከወኑ ከበራዎችንና ሂደታቸውን በዝርዝር ያሰረዱና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 8 | ሳንባቴ በዳዳ | ሴ | 30 | ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | 8ኛ ክፍል፣ የቤት እመቤት | ቃሉ በተራራዎች ላይ በመውጣት መስዋት እንደሚያቀርቡና የተሳታፊዎቹን መጠን በተመለከተ ከምታውቀው የገለጸች፡፡ |
| 9 | ረጋቱ በሪሶ | ሴ | 45 | ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | የቃሉ እናት (ሀዳ ኦዳ)፣ አልተማሩም | ስለሀዳ አንባ የስራ ድርሻ፣ስለቃሉ ተግባርና በሂሮ ስለሚደረገው መስዋዕትና የክዋኔውን ሂደት በተመለከተ መረጃ የሰጡ፡፡ |
| 10 | ሮባ ኤሌማ | ወ | 70 | አባያ ወረዳ፣ ሚኤሳ ቀ/ገ/ማ | ገበሬ፣ መሰረተ ትምህርት የተከታተሉ | የጉጂ ኦሮሞ ባህላዊ ምግብ ውስጥ ስለ ቡና ቃላ ጥቅም ያሰረዱ፡፡ |
| 11 | ቃባሌ ጃልዴሳ | ሴ | 32 | የዱግዳ ዳዋ ወረዳ ነዋሪ | ሀዳ ቦላ የነበሩና አልተማሩም | ስለ ጉጂ ኦሮሞ ቁሳዊ ባህል በከፊል መረጃ የሰጡ፡፡ |
| 12 | በሪሶ ጃልዴሳ | ወ | 54 | የዱግዳ ዳዋ ወረዳ ነዋሪ | በዶሪ የእርከን ደረጃ ያሉ፣ አልተማሩም | ስለ ጉቱ ጉዞ፣ ስለቁንቢ አወሳሰድ ስርዓትና ሂደቱ መረጃ የሰጡ፡፡ |
| 13 | ባሊ ጃርሶ | ወ | 74 | የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | በሉባ ደረጃ የሚገኙ፣ አልተማሩም | በግል ከሰጡት መረጃዎች በተጨማሪ በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ ተሳትፏል፣ ስለሞራ አንባቢ፣ ስለሁሉቃ፣ ስለቁንቢና የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ መረጃ የሰጡ፡፡ |
| 14 | ባሾ ሮባ | ሴ | 35 | በአባያ ወረዳ፣ የሀሴ ጎላ ነዋሪ | የቤት እመቤት፣ አልተማሩም | ሴቶች በቃሉ ከበራዎች ላይ ያላቸውን ሚና የገለጸች፡፡ |
| 15 | ብርሃኑ ንጉሴ | ወ | 45 | ቦሬ ወረዳ ቦሬ ከተማ ነዋሪ | የቦሬ ወረዳ የቀድሞ ባህልና | ስለጎንዶሮ ዓይነቶች፣ ፋይዳዎቻቸው፣ ስለሞራ አንባቢና ስለሁሉቃ መረጃ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊ የነበሩ | የሰጡ |
| 15 | በሩ ሚጣ | ወ | 80 | የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | ባሱራ፣አልተ ማሩም | ስለባሱራ እርከንና የስራ ድርሻ ገለጻ ያደረገና በቡድን ውይይት ላይ የተሳተፈ። |
| 16 | ታከለ አብዲሳ | ወ | 62 | ም/ሀረርጌ (ድሬዳዋ) | የመንግስት ሰራተኛ | ስለገዳ ማንሰራራትና የስልጣን ሽግግር መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ አንድ ጊዜ የተሳተፉ ናቸው። |
| 17 | ታደሰ ደንቦባ | ወ | 30 | አባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | ተማሪ፣ የገዳ ደንቦባ ጉሚ ልጅ | ስለገዳ ተግባራት በቡድን ውይይት ላይ መረጃ በመስጠት የተሳተፈና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፈ ነው። |
| 18 | አለማየሁ አድማሱ | ወ | 40 | አባያ ወረዳ፣ ጓንጓ ከተማ ነዋሪ | 12+2፣የመን ግስት ሰራተኛ | ስለፋጭ ከበራ ሂደትና ፋይዳው መረጃ የሰጡ። |
| 19 | አባ ሚኤ | ወ | 76 | ዱግዳ ዳዋ ወረዳ ነዋሪ | በዩባ ደረጃ ላይ ያሉ፣ አልተማሩም | ስለዩባና ባሱራ፣ ስለሙዳ ጉዞ መረጃ የሰጡ። |
| 20 | አባባ ቃሉ ቶቴ | ወ | 50 | ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | የቃሉ ቶቴ ልጅ | ስለቃሉና የቁንቢ አወሳሰድ ሂደት፣ስለቃሉ መስፈርቶች፣ ስለተቋሙ ለውጥና ቀጣይነት ላይ ያለውንና የነበረውን ሁኔታ የገለጹና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው። |
| 21 | አዱላ ሀላከ | ወ | 80 | ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | አልተማሩም፣ ገበሬ | ስለቃሉ ጋብቻ፣ ለቃሉ የሚሰጡ ስጦታዎች፣ |
| 22 | አዱላ ዋታ | ወ | 57 | ቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | አልተማሩም፣ ገበሬ | ስለገዳና የተለያዩ ሃይማኖቶች ያለውን ግንኙነት በተመለከተ መረጃ የሰጡ። |
| 23 | ኡዴሳ ዲራሞ | ወ | 36 | የአባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | አልተማሩም፣ ገበሬ | ስለፋጭ፣ ስለሁሉቃ፣ስለ መስዋዕት ማቅረብና ጎንዶሮ ከበራዎች መረጃ የሰጡ። |
| 24 | ወርቁ ካባባ | ወ | 54 | የአባያ | 8ኛ ክፍል፣ | ስለቀጣይነትና ለውጥ ላይ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወረዳ፣ካላል ቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | ገበሬ | በቡድን ውይይት ላይ የተሳተፉ:: |
| 25 | ዘላለም በቀለ | ወ | 32 | አባያ ወረዳ፣ ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | 10ኛ ክፍል የቀበሌው ማናጀር | በቀበሌያቸው ዙሪያ ስላሉ መንፈሳዊ ስፍራዎች አስመልክቶ መረጃ በመስጠትና ለወደፊት ጥበቃውን እንደሚያጠናክሩ ያስረዱ ናቸው:: |
| 26 | ደሳለኝ ሆርዶፋ | ወ | 40 | በአባያ ወረዳ፣የጓንጓ ከተማ ነዋሪ | የአባያ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኛ፣12+2 | ስለቃሉ ተቋምና መስዋዕት ማቅረቢያ መንፈሳዊ ስፍራዎች አስመልክቶ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝና በጽ/ቤታቸው ያሉ መረጃዎች በመሳየት የተባበሩኝ፣ |
| 27 | ዲኮ ሚጁ | ሴ | 55 | አባያ ወረዳ፣ የካላልቱ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ | የቤት እመቤት | ስለቃሉ ተቋም ፋይዳና በአሁን ወቅት በቃሉ በኩል ያሉ ተግዳሮቶችን፣በቃሉ ተቋም የነበረውንና አሁን ያለውን ተግባራት በንጽጽር ማብራሪያ በመስጠት |
| 28 | ዳራሮ ሆርዶፋ | ወ | 77 | አባያ ወረዳ፣ የካላልቱ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ | ገበሬ፣ አልተማሩም | ስለጉጂ ማህበረሰብ የጋብቻ ሁኔታ መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው:: |
| 29 | ገላኖ ቦሩ | ሴ | 45 | የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | ሀዳ ቦላ | ስለቁሳዊ ባህል እና በመንፈሳዊ ጉዞው ውስጥ የሴቶችን ሚና በተመለከተ መረጃ የሰጡ |
| 30 | ገዳ ዋቆ ዱቤ | ወ | 70 | የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | የኡራጋ አባገዳ የነበሩ | ስለጉቱ መንፈሳዊ ጉዞና ቁንቢ አወሳሰድ ሂደት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ፣ |
| 31 | ገዳ ሀልቻዬ ዳራ | ወ | 65 | አባያ ወረዳ፣ የደበቃ ደቦቤሳ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ | የዌስቱ ጎሳ አባገዳ | ስለቁሳዊ ባህል፣ስለሂሮ ከበራ ሂደትና ስለቃሉ ተቋም ጥቅም መረጃ በመስጠትና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው:: |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 37 | ጎባና ቶቴ | ወ | 59 | የአባያ ወረዳ ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | ገበሬ፣ አልተማሩም | ስለጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ በተመለከተ እነማን እንደሚሄዱና ሂደቱም ምን እንደሚመስል በመግለጽ የተባበሩና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው። |
| 38 | ፍቅሩ ወ/ሰንበት | ወ | 36 | የጓንጓ ከተማ ነዋሪ | 12+4፣ የአባያ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኛ | ስለቃሉ ጋብቻ ክብራ በተመለከተ የማህበረሰቡን ተሳትፎ አስመልክቶ መረጃ በመስጠት የተባበሩ፣ ስለቃሉ ተግባራት የቀድሞውና የአሁኑን በማነፃፀር የገለጹልኝ። |

## አባሪ-ሁለት

ከቃለመጠይቁ በፊት ለቃለመጠይቁ የሚሆኑ ሰዎች ተመርጠዋል። በመቀጠል የሚመቻቸውን ሰዓት አብሮ በመወያየት ቀጠሮ ለመያዝ ተሞክሯል። ስለስራው ባጭሩ ለማስረዳት ዝግጅት ተደርጓል።

**ለጥናቱ መረጃ ማሰበሰቢያነት የቀረበ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች**

**ቃለመጠይቁን የሰጠው አካል ሙሉ መረጃ፡-**

1. ሙሉ ስም ______________________
2. ዕድሜ ______________________
3. ቀበሌ ______________________
4. የስራ ድርሻ______________________
5. ቀን ______________________

በቅድሚያ ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለዚህ ቃለ-መጠይቅ ፍቃደኛ ሆነው በመገኘትዎ ከልብ አመሠግናለሁ። በመቀጠል እነዚህ ጥያቄዎች ለዶክትሬት ዲግሪ የማሟያ ጥናት አገልግሎት ብቻ የሚወሉ በመሆናቸው የሚሰጡኝ መረጃ በእውነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ።

1. ላንተ/ላንቺ/ለእርሶ ቃሉ ምንድነው?
2. የቃሉ መማክርት አባላት እነማናቸው? ተግባራቸውስ ምን ምንድነው?
3. የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምን ምንድናቸው? ለምን ይከበራሉ?
4. እነዚህ የቃሉ ከበራዎች ከሰሙትና ካዩት ላይ በመነሳት ምን ምን ለውጦችን አስተውለዋል?
5. የጉቱ ጉዞ ማለት ምን ማለት ነው? ፋይዳውስ ምንድነው?
6. በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ መስዋዕት ለምን ይቀርባል? የክዋኔው ተምሳሌት ምን ያመለክታል?

7. ቃሉ ለእግዚኣብሔር መስዋዕት የሚያቀርበው መቼ ነው?፣ የት ነው?፣ ለምን ያቀርባል?፣ ከማን ጋር ያቀርባል? የሚሉትን በማቅረብ የተገኘውን መረጃ በመቅረጸ ድምጽ፣ በማስታወሻ ይያዛል፡፡
8. በመጨረሻም ከሚሰጡት መልስ ላይ በመንተራስ ማስታወሻ በመያዝ ማብራሪያ የሚፈልጉ ምላሾችን መልሶ በመጠየቅ ማስታወሻ ይያዛል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** በተራ ቁጥር 5 እና 6 ላይ የሚገኙ ጥያቄዎች ባህሉን በደንብ ለሚያውቁ የሀገር ሽማግሌዎች እና የባህል ኤክስፐርት (ባለሙያዎች) የቀረቡ ሲሆኑ የተቀሩት ሁሉንም ተሳታፊዎች የሚመለከቱ ናቸው።

Af-gaaffiin dura namoota af-gaaffiin isaaniif taasifamu filatamaneeru. Itti aansuun, Yeroo isaaniif mijatu mari'achuun walii beellamuuf yaalameera. Dhimma af-gaaffichaa gabaaban ibsuuf qophi'ii taasifamee jira.

Gaaffilee af-gaaffii odeeffannoo qorannichaaf ittiin funaanuuf dhiyaate

<u>Odeeffannoo ragaa kenitootaa፡-</u>

1. Maqaa guutuu ____________________
2. Umrii ____________________
3. Ganda ____________________
4. Gahee hojii ____________________
5. Guyyaa____________________

Hundaan dura af-gaaffii kanaaf yeroo hojii keessan wereeguudhan asitti naaf argamuu kessaniif guddoo isin galateeffadha. Af-gaaffiin kun qo'annoo Doktarummaa gutachuuf qofa kan oolu ta'uu isaa ibsaa, ragaan naaf kennamu dhugaarratti akka hundaa'u kabajaan isin gaafadha.

1. Qaalluu jechuun si'iif/ isiniif maal jechuudha?
2. Miseensonni gumii Qaalluu eenyufaadha? Gaheen isaan maal maalfaadha?
3. Jilli Qaalluu maal maalfaadha? Maaliif jilata?
4. Argaafi dhageetti keessanirran kaatanee Jila kanneen irratti jijjiirama hubatane jiraa?
5. Godaansa gutuu jechuun maal? Faayidaan isaa maal?
6. Qaalluun jila isaarratti maaliif falata? Fakkeenyummaan isaa maal agarsiisa?
7. Qaalluun yoom yoom fala? Eessatti fala? maaliif fala? eenyufaan wal fala? ragaalee jedhanu Teep-rikerderiini woraabuufi yaadannoo qabachuun walitti qabama.

8. Dhumarrati deebii af-gaafficharratti hunda'uun wantoota ibsa barbaadanu yaadannoo qabachuun kan ibsa dabalata barbaadanu gaafachuun deebii isaa yaadannoo ni qabama.

Hubachiisa:- Gaffileen lakkoofsa 5 fi 6 irraatti jiran jaarsoolee aadaa beekanii fi ogeessoota aadaatiif kan dhiyaatan yoo ta'an kan hafan hirmaattoota hunduma kan ilaallataniidha.

## አባሪ-ሦስት

<u>የቡድን ተኮር ውይይት ጥያቄዎች</u>

1. የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ቀደም ካሉ ስርዓቶች አንስቶ እስካሁን ባለው ውስጥ ያሉት ለውጦች ምን ምንድናቸው? አሁንስ ምን ደረጃ ላይ ይገናሉ?
2. የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች እየተዳከመ ነው ወይስ እየዳበረ እየሄደ ነው ትላላችሁ? ምክንያታችሁ ምን ምንድናቸው?
3. የቃሉና የገዳ ስርዓት የዋቄፋታ ሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞዎች ብቻ ነው ትላላችሁ? ለምን?

ከሁሉም በፊት ለዚህ ቡድን ተኮር ውይይት እዚህ ስለተገኛችሁልኝ ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። እዚህ ቡድን ተኮር ውይይት ላይ የቀረቡ ጥያቄዎችም ሆኑ የሚሰጡ መልሶችና አስተያየቶች ለዶክትሬት ዲግሪ የማሟያ ጥናት አገልግሎት ብቻ የሚውሉ በመሆናቸው፤ ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ በመስጠትም ሆነ አስተያየት በማቅረብ ንቁ ተሳትፎ እንዲታደርጉ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ።

Jaarsummaa

Jaarsummaa jechuun maali?yaada jedhurratti Obboo Mokkonnaa, Obboo Roobaa Elemaafi gadaa Halchaayyee wal marii taasifame

Guyyaa 10/12/2007,Obbo Mokkonnaa Naga'oo, umriin woggaa 75, Qootii (Galma)fiGadaa Halchaayyee Daarraa, umrii 65, Ganda Dabaqqaa Daboobeessa yoo ta'anu, lachuu Galma abbaa Qaalluu keessatti yeroo baay'ee waliin hojjatu. Kanaafuu,waa'ee jaarsummaa ilaalchisee muuxannoo guddaa akka qabanu isaan irraan hubaachuuf danda'eera. Kanaafuu, Jaarsummaa jechuun maali?gaaffii jedhu isaaniifi dhiyeese.Isaanisi: dursanii,

Obboo Mokkonnaa:- Jaarsummaa jechuun akka aadaa keenyaatti adeemsa rakkoo hawaasa keessatti uumameef manguddoota naannoo sanitti jiranuu karaa ittiin hiikaniidha. Amma akka fkn, name mana tokko keessatti jiraatu, ykn immoo,olla wal sababa adda addaatiin walitti bu'uu danda'a. Dhimma kana mana murtiitti hingahin dura ykn immoo, erga gaheen booda kan balleessa abbaa dhiibban itti gaheef gama aadaatiin waan isaaf ni madaala kan jedhame akka muru taasifamee araarri bu'a.

Obboo Halchaayyee:-dhimmi Jaarsummaa kun gama aadaa Gujiitti nami tokko cadhi jedhee hin himatu. Haalli ittiin himatu jira.Innisi, dursee abbuma isa yakke san "abboo ani si himadhaara?" jedhee gaafata. Deebin isaa:-

1. Ana hin himatin balleessa kiyya anuu beekera si kiisa. Kan jedhu ta'uu danda'a,
2. Lafti yoo dhiyeeru taanaan lafti olii gadi jedha.sababi isaas, halkan hayyuu hin gaafatanu name bishaan wayii fudhate waan jaarsi jedhu fudhachuu dhiisuu danda'a,
3. Erga gaaffin eegalameen booda, himadhu; maal balleessan kiyya jedhee dhimmi ka'u sun jabaa yoo ta'ee isa rakkistu taanaan, ani abbaa qaba. Jedha.Yeroosan, Jaarsummaa abbaa kee fidi; meerre abbaan kee?jedhu. Karaa deemeera jedha. Jaarsoliin akka tole jedhee dhimmichi ilaalamu yoo dhiibba itti uumanille nama abba qabu; abbaattu gaafatama jechuun mormee dubbiin akka bultu taasisu.Yeroo ammaa namu dubbii baratee xinnoo rakkisaara malee, dhimmi jaarsi dadhbu hinjiru.Tasa dimma ulfaate yoo ta'e galma abbaa Qaalluutti dhuma jedhane.

## አባሪ-አምስት

ከ1424-2015 ስልጣን ላይ የነበሩ የገዳ አባቶች ስም ዝርዝር

| የገዳ ስልጣን ዙር | የገዳው ስም | የስልጣን ዘመኑ | የገዳው መደብ ስም |
|---|---|---|---|
| 1 | አባ ገዳ ጃጄ ጎባ | 1424-1431 | ሙዳና |
| 2 | // // ጂሎ ወላጎ | 1432-1439 | ሀልቺሳ |
| 3 | // // ጂሩ ኡታ | 1440-1447 | ዳላና(dhallana) |
| 4 | // // ጉሉ ጋራሮ | 1448-1455 | ሀርሙፋ |
| 5 | // // ሄባኑ ጃልዶ | 1456-1463 | ሮባሌ |
| 6 | // // ቢላ ማናኮ | 1464-1471 | ሙዳና |
| 7 | // // ባሪሶ ጉሚ | 1472-1479 | ሀልቺሳ |
| 8 | // // አዶላ አኖሌ | 1480-1487 | ዳላና |
| 9 | // // ጎቡ ሻሮ | 1488-1495 | ሀርሙፋ |
| 10 | // // ጎሉ ሱባ | 1496-1503 | ሮባሌ |
| 11 | // // ጭሪ ጋሎ | 1504-1511 | ሙዳና |
| 12 | // // ቡርጭሳ ሻኩ | 1512-1519 | ሀልቺሳ |
| 13 | // // አጋ ካላቻ | 1520-1527 | ዳላና |
| 14 | // // ጂሎ ቢዶ | 1528-1535 | ሀርሙፋ |
| 15 | // // ጋናሌ ሮቤ | 1536-1543 | ሮባሌ |
| 16 | // // ዱባ አዲ | 1544-1551 | ሙዳና |
| 17 | // // አቦ ራሶ | 1552-1559 | ሀልቺሳ |
| 18 | // // ሀላኬ ሉሌ | 1560-1567 | ዳላና |
| 19 | // // ጎቡ ዳዬ | 1568-1575 | ሀርሙፋ |
| 20 | // // ጋናሌ ሎሌ | 1576-1583 | ሮባሌ |
| 21 | // // ቃናሾ አኖሌ | 1584-1591 | ሙዳና |
| 22 | // // ጃቦ ስቡ | 1592-1599 | ሀልቺሳ |
| 23 | // // ቃልቃልቻ ቱካሾ | 1600-1607 | ዳላና |
| 24 | // // ጎሎልቻ ሻሩ | 1608-1615 | ሀርሙፋ |
| 25 | // // አባ ዶላ | 1616-1623 | ሮባሌ |
| 26 | // // አጋ ሳቆ | 1624-1631 | ሙዳና |
| 27 | // // ጂሎ ባንሳ | 1632-1639 | ሀልቺሳ |
| 28 | // // ሀሮ ሾቴ | 1640-1647 | ዳላና |
| 29 | // // ጃርሶ ዱጎ | 1648-1655 | ሀርሙፋ |
| 30 | // // ኡሾ ዋሬ | 1656-1663 | ሮባሌ |
| 31 | // // ጋናሌ ዳናባላ | 1664-1671 | ሙዳና |
| 32 | // // ጎዳና አጋ | 1672-1679 | ሀልቺሳ |
| 33 | // // ጎዳሬ ቦኮ | 1680-1687 | ዳላና |
| 34 | // // ጃርሶ ሶሬ | 1688-1695 | ሀርሙፋ |
| 35 | // // አጋ ቡዴ | 1696-1703 | ሮባሌ |
| 36 | // // ቱኬ ሽፋ | 1704-1711 | ሙዳና |
| 37 | // // ጂሎ ባዳ (Badhaa) | 1712-1719 | ሀልቺሳ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 38 | // // አጋ ዋሬ | 1720-1727 | ዳላና |
| 39 | // // ብራ ሉኬ | 1728-1735 | ሀርሙፋ |
| 40 | // // ጂሎ ጡሎ | 1736-1743 | ሮባሌ |
| 41 | // // ባላኮ ጂሎ | 1744-1751 | ሙዳና |
| 42 | // // ቡዱሾ ሀላኬ | 1752-1759 | ሀልቺሳ |
| 43 | // // ሶራ ቡሉልታ | 1760-1767 | ዳላና |
| 44 | // // እጁ ጋላቤ | 1768-1775 | ሀርሙፋ |
| 45 | // // ሱሮ ጨኮ | 1776-1783 | ሮባሌ |
| 46 | // // ጂሎ ዋሬ | 1784-1791 | ሙዳና |
| 47 | // // ጋልቹ ኬማ | 1792-1799 | ሀልቺሳ |
| 48 | // // ሚዶ ኒቲ (Miidhee) | 1800-1807 | ዳላና |
| 49 | // // ዳዳ ኩራ | 1808-1815 | ሀርሙፋ |
| 50 | // // ጥሎ ሾሌ | 1816-1823 | ሮባሌ |
| 51 | // // ቡኖ ዳኤ (Dhaa'ee) | 1824-1831 | ሙዳና |
| 52 | // // ዳሼ ሀላኬ | 1832-1839 | ሀልቺሳ |
| 53 | // // ቡኔ ቦሩ | 1840-1847 | ዳላና |
| 54 | // // አጋ ካላቻ | 1848-1855 | ሀርሙፋ |
| 55 | // // አዱላ ካራ | 1856-1863 | ሮባሌ |
| 56 | // // ዋቆ ጋራሮ | 1864-1871 | ሙዳና |
| 57 | // // ብራ ጨቄ | 1872-1879 | ሀልቺሳ |
| 58 | // // አኖሌ ባዳ (Badhaa) | 1880-1887 | ዳላና |
| 59 | // // ሮባ ቦሩ | 1888-1895 | ሀርሙፋ |
| 60 | // // ጂሎ ከንዶ (Kendhoo) | 1896-1903 | ሮባሌ |
| 61 | // // ጋልቹ ጨኑቆ | 1904-1911 | ሙዳና |
| 62 | // // ጂሎ ቦኮ | 1912-1919 | ሀልቺሳ |
| 63 | // // ጂሎ ሳዬ | 1920-1927 | ዳላና |
| 64 | // // አጋ አዲ | 1928-1935 | ሀርሙፋ |
| 65 | // // ኡሾ ጂሎ | 1936-1943 | ሮባሌ |
| 66 | // // ቱኬ ጉዬ | 1944-1951 | ሙዳና |
| 67 | // // ጂሎ ሚጠ | 1952-1959 | ሀልቺሳ |
| 68 | // // አዶላ ጂሎ | 1960-1967 | ዳላና |
| 69 | // // ጊርጃ ጂሎ | 1968-1975 | ሀርሙፋ |
| 70 | // // አዶላ አጋ | 1976-1983 | ሮባሌ |
| 71 | // // ጎዳና ካታ | 1984-1991 | ሙዳና |
| 72 | // // አጋ ጤንጣኖ | 1992-1999 | ሀልቺሳ |
| 73 | // // ዋቆ ዱቤ | 2000-2007 | ዳላና |
| 74 | // // ጂሎ ማንዶ (Maandhoo) | 2008-2015 | ሀርሙፋ |

**ምንጭ**:-Waajjira Aadaafi Turizimii Godina Gujii፡Baallii 74[ffaa]. Maxxansa addaa,Gurr./2008.

## አባሪ-ስድስት

Dhuftee Qaalluu

Yoona akka dhage'aa guddannetti Qaalluun Gujii Waaqarraan gadi bu'e.Yemmuu gadi bu'u waan akka sabbata waaqaa jiruun maramee irraangadee hiikamaa isa erga lafa geessiseen booda gara waaqatti maramee deebi'e. Iddoon itti gadi bu'e godina Gujiitti, aanaa Adoola keessatti lafa Obbaa(obbittii) jedhama. Yeroo sana Qaalluun ruufaan maramee, qumbiifi kallacha waliin bu'e. Akkaataa kanaan akkuma bu'een, dursanii nama gosa waajjituu ta'anettuu isa argane. Maalummaa isaa baruuf itti siiqane; Sodaachatuma irra maraa erga turaneen booda hawaasa olla sani jirutti himane jedhama. Namoota sana keessan name lamaan itti siqee yoo ilaalanu ruufa keessa namni akka jiru hubatane. Nami kuni kallacha ofirratti qaba ture. Ruufa sana keessatti Qaalluun cinaa qumbiin marsee jira ture. Gujiin olla sanii itti dhiyaatee; "Nami kuni woyyuudha."Jechuun dubbisuuf yaalani. Inni garuu nama tokkoofille deebii hin laanne ture. Nami adda addaa akka dubbisu yaalameeruun nami tokkolle isa dubbisuu hindandeenye.Dhumaratti, intalti durba gosa galalchaa taatu tokko yoo dhuftu Qaalluun itti seeqate.Intalti durba geese turte.Ishiinissi, "gara manaatti haagallu?" jettee isa gaafate. Yeroo sana innisi ishii wal dubbachuu eegale. "Ani mana namaa hin galu.Galma naaf ijaaraa." jedhe.Gujiin walitti dhufee galma ijaareef.Itillee afanii teesisane. Aannaan buchumaan(qodaan) yoo itti kennanu; fudhachuu dide. Boodarratti, Okoleen akka isaaf gumaachanu isaanitti hime.Isaanissi waanuma jedhame raawwatane. Gumaachi Qaalluuf taasifamu dhufteen isaa kanumarraan madde jedhama.Intalti durba gosa galalchaa sani isuma bira dhiisanee deemane. Achiin ijooleessi horatane. Dhugaani jirusi kanuma Jechuun naaf ibsan.

Qaalluun tokko umriin angoo isaa hagam?gaaffii jedhuuf Obboo Mokkonnaan yemmuu deebisanu "Qaalluun tokko umrii isaa guutuu hojjata. Hanaga waaqni si gaheera jedhutti; jechuun koo hanaga hanachufa liqiinfatutti ni tajaajila. Qaalluun Yoo hanachufa liqimse ayyaaan isarratti bule jiru garuu nijiraata; hin du'u.Kanaafuu, ijoollee isaa keessaan kan ulaagaa barbaachisan kan guutu yoo jiraate filuudhaan ni moggaafama. "Jechuun deebisane. Itti aansuun, ulaagalee qaalluu moggafamuuf barbaachisan aakkaata armaan gaditti ibsaniiru.(Obboo Mokkonnaa Naga'oo, umriin woggaa 75, Aanaa Wonagoo, Ganda Qootii, Guyyaa 1/12/2006 A.L.I)

durba gosa galalchaa sani isuma bira dhiisanee deemane. Achiin ijooleessi horatane. Dhugaani jirusi kanuma Jechuun naaf ibsan.

Qaalluun tokko umriin angoo isaa hagam?gaaffii jedhuuf Obboo Mokkonnaan yemmuu deebisanu "Qaalluun tokko umrii isaa guutuu hojjata. Hanaga waaqni si gaheera jedhutti; jechuun koo hanaga hanachufa liqiinfatutti ni tajaajila. Qaalluun Yoo hanachufa liqimse ayyaaan isarratti bule jiru garuu nijiraata; hin du'u.Kanaafuu, ijoollee isaa keessaan kan ulaagaa barbaachisan kan guutu yoo jiraate filuudhaan ni moggaafama. "Jechuun deebisane. Itti aansuun, ulaagalee qaalluu moggafamuuf barbaachisan aakkaata armaan gaditti ibsaniiru.(Obboo Mokkonnaa Naga'oo, umriin woggaa 75, Aanaa Wonagoo, Ganda Qootii, Guyyaa 1/12/2006 A.L.I)

Qaalluun tokko Moggaafama ulaagaan barbaachisan maalfaadha?
"Qaalluun tokko Moggaafama ulaagaa barbaachisan hedduudhaa. Akkuma seerri durumarraan jalqabee kan argaa dhageettiin dhalootarraan gara dhalootaatti darbaa kan dhufe jiran, Isaanissi:

1. Ilma Qaalluurraan dhalate ta'uu qaba,
2. Ilmi kuni kan dhalate haadha manaa Qaalluu keessaan ishee dubartii gosa galalcharraan (haadha ambaarraan) kan dhalate ta'uu qaba,
3. Mil'uu (mul'ii) isaa ilaalchise kan ija hindabsine,
4. Qaamni isaa guutuu kan ta'e,
5. Harka bitaacha'aa kan hin taane,
6. Biduu kan hinqabaanne,
7. Goddaannisa kan hin qabaanne,
8. Kan ruufaan dhalate (kan ruufaan maramee kan dhalate),
   Yoo ta'nu, gama biraatiin, kan dhugaa dubbatu, nama karaa waaqaa akeeku, hawaasa isa jala bulu hunda ija tokkoon kan ilaalu ta'uu qaba.

Gama moggaasa Qaalluu yoo ilaalle bifa lamaan raawwatamuu danda'a.
1[ffaan,] gaa'elaafi moggaasi Qaalluu isa yeroo jalqabaaf kan raawwatamuu yoo ta'u,inni biroo immoo, ijoollee Qaalluu keessaan name moggaafamu yoo dhabame kan duratti gaa'ela raawwatan keessan yeroo filamu jira. Kanaafuu, namni moggaafamu kun gaa'ela duraan raawwatu sun akaakuu gaa'ela adda addaa ta'uu danda'a. Gama biraatiin immoo, dubartiin inni fuudhe sunissi gosti ishii adda addaafi saba adda addaarran ta'uu ni danda'a.
Ega ulaagaalee amma ibsamane kana kan guutu yoo hin jiraanne hoo maaltu raawwatama?
Obboo Mokkonnaa

«Obboleessi Qaalluu keessan kan ulaagaa guutu yoo jiraate isaan keessaan ni filama.»

Ega ulaagaalee amma ibsamane kana kan guutu yoo argame hoo maaltu raawwatama?

Obboo Mokkonnaa

«Ulaagaalee amma ibsamane kana ijoollichi jira taanaan woggaa kudhanittille moggaasuu ni danda'ma. Garuu bakka ijoollichi hinjiraanneetti nama guddaa jiranu keessaan nifilatama.

Sanaan booda moggaasa Qaalluuf ulaagaa guddoon gaa'ela raawwachuudha.»

Gaa'glli (fuudhi) Qaalluu Gujii Oromoo gaa'ela hawaasa Gujii biroorraan wanta adda taasisan jiru?

Obboo Mokkonnaa

«Garaagarummaa wanta hedduu qaba.Akkuma beektu fuudhi gosa adda addaattuu jira. Fkn, butin, addibaanaa, hawwadii dhaalaa/ sigabaafi kadhaadha. Kanneen keessan Qaalluun gaa'ela kan raawwatamuuf isa sirna Kadhaan kan raawwatamu saniidha.

Haalli adeemsi sirni kadhaa kuni hanga guyyaa fuudhaa jiru yoo ilaale iddoo hedduuti garaagarummaa jiru ilaaluu dandeenya. Isaanisi:

Inni jalqabaa durba Qaalluuf taatu Kaadhimachuu barbaachisa. Kaadhimachuuf immoo, durba filachuun, kadhaa (gaaffii), marii, gaa'ela (fuudha) ni raawwatama.

Akka fakkeenyaatti fudhannee gaa'ela abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo haa ilaallu. Abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo dura kan ture obboleessa keenya kan ture Qaalluu Saqoo Naga'oo jedhama. Abbaa Qaalluu Naga'oo Totteerraan dhalate.Guyyaa dhalate, ruufaan dhalate. Ulaagaalee hafanessi ni guuta ture. Garuu, Abbaa Qaalluu Naga'oo Totteen osoo tajaajilarra jiruu umriin isaa gaa'elaaf gahe.Akkuma aadaa keenyaatti fuusisane.Innissi, jiruu isaa eegale. Dubartii Gujii adda addaafi kan saba biraarran dabalee fuudheera. Dhumarratti,yoo abbaan Qaalluu 14ffaa'n yoo hancufa liqiimsu nama bulii hinqabne keessan ijoolleen ulaagaa guuttu keessan tokko ana ture. Abbaan keenya ,ana yaamee harka na qabee eebbise. Uummata akka bulchu bakka nabuuse. Ani garuu,imaanan kun ibidda; nama guba. Dhugaa dubbachuu qaba. Dubartii name biraa tarkaafate hin tarkaanfatu. Ardaa bulchuu sababoota kanaaf kan birootiin waan sodaadhuuf didadhe. Kanaafuu, akkuma aadaa kanaaan dura itti bulame namuma guddaa jiranu keessan kan ulaagaa guuttatu filama. Sababi isaasi waaqni ganamumaan waan isassi filatee; qopheeffateef ta'e.

Sanaan booda, name qaalloomu akka eenyummaa isaa beekameen,sirna moggaasaaf qaphiin eegale.Akkuma dura sitti hime abbaa baallii guutuu ta'uuf

wanti lama isa hafa ture. Inni tokko, gama amantaa duudhaafi aadaa Gujiitti durba gasa galalchaa keessaan gaa'ela raawwachuu isarraan eegama ture. Sababi isaasi, boru haadha ambaa kan taatu ishii waan ta'eef;cinaa isaatti kan faltu waan ishii taateef.Inni lammeessoon immoo, sirna moggaasa isaa raawwatamuu qaba ture. Kanaafuu,seera guuttachuuf durba gosa galalchaa erga fuusisneen booda akkuma aadaa ganamaatti guyyaa lammeessootti sirni moggaasi isaa raawwatame. Erga baallii guuttateen booda abbaan Qaalluu 15ffaa ta'uun hanga guyyaa hancufa liqiimseen tajaajilaa turaniiru.

Asirratti wanta kaasuu barbaadee durba abbaa qaalluuf taatu filachuurraan kaasee hanga guyyaa fuudhaa inni galmaan gadi hinba'in dhimma jiru hunda fixanii kan fidadun abuyyaa (bakka abbaa) gadoota, kallootaafi manguddoota, obboleetti isaa taniiti.Baasiin fuudhaaf ba'ulle uummata Gujiitiin guuttama. Gumaachaa guyyaa fuudhaa jabillee dhibbaatamaan lakkawaman uummataaraan galaaf.

Itti aansuun kan iddoo fudhate immoo, isa Qaalluu 16ffaa dha; abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo jedhama. Haadhotii manaa abbaa Qaalluu Saqoo keessan haadha ambaarraan kan dhalatee, ulaagaa barbaadamu sana kan guute isa waan ta'eef filatame.»(Obboo Mokkonnaa Naga'oo, umriin woggaa 75, Aanaa Wonagoo, Ganda Qootii, Guyyaa 12/11/2007 A.L.I)

Guyyaa darbe abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo Qaalluu 16ffaa ta'anii akka filatamane ibsatanii dhaabbachiisne turre.Mee haala akkamiin moggaafamaneree?

Obboo Mokkonnaa

«Akkuma duratti dubadhetti abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo waan akka qaalloomu kan filatameef inni guddaan waan ulaagaa gama aadaafi amantaa keenyaan taa'e sana waan guutuuf dargaggeesa yoo ta'elle waaqni waan isa qopheesseef isattuu filatame. Sababni isaasi,inni tokkoffaan inni kan dhalate hadhootii mana abbaan Qaalluu 15ffaa hadha ambaarraan waan ta'eef.Gama biraatiin name qaalloomu gosa Gujii keessaan gosa obbituu keessan ta'a. sababini isaa Qaalluun Gujii inni jalqabaa yemmuu waaqarraan bu'u iddoon inni lafa bu'e sun "Obbaa" ykn "Obbitti" jedhama.Kanaafuu, gosti qaccee mana isarraan ba'ane Obbituu jedhamu. Sababa kanarran kan ka'e nami qaalloomu tokko gosaan Obbituu ta'uu qaba.Obbituun hundi gosa Qaalluu jedhamti; kabajasi qabdu.

Gama biraatiin dubartiin haadha ambaa taatu immoo,durba gosa galalchaarran waan taateef qabdi. Akkuma dhuftee Qaalluu Gujii keessatti akka kaaseetti; durbi Qaalluu isa yeroo jalqabaa haasofsitefi isaa wal galte waan gosa galalchaa taateef.Intalti sun durba geese turte.Achumaan waliin jiraachuu eegalane; ijoolleessi horatane.Baalliin isaasi gara ilmasaatti darbe. Haaluma kanaan ergasi,

baalliin abbaarran gara ilmaatti darbaa dadarbaa akka asiin gahe himteen waa'ee dhuftee Qaalluu keessatti ni himama.

-Faaydaani Dhaabbati (galmi) Qaalluu Gujii hawaasaaf qabu maalfaa jettu? Mee amma immoo, obboo Halchaayyerraan eegala.

-Obboo Halchaayyee "miti erga Obboo Mokkonnaan ibseen booda inninuu hin hafu malee yeroo sana itti dabala; Itti fuufaa isin."

Obboo Mokkonnaan «Tole kaa, dursinee waaqa haa kadhannu.

Ee waaqa nagaan nu bulchiteetta nagaan nu oolchi. Nu oolchi !

Faroo hamaa falafaltuu hamaa nurraa qabi. Nurraa qabi!

Ee muchaan kunillee waa'ee aadaa keenyaa qo'adha

jedhuutti jira nu'uufi afaan ittin haasofnu, isaafi immoo,

hojii isaa haa qajeelchu. Haa qajeelchu.

Waa'ee faaydaani galmi Qaalluu Gujii uummataaf qabu maalfaadha jedhee mitii? Abbaa gadaa Halchaayyee «Eeyyee! akkasuma jedhe.»

Obboo Mokkonnaan "Maalree, akkuma qaalluu kanniisaa kan oolmaa keenya, bulii keenya, horii keenya, maatiifi qa'ee keenanya akka naagaa argatu, kandhalate akka guddatu, kaguddate akka le'u iddaa falatufi jilatuudha. Waaqarraan iddoo araara kadhatuu dha. Galmi kan rakkate dhufee iddoo himatuu dha. Kan himatame immoo, dhufee iddoo dhaagaa baafatuudha.Galmi Qaalluu malee; Qaalluunisi galma malee hin ta'u.Halchaayye waan itti dabaltu yoo jiraate itti jedhi."

Abbaa gadaa Halchaayyee «waanti hedduun jedheemeera. Galmi gama tokkoon mallattoo eenyummaa Gujiitii. Gujiin Qaalluun bula.Qaalluun immoo galma isaatiin bula.Qaalluun abbootii gadaa wal, jaarsolee wal waa'ee biyyaa, waa'ee sabaa iddoo ittiin mari'atuudha.Iddoo murtii ittiin dabarfatuudha.Nami rakkate iddoo itti dheessuudha. Nami nama akka tasaa ajjeese maatii isaa wal iddoo dheessee baafatuudha.» (Obboo Mokkonnaan Naga'oo, umrii woggaa 75, Aanaa Wonagoo, Ganda Qootii, fi Abbaa gadaa Halchaayyee Dharraa, umrii woggaa 65, Aanaa Abbaayyaa, Ganda Dabaqqaa Daboobessa,Guyyaa, 16/12/2007 A.L.I.

## አባሪ-ሰባት

**Bokuu**

Gaheen abbaa gadaa ardaafi looniif waaqa kadhata. Gama biraatiin yoo nami sababa adda addaatiin lolamee dhufe jaarsaaf akka dubbii ilaalan isaaniif dabarsa.Haalli lola isaa yoo afaan taree jiraate, ykn balleessa biraa yoo raawwate horiin ykn ganzabaan qaxxa'a. Saniin booda araarsee lakkisa. Yeroo himannaa san nami himatame sun yoo waakkate name himate, dhugaa qabu fidee raggaasifata.dhugaan sun himteetuun; ammale dide kan jedhu yoo ta'e gara galma qaalluutti dabarsan.

Ishi amma dhugaan kan abbaa gadaa, abbaa qaalluuti. Dhuguma akka dubbii ammaa dubartiin bada akkasi, bada akkana jedhanii hin arrabsanu. Yoo dubartii maqaa badaan yoo takaalane seera qabdi.Maal qabdi?Yoo abbaa gadaa ykn abbaa qaalluu bira yoo deemte Korma qalsiisan.
Adabbii abba qaalluun dabre sana yoo dide jedhe, ni bokama. Bokuu jechuun name kun olla isaatti yoo iyye reebuu akka hindeemnef, yoo du'e akka hin awwaallef, ibidda akka hinkennamneef...ergaan qaalluurran gara abbaa gadaatti; abbaan gadaa immoo, gama jaarsoleen ollaaf dabarsu. Yoosuu ollaan boka san hojiirra oolcha.Yeroo san name bokame sun ariitiidhaan galma qaalluu deemuun boka san hiikisiisee dhufa. Sanii booda, adabbiin kun akka ka'een haaluma akka yeroo bokaa; ergaan adabameera, sirro'e jira; bokni haa ka'uuf jedhamee gara gadiitti ergaan dabaree niraawwatama.

Inni guddaan qaalluufi gadaan kabaja qaban.Kanaafuu, namootiin himatamane ragaa akka dhiyeesan yeroo hintaasifamne jira.Maaliif yoo jedhame, namni dhufee isaan kaadu hin jiru. (FKN, dhihoo kanatti nami tokko lowwan hatee, gama seeratiin wal himanii fala dhabe, anattuu hateera jedhee amanee horii san deebisiisanii araarri bu'eera.
Balbalti kunuu dhugaadha, gadaanu dhugaadha, qaalluun dhugaadha.Nami isaan sobee hinba'u; ija isaanii dhaabbatee sobuu waan hindandeenyeef dhugaa kee fidi hin jedhanu.Qaalluun waaqa, gadaan waaqa, nami waaqa kaadu jiraa?Hin jiru, kanaafuu hin kaadanu.Garuu tasa yoo hammaate akka ragaa isaa fidatu taasifama. (Obboo Taddasaa Danboobaa, aanaa Abbaayyaa,Ganda Bunnaata, 23/4/2007 A.L.I.)

# አባሪ-ስምንት
## የተለያዩ መረጃዎችን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች




ሀዳ ቦላ ቃባሌ ጃልዴሳ (የቀድሞው የኡራጋ ገዳ ባለቤት) በመንፈሳዊ ጉዞ ወቅት የዋንዣን እንጨት ጨምሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ቁሶችን እንዴት እንደሚያዝ የሚያሳይ ፎቶ በሚኤ ቦኮ




ከመረጃ አቀባዮች ውስጥ የወ/ሮ ዲኮ እና  የአቶ ሞኮና ናጋኦ ፎቶ




በሚኤ ቦኮ አርዳ ጂላ ላይ የገዳ ስልጣን ለመረከብ በዝግጅት ላይ እያሉ



ስለፋጭና ጉጆማ ከበራ የተዘጋጀ አርቴፊሻል ሰ[illegible]ት በከፊል የሚያሳይ




ከጃልዳባዎች መረጃ በመሰብሰብ ላይ እያለሁ የሚያሳይ ፎቶ



ከላልቱ ቀበሌ የሚገኙ መረጃ አቀባዮቼ በከፊ የሚያሳይ ፎቶ




ከምስራቅ ሐረርጌ በሚኤ ቦኮ በዓሉ ላይ ለመታደም የመጡና መረጃ አቀባዮቼ የነበሩ



በሚኤ ቦኮ የአዋጅ ነገራው ላይ ሴቶች ታድመው ሲከታተሉ የሚያሳይ ፎቶ



የሰው ሁሉቃ መቼት የሚያሳይ ፎቶ፡-



አዲሶቹ አባገዳዎች የመሀሉ የኡራጋ አባገዳ ጂሎ ማንዶ፣ በስተግራ ያሉቱ የሆኩ አባገዳ ሲሆኑ በስተቀኝ ያሉት ደግሞ የማቲ አባገዳ ሚዳጋ ይባላሉ።



በሚኤ ቦኮ የበዓሉ እድምተኞች በከፊል የሚያሳይ ፎቶ



ከአማካሪዬ ዶ/ር ታደሰ በሪሶ ጋር በሚኤ ቦኮ አረዳ ጂላ ላይ የተነሳነው ፎቶ

ይህ ሥራ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ በአግባቡ ጠቅሼ መጠቀሜን
ያረጋገጥኩ ይህ ሥራም የራሴ ስለመሆኑ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡
ም፡- ዘላለም አበበ
ርማ፡- ____________________
ን፡- ____________________

# የቃሉ ሃይማኖታዊ ክበራዎችና ፋይዳዎቹ፡ በጉጂ ኦሮሞ

በ

ዘላለም አበበ

ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪዎች

ፍቃዱ አዱኛ (ዶ/ር)

ታደሰ በሪሶ (ዶ/ር)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር



ነሐሴ /2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
አማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹ፡ በጉጂ ኦሮሞ

ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ዘላለም አበበ

ነሐሴ /2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹ፡ በጉጂ ኦሮሞ


በ

ዘላለም አበበ


ነሐሴ /2008 ዓ.ም.

## የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪዎች ስም ፊርማ

1. ____

2. ____

የውጭ ፈታኝ ስም ፊርማ

____

የውስጥ ፈታኝ ስም ፊርማ

____

## ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን ጥናት ለማማከር ሙሉ ፍቃደኝነታቸውን በማሳየት ጊዜያቸውንና ዕውቀታቸውን ለቸሩኝ፤ እንዲሁም ለስራዬ መሳካት በማሰብ ስለጉጂ ቃሉና ገዳ ከበራ ከእኔ ይበልጥ ዶ/ር ታደሰ በሪሶ ያውቃሉ በማለት እሳቸውን በማግባባት አብረው ለማማከር በማመቻቸት ለስራዬ መሳከት ከፍተኛ ጥረት ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ፍቃዱ አዱኛ ያለኝ አድናቆትና አክብሮት ከፍተኛ ነው፡፡

በመቀጠል በወቅቱ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ወቅት በነበረባቸው የስራ ጫና ሳይታክቱ ከዶ/ር ፍቃዱ የቀረበላቸውን ጥያቄ በመቀበል ለጥናቱ ወሳኝ የሆኑ ምንጮችን በመጠቆምና በማዋስ፣ እንዲሁም በፍጥነት አንብበው ገንቢ አስተያየት በመስጠትና አንድም እንደ አማካሪ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደመረጃ አቀባዬ በመሆን የነበሩብኝን ክፍተቶች በመሙላት ለስራዬ መሳካት ክፍተኛ ድርሻ ለነበራቸው አማካሪዬ ዶ/ር ታደሰ በሪሶ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ሌላው በትልመ-ጥናቱም ሆነ በደረጃ ማበልጸጊያው ወቅት የስራዬን ጥረት በመረዳት የነበሩኝን ጉድለቶች አብጠርጥረው በማውጣት፣ ሊከተል የሚገቡኝን የአማራጭ መንገዶችን በመጠቆም፣ እንደፈታኝ ብቻ ሳይሆኑ፤ እንደአማካሪም ዕውቀታቸውንና ልምዳቸው ላካፈሉኝ ዶ/ር ዘላለም ተፈራ ውስጣዊ አክብሮቴና ምስጋናዬ ይድረሶት እላለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለአባቃሉ አጋ ሳቆ፣ እንዲሁም በ75 ዓመታቸው የአያታቸውንና የአባታቸውን የማምለክያ ቅዱሳን ስፍራዎች ከተራራ ተራራ በመውጣት ያለመሰልቸት ሙሉ ጊዜያቸውን በመረጃ ማቀበል ላገለገሉኝ የአባቃሉ አጋ ሳቆ አጎትና የቅርብ አማካሪ ለሆኑት ለአቶ ሞኮና ናጋኦ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል አባገዳ ዋቆ ዱቤ የኡራጋ ገዳ የነበሩ፣ አባገዳ ዳንቦባ አጋ የማቲ ገዳ የነበሩ፣ አባገዳ ጋንቤላ በርሶ የሆኩ ገዳ የነበሩ እና ለአሁኑ የኡራጋ አባገዳ ጂሎ ማንዶ (Maandhoo) እንዲሁም ለሀሎ አባገዳ ደንቦባ ጉሚና የዌስቱ አባገዳ ሀልቻዬ ዳራ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል ለአባያ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኞችና በወረዳ ውስጥ በተለያዩ ቀበሌዎች ለሚገኙ መረጃ አቀባዮቹና በሚኤ ቦኩ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ የጉጂ ዩባዎች፣ ሀዩዎችና የሀገር ሽማግሌዎች በሙሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ጠቃሚ ሀሳቦችን በማንሸራሸር ለጥናቴ አስተዋጽኦ የነበራቸው ጓደኞቼ ለዶ/ር በጅጋ ተካ እና ለአቶ ተመስጌን ምንዋጋው ምስጋና አቀርባለሁ::
በመጨረሻም በስራዬም ሆነ የቤቱን ኃላፊነት በመወጣት ከጎኔ ላልተለየችኝ ለውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ንግስት አዳነ እና አንዳንድ ጽሑፎችን በማገዝ ለረዳኝ ለልጄ አያልቅበት ዘላለም ያለኝን አክብሮትና ምስጋና በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ............ i
ማውጫ ............ ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ............ v
የምስል ማውጫ ............ v
የፎቶ ማውጫ ............ vi
ሙዳዬ ቃላት ............ vii
አጠቃሎ ............ x
ምዕራፍ አንድ ............ 1
መግቢያ ............ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ............ 2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ............ 4
1.3. የምርምሩ ጥያቄዎች ............ 5
1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ............ 5
1.4.1. ዓቢይ ዓላማ ............ 5
1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች ............ 6
1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ............ 6
1.6. የጥናቱ ወሰን ............ 7
1.7. የጥናቱ ውስንነትና የተወሰዱ መፍትሔዎች ............ 8
ምዕራፍ-ሁለት ............ 10
ክለሳ ድርሳናት ............ 10
2.1. ፅንሰ-ሀሳባዊ ፅሁፎች ............ 10
2.1.1. ፎክሎርና ሃይማኖት ............ 10
2.1.2. የሃይማኖት ፅንሰ ሀሳብ ............ 12
2.1.2.1. የሃይማኖት ምንነት ............ 12
2.1.2.2. የሃይማኖት ባህሪያት ............ 13
2.1.3. የከበራ ፅንሰ ሃሳብ ............ 14
2.1.3.1. የከበራ ምንነት ............ 14
2.1.3.2. የከበራ ዓይነቶች ............ 16
2.1.3.3. የከበራ ባህሪያት ............ 18
2.1.3.4. የከበራ ፋይዳዎች ............ 19
2.1.4. ሚት ............ 20
2.1.5. ቁሳዊ ባህል ............ 21
2.1.6. ስነ-ፍችና አውድ ............ 23
2.1.6.1. ስነ-ፍች ............ 23
2.1.6.2. አውድ ............ 25

2.2. የንድፈ-ሀሳብ ቅኝት ........................................................ 26
2.2.1. የማህበራዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ .................................... 27
2.2.2. ተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ ............................................ 28
2.2.3. አውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ........................................................ 31
2.2.4. ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ........................................................ 32
2.2.5. ክልላዊ ንድፈ-ሀሳብ ........................................................ 34
2.3. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........................................................ 36
ምዕራፍ ሦስት ........................................................ 46
የአጠናን ዘዴ ........................................................ 46
3.1. የጥናቱ ዓይነት ........................................................ 46
3.1.1. የጥናቱ ስነ-ዘዴ ........................................................ 50
3.1.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ........................................................ 52
3.1.2.1. ምልከታ ........................................................ 52
3.1.2.2. ቃለ-መጠይቅ ........................................................ 53
3.1.2.3. የቡድን ውይይት ........................................................ 54
3.1.2.4. ንጥል ጥናት ........................................................ 55
3.1.3. የናሙና መረጣ ሂደት ........................................................ 56
3.2. የመረጃ ምንጮች ........................................................ 57
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መቼት ........................................................ 57
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................................................ 57
3.5. መረጃዎችን መሰብሰቢያ አንጻሮች ........................................................ 58
3.6. የተሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች ........................................................ 59
3.6.1. ትራንስክሪፕሽን ........................................................ 60
3.6.2. አተረጓገም ........................................................ 60
3.7. ከመስክ ውሎ የተገኘ ልምድ ........................................................ 60
3.8. የምርምር ሥራ ሥነ-ምግባር ........................................................ 62
ምዕራፍ አራት ........................................................ 63
የጉጂ ኦሮሞ ማሕበረ-ባሕላዊ ዳራ ........................................................ 63
4.1. የጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ፣ አካባቢያዊና ታሪካዊ ዳሰሳ ........................................................ 63
4.1.1. የጉጂ ኦሮሞ መገኛ ........................................................ 63
4.1.2. የጉጂ ኦሮሞ ዘር ሐረግ ........................................................ 68
4.1.3. ሃይማኖት ........................................................ 72
4.1.4. ቋንቋ ........................................................ 73
4.1.5. መተዳደሪያ ........................................................ 74
ምዕራፍ-አምስት ........................................................ 75
ቃሉና የቃሉ ተቋም ........................................................ 75
5.1. ቃሉ ........................................................ 75

5.1.1. የቃሉ አመጣጥ ሚት ....................................................................77
5.1.2. የቃሉ ስያሜና መስፈርቶቹ ..............................................................79
5.1.3. የቃሉ መማክርት አባላትና ተግባራቸው ...............................................84
5.1.3.1. የቃሉ ተግባራት ..................................................................84
5.1.3.2. የገዳ ተግባራት ...................................................................91
5.1.3.3. የኮከብ ቆጣሪዎች ተግባራት ...................................................100
5.1.3.4. የካሎዎች ተግባራት ..............................................................103
5.1.3.5. የሞራ አንባቢዎች ተግባራት ...................................................105
5.1.3.6. የሀገር ሽማግሌዎች ተግባራት .................................................107
5.1.3.7. የሀዳ አንባ ተግባራት ..........................................................108
5.2. የቃሉ ከበራዎች መቼቶች ..........................................................................110
ምዕራፍ-ስድስት ......................................................................................127
የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ትንተናና ገለጻ ..........................................................127
6.1. የገዳዎች ስልጣን ማጽደቂያ ከበራ ..................................................................127
6.2. የጎንዶሮ ከበራ ........................................................................................154
6.2.1. የግጭት አፈታት ሂደቶች ..........................................................155
6.2.2. የጎንዶሮ ዓይነቶች ..........................................................................156
6.2.2.1. የግጭት ማሳረጊያ ጎንዶሮ ....................................................158
6.2.2.2. የምልጃ ማሳረጊያ ጎንዶሮ .....................................................182
6.3. የሁሉቃ ከበራ ........................................................................................183
6.4. የፋጭ ከበራ ............................................................................................190
6.5. የቃሉ ስያሜ ከበራ ....................................................................................200
6.5.1. የቃሉ ጋብቻ ከበራ ..................................................................201
6.5.2. የቃሉ ስያሜ ከበራ ሂደት ..........................................................207
6.5.3. ለቃሉ የሚሰጡ ስጦታዎች ..........................................................210
ምዕራፍ-ሰባት ........................................................................................212
የቃሉ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት ..............................................................212
7.1. የገዳዎች ስልጣን ማጽደቂያ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት ...........................................223
7.2. የጎንዶሮ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት ...................................................................232
7.3. የሁሉቃና የፋጭ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት ....................................................235
7.4. የቃሉ ስያሜ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት ...............................................................237
ምዕራፍ-ስምንት ......................................................................................239
ማጠቃለያና ይሁንታ .................................................................................239
8.1. ማጠቃለያ ..............................................................................................239
8.2. ይሁንታ ................................................................................................247
ዋቢዎች ....................................................................................................

## የሠንጠረዥ ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- |
| ሠንጠረዥ፡- 1. የጉጂ ኦሮሞ ገዳ ደረጃዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ | 93 |
| ሠንጠረዥ፡- 2. የቃሉና ቃሊቻ/ቃሊቲ አንድነትና ልዩነት | 125 |
| ሠንጠረዥ፡- 3. የፋጭን ቅደመ-ተከተላዊ ሂደት የሚያሳይ | 197 |


## የምስሎች ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- |
| ምስል፡-1. የኦሮሚ ዞኖች መገኛ የሚያሳይ ካርታ | 64 |
| ምስል፡-2. በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር፣ የቦረናና ጉጂ ዞኖች የሚያሳይ ካርታ | 65 |
| ምስል፡-3. የጉጂ ኮንፌድረሺኖች መገኛ የሚያሳይካርታ | 67 |
| ምስል፡-4. የኮንቶማና ዳሪሙ አከፋፈልን የሚያሳይ ቻርት | 71 |
| ምስል፡-5. የኮንቶማና ዳሪሙ አሰፋፈር የሚያሳይ ምስል | 72 |
| ምስል፡-6. የሰባቱ ከዋክብት ስሞችና ምስል | 103 |
| ምስል፡-7. የጉጂ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች ተስተሳልፎ አቅጣጫ የሚያመለክት | 142 |
| ምስል፡-8. የጉጂ ገዳ መደቦች የስልጣን ሽግግር ዑደት የሚያሳይ ምስል | 143 |
| ምስል፡-9. የዋቂፋታ፣ ገዳ፣ ቃሉና ዋቃ ግንኙነትና ከበራዎች ፋይዳ የሚያሳይ ሞዴል | 240 |

## የፎቶ ግራፍ ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ፎቶ፡- 1. 16ኛ አባቃሉ አጋ ሳቆ በገልማ ውስጥ ሆነው ....76
ፎቶ፡- 2 አባ ቃሉ አጋ፣ አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ገዳ ሀልቻዬና ሌሎች የመማክርት አባላት ....91
ፎቶ፡- 3 የጃልዳባ አባላትን የሚያሳይ ፎቶ ....96
ፎቶ፡- 4 ሲቄ፣ ሆሮሮ፣ የዋንዛ እንጨት እና ቦኩ የሚያሳይ ፎቶ ....98
ፎቶ፡- 5 መረጃ ሰጪዎች በሚኤ ቦኮ ....98
ፎቶ፡- 6 እና 7 ሞራ አንባቢዎች ስተነቢዩ የሚያሳዩ ፎቶዎች ....106
ፎቶ፡- 8 የቂሊጦ ጋራ የሚያሳይ ፎቶ ....113
ፎቶ፡-9 የቃሉ ቤተ-አምልኮ እና ሂሮ የሚያሳይ ፎቶ ....114
ፎቶ፡-10 እና 11. በሚኤ ቦኮ የተሰሩት ጊዚያዊ ማረፊያ (ቃቻ) በከፊል የሚያሳዩ ፎቶ ....129
ፎቶ፡-12. የቀድሞ የኡራጋ ገዳ አጋ ጤንጣኖና የመማክርት አባላቱን የሚያሳይ ፎቶ ....132
ፎቶ፡-13 እና 14. ስልጣን ተረካቢ ገዳዎችና የመደቡ አባላት ለርክክብ ሲሄዱ የሚያሳዩ ፎቶዎች ....147
ፎቶ፡-15. የከብት ሁሉቃ መቼት ....187
ፎቶ፡-16. የቃሉ እህት፣ የቃሉ አጎት፣ ገዳ ሀልቻዬና ሌሎችም ከስጦታዎቹ ጋር ሙሽሪትን ለማምጣት ሲሄዱ ....205

## ሙዳዬ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሀዳ አንባ (haadha ambaa) | የቃሉ ሚስት |
| ሀዳ ቦላ (haadha bollaa) | የገዳ ሚስት |
| ሀሪራቴ (Harirate) | ለመስዋዕት የሚቀርበውን ከብት ጀርባ በእጅ ወይም በበትር በመዳሰስ እግዚኣብሔር መለማመን ነው |
| ሁሉቃ (hulluuqaa) | በቋሚ እንጨቶች ላይ ሀረግ በማሰር የሚዘጋጅ መሹለኪያ ስፍራ ሲሆን ለጦስ ማውጫ የሚያገለግል ነው |
| ሂሮ (hirroo) | ከአባዩ(abbayyii) እንጨት እንደ ዳመራ የሚዘጋጅ ስፍራ ነው፡፡ |
| ሆዳ (hooda) | ማንኛውንም ችግር እንደ እግዚሃብሔር ፍቃድ ይሁን ብሎ በፀጋ መቀበል |
| ላላባ (lallaba) | ዐዋጅ ነገራ |
| ላዱ (laduu) | የቃሉ አንባር (የስልጣን ምልክት) |
| ላጉ (laguu) | በባህላዊ ህግጋት ክልክል (የማይፈቀዱ) ነገሮች ወይም ክዋኔዎች |
| መቼት | የክዋኔ ጊዜና ቦታ |
| ሙዳ (muuda) | በቃሉ ለስልጣን ይሁንታ ወይም ምርቃት መስጠት |
| ሜዲቻ (meedhicha) | ለከበራ ከታረደው በሬ ቆዳ በቀጭኑ ተተለተትሎ የሚወጣና በእጅ የሚጠለቅ (የባለቤትነት መታወቂያ) |
| ሳፉ(safuu) | ህገ-ልቦና |
| ሩፋ (ruufa ) | ረጅም ፀጉር፣ የቃሉ ፀጉር እንዲሁም የሃይማኖት አባቶች በእራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት ፎጣ መሰል ጥምጣም |
| ቁብሱማ (qubsuma) | የገዳ አባላት የሚሰፍሩበት ቦታ |
| ቁቶ (quttoo) | የልጃገረድነት ምልክት ሲሆን፤ ልክ እንደ አንቴና የሚቆም፣ በቀጭን ቆዳ ላይ ጨሌ በመሰካት ተሰርቶ በጸጉራቸው ላይ የሚያስሩት ጌጥ |
| ቁንቢ (qunbii) | ከርቤ (እጣ መሰል) ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል |
| ቃሉ (qaalluu) | የኦሮሞ ሀገረሳባዊ ሃይማኖት መሪ ነው፡፡ |
| ቡና ቃላ (buna qalaa) | ድፍኑን ቡና ቆልቶ፣ በለጋ ቅቤ፣ በማርና በትኩስ ወተት ተቀላቅሎ የሚዘጋጅ ባህላዊ የምግብ ዓይነት ነው፡፡ |
| ባቤ (baabbee) | ሙሉ ዘንግ (ለሸንኮራ፣ ለጥንቅሽ፣ ለቀርከሃ...) |
| ቦኩ (bokkuu) | የቃሉና የገዳ በትር (የኦሮሞ ህዝብ ከፍተኛ የሥልጣን ምልክት) |
| ቦኩ (bokuu) | ከማህበረ-ባህላዊ አገልግሎቶች ላይ ማዕቀብ ማድረግ |
| ቦካ (booka) | ከማር ብቻ የሚጣል የጠጅ ዓይነት |
| አውድ | አንድ ፎክሎራዊ ቅንጣት የሚከወንበት መቼትና አጠቃላይ ድባብ |
| አያንቱ (ayyaantuu) | የእግዚሃብሔር መንፈስ ያደረባቸውና ትንቢት የሚናገሩ ሰዎች |

| | |
|---|---|
| ኡሉፋ (ulfaa) | መንፈሳዊና ባህላዊ ቁስ |
| እችማ (ichima) | አስቴ |
| ካላቻ (kallachaa) | ቃሉና ገዳ በግንባራቸው ላይ የሚያደርጉት መንፈሳዊ ምልክት ሲሆን፤ ከነሀስ ወይም ከእንጨት በወንድ ብልት ቅርጽ የሚሰራ |
| ካሎ (kalloo) | የቃሉ አገልጋዮች (ባለካላቻ) |
| ወዲዳ (wadiida) | ፍም እሳት |
| ዋቃ (waaqaa) | እግዚሃብሔር /ፈጣሪ/ |
| ዋቄፋታ (Waaqeefataa) | በዋቃ የሚያመልኩ/የሚያምኑ ምዕመን |
| የጉቱ ጉዞ | ገዳዎችና የመማክርት አባላቱ ወደቃሉ የሚያደርጉት የስልጣነ ሢመት ማጽደቂያ መንፈሳዊ ጉዞ |
| ዲባሱ (dhibaasuu) | ፈጣሪን መስዋዕት (ወተት ወይም ቦካ) አቅርቦ መለማመን |
| ዲኪቻ (dikichaa) | በቆላ የሚገኝ የሀረግ ዓይነት |
| ዳሪሙና ኮንቶማ | የጉጂ ጎሳዎች ለሁለት ተከፍለው ያላቸው አሰፋፈር ሁኔታ መጠሪያ |
| ዳኑ (danuu) | ባጋጣሚ ወይም ሳይታሰብ የሚፈጠር ክስተት |
| ጂላ (jila) | የቃሉ/የገዳ ከበራ |
| ገልማ (galma) | የቃሉ ቤተ-አምልኮና መኖሪያ እንዲሁም የተቋሙም መጠሪያ ስም ነው፡፡ |
| ገዳ/አባገዳ (gadaa) | የገዳ ስርዓት መሪ |
| ጉማ (gumaa) | ለደም ካሳ የሚሰጥ ከብት ወይም ገንዘብ፣ የስርዓቱም መጠሪያ ስም ነው፡፡ |
| ጎንዶሮ (gondooroo) | የችግሩ ወይም የሀዘኑ ዳርቻ ያድረገው |
| ጨቡ (cubbuu) | ሀጢያት |
| ፋጭ (faacii) | ንስሃ መግባት |

## ለእንግሊዚኛ ቃላት የተሰጡ ፍችዎች

| | |
|---|---|
| Accommodation | ማስማማት |
| Acculturation | መቀየር/ማዋሃድ |
| Adaptation | መላመድ |
| Case study | ንጥል-ጥናት |
| Disappearance | መጥፋት |
| Hemispheric theory | ክልላዊ ንድፈ ሀሳብ |
| Recession | መዘንጋት/ትዝታዊ |
| Retention | መቋቋም |
| Revitalization | ማንሰራራት |
| Ritual | ከበራ |
| Social Construction theory | የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ |
| Symbolic Interpretations theory | ተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ |
| Syncretism | ማጣመድ/ማጣመር |

## ምህፃረ-ቃላት

| | |
|---|---|
| ቀ/ገ/ማ | ቀበሌ ገበሬ ማህበር |
| ት/ቤት | ትምህርት ቤት |
| አ.አ.ዩ. | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ |
| ጽ/ቤት | ጽሕፈት ቤት |
| ዓ.ም. | ዓመተ ምህረት |
| የኢ. ፌ. ዴ. ሪ. | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐቢሊክ |
| CSA | Central Statistical Agency |
| GTAGO | Gumii tokkummaa abbooti gadaa Oromoo) |
| WAWA | Waldaa Amantii Waaqeffannaa Addunyaa |
| A.L.I. | Akka Laakkofsa Itiyoophaatti |

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹ ትንተናና ገለጻ ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ ርዕስ ዙሪያ በቀጥታ ግንኙነት ያለው ሰፋ ያለ ጥናት አይታይም። በተዘዋዋሪ መንገድ የተካሄዱት ጥናቶችም አብዛኛዎቹ ከገዳ ስልጣን ሽግግርና ከጎንዶሮ ከበራዎች ጋር ያላቸውን ሂደቶች ከማሳየቱ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ሌሎች ደግሞ በቃሉ ተቋም ላይ የተካሄዱትን ጥናቶች የተመለከትን እንደሆነ አብዛኛዎቹ በይዘታቸውም ሆነ በፅንሰ-ሀሳባቸው ሰፊ ልዩነቶች ይታይባቸዋል። ይህ ደግሞ ስለሀገረሰባዊ ሃይማኖቱና ዕውቀቱ ላይ ስላለው ግንዛቤ ክፍተቶች እንዲፈጠሩ ምክንያቶች ሆነዋል። ይኸውም፡- ቃሉን ከ‹‹ቃልቻ›› ለይቶ አለመግለጽ፣ እንዲሁም ግብራቸውንና ተግባራቸውን ቀላቅሎ የመግለጽ ሁኔታዎች ይታያሉ። ስለዚህ ይህን መነሻ በማድረግ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዓላማ፡- የቃሉን ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በመተንተን፤ ያላቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳዎችን ማሳየት ነው። ይህንንም ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የምርምር ጥያቄዎችን በማንሳት ማለትም፡- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምን ምንድናቸው?፣ ለምን ይከወናሉ?፣ መቼቶች ምን ይመሳላሉ?፣ ለሚሉትና ሌሎችም ጥያቀዎች በጥናቱ መልስ ተሰጥቶባቸዋል። በጥናቱም ማህበረሰቡ ይህን ዕውቀት እንዴት እንዳዋቀሩ ኢፒስቲሞሎጂያዊ አተያይን መሰረት በማድረግ ለማት ተችሏል። መረጃዎችንም ኢትኖግራፊያዊ ስነ-ዘዴን መሰረት በማድረግ፡- በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅና በቡድን ውይይት ተሰባስበዋል። ከዚያም ንጥል ጥናቶችን በመጠቀም በዋናነት በማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያንና በተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳቦች የተተነተኑ ሲሆን፣ በአጋዥነት በአውዳዊ፣ በፋይዳዊና በክልላዊ ንድፈ-ሀሳቦች በመተንተን ተገልጸዋል። በትንተናውም በቃሉ ከበራዎች ማህበረሰቡ በሚከወኑት ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች በመጠቀም፤ በሰዎችና ከብቶች በሽታ፣ በድርቅ፣ በግለሰቦችና በአጎራባች ማህበረሰቦች መካከል በሚፈጠሩ ግጭቶች የተነሳ ሰላማቸውን በማጣት የነበረባቸውን ስነ-ልቦናዊ ጭንቀቶች በማረጋጋት፣ በግጭቶቹም ምክንያት ተበላሽቶ የነበረውን ማህበራዊ ግንኙነት በመጠገን፣ የገዳን ስርዓት ዴሞክራሲዊ ሂደት በማስከበርና አንድነታቸውን ጠብቀው መቆየታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። በመጨረሻም በጥናቱ መሰረት በማንሰራራት ላይ ያሉ ከበራዎች እንዳሉ ሁሉ፤ አንዳንድ ቢስተካከሉ ተብሎ የቀረቡ የይሁንታ ሀሳቦች በሚመለከተው አካል ትኩረት ቢደረግባቸው ይህን ዘርፈ-ብዙ የሆነውን የቃሉና የገዳ ተቋማትን ጠቀሜታዎች ማስቀጠል ይቻላል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የጉጂ ኦሮሞ እንደማንኛውም የኦሮሞ ማህበረሰብ የሚያመልኩት የራሳቸው የሆነ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት አላቸው። የሃይማኖቱም መጠሪያ «ዋቄፋና» ይባላል። የዋቄፋናን ሃይማኖት በበላይነት የሚመራው ደግሞ ቃሉ ይባላል። በቃሉ አማካይነት በተለያዩ ወቅቶችና ክስተቶች የሚከናወኑ ሃይማኖታዊ ከበራዎች አሉ። ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት «በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹ ትንተና» በሚል ርዕስ ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. በከፊል ማሟያ የቀረበ ነው። ከርዕሱ ለመረዳት እንደሚቻለው ጥናቱ በዋናነት የሚያጠነጥነው እነዚህን ከበራዎች በመተንተን ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳዎች መግለጽ ነው። ይኸውም፦ ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ በምን ዓይነት መንገዶች እንደሚከሰቱና ፋይዳዎቹንም ለይቶ ለማውጣት እንደተሞከረ በትንተናው ወቅት ተዳሰዋል። ለዚህም እንዲረዳኝ እነዚህ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምን ምንድናቸው?፣ ከበራዎቹ ለምን ይከወናሉ? የሚሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በማንሳት መረጃዎችን በዋናነት ከቃሉና ከገዳ ተቋማት በቀዳማይ ምንጭነት ተሰብስቧል። ለጥናቱ ማስተንተኛ የዋሉትን ፅንሰ-ሀሳቦችና ንድፈ-ሀሳቦችን ደግሞ ከካልኣይ ምንጮች በማጠናቀር አግባብነት ባለው መልኩ ተተንትነው፣ በገለጻ ዘዴ በማቀናበር በስምንት ምዕራፎች ተከፍለው ቀርበዋል።

ይኸውም፦ የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ሲሆን፤ በስሩ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱን ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰንናውስንነት ያካተተ ነው።

ምዕራፍ ሁለት ደግሞ ለጥናቱም እንደማስተንተኛ ያገለገሉ ጽንሰ-ሀሳቦችና ንድፈ-ሀሳቦች የቀረቡበትና ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት አላቸው የተባሉ ቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ የተደረገበት ክፍል ነው።

የአጠናን ዘዴው ከኢፒስትሞሎጂና ኦንቶሎጂ አተያይ ምን እንደሚመስል፣ የጥናቱ ስነ-ዘዴ (methodology)፣ ዘዴዎች(methods)፣ ናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የተሰበሰበው የመረጃ ዓይነቶችና የመሳሰሉት ደግሞ በዝርዝር በምዕራፍ ሦስት ስር ቀርበዋል።

የጉጂ ኦሮሞ ማሕበረ-ባሕላዊ ዳራ ማለትም፦ የጉጂ ኦሮሞ መገኛ፣ የጉጂ ኦሮሞ ማንነት፣ ሃይማኖቱ፣ ቋንቋውና መተዳደሪያው ተጠናቅረው በምዕራፍ አራት ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል።
ምዕራፍ አምስት ቃሉና የቃሉ ተቋምን በተመለከተ ከመስክ በተሰበሰቡትና ከካልኣይ ምንጮች በተገኙ መረጃዎች ስለቃሉ ማንነት፣ የቃሉ መማክርት አባላትና ተግባራቸው፣ የቃሉን ስልጣነ-ሢመትና የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እንዲሁም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ መቼቶች በዝርዝር ታይተዋል።

ስለ ከበራዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለይቶ በማውጣት፤ ከቀረቡት ተያያዥ ጽንሰ-ሀሳቦችና ንድፈ-ሀሳቦች አንጻር በንጥል ጥናቶች (Case Studies) በመጠቀም ለማሳያነት ትንታኔና ገለጻ በተመለከተ በምዕራፍ ስድስት ስር በሰፊው ቀርበዋል።
ምዕራፍ ሰባትን የተመለከትን እንደሆነ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት አስመልክቶ የተቃኘበት ሲሆን፣ ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች አሁን ያሉበትን ደረጃም ተዳሰዋል።

በመጨረሻም በምዕራፍ ስምንት ስር የጥናታዊ ጽሑፉ ማጠቃለያ ሀሳብና አጥኚው በጥናቱ ወቅት ያያቸውን፣ የታዘባቸውንና ይህ ቢሆን በማለት ያቀረባቸው የይሁንታን ክፍል አጠቃሎ የያዘ ነው።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የኦሮሞ ማህበረሰብ በገዳ ስርዓት ተደራጅቶ እራሱን በራሱ የማስተዳደር ባህል የረጅም ጊዜ ተግባርና ልምድ ውጤት ነው። ይህ የማህበረሰብ ዕውቀት ዴሞክራሲያዊ መሰረት እንዳለው ብዙ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር አጥኚዎች አረጋግጠዋል። ለዚህ የገዳ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ ገጽታዎች መሰረት የቃሉ ተቋም አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ በዚህ ጥናት ውስጥ ለማረጋገጥ ተችሏል። በቃሉ ተቋም ውስብስብ ተግባራትን ማለትም፦ ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይከወናሉ። ከእነዚህም ውስጥ የገዳ ስልጣነ-ሢመት ማጽደቂያ ከበራ፣ የጎንዶሮ ከበራ፣ የፋጭ ከበራ፣ የሁሉቃ ከበራና የቃሉ ስያሜ ከበራ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህን ከበራዎች የጉጂ ኦሮሞ ከተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ለመውጣትና ለተለያዩ ጉዳዮች ይገለገሉባቸው ነበር፤ እየተገለገሉበትም ይገኛሉ። እነዚህ የማህበረሰብ

ዕውቀቶች በግለሰቦችና በማህበረሰቡ እንዴት እንዳወቁትና ኦንቶሎጂዎቹም በጥናቱ ውስጥ ተዳሰዋል፡፡

የሃይማኖታዊ ከበራን የተመለከተን እንደሆነ ከፎክሎር ዘውጎች ውስጥ በዋናነት በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ይመደባል፡፡ ይሁን እንጂ የቃሉ ከበራ ከዚህ በቀር ሌሎችን የፎክሎር ዘውጎችን ባህሪያት አይጋራም ለማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በክዋኔው ላይ የሚዜሙት ዜማዎች፣ የሚነገሩት ሚቶች፣ እንዲሁም ምርቃትና እርግማን ከተመለከተን ከስነ-ቃል ዘውግ የሚጋራው ባህሪያት እንዳሉት ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በከበራዎቹ ላይ የሚለበሱ አልባሳት፣ የሚቀርቡት ምግቦችና መጠጦች ደግሞ ቁሳዊ ባህሉን ያመላክታል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያመለክተው የፎክሎር ዘርፎች እርስ በርስ ተሳስረው እንደሚገኙ ነው፡፡ ይህንን ማወቅ የሚቻለው በከበራዎቹ፣ በሚቶቹና በቁሳዊ ባህሎቹ ላይ ጥልቅ ምርምር በማካሄድ ነው፡፡ ይኸውም፡- እነዚህ ማህበረሰባዊ ዕውቀት እንዴት እንደተዋቀሩና ለማህበረሰቡ ተመልሰው እንደመተዳደሪያ ህግ፣ እንደ ባህል ማስቀጠያና እራሳቸውን ከሌሎች ማህበረሰብ ለየት የሚያረጋቸውን ማንነት እንዲይዙ እንዳደረጉ በጥልቀት ተዳሰዋል፡፡ በመሰረቱ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ሲከወኑ፡- የሚከወነው ቴክስት፣ የአነጋገር ለዛ፣ የሚከወንበት አውድ፣ ቁሳዊ ባህሉና በዚህ ዙሪያ የሚባሉ ተረኮችን በውስጣቸው ያጠቃልላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ተዳምረው ሲተነተኑ ሃይማኖታዊ ከበራው ፍቾ ያገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ተተንትነዋል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው በተለያዩ የትምህርት መስኮች ላይ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ነገር ግን አብዛኞዎቹ የቃሉ ተቋም ግጭትን ከመፍታትና ከማስወገድ አኳያ ያለውን ሚና የሚያትቱ ሲሆን፤ የተወሰኑት ደግሞ በገዳ ስርዓት ውስጥ ቃሉ ያለውን ሚና የገለጽበትን ሁኔታ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ነገር ግን አብዛኞዎቹ የቃሉ ተቋምና ከበራ ብለው ያነሱት፤ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ከሚከወነው ሃይማኖታዊ ከበራ ጋር በብዙ መልኩ ያለመመሳሰል ይታይባቸዋል፤ በጥልቀት ለተመራመረም ከገዳ ስርዓት ጋር ያላቸው ተዛምዶም ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ናቸው፡፡

ይህንኑ የቃሉና የቃሊቻ ከበራን በተመለከተ ያለውን ብዥታ በኦሮሞ ተወላጆችም ሆነ፤ በሌላው ብሔር ተወላጆች ላይ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ከዚህም የተነሳ እንደ አጠቃላይ ኦሮሚያ ይህ ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያለውን ተቋም በውስጡ የሚከወኑ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በሎሎች ሃይማኖት ተከታዮች (በክርስትናና በእስልምና) ዘንድ አልባሌ ስም በመስጠት፤ ያለ ግብሩ

እየተነቀፈ ይገኛል፡፡ ስለዚህ የቃሉን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምንነት፣ መከዋኛ መቼቶቹን፣ የሚከወኑበትን ዓላማና ከገዳ ስርዓት ጋር ያላቸውን ጥብቅ ግንኙነት በመረጃ በማስደገፍና ትንታኔዎችንም በመስጠት ያለውን የመረጃ ክፍተቶች ለማሳየትና መሙላት ተችሏል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

የዚህ ጥናት አቅራቢ የአካባቢው ተወላጅ በመሆኔ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ በተወሰነ ደረጃ ታድሜያለሁ፡፡ ይኸውም፡- በዓመት ከአንዴም ሁለቴ በቃሉና በገዳ ተቋማት በጋራም ሆነ በተናጥል ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ያካሄዳሉ፡፡ ማህበረሰቡም ለቃሉ ተቋም ያላቸው አመለካከት ጥብቅ ነው፡፡ ይህን የሚያስረዱ የተለያዩ የፎክሎር ዓይነቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ሲንፀባረቁ ይስተዋላል፡፡

ለአብነት ያህል ልጆች እንቆቅልሽ በሚጫወቱበት ወቅት ለተጠየቁት እንቆቅልሽ ምላሽ ካጡ፤ በጫወታው ህግ መሰረት ሀገር ይሰጡና፤ እንዳይሰደቡ(arrabsoo) ፍራቻ ቶሎ ብለው «ቃሉ ቤት ገባሁ (mana Qaalluu seene.)፡፡» ወይም «ከቃሉ ቤት ጥልቅ (caca'u mana Qaalluu.)» ይላሉ፡፡ ቃሉ በኦሮሞ ባህልም ሆነ በዋቄፋና ሃይማኖት የተከበረ ስለሆነ፤ የሱ የሆኑ ሁሉ ይከበራሉ፡፡ ስለዚህ ስድቡ ይቀርና መልሱን ብቻ እንዲመልሱ ይደረጋል፡፡ ሌላው በደቦ ስራ ላይም ሆነ በተለያዩ ጭፈራዎች (Qeexala) ወቅት ቃሉን የሚያሞግሱ ዘፈኖች ይደመጣሉ፡፡ አንዳንዴም ሴቶች እራሳቸውን ከወሲባዊ ጥቃት፣ ከተለያዩ የዱር አራዊት በቃሉ ስም በማውገዝ ከጥቃቱ እንደሚታደጉ ይነገራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ምስክር ላለው፣ ምስክር ለሌለውና በህግ ፊት የተካዱ ወንጀሎች በቃሉ ተቋም አምኖ ለይቅርታ መዘጋጀት ወይም የበደሉትን ክሰው ለመታረቅ ያለው ሂደት የጠበቀ ነው፡፡ በግለሰቦች፣ በአጎራባች ጎሳዎችና በገዳዎች መካከል ግጭቶች ሲፈጠሩ የመፍታትና የማስቀም ስልጣን እንዳለውም ይታመናል፡፡ ሌላው በቃሉ መማክርት የሚወጡ ህጎችንና ደንቦችን የማክበር ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡ ታዲያ እነዚህንና የመሳሰሉ ተግባራት የማስፈጸም አቅም እንዴት ሊኖረው ቻለ? የቃሉ ተቋም ከበራዎች ለማህበረሰቡ ምንድናቸው? የሚሉትንና ሌሎችንም ፋይዳዎች በጥልቀት የማወቅ ጉጉት ለዚህ ጥናት አንደኛው አነሳሽ ምክንያት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ለሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ በከፊል የማሟያ ጥናት «Sirna Gaa'ilaafi Moggaasa Qaalluu Oromoo Gujii.» በሚል በቃሉ የጋብቻና ስያሜ አሰጣጥ ከበራ ላይ በአ.አ.ዩ. ለአፋን ኦሮሞ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ጥናት አካሂጄ ነበር፡፡ በወቅቱ

ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ስራዎች ዙሪያ የተደረጉ የዳሰሳ ንባብ ለአሁኑ ርዕሰ-ጉዳይ መነሻ ሀሳብ ሆነውኛል፡፡ ይኸውም፡- በተለያዩ የቃሉ ተቋማት ተብለው የቀረቡት የሃይማኖታዊ ከበራዎች ጥናት ከይዘታቸውና ከፅንሰ ሀሳባቸው አኳያ የጎላ ልዩነቶች የታየባቸው ነበሩ፡፡ ይኸውም፡- ከይዘታቸው አኳያ አብዛኛዎቹ ያነሱት ከገዳ ስልጣነ-ሲመት ጋር ያለውን ግንኙነትና ከግጭት መፍታትና ማስወገድ ጋር ያሉትን ፋይዳዎች ናቸው፡፡ ሌላው ከፅንሰ-ሀሳብ አኳያ በአብዛኛው አካባቢ በተካሄዱት ጥናቶች ውስጥ ቃሉ (Qaalluu) እና ቃልቻ/ቃሊቲን (qaallichaa/qaallittii) እንዲሁም የሙገሳ ዘፈን (weedduu) እና ወዳጃን (wadaajaa) አንድ እንደሆኑ በመቁጠር ሲጠቀሙበት ይታያሉ፡፡ የዚህ ማብራሪያ በ 2.3. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ስር በስፋት ተገልጿል፡፡

ስለዚህ እኔ ሊሰራ የፈለኩት ቃሉ ምንድነው?፣ ምግባሮቹስ ምን ምንድናቸው? የማህበረሰቡ ዕውቀትስ ምን ይመስላሉ? ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ለማህበረሰቡስ ምን ምን ፋይዳዎች አሉት? የሚሉትን ከጉጂ ቃሉ አኳያ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና ተንትኖ በመግለጽ የነበረውን የዕውቀት ክፍተት ለመሙላት በማሰብ ነው፡፡

## 1.3. የምርምሩ ጥያቄዎች

- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምን ምንድናቸው?
- የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለምን ይከወናሉ?
- የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ መቼቶች ምን ይመስላሉ?
- በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ የሚቀርቡ ተምሳሌቶች ምን ይመስላሉ?
- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት ምን ይመስላሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በጥናቱ ምላሽ ይሻሉ፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ዓቢይና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

### 1.4.1. ዓቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በመተንተን ያላቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳዎችን ማሳየት ነው፡፡

### 1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ለይቶ መግለጽ፣
- የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች መቼቶችን መግለጽ፣
- የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን መተንተን፣
- በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ የሚቀርቡ ተምሳሌቶችን በመተንተን መግለጽ፣
- በቃሉ ተቋም ውስጥ የታዩ ለውጦችና ቀጣይነታቸውን ማሳየት የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ በቀጥታ የተሰሩ ጥናቶች ባይኖሩም፤ በገዳ ስርዓት ውስጥ ስለቃሉ በታሪክ፣ በስነ-ሰብ፣ በህግ፣ በፊሎሎጂና በፍልስፍና የትምህርት መስኮች ስር በተደረጉ ጥናቶች የተነሱ ሀሳቦች አሉ፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ የተካሄደው ከፎክሎር የጥናት መስክ አኳያ ነው፡፡ ጥናቱም የታየው ከበራውን ከተከወነበት አውድ አኳያ በመተንተን፤ እያንዳንዱን ሃይማኖታዊ ከበራዎች በስፋትና በጥልቀት ያየ በመሆኑ የሚከተሉት ነጥቦች ተፈላጊ ያደርጉታል ተብሎ ይገመታል፡፡ እነሱም፡-

- በክለሳ ድርሳናት ውስጥ እንደታየው በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራና ፋይዳ ዙሪያ በይዘትና በፅንሰ-ሀሳብ ደረጃ የተፈጠረውን የዕውቀት ክፍተት ይሞላል ተብሎ ይገመታል፡፡
- የቃሉ ተቋም በማህበረሰቡ ዘንድ ካለው ተሰሚነትና ተዋረዳዊ መዋቅር ላይ በመመርኮዝ በህዝቡና አካባቢው ላይ ተመስርተው ለሚወጡ ፖሊሲዎችና መርሃ-ግብሮች አቅጣጫ እንደ ግብአትነት ሊያገለግል ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል በጤናው መስክ፡- በስነ-ተዋልዶ፣ በኤች.አይ.ቭ ኤድስና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ በሰፊው መስራት ይቻላል፡፡
- ለቋንቋ መምህራን፣ ለመጽሐፍ አዘጋጆች፣ ለኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች እንደ መረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡
- ስለቃሉ ተቋምና ስለሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ማወቅ ለሚፈልጉ የጋራ ግንዛቤ ይፈጥራል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የጉጂ ኦሮሞ በአሁን ወቅት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ አስራ ዘጠኝ ዞኖቹ ውስጥ ባብዛኛው በቦረናና ጉጂ ዞኖች ውስጥ ሰፍረው ይገኛሉ።[1]የቃሉ ተቋም ደግሞ ከአዲስ አበባ በስተ-ደቡብ ወደ ሞያሌ-ኬንያ በሚወስደው አስፓልት መንገድ በ375 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ይህ ተቋም ቀደም ሲል በጉጂ ኦሮሞ የአላብዱ ጎሳ ወሰን ውስጥ ነበር። ነገር ግን በጉጂና ጌዴኦ የድንበር ይገባኛል ጥያቄ በቀድሞው የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት የድንበር ማካለል ሂደት ከተወሰኑ መንፈሳዊ ስፍራዎች ጋር ወደ ደ/ብ/ብ/ክ/መ፣ ጌዴኦ ዞን፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀበሌ ልዩ መጠሪያው ካራ ሶዲቲ ተከልሏል (Asebe, 2007) እና (ዘላለም፣ 2000)።

ስለዚህ አንደኛ ከዞኑ የመሬት አቀማመጥና ስፋት የተነሳ ሁሉንም ማዳረስ ባለመቻሉ፣ ሁለተኛ ጥናቱ የሚያጠነጥነው በቃሉ ተቋም ዙሪያ በመሆኑ ከቦታ አኳያ የቃሉ ተቋም በዋናነት ትኩረት ተሰጥቶታል። ከዚህ በተጨማሪ በቦረና ዞን፣ አባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀበሌ የሀሎ ገዳ ተቋም እና በጉጂ ዞን የሚገኘው የገዳዎች ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ማዕከል፤ ሚኤ ቦኮንም ያማከለ ነው። ምክንያቱም በሁለቱም ዞኖች ውስጥ ያሉት ሶስቱም የጉጂ ኮንፌድረሲ ገዳዎች የስልጣን ርክክብ የሚፈጽሙበት መንፈሳዊ ስፍራ በመሆኑ ነው።

ሌላው የጉጂ ኦሮሞ ሁለት ዓይነት የገዳ ስልጣን ሽግግር ይከተላሉ። ይኸውም በዘር ከአባት ወደ ልጅ የሚሸጋገር እና በየስምንት ዓመት ልዩነት የሚካሄድ የስልጣን ሽግግር ነው። ዝርዝሩን በ4.1.1. ስር ተገልጿል። ከእነዚህ የስልጣን ሽግግር ውስጥ የመጀመሪያውን የተወሰነ ገለጻ ብቻ በመስጠት፤ በሁለተኛው ዓይነት ማለትም በየስምንት ዓመቱ የሚካሄደው የስልጣን ሽግግር ላይ በጥልቀት ትንተና ተደርጓል።

የጥናቱም መረጃዎች የተሰበሰቡት በተለይም ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች ከአባቃሉና ከመማክርት አባላቱ ላይ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪያ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በአውዱ ላይ በመገኘት በምልከታና በቃለ-መጠይቅ ስልጣኑን ከሚረከቡትና ከሚያስረክቡ አባገዳዎች፣ ከዩባዎች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከሴቶችና የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮችን በማሳተፍ ቃለ-መጠይቆችና የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል።

---

[1]. ይህ ጥናት በተካሄደበት ወቅት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር አስራ ዘጠኝ ዞኖቹ ነበሩ። አሁን ግን የበደሌ ቡኖና የምዕራብ ጉጂ ዞኖች ተጨምረው ተቋቁመዋል።

የጥናቱም ትኩረት በአካባቢውና በህዝቡ ከሚከወኑ ከበራዎች ውስጥ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ ሲሆን፤ ይህም በአውዳዊ ክዋኔዎቹና ፋይዳቸው ላይ ያነጣጠረ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በባህላዊ ከበራዎቹ ወቅት የማህበረሰቡ ዕውቀት፣ ጎልተው የወጡ ስነቃሎችን፣ ቁሳዊ ባህሎችንና ተምሳሌቶቹን እንዴት እንደሚመሰርቱ የመመዝገብ፣ የመተንተንና የመግለፅ ስራን ያካተተ ነው።

## 1.7. የጥናቱ ውስንነትና የተወሰዱ መፍትሔዎች

አጥኚው የአካባቢው ተወላጅ በመሆኑ ቋንቋውንና ባህሉን ያውቃል። ነገር ግን ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በአብዛኛው የሚገኙት በቃሉና በገዳ ተቋማት ውስጥ ነው። ስለዚህ በግልጽና በስውር የሚከወኑ ስርዓቶች እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ በስውር የሚከወኑትን በተመለከተ መረጃዎችን በምልከታም ሆነ በቃለ-መጠይቅ ለማሰባሰብ ፍቃደኛ ያለመሆን ክፍተቶች ተከስቶ ነበር።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከየካቲት 6-13/2008 ዓ.ም. በጉጂ ዞን ሚኤ ቦኮ ላይ በተደረገው የገዳ ስልጣን ሽግግር የመከታተሉ አጋጣሚው ተፈጥሮ ነበር። በሂደቱም በመጨረሻው መርሃ-ግብር ወደ ቃሉ ተቋም ስልጣነ-ሢመታቸውን ለማጽደቅና ቃለ-መሃላ ለመፈጸም ይደረግ የነበረው የጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ ሳይካሄድ ቀርቷል። ምክንያቱም በውስጣዊ ተግዳሮቶች እንደሆነ በዝርዝር በ7.1.1. ስር ተገልጿል። ከዚህም የተነሳ የገዳ ስልጣነ-ሢመት ሃይማኖታዊ ከበራ በቃሉ ተቋም ከአውዱ ላይ በምልከታ ሊሰበሰብ ታቅዶ የነበረው መረጃ ሳይሳካ ቀርቷል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሚኤ ቦኮ በተደረገው የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ ላይ ከነበረው የሰው ብዛትና ግፊያ፣ እንዲሁም ከጋዜጠኞች በቀር አብዛኞዎችን ለቀረጻ ከመከልከላቸው የተነሳ፣ የተወሰኑ መረጃዎችን ለመከታተል አልታደልኩም ነበር።

ሌላው በአሁኑ ጊዜ ባለው የኑሮ ውድነትና ለጥናቱ ተብሎ ከዩኒቨርሲቲው የሚመደበው ገንዘብ ስለማይበቃ የበጀት እጥረት ተከስቶ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ጥናቱን በወጣው ዕቅድ መሰረት ለማካሄድ የጊዜ እጥረትም ተፈጥሮ ነበር።
ይሁን እንጂ እነዚህን ችግሮች ለማቃለል፣ የበጀትና የጊዜ እጥረቱን አስመልክቶ ከትምህርት ክፍሉ ጋር በመነጋገር የመፍትሄ አቅጣጫ ተሰጥቶበታል። የመረጃ ክፍተት እንዳይፈጠር ደግሞ በተቻለ መጠን ባህሉንና እምነቱን በማይጋፋ መልኩ በማግባባት በተወሰነ መልኩ በቃለ መጠይቅና የተወሰኑ መረጃዎችንም ከቀረጹ አካላት በማግባባት ወስጄ ክፍተቶቹን ለመሙላ

ጥሪያለሁ፡፡ ያልተከናወነው የጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ በተመለከተ በቃለ-መጠይቅ በተወሰነ ደረጃ መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡

ሌላው በመስክ ቆይታዬ ወቅት መረጃ አቀባዮቼ በቀጠሮ ዕለት ያለመገኘት፣ በመብራት መቆራረጥ ምክንያት የካሜራ ባትሪ በማለቁ የተነሳ የተሟላ ክዋኔ ያለመቅረጽ ክፍተቶች ተፈጥረው ነበር፡፡ እነዚህን ክፍተቶች ተለዋጭ ቀጠሮ በማድረግና የተቋረጡ ክዋኔዎችን በተቻለ መጠን በማስታወሻ በማስቀረት ክፍተቱን ለመሸፈን ተችሏል፡፡

በመጨረሻም በሚኤ ቦኮ መንፈሳዊ ስፍራ በአንድ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች፤ የተለያዩ እርከን ውስጥ ያሉ የገዳ መደብ አባላት የተለያዩ ክዋኔዎችን ይከውኑ ስለነበር እነዚህን ተሯሩጦ ለመመልከት አስቸጋር ነበር፡፡ እንደመፍትሔ የተጠቀምኩት ባጋጣሚ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ጓደኞቼን አንዱ ክዋኔ ላይ እንዲከታተሉልኝና ክዋኔውን እንዲቀርጹልኝ በማድረግ፤ የተቀረጸውን ቪዲዮ ተመልክቼ፣ ያልገባኝንና ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን ለይቼ በማውጣት፤ የሚመለከታቸውን አካላት በማፈላለግ በቃለ መጠይቅ የነበረውን የመረጃ ክፍተት ለማሟላት ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ስር በርዕሰ-ጉዳዩ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ፅንሰ-ሀሳባዊ ፅሁፎች፣ የጥናቱን መረጃዎች ማስተንተኛ ንደፈ-ሀሳባዊ ፅሁፎችና የተጠኑ ተዛማጅ ስራዎች ተዳሰው ቀርበዋል፡፡

### 2.1. ፅንሰ-ሀሳባዊ ፅሁፎች

በዚህ ርዕስ ስር ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ ፅንሰ-ሀሳቦች የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ ይኸውም፡- ስለፎክሎር፣ ስለሃይማኖት፣ ስለከበራዎች፣ ስለሚት፣ ስለቁሳዊ ባህል፣ ስለአውድና ከነሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፅንሰ-ሀሳቦችና የእያንዳንዱን ተግባር በተመለከተ ተዳሰዋል፡፡ ምክንያቱም የተሰበሰቡት መረጃዎች የተተነተኑት ከንደፈ-ሀሳባዊ ፅሁፎች በተጨማሪ በነዚህ ጽንሰ-ሀሳቦች አጋዥነት ነው፡፡

#### 2.1.1. ፎክሎርና ሃይማኖት

ፎክሎር የአንድ ማህበረሰብን ልማዶች፣ ወጎች፣ እምነቶችና ህዝባዊ ጥበቦችን ያካተተ ሰፊ የባህል ጥናት ዘርፍ ነው፡፡ Bauman, (1972) የAlan Dundes'ን ሀሳብ በመጥቀስ ፎክሎርን ሲበይን ከሁለት ቃላት የተመሰረተና ቃላቱም የቆሙለትን እሳቤ፡- ፎክ (folk) የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቢያንስ አንድ የጋራ የሆነ ጠባይ ያላቸው ማንኛውም ቡድንን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ቡድን ምናልባትም የጋራ ቋንቋ፣ ስራ፣ እምነት ያላቸው ሲሆኑ፤ ይሄነው የሚባል የራሳቸው የሆነ ትውፊት (tradition) ይኖራቸዋል፡፡ በቲዮሪ ደረጃ ቡድን የሚባለው ቢያንስ ሁለት ሰው ያለበት ነው፡፡ ትውፊቱ ደግሞ ቡድኑን የራሱ ቡድናዊ ስሜት (sense of group identity) እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ፡- የእንጨት ፈላጭ ቡድን ካለ፤ ፎክሎሩ የሚሆነው የእንጨት ፈላጭ ነው፡፡ ወታደሮችና የኮሌጅ ተማሪዎች እንኳን ፎክ ናቸው በማለት ይገልጻል፡፡ ሎር(lore) ደግሞ ጥበብ ነው፤ ቡድናዊ ጥበብ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የአንድ ሃይማኖት ተከታዮችን የተመለከትን እንደሆነ እራሳቸውን የቻሉ ፎክ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የእምነቱ ተከታዮች የጋራ የሆነ የአምልኮት ስርዓት፣ የጋራ የሆነ የማምለኪያ ስፍራ፣ የጋራ የሆነ አንድ ስያሜ ያለው ሃይማኖትና የሚከተሏቸው የጋራ የሆነ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡

ፎክሎርን ለማጥናት በድንበር ቀንብቦ መመልከቱ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተገለጸው ዘርፈ-ብዙ የጥናት መስክ ነው፡፡ የተለያዩ ምሁራን ፎክሎርን በተለያዩ ዘርፎች ይከፍሏቸዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ Wilson, (1986:228) እና Schoemaker, (1990:3) ፎክሎርን በሦስት ምድቦች ይከፍላሉ:: እነዚህም:- ሰዎች በቃላቸው የሚያስተላልፉት (verbal lore)፣ በእጃቸው የሚሰሩት (material lore) እና በተግባር የሚተገብሩት (customary lore) ናቸው:: በሌላ በኩል በሙያ ዙሪያው በስፋት የሚጠቀሰው አቀራረብ በ Dorsen (1972:3-4) የተከፈለው አመዳደብ ነው፡፡ ይኸውም:- ፎክሎር በዋናነት ስነ-ቃልን፣ ቁሳዊ ባህልን፣ ሀገረሰባዊ ልማድንና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን ያካትታል፡፡ እነዚህ የፎክሎር ዘርፎች ለየብቻቸው የቆሙ ሳይሆኑ፤ በመካከላቸው ግንኙነት፣ መስተጋብርና ተደጋግፎ አላቸው፡፡ በሌላ በኩል እያንዳንዱ የጥናት ዘርፍ በውስጡ የተለያዩ ዘውጎች ይኖሩታል፡፡

ለአብነት ያህል ሀገረሰባዊ ልማድ በስር እንደፌስቲቫሎች፣ ክብረ በዓላት፣ መዝናኛዎች፣ ጨዋታዎች፣ ሀገረሰባዊ መድኃኒቶች፣ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቶችና ሌሎችንም እንደሚያካትት Dorson'ን በመጥቀስ ፈቃደ (1991:13) ይገልጻል፡፡

የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ በዋናነት ከሀገረሰባዊ ልማድ የፎክሎር ዘውግ ስር ይመደባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሌሎችን የፎክሎር ዘውጎች ባህሪያትንም በተወሰነ ደረጃ እንደሚጋራ በመግቢያው ላይ ለማየት ተችሏል፡፡

ሌላው የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራን ፎክሎር ሊያስብለው የሚችለው የጉጂ ኦሮሞ የዋቄፋና ሃይማኖት ተከታዮችን እንደ አንድ እራሳቸውን የቻሉ ፎክ ልናያቸው ስለሚያስችለን ነው፡፡ ምክንያቱም የጋራ ጉዳያቸው የዋቄፋና ሃይማኖትና በስሩ የሚከናወነው የቃሉ ከበራዎች፣ ለከበራዎቹ ማጀቢያ የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ ምግቦቹና መጠጦቹ፣ ባህላዊ ጭፈራው፣ ከስርዓቱ ጋር አብረው የሚከወንባቸው ማንኛውም ቁሳዊ ባህሎች ሁሉ የዚህ ፎክ ቡድን ጥበብ ውጤትና የጋራ መገለጫዎች መሆናቸው ነው፡፡ ይህን እውቀት ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በትውልድ እየተዋቀረ ወይም በአምሳያው (ሞዴል ተደርጎ) የተፈጠረ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ይህ የጋራ እውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃልና በድርጊት ሲተላለፍ ማህበረሳባዊ ተቋም ሆኖ ማገልገሉ አይቀርም፡፡ የቃሉና የገዳን ተቋማት የተመለከትን እንደሆን የዚህ እውቀት ጥምረት ይመስላሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ይመስላል የጉጂ ኦሮሞ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለየ እንዲታወቅና እንዲጠራ ያስደረገው፡፡ ስለዚህ ይህ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ከፎክሎሩ ጋር ያለውን ጥምረትና ፎክሎራዊ ገፅታዎቹን በሚገባ ለመመልከት ያስችላል፡፡

### 2.1.2. የሃይማኖት ፅንሰ ሀሳብ

በዚህንዑስ ርዕስ ስር ስለ ሃይማኖት ምንነት፣ በተለይም ስለ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ወደ ሆነው የኦሮሞ ዋቄፋና ሃይማኖት የሚያንደረድሩንን ፅንሰ-ሀሳቦች በመዳሰስ ወደ ዋናው ርዕሰ-ጉዳይ የሆነው የቃሉ ሃይማኖት ከበራዎች ምንነት እንሸጋገራለን።

#### 2.1.2.1. የሃይማኖት ምንነት

ስለ ሃይማኖት ምንነት የተለያዩ ጸሐፍት በተለያየ መልኩ፣ ነገር ግን ተቀራራቢ ይዘት ባላቸው አገላለጽ ለማስረዳት ሞክረዋል። ለአብነት ያህል O'Neil, (2009) ሃይማኖት ማለት ሰዎች ዘወትር በልዕለ-ተፈጥሮ (supernatural being) ኃያልነት የማመን ስርዓት እንደሆነ ይገልጻል። Schoemaker,(1990:238) ደግሞ የሃይማኖት ቢያኔ መታየት ያለበት ከመንፈሳዊ ልምዶች አንጻር እንደሆነ ያስረዳል። ይኸውም እነዚህን በሚመስሉ የሕይወት ልምዶች ስርዓት የተደራጀ ሲሆን፣ ሃይማኖቶች በቅርጻቸውና በይዘታቸው ሊለያዩ ይችላሉ። በሌላ በኩል ሃይማኖት የእምነት ስርዓት ሆኖ በሃይማኖቱ ተከታዮች እንደ ፈጣሪያቸው ከሚያምኑት ጋር በማስገባት አብሮ የሚከወኑ ከበራዎች አሉ። እነ Peoples, J. and Bailey, G. (1991:293). ይህንኑ ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> *The three components of all religions, then are (1) belifes about the existence and nature of supernatural powers, (2) mythologies about the historical deeds of these powers, and (3) rituals intended to influence these powers to intervene favorably on behalf of the performances.*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሃይማኖት በውስጡ እምነቶች (belifes)፣ ሚቶች (mythologies) እና ከበራዎች (rituals) እርስ በርስ የሚደጋገፉ ጽንሰ ሀሰቦችን እንደሚያካትት ነው።

ጠቅለል ባለ አገላለጽ ሃይማኖት ዓለምን በፈጠረና ተፈጥሮን በበላይነት ይቆጣጠራል ተብሎ በሚያምኑት ልዕለተፈጥሮ (supernatural being) ልዩ ኃይል በእምነት መቀበል፣ ስለልዕለተፈጥሮው እውነትነትና ሀያልነት የሚያስረግጡ ሚቶች ያለውና ሃይማኖታዊ ድርጊቶቹ የተሸከሚቸውን ጉዳዮች የሚገልጹ ከበራዎች ውጤት እንደሆነ ከተለያዩ ቢያኔዎች ለመረዳት እንችላለን።

በአለማችን ላይ የተለያዩ ዓይነት ሃይማኖቶች አሉ። ለምሳሌ የክርስትና፣ የእስልምና፣ ህንዱዝም፣ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ወ.ዘ.ተ. መጥቀስ ይቻላል (Jonathan, 1996)። ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ሰዎች በቡድን የሚያከናውኗቸው ተግባራት ናቸው። በዚህ ቡድናዊ ክዋኔ ውስጥ ሃይማኖት የሚያካሂዳቸው ከበራዎች አሉ ፈቃደ፣ (1991፡14)። የጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ከዋቄፋና ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ የተወሰኑት ናቸው።
ሃይማኖትና ከበራ የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸው የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ። ከበራና ሃይማኖት ፈጽሞ ተነጣጥለው የማይቆሙና መነሻቸውም ወይም ምንጫቸውም ሚት ነው (Rappaport, 1999፡158)።

ስለዚህ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ለማጥናት በይበልጥ ትኩረት የተደረገው የሃይማኖታዊ ከበራዎችን፣ ሚቶችንና ቁሳዊ ባህሉን በጥልቀት በመመርመር፤ ሃይማኖታዊ ከበራውና ቁሳዊ ባህሉ ለማህበረሰቡ ያለውን ፋይዳና የማህበረሰቡን እውቀት ማለትም ስለማንነቱ ያቆየውን አሻራ መግለጽ ላይ ነው።

## 2.1.2.2. የሃይማኖት ባህሪያት

ሃይማኖት የብዙ ባህሪያት ባለቤት ነው። ከነዚህም ውስጥ ትራዲሽን፣ ሚቶችና ተምሳሌቶች፣ የመዳን ፅንሰ-ሀሳቦች (concepts of salvation)፣ የተቀደሱ ቦታዎችና ቁሶች፣ ከበራዎች፣ መንፈሳዊ ጹሑፎችና መልዕክቶቻቸው፣ የተቀደሱ ማህበረሰብና ቅዱሳዊ ልምድ የተወሰኑት ናቸው (Schoemaker, 1990፣60-61)። እነዚህ የተለያዩ ባህሪያት በአንድ ተጣምረው ለሃይማኖቱ እንደ አንድ መገለጫ ባህሪ ሆነው ያገለግላሉ።

ከእነዚህ ሃይማኖታዊ ባህሪያት ውስጥ የዋቄፋና ሃይማኖት ከመንፈሳዊ ጹሑፎችና መልዕክቶቻቸው ባህሪያት በቀር ሌሎቹን ያሟላል። እነዚህን ባህሪያት መሰረት በማድረግ በተናጠልና እንደየሁኔታው በአንድ ላይ በፎክሎራዊ የጥናት መስክ ማጥናት ይቻላል። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ውስጥ በአጥኚው በዋናነት የተተኮረው በሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ላይ ነው። እነዚህን ባህሪያት በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ ምን ይመስላሉ? የሚለውን ከአውዳዊ ክዋኔው አኳያ ከተመረመረ በኋላ ያለውን ፋይዳ በጥልቀት ተንትኖ ለመግለጽ ረድተዋል።

ይኸውም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ትራዲሽን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው በቃልና በድርጊት ነው። ስለቃሉ አመጣጥ፣ ስለቃሉ ተቋምና ሌሎችም ክዋኔዎች

አጀማመርና እውነተኛነቱን ለማረጋገጥ የሚጣረው ደግሞ በሚቶቹ ነው፡፡ የመዳን ፅንሰ-ሀሳብን በተመለከተ ከዋቄፋና ሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞች የዓለም አተያይ አኳያ የእግዚአብሔርን አምስቱን አእማድ ህግጋት ማለትም፡- ማምለክ፣ እቀባ፣ ሳፉ፣ ቅዱስና ክቡር እና በፀጋ መቀበል የጠበቀ ከሀጢያት ነጻ ነው ተብሎ ይታመናል፤ ከዚህ በተቃራኒ ከፈፀመ ደግሞ ሀጢያተኛ ነው ይባላል፡፡ እነዚህ ህግጋት በ5.1.3. ስር በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ አንድ ሰው ሲያውቅ በድፍረት፤ ሳያውቅ ደግሞ በስህተት ሀጢያትን ከፈፀመ በሃይማኖቱ መሰረት ፋጭ ወይም የንስሀ ከበራ ይፈጸምለትና ከሀጢያቱ እንዲነጻ ይደረጋል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን ከበራዎች የሚከወኑት ደግሞ ማህበረሰቡ አምኖ የተቀበላቸው የተቀደሱ ቦታዎችና ቁሶች አሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሃይማኖታዊውን ከበራ በዋናነት የሚመሩ የተቀደሱ መሪዎችና ማህበረሰብ እንዲሁም ቅዱሳዊ ልምድ አሉበት፡፡ ታዲያ እነዚህን ማህበረሰባዊ እውቀት በራሱ አዋቅሮ፤ለራሱ እየተገለገለበት እንደሆነ በተለያዩ ንድፈ-ሀሳቦች በመታገዝ ተተንትነው ተገልጸዋል፡፡

## 2.1.3. የከበራ ፅንሰ ሃሳብ

ማንኛውንም ሃይማኖት የተመለከትን እንደሆነ የራሱ የሆነ የሚያካሂዳቸው ከበራዎች አሉት፡፡ ስለዚህ ከበራን በተመለከተ አንዳንድ ፅንሰ ሃሳቦችን ማብራራቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ስለከበራ ምንነት፣ ዓይነቱ፣ ባህርያቱና ፋይዳው በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

### 2.1.3.1. የከበራ ምንነት

የከበራን ምንነት ወይም ብያኔ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጸውታል፡፡ «ritual» የሚለው የእንግሊዘኛው ቃል ከላቲን «ritus» ከሚባል ቃል የመጣ እንደሆነና የሚወክለውም ለአንዳች ሃይማኖታዊ ነገር ተብሎ የሚከወንን ዝግጅት እንደሚያሳይ Robert, (2006፡199) ይገልጻል፡፡

ይህን «ritual» ለሚለው የእንግሊዘኛው ቃል በተለያዩ የአማርኛ ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ ከበራ፣ ስነ-ስርዓት፣ ሪችዋልና የመሳሰሉትን በማለት እንደሚጠቀሙበት ለማየት ተችሏል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት ውስጥ ከበራ የሚለውን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ምክንያቱም ካሉት የተሻለና በብዙዎቹም ዘንድ እየተለመደ የመጣ በመሆኑ ነው፡፡

ብያኔውን በተመለከተ በተለያዩ ጽሁፎች ውስጥ ይዘቱን ባልቀየረ መልኩ፤ በተለያየ መንገድ ሲገልጹ ይታያል፡፡ በአብዛኞቹ ጽሁፎች ውስጥ ከሚገኙት ብያኔዎች ውስጥ የሚታዩ የጋራ

ነጥቦች አሉ። እነሱም እንደ መዋቅራዊነት፣ ቅደም ተከተላዊነት፣ ታዳሚ፣ ውጤት፣ ቅዱሳዊነት፣ ቡድናዊነት፣ ተደጋጋሚነት፣ ቋሚነት፣ ጎን ለጎንም ተለዋጭነት፣ ውስን መዋቅርና የጊዜና የቦታ ጽንሰ ሀሳብ ያካትታል (Salamone, 2004፡321)።

ከበራ ቃላዊ ያልሆነ፤ ነገር ግን ልክ እንደ ስነ-ልሳናዊ ጉዳዮች በርከት ያሉ ትእምርቶች ያሉበትና እያንዳንዱ ትእምርት ደግሞ ትርጓሜ የሚያገኘው በበቀለበት ባህል ባለው የምግባርና የትውፊት ሁኔታ ውስጥ ነው። ሌላው ደግሞ ከበራ የአንድን ቡድን የተለመዱ ጽንሰ ሀሳባዊና ቅደም ተከተላዊ ሂደቶችን የሚገልጽ ጉዳይ ነው (Bell, 1997፡44)።

ከበራ የሰዎች ሃይማኖታዊ የሆኑ እምነቶች፣ ትእምርታዊ የሆኑ መግባቢያዎች፣ ማህበረሰባዊ የሆኑትን ንድፈ-ሃሳቦችና ሌሎችንም ማህበራዊ ትርጓሜዎች የሚያስተላልፍ የመግባቢያ መንገድ ነው (Myrvold, 2008፡21)። ከዚሁ ጋር በማያያዝ በስነ-ሰብዓዊያን ብያኔ መሰረትም ከበራ አውዳዊ የሆነና ሐቲታዊ ጽንሰ ሀሳብ እንጂ የሰዎች ድርጊት ዋናው ጉዳይ ምንድን ነው? ወደሚለው የሚወስድ እንዳልሆነ በመገንዘብ፤ በአንጻሩ ይህ ጉዳይ የሰዎቹ አስተሳሰብ (እይታ)ና የሚሰጠው ትርጓሜ እንደሆነ ይገልጻል።

ከዚህ በተጨማሪ ከበራ ማለት ሃይማኖታዊ ድርጊቶች የተሸከሟቸውን ጉዳዮች የመግለፅ ከበራ ሲሆን፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ወይም ከዘመን ዘመን የሚዘልቅ እንደሆነ Mazama and Asante, (2009፡ 575) ያስረዳሉ።

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ከበራ በራሱ አንድ ፎክሎራዊ ክዋኔ ነው። እያንዳንዱ ከበራ ደግሞ የሚቀርብበት የራሱ የሆነ አውድ ይፈልጋል። አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ከሚያከናውናቸው ሰፊ ከበራ ውስጥ በርካታ ከበራዎች ተጨምረው ይቀርባሉ። ከበራ ደስታን፣ ሀዘንን፣ ጭንቀትን፣ ብሶትንና ሌሎች ስነ-ልቦናዊ ስሜቶችን በመግለጽ እረፍት ለማግኘት ይከወናል። በመሆኑም ሰው እስካለ ድረስ ከበራ አለ። ስለዚህ ታዳሚዎች በኑሯቸው የሚጠቀሙባቸውንና የሚመሩባቸውን እሴቶችና ተምሳሌቶች መግለጫ አድርገው ይጠቀሙባቸዋል (Bell, 1997፡171-172)።

በአሁን ወቅት የስነ-ሰብና የባህል ተመራማሪዎች ትኩረታቸውን በከበራ ምንነት መግለጽና መተርጎም ላይ አድርገዋል። ለዚህም-እንደ ምክንያት የሚያነሱት በርካታ አዳዲስ ንድፈ ሀሳቦች ምንጫቸው ማህበረሰቡ የሚያከብራቸው ከበራዎች ናቸው የሚል ነው። ንድፈ ሀሳቡን

ለመረዳት ከበራውን የሚያከናውኑ ሰዎች ለከበራውና ለማህበራዊ ደንብ ያላቸው አመለካከት፣ እንዲሁም ክዋኔው የሚፈልጋቸው ህጎች ሁሉ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች እንደሆኑ McCormick & White (2011፡1105) ይገልጻሉ።

ከዚህም በተጨማሪ የአንድ ማህበረሰብ ከበራ ማህበረሰቡ ህይወቱን፣ኑሮውን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የግድ አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር፤ የተሳታፊዎችን ስሜታዊና ስነ-ልቦናዊ ጥንካሬ የሚያዳብር መሆኑን Mazama and Asante, (2009፡575) ያስረዳሉ።
ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣እምነት፣የሚያስደስታቸውንና የሚያሳዝናቸውን ነገሮች ለመለየትና ስሜታቸውን የሚገልጽበትን መንገድ ለመረዳት ብሎም ማንነታቸውን ለማወቅ በህይወት ዘመናቸው የሚያከብሯቸውን ከበራዎች ማጥናት ተገቢ ነው። ይኸውም ከበራው በማን፣ መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደሚከበር በማጥናት የሚኖሩበትን ዓለምና ማንነታቸውን መረዳት ይቻላል።

በዚሁ መሰረት የቃሉን ከበራዎች በመመልከትና በመተንተን ስለጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ እውቀት፣ የአብሮነት አኗኗር ዘይቤ፣ ተቻችለውና እሴታቸውን ጠብቀው የኖሩበትን መንገድ መግለጽ ተችሏል።

### 2.1.3.2. የከበራ ዓይነቶች

ከበራዎችን የተለያዩ ምሁራን ከተለያዩ አቅጣጫ እንደሚከተለው ከፋፍለው ያዩታል። Van Van, Gennep, (1960) ከበራዎችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይመድባቸዋል። እነሱም፡- አንደኛው አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ማህበራዊ ደረጃ በሚሸጋገርበት ጊዜ የሚከወን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በወቅቶች መቀያየር ምክንያት የሚከሰቱ ለውጦች፣ የአዲስዓመት፣ የአዲስ ወቅታዊ ክስተቶች ምክንያት በማድረግ የሚከወኑ ከበራዎችን የያዘ ነው። ሌላው Bell, (1997:93) Durkheim'ን በመጥቀስ ከበራን መንፈሳዊና ዓለማዊ በማለት በሁለት እንደሚከፈሉ ትገልጻለች። መንፈሳዊ ከበራ ለማንኛውም ቡድን የመንፈሳዊና የልዕለ ተፈጥሮ ዓለም ወይም ክስተቶች ከእምነቶች ጋር ተያያዥነት እንዳላቸው Sims,M. & M. Stephens, (2005:102) ይገልጻሉ። በመንፈሳዊና ዓለማዊ ከበራዎች መካከል ልዩነቶች አሉ (Salamone, 2004:xi)።

Turner, (1977) ደግሞ ከበራን በተለየ መልኩ በሁለት ይከፍላቸዋል። እነሱም፡- አንደኛው በሕይወት ላይ ለሚደርሱ ውድቀቶች የሚከወኑ ከበራዎች (Life Crisis ritual) ማለትም

በአንድ ሰው የህይወት ዘመን የሚያጋጥሙ እክሎች፣ ለምሳሌ በሞትና በፍቺ ሰበብ የትዳር ጓደኛ ማጣት ከመሳሰሉት ውጥረቶች ለመዳን የሚከወኑ ከበራዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ሁለተኛው ደግሞ በስነ-ልቦናዊና አካላዊ ከሚደርሱ መከራዎችና ችግሮች ለመውጣት የሚከወኑ ከበራዎች (Rituals of affliction) በማለት ይከፍላቸዋል።

በሌላ በኩል ከአውዳዊ ገጽታው አኳያ ደግሞ ከበራን በሁለት ሲከፍሉት ይታያል። እነሱም ባለዝቅተኛ አውድ ከበራና ባለከፍተኛ አውድ ከበራ ናቸው። ባለዝቅተኛ አውድ ከበራ የሚባለው በትክክለኛ መንገድ ዲዛይን ያልተደረገና በተለመደ መልኩ ያላስተዋወቁት ወይም በጥንቃቄ ያልታቀደበትን ነው። በተቃራኒው ባለከፍተኛ አውድ ከበራ የሚባለው ደግሞ በአግባቡ ዲዛይን የተደረገና በተለመደው መንገድ ያስተዋወቁት ወይም በጥንቃቄ የታቀደበት ነው። ይኸውም ተሳታፊዎቹ ለክዋኔው ሆን ተብሎ የተዘጋጁ አልባሳትና ጌጣጌጥ ይጠቀማሉ። ምናልባትም በዚህ ዓይነቱ አውድ ውስጥ የዚያ ፎክ ወይም ቡድን መሪ የተለየ አለባበስ ሊጠቀም ይችላል። ይህ ደግሞ ማን ምን እንደሆነ በአለባበሳቸው እንድንለያቸው ያስችለናል (Sims & Stephens, 2005:98-99)። የ Salamone, (2004) አከፋፈል የተመለከትን እንደሆነ ወደ አስራ ስምንት የተለያዩ የከበራ ዓይነቶች እንዳሉ በዝርዝር ያስረዳል።

በሌላ በኩል Bell, (1997) የ Ronald Grimmis አከፋፈል ማለትም፡- ከበራን በአስራ ስድስት ዓይነቶች መክፈሉን በመግለጽ፣ በራሷ መንገድ ደግሞ እንደሚከተለው በስድስት ዓይነቶች መድባ ለማየት ችላለች። እነሱም፡-

1ኛ. የሕይወት ዑደት (rites of passage)፣

2ኛ. ዓመታዊና የመታሰቢያ ከበራ (calendrical and commemorative rites)

3ኛ. ማህበረሰቡ ከፈጣሪያቸው ጋር ላላቸው ቀረቤታ (ለሚኒት) ና ላደረገላቸው መልካም ነገር የሚያደርጉት ምላሾች(rites of exchange and communion) የሚመለከት የከበራ ዓይነት፣

4ኛ. በስነ-ልቦናና አካላዊ ከሚደርሱ መከራዎችና ችግሮች ለመውጣት የሚከወኑ ከበራዎች (rites of affliction)፣

5ኛ. የድግስ፣ የአፅዒማትና የክብረ-በዓል ከበራ (rites of feasting, fasting, & festivals)ና

6ኛ. ፖለቲካዊ ከበራ (political rituals) ናቸው ።

ይሁን እንጂ እነዚህ የዣኔሮች ዝርዝር የተሟሉ ናቸው ለማለት አይቻልም፤ ብዙ ተቀባይነት ያላቸው ሌሎችም ከበራዎች በሌላ ምድብ ሊደለደሉ ይችላሉ፡፡ ሌላው ደግሞ ካለው እውነታ ተመርኩዘን ስንገምት ከበራ ከአንድ ቦታ በላይ ሊመደብ እንደሚችል Bell በማከል ታስረዳለች፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የከበራ ዓይነቶች ውስጥ ይህ ጥናት Bell ከከፈለቻቸው ምድቦች በ3ኛ እና 4ኛ ተራ ቁጥር ስር ባሉት ውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡ ምክንያቱም በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ውስጥ አንዱና ዋንኛው ክዋኔ የጉጂ ማህበረሰብ ከፈጣሪው (waaqa) ጋር ያለው ግንኙነትና ለፈጣሪውም የሚያቀርበው ምስጋናና ውዳሴ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቡ ላይ ከሚደርሱና ከደረሱ ስነ-ልቦናዊና አካላዊ ችግሮች፤ ማለትም ከሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ለመውጣት የሚከወኑ ከበራዎች ስላሉ ነው፡፡ ስለዚህ በነዚህ የከበራ ዓይነቶች ላይ በዋናነት በማተኮር ሌሎችንም፦ማለትም ቃሉ ከመንፈሳዊ ድርጊት ተነስቶ ወደ ዓለማዊ ከበራዎች ሊያመራ ስለሚችል፣ በሌላ በኩል ከአውዱ አኳያ ባለዝቅተኛ አውድ ከበራና ባለከፍተኛ አውድ ከበራን የተመለከትኩበት ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡

## 2.1.3.3. የከበራ ባህሪያት

የከበራ ባህሪያት ናቸው ተብለው በተለያዩ ምሁራን የተገለጹ መገለጫዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ክዋኔው ድግግሞሽ ያለው፣ መዋቅራዊ የሆነና በተከታታይ የሚቀርብ ድርጊታዊ ዝግጅት ሲሆን፤ በውስጡም ተምሳሌቶች፣ ድርጊቶች፣ የድግግሞሽ ባህሪያት ያለውና የከበራው መክፈቻና መዝጊያ ስርዓት የተበጀላቸው እንደሆኑ Myerhoff (1977)'ን በመጥቀስ Sims and Stephens, (2005፡95-97) ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል የከበራ ድርጊቶች ቅደም ተከተልን የጠበቁና ቡድናዊ ገፅታ ያላቸው ናቸው (ዝኒ ከማሁ)፡፡

Bell በበኩሏ የከበራን ባህሪያት ስትገልጽ ስርዓት ያለው፣ ባህላዊነት፣ አንዱን ከሌላው የሚለይበት ገደብ የሌለው፣ በህግ የሚመራ፣ ቅዱስ ተምሳሌነት፣ ክዋኔ የሚታይበት እንደሆነ ትገልጻለች (Bell,1997:139-160)፡፡

ከላይ ከተሰነዘሩት አጠቃላይ ባህሪያት እንደምንመለከተው ከበራ የመዋቅራዊነት፣ ቅደም ተከተላዊነት፣ ተደጋጋሚነት፣ ታዳሚ፣ ውጤትና ቅዱሳዊነት ይንፀባረቅበታል፡፡ ስለዚህ እነኚህ ባህሪያት የከበራ መገለጫዎች ናቸው፡፡ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራን የተመለከትን እንደሆነ እነዚህ ባህሪያት ሙሉ ለሙሉ በጥናቱ ውስጥ ታይተዋል፡፡

## 2.1.3.4. የከበራ ፋይዳዎች

አንድ ከበራ በዋል ፈሰስ አይከወንም፤ የራሱ የሆነ ፋይዳ ይኖረዋል። ከበራ ያለው ፋይዳ ማህበራዊ ወይም ግለሰባዊ ሊሆን ይችላል። ይህ የሚያሳየው ማህበራዊ የሆነውን ከበራ ግለሰቦች የሚፈጽሙት ለራሳቸው ግለሰባዊ ፋይዳ ሊሆን መቻሉን ነው። በሌላ አነጋገር እኛም ሆነን ሌሎች የሚያውቁትና የሚረዱት ከበራን እየከወንን መሆናችንን ነው (Myrvold, 2008፡19)። ስለዚህ ከበራዎች ሲጠኑ የሚከወኑበትን ማህበረሰብ ማንነት እና የሚጠናውን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት እንዲቻል የከዋኞቹን ማንነትና የክዋኔውን ምክንያት መረዳት ወሳኝ ነው። ይህም ከበራውን ከነአውዱ በጥልቀት በማጥናት የሚመጣ ይሆናል።

ህዝቦች ደጋግመው የሚከውኑዋቸው የእምነትና የባህላዊ እሴቶች ከበራዎች ናቸው። እነዚህ ከበራዎች ደግሞ ውስጣዊ ልምዶችን ወይም ወጎችን ለባህሉ ባለቤትም ሆነ ለውጭው ታዳሚ ገዝፈው እንዲታዩና እንዲለመዱ ያደርጋሉ (Sims & Stephens, 2005:94)።
Bell, (1997:37) የ Van 'ን ሀሳብ በመጥቀስ የከበራ ተግባር ቡድኖች የሚተዳደሩበት ስርዓት ወይም የሚያራምዱት አመለካከት፣ የሚመሩባቸውን ህግጋት እንዲያከብሩና እንዲጠብቁ የማነሳሻና ማደራጃ ዘዴዎች እንደሆኑ ትገልጻለች።
ከበራዎች ሁልጊዜ የሚከወኑት ታዳሚዎቹን ለማሳመን ነው። ባጠቃላይ ከበራዎች መንፈሳዊ ፍላጎትን ያረካሉ። የከዋኞቹን ማህበራዊ ግንኙነት እንዲሁም የቡድኖችን የማንነት ስሜትና የእርስ በርስ ግንኙነት ያጠናክራሉ። ከበራዎች ግጭቶችን ይፈታሉ። እንዲሁም ወጎችንና እሴቶችን ለመግለፅ ያግዛሉ። ከዚህም በተጨማሪ ለነገሮች ወሰን እንዲበጅ፣ የአብሮነት ስሜት እንዲራመድ ያደርጋሉ (ዝኒ ከማሁ: 24-25)። ከዚህ በመነሳት የማንነት ፖለቲካም ያራምዱበታል። ስለዚህ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች፣ ከተለያዩ አካባቢዎች ተሰባስበው በአንድ ላይ የሚያከብሩት።

ከዚህ ጋር በማያያዝ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ፋይዳዎችን በተመለከተ ከቀረቡት ፅንሰ ሀሳቦች አንጻር የታዩ ሲሆን፣ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በተመረጡት የመተንተኛ ዘዴዎች በተወሰነ ደረጃ ተፈትሸዋል።

ሌላው ስለ ሃይማኖታዊ ክበራ ሲነሳ በዋናነት ከሃይማኖት ጋር ቁርኝት ስላለው ሚትን ማንሳት የግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም ስለ ፍጥረታትና ፈጣሪ ምንነት የሚተርክ ሚት በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ለግንዛቤ ይረዳን ዘንድ ባጭሩ ስለሚት ምንነት እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 2.1.4. ሚት (Myth)

ቃላዊ ዝርው ተረኮች በመባል በዋናነት የሚታወቁት የፎክሎር ቅርጾች ሦስት ዓይነቶች ናቸው፡፡ እነሱም ሚት፣ አፈ-ታሪክና ተረት ናቸው (Bascom, 1965፡5)፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሚት ስለ አማልክትና ስለ ነገሮች አፈጣጠር የሚተርክ፣ በአማኞቹ ዘንድ የተቀደሰ ተብሎ የሚታመንበት ሰነድ ነው (ዝኒ ከማሁ፡ 4)፡፡

ይህንኑ ጉዳይ Oring, (1986፡124) ሲያጠናክረው ሚት እውነትነቱ መረጋገጥ የማይችል፣ ዓለምን ማን ፈጠረው ለሚለው ምላሽ የሚሰጥ፣ የተቀደሰ፣ ስለ ፍጥረታትና ፈጣሪ የሚያወጋ፣ ገጸባህሪያቱ ልዕለሰብ የሆኑ፣ ፍጹም መንፈሳዊነት የሚንጸባረቅበት፣ የሚታመን፣ የመክፈቻና የመዝጊያ ስርዓት የሌለው ወይም ያልተወሰነ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

እንደ ቴዎድሮስ (2001:xii) ገለጻ ደግሞ “ሚት የሰው ልጅ የነገረ ፍጥረትና የነገረ ህላዌ እንቆቅልሾችን ለመመለስ የሞከረበት፣ እየተመሰቃቀለ ለሚያስቸግረው ዓለም ህልው ሥርዓት ለማበጀት የባተለበት እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው፡፡ ሚት የማኅበረሰቡ የእሴት ስርዓትም ነው” ይላል፡፡
ከጥቅሶቹ ለመረዳት እንደሚቻለው ሚት የአማልክትና አምላክ አከል የሆኑ ልዕለ ተፈጥሮ ኃይላትን የያዘ፣ ስለ ፍጥረት አመጣጥና ስለ ተፈጥሯዊ ልዩ ልዩ ክስተቶች የሚያትት የሰው ልጅ ህልውና የተመሰረተበት እንደሆነ ነው፡፡

ሌላው ስለሚት መነሳት ያለበት፤ ሚት ከድሮ ጀምሮ ያለ መንፈሳዊ ተረክ (sacred narrative) ነው፡፡ ፎክሎረኛ ባልሆኑ ሰዎች ዘንድ ሚት ማለት ልክ እንደ ሞኝነት ወይም ውሸት ነገር እንደሆነ ይረዱታል፡፡ ነገር ግን ፎክሎረኞች የዚህን ቃል ትርጉም የሚረዱት በዚህ መልኩ አይደለም፡፡ ሚት ሰዎች ስለነገሮች አመጣጥ (አጀማመር) የሚናገሩት የፎክሎር ዘውግ ነው፡፡ ዘወትር ከሰዎች ሃይማኖት ጋር ይያያዛል፣ ከክበራና ዝግጅት (ሰሪሞን) ጋር ይጣመራል፡፡ ስለ መሬትና አጠቃላይ ነገሮች አፈጣጠር ያስረዳናል፡፡ ነገሮች ለምን ባሉበት መንገድ ሆኑ ለሚለው ማብራሪያ ይሰጣል (Schoemaker,1990፡237)፡፡

በሌላ በኩል በሚተረኩ ሚቶች ላይ ተንተርሰን የዚያን ቡድን ፖለቲካዊ ፍላጎት ማጥናት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ስለቃሉ ስርዓትና ሃይማኖታዊ ከበራዎች መረጃ ማግኘት የሚቻለው ከማህበረሰቡ ሚት ስለሆነ፤ የጉጂ ኦሮሞ ሚቶች በተወሰነ ደረጃ ተዳሷል፡፡ ምክንቱም ለተሰበሰበው መረጃዎችም ሆነ ለሚተነተኑበት ዘዴዎች አቅጣጫ የሚያመላክት በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው ስለሃይማኖታዊ ከበራዎች ጥናት የሚያካሂድ ተመራማሪ በከበራዎች ላይ ከሚተረኩ ሚቶች በተጨማሪ የሚከወኑባቸውን ቁሳዊ ባህሎች ሳያማክል ትንታኔ ማካሄድ አይታሰብም፤ ቢሞከርም እንኳን ትንታኔውን የተሟላ አያደርገውም፡፡ ስለዚህ በከበራዎቹ ላይ የቀርቡትን ቁሳዊ ባህሎች ምንነትና ተምሳሌትነታቸውን መመልከት ሰላስፈለገ ፅንሰ-ሀሳቦቹን እንደሚከተለው ለማየት ተችሏል፡፡

### 2.1.5. ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል ማለት ከአራቱ የፎክሎር ጥናት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ፈቃደ፣ (1991፡15) Dorson'ን በመጥቀስ በዚህ ዘርፍ ስር ሀገረሰባዊ እጅስራ፣ ሀገረሰባዊ ስዕል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰባዊ ልብስና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራርን የመሳሰሉ እንደሚጠኑ ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ቁሳዊ ባህል ሲባል ሰዎች በአካባቢያቸው ለማህበራዊ ግልጋሎት የሚጠቀሙበት፣ ለማህበረሰቡ ተምሳሌታዊ ፍች ያላቸው ዕቃዎች ናቸው (Woodword, 2007፡3)፡፡ ስለዚህ በቁሳዊ ባህል አማካኝነት የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ልናጠና እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ቁሳዊ ባህል በአንድ በተወሰነ ጊዜ የነበረን ማህበረሰብ እምነት፣ እሴት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብና እውቀትን ከእደ ጥበባቸው አንጻር የሚያጠና በመሆኑ ነው (Prown, 1982፡1)፡፡ ስለዚህ ባህላዊ ቁሶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያስተላልፉት መልእክት አሏቸው (Danesi, 2004፡33)፡፡

በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ በሃይማኖቱ መሪዎቹም ሆነ፣ በታዳሚዎቹ የሚለበሱ ሀገረሰባዊ አልባሳት፣ በዝግጅቱ ላይ የሚቀርቡ ባህላዊ ምግቦችና የመሳሰሉት ከተመለከትን ቁሳዊ ባህሉን እንድንቃኝ ያስገድዱናል፡፡ ምክንያቱም በከበራው ላይ የሚቀርቡት አልባሳትም ሆኑ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች ከወትሮው ዕለት የተለዩና የማህበረሰቡ የማንነት መገለጫ ስለሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን የፎክሎር ዘርፎች ከከበራው ለይቶ ማውጣት ያስቸግራል፡፡
ሃይማኖታዊ ተቋማትና ተያያዥነት ያላቸው ቁሳዊ ባህሎች ሲጠኑ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው በ Oring, (1986፡44) ውስጥ Danielson እንደሚለው፡- በቅድሚያ ቁሶቹን የሃይማኖቱ ባለቤት

ምን ይላቸዋል? እንዴትስ ይገለገልባቸዋል? የሚሉትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር ወደ ፎክሎራዊ ገጽታቸው መምጣቱ የተሻለ መሆኑን ይገልጻል።

ሌላው ቁሶችን ከሃይማኖታዊ ክበራው ጋር ለማጥናት የተፈለገበት ምክንያት ቁሶቹ ለማህበረሰቡ ከዕለት ተዕለት ግልጋሎታቸው ባሻገር ሰፊ ትርጉም አላቸው። ይኸውም ቁሶችን የዚያን ማህበረሰብ እሴቶች፣ አመለካከቶችና ፍላጎቶች እንዲሁም የዘመኑን መንፈስና የማህበረሰቡን የህይወት ልምድ ያንጸባርቃሉ (Jones, 2000፡9)። Glassie, (1999፡143) ይህንን ጉዳይ በምሳሌ ሲያስረዳ የእርሻ መሳሪያዎችን በማጥናት ስለ አራሾቹ፣ የአደን መሳሪያዎቹን በመመርመር ስለ አዳኞቹ ወይም የእምነት ተቋማትን በመመርመር የአማኞቹን የህይወት አተያይና እሴቶች መረዳት እንደሚያስችል ይገልጻል።

አንድ ሃይማኖታዊ ክበራ በሚከወንበት ወቅት እንደየእምነቱና ባህሉ ለየክበራው ማስፈጸሚያ፣ አሊያም ማጀቢያ የሚውሉ የተለያዩ ቁሳ ቁሶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ምግቦችና መጠጦች፣ አልባሳትና የመገልገያ ቁሳቁስ በዋናነት ይጠቀሳሉ። አብዛኛውን ጊዜ የነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ስያሜና አገልግሎቱ ከወትሮው በተለየ መልኩ ነው። ለአብነት ያህል ብንመለከት አንድ በቤታችን የምንጠቀመው ውሃ እና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ክበራ የሚጠቀሙት ጠበል (holy water) የተለያዩ ናቸው። ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ ጠበሉ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የተቀደሰ ነው ብለው ስለሚያምኑ ከተለያዩ ደዌዎች የመፈወስ ኃይል አለው ተብሎ ይታመናል። በሌላ በኩል ለእምነቱም ክበራ እንደመገለጫነትም ያገለግላል። ባጠቃላይ ለተለያዩ ግልጋሎት የሚውሉ ቁሳዊ ባህሎች ከመገልገያነታቸው ባለፈ የተጠቃሚውን ማንነትም የመግለጽ አቅም እንዳላቸው Danesi, (2004፡182) ያስረዳል። ስለዚህ በቃሉ ሃይማኖታዊ ክበራ ላይ የሚታዩ ከአባቃሉና የመማክር አባላቱ አልባሳት፣ በክበራው ላይ የሚቀርቡ ምግቦች፣ የክበራ ማስፈጸሚያ ቁሶችና የመሳሰሉት ሁሉ የየራሳቸው ተምሳሌትና ትርጉም አላቸው። ምክንያቱም ተምሳሌት አንድን ቁሳዊ አካል ሞራላዊና መንፈሳዊ እውነትን ወክሎ እንዲቆም በማድረጉ ነው (Ballenger,1998፡769)።

ስለዚህ የአንድን ሃይማኖታዊ ክበራ ምንነትና ፋይዳ መርምሮ ለመግለፅ የሚቻለው የክዋኔውንም ሆነ የቁሳዊ ባህሉን ትርጉም (ፍች) ስናገኝ ነው። ፍቹን ለማግኘት ደግሞ የቀረበው ቴክስት ምንድነው?፣ የቀረበበት አውድስ ምን ይመስላል? የሚሉትንና በክዋኔው ላይ

የቀረበው የቴክስቱ አገላለጽ ለዛ ምን ይመስላል? የሚሉትን በመተንተን የሚገኝ ነው። ስለዚህ የነዚህን ፅንሰ-ሀሳቦች ምንነት እንደሚከተለው ማየት ያስፈልጋል።

## 2.1.6. ስነ-ፍችና አውድ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የአንድን ፎክሎር መልዕክት ለመረዳት የቀረበውን ቴክስት፣ በምን ዓይነት የአነጋገር ለዛ እንደተገለጸና በምን ዓይነት አውድ ላይ እንደተከወነ መረዳት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የነዚህን ፅንሰ-ሀሳቦች ምንነትና ባህሪያቸውን ማወቁ የመጀመሪያ ጉዳይ ይሆናል። ስለዚህ በዚህ ርዕስ ስር እያንዳንዱን ጉዳዮች በዝርዝር እንመለከታለን።

### 2.1.6.1. ስነ-ፍች

ስነ-ፍች (semantics) ማለት በቋንቋ ውስጥ የፍቾች ፍልስፍናዊ ወይም ስነ-ልሳናዊ ጥናት ነው። የማንኛውም አገላለጽ በስነ-ፍች አስተሳሰብ ፍቾቹ ከቅርጻቸው ተቃራኒ እንደሆኑ Baldick (2001፡232) ይገልጻል።

የፎክሎርን ትርጉም የተሟላ ለማድረግ ሦስት የትንተና ዓይነቶች (ደረጃዎችን) እንዳሉ፣ እነሱም፡- ቴክስት (Text)፣ አውድ (context) እና የአቀራረብ ለዛ (Texture) እንደሆኑ Dundas, (1980) ይገልጻል። አንድን የፎክሎር ዓይነት ወይም ዘውግ (gener) በእነዚህ በሦስቱ ላይ ትንተና በማድረግ ለፎክሎሩ የተሟላ ትርጉም መስጠት ይቻላል።

በአብዛኛው የፎከሎር ዘውጎች በተለይም በቃላዊ የፎከሎር ዓይነቶች ውስጥ የአቀራረብ ለዛ (Texture) ቋንቋ ነክ ነው። ለዚህም ምክንያቱ የድምጽ (phoneme) እና የምዕላድ (morpheme) ጉዳይ ትኩረት ስለሚያገኝ ነው። በቃላዊ ፎክሎር ውስጥ ያለው ለዛ የሚከወነው ቴክስት ውበትን እንዲጎናጽፍ የሚያደርግ ነው ማለት ይቻላል።

Schoemaker, (1990፣37) እነካቲሪንግ እና ጀኒፈርን በመጥቀስ በንግግር ወቅት በአንድ ጊዜ በሦስት ደረጃዎች በመታገዝ እንደምንግባባ ይገልጻል። ይኸውም፡- ስነ-ልሳን (lingustic) ማለትም፡- ቃላትን፣ ንበትንና ሰዋሰውን ሲያካትት፣ ፓራሊንጉስቲክ (paralingustic) ደግሞ የድምጽ አወጣጥ ቅላጼያችን፣ የድምጽ ከፍና ዝቅ ማድረግና የንግግራችንን ፍጥነት ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ ካይነስክስ (kinesics) ሲሆን፡- የፊት ገፅታ መቀያየርና ምልክቶችን (በአካላዊ እንቅስቃሴዎች) በመታገዝ መልዕክት ማስተላለፍ ናቸው።

ይህንን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ እነ Sims M. & Stephens M., 2005,134). ሲገልጹ፡-

> *Folklorists pay attention to the performed act of expressive, artistic communication, the when, where, with whom, how, and why people communicate with each other. In addition to actual content, words, or actions (texts), folklorists consider literary, linguistic or physical nuances of those texts (texture); and they study these elements within specific groups and settings (contexts).*

በማለት እንደ አንድ ፎክሎርኛ ትኩረት መስጠት ያለበትን በንግግር ወቅት ከማን ጋር፣ ምን አይነት ርእሰ ጉዳይ፣ መቼ፣ እንዴት፣ ለምን ሰዎች እርስ በርስ ይግባባሉ? በማለት የንግግራችንን ዘዴ የምናቀናጀው ከሁኔታዎች ጋር ነው። በተለያዩ አውዶችና መቼቶች የተሳካ ንግግር ለማድረግ እንደየሁነቱ የተለያየ የንግግር ዘዴዎችን እንጠቀማለን። በተጨማሪ በቋንቋችን በትክክል ለመጠቀም በቋንቋው ውስጥ ያሉትን ቃላት በበቂ ሁኔታ መረዳትና ሰዋሰዋዊ ህጎችን ጠንቅቀን ማወቅና መጠቀም ይጠበቅብናል።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአቀራረብ ለዛ (Texture) ሙሉ በሙሉ ከቋንቋ ጋር የተያያዘ ብቻሳይሆን በሰውነት እንቅስቃሴም ታግዞ የሚከወነው ቴክስት ውብት ባለው ሁኔታ መልዕክቱን እንዲያስተላልፍ ማድረግ ነው።

ስለዚህ አንድ በቃል፣ በምልክት ወይም በድርጊት ያለ የፎክሎር ዘውግ ቴክስት ይባላል። በውስጡ ያዘለውን ስሜት፣ ጥበብ፣ መልዕክትና የመሳሰሉትን ደግሞ የአነጋገርለዛ (texture) ይባላሉ። ከዚያ በአንድ የተወሰነ አውድ (context) ሲተረክ ወይም ሲከወን በጥምረት የሚያስተላልፉት መልዕክት ደግሞ ፍች ይባላል። ይህም መልዕክት ወይም ፍች አንድም ቀጥተኛ ፍች፣ አሊያም ተጓዳኝ ፍችን ይመለከታል።

በመሰረቱ ፍች ማለት በመዝገበ-ቃላት ፍችው ቃል ወይም ቃላት ስለአንድ ነገር፣ ድርጊት፣ ስሜት፣ ሀሳብ፣ ወዘተ... በመወከል የሚያስተላልፉት መልዕክት ነው (Shovel, 2007፡933)። ፍችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መድበን ማየት እንችላለን። አንደኛው እማሬያዊ ፍች (literal meaning) ሲሆን፣ ቃሉ ወይም ቃላቱ የያዙት መሰረታዊው ቀጥተኛ ፍችን ይመለከታል።

ሁለተኛው ደግሞ ፍካሬያዊ ፍች (contextual meaning) ማለትም ቃሉ ወይም ቃላቱ የያዙት ቀጥተኛ ፍች ሳይሆን አውዳዊ ፍች ነው፡፡

ሌላው ስለ ፍች ስናነሳ ቃላት ከአገባባቸው አኳያ የተለያየ ፍች ይኖራቸዋል፡፡ እነሱም፡- አቻ ፍች፣ ሆሞኒየም (Homonymy)፣ ተቃራኒ ፍች፣ የጥምረት ፍች (Hyponymy)፣ ፍች-ብዙነት (polysemy)፣ ተዛማጅ ፍች (metonymy)፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች (idioms) እና ዘይቤያዊ አነጋገሮች (metaphor) እንደሆኑ Danesi, (2004፡66፣118) ይገልጻል፡፡ ስለዚህ እነዚህን አውቀን ትርጉሙን ለመረዳት የማህበረሰቡን ቋንቋና ባህል ማወቁ ግድ ይላል፡፡

ፎክሎረኞች በትንተና ሂደት በፎክሎር ቴክስት፣ ክዋኔና አውድ መካከልና በጋራ ያላቸውን ግንኙነት ለመረዳት እንደሚችሉ Sims & Stephens, (2005:28) ያስረዳሉ፡፡ ይህ ማለት አንድ የፎክሎር ቅንጣት ወይም ቴክስት ሲከወን አንድም በቃል ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በድርጊት ነው፡፡ ክዋኔ ካለ የሚከወንበት አውድ አይቀሬ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ሂደት ውስጥ የአነጋገር ለዛው የትርጉም ለውጥ ሊያመጣ ይችላል፡፡

### 2.1.6.2. አውድ

ለአውድ በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ተሰጥተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ Dundes (1994) አውድን አንድ ድርጊት የሚከወንበት ጊዜና ቦታ እንደሆነ በአጭሩ የገለጸው ይገኛል፡፡ ስለዚህ የአንድ ፎክ ቡድን አባላት ፎክሎርን የሚጋሩበት አካላዊ መቼቶችና ማህበራዊ ሁነቶች እንዲሁም የታዳሚዎችና ከዋኞች ግንኙነት አውድን ይመሰርታሉ፡፡ በመሆኑም አውድ የሚያመለክተው በቴክስትና ክዋኔ ዙሪያ የሚገኙ ማንኛውንም ክዋኔ፣ እውነታ፣ ቁሳቁስ፣ ሁነቶችና ክስተቶችን ጭምር ነው (Sims & Stephens, 2005:138)፡፡ የተለያዩ የአውድ ዓይነቶች አሉ፡፡ እነዚህን ለይቶ ማወቁ ለሚካሄደው ፎክሎራዊ ትንታኔ ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ የአውድ ዓይነቶች መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

የአውድ ዓይነቶች በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ሁኔታዊና ባህላዊ አውዶች ይባላሉ፡፡ ሁኔታዊ አውድ የሚባለው የሚከወነው ጉዳይ የሚቀርብበትን ማህበራዊ ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ ባህላዊ አውድ ደግሞ በውስጡ የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚቀርብበት ሰፊ ገጽታ ሲሆን፤ ክዋኔው በውስጡ የሚወክላቸውን ነገሮች፣ የሚከወነው ጉዳይ፣ የሚመራበት ማህበራዊ ደንብ፣ የተሳታፊዎች የእምነት ስርዓት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና የንግግር ስልት፣ የከዋኙ የታሪክ ዕውቀትና የስነ-ምግባር ህግጋትን ሁሉ ያጠቃልላል (Ben-Amos, 1993፡216)፡፡

ከስነ-ዘዴ አኳያ የፎክሎር ቅርጾችን በአውዳዊ ትንተና ዘዴ ለመተንተን የተለያዩ ዕቅዶች አሉ፡፡ አንድ ፎክሎረኛ ከመስክ የሚያገኘውን መረጃ ሲያደራጅ አውድን በተመለከተ ሊያተኩርባቸው የሚገባ ስድስት ነጥቦች እንዳሉ Bauman ያስረዳል፡፡ እነሱም፡- ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድና ሁኔታዊ አውድ ይባላሉ (Bauman, 1983፡367)፡፡ እነዚህን የአውድ ክፍሎች እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው በዝርዝር እንመልከት፡፡ እነሱም፡-

i. **ፍቻዊ አውድ**፡- የዚህ አውድ ትኩረት የሚያጠነጥነው ፎክሎራዊ ጉዳዩ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? የሚለውን ጥያቄ ከመመለስ ላይ ነው፡፡

ii. **ተቋማዊ አውድ**፡- ይህ ደግሞ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው፡፡

iii. **የተግባቦት ሂደት አውድ**፡- የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ቅርጽ ምንነት፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድናና አንዱ ከሌላው ለመለየት ማህበረሰቡ የሚጠቀሙበት ዘዴንም ያካትታል፡፡

iv. **ማህበራዊ መሰረት**፡- የፎክሎር ማህበራዊ መሰረት በመካከላቸው ዝምድና ባላቸው ቡድኖች መካከል የሚታይ ዋነኛው የአውድ መገለጫ ገጽታ ነው፡፡

v. **ግለሰባዊ አውድ**፡- ፎክሎር ግለሰቦችም ስሜታቸውንና ሀሳባቸውን የሚገልጹበት ጥበብ ነው፡፡

vi. **ሁኔታዊ አውድ**፡- ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዩን የሚከውነው በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? ሁኔታዊ አውድ ሲባል በባህሉ የተወሰነ የአንድ ባህሪ ወይም ገጠመኝ መግለጫ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት የሚከናወንበት አውድ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በእነዚህ የአውድ ዓይነቶች በመታገዝ የቃሉ ከበራዎች ከአውድ አኳያ ያላቸውን ፍች ተተንትነውበታል፡፡

## 2.1. የንድፈ-ሀሳብ ቅኝት

በፎክሎር ጥናት መረጃዎችን ከመሰብሰብ እስከ መጨረሻው የጥናቱ ውጤት ማጠናቀሪያ ድረስ በተለያዩ ሂደቶች ውስጥ ያልፋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ በፎክሎር የመስክ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች በሁለት ደረጃዎች ይገለጻሉ፡፡ ይኸውም፡- መረጃዎችን መለየትና መተርጎም እንደሆኑ Dundes, (1980:211) ይገልጻል::

ስለዚህ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ዙሪያ ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመጀመሪያ ደረጃ ካላቸው የድርጊቶች የእርስ በርስ ቅርበትና ቅደም ተከተላዊ ሂደታቸው ላይ በመመስረት ተለይተዋል፡፡ ከዚያ በመቀጠል ለእያንዳንዳቸው ትንታኔ ለመስጠት አመቺ ናቸው ተብለው የተመረጡና በስራ ላይ የዋሉ ንድፈ-ሀሳቦች ተለይተው ተገልጸዋል፡፡ እነሱም፡- የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን (Social Construction) እና ተምሳሌታዊ አተረጓገም (symbolic Interpretive) ንድፈ-ሀሳቦችን በዋናነት የጥናቱ ማቀንቀኛ ሲሆኑ፤ አውዳዊ፣ ፋይዳዊና ክልላዊ (hemispheric)[2] ንድፈ-ሀሳቦች ደግሞ እንደ አጋዥ ማስተንተኛ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በጥናቱ ውስጥ የእያንዳንዱ ንድፈ-ሀሳብ ሚና ምን ምን እንደሆነ ከዚህ በታች በዝርዝር ለማየት ተችሏል፡፡

### 2.1.1. የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ

አንድ ማህበረሰብ በሚኖርበት ዓለም ያሉትን ነገሮች የሚያውቅበትና ትርጉም የሚሰጥበት፣ ከዚያም አልፈው ተቋማትን መስርተው በእነሱ ተመልሰው የሚተዳደሩበት ህግና ደንብን ይመሰርታሉ፤ ይገዙለታልም፡፡ ይህ ዕውቀት ከየት መነጨ ሲባል ምሁራን የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የዕውቀት አዋቃሪያን አንደኛው ነው፡፡ በዕውቀት አዋቃሪን ስር የሚነሳው ንድፈ-ሀሳብ የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ነው፡፡ይህ ንድፈ ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ገኖ የወጣው እ.አ.አ. በ1966 በእነ *Berger,P. & Luckman T.* ካሳተሙት *"The Social Construction of Reality"* ከሚል መጽሐፋቸው በኋላ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

የዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ ማህበረሰቡ ከሚያከናውናቸው የዕለት ተዕለት ተግባራት በሂደት ልማድን እየፈጠሩ፤ በመቀጠል ተቋማትን እየገነቡ ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ ለተቋማቱ ቅደም ተከተላዊ ተግባራትን በመጀመሪያ ደረጃ ያዋቅራሉ የሚል እሳቤ አላቸው፡፡ ይህ የጋራ ዕውቀትም እያንዳንዱ ሰው በተናጠል ካለው ዕውቀት ተጠራቅሞ የተገነባ እንደሆነ Berger & Luckman, (1966:83) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> The primary knowledge about the institutional order is knowledge on the pretheoretical level. It is the sum total 'what everybody knows' about a social world, an assemblage of maxims, morals, proverbial nuggets of wisdom, values & beliefs', myth, and so forth....

[2]የእነዚህ ንድፈ-ሀሳቦች አቻ ትርጉም በትምህርት ክፍሉ የተለመዱና ቀደም ካሉ የፒ.ኤች.ዲ ድሰርቴሽን የተገኙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ከዚህ ንድፈ-ሀሳብ አተያይ ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማህበራዊ ውቅር ነው። ንድፈ-ሀሳቡ ማህበረሰቡ በጋራ ያዋቀሩት ዕውቀት በግለሰብ ደረጃም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ በእኩል የሚሰራ ድንጋጌ እንደሆነ ይገልጻሉ። ግለሰቦች ማህበረሰቡ ባኖሯቸው ድንጋጌዎች ይገለገላሉ፤ ይመራሉ፤ ይቀጣሉ። ንድፈ-ሀሳቡ ዕውቀቱ በሂደት ባዋቀሯቸው የጋራ ጉዳዮች ውስጥ በግለሰብ ደረጃና በማህበረሰብ ደረጃ ትርጉም አዘል ሆኖ ሊሰራ እንደሚችል ያወሳል። ሆኖም በግለሰብ ደረጃ ያለው ዕውቀት ከግለሰብ ግለሰብ ሲለያይ፤ ተቋማትም ባላቸው ሚናና አግባብነት ያለው የግንኙነት ህግ የተነሳ በየደረጃው ይለያያሉ (ibid)።

ብዙን ጊዜ ሰዎች በዓይናቸው ፊት ለፊት ስላላዩትም ሆነ በቀጥታ ልምዱ ስለሌላቸው ነገሮች ሲናገሩ ይደመጣሉ። በዚህ በኩል ቋንቋ ነገሩ በምን ዓይነት መጠን ፍችና ልምድ እንዳለ በወቅቱ የመግለጽና ለተተኪው ትውልድም የማስተላለፍ አቅም አለው (ibid፡ 52)። በተለይም ስለቃሉ አመጣጥና ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ሁኔታ የጉጂ ኦሮሞ በሚቶቻቸው በዚሁ መልክ ሲገልጹ ኖረዋል፤ እየገለጹበትም ነው። የማህበረሰብ ዕውቀት በማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ እያደገ የሚሄድ፣ የሚተላለፍና ማስተካከያ ሊደረግበት የሚችል ነው (Berger and Luckmann;1966:15)።

የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ፋይዳዎች በምናይበት ወቅት መቅደም የሚገባው ይህንን ማህበረሰባዊ ዕውቀት እንዴት አወቁት? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል። ይህን ጥያቄ ለመመለስ ቀደም ሲል አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ዕውቀት እንዴት ሊያውቁ እንደሚችሉ በ3.1. ውስጥ ስናነሳ አንደኛው በዕውቀት አዋቃሪያን መንገድ እንደሆነ ለማየት ችለናል። ስለዚህ ይህ የማህበረሰብ የዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ በመጠቀም የጉጂ ኦሮሞ ቃሉን፣ የቃሉ ተቋምን፣ የቃሉ መማክርት እነማን መሆን እንዳለባቸው፣ ተግባራቸውም ምን ምን መሆን እዳለበት፣ ሃይማኖታዊ ህጎቹ ምን ምን እንደሆኑና በህጉም እንዴት እንደሚመሩበት ያዋቀሩትንና ለህጉም እንደሚገዙና እንዴት እየተገበሩ እንደሆነ ተተንትኖበታል።

### 2.1.2. ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳብ (symbolic Interpretive)

ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳብ ጠንሳሽ George Mead ሲሆን በመቀጠል በ Herbert Blumer የዳበር የንድፈ-ሀሳብ አካል እንደሆነና ጥናትም በእነሱ ስራ እንደጀመረ ይነገራል።

*‹‹ Symbolic interactionism emphasises the construction of the social world and meaning through the human use of symbols in communication, most importantly language.››* (Burr, 2003:205).

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ይህ ንድፈ-ሀሳብ አጽንኦት የሚሰጠው ሰዎች ስለማህበረሰባዊ ዓለምና ፍችያቸው በተግባቦት ወቅት ተምሳሌቶችን፣ በአብዛኛው ቋንቋን በመጠቀም እንደሚያዋቅሩ ነው፡፡

ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳብ በቀጥታ የሚያወሳቸው ጉዳዩች እንደ ቋንቋ፣ ተግባቦትና በመካከላቸው ያሉ ግንኙነቶችንና ማህበረሰቡን ነው (Crotty, 1998:7-8)፡፡
ተምሳሌት ደግሞ በወካይና በተወካይ መካከል ያለውን ዝምድና ለመግለጽ ያገለግላል፡፡ መገለጫውም በቋንቋ፣ በቁሳቁስና በክዋኔ ሆኖ በውስጡም በርካታ ትርጉሞችን ይይዛል፡፡ ተምሳሌት እንደየባህሉ የተለያዩ ትርጓሜዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ለአንድ ማህበረሰብ ተምሳሌት የሆነው ለሌላው ላይሆን እንደሚችል Dundes, (1989:112-114) ያስረዳል፡፡ እንደ Bronner, (2007:63)፡፡ ገለጻ የአንድ ባህል ተምሳሌታዊነት የሚገለጸው ፎክሎሩ በተገለጸበት በዚያው ባህል ውስጥ ነው፡፡

መንፈሳዊ ተምሳሌትን የተመለከትን እንደሆነ ከሌሎች ለየት የሚያደርገው የራሱ የሆነ ባህሪይ አለው፡፡ እነ Sosis, R., የ Douglas (1966) ሀሳብ በመጥቀስ ስለመንፈሳዊ ተምሳሌት ሲያስረዱ፡- መንፈሳዊ ተምሳሌት የተለየ እእምሯዊ የአቀባበል ሂደት ያለው ነው፤ ነገር ግን አንድ ሰው የቅዱስነቱን ፍች የሚያገኘው በሚታየው ስሜት ውስጥ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ሃይማኖታዊ ተምሳሌቶች የሚፈጠሩት ከረቂቅ ነገሮች ሲሆን፤ እነዚህን ቁሶች የሚቀርቡት በአክብሮትና በመንቀጥቀጥ ስሜት ("awe")፣ ንጽህናን ("purity") እና አደገኛነትን ("danger") በማላበስ ይሆናል፡፡ እነዚህ በማንኛውም ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ የሚታዩ ወሳኝ ገጽታቸው ናቸው (Sosis, R., and C. S. Alcorta, 2005:332)፡፡
ከዚህ በተጨማሪ Turner, (1967:19) በመስክ ቆይታው ከተገነዘባቸው ውስጥ በዓይነታቸው ቁሶች፣ ክዋኔዎች፣ የማህበራዊ ግንኙነቶች፣ ክስተቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችና የከበራ ስፍራዎች ተምሳሌታዊ ፋይዳ እንዳላቸው እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡ *‹‹The symbols I observed in the field were, empirically, objects, activities, relationships, events, gestures, and spatial units in a ritual situation. ››*

ሌላው ተምሳሌት በቀለማት፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ፣ በቁሶች፣ በተለያዩ የፊት ገጽታዎችና የመሳሰሉት እንደሚገኙ Danesi, (2004:4) ይገልጻል።

በቃሉ ሃይማኖታዊ ክበራዎች ላይ የሚቀርቡ ቁሳዊ ባህሎች፣ ክዋኔዎች፣ አከዋወናቸው፣ የማህበራዊ ግንኙነቶች ደረጃዎችና የመሳሰሉት የሚያስተላልፉት መልዕክት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚወክሉት ነገሮች አሏቸው። ታዲያ እነዚህንና የመሳሰሉት ተምሳሌቶች ፍች በሦስት መንገድ ማግኘት ይቻላል። ይኸውም፦ 1) የክበራ ተሳታፊ መረጃ አቀባዮችን በመጠየቅ፣ 2) የክበራው ድርጊት ሲከወን በመመልከት በተምሳሌቱ የሚገለፀውን ድርጊት በመተንተን ፍችውን ማወቅ እና 3) ከሌሎች ተምሳሌቶች ጋር ባለው ግንኙነት የተደበቀ ፍችውን ማግኘት ናቸው (Turner, 1967:50-52)

ከዚህ በተጨማሪ Conner, (1996:8) የተምሳሌት ዓይነቶችን በስምንት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ እንደሚቻል ያስረዳል። እነሱም፦ ‹‹(1) Symbolic Objects (Human, Man made, Mineral, Objects in the Sky, Superhuman Objects, Vegetable), (2) Creatures, (3) Actions, (4) Numbers, (5) Names, (6) Colors, (7) Directions & (8) Places›› ተብለው ይጠራሉ)። እነዚህ ቀደም ሲል የተዘረዘሩት እያንዳንዳቸው በውስጣቸው ብዛት ያላቸውን ተምሳሌቶች አቅፈዋል።

በመሰረቱ ተምሳሌታዊ አተረጓገም እንደሰዎች ስለእኛ እና በመካከላችን የሚኖረውን ማንነቶች የምንገነባው በዕለት ተዕለት በምናደርገው ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ነው። በግለሰብም ሆነ ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ ያለው የዕውቀት ስርጭቱ እንዲጣጣም፣ ሽግግርም እንዲኖረው ቋንቋና ተምሳሌቶች ያሏቸው ድርሻ ትልቅ ነው። ሁለቱ እርስ በርስ ያላቸውም ትስስር ጥብቅ ነው። ይህን አስመልክቶ እነ Berger & Luckman, (1966:55) እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> *Language is capable not only of constructing symbols that are highly abstracted from everyday life experience, but also of 'bringing back' these symbols and presenting them as objectively real elements in everyday life.*

በእነርሱ አገላለጽ ተምሳሌት በቋንቋ ይፈጠራሉ፤ ይገለፃሉም። እነዚያ የተፈጠሩት ተምሳሌቶችም ከትውልድ ወደ ትውልድ ከሚሸጋገሩበት መንገድ አንዱ በቋንቋ እንደሆነ ነው።

ተምሳሌታዊ ሚና አለው ወይም አገኘ ማለት ፍች አዘል እንደማለት ነው። ይህ ፍች የተባለው በተምሳሌታዊ ነገሩ ውስጥ የታቀፈውና ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጠው ዕውቀት ነው። ከዚህም በላይ በተምሳሌታዊነቱና በፍችው ዝምድና ላይ አንዳች የሚቀርብ ምክንያት መኖሩ ስለማይቀር ያለውን ዕውቀት ተጨባጭ ያደርገዋል።

ስለዚህ የቃሉ ከበራን አስመልክቶ ከተሰበሰቡ መረጃዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ተምሳሌነትና የሚሰጡትን ግልጋሎት በዚህ ንድፈ-ሀሳብ ተቃኝተዋል። ለአብነት ያህል በጎንደሮ ከበራ ላይ ስለሚታረደው በግ መልክ፣ ስለሚጋረደው ነጠላ፣ የደሙ፣ የጠጁና የውሃው ተምሳሌታዊ ፍች፣ ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች ማለትም፡- ገዳዩ በጎንደሮ ከበራ ለመጀመሪያ ጊዜ ጀርባውን ዞሮ መሄድና የመሳሰሉት በዚህ ንድፈ-ሀሳብ ትንታኔ ተደርጎባቸዋል። ባጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቀሪያን ንድፈ-ሀሳብ በተጨማሪ ተምሳሌታዊ አተናተን በዋናነት መተንተኛ ሆኖ ቀርቧል።

## 2.1.3. አውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ

በዘመናዊ አጠቃቀም አውድ ማለት በስፋት ሲታይ ስለ አንድ ድርጊት ክንውን የሚገልጽ ሲሆን፤ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ደግሞ ንድፈ-ሀሳቦችንና ዘዴዎችን ይመለከታል (Ben Amos, 2006)። ከመስክ የሚገኘውን መረጃ የሚተነትንበት መንገድ በዋናነት አውዳዊ የትንተና ዘዴ ነው። ከተፈጥሯዊ መቼት የተሰበሰበ ክዋኔን ማዕከል ያደረጉ መረጃዎች የሚተነተንበት አተያይ ነው። በሌላ በኩል አካላዊ ነገሮች ማለትም በክዋኔ ወቅት እንደ የአካል እንቅስቃሴ፣ የፊት ገፅታ መለዋወጥ፣ የድምፅ መቀያየርና ዜማን የመሳሰሉት በራሳቸው የአውድ ክፍል ናቸው (Sims & Stephens,2005:138)።

አውዳዊ ትንታኔ የቡድኑን አባላት እይታ በፎክሎር ትንታኔ አቅጣጫ የሚታይበት ነው። ምክንያቱም የባህል ትርጉም የሚገኘው አውድን መሰረት ባደረገ መልኩ ትንታኔ ሲካሄድ በመሆኑ ነው (ibid: 26)። ከዚህ በተጨማሪ በቃሉ ተቋም የሚከወነው ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለታዳሚው የሚያስተላልፉት መልዕክት አላቸው። ስለዚህ አውዳዊ ትንተና በመጠቀም መረጃዎቹን በመተንተን መልዕክቱን መረዳት ያስችላል።

በአጠቃላይ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የአውድ ግንዛቤ ያለውንና የታየውን መረጃ መግለጽ ብቻ ሳይሆን ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን አካቶ መተርጎምንና መተንተንን የሚያካትት መሆኑን

Ben-Amos, (1993፡210-211) ያስረዳል፡፡ ስለዚህ በ 2.1.6.2. ስር የተዘረዘሩት የ Bauman የአውድ ዓይነቶች እንደ መረጃው ዓይነት በስራ ላይ ውለዋል፡፡ ይኸውም በጎንዶሮ ከበራ ውስጥ የሚከወኑት እያንዳንዱ ድርጊት ምን ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ በፍቻዊ አውድ፣ የገዳ ስልጣኑ-ሚመት በቃሉ ተቋም ውስጥ መከወኑ የሚያስገኘውን ተቋማዊ ፋይዳ ለመመርመር ደግሞ በተቋማዊ አውድ፣ በጎንዶሮ ከበራ ለመስዋዕት የቀረበውን ስርዓት መሳካቱንና ያለመሳካቱን፣ ምርቃትና እርግማን የሚከወነው በየትኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሆነ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉት አባላት በጾታ፣ በዕድሜ፣ በሙያ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በሃይማኖትና በመሳሰሉ ቡድኖች በመከፈል ለመለየት የማህበራዊ መሰረት አውድ በስራ ላይ ውለዋል፡፡

## 2.1.4. ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ

የፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ መነሻ የአዝግሞተ ለውጥ ንድፈ-ሀሳብ ሲሆን በተወሰነ መልኩ የራሱ ወደ ሆነው ስነ-ሰብዓዊ አመለካከት የመጣው በ Derkheim ተፅዕኖ ፈጣሪነትነው፡፡ የንድፈ-ሀሳቡ እሳቤ እየጎለበተ የመጣውግን Malinowski እና Radcliffe-Brown በተባሉ ተመራማሪዎችና በተከታዮቻቸው ስራዎች አማካይነትነው (Finnegan, 1977:44)፡፡ ይህ ንድፈ-ሀሳብ የሚያጠነጥነው አንድ የፎክሎር ቅንጣት ለማህበረሰቡ ትርጉምና አገልግሎት አለው በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ላይ እንደሆነ Okpewho, (1992:172-174) ያስረዳል፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ በግለሰቦች መካከል፤ እንዲሁም በማህበራዊ ተቋማትና በግለሰቦች መካከል ባሉ ግንኙነቶች ላይ ያተኩራል፡፡

በተጨማሪ የግለሰብ እርካታም፤ ፍላጎቶችን በባህላዊና ማህበራዊ ማዕቀፍ ውስጥ ያያል፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ አንድ የፎክሎር ቅንጣት ለቡድኑ ምን ማለት እንደሆነና ሰዎች ፎክሎርን የሚከውኑት በምክንያት መሆኑን ለመገንዘብ ያግዛል፡፡ ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማስተላለፍ፣ የማዝናናት እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው (Bascom, 1954፡344-346) ያስረዳሉ፡፡ ከዚያም በላይ የፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ እሳቤን ማወቅ አንድ ቡድን በአንድ ውስን ሁነትና ውስን ክዋኔ ውስጥ ምን እየሰሩ እንደሆነ ለመረዳት ያግዘናል፡፡

ይሁን እንጂ የዚህ ንድፈ-ሀሳብ ችግር የአንድ ክዋኔ ተግባር የማይቀየር ከሆነ ቡድኑ አይቀየርም የሚለው እሳቤ ነው፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ ሁሉም የቡድን አባላት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ይሰራሉ ብሎ ማመን ብቻ ሳይሆን ቡድኖች በዘመናት ሂደት ውስጥ ተመሳሳይ ሆነው ይቆያሉ ይላል፡፡ ይህም ማህበረሰብ አይለወጥም ወደሚለው ሃሳብ ያመጣናል፡፡ የፋይዳዊ አጠናን ዘዴ

ወግ አጥባቂና የማይለወጥ፣ ተግባራቱም ወግ አጥባቂ መሆናቸውን ያሳየናል፡፡ ይህ ደግሞ የዚህ ንድፈ-ሀሳብ ሌላው ድክመት ነው፡፡ ሌላኛው እንደ ድክመት የሚነሳበት ታሪክን እንደ አውድ አለመጠቀሙ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ፖለቲካዊ ተፅዕኖዎችን ያለፈ ሲሆን፤ ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ግን ፖለቲካን ከግምት አለማስገባቱ ነው፡፡

ሌላው ከፋይዳዊያን ንድፈ ሀሳብ ቀጥሎ ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበረው ኒዮ-ፋንክሽናሊስት አቀራረብ ነው፡፡ የዚህ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች J. C. Alexander, Luhmann, and P. Colomy ሲሆኑ ከበራ የማህበረሰቡን ወይም የግለሰቦችን ሕይወት የጠቀመበትን የተለያየ መንገድ መፈተሽ ላይ ማተኮር እንጂ፤ የከበራ ፋይዳዎች መዘርዘርና መግለጽ ምን ያደርጋል ባይ ናቸው፡፡ ይህ አዲስ አስተሳሰብ ፋይዳን በ Radcliffe-Brownወይም በ Malinowski ፋይዳዊ አስተሳሰብ ቀንብቦ ማስቀመጥ ተገቢ አይደለም፤ በአንጻሩ የተለያዩ ባህላዊ ከበራዎች ግንኙነትን በማዋሃድ ስለሚፈጠረው ሁኔታ መግለጽ ላይ ያተኮረ ቢሆን ይመረጣል የሚለውንለማጽናት የሚሞክሩት ናቸው፡፡ ቢሆንም የቀደሙትን የፋንክሽናሊዝም ንድፈ ሃሳብ አንዳንድ እሳቤዎች በከፊልም ቢሆን ሲጠቀሙ እናያለን፡፡

ኒዮ-ፋንክሽናሊስቶች ሊሰመርባቸው የሚገቡ ሁለት አስተሳሰቦች አሏቸው፡፡ የመጀመሪያው የሰው ልጅ ባህሪ በማህበራዊ ሁኔታዎች ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡ በተወሰነም ደረጃ ቢሆን የተለያዩ ሁኔታዎች ማለትም የኢኮሎጂያዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ዝርያዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ተለዋውጦዎች በሰው ልጅ ባህሪ ልዩነት ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ ሁሉም ባህሪዎች የተለመዱና ሊለመዱ የሚችሉ ላይሆኑ ይችላሉ የሚሉ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ እነዚህ ንድፈ-ሀሳባዊያን ነጠላ መገኛዎችን በማጥናት አለማቀፋዊ የሆነ የከበራ እንቅስቃሴ ተግባራት ሁኔታ ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ነው፡፡

ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት ጉድለቶች ቢኖሩትም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ፋይዳዎችን በተወሰነ ደረጃ ለመግለጽ በመቻሉ ለዚህ ጥናት እንደ አጋዥ ማስተንተኛ በስራ ላይ ውሏል፡፡ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች የገዳን ዴሞክራሲ ገጽታ ከመገንባት፣ የማህበረሰቡን ህልውና ከማስጠበቅ አኳያ፤ ባጠቃላይ ኒዮ-ፋንክሽናሊስቶች እንደሚሉት ከበራ የማህበረሰቡን ወይም የግለሰቦችን ሕይወት የጠቀመበትን የተለያየ መንገድ መፈተሽ ላይ በማተኮር ከባህል፣ ከፖለቲካ፣ ከማህበራዊና ከስነ-ልቦና አኳያ ያሉትን ፋይዳዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እንደ አጋዥ ማስተንተኛ በመሆን ክልላዊ ንድፈ-ሀሳብም በስራ ላይ ውሏል፡፡

### 2.1.5. ክልላዊ (hemispheric) ንድፈ-ሀሳብ

ክልላዊ ንድፈ-ሀሳብ እንደሚያመለክተው አንድ ማህበረሰብ ከሰፈረበት ቦታ ሲንቀሳቀስ ወይም ሌላው ሲመጣበት በሚከሰቱ መስተጋብሮች የተነሳ ቀድሞ የነበረው የማህበረሰቡ ዕውቀት በሌላው አካል ለውጥ ሊካሄድበት ይችላል። ንድፈ ሀሳቡ በለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚዳቀሉ፣ የሚዋዋጡ፣ የሚዘነጉ፣ የሚጠፉ፣ አሊያም ያን ተፅዕኖ ተቋቁመውና አንሰራርቶ ሊቀጥል የሚችሉ የማህበረሰብ ባህሎችን የሚመለከት ነው። ታሪካዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ነባር ልማዶችን ለመለወጥ አቅሙ ስላላቸው እነዚህ ጉዳዮች በፎክሎርስቱ ሊጤኑ ይገባል። ስለዚህ እንደ አጥኚው በመስተጋብሮች የተነሳ የሚፈጠሩትን ለውጦች ለመመርመር መላመድ (adaptation)፣ ማስማማት (accomodation)፣ ማጣመር (syncroticism)፣ መጥፋት/መረሳት (disappearanc)፣ ትዝታዊ (recession)፣ ማዋሃድ/መቀየር (acculturation)፣ መቋቋም (retention) እና ማንሰራራት (revitalization) እንደ መመዘኛ ተጠቅሞ መመርመር እንዳለበት Dorson, (1972:44) ያስረዳል። እነዚህን መስፈርቶች እያንዳንዳቸው ካላቸው ቀረቤታ በመነሳት በሦስት ክፍሎ ማየት ይቻላል። እነሱም፡- መላመድ፣ ማስማማት እና ማጣመር ባንድ ወገን፣ ቀጥሎ መረሳት፣ ትዝታዊ እና መቀየር እንዲሁም መቋቋም እና ማንሰራራት ደግሞ በሌላኛው ክፍል በማስቀመጥ መመልከት ይቻላል ጥላሁን (2007) ተሻሽሎ የተወሰደ።

#### i.መላመድ፣ ማስማማትና ማጣመር

የተለያዩ ማህበረሰብ በታሪካዊና አካባቢያዊ ግንኙነት የተነሳ ሁለትም ሆነ ከዚያ በላይ የማህበረሰብ እውቀቶች እርስ በርስ መላመድ ጀምረው በሂደት እየተስማሙ፣ ተጣምረው እስከ መከወን ደረጃ ያለውን የሚመለከቱ ናቸው።

#### ii.መርሣት፣ ትዝታዊ እና መቀየር

በተለያዩ ማህበረሰብ መካከል በሚካሄድ መስተጋብር ውስጥ በሚፈጠሩ አጋጣሚዎች፤ በተግባር ይፈፀሙ የነበሩ ነገሮች እየደበዘዙ፣ በትዝታ (Memory culture) እየሆኑ፣ እየተረሱ፣ በስተመጨረሻም ነባሩ እውቀትና ልማድ በሌላኛው እየተተካ፣ አዲሱ ደግሞ በነባሩ ላይ ገኖ በመውጣት በሂደት የማህበረሰቡን እውቀት መተካቱን የሚመለከት ነው።

iii.መቋቋምና ማንሰራራት

ይህ ደግሞ የአንድ ማህበረሰብ ባህል በአዲሱ ሳይገፋ በማህበረሰቡ ጥንካሬና በሌሎች አጋጣሚዎች ተቋቁሞ መቆየትና በሌላ መልኩ ደግሞ በጊዜ ሂደት ውስጥ በነባሩ ላይ በመመስረት በተለያዩ መልኮች በማንሰራራት ወደ ተግባራዊ ክዋኔ ለመመለስ የሚያደርገውን ሂደት ይመለከታሉ፡፡

በአጭሩ የክልላዊ ንድፈ-ሀሳብ ዋና ትኩረት እያንዳንዱ ማህበረሰብ ፎክሎራዊ ሀብቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት እንደሚያስተላልፍ፣ እንዴት ጠብቆ እንደሚያቆያቸው እና መልሶ ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንደሚያውላቸውም የሚታይበት ሲሆን፤ አዳዲሶቹን ደግሞ እንዴት ተለማምዷቸው የራሱ እንደሚያደርጋቸው የሚመለከት ንድፈ-ሀሳብ ነው Dorson, (1972:44)፡፡ለዚህ እንደማሳያ የሚያገለግለው በ Turner (1967:2) ስራ ውስጥ የአውሮፓውያን መስፋፋት ጋር ተያይዞ አፍሪካን በቅኝ ግዛት በመያዝ በነባሩ ባህልና ሃይማኖት ላይ ለውጦች እንደተከሰቱ ይገልጻል፡፡ ለምሳሌ የዛምቢያ ማህበረሰብ ነባር ሃይማኖታዊ ተቋማትና ከበራዎቹ በውጫዊ ሃይማኖት መዋጡን የዚህ ዓይነት ተፅዕኖ ውጤት እንደሆነ ይገልጻል፡፡

በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ ልክ እንደሌሎቹ ባህላዊና መንፈሳዊ ተቋማት በታሪካዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች አንዳንድ ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች ተከስተውበታል፡፡ በእነዚህም ምክንያት በተወሰነ ደረጃ የተፈጠሩ ለውጦች አሉ፡፡ በተለይም በገዳ ስልጣነ-ሢመት ላይ የነበረው ለውጥና ቀጣይነት በሀገራችን ከነበረው ታሪካዊ ጉዳዮች ማለትም፡- ካለፉት ሪዕዮተ-ዓለም የመንግስታት አገዛዝ ተፅዕኖዎች ጋር ያሳለፉትን ተግዳሮቶችና ውጤታቸውን በዚህ ንድፈ-ሀሳብ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ባጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ አግባብነት አላቸው የተባሉና በድጋፍ ሰጪነት ለማስተንተኛነት ይረዳሉ የተባሉ ንድፈ-ሀሳቦች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ይኸውም፡- በማህበረሰቡ ውስጥ የተቋቋሙት ሃይማኖታዊ ተቋማት፣ በውስጣቸው የሚከወኑ ተግባራት፣ የማከናወኛ ህጎቹና ደንቦቹ በዚሁ ማህበረሰብ የተዋቀሩ ዕውቀቶች መሆናቸውን በማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን (Social Constructio) ንድፈ-ሀሳብ የተተነተነ ሲሆን፣ በሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ውስጥ በተምሳሌታዊ አነጋገር፣ ክዋኔዎችና ቁሶች የመግባባቱንና የመከወኑን ፍች ደግሞ ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳብን በዋናነት በመተንተን ተገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል እንዳንዱ ሃይማኖታዊ ከበራዎች

የተተነተነ ሲሆን፣ ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ለማህበረሰቡ የነበራቸው ፋይዳዎች ደግሞ የተፈተሸበት በፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ነው። በመጨረሻም የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ አካላት በደረሰባቸው ተግዳሮቶች ምክንያት የደረሰባቸውን ለውጦችና ከእነዚያ ተፅዕኖዎች በመቋቋም የመቀጠልና የማንሰራራት ሂደቶችን በክልላዊ (hemispheric) ንድፈ-ሀሳብ አስፈላጊው ትንተናና ገለጻ ተደርጎበታል።

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ዙሪያ በተደረገው ቅድመ-ዳሰሳ ንባብ ወቅት ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለውን ጥናታዊ ስራ ለማግኘት አልቻልኩም። ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ተያያዥነት ያላቸውን፤ በተለይም በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች የተሰሩ ጥናታዊ ስራዎች ለማየት ችያለሁ። እነዚህን ስራዎች ካላቸው የይዘት ቀረቤታ በመነሳት በሁለት ተከፍለው ታይተዋል። ይኸውም:-የመጀመሪያዎቹ ቡድን ጥናታዊ ስራዎች የጉጂ ኦሮሞን ጨምሮ በሌሎች የኦሮሚያ አካባቢዎች በገዳ ስርዓት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው። ይኸውም በውስጣቸው ባነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችና ፅንሰ-ሀሳቦች የቃሉን ተግባራት በተወሰነ ደረጃ የዳሰሱ ናቸው። እነሱም:- (Hinnant, 1977,1981; Tedecha, 1988 & Al-Amin, 1998) ያካሄዱት ጥናቶች በጉጂ ኦሮሞ የገዳ ስርዓት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። እነ (Van de Loo, 1991; Zalaalam, 2000 & Asebe, 2007) ደግሞ በተለያየ ርዕሰ-ጉዳዮች ያጠነጠኑ ቢሆንም ስለጉጂ ቃሉ ተቋምና ተግባራት በስፋት የሚሉት አላቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ (Asmerom, 1973; Dejene, 2011; Dinsa, 1975; Israel, 2011; Emana, 2015 and Fille, 2015) እንዲሁም (ታቦር፣ 2006፣ አለማየሁና ሌሎች፣ 1998,1999, 2000) በቃሉ ተቋም ውስጥ የገዳ ስልጣነ ሢመትንና በግጭት አፈታት ዙሪያ ያለውን ሚና በዝርዝር አቅርበዋል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ስራዎች ከዋናው ጥናት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመረዳት ያስችል ዘንድ ከዚህ በታች በተወሰነ ደረጃ ከዋና ዋና ነጥቦች አኳያ ተያያዥነታቸውን ለመፈተሽ ተችሏል። ይኸውም:- አንዱ በ Hinnant, (1977)"The Gada System of the Guji of Southern Ethiopia" በሚል በቺካጎ ዩኒቨርሲቲ ለፒ.ኤች.ዲ ዲሰርቴሺን የቀረበ ጥናት ነው። በውስጡም በስፋት ስለገዳ ስርዓት የሚያወሳ ቢሆንም፤ የቃሉና ገዳ ስርዓት አንዱ ለሌላው የሚጫወተውን ሚና ያስረዳል። ስለዚህ ስለጉጂ ቃሉና አባገዳዎች ግንኙነትና ተግባራቸው፣ ስለፈጣሪና ፍጡር ያለውን ሚት፣ በተለይም ስለዋቃና የዋቃ መንፈስ ምን እንደሚመስል በዝርዝር ተመልክቷል።

እነዚህ ሀሳቦች በአዲሱ ጥናት ውስጥም ስለሚነሱ በተወሰነ ደረጃ ለዚህ ጥናት ያለውን ጠቀሜታ ያሳያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ (Hinnant, 1981) "Guji Affinity & Case of A Conflictful Marriage." በሚል ርዕስ በማንችስተር ዩኒቨርሲቲ በ ‹Oromo kinship & Marriage› ኮንፍረንስ ላይ ባቀረበው ስራው ውስጥ ስለ ጉጂ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በስፋት አንስቷል፡፡ በጥናቱ ውስጥ በተለይም ስለቃሉ ሃይማኖታዊ መሪነትና አመጣጡን በዝርዝር የገለጸ ሲሆን በተጨማሪም፡- ከገዳ ስልጣን ሢመት ጋር ያለው ሂደትም ተገልጿል፡፡ ከዚህ ሀሳብ በአዲሱ ጥናት ውስጥ የተጠቀምኳቸው አሉ፡፡ ነገር ግን ከእኔ ጥናት የሚለየው ከቃሉ ከበራዎች ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ስለገዳ ስልጣን ሢመት ከበራ ብቻ በማንሳቱ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልክ Tedecha, (1988) "The Politico-Legal System of the Guji Oromo." በሚል ርዕስ፤ በአ.አ.ዩ. ለህግ ት/ት ክፍል የቀረበ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የቃሉ ተቋምና በገዳ ስርዓት ውስጥ የገዳ መደቦች ክፍፍልና የስራ ድርሻ፣ የገዳ የስራ አመራሩ ፓርላመንታዊ ይዘት ምን እንደሚመስል፣ የጉሚ ቦኮ ህገ-ጉባኤውና በስርዓቱ ያለውን የማህበረ-ፖለቲካ ለውጥን ጭምር የተነተነ ነው፡፡ ነገር ግን ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ በተናጥልና በጥልቀት ከቀረበበት አውድ አኳያ አላነሳም፡፡ ስለዚህ አዲሱ ጥናት ይህንን ክፍተት በምክንያት፣ በቦታ፣ በጊዜና ሂደቱንም ጭምር የዳሰሰ በመሆኑ እነዚህ የተፈጠሩ ክፍተቶችን የመሙላት ስራ ስለሚታይበት ለየት ያደርገዋል፡፡

የ Al-Amin, (1998) "Gada System: Nature, Operations and Constraints, with the Reference of the Experience of Guji Oromo." በሚል ለፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል፣ የቀረበ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ ይህ ሥራ በይበልጥ ስለገዳ ስርዓት ተፈጥሮ፣ ተግባራቱና በመጨረሻም ውስንነቱ ምን ምን እንደነበሩ የሚያትት ነው፡፡ ይኸውም በጉጂ ኦሮሞ የገዳ ስርዓት፣ የማህበረሰቡን ፖለቲካና የአፈጻጸም ስርዓቱን መመርመርና በጉጂ አካባቢ ቀድሞ የነበረውን የማስፈጸም አቅም እንዲያጣ፣ እየተዳከመ እንዲሄድ ያደረጉትን ተግዳሮቶች ለይቶ ማውጣት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጋር በማያያዝ ከቃሉ ሃይማኖታዊ ተግባራት ውስጥ ለገዳ ስልጣነ-ሢመት ወሳኝ እንደሆነ ለማስረዳት ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ስለሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ያለው ነገር የለም፡፡

ሌላዉ በ Asmerom, (1973) እና Dinsa, (1975) የተሰሩ ጥናቶች ሲሆኑ፤ የሁለቱም ጥናቶች ባብዛኛው በገዳ ስርዓት ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለትካዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ላይ ያተኮሩ ናቸው። የAsmerom'ን የተመለከትን እንደሆነ "Gada: Three Approaches to The Study of African Society." በሚል ለሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ለፒ.ኤች.ዲ ዲሰርቴሽን የቀረበ ነው። በጥናቱም ስለ ቦረና ገዳ ስርዓት፣ የገዳ ደረጃዎች፣ የገዳ ስልጣን ዑደትና የሚከናወኑትን የገዳ ከበራዎች በጥልቀት ያተተ ሲሆን፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለቦረና ቃሉና የቃሉ ተቋም በገዳ ስርዓት ውስጥ ያለውን ሚና ይገልጻል። ይኸውም፡- የቃሉንና የገዳ ስርዓት እርስ በርስ የሚደጋገፉ እንደሆኑ ለማስረዳት ችሏል።

ሌላው እሱ ባጠናበት ወቅት በገዳ የስልጣን ሽግግር ማለትም የሙዳ ስርዓት በየስንምት ዓመት አንዴ የሚካሄደው ታላቅ ከበራ በደቡባዊ የኦሮሞ አካባቢ፤ ማለትም በአርሲ፣ በባሌና በቦረና አካባቢዎች በሚካሄድበት ወቅት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች ለመንፈሳዊ ጉዞ ከሰሜን እንደ ወሎ፣ ከምዕራብ ደግሞ ከወለጋና ጂማ ድረስ በመምጣት ይሳተፉ እንደነበር ያወሳል፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች እየተዳከመ እንደሄደና እስካሁን ይህ ስርዓት ተጠብቆ ያለው በጉጂና በቦረና አካባቢ እንደሆነ ገልጿል። ከዚህ ጋር በማያያዝ በወሎና በሜጫ ኦሮሞ እየተከወነ ያለው የቃሉ ተግባር ከእነዚህ በተለየ መልኩ እንደሆነም ይገልጻል። ነገር ግን በአንዳንድ ሁነቶች ላይ የተመለከትን እንደሆነ በጉጂና በቦረና ቃሉ መካከል የተወሰኑ ልዩነቶች ይታያሉ። ይኸውም ለምሳሌ ያህል በጉጂና በቦረና ኦሮሞ የቃሉ የጫቂላ ስርዓቱ፣ ቃሉ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የስልጣን መተካት ከበራው፣ እንዲሁም በቁጥር የጉጂ ቃሉ አንድ ሲሆን የቦረና ደግሞ ሁለት መሆናቸውና በመሳሰሉት ሂደቶች ላይ ሰፊ ልዩነቶች አሉ። ይሁን እንጂ በተዘዋዋሪ መንገድ በአብዛኛው የመቀራረብ ሁኔታዎች ይታያል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ጥናት በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ በጥልቀት በመመርመር ትንተና ያደረገ በመሆኑ ከእሱ ጥናት ለየት ያደርገዋል።

በ Dinsa, (1975) "The Gada System of Government" በሚል ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሕግ ትምህርት ክፍል የቀረበ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ ሌላኛው ተቀራራቢ ስራ ነው።ጥናቱም በዋናነት የሚያተኩረው በገዳ ስርዓት ስልጣንና የስልጣን ሂደቱንና ባህሪያቱን በጥልቀት የሚያስረዳ ሲሆን፤ በውስጡ ስለቃሉ አመጣጥ፣ የቃሉ ስልጣን በትውልድ የሚተላለፍ መሆኑንና ወደ ስልጣን የሚመጣ ቃሉ ምን ምን መስፈርቶችን ማሟላት እንዳለበት፣ በኦሮሞ ጉባኤ (ጫፌ) ውስጥ የቃሉን ቦታ በሚገባ ያሳየ ነው። ስለዚህ እነዚህ

ንዑስ ርዕሶች የተወሰኑት በአዲሱ ጥናት ውስጥም በተለያየ መልክ ተዳሰዋል። ይሁን እንጂ በእሱ ጥናት ውስጥ ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በተናጥል፣ በጥልቀትና ከቀረቡበት አውድ አኳያ አልተነሳም። ስለዚህ አዲሱ ጥናት ይህንን ክፍተት የመሙላት ስራ ያካተተ ነው።

ሌላው በ Van de Loo, (1991) «Guji Oromo Culture in Southern Ethiopia. Religious Capabilities in Rituals & Songs.» በሚል ጥናቱ ውስጥ ከበራዎችና መዝሙሮች ሃይማኖትን የመግለጽ ኃይላቸውን በገዳ ስርዓትና በስርዓቱ ወቅት የሚዜሙ ዜማዎችን ጥበብ በመተንተን ያሳየ ሲሆን፣ በከበራዎቹና መዝሙሮቹ ከዝምድና፣ ከጋብቻ፣ ከልደት፣ ከቀብርና የመሳሰሉት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ እንደሚንጸባረቅ ያሳየ ነው። ይኸውም፡- ከህዝቡ አሰፋፈር፣ ከከብት እርባታ፣ ከመጠጥ አዘገጃጀት፣ ከእህል ማምረት፣ ምግብ አዘገጃጀትና ከመሳሰሉት ጋር ያለውን ግንኙነት እንደሚያሳዩ በሰፊው ገልጿል። በተለይም ስለገዳ የስልጣን ሽግግርና መንፈሳዊ ጉዞውን በስፋትና በጥልቀት ያሳየ ነበር። ስለዚህ ይህ ስራ ከአዲሱ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ የሚጋሩት ነጥቦች አሉት። ይሁን እንጂ የቃሉን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ከሚከወኑበት አውድ አኳያ በጥልቀት ያልተዳሰሰ በመሆኑ እነዚህን ክፍተቶች በአዲሱ ጥናት የሚሞሉ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል።

ከዚህ በተጨሪማሪበ Zalaalam, (2000) የቀረበው ጥናት ደግሞ ‹‹Sirna Gaa'laafi Moggaasa Qaalluu Oromoo Gujii.›› በሚል ለአፋን ኦሮሞ ቋንቋና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ፣ በአ.አ.ዩ. የተደረገ ጥናት ነው። ጥናቱም በዋናነት ስለቃሉ ስልጣን አሰያየምና የጋብቻ ከበራው ላይ ያተኮረ ነው። በማያያዝም ሰለቃሉ ተቋም አመጣጥ፣ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች መኖራቸውን፣ የተወሰኑት ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለግንዛቤ ማስጨበጫ ያህል ሳይተነተኑ ተገልጸዋል። አዲሱ ጥናት ግን ዓላማ ያደረገው እነዚህን ጽንሰ-ሀሳቦች በቃሉ ስርዓት ውስጥ መኖራቸውን ከመጠቆም ባለፈ በየከበራዎች ውስጥ የሚታዩትን ሁሉ የዳሰሰ ነው። ይኸውም፡-የማህበረሰቡ ዕውቀት የሆኑትን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ክዋኔ፣ ከዋኙ፣ መከወኛው ቁሳቁስ፣ በአውዱ የሚታዩ ትዕምርቶችና የእነሱን ትርጉም፣ የክዋኔው ማህበራዊ ደንቦችን ጭምር በመመርመር ለማህበረሰቡ ያለውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ ተንትኖ ያቀረበ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል።

ሌላውበ Asebe, (2007) "Ethnicity & Ethnic Relation; The Ethiopian Experiment and The Case of Guji and Gedeo." የሚለው ጥናት በብሔር ብሔረሰቦች ላይ የተመሰረተ

አከላለልና የብሔረሰቦች እርስ በርስ ግንኙነት፡ ኢትዮጵያ ከተገበረችው አዲስ የአገር አወቃቀር ሀሳብ፤ ከጉጂና ጌዴኦ ብሔረሰቦች አኳያ ለሀገር በቀል ዕውቀት ፍልስፍና ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ፣ በቶሮምቶ ዩኒቨርሲቲ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በብሔር ብሔረሰቦች መካከል በሚፈጠረው ግንኙነት የመንግስት ጣልቃ ገብነት ያለውን ተፅዕኖ በጉጂና ጌዴኦ ግጭት ማሳያነት ያቀረበውና የጎንዶሮ ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓትን ያሳየ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የቃሉ ተቋም በዚህ የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ ግጭትን ለማስወገድ ያለውን ሚና ገልጿል፡፡ ይህ ስራ ከአዲሱ ጥናት የሚለየው፤ ከቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ አንዱን ብቻ የተመለከተ ሲሆን፤ አዲሱ ጥናት ግን ሌሎችንም የጎንዶሮ ዓይነቶችና የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ያካተተ መሆኑና የእያንዳንዱን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ፋይዳዎችን ጭምር የዳሰሰ በመሆኑ ነው፡፡

Emana, (2015) ‹‹Historical Documentation and Thematic Analysis of Waqeffannaa Religion and Song Among Tuulamaa Oromo.›› በሚል በአ.አ.ዩ. ለስነ-ልሳንና ፊሎሎጂ ትምህርት ክፍል ለፒ.ኤች.ዲ. ዲስርቴሽን የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት "በቱለማ ኦሮሞ የዋቄፈና እምነት ክብረ-በዓላት ልማዳዊ ድርጊቶችና መዝሙሮች ታሪካዊ አመለካከት" ከፎክሎር አኳያ የሚመለከት ሲሆን ጥናቱ ኢትኖግራፊክ የሆነ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ ከዋቄፈና ጋር ተያይዞ በተከበሩ እሬቻ፣ ጉማ ሥርዓት፣ ቃሉ ሥርዓት፣ አቴቴ እና ወዳጃ ክብረ-በዓላት ላይ በመገኘት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሥነቃል ዓይነቶች ከነተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው ጋር ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ የዋቄፈና እምነት ልማዳዊ ድርጊቶችና መዝሙሮች በቱለማ ኦሮሞና ሌሎችም የኦሮሞ ጎሳዎች የየዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ሠላምና ደህንነትን አስተማማኝ በማድረግ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን በማጠናከር፣ አንድነትንና የጋራ መግባባትን በመፍጠር እንዲሁም ተከባብረውና ተቻችለው መኖርን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር የጉማው ስርዓት በከፊል ከጎንዶሮ ከበራ ጋር ከመመሳሰሉ በቀር ሌሎቹን በእሱ ጥናት ውስጥ ተነስተው በእኔ ውስጥ የሌሉ እንደአቴቴ፣ እሬቻ እና ወዳጃ ክብረ-በዓላት ሲኖሩ፤ የቃሉ ሥርዓትም ቢሆን በክዋኔውም ሆነ በምግባሩ ከጉጂ ቃሉ ጋር የማይገናኝ ነው፡፡ እንዲሁም በእኔ ጥናት ውስጥ የተነሱት የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች አብዛኛዎቹ በእሱ ውስጥ አልተነሱም፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ሌላው ይህ አዲሱ ጥናት ከኢማና ለየት የሚያደርገው ዋንኛው ምክንያት ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች የማህበረሰቡን ዕውቀት በማሕበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ

መተንተኑና በከበራዎቹ ይደረግ የነበረው ተግባቦት ማለትም፡- በቋንቋው፣ በክዋኔውና በመከወኛ ቁሶቹ ተምሳሌታዊነቱን ያሳየና ትርጉሙን/ፍች የሰጠ በመሆኑ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Fille, (2015) ‹‹Documentation of Folk Law & Description of Grammatical sketch of the Macca Oromo.›› በሚል ርዕስ በአ.አ.ዩ. ለስነ-ልሳንና ፊሎሎጂ ትምህርት ክፍል ለፒ.ኤች.ዲ ዲሰርቴሽን የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት በሜጫ ኦሮሞ ከሚገኙት ውስጥ ከምዕራብ ሸዋ በኩታዬ ሊበንና ከምስራቅ ወለጋ ደግሞ ሊሙ ጃዊ ጎሳ ውስጥ ሀገረሰባዊ ህግ ከማውጣትና ህጉንም በማስፈጸም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በጥናቱም ውስጥ የሀገረሰባዊ ህግ አወጣጥና አተገባበር ሂደትና የህጋዊ ተምሳሌቶች (legal symbol) አጠቃቀምን የመሰነድ ነው:: የጥናቱ ዓላማ የሜጫ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ህጎችን መሰነድና ሰዋስዋዊ ንድፉን መግለጽ ነው፡፡ የፊሌ ጥናት ከእኔ ጋር የሚያዛምደው በሀገረሰባዊ ህግ (folk Law) በኩል ሲሆን ባህላዊ የግጭት አፈታትና ዘዴዎቹ በሚለው ንዑስ-ርዕስ ስር ሽማግሌዎች፣ ሻኔ (shanee) እና የቃሉ ተቋም በማለት ይዘረዝራቸዋል፡፡ ነገር ግን በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሰው የቃሉ ተቋም ከላይ ከተጠቀሰው የኢማና ስራ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ከእኔ ጥናት ጋር በአውድም ሆነ በተግባሩ አለመገናኘቱ ለየት ያደርገዋል፡፡

ሌላው በባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ ከሚለው ስብስብ ጥናታዊ ስራዎች ውስጥ በ Dejenee, (2011) «The Customary Courts of the Waliso Oromo.» የሚለው ጥናት አንዱ ነው:: በጥናቱ ውስጥ የቃሉ ተቋም ከገዳ ስርዓት በተጓዳኝ የሚገኝ ሃይማኖታዊ ተቋም እንደሆነና የቃሉ ችሎት ከግጭት መፍቻ ስርዓቶች መዋቅር ውስጥ አንዱ መሆኑን ያስረዳል፡፡ የቃሉ ተቋም የገዳ ስልጣንን ከማጽደቅ ባሻገር የተለያዩ የግጭት ዓይነቶችንና የተለያዩ ማህበረ-ፖለቲካዊ ችግሮችን የመፍታት ሚና እንዳለው ለማሳየት ችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው የቃሉ ተቋም ግን ከገዳ ስርዓት ጋር ተያያዥነት እንደሌለውም አመልክቷል፡፡ ስለዚህ አዲሱ ጥናት ከዚህ የሚለየው በመጀመሪያ ደረጃ በጥናቱ የተዳሰሰው የቃሉ ተቋም ከገዳ ስርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና እርስ በርስም ያላቸውን ተደጋግፎ በግልፅ ያሳየ መሆኑ ላይ ነው፡፡ ይኸውም፡- በቃሉ ተቋም ግጭቶችን ከመፍታት ባሻገር ያሉትን የገዳ ስልጣነ ሢመት ማጽደቅ ጨምሮ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ያካተተ በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው በ Israel, (2011) «The Quest for the Survival of Gada System's Role in Conflict Resolution.» በባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ ከሚለው ስብስብ

ውስጥ ሌላኛው ጥናታዊ ስራ ነው፡፡ በጥናቱም የገዳ ስርዓት ግጭቶችን በመፍታትና ሰላምን በማስፈን በኩል ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን አሳይቷል፡፡ ጥናቱ በገዳ ስርዓት የነበሩትን ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁመው በአሁን ወቅት በስራ ላይ ባሉት የቦረና፣ የጉጂና ምዕራባዊ አርሲ ዞኖች ላይ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግጭት መፍቻ ስርዓት መዋቅሮቹን፣ የግጭት አፈታት ሂደቶቹንና በሂደቶቹ ውስጥ የነበሩ ተግዳሮቶችን በሚገባ ገልጿል፡፡ ይህ ጥናት ከአዲሱ የሚለየው ልክ ከላይ እንደተገለጸው ጥናት ትኩረቱ በግጭት አፈታቱ ሂደት ላይ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ አዲሱ ጥናት ግን የግጭት አፈታቱን ከመግለጽ ባሻገር ከበራውንም የመተንተንና የመግለጽ ሂደቶች ተከናውነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችንም ያካተተ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የእነ (Knutsson, 1967; Lewis, 1970; Bartels, 1983; እና Meseret, 1995) ለማየት እንደተሞከረው ጥናታቸውን ያካሄዱት በቃሉ ተቋም ላይ ነው፡፡ በጥናታቸው ውስጥ የቀረቡት ሃይማኖታዊ አውዶች፣ የሃይማኖቱ መሪዎቹና ተግባራቸው፣ እንዲሁም በተቋማቱ ውስጥ የሚከወኑት ከበራዎች ጭምር ከአዲሱ ጥናት ጋር ያለመመሳሰል ይታይባቸዋል፡፡

ይኸውም፡- የ Bartels, (1983) «Oromo Religion Myths and Rites of the Western Oromo of Ethiopia.» የሚለውን ያየን እንደሆነ፤ በኦሮሞ ሃይማኖታዊ ሚቶችና ከበራዎቹ በሚል ዙሪያ ያካሄደው ጥናት ሲሆን፤ በጥናቱም ስለ ኦሮሞ ሃይማኖትና ከበራ ያሉትን ሚቶችና የመንፈሳዊ ጉዞ ከበራው ጠቀሜታ በሰፊው አስረድቷል፡፡ በሌላ በኩል የሃይማኖታዊ ተምሳሌቶችንም ጥቅም ለመግለጽ ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ስለቃሉ ተግባራት በሚገልጽበት ወቅት የቃሉና የቃሊቻ ተግባራት የሚመስሉ ተቀላቅለው የመታየት ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይህ ሀሳብ ደግሞ ከአዲሱ የጥናት ትኩረት በተወሰነ ደረጃ የተለየ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከእሱ የጥናት ወቅት አንጻር የነበሩትን ለውጦችና አሁን ያለበትን ሁኔታም ያካተተ በመሆነ የተለየ ያደርገዋል፡፡

በ Knutsson, (1967) «Authoity and Change: The Study of the Kalu Institution.» በሚል የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን፤ በውስጡ ስለቃሉ ጥንተ-አመጣጥ፣ ስለተቋም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ሚናና ውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ በተወሳሰበ መንገድና በዓላትን በማማከል እንዴት አገልግሎት እንደሚሰጥ በሰፊው ገልጿል፡፡

ነገር ግን በተወሰነ ደረጃ ልክ እንደ Bartels ጥናታዊ ስራ የቃሉና የቃሊቻን ምግባር ባደባለቀ መልኩ የቀረበበት ሁኔታ አለ፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት በሜጫ ኦሮሞ ያለው ቃሉ ከገዳ ስርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው ነው (Dejenee, 2011:254)፡፡ ነገር ግን በአዲሱ ጥናት የታቀፈው የጉጂ ቃሉ ግን ከገዳ ስርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና አሁንም እያገለገለ መሆኑ በጥናቱ መገለጹ ለየት ያደርገዋል፡፡

ሌላው Lewis, (1970) «Kud'arfan: A Multi-Functional Institution Among the Western Galla.» በማለት ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ ጥናቱ ስለቃሉ አመጣጥና ተግባር፣እንዲሁም ባለዘርፈ-ብዙ ፋይዳ ተቋም እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በውስጡ በአብዛኛው የተዘረዘሩት ልክ እንደቀደሙት ጥናቶች ሁሉ አብዛኛውን የቃሊቻን ተግባር የሚመስሉ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት አሁን ከቀረበው ጥናት አውድና ተግባራት ጋር የሰፋ ልዩነት አለው፡፡

በመጨረሻ Meseret, (1995) ‹‹Qaallu as a Dispute Setting Institution.›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሕግ ትምህርት ክፍል ያቀረበችው ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ለማየት ተችሏል፡፡ በጥናቷም ውስጥ ስለ ቃሉ በተለይም በግጭት አፈታት ስርዓት ያለውን ተግባር በጥልቀት ዳሳለች፡፡ ነገር ግን ልክ እንደላይኛዎቹ ጥናቶች፤ አዲሱ ጥናት የቀረበበት አውድና የቃሉ ተግባር ጋር ሰፊ ልዩነት አለው፡፡

በኦሮሞ ታሪክና በጥንቱ የገዳ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ «ቃሉ» (መንፈሳዊ መሪ) ከፍተኛ ታሪክና ትልቅ ስፍራ ያለው ነው፡፡ ዳሩ ግን ከ19ኛው መቶ ክ/ዘ በኋላ በታዩት ለውጦች ምክንያት በሰሜን አካባቢ ባሉት የኦሮሞ ጎሳዎች ዘንድ ከገዳ ስርዓት ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንደተቋረጠ ምሁራኖች ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው «ቃሉ» ከገዳ አስተዳደር ስርዓት ጋር የተያያዘ ኃላፊነት ያላቸው አለመሆናቸውን አለማየሁና ሌሎች (2000:108) በስፋት ገልጸዋል፡፡

ባጠቃላይ የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ በእነ (Knutsson,1967; Lewis,1970; Bartels,1983; & Meseret 1995) እና ሌሎችም ጥናት ውስጥ እንደሚሉቱ "ቃሉ" በሚባለው የሃይማኖቱ መሪ ላይ የሚወርድበት ለየት ያለ መንፈስ ያለው ሳይሆን፤ እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለጻና አጥኚው በምልከታ ወቅት እንደተገነዘበው የእግዚኣብሔር መንፈስ ያደረበትና የተረጋጋ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏ፡፡ በሌላ በኩል እጣን እያጨሰ፣ ድቤ እየመታ፣ አፍንጫውን እየጎረጎረና እያጓራ ስለግለሰቦች ዕጣ-ፈንታ የሚገልጽ አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሳ የከበራውም ሆነ፣ የክዋኔው

አውድ ያለመመሳሰል ይታይባቸዋል። በተዘዋዋርም መንገድ ግንኙነት አላቸው ከሚባሉት ጥናቶች ውስጥ የተወሰኑት ጥናቱ ከተካሄደበት አካባቢ መመሳሰል፣ በገዳ ስርዓት ውስጥ አንዳንድ ሀሳቦችን በማንሳታቸውና በስርዓቱም ውስጥ የቃሉ ሚና ምን እንደሚመስል ከማሳየት ረገድ ቀረቤታቸው የጎላ ነው። ነገር ግን ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በተደራጀና በጥልቀት ያዩት ነገር እንደሌለ ለማየት ተችሏል። ሌላው ይህ ጥናታዊ ስራ በተበታተነ መልክ የተነሱትን ሀሳቦች በአንድ ላይ በማካተት፣ ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን በማከል፣ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ዙሪያ በማተኮርና ከተከወኑበት አውድ አኳያ ተንትኖ በመግለጽ፣ የቃሉን ተቋም ለውጥና ቀጣይነት ምን እንደሚመስልና በመጨረሻም የተጠቀሱት የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱትን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎች የገለጸ ነው። ስለዚህ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱ ክፍተቶች መሙላቱና እራሱን ችሎ በቃሉ ተቋሙ የሚከናወኑ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በአንድ አካቶ በጥልቀት ማየቱ ከሌሎቹ የተለየ ያደርገዋል።

ሌላው ስለቃሉ ታሪካዊ አመጣጥና ከጉጂ ቃሉ ጋር ተቀራራቢ ፅንሰ-ሀሳቦችን በዝርዝር የያዘ በ አለማየሁና ሌሎች፣ (1999) የገዳ ስርዓት፡ የቱላማ ኦሮሞ ፖለቲካ በሚል የቀረበ ስራ ነው። ጽሑፉ በአብዛኛው ስለቱለማ የገዳ ስርዓትና ያለፈባቸውን በርካታ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ውጣ ውረዶችን የሚያስጨብጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የገዳ ስርዓቱ አሁን ያለበት ደረጃ የሚገልጽ ቢሆንም የተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎችንም ለመዳሰስ የሞከረ ነው። በጽሁፉ ውስጥ በኦሮሞ የገዳና የቃሉ ስርዓቶች የማይነጣጠሉ እንደሆኑ፣ ስለቃሉ አመጣጥና ትክክለኛው ቃሉ የቱ እንደሆነ፣ በተለይም ከ19ኛው ክ/ዘ በኋላ ወደሰሜኑ የኦሮሞ አካባቢ ያሉት የቃሉ ስርዓት ከገዳ ስርዓት ጋር ተያያዥነት እንደሌላቸው በምክንያት አስደግፎ አመልክቷል። በተቃራኒውም የቦረናና ጉጂ ቃሉዎች የመጀመሪያው የቃሉ አካል፡- ማለትም ከማዳ ወላቡ የነበረው ዝርያ የመጡ እንደሆኑ ያስረዳል።

ከዚህ በተጨማሪ ስለቃሉ ምንነትና ከየት ተነስቶ ወዴት እንዳመራና በምን ተፅዕኖ ከቀድሞ ቦታ እንደተሰደደ፣ በተለይም በየስምንት ዓመቱ በሚካሄደው የገዳ ስልጣን ማጽደቅያ ወቅት የሚካሄደውን ስርዓትና በከበራው ወቅት የሚቀርቡትን ቁሳዊ ባህሎች በመጥቀስ የያዙትንም ፍች ለማስረዳት ሞክሯል። እነዚህ ሀሳቦች በአብዛኛው በአዲሱ ጥናት ውስጥም የሚነሱ በመሆኑ ለእኔ ጥናት በተወሰነ ደረጃ እንደመረጃ ምንጭነት አገልግሏል። ይሁን እንጂ በጽሁፉ ውስጥ ከቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ የገዳ ስልጣን ሽግግር ወቅት የሚካሄደውን ስርዓት

በሰፊው ቢገለጽም፣ የስርዓቱን ክዋኔና አውዳዊ ትንተና ያልተደረገበት ነው። በሌላ በኩል ለሎችንም ሃይማኖታዊ ከበራዎች አለማካተቱ፣ ቁሳዊ ባህሎቹንና ተምሳሌትነታቸው ጭምር በጥልቀት አለመመልከቱ የተለየ ያደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ስለቃሉ የአገልግሎት ዘመን እስከ ዕለተ-ሞቱ ድረስ እንደሆነ በመግለጽ፣ ከዕልፈተ ሕይወቱ በኋላ የቃሉ ባለቤት ተተክታ «ቃሊት» ተብላ ተቋሙን እንደምታስተዳድር ገልጿል። አንዳንድ ቦታ ደግሞ የቃሉ የመጀመሪያ ልጅ በቦታው እንደሚተካም ያስረዳል። በአዲሱ ጥናት ውስጥ የቀረበው ቃሉ ግን ከዚህ የተለየ አካሄድ ያለውና ከቃሉ አመጣጥ ሚት ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ለየት ያደርገዋል።

በመጨረሻም በታቦር (2006) «የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች» በሚል የቀረበ መጽሐፍ ለመዳሰስ ተሞክሯል። በጽሑፉ ውስጥ የኦሮሞ እውነተኛ ታሪክ የቱ እንደሆነና የውገና ድርሰት በማለት በተለያዩ በሀገር ውስጥና በውጭ ፀሐፍቶች የቀረቡ፦ ስለኦሮሞ ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነት፣ ከየት-መጣነቱንና የመሳሰሉትን በመረጃ በማስደገፍ ያለውን እውነታ በሰፊው አትቷል። ከዚህ በተጨማሪ ስለዋቄፋና ከቀደምት ሃይማኖቶች አንዱ እንደሆነ፣ የሃይማኖቱ መሪ ደግሞ ቃሉ እንደሚባል፣ የቃሉ የስራ ድርሻና የማያከናውናቸውን ተግባራት ጭምር በግልጽ አሳይቷል። ነገር ግን ስለቃሉ ወይም «ቃሊቲ» ጽንሰ ሀሳብ ሲገልጽ «ቃሊቲ» (የሃይማኖቱ መሪ) ሆና ከዘርዋ በተዋረድ ባገኘችው የቃሉን ተቋም እስከ ዕድሜ ልኳዋ ድረስ መምራት እንደምትችል ይገልጻል። ይህ ጉዳይ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የተመለከትን እንደሆነ፦ «ቃሊቲ» የምትባል፣ እንደተባለው የቃሉን ተቋም የምትመራ አለመኖሯና ተግባሩንም የማትከውን ስለሆነች ከአዲሱ ርዕሰ-ጉዳይ ጋር ተመሳስሎ የለውም። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የኦሮሞ አካባቢዎች በተሰሩ ጥናታዊ ስራዎች ውስጥ የተመለከትን እንደሆነ ስለቃሉ እንጂ ስለ «ቃሊቲ» አመጣጥ የሚነገሩ ሚቶች ለማግኘት አልቻልኩም።

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች እንደ ዕውቀት ዘርፍ፤ እንደ ዕውቀት ምርት (production) የኦሮሞ ህዝብ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ይህንን ዕውቀት እንዴት እንደፈጠሩት የሚለውን ኢፒስቲሞሎጂያዊ የዕውቀት አረዳድ ስለሚመለከት፤ የተከተለው የአጠናን ዘዴ ማህበረሰቡ የማህበረ-ባህላዊ ሁኔታዎችን እንዴት አወቁት? የሚለውን ኢፒስቲሞሎጂያዊ የዕውቀት አረዳድ ከተለያዩ ማዕዘን የተመለከተ ሲሆን፤ ከቲዮሪያዊ አተያይ ደግሞ በዋናነት ተምሳሌታዊ አተረጓገም (Symbolic Interpretive) እና የማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን (Social Construction) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ጥናቱ አብዛኛውን ተፈጥሯዊ አውድን ተንተርሶ መረጃዎችን በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ በቡድን ውይይትና በንጥል-ጥናት ዘዴዎች የተለያዩ የናሙና አመራረጦችን መሰረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ በመግባትና አብሮ በመቆየት የኢትኖግራፊያዊ ስነ-ዘዴን (methodology) በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በተፈጥሯዊ መቼት ያልተሳኩትን አርቴፊሻል መቼት በማዘጋጀት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የማህበረሰቡ ዕውቀት ኦንቶሎጂያዊ ግምቶችን በዚህ ስር ተነስተዋል፡፡ ኦንቶሎጂያዊ ግምቶችን እነ Guba and Lincolin'ን በመጥቀስ Crotty ሲገልጽ፡- ‹በምናውቃቸው ነገሮች ዙሪያ ያለው እውነታ ምንድነው?› ወይም ‹የአኗኗር ዘይቤያቸው ተፈጥሯዊ ሁኔታ ምንድነው?› ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ እንደሆነ Crotty, (1998:2) ያስረዳል፡፡ ስለዚህ የማህበረሰቡ ዕውቀት እውነታ ምንድነው? ለምሳሌ፡- የትኛው ቃሉ እውነት ነው? ከማለት የተለያዩ እውነቶች /multiple truths/ ተፈጠሩ የሚለው ላይ ያተኩራል፡፡

ስለማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያንና ተምሳሌታዊ አተረጓገም ንድፈ-ሀሳቦች በ2.1. ስር ከሌሎች አጋዥ ቲዮሪዎች ጋር በስፋት ተዳሷል፡፡ ነገር ግን የተቀሩትን የአጠናን ዘዴ ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 3.1. የጥናቱ ዓይነት

ቀደም ሲል በሶሻል ሳይንስ የጥናት መስክ ባብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) የአጠናን ዘዴን በመምረጥ በተቃራኒዊ ወገን ደግሞ አሃዛዊ (quantitative) ዘዴ እንዳለ ይገመት ነበር፡፡ አሁን

ግን እንደ Crotty, (1998:14) ገለጻ በዓይነታዊ እና አሃዛዊ የአጠናን ዘዴ መካከል ያለው ልዩነት በዘዴዎች (methods) ደረጃ ብቻ እንደሆነ ያስረዳል። ልዩነቱ በኢፒስቲሞሎጂው ወይም በቲዮሪያዊ አተያዩ ደረጃ ላይ አይታይም።

ኢፒስቲሞሎጂ የዕውቀት ንድፈ-ሀሳብ ሲሆን ስለአንድ ነገር ወይም ሁነት ያወቅነው ፍች እንዴት እንዳወቅነው የሚገልጽ ነው። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉት ዕውቀቶች እንዴት ተረዱት ለሚለው በስሩ ሦስት ዓይነት መንገዶችን ያነሳል። እነሱም፡- ኦብጀክቲቭዚም፣ የዕውቀት አዋቃሪያንና ሳብጀክቲቭዚም ናቸው። ስለዚህ ኦብጀክቲቭዚም/ፖዘቲቭዚም ጥናት በአንድ በኩል ልክ እንደ አሃዛዊ የአጠናን ዘዴ፣ የዕውቀት አዋቃሪያን/ ሳብጀክቲቭዚምን ደግሞ በሌላ ወገን እንደ ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴ አድርጎ፤ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ማየት እንደሚቻል ይገልጻሉ። ከዚህ ባሻገር ሁለቱ የሚለያዩበት ዕውቀት ምንድነው? እንዴትስ ይመረታል? በሚለው ነው። ኦብጀክቲቭዚም እውነተ ማለት ነባራዊ እውነት፤ ልክ እንደ ነባራዊ ቁሶች የማይለወጥ እንደሆነ ያምናሉ። የዕውቀት አዋቃሪያን ደግሞ ዕውቀት ወይም እውነት በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ስለሚመረቱ፤ ከሁኔታዎች መቀያየር ጋር አብሮ እንደሚቀያየር ይገልጻሉ (ዝኒ ከማሁ)።

ከዚህ እሳቤ በመነሳት ይህ ጥናት በዋናነት የዕውቀት አዋቃሪያንና ሳብጀክቲቭስት ኢፒስቲሞሎጂን የተከተለ ነው። ምክንያቱም እውነት ወይም ፍች ከምንኖርበት ዓለም እውነታ ስናመጣው ከእኛ መደበኛ ስምምነት ውስጥ ወይም ውጭ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ፍችዎች (meaning) የነባራው ወይም የሁነቶች ግላው ባህሪያቸው አይደሉም፤ ውቅር ናቸው። ይህን አስመልክቶ Crotty ሲገልጽ፡-

> *There is not objective truth waiting for us to discover it. There is no meaning without mind. Meaning is not discovered, but constructed. In this understanding of knowledge, it is clear that different people may construct meaning in different way, even in relation to the same phenomenon* (ibdi).

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው እንደ ኦብጀክቲቭስት ኢፒስቲሞሎጂ ማለትም፡- የአንድ ነገር ፍች ፍጹም እውነት (absolute truth) እንደሆነ ያስረዳሉ። ነገር ግን ከላይ ለማየት እንደተቻለው የዕውቀት አዋቃሪያን ኢፒስቲሞሎጂስት ደግሞ ይህን ሀሳብ በመቃረን ፍች ይህ ነው መሆን ያለበት ተብሎ የተቀመጠ ግኝት ሳይሆን የተዋቀረ ነው ይላሉ። ይኸውም፡- ያለ አእምሮ ፍች

(ትርጉም) ሊኖር እንደማይችልና ፍች አዲስ ግኝት ሳይሆን ውቅር (constructed) ነው። በዚህ የዕውቀት አረዳድ፤ በተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ፍችዎች፤ በተለያዩ መንገዶች ሊዋቀሩ ይችላሉ የሚል እሳቤ አላቸው። ሦስተኛው የኢፒስቲሞሎጂ መንገድ ደግሞ ሳብጀክቲቭዚም ሲሆን፤ ከመዋቅራዊያን፣ ከድህረ-መዋቅራዊያንና ከድህረ-ዘመናዊያን በመምራት የመጣ አስተሳሰብ ነው:: በሌላ በኩል የዕውቀት አዋቃሪያን ፍችን ከነባራዊነት በመነሳት የሚዋቀር እንደሆነ ያነሱት አገላለጽ በነበረበት ወቅት የተፈጠረ አስተሳሰብ ነው።

በሌላ በኩል ስለኢፒስቲሞሎጂ ስናነሳ አይቀሬው ጉዳይ ኦንቶሎጂ ነው። ኦንቶሎጂ የስነ-ፍጥረት ጥናት ነው። የሚያጠነጥነውም ተፈጥሮ የያዘችውን እውነት ይዛ እንድትቆይ ያደረገው ምንድነው? ለሚለው ምላሽ የምንሻበት መንገድ እንደሆነ Crotty እንደሚከተለው ይገልጻል። "Ontology is the study of being. It is concerned with 'what is', with the nature of existence, with the structure of reality as such" (Crotty, 1998:10).

ቀደም ሲል ስለአንድ ነገር ወይም ሁነት ያወቅነው ፍች እንዴት እንዳወቅነው ከሦስቱም የኢፒስቲሞሎጂስት መንገዶች ለማየት ተሞክሯል። ባጠቃላይ ጥናቱ የተከተለው ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴ ነው።

ሌላው ደግሞ ነገሩ ወይም ሁነቱ ምንድነው? የሚለውን ደግሞ ከኦንቶሎጂያዊ አገላለጽ በመነሳት ያን የማህበረሰቡን ዕውቀት ምን ይሉታል። ለእነሱ ምንድነው የሚለውን የምናይበት መንገድ ነው።

ለአብነት ያህል ለዚህ ጥናት መረጃ ለማሰባሰብ የ2008 ዓ.ም. የገዳን ስልጣን ርክክብ ከበራ በጉጂ ዞን ሚኤ ቦኮ ቅዱስ ስፍራ የሚባለው ላይ ታድሜ ነበር። ከተለያዩ አካባቢዎችና የተለያየ ሃይማኖት ተከታዮችንም ለማነጋገር ሞክሬያለሁ። የመጀመሪያዎቹ በእነ ሀጂ መሀመድ ጅብሪል ከምስራቅ ሀረርጌ የመጡት ነበር። ይህን ከበራ ለእርሶ ምንድነው? እንዴት ተመለከታችሁት? የሚል ጥያቄ ሲያቀርብላቸው የእሳቸው መልስ «ይህ የቆዬ ባህላችን ነው። ነገር ግን ከወደ ሀረርጌ ካለው ስርዓት ጋር ከሞላ ጎደል የመመሳሰል ሂደቶች ይታያሉ። ስለእውነት ከተናገርን የጥንቱን ይዘት ይዞ ያለው ይህ የጉጂ ገዳ ነው» (ሀጂ መሀመድ ጅብሪል፣ በ8/6/2008)።

በተመሳሳይ መልክ ለአቶ አዱላ ዋታ፤ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የሆኑት ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡-

እኛ እንደ ኦሮሞነታችን የጋራ የሆነ ባህል አለን፤ ያደግነውም በዚሁ ባህል ውስጥ ነው። አሁንም በውስጣችን አለ። በዚህ ምክንያት ከእነሱም ጋር እንገናኛለን። የገዳ ስርዓትማ ከጥንት ወላጆቻችን ያቆዩትና እኛም ለልጅ ልጃችን የምናስተላልፈው ባህላችን ነው። ነገር ግን ከእምነት አኳያ የምንለያይበት ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ ያን ልዩነታችንን አውቀን ተከባብረን እየኖርን ነው። ሙሉ ለሙሉ ክርስቲያን ነህ ወይ? ብለህ ከጠየከኝ እንደእኔ መልሴ አይደለሁም እልሃለሁ። ምክንያቱም እኛ ቤተሰብ ውስጥ የሁለቱም ሃይማኖት ቅልቅል ነን። ለምሳሌ አባቴ ቤት ሲሄድ በጠዋት ቡና ሲቀርብ በዋቄፋና የጸሎት አካሄድ

| | |
|---|---|
| ‹Ee waaqa dhugoo, | የዱጎ አምላክ፣ |
| waaqa qaaluu, | የቃሉ አምላክ፣ |
| waaqa gadaa, | የገዳ አምላክ፣ |
| kan nagaan nu bulchite, | በሰላም ያሳደርከን፣ |
| nagaan nu oolchi! | በሰላም አውለን። |
| Kan qoonqootti kawwannu | የምንመገበውን ባርክልን! |
| nuu sifeessi! | በማለት ይለማመናል፤ |
| | እኛም በምላሹ፡- |
| nagaan nu oolchi! | በሰላም አውለን። |
| nuuf sifeessi | ባርክልን! እንላለን።» የሚል |

ነበር (አዱላ ዋታ፣ በ11/6/2008፣ ቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ)

በ12/6/2008 ዓ.ም. በስፍራው ሰብሰብ ያሉ ወጣቶች ደግሞ ስለገዳ ዴሞክራሲያዊ ሂደት እየተወያዩ፤ «ዴሞክራሲን መንግስት እራሱ ከገዳ ስርዓት መማር አለበት። እሱ ስልጣን ላይ እያለ የጉጂ ኦሮሞ ስንቴ ስልጣን አስረከበ።» በማለት በማነጻጸር ሁኔታ ያወሩ ነበር። ሌሎች በአራተኛ ደረጃ ነባሩን ማህበረሰብ የሚወክሉ ወይም የባህሉን ማህበረሰብ ሊወክሉ ይችላሉ ያልኳቸውን አዛውንቶች ውስጥ ደግሞ ባሊ ጃርሶ እና ሞና ጎዳና በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን ከበራ እንዴት ተመለከታችሁት? የሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው። እነሱም ሲመልሱ «ለእኛ ይህ ከበራ ከእግዚአብሔር ጋር የምንታረቅበት ነው። የተጣላ የምታረቅበት ነው። በማህበረሰባችን ውስጥ ያለው የልጃገረድና ጎረምሳ ልጅ ጉዳይ ስርዓት የሚበጅለት ነው። ስለዚህ ገዳ ሁሉ ነገራችን ነው ማለቱ ይቀላል።» (ባሊ ጃርሶ፣ 10/6/2008፣ የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ) በመቀጠል ሌላኛው «ይህ ከበራ በውስጡ ሁለት መልዕክት ያለው ነው። አንደኛው የቀድሞው ገዳ ቀደም ሲል ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ስልጣን የሚያስረክብበት (haaganaa kan galchuu) እና

አዲሱ ደግሞ በተራው ከእግዚአብሔር ስልጣን የሚረከብበት ሂደት ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ የቀድሞው ገዳ ስልጣኑን ለአዲሱ ገዳ የሚያስረክብበት ሂደት ናቸው፡፡ ታዲያ በአንድ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ወቅትም ነው፤ በሌላ በኩል ከተለያየ ቦታ ያለን የጉጂ ማህበረሰብ የምንገናኝበትና ስለጉዳዮቻችን የምንወያይበት ወቅት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ከበራ ለእኛ ሁሉ ነገራችን ነው፡፡» (ሞና ጎዳና፣ 10/6/2008፣ የዋደራ ወረዳ ነዋሪ)

ከነዚህ መረጃ አቀባዮቼ የተረዳሁት ነገር በአንድነት የታደሙትን የገዳ ስልጣን ርክክብ ክዋኔ የመጀመሪያውና ሁለተኛዎቹ መረጃ አቀባዮች ከባህል እይታ ፍች ሲሰጡ፣ በመቀጠል መረጃ የሰጡት ደግሞ ከፖለቲካ አኳያ የገዳን ስርዓት ዴሞክራሲያዊነትን ከኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት ጋር በማነፃፀር የገለጹበት ሁኔታ ነበር፡፡ በመጨረሻ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡት ደግሞ ከባህላዊና ሃይማኖታዊ እሳቤ በመነሳት ነበር፡፡ ይህ የሚያመለክተው ማህበረሰቡ ምንድነው? ብለን ስንጠይቀው ከማህበረ-ባህላዊ ሁኔታዊ በመነሳት የሚመልሱልን የዕውቀት ውቅር በመነሳት ነው፡፡ ስለዚህ አንቶሎጂያው አገላለጻቸውን ካየን ከተለያየ ማዕዘን የተመለከቱት እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ለዚህም ይመስላል Abdelhamid እንደማጠቃለያ ሀሳቡን ሲገልጽ፡- በዚህ ዓለም አጥኚዎች እንደሚሉት ባጠኑት ዓለም ውስጥ የራሳቸው የሆኑ አስተሳሰቦች (thoughts)፣ አገላለጽ (interpretations)ና ፍችዎች (meanings) ባላቸው ሰዎች እንደተሞላች አድርገው ይገምታሉ Abdelhamid, (2008:2) ይላል፡፡

### 3.1.1. የጥናቱ ስነ-ዘዴ (methodology)

ጥናቱ የተከተለው የኢትኖግራፊያዊ ስነ-ዘዴን ነው፡፡ ኢትኖግራፊ የአጠናን ዘዴ ማህበራዊ መስተጋብርን የሚያጠና ሲሆን አመጣጡ ከስነሰብ የትምህርት መስክ መሆኑን በመጥቀስ የአጠናን ስልቱ ተፈላጊነት እየጎላ የመጣው ከ1900ዎች ወዲህ ታዋቂ ተመራማሪዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይተው መረጃዎችን የመሰነድ ስልት ተግባራዊ ማድረግ ሲጀምሩ መሆኑን እነ Reeves እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *Ethnography is the study of social interactions, behaviours, and perceptions that occur within groups, teams, organizations, and communities. Its roots can be traced back to anthropological studies of small, rural (and often remote) societies that were undertaken in*

*the early 1900s, when researchers such as Bronislaw Malinowski and Alfred Radcliffe-Brown participated in these societies over long periods and documented their social arrangements and belief systems (Reeves,S. & et al, 2008፡512).*

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደተሞከረው የኢትኖግራፊ አጠናን ስልት በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ እነ Malinowski እና Radcliffe በማህበረሰቡ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይተው መረጃዎችን መሰነድ በጀመሩበት ወቅት የተገኘ የማህበራዊ አጠናን ስልት ነው፡፡ በመሆኑም ኢትኖግራፍ በማህበረሰቡ ውስጥ እየተኖረ የሚጠናውን ማህበረሰብ ባህላዊ ጉዳዮችን በጥልቀት ለማወቅ እየተሳተፉ መረጃዎች የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡

ይህ የጥናት መስክ ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች ያሉት ሲሆን እነሱም 1ኛ.የሚጠናውን ሕዝብ ወግና ልማዳዊ ድርጊቶችን መግለጽ 2ኛ.እነዚህን ወጎችና ልማዶች እንዴት እንደሚከውኑ መግለጽና 3ኛ. የሕዝቡን ባህላዊ አስተሳሰቦችና ስሜቶችን መዝግቦ በግልጽ ማሳየት መሆኑን የMalinowski, (1946) ሀሳብ በማንሳት O'reilly, (2005:8) ያብራራል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን ስነ-ዘዴ በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎችን ለማጥናትና ለማወቅ፤ እንዲሁም በፎክሎር መስክ በጥናቱና በግኝቱም ገለጻ አጥኚዎቹ ሀሳብ የሚካፈሉበት እንደሆነ እነ Sims እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> Ethnography is the process of studying and learning about groups of people, as well as the written description and analysis of those observations. It is through ethnographic research and the written descriptions of their findings in the field that folklorists share their ideas (Sims &Stephens, 2005:202).

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የኢትኖግራፊያዊ ጥናት በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎችን ለማጥናትና ለማወቅ፤ ከዚህ በተጨማሪ በመስክ የተመለከተውን የመግለጽና የመተንተን ሂደት በውስጡ እንደሚያካትት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ስነ-ዘዴ በመጠቀም በማህበረሰቡ ውስጥ በመቆት የተለያዩ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚያጋጥማቸው ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች እንዴት፣ መቼ፣ ለምን ምክንያት፣ በማን አማካይነት እንደሚከወኑና ፋይዳቸውስ ምንድነው? የሚለው ለማየት ተሞክሯል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከስነ-ዘዴው ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ የተለያዩ ዘዴዎች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ እነሱም፡- ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን ውይይትና ንጥል-ጥናት ናቸው፡፡

## 3.1.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች (methods)

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በመረጃ ማሰባሰቢያነት ያገለገሉት ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን ውይይትና የንጥል-ጥናት ዘዴዎች ናቸው፡፡

### 3.1.2.1. ምልከታ

ምልከታ አንዱና ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከናወን ተመራማሪው በአካል ተገኝቶ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው፡፡ ምልከታ የሚለው ቃል ፍች አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን ሁሉንም የስሜት ህዋሳት በማሳተፍ ነገሮችን መረዳትንም ያጠቃልላል፡፡ ማለትም የሚካሄደውን ክዋኔ በዓይናችን ከማየት ባሻገር በትኩረት በማዳመጥ፣ በማሽተትና በመቅመስ የክዋኔውን አጠቃላይ ድርጊቶችን መረዳትና መተርጎም እንደሆነ Goldstein, (1964:77) ያስረዳል፡፡ የምልከታ ቴክኒኮቹም ተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ስለምልከታ ዘዴ (Goldestein, 1964) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡ ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ አጥኚው በባህላዊ ክዋኔ ሳይሳተፍ መረጃ የሚሰበስብበት ቴክኒክ ሲሆን፤ የተሳትፏዊ ምልከታ ደግሞ አጥኚው በማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ በመሳተፍ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የተወሰኑ የከበራ መረጃዎችን ባጋጣሚና በታላሚ ናሙና ላይ ተመስርቼ በምልከታ ዘዴ ሰብስቢያለሁ፡፡ ይኸውም፡- የሚያጠናውን ማህበረሰብ ቋንቋ፣ ባህልና ሃይማኖት በሚገባ ስለማውቅ ከቃሉ ተቋም በውሎ ገብ ለመጀመሪያ ሁለት ሳምንታት ማለትም ከ29/11/2006- 12/12/2006 ዓ.ም. ድረስ ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት አንስቶ እስከ ቀኑ 11:00 ድረስ ከቃሉና ከአማካሪው አቶ ሞኮና ጋር በዋናነት በማሳለፍ፣ ባጋጣሚ የሚከሰቱ ሁነቶችንም በካሜራየና በመቅረጸ ድምፄ እያስቀረሁ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ችያለሁ፡፡ በመቀጠል በ21/2/2007 ከዩኒቨርሲቲው የትብብር ደብዳቤ ከተጻፈልኝ ጊዜ አንስቶ በተለያዩ ቀናት እስከ 14/12/2007 ዓ.ም. ለ20 ቀናት በመመላለስ በየዕለቱ የሚያጋጥሙኝን ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ስርዓታቸውን በማየትና በመጠየቅ መረጃዎችን አሰባስቤያለሁ፡፡

በመጨረሻም በ2008 ዓ.ም.በሚኦ ቦኮ የተካሄደውን የገዳ ስልጣን ርክክብ ከበራ በቦታዉ ቀደም ብዬ በ5/6/2008 ዓ.ም. በመገኘት ከ6/6/2008-13/6/2008 ዓ.ም. የነበሩትን የተለያዩ ከበራዎች በተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ አሰባስቤያለሁ። በዚህ ዘዴ ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ በሚከወኑባቸው ማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ የቀረበው ክዋኔ በማን፣ ለማን፣ መቼ፣ የትና እንዴት እንደተከወነ ተገልጿል። ይኸውም፡- በምልከታ ሽምግልናን፣ የጎንዶሮ ከበራን፣ የፋጭ ከበራንና የቃሉ ጋብቻ ከበራዎች በተወሰኑ ደረጃ በተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ ለመሰብሰብ ተችሏል።

አንድ ኢትኖግራፊያዊ ጥናት ከምልከታ በተጨማሪ ሌሎች ዘዴዎችንም ሊጠቀም ይችላል። ስለዚህ ከምልከታ የሾለኩና በቂ መረጃ ያልተገኘባቸውን በቃለመጠይቅ ዘዴ ለማሰባሰብ ተችሏል።

### 3.1.2.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ አንድ አጥኚ ከመረጃ አቀባዩ ጋር ፊት ለፊት ተገናኝተው ስለሚያጠናው ነገር ያለውን መረጃ በጥያቄና መልስ መልክ የሚያሰባስብበት ዘዴ ነው (Julia, 2008: 208)። ቃለ መጠይቅ የመረጃ ሰጪዎችን የግል ታሪክ፣ የሚያቀርቡትን ጥበብ፣ የዕውቀታቸውንና የስሜታቸውን ፍች፣ የፎክሎራዊ ጉዳዩን ተስተላልፎ፣ እንዲሁም በምልከታ ስላልተገኙ ከበራዎች ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል (Goldstein, 1964:104-108)።

ስለዚህ ይህን ዘዴ በመጠቀም ማህበረሰቡ ስለቃሉ ተቋም አመጣጥ፣ ስለ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምንነትና ዓይነት፣ ስለ ከዋኞቹ ማንነትና አከዋወናቸው፣ እንዲሁም ስለ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ፋይዳዎች ለመረዳት ቃለመጠይቅ በማዘጋጀት ስራ ላይ ውሏል። በዚሁ መሰረት ከሀገር ሽማግሌዎች በተጨማሪ ከተተኪሪ መረጃ ሰጭዎች፡- በታላሚ ናሙናና በጥቁም ናሙና፣ እንዲሁም ያጋጣሚ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ማለትም፡- ከቃሉ አጎት (አቶ ሞኮና ናጋኦ)፣ ከአባገዳ ደንቦባ፣ አባገዳ ሀልቻዬና በተቋሙ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ የቀድሞው ቃሉ ዘመዶች ስለቃሉ አመጣጥ፣ ስለቃሉ ስያሜና የጋብቻ ሃይማኖታዊ ከበራ፣ ስለጉጂ ኦሮሞ አመጣጥና ስለቃሉ ተቋም አጀማመር የሚነገሩ ሚቶችን እንዲሁም ስለ ሁሉቃ ሃይማኖታዊ ከበራዎች፣ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ የሚጨፈሩ ቄጣላዎች ማለትም፡- ማልጊቾ (Malggichoo)፣ ሳማጤ (Samaxee)፣ ቃሉ ቢፊ (Qaaluu biifi) የሚሉትንና አንዳንድ ጸሎቶችን፣ ምርቃቶችንና በቃሉ ተቋም ላይ የነበሩ ተግዳሮቶችን ለመሰብሰብ ተጠቂሜበታለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ በምልከታ ወቅት የተፈጠረውን የመረጃዎች ክፍተት ከማስታወሻዬ በማቅረብ ምላሽ ተገኝቶበታል፡፡

### 3.1.2.3. የቡድን ውይይት

በመጨረሻም በምልከታና በቃለመጠይቅ ያልተብራሩ ሀሳቦችን የበለጠ ለማብራራት፤ እንዲሁም በሁለቱ ዘዴዎች የተገኘውን መረጃ ተዓማኒነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችለን ዘዴ የቡድን ውይይት ነው፡፡ ቡድን ተኮር ውይይት የሚካሄደው በርዕሰ-ጉዳዩ ዙሪያ በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ሰዎችን በመምረጥ፤ በተለያዩ ዘዴዎች ምላሽ ያጣንበትን በቡድን በመሆን እየተወያዩ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡ በቡድን ተኮር ውይይት ላይ የተሳታፊ አባላትን ብዛት በሚመለከት እነ Marshal & Rossman, (2006:114) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡ ‹‹The groups are generally composed of 7 to 10 people (although groups range from as small as 4 to as large as 12 who are unfamiliar with one another and have been selected because they share certain characteristics relevant to the study's questions.››

ይህ ማለት የቡድን ውይይቱ አባላት ከ7 እስከ 10 ሊሆኑ እንደሚችሉና አነስተኛው የቡድኑ አባላት ቁጥር አነስተኛው ከ4 የማያንሱ፤ ከፍተኛው ደግሞ ከ12 እንደማይበልጡና በጣም የማይቀራረቡ ሆነው ሀሳብ ለሀሳብ መቀያየር የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል የቡድን ውይይት በምልከታ ወቅት የተፈጠሩና በቃለ-መጠይቅ ዘዴም ተፈትሸው በቂ ማብራሪያ ያልተገኘላቸው መረጃዎች ላይ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች በቡድን ሆነው በርዕሰ-ጉዳዩ ዙሪያ ስላላቸው ዕውቀት በመወያየት ልዩነቶቹ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአብላጫው ወገን ምን ያመላክታል የሚሉትን መረጃዎች የሚሰበሰብበት መንገድ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በተለያዩ ጊዜያት ከአምስት እስከ ሰባት ከሆኑ አባላት ጋር ማለትም፡- ከአባገዳ፣ የቃሉ አማካሪ ከነበሩትና የሀገር ሽማግሌዎች ጋር በታላሚ ናሙና መረጣ አምስት አባላት ባለው ቡድን፣ በሌላ በኩል የሀገር ሽማግሌዎችና ሴቶችንም ባሳተፈ መልኩ በጥቁም የናሙና ዘዴ በመምረጥ ሁለት ሴቶችና አምስት ወንዶች ካሳተፈ ቡድን ጋር ውይይት በማድረግ አስፈላጊ መረጃዎችን በቪዲዮና በማስታዎሻ ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ የሴቶችን ቁጥር ያሳነስኩበት ምክንያት ሴቶች ብዙን ጊዜ ለቃለመጠይቅ ፈቃደኛ ያለመሆንና ሁሉንም ጉዳይ ወንዶቹ

ይነግሯችኋል የሚል አስተሳሰብ እንዳላቸው ከመስክ ቆይታዬ ተረድቻለሁ። ስለዚህ በነዚህ የቡድን አባላት ጋር የቃሉ መማክርት አባላት ተግባራት ምን ምን እንደሆነ፣ ስለቃሉ ተቋም ተግዳሮቶችና እንደምክንያት የሚያነሷቸው ጉዳዮችንና በካልኣይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች የማረጋገጥ ስራ በውይይቱ ላይ ተካተዋል። ከዚህ በተጨማሪ በሚኤ ቦኮ የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ ላይ ከተሳተፉ ውስጥ ስምንት አባላት የነበሩት ከዶሪዎች፣ ከገዳዎችና ከባቱዎች እርከን ያካተተ ተተኳሪ የቡድን ውይይት በ8/6/2008 ዓ.ም. እና በ10/6/2008 ዓ.ም. ለሁለት ጊዜ በማካሄድ መረጃ ተሰብስቧል። ሌላው ሴቶችን ለብቻ ያሳተፈ 5 አባላት ያለው አንድ ቡድን በማዋቀር በ26/8/2007 ዓ.ም. በቃሉና በገዳ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ ሴቶች ያላቸውን ሚና መረጃ ተሰብስቧል።

### 3.1.2.4. **ንጥል ጥናት** (case study)

ንጥል ጥናት ልክ እንደ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ ሁሉ የጥናት ዘዴ ስር እንደሚመደብ Crotty, (1998:5) ያስረዳል። ንጥል ጥናት የሚባለው አንድ በተወሰነ ድርጅት፣ ፕሮግራም ወይም ሂደት ላይ የሚደረግ የጥናት ሪፖርት እንደሆነ Yim'ን በመጥቀስ እነ *Peoples,J. and Bailey,G., (1991:156)* እንደሚከተለው ያስረዳሉ። ‹‹*Report of research on a specific organization, program, or process (or some set of these) are often called Case Studies (Yim, 2003). Case Studies rely on historical and document analysis, interviewing, and typically, some forms of observation for data collection.*››

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ውስን ምክንያታዊ ጥናቶች የሚመሰረቱት በታሪካዊና ሰነድ ትንተና፣ቃለመጠይቅ በማድረግና በምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ወካይ በሆኑትና የተቀረውን ውጤት ሊያመላክቱ በሚችሉ መሆኑን ነው።

በሌላ በኩል እነ Best and Jems V., (1993:19) ንጥል ጥናትን ሲበይኑ፡- <<...case study is a way of organizing social data for the purpose of viewing social reality. It examines a social unit as a whole. The unit may be a person, a family, a social group, a social institution, or a community.>>

ከጥቅስ ለመረዳት እንደተቻለው ንጥል ጥናት ለማህበራዊ እውነታ አተያይ አገልግሎት የሚውሉ ማህበራዊ መረጃዎችን ማደራጃ መንገድ ነው። የተወሰነ የማህበረሰብ አካልን

በመውሰድ እንደ አጠቃላይ የሚመረምር ነው፡፡ ያ የማህበረሰብ አካል ምናልባትም ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰባዊ ቡድን፣ ማህበረሰባዊ ተቋም ወይም ማህበረሰብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ዘዴ በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ ግለሰቦች በግልም ይሆን በተወሰኑ ቡድን ሆነው ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክዋኔ ሲፈጽሙ መሠረታዊ መመሪያቸው በጋራ ያዋቀሩት እውቀት ይሆናል፡፡ ይህን ለማረጋገጥና ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ በተወሰኑት ከበራዎች ላይ የተደረጉና የቀረቡ ንጥል ጥናቶች በተግባር የተፈተኑ ውጤቶች ስለሆኑ ድርጊቶቹ የተከናወኑ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በቃሉ ጋብቻ ከበራ አንድ፣በጎንደሮ ከበራ ሁለት፣በፋጭ ከበራ ሁለት፣ በሁሉቃ አንድ ንጥል ጥናቶችን በማካሄድ በተወሰነ ደረጃ የዚህን ጥናት ዓላማ ለማሳካት ተችሏል፡፡

### 3.1.3. የናሙና መረጣ ሂደት

በዚህ ጥናት በመረጃ አቀባይነት የታቀፉት በከበራዎች ላይ ካላቸው ንቁ ተሳትፎና በውስን ጥቁም ናሙና (snowball sampling)፣ ታላሚ ናሙና (purposive sampiling) እና ያጋጣሚ ናሙናን በማቀናጀት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በፎክሎር ውስጥ የከዋኞቹና የታዳሚውን ስሜት ለማጤን፣ የዕድሜና ፆታ ተዋፅኦ ለማካተት በተገኘ ናሙና (Available Random Sampling) አመራረጥ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የጥናቱ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት ለባህሉ ካላቸው ቅርበትና ዕውቀት አንፃር ከተመረጡት ቦታዎች ማለትም፡- ከቃሉ ተቋምና ከሚኤ ቦኮ በተጨማሪ ከአባያ ወረዳ፡- ከከላልቱ፣ ሳማሮ፣ ቡናታና ዳባቃ ቀበሌዎች ለቃለ-መጠይቅና ለቡድን ውይይት ወደ 60 ሰዎች የተመረጡ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ሴት 8 ሲሆኑ፣ 52 ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት አንደኛ ለሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ቅርበት አላቸው፣ ስለጉዳዩ ያውቃሉ የተባሉትን በጥቁም ናሙና (snowball sampling) መረጣ የተመለመሉ ሲሆን፤ እንደ ቃሉ፣ የቃሉ አማካሪና ገዳዎችን ደግሞ በታላሚ ናሙና (purposive sampiling) አመራረጥ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ በተገኘ ናሙና (Available Random Sampling) የተወሰዱ ናቸው፡፡ በዚህ የመረጃ አቀባዮች መረጣ ላይ የሴቶች ቁጥር ሊያንስ የቻለበት ምክንያት በባህሉ ሴቶች ቢያውቁም ከወንዱ እኔ አውቃለሁ ብለው እንደመናገር ይቆጠርብናል በማለት ስለማይሳተፉ ነው፡፡

## 3.2. የመረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን በመስክ ቆይታ ከቃሉ ተቋም፣ ከሚኤ ቦኮና ሌሎች መንፈሳዊ ስፍራዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት አማካኝነት የተሰበሰቡ ሲሆኑ፤ ይኸውም፡- ከአባገዳዎች፣ ከዶሪዎች፣ ከዩባዎች፣ ከቀድሞ ሀዳ አንባ፣ ከሀገር ሽማግሎዎችና ከማምለኪያ ስፍራዎች በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶ ግራፍ፣ በቪዲዮና በማስታወሻ ተሰባስበው፣ ከተቀናበሩ በኋላ የተተነተኑ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስለከበራዎች፣ ስለቁሳዊ ባህል፣ ስለሚቶችና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የሚገኙባቸው ዶክመንቶችን ከቤተ-መጻህፍት፣ የድረ-ገጽ መረጃዎች፣ ተዛማጅ ጥናታዊ ስራዎች፣ ዶክሜንተሪ ፊልሞች ላይ በጥናቱ ዙሪያና ከጥናቱ አካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንድፈ ሀሳቦችና ዳራዊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መቼት

መቼት ማለት አንድ ፎክሎራዊ ቅንጣት የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ነው፡፡ መቼት ከሚከወንባቸው ሁኔታ በሦስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡- ተፈጥሯዊ መቼት፣ አርቲፊሻል መቼትና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት በመባል ይጠራሉ፡፡ ተፈጥሯዊ መቼት የሚባለው ባህሉ የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ነው፡፡ አርቲፊሻል መቼት ደግሞ ከአውዱ ውጭ ማንኛውም መረጃ አቀባይ በተገኘበት ጊዜና ቦታ ተመራማሪው የሚሰበስብበት መቼት ነው፡፡ ሌላው ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት የሚባለው ሲሆን፤ ተፈጥሯዊ የሚመስል መቼት በማዘጋጀት፣ በማደራጀትና በማቀናበር ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ለማሰባሰብ የሚያስችለን የመቼት ዓይነት ነው (ፈቃደ፣ 2002፡122-124)፡፡

የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች የሚከወኑት ወቅት ጠብቀው መሆኑና በክዋኔው ወቅትም ዝርዝር ጉዳዮች ሾልከው ሊያመልጡ ስለሚችሉ፤ የተጓደሉትን አሟልቶ ለመሰብሰብ ሦስቱም በጥምረት መጠቀም ይመከራል (ዝኒ ከማሁ)፡፡ ይህም ጥናት የተወሰኑ መረጃዎችን ማለትም፡- የቃሉ ጋብቻ ከበራ፣ የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ፣ የተወሰነ የጎንዶሮ ከበራዎችን ከተፈጥሯዊ መቼት ላይ የተሰበሰቡ ሲሆን፣ ሌሎችን መረጃዎች ደግሞ እንደ ፋጭ ከበራና የሁሉቃ ከበራ ከአርቲፊሻል መቼት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ይህንን ጥናት ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የፎክሎር ዘውጎችን ለመቅረፅ የሚያስችሉ መሣሪያዎችን መጠቀም የግድ በመሆኑ፤ ይኸው ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ከእነሱም ውስጥቪዲዮ

ካሜራ አንዱ ሲሆን አውዱ እስከፈቀደ ድረስ ለሁሉም የፎክሎር ዘውጎች መቅረጫነት ለመጠቀም የተሞከረ ቢሆንም በሙሉ ሳይሆን በከፊል ለመጠቀም ተችሏል፡፡ ነገር ግን በሚኤ ቦኮ በተካሄደው የክዋኔ ቀረጻ ላይ ግፊያ፣ በስርዓት አስከባሪዎች የቀረጻ ክልከላ ስለነበር የተወሰኑ ቀረፃዎች ብዥታ ሲኖራቸው፤ የተዘለሉም ነበሩ፡፡ በተሳትፏዊ ምልከታ ወቅት ደግሞ በረዳት የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያ አማካይነት የተካሄዱ ቀረጻዎችም አሉ፡፡

ቃላዊ የሆኑ የፎክሎር መረጃዎችን ከአውዱ ለመሰብሰብ እና ለቃለመጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያነት ደግሞ መቅረጸ ድምጽን ተጠቂሜያለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፎቶ ካሜራ የቃሉን ተቋም፣ መንፈሳዊ ስፍራዎችን፣ ቁሳዊ ባህሎችን የሚያመላክቱ ተምሳሌትነት ያላቸውን መረጃዎች ለመቅረጽ በተግባር ላይ ውሏል፡፡

## 3.5. መረጃዎችን መሰብሰቢያ አንጻሮች

አንድ የፎክሎር ተመራማሪ መረጃዎችን ሲያሰባስብ ከሁለት አንጻሮች ሊሆን ይችላል፡፡ እነሱም ውስጣዊና ውጫዊ አንጻሮች (emic & etic perspective) ይባላሉ፡፡ እነሱም፡-

### 3.5.1. ውስጣዊ አንጻር

ይህ አንጻር ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ከመስክ መሰብሰብ ያለበት የባህሉ ባለቤት የራሱን ባህል በሚገልጽበት መንገድ መሆን አለበት፡፡ ይኸውም አጥኚው በመስክ ቆይታው ወቅት ከማህበረሰቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥሮ፣ ማህበረሰቡን በወጉ ተረድቶ ዝርዝር ጉዳዮችን መሰብሰብና ለሌላው ማሳየትን ይፈልጋል (O'reilly, 2005:84)፡፡ በዚህ መሰረት በኢትኖግራፊ ስነ-ዘዴን በመጠቀም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለምን እንደሚከወኑ፣ እንዴት እንደሚከወኑና ለማህበረሰቡ ምን ምን ፋይዳዎች እሏቸው የሚሉትን ለማየት ተችሏል፡፡

### 3.5.2. ውጫዊ አንጻር

ውጫዊ አንጻር የሚባለው ደግሞ የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻሩ ለባህላዊ ጥናቱ አስፈላጊ የሆነ አመለካከት ነው፡፡ ይኸውም፡- ከባህሉ ውጭ የሆነው ተመራማሪ በሚያጠናው ባህላዊ ጉዳይ ላይ ያለውን አመለካከት የሚያንፀባርቅበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ የተመራማሪው አመለካከት በአሉታዊ ዓይን የሚታይ አይደለም፡፡ ሳይንሳዊ አመለካከት ነው፡፡ ለውስጣዊ አመለካከት ትርጓሜ መስጠትን ይመለከታል፡፡ በዚህ አካሄድ የተመራማሪው ተግባር የውስጣዊ አመለካከትን፣

ትርጓሜን ማካተት ብቻ ሳይሆን ከባህሉ ውጭ ላለውም ተደራሲ ግልፅ ሊሆን በሚችል መንገድ ማሳየት መቻል ነው፡፡ የውስጣዊና የውጫዊ አመለካከትን ሚዛን መጠበቅ ከአጥኚው ይጠበቃል፡፡ ይህ ሚዛን የተዛባ ከሆነ ነው አሉታዊ ገፅታ የሚኖረው፡፡ አጥኚው የሚያጠናውን ህዝብ (ቡድን) እንቅስቃሴና እምነት ገለልተኛ ሆኖ ማየትና መልሶ ማሳየት እንጂ የራሱን ሃሳብ ሊጭንበት አይገባም፡፡ ባህሉን በደንብ ተገንዝቦ ለማያውቀው ውጫዊ ተመልካች ሳያዛባ ማሳወቅ አለበት (Fetterman, 2010)፡፡ ስለዚህ አጥኚው የአካባቢ ተወላጅ በመሆኔ የውስጣዊ አንጻር እንዳያመዝንብኝ ሁለቱንም በማጣጣም ለመስራት ጥረት አድሪጊያለሁ፡፡

## 3.6. የተሰበሰቡት የመረጃ ዓይነቶች

ለዚህ ጥናት ስለቃሉ ሃይማኖታዊ ክበራዎች ምንነትና ፋይዳዎቹን ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህም የተሰበሰቡት የመረጃ ዓይነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በተያዩ መልኮች የሚገኙ ናቸው፡፡ ይኸውም፡- በቃላዊ ግጥሞች መልክ ያሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ጭፈራዎች (qeexalaa) ሲሆን እነሱም፡- ማልጊቾ (Malggichoo)፣ ሳማጤ (Samaxee)፣ ቃሉ ቢፊ (Qaaluu biifi) የሚሉትንና አንዳንድ ጸሎቶችን፣ ምርቃትና እርግማንን፣ በሚቶች መልክ ደግሞ ስለቃሉ አመጣጥ (Dhuftee Qaalluu)፣ ስለቃሉ ስያሜና ጋብቻ (Dhuftee Moggaasaafi Gaa'ila Qaalluu)፣ ስለጉጂ ኦሮሞ አመጣጥ (Dhuftee Gujii Oromoo)፣ ስለቃሉ ተቋም አመጣጥ (Dhuftee Galma Qaalluu)፣ ስለገዳና ስልጣነ ሢመቱ አመጣጥ (Dhuftee sirna muudafi gadaa)፣ ስለገፀ-በረከት/ስጦታ/ አሰጣጥ አመጣጥ (Dhuftee Gumaacha kennuufi fudhachuu) የተሰበሰቡ ሲሆኑ፤ ሌላው ከቁሳዊ ባህሎች ደግሞ ባህላዊ ምግቦች (Nyaata aadaa) ማለትም እንደ ጠጅ/ቦካ (booka)፣ ቡና ቃላ (buna qalaa)፣ ማር (damma)፣ ቅቤ (dhadhaa)፣ ገብስ (garbuu)፣ ወተት (aannan) እና የመሳሰሉትን፤ ከሃይማኖታዊ ቁሶች (Meeshaale amantaa) ውስጥ ደግሞ እንደ ከርቤ (qunbii)፣ ቦኩ (bokkuu)፣ ካላቻ (kallacha) እና የመሳሰሉትን፤ ሌላው ሃይማታዊ ክበራዎች፡- የገዳዎች ስልጣን የማጽደቅ ሃይማኖታዊ ክበራ፣ የጎንዶሮ፣ የሁሉቃ፣ የፋጭ እና የቃሉ ጋብቻ ሃይማኖታዊ ክበራዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በግጭት ማስወገጃ መዋቅሮች ስር (ግለ-ወቀሳ፣ ሽምግልና (በቤተሰብ፣ በንዑስ-ጎሳና በጎሳ ደረጃ)፣ በገዳና ቃሉ ተቋማት)፣ በገዳና ቃሉ ተቋማት ላይ ስለነበሩ ተግዳሮቶች፣ ስለ ቃሉና ቃሊቻ አንድነትና ልዩነት፣ ከካልኣይና ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች በታላሚ ናሙና፣ በጥቁም ናሙና እና ያጋጣሚ ናሙና ዘዴዎችን በመጠቀም ከመረጃ አቀባዮቹ ተሰብስቦ በተግባር ላይ ውለዋል፡፡

### 3.6.1. ትራንስክሪፕሽን

ከማህበረሰቡ የተገኙትን መረጃዎች ከመተርጎሙ በፊት እንደ ወረደ በአፋን ኦሮሞ ወደ ፅሁፍ ተቀይሯል። ይህም ከመቅረጸ ድምፅና ከቪዲዮው መላልሶ በማዳመጥ ቃል አቀባዩ በትክክል የተጠቀሙባቸውን አገላለፆች ለማስቀመጥ ተሞክሯል። ከድምፅ ጀምሮ ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን ቃላትና ቅደም ተከተላዊነት የአነጋገራቸውን ለዛ ባለቀቀ መልኩ ለማስፈር ጥንቃቄ ተደርጓል። በአውድ ላይ በመመስረት ለማስፈር ተሞክሯል።

### 3.6.2. አተረጓገም

ይህ ጥናት የተካሄደው በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ተቋምና አካባቢው ላይ ሲሆን መግባቢያ ቋንቋቸው ደግሞ አፋን ኦሮሞ ነው። ስለዚህ ለጥናቱ የሚያስፈልጉት መረጃዎች የተሰበሰቡት በምንጩ ቋንቋ (በአፋን ኦሮሞ) ሲሆን፤ በመቅረጸ ድምፅና በቪዲዮ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመጀመሪያ በመሰክረብ፣ በማስታወሻ የተያዙትን ጭምር ቃል በቃል (ቀጥተኛ ትርጉም)፣ አቻ ትርጉምና አውዳዊ ትርጉምን በመጠቀም ወደ ታላሚው ቋንቋ (ወደ አማርኛ) ለመተርጎም ተሞክሯል። በመረጃ ትርጉም ወቅት በተቻለ መጠን በምንጩ ቋንቋ ለማስተላለፍ የታሰበውን መልዕክትና ለዛ እንዳያጣ ጥረት ተደርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ታላሚው ቋንቋ ሲተረጎም በአማርኛ ቋንቋ መልዕክቱ ሳይዛባ ለዛውን በጠበቀ መልኩ ለመተርጎም ተሞክሯል። ነገር ግን አንዳንድ ቃላትም ሆኑ ሀረጋት በአማርኛ ቀጥተኛም ሆነ አቻ ትርጉም ሲታጣላቸው በምንጩ ቋንቋ በማስቀመጥ ስለጉዳዩ ማብራሪያ በመስጠት የተገለጸበት ሁኔታም አለ።

## 3.7. ከመስክ ውሎ የተገኘ ልምድ

በመጀመሪያ ደረጃ ከካልኣይ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን መልክ በማስያዝ፤ ከትምህርት ክፍሉ የሚሰጠውን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ፤ ከአባያ ወረዳ አስተዳደር እና የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤቶች ከሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመተዋወቅ፣ ስለ ጥናቱ ዓላማና የአጠናን ሁኔታ በመግለፅ የትብብር ደብዳቤ ከወረዳው መስተዳድር አካል በመውሰድ ወደ መስክ ወጣሁ። የመጀመሪያ ጉዞዬን ወደ ቃሉ ተቋም ነበር። በወቅቱ ከአባቃሉ አጋ ሳቆ ጋር በመተዋወቅ የተሰጠኝንም የትብብር ደብዳቤ በማሳየት ስለሄደኩበት ጉዳይም አስረዳሁ። በደብዳቤው ብቻ ከማመን፤ «ከአስተዳዳሪው ስልክ ሊደወልልኝ ይገባል» አሉኝ። እዚያው ሁኜ ወደ አስተዳዳሪው ስልክ ብንሞክርም በወቅቱ መስመሩን ማግኘት አልቻልንም። በቀጣይ ጊዜ ቀደም ሲል ለሁለተኛ ዲግሪዬ ማሟያ የሰራሁትን ጥናትና አንዳንድ መረጃዎችን በመያዝ

አሳይቼ፤ ስለ ሁኔታውም በመግለጽ፣ በቀጣይ ደግሞ የተሻለ ስራ ለመስራት መዘጋጀቴን በጥሞና ለማስረዳት ሞከርኩ። በተወሰነ ደረጃ እያቅማሙ ለሀሎና ዌሲቱ ገዳዎችና ካሎዎቼ መልዕክት አስተላልፋለሁ ሳምንት ተመለስ ተብዬ ተለያየን። በሳምንቱ ረዳት የካሜራ ባለሙያ በመያዝ ስሄድ መልዕክት እንዳላስተላለፉና የመማክርት አባላቱም እንደማይመጡ ተነገረኝ። በወቅቱ ለጊዜውም ቢሆን ፊቴን ወደሌላ አቅጣጫ እንዲያዞር ተገደድኩ። ከዚያ በወቅቱ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ የነበሩት አቶ ደሳለኝ ሆርዶፋን ስለሁኔታው አማከርኳቸው። እሳቸውም ቃሉን በተመለከተ አቶ ሞኮና ናጋኦ (የቃሉ አጎትና የቅርብ አማካሪ) ብታገኛቸው ሁሉንም ነገር ያቀሉልሃል አሉኝ። የቃሉ አንቢታ እንደሚመስለኝ ከሆነ ከአስተዳደር በኩል ያስተላለፉላቸው መመሪያ ያለ ይመስለኛል። ይሁን እንጂ እውነትም ከአቶ ሞኮና ናጋኦ ጋር በመተዋወቅ ለስራው አስረድቼ በቀጠሮ ተለያየን። ከአቶ ሞኮና ጋር በቀጠሮው ዕለት የቃሉን ገልማና የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይፈጸምባቸዋል በሚባሉ ቦታዎች በመዟዟር ስለሃይማኖታዊ መቼቱና የነበራቸውን አገልግሎትና አሁን ያሉበትን ሁኔታ በመጠየቅ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን የመሰብሰብ ሥራ አከናወንኩ።

በሁለተኛው ዙር ስምሪት ደግሞ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን በአቶ ሞኮናና በሌሎች የሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት በማፈላለግ፣ ስለጥናቱ አሳውቆ አብሮ ለመስራት በማስማማት በኩልም የአቶ ሞኮና ሚና ከፍተኛ ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለባህሉና ሃይማኖቱ ያውቃሉ የሚባሉ ሽማግሌዎችን አንዳንዴ ጠጅ ቤት እንደሚገኙ ሲጠቁሙኝ፤ እዚያው ድረስ በመሄድ በመጋበዝና እኔም አብሬ እየጠጣሁ እዚያው የሚከወነውን ምርቃት፣ በስርዓት እየተቀባበሉ ቀጠሮ ሲያስዙኝ በራሱ ፎክሎር ነበር።

በተለይ የሀሎው አባገዳ ከአካባቢያቸው ብዙም ርቀው ስለማይሄዱ እዚያው እስከ አምስት የሚደርሱ የሀገር ሽማግሌዎችን አዘጋጅተው እንዲጠብቁኝ በማድረግ ለመረጃ አቀባዮቼ ተረጋግተው መረጃ ለመስጠት እንዲያመቼኝ ከከተማ ምግብና ጠጅ በጀሪካን በመያዝ ከረዳት የካሜራ ባለሞያው ጋር በመሆን በሞተር ሄደን መረጃ ለማሰባሰብ ችለናል። በዚህም ስኬታማ ሆኜ ተመልሻለሁ። ምክንያቱም የገዳው ተቋም ወጣ ያለ ስለነበር፤ ለምሳና ውሃ ፍለጋ ሰበብ ተሰላችተው እንዳይበታተኑብኝ ረድቶኛል።

በመጨረሻም በጉጂ ዞን በሚኤ ቦኮ ያጋጠሙኝ ችግሮች ደግሞ በዋናነት በገዳ ስርዓት ውስጥ በገዳ የስልጣን ሽግግሩ ላይ የሚሳተፉት ከኡራጋ፣ ከሆኩና ከማቲ ገዳዎች ውስጥ ሦስት ሦስት

ቡድኖች ነበሩ። እነሱም፦ ራባ፣ ዶሪና ገዳ ናቸው። እነዚህ ሦስቱም ቡድኖች ያረፉበት ቦታ የተለያየና በመጠኑም ቢሆን የተራራቁ ስለነበሩ፤ ከዚህ ጋር ተያይዘው እያንዳንዳቸው ደግሞ የየራሳቸው ውይይትና ዝግጅቶች ስለነበሯቸው መረጃ ለማሰባሰብ ከወዲያ ወዲህ መሯሯጥ ነበረበረኝ። ስለዚህ መረጃዎችም እንዳያመልጡኝ በማሰብ፤ እንዳጋጣሚ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ጓደኞቼን በተወሰነ አቅጣጫ በመመደብ በአትክሮት እንዲቀርጹልኝ በማድረግ የተፈጠረውን ክፍተተ ለመቅረፍ ተሞክሯል።

በመጨረሻም በእነ አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ አቶ አባባ ቶተ፣ጎበና ቶተ እና ወ/ሮ ረጋቱ በሪሶ (የቃሉ ቤተሰቦች) አማካይነት ቃሉን በማግባባት መረጃ እንዲሰጡና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንም በማማከር በቪዲዮ እና ፎቶ ግራፍ በማንሳት መረጃዎቼን ለማጠናቀር ችያለሁ።

## 3.8. የምርምር ሥራ ሥነ-ምግባር

አንድ ተመራማሪ ወደ መስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በሚሰማራበት ወቅት ሊያጋጥሙት የሚችሉትን ችግሮችን ቀድሞ መገመትና የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ እንዳለበት ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል። ይኸውም የጥናቱ አውድ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እንደመሆኑ መጠን፤ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እንዲህ በቀላሉ ይገኛል ማለት ዘበት ነው። ይሁን እንጂ ያለነሱ መልካም ፍቃድ የተቋሙን ህልውና፣ የመረጃ ሰጪዎችን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ መረጃ ለማግኘት መጣር ከምርምር ስራ ስነ-ምግባር አኳያ አግባብነት የለውም። ስለዚህ አጥኚው ይህን ከግንዛቤ በማስገባት በመጀመሪያ የተጠኚውን ህዝብና የመረጃ አቀባዩን ባህልና እምነት ማክበርና ከስነ-ምግባሩ ውስጥ አንዱ በመሆኑ ባህሉና ሃይማኖቱ በሚፈቅደው መሰረት ሰላምታ በመጠየቅ፤ አቀራረቤን ከመግቢያው ለማስተካከል ጥሪያለሁ። ከዚያም ለመረጃ አቀባዩቼ ስለምርምሩ ዓላማና ውጤት በሚገባ በማስረዳት፣ መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆናቸውን በመጠየቅ፣ መረጃውን በመስጠታቸው ለችግር እንዳይጋለጡ ግላዊ መብታቸውን በመጠቀምና በመወያየት አላስፈላጊ የምስልና የድምፅ ጥበቃ፣ ስም አለመጥቀስ ተደርጓል፣ ስለሃይማኖታዊ ተቋሙ ሚስጥሬነውያሉትንለመጠበቅ በመስማማት፣ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማያሳድር መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ተችሏል።

በሌላ በኩል መረጃ አቀባዮች ለዚህ ስራ ሲሉ ከአንዱ ሃይማኖታዊ መቼት ወደ ሌላው ሲንቀሳቀሱ የትራንስፖርት፣ የምሳና የመጠጥ ወጪያቸውን በመሸፈን፣ በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ምግብና መጠጥ በማዘጋጀት እዚያው እየተወያየንና አብሮ በመቋደስ በቤተሰባዊ ስሜት በመግባባት መረጃዎችን ያለአንዳች ስጋት ለመለዋወጥ ተችሏል።

# ምዕራፍ አራት

## የጉጂ ኦሮሞ ማሕበረ-ባሕላዊ ዳራ

### 4.1. የጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ፣ አካባቢያዊና ታሪካዊ ዳራ ዳሰሳ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ስለጉጂ ኦሮሞ መገኛ አካባቢ፣ ስለዘር ሀረጋቸው፣ የመግባቢያ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ መተዳደሪያና ሌሎችም በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

#### 4.1.1. የጉጂ ኦሮሞ መገኛ

የጉጂ ኦሮሞ በአሁን ወቅት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ አስራ ዘጠኝ ዞኖቹ ውስጥ ባብዛኛው በቦረናና ጉጂ ዞኖች ውስጥ ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ከክልሉ ውጭ ደግሞ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ፡- በሲዳማ ዞን፣ በወንዶ ገነት አካባቢ ከሚኖሩት ውስጥ ወደ 8 ቀበሌዎች በሪፈረንደም እራሳቸውን ችለው በሼሎና ኡቱ ገዳ ተደራጅተው ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በብላቴ፣ በነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክና በአርባ ምንጭ ከተማ አቅራቢያ ለዘመናት ሰፍረው እንዳሉ (Tadesse, 2004፡13; አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ አባገዳ ሀልቻዬ፣ አባገዳ ደንቦባ) ያስረዳሉ፡፡

የጉጂ ኦሮሞ ከጥንት ጀምሮ በደቡብ ከቦረናና ከጋሪ ጋር፣ በሰሜን ከጌዴኦ፣ ከሲዳማና ከወላይታ ጋር፣ በደቡብ-ምዕራብ ከቡርጂ፣ ከኮይራ (ኮሬ) እና ከጋሞ፣ በምስራቅ ደግሞ ከአርሲ ኦሮሞ ጋር በዋናነት ይዋሰናሉ:: የጉጂ ኦሮሞን አንዳንድ አጎራባቾቻቸው ጃምጃም ወይም ጃምጃሚቱ ብለው ይጠሯቸዋል (Tadesse, 2004፡13)፡፡ ከነዚህ አጎራባቾቻቸው ጋር በተለያዩ ምክንያቶች ይጋጩ እንደነበር Tadesse, (1994:312) & Asebe, (2007፡53) ያስረዳሉ፡፡ በተለይም የጋራ የሆነ የመግባቢያ ቋንቋ፣ ባህልና ወግ ያላቸው፤ ሦስቱ ባላንጣዎች (siddi-saddin) በመባል የሚታወቁት ጉጂ፣ ቦረናና አርሲ አንዱ ከሌላኛው ጋር መዋጋታቸውን እንደ ጀብድም ይቆጥራሉ (ዝኒ ከማሁ)::

በአብዛኛው ጥናታዊ ስራዎች ውስጥ የጉጂ ኦሮሞ በሦስት ከንፌድሬሽን (ኡራጋ፣ ማቲና ሆኩ) እንደሚከፈሉ (Van de Loo,1991; Haberland,1963; Hinnant,1977; Tedecha,1988; Al-Amin,1998; & Tadesse,2004 ያወሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንደ አራተኛ ኮንፌድሬሲ የሚታወቁ አላብዱ የሚባሉ ጎሳዎች አሉ፡፡እያንዳንዳቸው ኮንፌድሬሽን የየራሳቸው ገዳ፣ የአሰፋፈር ቦታና ወሰን ያላቸው ሲሆን፤ የአላብዱው ገዳዎች ማለትም፡- የሀሎና ዌሲቱ ገዳዎች ግን በቃሉ ስር

ያሉና ከቃሉ ጋር በቅርበት የሚሰሩ መሆናቸው ለየት ያደርጋቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የገዳ ስልጣን ሽግግራቸውም የዘር ሀረግ ተከትሎ ከአባት ወደ ልጅ መሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያ ሦስቱ ገዳዎች ግን ከቃሉ ጋር የሚገናኙበት ጉዳዮችና ጊዜያት የተወሰኑ ናቸው፡፡ በማህበራዊ ግንኙነታቸው ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የደም/የስጋ ዝምድና ስላላቸው ከአጎራባች ጎሳዎች ጋር ግጭቶች ሲፈጠሩ አንዱ ለሌላው የመድረስና የመረዳዳት ባህል አላቸው፡፡ ለግጦሽና ለሌላ ጉዳይ አንዱ ወደ ሌላው በመጎዳኘት ያሳልፋሉ፡፡ እነዚህም ጎሳዎች አንዱ ከሌላው ጋር መጋባት ይችላሉ፡፡



ምስል፡-1 የኦሮሚያ ዞኖች መገኛ የሚያሳይ ካርታ (ምንጭ፡- CSA,2007)




ምስል፡-2 በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር፣ የቦረናና ጉጂ ዞኖች የሚያሳይ ካርታ (ምንጭ፡- CSA,2007)

ስለጉጂ ኦሮሞ ኮንፌድሬሽን ክፍፍልና የእርስ በርስ ግንኙነት በተመለከተ Abiyot, *(2005:310)* በተመሳሳይ መልኩ እንደሚከተለው ያስረዳል፡፡

> *Guji is a confederation of four independent, but by no means exclusive, subgroups known as Uraga, Mati, Hoku and Alabdu. The latter is in turn a confederacy of two interdependent groups called Halo and Woyestu. Despite their autonomy in their respective territories and right of exercising Gada system under their own leaders, each of these components of the confederation is mutually interdependent. They allied together in times of warfare, help each other during natural calamities and economic crisis, and more importantly conduct Gada rituals together.*

በሌላ መልኩ የጉጂ ኦሮሞ ሦስቱ እራሳቸውን የቻሉ ጎሳዎች ገዳዎች እንዳሉና አንድ የሉባ ፖለቲካዊ መሪዎች የሌላቸው ጎሳ እንዳሉ (Tedecha, 1988:17) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> *The only unique case is that of the Alladu group of which territorial unit is appeared as cradle of life and not that of authority as independent part. As a matter of fact Alladu dose not have the right to yield the leaders of the luba political office. From this follows, therefore, that the Guji people is a confederation of three independent tribes and one neutral group.*

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የአላብዱ ጎሳ የራሳቸው የሆነ የሉባ ፖለቲካዊ መሪዎች ተቋም መመስረት አይችሉም፡፡ ይህ ማለት በስሩ ያሉት ገዳዎች እንደ ሌሎቹ ሦስቱ ገዳዎች በየስምንት ዓመቱ የስልጣን ሽግግር የሚያደርጉ ሳይሆን፤ ልክ እንደቃሉ፤ የነበረው አባገዳ ከዚህ ዓለም ሕይወቱ ሲያልፍ ከልጆቹ መካከል የመተካት አካሄድ ስለሚከናወን ነው፡፡

እንደ አለማየሁና ሌሎች (1998:200) ገለጻ የሀሎ እና የዌስቱ ጎሳዎች አሰፋፈርና መስፋፋት ወደ ሰሜን አቅጣጫ ያደረጉበትን ምክንያት በተመለከተ የተለያዩ ሀሳቦች እንዳሉ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> *አንደኛ የአላብዱ ጎሳ መጀመሪያ ላይ የኡራጋ ጎሳ አካል ነበሩ፡፡ ከዘመናት በኋላ የጎሳው ቁጥር እጅግ በመበራከቱ ተለይቶ እራሱን የቻለ ጎሳ ሊሆን ችሏል፡፡ ሁለተኛው የአላብዱ ጎሳ አሰፋፈርና መስፋፋት የሰሜን አቅጣጫ የያዘው አንድ የሀሎ ጎሳ አባል ሌላ ጉጂ ሰው በመግደል እርቅ ሳይፈጽም በምስራቅ አባያ ወደሚገኝ አካባቢ ሸሽቶ በመስፈሩ ነው ይባላል፡፡ በዚህ ጥናት ሂደት በተሰበሰበ ትውፊት ደግሞ የተለየ ምክንያት ይቀርባል፡፡ ይኸውም በጉጂ የቃሉ ልጅ በአንድ የደቡብ ጉጂ ጎሳ አባል በመገደሉ ቃሉ ቅሬታ አድሮበት የአላብዱ ጎሳ ግዛት ወደሚገኝ የአሁኑ ማዕከል እንደተንቀሳቀሰና ከዚያን ወቅት ጀምሮ የጉጂ ቃሉ ከአቢቱ ሀረግ በሚወለዱ ጉጂዎች ሊያዝ ችሏል፡፡*

ከሌሎች በተሻለ መልኩ Haberland (1963:781) የጉጂ ኦሮሞ አሰፋፈርና አደረጃጀት ሲገልጽ፣ በመጀመሪያ በሁለት የሰሜናዊ ጉጂ ወይም አላብዱና የደቡባዊ ጉጂ ኮንፌድሬሺኖች በማለት

ይከፍላቸዋል። የደቡባዊ ጉጂ ኮንፌድሬሺኖች የሚባሉት ኡራጋ፣ ማቲና ሆኩ ሲሆኑ የሰሜናዊ ጉጂ ወይም አላብዱ ኮንፌድሬሺኖች ደግሞ ከዌስቱና ሀሎ በተጨማሪ ኡቱና ሼሎ እንዳሉ ያስረዳል።

> They may be divided into two smallest confederations differing markedly in culture: the northern Guji or Alabdu and the southern Guji, consisting of the Uraga, Mati and Hoku. The Alabdu originally inhabited what is now western and northern Sidamo, where we still find two minor Alabdu groups, the Out and Shelo.

በተመሳሳይ መልኩ የአላብዱን ጉጂ ኮንፌደረሺን ሀሎ፣ ዌሲቱ፣ ኡቱና ሼሎን እንደሚያካትትና ከመጨረሻ ያሉት ሁለቱ በሲዳማ ዞን ውስጥ ተነጥለው እንደሚገኙ Brehanu, (1993:24) ያስረዳል።




ምስል፡-3 የጉጂ ኮንፌድረሺኖች መገኛዎችን የሚያሳይ ካርታ (ምንጭ-አለማየሁና ሌሎች፣1998፡193)

እነዚህ ሁለቱም በሲዳማ ህዝብ መሀል ሰፍረው የሚገኙ ሲሆን፤ ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን «የወንዶ ጉጂ» በማለት ይጠራሉ። እነዚህ ጎሳዎች በሰፈራ አካባቢያቸው ከሌሎች የጉጂ ኦሮሞ የተለዩ ቢሆኑም በገዳና በሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ወቅት ተወካዮቻቸውን እየላኩ ሲሳተፉ

የቆዩ መሆናቸው ይነገራል (አለማየሁና ሌሎች፣ 1998፡200)። ከመንፈሳዊ ጉዞው በኋላም በአንድነት ያርፋሉ፣ ለቀጣይ ጊዜያት የሚመሩበትን ህግም አብረው ያወጣሉ።

ሌላው መላ ምት ደግሞ ከቃሉ አመጣጥና የማዕከል ለውጥ ያደረጉበትን ምክንያት Hinnant, (1977፤54) ከተነገረው ሚት መሰረት አድርጎ የሚገልጸው ቃሉ ወደ መሬት በወረደበት ወቅት፣ በአርሲ፣ በቦረና፣ በጉጂና በሲዳሞ መካከል ጦሪነት እየተካሄደ ስለ ነበር እሱን ወደ አላብዱ እንደወሰዱት ያስረዳል።

የጉጂ ኦሮሞ ከተጠቀሱት ዞኖች ውጭ ያሉትን ለማካተት ቢያስቸግርም በ2007 በተደረገ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት በቦረናና ጉጂ ዞኖች ከሚኖሩት 2,352,289 አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት ውስጥ ወደ 1,946,477 ኦሮሞዎች እንደሆኑ ያሳያል (CSA,2007፡ 11-12)።[3]

### 4.1.2. የጉጂ ኦሮሞ ዘር ሐረግ

ስለ ጉጂ ኦሮሞ አመጣጥ የተለያዩ ሚቶች ይነገራሉ። ከነዚህም ውስጥ በ Tadesse, (1994) ስለጉጂ ኦሮሞ የቀረበውና እንዲሁም ስለጌዴኦ ህዝብ አመጣጥ በጥላሁን፣ (1982) ጥናት ውስጥ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ይኸውም፡- እንደ ሁለቱም አገላለጽ ጉጆ፣ ዳራሶና ቦሮ የሚባሉ የአንድ አባት ልጆች ነበሩ። በቀረበው ሚት ገለጻ ጉጆ አሁን ጉጂ ለተባሉት ቀደምት አባት ነው። ዳራሶ ደግሞ አሁን ጌዴኦ ለሚባሉት ቀደምት አባት ሲሆን ቦሮ ደግሞ አሁን ቦረና ይባሉ ለነበሩት ቀደምት አባት ነው በማለት ስለሦስቱ የዘር ሐረግ ትስስር ይተርካል። ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩ ዳራሶ ታላቅ፣ ጉጆ ደግሞ ታናሽ ወንድም እንደሆነና ይህንኑ ሚት አሁንም ጠብቀው እንደሚገኙ፤ ማለትም በተለያዩ ከበራዎች ላይ ለምሳሌ፡- በምርቃት ከበራ ላይ የሚቀርብ ሙሉ ነገር (mijuu) ይኸውም እንደ ወተት፣ ቦካ (ጠጅ) ያሉትን በመጀመሪያ የጌዴኦ ሽማግሌ ሳይቀምስ የጉጂው እንደማይቀምስ ያስረዳሉ።

ከላይ ከተገለጹት በተለየ መልክ ይህን የጉጂና ጌዴኦ የጋራ የዘር ሀረግ አመጣጥ ታሪክ፡- ጌዴኦዎች ለግዛት መስፋፋት እንደመከላከያ ዘዴ የተጠቀሙበት እንደሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአቢሲኒያኖች የተለያዩ ቡድኖችን በአንድ ላይ አድርጎ ለማስተዳደር ሲሉ የፈበረኩት የጉድፈቻ አፈ-ታሪክ ሊሆን እንደሚችል ካገኘው መረጃ በማጣቀስ Asebe, (2007፡57) እንደሚከተለው ይገልጻል።

[3].የ2007 ዓ.ም.CSA በቦረናና ጉጂ ዞኖቹ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ብዛትን በመደመር የተገኘ ውጤት ነው።(በአጥኚው)

*Coming back to the myth, the views from Guji and some non-Guji informants provide us a different version. They see it as Gedeo's need for protection, as a mechanism constructed by the Gedeo as atool for expansion and as an extension of the myth of Deresso's adoption to the family of Guji. It is also argued that the myth of brotherhood was possibly fabricated by the Abyssinians from the myth of adoption as an administrative strategy so as to conglomerate the groups together).*

በሌላ በኩል ደግሞ የጉጂ ሚት እንደሚያስረዳው የጉጂ ኦሮሞ መጀመሪያ የተገኘው በአሁኑ የምስራቅ ጉጂ ዞን፣ አዶላ በሚባል ቦታ ውስጥ እንደሆነ ያስረዳል። ከዚህ ቦታ በመጀመሪያ የተገኙት ወደ ጊርጃ የሚባል ቦታ፤ ማለትም ከአዶላ ከተማ በስተሰሜናዊ- ምስራቅና ከገናሌ ወንዝ አጠገብ ወደምትገኘው ቦታ ተንቀሳቀሱ የሚሉ አሉ። ሌሎች ደግሞ የጉጂ መገኛ ስፍራ እራሱ ጊርጃ እንደሆነና እራሳቸውንም «ጉጂ ጊርጃ» ብለው እንደሚጠሩ Tedecha, (1988) ይገልጻል። ይህንኑ ሀሳብ አለማየሁና ሌሎች፣ (1998፡195) እንደሚከተለው ያጠናክራሉ፡-

> *ብዙዎቹ ጸሐፊዎች ጉጂ ከጊርጃ መጣ በማለት የሚገልጹት መዳወላቡ ላይ የነበረው የኦሮሞ ገዳ ማዕከል ተበታትኖ በምትኩ እያንዳንዱ የኦሮሞ አብይ ጎሳ የየራሱን የገዳ ማዕከል ከመሰረተበት ወቅት ጋር የሚገጣጠም ይመስላል። ይህ ክስተት የተፈፀመው በ16ኛው መቶክ/ዘ ማብቂያበ (1594) አካባቢ መሆኑን ከገዳ የዘመን አቆጣጠር ስሌት የተገኘ ማስረጃ ያመለክታል። ቀደም ሲል እንደተገለፀው ወደ ጊርጃ ከመምጣታቸው በፊት በአዶላ አካባቢ የቆዩ በመሆናቸው የጉጂ ኦሮሞዎች በተጠቀሰው የአዶላ አካባቢ ከ16ኛው መቶ ክ/ዘ በፊት የነበሩ መሆናቸውን ያመለክታል።*

ነገር ግን እንደ አለማየሁና ሌሎች አገላለጽ ከ16ኛው መቶ ክ/ዘ በፊት በአዶላ አካባቢ ያነበሩ መሆናቸውን ይግለጽ እንጂ በሌላ በኩል የጉጂ ጎሳ ቀደም ሲል የጂሌ ኦሮሞ አካል እንደነበሩ፤ ከዚያም አሁን ወዳሉበት አካባቢ ተገንጥለው በመሄድ እንደሰፈሩ የሚገልጹ እንዳሉም ያስረዳል። በሌላ በኩል የጉጂ ኦሮሞችን ቀደም ሲል በ15ኛ ክ/ዘ ውስጥ በላንጋኖ ሀይቅ አካባቢ ሰፍረው ከነበሩበት ዘረ ያዕቆብ (1434-1468) ወደ ደቡብ እንዲያፈገፍጉ እንዳደረጋቸው Alamaayyoofi kan biroo,(1999፡ 275) ይገልጻሉ።

እንደ Berhanu ገለጻ ደግሞ ሲዳማዎች ቀደም ሲል አሁን ካሉበት ግዛት (territory) በስተ-ምስራቅ በሚገኘው የገራንባ ፕላቶዋማ አካባቢ ነበሩ። ከዚያም ጉጂዎች ከዚህ ግዛት በስተ-ምዕራባዊና ደቡባዊ ክፍል ሰፈሩ። ሲዳማዎች ባጋጠማቸው የሕዝብ ብዛት ችግር ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እንዲስፋፉ አስገደዳቸው። ይህ የመስፋፋት እንቅስቃሴ የጉጂ ኦሮሞን ከሁለት እንደከፈለውና የተወሰነው ወደ ብላቴ ወንዝ አቅጣጫ እንዳፈገፈጉ፣ ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ ርቀው ከአባያ ሀይቅ በስተ-ምስራቅ እንደሰፈሩና ሰሜናዊ የጉጂ ኮንፈደሬሺንን እንደመሰረቱ፤ ሌላኛው ቡድን ደግሞ በሰተ-ደቡባዊ አቅጣጫ በማፈግፈግ ወደ ገናሌ ወንዝና የጌዴኦ ግዛት ከአባያ ሀይቅ ምስራቃዊ የባህር ዳሪቻ ካለው ሰንሰለታማ ተራራዎች ማለትም አሁን ያሉበት አካባቢ የሰፈሩት ደግሞ ደቡባዊ የጉጂ ኮንፈደሬሺንን እንደመሰረቱ Berhanu, (1993:24-25) ያስረዳል።

በአጠቃላይ የጉጂ ኦሮሞን በትክክል ከዚህ መጣ ብሎ ለማስቀመጥ በጣም ያስቸግራል። ምክንያቱም የተለያዩ ምሁራን ካገኙት መረጃዎች እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችም ሀሳቦችን ሰንዝረዋል። ይሁን እንጂ ከነዚህ ጭብጦች ተነስቶ እንዲህ ነው ለማለት ያስቸግራል። ስለዚህ ይህ ጉዳይ በራሱ ጥልቅ ጥናት እንደሚያስፈልገው የአጥኚው እምነት ነው።

የጉጂ ኦሮሞ ሦስት ጎሳዎች ማለትም፡- ኡራጋ፣ ማቲና ሆኩ እያንዳንዳቸው በስራቸው ንዑሳን ጎሳዎች አሏቸው። ይኸውም፡- በኡራጋ ስር ሰባት (ገላልቻ፣ ዋጂቱ፣ ሳርቦርቱ፣ አጋንቱ፣ ደራርቱ፣ ጕላና ሀሎ) ሲሆኑ፤ በሆኩም ስር ሰባት ንዑሳን ጎሳዎች (ገላልቻ፣ ኦቦራ፣ ሚቺሌ፣ ሔራ፣ ቡንዲቱ፣ ኪኖና ባላ) ይገኛሉ። በማቲ ስር ደግሞሦስት ንዑሳን ጎሳዎች (ኢንሳለ፣ ሐንዶዛና ሂሪቃርቱ) ይገኛሉ።

ማቲ ቀደም ሲል እንደነኡራጋ ሰባት ንዑሳን ጎሳዎች እንደነበራቸውና አራቱ ንዑሳን ጎሳዎች ከአርሲ ኦሮሞ ጋር በነበረው ጦርነት እንደተደመሰሱ ታደሰ በሪሶን በመጥቀስ አለማየሁና ሌሎች፣ (1998፡199) ያሰረዳል። በሌላ በኩል መረጃ አቀባዮችን በመጥቀስ ደግሞ እነዚህ አራቱ የማቲ ንዑሳን ጎሳዎች ያለቁበት ከአርሲ ኦሮሞ ጋር በነበረው ጦርነት ሳይሆን ከሲዳማ ህዝብ ጋር በተደረገ ጦርነት እንደሆነና ጦርነቱም በገናሌ ወንዝ አካባቢ ለረጅም ዓመታት የዘለቀ መሆኑን፤ ቦታውንም ሐዶ ባሌሳ የሚል መጠሪያ እንደተሰጠው ይገልጻሉ፤ ትርጉሙም «የሰው ዘር ያለቀበት ወይም ጥፋት የደረሰበት ስፍራ ማለት ነው።»

በመጨረሻም እነዚህን ሚቶች እንደ ታሪክነት አምኖ ለመቀበል የሚያዳግት መሆኑን በምክንያታዊነት የሚጠቅሱት ቀደም ሲል በህዝቦች መካከል የተደረጉ ጦርነቶች እጇግ በበዛ ከሰፈራ አካባቢ ከመንቀል ወይም ከመግፋት ባሻገር እንዲህ ጎሳዎችን ነጥሎ እስከማጥፋት ደረጃ አለማድረሱን አለማየሁና ሌሎች፣ (1998፡199) ያስረዳሉ፡፡

እነዚህ ሦስቱ የጉጂ ኮንፌድረሲዎች በሁለት ትላልቅ እርስ በርስ መጋባት በሚችሉ ቡድኖች ማለትም፡- ኮንቶማና ዳሪሙ በሚባሉ ማህበራዊ አደረጃጀት የተከፈሉ ናቸው፡፡ አከፋፈሉም በኮንቶማ ስር ከኡራጋ አራት (ዋጂቱ፣ ሳርቦርቱ፣ ጉላና ሀሎ)፣ ከሆኩ ሦስት (ገላልቻ፣ አቦራና ባላ)፣ ከማቲ ደግሞ ሁለት (ኢንሳለና ሂሪቃርቱ) ባንድ ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በዳሪሙ ስር ደግሞ ከኡራጋ ሦስት (ገላልቻ፣ አጋንቱና ደራርቱ)፣ ከሆኩ አራት (ሚቺሌ፣ ሔራ፣ ቡንዲቱና ኪኖ) እንዲሁም ከማቲ ደግሞ አንድ (ሐንዶዛ) ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ቡድኖች ስር ደግሞ አንድ ዓይነት ጎሳ ያልሆኑ (non-totemic) እና እርስ በርስ መጋባት የሚችሉ (exogamous) ጎሳዎች ሲኖሩ ከዚያም አንዱን ጎሳ የመሰረቱ (segments) ነገር ግን፤ የተለያዩ የዘር ሀረግ ያላቸውን ደግሞ በ ‹ቤት› (mana) በማለት እንደሚከፈሉ Tadesse, (2004፡14) ያስረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጉጂ በዘጠኝ ሀገና (ጉባኤ) እና በአስራ ሰባት ባልባላ (balbalaa) ወይም ቁዩዎች እንደሚከፋፈሉ መረጃ አቀባዮችን ዋቢ አድርጎ አለማየሁና ሌሎች፣ (1999፡197) ያሰረዳሉ፡፡




ምስል፡-4 የኮንቶማና ዳሪሙ አከፋፈለን የሚያሳይ ቻርት (ምንጭ፡-ከአለማየሁና ሌሎች፣ 1999፡ 190) ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአላብዱ ጉጂዎችን ያየን እንደሆነ በሀሎ ስር ሰባት (ኦቢቱ፣ ሜሪቱ፣ ዳንቱ፣ ማሲንቱ፣ ሐንጌቱ፣ አኖልቱና ባላ) የሚባሉ ንዑሳን ጎሳዎች ሲኖሩ፣ በዌስቱ ደግሞ አራት ንዑሳን ጎሳዎች (ቢቄ፣ ወንቲቱ፣ ሀርጋጋና ዳሪሙ) ይገኛሉ። ከእነዚህ ሌላ ሁለቱ በወንዶ የሚገኙት ዐቢይ ጎሳዎች ስር ደግሞ በሽሎ ሰባት፣ በኦቱ ሁለት ንዑስ ጎሳዎች እንደሚገኙ አለማየሁና ሌሎች ያስረዳሉ (ዝኒ ከማሁ፡191-192)።




ምስል፡-5 የኮንቶማና ዳሪሙ አሰፋፈር የሚያሳይ ምስል (ምንጭ፡- Haberland, 1963)።

## 4.1.3.ሃይማኖት

በታሪክ እንደሚታወቀው የኦሮሞ ህዝብ ከጊዜ በኋላ ከመጡ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች በፊት የሚያመልኩት ሀገረሰባዊ ሃይማኖት "ዋቄፋና" ይባላል። "ዋቄፋና" የሃይማኖቱ መጠሪያ ሲሆን፤ ትርጉሙም በአንድ እግዚሐብሔር (waaqa) የሚያምኑ ማለት ነው (Kuntsson, 1967፡47-48)። በዚህ ሃይማኖት ስር ቃሉ (kallu) ቀዳሚውን የመሪነት ቦታ ይይዛል። በማህበረሰቡ ዘንድ ቃሉ በሰው ልጆችና በፈጣሪ መካከል በመሆን የሚያገናኝ፤ ከፈጣሪ የተሰጣቸው ስጦታ እንደሆነ ይታመናል።

በቃሉ ተቋም (galma qaalluu) የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎቹ ይከናወናሉ። ቃሉ በስሩ ካሉት የመማክርት አባላት ጋር በመሆን ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ያከናውናል። ከነዚህም ውስጥ ለአብነት ያህል የአካባቢው ነዋሪዎች በአየር መዛባት፣ በጠላት ወረራ እንዲሁም በወረርሽኝ በሽታ ምክንያት እንዳይጠቁ፤ እግዚሐብሔር በምህረቱ እንዲታደጋቸው የተለያዩ የመለማመን፣ የማማለድና የምስጋና ከበራዎችን እንደሚፈጽምላቸው ያምናሉ። በጉጂ ኦሮሞ የሃይማኖታዊ ስብጥርን የተመለከተን እንደሆነ እንደ CSA, (2007፡ 359-360) መረጃ በጉጂና ቦረና ዞኖች ውስጥ ከሚኖሩት አጠቃላይ ህዝብ ወደ 52.5% ፕሮቴስታንት፣ 21% የሀገረሰባዊ ሃይማኖት ተከታይ፣ 12.7% እስላም፣ 6.65% ኦርቶዶክስ፣ 1.8% ካቶሊክ ሲሆኑ 5.35% ደግሞ የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች እንደሆኑ ያሳል።[4]

የሃይማኖት ስብጥሩ ይህን ይምሰል እንጂ በእነዚህ የሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞዎች መካከል ትክክለኛ የእምነት ድንበር አለ ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ከበራዎችን አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ሲከውኑ ይስተዋላሉ። አንዳንድ በአምልኮአቸው ውስጥ የነበሩትን ከበራዎች በአዲሶቹ ሃይማኖቶች ውስጥም መቀላቀል ይታያል። እንዲሁም ለቃሉ ከፍተኛ አክብሮት የሚቸሩና የቃሉዎችን ገልማ ለአምልኮ የሚቃኙም አሉ (Bartels, 1983:14) እና ከአጥኚው የመስክ ምልከታ ከተገኘ)። ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በጉጂ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በዋቄፋና ሃይማኖት ወይም በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ በአንዱ ወይም በሌላው የመሳተፍ ዕድላቸው የሰፋ መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ በገዳ የስልጣኑ-ሂመት ማጽደቅ ከበራ ይህን ክስተት ሊያሳዩ የሚችሉ በምዕራፍ ሦስት ስር በተወሰነ ደረጃ ለማየት ተችሏል።

### 4.1.4. ቋንቋ

የአካባቢው የመግባቢያና የስራ ቋንቋ ኦሮሚኛ (Afaan Oromo) ይባላል። አፋን ኦሮሞ ከምሥራቅ የኩሽ ቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል (Tadesse, 2004፡13)። አፋን ኦሮሞ በአፍሪካ ከሚነገሩ ቋንቋዎች ውስጥ ከአረብኛና ሀውሳ ቋንቋዎች ቀጥሎ በተናጋሪ ብዛት በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል (Gadaa, 1988፡15)። በጉጂ ኦሮሞ አካባቢ ሌሎች ቋንቋዎች አይነገሩም ማለት አይደለም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች መገኛ እንደመሆኗ መጠን፤ የጉጂ ኦሮሞ ከሰፈሩበት መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ፣ ከንግድ፣ ከማህበራዊና ፖለቲካዊ ትስስር፣

[4].የ2007 ዓ.ም.CSA በቦረናና ጉጂ ዞኖቹ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች ላይ የሃይማኖት ስርጭቱን በመደመርና ወደ ፐርሰንት በመቀየር የተገኘ ውጤት ነው።(በአጥኚው የተዘጋጀ)

እንዲሁም በአካባቢው በተለያየ ምክንያቶች በመጡ ነዋሪዎች እንደ ጌዴኦኛ፣ አማርኛ፣ ቡርጂኛ፣ ኮንስኛና የመሳሰሉ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡፡

### 4.1.5. መተዳደሪያ

የጉጂ ኦሮሞዎች የሰፈሩባቸው አካባቢዎች የአየር ንብረት ቆላ፣ ደጋና ወይና ደጋ ናቸው፡፡ የተወሰኑት በቆላማው አካባቢ ያሉት አርብቶ አደሮች ሲሆኑ፣ የቀንድ ከብቶችና የጋማ ከብቶችን በማርባት ይታወቃሉ፡፡ በተለይም የአላብዱ ጉጂ እስከ 20ኛው ክ/ዘ አጋማሽ ድረስ መተዳደሪያቸው በከብት እርባታ ነበር፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ከበሬታ የሚለካውም ባለው የከብቶች ብዛት ነው (Asebe, 2007፡41)፡፡ ከብቶች በጉጂ ዘንድ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ ማህበራዊና ከክበራ አኳያ ፋይዳቸው የጎላ ነው (Tadesse, 1994:311)፡፡ ይኸውም፡- አንድ ለአቅመ-አዳም የደረሰ ልጅ ጋብቻ ለመፈፀም ያለው የከብት ብዛት እንደ መመዘኛ መስፈርት ይታይ ነበር፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ወንጀል ከተፈፀመ ለተከሰተው ጥፋት ማካካሻ የሚሰጠውም ከብት ነው፡፡ በቃሉም ሆነ በገዳ ሃይማኖታዊ ክበራዎች ላይ ለመስዋዕት የሚቀርበው ከብት ነው፡፡ ስለዚህ ከብት ሁሉ ነገራቸው እንደሆነ ይቆጥራሉ፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እንደሌሎቹ የጉጂ ጎሳዎች ከአርብቶ አደርነት ወደ ከፊል አርብቶ አደርነት ተቀይረዋል፡፡ በአካባቢው በዋናነት ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ እንሰትና ማሽላ ያመርታሉ (Tadesse, 2004፡ 14)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተወሰኑ ወረዳዎች በቡና ምርታቸው ከሀገሪቷ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን አግኝተውበታል፡፡ በማዕድን ክምችት ከወርቅ አንስቶ እስከ ታንታለምና ራዲዮ አክቲቭ ማዕድን ድረስ ወደ ሃያ አምስት የማዕድን ዓይነቶች ባለቤት ናቸው፡፡ ታዋቂው የሻኪሶ ላጋ ዳንቢ ወርቅ ማዕድን የሚገኘው በጉጂ ውስጥ ነው (Danbalaa, 2000)፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ቃሉና የቃሉ ተቋም

በዚህ ምዕራፍ ስር ስለቃሉ ምንነት፣ አመጣጥ፣ የስያሜ አሰጣጥ ሂደቱን፣ የመማክርት አባላት ማንነትና ተግባራቸውንና የቃሉ ተቋም አመጣጥ ታሪክና ሌሎች መቼቶችን ከቀዳማይና ካልኣይ መረጃ ምንጮች የተገኙትን በዝርዝር ለማቅረብ ተችሏል፡፡

### 5.1. ቃሉ

በዚህ ጥናታዊ ስራ ውስጥ "ቃሉ" የሚለው ቃል ሲነበብ "ሉ" ትጠብቃለች፡፡ቃሉ (qaalluu) የኦሮሞ ዋቄፋና ሃይማኖት መሪ መጠሪያ ስም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች አባሙዳ፣ ኢሬሳ ገዳ እና ጂላ ማሊማ በመባል ይታወቃል (ታቦር፣ 2006፣198)፡፡ እያንዳንዱ መጠሪያ የራሱ የሆነ አመጣጥ እንዳለው የተለያዩ ጸሐፍቶች ያስረዳሉ፡፡

ለአብነት ያህል አባሙዳ የሚለው ስያሜ የመጣው በየስምንት ዓመቱ ከሚካሄደው መንፈሳዊ ጉዞና በቃሉ ተቋም በሚካሄደው የመቀባት (የመባረክ) ሃይማኖታዊ ከበራ የተወሰደ መጠሪያ ነው፡፡ ቃሉ የሚለው መጠሪያ ስም ደግሞ የተወሰደው "ቃሉ" የሚለው ሲነበብ "ሉ"ን በማላላት ቃሉ (qalu) ከሚለው የኦሮሚኛ ግስ የረባ ሲሆን ትርጉሙም መሰዋት ነው፡፡ ይኸውም የሚቀርበውን መስዋዕት ለሃይማኖታዊ ከበራው በቃሉ አማካይነት እንደሚከወንና ከዚህ ድርጊት (መሰዋት) እንደተወሰደ ያስረዳል (Mohammed,1994)፡፡

በሌላ አገላለጽ ቃሉ ልክ እንደ ክርስትና እምነት ቆዳስ፣ አለያሚ ልክ እንደ እስልምና እምነት ኢማም ሊመሰል ይችላል (Gada, 1988:24)፡፡

በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ግን በአብዛኛው የሚታወቀው ቃሉ፣ አባቃሉ፣ ሞቲ (mootii) በሚሉት መጠሪያዎቹ ነው፡፡ በባህሉ መሰረት አንድ የተከበረን፣ በዕድሜ የበቃን ሰው በነጠላ ስሙ አይጠራም፡፡ ወንድ ከሆነ «አባ» (abba)፡- ትርጉሙም አባት ማለት ነው፡፡ ሴት ከሆነች ደግሞ «ሀዳ» (haadha)፡- ትርጉሙም እናት ማለት ነው፡፡ ይህን የስም ገላጭ ከመጠሪያ ስሙ በፊት በማስገባት ይጠቀሙበታል፡፡ ሞቲ የሚለው ግን ታሪካዊ አመጣጡ ከፊውዳሉ ስርዓት ጋር የተያያዘና በዚያን ወቅት የተሰጠ ተጨማሪ ስም ሲሆን ትርጉሙም "ገዥ" ወይም "ንጉስ" እንደማለት ነው፡፡ ቃሉም ከኦሮሚኛ ‹moye› ከሚለው ግስ የረባ መጠሪያ ስም ሳይሆን

አይቀርም። ምክንያቱም ‹moye› ለሚለው የኦሮሚኛ ግስ ሲሆን፤ አቻ ትርጉም /አሸነፈ/ የሚለው ይይዛል።



ፎቶ፡-1 16ኛ የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ አጋ ሳቆ በገልማ ውስጥ እያሉ የሚያሳይ

ስለቃሉ ሲነሳ የትኛው ቃሉ ነው? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ለዚህ አለማየሁና ሌሎች፣ (2000፡108) በጽሑፋቸው ውስጥ እንደሚከተለው ገልጸዋል። ይኸውም፡- «ከተለያዩ የታሪክ ሰነዶች መረዳት እንደተቻለው የቦረናና የጉጂ ኦሮሞዎች «ቃሉ» ከጥንቱ የኦሮሞ «ቃሉ» ስርዓት የነበረውና መቀመጫውም መዳወላቡ ከሆነው የ«ቃሉ» ተቋም በእጅጉ የተሳሰረ እንደሆነ ነው»።

ቃሉ በተለያየ መጠሪያ ቢጠራም በዚህ ጥናት ውስጥ ቃሉና አባቃሉ የሚሉትን መጠሪያዎች ተጠቅሚያለሁ። ምክንያቱም የህገረሰባዊ ሃይማኖቱ ተቋም በስሙ «ገልማ ቃሉ» በማለት ስለሚጠራበት ነው።

### 5.1.1. የቃሉ አመጣጥ ሚት

ቀደም ሲል ስለቃሉ ምንነት በስፋት አይተናል፡፡ ነገር ግን ቃሉ ማን ነው? ከየትስ መጣ? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ለዚህ መልስ ከተለያዩ መረጃዎች የተገኙትን እንደሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በመጀመሪያ መረጃ አቀባዮቹ የአካባቢውን ሚት በመጥቀስ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *ቃሉ ከዕለታት አንድ ቀን ኘላስቲክ በመሠለ ከረጢት (ሩፋ) ተጠቅልሎ ከሠማይ ወረደ፡፡ የወረደውም ልክ እንደማሪያም መቀነት (ቀስተ-ደመና) ጥቅሉ ከላይ እየተፈታ እሱን መሬት አደረሰ፤ ከዚያም ጥቅሉ ወደሰማይ ተጠቅልሎ ተመለሰ፡፡ ይህ ክስተት የተፈፀመው በጉጂ ዞን፣ በአዶላ ወረዳ፣ ኦባ (ኦቢቲ) በሚባል ቦታ ነው፡፡ ቃሉ ኘላስቲክ በመሠለ ከረጢት (ሩፋ) ውስጥ እንዳለ፤ ከሱ አጠገብ ከርቤ (qunbii) እና ‹ካላቻ› አብሮት ተጠቅልሎ ነበር፡፡ ቀድመው ያዩት የዋጂቱ ጎሳ አባላቶች ነበሩ፡፡ አጠገቡ ደርሰው ለመንካት ስለፈሩ ወደመንደሩ በመሄድ የተፈጠረውን ተናገሩ፡፡የአካባቢው ሰዎችም ሊያናግሩት ቢሞክሩም ምንም መልስ አልሰጣቸውም ነበር፡፡ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በማገናኘት ለማዋራት ቢሞክሩም ውጤት ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም ከገለልቻ ጎሳ ወገን የሆነች ልጃገረድ ስትመጣ ፈገግታ አሳያት፡፡ ከዚያ ወደቤት እንዲሄዱ ጠየቀችው፡፡ እሱ ግን እኔ የሰው ቤት አልገባም፤ አደራሽ (ገልማ) ስሩልኝ አላቸው፡፡ ሰዎቹም ከእግዚኣብሔር የመጣ መልዕክተኛ ነውና ትዕዛዙን እንፈጽም በማለት ተሰራለት፡፡ ከዚያም ወደገልማው ተወሰደ፡፡ ቁርበትም ተነጠፈለት፡፡ ወተት በቅል አምጥተው ሲሰጡት አልቀበልም አላቸው፡፡ ከኋላ ግን በማለቢያ (Okolee) በስጦታ መልክ (gumaacha) ነው ሊሰጠኝ የሚገባ አላቸው፡፡ እነሱም እንዳላቸው አደረጉ፡፡ ሰዎቹም ያችን ከገለልቻ ጎሳ ወገን የነበረችውን ልጅ እዚያው ትተዋት ወደ ቄዬቸው ሄዱ፡፡ ከዚያ ሁለቱም አብረው መኖር ጀመሩ፡፡ ልጆችም አፈሩ፡፡* (ሞኮና ናጋዎ፣1/12/2006 ዓ.ም. አባያ ወረዳ፣ ከላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

በይዘቱ ብዙም ልዩነት ባይኖረውም Hinnant,(1977፡54) ደግሞ ከመረጃ አቀባዮቹ እንዳገኘሁት በማለት ስለቃሉ አመጣጥ ሲገልጽ፡-

አንዲት ልጃገረድ ከአረንጓደ መስክ ላይ ጥጆች ትጠብቅ ነበር። ጥጆቹ በድንገት ሳር ከሚግጡበት ወደ አንድ ቦታ ፍዝዝ ብለው ይመለከቱ ጀመር። በዚያ ቦታ የሆነ ልጅ ተጋድሟል (ትክክለኛ እድገቱን ጠብቆ የተወለደ ሰው፣ ነገር ግን ህጻን ልጅ የሚመስል።) ጥጆቹ ወደ ህጻን መሳዩ ሰውዬ ተጠጉ፣ ነገር ግን ወደ እሱ በቀጥታ መመልከት አልቻሉም። ከዚያ ወደኋላ ተመልሰው እንደገና ሳር መጋጥ ጀመሩ። ልጃገረዷ በርቀት ቆማ ስለነበር ምን እንደተከሰተ አላወቀችም ነበር። ጥጆቹ ይመለከቱት ወደ ነበረው ነገር ለማየት ተጠጋች። በጥጆቹ መሀከል በተለያዩ ከለር መስመር፣ መስመር ያለው ልብስ (ruufa) ተመለከተች። ምን እንደሆነ የምታውቀው ነገር የለም፣ ከዚያ ለወላጆቿ ለመንገር ሮጠች፣ያየችውንም ነገረቻቸው። እነሱም ወደቦታው በመምጣት ተመለከቱ። ሌሎችም በአካባቢው የነበሩ በመምጣት ሜዳውን ሞሉት። ቃሉ ከጨርቁ ውስጥ ለመውጣት ሞከረ፣ ነገር ግን አካሉ ሙሉ ለሙሉ ተሸፍኗል። በዚህ ምክንያት የተሰበሰበው ህዝብ ምን እንደሆነ ለመለየት አልቻሉም ነበር። አንድ ሰውዬ ጨርቁን ከመሀል በኩል ቢቀደድ የሚል ሀሳብ አቀርቦ፣ በሀሳቡ ተስማምተው ሲቀደድ እራሱ መንቀሳቀስ ጀመረ። ይህ በባህል አዋቂ አማካይነት ከፊት-ለፊት በእራሱ መካከል ቢቀድ ጥሩ እንደሚሆን ሀዩ (hayyuu) ተናገረ፣ እናም የሱ ቃል ተቃባይነት አገኘ። ወዲያውኑ ሀዩው የሀጻን መሳይ ሰውዬውን ፊት አየ፣ አይኑም ታወረ። ሁሉም የሚገርም ነበር። ህጻን መሳይ ሰውዬው በሀዩው ላይ ምራቁን እንትፍ አለበት፣ የሀዩውም ብርሃን ወዲያው በራለት። እስከዚያን ጊዜ ድረስ ህጻን መሳዩ ሰውዬ አይናገርም ነበር። ሰዎች ሲያናግሩት፣ እሱ ግን ምላሽ አይሰጥም።

በመጨረሻም መጀመሪያ ያገኘችውን ልጃገረድ አመጡለት። እሱም ተመለከታት፣ ከዚያም ፈገግታ አሳያት። ቃሉም ለህዝቡ እግዚኣብሔር (ዋቃ) እሱን ወደታች እንዳወረደው ነገራቸው። በቀኝ እጁ የቡና ፍሬዎች፣ በግራ እጁ ደግሞ ከርቤ (Qunbii) ይዞ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ ከብረት የተሰራ በርጨማ፣ገባሰም አብሮት ነበር።በሩፋው ጨርቅ ላይ እባብ ነበር፣የተለየ ዓይነት እባብ /ኮብራ/ (buuti) የሚባል ነው። ለህዝቡም ሄደው ከወንዝ በወንፊት ውሃ ቀድተው እንዲያመጡ፣ በልብሳቸው ደግሞ እሳት ይዘው እንዲያመጡ ነገራቸው። ወንፊቱ ውሃውን ሊይዝላቸው አልቻለም፣ ልብሱም ተቃጠለባቸው። እሱ በማንኛውም መንገድ ሁለቱንም በራሱ የማድረግ

*ችሎታ ነበረው። ነገር ግን እሱ ወደ መሬት በወረደበት ወቅት፣ በአርሲ፣ በቦረና፣ በጉጂና በሲዳሞ መካከል ጠሪነት እየተካሄደ ነበር። እሱን ወደ አላብዱ (Alaaddu) የተወሰደው በዚህ ምክንያት ነበር* በማለት አትቷል።

ከነዚህ ሚቶች የምንረዳው የመጀመሪያው ቃሉ የመጣው ወይም የወረደው ከሰማይ እንደሆነና በኋላም ከዚያች የገለልቻ ጎሳ ልጃገረድ ጋር አብረው እንደኖሩ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በቃሉ ተቋም ከቃሉ መቀመጫ ስር ወይም ምሶሶ ስር ጉድጓድ ውስጥ የሚቀመጡ እባቦች አሉ። እነዚህ እባቦች ሀጢያት ሰርቶ፣ በውስጡ ተንኮል ይዞ የሚመጣን ሰው ይናደፋሉ ተብሎ ይታመናል።

በተመሳሳይ መልኩ በተለያዩ የኦሮሞ አካባቢዎች ስለቃሉ አመጣጥ የሚነገሩት ሚቶች በተለያየ አገላልጽ ቢሆንም መሰረቱ ከሰማይ እንደሆነ (Kuntsson, 1967; and Mohammed, 1994) በስፋት ያስረዳሉ። «ቃሉ» በኦሮሞ ባህል መሰረት ታላቅና ክቡር ከመሆኑ የተነሳ ሰዎች ሊተዳደሩበት የሚገባቸውን ህግጋት ሁሉ ያውቁ ዘንድ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ቅዱስ ሰው ነው ተብሎ ይታመናል።

### 5.1.2. የቃሉ ስያሜና መስፈርቶቹ

በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የቃሉ ስልጣነ ሢመት ሂደትን የቃሉ ስያሜ አሰጣጥ (sirna moggaasa qaalluu) በመባል ይታወቃል። ይህ የስያሜ ከበራ የሚጀምረው ከመጀመሪያው የቃሉ አመጣጥ ሚት ጋር ትስስር ያለው ሂደት በመሆኑ ነው። ይኸውም፡- ቃሉ ከሰማይ ሲወርድ እንዴት ወረደ? ከዚያ የት ወረደ? ከማን ጋር ተገናኘ የሚሉት ሚቶች ለአሁኑ ተሰያሚ ቃሉ እንደ መሰረታዊ መመልመያ መስፈርቶች ተቀምጠው እናገኛለን።

አንድ በማገልገል ላይ ያለ ቃሉ በሕይወት ዘመኑ ሙሉ ያገለግላል። ነገር ግን የነበረው ቃሉ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ፤ እሱ ላይ የነበረው መንፈስ አይሞትም ተብሎ ስለሚታመን ስልጣነ መለኮቱ ይቀጥላል። ይህም የሚሆነው ከልጆቹ ውስጥ ማህበረሰቡ ባዋቀረውና ባስቀመጠው ሃይማኖታዊና ባህላዊ መስፈርቶችን የሚያሟላው ተፈልጎ ይሰየማል። ከቃሉ ስያሜ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ አንዱ ቀጣዩ አባቃሉ የሚሆነው ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች በማህበረ-ባህላዊ ዕውቀት ተዋቅረው የተቀመጡ አሉ። እነዚህ መስፈርቶች ምን ምንድናቸው? የሚሉትን ቀጥሎ እንመለከታለን።

የጉጂ ኦሮሞ የቀድሞው ቃሉ ሕይወቱ እንዳለፈች ስለእሱ መሞት ከመደናገጥ ይልቅ፤ ቀጣዩ ቃሉ ማን ይሆናል? የሚለው ነው የሚያሳስባቸው። ስለዚህ አስከሬኑ እዚያው እንዳለ መስፈርቱን የሚያሟላ ይመረጣል። ይኸውም፡-

1. ከቃሉ የተወለደ መሆን አለበት፣

እንደጉጂ ኦሮሞ የመጀመሪያው ቃሉ የዘር ሀረግ ተከትሎ ስልጣኑ-ሢመቱን መተካት ያለበት ከቃሉና ከሀዳ አንባ የተወለደ መሆን አለበት። በቦረና ኦሮሞ ዘንድ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው። ይኸውም አንድ የቦረና ቃሉ ሊሆን የሚችለው ከቃሊቲ የሚወለድ ልጅ ነው። እንደ ቦረናዎች ቃሊቲ ማለትም፡- ከቃሉ ባለቤቶች ውስጥ አንዷ ስትሆን፤ ከቃሉ ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንደማትፈጽም ይታመናል። በእሱ ፈንታ አንድ በስም የማይታወቅ ሰው፤ ነገር ግን ልክ እንደወዳጅ እንዲሆናት የተፈቀደለት ሰው ጋር በውስጠ ታዋቂነት ግንኙነት እንድትፈጽም ይደረጋል። ከዚህ በመነሳት የምወለደውን ልጅ ‹‹የቦረና ልጅ›› ይሉታል። የቃሉ እናት የመሆን መብት ያላትም እሷ ነች። ለዚህም እንደምክንያት የሚቀርበው ልክ በብዙዎች ባህል ውስጥ እንደሚደረገው ሁሉ አንድ መሪ ወደ ስልጣን ሲመጣ ከመጣበት ማህበረሰብ የዘር ሀረግ ጋር የማያያዝ ችግሮች እንዳይፈጠር ሊሆን እንደሚችል Asmarom, (1973:46) ይገልጻል። ይህ በራሱ አንድ እራሱን የቻለ ፍልስፍና ነው።

2. የሚሰየመው ልጅ ከገለልቻ ጎሳ ከሆነችው ሚስት የተወለደ መሆን አለበት፣

የመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጋብቻ የዘር ሀረግ መከተሉን የሚያመላክት ነው። ይኸውም የመጀመሪያው ቃሉ ከሰማይ እንደወረደ የተዋወቃትና በኋላም የትዳር አጋሩ የሆነችው የገለልቻ ልጃገረድ እንደነበረች ከቀረበው ሚት ለመረዳት ችለናል። ስለዚህ ያንኑ ፈለግ ተከትሎ የሚከናወን በመሆኑ ይህን መስፈርት ማሟላት ይጠበቅበታል። በቦረና ኦሮሞ ግን በተ.ቁ. አንድ ላይ እንደተመለከትነው ቃሉ ሊሆን የሚችለው ከመጀመሪያው ቃሉ ሚስቶች ውስጥ ከቃሊቲዋ ሲሆን የቃሉ የአብራኩ ክፋይ አይደለም።

3. ዓይኑ ሸውራራ ያልሆነ፣
4. አካሉ ሙሉ የሆነ፣
5. ግራኝ እጅ ያልሆነ፣
6. በተለምዶ ‹‹ማሪያም የሳመው›› የማይባል፣
7. ጠባሳ የሌለው፣አካሉና ተክለ-ቁመናው የተስተካከለ፣
8. ስስ ላስቲክ በሚመስል (ruufa) ነገር ተሸፍኖ የተወለደ፣

የመጀመሪያው ቃሉ ከሰማይ በሩፋ ውስጥ ተሸፍኖ ከመውረዱ ጋር የተያያዘ ሚት ስላለ አሁንም ያንኑ አካሄድ የሚያመላክት መስፈርት ይመስላል፡፡ *(አቶ አባባ ቶቱ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቶቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ18/11/2007 ዓ.ም.)*

9. በሌላ በኩል ደግሞ እውነት የሚናገር፣ ወደ እግዚኣብሔር መንገድ ሰውን የሚመራ፣ በስሩ የሚኖሩትን ማህበረሰብ ያለ አንዳች መድሎ በአንድ ዓይን የሚያይና የመሳሰሉት የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

የእግዚኣብሔር መልዕክተኛ የሚሰራው የእግዚኣብሔርን ስራ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ እነዚህንና ሌሎችንም መልካም ምግባር ያለው መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ነገር ግን አንዳንዴ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሁለት ውድማማቾች ሲኖሩና አባታቸው (ቃሉ) መሞታቸውን ሲያውቁ ከሁለቱ የተሻለ ባህሪይና ችሎታ አለው ብለው የሚያምኑትን አንደኛውን በመምረጥ እንዲዘጋጅና ስለስራዉም አንዳንዱ ምክር እንደሚለግሱ ከመረጃ አቀባዬ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

ከዚያም እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ተመርጦ ለስያሜ የሚያበቃውን ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይፈጸማሉ፡፡

ሌላው ቃሉዎች በአገልግሎት ዘመናቸው ደግሞ ከተወሰኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና ሥራዎች የተገደቡ ናቸው፡፡ ይኸውም፡-

- በተሰበረ ወይም በተሰነጠቀ ወንበር ላይ አይቀመጡም፣
- ፀጉራቸውን አይላጩም፣
- አያርሱም፣ አይቆፍሩም፣
- ከሰው ጋር ዘወትር አይገናኙም፣
- ከገዳ መሪዎች ጋር መንገድ አይተላለፍፉም፣
- በበዓላት ቀን ካልሆነ በስተቀር አያርዱም፣
- ገዳን ይመርቃሉ፣ የተጣሉትን ያስታርቃሉ፣
- የበዓላት ቀን፣ የሙዳ ቀን፣ የጸሎት ቀን፣ የምርቃት ቀን፣ ከለቻ በግንባራቸው ላይ ያደርጋሉ፣ ጫጩ ያጠልቃሉ፣ ሩፋ ይጠመጥማሉ (ታቦር፣ 2006፣198-199)፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የቃሉ ስያሜ ሲባል በሁለት መልክ ይከናወናል፡፡ ይኸውም፡- መጀመሪያ እንደ ማንኛውም የጉጂ ኦሮሞ ልጅ ከተወለደ በኋላ የመጠሪያ ስም ይሰየምለታል፡፡ ይኸውም፡- አንድ ልጅ ከተወለደ ወንድ ከሆነ ከአራተኛው ቀን በኋላ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ከሶስተኛው ቀን በኋላ፤ በሀገሬው ባህልና ወግ ላይ ተመስርተው የተወለደበትን ጊዜ፣ ቀን፣ ወርና ቦታ ላይ ተንተርሰው ይሰይማሉ፡፡

ሁለተኛው ስያሜ ደግሞ ቃሉ የሚሆነው ልጅ የአባቱን ቦታ ተክቶ እንዲሰራ የተቀመጠለትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ስልጣነ ሢመቱን ሲፈጽም የሚሰጠው ሰያሜ ሲሆን፤ ከዚያም አባቃሉ ሊባል ይችላል፡፡

እንደ መረጃ አቀባዩ አገላለጽ የቀድሞው ቃሉ ከዚህ ዓለም ሕይወቱ ካለፈች (yoo hancufa liqiimse) ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርርቶች የሚያሟላ ወንድ ልጅ ካለ የአስር ዓመት ልጅም ቢሆን የስያሜ ከበራ ይፈጸምለታል፡፡ ምክንያቱም ስያሜው የሚካሄደው ከመጀመሪያ የጋብቻ ስርዓት ጋር በመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ልጅ እግር ከሌለ ከትላልቆች ውስጥ ሊመረጥ ይችላል፡፡ አንዳንዴም መስፈርቶቹን የሚያሟላ የደረሰ የቃሉ ልጅ ከሌለ፤ ከሚቹ ቃሉ ወንድሞች ውስጥ መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሊሰየም ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ከቀድሞው ቃሉ ልጆች ውስጥ የሚሰየም ሰው ከታጣ፤ ትዳር ከመሰረቱት ውስጥ ሊሰየም ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህ የሚሰየመው ሰው ቀድሞ የፈጸመው ጋብቻ የተለያየ የጋብቻ ዓይነት ሊሆን ይችላል፡፡ ያገባትም ሴት ከጉጂ ኦሮሞ የተለያዩ ጎሳዎች ወይም ከሌላም ብሔር ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ለቃሉ ስያሜ የሚያስፈልገው ትልቁ መስፈርት ጋብቻ መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡ ይህ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ደግሞ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል የጋብቻ ስነ-ስርዓት የተለየ ክንዋኔዎችን የያዘ ነው፤ ብዙ ልዩነቶችም አሉት፡፡

እንደሚታውቀው በኦሮሞዎች ዘንድ የተለያዩ ዓይነት የጋብቻ ስርዓቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ማጨት (kadhaa)፣ ጠለፋ (buta)፣ ወደገባ (addibaanaa)፣ ማባበል (awadii)፣ የውርስ ጋብቻ (dhaaluu) እና ሲጋባ (sigabaa) ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ለቃሉ ስያሜ የሚፈጸመው የጋብቻ ስርዓት በልመና ወይም በማጨት የሚከናወነው ነው፡፡ ለቃሉ ስያሜ የምታስፈልገውን ልጃገረድ ከማጨቱ አንስቶ እስከ ጋብቻው ዕለት ድረስ ያለዉን የጋብቻውን ሂደት በስፋት በ 6.5 ስር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

እስካሁን ባለው መረጃ 16ኛው አባቃሉ ተሰይመዋል፡፡ እነሱም ከመረጃ አቀባዮቼ ባገኘሁት መረጃ መሰረት በቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው ያስቀምጧቸዋል፡፡

1ኛ. አባ ቃሉ ቁሉቤ ሎኮ
2ኛ. አባ ቃሉ ጋዶዬ ቁሉቤ
3ኛ. አባ ቃሉ ዳንቢ ጋዶዬ
4ኛ. አባ ቃሉ አጋ ዳንቢ
5ኛ. አባ ቃሉ ጋላኒ አጋ
6ኛ. አባ ቃሉ ቦሩ ጋላኒ
7ኛ. አባ ቃሉ አዳዮ ቦሩ
8ኛ. አባ ቃሉ ሳቆ አዳዮ
9ኛ. አባ ቃሉ ኮዮ ሳቆ
10ኛ. አባ ቃሉ በሪሶ ኮዮ
11ኛ. አባ ቃሉ ኤሉ በሪሶ
12ኛ. አባ ቃሉ ህርባዬ ኤሉ
13ኛ. አባ ቃሉ ቶቴ ህርባዬ
14ኛ. አባ ቃሉ ናጋኦ ቶቴ
15ኛ. አባ ቃሉ ሳቆ ናጋኦ
16ኛ. አባ ቃሉ አጋ ሳቆ ናቸው፡፡

ከነዚህ ውስጥ አባቃሉ ሂርባዬ ለየት ያለ ታሪክ እንዳላቸው ይነገርላቸዋል፡፡ ይኸውም አባቃሉ ሂርባዬ ብዙ ዓመት ካስቆጠሩ ቃሉዎች አንዱ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም የሶስት ትውልድ ዕድሜ ኖረው በአራተኛው ሰው ዕድሜ የሞተ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ስለ አሟሟታቸውም ሲያስረዱ፡-

> ብዙ በመቆየታቸው ፈጣሪያቸውን እንዲያሳርፋቸው በመጠየቅ ነው፡፡ ምክንያቱም የኖሩት በግምት ከ300 ዓመት በላይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚያም ሰባት የከብት ኮርማ፣ ሰባት ትላልቅ እንስራ ጠጅ (Duloo torba) አዘጋጅተው፣ ፈጣሪውን እንዲህ ብሎ ለመነ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ! ይሄው የሦስት ትውልድ ጓደኞቼን እድሜ ኖሬ አራተኛው ላይ ነኝ፤ ስለዚህ ውሰደኝ፡፡›› ብሎ ለፈጣሪው ነገረ፡፡ ሳይታመም፣ አንድ ነገር ሳይሆን፣ ህመም ሳያየው እግዚአብሔር ባለው ጊዜ ወሰደው፤ ይህንን አውቃለሁ፡፡ በዚያን ዘመን ወደ 300 ዓመት ያህል ኖረ፡፡ ልክ እንደ ማቱሳላ እንደሚባለው ነው፡፡ ሌላም እንዲሁ ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ አባቃሉ ኤሉ ወደ 200 ዓመት ኖሯል፡፡ የቀብሩም ቦታ ዶኬኖ የሚባል ቦታ ነው፤ አስከሬኑ ያረፈው እዚያ ነው፡፡ በባንቆ ቀበሌ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ በዚያን ዘመን የሰው ልጅ ዕድሜ በጣም ረጅም ነበር፤ እንዳሁኑ ሰው ዕድሜው አጭር አልነበረም፡፡ (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ 13/12/2007 ዓ.ም.፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

በዚህ ላይ በማከል አቶ ኀበና ጉጀ፡- ስለቃሉ ሲያብራሩ፡-

ጎሳቸው ትልቅ ነው፤ ዕድሜያቸውም ረጅም ነው፤ መርቀውም ያደርሳሉ። ከረገሙም ይደርሳል። የነሱ የሆነ ሁሉ ጥሩ ነው። ጥሩ ኑሮ ይኖራሉ፤ በዕድሜያቸውም ብዙ ይቆያሉ። የእሱ አባት እያሉ ወደ አቶ ሞኮና ናጋኦ እያመለከቱ (አባ ቃሉ ናጋኦ ቶቴ) እራሱ በጣም ቆያቷል። ወደ 150 አመት አይሆንም?፤ አዎ ይሆናል። እንዲህ ቆይተዋል፤ የእሱ አባት እንኳን። የሰው ልጅ 150 አመት የሚኖር አለ? የለም። በማለት ገልጸዋል። (አቶ ጎበና ጉጆ፣ 13/12/2007 ዓ.ም.፣ ካላሉቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

ከነዚህ መረጃዎች የምንረዳው አንዳንድ ቃሉዎች ረጅም ዓመት እንደኖሩና የስልጣን ሽግግሩም ከአባት ወደ ልጅ መሆኑን በቅደም ተከተል ያሳየናል።

## 5.1.3. የቃሉ መማክርት አባላትና ተግባራቸው

በመጀመሪያ ደረጃ ቃሉ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ክበራዎችን የሚከውነው ከተለያዩ የመማክርት አባላቱ ጋር በጋራም ሆነ በተናጥል በመሆን ነው። የቃሉ መማክርት አባላት ቃሉ ጨምሮ የገዳ አባቶች፣ ኮከብ ቆጣሪዎች፣ ካሎዎች፣ ሞራ አንባቢዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ሀዳ አንባ ናቸው። ለቃሉ ሀዳ አንባ እንደሆነችው ሁሉ፤ ለገዳም አዳ ቦላ ትሳተፋለች። በመማክርቱ ውስጥ ቃሉ የመሪነቱን ቦታ ይይዛል። በመቀጠል አባገዳዎች የሁለተኛውን ቦታ ሲይዙ፤ በራሳቸው ተቋም ደግሞ የመሪነቱን ቦታ ይይዛሉ። ሌሎቹ አባላት በአጋርነት የሚያገለግሉ ናቸው።

እያንዳንዱ የቃሉ መማክርት አባላት በሃይማኖታዊ ክበራዎች ወቅት የእነሱ መረጃዎች ተዳምሮ ያለፈው ወቅት ምን ይመስል ነበር? ወይም እንዴት አለፈ?፣ አሁንስ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንገኛለን? ለወደፊት ምን ይጠብቀናል? ለሚሉት ጉዳዮች ሁሉ ፍንጭ አመላካቾች ናቸው። ቃሉ ደግሞ በነዚህ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ለየትኛው ክስተት ምን ዓይነት ክብት ለመስዋዕት እንደሚቀርብ፣ በየትኛው የአምልኮ ስፍራ እንደሚከወን ያሳውቃል። ገዳዎችና ሽማግሌዎች ህብረተሰቡን የማስተባበሩን ኃላፊነት ይወጣሉ። ይህንና የመሳሰሉትን ተግባራት በእያንዳንዱ የመማክርት አባላት ምንና እንዴት እንደሚከወኑ በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### 5.1.3.1. የቃሉ ተግባራት

የቃሉ ተቋም ለጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰብ ያለውን የጎላ ባህላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች በስፋት ለማየት ችለናል። እንደ ሃገረሰባዊ ሃይማኖቱ ተከታዮች እምነት ቃሉ በመጀመሪያ ደረጃ እግዚኣብሔር ከሰማይ ወደ ምድር ያወረደው የሰው ልጅ በምድር ሲኖር

እንዴት መኖር እንዳለበት ከፈጣሪ የተሰጠውን ህጋጋት ለማስተማርና ህግጋቶቹንም ለማስከበር ነው። ቃሉ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚያደርገው በመንፈስ (ayyaana) በኩል ነው።

እንደሚታወቀው የዋቄፋና ሀገረሰባዊ ሃይማኖት በጽሑፍ የሰፈረ የእምነቱ ህግ (ዶግማ) የለውም። እግዚሐብሄር የእምነቱን ህግጋትን ለምዕመኑ እንዲያስተምርና እንዲያስጠብቅ የሰጠው፤ በሰው ልጆችና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ እንዲያገለግል፤ ከሰማይ ያወረደው ቃሉን እንደሆነ አብዛኛው በጉዳዩ ላይ ጥናት ያካሄዱ አጥኚዎችና የጉዲ አዛውንቶችም ይገልጻሉ። ስለዚህ የቃሉ ተቋምና የቃሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ለሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ማዕከል ናቸው (Mohammed, 1994:6-9)። ምክንያቱም ቃሉ ለሰው ልጆች መተዳደሪያና ሊከበሩ የሚገባቸውን ህግጋት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠውና እነሱንም የሚያስተምርና የሚያስከብ እንደሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታመናል።

ታቦር (2006) የብሩ ፀጋዬን ሀሳብ በመጥቀስ ዋቃ ለቃሉዎችና ለአያንቱዎች ነቢያትና ሐዋርያት የገለጹላቸውና እንዲከበሩ ያስተምሩ ዘንድ ያዘዛቸው ምሰሶ (አእማድ) ሕግጋት እንደሚከተለው ይዘረዝራል። እነሱም፡-

1. ***ማምለክ (Waaqeeffachu)፡-*** *ዋቃን የማምለክ ትዕዛዝ፤ እያንዳንዱ ግለሰብ፣ ቤተሰብና የአካባቢ ነዋሪ በግልና በጋራ የሚያከናውነው የዕለታዊና ወቅታዊ ስርዓተ ጸሎትና ምስጋና እንዲሁም፣ የስርዓተ መስዋዕት እንዲሁም፣ የስርዓተ ቀብር ትግበራዎች ያሉት ነው።*
2. ***እቀባ (Laguu)፡-*** *የእቀባ ትዕዛዝ መደረግ የሌለበትንና መበላት የሌለበትን ማናቸውንም ነገር ያካተተ ነው። በዋቄፋና ሃይማኖት መደረግ የሌለባቸውና ክልክል "ላጉ" የሆኑት የሰው ነፍስ ማጥፋትን፣ ስርቆሽን፣...ያካትታል።*
3. ***ሳፉ (Safuu)፡-*** *በዋቄፋና ሃይማኖት ልጆች ወላጆቻቸውን፣ ታናናሾች ታላላቆቻቸውን፣ ወጣቶችና ጎልማሶች አረጋዊያንን፣ እያንዳንዱ ዋቄፈታ ቃሉዎችንና አያንቱዎችን ማክበርና ቀድሞ ወንዝ ከመሻገር፣ ቀድሞ ከመመረቅ፣ እንደተቀመጠ ሰላምታ ከመስጠትና በነጠላ ስም ከመጥራት መታቀብ ይጠበቅበታል። ዋቃ ቀኑን ለሰዎችና ለቤት እንስሳት፣ ሌሊቱን ለዱር አራዊት የፈቀደ በመሆኑ ይህ መሻር እንደሌለበትና የደኖች ልምላሜና የወንዞች ንጽህና መጠበቅ እንዳለበት የሚያዝ ሕግ ነው። ፈረሃ-እግዚሐብሔርን፣ ወግና ባህልን መጠበቅ እንደማለት ነው።*

4. ***ቅዱስና ክቡር*** *(Ulfaa)፦ ወንዞች፣ መልካዎች፣ ተራሮችና ኮረብቶች፣ አዳ፣ በኩ፣ ጫጩ (ሣጎል) እና ከለቻ፣ ሲቄ፣ ቀነፋና የጫጩና ከለቻ መጎናጠፊያዎችና የገዳ ገዞ፣ ባንዲራዎች (Faajjii) ክቡረ ክቡራን ናቸው፡፡*

5. ***በፀጋ መቀበል*** *(Hooda)፦ እንደ አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እህትና ልጅ ያሉ የቅርብ ስጋዎች እንኳን ሲሞቱ ከቀብራቸው በኋላ እንደ ዋቃ ፈቃድ በፀጋ ተቀብሎ፤ በዚህ በቃ ይል ዘንድ "ሆዳኔ" ይባላል እንጂ፣ ሀዘኑ ለምን ደረሰብኝ በሚል ዋቃን አያማርሩትም በማለት ያስረዳል፡፡*

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ሳፉ (safuu) የምንለው የባህላዊና ተፈጥሯዊ ሕጎች ጥምረት ነው፡፡ በኦሮሞ ዘንድ ባህላዊ ሕጎች የምንላቸው ታናሽ ታላቁን የማክበር፣ ልጆች ወላጆቻቸውንና አዛውንቶችን የማክበርና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ተፈጥሯዊ ሕጎች የሚባሉት ደግሞ ጋብቻ በተመለከተ በተቃራኒ ጾታዎች መካከል ካልሆነ አይፈቀድም፣ እንዲሁም ከእንስሳት ውስጥ የሚበሉና የማይበሉ አሉ፡፡ ባጠቃላይ ሳፉ ፈርሃ-እግዚሐብሔርን፣ ወግንና ባህልን መጠበቅ እንደማለት ነው፡፡

እነዚህን የዋቄፋና እምነት ህግጋቶች ከእግዚሐብሄር ወደ ቃሉ፣ ከቃሉ ደግሞ ወደ ምዕመኑ፤ እንዲሁም ከምዕመኑ ወደ ምዕመኑ እየተላለፈ እዚህ የደረሰው በስነቃልና በድርጊት አማካይነት ነው፡፡ ይህ ባህሪይ ደግሞ የማንኛውም ሀገረሰባዊ ሃይማኖት መተላለፊያ መንገድ ናቸው፡፡

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን የእግዚሐብሄር ህግጋት በዋናነት የሚያስከብረው ደግሞ ቃሉ እንደሆነ Alemayehufi kan biroo, (1999፡115) ያስረዳል፡፡

እግዚኣብሔርን ማመን የሚያመለክተው እግዚኣብሔር በዓለም ላይ ለሚኖሩ ሁሉ ምንጭና መገኛው እሱ እንደሆነ የሚያሳይ መሰረታዊ እምነት ነው (Van de Loo, 1991፡284)፡፡ የጉጂ ኦሮሞ እግዚኣብሔር ብሎ የሚጠራው ፈጣሪውንና ሰማዩን ባንድ ላይ ነው፡፡ አንዳንዴ ሰማዩን ወይም ህዋውን ላይ (gubbaa) በማለት ከላይ ያለው እግዚኣብሔር በማለት የሚጠሩበት ጊዜም አለ፡፡ በሁለቱም አቅጣጫ እግዚኣብሔርን ሲጠሩ ፈጣሪና ማደሪያዉን/ መኖሪያውን ጭምር ነው፡፡ ለዚህ ጥሩ መገለጫው አንዳንድ የጉጂ ሽማግሌዎች በምርቃንና በእርግማን፤ እንዲሁም በምልጃ ፀሎት ወቅት ወደላይ በማንጋጠጥና እግዚኣብሔርን ከመገኛው በመለማመን ነው፡፡

ሌላው የጉጂ ኦሮሞ እግዚኣብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ (uuma) እንደሆነና በሰማይና በምድር መካከል ከሱ የተሰወረ ነገር እንደሌለ ያምናሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ በሰው ዘንድ ለተሰሩ

ጥሩ ስራ (waan gaarii) እና ኩነኔ (cubbuu) ሲሆኑ፤ ለእግዚአብሔር ማስረጃዎቹ ደግሞ ሰማይና ምድር እንደሆኑ ያምናሉ፡፡

አንዳንዴ ይህ ሁሉ ልመናና መስዋዕት ቀርቦ ነገሮች እንደቀድሞው በሰላማዊ መንገድ ላይቀጥል ይችላል፡፡ ይኸውም ልጅ ያልወለደች ሴት መሀን ሆና ትቀራለች፣ ሰዎች ይታመማሉ፣ ከብቶች ይሞታሉ፡፡ የጉዲ ህዝብ በሌሎች እጅ ወድቀው ሊጨቆኑ ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም ይህ ሁሉ የሚሆነው በእግዚአብሔር ፍቃድ እንደሆነ እግዚአብሔር ያችን ሴት በዚህ መልኩ እንዲትኖር ፈጥሯታል ወይም "እግዚአብሔር ከእኛ ዘንድ ርቋል" በማለት ይገልጻሉ (Van de Loo, 1991፡284)፡፡ እንደ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ይህ ከእግዚአብሔር ህግጋት ውስጥ የእግዚአብሔር ስራ ነው ብሎ በፀጋ መቀበልን ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በኦሮሞ አተያይ ይህ ዓለም ሦስት ነገሮችን ይዟል፡፡ እነሱም፡- “አያና”፣ ”ኡማ” እና, ”ሳፉ” ናቸው፡፡ “አያና” ቀደም ሲል እንደተገለፀው መንፈስ እንደማለት ሲሆን፤ የዋቃ አንዱ መከሰቻ ነው፡፡ ”ኡማ” የሚለው ቃል ደግሞ ድርብ ፍች አለው፡፡ አንዱ ፈጣሪ የሚል ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ፍጡር ማለት ነው፡፡ ይህ ድርብ ፍች ዋቃና እርሱ የፈጠረውን እንደ እንስሳዊ፣ ዕፅዋቱ፣ ማዕድናቱ እና መንፈሳዊ፤ ባጠቃላይ ይህን ዓለም ይመለከታል፡፡ ”ሳፉ” ደግሞ የሰው ልጆች እንቅስቃሴዎች የሚመዘኑበት የሥነ-ምግባር መርሆች ናቸው፡፡ ስለዚህ በኦሮሞ አተያይ ይህ ዓለም የነዚህ ሦስት ነገሮች መስተጋብር ውጤት ነው፡፡ ለተለያዩ ነባር ባህላዊ ክዋኔዎች መቀጠልም አስተዋጽኦ ያበረከቱት የነዚሁ ጽንሰ ሃሳቦች ቀጥሎ መገኘት ነው (*Gemechu, 2005:70-71*)፡፡

እነዚህ የኦሮሞ የዓለም አተያይ መግለጫዎች የተባሉት ጽንሰ ሀሳቦች የደስታና ሀዘን፣ የሀጢያትና የጽድቅ መግለጫ ክዋኔዎች መጠበቂያ ከበራዎች ማራመጃም ስለሆኑ በከበራዎች ውስጥ በመምጣታቸው እንደ አገባባቸው ተተንትነዋል፡፡

እንደ መረጃ አቀባዮቼ ገለጻ በቃሉና በእግዚአብሔር መካከል የሚያገናኘው የእግዚአብሔር መንፈስ የሆነ፣ መንፈሱም የተቀደሰ፣ የተረጋጋና ለቃሉ፣ ለገዳ፣ ለሀገር ሽማግሌዎች በተለያዩ ድርጊቶችና መልኮች የሚገለጽ፤ ይኸውም፡- በህልም፣ በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶች መልክ የሚገለጹ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ክስተቶች እንደየቅለታቸውና ክብደታቸው በየደረጃው የሚፈቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ በአካባቢው ጦርነት፣ ድርቅ፣ የሰውና የከብት በሽታ ቀድሞ እንዳይከሰት፤ ባጋጣሚ ከተከሰተ ደግሞ ባለበት ሁኔታ እንዲያበቃና ዳግም እንዳይከሰት ቃሉ

ለፈጣሪው መስዋዕት በማቅረብ ይለማመናል፤ ህዝቡም ከፈጣሪ ጋር ያማልደናል ብለው ያምናሉ።

የጉጂን አካባቢና ህዝቡን የሚጠብቀው በሰማይ የሚኖረው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የጉጂ ቄዬዎችን፣ ከብቶቻቸውንና የከብቶቻቸውን በረት ይጠብቃል። እሱም ከአድማስ እስከ አድማስ በጉም የተሸፈነ ነው። እንደ ጉጂ ኦሮሞ የዓለም አተያይ እግዚአብሔር ሁሉም ነገር በተትረፈረፈበት ዓለም ውስጥ የሚኖር እንደሆነና ከሰው ልጅ በመስዋዕት መልክ የሚቀርብለትን ይቀበላል ብለው እንደሚያምኑ Hinnant, (1977፡35) ያስረዳል። ታዲያ ይህንን ለእግዚአብሔር መስዋዕት ማቅረብና የምህረት ልመናን በዋናነት የሚያከናውነው ቃሉ ነው።

ሌላው የቃሉ ተግባር በዋናነት ለገዳ ስልጣን በየስምንት ዓመቱ ያለምንም ደም መፋሰስ የስልጣን ሽግግር እንዲያደርጉ፣ ህዝቡንም በቅንነትና ያለአንዳች መድሎ እንዲያስተዳድሩ ቃለመሀላ በማስፈጸምና ስልጣነ ሢመቱን የማጽደቅና የመባረክ ተግባራትን ሲፈጽም፣ ከዚህ በተጨማሪ በተዘዋዋሪ መንገድ ለገዳነት የሚቀርቡ ዕጩዎችን ምርጫ ጭምር አስተያየት በመስጠትም ይሳተፋል። ባጠቃላይ በገዳ ስርዓት ፖለቲካ ውስጥ ቃሉ በስልጣን ሽግግር ላይ ከፍተኛ ሚና አለው (Alemayehufi kan biroo, 1999፡110)።

የጉጂ ቃሉ የጌዴኦ ብሔረሰብም ቃሉ ነበር፤ የጌዴኦ አባገዳም ልክ እንደ ሀሉና ዌስቱ ገዳዎች ለቃሉ ስጦታዎችን ይዞ በመምጣት ምርቃትና ከርቤ (qunbii) ይቀበል ነበር። ነገር ግን በአሁን ወቅት ይህን ሂደት እንደማያከናውኑና እዚያው በራሳቸው በጉሳ ሀለቃ አማካይነት ይፈጽማሉ (አባገዳ ደንቦባ ጉሚ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ እና አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ8/9/2007 ዓ.ም.)። ይህ ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ በምዕራፍ ሰባት ስር በዝርዝር ታይቷል።

ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ግጭቶችን ማስወገድና መፍታት እንዲሁም ለግጭቱ የመጨረሻ እልባት መስጠት ከቃሉ ተግባራት ውስጥ አንዱ ነው። በተለይም ምክንያቶች በግለሰቦች፣ በቡድኖችና በአጎራባች ብሔርና ብሔረሰቦች መካከል ለሚፈጠሩ ግጭቶችና በግጭቱም ምክንያት የሰው ነፍስ ከጠፋ በጎንዶሮ ከበራ ለግጭቱ የመጨረሻ ገደብ የሚበጀው በቃሉ ነው። ታቦር፣ (2006፣199) ይህንኑ ሀሳብ አጠር ባለ መልኩ ቃሉዎች ካሉባቸው ኃላፊነቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ በማለት እንደሚከተለው ያስረዳል። እነሱም፡-

- ✓ ምርጫ ላይ ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ መስጠት፣
- ✓ ለተመረጡ የገዳ ባለስልጣኖች ምርቃትና እውቅና መስጠት፣

- ✓ ሕግና ልማዶች እንዲከበሩ ማስተባበር፣
- ✓ የተፈጥሮ ሕጎች (ሳፉ) እንዳይጣሱ መጠበቅ፣
- ✓ የፈውስ ጸሎት ማድረግ፣ የበደሉ ክሰው፣ የተበደሉ ተክሰው እንዲታረቁ ማድረግ፣
- ✓ የፈጣሪን ሕግጋት ማስተማር፣
- ✓ በአካባቢያቸው በሚካሄዱ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ላይ መሪዎችን ማበረታታትና እውቅና መስጠት ናቸው።

ነገር ግን የጉጂ ቃሉ እነዚህን ተግባራት ሲያካትት የኃመቺሳን ስርዓት ግን በቃሉ ተቋም ውስጥ አይከወንም።
ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ ተግባር ምንድነው በማለት አቶ ሞኮናን ለጠየኳቸሁ፤ እሳቸውም ሲመልሱልኝ፡-

> *አንድ ሰው በማንኛውም ሰው ላይ ይሁን በራሱም ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል። አንድ ሰው እንዳጋጣሚ ሰው ሊገድል ይችላል። ወደ አባ ቃሉ ተቋም ("ገልማ") ከሸሸ የገዳዩ ቤተሰብና ንብረት ላይ የሟች ቤተሰብ ጥቃት እንዳያደርስ ይታደጋል። አባ ቃሉ ከተቋሙ ድረስ እንዲመጡ ወይም ጫን ያለ እንደሆነ ከመማክርትአባላቱ ጋር ችግር የተፈጠረበት አካባቢ በመሄድ ጉዳዩን ይፈታል። በአብዛኛው የመማክርትአባላቱ የቃሉ የሰላም መልክተኛ በመሆን በተላኩበት ሁሉ በመሄድ በተቻላቸው መጠን ለመፍታት ይጥራሉ። ከአቅማቸው በላይ ከሆነ ጉዳዩን ወደ ተቋሙ በማምጣት ለቃሉ ያቀርባሉ። ከዚያም ለአባቃሉ የነበረውን ሂደት በማስረዳት ያስተላልፋሉ። አባ ቃሉም ያለው እውነት ላይ ተመስርቶ ይወስናል። የአባ ቃሉ ውሳኔ ውሎ ያድራል እንጂ ይፈፀማል። 'አሞራ በራ፣ በራ ሞቷ ከመሬት ነው (allaattiin martee, martee duuti ishii lafa.) ይባል የለ?' "አሉኝ።* (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ 13/12/2007 ዓ.ም.)

ሌላው በቃሉ መማክርት አባላት የተላለፉ የውሳኔ ሀሳቦች አልተገበርም የሚል ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ካለ በስተመጨረሻ ላይ ቃሉ የማህበረ-ፖለቲካ ማዕቀብ (bokuu) ያስተላልፋል። ይህን ማዕቀብ ማህበረሰቡም እንዲተገብሩት በተዋረድ ይተላለፍና በተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል። የቃሉና የገዳ ተቋማት አንዱ ከአንዱ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና አንዱ ውስጥ ሌላኛው እንዳለ Hinnant, (1977) እንደሚከተለው ይገልጻል፡-

*The issue of dispute settlement is intertwined both in Gada and spiritual institutions. Guji believe in supernatural power called"Waqa", which literally means both "Sky" and "God". But it is the second meaning that is attached to their belief. They assume that Waqa lives far above the earth and sent Qallu for the people with Gada, law of peace and ways of life. Therefore, it is believed that disobeying any Gada laws and principles of peace (nagaa) would create misfortunes upon the person(s) or group(s)...*

*...If disputes could not be resolved at jarsa biyya level, the offices of Abba Gada and his advisors were the highest court of appeal in traditional Guji legal system.*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በጉጂ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ሃይማኖትና የባህላዊ ህጉ ስርዓት በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ጠቦች ወይም ግጭቶች ቢከሰቱ ቀድሞ በሀገር ሽማግሌ የሚታይ ሲሆን፤ ከእነሱ አቅም በላይ የሆነው ወደቃሉና አባገዳ ተቋም በማድረስ እንደሚፈታ ነው። በመቀጠል Hinnant በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የእግዚሐብሄር፣ የቃሉ፣ የገዳና የማህበረሰቡን ትስስር ያስረዳናል። ይኸውም፦ ጉጂዎች በእግዚሐብሄር እንደሚያምኑና እግዚሐብሄርም ከምድር ርቆ በሰማይ እንደሚኖርና ለህዝቡም ቃሉንና የገዳን የሰላምና የምዕመኑ የሕይወት መንገድ ማሳያ ህግጋት ጋር እንደተሰጣቸው ያምናሉ። ለዚህ መመሪያዎችና ህግጋት አለመገዛት ወይም አለመታዘዝ ደግሞ ድርጊቱን አሻፈረኝ ባለው/ባሉት በግለሰቡ፣ በግለሰቦቹ ወይም በቡድኖቹ ላይ መጥፎ ክስተት እንደሚያስከትልባቸው ያምናሉ።

የጉጂ ኦሮሞ ስለቃሉ ተግባር ሲገልጹ፦ ‹‹እኛ ቃሉን የምንፈልገው በጎሳው በሽታ እንዳይኖር፣ ጎሳው ሰላም እንዲሆን፣ ከብቶቻችን ጤናማ እንዲሆኑ፣ ከዚያም ኮርማው ለስሪያ እንዲነሳሳ (korma gaanaf kaasi)፣ አዱኛችንን መልስልን፣ ረድኤተ-በረከቱን አምጣልን እያለ ስለምጸልይና ስለሚያሳካልን ነው። እንዲህ እያለ ካልጸለየ ችግር ይፈጠራል።›› ብለው ያምናሉ። (ወ/ሮ ዲኮ ሚጁ፣ አባያ ወረዳ፣ የካላልቱ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ፣ 13/12/2007 ዓ.ም.)




ፎቶ፡-2 አባ ቃሉ አጋ፣ አቶ ሞኮና (የቃሉ አጎት)፣ አባገዳ ሀልቻዬ እና ሌሎች የመማክርት አባላቱን የሚያሳይ

### 5.1.3.2. የገዳ ተግባራት

ወደ ገዳ ተግባራት ከመግባታችን በፊት ስለ ገዳ ምንነትና አንዳንድ ተያያዥ ጉዳዮችን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ገዳ የተወሰነ ዑደት ያለው ሆኖ በየስንምት ዓመቱ ከአንዱ የገዳ እርከን ወደሚቀጥለው እርከን የሚሸጋገሩበትና ስልጣን በሰላማዊ መንገድ የሚሸጋገርበት ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርዓት ነው፡፡ በአንዳንድ አካባቢ በስድስተኛ የገዳ እርከን ላይ የሚገኘውንና በስልጣን ላይ ያለውን ገዳ ብለው ይጠራሉ፡፡

አባ ገዳ ደግሞ በገዳ ስርዓት ህግ ለስምንት ዓመታት እንዲያገለግሉ በህዝብ ተመርጠው ስልጣን ላይ የሚወጡ ባለስልጣኖች ወይም የአስተዳደር አባላት ቁንጮ ነው፡፡ አባ ገዳ በቤተሰቡ ውስጥ ታላቅ የሆነና አክብሮት ያገኘ፣ የእሱ ጎሳ የሆኑት ሁሉ ምንም ዓይነት ግፍ ያልዋሉና የገዳን ስርዓትና ደንብ የሚያከብሩ፣ ባለትዳር፣ ጤናማና ትዳር መስርቶ ልጆች ያፈራ፣ የማይዋሽ፣ ብልህ፣ የንግግርና የአመራር ችሎታ ያለው ሰው መሆን አለበት (ታቦር፣ 2006፡ 218)፡፡ ከዚህ መስፈርት ውስጥ በሰው ልጅ ዘንድ አንድ ሰው ከተለያዩ ሀጢያትና ግፍ እራሱን ጠብቆ ሊኖር

ይችል ይሆናል። ነገር ግን የእሱ ጎሳ የሆኑት ሁሉ ከዚህ ዓይነት እንከን ነጻ መሆን ትንሽ የሚከብድ ሁኔታ ይመስለኛል። ያም ሆን ይህ የዕጩው ስብዕና ግን ወሳኝ ነው።

ከላይ እንዳየነው በገዳ ስርዓት አንድ አባገዳ በስልጣን ላይ የሚቆየው ለስምንት ዓመታት ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ማለትም፡- በስደት፣ በመጥፎ አደጋ ሰዎች ከስፈራቸው ሲፈናቀሉ፣ ከብቶቻቸው በተለያዩ ችግሮች ካለቁባቸው፣ ረሃብ ባገሩ ከገባ፣ ሀገሩ በጦርነት ከታመሰ፣ መረጋጋት ከጠፋና ይህን የሚመስሉ አስቸጋር ክስተቶች ከተፈጠሩ የአባገዳዎች የስልጣን ሽግግር ሂደቱ ሊተላለፉ ይችላሉ። ስምንት ዓመት የሞላው አባገዳ ለተወሰኑ ተጨማሪ ጊዜያት ሊያስተዳድር ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች እልባት በሚያገኙበት ወቅት ስልጣኑን ለቀጣዮቹ የገዳ አባላት በደረጃው ያላንዳች ችግር እንዲተላለፍ ይደረጋል። ይህን የስልጣን ሽግግር ለቀጣዩ የገዳ አባላት ያለማስተላለፍ ማለት የእግዚኣብሔር ህግ እንደተጣሰ ይቆጠራል። ከዚህ በተጨማሪ የገዳ ስልጣን ዑደቱን ማዛባት እንደ ሀጢያት (cubbuu) ስለሚቆጠር ለችግሩ ምክንያት በሆኑት አካላት ላይ ጫን ያለ ቅጣት ያስከትላል (Alemayehufi kan biroo, 1999፡169)። ተተኪው የገዳ እርከንም በባህሉና እምነቱ መሰረት ህጉ ስለሚፈቅድለት ስልጣኑን ያላንዳች ችግር አስገድዶ እስከመውሰድ ይደርሳሉ።
በማህበረ-ባህላዊ መሰረት ቦታውን ለሚለቀው አባገዳ ለመጦሪያው የሚሆነው ከብቶች ይሰጠዋል።ከብቶቹም በጃልዳባ አማካይነት ለማዋጣት ፍቃደኛ ከሆኑ ቤተሰቦች ላይ ይሰበሰባል። ነገር ግን ስርዓቱን አዛብቶ ወይም በጫና ቦታውን ለለቀቀ አባገዳ ግን ምንም እንደማይደረግለት ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ።

የጉጂ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በ 2008 ዓ.ም. ባሳተመው ልዩ እትም ላይ የካቲት/2008 ዓ.ም. የተካሄደውን የገዳ ስልጣን ርክክብ 74ኛው እንደሆነ ይገልጻሉ። እያንዳንዱን የስልጣን ሽግግር ያላንዳች የጊዜ መዛነፍ በየ8 ዓመት ልዩነት እንደተከናወነም ተገልጿል። ይሁን እንጂ ከመስክ የተገኘው መረጃ ግን የሚያሳየው ከዚህ የተለየ ነው። ምክንያቱም እንደነ አባገዳ አጋ ጤንጣኖ ያሉ ማህበረ-ባህሉ ከሚፈቅድላቸው ጊዜ ያሳለፉ እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህን በተመለከተ በምዕራፍ ሰባት ስር ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ተተንትኖ ቀርቧል።

በመግቢያው ውስጥ እንደተጠቀሰው በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ሁለት ዓይነት የገዳ ስልጣን አያያዞች አሉ። እነሱም፡- አንደኛው ከላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በየስምት ዓመቱ የሚመረጥና ሁለተኛው ደግሞ በዘር የሚተላለፍ ማለትም ከአባት ወደ ልጅ የሚሸጋገር ናቸው። የሁለተኛው

ዓይነት የሚገኘው በአላብዱ ጎሳዎች ውስጥ ነው፡፡ ከነዚህ የገዳ ዓይነቶች ውስጥ በቅርበት የቃሉ መማክርት አባላት ሆነው የሚያገለግሉት የሁለተኛው ዓይነት ገዳዎች ናቸው፡፡ እነሱም፡- አሁን ያሉት የሀሎ አባገዳ (ገዳ ደንበባ) እና የዌስቱ አባገዳ (ገዳ ሀልቻዬ) ናቸው፡፡

### i. የገዳ እርከን ደረጃዎች

በዕድሜ አደረጃጀት (አወቃቀር) መሰረት የገዳ ስርዓት እርከኖች አሉት፡፡ እነሱም፡- በገዳ ስርዓቱ ውስጥ ካላቸው ማህበረ-ፖለቲካዊ ተሳትፎ አንጻር የንቁ-ተሳታፊ ገዳ አባላትና የኢ-ንቁ ተሳታፊ ገዳ አባላት ናቸው፡፡ ይኸውም፡- በንቁ ገዳ አባላት ስር የሚዘረዘሩት ጋሜ፣ ደበሌ፣ ኩሳ (ፎሌ)፣ ራባ፣ ዶሪ እና ሉባ (ገዳ) ናቸው፡፡ በኢ-ንቁ ገዳ አባላት ስር የሚገኙት ደግሞ ዕድሜያቸው ከ48 ዓመት በላይ የሆኑ ማለትም፡-1ኛ ጉላ/ዩባ፣ 2ኛ ዩባ፣ 3ኛ ዩባ እና ሽማግሌ (ጃርሳ/ቁሉሉ) ይባላሉ (Alemayehufi kan biroo, 1999፡145)፡፡ ይህ እርከን የገዳ ስልጣን ካስረከቡት ደረጃ በላይ ያሉትን ያካትታል፡፡ እነዚህ እርከኖች የቱለማ ኦሮሞ ያማከሉ ናቸው (ዝኒ ከማሁ፡,2000፡69)፡፡

የጉጂ ኦሮሞን የገዳ አደረጃጀት የተመለከትን እንደሆነ በዋናነት የልጅነት ደረጃ የጎልማሳነት ደረጃ የአዛውንትነት ደረጃ እና የሽምግልና ደረጃ የተከፋፈሉ ሲሆን፤ በስራቸው እነማንን እንደሚያቅፉ የሚከተለው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | የገዳ ደረጃ | ዕድሜ | ተ.ቁ | የገዳ ደረጃ | ዕድሜ |
|---|---|---|---|---|---|
| I. | የልጅነት ደረጃ | | III. | የአዛውንትነት ደረጃ | |
| 1 | ጉዱሩ፣ ዳባሌ | 0-8 | 7 | ባቱ | 49-56 |
| 2 | ቃሬ | 9-24 | 8 | ዩባ | 57-72 |
| | የመጀመሪ ቃሬ | 9-16 | | ዝቅተኛ ዩባ | 57-64 |
| | የኋለኛ ቃሬ | 17-24 | | ከፍተኛ ዩባ | 65-72 |
| 3 | ኩሳ | 25-28 | IV. | የሽምግልና ደረጃ | |
| II. | የጎልማሳነት ደረጃ | | 9 | ጃርሳ ጉዱሩ | 73-80 |
| 4 | ራባ | 26-39 | 10 | ጃርሳ ቁሉሉ | 81-88 |
| 5 | ዶሪ | 37-40 | 11 | ጃርሳ ራቀያ | 89-96 |
| 6 | ገዳ | 41-48 | 12 | ጃርሳ ጊኛ | ከ97 በላይ |

ሠንጠረዥ፡-1 የጉጂ ኦሮሞ ገዳ ደረጃዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ (ምንጭ፡- ከ Dirribii Damusee (2009) ላይ ተሻሽሎ የቀረበ)፡፡

ይሁን እንጂ ከመስክ ምልከታ እንደተረዳሁት አንድ የገዳ አባል በራባ ደረጃ እያለ ትዳር መስርቶ ልጅ መውለድ ይጠበቅበታል፡፡ ታዲያ በዚህ ወቅት የተወለደ ልጅ በዶሪ እርከን ውስጥ ከጉዱሩ ደረጃ ወደ ዳባሌ የማሸጋገር ስርዓት ይከወንለታል፡፡ ይህ ሳይሆን ዘግይቶ ከተወለደ የዳባሌ እርከን አመለጠው ይባላል፡፡ ከዚህም የተነሳ በዕድሜ ላይ መሰረት ያደረገ ምደባ የሚፋለስበት ወቅት አለ፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ ውስጥ ለማየት እንደተቻለው በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የገዳን ደረጃ በአራት ዐቢይ ክፍሎች ተመድበው እናገኛለን፡፡ ከእነዚህ ከልጅነት ደረጃ ውስጥ ኩሳን፣ እንዲሁም ከጎልማሳነት ደረጃ ውስጥ ደግሞ የዶሪን እርከን በጥልቀት ለማየት ወስኛለሁ፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች በይበልጥ ለገዳ ስርዓት መሰረታዊ የሆኑ ማህበረሰባዊ ዕውቀት የሚያዋቅሩበትና የተለያዩ ተምሳሌታዊ ክዋኔዎችን የሚከውኑበት ደረጃ ስለሆነ ነው፡፡

### ሀ. የኩሳ ደረጃ

ለገዳ ስርዓት እያንዳንዱ እርከን የራሱ የሆነ ሚና ቢኖረውም በኩሳ (ከ25-28 ዕድሜ ውስጥ ያሉ) ወደፊት ኃላፊነት ለመረከብ የሚዘጋጁበት ወቅት ያሉ ስለሆነ በንቃት የሚሳተፉበት እርከን ነው፡፡ ይኸውም፡- የዚህ ደረጃ መጨረሻ ላይ ይህን የገዳ እርከን የሚመራና ከ20 ዓመት በኋላ በ48ተኛ ዓመቱ ደግሞ ገዳ ሆኖ ህዝቡን የሚያስተዳድር የሚመረጥበትና የተለያዩ ልምምዶችና ዝግጅቶች የሚደረግበትበት ደረጃ ነው፡፡ ስለዚህ የቡድኑ አባላት በተለያዩ ፕሮግራሞች እየተገናኙ የእርስ በርስ ትውውቅ (waldhaggii) ያደርጋሉ፡፡ በመቀጠል የቡድኑን አባላት የማብላት ፕሮግራሞች (nyaachisa) ይካሄዳል፡፡ ይኸውም፡- የነዚህ ልጆች አባቶች የሆኑት ዩባዎች እያንዳንዳቸው ኮርማ በማረድ ያበላሉ (gubbisa gaggeessuu)፡፡ በዚህ ጊዜ የኩሳዎች ሚና እርስ በርስ በአግባቡ መተዋወቅ፣ መብላት፣ መጠጣት፣ መጨፈርና መዝናናት ነው፡፡

ሌላው ኩሳዎች ከገዳ ቡድን (yaa'a gadaa) ጋር አብረው ይጓዛሉ፡፡ በዚህ ጉዞ ላይ አብዛኛውን የጉልበት ስራ በተመለከተ የሚያከናውኑት ኩሳዎች ናቸው፡፡ ይኸውም፡- ወደ ሚኤ ቦኮ የሚጎዳኙ ከብቶችን ማጎዳኘት፣ ለተጓዦቹ ከፊት ፊት ጥርጊያ መንገዱን መመንጠር፣ ባህላዊ ዕቃዎችን፣ የተለያዩ ምግቦችንና ቁሳቁሶችን ማጓጓዝ፣ የቡድኑን ማረፊያ (qachaa yaa'a) መስራትና የመሳሰሉትን ድጋፍ በመስጠት ከአባገዳዎች ስር ስር እያሉ የሚከውኑትን በመመልከትና በማዳመጥ ትምህርት ይቀስማሉ፡፡ እንዲህ እያሉ ወደ ፖለቲካዊ አመለካከትና ተግባር መሳተፉ ይጀምራሉ፡፡

በዚህ እርከን መጨረሻ ላይ ይህን ቡድን ሊመሩ ይችላሉ የሚባሉ የማስተዳደር ችሎታ፣ መልካም ስነ-ምግባር፣ መልካም ዕጣ-ፈንታ ያላቸው የሚባሉትንና የተስተካከለ ቁመና ያላቸውን፤ የጉጂ ሰባት ቤት እንዲወክሉ ተደርጎ በጥንቃቄ ስምንት ሰዎች ይመረጣሉ፡፡ እነዚህ የተመረጡት አባላት ወደፊት ከሃያ ዓመታት በኋላ የገዳን ስልጣን እስከሚረከቡ ድረስ ቡድኑን የሚመሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ ከወዲሁ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ ሂደቱም ስልጠና መግባት (Fooqa/ agaallaa Seenuu) ይባላል፡፡ እነዚህ ስምንቱ ሰዎች የየራሳቸው የስልጣን መጠሪያና የስራ ድርሻ አላቸው፡፡ መጠሪያቸውም 1ኛ. ፋጋ (ሁለት ሰዎች ይመረጣሉ)፣ 2ኛ. አባ ሙርቲ 3ኛ. ጃልካያ/እርኪሳ አባገዳ፣ 4ኛ. ሀዩ፣ 5ኛ. ጃልዳባ፣ 6ኛ. ዋሙራ እና 7ኛ. ቶርቢ ይባላሉ፡፡ እነዚህ አሁኑ አባሙርቲ የሆነው ስልጣን ሲረከብ የገዳ መማክርት አባላት ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ የስራ ድርሻቸውም፡-

1. **ጃልኬያ** (Jalkeya)

ጃልኬያ በገዳ ስርዓት ውስጥ አንዱ የመማክርት አባል ሲሆን አንዳንዴ እንደ ምክትል (irkisaa abbaa yaa'aa) ተብሎ ይጠራል፡፡

2. **ፋጋ** (Faga)

ፋጋ የሚመረጡ ከገላልቻ ጎሳ ሲሆኑ አብዛኛው ስራቸው ሃይማኖታዊ ትንበያዎችን ነው፡፡ ምክንያቱም ገላልቻዎች ወዩ ናቸው ይባላሉ፡፡

3. **ዋሙራ** (Waamura)

ዋሙራ የጉጂ ኦሮሞ ሰባት ቤት የሚወክሉ ሰባት ሰዎች ከጉባኤ ውስጥ የሚመረጡ ሲሆኑ፤ አብዛኛውን ጊዜ ስራቸው ጉባኤውን የመምራትና ድጋፍ መስጠት ነው፡፡

4. **ቶርቢ** (Torbii)

ቶርቢ ከጉጂ ሰባት ቤት የሚወክሉ ሰባት ሰዎች በጉባኤው የሚመረጡ ሲሆኑ፤ እነሱም የሚተላለፉ ደንቦችንና ውሳኔዎችን በማዳመጥ በስራ ላይ የሚያውሉ አካላት ናቸው፡፡

5. **ጃልዳባ** (Jaldhaaba)

ጃልዳባ ከጉጂ ሰባት ቤት የሚወክሉ ሰባት የሚመረጡ ሲሆኑ፤ እነሱን የሚመራና የመማክርት አባል የሚሆነው ማካላ (Makkala) ይባላል፡፡ እነሱ አባዛኛውን ጊዜ ስርዓት የማስከበር ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡




ፎቶ፡-3 የጃልዳባ አባላትን የሚያሳይ ፎቶ በሚኤ ቦኮ

6. ሀዩ (Hayyuu)

ሀዩ የሚባሉት ቀደም ሲል በገዳ የመማክርት አባልነት ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ለብዙ ዓመታት ያገለገሉና የካበተ ዕውቀት ያላቸው ሆነው በአዲሱ መዋቅር ውስጥ የሚመረጡና በማህበረ-ፖለቲካው እና ማህበረ-ባህላዊ ጉዳዮች ዙሪያ በማማከር የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

እነዚህ የተመረጡት አባላትና የእርከኑን ቡድን አባላት ሁሉም ለአንድ ወር ያለማቋረጥ በተዘጋጀላቸው የስልጠና ማዕከል በመግባት ይሰለጥናሉ፡፡ የስልጠናው ቦታ ከሰዎች መኖሪያ ራቅ ያለና ፀጥታ ያለው ቦታ ይመረጣል፡፡ በዚያ ስልጠና ቦታ መሀሉ ይታጠርና እነዚያ የተመረጡ ስምንቱ አባላት በስልጠናው ወቅት መሀል ሆነው ሲሰለጥኑ፣ የተቀሩት የመደቡ ቡድን አባላት ደግሞ አጥሩን ከበው በመንቀሳቀስ ስልጠናውን ይካፈላሉ፡፡ ስልጠናው የሚሰጠው በተሳታፊዎቹ አባቶች፣ በዩባ ደረጃ ባሉትና በቂ ልምድና ችሎታ ባካባቱት ነው፡፡ ይህ ሂደት የጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ ዕውቀት ሽግግር ያመላክታል፡፡

የስልጠናው ርዕሰ-ጉዳዮች በገዳ ስርዓት አስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ፣ በባህል ዙሪያ፣ የስራ ድርሻቸውንና ህጎች፣ ስነ-ምግባርን በተመለከተ፣ ስለውጊያ ስልቶችና ህጎች፣ ስለተለያዩ ሃይማኖታዊ ክበራዎች፣ ስለቅዱሳን (Woyyuu) እና የመሳሰሉትን ሌት ተቀን ያለ አንዳች እረፍት ጠበቅ ያለ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ ስልጠናው በፍጹም ጸጥታና መልካም ስነ-ምግባር

የሚከታተሉበት ነው። እነዚያ ለአንድ ወር ስልጠናዉን የተከታተሉት ስልጠናው እንዳበቃ በቡድን በቡድን በማደራጀት ወደ ማህበረሰቡ ውስጥ በመግባት የሰለጠኑትን ወደ ተግባር ይለውጡታል። በእንቅስቃሴያቸው ወቅት ከስልጠናውና የቀድሞ ልምዶቻቸው ያካበቱትን ህጎች፣ ባህል፣ ስነ-ምግባርና የመሳሰሉትን በመጠበቅ ይጨፍራሉ፣ እየተደገሰ ይበላሉ፣ የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች ይወጣሉ። በዚህን ጊዜ አሰልጣኞቻቸውም ከጎናቸው በመሆን ድጋፍ ይሰጧቸዋል።

የዚህ እርከን መጨረሻና ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለመሸጋገር ከሚከወን ስርዓት ውስጥ አንዱ የባንቲ መላጨት (bantii haadataa/ yoosittii/ gonaadittii) ነው። ይህን በማከናወን ወደ ቀጣዩ ራባ እርከን ይሸጋገራሉ። (ሞና ጎዳና 9/6/2008 ዓ.ም.፣ የዋደራ ወረዳ ነዋሪ)
ይህ የባንቲ መላጨት የሚያመለክተው ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላኛው ደረጃ የሚያደርጉትን የሽግግር ከበራ ነው።

### ለ. ዶሪ

ዶሪ በገዳ ስርዓት እርከን ውስጥ አምስተኛው ደረጃ ላይ የሚገኙ አባላት ናቸው። የቆይታ ጊዜያቸውም አራት ዓመታት ብቻ ነው። ስለዚህ ያለ እረፍት የተለያዩ ከበራዎችን በማከናወን ይጠመዳሉ። ከነዚህም ውስጥ ቃጅማና ወዴሳ ቆረጣ፣ የደበሌዎችን የእርከን ሽግግር ከበራ መፈፀም፣ ሁሉቃና ድባዩ (dhibaayuu) ተጠቃሾች ናቸው። ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ የመሸጋገር ከበራዎቹም ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች ናቸው። እነሱም፡-

i. ቃጅማ ቆረጣ

በዚህ እርከን ውስጥ ያሉ ሴቶች የራሳቸውን የመጀመሪያቸውን ሲቄ (siiqqee) ቆርጠው የሚገቡበት ስርዓት ነው። የቃጅማ ቆረጣ የተባለበት ምክንያት ሲቄ የሚቆረጠው ቃጅማ ከሚባል የቆላ እንጨት ላይ ስለሆነ ነው።

ii. ወዴሳ ቆረጣ

ወዴሳ (weddeessa) የዋንዛ እንጨት ነው። መረጃ አቀባዮቹ እንደገለጹልኝ፡-ከእንጨቶች ውስጥ ለዚህ ከበራ ተብሎ የሚመረጠው ዋንዛ ነው። ምክንያቱንም ሲገልጹ ዋንዛ ለሰው ልጅ ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ አለው። ፍሬው ይበላል፣ እንጨቱ የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን ለመስሪያነት

ተፈላጊና ተመራጭ በመሆኑ ነው። (በሪሶ ጃልዴሳ፣የዱግዳ ዳዋ ወረዳ ነዋሪ፣ በ8/6/2008 ዓ.ም. እና አባ ገዳ ሀልቻዬ ዳራ፣ አባያ ወረዳ፣ ደበቃ ደቦቤሳ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣በ 26/7/2008 ዓ.ም.)

ስለዚህ ወደ ዶሪ እርከን የተሸጋገሩ አባላት ከራባ ወደ ዶሪ እርከን መሸጋገራቸውን አመላካች ከዋንዛ እንጨት ላይ ሙካ ወዴሳ የሚባለውን መካከለኛ ቁመት ያለውና ወፈር የሚል ዱላ መሰል ተጠርቦ ይዘጋጃል።

እንጨቱን ከመቁረጣቸው በፊት በስሩ እርጎና ከገብስ የተዘጋጀ ገንፎ በመጨመር (dhibaasanii) እግዚኣብሔርን ይለማመናሉ።የወዴሳውን እንጨት የሚቆርጡት ዝግ ባለድምፅ (shookkisanii) "Weddeessi woddeessa nageyaati!" ወዴሳ የሰላም ወዴሳ ነው! እያሉ በማዜም ነው።[5]




ፎቶ፡-4 ከታች ወደ ላይ ሲቄ፣ ሆሮሮ፣ የዋንዛ እንጨት፣ ከላይ ያሉት ሦስቱም የቦኩ ዓይነቶች ናቸው።




ፎቶ፡-5 መረጃ ሰጪዎች በሚኤ ቦኮ

ባቱዎች ደግሞ ያን የቀረውን እርጎና ገንፎ በመያዝ ዶሪዎቹን "Dooriin doorii nageyaati! Dooromtee gadoomii addee an geye tana geyi!" "ዶሪው የሰላም ዶሪ ነው። ዶሪ ሆናችሁ፤ ገዳ ሁኑ፤ እኔ የደረስኩበት ድረሱ" እያሉ በመመረቅ ያቀምሷቸዋል። ከዚያ የዶሪ አባላት ወዴሳውን ቢቆርጡም እንደገና "Addee ati geetteen na geyi!" "አንተ ከደረስክበት እኔንም ያድርሰኝ" በማለት እየተለማመኑ ወዴሳውን ይጠርባል። ከዚያ ያን የወዴሳ እንጨት አምጥቶ ለባለቤቱ ይሰጣታል። እሷም ከቤታቸው ጓሮ አስቀምጣ እንድትንከባከበው ወይፈን

[5] ሙካ ወዴሳ ጨምሮ ሌሎችን ቁሳዊ ባህል በተመለከተ ከሚከተለው ገጽ ላይ ምስሉን መመልከት ይቻላል።

ይሸልማታል። የወይፈኑም ስም ከዚያን ዕለት ጀምሮ ዎዴሌ (woddeelle) ተብሎ ይሰየማል። እሷም የራሷን ሲቄ በጭስ እንዲያብረቀርቅ በማድረግ የባሏንም አደራ በአግባቡ ትጠብቃለች። ይህ ከአንድ ደረጃ ወደሌላ መሸጋገሪያ ከበራ ሲሆን እርጎው ስልጣናቸው ይርጋ (ይረጋገጥ) ወዴሳው ደግሞ ለሁሉም የሚጠቅሙ፣ የሚያገለግሉ መሆናቸው የሚያመላክት ተምሳሌት ነው። ገንፎውን የተመለከትን እንደሆነ ዝም ብሎ ገንፎ ሳይሆን የገብስ ገንፎ ነው። ገብስ ደግሞ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ልክ እንደ ቡና እግዚኣብሔር ከሚለማመኑበት የእህል ዓይነቶች ውስጥ ተቀዳሚ ያደርገዋል። ገብስ ለብዙ ዓይነት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ከመዋሉና ከጥንት ጀምሮ የሚታረስ የእህል ዓይነትነቱ ጋር ያያይዛሉ።

iii. **የደበሌዎችን እርከን ሽግግር ከበራ መፈፀም**

በዚህ በዶሪ እርከን ውስጥ ከሚከወኑ ከበራዎች ውስጥ ሦስተኛው ደግሞ ልጆቻቸውን ከጉዱሩ ደረጃ ወደ ዳባሌ የማሸጋገር ስርዓት ነው። የዶሪዎች አባላት ልጆቻቸውን እራሳቸው ወደሚቀጥለው ደረጃ እንደተሸጋገሩ ያረጋግጡላቸዋል። በዚህ ወቅት የልጆቹ እናቶች የሚሉት አባባል አለ። ይኸውም፦ “Dur dhoksee guddisaa, hardha qoffee mudhisa...” ማለትም፦ “ቀደም ሲል ደብቄ አሳድገው ነበር፣ አሁን ግን አንገቱ ቀና አድርጓል።...” እያሉ ይዘፍናሉ። ይህ የደረጃ ሽግግር በገዳ ስርዓት ውስጥ የመጀመሪያው በመሆኑ የሁሉም ወገን ደስታ የላቀ ነው። ይህ ሂደት አንድ የገዳ ደረጃ ወደ ሌላኛው እርከን የሚያደርገውን ሽግግር የሚያሳይ ከበራ ነው።

iv. **ሁሉቃና ድባዩ**

ሌላው ከበራ የዶሪና የገዳ አባለት የስልጣን ርክክብ ከማድረጋቸው በፊት ዶሪዎች መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ (kaayoofi faroo hamtuu) ተከትሏቸው የወደፊት ስራቸውን እንዳያደናቅፍ በማሰብ፣ ስልጣን ላይ የቆዩት ገዳዎች ደግሞ ምናልባትም በስልጣን ዘመናቸው ወቅት አብሯቸው የነበረ መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ አሁንም እንዳይከተላቸው በሚል የሚፈጽሙት የጦስ ማውጣት ሃይማኖታዊ ከበራ ነው።

በመጨረሻ የአሁኖቹ የዶሪ አባላት መጭውን የገዳ አስተዳደር የሚረከቡትና የሚያስተዳደሩት እነሱ ስለሆኑ ዘመኑ የጥጋብና የፍስሀ (kan quufaa gabbinnaa,kan misaafi mirgaa) እንዲሆንላቸው እርጎ በቅል እንዲሁም ቅቤ በጭጮ ሞልተው በመያዝ ድባዩ (ምስጋና) በሚካሄድበት እንጨት ስር እና በሚጎዳኙበት ወቅት ደግሞ መልካ (ወንዞች) ላይ ትኩስ ወተት

በመጨመር እግዚአብሔርን የሚለማመኑበት ሃይማኖታዊ ከበራ ነው፡፡ እነዚህ የሁሉቃና ድባዩ ከበራ ትንተና በተመለከተ በ6.3. ስር በስፋት ቀርቧል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ወደ ገዳ እርከን ይሻጋገራሉ፡፡ ይህን በተመለከት ደግሞ በ6.1. ስር በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ታዲያ በቃሉ የመማክርት አባልነት ውስጥ የአባገዳዎች ተግባር በስራቸው ያሉትን የየራሳቸውንየጎሳ አባላትን በባህላዊና ሃይማኖታዊ መንገድ ከማስተዳደርና በውስጣቸው የሚከሰቱ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳዮችን በራሳቸው የሃይማኖታዊ ከበራ መቼቶች ላይ ተመስርተው ለህዝባቸው እግዚአብሔርን ይለማመናሉ፡፡ ከአቅማቸው በላይ የሆኑ ክስተቶች ሲያጋጥማቸው ጉዳዩን ወደ ቃሉ ተቋም በማምጣት በጋራ የሚፈቱበት ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፡፡

## 5.1.3.3. የኮከብ ቆጣሪዎች ተግባራት

ኮከብ ቆጣሪዎች ከቃሉ መማክርት አባላት አንዱ ሲሆኑ፤ በምሽት በመውጣት ከሰማዩ ላይ ያሉትን ከዋክብት ከአቀማመጣቸው፣ ከወጡበት አቅጣጫና በወቅቱ ከሚኖራቸው ከለር በመመርኮዝ ምን ዓይነት ክስተቶች ሊፈጠር እንደሚችል የመግለጽ ተስጦ ያላቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከከዋክብቶቹ ውስጥ ስለማህበረሰቡ እምነትና ባህል መልካሙንና መጥፎውን የሚያመላክቱ አሉ ብለው ያምናሉ፡፡ እነሱም፡- ከዋክብት (ቡሳ ዋቃ፣ ሶስት ተከታትለው የሚወጡ ኮኮቦች)፣ ፀሐይና ጨረቃ የመሳሰሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ከዋክብት አይተው ስለወቅቱ ዝናብ፣ በሽታ፣ ጦርነትና የመሳሰሉ ክስተቶች ለጉጂ ኦሮሞ ያለውን ጥሩነትና ጥፋት ለይተው የመተንበይ ተሰጦ እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም፡- ሰባት ከዋክብቶች አንድ ላይ ተያይዘው የሚወጡ አሉ፡፡ እነዚህን ከዋክብት ቡሳ ዋቃ (buusaa waaqa) ይሏቸዋል፡፡ እነዚህ ሰባቱ ከዋክብት ወደ ሰማዩ መሀል ክፍል ከተጠጉ ክረምት መግባቱን ማብሰራቸው እንደሆነ ተረድተው ለህብረተሰቡ የእርሻ መሬታቸውን እንዲያዘጋጁ የሚያሳስቡበት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ክዋክብቶች ወደ ምዕራብ አቅጣጭ ካዘቀዘቁና ከቆዩ፤ አውሎንፋስ የቀላቀለ ዝናብ ይዘንባልና በእረኝነትም ወቅት ሆነ በሌሎች እንቅስቃሴዎች ላይ ተጠንቀቁ ብለው ይናገራሉ፡፡ (ባሊ. ጃርሶ፣ የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ፣ 12/6/2008 ዓ.ም. በሚኤ ቦኮ)

ሌላው ፀሐይዋን የተመለከትን እንደሆነ በተለመደው መንገድ በሰላም ወጥታ የምትጠልቅ አለች። በዚያ መልኩ ከተካሄደ ሰላም ነው፤ነገር ግን ደም ለብሳ ከጠለቀች ችግር አለ ብለው ያምናሉ፤ ለዚያም ችግር ማሳለፊያ መስዋዕት ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ፤ ልመና ይከናወናል። ጨረቃዋም ከወትሮዋ ከለሯ ለየት ካለ የምታመላክተው ነገር እንዳላት ያምናሉ። ይኸውም፡- ጨረቃዋ ሙሉ ለሙሉ ደም ለብሳ፤ ቀልታ የወጣች እንደሆነ ጦርነት ይከሰታል፣ አሊያም ወረርሽኝ በሽታ ሊከሰት ይችላል፣ ከዚያም ሞት ይበዛል ተብሎ ይታመናል።

ከእነዚህ በተጨማሪ ሶስት ተከታትለው የሚወጡ ከዋክብቶች አሉ። እነዚያ ከዋክብቶች አወጣጣቸው ከቀድሞ ስርዓታቸው በተለየ መልኩ ከሆነ የተለያየ መልዕክት እንዳላቸው ይተነብያሉ። ይኸውም፡- ኮኮቦቹ ወደ ቀኝ ቀና ካሉ ሰላም ነው ይላሉ። ኮኮቦቹ ወደ ግራ ቀና ካሉ ደግሞ ችግር እንዳለ ይገመታል።

ከዚያ ቀጣዩ ስራ የሚሆነው የሰላም ከሆነ ተመስጌን ተብሎ በተገኘው መልካም አጋጣሚ እንዲጠቀሙበት መልዕክት ይተላለፋል። ነገር ግን የትንበያው ውጤት ችግር እንዳለ የሚያመላክት ከሆነ በቅድሚያ ስለ ክስተቱ ማጣራት ይኬዳል (qortii dhaqan)። ይኸውም ወደ አባገዳ በመሄድ ችግሩን በማስረዳትና ይህን ዓይነት ችግር ከምን ሊመጣብን ቻለ? ከዚያ ለጉዳዩ ማስታገሻ ሊሆን የሚገባ መስዋዕት ያስፈልጋል ማለት ነው፤ ፀሎት ይከናወናል። ከብት ታርዶ ሞራና አንጀቱ እንዲታይ ይደረግና፤ እግዚአብሔር በዚህ ያሳልፍልን! በማለት ወደ መስዋዕት ማቅረብና እግዚአብሔርን መለማመኑ ሂደት ይገባል።

በድሮ ጊዜ ኦሮሞ ታሞ ወደ ሐኪም ቤት አይሄድም ነበር፤ ከበሽታው የሚፈወሰው ወይም ከእግዚኣብሔር ምህረትን የሚጠይቀው በፋጭ፣ በሁሉቃ እና መስዋዕት በማቅረብ ነበር (ኡዴሳ ዲራሞ፣ የአባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ12/12/2007 ዓ.ም.)።
የአጥቢያ ኮከብ (bakkalcha) አቅጣጫዋን ጠብቃ ከወጣችና ለሊቱ ሊነጋጋ ሲል፤ ጎህ ሲቀድ ቃሉ ከመኝታው ተነስቶ ለህዝቡ እግዚኣብሔርን እንዲህ እያለ ይለማመናል፡-

| | |
|---|---|
| Borulle nage'i | የወጣሽው ጎህ ሰላም ላንች ይሁን፣ |
| Guji nage'i, | ጉጂ ሰላም ለናንተ ይሁን፣ |
| Ardaa nage'i. | ምድሯም ሰላም ሁኚ። በማለት ይፀልያል። |

ጠቅለል ባለ መልኩ የኮከብ ቆጣሪዎችን ተግባር ስንመለከት የለሊቱን ከዋክብት ተከታትሎ በመመልከት ስለወቅቱም ሆነ ስለቀጣዩ ጊዜያት መልካምነትና አለመሆን፣ ስለጉጂ ኦሮሞ ዕጣ-

ፈንታና ስለተለያዩ የሚከሰቱ ክስተቶችና ውጤታቸውም ምን ሲሆን እንደሚችል የሚያመላክቱ ከመማክርት አባላቶች ውስጥ አንዱ ናቸው።

ስለ ኮኮብ ቆጣሪዎች Dirribii, (2009:141) እንደሚከተለው ሲያስረዳ፡- የኦሮሞ አያንቱዎች ዓርብ ለሊት በቡድን ሆነው ተራራ ላይ ወጥተው ኮከብ እየቆጠሩ ያድሩ ነበር። በወቅቱም የሚበሉት ቆሎና ቡና ቃላ ሲሆን የከዋክብቶቹን ልዩነት በአንድ ወይም በሁለት ወራት ውስጥ ምን እንደሚመስል ተረድተው ያስረዱ እንደነበር ይገልጻል። ከከዋክብት ዓይነቶች ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶባቸው የሚቆጠሩና የሚተነበይባቸው ሰባት ናቸው። እነሱም፡- ላሚ (Triangulum)፣ ቡሳን (Pleiades)፣ ባካልቻ (Aldebaran)፣ አልጋጂማ (Bellatrix)፣ አርባ ጋዱ (Centeral Orion)፣ ኡረጂ ዋላ (Saiph) እና ባሳ (Sirius) ይባላሉ።

> *Ayyaantuu Oromoo Jimaata halkan koreedhaan gaaratti bahuudhaan urjii laakka'aa bula ture. worri urjii lakkaa'u kuni waa hedduu lagata. Guyyaa sana akaayii fi buna qalaa malee midhaan (nyaata) biroo hin nyaatan. Halkaan guutuu manatti hin galani. Alatti ibidda bobeessanii taa'uudhaan akkaata taa'umsa urjii ilaalu, adda addummaa isaan ji'a tokko ykn lama kessatti mul'isan hubatanii wal hubachiisaa turan. Hubannoon isaanii kuni immoo dhahaa Oromoo qopheessuuf isaan qarqaare* (Dirribii, 2009:141).

| Borana Terms | Technical Terms |
|---|---|
| Lamii | Triangulum |
| Busan | Pleiades |
| Bakkalcha | Aldebaran |
| Algajima(Alqajima) | Bellatrix |
| Arba Gaadduu | Centeral Orion |
| Urjii Walla | Saiph |
| Basa | Sirius |




ምስል፡-6 የሰባቱ ከዋክብት ስሞችና ምስል (ምንጭ፡- Asmarom,1973:181)

## 5.1.3.4. የካሎዎች ተግባራት

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ካሎ ማለት ባለከለቻዎች የሚጠሩበት ስያሜ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ እነሱም በቃሉ የሚወከሉ ሲሆኑ ተግባራቸውም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለጻ ካሎዎች ወደ ሃይማኖታዊ ክበራዎች ላይ አምስት ሰዎች በግንባራቸው ላይ ካላቻ አስረው የሚላላኩት ናቸው፡፡ በቃሉ ተቋም ውስጥ የተለያዩ ስጦታዎችንም ሆነ ቅጣቶች ካሉ የሚቀበሉት እነሱ ናቸው፡፡ ዳንቢ፣ ሚኤሳ እና ዲኪቻ ቆርጠው (ሁለቱ የዛፍ ዓይቶች ሲሆኑ፤ ዲኪቻ ደግሞ ሀረግ ነው) የሀገሬውን ባህል ያሟላሉ፡፡ ቃሉ ያለ እነሱ መስዋዕት ማቅረብ አይችልም፤ ሃይማኖታዊ ክበራዎች (tolcha) ማከናወን፣ ከዋንዛ የሚዘጋጅ እንጨት መያዝም አይችልም፡፡

ካሎዎች ማለት በሌላ አገላለጽ እንደ ቃሉ ባለቤት (ibidda isaa) ይመሰላሉ፡፡ እንደቃሉ አስቴ (ichima) ይቆጠራሉ፡፡ ለመስዋዕት የቀረበውን ከብት ጭንቅላት በገልማ ከሆነ ባለቤቱ፤ በተለያዩ መንፈሳዊ ተራራ ላይ ከሆነ ደግሞ እነሱ ካልያዙት በቀር እርዱ አይከናወንም፡፡ ለመስዋዕት በስጦታ ያበረከተው አካል ከብቱን ለማስረከብ እነሱን ይፈልጋል፤ ከዚያም የተረከቡትን ከብት ወደተራራው ይዘው የሚወጡትም እነሱ ናቸው፡፡

የመስዋዕት ከብት ተይዞ ከተራራው ሲከሄድ አባቃሉን፡- አባገዳዋች፣ ሽማግሌዎችና የአካባቢው ነዋሪዎችና አጎራባቾች ከወጣት እስከ አዛውንት አጅቦት እየተጨፈረ (qeexalee) ይሄዳሉ። ከመስዋቱ ቦታ እንደደረሱ ወጣቶቹ አስቴውን እንዲሰብቁት (ichima akka buusu) ይደረጋል። ከዚያም ያንን አስቴ እየተቀባበሉ ሲሰብቁ ይጨስና ከኋላ እሳት ይወጣዋል። በዚያ ጊዜ ከተራራው ጥግ ጥግ ሳር በመንጨት እሳቱ ላይ ይጣላል፤ ወይራ (ejersa) ተተክሎ ተራራውን ሦስት ጊዜ እየተጨፈረ ይዞራል። በመጨረሻም ማልጊቻ (malgichcha) የሚባለውን መንፈሳዊ ጭፈራ ተጨፍሮ መስዋዕት የቀረበበት ጉዳይ መሳካት፤ አለመሳካቱን እዚያው ሊታወቅ ይችላል፤ አሊያም በሂደት ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

Malgichcha! Malgichcha koyyaa,
hujiin waaqaa meerree?
Hoo hoo!

ትርጉሙም፡- የጥንቱ/ቀደምቱ ጉጂ፣ የእግዚአብሔር ስራ/ተዓምር የታል? ሆ ሆ! እንደማለት ነው። በዚህ ከበራ ላይ የሚከወኑት እያንዳንዱ ድርጊት ምክንያታዊ ነው። ይኸውም፡- አስቴውን እንዲሰብቁት (ichima akka buusu) የሚደረገው ለከበራዎቹ የሚያገለግል እሳት ከግለሰብ ቤት ስለማይወሰድ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ቃሉ ባለቤትም ሆነች ማንኛውም ሴት ወደ ተራራው መስዋዕት ማቅረቢያ ስፍራ ስለማይወጡ ይህን ተግባር ባብዛኛው የሚሸፍኑት ካሎዎች ይሆናሉ። ለዚህም ነው ማህበረሰቡ ካሎዎችን በቃሉ ባለቤት ምትክ ስለሚከውኑ ልክ እንደሚስቱ የሚቆጥሩት። በመጨረሻም «ማልጊቻ ኮያ» የሚለውን መንፈሳዊ ጭፈራ ቃሉ የሚያወጣው በዜማ እግዚአብሔርን የመጡበትን ጉዳይ ልክ ለድሮዎቹ ጉጂ ያደርግላቸው እንደነበረው፤ ለእኛም አድርግልን፤ ተዓምራትህን አሳየን በማለት የሚጠይቁበት ስልት ነው። እንደ ጉጂ አዛውንቶች ገለጻ በዕለቱ ከእግዚሃብሔር የሆነ ምልክት እንደሚያዩ ይናገራሉ። ይህም ሊሆን የሚችለው አንድም በተግባር ወዲያው ለምሳሌ የዝናብ እጦት ከሆነ በዝናብ፤ አሊያም ለመስዋዕት በቀረበው ከብት ሞራ ሊገለጽ እንደሚችል ይገልጻሉ። በተለይም ይህንን ጉዳይ የሚያረጋግጡት ከመማክርት አባላቱ ውስጥ ሞራ አንባቢዎቹ ስለሚሆኑ ከዚህ ቀጥሎ የእነሱን ተግባራት የምናይ ይሆናል።

## 5.1.3.5. የሞራ አንባቢዎች ተግባራት

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ሞራ አንባቢዎች በተለያዩ አውዶች ላይ ለመስዋዕት የቀረበውን ፍየል ወይም በግ ከሆኑ ሞራቸው በስርዓት ይወጣና በገበቴ ላይ ተደርጎ ይቀርብላቸዋል፡፡ ለመስዋዕት የቀረበው ከብት ከሆነ ደግሞ አንጀቱን እዚያው የታረደበት ቦታ በመሄድ ያዩታል፡፡ የዘርፉ አዋቂዎች ያን አንጄቱን ከነሞራው በመመልከት ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ፀጋ በውስጡ ያሉትን የተለያዩ መስመሮች፣ በመስመሮቹ ከሚታዩ የተለያዩ ክስተቶች ተነስተው ከታያቸው (ካነበቡት) መረጃ ተመርኩዘው የቀረበው መስዋዕት ተሳክቷል፤ አሊያም ችግር አለው በማለት የመግለጽ ተሰጦ እንዳላቸው ይታመናሉ፡፡

ስለሞራ ማንበብ አጀማመር በተመለከተ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሰው ልጅ እንዲተዳደርበት ህግጋትንና ደንቦችን የሰጠው በመጽሐፍ መልክ ነበር፡፡ ከዚያም ከዕለታት አንድ ቀን ያ ለሰው ልጅ የተሰጠው የህግ መጽሀፍ አንዲት ላም ትበላዋለች፡፡ ሰዎቹም ተናደው ላሚቷን ያርዷታል፡፡ በመቀጠል ሆዷን ሰንጥቀው መጽሀፉን ቢፈልጉ ሊያገኙት አልቻሉም፡፡ ነገር ግን በላሚቷ ሞራና አንጀት ላይ የተለየ ክስተት ተመለከቱ፡፡ እሱንም እያገጣጠሙ ትርጉም ይሰጡት ጀመር፡፡ ከዚያም በሌላ ጊዜ እንዲሁ ከብት አርደው አንጀቱን ሲያዩ በሚያገኟቸው ምልክቶች ተንተርሰው ስለሰላም፣ ስለጦርነት፣ ስለበሽታ፣ ስለዘንድሮ፣ ስለመጭው መተንበይ ጀመሩ፡፡ ለዚህ ነው አሁንም እግዚአብሔር ይህንን ተሰጦ ያደላቸው አዋቂዎች በማንበብ እግዚአብሔር ያመላከታቸውን የሚገልጹበት በማለት ያስረዳሉ፡፡

ስለዚህ በቃሉ የቀረበው የመስዋዕት ከብት አንጀት ሲታይ ችግር እንዳለ ካመላከተ ሌላ ተመሳሳይ ከብት እንደገና ከዚያው ተራራ ሳይወርዱ፤ ካለበት ባሳቸኳይ ወጣቱ ተሯርጦ እንዲመጣ ይደረጋል፡፡ በመቀጠል ቃሉ እግዚአብሔርን ተለማምኖ ወዲያው ሳይውል ሳያድር ከብቱ ይታረዳል፡፡ ሞራና አንጀቱን ሞራ አንባቢዎቹ ይመለከታሉ፤ ሰላም ከሆን እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ፤ ደስታቸውንም በጭፈራ ይገልጻሉ፡፡ ያ የታረደው ከብት ስጋ አንድም ሳይቀር እዚያው ይበላል፡፡ አጥንቱንና የማይበሉ የከብቱ አካላት ደግሞ ተሰባስበው ይቃጠላሉ፡፡




ምስል፡-6 ሞራ ሲያነቡ



ምስል፡-7 ከብት ታርዶ እዚያው ሞራውን ሲያነቡ (ምንጭ፡- Haberland, 1963)

እንደ መረጃ አቀባዮቹ በዚያን ወቅት ችግሩ ሀይለኛ ዝናብ እየዘነበ አስቸግሮ ከሆነ ወዲያውኑ ወቅቱንና መጠኑን የጠበቀ ዝናብ መዝነብ ይጀምራል፡፡ ወቅቱን ጠብቆ መዝነብ ሲገባው ካልዘነበ ደግሞ በዚያን ዕለት ዝናቡ ከየት መጣ ሳይባል ያወርደዋል፡፡ የጠላት ጦር እየመጣ ከሆነ እዚያው ይቆማል፤ አሊያም የእነሱ ጦር ተንቀሳቅሶ ድል በድል ሆኖ ይመለሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

በሌላ በኩል አንድ አባወራ ከታመመ ቤተሰቡ ተሰባስቦ ከብት ይታረዳል፡፡ እንደ ጉጂ አባውንቶች ገለጻ የከብቱ ሞራ ስለሰውዬው ጤንነት ይገልጻል፡፡ ለምሳሌ ወንድማችሁን ሞራው ገሎታል፤ ስለዚህ ሌላ ከብት እረዱ ይባላል፡፡ እንቢ ካሉ ሰውየው ይሞታል፤ሚስቱን ሌላ እንደሚወርሳት፡፡ በሌላ በኩል አባወራውም ሆነ እማወራዋ ሂያጅ (የሚማግጡ) ከሆነ ያ ሞራ ይናገራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ችግሩ ከእሷ በኩል ከሆነ ችግር ተፈጥሯል፤ ባለቤትህን አረጋጋት፤ ደም ርጭባት ተብሎ ይነገረዋል፡፡ ችግሩ ከእሱ በኩል ካለ ደግሞ በዚሁ መልክ ይነገረዋል፡፡

> ሞራና አንጀቱን በማየት ስለፋልፋላ (falfalaa)፣ ስለሀብት፣ ስለቤተሰብ ችግር፡- ሆድ ለሆድ ተግባብተው መኖራቸውን፣ ሆድና ጀርባ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ ለአብነት ያህል ሞራው ከወደ አናቱ ጫፍ አበጥ ብሎ ነጣ ካለ፤ በዚያ ሰው ላይ ሟርት (ፋልፋላ) እንደተደረገበት ያመለክታል፡፡ በዚህ ጊዜ ያን ድርጊት ማርከሻ ሌላ ከብት እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰውዬው ልጆች ካሉት

ሁሉም ልጆች ማር እንዲገዙ ይደረጋል፡፡ ጠጅ ይዘጋጃል፡፡ ከዚያም የተነገረው መልክ ከብት ታርዶ፣ ጠጁ ተዘጋጅቶ፣ ዩባዎች ይጠሩና እግዚአብርን በመለማመን ስውዬውን ይመርቁታል፡፡ ከዚያም እንዲህ ያለ መልክ ከብት እረድ፣ በዚህ አቅጣጫ ተጎዳኝ፣ ከዚያ ቦታ ስፈር፣ በዚህ ላይ ውለድና ክበድ በማለት ይመርቃሉ፤ የወደፊት ኑሮውን ያመላክቱታል፡፡ ይህ ድርጊት የሚከውኑት በአብዛኛው ዩባዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ዩባዎች በተግባርና በማየት (dhaggaafi dhageettiin) ለምድና ዕውቀት ያካበቱ ስለሆኑ ለማህበረሰቡ ስለ ዕጣ-ፈንታና ዕድል (faroofi kaayoo) የመተንበይ፣ ሞራና አንጀት የማንበብ፣ በቡና ቃላ እና በቦካ (ጠጅ) መተንበይ ስለሚችሉ ነው፡፡ (ባለ. ጃርሶ፣ ዕድሜ 74፣ ቡሌ ሆራ ነዋሪ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም.)

## 5.1.3.6. የሀገር ሽማግሌዎች ተግባራት

ለቃሉ በመማክርት አባልነት የሚሰየሙት የሀገር ሽማግሌዎች እነማን እንደሆኑ ቀደም ብሎ ተጠቅሷል፡፡ የነዚህ የሀገር ሽማግሌዎች በመማክርት አባላቱ ውስጥ ያላቸው ተግባር ባብዛኛው በተቋም ውስጥ በመገኘትና አንዳንዴም በቃሉ ትዕዛዝ መሰረት በመላክ ጭምር በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ አነስተኛ ማህበራዊ ችግሮችን በቃሉ ስም ይፈታሉ፡፡ ጉዳዩ ከመግባባት አልደርስ ብሎ ካስቸገራቸው የደረሱበትን ውሳኔና እንቢተኛው ማን እንደሆነ ለቃሉ ተቋም ሪፖርት በማቅረብ ያስተላልፋሉ፡፡

አንዳንድ በሳል የሀገር ሽማግሌዎች ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ ለሚቀርቡ ችግሮች ጠጠር ያሉ ሀሳቦችን በማቅረብ ነገሮችን ሳይንዛዙ እንዲፈቱ የሚያደርጉ አሉ፡፡ ሌላው አባቃሉንም ከገዳዎች ጋር በመሆን በማማከር የሚያገለግሉም እንዳሉ በመስክ ቆይታዬ ወቅት ለማየት ችያለሁ፡፡ ከመማክርት አባላቱ ውጭ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትም ይህንኑ ፈለግ ተከትለው አብዛኛውን ማህበራዊ ጉዳዮች በመፍታትና መጭው ትውልድ የማንነቱ መገለጫ የሆነውን ትውፊትና ስነ-ምግባር እሴቶች ይዞ እንዲያድግ የበኩላቸውን እየተወጡ ያሉት እነሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሀገር ሽማግሌዎች ተግባር ቀላል ግጭቶችን ከመፍታት አንስቶ በቃሉ መማክርት ውስጥ አባል በመሆን ትላልቅ ችግሮችን አብረው ይፈታሉ፡፡ በዋናነት ደግሞ ትውልድን ከስር ይቀርጻሉ፤ መልካም ስብዕና እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡

## 5.1.3.7. የሀዳ አንባ ተግባራት

የቃሉን ባለቤት በአላብዱ ጉጂ ዘንድ ሀዳ አንባ ትባላለች። ትርጉሙም የህዝብ እናት እንደማለት ነው። ነገር ግን ጉጂዎች የቃሉን ባለቤት «ቃሊት» ብለው አይጠሩም። እንደእነሱ ገለጻ «ቃሊት» የጥንቁልና ተግባር የምትፈጽም እንስት ናት። ሀዳ አንባ ግን የቃሉን ተግባራት ልትከውን ይቅርና ቃሉ መስዋዕት ለማቅረብ ወደ ተራራዎቹ ሲወጣ እንኳን እንደማንኛውም ሴቶች በቦታው አትገኝም።

"እንደሚታወቀው በእኛ ባህል ሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ እናቶችም ይመርቃሉ።" (ረጋቱ በሪሶ (የቃሉ እናት)፣ በወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ *በ18/11/2007 ዓ.ም.)* ለምሳሌ የተመለከትን እንደሆነ የቀድሞው አባቃሉ ባለቤት የሆኑት (የአንባ እናት) ይገለገሉበት የነበረውን የሃይማኖታዊ ቁሶች ለተተኪዋ የቃሉ ባለቤት መርቃ ታስረክባለች። ይኸውም ደረቅ ድፍን ቡናና ገብስ የእሳት ፍም ውስጥ በመጣል "ዳንቢ" (danbii) ከሚባል ከቆላ እንጨት በተሰራ መቁያ (qajimaa) በመነካካት ጭሱን በአደራሹ በማሽተት፣ የቡናውንና ገብሱን ጭስ ጎሳዎቹን ያጥኑታል። ይህ የምርቃት ሂደት ያፋቅራል፤ አንድ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ በመቁያው ቆስቆስ በማድረግ አካባቢውን ታውደዋለች። በመጨረሻ በዚያ በጋለ ፍም ላይ የቆየውን መቁያ በተዘጋጀው ቅቤ እየቀባች ሰላምና ምህረትን ከፈጣሪ እንዲያድለን በማለት እንደሚከተለው ትመርቃለች፤ ትለማመናለች።

| <u>ሀዳ አንባ</u> | <u>ታዳሚዎቹ</u> |
|---|---|
| አቤቱ ፈጣሪ ሰላሙን አምጣልን። | አምጣልን። |
| ለሰው ሰላሙን አምጣ። | አምጣ። |
| ለከብቶቻችን ሰላሙን አምጣ። | አምጣ። |
| መጥፎ በሽታን አርቅልን። | አርቅልን። |
| አማን አድርግልን። | አሜን አድርግልን። |
| መንደሩንም ዓለሙንም ሰላም አድርግልን። | አሜን አድርግልን። |

እየተባለ እሷ የጋለውን መቁያ በቅቤ እያቀዘቀዘች በሽታውን፣ ጦርነቱን፣ ረሀቡን እንዲቀዘቅዝ እግዚአብሔርን ስትለማመን፤ ታደሚዎቹ ደግሞ ከስር ከስር የመጨረሻዋን ቃል በመድገም ይሁንታቸውን ይገልጻሉ።

ታዲያ ታዳሚዎቹ የምርቃቱ ስርዓት ሲካሄድ ሁለቱን እጃቸውን ዘርግተው ምርቃቱ የምህረተና የሰላም ሲሆን ይሁን፤ አሜን ይላሉ። ክፉውን አርቅልን ሲባል፤ ትንሿን ጣታቸውን ቀስረው ወደ ግራ አቅጣጫ በማወራጨት በህብረት እየቀሰሩ፤ አርቅልን ይላሉ።" በማለት ቃላቱን ከድርጊቱ ጋር በማዛመድ ገልጸውልኛል።

የቀድሞዋ የሀዳ አንባ ስልጣን ማሽጋገር፣ መመረቅ፣ ከአዲሷ ሀዳ አንባ አጠገቧ ሆና ልምድ ማካፈልና ማማከር፣ እቤት ያሉትን ስራዎች በማስተባበር ተተኪዎችን ማሰልጠን የእሷ ተግባራት ናቸው።

ከእነዚህ በተጨማሪ በቃሉ ስር ሆነው የተለያዩ መንፈሳዊ ተግባራትን የሚከውኑ ወዩ (woyyuu)፣ ሀዩ (hayyuu)ና ጪዴሳ (cidheessa) የሚባሉ አሉ። ወዩ (woyyuu) ቅዱስ ማለት ነው። ቅዱስነት በሁለት መልክ ይገኛል። አንደኛው ከእግዚኣብሔር በሚሰጠው ፀጋ ሲሆን፣ ይኸውም እንደቃሉ ዓይነቱ ቅድስናው ከእግዚኣብሔር የተሰጣቸው አሉ። ሌላኛው ደግሞ የቅዱሳን ማደሪያ በመሆን፣ ቅዱስ ከበራዎች የሚፈጸምበት በመሆኑ ቅዱስ ስፍራ ተብለው ይሰየማል። እንዲህ ዓይነቱ ቦታዎች በቃሉዎችና በገዳዎች ተቋማት አማካይነት በአዋጅ መልክ በመንገር ይቀደሳሉ። ለምሳሌ ሚኤ ቦኮ በአዋጅ በመነገር የተቀደሰ ስፍራ ነው። በገዳ አዋጅ ነገራ ወቅት «Me'ee bokkuu woyyuu, muka irraa hinmuramu beekkadhu!...» ማለትም ሚኤ ቦኩ ቅዱስ ስፍራ ነው፣ እንጨት ከውስጡ አይቆረጥም ተጠንቀቅ። እያሉ ቅዱስነቱንም ያረጋግጣሉ። ሀዩ (hayyuu) ደግሞ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዕውቀት ያለው ሰው ነው። ይህ ሰው በዕድሜና ልምድ ስለማህበረሰቡ፣ ስለአካባቢው፣ ስለማህበረሰባዊ ኑሮው፣ ስለነበረውና ስለሚመጣው መናገር የሚችል ሰው ነው።ሌላው ጪዴሳ (cidheessa) የሚባለው ደግሞ ባህላዊ መድኃኒት አዋቂ ነው። በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ሻቦላ (shaaboola) የሚባሉ ቤተሰብ እና ዳላጫ (dallaacaa) የሚባሉ ጎሳዎች አሉ። የእነዚህ ቤተሰብ አባላት ከፈጣሪ ልዩ ችሎታ የተሰጣቸው ቅዱሳን (woyyuu) ናቸው። እርግማናቸውም ሆነ ምርቃታቸው ይደርሳል ተብሎ ይፈራሉ። ሻቦላዎች መብረቅን የመቆጣጠር ተሰጦ አላቸው ብለው ስለሚያምኑ የእነሱ የሆነውን ነገር አይነኩም። ደላጫዎች ደግሞ የሆድ ውስጥ ህመም ይፈጥራሉ ተብለው ይፈራሉ። በእነዚህ ሰዎች አማካይነት የግለሰቦች ምርት ጥበቃ ይደረግላቸዋል። ይኸውም፡- ጣሬ የሚባል በአዝመራው መካከል በእንጨት ይተክላሉ። ያን አዝመራ የእነሱ የሆነ ሰው መጥቶ ታሬውን ነቅሎ ካልመረቀው በስተቀር ያን አዝመራ ማንኛውም ግለሰብ ቢነካው፡- ሻቦላዎች በዚያ በነካው ቤተሰብ ላይ መብረቅ በማስጣል አደጋ

ያደርሳሉ ተብሎ ይታመናል። ዳላጫዎች ደግሞ ከዚያ አዝመራ ላይ የወሰደውን ሰው ሆድ በመንፋት እስከሞት ያደርሳሉ ተብሎ ይታመናል። ነገር ግን እንደ መረጃ አቀባዮቹ ገለጻ ይህን ዓይነት ስህተት ፈጽሞ ችግር የደረሰበት ግለሰብ ወይም ቤተሰቡ ችግሩን ለማስቆምና ከአደጋውም ለማምለጥ ሲሉ ወደነዚህ ወዩዎች በመሄድ ያጠፉትን ነግረው፣ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ላጠፉት ጥፋት የሚቀጡትን ተቀጥተው ይመረቁና ይድናሉ ተብሎ ይታመናል። በሚኤ ቦኮ አዋጅ ነገራ ላይ እነዚህን ወዩዎች ማክበርና የእነሱ የሆነውን መነካት እንደሌለበት ተገልጿል። (ገዳ ጋምቤላ ባርሶ፣ በ9/6/2008 ዓ.ም.፣ በሚኤ ቦኮ ቅዱስ ስፍራ በመገኘት)

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን የቃሉ መማክርት አባላትና ሌሎች በስሩ መንፈሳዊ ክዋኔ የሚከውኑ እያንዳንዳቸው በተናጥል ያላቸውን ተግባራት ለማየት ተችሏል። እንዲሁም የነዚህ መማክርት አባላት በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ የእያንዳንዱ የጋራ ውጤት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

## 5.2. የቃሉ ከበራ መቼቶቹ

በቃሉ ተቋም ስር የተለያዩ የከበራ መቼቶች አሉ። መቼት ማለት አንድ ፎክሎራዊ ቅንጣት የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ነው (ፈቃደ፣ 2002)። የቃሉ ከበራዎች ገልማውን ጨምሮ የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቦታዎች ላይ ይከወናሉ። ከጊዜም አኳያ ቀናት፣ ወራትንና ዓመታትን ከክስተቶች ጋር በማያያዝ ባካበቱት ማህበረሰባዊ ዕውቀት በመጠቀም ምን ዓይነት ከበራን መቼ ይከወን ለሚለው ምላሽ የሰጡበት ሁኔታዎች ይታያሉ።
ስለዚህ እነዚህን መቼቶች ማህበረሰቡ ምን ይላቸዋል? ለምን ዓይነት ግልጋሎቶችስ ይውላሉ? በመቼቶቹ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነታቸው ምን ይመስላል? የሚሉትንና ሌሎችንም ጥቄዎች በሚመልስ መልክ ከመረጃ አቀባዮቹ ባገኘሁት መረጃ መሰረት እንደሚከተለው ተቀናብረው ቀርበዋል።

### i. ተፈጥሯዊ መቼት

ተፈጥሯዊ መቼት የሚባለው ማህበረሰቡ ለሃይማኖታዊ ከበራው ይበጃል፣ ይሆናል ብለው ያመኑበትና የሰየሟቸው ስፍራዎች ናቸው። እነዚህም ስፍራዎች በቃሉ ጠቋሚነት ህዝቡ ምስጋና እንደሚያቀርቡበት ይነገራል (አለማየሁና ሌሎች፣ 2000፡80)።

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ከተፈጥሯዊ መቼቶች ውስጥ ሀሮ ወላቡ ተጠቃሽ ነው፡፡ «...የጉጂ ጎሳ ቃሉ በሀሮ ወላቡ የሚገኘውን የኦብቱ ወገን «ቃሉ»ን እና ቀየውን በተለየ መልኩ የሃይማኖት ማዕከሉ እንዳደረገ ይነገራል» (ibid: 107-108)፡፡

በኦሮሞዎች ዘንድ መንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ ጉዳዮቻቸውን የሚፈቱት በየደረጃው ባሉት ባህላዊና ሃይማኖታዊ መዋቅሮቻቸው አማካኝነት ነው፡፡ እነዚህ መዋቅሮች እንደየአካባቢ የተለያየ ስያሜ ይኑራቸው እንጂ አገልግሎታቸው ተመሳሳይ ነው፤ ይኸውም የባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ማዕከሎች ሆነው ማገልገላቸው ነው፡፡ የማዕከሉ መጠሪያ በጉጂና በቦረና ኦሮሞ ዘንድ ጉሚ (Gumii) ሲባል፣ በሌላው የኦሮሚያ አካባቢ ደግሞ ጫፌ (Caffee) በመባል ይታወቃሉ፡፡

ጉሚ ማለት በአባገዳዎችና በኦሮሞ የባህል አዋቂዎች (hayyoota Oromoo) የሚካሄድ ከፍተኛ ጉባኤ (yaa'ii) ነው፡፡ በጉጂ ኦሮሞ አካባቢ ጉሚ ሚኤ ቦኮ፣ ጉሚ ዳራርቱና ጉሚ ዳሪቱ (Gumii Dharritoo) የሚባሉ ታዋቂዎቹ ናቸው (Alamaayyoofi kan biroo, 1999፡147)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደ ኦዳ ዶላ (Odaa Doolaa)፣ ፉቶ (Fuutoo) የቀድሞው የገዳ አባቶቹ የስልጣን ርክክብ የሚፈጽሙበት ቦታዎችም ይገኛሉ (Van de Loo, 1991፡42)፡፡

በአሁኑ ወቅት የጉጂ ኦሮሞ ገዳዎች በየስንምት ዓመታት ልዩነት የስልጣን ሽግግር ከበራዎችን የሚፈጽሙት በሚኤ ቦኮ (Me'ee Bokkoo) ተፈጥሯዊ መቼት ነው፡፡ በዚህ መንፈሳዊ ቦታ በአንድ ወቅት ሁለት ዓይነት የሽግግር ከበራዎችን ይፈጸማሉ፡፡ እነሱም፡- አንደኛው በከራባ ወደ ዶሪ፤ በዶሪ ደረጃ ያሉ አባላት ወደ ገዳ ደረጃ የሚሸጋገሩበት እና እንዲሁም በገዳ ደረጃ የነበሩት ደግሞ ወደ ቀጣዩ ዩባ ደረጃ የሚሸጋገሩበት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለስምንት ዓመታት ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መሪነቱን የሚያስፈጽም አባ ገዳ የሚመረጥበት፣ የሚጸድቅበት፣ ያለፈውን ህግና የአባገዳን የስራ አፈጻጸም የሚገመገምበት፣ ህግ የሚያወጡበትና የሚያውጁበት ቦታ እንደሆነ የሀገር ሽማግሌዎች ያስረዳሉ፤ በአጥኚው ምልከታ ወቅትም የታዩ ክዋኔዎች ናቸው፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም ሃይማኖታዊ መቼቶች ያየን እንደሆነ ቅድስናውን የሚያገኙት በሁለት መልክ ነው፡፡ ይኸውም፡- አንደኛው በተፈጥሮ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ተዓምራትን የሰራባቸው ቦታዎች ናቸው ተብለው የሚታመኑ ሲሆኑ፤ ለምሳሌ ቃሉ መጀመሪያ ወረደ የሚባለው ቦታ በአዶላ ወረዳ፣ ኦባ (ኦቢቲ) ቅዱስ ስፍራ ነው፡፡ ሁለተኛው መቼት ደግሞ በአዋጅ ቅድስናውን ይላበሳል (lallabaan ni woyyoomsu)፡፡ ለምሳሌ እንደ ሚኤ ቦኮ ያሉ

ቅዱስ ስፍራዎች ስያሜውን በአዋጅ ያገኛሉ። (ዋቆ ዱቤ፣ የኡራጋ አባገዳ የነበሩ፣ ጋንቤላ በሪሶ፣ የሆኩ አባገዳ የነበሩና ሞና ጎዳና በዩባ ደረጃ ያሉ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም. በሚኤ ቦኮ በመገኘት)

የቃሉ ከበራዎች ተፈጥሯዊ መቼቶችን ስናይ አብዛኛዎቹ ተራሮች ናቸው። በተራራ ላይ መስዋዕት ማቅረብ ጥንተ-መጥ እንደነበርና በስፍራውም የሚመለከውም ይሁን፤ የሚመሰገነው አንድ እግዚአብሔር እንደሆነ ታቦር፣ (2006፣211-212) እንደሚከተለው ያስረዳል።

> ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር አብርሃምን በመጥራት ‹የምትወደውን ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ከፍ ወዳለችው ተራራ (የሞሪያ ተራራ) ሂድ። እኔም ከምነግርህ ከተራሮች ወደ አንዲት ተራራ አውጣውና መስዋዕት አቅርብልኝ። ... በተጨማሪም ንጉሥ ሰለሞን በአባቱ በዳዊት ሥርዓት ስለሄደ እግዚአብሔር ይወደው ነበር። እርሱም መስዋዕት ለማቅረብ ገባኦን ወደ ተባለው ተራራ ሄደ። አንድ ሺህ የሚቃጠል መስዋዕት አቀረበ።... ተራራዎች፣ ወንዞችና ዛፎች ለዋቃ ቶኮቻ (ለአንድ ፈጣሪ) መስዋዕት ማቅረቢያ ቦታዎች ናቸው፤ እንጂ የሚመለኩ አይደሉም። በመሆኑም ኦሮሞ በተራራ፣ በወንዝና በዛፍ አያመልክም፤ አምልኮም አያውቅም።

ቃሉ ለእግዚአብሔር መስዋዕት የሚያቀርብበትና የምልጃ ጸሎት የሚያካሂድበት ተፈጥሯዊ ቦታዎችን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። ይኸውም፦ የቀድሞውና ያሁኑ ይባላሉ። የቀድሞው የሚባሉት የወንዶ ወንድር፣ ሲሶ ቁሉሉ፣ ዳማ ዳንቼ፣ ቱቱ ፋላ፣ ሜዴዶ ኮባዎች (ጋራዎች) ሲሆኑ፣ ያሁኖቹ ደግሞ የሾምቦ፣ የጎላ፣ የቂሊጦ፣ የሚኤሳ፣ የኤጀርሳ እና የግምባ ጋራዎች ናቸው። በእነዚህ ስፍራዎች የሚቀርቡት የመስዋዕት ከብት ዓይነት እንደየሚከወነው ሁነቶች የተለያዩ እንደሆኑ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ። ይኸውም፦

| <u>መስዋዕት የሚያቀርብበት ስፍራ</u> | <u>ለመስዋዕት የሚቀርቡት የከብት ዓይነት</u> |
|---|---|
| 1.የሾምቦ/ሙጥቻ ጋራ (ሀሴ ጎላ) | -ጥቁር ቦቃ ሰንጋ |
| 2. የጎላ ጋራ (ሀሴ ጎላ) | -ቀይ የፍየል ሙኩት |
| 3. የቅልጦ ጋራ (ቆቲ) | -ቀይ የፍየል ሙኩት |
| 4. የሚኤሳ ጋራ (ቆቲ) | -ቀይ የፍየል ሙኩት |

5. የኤጀርሳ ጋራ (ቆቲ) -ቀይ የፍየል ሙኩት

6. የግምባ ጋራ (ቆቲ) -ቀይ የፍየል ሙኩት ናቸው።

በእነዚህ ስፍራዎች ላይ ቃሉ ለሰላም፣ የሰውና የከብቶችን በሽታ ለመከላከል፣ የተዘራው እንዲበቅል፣ የተወለደው እንዲያድግ፣ ከብቶች በኮርማ እንዲጠቁ፣ ጥገቶች እንዲያግቱ ወዘተ ለእግዚኣብሔር መስዋዕት በማቅረብ ፈጣሪውን ይለማመናል።›› (አቶ ሞኮና ናጋዎ፣ በ10/12/2006)




ፎቶ፦8 ከተፈጥሯዊ መቼት ውስጥ የቂሊጦ ጋራ (kooba Qilixoo) የሚያሳይ ፎቶ

## ii. ሰው ሰራሽ መቼት

ሁለተኛው የቃሉ ከበራ የመቼት ዓይነት ሰው ሰራሽ ናቸው። እነሱም፦ ገልማና ሂሮ ይባላሉ። ገልማ የሚሰራበት ቁሶችና የአሰራር ዲዛይኑ እንደየዘመኑ የተለያዩ ናቸው። ቀደሞ ባሉት ዘመናት ከሳር እንደሚሰራና ቅርጹም ክብ እንደነበር የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ። አሁን ደግሞ በቆርቆሮ ክዳን ሆኖ ቅርጽም እንደመኖሪያ ቤት ዛንጋባ አሰራርን የተከተለ ነው። ገልማ ከሃማኖታዊና ባህላዊ ክዋኔዎችን መከወን ባሻገር እንደቃሉ መኖሪያ ቤትነትም ያገለግላል። (አባቃሉ አጋ ሳቆ፣17/3/2008 ዓ.ም.)

ገልማ ቃሉ እንደ ቃሉ ተቋምነትም ይቆጠራል። ገልማ ባብዛኛው የሚመሰረቱት በተራራ ጫፍ፣ በተራራ ጥግ ወይም በትላልቅ ዛፎች በተከበቡ ቦታዎች ላይ ነው (Gada, 1988:25)። የጉጂ ኦሮሞ ስለቃሉ ተቋም (ገልማ) አመሰራረት የሚያነሱት ከቃሉ አመጣጥ ሚት ጋር በማያያዝ ነው። በ 5.1.1. ውስጥ እንደተገለጸው ቃሉን ያገኘችው ልጃገረድ ወደቤት እንሂድ ስትለው፤ ቃሉ መለስላት የሚባለው ሚት እንደሚገልጸው «እኔ የሰው ቤት አልገባም፤ ስለዚህ ገልማ ስሩልኝ።» እንዳላት ነው። ከዚያም በቦታው የተሰበሰቡ ሰዎች ይህ ከእግዚአብሔር የመጣ ስለሆነ ያለውን እናድርግለት በማለት ገልማውን እንደሰሩለት ይተረካል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቃሉ የመጀመሪያው ማምለኪያውም ሆነ መኖሪያው ገልማ እንደሆነ ይገልጻሉ።




ፎቶ፡-9 የቃሉ ቤተ-አምልኮ (ገልማ) እና ሂሮ (ዳመራ መሳይ) የሚያሳይ ፎቶ

ሂሮ ደግሞ ከገልማው ፊት ለፊት በግምት አስር ሜትር ላይ የሚዘጋጅ ሰው ሰራሽ መንፈሳዊ ስፍራ ነው። ሂሮ ማለት አባቃሉ በተቋሙ (ገልማ) አካባቢ መስዋዕት የሚያቀርብበት አባይ (abbayyii) ከሚባል እንጨት እንደልምጭ ዓይነቶች ተቆርጠውና እንደዳመራ ተተክለው፣ ዙሪያው በሀረግ ታስሮ የሚዘጋጅ መንፈሳዊ ስፍራ ነው። ይህ እንጨት በየአመቱ እዚያው ላይ እየተጨመረ ይታሰራል። የቀድሞዎቹ እየደረቁ፤ እዚያው ረግፈው ይበሰብሳል፤ ደግሞ በላዩ ሌላ ይታሰራል። ይህ ድርጊት የሚከናወነው ቃሉ በሂሮ ስር መስዋዕት በሚያቀርብበት ወቅት ነው። ሂሮ ተቆርጦ የሚታሰረው በካሎዎች አማካይነት ነው። ሀዳ አንባ በገልማው ሳሎን ውስጥ ባለው ስፍራ እሳት አቀጣጥላ፣ በፍሙ ውስጥ ድፍን ቡናዎችን፣ የገብስ ፍሬ

በመጨመር በደጋን መሰል እንጨት (ቃጂማ) ወዲያና ወዲህ እየቆላችው ከሚወጣው ጭስ እያስከተለች ህዝቡን፣ አካባቢውን፣ ከብቶቹን ወዘተ ትባርካለች፤ ትመርቃለች። በዚህ ጊዜ ቃሉ ካላቻውን አድርጎ ሙኩት በመያዝ በዚያ ስፍራ ይሰዋል። ከዚያም ደሙን በገበቴ ይጠራቀምና ከዳንቢ እንጨት ልጥ ተተልትሎ እንደጭራ የተዘጋጀውን በመንከር ግራና ቀኙን እየረጨ፤ እየመረቀ ይገባል። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Galma anaa naga'l | ገልማውን ሰላም አድርግልኝ! |
| Mi'ee bokkoo anaa naga'l | ሚኤ ቦኮን ሰላም አድርግልኝ! |
| Galma anaa naga'l | ቦረና ዳዋን ሰላም አድርግልኝ! |
| Bitaafi mirga anaa naga'l | ግራ ቀኙን ሰላም አድርግልኝ! |
| Ardaa anaa naga'l | ህዝቡን ሰላም አድርግልኝ! |
| Biyya anaa naga'l | ሀገሩን ሰላም አድርግልኝ!፣ |
| Horii anaa naga'l | ከብቶቹን ሰላም አድርግልኝ!.. |

በማለት ከሂሮ ስር ጀምሮ እየመረቀ፤ እየተለማመነ ወደ ገልማው ውስጥ ይገባል። ከዚያ ያን ገበቴ ሀዳ አንባ (የቃሉ ባለቤት) ተቀብላ ታስቀምጣለች። አንዳንዴም ከማህበረሰቡ ውስጥ ወይፈን ወይም ኮርማ አምጥተው እንዲለማመንላቸው የሚያደርጉም ወቅት አለ። ከዚያ ከታረደው ኮርማ ቆዳ ተተልትሎ እንደጌጥ ይወጣና (eenjicha) በቃሉ እጁ ላይ ያደርጉለታል። ከታረደው ከብት ስጋ ውስጥም ከጎድኑ (Cinaacha) ላይ በማውጣት እንዲቀምስ (dhadhaama) ይደረጋል። ከዚያ በሀገሩ ላይ፣ በህዝቡ ላይ፣ በከብቶች ላይ የሚመጣውን መልካም ዕድልም ሆነ መጥፎ ነገር ለመረዳት ሞራ አንባቢዎቹ ቁጭ ብለው ሞራውን ያያሉ። (አቶ አባባ ቶቴ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ እና አባገዳ ሀልቻዬ ዳራ፣ አባያ ወረዳ፣ ደበቃ ደቦቤሳ ቀ/ገ/ማ፣ በ13/7/2008)

የዳንቢ እንጨት ለከበራው የተመረጠበት ምክንያት፤ የዳንቢ እንጨት ክረምት ከበጋ አይደርቅም፣ ውስጡ ወተት አለው፣ ተቆርጦ ቢተከል ይፀድቃል፣ ከሌሎች እንጨቶች ጋር ተጣብቆ ቢበቅል በመጨረሻ ሌሎችን በማጥፋት ቦታውን የሚሸፍነው እሱ ነው። ስለዚህ ለማህበረሰቡ መልካም ተምሳሌት ስለሚሆን፤ ከእንጨትም ውስጥ ለከበራ የሚውል እንጨቶች አሉ የሚባለው ለዚህ ነው። «ከእንጨት መርጦ ለታቦት፣ ከሰው መርጦ ለሹመት» ይባል የለ። በተራራና በገልማ (ሂሮ ስር) የሚደረገው ከበራ ልዩነት አላቸው። በሂሮ ስር የሚደረገው ከበራ የቃሉ ነው፤ ለመስዋዕት የሚሆነውን ከብት የሚያቀርበው ቃሉ ነው። ይኸውም በዘመን

መለወጫ ማለትም መስከረም (birraa) ላይ ከክረምቱ፤ ከጨለማዋ በሰላም ላወጣኸን አምላክ ምስጋና ይግባህ ለማለትና ቀጣዩ ጊዜ ደግሞ ከበሽታ፣ ከጦርነት፣ ከረሃብ፣ ከድርቅ፣ ህዝቡን፣ ከብቶቹንና እርሻውን እግዚአብሔር እንዲጠብቅ አደራ የሚሰጥበት ከበራ ነው። ከዚህ ባሻገር አንዳንዴ የእግዚአብሔር መንፈስ (ayyanni) እንዳመላከተው ሊከወን ይችላል። ይኸውም ኮኮብ ቆጣሪዎች፣ ሞራ አንባቢዎች እንዲሁም በባህሉና ሃይማኖቱ የበቁ አዛውንቶች (woyyuu) አማካይነት እግዚአብሔር በመንፈሱ ያመላከታቸው እንደሆነ ቃሉን እንዲህ ዓይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል፤ እንዲህ ታይቶናል ካሉ በመሀከሉም የሚያከብርበት ወቅት አለ። ከብቱንም በፍላጎት የሚያቀርብም ሊኖር ይችላል።

በተለያዩ ተራራዎች ወይም መንፈሳው ስፍራዎች ላይ የሚካሄደው ከበራ ደግሞ የጎሳው ነው ይባላል። ምክንያቱም ቃሉ በነዚህ ስፍራ መስዋዕት አቅርቦ እግዚአብሔርን እንዲለማመን ሲፈለግ፤ ጎሳው ለመስዋዕት የሚሆነውን ከብት የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት። ከዚያም ቃሉን በካሎዎች አማካይነት ወደተራራው እንዲወጣ («Qaalluu kooba nuuf ba'i.») በማለት ከብቱን ይዘው መጥተው ይጠይቃሉ። ለዚህም ነው በተራራ ላይ የሚደረገው ከበራ የጎሳው ነው የሚባለው። ያ ለመስዋዕት የቀረበው ከብት ከታረደ በኋላ ከከብቱ ላይ ከአፍንጫው ጀምሮ፣ የግንባሩን ቆዳ ከቀንዱ ጋር እንደተያያዘ፣ ሽንጡን ተከትሎ በቁመት ከነጭራው በመግፈፍ ይቀመጣል። በመጨረሻም ከበራው እንዳበቃ ያን ቆዳ ቃሉን ከጭንቅላቱ አንስቶ ጀርባው ድረስ በማልበስ፣ እየተጨፈረ ወደ ገልማው ይመለሳሉ። ከዚያም ለዚህ የመስዋዕቱ ምላሽ ማስቀመጫ ወደተዘጋጀ በስተቀኝ ካለው ጓዳ (Karba) ውስጥ ባለው ባለባላ እንጨት ላይ ይሰቀላል።

| | |
|---|---|
| Kallacha ati dhaga'I | ካላቻ አንተ ስማ! |
| Hirroo ati dhaga'I | ሂሮ አንተ ስማ! |
| Galma kan ati dhaga'I | አንተ ገልማ ስማ! .... እያለ አስገብቶ |

ይሰቅላል። (ሀዳ ኦዳ ረጋቱ በሪሶ፣ ዕድሜ 40፣ ወናጎ ወረዳ፣ የቃሉ እናት (የቀድሞዋ ሀዳ አንባ) በ13/7/2008)

ከዚህ በተጨማሪ ለምሳሌ ይህ ከገልማው ፊት ለፊት የሚታየው ሂሮ ከአያት ቅድመ-አያታችን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣ እየሰማን አድገናል። ከዚያም አባታችን እዚሁ ላይ እየደመረ ያከብር ነበር። አሁን ደግሞ ወደ ልጁ ተላልፏል። ስለዚህ በየወቅቱ ይሄ እያረጀ ሲሄድ መስዋዕት በሚቀርብበት ወቅት አዲስ ተቆርጦ በዚያው ላይ እየተጨመረ ይታሰራል። ከዚህ

ጋር አብሮ የሚነሳው ለመስዋዕት የቀረበው ከብት ሞራ ስታይ ችግር ካለው በሉ ይህን ዓይነት ከብት ይታረድ፤ ሞራው እንዲህ አመላክቷል፤ በማለት የዳለቻ ቦቃ ከብት ሊታረድ ይችላል። ፍዬል ወይም በግ አሊያ ከብት ሊሆንም ይችላል። ከዚያ ሞራው አምሯል፤ ጥሩ ነገር አመላክቷል፤ ለቃሉ መልካም ጊዜ ነው፣ ለህዝቡም፣ ለከብቱም፣ ለሀገሩም ሰላም ነው ካሉ በዚያው ያበቃል።

የመማክርቱ አባላትና የሀገር ሽማግሌዎቹም በተራቸው ይመርቃሉ። ይኸውም:-

| | |
|---|---|
| Qaalluun nu'uu naga'a | ቃሉዋችን ሰላም ነው፣ |
| Gadaan nu'uu naga'a | ገዳችን ሰላም ነው፣ |
| mangudoon nu'uu naga'a | አዛውንቶቻችን ሰላም ናቸው፣ |
| biyyi nu'uu naga'a | ሀገራችን ሰላም ነው፣ |
| ilmi nu'uu naga'a | ወንዶች ልጆቻችን ሰላም ናቸው፣ |
| durbi nu'uu naga'a | ሴቶች ልጆቻችን ሰላም ናቸው፣ |
| Ee! nu'uu nageessi | አዎ! ሰላም አድርግልን። በማለት |

ይመርቃሉ።

በመቀጠል የከበራውን ማብቃት በሚገልጽና የእግዚአብሔርን ተዓምር አሳየን በሚል መልክ ቃሉ ‹‹Malgicha kooyyaa›› የሚለውን መንፈሳዊ ዘፈን በማውጣት ይጨፈራል። በመጨረሻው ቃሉ ለእኛ አማረልን፣ እኛን አኮራን እያሉ የታደሙት ሰዎች እየጨፈሩ ገልማውን ለቀው ይሄዳሉ። (አቶ አባባ ቶቴ፣ ዕድሜ 55፣ ወናጎ ወረዳ ቆቲ ቀ/ገ/ማ፣ የቃሉ ቶቴ ልጅ በ13/7/2008)

ባጠቃላይ ከላይ ለመመልከት እንደተሞከረው የቃሉና የገዳ ከበራዎች የሚከወኑባቸው መቼቶች አንድም ተፈጥሯዊ ሲሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሰው ሰራሽም እንዳሉ አይተናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጉዳይ ደግሞ መቼ ነው የሚከወነው ለሚለው የጊዜን ጥያቄ ለመመለስ የጉጂ ኦሮሞ ያዋቀረውን ማህበረሰባዊ ዕውቀት ማየት ያስፈልጋል። ስለዚህ ይህን በተመለከተ እንደሚከተለው ተቃኝቷል።

### iii. የቀናት ሃይማኖታዊ እሳቤዎች

መቼት የቦታ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የጊዜም ጉዳይ እንደሆነ ቀደም ሲል ለመግለጽ ተሞክሯል። ጊዜ ስንል እያንዳንዱ ሃይማኖታዊ ከበራ በዘፈቀደ የሚከወን ሳይሆን በዓመት ስንት ጊዜ

ይከወናሉ፣ በየትኛ ወርና ዕለት የሚሉት በማህበረሰቡ ዕውቀት ተዋቅሮና ተቀምረው የተቀመጡ ናቸው።

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰብ እያንዳንዱ ወር የራሱ የሆነ ዕድል አለው። እንዲሁም የተለያዩ ቀናት የየራሳቸው የሆነ መልካም ወይም መጥፎ ዕድል (kayo) አላቸው ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ ለሚከወኑ ከበራዎችና በዓላት መቼ መከወን እንዳለባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። አንድ ሰው የሞተበት ወይም የተወለደበት ቀን በራሱ ስለዚያ ሰው፣ ስለቤተሰቡ ወይም ስለማህበረሰቡ የሚከሰተውን ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር ያመላክታል ተብሎ እንደሚታመን *(Elfineh, 1994:62)* .እንደሚከተለው ያስረዳል።

> *According to the society, each day of the month has specific significance. Different days have good and bad kayo, roughly, "fortune". Therefore, serious attention is paid to dates to practice ritual activities or to hold ceremonies. Birth or death on a given day is prognosticative of either the peace or trouble to happen to a person, family or the society at large.*

ምንም እንኳን ስም ከተሰያሚ ጋር የባሕርይ ግንኙነት ባይኖረውም፤ የጉጂ ኦሮሞ በወራቶች ውስጥ ያሉት ቀናት ለማህበረሰቡ ነበራቸው ወይም አላቸው ብለው ባመኑት መሰረት ከሃይማኖታዊ ጠቀሜታቸው አኳያ ለቀናቱ ከተሰጡት ስያሜ ውስጥ የተወሰኑትን በመውሰድ ያላቸውን ማህበረሰባዊ ፋይዳዎች እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

ለአብነት ያህል ዱሬቲ (Dureetti) የመጀመሪያዋ ቀን ስትሆን ትርጉሙ ሀብታሟ ማለት ነው፤ ከሀብት ጋር ተያያዥ ለሆኑ ጉዳዮች ከበራ የሚፈጸምበት ዕለት ነው። ለአብነት ያህል ከብቶች ይመረቃሉ፤ ነገር ግን በዚህ ዕለት ከብት አይታረድም።

በመቀጠል ዱላቲ (Dullatti) አሮጌዋ የሚል ትርጉም አላት። በሌላ መልኩ የአረጋዊያን ቀን በመባል ይታወቃል። በዚህ ዕለት አዛውንቶች ለራሳቸውና በአካባቢያቸው ላሉ ሁሉ መልካም ነገር እንዲገጥማቸው የሚጸልዩበት ዕለት ነው። ሦስተኛዋ ቀን ሻልባና ዴቲ (shalbana deettii) ስትሆን፤ ይህች ዕለት ዕድለ-ቢስ ቀን ይሏታል። በዚች ቀን ውጤታማ አይኮንም ተብሎ ስለሚታመን ምንም ነገር አይከወንም።

አራተኛዋን ቀን ሻልባና ብድርሳ (Shalbaana bidirsa) በማለት ይጠሯታል። ይቺን ቀን የንቦች ቀን፤ ንቦች የሚናደፉበት ዕለት ይሏታል። ተምሳሌነቱም የማጥቃት እንቅስቃሴ፣ በሙሉ አቅም የመናርና ለመከላከል ብቃት ያለው የሚል ነው። በዚህ ዕለት የሚወለድ ልጅ እነኚህን ብቃቶች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል። የእሱም ምርቃትና እርግማን ትልቅ ተፅዕኖ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል።

ስድስተኛዋን ቀን ደግሞ ጋርዳዱማ (Gardaaduma) የምርቃት ቀን ትባላለች። መልካም ምኞት አላት ተብላ ስለሚታመን ማንኛውንም ዓይነት ከበራ መፈጸም የሚቻልበት ዕለት ናት።

ከሰባተኛው እስከ ዘጠነኛው ቀናት ድረስ ባጠቃላይ ቡሳዋ (Busawa) የአራዊት ቀን በመባል ይታወቃሉ። ቡሳዋ ሦስት ዓይነት ናቸው። እነሱም፡- የመጀመሪያዋ ቡሳዋ (Busowaa qara) ጅብን የሚወክል ሲሆን፣ መካከለኛዋ ቡሳዋ (Busowaa gidduu) ነብርን ይወክላል፣ የመጨረሻዋ ቡሳዋ (Busowaa eegee) ደግሞ አንበሳን ይወክላል። በቡሳዋ ከበራ ለመፈጸም ጥሩ እንዳልሆነ ይነገራል።

አስረኛዋ ቀን ጊዳዳ (Gidaadaa) የውርስ ቀን በመባል ትታወቃለች። በዚህ ዕለት አንድ ወንድሙ የሞተበት ሰው የወንድሙን ሚስት የውርስ ጋብቻ የሚፈጽምበትና በንብረቱም የሚወስንበት ዕለት ነው። በዚህ ዕለት የሚወለድ ልጅ አሟሟቱ ከሁሉም ወንድሞቹ በኋላ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። በሌላ በኩል አንድ ሰው በዚህ ቀን ከሞተ በሚቀጥለው ከቤተሰቡ አባል ወይም አባላት ውስጥ መሞቱ/መሞታቸው የማይቀር መሆኑን አመላካች እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።

አስራ አንደኛዋ ቀን ሩዳ (Ruuda) የከብት ቀን ትባላለች። ከብቶችን በተመለከተ ለሚደረጉ ከበራዎች ጥሩ ቀን እንደሆነ ይታመናል። በጉጂ ዘንድ በዚህ ዕለት ጋብቻ አይፈጸምም። ምክንያቱም በጋብቻ ስነስርዓቱ ላይ ልጃገረዷ ከቤቷ ወተት ተሸክማ መሄድ ይጠበቅባታል። ይህ ደግሞ ለእሷ ቤተሰቦች ከቤታቸው ወተት ከወጣ እንደ መጥፎ ዕጣ-ፈንታ ይታያል።

አስራ ሁለተኛዋና አስራ ሦስተኛዋ ቀናት አሬሪ (Areerii) ተብለው ይጠራሉ። እነኚህ ቀናት በገዳ ስርዓት ስያሜ ላላገኙ ሰዎች በዚያ ዙሪያ ከበራ የሚከናወንላቸው ቀናት እንደሆኑ ይታወቃል። በእነዚህ ቀናት ጋብቻ አይከናወንም። የከበራ እንቅስቃሴዎች ግን ይከናወናሉ። ሁለት ዓይነት አሬሪዎች አሉ። እነሱም፡- የመጀመሪያዋ አሬሪ (Areerii qara/garbittii) እና የመጨረሻዋ አሬሪ (Areerii eegee/badhoo) ይባላሉ። በተወሰነ ደረጃ ሁለቱም ተመሳሳይ ጠቀሜታ አላቸው ተብሎ ይታመናል።

አስራ አራተኛዋና አስራ አምስተኛዋ ቀናት ደግሞ አዱላ (Adulaa) ተብለው ይጠራሉ፡፡ በእነዚህ ቀናት ሁሉም ባህላዊ ከበራዎችን ማካሄድ ይቻላል፡፡ ይኸውም እንደ የጋብቻ ስርዓት፣ የምርቃን ስርዓት፣ የስም ማውጣት ስርዓትና ሌሎችም ስርዓቶችን ሊያካትት ይችላል፡፡ ሁለቱም ቀናት የተለያየ ቅጥያ መጠሪያ አላቸው፡፡ እነሱም፡- የመጀመሪያዋ አዱላ (Adulaa qara ) እና የመጨረሻዋ አዱላ (Adulaa eegee) ይባላሉ፡፡

ሃያ አምስተኛዋን ቀን ባላ-ሆላ (Balla-holla) በመባል ትጠራለች፡፡ እንደ መረጃ አቀባዮቹ ገለጻ ይህች ዕለት የቃሉ ቀን በመባል ትታወቃለች፡፡

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው በየወራቶቹ ውስጥ ካሉት ቀናት መካከል ለማሳያነት የተወሰዱ ሲሆን ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ከበራዎች ለማከናወንም ሆነ ላለማከናወን በማህበረሰቡ የተዋቀሩ ዕውቀቶች ሲሆኑ ተመልሰው ማህበረሰቡን እንደህግና ደንብ ሆነው ሲገለግሉ ይታያሉ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ለጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ከበራ ከጊዜ ውስጥ ወራትን ለይተው እንደሚከወኑ የሃይማኖት መሪዎችና የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ያስረዳሉ፡፡ ገዳዎች ወደ አባቃሉ ተቋም ለመባረክና ስልጣነ-ሢመታቸውን ለማጽደቅ ስጦታቸውን ይዘው ሲመጡ፤ በቅድሚያ የሚጠይቁት መቼ፣ የት ቦታና ከበራዎቹን አሳውቅ በማለት እንደሚከተለው ይማጸኑታል፡፡ ይኸውም፡- ዓመቱን እወቅልን፣ ወራቱን እወቅልን፣ ሃይማኖታዊ ከበራችንን እወቅልን፣ የምናመልክበትን ተራራ እወቅልን በማለት እንደነበርና መባልም እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ (አቶ ሞኮና ናጋአ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ፣ በ14/12/2007 ዓ.ም.)

ይህ ማለት እያንዳንዱ ክስተት የራሱ የሆነ መቼት እንዳለውና ያንንም መቼት ቃሉ ለየገዳዎቹ አንተ ይሁነኝ ያልከው ይሁንህ! በታየህ ወር፣ ዕለትና ቦታ አምልክ በማለት ስለመቼቱ ይባርኳቸዋል ይባላል፡፡

ስለዚህ ካሉት አስራ ሁለቱ ወራቶች ውስጥ ሃይማኖታዊ ከበራዎቹን ሊከወንባቸው ይቻላል የሚሉትን ልክ እንደ ቀናቱ ሁሉ ወራቱንም ማህበረሰቡ ለይተው እንደሚከውኑበት *Elfineh,* (*1994:*;65) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> Nowadays, the Guji calendar has a year made up of twelve months or 360 days. There is no allowance for a leap year or intercalation. The twelve months are hageyya, birra, onkoleessa, sadaasa,

arfaasaa, qaamuu, badheessa, bisdottessa, caamsaa, ella, wocabajjii, and adoolessa.

Four important Months. Jia ilma orma, “the month of a stranger's son”. Among the twelve months arfasa, badheessa, camsa and adolesa are of extra-ordinary importance. The society believe that, if ritual activities or ceremonies like cultural naming, weddings and so on are held in these months, wishes will be fulfilled, plans will be successful. These months are the best ones for all activities. The phrase ji'a ilma orma is coined after a wedding ceremony- the most important deed, that assures the continuity of the society.

እንደ አስራ ሦስተኛ ወር ኦሪቶ ወይም ጮጮፏ ሀጌያ (orito ykn cocopha hageyya) ትቆጠራለች። እንደ Elfineh (*1994*:,65) አገላለጽ ለዚህም እንደምክንያት የሚቀርበው፡-

> rains are expected to begin as soon as the month of hageya sets on. But once upon a time the Guji felt that there was a gap of some days b/n adoolessa- the last month of the previous year and hageyya- the first month of the new year.

ይቺን ወር ለብዙ ሞቶች መከሰቻ፤ ልክ እንደ መጥፎ ዕድል አምጪና በጠላት ብዙ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ከነበሩት ክስተቶች እያመኑ እንደመጡ ይገልጻል።

ነገር ግን በተለያዩ የጉጂ ኦሮሞ ኮንፌድረስዎች ዘንድ የጊዜ ስሌት ልዩነቶች ይታያሉ። ይህ ዓይነት ክስተት ሊፈጠር የቻለው የጉጂ ቀን መቁጠሪያ መሰረት ያደረገበት የተለያዩ ተፈጥሯዊ ሁነቶችና የአየር ሁኔታ ክስተቶች እንዳሉና የነዚህ ክስተቶች በተለያዩ ቦታዎች ተለዋውጠው በመፈጠራቸው ምክንያት እንደሆነ Elfineh እንደሚከተለው በማከል ያስረዳል።

> *There are some variations among the three tribal divisions of the Guji-the uraga, the matti and the hokku in time calculation. This is due to the dependence of the Guji calendar on the variable natural environment and weather condition. The early or late coming rains appearance or dis- appearance of busan a group of seven stars,*

*getting or losing sight of the moon have great influence on the time reckoning (ibid, 66).*

ባጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ስር ቃሉ ማነው? ለሚለው የእግዚኣብሔር መልዕክተኛ እንደሆነና አመጣጡም ከሰማይ መሆኑን በሚቶቻቸው ያስረግጣሉ፡፡ የቀድሞው ቃሉ ሲሞት ደግሞ ከአብራኩ ክፋይ ውስጥ ማህበረሰቡ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት መሰየም እንደሚቻል ከቀረበው ሚት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ቃሉ እያንዳንዱን ከበራ ሲከውን አብረውት የሚያከናውኑ የተለያዩ ተግባራት ያላቸው የመማክርት አባላቶች አሉት፡፡ አነሱም ግለሰባዊ ዕውቀትና ቡድናዊ ዕውቀታቸውን በማቀናጀት እንደ ቃሉ ተቋም ለማህበረሰቡ ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡ ይህንንም ክዋኔ የሚያስፈጽሙበት ጊዜና ስፍራ መቼት ይባላል፡፡ የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች መቼቶች ከላይ እንደተመለከትነው እያንዳንዱ ከበራ በተመለከተ የት ይከወናል?፣ መቼ ይከወናል? የሚሉትን ከተሰበሰቡት መረጃዎች የተገኙትን ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ይኸውም፡- የት ይከወናል? ለሚለው በማህበረሰቡ ዕውቀት የተዋቀሩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ መቼቶችን በመጠቀም ነው፡፡ ከበራዎቹ መቼ ይከወናል? ለሚለው አንደ ጉጂ ኦሮሞ የዓለም አተያይ እያንዳንዱ ቀን፣ ወር፣ ወቅትና ዓመት የራሱ የሆነ መልካም ወይም መጥፎ ዕድል አላቸው ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ከበራው ማን እንደሚከውን፣ ለምን እንደሚከወንና ከሃይማኖታዊ ከበራዎች ጋር ያላቸውን ትስስር የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ እነዚህ የማህበረሰብ ዕውቀቶች ሃይማኖታዊ ተምሳሌትን በማላበስ ሲግባቡበት ኖረዋል፤ እየተግባቡበትም ይገኛሉ፡፡

ቀደም ሲል በ 2.3. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ስር በቃሉ እና ቃሊቻ/ቃሊቲ መካከል ያለውን የፅንሰ ሀሳብ ልዩነት ባላገናዘበ መልኩ በመተካካት በስራቸው ውስጥ ሲገለገሉበት ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ ልዩነት ደግሞ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ከዋኞቹ (ቃሉ ወይም ቃሊቻ) በተቀየሩ ቁጥር፣ ክዋኔውም ይለያል፡፡ በሌላ በኩል መከወኛው መቼትም ይለያያል፡፡ ከዚህ በመነሳት በቃሉና ቃልቻ መካከል ያለውን ልዩነቶች ከቀዳማይና ካልኣይ መረጃዎች የተገኘውን ከራሴ ልምድ ጋር በማቀናበር ስለ ሁለቱ አንድነትና ልዩነት እንደማጠቃለያ ለማሳየት ችያለሁ፡፡

ይኸውም፡- ስለቃሉና ቃሊቻ/ቃሊቲ አንድነትና ልዩነት ለማውጣት እንደማነጻጸሪያ የተጠቀምኩት የክዋኔውን አውድና ተግባራቸውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ከአውድ አኳያ ስናይ አውድ

በውስጡ መቼት፣ ከዋኝ፣ ክዋኔ፣ ታዳሚዎች፣ ቁሶችና የመሳሰሉትን ያካትታል። ስለዚህ ከእነዚህን ነጥቦች አኳያ በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ በዝርዝር ተገልጿል።

| ተ.ቁ. | ቃሉ | ቃሊቻ/ቃሊቲ |
|---|---|---|
| 1 | የቤተ-አምልኮው መጠሪያ "ገልማ" ይባላል። | በተመሳሳይ "ገልማ " ይባላል። |
| 2 | "ገልማ "የሚሰራው ከፍታ ቦታ ላይ ነው። | እዚህም ተመሳሳይነት አለው። |
| 3 | "ገልማ " ከባህላዊ ቁሶች በቀር በሌሎች ባዕድ ነገር አያሸበርቅም። | "ገልማ " በጃኖ ጨርቅ፣ በባንዲራ፣ በግምጃ ያሸበርቃል። |
| 4 | የቃሉ ገልማ ዕጣን፣ ሰንደል፣ ድኚ አይጨስም፤ ድቤም አይመታም። | ድቤ እየተመታ፣ ዕጣን፣ ሰንደል፣ ድኚ ይጨሳል። |
| 5 | ባህላዊ ዘፈኖች ያወጣሉ (weedduu baasu) | ይዘየራል፣ ወዳጃ ይወጣል። |
| 6 | ከመማክርት አባላቱ ጋር ይሰራል። | ከካዳሚዎቹ ጋር ይሰራል። |
| 7 | የሚቀመጠው ሳሎን በግልጽ ቦታ ነው። | የሚቀመጡት በመጋረጃ በተጋረደ ክፍል ውስጥ ተከልለው ነው። |
| 8 | መንፈሳዊ ጉዞ "የሙዳ" ከበራ ያከናውናል። | "የሙዳ" ከበራ አያከናውንም። |
| 9 | እንደቦኩ፣ ካላቻ፣ ሩፋና የመሳሰሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ቁሶችን ይገለገላል። | እንደ ቦኩና ካላቻ ያሉትን የመገልገል ስልጣን የለውም፤ አንካሴ፣ ባለባላ በትር ይይዛል። |
| 10 | በማህበረሰቡ ውስጥና ከአጎራባች ጎሳዎች ጋር ግጭቶች ሲከሰቱ የማስማማት/ ግጭቱን የመፍታት አቅም አለው። | የግለሰቦች ግጭት መፍታት፣ አንዳንዴም ጠላትህ እገሌ ነው በማለት ሊያጋጭም ይችላል። |
| 11 | የጎንዶሮን ከበራ ይፈጽማል። | የጎንዶሮን ከበራ አይፈጽምም። |
| 12 | ከገልማ ውጭ በመንፈሳዊ ተራራዎች ላይ ሃይማኖታዊ ከበራ ይፈጽማል። | አብዛኛዎቹ ከበራዎቹ በ"ገልማ " ውስጥ ብቻ ነው። |
| 13 | የመሪነቱን ቦታ ከአባት ወደ ልጅ ሲሸጋገር ልጅ ሊያሟላ የሚገባው ቅድመ-ሁኔታዎች አሉ። | ከአባት/ከእናት ወደ ልጆች (ሴት/ወንድ) ሊተላለፍ ይችላል። |
| 14 | የመሪነቱን ቦታ የሚይዘው ከመጀመሪያዋ (ከገለልቻ ጎሳ) የተወለደው መሆን አለበት፣ | ከ1ኛዋ፣2ኛዋ ወይም ሌላኛዋ ሚስት የተወለደው ሊሆን ይችላል። |
| 15 | በገልማና በመንፈሳዊ ተራራዎች ላይ ስለማህበረሰቡ መልካም አጋጣሚዎች ለማመስገን፣ ለደረሰባቸውና ሊደርስባቸው ይችላል ከተባለው ችግሮች እንዲታደጋቸው እግዚኣብሔርን ለመማጸን ዓመታዊ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በጋራ ይፈጽማል። | ተቸገርኩ ብሎ ስለሚመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች እዚያዊ በ"ገልማ " ውስጥ መላ ይላል እንጂ ስለማህበረሰብ ባጠቃላይ ደንታ የለውም። |
| 16 | ምርቃት የሚያከናውነው በሚጁ (ቦካ፣ | በቡና፣ በጫት፣በዕጣን..ይመርቃል። |

| | | |
|---|---|---|
| | ወተት፣ቡና ቃላ) ነው | |
| 17 | የወር አበባም ሆነ፣ሴት ልጅ ወልዳ 40/80 ቀናት ሳይሞላት፣ "ገልማ " ውስጥ ለመግባት አያግዱም:: | ሴት ልጅ ወልዳ 40/80 ቀናት ሳይሞላት፣ የወር አበባ ታይቷት ሳትፀዳ ወደ "ገልማ " ውስጥ መግባት አትችልም:: |
| 18 | ሰው ሞቶ የቀብር ስርዓት ላይ መሳተፍ "ገልማ " ከመግባት አያግድም:: | ሰው ሞቶ የቀብሩን ስርዓት ላይ የተሳተፉ የሟቹ 40ው ሳይወጣ ወደ "ገልማ " ውስጥ መግባት አይችሉም:: |
| 19 | የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም "ገልማ " ከመግባት አያግድም:: | የግብረ-ስጋ ግንኙነት የፈጸመ ሰው በዕለቱ ወደ "ገልማ " ውስጥ መግባት አይችልም:: |
| 20 | በላዩ ላይ የሚወርድበት/ የሚሰፍርበት አውሊያ/ ውቃቢ/ዛር የለም:: የተረጋጋ፣ ቅዱስ መንፈስ ነው የሚቀርበው:: | አውሊያ/ውቃቢ/ዛር በላዩ የሚወርድ/ የሚሰፍርበትና በእሱ ላይ አድሮ የሚናገር መንፈስ አለ:: |
| 21 | የገዳዎችን ስልጣነ ሢመት ያፀድቃል:: ነገር ግን ዛር፣ ውቃቢና አጋንንት በመለየት ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት የለውም:: | ዛር፣ ውቃቢና አጋንንትን በመለየት ውሳኔ ይሰጡበታል ይባላል:: ነገር ግን የገዳዎችን ስልጣነ ሢመት የማጽደቅ ተሰጥኦም ሆነ፣ ስልጣኑ የለውም:: |
| 22 | የ"ሀማቺሳ" ስርዓት አያከናውንም:: | የ"ሀማቺሳ" ስርዓት ያከናውናል:: |
| 23 | -የተለያዩ ከበራዎች የተወሰኑ መቼት ቢኖራቸውም፣ ባለጉዳዮችን ዘወትር ከማስተናገድ የሚያግደው ነገር የለም:: ምክንያቱም ቀናትን ለይቶ የሚቆም ዛር/ውቃቢ የለውም:: | -ከተወሰኑ ቀናት ውጭ ባለጉዳዮችን ማስተናገድ አይችልም:: ላስተናግድ ቢል እንኳን በባህሉ መሰረት የመሸምገል እንጂ እንደቀድሞው መከወን አይችልም፣ ምክንያቱም መንፈሱ ሲወርድበትና መንፈሱ ትቶት ሲሄድ የተለየ ባህሪይ ስለሚላበሱ ነው፣ |
| 24 | በስጦታ መልክ እንደ ብር፣ ከብቶች፣ እርጎ፣ ጨኮ፣ ቡና፣ ገብስና...የመሳሰሉትን ይበረከትለታል:: | በስጦታ መልክ እንደ ብር፣ ሀረቄ፣ እጣን፣ ሰንደል፣ ዶሮ፣ ግምጃ፣ ጃኖ፣ መርፌ፣ ሻማ፣ ሽቶ፣ ቡናና የመሳሰሉት ናቸው:: |
| 25 | የተለያዩ ስጦታዎችን ከማህበረሰቡ በገዳ አስተባባሪነት የሚበረከትለት:- በሠርጉ ዕለት፣ በሙዳ ከበራ ወቅት፣ የዓመት ጉርሱን በማሳረስና ሃይማኖቱንና ባህሉን በከፋ ሁኔታ ከጣሱ አካላት እንደካሳ ከሚሰጡት ነው:: | ስጦታ የሚበረከትለት ግለሰቦች ከችግራቸው አኪያ ተሳካልን ወይም እንዲሳካልን በማለት ከሚያቀርቡት ውጭ፣ በገዳ አባቶችና በአብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል የሚሰጠውና የሚገበኝ |

| | | |
|---|---|---|
| | | አይደለም፡፡ |
| 26 | በቃሉ ስር የሚገኙ የመማክርት አባላት በየሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ የራሳቸው አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ | በስሩ የሚገኙት የመማክርት አባላት ሳይሆኑ፤ ካዳሚዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን የተወሰኑ ሽማግሌዎች አንዳንድ ጉዳዮችን የማከናወን ሁኔታ ይታያል፡፡ |
| 27 | የውሳኔ አሰጣጥ ሂደታቸው ይለያያል፡፡ ያኸውም፡- ቃሉ እያንዳንዱን ጉዳዮች ከስረኛው መዋቅር እንዴት አልፎ እንደመጣ ያጣራል፣ እንደ ጉዳዩ ቅለትና ክብደት በተዋረድ እንዲታይ ያደርጋል፡፡ | ቃሊቻ ግን በመንፈሱ አማካይነት ደረሰኩበት ባለው መረጃ መሰረት ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡ ማንኛውንም ጉዳይ ከእሱ ገልማ ከደረሰ እዚያው በመሰለው መሰረት ይጨርሳል፡፡ አንዳንዴም ለሽማግሌዎች የሚያስተላልፍበት ሁኔታዎች አሉ፡፡ |
| 28 | ያገልማው አሰራር በአብዛኛው ይመሳሰላል፡፡ | ተመሳሳይ ነው፡፡ |
| 29 | ለተቋሙ ህግና ደንብ አልገዛ ያለውን የሚቀጣው በደረጃ ነው፡፡ የመጨረሻው ቅጣት ቦካ (boka) ማለትም ከማህበራዊ ግልጋሎቶች የማግለል ሁኔታ እንዳለ ይገልጻሉ፡፡ | ከተቋሙ የሚተላለፈውን የጥሪና የውሳኔ ሀሳብ አልቀበልም ካለ፣ በመንፈሱ ባለቤቱን አሊያም ከቤተሰቡ አባል ማሳበድ ወይም መግደል እንደሚችል ያስፈራራል፡፡ ተሰሚነቱ ያነሰ ቢሆንም ማህበረሰቡ እንዲያገለው መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ |
| 30 | ቃሉ በስሩ ገዳን ጨምሮ አብሯቸው የሚሰራ የመማክርት አባላት አሉት፡፡ | እዚህ ግን ሁሉም ነገር የሚከወነው በቃሊቻው ብቻ ሲሆን፤ የተወሰኑ የመላላክና ወዳጃውን የማሞቅ ስራዎች በካዳሚዎቹ ይፈጸማል፡፡ |
| 31 | የቃሉ ባለቤት ሀዳ አንባ ስትባል፤ ቃሉን ተክታም ሆነ፤ እራሷን ችላ ተቋሙን የመምራት ስልጣኑ የላትም፡፡ ባሏ ሲሞትም ተክታ አትሰራም፡፡ | የቃሉ ባለቤት ቃሊት ይሏቸዋል፡፡ ባሏ ሲሞት ተቋሙን እስከ ሕልፈተ-ሕይዎታ እንደምትመራ ይነገራል፡፡ ነገር ግን አንዲት ሴት ዛር ከሰፈረባት ቃሊት ተብላ ተቋሟን መምራት ትችላለች፡፡ |
| 32 | የከበራ ቀናትና ወራት የተወሰኑት ባላቸው ዕጣ-ፈንታ ላይ ተንተርሶ የተደለደሉ ሲሆን፤ ተቋሙ የተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካው ጉዳዮችን በማንኛውም ቀናት ለማስተናገድ ክፍት ነው፡፡ | የከበራ ቀናት አብዛኛውን ጊዜ ረዕቡ እነ ዓርብን ይመርጣሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቅዱሳንን (የሚካኤል፣ የጊዮርጊስ፣ የማሪያምና የመሳሰሉትን) ክብረ-በዓላት ተንተርሶ ሲከውኑ ይታያል፡፡ |

ሠንጠረዥ-2 የቃሉና ቃሊቻ/ቃሊቲ አንድነትና ልዩነት (በአጥኚው የተዘጋጀ)

ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ እንደተመለከትነው በቃሉና ቃሊቻ/ቃሊቲ መካከል ያለው ተመሳስሎ በጣም ውስንና ያውም ከቅርጽ ላይ ሲሆን፤ ይዘታቸውንና ተግባራቸውን ያየን እንደሆነ ሰፊ ልዩነቶች የታዩባቸው ነው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ትንተናና ገለጻ

በቃሉ ተቋም ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይከወናሉ። ከነዚህም ውስጥ የገዳዎችን ስልጣነ-ሢመት ማጽደቅ፣ የግጭት መፍቻና ማስወገጃ ጎንዶሮ፣ የፋጭ፣ የሁሉቃ (ጦስ ማውጣት) እና የቃሉ ስያሜ ከበራዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ከበራዎች የማህበረሰቡ ዕውቀት ውጤቶች ሲሆኑ፣ እያንዳንዱ ከበራ የራሱ የሆነ መቼት፣ የራሱ የሆነ ፍችና ተግባር ወይም ፋይዳ አለው። እነዚህን ከበራዎች በንጥል ጥናት ዘዴ በመጠቀም ከኢፒስቲሞሎጂና ኦንቶሎጂ አተያይ ምን ይመስላሉ? እንዲሁም ከማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብና ተምሳሌታዊ አተረጓጎም አንጻርስ የሚሉትንና ከአውዳዊና ፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ተተንትነው በዝርዝር ቀርበዋል።

## 6.1. የገዳ ስልጣን ማጽደቂያ ከበራ

የገዳ ስልጣነ ማጽደቂያ ከበራ የሚባለው በየስምንት ዓመት አንዴ በሚካሄደው የስልጣን ሽግግር ወቅት የሚከናወኑ ባህላዊ፣ መንፈሳዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ክዋኔዎችን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው። እነኚህ ክዋኔዎች ደግሞ የሚፈፀሙት የተለያዩ ሂደቶችን ደረጃ በደረጃ በማከናወን ነው። ስለዚህ በየደረጃው የሚከናወነው ምንድነው?፣ በሂደቶቹ ውስጥ ማን ምን ዓይነት ሚና አለው?፣ ሂደቶቹ የሚከወኑበት መቼት ምን ይመስላል? የሚሉትና ሌሎች ተዛማጅ ጥያቄዎችን በማንሳትና ለእነዚህ ጥያቄዎች ከቀዳማይና ካልኣይ የመረጃ ምንጮች የተገኙትን መረጃዎች በወጉ በማቀናበር፤ አግባብነት ይኖራቸዋል በተባሉ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች በመጠቀም ተተንትነዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ የሃይማኖታዊ ከበራው በገዳ የስልጣን ሽግግር ወቅት ያለውን ባህላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች ለመግለጽ ተችሏል።

በገዳ ስርዓት ውስጥ የቃሉ ተቋም ሚና ከፍተኛ ነው። ይህን በተመለከተ በ 5.1.3.1. በስፋት ተገልጿል። ከነዚህ ተግባራት ውስጥ አንዱ የገዳዎች ስልጣን በማጽደቅ ወቅት የሚከወነው ሃይማኖታዊ ከበራ ነው።

ቃሉ የገዳ መሪዎችን በመምረጥና ከበራዎችን በማከናወን፣ የገዳ ስርዓት ሕጋዊ መሰረት እንዲይዝና በገዳ መሪዎች መካከል የተካሄደውን የስልጣን ሽግግር የማጽደቅ ከበራዎች ጭምር

ያከናውናል፡፡ ነገር ግን የገዳ መሪዎችን በመምረጥ ሂደት ላይ ይሳተፋል ሲባል ቀጥተኛ ተሳትፎ አያደርግም፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ለገዳነት በሚቀርቡ ዕጩዎች ላይ ችግሮች ካሉ በህዝብ ተወካዮች አማካይነት በሚቀርብለት ጥቆማ መሰረት አስተያየት በመስጠት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ያደርጋል፡፡ ያን ካልፈጸሙ በመጨረሻው ሂደት ላይ አለአግባብ ስልጣን ይዞ ቢመጣም ቃሉ የማጽደቅ ከበራውን አይፈጽምለትም፡፡ ይህ ከበራ ካልተፈጸመለት ደግሞ አንደኛ መንፈሳዊ ኃይል አልተጎናጸፈም እንደ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ተኣማንነትና ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ስለዚህ እንደነዚህ ዓይነት ተፅዕኖ በማሳደር የገዳን ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት ያስጠብቃል፡፡

አዲሱን የገዳ የአስተዳደር ጊዜያት የሚመሩ ገዳዎች የስልጣን ርክክብ የሚያከናውኑት በየራሳቸው መንፈሳዊ አረዳ (araddaa jilaa) ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ የቀድሞው የሆኩ አባገዳ በሀሩ ጎባ (Harru Gobba)፣ የማቲ አባገዳ ደግሞ በድባ (Dibba) ሲሆን የኡራጋው አባገዳ ደግሞ በገደብ (Gadabi) እንደነበር Van de Loo, (1991፡41) ያስረዳል፡፡ ይህ የገዳ የስልጣን ሽግግር እራሱን የቻለ ሃይማኖታዊ ከበራዎች አሉት፡፡ ነገር ግን የአጥኚው ትኩረት በቃሉ ተቋም ላይ ስለሚያጠነጥን ከገዳዎች ስልጣን ሽግግር በኋላ በቃሉ ስለሚከናወነው የስልጣን ማጽደቁ ሃይማኖታዊ ከበራና ፋይዳው ላይ በጥልቀት ተፈትሿል፡፡ ስለዚህ ስለገዳ የስልጣን ሽግግር ሂደቶችን በየራሳቸው መንፈሳዊ አረዳ የሚያደርጉት በዝርዝር አልተመለከትኩም፡፡ ምክንያቱም ከጥናቱ ትኩረት አኳያ በዋናነት የሚመለከተው በሚኤ ቦኮ የሚደረገውንና በቃሉ ተቋም የሚከናወነውን የማጽደቅ ከበራ ስለሆነ ነው፡፡

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ሁለት ዓይነት የገዳ ስልጣን እንዳሉ በ4.1.1. ስር ተገልጿል፡፡ ይኸውም፡- በአሳብዱ ኮንፌድረሲ ስር የሚገኙ የሀሎና ዌስቱ ገዳ የስልጣን ሽግግራቸው የዘር ሀረግን ተከትሎ ከአባት ወደ ልጅ ሲሆን፣ አባትዬው እስከ እልፈተ-ሕይወቱ በስልጣኑ ያገለግላል፡፡ ከዚያን በኋላ ከልጆቹ ውስጥ ተመርጦ ይሾምና ጎሳው ስጦታዎችን በመያዝና ወደቃሉ በመውሰድ ስልጣኑ እንዲጸድቅ ያስደርጋሉ፡፡

ቀደም ሲል በጥናቱ ወሰን ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጥናት በዝርዝር የተመለከተው በየስምንት ዓመቱ በዴሞክራሲያው መንገድ የስልጣን ሽግግር በሚያደርጉት የኡራጋ፣ የሆኩና የማቲ ኮንፌድረሲዎች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ገዳዎች ከየተቋሚቸው በመነሳት ለብዙ ወራት ከመማክርት አባላቶቻቸውና ታዳሚዎች ጋር በመሆን ወደ ሚኤ ቦኮ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ሚኤ ቦኮ

(Me'ee Bokkoo) በጉጂ አካባቢ ከሚገኙ ባህላዊና ፖለቲካዊ ክበራዎች ከሚካሄዱባቸው ቦታዎች አንዱ ነው። ከጉጂ ኦሮሞ ገዳ መደብ ውስጥ ራባ (Raaba)፣ ዶሪ (Doorii) እና ገዳ (Gadaa) እርከን ላይ የሚገኙት በየስንምት ዓመቱ የገዳ ስልጣን የሚረካከቡበት መንፈሳዊ ቦታ ነው። ታዲያ እዚህ ቦታ ከመድረሳቸው በፊት እድምተኞቹ በመስመራቸው ላይ በሚገኙ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ክበራዎች በሚከናወኑባቸው ቦታዎች እርድ እየፈፀሙ፣ መስዋዕት እያቀረቡ፣ እግዚአብሔርን እየተለማመኑ፣ ህዝባቸውን፣ ከብቶቻቸውንና ምድሯን እየመረቁ ይጓዛሉ። በጉዞው መስመር ላይ የሚገኙ ምዕመኑም በየቦታው ለታዳሚዎቹ የሚሆን ምግብና የሚጠጡትን ወተት ከየቤታቸው በማምጣት፣ ለመስዋዕት የሚሆኑ ከብቶችንም በማዘጋጀት ይጠባበቃሉ። እዚያም ሲደርሱ ያስተናግዷቸዋል። ሚኤ ቦኮ እንደደረሱ የአካባቢው ማህበረሰብ ለእድምተኞቹ ማረፊያ ‹ቃቻ› ይሰራሉ። በዚህ ቦታ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ይፈጸምባቸዋል ተብሎ የሚያምኑባቸው "ሚኤ" የሚባሉ ዛፎች (Muka woyyuu) ስር ይገናኛሉ።




ፎቶ፡- 10 እና 11 በሚኤ ቦኮ የተሰሩት ጊዚያዊ ማረፊያ (ቃቻ) በከፊል የሚያሳዩ

በመቀጠል ከነዚህ የገዳ መደቦች ሰባት ሰባት ሰዎች ይወከላሉ። ይኸውም፡- ከኡራጋ ገዳ መደብ ውስጥ ከራባ ሰባት፣ ከዶሪ ሰባት እንዲሁም ከገዳ መደብ ሰባት በድምሩ ሃያ አንድ ተወካዮች ይዘጋጃሉ። ከተቀሩትም ሁለቱ ገዳዎች ውስጥ እንዲሁ ሃያ አንድ፣ ሃያ አንድ ተወካዮች በድምሩ ወደ ስልሳ ሦስት የሚሆኑ ተወካዮች ለጉዞው ይዘጋጃሉ። የተቀሩት በሚኤ ቦኮ ከትመው ይጠባበቃሉ። ከአዲሶቹ ገዳዎች ጋር በአባቃሉ ስልጣናቸውን ለማጽደቅ፣ ምርቃትና ክርቤ (qunbii) ለመቀበል፤ ስጦታዎችን ይዘው ቃሉ ወደሚኖርበት ስፍራ (galma qaalluu)፤

ወደ ቆቲ መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ጉዞ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የጉቱ (guttuu) ጉዞ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ተምሳሌትነቱም የመሞላት ጉዞ፤ የመባረክ ጉዞ መሆኑን ነው፡፡ (ጎባና ቶቴ፣ አባያ ወረዳ፣ ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ ገዳ ዋቆ ዱቤ፣ 9/6/2008 ዓ.ም. የኡራጋ አባገዳ የነበሩ)

ይህን መንፈሳዊ ጉዞ ቀደም ሲል በማቲ፣ ሆኩና ኡራጋ ገዳዎች ቡድን እንዴት እንደነበር Van de Loo, (1991፡53-54) ባጭሩ ሲያስረዳ፡- እነዚህ ከተለያየ አቅጣጫ የተነሱት የገዳዎች ቡድን የተለያዩ ሀገራትን አቋርጠው፤ በመጨረሻ በሀራ ቃሎ (Hara qalloo) አካባቢ በሚገኙ መስኮች ላይ ይገናኛሉ፡፡ ከሀራ ቃሎ ሦስቱም ቡድን ወደ ድባ (Dibba)፣ ቦሬ ጎሮ፣ ሀሮ ጋርቤ (ጋርቢቾ)፣ ዳማ፣ ብርብርሳ፣ እያሉ ዲላ ይደርሳሉ፡፡ ከዚያ ወደ ወናጎ፣ በመጨረሻም ወደ ቆቲ፤ የአላብዱ ቃሉ ገልማ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡

ይህን ወደ ቃሉ ተቋም የሚደረገውን የጉቱ ጉዞ በሌሎች የኦሮሞ አካባቢዎች የሙዳ ጉዞ በመባል ይታወቃል፡፡ ቃሉን አባ ሙዳ ይሉታል፡፡ ከበራውን ደግሞ የሙዳ ከበራ (sirna muuda) ይባላል፡፡ አባገዳ ከተመረጡ በኋላ ወደ አባሙዳ ወይም ቃሉ ዘንድ ገፀ-በረከት ይዘው ይሄዳሉ፡፡

ይህ መንፈሳዊ ጉዞ የሚታቀደው በየስምንት ዓመቱ አንዴ ወደ መጨረሻው አካባቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ጉዞው የሚያበቃውና አዲሶቹ ገዳዎች ስራቸውን የሚጀምሩት ደግሞ ወደ እራሳቸው ተቋም ከተመለሱ በሁለት ወራት አካባቢ እንደሚሆን መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡

የጉጂ ማህበረሰብ ይህን መንፈሳዊ ጉዞ በዋናነት እንደ ማህበረሰባዊ ግንኙነት ማጠናከሪያ፣ ስለእራሳቸውና ስለአለም አፈጣጠር የሚረዱበት፣ እንደ ሃይማኖታዊ ከበራ የሚያዩበት፣ ቡራኬ (ምርቃት) ለመቀበል እና ህብረት ለመፍጠር እንደሚገለገሉበት ይገልጻሉ፡፡

የጉጂ ኦሮሞ አባገዳዎች ቡራኬ ለማግኘትና ስልጣናቸውን ለማጸደቅ ወደ ቃሉ ገልማ የሚያደርጉት የጉቱ ጉዞን ጥንተ-መጥነቱን በሚታቸው ውስጥ ሲያረጋግጡም ይታያሉ፡፡ ይኸውም፡-

> የቃሉ ቅምቅም አያት ከሰማይ ወረደ፡፡ ድሮ አንድ የጉጂ ሰው ነበር፡፡ አንድ በጣም ግዙፍ የሆነ ሰው አየ፡፡ ያ ሰው ሰውነቱ በረጃጅም ጸጉር የተሸፈነ ነበር፡፡ ይህ ሰው ዙሪያውን ቸል ብሎ ይመለከት ጀመር፡፡ እንዲረዱትም ጠየቀ፡፡ ቀደም

ብሎ ያየው ሰው ምንም ሊረዳው አልቻለም። ከዚያም ወደ ባህል አዋቂ (cidheessa) ሄደ። ያም የባህል አዋቂ ሰውዬም አሰብ አድርጎ ሰውነቱን ሸፍኖት የነበረውን ጸጉር ላጨለት። በመቀጠል ትንሽ ልብስ ብጤ አምጥቶ አለበሰው። ከዚያም ያን የባህል አዋቂ ሰው ባረከው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ የተመረቀው ሰው የጉጂ የመጀመሪያ አባገዳ ሆነ። የሚል ነው

ከዚህ ሚት የምንረዳው የመጀመሪያው ቃሉ ከሰማይ መውረዱንና በወቅቱ መላ ሰውነቱ በጸጉር የተሸፈነ ስለነበር ሃይማኖታዊና ባህላዊ ዕውቀት ያለው ሰው እንደረዳውና በምላሹም እሱን እንደባረከው ነው። በመጨረሻም ይህ የተባረከው ሰው የጉጂ የመጀመሪያ አባገዳ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው። ይህን ከማህበረሰብ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ስናየው ቃሉ ሰው እንደሆነና ነገር ግን በተክለሰውነቱ ደግሞ ከሰው ገዘፍ የሚልና መላ ሰውነቱ በጸጉር የተሸፈነ አድርጎ መሳላቸው ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ ሀሳብ አኳያ ሰው ሆኖ ነገር ግን ከሰው ለየት ያለ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ምግባሩንም በተመለከተ በፊት የተወሰነ ባህላዊ ዕውቀት ያለውን ሰው በመመረቅ የተሻለ መንፈሳዊና የማስተዳደር ኃይል እንዳላበሰው ያሳየናል። ይኸውም መጀመሪያ በማህበረሰቡ ውስጥ በተወሰነ ደረጃ የነበረውን አቅም ወደ ጎላን የመምራትና ማስተዳደር ማለትም ገዳ ደረጃ እንዳሳደገው ነው።

ሌላው ከዚህ ሚት የምንረዳው ቃሉ ገዳዎችን መመረቅና መንፈሳዊ ኃይል እንደሚያላብስና ገዳ ደግሞ ይህን ጸጋ ለማግኘት ለቃሉ ስጦታ በማቅረብ መባረክ እንዳለበት አመላካች ነው። በመሆኑም አባገዳዎች ከቃሉ ገልማ (ቆቲ) የሚሄዱት ቡራኬ (ምርቃት) ለመቀበልና ለስልጣናቸውም እውቅና እንዲሰጣቸው በማሰብ ነው። ይህ ምርቃት ደግሞ አባገዳዎቹ ከፖለቲካዊ የአስተዳደር ስልጣን በተጨማሪ ሃይማኖታዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ መንፈሳዊ ኃይል ያላብሳቸዋል ተብሎ ስለምታመንም ጭምር ነው። ስለዚህ የአባገዳና የአስተዳዳሪዎቹ ጉባኤ መደብ ላይ ያሉትን ቡድኖች ፀጋ እንዲላበሱ የሚደረገው የገዳ ስልጣን በሚጸድቅበት ወቅት በቃሉ አማካይነት ከርቤ (ቁንቢ) በማስነከስ እንደሆነ ይታመናል።



ፎቶ፡-12 የቀድሞ የኡራጋ ገዳ የነበሩ አጋ ጨንጣኖና የመማክርት አባላትን የሚያሳይ ፎቶ

ክርቤ (ቁንቢ) ከዋቄፋና ሃይማኖት አኳያ የተቀደሰ ቁስ ነው፤ እውነት ያናግራል ተብሎ ይታመናል፡፡ እንደእምነቱ ከአባሙዳ ክርቤ ተቀብሎ የበላ ሰው፤ የእግዚኣብሔር ህግ፣ የጥንቱን የኦሮሞ ስርዓት ማዛመም፣ ሀጢያት መስራት፣ ውሸት መናገር የለበትም፡፡ ህብረተሰቡንም በእውነተኛ ህግ እንዲያስተዳድር በቃሉ ምክር ይለገሳል፡፡ በሌላ መልኩ ይህ የአባ ሙዳ ምክር ደግሞ አባቃሉ በኦሮሞ ፖለቲካ ውስጥ ያለውን ድርሻ የሚያመላክት ነው፡፡

ከዚህ የተነሳ ገዳዎች ቡራኬ ለመቀበል ከነመማክርት አባላቶቻቸው ጋር ሆነው ለቃሉ የሚሆኑ ብዙ ከብቶችን በስጦታ መልክ ይወስዱ ነበር፡፡ እንደ Van de Loo (1991) ገለጻ ከሆነ በሚቀጥለው ቀን ዘጠና ዘጠኝ ኮርማዎችና ጊደሮች (kormaafi raada) እንዲሁም ዘጠና ዘጠኝ የበግ ጠቦቶች (korbeessaafi goromtii) ለቃሉ ይሰጡታል፡፡ የበግ ወጠጤዎቹንና ኮርማዎቹን በቀጭኑ በተተለተለ ቆዳ በዛጎል አስውቦ እንደታሰሩ እንደሚሰጡ ያስረዳል፡፡ ከዚያም በቅድሚያ ካሉዎቹ ከብቶቹን ይቀበላቸዋል፡፡ በመቀጠል ወደ ሰፌ መስክ እንዲሰማሩ ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ውክልናቸውን (ኃላፊነታቸውን) የመወጣት ልምምድ፤ ድንገተኛ የማጥቃትና መከላከል ተምሳሌት የሆነውን ክዋኔ በቃሉ ገልማ አካባቢ ያካሂዳሉ፡፡ ይኸውም፡- የእነሱን ስኬታማነት ለማረጋገጥ ከአላብዱ ጉጂ ወገን የሆኑት በአንድ ወገን ሆነው አንድ ላም ለመውሰድ ይጣጣራሉ፡፡ እነሱ ደግሞ እንዳይወሰድባቸው በጦር ለማጥቃት ሲነሱ፤ የአላብዱ ጉጂዎች ደግሞ ይከላከላሉ፡፡ ከዚያ በዚህ ሂደት ውስጥ የተወሰኑ ሰዎች ይቆስላሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ሁለቱም

ወገን ደንገጥ ይላሉ፤ ከዚያ ግጭቱን ቀሰ ብለው ያረግባሉ፡፡ በመቀጠል ሁለቱም ወገን አንድ በግ በማንሳት ከአጥሩ ላይ ከፍ አድርገው ወደ ውስጥ ይወረውራሉ፡፡ ይህም ክዋኔ በላምቱ ምክንያት የተደረገው ግጭት ተምሳሌትነቱ እዚያ የተሳተፉት አካላት የኦሮሞን ህዝብ የጋራ መነሻ (Origin)፣ እርስ በርሳቸው በሰላም የሚኖሩ፣ በክብት የተነሳ የሚያደርጉትን ግጭትና ክርክር መርሳታቸውን የሚያመላክት እንደሆነ ያስረዳል፡፡

ነገር ግን ከመረጃ አቀባዮቼ እንደተረዳሁት ከሆነ የከብቶቹም ብዛት ሆነ ክዋኔው ከዚህ በተወሰነ ደረጃ የተለየ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ይኸውም፡- የኡራጋው ገዳ ሰላሳ ሦስት ከብቶች፣ የማቲና የሆኩም እንዲሁ ሰላሳ ሦስት፣ ሰላሳ ሦስት በድምሩ ዘጠና ዘጠኝ ኮርማዎችና ጊደሮች (kormaafi raada) እና አንድ በግ አዳማ የሚባልበት ቦታ ላይ ይሰባሰባል፡፡ ከበጉ ጋር መቶ ይሆናሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ የቦታው መጠሪያ አዳማ ድባ (adaamma dhibbaa) ይባላል፡፡ ከዚያን በኋላ እነዚያን ዘጠና ዘጠኝ ከብቶችና አንድ የስጦታውን ይሁንታ መግለጫ በግ (hoolaa batalaa) በቀጭኑ የተተለተሉ ቆዳዎች በዛጎል አጊጤው የበጉን መላ ሰውነቱን አስውበው በመንዳት ወደ ገልማው ይጓዛሉ፡፡ የአላብዱ ህዝብ በቃሉ ተቋም ተሰባስበው ለምርቃትና ስልጣነ-ሢመታቸውን ለማጽደቅ የመጡት አባገዳዎች ካመጡት የስጦታ ከብቶች ምንም አይወስዱም፡፡ ነገር ግን ወደ ቃሉ የከብቶች ማቆያ መስክ ቀድሞ ለማስገባት የሚያደረጉት ፉክክር ማለትም የኔ ይቅደም፤ የእኔ ይቀደም ሲሉ፣ አላብዱዎች ደግሞ የሁሉንም ወደ ኋላ በመመለስ ሂደት የሚፈጠር ቀለል ያለ ግጭት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ያን ድርጊት የሚያከናውኑት ረጃጅም ልምጮች (baabbe) በመቁረጥ በፀሐይ ላይ ያሞቁታል፡፡ በሌላ በኩል የገዳዎቹም ወገን እንዲሁ ይዘጋጃሉ፡፡ ከዚህ ባለፈ ጦር ይዘው ግጭት አይፈጥሩም፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚያስቀምጡት በቃሉ ተቋም የሰው ደም መፍሰስ እንደሌለበት ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ክዋኔ መካከል ላይ ከቃሉ መማክርት አባላት ሄደው ያንን በዛጎል ያጌጠውን በግ ይይዛሉ፡፡ የገዳዎቹም ቡድን ‹‹የቃሉ ወገን ማርኮናል፡፡›› (worri Qaalluu boji'eera.) በማለት አሸናፊነታቸውን ያረጋግጡላቸውና ጊዜያዊ ግጭቱ እልባት ያገኛል፡፡ ከዚያን በኋላ ገዳዎቹም ከነስጦታቸው ወደ ግቢው እንዲዘልቁ ይደረጋል፡፡ ወዲያውኑ አባ ገዳዎቹም በጓሮ በኩል ዞረው ዘጠኝ ጊዜ ደጋግመው አባቃሉን እጅ ይነሳሉ፡፡ ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Abba Qalluu Yooyyaa! (9x) | ጤና ይስጥልኝ አባቃሉ (9x) |
| Haadhabola Yooyyaa!! | ጤና ይስጥልኝ የእኛ እናት |

worri kun worra maaliiti? እዚህ ቤቶች፤ ምን የሆኑ ሰዎች ናቸው?

(gidduutti jedhu) (በየጣልቃው)

bultanee namaa kan hin qabne; ለሰው ሰላምታ ምላሽ የማይሰጡ።

nama jalaan kan hin owwaatne. ሲጠሯቸው አቤት የማይሉ። እያሉ በተደጋጋሚ ዘጠኝ ጊዜ ብለው በአስረኛው ላይ አባቃሉ ጤና ይስጥልኝ (Yooyyaa!) በሚሉበት ጊዜ ቃሉም ጤና ይስጥልኝ (Yooyyaa!) በማለት ምላሽ ይሰጣሉ። በመቀጠል የአባ ገዳዎቹ ቡድን፡-

Ee! Qaalluu keenya nuuf jiraadhu, አዎ! የእኛ አባቃሉ ኑርልን፣

Qaalluu keenya nuuf naga'l, የእኛ አባቃሉ ሰላም ሁንልን፣

Qaalluu keenya gabadhu. የእኛ አባቃሉ ይመችህ። በማለት ለሰላምታቸው ምላሽ በመስጠቱ ደስታቸውንና መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ።

ከዚያም በፊት ለፊት ዞረው ያመጡትን ስጦታ ማለትም፡- ዘጠና ዘጠኝ ኮርማዎችና ጊደሮች፣ እንዲሁም ለቡና ቃላ የሚሆን ድፍን ደረቅ ቡና፣ ማርና በዛጎል ያጌጠውን በግ ይሰጣሉ። አባቃሉ ያንን በግ ወዲያውኑ ያርደዋል። (አባገዳ ጋምቤላ በርሶ፣ የሆኩ አባገዳ የነበሩ፣ በ8/6/2008፣ ሚኤ ቦኮ ላይ)

ገዳዎቹ እኚህን ስጦታዎች ይዘው፤ እነሱ በጓሮ በኩል አልፈው ሰላምታ መጠየቃቸው፣ እንዲሁም ከአንዴም፤ ዘጠኝ ጊዜ «ዮያ አባቃሉ» ሲሉ ዝም ብሎ በአስረኛው ምላሹን «ዮያ» ማለቱ ከፍቻዊ አውድ አኳያ የቃሉን ክቡርነት አግዝፎ ማሳያ ናቸው። በሌላ በኩል ካየነው ከተቋማዊ አውድ አኳያ ደግሞ በባህሉ መሰረት የሰው ቤት የሄደ ሰው ሰላምታ የሚያቀርበው ከፊት ለፊት በኩል ነው። ነገር ግን ከኋላ በኩል ማለፋቸው ለተቋሙና ለተቋሙ መሪ ካላቸው አክብሮት፣ ያለእሱ ፍቃድ ከፊቱ መቆም አለመቻላቸውን የሚገልጹበት ክዋኔ መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ማህበራዊ መሰረቱን የተመለከትን እንደሆነ እነሱ ከቃሉ ቁንቢ በመቀበል፤ ተመርቀው ስልጣናቸው የሚጸድቅላቸው አካላት ሲሆኑ፤ ቃሉ ደግሞ የማጽደቅና ቡራኬ የመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑን ያሳያል።

በሌላ በኩል ዘጠኝ ጊዜ ዮያ «Abba Qalluu Yooyyaa!» ማለታቸውን አረጋግጦ በአስረኛው ምላሽ መስጠቱ ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ የሦስቱም አባገዳዎች ሦስት፣ ሦስት የገዳ ክፍሎች ማለትም የገዳ፣ የዶሪና የራባ አባላት ተሟልተው ዘጠኙም መምጣታቸውን ማረጋገጫ ሲሆንና የመጨረሻዋ ዮያ ደግሞ በአንድነት ሰላም ማለቱን ያመላክታል።

ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ ምላሽ መስጠት (ዮያ ማለት) እንደ እሺታ ስለሚቆጠር ከፊት ለፊት አልፈው ስጦታቸውን ያበረክታሉ፡፡ በዚያን ጊዜ ቃሉ በዛጎል አጊጦ የመጣውን በግ ወዲያ ከገልማው ፊት ለፊት ያርደዋል፡፡ ይህን ድርጊት ከግለሰባዊ አውድ አኳያ ቃሉ ስጦታዎቹን በፀጋ ለመቀበሉ እንደማሳያነት ያገለግላል፡፡

ነገር ግን ከመጡት እጬ ገዳዎች (አባ ሙርቲዎች) ውስጥ ያለህዝቡ ፍላጎት የተመረጠና ቀደም ብሎ ለቃሉ ችግሩ ተገልጾለት እያለ እንዲያስተካክሉ ተነግሯቸው በምንቸገረኝነት የመጣ ካለ፤ ቃሉ በአስረኛው ጊዜም «ዮያ» በማለት ሰላምታውን ምላሽ አይሰጥም፡፡ ሰላምታውን ካልመለሰ ደግሞ ስጦታቸውን አይቀበልም ማለት ነው፡፡ ስጦታውን ተቀብሎ፤ ያን የይሁንታ መግለጫ በግ (hoola batalaa) አያርድም፡፡ ሁሉም ክዋኔ እዚህ ላይ ይቆማል፡፡ ይህን ስርዓት ካልፈጸሙ ደግሞ ወደ ጎሳቸው ሲወርዱ ተቀባይነት አያገኙም፡፡ ስለዚህ ቀድሞውኑ ተዘጋጅተውና አሟልተው ይሄዳሉ፡፡ በዚህ መልኩ የቃሉ ተቋም የገዳን ስልጣን ሽግግር ዴሞክራሲያዊ አካሄዱን ያስጠብቃል፡፡ ይህ ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ የቃሉን የገዳ ስልጣን ማጽደቅ ፖለቲካዊ ፋይዳን ያሳየናል፡፡

በሌላ መልኩ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ጎዶሎ ቁጥሮች የመጥፎ ዕድል እና የመጥፎ ክስተቶች ተምሳሌት እንደሆኑ ይታመናሉ፡፡ በተለይም ዘጠኝ ቁጥርን ከጣረሞት (ghost)፣ ሕመም (illness) እና ሞት (death) ከመሳሰሉ አስጊ ክስተቶች ጋር ያያይዙታል (Taddesse, 2013፡65)፡፡

ለዚህም እንደ መገለጫ የሚያገለግሉ የተለያዩ የፎክሎር ቅንጣቶች እንዳሉ ተገልጸዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ስለዘጠኝ ቁጥር የሚነገር እንቆቅልሽ አንዱ ነው፡፡ ይኸውም፡- ልጆች ቁጥር ነክ የሆነውን «Tokko maali?» የሚለውን እንቆቅልሽ በሚጫወቱበት ወቅት እራሱን የቻለ የአጠያየቅና አመላለስ ስርዓት አለው፡፡ በጫወታው ህግ መሰረት አንድ ቁጥር በሚጠየቅበት ጊዜ ከዚያ ቁጥር ጋር ቀደም ሲል ከሚታወቁ ነገሮች፣ ክስተቶችና ሁነቶች ጋር በማያያዝ «ይሄማ እንትን ነው» በሚል ስሜት ይመልሳሉ፡፡ ለምሳሌ

| ጠያቂው | መላሹ |
|---|---|
| Tokko maali? | Tokko quboolee. |
| አንድ ምንድነው? | አንድማ ጣት ናት፡፡ |
| Lamma maali? | Lamma mucha re'ee, tokko quboolee. |
| ሁለት ምንድነው? | ሁለትማ የፍዬል ጡት፣ አንድ ጣት ናት፡፡ |
| Sadi maali? | Sadi sunsuma aayya, Lamma mucha re'ee, tokko quboolee... |

| | |
|---|---|
| ሦስት ምንድነው? | ሦስትማ የማዬ ጉልቻ፣ ሁለት የፍዬል ጡት፣አንድ ጣት ናት።... |
| Jahaa maali? | Jahaa jabbii qaraxaa... |
| ስድስት ምንድነው? | ስድስትማ የጥሎሽ/ ስጦታ ጥጆች... |
| Sagali maali? | Sagali lakkofsa ekeraa... (Taddessee, 2013:58-59) |
| ዘጠኝ ምንድነው? | ዘጠኝማ የጣረሞት ቁጥር... በማለት እስከ መቶ ቁጥሮች |

ለሚጠየቁት ከባህሉ፣ ከተፈጥሮው፣ ከተለያዩ ክስተቶችና ሁነቶች ጋር በማዛመድ በእንቆቅልሽ ብዙ ነገሮችን እንደሚማሩ ለመረዳት ችያለሁ። ነገር ግን ዋናው ሀሳብ በዚህ እንቆቅልሽ ውስጥ የዘጠኝ ቁጥር ከጣረሞት ጋር መያያዙ ምናልባትም ቃሉ ዘጠኝ ጊዜ አባቃሉ ጤና ይስጥልኝ (Yooyyaa!) ሲባሉ ዝምታቸው ከዚህ የመነጨ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም የቀደምት አባቶች ጣረሞት ከአከባቢው እንደማይርቅ ስለሚታመን ምናልባትም ይህ ጥሪ የገዳዎቹ ነው ወይም የጣረሞቱ ነው በማለት በማጣራት በአስረኛው ጤና ይስጥልኝ በማለት የሚመልሰው።

ዘጠኝ ቁጥር በሌላ በኩል ከዘጠነኛ ልጅ እርግዝናና ወልድ ጋር ተያይዞ በቤተሰብ ደረጃ ይዞ ይመጣል ተብሎ የሚታመን መጥፎ ዕድልና ስጋት፤ እንዲሁም ይህን ስጋት ለመቀነስና ለማስቀረት የሚደረገውን ከበራም ተገልጿል (ዝኒ ከማሁ: 60)።

ከዚህ በተጨማሪ «Gaalli Sagali bule, Kudhan bulu hindadhabu.» የሚል ምሳሌያዊ አነጋገርም አለ። ትርጉሙም፡- «ዘጠኝ ቀን ያደረ ግመል፣ አስረኛው ማደር አያቅተውም።» እንደማለት ነው። ከትንተናው ለመረዳት እንደተቻለው፤ አንድ ግመል ዘጠኝ ቀን ሙሉ ያለውሃ ካደረ፤ አስረኛውንም ሊያድር እንደሚችል ነው። ይኸውም፡- ዘጠኝ ጎዶሎ ነው፤ የመጥፎ ዕድል፣ የሞት ተምሳሌት ነው። ስለዚህ ያን መጥፎ ቀን ካለፈ ምንም አይሆንም እንደማለት ነው። በተምሳሌትነቱ ለማስተላለፍ የተፈለገው የትዕግስትን አስፈላጊነት ለማሰረዳት ነው።
ሌላው ከዘጠኝ ቁጥር ጋር ተያይዞ የሚነገር ምሳሌያዊ አነጋገር «Haluun dhiira wagaaa sagalti bati.» የሚል ነው። ትርጉሙም፡- «ወንድ ልጅ ቂሙን በዘጠኝ ዓመትም ይወጣል።» እንደማለት ነው። ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር አንድ ዘመዱ በጠላት የተገደለበት ሰው፤ የሟቹን ደም ዘጠኝ ዓመት ቢሞላውም እንኳን እንደሚበቀል የሚገልጽ ነው ((ዝኒ ከማሁ)።

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተገለጹትና ሌሎችም ከዘጠኝ ቁጥር ጋር በመጥፎ ዕድልነት የተያያዙት ተምሳሌታዊ መገለጫዎች ባንድ ላይ ተዳምረው ቃሉን ምናልባትም እስከ ዘጠነኛው ጥሪ ዝም ብለው በአስረኛው ላይ አባቃሉ ‹ዮያ› በሚሉበት ጊዜ ቃሉም ‹ዮያ› በማለት ምላሽ እንዲሰጡ ምክንያት ሊሆናቸው ይችላል።

በመጨረሻም ይህ ክዋኔ በአግባቡ ከተከናወነ በኋላ በቃሉ ገልማ ቀድሞ ከተጣለው ጠጅ ካሎዎቹ በቅል (duloo) እየቀዱ ያቀርባሉ። ገዳ እንኩ፣ ዩባ እንኩ፣ እያሉ በየደረጃቸው ያን ጠጅ ይሰጧቸዋል። ገዳዎቹ ያንን ጠጅ እየተጎነጩ እንትፍታ (biifee) እያሉ፡-

| | |
|---|---|
| Qaalluun nu'uu naga'i | ቃሉ ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| Gadaan nu'uu naga'i | ገዳ ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| mangudoon nu'uu naga'i | አዛውንቶቻችን ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| biyyi nu'uu naga'i | ሀገራችን ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| ilmi nu'uu naga'i | ወንዶች ልጆቻችን ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| durbi nu'uu naga'i | ሴቶች ልጆቻችን ለእኛ ሰላም ይሁን፣ |
| Galmi nu'uu naga'i | ገልማው ለእኛ ሰላም ይሁን በማለት ይመርቃሉ። |

ከዚያም አባቃሉ አንተም ጠጣና ለእኛም ፍቀድልን በማለት ይጠይቃሉ። ቃሉ ከቦካው ሲቀምስ ወዲያውኑ ያን በቅል እየተሞላ የተሰጣቸውን ጠጅ እየጠጡና እየጨፈሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ማረፊያቸው ይሄዳሉ። በማግስቱ አባቃሉ ደግሞ ለአባገዳዎቹ በየስማቸው የሰቡ ሰንጋዎችን ነድቶ ይሰጣቸዋል። እነኛን ሰንጋዎች በየቦታው ያርዱና ስጋውን ብቻ በመለየት ይቀቅላሉ፤ ከዚያም ቀኑን ሙሉ ይመገቡታል። በመጨረሻም ባህላዊ ጭፈራ ይጨፈራል። (ገዳ ጋምቤላ በርሶ፣ በ9/6/2008 ዓ.ም. ሚኤ ቦኮ፤አቶ አባባ ቶቴ፣ 22/7/2008 ዓ.ም. በወናጎ ወረዳ፣ የቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

በመቀጠል ከአባቃሉ ቂንቢ ለመቀበል ከማረፊያ ቦታቸው ወደገልማው ሲመጡ አባገዳዎቹ በጋራ ቃሉን የሚጠይቁት (የሚለምኑት) ነገር አለ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| bara nuu beeki, | ዓመቱን እወቅልን፣ |
| ji'a nuu beeki, | ወራቱን እወቅልን፣ |
| jila nuu beeki, | የሃይማኖታዊ ክበራዎችን እወቅልን፣ |
| kooba nuu beeki, | የመስዋዕት ማቅረቢያ ተራራውን እወቅልን |

በማለት ይጠይቃሉ። (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ የሆኑት፣ በ25/6/2008 ዓ.ም.)

ከዚያም አባቃሉ ስጦታውን በመረከብ ይመርቃል፤ የሚቀጥለውን ፀሎትም ያደርሳል።

| | |
|---|---|
| Naga'e abbaa Gadoo | ሰላም ሁን አባገዳ፣ |
| Ee dhugaa jilaa hin wollaaliin, | አዎ! የሃይማኖታዊ ክበራውን መሰረቱን አትርሳ፣ |
| ji'a hin wollaaliin, | ወራቱን አትርሳ፣ |
| ayyaan hin wollaaliin, | የእግዚአብሔርን መንፈስ አትርሳ፣ |

| | |
|---|---|
| bantittiin kan bantichaati, | ልጃገረድ ላላገባው ነች፣ |
| ardaan Gujii micciirraa hin qabu, | የጉጂ ህዝብ ተንኮል የለውም፣ |
| ilmi Gujii micciirraa hin qabu, | የጉጂ ልጅ ተንኮል የለበትም፣ |
| bantittiin micciirraa hin qabud, | ልጃገረድ(ድንግል) ተንኮል የለባትም፣ |
| Gujiin Gujii, Gujiin wal-hin ajjeessuu, | ጉጂ ጉጂ ነው፤ ጉጂ እርስ በርሱ አይገዳደልም፣ |
| Wal-hin ajjeessinaa, | እርስ በርስ አትገዳደሉ፣ |
| Oboleettii teessan hin fuudhinaa, | የራሳችሁን እህት አታግቡ፣ |
| Dhugaan waan duri jirati, | እውነት ጥንትም ያለ ነው፣ |
| danuu danuu beeka, | ያጋጣሚ ክስተት ያጋጣሚ ነው እወቁ፣ |
| isii wonni Gujii, | ይህ ነው የጉጂ ወግ፣ |
| ifii dhiigaan baddani, | እጃችሁ በደም ይበላሻል፣ |
| Gujiin wal hin ajjeessitn, | ጉጂ እርስ በርስ አይገዳደልም፣ |
| danuu gaafa wal-ajjeesse, | ባጋጣሚ ከተገዳደለ፣ |
| dhugaa sani dhaggi...... | ያንን እውነት አጣራ(በአግባቡ እየው) |
| Jedhee gorsa Gadaa, | በማለት ገዳ ይመክራል፣ |
| Jedhee gorsa Qaalluun, | በማለት ቃሉ ይመክራል፣ |
| Jedhee qooda, | በማለት ይከፋፍላል፣ |
| Qooda Gadaa gorsasaan qooda, | የገዳን የስራ ድርሻ በምክር ይከፍላል፣ |
| Raabaatti hima, | ለራባ ይነግራል፣ |
| Jadhaabaatti hima, | ለጃልዳባ ይነግራል፣ |
| Waamuratti hima, | ለሙራ ይነግራል፣ |
| Murtiitti hima, | ለሙርቲ ይነግራል |
| Akkana jedhee gorsa. | እንዲህ ብሎ ይመክራል። (አቶ ሞኮና |

ናጋኦ፣ በቆቲ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ የተወሰደ)

ይህ በምርቃት መልክ የሚተላለፈው ማህበረሰባዊ ዕውቀት ቀድሞ በሚት መልክ በሳብጀክትቭዚም ኢፒስቲሞሎጂ አተያይ ያደራጁት ነው። ይኸውም ጉጂ ጉጂን አይገድልም፤ ነገር ግን በስህተት ከተከሰተ ደግሞ ምን ይደረግ ለሚለው፤ የጎንዶሮ ከበራን ማህበረሰባዊ

ዕውቀት በማዋቀርና ወደቃሉ ተቋም ከገባ በኋላ ልክ እንደ ህግ፣ ልማድና ባህል ሆኖ መልሶ በቃሉና ገዳ አማካይነት ማህበረሰቡ እንዴት መተዳደር እንዳለባቸው ተመልሶ ወደታችኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሚወርድ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ለገዳዎቹም በምን ላስተዳድር፣ ከእነማን ጋር ላስተዳድር የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ ከማህበረሰቡ በፈለቁና በቃሉ ተቋም አማካይነት ተመልሰው ለማህበረሰቡ በምርቃትና ምክር መልክ እንደ ህግ፣ ደንብና ልማድ የሚያገለግሉ ዕውቀቶች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ሌላው ከማህበረሰቡ በኩል ደግሞ እንዴት ተጠባብቀው፣ ተከባብረውና ተደማምጠው መኖር እንዳለባቸውም ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ይህን ሂደት በሌላ በኩል ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ ሃይማኖታዊ ከበራው ያለውን ማህበረሰባዊ ፋይዳ ያሳያል፡፡

ሌላው በማግስቱ እንደታላቅነትና ተከታይነታቸው በቅድሚያ የኡራጋ ገዳ ከመማክርት አባላቱ ጋር፣ ቀጥሎ የማቲ ገዳና እንዲሁም በስተመጨረሻ የሆኩ ገዳ ተራ በተራ ከገልማው ፊት ለፊት ካለው ሂሮ መነሻ በማድረግ እስከ ገልማ ውስጥ አንድ በአንድ ተቀምጠው በመንፏቀቅ ይሄዱና ከቃሉ እጅ በአፋቸው ከርቤ (qumbii) ይቀበላሉ፡፡ ይህ ስርዓት ከተጀመረበት ሰዓት አንስቶ ለእያንዳንዱ እስከሚዳረስ ድረስ መተኛት አይቻልም፡፡ ከርቤውን የቀመሱትም ምንም ነገር አይናገሩም፤ በተቀመጡበት እስኪነጋ ይጠባበቃሉ፡፡ አባቃሉም ከርቤውን በአንድ እጁ እያቀመሳቸው፣ ከታረደው ከብት በገቡቴ የቀረበውን ደሙ እየነከረ በላያቸው ላይ ግራና ቀኝ እየረጨ፣ ከጠጁ እያቀመሳቸው ይመርቃቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ህዝባቸውን በባህሉና በሃይማኖቱ መሰረት እንዲመሩ፣ ያለአድሎ እንዲያስተዳድሩ ቃለ-መሀላ ያስፈጽማል፡፡

ከርቤውን በአፋቸው ሲቀበሉ ገዳዎቹ በእጃቸው ጋርደው በመውሰድ የተወሰነውን በማስቀረት ሌላውን በተጎነጬት ጠጅ ያወራርዱታል፡፡ አባገዳ ከርቤ (qumbii) ከቀመሰ በኋላ ውሃ እንኳን በራሱ እጅ አይጠጣም፤ ሰው ነው የሚያጠጣው፡፡ ሀዩ የሆነ ሰው ከአጠገቡ ከሌለ በግራ እጁ ወስዶ ይጠጣል፡፡ ማር እንኳን ከቀፎ ውስጥ ሲያወጣ በግራ እጁ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀኝ እጁ ወዩ ነው፡፡ በእጁ ሰው አይመታም፡፡ አይረግምም፡፡ የከፋ ነገር እንኳን ቢገጥመው ቁጡቱን ያራግፋል፤ ያ እንደ እርግማን ይቆጠራል (ገዳ ጋምቤላ በርሶ፣ 9/6/2008 ዓ.ም. የሆኩ አባገዳ የነበሩት፣ ሚኤ ቦኮ ላይ)፡፡

ከርቤው (qumbii) ቀደም ሲል እንደተገለጸው መራር መንፈሳዊ ቁስ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ በቃሉ ተቋም ከሂሮ ስር ጀምሮ በእንፉቅቅ በመሄድ ከቃሉ እጅ ከርቤ መቀበልን ያየን እንደሆነ

ማህበረሰቡ ቀደም ብሎ ያዋቀረው ዕውቀት ነው፡፡ ምክንያቱም ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማህበራዊ ውቅር ነው፡፡ ይህን ዕውቀት ወደ ቃሉ ተቋም በማስገባት ለቃሉ፣ ለተቋሙና ለቁሳዊ ባህሉ ክበሬታና ተቀባይነት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ቃሉ በወንበሩ ላይ ተቀምጦ ሳለ ገዳዎቹ እየተንፏቀቁ መሄዳቸው ቃሉን ማክበር እንዳለባቸውና የአክብሮታቸው መገለጫ አድርገው ያዋቀሩት ዕውቀት ውጤት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይኸውም በሌላ በኩል ቃሉን የእግዚአብሔር መልዕክተኛ አድርገው ስለሚያምኑት፣ ለቃሉ ክበሬታ አሳዩ ማለት በተዘዋዋሪ መንገድ የላከውንም እግዚአብሔርን እንደማክበር ስለሚቆጠር ነው፡፡

በሌላ በኩል ከሚከወንበት አውድ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ ይህ ክበራ የሚከወነው ከተቋማዊ አውድ አኳያ በቃሉ ተቋም ሲሆን፤ ከግለሰባዊ አውድ አኳያ ደግሞ መከወን ያለበት በቃሉ እጅ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ ሰባት ስር እንዳየነው የቦታና የከዋኝ ለውጥ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የከርቤ መራርነት ለእውነት ተምሳሌት ሆኖ ቀርቧል፡፡ እውነት መናገር ከራስ ጋር ያጣላል፤ እውነት መናገር ከቤተሰብ ጋር ያጋጫል፤ እውነት መናገር በጎሳ ደረጃም ጥላቻን ሊያመጣ ይችላል፡፡ እንዲሁም በእውነት መስራት ከመንግስት ጋርም ሊያጋጭ ይችላል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ጫናዎች ተቋቁሞ ማህበረሰቡን በእውነት ማስተዳደር ምንኛ እንደሚከብድና መጨረሻው ደግሞ ያማረ መሆኑን ደግሞ በጠጁ ሲያወራርዱት የሚያሳየው ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው፡፡ በመጨረሻም ይህን ተምሳሌታዊ ክዋኔ ከፈጸሙ በኋላ ስለተቀደሱ ወዩ (woyyuu) ይሆናሉ፡፡

ሌላው ክዋኔ ቃሉ ለመስዋዕት ከታረደው ከብት በገበቴ የቀረበውን ደም እየነከረ በላያቸው ላይ ግራና ቀኝ እየረጨ፣ ከጠጁ እያቀመሳቸው መመረቁ ነው፡፡ እንደ ኦሮሞ የዓለም አተያይ መስዋዕት በሚቀርብበት ወቅት ደሙን ወደ ላይ ሲረጭ ለእግዚአብሔር እንደመስዋዕት ማቅረብ ይቆጠራል፤ በተቃራኒው ደግሞ ደሙ ከተረጨበት ወደታች ሲወርድ እንደእግዚአብሔር ምርቃት ስለሚቆጠር ነው (Hinnant, 1972)፡፡ ይህ ተምሳሌታዊ ክዋኔ ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ስንመለከተው ተመራቂዎቹ በቃሉ ብቻ ሳይሆን፤ በቃሉ አማካይነት በደሙ በእግዚአብሔርም እንደሚመረቁና ምርቃቱንም ወደውስጣቸው የሚያስርጉት በከርቤውና በጠጁ እያወራረዱ መሆኑን ነው፡፡

የመጨረሻውን መስዋዕት ተከትሎ ቃሉ አባገዳዎችንና ህዝቡን ወደሚመለከታቸው የሃይማኖታዊ ከበራ (jila) ቦታ ወይም ወደ ራሳቸው የገዳ ስርዓት የሚከውኑበት ይሸኛቸዋል፡፡ በሽኝቱም ሲመርቃቸው፡-

| | |
|---|---|
| Gadaa murtii nageessi, | የገዳ ውሳኔን ሰላም ያድርገው፣ |
| ardaa nageessi, | ቀዬውን ሰላም ያድርገው፣ |
| Kolbaa nageessi, | ህዝቡን ሰላም ያድርገው፣ |
| Hulaa nageessi, | ደጃፋችንን ሰላም ያድርገው፣ |
| afaan nu beessisi, | አፍ ለአፋ እንድንጣጣም ያድርገን፣ (እንድንግባባ አድርገን) |
| Ardaa nu teessis, | በቀዬው አኑረን፣ |
| ilmee nuu bulchi, | ልጆችን አኑርልን፣ |
| abbaa nuu bulchi, | አባቶችን አኑርልን፣ |
| intala nuu bulchi, | ሴት ልጆችንም አኑርልን፣ |
| sa'a namaan bulchi, | ሰውን ከከብቱ አኑረው |
| biyya teenya nagaa nuu godhi. | ሀገራችንን ሰላም አድርግልን፡፡ በማለት |

እንደሚባርካቸዋል፤ እንደሚመርቃቸዋል ተገልጿል፡፡ (አቶ ሞኮና ናጋኦና አቶ አባባ ቶቴ በ15/7/2007 ዓ.ም. በወናጎ ወረዳ የቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ የሆኑ)

ከዚያም የፕሮግራሙ መጨረሻ ይሆናል፡፡ ታዳሚዎቹም በመጨረሻ የምስጋናና መልካም ምኞት መግለጫ የሆነውን ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው ይጨፍራሉ፤ ደስታቸውን ይገላጻሉ፡፡ ከዚያ ወደ ሚኤ ቦኮ ይመለሳሉ፡፡ ይህ የጉቱ ጉዞ ከተከናወነ በኋላ የገዳ አባቶቹ የስልጣን ርክክብ ለመፈፀም ወደ ሚኤ ቦኮ በመመለስ ይዘጋጃሉ፡፡ ይህ ከፍተኛው ጉባኤ ሲሆን አባገዳዎቹ ጎሳዎቻቸውን የሚያስተዳድሩበት ህጎች የሚታወጅበት (itti lallabuunu) እና የህዝቡን የተለያዩ ችግሮች የሚፈቱበት ጉባኤ (gumii) ነው፡፡

በመጨረሻም የቀደሙት አባገዳዎች በስልጣን ዘመናቸው አቅደው ያከናወኑትን መልካም ስራዎች በማሳወቅ፤ ጀምረው ከግብ ያላደረሱትን ሂደቶች ቀጣዮቹ ተረካቢዎች እንዲያስፈጽሙ ያሳስቧቸዋል፡፡ አዳዲሶቹ የገዳ አባቶች ደግሞ ስልጣኑን ከተረከቡ በኋላ የመተዳደሪያ ህጋቸው ሊሆን የሚገቡትን እዚያው ይታወጃል፡፡ አዋጁም አጠቃላይነት ባለው መልክ ስለህግ፣ ስለባህል፣ ስለአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲሁም ስለወዩነት ይታወጃል፡፡ አዋጁ የሚነገረው በዩባዎች

አማካይነት እንደሆነ በሚኤ ቦኮ ለመመልከት ችያለሁ። ከዚያም ዝርዝር ህጎችና ባህል ነክ ጉዳዮችና ወዩን በተመለከተ የሚከናወነው ከሚኤ ቦኮ በመነሳት በየጎሳዎቻቸው ውስጥ በመዝለቅና ወደ የራሳቸው የገዳ ማዕከል በሚጓዙበት ወቅት ይሆናል።

በመጀመሪያ ደረጃ ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ስናየው ማህበረሰቡ የገዳን ስርዓት ሲያዋቅሩ ጋሜ →ዳባሌ →ኩሳ →ራባ →ዶሪ →ገዳ → ዩባ... እያለ በዕድሜ እርከን ካስቀመጡ በኋላ፣ በእያንዳንዱ ደረጃ ምን መከወን እንዳለባቸውና የደረጃ ሽግግር በምን ዓይነት ህግና ደንብ እንደሚያከናውኑ ተዋቅሯል። ከዚያም ይህን ዕውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ አንድም በከበራ መልክ፣ በሚትና በመሳሰሉት ሽግግር ሲያደርጉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ልክ እንደባቱና ዩባዎች ያሉት ደግሞ በልምድ ያዳበሩትን ዕውቀት ማለትም፡- እንደ ጋሜ ያደጉበትን፣ እንደዳባሌ ያለፉበትን፣ እንደኩሳና ራባ ደግሞ የተማሩትን፣ እንዲሁም እንደገዳ ከቃሉ ያገኙትን ዕውቀቶች (የእግዚኣብሔርን ህግጋት)፣ እንዲሁም ማህበረሰቡን ባስተዳደሩበት ወቅት ያጋጠማቸውን ልምድ ጥርቅም ዕውቀት በአዋጅ ነገራ መልክ ለተተኪው ትውልድ ያሸጋግራሉ። የዕውቀት ተስተላልፎውን የተመለከትን እንደሆነ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እንዲሁም ተመልሶ ወደ ዝርዝር መሆኑን ያሳያል። ምክንያቱም በእያንዳንዱ የእርከን ደረጃዎች ያሉት ዕውቀቶች ከስር ወደ ላይ ተዳምረው፣ በነዚህ ደረጃው ውስጥ ሰያልፉ በልምድ ያካበቷቸውን ጨምሮ ጥቅል የሆነ ስለባህል፣ ስለወዩና ስለህግ ዕውቀቶቹ በይበልጥ ያሉት በባቱዎችና በዩባዎች እጅ ነው። ስለዚህ ከዩባዎች ተመልሶ ወደታች ላሉት ሁሉ በአዋጅ (lallabaa) መልክ ይተላለፋል።




ምስል፡-8 የጉጂ ኦሮሞ ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች ተስተላልፎ አቅጣጫ የሚያመለክት(ምንጭ፡- በአጥኚው የቀረበ)

### i. የጉጂ ገዳ የስልጣን ሽግግር ዙር

የጉጂ ኦሮሞ ገዳ ስልጣን በአምስት መደቦች ተከፋፍሎ የተደራጀ ነው፡፡ እነሱም፡-ሙዳና (Muudana)፣ ሀልቺሳ (Halchiisa)፣ ዳላና (Dhallana)፣ ሀርሙፋ (Harmuufa) እና ሮባሌ (Roobalee) ይባላሉ፡፡ እነዚህ እያንዳንዱ መደብ በስሩ በሺዎች የሚቆጠሩ አባላቶች ይኖሩታል፡፡ ታዲያ እያንዳንዱ መደብ በየስምንት ዓመቱ በሚደረገው የስልጣን ሽግግር ህዝቡን በዙር ያስተዳድራሉ፡፡ አንድ የገዳ መደብ፤ ለምሳሌ ሙዳና ስልጣን ቢይዙ ለስምንት ዓመታት በማገልገል ስልጣኑን ለሚቀጥለው ማለትም ለሀልቺሳ ያስረክባሉ፡፡ ሙዳና ለቀጣይ ወደ ስልጣን መጥቶ ለማስተዳደር 40 ዓመታትን ይፈጅባቸዋል፡፡ ይህ ማለት ስልጣን ካስረከበ በኋላ ተመልሶ ወደ አምስተኛው ዙር እስኪደርሱ የሚፈጅባቸው ጊዜ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የሚከተለውን ምስል ይመልከቱ፡፡




ምስል፡-9 የጉጂ ገዳ መደብዎች የስልጣን ሽግግር ዑደት የሚያሳይ ምስል (ምንጭ፡ አጥኚው በንባብ ካዳበረው ተሻሽሎ የቀረበ)

በእነዚህ አምስቱ መደቦች ውስጥ የሦስቱም ኮንፌዴረሲ አባላት ተመሳሳይ ስያሜ ባለው አደረጃጀት ተዋቅረው እንዳሉ ለማየት ተችሏል። ይኸውም፡- በሙዳና መደብ ስር የኡራጋ ሙዳና፣ የማቲ ሙዳና እና የሆኩ ሙዳና መደቦች አሉ። ስለዚህ የሙዳና መደብ ወደ ስልጣን በሚመጣበት ወቅት የሦስቱም ኮንፌዴረሲ ሙዳናዎች ገዳ ይሆናሉ ማለት ነው። በዚህ መሰረት በየስምንት ዓመቱ ለሌሎችም ስልጣኑን ያስተላልፋሉ።

ii. **የገዳ ስልጣን ማስረከብ ሂደቶች**

የገዳዎች ከስምንት ዓመት የስልጣን ቆይታ በኋላ ያለአንዳች ማቅማማት በዴሞክራሲያዊ አካሄድ ስልጣናቸውን ለማስረከብ የሚከተሉትን ቅደም ተከተላዊ ክዋኔዎችን ይፈጽማሉ። ይኸውም፡-

*ሀ. ሀጋና ማስገባት/መመለስ* (Haaganaa Galchuu)

እንደ ጉጂ ማህበረሰባዊ ዕውቀት አወቃቀር አንድ ገዳ ወደ ስልጣን ሲመጣ ሁለት ዓይነት ስልጣን እንደሚጎናጸፍ ይነገራል። ይኸውም፡- አንደኛው ከቀድሞው አባገዳ የሚረከበው ፖለቲካዊና ባህላዊ አስተዳደር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከእግዚኣብሔር የሚረከበው መንፈሳው የማስተዳደር ኃይልና ተሰጥኦ እንዳለ ይታመናል። ታዲያ አንድ ገዳ የስምንት ዓመቱ የስልጣን ጊዜው ሲያበቃ ከቀድሞው ገዳ ላይ የወሰደውን አስተዳደራዊ ስልጣን ለተተኪው አባገዳ ሲያስረክብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከእግዚኣብሔር የወሰደውን መንፈሳዊ ኃይል ደግሞ ለእግዚኣብሔር ይመልሳል ይባላል። ይህ ሂደት ደግሞ ሀጋና መመለስ ተብሎ ይጠራል። አባገዳ የፖለቲካዊ ስልጣኑን ከማስረከቡ በፊት ወደ ገናሌ፡- ካዶ (kaadho) ወይም ሀሮ ሱታሜ (haroo sutamee) የሚባልበት ቅዱስ ስፍራ በመሄድ ሀጋናውን ያስገባል።

ገዳ ሀጋና ለማስገባት ሲሄድ ከገዳ መማክርት አባላት ውስጥ ማካላ፣ፋጋ፣ሀዩና የእሱ አባላቶች እንዲሁም የጉጂን ሰባት ቤት የሚወክሉ በአንድነት በመሆን ነው። በጉዞው ወቅት ማካላው ጋሻ፣ ጦር፣ አስቴ (ichima)ና ሁለት ረጃጅም የቀርከሃ ልምጮች በመያዝ ነው። እዚያ ሀጋናው የሚቀመጥበት ኦዳ ዛፍ አጠገብ እንደደረሱ፤ ፋጋው የግራር እንጨት (Muka waaccuu) ስር "ተቀመጡ" ("taa'aa") በማለት አባታዊ መንፈስ ይላበሳል (abbooma). ከዚያን በኋላ አባገዳው ለዝግጅቱ የሚያገለግል እሳት አስቴውን በመስበቅ ያቀጣጥላል። ከዚያም ኮርማ በማረድ በከለቻው ላይ ደም ይቀባል። በመቀጠል ፋጋው ግንባሬን አጠንክርልኝ በማለት በከለቻው ላይ ደሙን ይቀባል። "adda na jabeessi, jadhu'uu na baasi!" በመቀጠል በኋላ እዚያ የታደሙት እንደየቅደም ተከተላቸው ግንባራቸውን ደሙን ይቀባሉ። በመቀጠል ሞራና አንጀቱን

ከተመለከቱ በኋላ እየመረቁ ሞራውን በአባገዳው አንገት ላይ ያደርጉታል፡፡ ከዚያ ባላ ተቆርጦ፣ ስጋውን ዘልዝሎ (babanii) በመጥበስ በአካባቢው ከሚገኙ ማህበረሰብ ጋር በመሆን ወዲያውኑ በልተው ይጨርሱታል፡፡ ቆዳውን እየተተለተለ (injicha baasanii) ሁሉም ሰው በቅደም ተከተል "Nageyi!, nageyi!, nageyaan gadoomtee nageyaan baatomi!, akka gadaa nageyaa teete baatuu nageyaa te'i!" ማለትም፡- ሰላም ሁን!፣ ሰላም ሁን!፣ በሰላም ገዳ እንደሆንክ፤ በሰላም ባቱ ሁን፤ የሰላም ገዳ እንደሆንክ፤ የሰላም ባቱ ሁን! በማለት እርስ በርስ እየተመራረቁ፣ እየተለማመኑ በየእጃቸው ላይ "ኤንጂቻውን" ያደርጋሉ፡፡

ይህ በሀሮ ሱታሜ ላይ የታረደውን ኮርማ ደም ገዳውና ፋጋው በከለቻቸው ላይ፣ ሌሎችን ደግሞ ግንባራቸው ላይ ደም የመቀባቱ ተምሳሌታዊ ክዋኔ ሀገና ካስገቡ በኋላ እርኩስ መንፈስ እንዳይጠናወታቸውና መልካም የባቱነት ዘመንን ለማሳለፍ ያላቸውን ምኞት መግለጫ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመቀጠል በዚያ ከበራ ላይ የተሳተፉት ሁሉ ጥሩ የገዳ ጊዜ እንዳሳለፍክ፤ ጥሩ ባቱ ያድርግህ በማለት እግዚአብሔርን እየተለማመኑና እርስ በርስ እየተመራረቁ የኮርማውን ቆዳ በመተልተል (injicha) እያወጡ በእጆቻቸው ላይ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ክዋኔ የሚያመለክተው ገዳውና አባላቱ ወደ ቀጣዩ ደረጃ መሸጋገራቸውን ማመላከቻና አምነው ለመቀበላቸውም በመረጃነት የሚያገለግል ተምሳሌት ነው፡፡

ከዚያ ቂጠላ ይጨፍራሉ፤ቂጠላውን የሚያወጣው አባገዳውና ማካላው ሲሆኑ ሌሎቹ ይቀበላሉ፡፡ ቂጠላውም፡-

| | |
|---|---|
| "Ilma abbaan bobbaasee!, | አባት ልጁን አሰማራ! |
| dhageettaa hobbaasee!, | ማዳመጡን አበቃ! |
| Gadabitti qajeelee!, | ወደ ገደብ አቀና! |
| Baatomuu kajeelee!" | ባቱ ለመሆን ከጀለ፡፡ |

ከቂጠላው (ጭፈራው) የምንረዳውም የቀድሞው አባገዳ ስልጣኑን ለማስረከብ እንዳሰበና፣ ወደ ቀጣዩ ደረጃ (ባቱ) ሊሸጋገር መሆኑን ማብሰሩ ነው፡፡ ከዚያም ስልጣኑን በሰላማዊ መንገድ ለማስረከብና ወደቀጣዩ እርከን ለመሸጋገር እንደሚፈልግ ያበስርበታል፡፡

በመቀጠል ከየትም ተብሎ እባብ ተገድሎ ይመጣል፡፡ ከዚያም ሀጋና የማስገባት ከበራውን ለመከወን ከግራሩ ስር ተነስተው በጸጥታ ወደ ኦዳው እንጨት ይሄዳሉ፡፡ ኦዳው አጠገብ እንደደረሱ ማካላው በእጁ በያዘው ልምጭ ኦዳውን ነካ ነካ በማድረግ "kaan ulfaataa mare massee, kaan gabalaa kiyyaa mare massee." ማለትም «የተከበረውን ጠቅልዬ

አስቀመጥኩ፣ የእኔን ድንበር ጠቅልዬ አስቀመጥኩ፡፡» በማለት በእጁ የያዘውን (የተቃጠለውን እባብ አመዱ ጠቅልሎ) አስቀምጦ ወደ ሚኤ ቦኮ መልስ ይሆናል፡፡ በዚህ መልኩ አንድ የስልጣን ዘመኑን የጨረሰ ገዳ ቀድሞ በፋጋው አማካይነት ያን መንፈሳው ስልጣን (ሀጋና) የማስገባት ከበራ ይፈጽማል፡፡

በሌላ በኩል ወደ ስልጣን የመጣው ገዳ ደግሞ እዚያው ቦታ በመሄድ ሀጋና ይወስዳል፡፡ ይኸውም፡- ሀሮ ሱታሜ በመሄድ እባብ በመግደል ያቃጥልና አመዱን በማሸት ከለቻው ላይ ይቀባል፡፡ እንደገናም ያን መርዛማ አመድ ሀዳ (hadhaa) የሚባለውን በጣታቸው ነክተው ምላሳቸውን ያስነኩታል፡፡ ምክንያቱም አዲሱን ገዳ መንፈሳዊ ኃይል በማላበስ እሱ የመረቀውም ሆነ የረገመው ከመሬት ጠብ አይልም ይባላል፡፡ ስለዚህ የገዳን ህግ የጣሰን ቢራገም ያደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

እባቡ የአደገኛነት ተምሳሌት ነው፡፡ እባብ መርዙን ይዞ የምንቀሳቀሰው በአፉ ውስጥ ነው፡፡ በተለይም ውሃ ሊጠጣ ሲል ድንጋይ ላይ አስቀምጦ ነው፡፡ የጉጂ ኦሮሞ እባብ ቅንና ንጹህ ልብ ያለውን አይተናኮልም ብለው ያምናሉ፡፡ ለዚህም እንደማስረጃ የሚያቀርቡት እባብ ሕጻናትን አይተናኮልም፡፡ ሕጻናት በእጃቸው ይዘውት ወደ አፋቸው ሲወስዱት እንኳን ለሃጫቸውን ይልሳል እንጂ አይነድፋቸውም፡፡ ነገር ግን አዋቂዎች ሲያገኙት ሊገድሉትና ሊያጠፉት ስለሚያስቡ ይነድፋቸዋል ይላሉ፡፡ ስለዚህ ገዳም ለሰላማዊ ሰው ሰላማዊ ተግባራትን የሚከውን ሲሆን፣ ለጠላቶቹ ደግሞ ኃይለኛ እንደሆነ በተምሳሌታዊ ክዋኔ ይገልጻሉ፡፡ የአበው አባባልም «እንደ እባብ ብልህ፣ እንደ እርግብ የዋህ ሁን፡፡» አይደል፡፡

**ለ. የገዳ ስልጣን ርክክብ** (Baallii kennuufi fuudhuu)

የሦስቱም ጎሳዎች በዶሪ እርከን ላይ የሚገኙት በሚኤ ቦኮ በተዘጋጀላቸው ቦታ ሰፍረው የርክክቡ ዕለት እስክደርስ በአዋጅ ነገራው ላይ ከገዳዎች ቡድን ቀጥለው በመቀመጥ ለወደፊት መተዳደሪያቸውና ማስተዳደሪያ የሚሆናቸውን ዩባዎቹ የሚያስተላልፉትና አጠቃላይነት ይዘት ያለውን ህግጋትና ደንቦችን (seera gooroo) ያዳምጣሉ፤ አካሄዱን ይማሩበታል፡፡ በመጨረሻም በነጋታው ስልጣን በሚረከቡበት ዕለት መንገዱ እንዳያስቸግራቸው ማታውን አባገዳዎቹ ወደሰፈሩበት ቦታ መሄጃውን መንገድ ይመነጥራሉ፡፡ በምሽት የሚመነጥሩበት ምክንያት የገዳዎቹ ጠባቂዎች (Jadhaaboota) የገዳ ማረፊያ ስፍራ ቅዱስ (woyyuu) ስለሆነ መመንጠር የለበትም በማለት ስለሚጠብቁና ስለሚጋረፉ ነው፡፡ እነዚህ ያሁኖቹ ዶሪ በነጋታው ስልጣኑን

ከተረከቡ በኋላ ፈረስ ላይ ወጥተው የሚፎክሩበትና የሚሸልሉበት መንገድ አመቻችተው ያድራሉ፡፡




ፎቶ፡-13 እና 14 **ስልጣን ተረካቢ ገዳዎችና የመደቡ አባላት ለርክክብ ሲሄዱ የሚያሳዩ ፎቶዎች**

በማግስቱ የሦስቱም ጎሳዎች የዶሪ እርከን አባላት ሁሉም ወደ ገዳዎቹ ማረፊያ (qachaa) ታጅበው ይሄዳሉ፡፡ እንደተቃረቡም ሦስቱ ዕጩዎች (አባሙርቲዎች) እና የጉጂ ኦሮሞ ሰባት ቤት ተወካዮች የሆኑት አማካሪዎች ጋር በመሆን ወደ ገዳዎቹ ማረፊያ ሲዘልቁ፤ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ታዳሚዎች ወደ ማረፊያው ቀረብ ብለው መንገድ ላይ ይጠባበቃሉ፡፡ አባሙርቲዎቹ ወደ ገዳዎቹ ማረፊያ ሲዘልቁ በባዶ እግራቸው ነው፡፡ ከዚያም ከደጃፉ እንደደረሱ ገዳዎቹን በነጠላ ስማቸው ይጠራሉ፡፡

ለአብነት ያህል የኡራጋውን አባገዳ እንደ ንጥል-ጥናት ብንመለከት፡- መጀመሪያ ከደጃፍ ቆሞ አባገዳውን ይጠራዋል፡፡ ይኸውም፡-

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** የኡራጋ አባገዳ የነበሩትን ገዳ ዋቆ ዱቤን በነጠላ ስማቸው ሦስቴ ‹‹ዋቆ! ዋቆ! ዋቆ!›› ብሎ ሲጠራው ምላሽ አይሰጠውም፤ በአራተኛው ‹‹ዋቆ!›› ሲለው፤

**ገዳ ዋቆ፡-** ‹‹አቤት! (yaa!)›› ይለዋል፡፡

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** በመቀጠል ‹‹ገዳው ያንተ ነው፤ የኔ?›› ("gadaan tiyya moo, teeti?") በማለት ገዳ ዋቆን ይጠይቃል፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-** «gadaan teeti, gaarri tiyya» ማለትም፡- «ገዳው ያንተ ነው፡፡ ጋሪ (ዕድሉ) ግን የኔ ነው፡፡» በማለት ይመልሳሉ፡፡

ከዚያን በኋላ ፋጋው ወደ ገዳው ማረፊያ ቀድሞ ዘልቆ ይገባል፡፡ በተሰጠው መቀመጫ ከገዳው በስተግራ በኩል ይቀመጣል፡፡ ከዚያ በመቀጠል ለሌቹም ወደ ውስጥ ይዘልቁና ይቀመጣሉ፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-** ባለቤታቸውን (haadha bollaa) «ወተት አምጭ» በማለት ትኩስ ወተት ተቀብለዋት፤ ለአባሙርቲ ጂሎ ማንዶ « እንካ የኔን ገዳ ትኩስ ወተት» («hoo'o Mi'ii gadaa tiyyaa!») ሲሉ፣

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-**«በኔ ገዳ ጣፍጥ» («gadaa tiyya mi'aayi!») በማለት ተቀብሎ ይቀምስና አብረውት ለመጡት ያቀብላል፡፡ እነሱም ይቀምሳሉ፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-**አሁንም እርጎ ወተት ከባለቤታቸውን ተቀብሎ «እንካ የኔን ገዳ እርጎ» («hoo'o Itittuu gadaa tiyyaa!») ሲሉ፣

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** «በኔም ገዳ ከሰዎችና ከብቶችህ ጭምር ሰላም ይስፈንልህ» («gadaa tiyyallee namaa, sa'aan ititi!») በማለት ተቀብሎ ይቀምሳል፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-** አሬራ ተቀብሎ «እንካ የኔን ገዳ አሬራ» («hoo'o Areera gadaa tiyyaa!») ሲሉ፣

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** «በኔም ገዳ ኮረማው ይባረክልህ» («gadaa tiyyallee Kormi sii areeru!») በማለት ተቀብሎ ይቀምሳል፡፡

**ገዳ ዋቆ፡-** ጠጅ ተቀብሎ «እንካ የኔን ገዳ አበባ» («hoo'o Daraaraa gadaa tiyyaa!») ሲሉ፣

**አባሙርቲ ጂሎ ማንዶ፡-** «በኔም ገዳ በሰውና በከብትህ አብብ» («gadaa tiyyallee namaa, sa'aan daraari!») በማለት ተቀብሎ ይቀምሳል፡፡ ከዚያም ለሌሎቹም በማስተላለፍ እንዲህ እያሉ ይመራረቃሉ፡፡

ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አንጻር አባሙርቲው (አዲስ ገዳ የሚሆነው ሰው) ቀድሞውኑ አባገዳን በነጠላ ስም መጥራቱ የራሱ ማህበራዊ ፋይዳ አለው፡፡ በመሰረቱ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ አንድ በገዳነት የመራን ሰው ይቅርና አንድን ተራ አባወራ በነጠላ ስም የመጥራቱ ልምዱ የለም፡፡ ሁለተኛ በሚኤ ቦኮ መንፈሳዊ አረዳ ውስጥም እንዲህ ዓይነት ንቀት መሰል ሲህተትም ሊፈጸም እንደማይቻል ሁሉም ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ይህን የስልጣን ርክክብ ከበራ ስርዓት ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አኳያ በምናይበት ወቅት ማህበረሰቡ ስልጣን ሲሰጠው ገዳ በመሆኑ ከሌላው የገዳ መደብ እርከን መሪ መሆኑን የሚያሳይ፣ ማህበረሰቡ

ደግሞ ስልጣኑን እንዲያስረክብ በሚያደርግበት ወቅት ደግሞ እንደማንኛውም ዩባ እንደሚሆን አመላካች ክዋኔዎችን በመፍጠር፤ ያንኑ ክዋኔ በመከወን ስልጣኑን የሚያስረክበውም ሆነ የሚረከበውን ማንነት ይለዩበታል።

በሌላ በኩል ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ስንመለከተው በዚያ አወድ ላይ የቀድሞውን አባገዳ በነጠላ ስሙን ሲጠራው ከዚያን ቀን ጀምሩ የቀድሞውና አዲሱ ገዳ ማህበራዊ መሰረታቸው የት እንደሆ አመላካች ነው።

ከተምሳሌታዊ አተረጓገም አተያይ በክዋኔው ውስጥ የቀረበው ትኩስ ወተት ገዳው በንቃት የሚሰራበት ወቅት፤ ትኩስ ኃይል እንደሆነ ሲያመላክት፣ እርጎ ደግሞ ስከን ብሎ ማህበረሰቡን የሚመክርበትና የሚያስተምርበት ጊዜ ተምሳሌት ነው። ሌላው አሬራውን የተመለከትን እንደሆነ መጀመሪያ እርጎ ነበር፤ ተንጦ አሬራና ቅቤ ወጣው። አሬራው የመጨረሻ ውጤት ይመስላል። ነገር ግን አይብ፣ አጓት አሁንም በውስጡ ይገኛል። ስለዚህ ያ እርጎው ጊዜው ደርሶ በሚናጥበት ወቅት ቅቤና አሬራው ተለይቶ እንደሚወጣው ሁሉ አዲሱ ገዳም በቅቤው ይመሰላል። ምክንያቱም አዲሱ ገዳ ከስረኛው የገዳ ደረጃ እርከን አንስቶ እየሰለጠነ፣ እየበሰለ የመጣው በቀድሞው ገዳ ውስጥ ነው። ቅቤውም ቀድሞ በትኩሱ ወተት ውስጥ ነበር፤ በኋላም በእርጎው ውስጥ ነበር፤ በመጨረሻ ተንጦ ከዚያው ወተት ውስጥ መውጣቱ ሂደቱም ተምሳሌታዊ ያደርገዋል።

ከዚያም የቀድሞው ገዳ የመሪነት አገልግሎት በስተመጨረሻ ማብቃቱንና የገዳነት ሚና እንደሌለው በአሬራው ይመሰላል። ነገር ግን በገዳነት ማገልገል ባይችልም፤ አዲስ ስልጣኑን የተረከበው ገዳ የእሱ ውጤት መሆኑን አመላካች ነው። ለዚህም ተምሳሌት ጠጁን ከተመለከትን፦ ጠጅ የሚጣለው ከማር ነው፤ ማሩ ደግሞ የአበባ ውጤት ስለሆነ ተምሳሌነቱ በገዳነቱ ወቅት እሱ የመረቀው፣ በእሱ ስር የተማረውና የተደራጀው ቡድን እንደሚያብብና ፍሬ እንደሚያፈራ አመላካች መሆኑን ያሳያል።

በመጨረሻ ያን የተሰጣቸውን ወተትና ጠጅ ከጠጡ በኋላ ፋጋው ቀስ ብሎ ከአባገዳው እራስ ላይ ከግራ በኩል ያለውን የሰጎን ላባ (baarguda ykn baallee guchii) በመንቀል በአዲሱ አባገዳ እራስ ላይ ይሽጠዋል። የሰጎን ላባው ልክ እንደዘውድ ከቀድሞው አባገዳ በማንሳት በአዲሱ መደረጉ የስልጣን ሽግግሩን አመላካች ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው። ከዚያች ክዋኔያዊ ቅጽበት በኋላ ሙሉ አባገዳ ይሆናል። ከዚያም አባገዳ ጂሎ ማንዶ ስልጣን ከተረከቡ በኋላ ወደ

ውጭ በመውጣት በተዘጋጀላቸው ፈረስ በመውጣት (odolcha koranii) ገዳ! ገዳ! ገዳ! እያሉ እያቅራሩና እየሸለሉ ሲዟዟሩ ታዳሚዎቹም ተቀብለው እየተከተሉት ገዳ! ገዳ! ገዳ! እያሉ እውቅና ይሰጣሉ፡፡ ከዚያም ከሚጠባበቋቸው የቡድኑ አባላት ጋር በመቀላቀል፤ ቡድኑም ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ገዳ! ገዳ! ገዳ! እያሉ ወደ ማረፊያቸው አረዳ ይመለሳሉ፡፡ ከዚያም ቀጣዩን ስምንት አመት የኡራጋን ጎሳ የሚያስተዳድረው ይህ ገዳ ይሆናል፡፡

ይህ የገዳ አስተዳደር ስርዓት መማክርት አባላት የሚመረጡት ቀደም ብሎ በኦዳ ስር አዳር ከበራ (jila Odaa buliinsa/ gaafa yaa'l Odaa bulu) በአዋቂዎች ጉባኤ ይወከላሉ፡፡ እነሱም፡- አባገዳ (abbaa Gadaa)፣ ጃልኬያ (Jalkeya)፣ ፋጋ (Faga)፣ ሀዩ (Hayyuu)፣ ጃልዳባ (Jaldhaaba)፣ ዋሙራ (Waamura) እና ቶርቢ (Torbii) ይባላሉ፡፡ እነዚህ የመማክርት አባላት እያንዳንዳቸው በገዳ የአስተዳደር ስርዓትና የስልጣን ሽግግር ወቅት በሚካሄዱት ከበራዎች ላይ የየራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ ምርጫቸው የሚከናወነው በኩሳ ደረጃ እያሉ ለስልጠና በገቡበት (fooqa seenane) ወቅት ነው፡፡ የዚህ ዝርዝር ሀሳብ በ5.1.3.2. ስር ተካቷል፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ በዚህ ምዕራፍ ስር የምናየው ገዳን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡

i. አባገዳ (abbaa Gadaa)

አባገዳ የገዳ አስተዳደራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርዓቱን በበላይነት የሚመራ ሰው ነው፡፡ አመራረጡም አጠቃላይ ጉባኤው ኦዳ ስር በሚያድሩበት ዕለት ለሊት በአዋቂዎች ጉባኤ ከታጩ በኋላ ለጉባኤው እንደሚያሳውቁ ቀደም ብለን አይተናል፡፡ ለጉባኤው ዕጩዎቹን ሲያስተዋውቁ የቀድሞው አባገዳው ውይይቱን ወይም ጉባኤውን ከሚመራበት ትቶ ጉባኤው መካከል ይቀመጣል፡፡ ጉባኤውን የሚመራው ታላቅዬው ፋጋ ይሆናል፡፡ ዕጩዎቹን ለጉባኤው በሚያስተዋውቁበት ወቅት የመለመሉበትን መስፈርቶች፣ የዝምድናና የዘር ሀረጉ ሁሉ ይገልጻሉ፡፡

ይህን ስልጣን ስገለጽና ቃለ-መሃላ የሚፈጽሙት (ከርቤ የሚሰጡት) እንደየቀደም ተከተላቸው ይሆናል፡፡ ከርቤ በመስጠት ቃለ-መሃላ የሚያስፈጽመውም ፋጋ እንደሆነ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

አባሙርቲ ወይም ገዳ በጉባኤው ከማጽደቃቸው በፊት ጃልዳባዎች ቄጣሌ እያሉ አጅበው ከጉባኤው ፊት በማስቀመጥ ከርቤ ያበሉትና ካለቻ ያስሩበታል (haagana itti gambisan/

kallacha itti hidhan)። ከዚያን በኋላ የዶሪ አባሙርቲ ወይም አባገዳ በመሆን ህዝቡን ያስተዳድራል ወይም የገዳውን መደብ ይመራል።

ከከርቤው የማይቀምሰው ፋጋው ብቻ ነው። ምክንያቱም እሱ በመጀመሪያውኑ ከእግዚኣብሔር የተሰጠው ፀጋ አለው (hadhaa qaba/woyyuu)፤ ስለዚህ ዳግም እንዴት ይሰጠዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ለሌሎችን ፋጋው ከርቤ ስያበላቸው፡-

| | |
|---|---|
| Dhugaa afaan sikaaye! | እውነትን በአፍህ ውስጥ አስቀመጥኩ! |
| Dhara afaanii sifuudhe! | ሀሰትን ከአፍህ ውስጥ አውጣሁ! |
| Daba hin qorini! | በደባ አታጣራ! |
| Qorii mooqaan hin qoriin! | ገቡቴ በሞቃ(ማንኪያ መሰል) አትጧጥ! |
| Buna bulluqaan hin qoriin! | ቡና በሙቅ (የማይመስል ነገር) አታጣራ! |
| Haqa hariyaan hin qoriin! | በቀረቤታና በጓደኝነት አታጣራ! |
| Fira worraan hin qoriin! | በዘመድ አዝማድ አታጣራ! |
| Dhugaa waaqaa lafaa qori! | የምድር የሰማይ እውነትን አጣራ! |
| Yoo daba qorte afaan dabi! | አጣመህ ከሰራህ አፊህ ይጣመም! |

በማለት ቁንቢውን ካበላው በኋላ ለህዝብ አገልግሎት ዝግጁ ይሆናሉ ማለት ነው።

ይህ አካሄድ ቀደም ሲል ከቃሉ ገልማ የጉቱ ጉዞ በማድረግ፣ ስጦታዎችን በመስጠት ቁንቢ ይወሰዱ የነበረውን በተለያዩ ምክንያቶች ለተወሰኑ ጊዜያት በማቋረጥ በሌላ ከበራ ተክተውታል። ምክንያቶቹም በምዕራፍ ሰባት ስር በዝርዝር ቀርበዋል።

ነገር ግን ፋጋው ቀደም ሲል በአባቃሉ ሳቆ አዶዮ (8ኛው አባቃሉ) ጋ በመሄድ መቶ ከብት በስጦታ መልክ በመስጠት ስልጣኑን አጸድቆ የወሰደውን ቁንቢ ይዞ በመምጣትና ሌሎችን በማብላት ስርዓቱን እያስፈጸመ እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ያስረዳሉ። ይህ ሂደት ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ያየን እንደሆነ በተለያየ ምክንያቶች በቃሉ ገልማ የተቋረጠውን የገዳ ስልጣን ማጽደቅ ከበራ አሁን ካለው ሁነቶች (situation) ጋር በማጣጣም ያዋቀሩት ዕውቀት መሆኑን ያሳያል።

ለዚህ ማረጋገጫ ሊሆነን የሚችለው በሚኤ ቦኮ ጉባኤ ላይ በ8/6/2008 ዓ.ም. ከተነገረው አዋጅ አንዱ ስለቃሉ ነበር። የአዋጅ ነገራው አካሄድ አፋዊ ሲሆን የራሱ የሆነ የአነጋገር ስርዓቶች አሉት። ይኸውም፡- በመጀመሪያ ደረጃ የሚኤ ቦኮን ጉባኤ የኡራጋው አባገዳ በምርቃት

ይከፍቱና እንዲቀጥሉ ፍቃድ ይሰጣሉ። ይኸውም፡-የኡራጋው ገዳ ከኡራጋ ዩባዎች አንዱን በስሙ ጠርተው «Ani asiin dura gumii teessisee hin beekuu kunoo gumii hardha teessisee seera jiru, aadaafi woyyuu naa lallabi.» ማለትም፡- «እኔ ከዚህ በፊት ጉባኤ አስቀምጬ አላውቅም፤ይሄው ዛሬ አስቀመጥኩ ያለውን ህግ፣ ባህልና ወዩ ለእኔ አውጅልኝ።» በማለት ይጋብዙታል። በባህሉ መሰረት ይህንኑ ሀሳብ መልሶ ለሌሎች ዩባዎች ያቀርብና እንዲህ ተባለ ምን እናድርግ ተባብለው፤ ያው ስለጉጂ ህግና ደንብ፣ ስለባህሉና ስለወዩ ማንኛውም ህብረተሰብ እንዲያውቀውና እንዲያከብረው፤ እንዲሁም እንዲያስከብረው አዋጅ ነገራው ይቀጥላል። አዋጅ ነገራውን የሚያካሂዱ ዩባዎች ናቸው። በመቀጠል ለመናገር የፈለገ ሰው በስርዓቱ መሰረት ቆጲሴ (qophise)፣ ተናግሮ ሲጨርስ ደግሞ ቶጊሴ (toggise) ይላሉ። እንዲሁም ቀድሞ የተናገረውን ሰው የሀሳብ ስህተት ካለበት ምክንያታዊ የሆኑ ማስተካከያ ለመናገር ደግሞ ቆጢሴ (qoxxise) በማለት ዕድሉ እንዲሰጠው በመጠየቅ አዋጅ ነገራውን ያካሂዳሉ። አዋጅ ነገራው በአንድ ቀን የሚያልቅ አይደለም። ቀደም ሲል ከ28 ቀናት እስከ አንድ ወር ይፈጅ የነበረውን አሁን ደግሞ ከተለያዩ ችግሮች ማለት፡- በከበራው ላይ የሚሳተፉ እድምተኞች ቁጥራቸው መብዛት፣ ከዚህ በተጨማሪ ለወር ያህል የሚቆይ ከሆነ፣ ለተለያዩ ከበራዎች እርድ ስለሚያስፈልግና ለእነዚህ የሚሆን ወጭዎችም በመብዛቱና የመሳሰሉት ችግሮች የተነሳ ለሳምንት የሚካሄድ መሆኑን ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። ስለዚህ የዕለቱን አዋጅ ነገራ ሲያበቁ አሁንም የኡራጋው አባገዳ ለጃልዳባ ጉባኤውን እንዲበትን በስነቃል እንደሚከተለው በማለት ያዛሉ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| hojjataan hujii yaadee, | ሰራተኛው ስራውን አሰታወሰ፣ |
| hafuuraan qorii yaadee, | ውስጣችንም ምግብ አሰታወሰ፣ |
| hinaafaan niitii yaadee, | ቀናተኛውም ሚስቱን አስታወሰ፣ |
| araadaan tamboo yaadee. | ሱሰኛውም ትንባሆውን አስታወሰ፣ |
| Jadhaaba gumii kaasi. | ስለዚህ ጃልዳባ ጉባኤውን በትን። በማለት |

ትዕዛዝ ይተላለፋል።

ከዚያም ከኡራጋ አባገዳ ትዕዛዙን የተቀበለው የኡራጋ ጃልዳባ ቀበል አድርጎ፡-

| | |
|---|---|
| hojjataan hujii yaadee, | ሰራተኛው ስራውን አሰታወሰ፣ |
| hafuuraan qorii yaadee, | ውስጣችንም ምግብ አሰታወሰ፣ |
| hinaafaan niitii yaadee, | ቀናተኛውም ሚስቱን አስታወሰ፣ |
| araadaan tamboo yaadee. | ሱሰኛውም ትንባሆውን አስታወሰ፣ |

gumiin galti geette. ጉባኤው መግቢያው ጊዜ ደርሰ፡፡ በማለት ያስተጋባል፡፡

በመቀጠል አባገዳው የጉባኤውን መቀመጫ ስፍራ አጥረው የሚጠብቁትን የዶሪ ጃልዳባ «Jadhaaba karra bani!» ማለትም ያጠርከውን ክፈትና አሳልፍ እንደማለት ትዕዛዝ ይሰጣሉ፡፡ ከዚያም በመጡበት መልክ ተመልሰው ወደ ማረፊያቸው ይሄዳሉ፡፡

ከአዋጅ ነገራው ውስጥ በ8/6/2008 ዓ.ም. የጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ መቅረቱ አግባብ አለመሆኑንና ከአሁን በኋላ መከናወን እንዳለበት እንደሚከተለው ሲነገር ለማዳመጥ ችያለሁ፡፡ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Gujiin qaalluu qaba aadaa, | ጉጂ ቃሉ አለው ባህል ነው! |
| Qaalluun Obituu abbaayyaa jira aadaa, | የኦቢቱ ቃሉ አባያ አለ ባህል ነው! |
| Yaa'aan dhaquun aadaa, | በቡድን ይኬዳል ባህል ነው! |
| Jabbii guttuu fo'anee qaalluu lolan aadaa, | የጉቱ ጥጃዎች ተይዞ በመሄድ መጣላት ባህል ነው! |
| Jabbiin sun karaan hafuun aadimalee, | እነዚያ ጥጃዎች መቅረታቸው የእኛ ባህል አይደለም! |
| Gadaan seera ittiin kennane karaatti hinkutu aadimalee, | ገዳ የሰጡትን ደንብ ከመንገድ አያስቀርም የእኛ ባህል አይደለም! |
| Karaan gaha aadaa,... | ከቦታው ድረሱ ባህል ነው.... በማለት |

መታወጁ ያለፈው ስህተት ነው፤ ከአሁን በኋላ ሂደቱ መሰረቱን ሳይለቅ እንዲከናወን ማሳሰባቸው ነው፤ ማሳሰብም ብቻ ሳይሆን ይህ የታወጁት አዋጆች በተቻለ መጠን መፈጸም ስላለባቸው ለቀጣይ እንደሚከወን ከገዳዎቹ አንደበትም ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

በሌላ በኩል ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርግ አካሄድ የሚመስል የገዳ አባቶች ሽማግሌዎችን በመምረጥ ወደቃሉ ተቋም እንደተላኩና የባለፈውን በይቅርታ ታልፎ፤ ለቀጣዮቹ በስርዓቱ ለመመለስ ቅድመ ውይይት እንዳደረጉ በአባቃሉ አጋ ሳቆ ገልማ ተገኝቼ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

## 6.2. የጎንደሮ ከበራ

ጎንደሮ ማለት ይህ ክስተት ዳግም እንዳይመለስ ወይም እንዳይከሰትብህ/ሽ እንደ ማለት ነው። የጎንደሮ ከበራ ከሚከወንባቸው ጉዳዮች አንዱና ዋንኛው ምክንያት ለተለያዩ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሔ ስለሚያስገኝ ነው። ግጭቶች በባህሪያቸው የተለያዩ ናቸው። ጠቅለል አድርገን ስናያቸው ሰው ሰራሽም ሆነ፣ ተፈጥሯዊ ችግሮች ከሚያደርሱት ጉዳት አንጻር ግጭቶችን ቀላልና ከባድ በማለት ልንከፍላቸው እንችላለን። ይኸውም፡-

### i. ቀላል ግጭቶች

ቀላል ግጭቶች የሚባሉት የባልና የሚስት ፀብ፣ የጓደኛሞች ግጭቶች፣ የቤተሰብ ግጭቶች፣ የጎረቤታሞች ግጭቶች ሊሆን ይችላል። እነዚህ ግጭቶች በተበዳዩ ላይ ቀለል ያሉ ጉዳቶች ያደረሱ ከሆነ፣ የሚፈቱት በቤተሰብ ደረጃ አለያም በአካባቢው ሽማግሌዎች ደረጃ ነው። ነገር ግን በዚህ መልክ የተነሱ ግጭቶች አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ሳይፈቱ ቀርተው ወደ ከባድ ግጭቶች የሚያመሩበትና ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱበት ሁኔታዎች ሊከሰት ይችላሉ።

### ii. ከባድ ግጭቶች

ከባድ ግጭት ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው ከባድ ለሆነ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና እኮኖሚያዊ ቀውስ ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ነው። በዚህ የግጭቶች ዓይነት ስር ምናልባት በገዳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ካሉ፣ በግለሰቦች መካከል በተፈጠረ ግጭት መንስኤ የነብስ መጥፋት ካጋጠመ፣ የጎሳ ለጎሳ ግጭቶችና የብሄር ግጭቶች ሳቢያ የነብስ መጥፋት ከተከሰቱና የመሳሰሉት በዚህ ስር ይመደባሉ።

እነዚህ ግጭቶች በበዳዩ ወገንም ሆነ በተበዳይ ወገን የሚያደርሱት ጉዳት በጣም የከፋ ስለሚሆን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በመፈጸም እርቀ ሰላም ማውረድ ግድ ይላቸዋል። እርቀ ሰላም ወርዶ ወደ ቀድሞ የሰላማዊ አኗኗር ዘይቤ ውስጥ ካልገቡ በቂም በቀል ወደ ከፋ ደም መፋሰስ ያመራሉ። በመጨረሻም በሁለቱም ወገን አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ግንኙነታቸው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ። ስለዚህ ማህበረሰቡ ከእንደነዚህ ዓይነት ችግሮች ለመውጣት ካዋቀረው ማህበረሰባዊ ዕውቀት ውስጥ አንዱና ዋንኛው የጎንደሮ ከበራ ነው።

ይሁን እንጂ ለሁሉም የግጭት ዓይነቶች የጎንደሮ ከበራ ይከወናል ማለት አይደለም። ሌላው እያንዳንዱ የግጭት ዓይነቶች እንደየደረጃቸው የሚፈቱበት የራሳቸው የሆነ ሂደቶች አሏቸው።

### 6.2.1. የግጭት አፈታት ሂደቶች

አንድ ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ያን ችግር ለመፍታት በተሰየመው አካል የሚከናወኑ ሂደቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- የግጭቱን ምክንያት ማወቅ፣ የግጭቱን ምክንያት ማዳመጥ፣ መረጃዎቹን ማረጋገጥ፣ ውሳኔ መስጠት፣ የማስማማት ከበራና በመጨረሻም ውሳኔውን ማስከበር ናቸው፡፡ እነዚህን ሂደቶች ምን እንደሚመስሉ ባጭሩ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

i. የግጭቱን ምክንያት ማወቅ

ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት በቅድሚ በምን ምክንያት እንደተጋጩ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፡- በግጦሽ መሬት (የጉጂና የቦረና)፣ በድንበር ይገባኛል ጥያቄ (የጉጂና የጌደኦ፣ የጉጂና የኮይራ)፣ ውል ወይም እምነት ማፍረስ (በእምነት የተሰጠን ነገር መካድ፣ ቃል ገብቶ ቃል ማፍረስ....)፣ ድንገተኛ ክስተቶች (በስካር፣ አውሬ መስሎት በስህተት ሰውን መግደልና የመሳሰሉት) እንዲሁም የመልሶ ማጥቃት ሂደቶች (አንድ ቡድን ከብቶቻቸውን ቢዘረፉ፤ እነሱም በተመሳሳይ ሁኔታ ለማስመለስ ሲጥሩ የሚፈጠሩ ግጭቶች....) እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በየትኛው ምክንያት ግጭቱ እንደተቀሰቀሰ ማወቅ ወይም መለየት የግጭት አፈታቱ የመጀመሪያ ሂደት ነው፡፡

ii. የግጭቱን ምክንያት ማዳመጥ

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ግጭቱን ለመፍታት የተሰየሙት አካላት፤ በዚህ የሂደት ደረጃ በመጀመሪያ እግዚኣብሔር እርቁን በሰላም እንዲያስፈጽምላቸው ይለማመናሉ፡፡ በመቀጠል አካሄዱን የሚመሩ ሁለት ግለሰቦች በባህሉ፣ በሃይማኖቱና በጎሳ ደረጃ ካላቸው ቦታ ታይተው ይመረጡና ይሰየማሉ፡፡ ከዚያ ከተበደልኩ ባዩ የግጭቱን ምክንያት እንዲያስረዳ ይጠየቃል፡፡ በዚህ መሰረት የግጭቱን ምክንያት ከስረ መሰረቱ ያዳምጣሉ፡፡

iii. የግጭቱን ምክንያት መረጃዎች ማረጋገጥ

በዋቄፋና እምነት መዋሸት በራሱ ጨቡ ነው፤ እውነት የእግዚኣብሔር ልጅ ናት (“dhugaan ilmoo waaqati.”) ይላሉ፡፡ ስለዚህ በተቻለ መጠን እራሳቸው እውነቱን እንዲያወጡ ወይም እንዲያረጋግጡ ለሁለተኛ ጊዜ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህም ካልተሳካ ደግሞ በሰው፣ በሰነድ ማስረጃ እንዲያረጋግጡ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ሌላው አማራጭ ወኪሎቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው ስለግጭቱ ምክንያት የሚያውቁት ነገር ካለ እንድገልጹ ይጠየቃሉ፡፡ በእነዚህ

ሁሉ ምላሽ ከጠፋ፤ ሽማግሌዎቹ በሁለቱም ወገን ከአነጋገራቸው ውስጥ ከታዘቡት ጉዳይ ተነስተው በተረትና በምሳሌያዊ ንግግሮች ወደ እውነቱ መንገድ እንዲመጡ ምክር አዘል ንግግር ጣል ያደርጋሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሂደት መሰረት ተደርጎ ከተረጋገጠ በኋላ ወደ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ይገባል፡፡

iv. ውሳኔ መስጠት

ይህ የውሳኔ መስጠት ሂደት የተበዳይን በደል የሚያካክስ፣ አንዳንዴም ደግሞ የበዳይን አቅምና ለይቅርታው ምን ያህል እንደተፀፀተ ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ተበዳይን በመለመን የማግባባት ስራ የሚሰራበት ሁኔታም እንዳለ ከመረጃ አቀባዮቹ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

v. የማስማማት ከበራ

ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዳዩ የተወሰነበትን ነገር እንድፈጽም ይደረግና ሁለቱንም ግለሰቦች ወይም ቡድኖች አቀራርቦ እንዲጨባበጡ፣ ዳኤ እንዲባባሉ ይደረጋል፡፡ በዚህ ጊዜ እንደስልጣንና ዕድሜ ደረጃ ጎንበስ ብሎ ይቅርታ መጠየቅም የሚካሄድበት የሂደት ደረጃ ነው፡፡

vi. ውሳኔውን ማስከበር

የጉጂ ኦሮሞ በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠሩ ግጭቶችን በእርቅ ከፈቱ በኋላ ያ ችግር ዳግም እንዳይመለስ በመጀመሪያ ደረጃ የታረቁትን አካላት እየመረቁ፤ በምርቃቱ ውስጥ ዳግም በዚያ ድርጊት እንዳይመለሱ በማውገዝ ውሳኔው እንዲፀና ይደረጋል፡፡ ሌላው በቃሉና ገዳ ተቋማት በኩል ከሆነ የጎንዶሮ ከበራና ቦኩ (boku) ማለትም ማዕቀብ በመጣል ውስኔዎችን ማስከበር እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡

### 6.2.2. የጎንዶሮ ዓይነቶች

በዋናነት ሁለት የጎንዶሮ ዓይነቶች አሉ፡፡ እነሱም የግጭት ማሳረጊያና የምልጃ ማሳረጊያ ጎንዶሮ ይባላሉ፡፡ የነዚህን ልዩነትና አንድነት ከተሰበሰበው መረጃ አኳያ ለማየት ተችሏል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ለማየት እንችላለን፡፡

#### 6.2.2.1. የግጭት ማሳረጊያ ጎንዶሮ

ቀደም ሲል እንዳየነው ከባድ ግጭት በግለሰብ ደረጃ፣ በቤተሰብ አባላት ውስጥ ወይም በተለያዩ ቤተሰብ ውስጥ ካሉ ግለሰቦች፣ ጎሳዎች ወይም ከአጎራባች ብሔሮችና ብሔረሰቦች ጋር ሊፈጠር ይችላል፡፡ የግጭቱም ምክንያቶች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በጉጂ አካባቢ ከሚነሱ ግጭቶች ውስጥ አንድ መንስኤው ይህ ነው። ምክንያቱም እንደ ከፊል-አርብቶ አደርነታቸው ከአጎራባች ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ጋር አልፎ አልፎ ግጭቶች ይከሰታሉ። እነዚህ ግጭቶች ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርሱበት ጊዜም አለ።
የገዳ ስርዓት ግጭቶችን በመፍታትና ሰላምን በማስፈን በኩል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው (Israel, 2011፡300)። ለዚህ ስኬት ደግሞ የቃሉ ተቋም ያለው አስተዋጽኦ የጎላ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ ተቋም በራሱ ከፍተኛ ግጭቶችን የመፍታት አቅምና ችሎታውም እንዳለው ማህበረሰቡ ያምኑበታል።

ይህ የጎንዶሮ ከበራ እያለም አልፎ አልፎ በአጎራባች ህዝቦች መካከል በተለያየ ወቅት ግጭቶች ይነሳሉ፤ ብዙ ደም መፋሰስ ደረጃም ይደርሳሉ። ለዚህ የሚስማማ አንድ የጉጂ ኦሮሞ ምሳሌያው አባባል አለ። ይኸውም፡-
“kaleessa hin kakannee?” jennaan “edana hin bullee.” Jedhe
አቻ ትርጉሙም “ትላንትና አልማልክም ነበር?” ቢባል “ምነው ትላንት አድረን የሌ።”
አለ ይባላል።
ከዚህ አባባል የምንረዳው በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም፡- በግጦሽ መሬት ይገባኛል፣ ከህዝብ ቁጥር መብዛት የተነሳ፤ የእርሻና የግጦሽ መሬት ፍለጋና በመሳሰሉ ምክንያቶች ዳግም የሚያገረሽበት ሁኔታ ይከሰታል። በሌላ በኩል የገዳዎች ቁርጠኝነት ማጣት እንደሚታይና የጎሳዎቻቸው ክፍተት የመሸፋፈን ሁኔታዎች እንዳሉና ለዳግም ግጭት እንደሚዳርጋቸው መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ። ይህ በዝርዝር በ7.2. ስር ተገልጿል።

### I. በጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ ውስጥ የቃሉ ሚና

ቀደም ሲል እንደተገለጸት የቃሉ ከበራዎች፡- የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች እንዳይከሰቱ ቅድመ-መከላከል፣ አሊያም ችግሮቹ ከተከሰቱ በኋላ እንዳይስፋፉ፣ ጉዳታቸው እንዳይበዛና ከናካተው እንዲያበቃ የሚከወኑ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶችና አካላት የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት የሚፈጸም የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የቃሉና የገዳ ስርዓት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። የገዳ ስርዓት እርስ በርስ የተሳሰሩ ሶስት አካላት አሉት። እነሱም፡- ሃይማኖታዊ ተቋም (የቃሉ ተቋም)፣ ጠቅላላ ጉባኤ

(gumii) እና ገዳ ማለትም የስርዓቱ ፖለቲካዊ አመራር እንደሆኑ Asmarom, (2000:100) ያስረዳል።

ከነዚህ ሶስቱ አካላት ውስጥ በጣም ብዛት ያለው ሰው የሚሳተፍበት ጠቅላላ ጉባኤ (gumii) ነው። ምክንያቱም ይህ ጉባኤ አዲስ ሕግ የሚወጣበት፣ በነባሩ ሕግ ውስጥ ያረጁ፣ ያፈጁ ሕግጋት የሚታደሱበት፣ ማለትም ከወቅቱ ጋር የማይሄዱ ከውስጡ የሚወገዱበት፣ ምናልባትም አዳዲስ ሕግጋት የሚታከልበት ቦታ ስለሆነ፤ እዚህ ቦታ ላይ ደግሞ ስለ ባህሉና እምነቱ ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትና የኦሮሞ አዋቂዎች (hayyuu) የሚሳተፉበት መሆኑን Asmarom በማከል እንደሚከተለው ያስረዳል።

> Gumi means 'the multitude' because it is a very large assembly made up of many councilors (hayyu) and assemblies (ya'a) drawn from different section of the gada institution as well as ordinary citizens who have the ability to express their thoughts on matters of national concern (Ibid:97).

ይሁን እንጂ ለነዚህ ሶስቱ አካላት ትስስር ውሉ የቃሉ ተቋም ነው። ምክንያቱም የገዳ ስርዓት መሰረቱን ሳይለቅ በየስምንት ዓመቱ የሚያደርጉት የስልጣን ሽግግር እንዲቀጥል የሚያደርግ ማዕከላዊ ተቋም በመሆኑ ነው። ሌላው ጠቅላላ ጉባኤውንም የተመለከትን እንደሆነ ከዚሁ ሂደት ጋር አብሮ የሚነሳና ከገዳ ስልጣን ሽግግር በኋላ አሮጌው ሕግ የሚከለስበት ጉባኤ ነው። ስለዚህ የነዚህ ከበራዎች መጀመሪያውም ሆነ መጨረሻውም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች በመሆኑ ነው።

ቃሉ በገዳ ስርዓት ውስጥ በሀገረሰባዊ ሃይማኖት ዙሪያ ለሚካሄዱት ከበራዎች ኃላፊነት ያለው አካል ነው።

ከዚህም ባሻገር የቃሉ ተቋም በዋናነት በገዳዎች መካከል ግጭቶች ቢፈጠሩ፣ እንዲሁም በጎሳዎች መካከል ግጭቶች ቢከሰቱ፣ ከአጎራባች ብሔሮችና ብሔረሰቦች ጋር ግጭት ቢፈጠር እነዚህንና የመሳሰሉት ግጭቶች ከመፍታትና የመጨረሻ መቋጫ ከማበጀት አኳያ ያለውን ሂደት የማስፈጸም ድርሻ ከፍተኛ ነው።

ይህ ሲባል የገዳ ተቋማት ሚና የላቸውም ማለት አይደለም። የገዳ ተቋማት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነሱ ግጭቶችን ከመፍታትና ለማህበረሰቡም ያለው ቅርበትና ተደራሽነቱም ሰፊ ነው። እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለጻም ገዳዎች የእርስ በርስ ችግራቸውንም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን የመፍታትና ዘላቂ መፍትሔ ከማስገኘት በኩልም ከፍተኛ ሚና አለው። ነገር ግን ከነሱ በላይ የሆነውን ጉዳይ ሊፈታ የሚችለው ግን የቃሉ ተቋም ነው።

## II. የግጭት አፈታት መዋቅሮች

በጉጂ ኦሮሞ አካባቢ የተለያዩ ማህበራዊ ግጭቶችና ክርክሮች ሲከሰቱ የሚፈቱባቸው የተለያዩ መዋቅሮች አሉ። እነሱም፡- ግለ-ወቀሳ (si himadhaara)፣ ሽምግልና (Jaarsummaa) እና የቃሉ መማክርት (gumii qaalluu) ናቸው። ከእነዚህን መዋቅሮች ውስጥ የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን የተወሰነ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ገለጻ በማቅረብ የሚታለፉ ሲሆኑ፤ ሶስተኛው መዋቅር ግን ከጥናቱ ትኩረት አንዱ ስለሆነ በጥልቅት ትንተና ተካሂዶበታል። ስለዚህ ከዚህ እይታ አኳያ እንደሚከተለው አንድ በአንድ እንመለከታለን።

### 1. ግለ-ወቀሳ (si himadhaara)

ግለ-ወቀሳ ማለት ሁለት ግለሰቦች በተለያዩ ነገሮች ላይ ያለመግባባትና ተበዲያለሁ ባይነት ስሜት ሲሰማቸው አንዱ ሌላውን የእንወቃቀስ ፍቃድ ጠይቆ እርስ በርስ የሚተራረሙበት የመጀመሪያው መዋቅር ነው።

እንደ ጉጂ ኦሮሞ የግጭት አፈታት መዋቅር በግለሰቦች መካከል ካለ ቀረቤታ፣ ከሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ፣ እንዲሁም ከወግና ባህሉ ተነስቶ ከአንድ ሰው የሚጠበቅበት ስነ-ምግባሮች አሉ። ለምሳሌ፡- እንደዋቄፋና እምነት እግዚኣብሔር በቃሉ አማካይነት ምዕመኑ እንዲያከብራቸው ያስተምር ዘንድ ካዘዛቸው ሕግጋት ውስጥ አንዱ ስለ ሳፉ (Safuu) እንደሆነ በ4.2.5. ስር ተመልክተናል።ይኸውም፡- በዋቄፋና ሃይማኖት ልጆች ወላጆቻቸውን፣ታናናሾች ታላላቆቻቸውን፣ ጎልማሶችና አረጋዊያንን፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ዋቄፋታ ቃሉዎችንና አያንቱዎችን ማክበርና ቀድሞ ወንዝ ከመሻገር፣ ቀድሞ ከመመረቅ፣ እንደተቀመጠ ሰላምታ ከመስጠትና በነጠላ ስም ከመጥራት መታቀብ ይጠበቅበታል። ዋቃ ቀኑን ለሰዎችና ለቤት እንስሳት፣ ሌሊቱን ለዱር አራዊት የፈቀደ በመሆኑ ይህ መሻር እንደሌለበትና የደኖች ልምላሜና የወንዞች ንጽህና መጠበቅ እንዳለበት የሚያዝ ሕግ ነው። እነዚህ ትዕዛዛት ደግሞ ፈረሃ-እግዚሐብሔርን፣ ወግና ባህልን መጠበቅ እንደሚያስፈልግ የሚያስጠነቅቁ ናቸው (Bartels,1983 & Dejene, 2007)።

ይህ ከላይ የተመለከትነው የዋቄፋና እምነት ህግጋቶች ከእግዚኣብሔር ወደ ቃሉ፣ ከቃሉ ደግሞ ወደ ምዕመኑ፤ እንዲሁም ከምዕመኑ ወደ ምዕመኑ እየተላለፈ እዚህ የደረሰው በስነቃልና በድርጊት አማካይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ነው። ይህ ባህሪይ ደግሞ የማንኛውም ሀገረሰባዊ ሃይማኖት መተላለፊያ መንገድ ነው።

እንደ መረጃ አቀባዮቹ ታላቅን ማክበር (በሰላምታ፣ ወንዝ ሲሻገሩ ቅድሚያ በመስጠት፣ ተራ ጠብቆ አነጋገር፣ ምርቃት....)፣ እንግዳ መቀበል (እግር አጥቦ፣ በቅቤ አሽቶ፣ አብልቶ፣ አጠጥቶ ማሳደርና መሸኘት...)፣ የታመመን መጠየቅ፣ የሞተ መቅበር... ማህበረሰቡ ከባህላዊ አኗኗሩና ከእምነታቸው ያካበቱት እሴቶች እንደሆኑ ይገልጻሉ። በሌላ በኩል መፋቀር፣ እውነት መናገር፣ በሰላም መኖር፣ ለሰው ልጅ ክብር መቆርቆርም በባህላቸው ውስጥ እንደሚታይ ይገልጻሉ።

ለምሳሌ፦ ልጅ ለአባቱ መታዘዝና አባቱን ማክበር እንዳለበት እየታወቀ፤ ጎረመስኩ ብሎ አባቱን ቢንቅ ወይም ቢያንጓጥጥ ቤተ-ዘመዱም ሆነ ጎረቤቱ ዝም ብሎ አይመለከትም። ምክንያቱ በአንድ በኩል የቃሉ አስተምሮትም ተጥሷል። በሌላ በኩል እንዲህ ዓይነቱ ጋጠ-ወጥ ልጅ ነገ ለሌሎች የዕድሜ እኩዮቹ የሚያስተምረው መጥፎ አርኣያ በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳይሰራጭ ከማሰብ ነው። ስለዚህ ቀድመው ይመክሩታ። በዚህ የማይመለስ ከሆነ ቤተሰብ ተሰብስቦ የአካል ቅጣት ይፈጽሙበታል።

ሌላው የቃሉን ግለሰባዊ ልዕልና የተመለከትን እንደሆነ በመጀመሪያ ደረጃ በማህበረሰባዊ እሴቶች የተገነባ፤ ከዚያ ባለፈ ለቀሪው ማህበረሰብም ተምሳሌት በመሆን የሚያገለግልና በተቋሙም ውስጥ የካደ እውነቱን የሚያወጣበ ወይም የሚናገርበት፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ የበደለ የሚካስበት፣ ባህልና ወጉን የጣሰ ተወቅሶ የሚታረምበት፣ ታላቅን ካላከበረና የባህል ጥሰት ከፈፀመ፤ ይህን ጥሰት የፈፀመ መውቀሻ/ቅሬታ ማሰሚያ መንገድም አለ። ይኸውም፦ ቅሬታ አለኝ፤ ልወቅስህ ነው (Quuxxee qaba, Si himadhaa.) የሚል ቅሬታ ማቅረቢያ ባህላዊ አውድ ነው።

ታዲያ ተበደልኩ ባዩ ግለሰብ ከላይ የተጠቀሰውን ግለ-ወቀሳ በሚልበት ወቅት፤ በዳዩ በባህሉ መሰረት ጥፋቱን ተረድቶ ቶሎ ብሎ "አትውቀሰኝ በድየሃለውኝ፤ ባጠፋሁት እቀጣልሃለሁ።" በማለት በሁለቱ ስምምነት ሊፈታ ይችላል። በዚህን ጊዜ ስህተቱን በምን ምክንያት ሊፈጽም እንደቻለ በማስረዳት ይቅር እንድለው ይማጸነዋል። ይኸውም፦

| | |
|---|---|
| Balleesan kiyya. | ጥፋቱ የኔ ነው። |
| Yaadoo ta'e tokko keessa ta'ee | የሆነ ሀሳብ ውስጥ ሆኜ |
| si hin argin, | አላየሁም፣ |
| Kanaaf malee, akkamiin si | ይህ ባይሆን ኖሮ! ሰላም ሳልልህ |
| hin yooyyifatin darba? | እንዴት አልፋለሁ? |
| Kanaafuu,hattoo naan jedhe. | ስለዚህ ይቅር በለኝ። በማለት |

ይቅርታውን ይጠይቀዋል። ከዚያ ያም የወቀሰው እምነቱ፣ ባህሉና ወጉ እንዳይሸረሸር ለመቆጣጠሪያነት ያህል ተቆርቁሮ መሆኑን በማስረዳት የተጠየቀውን ይቅርታ ተቀብሎ በሰላማው መንገድ እንደዱሮዋቸው መኖር ይጀምራሉ።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ አጥፊው መስሎት ያደረገው ነገር ከሆነ "ውቀሰኝ፤ ሽማግሌ ይየው።" በማለት ሽማግሌዎች እዚያው ይሰየሙና በባህሉ መሰረት ጉዳዩን እንዲጣራ ይደረጋል፤ ውሳኔ ይሰጥበታል። ውሳኔውም እንደሁኔታዊ ተፈጻሚ ይሆናል።

መቼቱ ድርጊቱ በተፈፀመበት ቦታና ዕለት (መጠጥ ቤት፣ ገበያ...) አካባቢ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ወቀሳውን እንዲካሄድና እንዳይካሄድ የሚወስኑ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ።

ለአብነት ያህል ጊዜው ምሽት ከሆነ ተወቃሹ፤«ጀንበር አዘቅዝቃለች፤ በዚህ ሰዓት ሽምግልና አይታይም።» (lafti oliifi gadi, hayyuu gaafachuu hindande'amu.)፣ በሌላ በኩል «እኔ አባት አለኝ» (ani abbaa qaba.) በማለት ይከራከራል። ምክንያቱም በባህሉ መሰረት አባት ያለው ልጅ፤ አባቱ እያለ እሱ አይወቀስም። ስለዚህ አባትህን አቅርብ ይባላል። በዚያን ጊዜ ደግሞ «አባቴ መንገድ ሄዷል» (abbaan kiyya Karaa deeme jira.) የሚሉትንና የመሳሰሉትን የማምለጫ ሀሳቦች እየሰነዘረ ጉዳዩን በይደር እንዲታለፍ የሚደረግበትም ሁኔታዎች እንዳሉ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ።

ተወቃሹ ይህን የሚያደርገው ሳለመካድ፣ ሳለመዋሸትና ሳጠፋው ጥፋት የሚክሰው ነገር ከሌለው ባህልና ወጉን ሳለመጣስ፤ ከባሰበት ባህሉ ያስቀመጣቸው የማምለጫ ዘዴዎች መጠቀሙን ያሳያል። ስለዚህ ቀጠሮ ይያዛል። ይኸውም፡- የተወቃሹ ጥያቄ የጊዜ ጉዳይ ከሆነ በማግስቱ ጠዋት ይታያል። አባቱ መንገድ ሄዷል ካለ መመለሻው ተጠይቆ በዚያን ዕለት ይዞት እዲቀርብ ይነገረውና በዚያን ወቅት ጉዳዩ ይፈታል። ስለዚህ በዚህ ምክንያት ነገሩን ሊያሳድሩት ይችላሉ። ነገር ግን ተወቃሹ እንዲህ መወትወቱ በራሱ በውስጠ ታዋቂነት በጉዳዩ እንዳመነና ከቅጣት

ለመሸሽ መጣጣሩ ይታወቃል። ለማንኛውም የማህበረሰባዊ እሴቶች መጣስ እንደሌለባቸውና ከተጣሰ ደግሞ ወደ መስመሩ የመመለሻ ስርዓት እንዳለ ያሳየናል። ከዚህ ውጭ ከሆነ ያ ሰው እንደባለጌ፣ ወሮበላ...ይታያል።

ስለዚህ እነዚህ እሴቶች የእያንዳንዱ ግለሰባዊ ልዕልና በማህበረሰባዊና አለማቀፋዊ እሴቶች እንደተገነባ ያመላክታሉ።
ይህ ሳይሆን ሲቀር ቀላል ግጭቶች ሲፈጠሩ ደግሞ ወደሚቀጥለው የሽምግልና የግጭት መፍቻ መዋቅር ይተላለፋል።

1. ሽምግልና (Jaarsummaa)

ከስያሜውን ብንነሳ "ሽምግልና" (jaarsummaa) የሚለው ስም የመጣው ጉዳዩን ከሚመለከተው ሽማግሌ (jaarsa) ከሚለው ስም እንደሆነ የሀገር ሽማግሌዎች (መረጃ አቀባዮቹ) ይናገራሉ። ይኸውም የበዳይንና የተበዳይን ጉዳይ በሽማግሌዎች አማካይነት አቀራርቦ መረጃዎቹን አያችሁ፣ ሰማችሁ በማለት ይፈቱታል። ስለዚህ የዚህ ችግር መፍቻ ባህላዊ ተቋም ስያሜም ሽምግልና ተባለ። በአፋን ኦሮሞ የግስ ርባታ ሂደት የተመለከትን እንደሆነ "jaarsa" ስም ሲሆን "jaarsummaa" ሂደት ነው። ስለዚህ ይህ የሽምግልና ሂደት ስያሜ የመጣው በሽማግሌ አማካይነት ጉዳዮቹ ስለሚታዩ (ስለሚዳኙ) ነው። በመሆኑም የጉጂ ማህበረሰብ ይህን ስያሜ የሰጠው ከዚህ አኳያ እንደሆነ ያስረዳሉ።

እንደጉጂ ኦሮሞ የሽምግልና ደረጃዎች አሉ። ይኸውም:- ማንኛውም ችግር በተቻለ መጠን በታችኛው መዋቅር እንዲፈቱ የመከራል። በተለይም ጥቃቅን ነገሮችን ወደ ላይኛው ደረጃ ማምጣት አይጠበቅም። ይኸውም በቤተሰብ ደረጃ፣ ቀጥሎ በዘመድ ደረጃ፣ በጎረበት ደረጃ፣ በመጨረሻም በጎሳ ደረጃ ሊታይ ይችላል። እነኝህን መዋቅሮች ጥሶ የሚሄድ ጉዳይ ካጋጠመ በገዳና ቃሉ ደረጃ ይታዩና ይፈታሉ።

ለዚህም የሚረዳ የጉጂ ኦሮሞ ምሳሌያው አነጋገር አለ። ይኸውም:-

| | |
|---|---|
| «dubbii worra gowwaa olla gahaa, | የሞኝ ቤተሰብ ጉዳይ ከጎረቤት ይደርሳል፣ |
| dubbii ollaa gowwaa fira gahaa, | የሞኝ ጎረቤት ጉዳይ ከዘመድ ይደርሳል፣ |
| dubbii fira gowwaa gadaa gahaa. | የሞኝ ዘመድ ጉዳይ ከገዳ ይደርሳል ይባላል። |

ከላይ ካየነው ምሳሌያዊ አነጋገር የምንረዳው አንድ የተወሰነ ግጭትም ሆነ ችግር በቤተሰብ ውስጥ ከተከሰተ እርስ በርስ የመደማመጡና የመከባበሩ ባህል ስላለ በዚያው ቤተሰብ ደረጃ ይፈታል የሚል እምነት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሳያውቁበት ዕድሉን ካልተጠቀሙ የጎረቤት ሽማግሌዎች ጣልቃ ይገቡና ይፈቱታል፡፡ ይህም ሳይሆን ቀርቶ ከዘመዶቻቸው በቤተሰብ ጉባኤ አማካይነት የተከበሩና ተሰሚነት ያላቸውን በማስጠራት ለመፍታት ጥረት ይደረጋል፡፡ ከዚህ ደረጃ በላይ ከሆነ ጉዳዩንና ባለጉዳዮቹን በመያዝ ወደ ገዳ ተቋም ያቀርቡታል፡፡ በሚኤ ቦኮ የአዋጅ ነገራ ወቅትም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት የባልና ሚስት ጉዳይ ይዘው ወደ ፖሊስ ጣቢያና ፍርድ ቤት መሄድ ባህላቸው እንዳልሆነና በእነዚህ ባህላዊ የግጭት መፍቻ መዋቅሮች መፍታት እንዳለባቸው ይደነግጋሉ፡፡

በሽምግልና ወቅት ቀድመው ፈጣሪ (ዋቃ) በሰላም ስላገናኛቸው ያመሰግኑታል፡፡ በመቀጠል እርቁን እርቅ ሰላም እንዲያደርግና በመካከላቸው ተገኝቶ ጉዳዩን እንዲፈታላቸው እግዚአብሔርን ይለማመናሉ፡፡

የሽምግልና ስርዓት በባህላዊ አካሄድ ተበደልኩ ባይ ባቀረበው የጉዳዩን እዩልኝ ጥያቄ መሰረት ሽማግሌ ከመንደሩ ነዋሪዎች በማህበራዊ መዋቅሩ መሰረት የዘር ሀረጉ ይታያል፣ በዕድሜ፣ በንግግር ችሎታ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ባለቸው ተቀባይነት ተመርጠው የሚሰየሙ ናቸው፡፡
የሽምግልናውን ይዘት ስንመለከት በመጀመሪያ ከግራ፣ ቀኙ ወገን መረጃ ይሰበሰባል፡፡ ከቀረበው ምልልስ ከጭብጡ በመነሳት፤ በምን ምክንያት ሊበድል እንደቻለ ማለትም፡- ሆን ብሎ ነው ወይስ በድንገት የተከሰተ ነው? የሚሉት ይታያሉ፡፡ ከዚያ ለበዳዩ አውቆ አድርጐት ከሆነ “የቀን ነገር ነው፤ፍርጃ ነው፡፡ በማለት ተበዳዮ ቂም እንዳይዝ በማስተባበል፤ ለተበዳዩ ደግሞ አውቆ ባይሆንም «ይህ ሰው ተጉድቷል፤ ሊካስ ይገባዋል፡፡» በማለት ሰላምን የማውረድ ሀሳብ እንዳለው ከመረጃ ሰጪዎቼ ገለፃ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

የሚከውኑት (የምናገሩት) ሽማግሌዎችና በሽምግልናው ውስጥ ደግሞ ምልልስና ክዋኔዎችም አሉ፡፡ እንደመረጃ አቀባዬ ገለፃ በሽምግልና ሂደት ወቅት የሽማግሌዎች የእርስ በርስ ምልልስ ከተመለከትን፤የመጀመሪያው ጠያቂ ሽማግሌ የሚሰየመው ካሉት ሽማግሌዎች ውስጥ ማህበረሰቡ ባስቀመጠው ተዋረዳዊ መዋቅር መሰረት በተሻለ ቦታ ላይ ነው ብለው የሚሉትን ነው፡፡ ይኸውም ጎሳው፣ሃይማኖታዊና ባህላዊ ዕውቀት ደረጃው ይታያል፡፡ በዚህ መልኩ ሁለት ሽማግሌዎች ይመረጡና እናንተ እዩ ይባላሉ፡፡ ሌሎች የተበዳዩን፣ የበዳዩን፤ እንዲሁም የሽማግሌዎቹን አጠያየቅ በጥንቃቄ ያዳምጣሉ፡፡ ከዚያ አንዳንድ ነገሮች ፈር ከሳቱ “የትንባሆ

መያዥሀን ልሰርልህ" (coraa siif hidhuu) በማለት ይቅርታ ጠይቆ ተራ በመወሰድ የተሰማውን ስሜት ይናገርና ሀሳቡን እንደጨረሰ መልሶ ለቀድሞዎቹ ሽማግሌዎች ይሰጣል፡፡ ይህ እንግዲህ "አፍህን በማር..." ተብሎ ጣልቃ እንደመግባት ማለት ነው፡፡

አንዳንዴ ጉዳዮች ይካረሩና በአካባቢ ሽምግሌዎች ሊፈታ ካልቻለ ወደ ጎሳ መሪዎች ማለትም ወደ አባገዳዎች ወይም አባቃሉ ደረጃ የሚደርሱበት አጋጣሚዎችም ይፈጠራሉ፡፡ ለምሳሌ ከግለሰቦች በተነሳ ግጭት የሰው ነፍስ መጥፋትና የንብረት ውድመትን ካስከተለ፤ ፀቡ ከግለሰባዊ ባህሪይ ወደ አካባቢያው መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡ በተለይም የእርስ በርስ ግድያን በተመለከተ፣ የንብረት ውድመትን በተመለከተ ከአካባቢው ሽማግሌዎች አቅም በላይ ስለሆነ ከላይ በተጠቀሱት ትላልቅ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ተቋማት ዘንድ እንደሚታዩ ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

በሽምግልና ወቅት የሚነገረው በዋናነት ለበዳይና ተበዳይ ነው፡፡ ቀጥሎ በቦታው ለተገኙት የሀገር ሽማግሌዎችና የበዳይና የተበዳይ ወገን ነው፡፡ ከአጥኚው የቀድሞ ተሞክሮና ከተሰበሰው መረጃ፣ ለመገንዘብ እንደተቻለው፣ በቦታው የተገኙ ታዳሚዎች ከሽማግሌዎቹ ተግሳጽና ምሳሌያዊ ንግግሮች ከሚሰሙት መልዕክት ተነስተው እራሳቸውን ወደሚፈለገው አቅጣጫ እያስተካከሉ ይሄዳሉ፡፡ ከቀረበው ጭብጥ ተነስተው ነገሮች እንዲፈቱ ሁሉም የራሳቸውን ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የሽማግሌዎችን ቃል አልቀበልም ባለው ላይ በዝምድናና በታላቅነት ጫና ለመፍጠር ይጥራሉ፡፡ በተለይም የበዳይና ተበዳይ ዘመዶች፤ ሽማግሌዎቹ ያዩትን ጠንካራና ደካማ ጐን በማንሳት ምን መሆን እንዳለበት ለመወያየት አስፈቅድው ዞር ብለው ይወያየሉ፡፡ በአካሄዱም "እስቲ ሽንተን እንመለስ"(fincoofnee haadeebinu) በማለት ፍቃድ ይጠይቃሉ፡፡ አሊያም ሽማግሌዎቹ እራሳቸው (mee finco'aa kootta) በማለት ተማክረው የመፍትሔ ሀሳብ ይዘው እንዲመጡ ይደረጋሉ፡፡ ይህ አባባል በኦሮሞዎች ዘንድ ከሚጠቀሙት ፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ አንዱ ሲሆን አቻ ትርጉሙም በቅደም ተከተል ተማክረን እንመለስ የሚልና ተማክራችሁ ኑ እንደማለት ነው፡፡

የዚህ ሂደት ጠቀሜታ በዳዩም ይሁን ተበዳዩ ያልተረዳውን ነገር በማስረዳት እሺ ወይም እንቢ እንዲሉ ቤተሰባዊ ጫና መፍጠሪያ መንገድ ነው፡፡ ከዚያ ሲመለሱ "ሽንታችሁ መጣችሁ?» በማለት ሽማግሌዎች ይጠይቃሉ፡፡ "አዎ! መተናል"፡፡ በማለት የደረሱበትን ሀሳብ ያስረዳሉ፡፡

በዚያም ጉዳዩ እንደ ሁኔታው ይፈታል፡፡ አሊያም በይደር ይተላለፍና ጉዳዩ በቀጠሮው ቀን ይታያል፡፡

የሽምግልናውን አውድ በተመለከተ ማህበረሰቡ ለሽምግልና በዋናነት የሚጠቀምበት ቦታ "ኦዳ" ስር ነው፡፡ "ኦዳ" የዋርካ እንጨት ሲሆን የጉጂ ኦሮሞ እንደ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ማዕከል አድርጎ ይጠቀምበታል፡፡ ማህበረሰቡ አንድ ማህበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ወይም ሃይማኖታዊ ጉደዩችን ተሰባስቦ የሚፈታበት ስፍራ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ መረጃ አቀባዩ ገለፃ እንደተረዳሁት የተበዳዩም ሆነ የበዳዩ ቤት ተሂዶ አይታይም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ሳይታይ ማን እንደበደለ፤ ማን ደግሞ እንደተበደለ ሳይታወቅ አንዱን ከፍ አንድን ደግሞ ዝቅ አርጐ ማየት ስለሚመስል ነው፡፡ ስለዚህ ለሁሉም አማካይ በሆነ ቦታ ተመርጦ የሚካሄድ ሂደት ነው፡፡ አሊያም አማካይ ቦታ ላይ በጠዋት ይከናወናል፡፡ የባልና ሚስት ጉዳይ ከሆነ ደግሞ በራሳቸው ቤት ወይም ተበዳይዋ ከተከለለችበት ቤት ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡

የሽማግሌዎቹ አቀማመጥ እርስ በርስ እየተያዩ ለመነጋገር እንዲያመቻቸው ተብሎ ክብ ሰርተው ይቀመጣሉ፡፡ በዳይና ተበዳይ ደግሞ ጐን ለጐን አይቀመጡም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ እስካልተፈታ ፀበኛ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ሽምግልና ብዙውን ጊዜ የሚከናወነው በጠዋት ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም ሽማግሌዎች ቡሉኮዋቸውን ተከናንበው ሜዳው ላይ ቁጭ ብለው የዕለቱን ጉዳይ ይፈታሉ፡፡ ጊዜው በጠዋት የተመረጠበት ምክንያት፡- ታዳሚው ባዶ አፉን ማለትም መጠጥ ሳይጠጣ በትክክለኛ አእምሮው ለመወያየት እንዲያመች ሲሆን፣ ሌላው በጠዋቱ ጉዳዩን ከፈቱ በኋላ ወደየግል ስራቸው ለመስማራት እንዲያመቻቸውም ጭምር እንደሆነ የአጥኚውም የቆየ ግንዛቤ ነው፡፡

በመጨረሻ በዳይ ለተበዳይ እንደጥፋቱ መጠን ባህሉ ባስቀመጠው ህግ መሰረት እንድክስ ተደርጎ የማስማማት ሂደቱ ይፈጸማል፡፡ በዚህ ወቅት አንዳንድ ተበዳዮች የተካሱትን ከወሰዱ በኋላ እኔ በእናንተ (በሽማግሌዎች) አማካይነት እውነትን አግኝቻለሁ፤ ነገር ግን ከወንድሜ/እህቴ ላይ ካሳ አልበላም በማለት የሚመልሱም እንዳሉ ካገኘሁት መረጃ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የግጭጥት አፈታት መዋቅሮች እንደየችግሩ ወይም ጥፋቱ መጠን በሂደት ከስር ወደላይ የሚመጡ ናቸው፡፡ በቃሉና ገዳ ተቋም ደረጃ ትናንሽ ችግሮችን

ይዘው መሄድ አይፈቀድም፤ ቢኬድም እንደገና ወደሚመለከተው ክፍል ሄደው ጉዳያቸውን እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡

2. የቃሉ መማክርት (gumii qaalluu)

በቃሉ አማካይነት ከሚፈቱ የግጭት ማስወገጃ ከበራዎች ውስጥ የጎንዶሮ ከበራ አንዱና ዋንኛው ነው፡፡ ይህ ከበራ የሚካሄደው ደግሞ በቃሉ መማክርት አባላት በኩል ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ሂደት እንዴት እንደሚያስፈጽሙና በምን ዓይነት መንገድ እንደሚቋጩት ከዚህ በመቀጠል በዝርዝር ለማየት እንችላለን፡፡

I. የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ ሂደት

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ጎንዶሮ ማለት ይህ ክስተት ዳግም (ሁለተኛ) በእኔ/በእኛ እንዳይመለስ ወይም እንዳይከሰትብን እንደማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ከዱር አራዊቶች ውስጥ ጅብ ወይም አንበሳ ሊሆን ይችላል፤ በተደጋጋሚ እየመጡ ከብቶች ከመስክም ሆነ ከበረት የሚያጠቁ ከሆነ፤ ይህ ነገር ጥሩ አይደለም፤ የጎንዶሮ ከበራ መፈጸም አለብኝ በማለት ያከናውናል፡፡ ይኸውም ከበራውን ሀብት ያለው በግ ወይም ከብት በማረድ ያካሂዳል፡፡ የሚያርደው የሌለው ደግሞ በምትኩ ውሃ በማዞር፣ እንቧይ በማረድ ይህን ችግር ዳግም እንዳይከሰትበት ክዋኔውን ይፈጽማል፡፡

በማንኛውም የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራ ወቅት የሚከናወን እርድ ሞራው ይታያል፡፡ ከዚያም ስለተከወነው ሁኔታ ከሞራው በማየት የሚሉት አላቸው፡፡ ስለክዋኔው መሳካቱን አሊያም አለመሳካቱን ይናገራሉ፡፡ ካልተሳካ ሌላ እንዲታረድ ይደረግና ሞራው እንደገና ይታያል፡፡ ለዚህ ክዋኔ ከጉረኖው ውስጥ ሲወጣ ቀልቡ ያረፈበትን እንጂ እንዳገኘ ወስዶ አያርድም፡፡ እንደነሱ አባባል ‹‹እኔን እረደኝ ብላ (kan fariste) የምትለውን›› ነው የሚያርደው፡፡

ሌላው ግለሰብ ከግለሰብ ጋር አሊያም ከአጎራባች ክልል ህዝብ ጋር በሚፈጠሩ ግጭቶች ደም መፋሰስ ሊከሰት ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት ግጭቱ እንዲያበቃ፣ ለወደፊት ደግሞ በሰላም እንዲኖር የጎንዶሮ ከበራ ይፈጸማል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚፈጸመው ጎንዶሮ በአባቃሉና በመማክርት አባላቱ አማካይነት የሚከወን ነው፡፡ ይህንኑ ሀሳብ Asebe እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

> The leaders of the qaalluu institution were the only legitimate and respected officials in prayers, blessings and conflict mediation processes together with gadaa leaders (Asebe, 2012፣16).

ሌላው እንደ መረጃ አቀባዮቼ ገለጻ አንድ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም፡- በጊዚያዊ ግጭት ወይም በመጠጥ መንፈስ አሊያም ሳያስበው አውሬ መስሎትና እንዲህ ባሉ ክስተቶች እገላለሁ ብሎ ሳያስብ በእጁ የሰው ነፍስ ሊጠፋ ይችላል፡፡ይህ ክስተት ደግሞ በማንኛውም የሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከሰት ነው፡፡ ነገር ግን ጉጂነታቸው እንደሚያገናኛቸው ያምናሉ፡፡ እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለጻና ከአጥኚውም የቀደመ ዕውቀት ወንጀል ፈፃሚው በዚህ ጊዜ በራሱም ሆነ በቤተሰቦቹ ላይ የበቀል ጥቃት ሊሰነዘር እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል ባደረገው ነገር ተፀፅቶ ለቤተሰቦቹ በፍጥነት መልዕክት እየተቀባበሉ ካስተላለፉ በኋላ እግሬ አውጭኝ እያሉ ወደ አባቃሉ ተቋም ይሸሻሉ፡፡ አሊያም ወደገዳ ማዕከል ይሸሻሉ፡፡ ይህ ማድረገረ ካልተቻለው በአቅራቢያ ተቀባይነት ወዳላቸው የባህል ሰዎች ዘንድ በመጠለል ለገዳ ወይም ለቃሉ እንዲያሳውቁላቸው ያደርጋሉ፡፡ ከዚያም የተፈጠረውን ክስተት ለአባቃሉ ያስረዳሉ፡፡ አባቃሉም በአስቸኳይ ወደስፍራው አባገዳንና ሽማግሌዎችን፣ አሊያም ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችን መርጦ ወደተበዳዮቹ ቤተሰብ ጎንዶሮ እንዲሉ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ መልዕክቱም «የሞተውም የእኔ ነው፤ የገደለውም የእኔ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ እምነታችን፣ እንደ ባህላችን ጎንዶሮ በሉ» በማለት መልዕክቱን ይዘው ይላካሉ፡፡ እነዚያም የተባሉበት ቦታ በመሄድ በአካባቢው የሚገኙ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችን መርጠው፤ ጉዳዩን በማጣራት የበደለ ክሶ እንዲታረቁና የጎንዶሮ ክዋኔ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

ይህ የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ በተለይ በጉጂና በጌዴኦ መካከል ለዘመናት ተጠብቆና ተከብሮ ያለና የሚኖር ነው፡፡ በተለይም በግጭት ማስወገድ ሂደት ላይ ጎንዶሮ ከተከወነ በኋላ ዳግም ወደዚያ ጉዳይ መግባት እንደመቅሰፍት ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም ይህን ቃል ያፈረሰ አካለ ጎዶሎ ይሆናል፣ ይቆመጣል፣ ሕይወቱ የተመሰቃቀለ ይሆናል፤ አሊያም ይሞታል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ስለዚህ በክዋኔው በስተመጨረሻ ላይ ከዛሬ በኋላ በእንዲህ ዓይነት ስህተት ውስጥ አንገባም፤ ስለተከሰተውም ሁኔታ ዳግም አናስታውሰውም በማለት ቃለ-መሃላ ይፈጽማሉ፡፡ ይህን የጣሰ ደግሞ ያ የእርግማን ቃል ሊደርስበት ይችላል ብለው ያምናሉ፡፡

የጎንዶሮ ክዋኔ የሚካሄደው በስተ-መጨረሻው ላይ ውሳኔውን በዘላቅነት ለማስከበር ነው፡፡ ይህን በዋናነት ማስከበር የሚችለው ደግሞ ቃሉ ነው፡፡ ቃሉ በስተመጨረሻው ሁለቱም ወገን እሺ ብሎ እርቁን በመፈጸማቸው፤ በመጀመሪያ ይህን ጉዳይ ያስፈጸመውን ፈጣሪን ያመሰግናል፡፡ በመቀጠል ሁለቱን ወገኖች ተሯርጠው ለዚህ ያበቁትን የካውንስሉን አባላት ይመርቃል፡፡ ከዚያ ተበዳዮቹ የዕለቱን ግጭት ሳይሆን፤ የድሮ ወዳጅነትንና በሰላም አብሮ መኖራቸውን በማስታወስ ይቅር በማለታቸው ሰላም ከቤታቸው፣ ሰላም ከቁያቸው፣ ሰላም ከጎሳቸው፣ ሰላም ካገራቸው እንዲገባ፣ ዳግም እንዲህ ዓይነት አደጋ አይግጠማችሁ በማለት ይመርቃል፡፡ በመቀጠል በዳዮቹንም ቢሆን ካሁን በኋላ ከእንዲህ ዓይነት አደጋ ይሰውራችሁ፤ ዳግም አይግጠማችሁ በማለት ይመርቃል፡፡ በመጨረሻም አባቃሉ ይህን የሰላም ውል በተለያየ መንገድ በማስታወስ እንዳያገረሽና ዳግም እንዲህ ዓይነት ግጭት ውስጥ እንዳይገቡ ይረግማል፤ ታዳሚዎቹም እርግማኑን ከአባቃሉ በኋላ ደግመው በማለት ያረጋግጣሉ፤ ይህም ድርጊት እንደ ቃለ-መሃላ ይቆጠራል፡፡ ታዲያ ይህን ቃለ-መሃላ የጣሰ ደግሞ ያ የእርግማን ቃል ሊደርስበት ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ሁሉም በፍርሃት እንደሚያከብሩት ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ይህንኑ ሀሳብ Asebe በሚያጠናክር መልኩ ሲገልጸው፡-

> Finally, the *Abba* Qallu concludes the ceremony by blessing the peace to be durable and at the same time cursing any attempt of retaliation/ avenge (Asebe, 2007:67).

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አባቃሉ በስተመጨረሻ ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራው ላይ በመመረቅ፤ ዳግም ለበቀል እንዳይነሳሱ ደግሞ በዚህ ድርጊት ውስጥ እንዳይሳተፉ የሚያስጠነቅቅ እርግማን ይፈጽማል፡፡

ጎንዶሮ በሀገር ሽማግሌዎች፣ በአባገዳና እንዲሁም በቃሉ ደረጃ ይከወናል፡፡ ይህ እንግዲህ ከከዋኞቹ አኳያ ሲሆን፤ ጎንዶሮ ሊፈጸምለት ከሚገባው ክስተቶች አኳያ ደግሞ ያየን እንደሆነ በጉጂ ኦሮሞ ጎሳዎች መካከል የእርስ በርስ ግጭት የተፈጠረ ከሆነ እንደ ችግሩ ስፋትና ክብደት፤ ማለትም የጉጂ ኦሮሞ ከቦረናና ከአርሲ ኦሮሞ ጋር እንዲሁም ከሲዳማ፣ ከኮይራና ከጌዴኦ ብሄር ብሄረሰቦች በተለያየ ወቅት፤ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶች የሚፈቱት በቃሉ፣ በአባገዳዎች፣ ሀዩዎች (የባህልና ሃይማኖት አዋቂዎች)ና የሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት ነው፡፡

እንደ መረጃ አቀባዮቹ ገለጻ ከተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ጋር የተከሰተን ግጭት እርቅ ለማውረድ የፈለገው ወይም እርቅ እንዲወርድ የሚፈልገው አካል አባገዳዎች፣ ሀዩዎችና የሀገር ሽማግሌዎች በአንድ ላይ ይሆኑና በየራሳቸው ጎሳ ውስጥ ሆነው ሰላሙን እንዲያወርድላቸው ለአምላካቸው ጸሎት ያደርሳሉ። ጦርነቱ እንዲቆም ከህዝቡ ጋር ይለምናሉ።

ለምሳሌ ግጭቱ በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ብሄር መካከል የተከሰተ እንደሆነ፤ በሁለቱም ህዝቦች የእርስ በእርስ ጦርነት ያስከተለ ከሆነ፤ ከጌዴኦ ብሄር በኩል ወደ ጉጂ ኦሮሞ አሊያም ከጉጂ ኦሮሞ በኩል ወደ ጌዴኦ ወገን አምስት ሴቶችን በመምረጥ ጦርነቱ በሚካሄድበት ድንበር አካባቢ ይላካሉ። እነዚያ አሮጊቶችም ጩኸት እያሰሙ ይሄዳሉ። ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት በኦሮሞም ሆነ በአጎራባች ብሄር ብሄረሰቦች ባህል ሴቶችን መግደል የተወገዘ በመሆኑ ማንም ስለማይገድላቸው ነው። ስለዚህ ለግጭቱ መንስኤ የሆነው አካል ወኪል ሴቶቹ የእግዚሐብሄር ሰላምታ በመጠየቅ፣ ከጉጂ ኦሮሞ ወይም ከጌዴኦ የተላኩትን የሰላም መልዕክት ይዘው እንደመጡና እነሱ በራሳቸው በተለይም፡- በጉጂ ኦሮሞ «እኛ ሰላም ነን፤ እኛ መልዕክት ነን፤ ተቀበሉን» («nuuti nagaadha; nuuti ergaadha; nurraan fuudha.») ይላሉ። የተቃራኒው ወገን ደግሞ ሴቶቹ ይህን ዓይነት መልዕክት ይዘው ሲመጡ አንደኛ የሰላም ተምሳሌት በመሆናቸው፣ ሁለተኛ ሴቶች በመሆናቸው፣ ሦስተኛ ከሩቅ አካባቢ ተጉዘው ስለመጡ፤ ጩኸቱን ሰምተው የተሰበሰቡት የሀገር ሽማግሌዎች «ጥሩ ነው፤ ለማንኛውም አረፍ በሉ።» በማለት ማልደው ስለወጡ ውሃ፣ ወተትና ምግብ ጋብዘው፤ እንዲህ ዓይነት ችግሮች ድሮም እንዳሉና፤ አሁንም የሚከሰት መሆኑን በማስረዳት የተሰበሰቡት ሽማግሌዎች በአባገዳ መሪነት እሽታውን ይገልጹና ሴቶቹን ይሸኛሉ። ሴቶቹም ተሰናብተው ምላሹን ይዘው ወደ ላካቸው ወገን ይመለሳሉ። የላከውም አካል መምጣታቸውን በጉጉት እየጠበቀ ስለሚቆይ ሲመጡ እንኳን በደህና መጣችሁ በማለት ምላሻቸውን ይጠይቃሉ። እነሱም ያኛው ወገን ለእርቅ ዝግጁ ከሆነ የሁለቱም ወገን አባገዳዎችና የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የተጋጩ ቤተሰቦች በተገኙበት እርቁ ይከናወናል።

በእርቁ ወቅትም የጉጂ ኦሮሞ ከብት ያቀርባል። የጌዴኦ ብሄር ደግሞ ቦካ (የማር ጠጅ) ያቀርባል። ለጎንዶሮ የቀረበውን ከብት የሚያርደው ከሁለቱም ወገን ያልሆነ ሰው ይደረጋል። ምክንያቱም ጎንዶሮ በራሱ ይህ ግጭት በዚህ ይብቃ፤ ዳግም አያምጣው፤ የሚል ሀሳብ ያለው ስለሆነ ያን ጦስ ይዞ ወደ ማህበረሰቡ እንደመመለስ ስለሚቆጠር ነው።

በቃሉ የሚከወን የጎንዶሮ ከበራ በከባድ ግጭጦች መፍታት ላይ ያለው ሚና ከሌሎች በበለጠ ወሳኝ ነው፡፡ ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው የ Asebe, (2007) ጥናታዊ ስራ ውስጥ በጉጂና ጌዴኦ መካከል ከተከሰቱት ግጭቶች ውስጥ በመንግስት መከላከያ ሰራዊት ጣልቃ ገብነት የተካሄደው የግጭት አፈታትና በቃሉ ከበራ የተፈታው የሁለቱ ህዝቦች ግጭት ዘለቄታ የነበረው ሁለተኛው እንደነበር እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

> *The 1995 conflict for example, ended up by the military intervention. Without resolving the fundamental question of the groups by the time - fair and free territorial rearrangement - the government opted for process of 'peace formation', which the Guji in Wonago district reject as illegitimate both from the practical means used and intended goals desired. They argue that no peace formation would be legitimate unless the root causes of the conflict are resolved. Practically, they saw it as violation of the principles of gondoro tradition as the practice would only be conducted by Guji Abba Qallu in cooperation with the two Abba Gadas. Coming back to the post 1998 period, informants are divided in their views. There is a common understanding that the 1998 conflict ended by intervention of elders. Unlike the 1995 case, government authorities also recognised the role of traditional methods of conflict resolution through the gondoro practice. The Guji Abba Qallu was brought from the jail to perform the blessing on the ceremony and taken back to prison up on completion of the ceremony (Asebe,2007:8)*

ከዚህ በተጨማሪ ስለጎንዶሮ ጥቅም ሲገልጹ በዚህ መንገድ የተፈታ ግጭት ዘላቂ ሰላምን ያመጣል፡፡ ነገር ግን በዘመናዊ ህግ መሰረት በፍርድ ቤት ቀርቦ የተፈረደበት ወንጀለኛ ቅጣቱን ጨርሶ ከማረሚያ ቤት ሲውጣ ከሟች ቤተሰብ ውስጥ ለበቀል የሚነሳ አይጠፋም፤ የሟች ቤተሰብ እንዲህ ዓይነቱን ባያስብም ያ የህግ ታራምው በራሱ በስጋት ይኖራል፡፡ ነገር ግን በጎንዶሮ ከበራ የተፈታ ከሆነ ሁለቱም ወገን ለቃለ-መሃላቸው ተገዥ ስለሚሆኑ ስጋት አይፈጠርም፡፡

ስለቃሉና አባገዳ ተቋማት ክብር ሲገልጽ በአጎራባች ክልሎች አካባቢ የፈለገ ግጭቶች ቢከሰት ሌላውን አከባቢ ቢዳፈሩም፤ የቃሉና የገዳ ተቋም ወሰን ጥሶ የሚጋጭ አይኖርም፤ ያከበራል። ለዚህ ማሳያ እንደመረጃ አቀባዩ በ1987 ዓ.ም. በጉጂና በጌዴኦ መካከል በነበረው ግጭት የአባቃሉ ተቋም አካባቢም ሆነ በአባገዳ ደንቦባ ወሰን ከውስጥ ባሉ የጌዴኦ ህዝብ ላይም ሆነ፤ በጌዴኦ ክልል ውስጥ ባሉ የጉጂ ኦሮሞ ህዝብ ላይ ጥቃት እንዳልተሰነዘረ ይገልጻሉ። በወቅቱ አባገዳ ደንቦባ የሁለቱ ድንበር በሆነው (የጨጨ ወንዝ) ላይ በመሄድ ባንድራ እንደተከሉና ከሁለቱም ወገን ያን ጥሶ ጥቃት እንዳላደረሱ መረጃ አቀባዮቹ ገልጸውልኛል።

ይሁን እንጂ የቃሉ ወሰን የተቋሙ መገኛ ብቻ ሳይሆን በስሩ ያሉ ጎሳዎች ወሰን እንደሆነ ነው። በሌላ በኩል የገዳዎች ወሰንም እንዲሁ የተቋማቸው ዙሪያ ብቻ ሳይሆን በስራቸው የሚያስተዳድሩት ቦታና ህዝብ ማካተት አለባቸው። ስለዚህ የቃሉንም ሆነ የገዳን ወሰን ማክበር ካለባቸው ይህን ሁሉ ማካተት ነበረባቸው።

ከዚህ በመቀጠል የጎንዶሮን ሙሉ ክዋኔ በንጥል-ጥናት ከነትንተናው እንደሚከተለው እንመልከት።

### የጎንዶሮ ንጥል ጥናት-1

በጉጂ ኦሮሞዎች ዘንድ እርስ በርስ የሚፈጠር የግዲያ ወንጀል ግጭትን የማስወገድና የጎንዶሮ ከበራ ክዋኔ።

> የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ (2001 ዓ.ም.) አንዱ የአጎታችንን ልጅ የሆነውን መሳሪያ ባርቆበት ባጋጣሚ ገደለው። እኛ ታዲያ ከነዚያ ሰዎች ጋር ተቀያይመን እያለን እነሱ ቶሎ ብለው ወደ አባቃሉ ገልማ ሄደው የተፈጠረውን አስረዱ። ጉጂ ደግሞ ጎንዶሮ ማለት ስላለበት ቃሉ ለእኛ(የሟች ቤተሰብ) በሽማግሌዎች «የሞተውም የእኔ፤ የገደለውም የእኔ ነው። ስለዚህ በሽማግሌዎቹ አማካይነት ጉዳዩን በመያዝ ጎንዶሮ በሉ» በማለት ደብዳቤ ጽፎ ላከ። እኛ አሁን ጎንዶሮውን ፈጽመናል። ነገር ግን የታረደውን ከብት ስጋ አላየንም። የጦስ መጣያ ገደል (bowwaa bitaa) የሚባል አለ፤ ምንድነው ይሄ ፉርፉርሳ የሚባልበት ቦታ፣ ከለዶ ቀበሌ ወዲያ የጦስ መጣያ ገደል፣ ለጦስ ማውጫ የታረደውን ከብት

የሚጣልበት ቦታ፣ ወደዚያ ወስዶ ነው የተጣለው፡፡ የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ተምሳሌተ ክዋኔ በቃሉ ተቋም (ገልማ) ውስጥ አይፈጸምም፤ ጎንዶሮ የራሱ የሆነ ቦታ አለው፡፡ ለዚህ ነው የፉርፉርሳ ጦስ መጣያ ገደል ላይ የተፈጸመው፡፡

ከእኛ ወገን የሆኑት በሽማግሌዎች እየተመራን ወደ ጎንዶረሮው ቦታ አመራን፡፡ የገዳይ ወገን እንደዚሁ መጡና ማዶ ለማዶ አስቀምጠውን በመካከላችን ደግሞ ውሃ አለ፡፡ ከዚያ ሽማግሌዎች ከመሀል ሆነው፣ ነጭ መጋረጃ ጋርደው (ነጠላ ጋቢ) ከመሀል ተደርጎ፣ ጥቁር በግ መጣ፡፡ ጠጅ (ቦካ) መጣ፡፡ በጉን የሚያርድ ከሌላ ወገን የሆነ ሰው መጣ፡፡ ያን በግ አርደው፣ አንጀቱን አውጥተው እዚያ የተገኙትን ቤተሰብ ባጠቃላይ በእሱ ይተበተብና የታሰራል፡፡ ያ ቀድሞ የተጋረደውን መጋረጃ የሃይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎቹ ከቀረበው ጠጅ ላይ እንትፍትፍ (biifuu) እያሉ ይገልጡትና ቅድም ጀርባ ለጀርባ ቆመን የነበርነውን ወገኖች፤ ፍታቸውን አዙረው እንዲገናኙና እንዲሳሳሙ ተደረገ፡፡ ያን የታረደውን ከብትም አልተበላም፤ ያ ለጎንዶሮው የቀረበውን በግ ያረደው ሰው ነው ስጋውን ይዞት የሄደው፡፡ ምክንያቱም ጦስ የወጣበት አይደል? (mulqaa mitii?) ስለዚህ ያንን ጠጅ ብቻ እዚያው ጠጥተው፤ ጎንዶሮ ብለው ተለያየን፡፡ እነዚያ ሰዎች ለብዙ ዓመት ተሸክመውት የነበረውን ጭንቅ አውርደው ወደ እኛ ቤተሰብ በመምታት፤ በልተው፣ ጠጥተው ሄዱ፡፡ ከዚያ በኋ እኛም ተጠርተን እነስ ቤተሰብ ጋ በመሄድ እንደዚያው በልተን፣ጠጥተን ተመለስን፡፡ ከዚያ በኋላ እንደቀድሞው ሰላም ወርዶ አብሮ መኖር ተጀመረ፡፡ (6/7/2007 ዓ.ም. ኡዴሳ ዲራሞ ዱካሌ፣ ዕድሜ 36፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

## የጎንዶሮ ንጥል ጥናት-2

ሌላው አንድ የጉጂ ኦሮሞ ተወላጅ ሆን ብሎ፣ አስቦበት የራሱን ወገን አይገድልም፡፡ ነገር ግን ባጋጣሚ በተፈጠረ ጠብ፣ መሳሪያ ባርቆበት፣ ወይም አውሬ መስሎት በርቀት ተኩሶ ወይም በጦር ወግቶ ሊገለው ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ በመግደሉ በወኔ፣ በጀግንነት ስሜት አያቅራራም፡፡ በተከሰተው ጉዳይ በመደናገጥ እንደሚገልጽና ጉዳዩ ወደ አባቃሉ ወይም አባገዳ ደርሶ እንዴት የጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራው እንደሚከናወን መረጃ አቀባዮቹ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

አንድ ወቅት ማለትም ወደ 1978 ዓ.ም. ገደማ ነው፡፡ አቶ አዱላ ጫራቃ የሚባል ሰውዬ ነበር፡፡ በእጁ ጦር ይዞ ወደ ዳንጎ ቀ/ገ/ማ ጫካ ለጫካ እያቆራረጠ ከቢዮ ተነስቶ ይሄድ ነበር፡፡ የሆነ ሀሳብ ውስጥ ሆኖ ሲጓዝ በድንገት ገጫካው

ውስጥ የኮሽታ ድምጽ ይሰማና ደንገጥ ብሎ ይመለከት ጀመር፡፡ አሁንም ሲንኮሻኮሽበት ድምጹን በሰማበት አቀወጣጫ ጦሩን ይሰደዋል፡፡ ከዚያም የሚያቃስት ሰው ድምጽ ይሰማል፡፡ ከዚያም በስህተት ሰው እንደወጋ ተረዳ፡፡ ገዳዩ ጭንቅላቱን ይዞ፣ ጦሩን ጥሎ፣ ‹ጉድ ሆንኩ!፣ ወይኔ ጠፋሁ!፣ ኡ!-ኡ!-(nan bade! Uu..arrii..)› እያለ ይጮህ ጀመር፡፡ ከዚያ ያንን ጩኸት ሰምተን በአቅራቢያው የነበርነው ሁሉ ወደዚያ ሰው እንሮጥ ጀመር፤ ከዚያም እደደረስን ገዳዩን ይዘን እንዲረጋጋ አደረግነው፡፡ ያ የተወጋው ሰውዬ ድንገት የመትረፍ ዕድል ካለው ብለን የተወሰኑት ሄደው እንዲያዩት ተደረገ፡፡ ነገር ግን ተስፋ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ ገዳዩን ዞር እንዲል አደረግነው፡፡ ምክንያቱም በድንገተኛ ክስተቱ አንዳንድ መታገስ የማይችል የሚቹ ቤተሰብ ሊበቀል ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ደም መቃባቱን ያባብሰዋል፡፡

ስለዚህ ያ ሰው ጉማ ከፍሎ፤ ጎንዶሮ እስከሚባልና እስከሚታረቁ ድረስ እራሱን ይሸሽጋል፡፡ ከማንም ጋር ግንኙነት አይፈጥርም፤ እራሱን አግልሎ ይኖር ነበር፡፡ ከባለቤቱም ጋር አብሮ አይተኛም፡፡ ጸጉሩን፣ ጺሙንና ጥፍሩን አይቆረጥም፡፡ የቀን ልብሱንም አይለውጥም፡፡ በዚህ መልክ በጉዳዩ ማዘኑን ይገልጻል፡፡ በጣም ይሰቃያል፡፡ ስለዚህ ችግሩ እንደተከሰተ ይህን ጉዳይ ቶሎ ብለው ወደ አባቃሉ አደረሱ፡፡ ቃሉም ወደ ሚች ቤተሰብ ሽማግሌዎችን ለእርቅ ተያዙልኝ/ እሺ በሉኝ (naaf qabamaa) በማለት ይልካል፡፡ ሽማግሌዎቹም መልዕቱን በመያዝ አባቃሉ እንዲህ ብሏል በማለት ያቀርባሉ፡፡

የሚች ቤተሰብም የቃሉን መልዕክት እንቢ፣ አሻፈረኝ እንደማይባል፤ በባህሉም ሆነ በእምነቱ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ መልካም ነው፤ እሺ እንያዛለን (ለውይይት እንቀርባለን)፤ ነገር ግን ይህ የቤተሰብ ጉዳይ ነው፤ የጎሳ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ተማክረን መልሱን እንመልሳለን በማለት ይገልጻሉ፡፡ የተላኩትም ሽማግሌዎች ቀጠሮ በመያዝ ይመለሱና ለቃሉ የዋሉበትን ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

በቀጠሮው ዕለት በህዝብ በዓል ማክበሪያ ስፍራ (araddaa jilaa) ለመገናኘት ተቀጣጠሩ፡፡ ከዚያ የሚች ቤተ-ዘመድ ቀድመው በሀገር ሽማግሌዎች እየተመሩ ከቦታው ደረሱ፡፡ በመቀጠል የገዳይ ቤተ-ዘመድ እንዲሁ በተቃራኒ በኩል በሀገር ሽማግሌዎች እየተመሩ ከተዘጋጀላቸው ቦታ አስቀመጧቸው፡፡

ከዚያን በኋላ በቅድሚያ በባህሉ መሰረት ጸሎት ተደረገ፡፡ በመቀጠል ስለአሟሟቱ በደንቡ መሰረት ቅድመ ማጣራት ያደርጉ ገቡ፡፡ በመጀመሪያ አባገዳ ከሽማግሌዎቹ ጋር በመሆን ከሟች ቤተሰብ ‹እንዴት ነው የገደለው? ቂም፣ ጠብ ብጤ ነበራችሁ?› በማለት ያጣሩ ገቡ፡፡ የሟች ቤተሰብም ከዚህ በፊት ቂም ብጤ እንዳልነበራቸውና እንደጣሩትም ለዚህ የሚያደርስ ግጭት እንደነበሩ መለሱ፡፡ በማከል እንደ እኛ አስተሳሰብ ይሀን ማለት የምንችለው፡፡ ነገር ግን ከእሱ ጋር ምን እንዳላቸው የምናውቀው ነገር የለም› አሉ፡፡ ከገዳይ ቤተሰብም ተጠየቁ፡፡ ገዳዩም በተናጥል ጠጠየቀ፡፡ እሱም የአጋጣሚ እንደሆነ ገለጸ፡፡ በሂደቱም ቀደም ሲል የነበራቸውን መልካም ግንኙነት፤ ተከባብረው እንደኖሩ ከሦስቱም ወገን ምላሽ ተደመጠ፡፡

የሟችም ቤተሰብ «እኛ እንኳን ምንም ዓይነት ችግር የለብንም፤ ስንገናኝ ሰላምታ ተጠያይቀን፣ ካለን ተገባብዘን ነው የምንለያየው፡፡» በማለት በተለያየ መልኩ ጠብ እንደሌለባቸው አስረዱ፡፡ ከዚያን በኋላ ለአባገዳም ሆነ ለሌሎች ታዳሚዎች ስለጉዳዩ ውይይት ለመጀመር መንገድ መክፈቻ አካሄድ ነው፡፡

አደጋውን ያደረሰው አንድ ሰው ቢሆንም ጦሱ (መዘዙ) የሁላቸውም እንደሆነ የገዳይ ቤተ-ዘመድ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ለግለሰቡ ሰላም መውረዱ፤ ለሁላቸውም እንደሆነ ስለሚረዱና በጎሳ ውስጥ አንድ ችግር ከደረሰ የመረዳዳት የቆየ ባህልም ስላለ፤ ለጉማ (የደም ካሳ) የሚሰጡትን ከብቶች በማዋጣት እየነዱ ይመጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለጎንዶሮው ከበራ ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ጥቁር በግ፣ ቦካ (የማር ጠጅ) እና ውሃ አቀረቡ፡፡

በመቀጠል ገዳዩ ቀደም ሲል ከቤተ-ዘመዶቹ ጋር አብሮ አልመጣም ነበር፡፡ ከበስተኋላ በሌሎች ሽማግሌዎች ተከልሎ እሱ የኋልዮሽ ዞሮ ወደ ጎንዶሮው ስፍራ አመጡት፡፡

አጠቃላይ አካሄዱን ስንመለከት፡- በመጀመሪያ አባገዳ ከመማክርት አባላቱ ጋር ስለግድያው ሁኔታ ካጣሩ በኋላ፤ ‹ለነገሩ ጉዷ ጉዷን አይገድልም፡፡ ነገር ግን ያጋጣሚ ነገር ሆኖ ይህ ከተከሰተ፤ «ዳኑ» ነው፡፡ ሁለቱም ወገን አንድ ዘር፤

አንድ ጎሳ ናቸው እኮ!፡፡ ስለዚህ መቼም ደም ፈሷል፡፡ ገዳዩም የእኔ፣ ሟቹም የእኔ ነው፡፡ ስለዚህ ጎንዶሮ ሊባል ይገባል› አሉ፡፡

ከዚያም በቦታ ላይ ከብቶቹን ማምጣታቸው ቢታዩም ለደንቡ ያህል፣ አምጥተው እንደሆነ ተጠየቁ፡፡ የገዳይም ቤተሰብ ብድግ ብሎ ‹‹አዎ! ይቅር በሉን! ከብቶቹም ቀርበዋል፣ ተቀበሉን›› አሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም ‹‹እግዚኣብሔር ይሁንላችሁ!›› አሉ፡፡ ሽማግሌዎቹ በመቀጠል የሟችን ቤተሰብ ደግሞ ‹‹በሉ በባህላችን መሰረት የበደለ ይክሳል፡፡ ስለዚህ ከብቶቹን ተቀበሉን›› በማለት ጠየቁ፡፡ የሟችም ቤተሰብ እርስ በእርስ ‹‹ሰማችሁ አይደል?›› በማለት የማረጋገጥ ያህል ተጠያየቁ፣ ሌሎችም በተራ ‹‹አዎ! ሰምተናል፡፡›› አሉ፡፡ በመጨረሻም ለሽማግለዎቹ ‹እናንተ ካላችሁ፣ መቼስ ምን ይደረጋል፡፡› በማለት የቀረበውን ሀሳቡ መቀበላቸውን ገለጹ፡፡

ቀጥሎ የገዳዩን ጸጉርና ጺሙን በመላጨት፣ ጥፍሮቹን በመቁረጥ፣ በላዩ ላይ የከረሙትን አልባሳት አውልቆ በመጣል፣ ወደ ጎንዶሮው መቼት ይወሰዳል፡፡ ከዚያም ለጎንዶሮው ክዋኔ የመጣውን ጥቁር በግ፣ ቦካና ውሃ ተይዞ ይኬዳል፡፡ በጉን በገዳዩ ጭንቅላት ላይ ለሁለት ሰዎች በማንጠልጠል ይታረዳል፡፡ በግ ያረደው ከጉጂ ኦሮሞ ውስጥ ያልሆነ ሰው ነው፡፡ ምክንያቱም ጎንዶሮ በራሱ ይህ ግጭት በዚህ ይብቃ፣ ዳግም አያምጣው የሚል ሀሳብ ያለው ስለሆነ፣ በጉም የጦስ ማውጫ በግ በመሆኑ፣ ያን ንኪኪ ከዚያው ለማስቀረት ከማሰብ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ከዚያም በላዩ ላይ በፈሰሰው የበግ ደም ይታጠባል፡፡ በመቀጠል በቦካው (ጠጁ) ደሙን ያስለቅቁታል፡፡ በወቅቱም ቃሉ ከአባገዳውና ሽማግሌዎቹ ጋር በመቀባበል ‹እንደዚህ ማር ሽተት!፣ ዳግም እደዚህ ዓይነት ክስተት አይግጠምህ፣ እንደዚህ ማር ጣፍጥ፣ ከወገንህ ያስማማህ!› እያሉ ይመርቃሉ፡፡ በመጨረሻም በንጹህ ውሃ ያንን ሰውነቱን ያፀዱታል፡፡ ከዚያን በስተመጨረሻ ላይ የተዘጋጀለትን ንጹህ ልብስ በማልበስ ሁለቱን ወገን ወደ ማቀራረቡ ምዕራፍ ይታለፋል፡፡

እስከዚህ ደረጃ ድረስ የማችና ገዳይ ቤተሰብ ፊት ለፊት አልተገናኙም፡፡ ስለዚህ ሁለቱንም ወገን ለማቀራረብ በመጀመሪያ፡-ሽማግሌዎች ነጭ ነጠላ ጋርደው

የሚችን ወገን በአንደኛው አቅጣጫ፣ የገዳይን ወገን ደግሞ በተቃራኒው አቅጣጫ አቆሙ፡፡ በመቀጠል ገዳዩን ሽማግሌዎች ከልለው ከእሱ ወገን ተርታ አስገብተው አቆሙት፡፡ ከዚያም በእሱ ትይዩ በስተጀርባ የሚቹን የቅርብ ዘመድ አቆሙ፡፡ በመቀጠል ቅድም ከታረደው የጎንዶሮ በግ ስጋ ውስጥ አንድ የጎድን አጥንት በማውጣት በእሳት ተጠብሶ መጣ፡፡ ከዚያም ያን አጥንት በቅድሚያ ለገዳዩ ተሰጠው፡፡ እሱም አጥንቱን በጥርሱ እየነከሰና ወደመሬት እንትፍ እያለ፤ በእሱ ትይዩ ከኋላ ላለው የሚች ዘመድ ስሙን እየጠራ «ከኋላዬ የለህም» በማለት ያንን አጥንት ከነጠላው በላይ በኩል እጁን በመዘርጋት ይሰጠዋል፡፡ ያኛውም ሰው በተራው «ከኋላህ አለሁ» በማለት የጎድኑን አጥንት ነክሶ፤ ወደ መሬት በመትፋት መልሶ ይሰጠዋል፤ እንዲህ እየተባባሉ ለሦስት ጊዜ ሳይተያዩ ተቀባበሉ፡፡ በመቀጠል ሽማግሌዎቹ ከመሀል እንደቆሙ፤ የሁለቱም ወገን ቀኝ እጆቻቸውን የኋሊት በመዘርጋት ለሽማግሌዎቹ አሲያዙ፣ ከዚያም ሽማግሌዎቹ በመካከላቸው ተጋርዶ የነበረውን ነጠላ በማንሳ፣ ተቃራኒዎቹን እጅ ለእጅ አያያዙ፡፡ ከዚያም ዞረው እንዲተቃቀፉና እንዲሳሳሙ ተደርጎ፤ እርቁ ወረደ፡፡ (አቶ አዱላ ዋሬ፣ አባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ ጉሚ 5/3/2006 ዓ.ም.)

የታረደው በግና የታረደበትም ብላዋ ወደ ጦስ ማውጫ ገደል (bowwaa bitaa) ይጣላሉ፡፡ ለዚህ ከበራ እርዱን ለፈጸመው ሰው ደግሞ ገንዘብ እንደሚሰጠው ለመረዳት ችያለሁ፡፡ እንደ Salamone, (2004፡141) ገለጻ ይህ የሚያመለክተው ለከበራ የሚዘጋጁ ምግቦች በዝግጅቱ ማንን እንደሚያሳትፍና ማንን ደግሞ እንደማያሳትፍ፣ እንዲሁም የትኛው የምግብ ዓይነት ለማን እንደሚሰጥና እንዴት እንደሚሰጥ ነው፡፡

በሌላ በኩል ከሁኔታዊ አውድ አኳያ የተመለከትነው እንደሆነ ማህበረሰቡ ይህን የጎንዶሮ ከበራ የሚከውነው በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? የሚለውን ይመልስልናል፡፡ ይኸውም፡- ማህበረሰቡ በባህሉ የተወሰነ የአንድ ባህሪ ወይም ገጠመኝ መግለጫ የሆነ፤ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት የሚከናወንበት አውድ ሲለሆነ ነው፤ እሱም የጎንዶሮ ከበራ፡፡ በዚህ ውስጥ መቼቱ፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ ክዋኔውን የሚገዙት የተለያዩ ህግጋት፣ በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ተግባቦት፣ የክዋኔው አተረጓገም የሚከናወንበት መርህና የመሳሰሉት ይካተታሉ፡፡

ይህን የጎንዶሮ ከበራ ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ አተያይ ስንመለከተው የሰው ልጅ በማህበራዊ ተራክቦ ውስጥ በሚያደርገው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ውስጥ ግጭት ሊኖር እንደሚችል፣ ግጭቶቹ ደግሞ ከቀላል እስከ ከባድ ማለትም፡- የሰው ነፍስ ማጥፋትና የንብረት ውድመት ሊስከት መቻሉን፣ ከዚያም አጥፊው የጥፋተኝነት ስሜት አድሮበት መሰደዱን፣ ተበዳዩ ደግሞ ቂም ቋጥሮ የመበቀል አዝማሚያ መፍጠሩን በማሰብ፣ በመጨረሻም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጎጂው የጉጂ ኦሮሞው መሆኑን ተገንዝበው የጎንዶሮ ከበራን እንዳዋቀሩ ያሳየናል፡፡ ይህ ሀገረሰባዊ ዕውቀት በዋናነት በቃሉ ሲገለጹ ይታያሉ፡፡ ይኸውም፡- ቃሉ የገዳና ስልጣን ስያጸድቅ በምርቃት መልክ ምክር አዘል መልዕክቶቹ ውስጥ ይንጸባረቃሉ፡፡ ይኸውም፡- «...ጉጂ ጉጂን አይገድልም፣ ሳያቅ ከገደለ (danuu)፣ ያን አለማወቁን (danuu sana) ተረዱለት...» የሚሉ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል ከላይ ከተመለከትነው የጎንዶሮ ክዋኔ፣ ቃሉም ሆነ ገዳ ወደ ሚች ቤት ሽማግሌዎችን እርቅ ለማስጀመር ሲልኩ «ሚቹም የእኔ፣ ገዳዩም የእኔ ነው፡፡» በማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ልክ

«ሀዘንሽ ቅጥ አጣ፣ ከቤትሽ አልወጣ፣
የገደለው ባልሽ፣ የሞተው ወንድምሽ፡፡» እንዲሉ ማለት ነው፡፡

ምክንያቱም ሁለቱም ወገን የጉጂ ናቸው፤ በሌላ አባባል ሁለቱም ወገን የቃሉና የገዳ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቃሉም ሆነ ገዳ ለሁለቱም አንድ መሆኑንና እነሱንም በማስማማት አንድ ለማድረግ የተጠቀሙባቸው አገላለጽ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ለክዋኔዎቹ ማስፈጸሚያ ስነ-ልቦናዊ እርካታን በሚፈጥር መልኩ ለባህላዊ ቁሶቹ ተምሳሌታዊ በማድረግ በገዳይ፣ በሚች ቤተሰብ፣ ለጎንዶሮ ከበራ በቀረቡ መከወኛዎችና ድርጊቱን በሚከውኑት መካከል ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች እንዲከወኑ ተደርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከበራ ቃላዊ ያልሆነ፤ ነገር ግን ልክ እንደ ስነ-ልሳናዊ ጉዳዮች በርከት ያሉ ትእምርቶች ያሉበትና እያንዳንዱ ትእምርት ደግሞ ትርጓሜ የሚያገኘው በበቀለበት ባህል ባለው የምግባርና የትውፊት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ Bell, (1997፡44) ትገልጻለች፡፡

ስለዚህ እነዚህን ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም አተያይ ብንመለከት፡- በመጀመሪያ ደረጃ የክዋኔው ማጀቢያና ማስፈጸሚያ ቁሳዊ ባህሎችን በኦሮሞ ዘንድ ጥቁር የጥሩ ነገር ተምሳሌት ነው፡፡

ይህ ማለት በጉጂ ኦሮሞ የዓለም አተያይ ‹ዋቃ ጉራቻ›፣ ጉጂ ‹ጉራቻ›፣ ‹ቢሻን ጉራቻ› በማለት ንጹህነትን ወይም ጥርት ያለ ያለ የሚለውን ፍች እንዲይዝ አድርገው ሲጠቀሙበት እናያለን፡፡

ለአብነት ያህል፦ አንድ የጉጂ ኦሮሞ ‹‹እኔ ጉጂ ‹ጉራቻ› ነኝ፡፡›› ካለ የቀለሙ ተምሳሌትነት እራሱን ንጽህ ጉጂ (typical) ነኝ ለማለት የተጠቀመበት አባባል ነው፡፡ የበጉ መልክ ጥቅር የሆነበት ጥቁር ጥሩ ተስፋን፣ ለደስታ ማብሰሪያነት እንደሚወክል ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከበራ የሚያመለክተው ሰውነቱ በደም መቆሸሹን (የሰው ነፍስ በእጁ መጥፋቱን) ሲሆን፤ ይህ የሰው ደም ደግሞ የሚጠራው፤ በበጉ ደም መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንደ ኦሮሞ አተያይ ደም አንድም መጥፎ ዕድልን ማሳለፊያ ተደርጎ ይታመናል፡፡ ሌላው መስዋዕት በሚቀርብበት ወቅት ደሙን ወደ ላይ ሲረጭ ለእግዚአብሔር እንደመስዋዕት ይቆጠራል፤ ለሰው ደግሞ ደሙ ተመልሶ ሲወርድ እንደምርቃት ወይም በረከት ይቆጥሩታል፡፡

ስለዚህ ለገዳዩ ተስፋንና ጥሩ ስሜትን ያጎናጽፈዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመቀጠል በቦካው ያንን ደም የሚያጸዱት ተምሳሌታዊ ክዋኔ ደግሞ ቦካ በጉጂዎች ዘንድ አበባን (daraara)፣ ጣፋጭነትን (Mi'aa) ፣ መልካም መዓዛን (hurgaa) ይወክላል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል ነፍስ በማጥፋቱ መልካም ስሙ፣ ምግባሩ፣ ጉጂነቱ ሁሉ ጠፍቶ ነበር፡፡ ከማህበረሰቡም ተገልሎ ነበር፡፡ ታዲያ በዚያ ቦካ ሲያጥቡት በቃሉ ወይም በአባገዳና ሽማግሌዎቹ በመቀባበል እንደዚህ ማር ሽትት!፣ ዳግም እደዚህ ዓይነት ክስተት አይግጠምህ፣ እንደዚህ ማር ጣፍጥ፣ ከወገንህ ያስማማህ ወ.ዘ.ተ. እያሉ ይመርቁታል፡፡ ከዚያን በኋላ ይህ ክዋኔ የቀድሞውን መልካም ስምና ምግባር የማስመለስ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመጨረሻ በውሃ እንዲታጠብ የሚደረገው ተምሳሌታዊ ክዋኔ ደግሞ በጉጂ ኦሮሞ አተያይ ውሃ የንጽህነት ወይም የምርጥነት ገላጭ ነው፡፡ ንጹህ ውሃ ለማለት ጥቁር ውሃ (bishaan gurraacha) ይላሉ፡፡ ባጠቃላይ ውሃ ከፈጣሪ የተሰጠ፤ ንጹህ ነገር እንደሆነ በጉጂዎች ይታመናል፡፡ ሰለዚህ በስተመጨረሻ በውሃ መታጠቡ ገዳዩ ከአሁን በኋላ ከሀጢያትህ ነጽተሃል እነደማለት ነው፡፡ እነዚህ ከበራዎች የማንጻት ክዋኔዎች ናቸው፡፡ ከዚያ አዲስ ልብሶቹን ለብሶ ወደሚቀጥለው ክዋኔያዊ አውድ ይሸጋገራል፡፡

በሚቀጥለው ክዋኔ የተገለጸው ተጋርዶ የነበረው ነጭ ነጠላ ደግሞ በመካከላቸው ችግር ተከስቶ መለያየታቸውን የሚያመላክት ነው፡፡ ምክንያቱም በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ የቀለሙ ተምሳሌት የሚመሰለው በአመድ፣ በዱቄት፣ በረሃብና እርዛት ነው፡፡ ባጠቃላይ የመጥፎ ነገር መገለጫ ተምሳሌት እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ከግዲያው ዕለት አንስቶ በሁለቱም ወገን መካከል ሰፍኖ የነበረውን የሀዘን ድባብ፤ በዚያ ነጭ ነጠላ ይመሰላል፡፡ ነገር ግን ይህ ተምሳሌትነት አንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢ እንደ ጥሩ ነገር የሚታይበት ሁኔታም አለ፡፡ ይኸውም፦ በምርቃት መካከል <<adii nyaadhu, adii uffadhu!>> ቢባል፤ አቻ ትርጉሙ ‹‹ነጭ ልበስ፣ ነጭ ብላ!›› እንደማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ነጭ ልበስ ሲባል ለጋቢ፣ ለእጀ ጠባብና የመሳሰሉ ከጥጥ የሚሰሩ

ባህላዊ አልባሳትን ሲሆን፤ ነጭ ብላ የሚለው ደግሞ ደግሞ ለጮማ፣ ነጭ ጤፍና የመሳሰሉትን ይወክላል፡፡

ሌላው ከክዋኔያዊ ተምስሌት አኳያ ያየን እንደሆነ ገዳዩን ወደ አርዳ ጅላ ሲያመጡት ከልለውት፤ ጀርባውን አዙሮ ነው፡፡ ይህ የሚያመለከትው በሰራው ሀጢያት የተነሳ ከቤቱ፣ ከቤተሰቦቹና ከማህበረሰቡ ተገልየ ነው ያለሁት፤ በዚህም ምክንያት ተጎሳቁያለሁ፤ ውስጤም በጣም ተጎድቷል የሚል ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው፡፡ ይህም በጀርባው ሲመጣ እሱ ሳይሆን ሁሉም ሰው በእሱ ላይ ጀርባውን እንዳዞሩበት የሚያመላክት ነው፡፡ ምክንያቱም ጉጂ ጉጂን አይገድልም፡፡ ነገር ግን ባጋጣሚ ከገደለ የጎንዶሮ ከበራ ካልተፈጸመ በቀር ገዳዩ እንደረከሰ ሰው ይቆጠራል፡፡ ይኸውም የሰውን ደም የሚያስፈስስ እርኩስ መንፈስ ጋር አብሮ እንዳለ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ በቃሉ ሃይማኖታዊ አስተምሮት አንጻር ባጋጣሚ የተፈጠረ ክስተት (danuu) መሆኑ ከታወቀ በጎንዶሮ ሃይማኖታዊ ከበራ ሊፈታ ግድ ይላል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የሁለቱን ወገን አቋቋም ደግሞ ጀርባ ለጀርባ ተሰጣጥተው መቆማቸው፤ በመካከላቸው አለመግባባት እንዳለ አመላካች ይህን ሀሳብ ከሚያጠናክሩ የጉጂ ኦሮሞ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ውስጥ አንዱ «ጀርባውን ሰጠኝ፡፡» (dudda natti gale.) የሚለውን ከተመለከትን ተቀይሞኛል/ሬት እየነሳኝ ነው የሚል ፍች ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ያ ችግሩ እስከሚፈታ ድረስ እንደደመኛ ስለሚተያዩና በሟች ቤተሰብ ውስጥ የእልህና ቁጭት መንፈስ ሰላለ አንዳንድ ግጭቶች እንዳይጫሩ፣ የሟች ቤተሰብ ልጃቸውን አስታውሰው ሆድ ሲብሳቸው፤ የሞተው ሰው ነውና በክፉ ዓይን እንዳይተያዩ በማሰብ ነው፡ ፡ ከዚያ ጀርባ ለጀርባ እንደተሰጣጡና ነጠላው (ችግሩ መካከላቸው) እያለ ያን የተጠበሰ የጎድን ስጋ፤ ከተምሳሌታዊ አተረጓገም አተያይ ስጋ ዝምድናን ይወክላል፡፡ የመጠበሱ ወይም እንዲበስል የመደረጉ ተምሳሌት ደግሞ ጉዳዩ ወይም የዕርቁ ሂደት መስመሩን መያዙን፣ ወደ መቋጫ ደረጃ መድረሱን አመላካች ነው፡፡ የጉጂ ኦሮሞ ‹‹Dubbiin dheedhii.›› ካለ ቀጥተኛ ትርጉሙ ‹‹ነገሩ ጥሬ ነው፡፡›› እንደ ማለት ነው፡፡ ይኸውም፡- ነገሩ ምንም ፈር አልያዘም ለማለት ያገለግላል፡፡ በሌላ በኩል የጎድኑ አጥንት የሚወክለው አንድ ወገን ለመሆናቸው ነው፡፡ ባጠቃላይ የክዋኔው ተምሳሌት በመካከላቸው የተፈጠረው ክስተት በዘመዳሞች መካከል በመሆኑ አቅልለው ማየት እንዳለባቸውና ወደ ስምምነት ደረጃ መቃረባቸውን አመላካች ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አጥንቱን በመንከስ እንትፍ የማለቱ ክዋኔ ደግሞ ሰው እንዴት ስጋውን (ዘመዱን) ይነክሳል (ይገላል)፤ እርም ነው የሚለውንና ከአሁን በኋላ አለመፈላለጋቸውን ማሳረጊያ ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው፡፡ ገዳዩ ስሙን

እየጠራ ሶስቴ ‹‹የለህም፡፡›› እያለ አጥንቱን ሲሰጠው የሚች ወገን ‹‹አለሁ›› እያለ መቀበሉ ደግሞ አደጋው ከተከሰተበት ዕለት አንስቶ ተቃራኒ የነበሩ ወገኖች፤ ከአሁን በኋላ አንዱ አንዱን ሲጠራው፤ማለትም ለችግሩ እንዲደርስለት ሲፈልገው ቂም ይዞ ችላ እንደማይለውና የድሮ ትብብራቸውንና መደጋገፋቸውን ማስቀጠያና ማረጋገጫ ከበራ ነው፡፡ የከበራ ግብም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠርን ግጭት ማረጋጋት እንደሆነ (Myrvold, 2007,19) ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አንጻር የተመለከትን እንደሆነ በተፈጠረው ግጭት አጋጣሚ ተበለሻሽቶ የነበረውን ማህበሪዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነታቸውን በዚህ ከበራ ያድሱበታል፡፡

ከዚያም ያን የመጥፎ ክስተት ትእምርት የሆነውን ነጠላ ከመካከላቸው ተገልጦ መነሳቱና እጅ ለእጅ እንዲጨባበጡ መደረጉ፣ እርስ በርስ ዞረው እንዲሳሳሙ የሚደረገው ተምሳሌታዊ ክዋኔ የሚያመለክተው ችግሩ ከመካከላቸው ተወግዶ፣ እንደድሯቸው ሆድ ለሆድ ተገናኝተውና ተያይዘው ለመቀጠል ቃል መግባታቸውን ማሳያ ነው፡፡

በመጨረሻም ይህንኑ ሀሳብ ለማጠናከሪያነት ቃሉ ወይም ገዳና ሽማግሌዎቹ በቦካው እንደማሩ ጣፍጡ፣ እንደ አበባው ሽተቱ እያሉ በቦካው እንትፍትፍ (biifee) እያሉ ሁለቱንም ወገን እያቀመሱ ይመርቃሉ፡፡ ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Waaqa qaalluu, Waaqa gadaa, | የቃሉ አምላክ፣የገዳ አምላክ፣ |
| Ee Waaqa me'ee bokkoo, | የሚኤ ቦኮ አምላክ፣ |
| Ati nu nageessi! Ardaa nageessi! | አንተ ሰላም አርገን! |
| Araddaa nageessi! | ህዝቡን ሰላም አርግልን! |
| Balaa akkasii lammuu isinitti hin deebi'in, | እንዲህ ዓይነቱ አደጋ ዳግም አይግጠማችሁ! |
| Jaarsaatti hin deebisin, | በሽማግሌው አይመልሰው! |
| Jaartiitti hin deebisin, | በአሮጊቷ አይመልሰው! |
| Kaa'imaatti hin deebisin, | በወጣቱ አይመልሰው! |
| Araddaatti hin deebisin, | በህዝቡ አይመልሰው! |
| Akka nuuf toltane isiniif haa tolu, | ለእኛ እንደተመቻችሁ ለናንተም ይመቻችሁ! |
| Bishaaniifi Marga ta'aa! | ውሃና ሳር ሁኑ!፣ |
| Aannaniifi Damma ta'aa! | ወተትና ማር ሁን!፣ |

Kan wal-jaallattan, kan wal-fuutan ta'aa! የምትዋደዱ፣ የምትጋቡ ያድርጋች!
Wal-fuutanii kan hortanu ta'aa! ተጋብታች የምትረቡ ሁኑ! ብዙ ሁኑ!...
እያሉ ይመርቃሉ። ሁለቱም ወገን አሜን እያሉ ምርቃቱን ይቀበላሉ። (አባገዳ ሀልቻዬ፣ አቶሞኮና ናጋኦ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ በ25/11/2007 ዓ.ም. እና አቶ ብርሃኑ ንጉሴ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም. ጉጂ ዞን፣ ቦሬ ከተማ ነዋሪ)

ይህ ከበራ የሁለቱን አንድነት ከማጠናከር አኳያ ከፍተኛ ሚና አለው። ይኸውም በዚህ ክዋኔ ላይ በመጀመሪያ ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አንጻር አውዱን የተመለከትን እንደሆነ ይህ የጎንዶሮ ከበራ የሚፈጸምበት ተቋማዊ ትርጉሙ ግጭትን ለአንዴና መጨረሻ ጊዜ መፍቻ ቦታ መሆኑን ነው። በዚህ ክዋኔ ውስጥ የአባቃሉና አባገዳ ማህበራዊ መዋቅራቸውን ያየን እንደሆነ በባህሉም ሆነ በሃይማኖቱ ያላቸው ደረጃና ተሰሚነት፤ ምን ያህል ተፅዕኖ ፈጣሪ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የማሳረጊያው ምርቃት ሰላም ያድርጋችሁ!፣ ይህን ዓይነት ክስተት ዳግም አይመልሰው!፣...ሁለቱን ወገን አንድ እንዲያደርጋቸውና እንዲያስማማቸው ደግሞ ውሃና ሳር ሁኑ! ወተትና ማር ሁኑ!፣ የምትዋደዱ፣ የምትጋቡ ያድርጋች!፣ተጋብታች የምትረቡ ሁኑ! ብዙ ሁኑ!... የሚሉትን ስንመለከት ተምሳሌታዊ ይዘት አላቸው። ይኸውም፡- ያንዱ መኖር ለሌላኛው መኖር እንደሚያስፈል፣ተጋብተውና ተዋልደው አንዱ ከሌላው ጋር በደም፣ በስጋ/ በዝምድና የሚተሳሰሩ ያድርጋችሁ የሚለው ዝምድናቸውን እንዲያጠናክሩና ከአሁን በኋላ መልካም መልካሙን እንዲያስቡ የሚያደርግ ነው።

በመጨረሻም ወደየመጡበት አቅጣጫ ተሰነባብተው ይሄዳሉ። ከዚህ በመቀጠል በፕሮግራም የገዳይ ቤተሰብ ድግስ ብጤ አዘጋጅቶ የሟቾቹን ቤተሰብ ይጋብዛሉ። በሌላ ጊዜ ደግሞ የሟች ቤተሰብ ደግሶ የገዳይን ቤተሰብ ይጠራሉ። በዚህ መልኩ ሰላማቸውን ወደ ቀድሞው ደረጃ ያሸጋግሩታል። ይህ ደግሞ ከከበራ የማህበራዊ ትስስር ማጠናከሪያ ፋይዳ ውስጥ አንዱና ዋንኛው ነው። ከዚህ በኋላ ገዳዩም ሆነ የእሱ ቤተሰቦች ከሟቹ ቤተሰብ የበቀል እርምጃ ይደርስብናል የሚል ስጋት አይገባቸውም። ነገር ግን ይህን ጉዳይ በዘመናዊ የህግ መዋቅር ቢፈታ ኖሮ ገዳዩ ከሟች ቤተሰብ የሚበቀለው ሰው ባይኖርም ገና ለገና ይበቀሉኝ ይሆን የሚል በእሱና በቤተሰቡ ውስጥ ስጋት ያድርባቸዋል። በጎንዶሮ ስርዓት የተከናወነው ግን እንዲህ ያለ ጭንቀትን የሚያቃልል መሆኑ የጎንዶሮ ከበራን ስነ-ልቦናዊ ፋይዳን ያመላክታል።

### 6.2.2.2. የምልጃ ማሳረጊያ ጎንዶሮ

ሌላው የጎንዶሮ ዓይነት የምልጃ ማሳረጊያ የጎንዶሮ ከበራ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው የግልቢያ (የኮርቻ) ፈረሱ እየሞተ ሊያስቸግረው ይችላል። ለዚህም የጎንዶሮ ከበራ ይከወናል። ሌላው አንድ ሴት ልጅ እየወለደች፣ የተወለደው ልጅ የማያድግላት ከሆነ፣ ልጅ ወልዳ እንዲያድግላት ሲፈልጉ ለመስዋዕት የሚሆን ከብት በማዘጋጀት፣ ሃይማኖቱና ባህሉ በሚፈቅድላቸው መንገድ ወዩ (Woyyuu) በመጥራት ተለማምነው ዲባሴ (ni dhibaafatu) ያደርጋሉ። እንደ መረጃ አቀባዩ ጠጅ (በካ) በመጣል፣ ታዋቂ ሽማግሎዎችን ጠርቶ፣ ከብት አርደው፣ እነዚያን ባልና ሚስት እንዲመረቁ ይደረጋል። ይህ ሰው የአብራኩን ክፋይ አጥቷል። ስለዚህ የአብራኩን ክፋይ (ልጅ) እንዲያገኝ ይመረቃል፣ ወዲያው ደግሞ እንደዚያ ዓይነት አስደንጋጭ ክስተት ካሁን በኋላ እንዳያጋጥመው የጎንዶሮ ከበራ ይፈጸማል።

ድሮ ሰዎች ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ማለትም፡- ድርቅ ሲከፋ፣ የከብቶች በሽታ ከመጣ ወንዝ ወርደው/ይዘው/ (malkaa qabatan) እግዚኣብሔርን እንደሚለማመኑ ከመረጃ አቀባዩ ለመረዳት ችያለሁ። ይኸውም ወደ ወንዝ ሲሄዱ ቡናና ቅቤ ተይዞ ነው። ከዚያ ወንዝ ወርደው እግዚኣብሔር በመለማመን ዝናብ እንዲዘንብ የማድረግ ተስጥኦ እንደነበራቸው ይገልጻሉ። ጉጂሚ ወንዝ ወርዶ እግዚኣብሔርን ይለማመናል? የእኔ ጥያቄ ነበር። እሳቸውም «አዎ! ጉጂሚ ወንዝ ወርዶ ይለማመናል። ከዚህ በተጨማሪ በመንቲያ መንገድ ላይም (woldeena irratti) ወጥቶ ይለማመናል።» በዚህ መልክ በድርጊት እየተቀባበሉ እዚህ እንዳደረሱና በአሁኑ ትውልድ ችላ ባይነት የተነሳ ወደፊት የመቀጠሉን ስጋት እንደገባቸው ገልጸውልኛል። (አቶ ብርሃኑ ንጉሴ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም. ጉጂ ዞን ቦሬ ከተማ ነዋሪ)

በክዋኔው ወቅት ስለጉዳዩ በጥልቀት የማጣራት (qortuma) ሂደት ይከናወናል። በጉጂ ኦሮሞ አራዊቶች የራሳቸው ክልል አላቸው። አለአግባብ አይገደሉም። እንደ ጉጂ ኦሮሞ እነሱ የአራዊቶቹንና የአዕዋፋትን ድምጾቻቸውንየመረዳት፣ በሌላ በኩል አራዊቶቹና አዕዋፋቱ ደግሞ የእነሱን ቋንቋ ይረዱናል የሚል እምነት አላቸው። ስለዚህ አንዱ አንዱን ሳያጠቃ ተስማምተው የመኖር ልምድ አላቸው። ነገር ግን ችግሮች ሊፈጠሩ የሚችሉት ይህን የተፈጥሮ ስምምነት ሲጣስባቸው እንደሆነም ያምናሉ። ስለዚህ ከቤተሰቡ ውስጥ ወይም ከማህበረሰቡ ውስጥ ጥሰት የፈፀመ ካለ ይጣራል። በሂደቱም በማወቅም ይሁን ያለማወቅ የተፈጠረውን ስህተት ከታወቀ በኋላ ለጎንዶሮው ክዋኔ የሚያስፈልጉ ነገሮች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

ለምሳሌ ከላይ እንደተገለጸው አንድ አውሬ ማለትም ጅብ ወይም አንበሳ ለብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ እየመጣ ከብቶቹን ከበረትም ሆነ ከጉረኖ የሚያጠቃበት ከሆነ፤በመጀመሪያ ስለጉዳዩ በጥልቀት የማጣራት (qortuma) ሂደት ይከናወናል። እነሱን ያለ አግባብ ተተናኩለው ከሆነ፣ አለአግባብ ከመኖሪያቸውን አፈናቅሏቸው ከሆነና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ያጣራሉ። በመጨረሻም ይህ ክስተት እንዳይደገም፣ አውሬውም ወደ መኖሪያው እንዲመለስ፣ ዳግም አንደርስብህም፤ አንተም አትድረስብን ተብሎ የጎንዶሮ ከበራ እንደሚያከናውኑ ገልጸውልኛል።

በማንኛውም ከበራ ወቅት የሚከናወን እርድ ሞራው ይታያል። ከዚያም ስለተከወነው ሁኔታ ሞራ አንባቢዎቹ ከሞራው በማየት የሚሉት አላቸው። ይኸውም መስዋዕቱ መሳካቱን፤ አሊያም አለመሳካቱን በመተንበይ ተሰጦአቸው ይናገራሉ። ካልተሳካ ሌላ እንዲታረድ ይደረግና እንደገና ይታያል።

## 6.3. የሁሉቃ ከበራ

ሁሉቃ (hulluuqa) ከቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ አንድ ክዋኔ ነው። የክዋኔውም ሆነ የመከወኛ ቁሳዊ ባህሉ መጠሪያ ስም ሁሉቃ ይባላሉ። ሁሉቃ በጉጂ ኦሮሞ ማህበረሰባዊ ዕውቀት የተዋቀረ የከበራ መቸት ነው። አዘገጃጀቱም በዋናነት በቃሉና በገዳ ተቋማት አቅራቢያ ባሉ ቦታዎች፣ግራና ቀኝ በቆሙ እንጨቶች፣ በሀረግ ከአንዱ አቅጣጫ ወደሌላው ተሻግሮ የታሰረ ነው።ለሰው መጠኑ ከፍታው ረጅም የሚባል ሰው ሊያሻግር የሚችል፣ወደጎን ደግሞ ብዙ ሰው በአንድ ላይ ሊያሳልፍ በሚችል መልኩ የሚዘጋጅ ሲሆን፤ለከብቶች ደግሞ ከፍታው ከብቶቹን በማይነካ መልኩ ከፍ ተደርጎ፣ ወደጎን ደግሞ ብዙ ከብቶች ሊያሳልፍ የሚችል መሆን እንዳለበት ለማየት ተችሏል። ወደ ጎን የሚታሰረው የዲኪቻ ሀረግ ወይም ቀርከሃ ሊሆን እንደሚችል ከመረጃ አቀባዬቼ ለመረዳት ችያለሁ።

በአላብዱ ጎሳ አካባቢ ዲክቻ (dikicha) የሚባል ሀረግ አለ። ይህ ሀረግ ተቆርጦ፣ ግራና ቀኝ በቆሙ እንጨቶች ላይ በማሰር የሚዘጋጅ ሃይማኖታዊ መቼት ነው። ከዚያ በስሩ በመሸሎክ እርኩስ መንፈስንና በሽታን የማስወገድ ከበራ ሁሉቃ በመባል ይታወቃል። ያነጋገርኳቸሁ የሀገር ሽማግሌዎች እንደሚሉት ይህን ከበራ የሚያካሂዱት ለቅድመ-በሽታ መከላከል እንደሆነ ነው። ወደ ኡራጋ አካባቢ ደግሞ ቀርከሃ በመሰንጠቅና ግራና ቀኝ በቆሙ ጉዱባ የሚባል የሚመር እንጨት ላይ በማሰር እንደሚሾልኩ መረጃ አቀባዬ ይገልጻል። በሚሾልኩበት ወቅት ከእንደዚህ ዓይነት መጥፎና መራር ወቅት ውስጥ አውጣን በማለት እንደሆነ ያስረዳሉ።

እንጨትም ተይዞ በማሹለክ ያንን እንጨት በገዳዎች አማካይነት በግራ አቅጣጫ የሚጥሉትም (bita gatanu) የሁሉቃ ዓይነት አለ። የዚህ ዓይነቱ ሁሉቃ ይህ ነገር (መጥፎ ዓመትና በሽታ) ዳግም እንዳይመለስብን ተብሎ ወደ ገደል ወስዶ በመጣል የሚከወን እንደሆነ ይገልጻሉ።
በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ በዋናነት ሁለት የሁሉቃ ከበራ ዓይነቶች አሉ። እነሱም፡- የሰውና የከብት ሁሉቃ በመባል ይታወቃሉ። (አቶ ብርሃኑ ንጉሴ፣በ7/6/2008 ዓ.ም.፣ጉጂ ዞን፣ቦሬ ከተማ ነዋሪ)

## 6.3.1. የሰው ሁሉቃ ከበራ

ሁሉቃ ለሰው ልጆችጤንነት መታወክ፣ ሰላም ማጣት፣ ለምርት ማነስ፣ ለትውልድ አለመቀጠል፣ ለክፉ ዘመን፣ ለጦርነትና የመሳሰሉት ሰበብ ወይም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ የሚሉትን እርኩስ መንፈስ ማንጫ ከበራ አድርገው እንደሚጠቀሙበት ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። (ገዳ ደንበባ ጉሚ፣ አባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)
ሁሉቃ በቃሉ፣በገዳና በማህበረሰቡ ደረጃም ይከወናል። ሁሉቃ በግለሰብ ደረጃ አባት ለልጆቹ፣ እናት ለልጆቿ ታከናውናለች። አባት ወይም እናት ልጆቻቸውን ለሆነ ጉዳይ ከቀዬው ርቀው ሲሄድ፣ ሲታመሙ፣ ስለነሱ መጥፎ ህልም ካዩ፤ ግራ እጃቸውን በልጆቹ እራስ ላይ ሦስት ጊዜ በማዞር፤ አሊያም እንጨት ቢጤ ቆርጠው በማዞር፤ ወይም ልጆቻቸውን ከብብቷ/ቱ ስር በማሾለክ እንዲሁም በእግሮቻቸው ስር በማሽሎክ ጭምር ክፉ መንፈስ እንዳያያቸው ወይም እንዳይነካቸው እግዚሐብሄርን በመለማመን ያን እንጨት ወደ ውጪ ይጥሉታል። በእጃቸው፣ በእግሮቻቸው ስር እና በብብታቸው ስር ሲከውኑ ደግሞ ያ ጦስ ከእናንተ ይልቅ ለእኛ ያድርገው እንደማለት ነው።

በተለይ በቃሉ ተቋም የሁሉቃ ከበራ የሚካሄደው በጥቅምት ወር ነው። መቼቱም የሁሉቃ መግቢያ (karra hulluuqa) የሚባል አለ። ከዚያ አካባቢ ባሉ ትላልቅ የብሳና እንጨቶች ላይ በታሰረው ሀረግ በመጀመሪያ ቃሉ፣ በመቀጠል የመማክርት አባላቱ፣ ከዚያ እንደየጎሳውና ዕድሜ በቅደም ተከተል ይሾልካሉ። ቃሉ በመጀመሪያው ላይ እየመረቀ ይሾልካል። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Aara hamaa nu hulluuqsis, | ከመጥፎ ጭስ አሽሉክን፣ |
| ibidda hamaa nu hulluuqsis, | ከመጥፎ ንዳድ አሽሉክን፣ |
| dhibee hamaa nu hulluuqsis, | ከመጥፎ በሽታ አሽሉክን፣ |
| kan namaan dhufte nu hulluuqsis, | በሰው ላይ ከመጣው አሽሉክን፣ |
| kan guddaan dhufte nu hulluuqsis, | በአዛውንቱ ላይ ከመጣው አሽሉክን፣ |

kan xiqqaan dhufte nu hulluuqsis. በትናንሾቹ ላይ ከመጣው አሽሉከን፣ በማለት ይመርቃል፤ እግዚአብሔርን ይማጸናል፡፡

በገዳ የደረጃ እርከን ስር ካሉት ውስጥ የዶሪና የገዳ አባለት የስልጣን ርክክብ ከማድረጋቸው በፊት የሁሉቃ ከበራ ይፈጽማሉ፡፡ ምክንያቱም ዶሪዎች መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ (kaayoo fi faro hamtuu) ተከትሏቸው በመምጣት የወደፊት ስራቸውን እንዳያደነቃቅፍ በማሰብ ሲሆን፣ ስልጣን ላይ የቆዩት ገዳዎች ደግሞ ምናልባትም በስልጣን ዘመናቸው ወቅት አብሯቸው የነበረ መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ አሁንም እንዳይከተላቸው በሚል የሚፈጽሙት የጦስ ማውጣት ከበራዎች ናቸው፡፡

ሴቶች ወጠባ (ባህላዊ ጭፈራ) ሲጫወቱ በቦታው የታደሙትን ህዝብ በእጃቸው ገብስ (የተቆላ) በመያዝ፣ህዝቡን ወደ መሃል በመተው (ልክ ልጆች «መሀረቤን ያያችሁ» እያሉ እንደሚጫወቱት ዓይነት) ለአራት ሆነው ሶስት ጊዜ እልል እያሉ ይዞራሉ፡፡ ከዚያም በእጃቸው ይዘውት የዞሩትን እህል የሁሉቃው እንጨት (ብሳና) ስር ያስቀምጣሉ፡፡ በዚያ በገብስ አዙረው እንደጦስ መጣላቸው ነው፡፡እንደ ጉጂ አዛውንቶቹ አባባል ልክ አባት ወይም እናት ልጆቻቸውን በራሳቸው እንደሚያሾልኩ ሁሉ ሴቶቹም በእራሳቸው ተጠቅመው ህዝቡን ማሾለካቸውን ያስረዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ በገዳ ስርዓት ውስጥ የሴቶችን ሚና ያሳያል፡፡

ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ የሁሉቃ መቼት የሰውን ልጅ መልካም እንዳይገጥመው የሚተናኮሉ መጥፎ መናፍስት በላዩ ላይ ካሉ አስሮ መያዣ አውዱ እንደሆነ ነው፡፡ ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም አንጻር ሀረጉ፣ ገብሱ፣ እንጨቱ የጦስ ማውጫ ተምሳሌት ሲሆን ሀረጉ በሁለት እንጨት መሀል መታሰሩ ደግሞ ያ ይኖራል ተብሎ የሚታመነው መንፈስ ማስቀሪያ አመላካች ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው፡፡ ከፋይዳዊ ንደፈ-ሀሳብ አኳያ ደግሞ በቦታው ተገኝተው የሾለኩ ምዕመናን ከዚያን ጊዜ በኋላ እስከ አመቱ መጨረሻ መጥፎ ነገር እንደማይገጥማቸው አድርገው ስለሚያስቡ ስነ-ልቦናዊ እርካታ ያገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ ከከበራ ፋይዳዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በገዳ ስልጣን ሽግግር ወቅት የሚያስረክቡት የገዳ አባላት ቀድመው ሾልከው እራሳቸውን ስላነጹ፤ ለሚያስረክቡት የዶሪ እርከን ላይ ላሉት ጥሩ ዕድልና ዕጣ-ፈንታን እንደሚያስረክቡ ሲያስቡ ውስጣቸው በደስታ ይሞላል፡፡ በዶሪ ደረጃ ላይ ያሉትም የሁሉቃን ከበራ ፈጽመው ስልጣኑን መረከባቸው የአገልግሎት ዘመናቸው ውጤታማ እንደሚሆን

ስለሚያስቡ በውስጣቸው መልካም ተስፋን ሰንቀው እንዲሰሩ ያነሳሳቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የመንፈስ ጥንካሬን ይፈጥርላቸዋል፡፡ Bell የከበራን ተግባር ስታስረዳ ቡድኖች የሚተዳደሩበት ስርዓት ወይም የሚያራምዱት አመለካከት የሚመሩባቸውን ህግጋት እንዲያከብሩና እንዲጠብቁ የማነሳሻና ማደራጃ ዘዴዎች እንደሆኑ ትገልጻለች (Bell, 1997:37)፡፡ ስለዚህ የሰው ሁሉቃ ተግባር የሰውን ልጅ ለቀጣይ ዘመኑ ተነቃቅቶና እራሱን በሞራል ገንብቶ እንዲነሳ ማድረግ ነው፡፡

## 6.3.2. የከብት ሁሉቃ ከበራ

የከብቶች ሁሉቃ ልክ እንደሰው ሁሉቃ በቃሉ፣ በገዳና በግለሰብ ደረጃ ይከወናል፡፡ በቃሉና በገዳ ተቋማት በተዘጋጁ የሁሉቃ መቼት ላይ ሲያከናውኑ፤ አርብቶ አደሩ ግን ከብቶቹን በብትሩ ስር እንዲሾልኩ በማድረግ ከበራውን ይፈጽማል፡፡

መቼቱም በቃሉና በገዳ ተቋም አካባቢ ለሚደረጉ የሰውና የከብት ሁሉቃ ክዋኔዎች ጎን ለጎን ይፈጸማሉ፡፡ የሚዘጋጀውም ከአንድ ዓይነት ቁሶች ሲሆን፤ ልዩነታቸው ለከብቶች የሚዘጋጀው ጎኑና ቁመቱ ላይ ነው፡፡ይኸውም የከብቶች ሁሉቃ ጎኑ ሰፋ ማለት አለበት፡፡ ለሰዎች የሚዘጋጀው ግን ከአምስት እስከ አስር ሰዎችን ጎን ለጎን ሊያሾልክ በሚችል ሁኔታ የሚዘጋጅ ነው፡፡

ይህ የሁሉቃ ከበራ የሚካሄደው በአመት አንድ ጊዜ ሲሆን እሱም መስከረም ሲጠባ ነው፡፡ ምክንያቱም በዘመን መለወጫ ማለትም መስከረም (birraa) ላይ ከክረምቱ፤ ከጨለማዋ በሰላም ላወጣኸን አምላክ ምስጋና ይግባህ ለማለትና ቀጣዩ ጊዜ መልካም እንዲያደርግላቸው የሚከውኑት ነው፡፡

ሁሉቃ የማህበረሰባዊ ውቅር ዕውቀት ነው፡፡ አዘገጃጀቱም ለዚህ ተግባር ተብሎ በተመረጠው ቦታ ማለትም ሜዳማ ሆኖ ከግራና ቀኝ በተፈለገው ስፋት የቆሙ ሶስት ወይም አራት ዛፍ እንጨቶች ይመረጣሉ፡፡ ከዚያም በስተቀኝ በኩል የሰው ሁሉቃ፣ በስተግራ በኩል ደግሞ የከብት ሁሉቃ ይዘጋጃል፡፡ ይኸውም፡-ዲክቻ የሚባለውን ሀረግ ተቆርጦ ይመጣል፣ ከዚያም በተመረጡት እንጨቶች ላይ ለሰውም ሆነ ለከብት በሚያሾልክ ቁመት ከግራና ከቀኝ ይታሰራል፡፡ ቋሚው ከስሩ የበቀለ እንጨት ቢሆን ይመረጣል፡፡ ያ የሁሉቃ እንጨት ምን ጊዜም ቢሆን አይቆረጥም፤ አይመለመልም፡፡ ምክንያቱም መጥፎው በሰዎችና በከብቶች ላይ ነበር ተብሎ የሚታመነው መንፈስ በእሱ ላይ ቀርቷል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ቦታውም

የተከበረና ጥብቅ ነው። እንደመረጃ አቀባዬ ገለጻ የበቀለ ወጥ ዛፍ ከሌለ ዘለግ ያሉ እንጨቶች ተቆርጠው ይተከሉና ሀረጉን በእነሱ ላይ በማሰር ሊዘጋጅ ይችላል። (አቶ አባባ ቶቴ፣ 23/2/2007 ዓ.ም.፣ በወናጎ ወረዳ የቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ)

የከብት ሁሉቃ ክዋኔ የሚከወነው ይህን ዓመት ከመጥፎ የከብቶች በሽታ ያሾለከን አምላክ ምስጋና ይግባህ፣ለቀጣዩም ከክፉ በሽታ ሰውረን፣ አውጣን፣ አሹልከን፣ መጥፎ በሽታን አሁንም ያዝልን፣ የግጦሹን ሳር አሳምርልን ወዘተ...በማለት እግዚሐብሄርን የሚያመሰግኑበት፣ የሚማፀኑበትና ከብቶቹን ከመጥፎ ነገሮች የሚያነጹበት ከበራ ነው። ይንንም ተግባር ቃሉ ወይም አባገዳ ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ከሁሉቃው እንጨት ጎን ቆመው፣ በእርጥብ የእንጨት ዝንጣፊ ከብቶቹን ቸብ ቸብ እያደረጉ፤ በሁሉቃው ስር ተራ በተራ ያሾልካሉ። ከብቶቹ በብትር አይመቱም። በዚህ ጊዜ ያን የእንጨት ዝንጣፊ ቅጠሉ እንዳይበጣጠስና ሁሉንም በአንድ ዓይነት ሁኔታ ለማሾለክ ከማሰብ የተነሳ በቀስታ ቸብ ቸብ እንደሚደረግ ይናገራሉ።




ፎቶ፤-15 የከብት ሁሉቃ መቼት

የምርቃቱም ሂደት እንደሚከተለው ይከወናል። ይኸውም፡- ቃሉ ወይም አባገዳው

ከብቶቹን ሰላም አድርግልኝ!

ላሞቹ ያግቱ!

ኮርማው ለስሪያ ይነሳሳ!

ጥጆቹ በመስክ ላይ ይቦርቁ!

ጋንዲ (የከብት በሽታ) አጥፋልን! (አቶ ብርሃኑ ንጉሴ፣ጉጂ ዞን፣ ቦሬ ከተማ ነዋሪ፣ በ7/6/2008 ዓ.ም.)

ቃሉ የሁሉቃ ከበራ ላከናውን ነው ብሎ መልዕክት ካስተላለፈ፤ የቅርቡም ሆኑ በርቀት ያሉት ከብቶቻቸውን ነድተው ይመጣሉ፡፡ በመጀመሪያ በቃሉ ተቋም ዙሪያ ያሉት ከብቶች እንዲሾልኩ ይደረጋሉ፡፡ ከዚያም እንደየአመጣጣቸው ከርቀት የመጡትንም ያስተናግዳሉ፡፡ ከብቶች የምሾልኩት ከእረኞቻቸው ጋር ነው፡፡ በዚያን ቀን በደረቅ ዱላ አይመቱም፤ ልምጭ ይዘው ለአመል ያህል እየመቱ አብረው ይሾልካሉ፡፡ በሁሉቃ ወቅት በእጁ ጦርም ሆነ መሳሪያ የያዘ ሰው ካለ ከነጦሩ አይሾልክም፡፡ ሰውዬው ከስር ስሾልክ፤ ጦሩን ወይም መሳሪያውን ከላይ አሳልፎ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን ሲቄ፣ ቦኩ፣ የወተት ማለቢያ ጮጮውንና ማሰሪያ ጋዱን በመያዝ ከብቶቻቸውን እየነዱ በስርዓቱ ላይ ይታደማሉ፡፡

ቀደም ሲል እንዳየነው ጦር፣ የጦር መሳሪያ ተምሳሌነታቸው የጦርነት በመሆኑ በሁሉቃ ስር አያልፉም፡፡ ነገር ግን ሲቄና ቦኩ ቅዱስ ቁሳዊ ባህሎች በመሆናቸው እነሱም ለቀጣዩ ዘመን መንጻት ስላለባቸው ከሰውና ከብቱ ጋር ይሾልካሉ፡፡ የወተት ማለቢያ ጮጮ (Okolee) እና ጋድ (gaadii) ያየን እንደሆነ ከከብቶቻቸውና ከከብቶቹ ውጤት ጋር ተያያዥነት ስላላቸው እነሱም መንጻት አለባቸው፡፡ ስለዚህ በላያቸው ላይ እርኩስ መንፈስ አርፎ ወተቱንና ከብቱን ለበሽታና ምርት መቀነስ ምክንያት እንዳይሆን የሁሉቃ ተምሳሌታዊ ክዋኔ በማድረግ እንዲነጹ ይደረጋሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ አርብቶ አደሩ ከብቶቹን በብትሩ ስር እያሾለከ የሚመርቅበት ሁኔታ አለ፡፡ምርቃቱ ያው ከመጀመሪያዎቹ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይኸውም፡- ከብቶቹን ከመጥፎ በሽታ፣ ከድርቅ፣ ከውሃ እጦት አውጣቸው፡፡ በማለት ስለነሱ መልካም መልካሙን እየተመኘ ማሾለክ ነው፡፡(አቶ ታደሰ ደንበባ፣አባያ ወረዳ፣ቡናታ ቀበሌ ነዋሪ)

በመጨረሻም ታድመው የነበሩ እናቶች፣ወጣቶችና እረኞች ከብቶቻቸውን እየነዱ በደስታና በጭፈራ ወደ ቂያቸው ሲመለሱ፤ገዳዎች፣ወዩዎችና አዛውንቶች ቃሉን አጅበው እጨፈሩ ወደ ገልማው ይሄዳሉ፡፡ በአቅራቢያ ያሉ እናቶች ከቤታቸው ጠጅ ያመጣሉ፡፡ ቡና ቃላ ይዘጋጅል፡፡ ከዚያ በመጀመሪያ ቃሉ ቡና ቃላውን እግዚአብሔርን ተለማምኖ ይቀምስና ባለቤቱንም ያቀምሳል፡፡ በመቀጠል እንደ ስልጣን ቅደም ተከተላቸውና እንደ ጎሳ ታላቅነትና ታናሽነት እየተቀባበሉ ይበላሉ፡፡ ከጠጅም ለቃሉ በራሱ መጠጫ (duloo)፣ ለጎሳውም በሌላ መጠጫ

(duloo) ተቀድቶ ይሰጣል። ጎሳው ያን ቡና ቃላ እየበላ፣ ከጠጁም ጎንጨት እያደረጉ ቃሉን ይመርቃሉ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Nu'uu buli ati, | አንተ ከእኛ ኑር፣ |
| nu keessa buli, | እኛ ውስጥ ኑር፣ |
| nu keessa ool, | እኛ ውስጥ ዋል፣ |
| nu'uf jiraadhu, | ኑርልን፣ |
| jireenni kee nagaa ta'u, | ሕይወትህ ሙሉ ሰላም ይሁን። እያሉ በእንትፍትፍ |
| (biifee) | ምርቃቱን ያጸድቃሉ። |

በመቀጠል ቃሉም እነሱን በመመረቅ ያሰናብታቸዋል። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Isinille bulaa, | እናንተም ኑሩ፣ |
| ardaa nagaa ta'aa, | ሰላማዊ መንደር ሁኑ፣ |
| Gujii nagaa ta'a, | ሰላም የሰፈነበት ጉጂ ሁኑ፣ |
| Gujii gabbinnaa ta'a, | ኑሮዋችሁ ያማረ ጉጂ ሁኑ፣ |
| Qayeen isin nagaa haata'u, | መንደራችሁ ሰላም ይሁን፣ |
| Nagaan gala. | በሰላም ግቡ ይላል። |

የከብት ሁሉቃ በሚካሄድበት ወቅት በከብቶቹ ላይ ምናልባትም በሽታ አምጭ፣ ኮርማዎቹ እንዳይሰሩ የሚያፈዝና ላሞቹም እንዳይግቱና ወተት እንዳይሰጡ የሚያደርግ እርኩስ ሰፍሮባቸው ከሆነ እንዲነሳ፤ አልሰፈረባቸው እንደሆነ እንዳይተናኮላቸው እግዚአብሔር እንዲጠብቅላቸው የሚለማመኑበት ሂደት ነው። ከሁሉቃው ከበራ በኋላ እያንዳንዱ ግለሰብ ለከብቶቹ ደህንነት መድህን እንደገባላቸው ይቆጥራል። መንፈሳዊ እርካታም ይሰማዋል። ይህ ደግሞ የከበራ ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ነው። በሌላ በኩል ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ የተመለከትን እንደሆነ የሁሉቃው መቼት ከብቶችን የሚተናኮሉ መጥፎ መናፍስትን ማስቀሪያና ማስሪያ በመሆን ለከብቶቹ ደግሞ መንጽያ አውድ እንደሆነ ይቆጠራል።

ከተምሳሌታዊ አተረጓጎም አንጻር ከብቶቹ ሁሉቄ ሲሉ በእርጥብ ቅጠል ቸብ ቸብ የሚደረገው፡- እርጥቡ ቅጠል የልምላሜ፣ የምርታማነት ተምሳሌት በመሆኑ ከብቶቹ ማህጸናቸው እርጥብ

እንዲሆን፣ ከወለዱም በኋላ ወተታማ እንዲሆኑ፣ ከርማዎቹ ለስሪያ ንቁ እንዲሆኑ ምኞት መግለጫ ነው።

## 6.4. የፋጬ ከበራ

እንደ ዋቄፋና ሃይማኖት ተከታዮች እምነት እግዚኣብሔር (ዋቃ) ለቃሉዎች የገለጹላቸውና ሰዎች እንዲያከብራቸው ያስተምሩ ዘንድ ያዘዛቸው ዋና ዋናዎቹ ሕግጋቶች አሉ። እነዚህን ሕግጋት በሰው ልጆች ዘንድ ተምረውና አውቀው በስራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው ይታመናል። ነገር ግን ሰዎች አንድም በማወቅ፤ አሊያም በስህተት ወይም ባለማወቅ ከእነዚህ ሕግጋት ውስጥ የተወሰኑትን ሊጥሱ ይችላሉ። እንደ ዋቄፋና ሃይማኖት እነዚህ ጥሰቶች እንደ ሀጢያት (cubbuu) እንደተሰራ ይታመናል።

በሌላ አባባል እንደ ጉጂ ኦሮሞ ሀጢያት ማለት የእግዚኣብሔር ቀደምት እውነቶችን (dhugaa ganamaa) በመጣስ በተፈጥሮ ላይ የሚደርስ ጉዳትና እግዚኣብሔርን ማሳዘን እንደሆነ ያምናሉ። እነዚህም እውነት ሳለ መዋሸት (በሀሰት መመስከር፣ የሰውን ሀቅ መካድ፣ አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት መሞከር)፣ ነፍስ ማጥፋት፣ የሰውን መመኘት፣ ሌብነትና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ባጠቃላይ እነዚህን እግዚኣብሔር የማይፈቅደውን ስራዎች መፈጸም ሀጢያት እንደሆነ ያምናሉ።

ሌላው ጉጂ እግዚኣብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ (uuma) እንደሆነና በሰማይና በምድር መካከል ከሱ የተሰወረ ነገር እንደሌለ ያምናሉ። ከዚህም የተነሳ በሰው ዘንድ ለተሰሩ ጥሩ ስራ (waan gaarii)ና ሀጢያትን (cubbuu) ምን ምን እንደሆኑ እግዚኣብሔር ለቃሉ ህግጋቱን ለህዝቡ እንዲያስተምር ተገልጾለታል በማለት የሚያከብሯቸው እንዳሉ አይተናል። እንደ ጉጂ ኦሮሞ ጥሩ ስራም ሆነ ሀጢያት በሰው ልጅ ቢሰራ ለእግዚኣብሔር ማስረጃዎቹ ሰማይና ምድር እንደሆኑ ያምናሉ። እንደመረጃ አቀባዮቼ አገላለጽ አንዳንድ ሰዎች የሰው ማስረጃ ኖረም፤ አልኖረም ስላደረጉት ድርጊት ለሌላኛው ወገን ሲያረጋግጡ፡- በጣታቸው ወደ ሰማይና ምድር እያመለከቱ «ይኸው! ሰማይና ምድር በሚያውቀው» «Kunoo! Waaqiifi lafti tun kan beektu» በማለት እንደሆነ ያስረዳሉ። ኦሮሞ እግዚሐብሄርና ሰማዩን በአንድነት ዋቃ (Waaqa)

ብሎ እንደሚጠራ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ከዚህ የምንረዳው በአፋን ኦሮሞ ዋቃ (Waaqa) የሚለው ስም አውዳዊ ፍች አለው ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡-1. Qaalluun **Waaqaa**fi nama gidduuti ta'ee seera **waaqaa** barsiisa.

ቀጥተኛ ትርጉሙ፡- ቃሉ በእግዚሐብሄርና ሰው መካከል ሆኖ የእግዚሐብሄርን ህግ ያስተምራል የሚል ነው፡፡

2. Xiyyaarri **waaqa**rra ka'e; balala'e.

ቀጥተኛ ትርጉሙ፡- አውሮፕላኑ በሰማይ ላይ ተነስቶ በረረ የሚል ነው፡፡

ከነዚህ ምሳሌዎቹ የምንረዳው ዋቃ (Waaqa) የሚለው በአንደኛው ዐ.ነገር ውስጥ ያለው ፍች «እግዚሐብሄር» የሚለውን የሚገልጽ ሲሆን፤ በሁለተኛው ዐ.ነገር ውስጥ ያለው ፍች ደግሞ «ሰማይ» የሚለውን እንደሚገልጽ ያሳየናል፡፡ ስለዚህ የዋቃ (Waaqa) አውዳዊ ፍች የሚገኘው ከገባበት አውድ አኳያ መሆኑን ለማየት ችለናል፡፡

አንድ ሰው ሀጢያት ቢሰራ ምን ይሆናል? ለምለው ጥያቄ መረጃ አቀባዮቼ ሲመልሱ፡- ሀጢያት የሰራ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተለያዩ ችግሮች ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይኸውም፡- በቀጥታ በራሱ ሕይወትና በንብረቱ ላይ አነስተኛ ጉዳት እንደ ማስጠንቀቂያ ደወል ይደርስበታል፣ ሌላው ባጠፋው ጥፋት መጠንና ዓይነት ሊደርስበት ይችላል፣ አሊያም ከዚያ የከፋ ችግር ሊደርስበት ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ሀጢያት የሰራ እንደሆነ ያ ግፍ በራሱ ሳይሆን በልጆቹ ወይም በልጅ ልጆቹ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ «Guji are not interested in eschatology, a purely spiritual development of the person, or life after death» (Van de Loo, 1991:286). ከዚህ ጥቅስና ከአጥኚው የካበተ ልምድ እንደጉጂ ኦሮሞ አተያይ የሰው ልጅ ሀጢያት ሰርቶ ከሞተ ገሀነብ፣ ጽድቅ ሰርቶ ከሞተ ገነት ይገባል የሚል አስተምሮት የለም፡፡ ሀጢያት የሠራ፣ ለክፉ ሥራው በምድር እያለ ቅጣቱን ያገኛል (Hussein, 2002:66)፡፡

### i. የሀጢያት መገለጫ ወይም አመላካች ችግሮቹ

የሀጢያት መገለጫ ወይም አመላካች ችግሮቹ የሚባሉት አንድ ሰው በራሱ ላይ፣ በንብረቱ ላይ፣ በቤተሰቡ ላይ ያልተለመዱ ክስተቶች ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች እንደ አጋጣሚያቸውና

ድግግሞሻቸው ይለያያሉ። ጉጂዎች እንዲህ ዓይነቱ ችግር ሲያጋጥማቸው በምን ምክንያት መጣብኝ ወይም መጡብኝ በማለት እራሳቸውን እንዲጠይቁ ስለሚቀሰቅሳቸው እንደ ሀጢያት መገለጫ ይቆጥሩታል።

ያም ሆነ ይህ የሀጢያት መገለጫው እንደታየ ከችግሩን መውጫ መንገድ ፋጭ (ንስሀ) እንደሆነ ይገልጻሉ።

**ፋጭ** (faacii) ደግሞ አንድም እንደ ሀገር፣ አንድም እንደጎሳ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ቤተሰብና እንደ ግለሰብ ሊከወንላቸው ይቻላል። ይኸውም፡- ከእግዚአብሔር ቁጣ የተነሳ፤ የችግሩ ተፅዕኖ የደረሰው እንደ ሀገር ከሆነ፡ ቃሉና ገዳ በመሆኑ ማህበረሰቡ ምን ቢሰራ/ ምን ጥሰት ቢፈጽሙ ነው/ ይህ ሊከሰት የቻለው በማለት የሚከውኑት የማጣራትና የንስሀ ከበራ ሲሆን፣ ሌሎቹም በየደረጃቸው ምን ቢያጠፉ ነው የምለውን በማጣራት የሚከውን ይሆናል። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በሰራው ሀጢያት ተፀፅቶ፤ ከበደለው አካል ይቅርታን በማግኘት፣ ይቅር ለእግዚአብሔር ለመባባልና ከፈጣሪውም ምህረት እንዲደረግለት የሚከወን የንስሀ ከበራ ነው። ይህ ከበራ የሚፈጸመው አብዛኛውን ጊዜ አንድም አንድ ሰው በራሱ ላይ፣ አሊያም በቤተሰቡ ላይ ወይም በንብረቱ ላይ ያልተለመዱ ክስተቶች ከተፈጠሩ፤ እንደነዚያ ዓይነት ችግር ዳግም እንዳይከሰት ለመከላከል የሚደረግ ሃይማኖታዊ ከበራ እንደሆነ ያምናሉ።

ሌላው ደግሞ ቀደም ሲል በምን ይመጣብኛል ትዕቢት ወይም ንዴት ውስጥ ሆኖ ሀጢያትን ይሰራና በኂላ ላይ መፀፀት ይመጣል። በዚያን ጊዜ ጥፋቱን በመግለጽ መፀፀቱን ያስረዳና በራሱ ላይ ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት አስቀድሞ የሚከወን የፋጭ ዓይነትም እንዳለም መረጃ አቀባዮቼ ያስረዳሉ። ስለዚህ በጥፋቱ ምክንያት የሀጢያት መገለጫ ወይም አመላካች ችግሮች ከተፈጠሩ፤ ይህ ችግር ከምን መጣብኝ? ከደረሰው ችግር እንዴት ሊወጣ ችላለሁ? አሊያም እንዴትስ ነው ችግሩ ሊያበቃ የሚችለው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኘው በፋጭ ሃይማኖታዊ ከበራ መሰረት እንደሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታመናል።

ከዚያን በኂላ ችግሩ የተከሰተበት ሰው የሀገር ሽማግሌዎችን በመሰብሰብ ችግሩን ይነግራል፣ አንዳንዴም ችግሩ በተፈጠረበት ወቅት የነበሩ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ያዩታል፣ እንደሁኔታው ቅለትና ክብደት ችግሩ የቃሉ ተቋም ሊደርስ ይችላል።

በዚህ መሰረት ፋጭ አንድን ሰው በፈፀመው ስህተት እንዳይፀፀትና ዳግም ወደ ስህተት ውስጥ እንዳይመለስ ለማድረግ የሚከወን ሃይማኖታዊ ከበራ ነው። ይህ ከበራ የማህበረሰቡ ውቅር ዕውቀት ነው። ይኸውም እንደ ጉጂ ኦሮሞ በፋጭ ከበራ ማንኛውም ሀጢያት ይቅር ሊባል እንደሚችል፤ ይቅርታውም አንድም ከተበደለው ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ከእግዚኣብሔርም ይቅርታ እንደሚያገኝ ያምናሉ።

በጉጂዎች ዘንድ በፋጭ ሂደት ውስጥ ሰውን በመፍራትም ሆነ፤ ምን ይሉኛል ተብሎ የሚሸሸግ ሚስጥር የለም። ምክንያቱም አንድ ሰው ጥፋቱን በፍርሃትም ሆነ በማንአለብኝነት ቢደብቅ፤ የሰውን ልጅ ዋሽቶ ከሰው ዘንድ ይቅርታን ሊያገኝ ይችላል። ነገር ግን እውነተኛውን ይቅርታ፤ ከእግዚኣብሔር የሚገኘውን ይቅርታ እንደማያገኝ ያምናሉ። ስለዚህ ችግሩ ይቀጥላል፤ ከዘር ወደ ዘር ይተላለፋል ተብሎ ስለሚታመን እውነቱን አውጥተው መናገር እንዳለባቸው ይታመናል።

በዚህ የፋጭ ሂደት ውስጥ እንዳጋጣሚ በደል የደረሰበት አካል በወቅቱ ቢኖር፣ አሊያም በወሬ ወሬ ቢሰማ እንኳን ቂም መያዝ እንደሌለበት በባህሉም ሆነ በእምነቱ ውግዝ እንደሆነ የጉጂ የሀገር ሽማግሌዎች ይገልጻሉ። ስለዚህ በፋጭ ጊዜ በድያለሁ የሚለው አካል ሀጢያቱን ያለአንዳች ፍርሃትና ስጋት ይናዘዛል።

ለአብነት ያህል በጉጂ ኦሮሞ አንድ ሰው በድንገት በመኪና አደጋ ከሞተ ዝም ተብሎ አይቀበርም፤ እንዲሁም የደም ካሳ አይወሰድም፤ ተቻኩሎም ለክስ አይሮጥም። አስከሬኑን አስቀምጠው ይህ አደጋ ከእኛ ቤተሰብ ውስጥ እንዴት ሊከሰት ቻለ? ብለው ቀድመው ያጣራሉ። በዚህ የማጣራት ሂደት ወቅት ከዚህ በፊት በማወቅም ይሁን፤ ባለማወቅ በተመሳሳይ አደጋ የደም ካሳ የወሰደ ሰው ካለ አደጋውን ይደግማል ተብሎ ስለሚታመን ይህም ጉዳይ ተነስቶ ይጣራል። ምክንያቱም እንደ ጉጂ ኦሮሞ አተያይ ባለመኪናው ከቤቱ ሲወጣ እገሌን በመኪናዬ ገጫለሁ፤ ገድለዋለሁ ብሎ አልወጣም ብለው ያምናሉ። እንዲሁም ሟቹም ከቤቱ ሲወጣ ሞታለሁ ብሎ አልወጣም። ስለዚህ ይህ ክስተት ፍርጃ ነው፤ የእግዚሐብሄር ትዕዛዝ ነው ብለው ያምናሉ። ታዲያ አንዳንድ የቤተስቡ አባል «በምን ይመጣብኛል» አስተሳሰብ አደራዳሪ መስለው በመቅረብ፣ ለቀብር ማስፈፀሚያ ብቻ የተባለው ላይ ጨምሮ በመወሰድ የቀድሞውን ስርዓት የሚጠሱ ስለማይጠፉ እነዚህ ሁሉ በንስሀ ከበራው ሂደት ላይ ይጣራሉ። እንዲህ እንዲህ እየተባለ የማጣራቱ ሂደት ይቀጥላል።

የፋጭ ሂደት በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ ደረጃ እንዲሁም በአባገዳዎችና በአባቃሉ ደረጃም ሊከወኑ ይችላሉ። ስለዚህ በአንድ የጉጂ ጎሳ ውስጥ የተለያዩ ችግሮች ቢከሰቱ ለነዚያ ችግሮች መንስኤው ምናልባትም ከላይኛው ደረጃ ላይ ባሉት በተፈጠረ የእግዚኣብሔር ህግጋት ጥሰት ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ እግዚኣብሔርም ቅጣቱን እንደ ህዝብ ወይም በጎሳው ላይ ሊያወርድ እንደሚችል ይታመናል። እነዚህን ችግሮች ሲከሰቱ ሁሉም በየደረጃው እራሱን መፈተሽና የንስሀ ክዋኔ መፈጸም እንዳለበትም ይታመናል።

እንደ Van De Loo አገላለጽ አንዳንዴ ይህ ሁሉ ንስሀ፣ ልመናና መስዋዕት ቀርቦ ነገሮች እንደቀድሞው በሰላማዊ መንገድ ላይቀጥል ይችላሉ። ይኸውም አንድ ሴት መሀን ሆና ልትቀር ትችላለች፣ ሰዎች ይታመማሉ፣ ከብቶች ይሞታሉ። የጉጂ ህዝብ በሌሎች እጅ ወድቀው ሊጨቆኑ ይችላሉ። በዚህ ወቅት ይህ ሁሉ የሚሆነው በእግዚኣብሔር ፍቃድ እንደሆነ ያምናሉ። አሊያም «እግዚኣብሔር ከእኛ ዘንድ ርቋል» እንደሚሉ (Van De Loo,1991፣284) ይገልጻል።

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አንዳንድ ጊዜ ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ የፋጭ ሃይማኖታዊ ከበራ ተካሂዶ፣ ለእግዚኣብሔር መስዋዕት ቀርቦና ተለማምኖ እንኳን ነገሮች ወደቀድሟቸው ቦታ ላይመለሱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ማህበረሰቡ እግዚኣብሔርን ከማማረር ይልቅ ከአምስቱ የዋቄፋና ህግጋት ውስጥ አንዱ የሆነውን፡- የመጣውን ችግር የእግዚኣብሔር ስራ ነው ብሎ በፀጋ መቀበልን ያሳያል። አሊያም «እግዚኣብሔር ከእኛ ዘንድ ርቋል» የሚሉት ደግሞ ከሀጢያታቸው ብዛት የእግዚኣብሔር ጥበቃ እንደተለያቸው በማመልከት ለችግሩ ኃላፍነቱን መውሰዳቸውን ያሳያል።

በሌላ መልኩ በአንድ የማህበረሰቡ አባል ወይም በማህበረሰቡ ጥፋት ወይም አባገዳዎች፣ አባቃሉ እንዲሁም የመማክርት አባላቶቻቸው ከተሰጠጣቸው ደንብና መመሪያ ውጭ ሲሆኑ ሀጢያትን እንደፈጸሙ ይቆጠራል። ለምሳሌየገዳ ስልጣን ዑደቱን ማዛባት እንደ ሀጢያት (cubbuu) ስለሚቆጠር ለችግሩ ምክንያት በሆኑት አካላት ላይ ጫን ያለ ቅጣት ይወሰዳል (Alemayehufi kan biroo, 1999፡169)። ታዲያ እግዚኣብሔርም በዚህ ድርጊታቸው ያዝናል። አዝኖም ዝም አይልም። የቅጣት ጅራፉን ይሰነዝራል። ይኸውም፡- በድርቅ፣ የዝናቡን መጠን

በመጨመር ወይም በመቀነስና ወቅቱንም በማዛባትና የመሳሰሉትን በማድረግ ህዝቡን ሊቀጣ እንደሚች ያምናሉ፡፡

ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ እንደጎሳ ከተከሰተ፡- ከስር ጀምሮ ህዝቡ ውስጥ ምን ሀጢያት ቢፈፀም ነው እንዲህ ዓይነቱ የእግዚኣብሔር ቁጣ የመጣብን በማለት ያጣራሉ፡፡ በመቀጠል አባገዳውና የመማክርት አባላቶቹ አካባቢስ ምን ምን ክፍተቶች አሉ?፣ እያለ ወደ አባቃሉና የመማክርት አባላቱም ጋ እየተጣራ ይመጣል፡፡ ካለመሰልቸት በየደረጃው ፋጭ እየተባለ፤ መስዋዕት በማቅረብ እግዚኣብሔርን በመለማመን ሊፈታ እንደሚችል ይታመናል፡፡

### ii. የፋጭ ከበራ ሂደት

ቀደም ሲል እንዳየነው የፋጭ ከበራ ሂደትን በቅድመ-ፋጭ፣ ፋጭና ድህረ-ፋጭ ደረጃ መመልከት ይቻላል፡፡ እነዚህን ሂደቶች ለመተንተን የሚከተለውን የፋጭ ንጥል ጥናት እንመልከት፡፡

### የፋጭ ንጥል ጥናት-1

አንድ በምዕራብ ጉጂ ዞን፣ በአባያ ወረዳ፣ የፎጌ ቀበሌ ነዋሪ የሆነ አቶ ዋቆ ኦቶሮ የሚባል ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ከዕለታት አንድ ቀን በጠና ይታመማል፡፡ በሽታውም እየጠናበት ሄዶ ነፍስ ውጭ፣ ነፍስ ግቢ፤ ሲቃይ ሆነ፡፡ ከዛሬ ነገ ይሞታል እየተባለ ሲጠበቅ ዝም ብሎ እንደታረደ በሬ ያንኮራፋ ጀመር፡፡ ቤተሰቦቹና የአካባቢው ሽማግሌዎች ተመካከሩ፤ ይህ ሰው እኮ ተሰቃዬ፤ እንዲሻለው ወይም ከስቃዩ እንዲገላግለው ለምን ፋጭ አይደረግለትም አሉ፡፡ በሀሳቡ ተስማምተው በማግስቱ ከአካባቢው የባህልና ሃይማኖት አዋቂዎች (Woyyuu)ና ሽማግሌዎች ተነግሯቸው በጠዋቱ መጡ፡፡ ከዚያም በባህሉ መሰረት ተጠያይቀው ሽማግሌዎች ተሰየሙ፡፡ ቀድሞ እግዚኣብሔር መለመን ያለበት ሰው በመጀመሪያ ጸሎት አደረሰ፡፡ ተራ በተራ ሶስት ሽማግለዎች ጸሎት አደረሱ፡፡ ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Ee Waaqa! | አቤቱ እግዚኣብሔር፣ |
| Ee Waaqa Qaalluu, | አቤቱ የቃሉ አምላክ፣ |
| Ee Waaqa Gadaa, | አቤቱ የገዳ አምላክ፣ |
| Kan nagaan nu bulchite, | በሰላም ያሳደርከን፤ በሰላምአውለን! |
| nagaan nu oolchi, | |

Afaaniifi arraba nuu bani, | የምንናገርበትን አንደበታችንን ክፈትልን!
Ee Waaqa faacii nama kanaa, | አቤቱ እግዚአብሔር የዚህን ሰውን ስህ ተቀበል!
nuu dhage. | ይቅርም በለው። በማለት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ

ሦስቱም ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን ከተለማመኑ በኋላ የመጡበትን ጉዳይ ብያውቁትም፤ ለምን እንደተጠሩና እዚህ እንደተሰበሰቡ ይጠያየቃሉ። ከዚያም ችግሩ ከደረሰበት ቤተሰብ አባላት መካከል አንድ ሰው (ባለቤቱ፣ ወንድሙ፣...) ተነስቶ ለሽማግሌዎቹ ይሄ ወንድማችን/እህታችን ወይም ልጃችን አልጋ ከያዘ ቆዬ። ከዛሬ ነገ ይሻለዋል ስንል ባሰበት፤ የተለያዩ ባህላዊ መድኃኒቶችንም ሞከርንለት። ነገር ግን ከበሽታው ሊድን አልቻለም፤ እረፍትም ነሳው። ስለዚህ ከእሱም ሆነ ከእኛ ጥፋት አይታጣምና ለፋጭ ነው የጠራናችሁ ይላል።

ከዚያ ሽማግሌዎቹ በባህላዊ የአነጋገር ስልት ለሁለት በመከፈል፤ ግራና ቀኝ በመቀባበል ውይይቱን (hayyuu gaafachuu) ጀመሩ።

ይህንን የፋጭ ክዋኔ ሂደት በውይይቱ ላይ በተካሄደው ቅደም ተከተላዊ ሂደት እንደሚከተለው በቀጣዩ ሠንጠረዥ ውስጥ ቀርቧል።

| 1ኛው ሽማግሌ (Jaarsa 1ffaa) | 2ኛው ሽማግሌ (Jaarsa 2ffaa) | ተጠያቂው/ወኪሉ (kan faaci'atu) | በጋራ የሚባለው |
|---|---|---|---|
| 1. ጃል! (abboo!) | 2. እሺ ጃል (abbatto!) | | |
| 3. ይህ ሰው ታሞ እያጣጣረ ነው። (nami kun baay'ee dhukkubsatee jira.) | 4. አዎ!በሞትና በሕይወት መካከል ነው። (lubbuun ba'uuf jedha jirt.) | | |
| 5.ታዲያ ይህ ነገር ከምን መጣባችሁ አንልም? (wanti kun maal irraan isnitti dhufe hinjennuure?) | 6.አልን ይሄው። አቦ! እየሰማህ ነው? (jenne. Abboo dhageettee?) | 7. አባቶች! እኔ በሕይወቴ ብዙ ሀጢያቶችን ሰርቻለሁ። የቱን ተናዝዤ፤ የቱንስ እተዋለሁ? ስለዚህ አንድም ንስህ አልገባም በማለት መለሰ፣ (abbooti kiyya! Ani cubbuu hedduu hojjadheera. Kami faaci'adhee, kami ba'a. kanaafuu tokkolle hin faaci'adhu.) | |
| 8. ጃል! (abboo) | 9. እሺ ጃል (abbatto) | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10. ያለውን ሰማህ? ?(waan deebifate dhageettee) | 11. አዎ! «ምንም ፋጭ አልልም።» ነው ያለው። (Ee dhaga'e;« tokkolle hin faaci'adhu» jedhe. | | |
| 12.ፋጭ ትላንትም ያለ ነው፣ ከእግዚአብሔር የምንታረቅበት መንገድ ነው።( faaciin waan kale jiru;karaa Waaqaan ittiin araaramnu.) | 13. ፋጭ አልልም ማለት ነበረበት? (hin faaci'adhu jechuu qabaa? | | |
| 14.አልነበረበትም። ለምን አልክ አንለውም? (hin qabu ture. Maaf jette hin jennuure?) | 15.ይሄው አልነው። (kunoo jenne.) | 16. አባቶች! እኔ ፋጭ አልልም ያልኩበት ምክንያት ከንቀት መንፈስ ሳይሆን፤ ከሀጢያቴ ብዛት የተነሳ ነው።ያላሳዘንኩት ሰው የለም። (abbooti kiyya! Ani hin faaci'adhu kan jedhe; marroo cubbuu hedduu hojjadheef;nama ani hinboochisne hinjiru. Kanaaf jedheeti.) | |
| 17. ቢሆንም እንዲህ ማለት ነበረበት? (waan fedhe yoo ta'e akkas jechuu qaba?) | 18. አልነበረበትም። (Hinqabu.) | | |
| 19. ለምን አለ? (maaf jedheree?) | 20. አልአግባብ ነው። (Uddi maleedha.) | | |
| 21. ለእግዚአብሔርስ? (Waaqaaf hoo?) | 22. እውነት አለው። ፈጣሪ ሆይ ታረቀን። (dhogaa; nu araaram waaqa.) | | 23. ሁሉም በአንድ ላይ እጃቸውን በመዘርጋት «አቤቱ ታረቀን» ይላሉ።(Nu araaram ya Waaqa.Jedhan ) |

ሠንጠረዥ፡-3 የፋጭን ቅደመ-ተከተላዊ ሂደት የሚያሳይ

ከዚህ በኋላ ቡና ቃላ ተዘጋጀ፣ በካም (ጠጅም) መጣ፣ ሽማግለዎቹ ተራ በተራ እየተቀባበሉ እግዚአብሔር ይቅርታውን ወይም ፋጭውን እንዲቀበለው፣ ምህረቱንም እንዲያወርድለት እየተለማመኑ በቦካው ግራና ቀኝ እንትፍትፍ (biifee) እያሉ ይመርቁ ጀመር፡፡ ቡና ቀላውም በኦሮሞ ዘንድ እንደ ሙሉ (Mijuu) ስለሚቆጠር እሱንም በዙር በመቅመስ እየመረቁ ያስቀምሳሉ፡፡ በመጨረሻም ሰውዬው ትንፋሹ መለስ ብሎለት ቀና እንዳለና እንደተሻለው ከሰሙት ታሪክ ገለጸውልኛል፡፡ (አለማየሁ አድማሱ፣የሀሩ ቀበሌ ነዋሪ፣ዕድሜ 45፣14/5/2007)

ከዚህ የፋጭ ከበራ የተገነዘብኩት ለፋጭ ክዋኔ መኖር፤ ማህበረሰቡ ከእምነቱ አኳያ ጨቡ ናቸው የሚሏቸውን የማይጣሱ ትዕዛዛት ወይም ህግጋቶች መጣሳቸው እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህ በፋጭ ከበራ አካሄድ መሰረት እንደሚከተለው መከወኑን ያሳየናል፡፡ ይኸውም፡-

**በቅድመ-ፋጭው፡-** በዚህ የሂደት ደረጃ የሚከወነው የፋጭው ቅድመ-ክዋኔ ሂደት ሲሆን ነው፡፡ ይኸውም፡- በመጀመሪያ ደረጃ ፋጭውን የሚከውኑ፡- ወዩዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችን (የሚመለከተውን አካል) መርጦ መሰየም፣ የሚመለከታቸው የተባለበት ምክንያት፡- እንደ ችግሩ ቅለትና ክብደት በአባቃሉ፣ በአባገዳ፣ በሀዩ ወይም ሀገር ሽማግሌዎች የሚያዙ ጉዳዮች ስላሉ ነው፡፡ ከዚያ ሽማግሌዎቹ በተሰራው ጨቡ ምክንያት በቀጥታ ችግር ላይ የወደቀውን አካል የመለየት(የማወቅ)ና በተሰየሙት ሽማግሌዎች አማካይነት እግዚሐብሄርን በመጀመሪያ ለዚህ ስላበቃሄን ምስጋናችን ይድረሰህ፣ አሁን ደግሞ ለበደልንህ ንስሀችንን ተቀበለን፤ ይቅርም በለን፣ አንደበታችንን ክፈትልን፣ እውነትን አናግረን በማለት የመክፈቻ ጸሎት እየተቀባበሉ የሚያደርሱበት ሂደቶችን ያካትታል፡፡ ከዚያም ወደሚቀጥለው የፋጭ ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡

**ፋጭ፡-** በፋጭ የሂደት ደረጃ ሽማግሌዎቹ ለፋጭ የተዘጋጀውን ሰው በስም በመጥራት ምን ተቸግሮ እንደጠራቸው ይጠይቁታል፡፡ ተጠያቂውም በመጀመሪያ ይቅር በሉኝ በማለት ለመናገር ፍቃድ ይጠብቃል፡፡ ከዓይን ትረፍ (mucuca'i/hobba'i) ቀጥል ይሉታል፡፡ ከዚያ በቤታቸው ውስጥ ልጅ አላድግ ብሏቸው ይሆናል፤ አለያም ድርስ ላም፣ ፈረስ እየሞተባቸው ተቸግረው ይሆናል፣ የመኪና አደጋና ከመሳሰሉት ውስጥ አንዱን በተደጋጋሚ እንደደረሰበት ያስረዳል፡፡ በመቀጠል «የሆነ ጨቡ ስለሰራሁ እንጂ እግዚሐብሄር እንዲህ አድርጎ የሚቀጣኝ» በማለት ይገልጻል፡፡ ሽማግሌዎቹም ችግሩን በጽሞና ካዳመጡ በኋላ እየተቀባበሉ ጉዳዩን ያጣራሉ፡፡ ይኸውም ከእግዚሐብሄር ህግጋት ውስጥ የቱን በመጣስ ነው ጨቡ የተሰራው?፣ ጨቡውን በማወቅ ነው ባለማወቅ የተሰራው?፣ ለፋጭ የተነሳሳው በሰራው ጨቡ በወቅቱ ተፀፅቶ ነው?

ወይስ ችግሮቹ በመደጋገማቸው ፈርቶ ነው? የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጥያቄዎች አንዱ የረሳውን ሌላው እያነሳ ያጣራሉ። ለዚህም እንደምክንያት የሚያቀርቡት እግዚሐብሄር የእውነት አምላክ ነው። ስለዚህ እውነቱን ከስር አጣርተን በአግባቡ ስንለምነው ይታረቀናል ብለው እንደሚያምኑ መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ።

ከዚያ ሽማግሌዎቹ ጉዷ ሳፉ ያውቃል። ላጉ ያውቃል። አንተ ግን ይህን ጣስኩ አልከን። አንደኛው ሽማግሌ ‹‹ትሰሙ የለም?›› ይላል።

ሌሎቹ ሽማግሌዎች ደግሞ ‹‹አዎ! ሰማን፤ ለምን ይጥሳል?››

አንደኛው ሽማግሌ ቀበል አድርጎ ‹‹አግባብ አይደለም።›› ሲል

ሌሎቹ ሽማግሌዎች ደግሞ ‹‹ለዋቃስ?›› ይሉና ሁሉም በአንድነት ‹‹እውነት አለው። ፈጣሪ ሆይ ታረቀን።›› ይላሉ። በዚህ መልኩ አንድ በአንድ ፋጭውን ያካሂዳሉ።

እግዚኣብሔር በመጀመሪያ ይህን አድርጉ፤ ይህን ደግሞ አታድርጉ ብሎ በቃሉ አማካይነት ለምዕመኑ ትምህርት ተሰጥቷል። ስለዚህ አታድርጉ ያለውን ማድረግ ጩቡ ነው። ከዚህ በመነሳት የዋቃ ቅጣት አግባብ ነው፤ነገር ግን መሐሪ ነውና ይቅር ይበለን እያሉ በዳዩንና ተበዳዩን ያስማማሉ። በዚህ አውድ ተበዳዩ እግዚኣብሔር ነው። ስለዚህ እግዚሐብሄር ሆይ ታረቀው፤ ይቅር በለው። በማለት ሽማግሌዎቹ በመቀባበል የፋጭውን ሂደት ያስፈጽማሉ። ጩቡ የተሰራው በተደጋጋሚ ከሆነ ለእያንዳንዱ ጩቡ ከላይ ባየነው መሰረት የፋጭ ከበራ ተራ በተራ መከወን እንዳለበት ይገልጻሉ። በመጨረሻም ወደ ድህረ-ፋጭ ሂደት ይሸጋገራሉ።

**ድህረ-ፋጭ፡-** እንደየጩቡው ዓይነትና መጠን ቦካ፣ ቡና ቃላና ቅቤ እንዲሁም የመስዋዕት ኮርማ ተዘጋጅቶ የዚህ ዓይነቱ አደጋ ከዚህ ሰው፣ ከዚህ ቤት፣ ከዚህ ቤተሰብ ራቅ (ati hanqadhu), ዳግም አይመልስህ (lammuu si hindeebisin) በማለት በጎንደሮ ከበራ የሚያሳርጉ አሉ።

ባጠቃላይ እንደጉጂ ኦሮሞ ልምላሜ፣ ጤንነት፣ ጥጋብ ሊኖር የሚችለው የእግዚሐብሄር ህግጋት ሲከበር እንደሆነ ያምናሉ። ነገር ግን ህግጋቶቹ ተጥሰው፣ ነገሮች በተሳሳተ መንገድ ከተከናወኑ እነኚ የተጠቀሱት ጥጋብ፣ ሰላም፣ ልምላሜና የመሳሰሉት ሁሉ አይኖሩም ተብሎ ይታመናል። የዚህ ዓይነት ክስተት ሲፈጸም በቅድሚያ ምክንያቱን የማጣራት ሂደት ያከናውናሉ። ይኸውም ጉጂ ኦሮሞ በመጀመሪያ ለዚህ ችግር ምን ሀጢያት ብንሰራ ነው ይህ የሀጢያት መገለጫ ሊከሰትብን የቻለው በማለት ያጣራሉ። ችግሩ ሰውን መበደል፣ መስረቅ፣ ሳፉ ያለማክበር፣ ቀድሞ ይከወን የነበረ ከበራን ወደ ጎን መተውና ከመሳሰሉቱ ውስጥ አንዱን

ወይም ከዚያ በላይ ተፈጽሞ ሊሆን ይችላል። ከዚያን በኋላ ለዚያ ጉዳይ ኃላፊነት የሚወስድ አካል ተፈልጎ ግለሰብ/ቡድን የፋጭ ከበራ ይካሄዳል። ብዙን ጊዜ የፋጭ ከበራ የሚካሄደው ሰዎች ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ሲገቡ ነው። ይኸውም፡- በግለሰቦች ደረጃ በጣም ታመው ሲያጣጥሩ፣ በወልድ ወቅት ምጥ ጠንቶባት ነፍስ ውጭ፤ ነፍስ ግቢ ሲሆን፣ በሚወዱት ነገር ላይ ተደጋጋሚ አደጋ ሲደርስና የመሳሰሉት ናቸው። እንደ ቡድን ወይም ማህበረሰብ ደግሞ ከብቶቻቸው ባልታወቀ በሽታ ሲጠቁ፣ የእርባታው መጠን እየቀነሰ ሲሄድ፣ የግጦሽ ሳር እጦት፣ የተዘራው እህል ምርት ማነስ፣ የሰዎች ባልታወቁ በሽታዎች መሞትና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው። በመቀጠል ያን የበደሉት ነገር በፋጭ የሚስተካከልበትን መንገድ በማሳየት ቀጣዩ ጊዜ እንደቀድሞው እንደሚሆንላቸው ያምናሉ፤ያም ካልሆነ ችግር የእግዚሐብሄር ስራ ነው ብሎ በፀጋ ይቀበላሉ። አሊያም«እግዚሃብሄር ከእኛ ዘንድ ርቋል» በማለት በራሳቸው ስራ በመፀፀት በጸሎትና መስዋዕት በማቅረብ የእግዚሐብሄርን ምህረት ይጠባበቃሉ።

ከአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ከመስኩ ልምላሜ፣የጥጆችና ሕጻነቱ ፋፍተወ መቦረቅ፣ የጎተራ በእህል መሙላትና የመሳሰሉት እግዚኣብሔር ከእነሱ ጋር እንዳለ አመለካች ነው። በተቃራኒው አካባቢው በድረቅ ተመቶ፣ ጥጆችና ልጆች በመቦረቅ ፈንታ ኩስምን ካሉ፣ጎተራው ከሳሳባቸውና የመሳሰሉ ክስተቶችን ደግሞ ከሚያዩት ነገር ተነስተው እግዚኣብሔር እንደተቀየማቸው፤ ፊቱንም ከእነሱ ላይ እንዳዞረ አድርገው ያምናሉ።

ባጠቃላይ ይህ የፋጭን ከበራ ያየን እንደሆነ የጉጂ ኦሮሞ ከደረሰበትና ከሚደርስበት ችግሮች መውጫና ከፈጣሪው ጋር የሚገናኝበት ማህበረሰባዊ ዕውቀት ነው። ለዚህም ክዋኔ ደንብና ስርዓት አበጅተውለት በዚያ ስርዓትና ደንብ በመመራት ይከውናሉ። ይህን ዕውቀት ከኦበጀክቲቭዝም ኢፒስቲሞሎጂ አተያይ ስንመለከተው በአቅራቢያቸው የማይታያቸውን እግዚኣብሔር፣ በሚታዩ ምድራዊ ክስተቶች መገለጫነት ተግባቦት መፍጠር ችለዋል። ከነዚህ የተግባቦት መንገድ አንዱ ደግሞ የፋጭ ከበራ ነው።

## 6.5. የቃሉ ስያሜ ከበራ

ቀደም ሲል እንዳየነው ስለቃሉ ስያሜ አሰጣጥ በተነሳበት ወቅት አንድ ወደ ስልጣነ-ሚመት የሚመጣ የቀድሞው ቃሉ ልጅ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ካለ የስያሜ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ይፈጸሙለታል። ስለዚህ ከመረጃ አቀባዮቼ ባገኘሁት መረጃዎችና የ16ኛው አባቃሉ

አጋ ሳቆ ጋብቻና ስያሜ ከበራዎች እንደ ንጥል-ጥናት በመመርመር ከዚህ በታች ለመተንተንና መግለጽ ችያለሁ።

### 6.5.1. የቃሉ ጋብቻ ከበራ

ቃሉ እንደማንኛውም ኦሮሞ ከባህላዊ ጋብቻዎች ውስጥ በማጨት (kadhaan /naqataan) ስርዓት የሚከናወነውን ጋብቻ ይፈጽማል። ነገር ግን የስነ-ስርዓቱ ሂደት ለሌላው የማህበረሰብ ክፍል ከሚደረገው የተለየ ነው። ለዚህ እንደማሳያ የ16ኛውን ቃሉ የጋብቻ ሂደትና ሃይማኖታዊ እሴቱን ከዚህ በታች እናያለን።

የአባቃሉ አጋ ሳቆ ለጋብቻና የስልጣነ-ሢመት ሃይማኖታዊ ከበራ የመጀመሪያው ምክንያት የእሱ አባት የነበሩት 15ኛው አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ነው። ጉጂዎች አንድ ቃሉ ከዚህ ዓለም በሞት ስለይ «ሞተ» አይሉም፤ «ምራቁን ዋጠ» (hancufa liqimse) ይላሉ። የአሁኑ አባቃሉ አጋ ሳቆ የተመረጠው ታዲያ ቀደም ሲል ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ የመጀመሪያ የሆነውን ከእናቱ ከገለልቻ ጎሳ ካገቧት ባለቤታቸው የተወለደ መሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎችንም መስፈርቶች ስላሟላ ነበር።

በሌላ በኩል ለቃሉ የወደፊት የትዳር አጋሩ እንድትሆን የምትመረጠው ልጃገረድ ከጉጂ ኦሮሞ ጎሳዎች ውስጥ የገለልቻ ጎሳ ልጃገረድ መሆን አለባት። ምክንያቱም ቃሉ ከሰማይ ወረደ በተባለ ወቅት በተለያዩ ሰዎች ለማነጋገር ተሞክሮ ነበር። ነገር ግን ለማንም ምላሽ አልሰጠም ነበር። በመጨረሻም ከገለልቻ ጎሳ ወገን የሆነች ልጃገረድ ስትመጣ ፈገግታ እንዳሳያትና በመጨረሻም ሁለቱም አብረው መኖር እንደጀመሩ፣ ልጆችም እንዳፈሩ በምዕራፍ አምስት ስር በቀረበው ሚት ውስጥ ለማየት ችለናል። ታዲያ ይህ የገለልቻን ልጃገረድ መረጣ ከዚህ ሚት ተከትሎ የመጣ ነው።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የቃሉ ጋብቻ ሃይማኖታዊ ከበራን የምንመለከተው በመተጫጨት ላይ በተመሰረተው ባህላዊ የጋብቻ ዓይነት ላይ ነው። ይህ የመተጫጨት ሂደት እስከ ጋብቻው ዕለት ድረስ የተለያዩ ስርዓቶችን ተከትሎ የሚፈፀም ነው። ይኸውም፡- በመጀመሪያ ለትዳር አጋር የምትሆነውን ልጃገረድ መረጣ ይካሄዳል፣ በመቀጠል ማጨት፣ ከዚያም የሴቷ ቤተሰብ ምክክር ያደርጋል፤ በመጨረሻም እሽታውን ተከትሎ ጋብቻው ይፈፀማል።እነዚህን ሂደቶች ምን እንደሚመስሉ ከዚህ በመቀጠል አንድ በአንድ እንመለከታለን።

ከላይ እንደተገለጸው በማጨት ሂደት የሚከናወነው ባህላዊ ጋብቻ በስሩ የተለያዩ ክዋኔዎችን በቅደም ተከተል ይታለፋሉ፡፡ እነሱም፡-

i. ልጃገረድ መረጣ

ልጃገረድ መረጣ ሲባል ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አንድ ለአቅመ-አዳም የደረሰ ልጅ በባህሉ መሰረት የወደፊት የትዳር አጋር ልትሆነው የምትችል ልጃገረድ መምረጥ የወንዱ ቤተሰብ መብት ነው፡፡ ለቃሉ የምትሆነውን ልጃገረድ ግን የሚመርጠው እራሱ ወይም የእሱ ቤተሰብ ሳይሆኑ፤ ህዝብ (kolbaa) ነው:: ከማህበረሰቡ ውስጥ እንዲሁም ከገለልቻ ጎሳ ልጃገረዶች ውስጥ የትኛዋ ብትሆን ትሻላለች ብለው፤ በባህሉ መሰረት የሚመርጡት አባገዳዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ካሎዎችና የጎሳ አባላት ናቸው፡፡ እነዚህ ከቃሉ ጋር በመገናኘት መረጃዎችን ይለዋወጣሉ፡፡ ከዚያም እኔ ከገለልቻ ጎሳ ወገን የሆነች መልካም ልጃገረድ አግኝቻለሁ ከሚለው ሰው መረጃ ይደመጣል፡፡ ከዚያ ለጊዜው በምርጫው ከተስማሙ ዕጣ-ፈንታ (faroo) ታይቶ፣ እግዚሐብሄርን ተለማምነውና ጠይቀው፣ ስለጉዳዩ የታዩ ህልሞች ተፈተው፣ ከሰሙትና እግዚሐብሄር ካመላከታቸው ላይ ተመርኩዘው ይመርጣሉ፡፡

ለቃሉ ባለቤትነት የምትታጨው ልጃገረድ ማሟላት ያለባት መስፈርቶች አሉ፡፡ ይኸውም፡- ከገለልቻ ጎሳ ከመሆኗ በተጨማሪ ከነክብረ-ንጽህነዋ የቆየች (quttoo kan qabdu)፣ መልካም ፀባይ ያላት፣ ባህልና እምነቷን ጠብቃ የኖረችና ጨዋ የጨዋ ቤተሰብ ልጅ መሆኗንና የመሳሰሉት ሁሉ ይታያሉ፡፡ በመጨረሻም የእገሌ ልጅ ትሆናለች ተብሎ ከተስማሙ በኋላ ልጅቷን ለማጨት የሚሄዱበትን ዕለት ወስነው ይለያያሉ፡፡

ii. ማጨት

በጉጂዎች ዘንድ በባህላዊ ጋብቻ ውስጥ የሴቷ ወገን ለልጃቸው የትዳር አጋር እንዲሆናት ከወንዱ ወገን ጥያቄ ሲቀርብላቸው በቀጥታ የሚገቡት ስለማንነቱ ከማወቁ ላይ ነው፡፡ ይኸውም፡- ጎሳው፣ መተዳደሪያውን፣ እምነቱንና የመሳሰሉትን በመጠየቅ ለዝምድና የቀረበላቸውን ጥያቄ የመቀበል፤ አሊያም ውድቅ የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ፡፡ ነገር ግን በቃሉ በኩል ለመጡ ሽማግሌዎች እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች አይቀርቡም፡፡ ምክንያቱም በጎሳ በኩል ለሚነሳው ጥያቄ ከቃሉ ቤተሰብ የበለጠ እንደሌለ ይናገራሉ፡፡ በንብረትም በኩል ከሆነ የእሱ ንብረትና ለእሱ በስጦታ መልክ የሚበረከትለት ተቆጥሮ መዝለቅ እንደማይቻል ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ለአባቃሉ የወደፊት ባለቤት የሚያጩት፡- የቃሉ አጎት፣ አባገዳዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ካሎዎች ፈጣሪያቸውን ተለማምነው፣ የታያቸውን ህልም ፈተው፣ ዕጣ-

ፊንታቸውን (faroo) እያዩ ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ጉዞ ያደርጋሉ። ከዚያም እንደደረሱ በኦሮሞ ባህል መሰረት የልጅቷን ቤተሰብ ሰላምታ በመጠየቅ የመጡበትን ጉዳይ ይገልጻሉ። የልጅቷም ቤተሰብ ከቃሉ ወገን የቀረበላቸውን ጥያቄ በታላቅ ክብር ይመለከቱታል። እንደባህሉ ልጃቸውን ለመከልከል ያልሆኑ ምክንያቶችን መደርደር የለባቸውም። ይሁን እንጂ እንዲያው ለወጉ ተብሎ «ከዘመድ ተማክረን፣ ዕጣ-ፈንታ አይተን መልስ እንሰጣለን»በማለት በቀጠሮ ይለያያሉ።

iii. **የቤተሰብ ምክክር**

እንደ ጉጂ ኦሮሞ አንድ ሰው ልጃችሁን ለልጄ ብሎ ከጠየቀ፤አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎችን በመጠየቅ ዝምድናውን የሚከለክል ጉዳይ ከሌለ ወላጆቿዋ ጋብቻው ለብቻቸው እሺ አይሉም። ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ያሉ ዘመድ አዝማድ ተጠርቶ በጉዳዩ ይመክሩበታል። ሲተርቱም“worri marii qabu jibicha qalate, kan marii hinqabne immoo, raada qalate.” ይላሉ። ይህም «ተማክረው የፈሱት...» እንደማለት ነው። ታዲያ የልጇቷ ቤተሰብ ቀደም ብሎ ይጠራራና ልጅቱን እንስጥ ወይም አንስጥ በሚሉት ሀሳቦች ላይ ሳይሆን የሚመካከሩት፡- «ሀላፊነቷን በአግባቡ ትወጣለች?» የምል ሀሳብ ላይ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

በቀጠሮው ዕለት ከቃሉ ወገን ሽማግሌዎች ይሄዳሉ። በአዳራቸውም ሆነ በመንገዳቸው ላይ የታያቸውን ዕጣ-ፈንታ እያጤኑና እየፈቱት ይጓዛሉ። እዚያም እንደደረሱ እንደተለመደው የእግዚሐብሄር ሰላምታ በመስጠት «እኛ መልካም መልካሙን እያየን ነው የመጣነው። እናንተስ ምን ታያችሁ?» በማለት ይጠይቃሉ። የልጅቷም ቤተሰብ «እኛም ያየነው መልካም ነው፤ ነገር ግን ልጃችን የሀዳ አንባነቱን ኃላፊነት እንዴት ልትወጣው ትችላለች የሚል ስጋት ፈጥሮብናል።» በማለት ቅር የተሰኙበትን ነገር ያቀርባሉ።

የቃሉ አጎት «ይህን ክፍተት የመሙላቱን ጉዳይ እኔ እወጠዋለሁ። የቀደሞዋ የአንባ እናት ታስተምራታለች፤ አስተምራታለሁ።» በማለት አደራውን ለመረከብ ቃል ገቡ።
ከዚያ በኋላ የልጅቷ ቤተሰብ ለዝምድና የቀረበላቸውን ጥያቄ መቀበላቸውን ገለጹ። በመቀጠል ለሽማግሌዎቹ የተዘጋጀ ሙሉ መጠጥ (Mijuu) ቀረበ። ሁለቱም ወገን ደስታቸውን በጭብጨባ ገለጹ። ባህላዊ ጭፈራም ይጨፍሩ ገቡ።

በመጨረሻም የጋብቻውን ዕለት መወሰን ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ የሚሆነው ከቃሉ ወገን በመጡት ሽማግሌዎች አማካይነት ነው። ይኸውም የጋብቻውን ዕለት ሞራ አንባቢዎች፣ ኮከብ ቆጣሪዎችና ሽማግሌዎቹ አብረው ተቀምጠው ቀኑን፣ ወሩንና ዓመቱን መች መሆን እንዳለበት

ፈጣሪያቸውን በመጠየቅ የሚወሰን ይሆናል። ከዚያም ለልጅቷ ቤተሰብ ወቅቱ እንደደረሰ እንደሚነገራቸው ተገልጾ በቀጠሮ ይለያያሉ።

iv. የጋብቻ ስነ-ስርዓት

በቃሉ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ላይ አግቢው ከአጃቢዎቹ ጋር አብሮ በመታደም ወደ ልጅቷ ቤት አይሄድም። ቃሉ በጉጂ ማህበረሰብ ዘንድ በሀገረሰባዊ ሃይማኖቱም ሆነ በባህሉ በኩል ከፍተኛ ከበሬታ አለው። ስለዚህ ቃሉ ልጃገረድ ከመምረጥ አንስቶ እስከ ጋብቻው ስነ-ስርዓት ድረስ ያለው ሂደት ላይ አይሳተፍም፤ ከቤተ-አምልኮው (galma) አይንቀሳቀስም። ከአባቃሉ አጋ ሳቆ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ላይ ለማየት እንደተቻለው፡- የቃሉ አጎት፣ የቃሉ እህት፣ አባገዳዎች፣ ካሎዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የቅርብ ዝምድና ያላቸው በአንድ ላይ ሆነው ከሙሽራዋ ቤተሰብ ዘንድ በመሄድ ሙሽሪትን ይዘው፣ እየጨፈሩ ይመጣሉ።

በዚያን ዕለት አባገዳዎች፣ ካሎዎችና የሀገር ሽማግሌዎቹ ጎንፋ (gonfaa) እና ቡሉኮ መሳይ (ejja) የሚባሉ ባህላዊ አልባሳታቸውን ለብሰው፣ አባገዳዎችና ካሎዎች በተጨማሪ በግንባራቸው ላይ ካላቻ አስረው፣ቦኩ (bokku) ይዘው፣ የቃሉ እህት ደግሞ የጉጂ ልጃገረድ ባህላዊ ልብስ የሆነውን ቆሎና ቆሜ (Qoloofi qomee) ለብሳ፣ ጸጉሯን ባህላዊ ሹሩባዋ ተሰርታ፣በላዩ ላይ ልክ እንደ አንቴና የሚቆም የልጃገረድነት ምልክት የሆነውን ቁቶ (quttoo) አድርጋ ከእነሱ ጋር ትሳተፋለች። ለሙሽሪቷ የሚሰጥ ቡሉኮ (ejja) በመያዝ፣ ሌሎቹ ደግሞ ለልጅቷ ቤተሰብ የሚሰጥ ስድስት ጥጃዎች በመንዳት ይወሰዳል። ከባህሉም አኳያ መኬድ የነበረበት በእግር ሲሆን፤ ከቦታው ርቀት የተነሳ በመኪና እንዲጓዙ ተደርገው፤ ወደ ሙሽሪት ቤት ሲቃረቡ በስርዓቱ መሰረት እየተጨፈረ ከደጃቸው ሲደርሱ የእሷ ቤተሰብ በገበቴ ቦካ (ጠጅ) ሞልተው ጠጋ ብለው ይቀበሏቸዋል። ይህ ክዋኔ ከተምሳሌታዊ አተረጓገም አኳያ ስንመለከተው የመጡበት ጉዳይ እንደተሳካና መልካም ምኞት መግለጫ ተደርጎ ይቆጠራል። ከቃሉ ወገን ለሄዱት ደግሞ የሄዱበት ጉዳይ መሳካቱን አመላካች እንደሆነ ይቆጠራል። ከዚያ ሽማግሌዎቹ ደግሞ ቃሉን የሚያሞግሱ ጭፈራዎችን እየጨፈሩ ይጠጋሉ። ከዚያም ያንን ሙሉ ጠጅ ከአማቻቸው እጅ በመቀበል ይዘዋቸው በመጡት ጥጆች ጀርባ ላይ እንትፍትፍ (biifee) እያሉ፤ እርቡ! በረት ሙሉ! በማለት ይመርቋቸዋል።




ፎቶ፡-16 ከመሀል የቃሉ እህት፣ ከበስተቀኟ ሁለተኛው የቃሉ አጎት፣ ከበስተግራ ገዳ ሀልቻዬና ሌሎችም ስጦታዎቹን ይዘው ሙሽሪትን ለማምጣት ሲሄዱ።

የልጅቷም ቤተሰብ የመጡትን እንግዶች በአክብሮት ወደ ውስጥ እንዲዘልቁ በማድረግ ይጋብዟቸዋል። ሙሽሪትን ከጓዳ ይዛት የምታወጣት የቃሉ እህት ናት። ምክንያቱም ከጋብቻው ቀን ቀደም ብሎ የቃሉ አጎት መጥቶ ቁንቢ ስላሰቀመሳት ሌላ ሰው ሊይዛት አይችልም። ስለዚህ የቃሉ እህት ይዛ የመጣችውን ቡሉኮ የሙሽራዋ ትከሻ ላይ ጣል አድርጋ ይዛት ትወጣለች።

ሙሽሪትን ቤተ-ዘመዷና የአካባቢው ሴቶች ቅቤ አምጥተው እየመረቁት ይቀቧታል። የቅቤው ተምሳሌት እርጥበትን አመላካች ነው። መሀጸኗ እርጥብ እንዲሆኖ፤ልጆች እንድታፈራ መልካም ምኞት መግለጫ ነው። የልጅቷ እናት ደግሞ ሲቄ፣ ቦራቲ፣ በቅል እርጎ፣ የፊት ቅቤ፣ ቡና ቃላና እርጥብ ሳር ታስዛታለች። የሲቄው ተምሳሌት ከልጃገረድነት ወደ ሴትነት መቀየር እየሄደች እንደሆነና ከጋብቻ በኂላ የምትይዘው መሆኑን አመላካች ነው። ቅቤው፣ ቡና ቃላውና እርጥቡ ሳር ደግሞ የሙሉነትና ልምላሜ ተምሳሌቶች ናቸው። በመቀጠል አጃቢ ሽማግሌዎቹ ሸኙን ይላሉ። የልጅቷም ቤተሰብ በሰላም ግቡ በማለት ያሰናብታሉ። ሙሽሪትም ባህላዊ አልባሳቷን ለብሳ፣ የቃሉ እህት ቀኝ እጇን ይዛ፣ አጃቢዎቹ እነሱን መሃል አርገው ቃሉን እያወደሱ በመጨፈር ወደ ቃሉ ተቋም ጉዞ ይጀምራሉ።

በመጨረሻ ወደ ቃሉ ተቋም ሲቃረቡ ከተለያዩ ቦታ በዝግጅቱ ለመታደም የመጡ አዛውንቶች፣ ሴቶችና ወጣቶች አካባቢውን በማጥለቅለቅ እንደየደረጃ እኩዮቻቸው በቡድን በቡድን እየሆኑ በባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎች መንደሩን እያቀለጡ ይጠብቃሉ፡፡ ቃሉ ደግሞ በቤተ-አምልኮው ውስጥ በመጋረጃ በተጋረደ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ ይጠባበቃል፡፡ ከዚያም የእነሱን መምጣት እንዳወቀ ወደ ደጃፉ ጠጋ ብሎ ይቆማል፡፡ በመቀጠል አጃቢዎቹ ቃሉ እንትፍትፍ በልብን (Qaalluu biifi)፣መርቀን (Qaalluu eebbis) እያሉ በመጨፈር ሙሽሪትን ወደ ገልማው ያስጠጋሉ፡፡ ለሙሽሪቷ የተዘጋጀችውን ጊደር ይሰጧትና የዚያች ጊደር ጭራ ይዛ፣ ከቤተሰቦቿ የተሰጣትን ስጦታዎች እንደያዘች የቃሉ እህት ቀኝ እጇን ይዛ ለቃሉ ታስዘውና ተያይዘው ወደ ውስጥ ይገባሉ፡፡ የዚያችን ጊደር ጭራ ይዛ ወደ ውስጥ እንድትዘልቅ የሚደረገው ተምሳሌታዊ ትርጉም አንደኛው ይቺ ጊደር የዚያ ቤት የመጀመሪያዋ ስጦታ መሆኗን አመላካች ናት፡፡ በሌላ በኩል በባህሪያቸው በማመሳሰል የልጃገረድነቷ መገለጫም አድርገው ያዩታል፡፡ በመቀጠል የጫቁላ ስነ-ስርዓቱ (quttoo kaasuu) ይፈፀማል፡፡

በመቀጠል ሙሽሪትን ከጋብቻው በፊት በቃሉ እኅት አማካይነት ቁንቢ እንድትቀምስ የሚደረግበት ምክንያት እሷም ከጋብቻዋ ዕለት አንስቶ ከቃሉ ጋር ስትኖር ውሸት ላለመናገርና ከጎኑ ሆና አብራው ለመስራት ቃል የማስገባት ስርዓት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በከበራ ውስጥ እንድ ሰው በፊት ከነበረበት ደረጃ ወደ ሌላው የሚያደርገው ሽግግር ነው፡፡ ይኸውም ሙሽሪቷ ቁንቢውን ከቀመሰችበት ዕለት አንስቶ ከተራ ምዕመንነት ወደ ቅዱስ ሰውነት ተሸጋግራለች ማለት ነው፡፡

የጉጂ ቃሉን የጫቁላ ስነ-ስርዓቱ (quttoo kaasuu) ከተመለከትን ከቦረና ቃሉ ለየት እንደሚያደርገው በምዕራፍ አምስት ስር ተመልክተናል፡፡ የጉጂ ቃሉ የሙሽሪቷን ክብረ-ንጽህና የሚወስደው እራሱ ነው፡፡ የነገው አባቃሉ የሚወለደውም ከዚች ሴት እንደሆነ ከቃሉ አመጣጥ ሚት እንረዳለን፡፡ እንደ ጉጂ ኦሮሞ አተያይ ቃሉ በባህሪው ከሌላ ሰው ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ከፈጸመች ሴት ጋር ግንኙነት አይፈጽምም፡፡ በኦሮሚያ «Qaalluun dubartii namni biraa tarkanfate, hintarkanfatu.» ማለትም የጉጂ ቃሉ ሌላ ሰው የተገናኛትን ሴት አይገናኛትም ለማለት ነው፡፡

የቃሉን ስልጣን በዘር ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ነው ካልን የጉጂው ቃሉ የመጀመሪያ ሚስቱን የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማድረጉ፣ ስልጣኑን ከእሱ ወደ ልጁ እንዲተላለፍ ማስቀጠያው መንገድ መሆኑን እንረዳለን፡፡

## 6.5.2. የቃሉ ስያሜ ከበራ ሂደት

ለቃሉ ስም የምሰየምለት ሁለት ጊዜ ነው፡፡ ይኸውም፡- አንደኛው እንደተወለደ እንደ አንድ የጉጂ ወንድ ልጅ በአራተኛው ቀን የተፀኦ ስም ይሰየምለታል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ስልጣኑ-መለኮቱን ሲያጸድቁለት የሚኖረው ስያሜ ነው፡፡ ከቀድሞው ቃሉ ሞት በኂላ ለተተኪው ልጅ ቃሉ ለመሆኑ የማጽደቅ ክዋኔ አለ፡፡ አዲስ ቃሉ የሚሆነው ልጅ ቀደም ሲል ያየናቸውን መንፈሳዊና ሰዋዊ መስፈርቶችን ካሟላ በኂላ የመጨረሻ ጋብቻ መፈጸም አለበት፡፡ የጋብቻውን ሁኔታ በ 6.5.1. ስር በዝርዝር ተገልጿል፡፡ ከዚያ በመቀጠል የአዲሱ ቃሉ አጎት በጋብቻው ማግስት ከተሰያሚው ጎን በመቀመጥ እንደ ባህላቸውና እምነታቸው መሰረት ለታዳምዎቹ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ ከአደራሹ የሚገኙት ታዳሚዎችም በተራቸው በማጽደቅ መንፈስ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ክዋኔውም ከቃሉ አጋ ሳቆ ስያሜ ከአውዱ ላይ ለመመልከት እንደተቻለው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| <u>Abbaan (wasiilli ykn abuyyaan)</u> | <u>Jamaan</u> |
| --- | --- |
| Ani ilmaaf maqaa baafadhaara anaa-dhaga'aa. | Ilmi si'iif guddatu;guddatee si'ii uddo'u. |
| Ani ilmaaf maqaa Aagaa baafadhaara-anaa dhaga'aa. | Aagaan si'iif guddatu; guddatee si'ii uddo'u. |
| Ammalle intalaaf maqaa baafadhaara-anaa dhaga'aa. | Intalti si'iif guddattu;guddattee si'iif uddoottu. |

ሲተረጎም፡-

| <u>ሰያሚው (አጎቱ)</u> | <u>ታዳሚው</u> |
| --- | --- |
| እኔ ለወንድ ልጅ ስም ላወጣ ነውና-አድምጡኝ፡፡ | ልጁ ይደግልህ፣ አድጎ ላንተ ጥሩ ይሁንልህ፡፡ |
| እኔ ለወንድ ልጁ አጋ ብየ ስም ላወጣ ነውና አድምጡኝ፡፡ | አጋ ይደግልህ፣ አድጎ መልካም ይሁንልህ፡፡ |
| አሁንም ለሴት ልጁ ስም ላወጣ- ነውና አድምጡኝ፡፡ | ልጅቷ ትደግልህ፣ አድጋ መልካም ትሁንልህ፡፡ |

በማለት እሱን በቃሉነት፣ እሷን ደግሞ በሀዳ አንባነት ስያሜው ይጸድቃል፡፡ ከዚያን ዕለት አንስቶ ይህ ስም ለሕዝቡ ይለፈፋል፡፡ ከዚያን ዕለት አንስቶ ማህበረሰቡ በዚያ ስም አባ ቃሉ አጋ ብለው ይጠሩታል፡፡

### i. እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ልጅ ከሌለ ምን ይደረጋል?

አቶ ሞኮና ይህ የተጠቀሰውን መስፈርቶች የሚያሟላ ልጅ ካለ የአስር ዓመት ልጅም ቢሆን ይሰየማል። ነገር ግን ልጅ እግር ከሌለ ከትላልቆች ውስጥ ሊመረጥ እንደሚችል ይገልጻሉ። ይኸውም፡-

> እንደ ምሳሌ አድርገን የአባቃሉ ሳቆ ናጋኦን ጋብቻ እንመልከት›› አሉኝ አቶ ሞኮና። *ከአባቃሉ አጋ ሳቆ በፊት የነበረው የሱ አባት፣ የኔ ደግሞ ወንድሜ የነበረው አባቃሉ ሳቆን ናጋኦ ይባላል። ከአባቃሉ ናጋኦ ቶቴ ነው የተወለደው። የተወለደ ቀን ከነከረጥት ተሸፍኖ ነበር የተወለደው። የተቀሩትንም መስፈርቶች ያሟላ ነበር። ነገር ግን፣አባቃሉ ናጋኦ ቶቴ በሕይወት እንዳሉ እሱ ለአቅመ አዳም ደረሰ። እንደባህላችን ተዳረ። ከዚያም የራሱን ሕይወት ይኖር ጀመረ። ከጉጂ ብሔር በተጨማሪ ከሌላም ብሔር ሚስት አግብቷል። ታዲያ እኝህ 14ኛው አባቃሉ ሲያርፉ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ካሳገቡት መካከል መስፈርቶቹን የማሟላው እኔ ነበርኩ። አባታችን ጠርቶኝ እጄን ይዞ መረቀኝ። ህብረተሰቡንም እንዳስተዳድር ወከለኝ። እኔ ግን ይህ ኃላፊነት እሳት ነው፤ያቃጥላል። እውነት መናገር ይጠበቅብሃል። ሌላ ‹ሰው የተራመዳትን ሴት መራመድ› የለብህም። ስለዚህ በብዙ በኩል ካንተ የሚጠበቁትን ማሟላቱ ትንሽ ከብዶ ስለታየኝ እንቢ አልኩ። ስለዚህ በባህላችን ቀደም ሲል እንደሚደረገው ሁሉ ከልጆች ውስጥ ሲታጣ ከትላልቆቹ መስፈርቱን የሚያሟላ ይሰየማል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ቀድሞዉኑ እሱን ስለመረጠና ስላዘጋጀው ነው። አሉኝ ከዚያ በኋላ ቃሉ የሚሆን ሰው ማንነቱ ከታወቀ በኋላ ለስያሜ ስርዓት ዝግጅት ይጀመራል። ቀደም ስል እንደነገርኩህ ባለ ሙሉ ስልጣን ለመሆን ሁለት ነገር ይቀረው ነበር። አንደኛው እንደ ጉጂ ባህልና እምነት ከገለልቻ ጎሳ ወገን ከሆነች ልጃገረድ ጋር ጋብቻ መፈፀም አለበት። ምክንያቱም ነጌ የአንባ እናት ተብላ የምትሰየመው እሷ በመሆኗና ከሱ ጎን ሆና መስዋት ስለምታቀርብ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሱ ስያሜ ስርዓት መፈፀም ነበረበት። ስለዚህ ስርዓቱን ለማሟላት ከገለልቻ ጎሳ ወገን ከሆነች ልጃገረድ ጋር ጋብቻ እንዲፈጽም ከተደረገ በኋላ ቀድሞም እንደሚደረገው በሁለተኛው ቀን ስያሜው ተከናወነ። ከዚያ ስርዓቱን እንዳሟላ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ 15ኛው አባቃሉ ሆኖ ሲያገለግል ነበር።አሁን ያለው አባቃሉ 16ኛው አባቃሉ አጋ ሳቆ ይባላል። ከቀድሞው አባቃሉ ሚስቶች ውስጥ የአንባ እናት ከሆነችው የተወለደና የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ስለሚያሟላ ተመርጦ የተሰየሜ ነው። (አቶ ሞኮና ናጋኦ፣ቆቱ* ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ በ12/11/2007 ዓ.ም.)

ከዚህ መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው ለቃሉ መሰየም ሁለት ዓይነት መስፈርቶች ናቸው። አንደኛው መንፈሳዊ ሲሆን፣ይኸውም፡- ከቃሉ አመጣጥ ሚት ጋር የተያያዘ ነው። ቃሉ ከሰማይ በፕላስቲክ መሰል ነገር ውስጥ ተሸፍኖ ከከበሩ ቁሶች ጋር እንደወረ ይነገራል። ስለዚህ ከዚህ ጋር በሚያያዝ መልኩ አንድ ልጅ ከቃሉ ቤት ሲወለድ በስስ ሞራ መሰል ነገር ተሸፍኖ

የተወለደ ከሆነ ነው ቃሉ መሆን የሚችለው። ይህ ተምሳሌት ከሚቱ ጋር የተያዘ ነው። ከዚህም በመነሳት እግዚአብሔር ቃሉ የሚሆነውን ቀድሞ በዚህ ዓይነት ስለሚፈጥረው የመጀመሪያው መንፈሳዊ መስፈር ሆኖ ያገለግላል። ሁለተኛው መስፈርት ደግሞ ሰዋው ተክለሰውነቱንና ባህሪያቱን ያካተተ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ ከማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን አኳያ እነዚህን መስፈርቶች ተዋቅረው፤ በነዚህ መስፈርት መሰረት በመምረጥ፣ በመጨረሻ ቃሉ ብሎ በመሰየም መሪያቸው አድርገው ይገለገሉበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉን መልሰው ሰው እንደሆነና ገልማውም ቤት እንደሆነ የሚያሳይ ፎክሎራዊ አገላለጾችን ሲጠቀሙ ይታያል። ከነዚህም ውስጥ ቃሉን እያወደሱ በውስጡ ሰዋው ባህሪውን በጭፈራ (qeexala) እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

| | |
|---|---|
| Samaxee yoo hoo | hayaa hayaa |
| ሳማጤ ዮሆ ዮሆ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |
| ሳማጤ | ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን |
| Qaalluu waaqa seyee | hayaa hayaa |
| ቃሉ እግዚአብሔር መስሎኝ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |
| ሳማጤ | ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን |
| Biraa geenyaan nama abboo | hayaa hayaa |
| አጠገቡ ስደር ሰው ነው ለካ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |
| ሳማጤ | ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን |
| Galmaan tulluu seyee | hayaa hayaa |
| ገልማ ጋራ መስሎኝ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |
| ሳማጤ | ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን |
| Biraa geenyaan mana abboo | hayaa hayaa |
| አጠገቡ ስደር ቤት ነው ለካ | ሃያ ሃያ |
| Samaxee | yoo hoo yoo hoo Qaalluu biifi |

ሳማጤ ዮሆ ዮሆ ቃሉ ባርከን በማለት ይጨፍራሉ፡፡

ከዚህ ዘፈን ግጥም የምንረዳው ቃሉ ቅዱስ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ወይም ፈጣሪ አይደለም፤ እንደኛውን ሰው ነው የሚል አንድምታ ሲኖረው፤ ገልማም መንፈሳዊ ስራ ይሰራበት እንጂ ያው ቤት ነው የሚል መልዕክት የያዘ ነው፡፡

### 6.5.3. ለቃሉ የሚሰጡ ስጦታዎች

እንደ ጉጂ ኦሮሞ በጋብቻ ወቅት ለተጋቢዎቹ ጎጆ መውጫ ተብሎ ስጦታ ማበርከት የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን ለቃሉ የሚሰጡ ስጦታዎች ከሌላው ማህበረሰብ ለየት ይላል፡፡ ይኸውም፡- ምዕመኑ ለቃሉ ከጋብቻው በፊት፣ በጋብቻው ዕለትና ከጋብቻው በኋላ የተለያዩ ስጦታዎችን (gumaacha) ያበረክታሉ፡፡ እነዚህም ስጦታዎች በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡ እነሱም የጋብቻ ወቅትና የሃይማኖታዊከበራዎች ወቅት ስጦታዎች ይባላሉ፡፡

የቃሉን ጋብቻ ለየት ከሚያደርጉት ጉዳዮች ውስጥ ሌላኛው ባህሪይ ድግሱ የሚደገሰውና ወጭውም የሚሸፈነው በማህበረሰቡ መሆኑ ነው፡፡ ይኸውም፡- ለእርድ የሚውሉ ሰንጋዎች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ጤፍ፣ ቅቤ፣ ማር፣ እርጎ፣ ጩከና የመሳሰሉ ማንኛውንም ነገር በፍላጎት ላይ ተመስርቶ ማህበረሰቡ ያቀርባሉ፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የወጪ ክፍተቶችን ለመሸፈኛ የሚውል በጥሬ ገንዘብ በአባገዳዎች አማካይነት ተሰባስቦ ለቃሉ ይሰጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለወደፊት በሕይወት ዘመኑ ሊጠቀምበት የሚያስችለውን በመቶዎቹ የሚቆጠሩ ጊደሮችና ወይፈኖች እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠር በጥሬ ገንዘብ በአባገዳዎች አማካይነት በስጦታ መልክ ይበረከትለታል፡፡ቃሉ ደግሞ በምላሹ ስጦታውን ያበረከቱትንም ሆነ ጎሳውን ባጠቃላይ ይመርቃል፡፡ ህዝቡንና ምድሪቷን ጭምር ሰላም እንዲሆኑ፣ ከብቶቻቸውም እንዲረቡ፤ እንዲበዙ ይመርቃል፡፡ እነዚያ በስጦታ የተበረከቱትን ከብቶች ተመልሶ ማህበረሰቡ እንዲጠብቃቸው ተከፋፍሎ ይሰጣሉ፡፡ እንደመረጃ አቀባዩ ገለጻ እነዚያ ከብቶቹ የተሰጣቸው ሰዎች ከብቶቹ ደርሰው ሲወልዱ፤ ከወተቱና ከቅቤው እየያዙ ለቃሉ እንደሚያመጡና እነሱም የተረፈውን ለራሳቸው ይጠቀማሉ (Zalaalam, 2000; አቶ ሞኮና ናጋአ፣ ጌዴኦ ዞን፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ27/6/2008 ዓ.ም.)፡፡

ሌላው በሃይማኖታዊ ከበራ ወቅት የሚሰጡትን ስጦታዎች በተመለከተ በምዕራፍ አምስት ስር ለመጥቀስ እንደተሞከረው በሂሮ ስር ለሚከወነው መስዋዕት የሚያስፈልገውን ብቻ በቃሉ

የሚዘጋጅ ሲሆን በሌሎች የከበራ መቼቶች ላይ ለሚከወነው የሚያዘጋጀው ህዝቡ ነው። ይኸውም አንዳንዴ ግለሰቦች በፍላጎታቸው በረከት ለማግኘት ከመፈለጋቸው የተነሳ የሚፈለገውን ከብት ያቀርባሉ። ነገር ግን ባብዛኛው የሚደረገው በጃልዳባዎች አማካይነት ከምዕመኑ ላይ ገንዘብ ተሰባስቦ የሚፈለገው ዓይነት ከብት ይገዛል። ሌላው ሴቶች ትኩስና እርጎ ወተት፣ ቡና ቃላና ወንደሮ (ጩኮ) በስጦታ መልክ ያቀርባሉ።

# ምዕራፍ ሰባት

## የቃሉ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት

በዚህ ምዕራፍ ስር ስለጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ቀጣይነትና ለተከሰቱ ለውጦች በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ አስተዋጽኦ የነበራቸውን ዓለማቀፋዊ፣ ሀገራዊና ማህበረሰባዊ ክስተቶችን እንደ መግቢያነት ተዳሰዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዱን የቃሉ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት ከክልላዊ ንድፈ-ሀሳብ አኳያ ተተንትነው በገለጻ መልክ ቀርበዋል፡፡ የጉጂ ኦሮሞ ቀደም ባሉት ጊዜያት ማለትም ከምኒልክ ወረራ በፊት ልክ እንደሰሜኑ የኦሮሚያ አካባቢ ይህ ነው የሚባል የጎላ ጫና በማንኛውም ወገን አልደረሰበትም ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እንደ አለማየሁና ሌሎች ገለጻ በ15ኛ ክ/ዘ ውስጥ የክርስቲያኑ መንግስት እያየለ በመጣበት ወቅት በዘረ ያዕቆብ (1434-1468) በላንጋኖ ሀይቅ አካባቢ ሰፍረው የነበሩትን የጉጂ ኦሮሞዎች ወደ ደቡብ እንዲያፈገፍጉ ተደርገዋል (Alemayehufi kan biroo, 1999፡275)፡፡

ጉጂዎች አሁን ላሉበት የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችም ሆነ ሌሎች ተያያዥነት ላላቸው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያና ባህላዊ የይዘትም ሆነ የቅርጽ ለውጦች፤ ከምኒልክ መንግስት አንስቶ አሁን እስካለንበት የኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት አገዛዞች የየራሳቸውን አሻራ አስቀምጠዋል፡፡ በተለይም በገዳና የቃሉ ተቋማትና ተግባራቸውን ከማዳከም አንስቶ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለማጥፋት እስከመሞከር ደረጃዎች መድረሳቸውን ታሪክ ያወሰዋል፡፡

እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለጻ ስለነዚህ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ተቋማት መዳከም እያንዳንዱ የአገዛዝ ስርዓት በመጠንና ዓይነት ተፅዕኖ ያደርሱና እያደረሱ ያሉበት መንገድ ይለያይ እንጂ የሁሉም አስተዋጽኦ ነበረበት፡፡ ይህ ደግሞ ለቃሉም ሆነ ገዳ ከበራዎች መዳከምና ለውጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን መረጃ አቀባዮቼ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *ከድሮው ብነሳልህ የጉጂ ኦሮሞ ከውጭ ኃይሎች ተፅዕኖ ነፃ የነበረና ራሱን በራሱ በቃሉ ተቋምና በገዳ የሚያስተዳደር ህዝብ ነበር፡፡ ከዚያ በታች የተለያዩ የቃሉም ሆነ የገዳ መዋቅሮች አሉ፡፡ እነሱ በእራሳቸው አብዛኛውን የማህበረሰቡን ችግሮች ይፈቱ ነበር፡፡ ባይገርምህ ያኔ የህዝብ ብዛቱም እንዲህ አልነበረም፡፡ የከብቶቻችን ብዛትም በቁጥር መግለጽ እስከሚያቅትህ ድረስ በሰፊ መስክ ላይ*

*ይሰማሩ ነበር። ነገር ግን ከብቶቹ እርስ በርስ ይተዋወቃሉ። ባንድ ላይ ውለው ባንድ ላይ ወደ በረታቸው ይገባሉ። እረኛ የሚያስፈልገው ከብቶቹን ከዱር አራዊት ለመከላከል ያህል ነው። መሬቱም የሰጡትን በእጥፍ ድርብ ይመልስ ነበር። እግዜሩም ቅርብ ነበር፤ የጠየከውን ወዲያው ይመልስልሃል። ነፍጠኛ መሬታችንን ከረገጠ ወዲህ ብዙ ለውጦች ተከሰቱ። ፖሊስ ብትል ከእነሱ ጋር መጣ። ዳኛና መካሰስ አናውቅም ነበር። አዝመራው ስያምር ሲሶ አስገቡ እንባላለን። ከብቶቻችንን ካዩ ለልጄ ሰርግ፣ ለክርስትና፣ ዝክር አለብኝ እያሉ የተለያዩ ሰበቦች እየፈጠሩ ከስር ከስር ይለቅሙብን ጀመር፤ እንዴት እንደግ፤ አቀጨጩን። ከዚህ የተነሳ ይሆን አላውቅም ከጉጂውም ውስጥ ስልጣን ፍለጋ አንዱ የሌላውን «እገሌ ምን የመሰለ ሙከት አለው።» እያሉ ይጠቁሙ ጀመር። ውሸት የማያውቁት የነፍጠኛ ጫና ሲበዛበት መዋሸት ሁሉ ተጀመረ። አሁን ግን ሽማግሌው እውነትን ትቶ ላለው ሲያደላ ታያለህ። ገዳና ቃሉ ከገልማቸው ወጥተው ሆቴል የምታይበት ሁኔታዎች አሉ። ቃሉ የሚመገበው ምግብም ሆነ መጠጦች የተወሰኑ ናቸው። አሁን ግን ምርቃቱ በቢራ ሆኗል። ጋብቻው በመኪና ሆኗል። እንደድሮ ቢሆን ቃሉም ሆነ ገዳ ወገንተኝነታቸው ለህዝብ ነበር። አሁን ግን ከመንግስት ጋር በመተባበር እንቨስተር እያሉ ብዙ ሰዎችን እያፈናቀሉ የእርሻ መሬት ለአንድ ሰው በመስጠት፤ ከብቶቻችንን የምናሰማራበት እስኪጠበንና ከብቶቻችን ገደል እየገቡ እስከሚሞቱ ድረስ አንድ ሀገር መሬት ሲሰጥ አብሮ በመሄድ ይመርቃሉ። ቃሉም ሆነ ገዳ ክብር አላቸው። ከገልማቸው መውጣት የለባቸውም፤ ሲወጡም የሚወጡበት ምክንያት ውስን ነው፤ ርቀቱም ውስን ነበር። ያሁኖቹን ካየህ ከዚህ የተለዩ ናቸው። ከዚህም የተነሳ እግዚኣብሔርን ብንለምነው አልሰማ አለን (አቶ አየለ ጎዳና፣ ወናጎ ወረዳ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ በ16/6 2007 ዓ.ም.)*

ከዚህ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ወ/ሮ ሮዱ የቃሉንና የገዳን ከበራዎች በአግባቡ ይከውኑ እንደነበርና የህዝብ ወገንተኝነትታቸውም የላቀ እንደነበር በማስታወስ፤ አሁን ግን ያ ክዋኔ በተወሰነ ደረጃ እየተሸረሸረ መሆኑን በቁጭት እያስታወሱ፤ አሁኑ ያሉበትን ደረጃ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡-

*ቃሉ በኮባው ወጥቶ መስዋዕት አያቀርብም፤ ገዳዎቹም እንደዚያው ሆኑ። እግዜሩም ፊቱን አዞረብን መሰል፤ ከብቱ ደም የለውም (horiinu suga hinqabu; suga dhabe)፣ ሳሩ የበረከት ሳር አይደለም። ኮርማው እንደ ድሮው አያጠቃም። መሬቱም ማዳበሪያ የሚሉትን ነገር ለመደ መሰለኝ አንድ ዓመት ከሰጠ ሌላኛው ዓመት ላይ የለም። በረከት ጠፋ። ድሮ አባቶቻችን እንደሚነግሩንና እኛም እንደደረስንበት፡- የእኛን ከብቶች ከብዛታቸው የተነሳ በየቀኑ የሚወልዱትን ከብቶች መለየት ያቅተን ነበር። እኛ ሴቶች እንኳን የቷን አልበን፤ የቷን እንደምንተው ግራ ሲገባን ዝም ብለን ነካ ነካ እያደረግን እንተው ነበር። ያ ደግም እረኞቹም ሆኑ፤ ጥጆቹ እንደልባቸው ጠብተው እንዲፋፉ ያደርግ ነበር። ሰውም ከብቱም ወዝ ነበረው። ይህ ሁሉ በረከትና ሞገስ ከእግዚአብሔር ያገኘው፡- ከቃሉና ገዳ እውነት አጣን፤ እግዜርም ፊቱን አዞረብን። (ወ/ሮ ሮዱ ሚጁ፣ አባያ ወረዳ፣ ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ፣ በ16/6/2007 ዓ.ም )*

ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ የተመለከትን እንደሆነ ቀደም ሲል የነበረው የጉጂ ኦሮሞ አኗኗርና የቃሉና ገዳ ከህዝብ ጎን ሆነው ለህዝቡ እንዴት እንደሚያገለግሉን በወቅቱ ጥሩ ኑሮ እየኖሩ እንደነበር የሚያሳይ ነው። ነገር ግን የገዥው መደብ ስልጣኑን ወደ አካባቢው ተደረሻ ባደረገበት ጊዜ የተፈጠረውን ጭቆናና የመብት መጋፋት፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የቃሉና ገዳ ተግባራት መሸርሸሩንና የማስፈጸም አቅም እየላላ መምጣቱን ያመላክታሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ጉዳይ ቀደም ሲል በአካባቢው ሰፍሮ የነበረው የህዝብ ብዛት አነስተኛ መሆኑና በግለሰቦች ተይዞ የነበሩ መሬቶች በጣም ሰፋፊ የነበሩና የከብቱም ቁጥር በነጠላ ሳይሆን፤ በበረት የሚቆጠርበት ወቅት ነበር። ነገር ግን የተወሰኑ መረጃ አቀባዮች ደግሞ ከጊዜ በኋላ በስም የማያውቋቸው የከብት በሽታ እንደ አባሳንጋና የደስታ በሽታዎች እንደተከሰቱና ከዚህ ተዳምረው በተለያዩ ወቅቶች በተከሰቱ የአየር መዛባት ምክንያት ከብቶቻቸው በድርቅ እንደተጎዱባቸው ያስረዳሉ።

የለውጥና ቀጣይነቱን ሂደት በይበልጥ በሚያብራራ መልክ በድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ አካሄድ ከምኒልክ ወረራ አንስቶ እስከ ኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት የነበሩትን ውጣ ውረዶችና በጉጂ ኦሮሞ የራስ መተማመን ላይ የነበራቸውን ተፅዕኖዎች Taddese, (2004) በዝርዝር ገልጿል።

የምኒልክ ጦር በ1890ዎቹ አካባቢ የጉጂ ኦሮሞን ለመውረር ችሏል። የእነሱ ወታደራዊ አገዛዝ እና በኢትዮጵያ ግዛት ስር እንዲተዳደሩ መደረጋቸው በጉጂ ኦሮሞ አኗኗር ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል። ጉጂ ኦሮሞ ከውጭ ኃይሎች ተፅዕኖ ነፃ የነበረውና ራሱን በራሱ የሚያስተዳደር ህዝብነቱ እያከተመለት መጣ፤ ሀገረሰባዊ የመሬት አያያዝ ስርዓቱ ተለወጠ፤ የከተሜነት ፍላጎት እየተለመደ መምጣት፤ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የባህል ለውጥም ተፈጠረ። እነዚህ ለውጦች በጉጂ ኦሮሞ ማህበረ-ባህላዊ ሕይወትና በራስ መተማመናቸው (self-esteem) ላይ ለነበረው ተፅዕኖ ዋነኛ ምክንቶች ነበሩ። ከወረራው በፊት የጉጂ ኦሮሞ ነፃ ህዝብ የሆኑና የራሳቸውን ማህበረ-ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ያለ ውጫዊ ኃይል ጣልቃ ገብነት በራሳቸው ይመሩ ነበር። የወራሪው ተከታዮች የሀገሬውን ከብቶች ማሰማሪያ፤ በጣም ሰፊ መስኮችን እንደግል መሬታቸው አድርገው ወስደው ነበር። ቀስ በቀስ በጣም ሰፋፊ መሬቶች በመንግስት እጅ፣ በአብያተ-ክርስቲያን፣ በአስተዳደሮች፣ ወታደሮች እና ከሰሜኑ ክፍል ለመጡ ሌሎች ሰፋሪዎች በመስጠትና የነፍጠኛ ገባር ስርዓት ተቋቋመ። በዚህ ስርዓት ስር ነፍጠኛው በብዙ ገባሮች ይታገዙ ነበር። ይኸውም፡- ገባሮቹ ከሚያመርቱት እህል፣ ከሚያረቡት ከብት በመስጠት፣ እንዲሁም በጉልበታቸውም በማረስና የቤት ውስጥ ማንኛውንም ስራዎች ለነፍጠኞቹ ያሰሯቸው ነበር።

ነፍጠኛው በነባሩ የጉጂ ኦሮሞ የቅኝ አገዛዝ ያህል ግንኙነት መሰረተ፣ መሬታቸውን በመውሰድና በእነሱ ላይ ህግ አወጡባቸው። በተጨማሪ ከእያንዳንዱ አካባቢ ታክስ ይሰበሰባል፤ የተወሰነው ወደ ምኒልክ ማዕከላዊ ተቋም ይላክ ነበር። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለሀገሬው ተወላጆች በነፍጠኛው የበላይነት፤ ለበታቾቹ በደረጃ ስልጣን በመስጠት የጉጂ ባላባት፣ ባላንባራስ፣ ቆሮና ጭቃ ሹም በማለት ከእነሱ ጋር በመተባበር ታክስ (ግብር) መሰብሰብ፣ ሰላምን ማስከበርና በአስተዳደር የተወሰነላቸውን አካባቢ የማስተዳደር ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር።

ሌላው በምኒልክ የመስፋፋት ፖሊሲ መሰረት፤ በወረራቸው አካባቢዎች አቅራቢያ ላይ የራሱ ፖሊሶች የሚኖሩበትን ከተማ ያቋቁም ነበር። ይህን የሚያደርገው የወደፊት መስፋፋትን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፤ ከዚያም ክልሉን ለመቆጣጠር በማሰብ ነበር። ይኸውም ግብር ሰብሳቢውንና ሹማምንቱ ላይ ችግር እንዳይደርስ ለመከላከል ጭምር ነበር።

ከምኒልክ አገዛዝ በኋላ ወደ ስልጣን የመጣው የንጉሰ ነገስት ኃይለስላሴ መንግስት (ከ1930-1936 እና 1941-1974) ወቅት ነበር። ንጉሱም በጉጂ ኦሮሞ ላይ በምኒልክ ወቅት የነበረውን

አካሄድ ያስቀጠሉበት ሁኔታ ነበር። የጉጂ መሬት ከውጭ ሆነው በሹማምንቶቻቸው በኩል በመቆጣጠር ሲሶና እርቦ እንዲሁም ግብር እያሉ ያሰበስቡ እንደነበር ከታሪክ መረዳት ይቻላል። ሌላው የነበረው የታሪክ አጋጣሚ ከ1937-1940 ኢጣሊያ በሀገራችን በቆዬችበት ወቅት ጉጂን ጨምሮ በደቡባዊ ክፍል ትልቅ መነቃቃት ተፈጥሮ ነበር። ይኸውም «የጠላቴ ጠላት፣...» እንዲሉ በጉጂ ኦሮሞ ጫንቃ ላይ ተጭኖ የቆየውን የባርነት ቀንበር አሽቀንጥሮ የጣሉበትና የነፍጠኛውን ገባር ስርዓት ያስቀረበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛውን በደቡብ የሚገኙ ብሔረሰቦች፣ የጉጂ ኦሮሞን ጨምሮ ከምኒልክ ወረራ በኋላ የነፍጠኛው ስርዓት ላደረሱት አስከፊ አስተዳደር ምላሽ የተሰጠበት ሁኔታ ነበር። ለዚህ እንደጥሩ ምሳሌ የሚነሳ የጉጂ ዘፈን አለ። ይኸውም፡-

| | |
|---|---|
| Hidhee nu hiika Axaalan | አስሮ ይፈታናል አጣለ (የጉጂ ባላባት)፣ |
| Hidhee nu dhaana habashaan | አስሮ ይመታናል ሐበሻ (አማራ)፣ |
| Haluun sun baate barana | ያን እልህ ተወጣን ዘንድሮ። |

ማለትም፡- በወቅቱ እንደፈለገ አስሮ ይፈታ የነበረው ባላባት፤ እንደፈለግ አሰሮ ይገርፍ የነበረው ነፍጠኛ ጊዜው ተለውጦ ያን እልህ መወጣታቸውን የሚያመለክት ዘፈን ነው።
በኢጣሊያ አገዛዝ ዞግ የተገኘው ለውጥ ለረጅም ጊዜ መዝለቅ አልቻለም። በመጨረሻም የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ መጨረሻ ጭቆናውና ግፉ እየበዛ በመሄዱ ኦሮሞዎቹም የእነሱን አገዛዝ እየጠሉ እንደሄዱ ተገልጿል። ንጉስ ኃይለ ስላሴ በብሪታኒያ ጦር በመታገዝ ተመልሶ መጣ። የተወሰኑ የጉጂ ኦሮሞ ተዋጊዎች ከኢጣሊያ ጎን በመሰለፍ የነፍጠኛው ኃይል ወደ ቀድሞው ቦታ እንዳይመለስ ትግል አድርገው ነበር። ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ተመልሶ በቀድሞው አገዛዝ ስር ለመውደቅ ችለዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ያላቸውን ሃይል በመጠቀም የተያዙ ሰዎችን ሆን ተብሎና በዘዴ ማንነታቸውን ለመቀየር የማዋሃድ (assimilation) ፖሊሲ አካሂደዋል። የዚህ ፖሊሲ ዋናው ኢላማ የነበረው የብሔር ድንበር ምልክቶችን፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የአለባበስ ስታየልና ማህበረ-ፖለቲካዊ ተቋማትን ማጥፋት ነበር (Taddese, 2004)።

በወቅቱ ለጉጂ ኦሮሞ የነበራቸው አመለካከት አነስተኛ ነበር። ይኸውም፡- ጉጂን እንደኋለቀር፣ እርባና ቢስ ባህልና ወግ አራማጅ የመመልከት ችግር እንደነበረባቸው Clay and Holcomb,

(1986:15) ይገልጻሉ። ከዘህ የሚንረዳው የሌላው ባህልና ሃይማኖት በማጥላላት የገዥውን አማራና ባህሉን የበላይነት ማረጋገጥ እንደነበር ነው።

በመጨረሻ በኃይል የማዋሃድ ፖሊሲው እስከ መጨረሻው አልተሳካላቸውም። ምክንያቱም በተለያዩ የኦሮሞ አካባቢዎችን ጨምሮ በወራሪው ኃይል ስር በነበሩት ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞና ትግል በጭቆና ስር ለነበሩት ህዝብ ክብርና በራስ መተማመን ተፈጥሯል። ለዚህም የባሌ ገበሬዎች አመጽ እንደምሳሌ ተጠቃሽ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በእነ ዋለልኝ መኮንን በ1969 ዓ.ም. መሪነት የተቀሰቀሰው የኢትዮጵያ ተማሪዎች አመጽ እና መሰል አመጾች ጋር ተዳምሮ የኃይለ ስላሴን አገዛዝ በኃይል በመገርሰስ ወታደራዊ የደርግ አገዛዝ በ1974 ስልጣኑን ጨበጠ። በ1975 የመሬት ፖሊሲውን በመቀየር መሬት ላራሹ መታወጁ በተለይም በጭቆና ቀንበር ስር ወድቀው ለነበሩት የጉጂ ኦሮሞ ታላቅ ድል ነበር። ሌላው ለእያንዳንዱ ብሔር እና ብሔረሰብ የራሱን ቋንቋና ባህል ማሳደግ እንደሚችል አስታውቆ ነበር። ይህ ደግሞ ካለፈው አገዛዝ በኃይል ከማዋሃድ ፖሊሲ የተለየ ነበር። ይህ አስተሳሰብ በወቅቱ የየማህበረሰቡን ማንነትና ማህበረ-ባህላዊ ልነቶችን በመደበኛነት የተቀበለና የሚደግፍ ነበር። ማዕከላዊ መንግስትን አንድ ዓይነት ህዝብ እንዲኖረው የታቀደ አልነበረም። ነገር ግን የደርግ አገዛዝ ኃይሉን ቀስ በቀስ አጠናክሮ «የብሔራዊ ጥያቄ» ዐዋጆችን በመሻር እና የተጠየቁትን ማንኛውንም የብሔራዊ መብቶችን በመመደብ እንደ "ጠባብ ብሔራዊ ስሜት" "narrow nationalism" ማየት ጀመረ። ይህ የደርግን ብሔርን የማስማማት ፖሊሲ ወደ ብሔርን የማዋሃድ ፖሊሲ ቀየረው (Taddese, 2004:21)።

ከዚህ በመቀጠል በ1983 ኢ.ህ.አ.ድ.ግ የደርግን አገዛዝ በመገርሰስ ኢትዩጵያን እንደተቆጣጠረ ወዲያኑ የኢትዩጵያ ሽግግር መንግስት አቋቋመ። በ1994 የሀገሪቷ መተዳደሪያ የሆነው ሕገ-መንግስት ተዘጋጀ። በሕገ-መንግስቱም የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች «የራስን እድል በራስ የመወሰን፣ እስከ መገንጠል» በማካተት ጸድቋል። ሕገ-መንግስቱ አጽንኦት የሰጠው «የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን» ማንነት ያከበረና የራሳቸውን ጉዳይ ለራሳቸው እንዲፈቱ መብት የሰጠ ነው።

ለአብነት ያህል፡- በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 39 ንዑስ ቁጥር 2 "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ህዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባሕሉን የመግለጽ፣

የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው" (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1987፡26) የሚለው በዋናነት ተጠቃሽ ነው።

በሀገራችን ውስጥ ቀደም ብለን ካየናቸው መንግስታት የኢ.ፌ. ዴ. ሪ. መንግስት በአንጻራዊነት ይህንን እና ሌሎችንም በበጎነታቸው የሚታዩ ለውጦች የታየበት ነው። ነገር ግን ይህን ነፃነት ወደታች ወረድ ተብሎ በሚታይበት ወቅት፤ መንግስት ለራሱ የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ ከሚለው በቀር ተፈጻሚነቱ ላይ እምብዛም አይደለም። ለዚህ እንደማሳያ የሃይማኖት ተቋማት መሪዎችን በተለያዩ መደለያዎች በመያዝ የራሳቸውን ዓላማ ሲያራምድባቸው ይስተዋላል። የመንግስት ሚዲያዎችም የተለያዩ ሃይማኖቶች ዐብይ በዓላት በሚከበርበት ወቅት የሃይማኖት አባቶች ስለበዓሉ አመጣጥና ምንነት በመንፈሳዊ ቋንቋ ከመግለጽ ይልቅ፤ ይህን እናወግዛለን!፣ እነዚህን ከውስጣችን በማጋለጥ ለህግ እናቀርባቸዋለን! የሚሉትንና የመሳሰሉት ሲያስተጋቡ ማድመጥ የተለመደ ሆኗል። ከዚህም የተነሳ ምዕመኑ በሃይማኖት መሪዎቻቸው ያላቸው እምነትና ለእነሱ ያላቸው ከበሬታ እየቀነሰ መሄዱን ከመረጃ አቀባዮቼ ያገኘሁት አስተያየት ይህን ያረጋግጣል።

በሌላ በኩል አንዳንድ የመንግስት መዋቅር በቃሉና ገዳ የግጭት አፈታት ከበራዎች ላይ ጣልቃ ሲገቡም ይታያሉ። ለአብነት ያህል፡- የአስተዳደር አካላት፣ ፖሊስ እና ፍ/ቤት ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ አካላት በል ሲላቸው የሀገረሰባዊ ግጭት አፈታት ሂደቱን የማድነቅና ውሳኔያቸውንም እንደሚያከብሩ ከተገኙት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል።
እንደ ጉጂ ኦሮሞ ቃሉና ገዳ ተቋማት ያየን እንደሆነ ቀደም ባሉት መንግስታት ለመሪዎቹ የባላባትነትና የባላንበራስነት ማዕረግ በመስጠት ተከታዩቻቸውን ያለምንም ደም መፋሰስ እንዲያስገብሩ ለማድረግ በመሳሪያነት እንደተጠቀሙባቸው አይተናል።

በተመሳሳይ መልኩ በ1986 ዓ.ም የጉጂ ኦሮሞ በተለይም በደ/ብ/ብ/ክ/መ፣ የጌዴኦ ዞን አጎራባች የነበሩት የኦሮሞ ተወላጆች፤ በጌዴኦ ዞን እንዲተዳደር ሲካለልና በጌዴኢኛ ቋንቋ እንዲማሩ ሲደረግ፣ በጌዴኦ አመራሮች ሲመሩ ለምን እንዲህ ይሆናል? በሚል አብዛኛው የጉጂ ኦሮሞ ኮሚቴ አዋቅረው ለመንግስትን የመብት ጥያቄ ማቅረብ ጀመሩ። ይህን በተመለከተ Asebe, (2007) እንደሚከተለው ይገልጻል።

> Those who were included into Gedeo Zone were bureaucratically forced to conform to the realities in the zone. For instance, if at all

they had to go to school Guji children had to learn in Gedeo language (Gede'uffa) because that was the only language taught in the Gedeo Zone. For Guji civil servants, lack of language skill in Gede'uffa was presented as an excuse for inequitable job opportunity between the Gedeo and Guji.»

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በጉጂና ጌዴኦ መካከል አብረው በሚኖሩበት ወቅት በኦሮሞዎቹ ላይ የተፈጠረው በማያውቁት ቋንቋ እንዲማሩ መደረግና የተማሩትም የመንግስት ስራ ለማግኘትም የአከባቢውን ቋንቋ ባለማወቃቸው ምክንየት በጌደኦና በጉጂ መካከል ፍትኣዊ የስራ ዕድል ማግኘት አለመቻሉን ነው።

እንደ መረጃ አቀባዬ ገለጻ ከላይ ለተነሱት ጥያቄያቸው አግባብነት ያለውን መልስ ከመስጠት መንግስት የወሰደው እርምጃ በጋራ ኑሩ፤ ማህበረሰቡንም በጋራ አስተዳድሩ በማለት ከዞን እስከ ቀበሌ በጥምር አስተዳደር አዋቀረ። የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ከጌዴኦ ብሔር ሲሆን በምክትል አስተዳዳሪነት ማዕረግ የጉጂ ኦሮሞን እንዲወክሉ የተደረጉት አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ ነበሩ። ህዝቡም ማጉረምረሙን ቀጠለ። ‹‹ቃሉ ከገልማ መውጣት የለበትም፤ ቃሉ በገልማህ ተመለስ።›› ቢባሉም፤ እምቢ በማለት የመንግስት ተቀጣሪ ሆነው ማገልገል ጀመሩ። በሚገርም ሁኔታ ከሦስቱም የጉጂ ኮንፈደሬሲዎች ሽማግሌዎች ተመርጠው ስጦታና ገንዘብ ይዘውላቸው በመምጣት ወደገልማው እንዲመለሱ ቢጠየቁም እንቢታቸውን ገለጹ፤ ስጦታውንም አልተቀበሉም ነበር። በመጨረሻም የጉጂ ኦሮሞ በተለይም በአላብዱና ኡራጋ በኩል አዋሳኝ የነበሩት መንግስት ሰጥቶ የነበረውንና ነገር ግን እነሱ ግን የተነፈጉትን መብት ለማስከበር ጥቂያቸውን ቀጠሉበት። አባቃሉ ሳቆ ባሉበት የተለያዩ ስብሰባዎችም ተደርጎ ነበር። ቋንቋውን፣ ባህሉንና ማንነቱን የተነፈገ ህዝብ መሪው ከፊት ለፊቱ ቆሞ እረፍ ቢለውም በውስጡ የማያሳርፍ ጥያቄ ይዟል። ስለዚህ አባቃሉን «ከዓይን ትረፍ!» «Ilarraa hafi!; mucuca!» በለን በማለት አስፈቀዱ፤ አባቃሉም «mucuca!» «ከዓይን ያትርፋችሁ» በማለት ሲፈቅዱላቸው ጥቄዎችን ያቀርቡላቸው ነበር። ይኸውም፡- በሚያሳምን ንግግር ‹ወደ ገልማ መመለስ አለቦት። ስለዘመናዊ ፖለቲካ ብዙ የማያውቁት ነገሮች አሉ። እርሶን ከፊት ለፊታችን አቁመው እኛ ብዙ ነገሮችን እያጣን ነው።› በማለት ተቃውሟቸውን ይገልጹ ነበር። እሳቸው ግን ሌሎች ይሉት የነበረውን አባባል መልሰው ይሉ ነበር። ይኸውም፡- «ይህ የኦነግ አመለካከት ነው።

ስለዚህ መንግስት ባዋቀረው መልኩ መብታችንን እናስጠብቃለን።» እንዳሉ ከመረጃ አቀባዬ ለመረዳት ችያለሁ።

ከዚያም ይህ አካሄድ የትም ሊያደርስ እንደማይችል በመግለጽ፣ በየቦታው የተለያዩ ተቃውሞዎች ይቀሰቀሱ ጀመር። የተቃውሞ ሰልፎችም እየተበራከቱ መጡ። ‹‹ሕገ-መንግስታዊ መብታችን ይከበር!፣ በቋንቋችን እንድንማር ይደረግ!›› የሚሉና የመሳሰሉትን መፈክሮች ይስተጋቡ ነበር። ጥያቄዎቹ በሰላማዊና ሕገ-መንግስቱ በሚያዘው መሰረት እየተካሄደ እያለ፣ ከሰላማዊ ሰልፉ ሲመለሱ በአንድ ግለሰብ አማካይነት በተፈጠረ ስህተት የተነሳ ወደ ሁለቱ ህዝብ ግጭት አመራ። ጦርነትም ተቀሰቀሰ። በጦርነቱ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች ሞቱ፣ ብዙ ንብረቶች ወደሙ። እንዲሁም ግጭቱን ለማስቆም ከመጡት የመከላከያ ሰራዊት አባላትም ጭምር የሞቱ ነበሩ።

በመቀጠል ይህ ጥያቄ የህዝብ ሳይሆን የግለሰቦች፣ ያውም የስልጣን ጥመኞች ነው በማለት በጦርነቱ ላይ ጉልህ ሚና ነበራቸው የተባሉ ተጠርጣሪዎች እየታደኑ ወደ ወህኒ ቤት ተወረወሩ። ከእነዚህም ውስጥ አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ አንዱ ነበሩ። የእሳቸውም ክስ ጦሪነቱን ለማብረድ ከነበራቸው ሚና ይልቅ አባብሰዋል። ለዚህም እንደምክንያት የቀረበው፦ ‹‹የጉጂ ኦሮሞ ከእርሶ ቃል አይወጣም። ስለዚህ ከልቦ አቁሙ ብትሉ፣ ይችሉ ነበር›› የሚል ነው። ያም ሆኖ አባቃሉ ሳቆ ሳይፈረድባቸውም በዚያው ወህኒ ቤት እንዳሉ ሕይወታቸው አለፈ።
ከነዚህ ተግዳሮቶች እንዳየነው የጉጂ ኦሮሞዎች በተለይም በቦረና ዞን፣ በገላናና አባያ ወረዳዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩት በቋንቋቸው የመማርና የመዳኘት መብታቸውን እንዳሳጣቸው መረዳት ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የማንነታቸው መገለጫ የሆነውን ቋንቋ ካልተጠቀሙበት፣ በባህላቸውንና ሀገረሰባዊ ሃይማኖታቸውን እንደልብ መከወኑ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው። ቀደም ሲል በገልማ ተገናኝተው ይወያዩ የነበረው ባህል እየተቀዛቀዘ መጣ። ምክንያቱም አባቃሉ በጠዋት ተነስተው ወደ አስተዳደር ጽ/ቤታቸው ይሄዳሉ። የተወሰኑ የሀገር ሽማግሌዎችም ወደገልማው በመሄድ ከቃሉ ጋር ውይይት ለማድረግ ጥረት ባደረጉ ወቅት ልክ እንደ ‹‹ኦነግ›› በመቁጠር ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂዎች እንደደረሰባቸውና ይህ ደግሞ በወቅቱ በውስጣቸው ፍራቻ እንዳሳደረባቸው ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል የአባገዳ አጋ ጣንጣኖ የስልጣን ዘመን ታሪክ ያየን እንደሆነ ስለገዳ ስርዓት ማንሰራራት ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። በሀገረሰባዊ ዕውቀት የጠለቀ ግንዛቤ ያላቸውና

አንደበተ-ርቱኡ ገዳም ነበሩ። የገዳ ስርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲታወቅ በተለያዩ ጊዜያት ለሚዲያ በሰጡትና በሚሰጡት ገለጻዎች የበኩላቸውን የተወጡና እየተወጡም ያሉ ናቸው። ስለገዳና ቃሉ ከበራዎችና ስርዓቶች አስፈላጊ መረጃዎችን ለተመራማሪዎች በመስጠት ያገለገሉና እያገለገሉ ያሉ ናቸው። ከዚህም የተነሳ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክተሬት ተሰጥቷቸዋል።

ይሁን እንጂ እንደ መረጃ አቀባዮቼ ገለጻ በተወሰነ ደረጃ ህዝቡን በማማከል፤ ለማህበረሰቡ መንፈሳዊም ሆነ አስተዳደራዊ አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ፤ የመንግስት ቀኝ እጅ በመሆን በተለያዩ ስብሰባዎችና የሚመረቁ መሰረተ ልማቶች ላይ በመገኘት ምርቃት ሲያካሂዱና ስለመንግስት መልካም መልካሙን በመስበክና እንከን የለሽነቱን በማወደስ ያሳልፉ ነበር። ለዚህም ከመንግስትን በተለያዩ መልክ ጥቅማጥቅሞች ይደረግላቸው እንደነበር ማለትም፡- በአበል መልክ የገንዘብ ስጦታ፣ የማጓጓዣ መኪና በማዘዝና ጥሩ ሆቴሎች ምግብና መኝታ እየተዘጋጀላቸው እንደነበር ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። ከዚህም የተነሳ ማህበረሰቡ የነበረበትን ማህበረ-ፖለቲካም ሆነ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ለመፍታት ወደ ገልማቸው ሲሄዱ እንደማያገኟቸውና በመንግስታዊ አካላት በሚቀርብላቸው የይገኙልን ጥሪዎች ተጠምደው እንደሚያሳልፉ ያነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮች ያስረዳሉ። ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል። ከነዚህም ውስጥ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እስኪመስሉ ብዙ ስራዎችን ማስፈጸማቸውንና መንግስትም በቦታው እንዲቀጥሉ እጁን በተዘዋዋሪ መንገድ ማስገባቱን Israel, (2011:315) እንደሚከተለው ይገልጻል።

> *During the 2005 national election in Ethiopia, the then Abba gada elect was suspected of supporting dissident political groups that the regional government did not like him to ascend to power on the next traditional power transfer...Abba Gada Aga Tentano, delayed the traditional power transfer for almost a year and finally rejected the new Abba Gada and transferred power to somebody else in whom the people have no trust and whom the traditional screening process did not support.*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አንደኛው አንድ አባገዳ ከመንግስት በተቃራኒ ያለን የፖለቲካ ድርጅት ይደግፋል የሚል ጥርጣሬ ካሳደረበት ተለያየ መንገድ ጫና ለመፍጠር እንደሚሞክር ያሳየናል። የገዳ ስልጣን ቆይታ ጊዜ ስምንት ዓመት ሆኖ ሳለ በማን አለብኝነት ጊዜውን ማራዘሙን፣

ሁለተኛው ደግሞ በገዳ ስርዓት የዕድሜ እርከን ውስጥ ከኩሳ ደረጃ ጀምሮ የተመረጠና በተለያዩ የማህበረሰብ ዕውቀት እየተገነባና እየተደራጀ የመጣውንና ማህበረሰቡም ይሆናል ብሎ የሚጠብቀውን መሪ ወደ ጎን በመተው፤ በባህላዊውና ሃይማኖታዊ መንገድ ላልተመረጠውና የህዝብ እምነት ላልተጣለበት ሰው ስልጣን መሰጠቱ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ሊኖር እንደሚችል ጥርጣሬ መፍጠሩ አይቀሬ ነው።

ከላይ በዝርዝር እንዳየነው ኢትዮጵያን ከምኒልክ ጀምሮ በተለያዩ ወቅቶች ካስተዳደሯቸው መንግስታት እንደ ጉጂ ኦሮሞ የቃሉና የገዳ ተቋማት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማዳከም የማህበረሰቡ ማንነትና ነፃነታቸውን ሲፈታተኑ እንደነበር መረዳት ይቻላል። ይኸውም፡- የሃይማኖቱ መሪዎችንና የሀገረሰባዊ አስተዳደር መሪዎችን ከተቻለ በኃይል በማዳከም፤ አሊያም በአፄዎቹ ዘመን የባላባትነትና ባላንበራስነት ማዕረግ በመስጠትና ክርስትና በማንሳት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ እንዲሆኑ በማድረግ፤ እንዲሁም በደርግ ደግሞ እንደኊላ ቀር ባህል በመቁጠር በኃይል ሲያዳክሙ እንደነበር አይተናል። በመጨረሻም በኢ.ፌ.ድ.ሪ. መንግስት ደግሞ በገዳዎች ስልጣነ-ሢመት ሂደት ውስጥ ጣልቃ እስከመግባትና ከተመረጡም በኊላ በተለያዩ መደለያዎች በመያዝ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እንዳደረጓቸውና በተቃራኒው ደግሞ ገዳዎቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ተዓማኒነትና ከበሬታን እንዲያጡ በማድረግ ያሳደሩት ተፅዕኖ ይህ ነው የሚባል አይደለም።

በሌላ በኩል ደግሞ በጎሳዎች መካከል፣ በአጎራባች ህዝቦች መካከል ለሚፈጠሩ ችግሮች መንግስት ብቻውን ለመፍታት ስለሚያዳግተው የእነዚህ ተቋማት መኖሪን ይፈልጋል። ከዚህም በመነሳት የተለያዩ ከበራዎችን እንዲያስፈጽሙ ድጋፍ የሚያደርግበት ወቅቶች አሉ። በሌላ በኩል ተደጋጋሚ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ያስደርጋል።

እነዚህ በጉጂ ኦሮሞ ላይ በተለያዩ ወቅቶች፣ በተለያዩ አካላት የተፈጸሙት ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ጫናዎች በነባሩ ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ የማንነት ችግር ውስጥ ጥሏቸው ነበር። ስለዚህ እንደ ክልላዊ (hemispheric) ንድፈ-ሀሳብ በተለያዩ ምክንያቶች አንድ ማህበረሰብ ከሚኖርበት አካባቢ ሲንቀሳቀስ ወይም ሌላው ሲመጣበት፣ ወይም በሚከሰቱ ሌሎች መስተጋብሮች የተነሳ የማህበረሰቡ ዕውቀት የመዋዋስ፣ የመዋሃድ፣ የመዋዋጥ፣ የመጠናከር፣ እንዲሁም የመዘንጋት ክስተቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ በምዕራፍ ሁለት ስር አይተናል።

ባጠቃላይ ከታሪክ እንደምንረዳው ከ16ኛው መቶ ክ/ዘ መጨረሻ እስከ 19ኛ መቶ ክ/ዘ ድረስ የኦሮሞ ህዝብ ቀደም ሲል እንደነበረው በማዕከላዊነት ደረጃ ሳይሆን በየጎሳው አባ ገዳ አስተዳዳሪነትና በአባ ሙዳ ሃይማኖት መሪነት ያለምንም የውጪ ኃይል ጣልቃ ገብነት እራሱን ሲያስተዳድር ቆይቷል (ታቦር፣ 2006፡106)። ነገር ግን በአንዳንድ ውጫዊ ተግዳሮቶች የተነሳ ይሄን የማስፈጸም አቅም እያጡ እንደመጡ መረጃ አቀባዮቹና የተለያዩ ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ስለዚህ የቃሉን ሃይማኖታዊ ክበራዎች በእነዚህ የታሪክና አካባቢያዊ መስተጋብሮች ውስጥ በውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች የተነሳ የተለዋወጡ የዕውቀት መልኮችን፣ ተቋቁመው የተሻገሩና ያንሰራሩበት ሁኔታዎችን መመርመር ይጠበቃል። በዚሁ መሰረት ከተለየዩ ንድፈ ሀሳቦች አኳያ እንደሚከተለው ትንተናና ገለጻ ተደርጓል።

## 7.1. የገዳ ስልጣን ማጽደቅ ክበራ ለውጥና ቀጣይነት

የቃሉ ተቋም ከሚያከናውናቸው ክበራዎች ውስጥ አንዱና ዋንኛው የገዳ ስልጣን ማጽደቅ ክበራ እንደሆነ በ 6.1. ስር በስፋት ተመልክተናል። ይህ ተቋም ከነበረበት ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁመው በአሁን ወቅት በስራ ላይ ካሉት ውስጥ የጉጂ ኦሮሞ አንዱ ነው። ስለዚህ የገዳ ስልጣን-ሢመት ማጽደቅ ክበራ በተመለከተ ከማስማማት፣ መላመድ፣ ማጣመር፣ መዘንጋት፣ መረሣት፣ መቀየር፣ መቋቋምና ማንሰራራት አኳያ ምን ይመስል እንደነበር እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

እንደ ጉጂ ኦሮሞ ተከናወኑ ከተባሉት የገዳ ስልጣን ሽግግሮች ዙሮች ውስጥ ለ 69 ጊዜ ብቻ ነው የቀድሞውን ማህበረ-ባህላዊ ደንቡን ጠብቀው የተከናወኑት። ይህ ማለት ገዳዎቹ የስልጣን ሽግግር ካደረጉ በኋላ ለቃሉ ስጦታዎችን በመያዝ ከቃሉ ገልማው ቀርበው ስልጣናቸውን ያጸድቃሉ። ነገር ግን ይህ ሂደት የተቋረጠው ከ70ኛ አባገዳ አዶላ አጋ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ተገልጿል።

ይህ ሲባል እነዚህን ሁሉ ጊዜያት ያለምንም ተግዳሮቶች እዚህ ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይኸውም ከምኒልክ ጀምሮ እስካሁን ባሉት መንግስታት እየተደረጉ የነበሩትን ተፅዕኖዎች በጥቅል ለማየት ችለናል። ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዘርዘር አድርገን ለማየት ሞክረናል።

በምኒልክ አገዛዝ በወረራቸው አካባቢዎች አቅራቢያ ላይ ፖሊስ ጣቢያዎች መቋቋማቸውን ተከትሎ የፓሊስ ጣቢያዎች እየተለመዱ ከገዳ ማዕከል ጋር በጥምረት የመስራት ሁኔታዎች

ብቅ ማለት ጀምረዋል። ይኸውም መጤው ሰፋሪ በነባሩ ነዋሪ የሚከሰሰውና የሚዳኘው በነዚህ ተቋማት እየሆነ መጣ። በመቀጠልም በሂደት በአስገባሪዎቹ የተቋቋሙት ከተሞች የህዝብ ቁጥር ከሰሜኑና ከአጎራባች አካባቢዎች ካሉት በመፍለስ እየጨመረ እንደሄድ አይተናል። በአካባቢዉ ት/ቤቶች፣ የጤና ተቋማትና መንገዶች አልነበሩም። ከዚህ ጋር በተያያዘ የክርስትናሃይማኖትና የአማርኛ ቋንቋን የማስራጫት ፖሊሲ ነበረው። ለዚህ ዓላማ ማሳኪያ ይሆን ዘንድ በጦር ጀነራሎቹም ጭምር ሳይቀር በወረሯቸው አካባቢ አብያተ-ክርስቲያናትን ያስገነቡ እንደነበር ከታሪክ ለመረዳት ተችሏል። ከዚያም ሀገረሰባዊ እምነት ተከታዩን ማህበረሰብ በማስጠመቅና የአማራውን ባህል እንዲከተሉም ተደርጓል (Taddese, 2004)። ማህበረሰቡም በወራሪው ክንድ ስር ከወደቁበት ጊዜያት ጀምረው አንድም በጫና፤ አሊያም በስብከት አዲስ እምነትና ባህል ከተላመዱ በኋላ ከሀገረሰባዊ እምነትና ባህል ጋር በማጣመር ይከውኑ ነበር። የንጉሳዊ አገዛዙ የማዋሀድ ፖሊስ (assimilative policy) በጉጂ ኦሮሞ ሀገረሰባዊና ባህላዊ ልምዶችን እንደባዕድ አምልኮና ህገ-ወጥ ድርጊት አስመስሎ ለማጥላላትና ለማጥፋት እንደተነሱ Hinnant, (1977: 25,217-220) በጥናቱ ውስጥ ያስረዳል።

በቀድሞ ነገስታት ተፅዕኖ የተነሳ ሲባል፡- ለምሳሌ በአጼ ኃ/ስላሴ ዘመን ቀደሞ የነበረውን ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ስያሜ በማጥፋት አባቃሉ በሚለው ስም ምትክ የባላባትነት ማዕረግ በመስጠት ንጉስ (ሞቲ) በማለት፣ እንዲሁም አባገዳን ደግሞ ባላንበራስ በማለት ስማቸውንና ተግባራቸውን የመሸርሸር ሁኔታ ተከስቶ ነበር። ለአብነት ያህል እነ አባ ቃሉ ቶቴ ሀርባዬ፣ ናጋኦ ቶቴ፣ ሳቆ ናጋኦ እና አጋ ሳቆ ከአባቃሉ እና ከቃሉ መጠሪያ በተጨማሪ ሞቲ በሚለው መጠሪያ ይጠሩ እንደነበር ለማውቅ ተችሏል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሀሉና ዌሲቱ ገዳዎችም በባላንበራ ማዕረግ የጠሩ ነበር። ለምሳሌ፡- አባገዳ ጉሚ ባላንበራስ ጉሚ ተብለው ይጠሩ ነበር። ልጃቸውም ገዳ ደንቦባ አንዳንዴ ነሸጥ ሲያደርጋቸው ‹‹እኔ የባላንበራስ ጉሚ ልጅ ነኝ፤ ባላንበራስ ከእነ ልዕልት ተናኜ ወርቅ ጋር ቀረቤታ ነበረው።›› በማለት በጫወታቸው መካከል ጣልቃ እያስገቡ ሲያወጉኝ ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በማግባባትና በመደለል የሃይማኖት ለውጥ እንዲያደርጉ ሆነዋል። የሌላውን ሃይማኖት የመከተል ተፅዕኖ በአሁኖቹም የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ መሪዎችና የቅርብ ዘመዶቻቸው ላይ ይታያል። ለአብነት ያህል በቃለ መጠይቅና በምልከታ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተሞከረው፡- አባቃሉ አጋ ሳቆ፣ አቶ ሞኮና ናጋኦ (የቃሉ አጎት)፣ አባገዳ ደንቦባ ጉሚ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች እንደሆኑና፤ የቃሉ ገልማ ውስጥም ጎልተው የሚታዩ የመላእክት ምስሎች ለመመልከት

ተችሏል። አልፎ አልፎም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ መንፈሳዊ መዝሙሮችንም እንደሚያዳምጡ ለመረዳት ተችሏል። ይሁን እንጂ ሃይማኖታቸውን በመቀየራቸው ምክንያት የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱን ማህበረ-ባህላዊ ክዋኔና ፋይዳ ላይ ያደረሰው ተፅዕኖም እንብዛም ነበር። ምክንያቱም በቃሉ ተቋምም ሆነ በገዳዎች ማዕከላት ከሞላ ጎደል የሚከናወኑት ምርቃቶች፣ የእግዚአብሔር ልመናና ምልጃ ሂደቶችም ሆኑ ለሂደቱ የሚቀርቡት ቁሳዊ ባህሎች አይጓደሉም ነበር። በተለይም በቃሉ ተቋም የመጤው ሃይማኖቶች ተፅዕኖ በሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ላይ የፈጠሩት ጫና ሙሉ በሙሉ የቃሉንና የገዳ ተቋማትን አለመቀየሩንና አሁንም በተቻለ መጠን እንዲንቀሳቀሱ ያደረገ ለመሆኑ አንዳንድ መረጃዎች በግልጽ ያሳያሉ። ይሄውም አባቃሉ አጋ ሳቆ፣ አቶ ሞኮና ናጋአ፣ አባገዳ ደንበባ ጉሚ በተለያዩ ገጠመኞች ላይ በተገኛኘንበት ወቅት ውይይታችንም ሆነ፣ በሌሎች ጉባኤዎች ላይ ምርቃት ሲያካሂዱ በዋቄፋና ሃይማኖታዊ ስርዓት እንደሆነ በምልከታ ከተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህ የሚያሳየው የመጤውን ሃይማኖትና ነባሩን ባህል በማጣመርና በማጣጣም ያስተናግዱ እንደነበር ነው። ከዚህ በተጨማሪ በጉጂ ኦሮሞ አካባቢ በክርስትናው እምነት በኩል በአብዛኛው የፕሮቴስታንት እምነት መስፋፋትና የእስላም ሃይማኖትም መጀመሩ በማህበረ-ባህላዊ (socio-cultural) እና በፖለቲካ ስርዓቱ ላይ ጣልቃ በመግባትና ከፍተኛ መሰናክል እየፈጠሩ እንደሆነ (Tadesse, 2004:3) በስፋት ያስረዳል።

ሌላው ስለ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ በህዝቡ ውስጥ የሚሰብክ እራሱን የቻለ አካል አለመኖሩ፣ መደበኛ በሆነ መልኩ መሰበክ አለመቻሉ፣ ህዝቡም በሳምንት፣ አሊያም በወር የመገናኘት አጋጣሚዎቹ የሉትም፤ ቢኖሩም ስለተከሰቱ ወቅታዊ ጉዳዩች ከመወያየት ባሻገር አዳዲስ አባላትን የመስበክና የመመለስ ስራ ላይ በትኩረት የሚሰራ አካል የለም። በተቃራኒው ግን በመጤው ሃይማኖቶች እንደ ባዕድ አምልኮ፣ በተራራና በወንዝ እንደሚመለክ መሰበኩ፤ የሰባኪዎቹ በመንፈሳዊ ትምህርት የማስተማር ስነ-ዘዴ መሰልጠንና በሚደረግላቸው የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ጭምር ስለሚደረግላቸው፤ የዋቄፋታ ሃይማኖት ተከታዮችን ከመስበክ ባለፈ በተለያዩ ጥቅማጥቅም እየደለሉ ሃይማኖታቸውን ለመቀየር አመቺ ሁኔታዎችን እንደፈጠረላቸው መረጃ አቀባዮቼ ያስረዳሉ። ይህም ሆኖ (Bartels,1983) እንዳለው በእነዚህ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞዎች መካከል ትክክለኛ የእምነት ድንበር አለ ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ከበራዎችን አውቀውም ይሁን ሳያውቅ ሲከውኑ ይስተዋላሉ። አንዳንድ በአምልኮአቸው ውስጥ የነበሩትን ከበራዎች በአዲሶቹ

ሃይማኖቶች ውስጥም መቀላቀል ይታያል፡፡ እንዲሁም ለቃሉ ከፍተኛ አክብሮት የሚቸሩና የቃሉዎችን ገልማ ለአምልኮ የሚቃኙም አሉ (ከአጥኚው የመስክ ምልከታ ከተገኘ)፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በጉጂ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በዋቄፋና ሃይማኖት ወይም በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ በአንዱ ወይም በሌላው የመሳተፍ ዕድላቸው የሰፋ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ በገዳ የስልጣን-ሢመት ማጽደቅ ከበራ ይህን ክስተት ሊያሳዩ የሚችሉ በምዕራፍ ሦስት ስር በተወሰነ ደረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቱን ከደረሰበት ጫና ማምለጥና መቋቋም ባይችልም፤ የመጤውን ሃይማኖት በመላመድና ከሀገረሰባዊው ጋር በማጣመር እየከወኑት መሆኑን ያመላክታል፡፡

ሌላው ለለውጥና ቀጣይነት እንደምክንያት እየተነሳ ያለው ችግር ድሮ ቃሉ ወገናዊነቱ ለህዝብ ነበር፡፡ አሁን ለራሱ ከተመቸው ስለህዝቡ ደንታ ያለው አይመስልም ተብለው ይታማሉ፡፡ ምክንያቱም ቃሉ የህዝቡን ጥቅምና ግዴታውን ወደጎን በመተው የመንግስትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲባል በመንግስታዊ የአስተዳደር ማዕቀፍ ውስጥ በማስገባት አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ በጌዴኦ ዞን የምክትል አስተዳዳሪነት ቦታ በመስጠት የቃሉነቱንና የአስተዳዳሪነቱን ስልጣን በማጣጣም ለማስኬድ ያደረጉት ጥረት ነበር፡፡ ነገር ግን ማህበረሰቡ ማንነታችንን እያጣን ነው፡፡ «መንግስት በአንቀጽ 39፣ ንዑስ አንቀጽ-2 ላይ የደነገገውን መብታችን ይከበር» በማለት ጉዳዩ ከጦርነት አልፎ በመንግስት ጣልቃ ገብነት በተወሰነ ደረጃ በሪፈረንደም መፍትሔ ተበጅቶለታል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ብዙ ስህተቶች ነበሩ፡፡ ይኸውም፡- የቃሉ ተቋም በሌላ ክልል ውስጥ መሆኑ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በጉጂ ኦሮሞና በጌዴኦ ብሄረሰብ መካከል በነበረው የድንበር ይገባኛል ግጭት የተነሳ የቃሉ ተቋም በሪፈረንደም ወደ ጌዴኦ ዞን መካተቱ ተገልጿል፡፡ ይህ ደግሞ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ቅሬታን ፈጥሯል፡፡ በመስክ ቆይታዬ ወቅት ባሰባሰብኩት መረጃ መሰረት የጉጂ ኦሮሞ የማንነታችን መገለጫ የሆነውን የቃሉ ተቋምና የተለያዩ ማምለኪያ ተራራዎች (Kooba) ለሪፈረንደም መቅረቡ በራሱ አግባብነት እንዳሌለውም ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ክስተት በራሱ ለቃሉ ተቋም መዳከም እንደ አንድ ዋንኛ የውጫዊ ተግዳሮት ሊቆጠር ይችላል፡፡ ይህ ክስተት ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ የማምለኪያ ቦታዎች የአከላለል ለውጥ መደረግ፤ ለምሳሌ፡- የቃሉ ተቋም፣ ገደብ የሚገኝ መንፈሳዊ ቦታና ለሌችም በሪፈረንደም ወደ ጌዴኦ ዞን መጠቃለላቸውና

የቦታዎቹ ስያሜና አገልግሎት መቀየርን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ የቂሊጦ ተራራ ቀደም ሲል የቃሉ መንፈሳዊ ቦታ የነበረው፤ በአሁኑ ወቅት ወደ መለስ ፓርክነት ተለውጧል፡፡

ሌላው ቀደም ሲል እንዳየነው የገዳዎች ቃሉ ተቋም ሄደው ቄንቢ መውሰድና ስልጣናቸውን ማጸደቅ ያቆሙት ከ70ኛ አባገዳ አዱላ አጋ (1976) ጀምሮ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በወቅቱ የነበሩት አባቃሉ ሳቆ ናጋኦ ነበሩ፡፡ በዚያን ወቅት አባቃሉ በመንግስት መዋቅር ውስጥ በማስገባት የጌዴኦ ዞን ም/አስተዳዳሪ ሆነው ሲያገለግሉ ከወደ ኡራጋ ለእሳቸው የሚሆን ስጦታ በማምጣት ወደገልማ ተመለስልን በማለት ጠይቀው እንደነበር ከላይ ተጠቅሷል፡፡ ነገር ግን እሳቸው አሻፈር ሲሉ ለገዳዎቹ የቃሉ ገልማ እንዳይሄዱ ክፍተት ፈጥሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለቃሉ ተይዞ የሚኬደውን ከብቶችና ሌሎች ስጦታዎችን ማህበረሰቡ ማዋጣት አለመፈለጋቸውና ገዳዎችም ይህንኑ የማሰባሰብ አቅም ማጣታቸው ተዳምሮ እንደ ውስጣዊ ተግዳሮቶች በመሆን ለጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ መስተጓጎል ምክንያት እንደሆኑ መረጃውን የሰጡኝ አባገዳዎቹ ይገልጻሉ፡፡ በምትኩም ያለውን የመዋቅርና የከበራ ክፍተቶች በፋጋ አማካይነት ቄንቢ በመስጠት እስከ 74ኛው ገዳ ስልጣነ-ሢመት መድረሳቸውን በ 6.1. ስር በስፋት ተነስቷል፡፡ ይህን ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ የቄንቢ አሰጣጥ ከበራ ሂደቱን፣ መቼቱንና ከዋኙ ላይም ለውጥ እንደተደረገ እናያለን፡፡ ከማህበረሰብ ዕውቀት አኳያ የተመለከትን እንደሆነ ይህ አሰራር ከተፈጠሩት ሁነቶች ጋር ሂደቱን ለማጣጣም ያዋቀሩት ማህበረሰባዊ ዕውቀት መሆኑ ያሳያል፡፡ ነገር ግን በደቡብ የኦሮሚያ አካባቢ ማለትም (በአርሲና በቦረና) በየስምንት ዓመት አንዴ በሚካሄድ ከፍተኛ ሃይማኖታዊ ከበራ ላይ ለመገኘትና ለመሳተፍ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ፡- ከሰሜን እንደ ወሎ እና ከምዕራብ እንደ ወለጋና ጂማ ኦሮሞዎች ወደዚያ ይጓዙ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ሂደት ቀስ በቀስ በተለያዩ ምክንያቶች ማለት፡ በኢትዮጵያ ንጉሳዊ መንግስታት ጫናና የክርስትና ሃይማኖት መጀመር የተነሳ እየተዳከመ መሄዱን Asmerom, (2000:102-103) ይገልጻል፡፡ ይህ ሂደት ከለውጥና ቀጣይነት አንጻር ስንመለከተው እየተዘነጋና እየተረሳ ሄዶ በከበራው ላይ መሳተፉ መቅረቱን ያሳየናል፡፡

ይሁን እንጂ እንደ ጉጂ ኦሮሞ የተመለከትን እንደሆነ በገዳ ስልጣነ-ሢመት ከበራ ክዋኔዎች ውስጥ የተረሱ የሚመስሉ አሉ፡፡ ለአብነት ያህል በስጦታ መልክ ድፍን ቡና፣ ከብቶች፣ ወተት፣ ቅቤ፣ ማር፣ ገንዘብና የመሳሰሉትን ለቃሉ ያበረክቱ ነበር፡፡ ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ እንዲህ ዓይነቱ የመተሳሰብና ለባህሉና ለሃይማኖቱ የመታዘዝ ሂደት እየተሸራረፈና እየቀዘቀዘ

መጥቷል። (ዲኮ ሚጁ ካላልቱ ቀበሌ ነዋሪ እና ሄሌሎ ሞኮና፣ ካላልቱ ቀበሌ ነዋሪ፣ በ30/3/2007 ዓ.ም.)

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ከማህበረሰቡ ለገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ ድፍን ቡና፣ ከብቶችና ወተት ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው ይታወቀል። የከበራ ጊዜ እርዝማኔ ከወራት በላይ ስለሚወስድ፣ በከበራው ላይ የሚታደሙ ሰዎች ብዛት በሺዎቹ ስለሚቆጠሩና ከብቶች በየከበራዎቹ የሚታረዱ ከብቶች፤ ያን ብዛት ያለውን ህዝብ ለማቆየት የሚወጣው ወጪ መብዛት፣ ከዚህ በተጨማሪ ቦታውን ለሚለቀው አባገዳ ለመጦሪያው የሚሰጡ ከብቶች መኖር፣ እነዚህ ከብቶች ደግሞ በጃልዳባዎች አማካይነት ለማዋጣት ፍቃደኛ ከሆኑ ቤተሰቦች ላይ ይሰበሰብ ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ጃልዳባዎች ይንን ጉዳ ለማስፈጸም ፍላጎቱ እንደሌላቸውና እናስፈጽምም ቢሉ ተቀባይነታቸው እንደቀድሞው እንዳልሆነ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ። ይህንን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ Hinnant, (1977:218-219) ይገልጻል። ስለዚህ ይህ ሂደት ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ የጃልዳባዎችን የማዘዝ አቅም ያሳጣና አካሄዱንም እንደተቀየረ ያመላክታል።

> አባቃሉ ከማንኛውም የጉልበት ሥራ ነፃ መሆን አለበት። እርሻውን የሚያርሱት የአካባቢዊ ህዝብ ነበር፤ አሁን ግን በራሱ ያሳርሳል፤ ከዕለት ጉርሱ እስከ ዓመት ቀለቡ በስጦታ መልክ ይበረከትለት ነበር። ሌላው መስዋዕት ለማቅረብ ወደ ተራራው ሲወጣ ህዝቡ የመስዋዕቱን ከብት በማዘገጀት አጀበውት እየጨፈሩ ይሄዳሉ፤ ባረፈበት ቦታም ገንዘብ በስጦታ መልክ በቡሉኮው ላይ ይጥሉለታል፤ እሱም በምትኩ ህዝቡን፣ ሀገሩን፣ ከብቶቹን ይመርቃል፤ ይባርክም ነበር። ይሁን እንጂ በአሁን ወቅት እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር በጣም በተወሰነ መልኩ እንጂ እንደወትሮው አይደለም።

በማለት በትዝብት መልክ (*አቶ ምኮና ናጋኦ፣ ቆቲ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ* በ3/11/2007 ዓ.ም.) ገልጸውልኛል። ይህ ሂደት ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ስንመለከተው ለቃሉ ይደረግ የነበረው ከበሬታና ታዛዥነት ድርጊት በተወሰነ ደረጃ እየተዘነጋ መሄድ ያሳያል።

ስለዚህ አባቃሉ ኑሮውን ለማሸነፍ ሲል ንግድ ቢጤ እንደ ጀመሩ ለመረዳት ችያለሁ። ይኸውም ወናጎ ከሚባልበት ከተማ ከብት በመግዛትና በማስቀለብ፤መልሶ አትርፎ በመሸጥ ላይ እንደተሰማሩ መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ። ይህ የቃሉ ከገልማው ወጥቶ በየገበያው መሄድ፤ ቃሉ ከገልማው ሆኖ ለማህበረሰቡ ከማገልገል ይልቅ ኑሮዉን ለማሸነፍ እንዲሯሯጥ አስገድዶታል። ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል ልጆች በገዳ የተለያዩ የደረጃ እርከኖች ውስጥ ለመሆናቸው አመላካች የነበሩ የጸጉር አቆራረጦች ነበራቸው፤ አለባበሳቸውም እንዲሁ። አሁን ግን በመስክ ቆይታ እንደተመለከትኩትና ከመረጃ አቀባዮቹ እንደተረዳሁት ከግሎባላይዜሽን ጋር በተያያዘ፡

የዘመናዊ ሃይማኖቶች መስፋፋት፣ የት/ቤቶች በየአቅራቢያቸው መከፈት፣ ቀደም ሲል ከተሜዎቹ ለጉጂ ሕዝብ የነበራቸው ዝቅተኛ አመለካከት በውስጣቸው ካሳደረው የስነ-ልቦና ተፅዕኖ ጋር ተዳምሮ፤ በተለያዩ ከበራዎች ላይ አብዛኛው ልጆቻቸው እንደማይቀረጡና አለባበሳቸው ዘመን ያፈራውን እንደሆነ ለማየት ችያለሁ። በከበራው ላይ የመሳተፉም ሁኔታ አሁን እየተሸሻለ መምጣቱን በመግለጽ፤ ቀደም ሲል በዘመናዊ ሃይማኖቶች አማካይነት በሚሰበኩ የማጥላላት ዘመቻ እየተሸበሩ በባህላቸው ላይ ባይተዋር ሆነው እንደነበር ያስረዳሉ።

በመጨረሻም ከዚህ የገዳ ስልጣነ-ሢመት ከበራ ጋር የሚነሳው፡- ቀደም ሲል በምዕራፍ ስድስት ስር እንደተገለጸው የጌዴኦ አባገዳም ለቃሉ ስጦታዎችን ይዞ በመምጣት ምርቃትና ቁንቢ ይቀበል እንደነበር ተገልጿል። ይሁን እንጂ በአሁን ወቅት ይህ አካሄድ ተቀይሮ በራሳቸው ማከናወን ጀምረዋል። ይህ ከለውጥና ቀጣይነት አንጻር ሲታይ የመቼትና የተግባር ለውጥ ተካሂዷል።

ይሁን እንጂ የጉጂ ቃሉ ተቋምና የገዳ ስርዓት እነዚህንና የመሳሰሉትን ጫናዎች በመቋቋምና በማንሰራራት አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። ይህንን ሂደት ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ በምን መልኩ ተቋቋመ? እንዲሁም እንዴትስ ማንሰራራት ቻለ? የሚሉትን በመተንተን እንደሚከተለው ለማየት ተችሏል።

በአሁኑ ወቅት በዋናነት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት ለህገረሰባዊ ባህል ማንሰራራት (revitalizátion) በፈጠረው ምቹ ሁኔታ የቃሉና ገዳ ተቋማትና ከበራዎቻቸው የማንሰራራት አዝማሚያ በማሳየት ላይ ይገኛሉ።

ለአብነት ያህል እንደ ኦሮሚያ በማዕከል ደረጃ የኦሮሚያ አባገዳዎች አንድነት ጉባኤ (Gumii tokkummaa abbooti gadaa Oromoo) መቋቋሙ በራሱ ቀደም ሲል በተለያዩ ተፅዕኖዎች የተዳከሙና የጠፉ ገዳዎችን በተሃድሶ ስርዓቱ እንዲመለሱ ለማድረግ ያለውን አጋጣሚ እያሰፋ በመሆኑ፤ በቀጣይ ስለአባቃሉ (አባሙዳ) መንፈሳዊ ጉዞም እንዲያስቡበት የሚያደርግና ስርዓቱም እያንሰራራ መሆኑን አመላካቾች ናቸው።

በሌላ በኩል ዓለም አቀፍ የዋቄፋና ሃይማኖት ማህበር (Waldaa Amantii Waaqeffannaa Addunyaa) መቋቋሙ በራሱ ሃይማኖቱ እንዲያንሰራራና ሃይማኖቱን በባለቤትነት ለማስተማርና ለማስፋፋት ባለቤት እንዲኖረው ያደርገዋል። ይህ ማህበር ከተቋቋመበት ዓላማ

እንዱ በአካባቢው የሚከወኑ የሃይማኖቱን ስርዓቶች በማቀናጀት ሃይማኖቱ ማዕከላዊነት እንዲኖረው ማድረግ እንደሆነ ይገልጻሉ (WAWA, 2006)፡፡ ስለዚህ እንደ ጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ተቋም ያሉትን በእነዚህ ማህበራት ስር የመታቀፍና የመጠበቃቸው እድል ሰፊ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሬዲዮና ቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን የተመለከትን እንደሆነ የየብሔረሰቡን ቱባ ባህል አውጥቶ በማሳየት፡ የማህበረሰቡን የአመጋገብ ስርዓትን፣ አለባበሱን፣ በተለያዩ ወቅት የሚጠቀሙባቸውን ባህላዊ ጌጣ ጌጦችን ከተለያዩ ከበራዎች ጋር በማያያዝ ለታዳሚዎች ተደራሽ እንዲሁንና እንዲታወቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ለአብነት ያህል በአብዛኛው የኦሮሚያ ክልል ውስጥ የተደረጉ የገዳ ተሃድሶ ስርዓት (haaromsa sirna gadaa) ያየን እንደሆነ፤ ስለገዳ ስርዓት ማንሰራራት አመላካች ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ በሐረርጌ የኦዳ ቡልቱም ገዳ፣ በቦረና የጉሚ ጋዮ ጉባኤና እንዲሁም በየካቲት 2008 ዓ.ም. በጉጂ ዞን፣ ሚኤ ቦኮ ላይ የተደረገውና ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያገኘው የጉጂ አባገዳዎች ስልጣን ሽግግር ከበራዎች ማንሰራራት የተወሰነ ድርሻ አላቸው፡፡

ሌላው በአሁኑ ወቅት የሚቀርቡ ዶክመንተሪ ፊልሞችና ባህላዊ ዘፈኖችን ያየን እንደሆነ የባህሉንና የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ መዳከምና መረሳት ያሳስባቸው የነበሩ አዛውንቶችንም ጭምር ተስፋቸውን እያለመለመ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ወጣቱንም ክፍል በማንነቱ እንዲኮራና እራሱንም እንዲመለከት እንደ ማንቂያ ደወል እያገለገሉ እንደሆነም መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም፡- በየት/ቤቱ፣ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ የተቋቋሙት የባህል ማዕከላት አዲሱን ትውልድ ከመቅረጽ አኳያ ያላቸው ሚና ሰፊ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላት ሲከበር ባህላዊ አልባሳትን ለብሶ መታደምና በባህላዊ ዘፈኖች ማጀብ በሰፊው እየተስተዋለ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ሲታይ ቀደም ሲል ወደ መዘንጋትና መረሳት ደረጃ የደረሱ ቁሳዊ ባህሎችንና ቃላዊ ግጥሞችን የመጠቀሙ ሁኔታ እያንሰራራ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል ዩባ ሞና ጎዳና ገለጻ የገዳ ስልጣን መያዝ ያለበት በዋቄፋና ሃይማኖት ተከታይ ነበር፡፡ ነገር ግን በአንድ ወቅት በሆኩ ገዳ ስር አባገዳ ጊርጃ ሶዱ የሚባሉ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የነበሩ በሚኤ ቦኮ ስልጣኑን ከተረከቡ በኋላ የገዳ ስርዓት የሚያዘውን ከበራዎች መከወን ተው፡፡ ይኸውም፡-

ተራራ ላይ ወጥቶ ለመስዋዕት ኮርማ ማረድ እንቢ አሉ፡፡ በቦካ (ደራራ) ህዝቡን አልመርቅም አሉ፡፡ ‹ይህ ሀራም ነው፡፡ ካፊር የሚሰራው ስራ ነው፡፡› በማለታቸው የተነሳ እሱእንዲህ ከናቀን የእኛ የሆነውን ከእሱ መውሰድ አለብን በማለት በዩባዎች አማካይነት ስብሰባ ተጠራን፡፡ ከዚያም ከአንደበቱ እንቢታውን መስማት ስለነበረብን፤ ዳግመኛ በባህሉ መሰረት ሊከውን እንደሚገባው ጠየቅነው፡፡ እሱም እንቢታውን ቀጠለበት፡፡ እኛም ከለቻውን ከእሱ ላይ በመውሰድ ይሰራልናል ብለን ላመነው፤ ለአባገዳ ጋምቤላ በሪሶ ከለቻውን ተደረገለት፡፡ አባገዳ ጋምቤላ ባህሉና ሃይማኖቱ በሚፈቅደው መሰረት በጥሩ ሁኔታ ከ2000-2007 ዓ.ም. በማገልገል ይሄው ለአሁን አባገዳ ሊያስረክብ በዝግጅት ላይ ነው፡፡ (ሞና ጎዳና፣ በ7/6/2008 ዓ.ም. ሚኤ ቦኮ ላይ)

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው የገዳ ስልጣን ሽግግር ላይ የነበረውን የመጤ ሃይማኖት ጫና ተቋቁመው ወደ ቀድሞው ስርዓትና የዋቄፋና ሃይማኖት መመለስን ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ባህላዊ ዘፈኖች እራሳቸውን ችለው፤ በሌላ በኩል ባህላዊ ዘፈኑን በዘመናዊ መልክ በማቀናበር ባህሉ እንዲያንሰራራ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በአርቲስት አቡሽ ዘለቀ የተሰራው ሙዴ (Muudee) የሚለው ኪሊፕ የጉጂ ኦሮሞን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከበራዎችን ለዛ ባለው ዜማና ክዋኔ የሚያሳይ ነው፡፡ ተደራሽነቱንም ያየን እንደሆነ ከጉጂ ኦሮሞ ባሻገር ብተለያዩ ክልሎች፣ ከገጠር እስከ ከተማ የሽፈነ ነው፡፡ እነዚህና መሰል የኪነ-ጥበብ ዘርፎች ለባህሉና ሃይማኖታዊ ከበራው ማንሰራራት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ያመላክታል፡፡

በሌላ በኩል ዓለም አቀፍ የዋቄፋና ሃይማኖት ማህበር (Waldaa Amantii Waaqeffa- nnaa Addunyaa) ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ በአካባቢው የሚከወኑ የሃይማኖቱ ስርዓቶች በማቀናጀት ሃይማኖቱ ማዕከላዊነት እንዲኖረው ማድረግ እንደሆነ ይገልጻሉ (WAWA, 2006)፡፡ ስለዚህ እንደ ጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ተቋም ያሉትን በእነዚህ ማህበራት ስር የመታቀፍ እድላቸው ሰፊ በመሆኑ ለወደፊት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቀጠልና አገልግሎቱን ለማስፋፋት ዕድሉ የሰፋ ይሆናል የሚል የአጥኚው እምነት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም በባህልና ቱሪዝም ቢሮ አማካይነት በገዳ ስርዓት ላይ የተደረጉና እየተደረጉ ያሉት ጥናትና ምርምሮች አሉ፡፡ እነዚህ

ጥናቶች የስርዓቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በማመላከት በሚቀርቡት ይሁንታ አማካይነት እውቅና እንዲያገኝና እንዲያንሰራራ የማድረግ አጋጣሚያቸው የሰፋ ነው፡፡

በምዕራፍ ስድስት በ6.1 ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው በየስምንት ዓመቱ መጨረሻ ላይ በሚደረገው የገዳ ማሻሻያ አዋጅ ነገራ (lallaba) ላይ የጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ መቅረቱ አግባብነት እንደሌለውና ይህን ሂዶት ከመንገድ ማስቀረቱ ባህላቸው እንዳልሆነ ተገልጾ፤ ለቀጣይ መከወን እንዳለበት ቃል የተገባበት መልዕክት ተላልፏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አዲስ የተመረጡት ገዳዎች ወደቃሉ ተቋም ሂደቱን በሚያስቀጥሉበት ሁኔታ ላይ ምክክር እንደጀመሩ ከአባቃሉ አጋ ላይ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ታዲያ እነዚህ ሁኔታዎች የቃሉን ተቋም እንቅስቃሴ እንዲያንሰራራ ከሚያፋጥኑ ሁነቶች ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በገዳ ስልጣነ-ሢመት ከበራ ላይ ዋንኛው ተዋናይ ገዳዎቹ በመሆናቸው ነው፡፡

በመጨረሻ በሚኤ ቦኮ በ2008 ዓ.ም. የተደረገው የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራን የተመለከተን እንደሆነ ቀደም ሲሉ ከተከበሩት ለየት የሚያደርገው ገጽታ እንደነበረው ከመረጃ አቀበዮቼ ገለጻና በቦታው ተገኝቼ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ይኸውም፡- በከበራው ላይ የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ፕረዝዳንትና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፕረዝዳንት ጨምሮ፤ የተለያዩ ባለስልጣናትም በስፍራው በመገኘት በከበራው ላይ ታድመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሩቅ የኦሮሚያ አካባቢ ለምሳሌ ከሐረርጌ አካባቢ በስርዓቱ ለመታደም እንደተገኙ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ የህዝብ ብዛቱም ቢሆን ቀደም ሲል፤ ማለትም ከደርግ መንግስት ወዲህ ባሉት ጊዜያት ውስጥ እንደዚህ ያለ ቁጥር ያለው ህዝብ እንዳልተሳተፈ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

## 7.2. የጎንዶሮ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት

በምዕራፍ ስድስት ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው የጎንዶሮ ከበራዎች ለተለያዩ ምክንያቶችና በተለያዩ አካላት ሲከወኑ ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን ጎንዶሮ በተወሰነ ደረጃ የቀድሞውን ያህል ግልጋሎት እንዳይሰጥ ያደረጉት ተግዳሮቶች ተፈጥረዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የዘመናዊ የህግ ስርዓት ጣልቃ ገብነትም እንደ አንድ ውጫዊ ተፅዕኖ ሊታይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ወይም ቤተሰብ ወደ ቃሉ ተቋም በመሄድ የተወሰነባቸውን ውሳኔ መቀበል ግድ ይላቸዋል፡፡ የቃሉን ውሳኔ አልቀበልም ካሉ ከማንኛውም ማህበራዊ አገልግሎቶች ማዕቀብ (bokuu) ይተላለፍባቸዋል፡፡ ታዲይ ይህን ማዕቀብ በሚያስፈጽሙበት ወቅት አድማ ተደረገብን በማለት ለፖሊስ፣ ፍ/ቤትና አስተዳደር ክስ እንደሚሄዱና አንዳንዴም ማዕቀቡን ያስተላለፉ የቃሉ

ተወካዮች እስከመታሰር ደረጃ እንደደረሱ ከመረጃ አቀባዬ ለመረዳት ችያለሁ። ይሁን እንጂ ይህ አሰራር ቀድሞም የነበረ በመሆኑ የቃሉ መልዕክተኞችና የአስተዳደር አካል በመስማማት በጋራ ወደ መፍትሔው ሀሳብ የሄዱበት ወቅት እንደነበረ ለማወቅ ችያለሁ። ይህ ታዲያ ዘመናዊ የህግ ስርዓቱን ከህገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ጋር በማጣመር ማካሄዳቸው አንዱ የለውጥና ቀጣይነት መገለጫ ሆኗል።

ሌላው በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ የመጨረሻው እርቁ እንዲሰምር፣ ልመናው እንዲያርግ የሚከወኑበት ቦታዎችና ቁሳዊ ባህሎች የተለዩ ነበር። አሁን ግን ከወቅቱ ጋር የተቀየሩ ወይም እንደ አማራጭ የሚጠቀሟቸው እንዳሉ ለማየት ችያለሁ። ለምሳሌ ከአንዳንድ ሽምግልናና የተለያዩ ከበራዎች በኋላ ላይ የሚመረቀው በጠጅ ወይም ቦካ ሆኖ ሳለ በቢራ የመመረቁ ሁኔታ እየተለመደ መጥቷል።

ሌላው የምልጃ ማሳረጊያ የጎንዶሮ የተመለከትን እንደሆነ ከዘመናዊ ሃይማኖት መምጣት ጋር ተያይዞ በተከታታይ ለሚከሰቱ ችግሮች የጎንዶሮን ከበራ ከመከወን ይልቅ ‹‹ስለ ጉዳዩ ማጸለይ›› በሚለው አብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንደሚያጸልዩ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ።

በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ አካላት፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለምሳሌ በመንግስት የቃሉንና የገዳና ተቋማት እራሳቸውን ችለው እንዳይቆሙ የሚያደርግባቸውን ጣልቃ ገብነት እንዳሉ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ መንግስት አንዳንዴም ሊጠቀምባቸው ሲፈልግ ከፍ ከፍ በማድረግ የጎላ ሽፋን ይሰጣቸዋል። ከነዚህም ውስጥ አንዳንድ የጎሳና የብሔሮች ግጭት በሚከሰትበት ጊዜ በእራሱ ብቻ ለመፍታት በሚያዳግተው ጉዳዮች በጋራና ተቋማቱ በራሳቸው እንዲፈቱ ያደርጋል፤ በሌላ ወቅት ደግሞ ቁብ እንደማይሰጣቸው መረጃ አቀባዮቼ ይገልጻሉ። ይኸውም፡- ተቀባይነታቸው እየጨመረ ማህበረሰቡ በእነሱ መገልገል ሲጀምር ደግሞ ተቀባይነታቸውን ለመሸርሸር የሚጠቀማቸው ሁኔታዎች አሉ። ለዚህም እንደ አስረጂ በመጀመሪያ በ1987 ዓ.ም. በጉጂና ጌዴኦ መካከል የተፈጠረውን የእርስ በርስ ግጭት በፌዴራል ፖሊስ ኃይል እንደተቆጣጠረውና ወቅታዊ መረጋጋትን ፈጥሮ ነበር። ነገር ግን በ1990 ዓ.ም. በድጋሚ የተካሄደው የሁለቱ ወገን ደም አፋሳሽ ጦርነት ተከሰተ። ጦርነቱን የፌዴራል ፖሊስ ኃይል እንደ በፊቱ ሊያስቆሙ አልቻሉም። የሁለቱም ወገን የሀገር ሽማግሌዎችን ጨምሮ በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

መሀል ገብተው ለመፍታት ሙከራ ጀመሩ። በመጨረሻም መንግስትም የቃሉን ሀገረሰባዊ ተቋም በመቀበል ችግሩ እንዲፈታ ተደረገ። ለሂደቱም የቃሉ መኖር ግድ ስለነበር አባቃሉ ሳቆ ናጋኦን ከታሰረበት ከሀዋሳ ወህኒ ቤት በማውጣት የጎንዶሮ ከበራ ተከወነ። በመጨረሻም ከከበራው መልስ ወደ ወህኒ ቤት ተመልሰው እንደታሰሩና በዚው ሕይወታቸው እንዳለፈ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ በዝርዝር ተገልጿል።

ባጠቃላይ እነዚህ የቃሉ ከበራዎች ስለቃሉና ገዳ ተቋማት ህልውና ምን ደረጃ ላይ እንዳሉና ወዴት እየሄዱ እንደሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አመላካች ናቸው። በሌላ በኩል በተቋማቱ ላይ የነበሩትና ያሉባቸውን የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት፣ የዘመናዊ ሃይማኖቶች መስፋፋትና የዓለምአቀፋዊነት (globalization) ተዳምረው፤ ተቋማቱ እነዚህን ተፅዕኖዎች ተቋቁመው የመዝለቅና የማንሰራራት ዕድላቸውን ከጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ዓለማቀፋዊ የአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በአካባቢዉና አጎራባች ክልሎች እየተቀሰቀሰ ያለው ድርቅና ወረርሽኝ በሽታዎች ለበርካታ ሰዎች መጎዳትና በብዛት ለሚቆጠሩ የቤትና የዱር እንስሳት ሞት ምክንያት ሆነዋል። ይህን ጉዳይ በተመለከት የመንግስት አካላት ከተፈጠረው የአየር ንብረት ጋር በማያያዝ ችግሩ ዓለማቀፋዊ፣ ከዚያም አህጉራዊ ብሎም ሀገራዊ እንደሆነ በሳይንሳዊ መረጃ በማስደገፍ በመግለጽ፤ ከክልሉ መንግስት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በሌላ በኩል የሃይማኖት አባቶች ደግሞ ይህ ክስተት የተፈጠረው ከእግዚኣብሔር ቁጣ እንደሆነ ያስረዳሉ። ይኸውም፦ በገዳ ስርዓት ደኖች የራሳቸው ህግ አላቸው። የሃይማኖት አባቶችም ሆነ የሀገር ሽማግሌዎች የእግዚኣብሔርን እውነት (dhugaa waaqaafi lafaa) መናገር፣ መመስከር፣ መጠበቅና ማስከበር ይጠበቅባቸዋል። ግጭቶች ሲቀሰቀሱ ጥፋተኛው ተጣርቶ፤ የበደለ ክሶ፤ ዳግም ወደዚያ ስህተት እንዳይመለሱና ጎንዶሮ ተብሎ ይቋጭ ነበር። ነገር ግን እነዚህ እውነቶች በአሁን ጊዜ በተለያዩ አካላት በሚደረጉ የመደለያ ቁሶች፤ ገንዘብን ጨምሮ እየተሸራረፉ እንዳሉ ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። በማከልም ለእነዚህን ጥሰቶች ደግሞ የእግዚኣብሔር ምላሹ ቅጣት ነው፤ ቅጣቱም ደግሞ በድርቅ፣ በበሽታና የመሳሰሉት ሁኔታዎች እንደሚሆን ይገልጻሉ።

ለአብነት ያህል በቦረና ዞን፣ ያቤሎ ከተማ በአጎራባች ወረዳዎችና ዞኖች መካከል ለሚነሱ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሔ ለማስገኘት በተደረገ ውይይት ላይ የተሳተፉ አንድ አባት የነገሩኝ ትዝ አለኝ፡፡ እሳቸው እንዳሉት፡-

*‹‹በውይይቱ ወቅት በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩ ግጭቶች ከተፈቱ በኋላ ዳግም ለምን ይቀሰቀሳሉ? የሚል ጥያቄ ከአወያዮቹ ቀርቦ ነበር፡፡ ከተሳታፊዎች የተለያዩ አስተያየቶች ቢቀርቡም እኔን የሳበኝ አንድ የፖሊስ አባል አለ የተባለው ነው፡፡ ይኸውም፡- በመጀመሪያ የገዳ አባቶችን ይቅርታ <(na hofkolchaa?) ‹ይቅር በሉኝ› በማለት ጠየቀ፡፡ እነሱም ‹ይቅር ይበልህ› (hofkol) በማለት ዕድሉ ተሰጠው፡፡ ከዚያም ‹በእውነቱ! በጉጂና ቦረና፣ በቦረናና ገብራ እንዲሁም ከሌሎች ጋር የተለያዩ ግጭቶች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህን ግጭቶች የሚመለከታቸው አካላት ባሉበት ተፈቶ፤ ከብት ታርዶ፤ ጎንደሮ ከተባለ በኋላ ግጥጭቶቹ ተመልሰው ያገረሻሉ፡፡ በዚያን ጊዜ የማንኛውም ወገን አባገዳ ይህ ትክክል አይደለም ከማለት ይልቅ ለራሱ ጎሳ ወገናዊነት ያሳያል፡፡ ስለዚህ እውነት ተናጋሪ በሌለበት እንዴት ተደርጎ እውነተኛ ሰላም ሊሰፍን ይችላል፡፡› አለ፡፡›› (አቶ ቦሩ ኢፋ፣ ዕድሜ 45)*

ከዚህ መረጃና ሌሎችም እንደተረዳሁት ቀደም ሲል ለቃሉና ገዳዎች በማህበረሰቡ በገንዘብም ሆነ በተለያዩ ቁሳቁሶችና የጉልበት ስራ ይደረግላቸው የነበሩ ስጦታዎች በአሁኑ ወቅት ወጥነት የላቸውም፡፡ ከዚህም የተነሳ በሃይማኖታዊና ባህላዊ ተቋማቱ ላይ ብቻ ተወስነው አገልግሎት ለመስጠት ያላቸው ፍላጎት እያተቀዛቀዘ መጥቷል፡፡ በሚትኩ የተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ፣ ለተለያዩ መሰረተ ልማቶች የመሰረት ድንጋይ ሲጣል አብሮ በመገኘትና የተሰሩም ካሉ መርቆ በመክፈት፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚከፈላቸው አበልና በሚደረግላቸው ለየት ያለ እንክብካቤ እየተሳቡ እየሄዱ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በገዳና የመማክርት አባላት ምርጫ ውስጥም መንግስት እጁን ሊያስገባ እንደሚችል ከመረጃ አቀባዮቼ ጥርጣሬ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

### 7.3. የሁሉቃና የፋጭ ከበራዎች ለውጥና ቀጣይነት

እንደ ሀገሪቷ ከግሎባላይዜሽን ጋር ተያይዞ፣ የዘመናዊ ሃይማኖት፣ ትምህርትና የህክምና ተቋማት መስፋፋት፣ እንዲሁም ተደራሽነታቸውም በቀበሌ ደረጃ መውረዱና የማህበረሰቡም በእነሱ መጠቀም ልምዱ እየዳበረ መጥቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ የተለያዩ ወረርሽኝ በሽታ ሲከሰቱ፤

ቀደም ሲል ለቃሉና ለገዳዎች ሪፖርት በማድረግ፣ በምላሹ ቃሉና ገዳዎቹ መስዋዕት በማቅረብ እግዚኣብሔርን ይለማመኑ ነበር። ሁሉቃና ፋጭ ይደረግ ነበር። አሁን ግን ችግር ሲከሰት የቀበሌው መዋቅር ለወረዳው ሪፖርት ያደርጋል። ከበላይ አካል አጥኚ ቡድን በመሄድና ችግሩን ከለየ በኋላ በዘመናዊ የህክምና ዘዴ የመከላከል ስራ ያከናውናሉ።

ይሁን እንጂ የሁሉቃና ፋጭ ከበራዎች ከነአካቴው ቀርተዋል ለማለት አይቻልም። ምክንያቱም የፋጭን ከበራ ያየን እንደሆነ በቤተሰብ ደረጃ ተደጋጋሚ ችግሮች ሲከሰቱ የሀገር ሽማግሌዎችና ወዩዎች በማስጠራት የፋጭ ከበራ እንደሚከወን ካነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ። ሌላው በቃሉና ገዳ ተቋማት ደግሞ የሰውም ሆነ የከብቶች ወረርሽኝ በሽታ፣ እንዲሁም ተከታታይ ድርቅ፣ ከመጠን ያለፈና በረዶ የቀላቀለ ዝናብ ከተከሰተ፣ እንደ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ ተከታዮች እምነት ይህ ክስተት ከመደበኛው ለየት ያለና በእግዚኣብሔር ቁጣ የመጣ መአት ነው ተብለው ይታመናል። ስለዚህ የፋጭ ከበራ ማካሄድ እንዳለባቸው ያስረዳሉ። ስለዚህ እንደ ቀድሞው ጊዚያት ሙሉ በሙሉ ይህን ከበራ የመከወኑ ሁኔታ እምብዛም አይታይ እንጂ አልፎ አልፎ እንደሚከወኑ ለማወቅ ችያለሁ።

ይኸውም፡- ሁሉቃን በተመለከተ እንደ መረጃ አቀባዮቼ በግለሰቦች ደረጃ በቤተሰቦቻቸው ችግር እንዳይደርስባቸው እንደሚከውኑ ይገልጻሉ።ከመከሰቻ አጋጣሚዎቹ ውስጥ ወላጆች ልጆቻቸውን ለትምህርት ወደ ከተማ ሲልኳቸው፣ ከዘመኑ መጥፎ በሽታ ያሽሉካችሁ!፣ ከሚወራው መጥፎ ወሬ ያውጣችሁ!፣ ክፉውን መንፈስ ያስቀርላችሁ በማለት በብብታቸው ስር፣ አንዳንዴም በእግሮቻቸው መካከል፣ አሊያም አጭር እንጨት ቆርጠው በጭንቅላታቸው ላይ በማዞር የጦስ ማውጫ ገደል (bowwaa bita) ይጥላሉ። እነዚህን ከበራዎች ከዘመናው ህክምናና ከመጤ ሃይማኖቶች ጸሎት ጋር በማጣጣም እየተከወኑ ይገኛሉ። መረጃ አቀባዮቼ እንዳስረዱኝ ከሆነ አንድ ሰው ከታመመ በመጀመሪያ በሀገረሰባዊ መድኃኒቶች የሞከርለታል። ከዚያ ልተሸለው እንደሆነ ወደ ህክምና ማዕከል ይወሰዳል። ነገር ግን ወደዚያ ከመሄዱ በፊት፣ በተለይም እናቶች እጃቸውን ወይም አጠር ያለች ልምጭ ቢጤ ከታማሚው አናት ላይ በማዞር ‹‹ጦስህን ይውጣ›› በማለት የበሽታው አምጭ እርኩስ መንፈስ እንዳይከተለው ወደ አቅሪቢያቸው ገደል የመጣል ሁኔታ አሁንም እንዳለ ለመረዳት ችያለሁ።

በሌላ በኩል በየስምንት ዓመቱ በሚካሄደው የገዳዎች የስልጣን ሽግግር ወቅት ከገዳ የደረጃ እርከኖች ውስጥ በዶሪ ደረጃ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን እንደሚከናወኑ አይተናል።

ከነዚህም ውስጥ ሁሉቃ አንዱ ነው። የዶሪና የገዳ አባላት የስልጣን ርክክብ ከማድረጋቸው በፊት ዶሪዎች መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ (kaayoofi faro hamtuu) ተከትሏቸው የወደፊት ስራቸውን እንዳያደነቃቅፍባቸው በማሰብ፤ እንዲሁም ስልጣን ላይ የቆዩት ገዳዎች ደግሞ ምናልባትም በስልጣን ዘመናቸው ወቅት አብሯቸው የነበረ መጥፎ ዕድልና ዕጣ-ፈንታ አሁንም እንዳይከተላቸው በሚል የሚፈጽምት የጦስ ማውጣት (ሁሉቃ) ሃይማኖታዊ ከበራዎች ናቸው። እነዚህ ሂደቶች ያለማቋረጥ በየስምንት ዓመቱ የሚከወኑ በመሆናቸው ከለውጥና ቀጣይነት አተያይ የነበሩትን ጫናዎች ተቋቁሞ መዝለቁን ያመላከተ ነው።

### 7.4. የቃሉ ስያሜ ከበራ ለውጥና ቀጣይነት

የቃሉ ጋብቻ ከበራ ከቃሉ ስልጣነ-ሢመት ጋር ተያያዥነት ያለው ከበራ እንደሆነና ሂደቱም ምን እንደሚመስል በ5.5. ስር በስፋት ተገልጿል። ይሁን እንጂ ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ምን እንደሚመስል ከዚህ ቀጥሎ ተገልጿል።

የቃሉ ተቋም እስካለ ድረስ የቃሉ ስያሜ ከበራ መኖሩ ግድ ይላል። ምክንቱም የቀድሞው አባቃሉ ሲሞት ለተተኪው የስያሜ ከበራ ይፈጸምለታል። ለአብነት ያህል የቃሉ አጋ ሳቆን የስያሜ ከበራ ከንጥል ጥናቱ ለማየት ችለናል።
ይኸውም፡- በአባቃሉ ሳቆ ናጋኦ እልፈተ-ሕይወት ምክንያት ከልጆቻቸው መካከል መስፈርቱን የሚያሟላ መተካት ነበረበት። ስለዚህ አባገዳዎችና የወረዳው የመስተዳድር አካላትን ጨምሮ በህዝቡ ውስጥ የቀድሞውን ያህል ንቅናቄ በመፍጠር የአባቃሉ አጋ ሳቆን ጋብቻና ስልጣነ ሢመት እንዲከናወን ተደርጓል። ከበራውንም በኦሮሚያ ቴሌቭዥን ሰፊ ሽፋን በመስጠት ተላልፎ ነበር። የከበራውን ሂደት በተመለከተ በምዕራፍ አምስት 5.5. ስር መመልከት ይቻላል።

ከቃሉ ስያሜ ከበራ ጋር አብረው የሚነስና አንዳንድ ለውጦች ቢኖሩም ቀጣይነታቸውን ያስመሰክሩ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህሎች አሉ። ከቁሳዊ ባህሎቹ ውስጥ ቀደም ሲል ከቆዳ በቀጥታ ለፍቶና አለስልሶ ይሰሩ የነበሩ አልባሳትና ጌጣጌጦች በዘመናዊ ሌዘርና ሴንቴቲክ እየተቀየሩ መጥተዋል። ይሁን እንጂ በሃይማኖት መሪዎቹም ሆነ፣ በታዳሚዎቹ የሚለበሱ ሀገረሰባዊ አልባሳት፣ በዝግጅቱ ላይ የሚቀርቡ ባህላዊ ምግቦችና የመሳሰሉት ከተመለከትን ቁሳዊ ባህሎች ከስያሜ ከበራው ጋር አብረው የመሻገር ዕድላቸውን አስፍቶታል። ከዚህ በተጨማሪ ከቃሉ

ስያሜ ከበራ ጋር ባህላዊ የጋብቻ ስርዓቱ፣ ባህላዊ ጭፈራዎች የነበረውንና ያለውን የተለያዩ ችግሮች ተቋቁመው እንዲያንሰራሩ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት እንደ ኦሮሞ የገዳ ስርዓት በዩኔስኮ የመመዝገብ አጋጣሚው ስፊ በመሆኑ የተቋማቱ ተጠብቀው መቀጠል እድላቸውን ያሰፋዋል፡፡ በሌላ በኩል የተለያዩ እምነት ተከታዮችም የገዳን ስርዓት እንደማንነታቸው መገለጫ ስለሚቆጥሩት በከበራዎቹ ላይ ኦሮሞዎችን ጨምሮ የሌሎች ብሔርና ብሔረሰቦች፤ እንዲሁም የተለያየ እምነት ተከታዮች በከበራዉ ላይ ተገኝተው ማክበራቸው ለቀጣይነቱ ፍንጭ አመላካች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ስምንት
# ማጠቃለያና ይሁንታ

## 8.1. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት የጉጂ ኦሮሞን የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቹን መተንተን ያስፈለገበት ዐቢይ ዓላማ ከበራዎቹ ያሏቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳዎችን ለማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ ያሉትን የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችን በመለየት፣ ከበራዎቹ መቼና የት እንደሚከወኑ ለመተንተንና ለመግለጽ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሱት በከበራዎቹ ውስጥ የሚቀርቡ ቁሳዊ ባህሎችና ተምሳሌቶቹ ያላቸውን ተግባርና ፍች በመግለጽ፣ እንዲሁም በቃሉ ተቋም የታዩትን ለውጦችና ቀጣይነታቸውንም ለማሳየት ተችሏል፡፡

የጉጂ ኦሮሞ የዋቄፉታ ሃይማኖት ተከታዮች በቃሉና ገዳ ተቋማት አማካይነት ከፈጣሪያቸው ጋር መስተጋብር እንደሚፈጥሩ ይገልጻሉ፡፡ አብዛኛውን መስተጋብር የሚያካሂዱቱ በከበራዎች አማካይነት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቃሉ ከበራዎች የገዳ ስልጣነ-ሢመት፣ የጎንዶሮና የመሳሰሉትን ከበራዎች ያካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህም ከበራዎች እያንዳንዳቸው የየራሳቸው የሆነ መቼት፣ ማህበራዊ ዓላማ፣ ክዋኔና መከወኛ ቁሳዊ ባህሎች አሏቸው፡፡ እንደ ማህበረሰቡ እምነት ከበራዎቹ በዋናነት የሚከወኑት የእግዚኣብሔር ህግጋት ናቸው የሚሉትን እንዲከበሩ፣ ህግጋቱንም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከተጣሱ ደግሞ በከበራዎች አማካይነት ከእግዚኣብሔር ጋር ለመታረቅና ምህረትንም ለማግኘት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይህም ሲባል እግዚኣብሔር ዝናቡን ዝናበ ምህረት፣ አዝመራው ጎምርቶ ጎተራ እንዲሞላ፣ ከብቶቻቸው እንዲረቡና ምርቶቻቸውም እንዲያምር፤ እንዲሁም ከበሽታ ነፃ እንዲሆኑላቸው፣ ሰውንም ከበሽታ፣ ከጦርነት፣ ካላስፈላጊ እስርና እንግልት እንዲታደጋቸው የሚለማመኑበትና በተጓዳኝም እግዚኣብሔር ላደረገላቸው መልካም ስራ ምስጋና የሚያቀርቡበት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በከበራዎቹ የጉጂ ኦሮሞ ማንነታቸውን አጠናክረውና የገዳን ስልጣን ሽግግር ዲሞክራሲያዊ ሂደት ማቆየታቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ባጠቃላይ እነዚህን ከበራዎች በማህበረሰቡና በፈጣሪያቸው፣ በቃሉና ገዳ መካከል ያሉትን መስተጋብሮች እርስ በርሳቸው ምን እንደሚመስሉ በተወሰነ ደረጃ ከሚከተለው ሞዴል ለማየት ይቻላል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በሞዴሉ ውስጥ የወከሉት ከለሮች ከጉጂ ኦሮሞ የዓለም አተያይ እሳቤ ላይ በመንተራስ የቀረቡና ከዚያ ጋር ቀረቤታ ያላቸውን ያካተቱ ናቸው። ይኸውም፡- ጥቁሩን ከፈጣሪያቸውና ከማንነታቸው ጋር ያያይዙታል ስለዚህ ዋቃን እንዲወክል ተደርጓል፣ ቃሉ ደግሞ የጥቁር ግራጫ ከለር እንዲወክለው የተደረገው መንፈሳዊ ኃይሉ ከዋቃ ያገኘው ስለሆነ ከዋቃ መለስተኛ ለመሆኑ ለማሳያነት ነው፣ ግራጫው ደግሞ ገዳን እንዲወከወል የተደረገው በመንፈሳዊ ኃይሉ ከቃሉ ሰለሚያንስ ነው፣ አረንጓዴ ደግሞ የጉጂን ማህበረሰብና አካባቢውን ይወከወላል፣ ነጭ የሚወክለው አመድ፣ ድርቅንና ኮቴ ደረቅነት ነው፣ እንዲሁም ቀይ ደግሞ ከደም ጋር ይያያዛል። ደም ደግሞ ለእግዝኣብሔር መስዋዕትና ልመና ማቅረቢያ እንደሆነና በምትኩ ከእግዚኣብሔር በረከትን ማውረጃ እንደሆነ ስለሚታመን ነው።




ምስል፡-10 የዋቄፋታ፣ ገዳ፣ ቃሉና ዋቃ መንፈሳዊ ግንኙነትና ከበራዎች የሚያሳይ ሞዴል (ምንጭ፡- የጥናቱ አቅራቢ)

## ስዕላዊ መግለጫ

- **ጥቁሩ ክብ ቀለም፡-** እግዚኣብሔርን (ዋቃን) ይወክላል፡፡ እንደ ኦሮሞ የዓለም አተያይ ጥቁር ከሰማይ፣ከንጹህ ውሃ ጋር በማያያዝ የጥሩ ነገሮች ተምሳሌት ሲሆን፤ነጩ ደግሞ የረሃብ፣ የእርዛት፣ የድርቅና የመሳሰሉት ተምሳሌት ነው፡፡ የጥቁሩ ክብ ቀለም ተምሳሌትነት እግዚኣብሔርን ለማመልከት ነው፡፡ ክብነቱ ደግሞ ሁሉም ፍጥረታትና ዓለም በእግዚኣብሔር እቅፍ ውስጥ መሆናቸውን አመላካች ነው፡፡ ከጥቁሩ ክብ እየፈነጠቁ ወደ ውስጥ የሚያመለክቱት ጥቋቁር ቀስቶች የእግዚኣብሔርን ህግጋት፣ ፀጋና በረከትን ወካይ ናቸው፡፡ ነጩ ጠመዝማዛ መብረቅ መሰሉ ደግሞ እግዚኣብሔር ህግጋቱ ሲጣሱ ቁጣና መከራን ማውረዱን የሚያመላክት ነው፡፡ ዝግዛጉ ቀስት ደግሞ የእግዚኣብሔር ቁጣ በቀጥታ ሀጢያት በሰራው ላይ ብቻ እንደማይደርስና ምናልባትም በልጆቹ፣ በንብረቱ፣ አሊያም በቅርብ ዘመዶቹና በመሳሰሉት ላይ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

- **የጥቁር ግራጫ ክብ፡-** አባቃሉን ይወክላል፡፡ የከለሩ ተምሳሌት አባቃሉ አመጣጡ ከሰማይ (ከእግዚኣብሔር) እንደሆነ ስለሚታመን፤ ከፊል መንፈሳዊ ባህሪይን ከእግዚኣብሔር ይዞ መምጣቱንና ከፊሉ ደግሞ ሰዋው ባህሪውን የሚወክል ነው፡፡ ከጥቁር ግራጫ ክብ (ከቃሉ) ውስጥ ወደ ዋቃ የሚያመለክተውቀስት የቃሉን ምልጃና ጸሎት ሲሆኑ፤ በተቃሪኒው ረጅሙ አረንጓዴ ቀስት ወደ ውስጥ የሚያመለክተው ደግሞ የምልጃውና የጸሎቱ መልካም ምላሽ ያተረፈውን ልምላሜንና ብልጽግናን በምርቃትና ቡራኬ መልክ ለምዕመኑ ሲያስተላልፍ የሚያመላክት ነው፣ በመጨረሻም የጥቁር ግራጫው ቀስት ወደ ግራጫው ክብ የሚያመላክተው ደግሞ ቃሉ ለገዳ ከርቤ (qunbii) በማስነከስና በመባረክ መንፈሳዊ ባህሪን ማላበሱን ለመግለጽ ነው፡፡

- **ግራጫ ክብ፡-** ገዳን ይወክላል፡፡ ከለሩ ግራጫ የሆነበት መንፈሳዊ ኃይሉ ከቃሉ ያነሰ ነገር ግን ከተራው ምዕመን ለቃሉም ሆነ ለእግዚኣብሔር ቀረቤታ እንዳለው ለማመላከት ነው፡፡ ከግራጫው ክብ (ገዳ) ውስጥ ወደ ቃሉና ዋቃ አቅጣጫ የሚያመለክቱት የገዳን ምልጃና ጸሎት ሲሆኑ፤ በተቃሪኒው አረንጓዴ ቀስት ወደ

ውስጥ የሚያመለክተው ደግሞ ከእግዚኣብሔር የምልጃውና የጸሎቱ መልካም ምላሽ ያተረፈውን ልምላሜንና ብልጽግናን በምርቃቱ መልክ ለምዕመኑ ማስተላለፉን ነው።

- **አረንጓዴ ክብ፦** ዋቄፋታን ይወክላል። አረንጓደው ከለር የዋቄፋታውን መልካምድርና መተዳደሪያውን የሚወክል ሲሆን፣ የከለሩ ተምሳሌት ልምላሜን፣ ጥጋብን፣ ሰላምን ይወክላል። ከውስጡ ወደ ውጪ የሚያመለክቱት ቀስቶች ደግሞ ዋቄፋታዊ የገዳ አምላክ፣ የቃሉ አምላክ፣ የፈጠርከን ጥቁር እግዚኣብሔር ሆይ! እያለ ሦስቱንም እርከን ጠብቆ መጸለያቸውን አመላካች ናቸው።

- **ነጩ ቀስት፦** ከዋቄፋታው መነሻ አድርጎ ወደ ውጪ የሚወጣው ነጭ ቀስት ሀጢያትን (Cubbuu) የሚወክል ነው። የከለሩ ተምሳሌት እንደ ኦሮሞ የዓለም አተያይ ነጩ የረሃብ፣ የእርዛት፣ የድርቅና የመሳሰሉት ተምሳሌት ነው። ስለዚህ ዋቄፋታ ሀጢያት ከሰራ ከዋቃ ህግ ውጭ ሆኗል ማለት ነው። ከዚህም የተነሳ ከለምለሙ ሕይወት፣ ከሰላማዊ ኑሮው ሊወጣና መከራን ሊቀበል እንደሚችል አመላካች ነው።
- **ቀዩ ግማሽ ክብ ቀስት፦** የቃሉን ከበራዎችና ፋይዳዎቹን አመላካች ነው። የቀስቱ መነሻ የሚያመለክተው የቃሉ ከበራዎች ማህበረሰባዊ ዕውቀት እንደመሆናቸው መጠን ከዋቄፋታው ውስጥ የወጡ መሆናቸውን ሲያመለክት፣ የቀስቱ ጫፉ ደግሞ ወደ ውስጥ የሚያመለክተው አንድ ሀጢያት የሰራ ግለሰብ በሚከወኑ ከበራዎች አማካይነት ወደ ማህበረሰቡ ሰላማዊ ሕይወት ሊመለስ መቻሉንና የከበራውም ፋይዳ ያ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ከለሩ ቀይ የሆነበት ምክንያት አብዛኛው ከበራዎች የሚከወኑት ለእግዚኣብሔር መስዋዕት በማቅረብ ስለሆነ የመስዋዕቱን ደም እንዲወክል ነው።

- **ነጩ ክብ መስመር፦** በአረንጓደው ክብ ላይ ዙሪያውን ከቦት ያለው ነጭ መስመር ዋቄፋታ በተለያዩ አካላት ይደርስበት የነበረውንና እየደረሰበት ያለውን ተግዳሮቶች አመላካች ነው።

በምዕራፍ አምስት ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው በቦረናና ጉጂ ዞኖች ከሚኖሩት ህዝብ የዋቄፋታ ሃይማኖት ተከታዮች የተወሰኑ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛው የሌላ እምነት ተከታዮች በገዳና በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ላይ እንደሚሳተፉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለአብነት ያህል በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ አንደ የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ሰው ባጋጣሚ የሰው ነፍስ በእጁ ቢጠፋ፤ እንደ ዋንኛ አማራጭ የሚጠቀመው ወደ ገዳ ወይም ቃሉ ተቋም እጅ በመስጠት ወይም በመጠለል ለዘለቄታ በጎንዶሮ ሃማኖታዊ ከበራ ችግሩን መፍታት ላይ ነው፡፡ አሊያም ወደ ፖሊስ ጣቢያ እጁን በመስጠት በፍርድ ቤት በኩል የሚሰጠውን ውሳኔ መቀበል ነው፡፡ ስለዚህ አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል በጎንዶሮ ከበራ መፈጸሙን እንደሚስማሙበት ከመረጃ አቀባዮቹ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ምክንያቱም የፍርድ ሂደቱንም ቢጨርስና ነፃ ቢለቀቅ፤ ህሊናው ሁሌም ነፃ እንዳልሆነ እንደሚሰማው ተደርጎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ለጥፋቱም ሆነ ለህሊናው እረፍት የሚሰማው በጎንዶሮ ከበራ ሂደት ሲያከናውን እንደሆነ አብዛኛዎቹ የሚስማሙበት መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ስለዚህ ከዚህ ሂደት የምንረዳው የማንኛውንም ሃይማኖት ተከታይ በቃሉና ገዳ ከበራዎች ከመሳተፍ እምብዛም እንደማያግደው ነው፡፡

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ሃይማኖታዊ ከበራዎቹና ሂደቶቹ የማህበረሰቡ ውቅር ዕውቀቶች ናቸው፡፡ ይኸውም፡- እንደ ማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ካጋጠማቸው ችግሮች የተነሳ፣ አሊያም ሊያጋጥመን ይችላል ከሚሉት ስጋት በመነሳት ማህበረ-ባህላዊ አደረጃጀታቸውን ጠብቀው ለማቆየት፣ ከፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ስጋት ለመታደግ ሲሉ የተፈጠረና በልማድ እየዳበረ የመጣ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ይህ ዕውቀት በግለሰቦችና ቡድኖች ተዋቅረው፤ ከዚያም ወደ ተቋማት በመግባት ለዚህ ማህበረሰብ እንደመተዳደሪያ ህግና ደንብ ሆኖ ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡

ከበራዎችን ያየን እንደሆነ ከቃሉ አንስቶ እስከ ሀገር ሽማግሌዎች ባሉ ደረጃዎች የሚከወኑ ሲሆን፤ አስተምሮቱ ግን የቃሉ እንደሆነ ከሚቱ ላይ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከበራዎቹ በቃሉና በመማክርት አባላቶቹ አማካይነት በየራሳቸው መቼት ላይ ይከወናሉ፡፡ የሚከወኑበትም ምክንያቶችና መከወኛ ቁሳዊ ባህሎቹ የተለያዩ ናቸው፡፡ ቀደም ስል እንዳየነው በዚህ ክዋኔ ላይ የቃሉ መማክርት አባላት የየራሳቸው የስራ ድርሻ አላቸው፡፡ ለምሳሌ በከበራው ላይ የቀረበው መስዋዕት መሳካት አለመሳካቱን የሚገልጹት ሞራ አንባቢዎቹ ናቸው፡፡ በዚህ መልክ በየዘርፉ

የእያንዳንዱ እይታ ምን ይመስላል? የሚለው ተዳምሮ ስለዚያ ከበራ መሳካት ይገለጻል፤ ይፈጸማል።

በከበራ ውስጥ የቃሉን ተግባር የተመለከትን እንደሆነ እንደ አብዛኛዎቹ ተመራማሪዎች ገለጻ ሃይማኖታዊ ፋይዳ እንዳለው ብቻ እንደሆነ ለማየት ተችሏል። ነገር ግን በዚህ ጥናት ለማየት እንደተቻለው ከዚህ በተጨማሪ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተግባራትም አለው። እነዚህ ተግባራት በግልጽ የሚታዩት ደግሞ በይበልጥ በገዳ ስልጣን ሢመት ከበራ ላይ ነው። ይኸውም ወደ አባ ሙዳው ቀዬ የሚደረገው ታላቅ መንፈሳዊ ጉዞ የተለያዩ ዓላማዎች አሉት። አንደኛው እያንዳንዱ የገዳ መሪዎች ከአባ ሙዳው ምርቃትና ይሁንታ ማግኘት ስላለባቸው ነው። ሌላውና ዋነኛው ደግሞ የጉጂ ኦሮሞ ጎሳዎች እያንዳንዳቸው በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ኩኔቶች ላይ ተገናኝተው ይወያያሉ፤ በተያያዘ መልኩ አንድነታቸውንም ጠብቀው እንዲኖሩ ያደርጋል። ስለዚህ የኦሮሞ ሃይማኖት ተቋም በኦሮሞ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። በሌላ በኩል የገዳን ስልጣን በማጽደቅ ሂደት ውስጥ በአግባቡ ተመርጦ ያልመጣውን ገዳ ቁንቢ በመስጠት እንደማያጸድቅና በተዘዋዋሪ መንገድ ዴሞክራሲያዊ አካሄዱን እንደሚያስጠብቅ ለመረዳት ተችሏል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የቃሉና ገዳ ተቋማት የተለያዩ ግጭቶችን በመፍታትና ዘላቅ ሰላምን በመመስረት የአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ሲያከናውን ይታያሉ፤ ቀድሞ የነበረውን ሰላማዊ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ከመመለስ አኳያ ያለው ፋይዳም ተጠቃሽ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በእያንዳንዱ ከበራዎች በተደረገው ንጥል-ጥናት መሰረት ተተንትነው ያላቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳቸውን ለመግለጽ ተችሏል። ለምሳሌ፡- ቃሉ የውስጥ ግጭቶችን (ገዳ ከገዳ፣ ግለሰብ ከግለሰብ፣ ግለሰብ ከማህበረሰብ ጋር) እንዲሁም የውጭ ግጭቶችን (ጉጂ ከአጎራባች ብሄርና ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጋር) በመፍታት (በጎንዶሮ) ሰላምን ከማስፈንና ማስጠበቅ አኳያ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቀድሞ የነበረውን ማህበራዊ ህይወት ከመገንባትና ወደ ቀድሞ ሰላማዊ ኑሮ ከመመለስ አኳያ ያለውን ድርሻ ለማየት ተችሏል። ስለዚህ እንደ Bell አገላለጽ ከበራዎቹን ታዳሚዎች በኑሯቸው የሚጠቀሙባቸውንና የሚመሩባቸውን እሴቶችና ተምሳሌቶች መግለጫ አድርገው ይጠቀሙባቸዋል (Bell, 1997)።

የቃሉ ተቋም ዘርፈ-ብዙ ተግባራት ያለው ቢሆንም በተለያዩ ጊዜያት በተነሱ መንግስታት፣ ዘመናዊ በሚባሉ ሃይማኖቶችና ግሎባላይዜሽን ሳቢያ አውንታዊም ይሁን አሉታዊ ለውጦችና ቀጣይነት የታዩባቸውም እንዳሉ ለማየት ተችሏል። አሉታዊ ለውጦችን የተመለከትን እንደሆነ በቃሉና ገዳ ስርዓትና ተቋማት ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በአጼዎቹ አገዛዝ፣ በደርግና በኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስታት በመጠንና በዓይነት ከመለያየቱ በቀር ተፅዕኖዎች ነበሩ፤ አሉም። የደርግ አገዛዝን የተመለከትን እንደሆነ የገዳን ስርዓት በኃይል ለማጥፋት መሞከሩና የቃሉን ተቋም ደግሞ እንደኋላ ቀር አስተሳሰብና ባህል በመቁጠር የማዳከም ሁኔታዎች ይታዩ ነበር። የአጼዎቹንና የኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት ደግሞ የሚያመሳስላቸው ቃሉና ገዳዎችን በመደለያ የመያዝ ስትራቴጂ በመጠቀም የእነሱ አስፈጻሚዎች ማድረጋቸው ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት አዲስ የአከላለል ስትራቴጂ የተነሳ የጉጂ ኦሮሞ መገለጫ ከሆኑት ውስጥ ያቃሉ ተቋም፣ የተለያዩ የቃሉ መንፈሳዊ ቦታዎችና በገደብ የሚገኘው የገዳ መንፈሳዊ ቦታ ወደ ጌዴኦ ዞን በመካለሉና ለተለያዩ ግልጋሎቶች እንዲውሉ በመደረጉ እንዲረሱ፣ ሲያሜያቸውም እንዲዛቡ ከማድረግ አንፃር እንደውጫዊ ተፅዕኖ አድራሽ ሊቆጠሩ ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህ ሃማኖታዊና ባህላዊ ተቋማት እነዚህንና የመሳሰሉትን ጫናዎች በመቋቋምና በማንሰራራት አሁን ላሉበት ደረጃ ደርሰዋል። ለዚህም በተወሰነ ደረጃ ከአጼዎቹ አገዛዝ፣ የደርግ የተሻለ ነበር። ከደርግ ደግሞ የኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት ለባህልና ቋንቋ ከሰጠው መብት አንጻር የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም በሀገሪቱ ስራ ላይ ያለው ሕገ-መንግስት አጽንኦት የሰጠው «የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን»ማንነት ያከበረና የራሳቸውን ጉዳይ ለራሳቸው እንዲፈቱ መብት የሰጠ ነው።

በሌላ በኩል ቀደም ሲሉ ከተከበሩት ከበራዎች፤ ማለትም ከደርግ የስልጣን ዘመን አንስቶ ከተከበሩት የተለየ የሚያደርጉት ብዙ ነገሮች እንዳሉት ከመረጃ አቀባዮች ለመረዳት ተችሏል። ይኸውም፡- ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ለከበራው መንግስት ክብር በመስጠት የኢ.ፌ.ድ.ሪ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ ሌሎችም ከፍተኛ ባለስልጣኖች ታድመዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በሚኤ ቦኮ በሚካሄደው ከበራ ላይ የፀጥታ ክፍሉን የሚቆጣጠሩት ጃልዳባዎች ብቻ ሲሆኑ፤የሚጠብቁትም በልምጭ ብቻ ነበር።ለዚህም እንደምክንያት የሚያቀርቡት ታደሚዎቹም ባህሉንና ስርዓቱን ስለሚያውቁና ስለሚያከብሩ ብዙ ያፈነገጡ የፀጥታ ችግሮች እንደማይከሰቱና ለስርዓቱም ተገዥ በመሆናቸው ነው። አሁን ግን ከበላይ አካል ከሚመጡትና ከዘመኑም ጋር

አንዳንድ የፀጥታውን ሁኔታ ሊያውኩ የሚችሉ አካላቶች ሊኖሩ ይችላሉ ከሚል ስጋት የተነሳ ከቀበሌ ታጣቂ እስከ ፌደራል ፖሊስና ልዩ ጥበቃዎች ሊሳተፉ ችለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ከዘመኑ ጋር አብረው የመጡ ለውጦችን ስንመለከት ቀደም ሲል ሀጋና ለማስገባት ከሚኤ ቦኮ ወደ ሱታኤ የሚኬደው በእግር ሲሆን አሁን የመንግስት አካላት ለመስዋዕት የሚቀርበውን ከብት ጭምር በመግዛትና በመኪና እዚያ ድረስ ማድረሳቸውን ለማየት ችያለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ በጥናቱ ለማየት የተቻለው በ2008 ዓ.ም. በሚኤ ቦኮ ላይ በተደረገው የጉጂ የገዳ ስልጣን ሽግግር ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተቋርጦ ለነበረው የጉቱ ጉዞ የተፈጠሩትን ስህተቶች አምነው ለቀጣይ ወደ ቃሉ ተቋም ስጦታ በመያዝና በመጓዝ የገዳን ስልጣን-ሢመት ለማከናወንም ቃል የተገባበት ክበራ ነበር።

ባጠቃላይ ይህ ጥናት በውስጡ በዓላማው ስር ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ የሰጠ ነው። ይኸውም፡- በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ክበራዎች የገዳ ስልጣን-ሢመት ማጽደቅ፣ የጎንዶሮ፣ የፋጭ፣ የሁሉቃና የቃሉ ጋብቻ ክበራ እንደሆኑ በዝርዝር ታይተዋል። እነዚህ ክበራዎች የማህበረሰቡ ውቅር እውቀት እንደሆኑና እሱንም እንዴት አወቁት የሚለውን ደግሞ በማህበረሰባዊ ዕውቀት አዋቃሪያንና በኢፒስቲሞሎጂ ንድፈ-ሀሳቦች ተተንትነው ቀርበዋል። እነዚህን ክበራዎች የሚከወኑትም ለማህበረሰቡ ካላቸው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳዎች ነው። ይህም ከፋይዳዊ ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ተተንትነው ተገልጸዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ እነኚህ ከላይ የተዘረዘሩት ክበራዎች የሚከወኑት በዋናነት በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሯዊ መቼቶች ላይ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የጊዜ ጉዳይ ነው። የቃሉ ክበራዎች ማህበረ-ባህሉ ባስቀመጠው ጊዜና ቦታ የሚከወኑ ናቸው። በክበራው ላይ የሚቀርቡ ቁሳዊ ባህሎችም ሆኑ ክዋኔዎቹ ከባህሉ አኳያ የራሳቸው ተምሳሌቶች አሏቸው። ታዲያ እነዚህን ተምሳሌቶች በተምሳሌታዊ አተረጓጎም ንድፈ-ሀሳብ አንጻር ተተንትነው ያላቸውን ፍች በዝርዝር ለማየት ተችሏል።

## 8.2. ይሁንታ

ስለቃሉ ክበራ ስናነሳ፣ የቃሉን ተቋም ክዋኔዎችና ፋይዳዎቹ ማለታችን ነው። ቃሉ ደግሞ የዋቄፋና ሃይማኖት መሪ ነው። ስለዚህ የእሱ ተግባራትና ሃይማኖታዊ ስነ-ምግባሩ፣ እንዲሁም የቃሉን ተቋም ውስጣዊና ውጫዊ አደረጃጀት በተወሰነ ደረጃ የቀድሞውን ማስቀጠል ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሌሎች የመጤ ሃይማኖቶች ተፅዕኖ አሻራዎች በቃሉ ተቋም ውስጥ ሰርገው በመግባት ሀገረሰባዊነቱ ላይ ጠባሳ እንደፈጠሩ ለማየት ተችሏል።

ለአብነት ያህል፡- በምዕራፍ ሰባት ስር እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አባቃሉንና የተወሰኑ አባገዳዎችን ክርስትና በማስነሳት፣ እምነቱንም እንዲቀበሉ በማድረግና ሌሎችንም ስርዓቶች እንዲከተሉ የማድረግ ሁኔታዎች ታይተዋል፤ ይታያሉም። ከነዚህም ውስጥ አፅጂማትን ማክበር፣ በአንገታቸው ላይ ማዕተብ ማሰር፣ የመላዕክት ምስሎችን በገልማው ውስጥ የመስቀልና መንፈሳዊ መዝሙሮችን ማስደመጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ነገር ግን ይህም ሆኖ ሳለ በቃሉ ተቋም ውስጥ የሀገረሰባዊ ሃይማኖቱን ተግባራትና ፋይዳቸውን በመቃወም ክዋኔዎቹን ማስቆም የቻለ አካል አልነበረም፤ እየተከወነም ይገኛል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ባዕድ ስርዓቶችና ሃይማኖታዊ ቁሶች የዋቄፋና ሀገረሰባዊ ሃይማኖት መገለጫዎች ስላልሆኑ ከሃይማኖት መሪዎቹም ሆነ ከተቋሙ ውስጥ ማስቀረት የሚቻልበትን መንገድ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/በት ከቃሉ መማክርት አባላት ጋር በመመካከር የመፍትሔ አቅጣጫ ቢፈለግ፤ ይኸውም፡- አሁን የኢ.ፌ.ድ.ሪ መንግስት ለሀገረሰባዊ ሃይማኖቶችና ባህል ማንሰራራት በፈጠረው ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም፤ የቃሉ ተቋም ወደ ቀድሞው ሁኔታ ማንሰራራቱን እንደጀመረ ሁሉ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮቹ ተፈተው ወጥነት ያለው ተቋም ማድረግ ቢቻል፡-

- ሌላው በአሁን ወቅት በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች የገዳ ተሃድሶ ስርዓቶች እየተካሄዱ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ ለገዳ ስርዓት ማንሰራራት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ለዚህ እንደ አብነት በ2007 ዓ.ም. በሀረርጌ የተካሄደውን የ«ኦዳ ቡሉቱም» የገዳ ክበራ ተጠቃሽ ነው። በምርቃት ስርዓቱም ሆነ ምርቃቱን በመቀበል የተሳተፉ ብዛት ያላቸው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እንደነበሩ ለማየት ተችሏል። ይህ ደግሞ የሚያመለክተው የገዳ ስርዓት ለኦሮሞዎች ሁሉ እንደ አንድ መገለጫ መሆኑን ነው። ስለዚህ እምነታቸው ሳይገድባቸው በስርዓቱ ላይ መታደማቸው ደግሞ የማንነታቸው መገለጫ በመሆኑ ነው።

ለዚህ ደግሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ተቋም መኖሩ ለባህሉም ሆነ ለህገረሰባዊ ሃይማኖቱ ወሳኝ በመሆኑ ማህበረሰቡ በቃሉና ገዳ ስርዓት የማንሰራራት ሂደት ውስጥ ተደጋጋፊነታቸው በግልጽ ማሳየትና ትኩረቱንም በሁሉም አቅጣጫ ቢያደርጉ፡-

- ከዚህ ጋር በተያያዘ አሁን በአዲስ መልክ ተዋቅሮ ያለው የኦሮሚያ አባገዳዎች አንድነት ጉባኤ (Gumii tokkummaa abbooti gadaa Oromoo) መዋቀሩ እንደ ኦሮሚያ የገዳ ስርዓቱ አንድ ዓይነት አካሄድ እንዲፈጠር እንደሚያደርግ ጥርጥር የለውም፡፡ ነገር ግን በዚህ ጉባኤ ውስጥ ለቃሉ ቦታ ሊሰጠው እንደሚገባ የአጥኚው እምነት ነው፡፡ ምክንያቱም አንዳንዴ አፈንጋጭነት ማለትም፡- ቀደም ሲል በምዕራፍ ሰባት ስር እንዳየነው አንዳንድ አባገዳዎች ከተፈቀደላቸው የስልጣን ጊዜ በተጨማሪ የማገልገል ፍላጎት ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል የመንግስት አካላትም በስልጣን ላይ ያለው ገዳ ለእነሱ አሰራር የተመቻቸው ከሆነ የማስቀጠል ሁኔታም ይታይ እንደነበር ተገልጿል፡፡ ስለዚህ ይህን ዓይነት ክፍተት ቀደም ሲል በባህሉና በሃይማኖቱ ይቆጣጠሩበት የነበረው በዋናነት በቃሉ ተቋም አማካይነት ነው፡፡ ታዲያ ይህ ባህልና ወግ ሳይሸረሸር መተላለፍ ስላለበት ከአባገዳዎቹ ጉባኤ መዋቅር በተጓዳኝ በአሁኑ ወቅት ስርዓቱን ጠብቆ ያለውን የጉጂ ቃሉ ቦታ ቢኖረው ስርዓቱን ምሉዕ ሊያደርግ ስለሚችል የሚመለከተው አካል ቢያስብበት፡-

- ሌላው ስለቃሉ ተቋም በሪፈረንደም ወደ ጌዴኦ ዞን፣ ወናጎ ወረዳ መካተቱ በጉጂ ኦሮሞ ዘንድ ቅሬታ እንዳሳደረባቸው ተገልጿል (Asebe, 2007)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመስክ ቆይታዬ ወቅት ባሰባሰብኩት መረጃ የማንነታችን መገለጫ የሆነውን ‹‹የቃሉ ተቋም›› ለሪፈረንደም መቅረቡ በራሱ አግባብነት እንዳሌለው ቅሬታ ባዘለ አነጋገር መግለጻቸውን ለማረጋጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ «ገልማ ቃሉ» ከቦታነቱ ባሻገር ለጉጂ ኦሮሞ ያለውን ፋይዳ የጉጂ ኦሮሞዎች ከተለያየ ቦታ መጥተው የሚገናኙበትና የተለያዩ መረጃዎችንም የሚለዋወጡበት ማዕከል እንደሆነና አሁን ግን እንደበፊቱ ለመሄድ ብዙም ምቾት እንደማይሰማቸው ካደረጉት ገለጻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዘው የማምለኪያ ስፍራዎቹም ወደ ወናጎ ወረዳ የተካተቱ እንዳሉና በአሁኑ ወቅት ከመንፈሳዊ ግልጋሎታቸው ይልቅ ለሌላ አገልግሎቶች እየዋሉ እንደሆነ በመስክ ቆይታው ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለአብነት ያህል የቂሊጦ ተራራን (kooba qilixoo) ትክል ድንጋይ አምጥቶ በመትከል ጥንታዊ ይዘቱንም ቀይረው የመለስ ፓርክ ተብሎ መሰየሙ እጅግ

እንዳስከፋቸው ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊና ሃይማኖታዊ አሻራዎችን ጥያቄ ውስጥ ከሚያስገቡ ድርጊቶች ተቆጥበው ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመወያየት ለወደፊት በሰላማው መንገድ ለጉዳዮቹ የመፍትሔ አቅጣጫ ቢቀመጥላቸው፡-

- ከመንግስት በኩል በቃሉና ገዳ ተቋማት ላይ ነባሩን ባህላዊ፣ መንፈሳዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተግባራት በሚጥስ መልኩ፤ ቀጥተኛ የፖለቲካ ተሿም እስኪመስሉና የፖለቲካዊ አስተዳደር ቦታ በመስጠት በተቋሙና በተቋሙ መሪዎች እጅ የማስገባቱ ሁኔታ የታየበት ወቅት እንደነበርና አሁንም በተወሰነ ደረጃ እየታየ እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ ለማየት ተችሏል፡፡ ስለዚህ ይህ ዓይነት አካሄድ የተቋማቱ ህልውና ነጻነት ስለሚያሳጣውና ተዓማኒነታቸውንም ስለሚቀንስ የመንግስት ከእንዲህ ዓይነቱ ጣልቃ ገብነት የሚታቀብበት መንገድ ቢፈጠር፡-

- በቃሉና በገዳ የከበራ መቼቶች ላይ ያለው ገጽታ የተሻለ ሁኔታዎች እንዳሉ ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የሚኤ ቦኮን መንፈሳዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስፍራ ያየን እንደሆነ በተወሰነ ደረጃ ጥብቅ ነው፡፡ ነገር ግን የቃሉ ማምለኪያ ተራሮችን የተመለከትን እንደሆነ ከበፊቱ ለምነቱን የማጣት፣ ቦታዎቹም በግለሰቦች እየተገፉ መወሰድና የመሳሰሉ ችግሮች እንዳሉ በምልከታ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህ እነዚህ የከበራ ስፍራዎች በመንግስት በኩል የህግ ጥበቃና እንክብካቤ ቢደረግላቸው፡-

- እንደ ጉጂ ኦሮሞ ዋንኛው የገዳ ስልጣን መረካከቢያ ስፍራ ሚኤ ቦኮ ነው፡፡ በሚኤ ቦኮ የገዳ ማዕከል ሊሰራ እንደታቀደ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጋር ተያይዞ የቃሉ ገልማ በዘመናዊ መንገድ የጉጂን ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች በሚገልጽ መልክ ወረዳው ማህበረሰቡን በማስተባበር ቢሰራ፤ ከባህላዊና ሃይማኖታዊ ተቋምነቱ ባለፈ እንደ ቱሪዝም መስዕብነት ሊያገለግልም ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡-

- በመጨረሻም ገዳን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እየተደረገ ያለው ጥረት ቢሳካ እነዚህ በጥናቱ ውስጥ የተነሱት ከበራዎችና ባህሉን ለማስጠበቅ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠሩ ጥርጥር የለውም የሚሉትን የይሁንታ ሀሳቦች አቀርባለሁ፡፡

## ዋቢዎች

### 1. በእንግሊዝኛ የተጻፉ

#### 1.1. Books


Asmerom Legesse. (1973). *Gada, the Three Approaches to the Study of African Society.* New York. The free Press of A division of Macmillan Publishing. Co. Inc.

______________. (2000). *Oromo Democracy.* An Indigenous African Political System. Lawrence Eville, NJ: The Red Sea Press.

Baldick C. (2nd ed.).(2001). *The Concise Oxford Dictionary of Literary Terms.* Oxford University Press.

Ballenger, E.W. (1998). *Figures of Speech Used in Bible; Explained & Illustrated.* Michigan; Baker Books house Grand Rapids.

Barnard A. & Jonathan S..(2002). *Encyclopedia Of Social & Cultural Anthropology.* London & New York.

Bartels, L. (1983) *Oromo Religion Myths and Rites of the Western Oromo of Ethiopia*-An Attempt to Understand Berlin: Dietrich Reimer Verlag.

Bauman, R. (1983). *The Field Study of Folklore in Context.* In Handbook of American Folklore, Richard Dorson, Bloomington: Indian University Press, PP 362-368.

Bell, C. (1997). *Ritual:Perspective and Dimensions.* Oxford: Oxford University.

Ben-Amos, Dan. (1993). *"Context in Context."* Western Folklore, vol, 52, no 214, PP 209-226.

Berger and Luckman. (1966). *The Social Construction of Reality.* United States of America.

Best Jhon, & Jems V. (7th ed.). (1993). *Research in Education.* New Delhi: Printice Hall of India Private Limited Press.

--------------. (2006). *Folklore in Context.* Nordic journal of African studies. New Delhi:Vol.15,No.3,South Asia Publishers.

Bronner, Simon J. ( 2007). **The Meaning of Folklore:** *The analytical essays of Alan Dandes.* Utah: Utah State University Press

Burr, V. (2nded.).(2003). *Social Constructionism.*Taylor & Francis Routledge

Campbell, Joseph.(1970).*The Hero With A Thousand Faces.* Princeton University Press.

Central Statistical Agency. *The 2007 Ethiopian Population and Housing Census: results for the Oromiya Region*. Volume II, Analytical Report.CSA. A. A..

Creswell, J.W. (2nd ed.).(2007). *Qualitative Inquiry Research Design:* Choosing Among Five Approaches. Thousand Oaks, London, New Delhi: Sage Publications, Inc.

Crotty, Michael. (1998). *The Foundations of Social Research*: Meaning & Perspective in the Research Process. Sage Publications.

Danesi M. (3rd ed.) (2004). *Messages, Signs, and Meanings*: A Basic Text book in Semiotics and Communication, Studies in Linguistic & Cultural Anthropology. University of Toronto, Canadian Scholars' Press Inc. Vol.1.

Dejene Gemachu. (2011). *The customary courts of the waliso oroimo*. Gebre & et al.(ed.).Customary Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia. P.p. 251-277. The Ethiopia arbitration and conciliation Center.A.A.

Dorson, Richard M. (1972). *Folklore and Folk life: An Introduction*. Chicago, the University of Chicago Press.

Dundes, A. (1980). *Interpreting Folklore*. Bloomington: Indian University Press.

Flick, Uwi. (2007). *An Introduction To Ultimate Research*. London: Sage Publication Ltd.

Finnegan, R. (1970). *Oral Literature in Africa*. Oxford University Press, Oxford.

Gadaa Melbaa. (1988). *Oromia: An Introduction*. Khartoum, Sudan.

Georges, A. & Michael, Jones. (1995). *Folkloristics; An Introduction*. Bloomington and Indiana polis; Indiana University Press.

Goldstein, Kenneth S. (1964). *A Guide for Field Works in Folklore*. Pennsylvania, Folklore Associates Inc.

Glassie, Henry. (1999). *Material Culture*.Bloomington; Indiana University Press.

Gray. E. David. (2004). *Doing research In The Real world,* Sage Publications, London: Thousand oaks', New Delhi,

Green. Thomas, A. (1997). *Folklorean Encyclopedia of Beliefs Customs, Tales, Music and Art,* Santa Barbara, California.

Geertz, Clifford.(1973). *The Interpretation of Cultures*. New York: Basic Books.

Haberland, E, (1963). *Galla Sud-Ethiopiens Stuttgart:* W. Kohl hammer Verlag.

Israel, Itansa.(2011). *The Quest for the survival of gada system's role in conflict resolution.*Gebre & et al. (ed.). Customary Dispute Resolution Mechanisms in Ethiopia. P.p. 299-320. The Ethiopia arbitration & conciliation Center. A.A.

Jonathan Z. Smith. (1996). *A Matter of Class: Taxonomies of Religion.* The University of Chicago,

Jones, M. Owen (ed.). (2000). *Putting Folklore to use.* The University of Kentucky.

Julia Riemer, Frances. (2008). *Ethnography Research*, Lapan.

Knutsson, K.E. (1967).*Authority and Change: The Study of the Kalu Institution Among the Macha Galla of Ethiopia*. Gothenburg.

Marshal, C. & Rossman,G. ($4^{th}$ Ed.). (2006). *Designing Qualitative Research*. United States of America: Saga Publication Inc.

Matthews, Bob. & Liz Ross.(2010). *Research Methods: A Practical guide for the Social Sciences.*University of Birmingham.

Mazama, Ama & Molefi Kete Asante.(eds.).(2009). *Encyclopedia of African Religion.* Sage Publications.Inc.

McCormick, C. T. and White, K. K. (eds.). (2011). *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.*

Mohammed Hassen. (1994).*The Oromo of Ethiopia.* A History, (1570-1860), Trenton, NJ: The Red Sea Press,

Myrvold, Kristina.(2007). *Inside the Gurus Gate Ritual Uses Text Among the Skins inVaranasi.* Sweden: University Lund.

Okpewho, Isidore (1992). *African Oral Literature*. USA: Indiana University Press.

O'Neil Dennis. (2009). *Anthropology of Religion:* Overview of Religion.

Oring, Elliott. (1986). *Folk Groups and Folklore Genres*; An Introduction. Logan; Utah State University Press

O'Reilly, Karen. (2005). *Ethnographic Methods*, London. Rout ledge,

Peoples, J. and Bailey, G. (2nded.).(1991). *Humanity:* An Introduction to Cultural Anthropology. West Publishing Company.

Population Census Commision (Dec 2008). *Summary and Statistical Report of 2007 Population and Housing Census.* Addis Ababa: United Nations Population Fund (UNDF).

Rappaport, Roy A. (1999). *Ritual and Religion in the Marking of Humanity.* Cambridge University press.

Robert, A. Segal (ed.). (2006). *The Black Well Companion to the Study of Religion.* United Kingdom: Black Well Publishing.ltd.

Reeves,S. & et al, (2008). *Qualitative Research Methodology Ethnography.*

Salamone, Frank A. (Editor). (2004). *Encyclopedia of Rites,Rituals and Festivals.* London:Rout ledge New York

Schoemaker H. George (ed.) (1990). *The Emergence of Folklore in Everyday life: A Field guide & Source Book.* Trickster press.Bloomington; Indiana: Trickster Press.

Shipley, J.T. (1970). *A Dictionary of World Literary Terms.* Aston, The Writers' Inc. Publisher,

Shovel M..(2nded.).(2007). *Macmillan English Dictionary: For Advanced Learners.* New edition Free online access. International Student edition. Macmillan Publishers Lim.

Sims, C. Martha & Stephen Martin. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition.* Lagon: Utah State University Press.

Turner, Victor (1977). *The Ritual Process structure and Anti- Structure.* New York: Cornell University Press.

Van. Gennep, A. (1960). *The Rites of Passage.* Translated by M.B. Vizedom and G.L. Caffee. London Rout ledge and Keg an Paul.

Van de Loo, Joseph. (1991). *Guji Oromo Culture in Southern Ethiopia.*Religious Capabilities in Rituals and Songs.Berlin: Dietrich Reiner Verlag.

Wilson, William A.(1986*)."Documenting Folklore" In Folklore Groups & Folklore Genres An introduction.* ed. Utah State University Press.

Woodword, Ian. (2007). *Understanding Material Culture.* London; Sage publ. Ltd.

## 1.1. Articles and Theses


Abiyot Negera. (2005) "Guji-Gedeo Relation from 1880s to 1974". BA thesis. Dilla College of Teachers Education

Al-Amin Sheyto. (1998). "Gada System: Nature, Operations and Constraints, with the reference to the experience of Guji Oromo." (Unpublished). A.A.U. BA Thesis in Pol. Science and Inter. Relation ship.

Asebe Regassa.(2007). "Ethnicity & Inter-Ethnic Relations: The 'Ethiopian Experiment & The case of GUji and Gedeo." Thesis Submitted for the Degree of Master of Philosophy in indigenous study, University of Toromso.

Bascom, W..(1965). "The Forms of Folklore Prose Narratives."The Journal of American Folklore. Vol. 78, No. 302, pp. 3-20.

Clay, J W and B K Holcomb.(1986). Politics and the Ethiopian Famine 1984-1985 Cultural Survival Report 20 Cambridge.

Dinsa Lepisa. (1975)."The Gada System of Government" Addis Ababa University: LLB Thesis.

Dorson, M. Richard. (1963). "Current Folklore Theories", in Current Anthropology. Vol.4, No.1.Accessed 17/02/2008,11:12

Elfineh Udessa. (1994)."The Guji Calendar. "Proceedings of the 11th International Confernce of Ethiopian Studies. ,P.P. 61-70. Institution of Ethiopian Studies, A.A..

Emana Beyene. (2015). «Historical Documentation & Thematic Analysis of Waqeffannaa Religion & Song Among Tuulamaa Oromo.» PhD Dissertation, University of A.A.U.

Fetterman, M. David (2010). **Ethnography Step- by- step (3rd ed.)** Los Angeles: Applied Social Research Methods Series, Volume 17 SAGE.

Fille Jalleta. (2015).«Documentation of Folk Law & Description of Grammatical sketch of the Macca Oromo.» PhD Dissertation, University of A.A.U.

Garada Rabindra. (2015)."Dynamics of Macro-Sociological Theories: A Critical Reflection in Indian Context." IOSR Journal Of Humanities & Social Science (IOSR-JHSS) Volume 20, Issue 4,PP 61-70.

Hinnant, John.(1977). "The Gada System of the Guji of Southern Ethiopia" PhD Dissertation, University of Chicago.

_________.(1981). "Guji Affinity & Case of A Conflictful Marriage." Presented at the ‹Oromo kinship & Marriage› Conference, Manchester University, England, Spring,

Hussein, Bedru. (2002.). «Contextualization of the Gospel» Among the Oromo Tribe of the Estern Wollegga Region: The Mesrete kristos Church Experience Mission Focus: Annual Review, Volume10.

Lewis,Herbert.(1970). "Kud'arfan: A multi-functional Institution Among the western Galla" In proceedings of the 3rd International conference of Ethiopian Studies.AA.I.E.S.

Meseret Abaye.(1995). "Qaallu as a dispute setting institution." Among Oromo with Specific Reference to Macca Tuulama.(Un pub.) A.A.U. BA. Thesis in Low.

Paul,C.(1986)."Recent Developments in the Functionalist Approach to Change." The University of Akron.Vol.15 No. 5.

Prown, J. David.(1982). "Mind in Matter; An Introduction to Material Culture Theory and Method."Winterthur Portfolio. Vol,17 No. 1. pp. 1-19

Song, Sarah. (2007). "The subject of Multiculturalism: Culture, Religion, Language, Ethnicity, and Race?." Law and Political Science. University of California.Berkeley Draft for Presentation at the Stanford Political Theory Workshop.

Sosis, R., & C. S. Alcorta. (2005). «Ritual, Emotion, and Sacred Symbols: The Evolution of Religion as an Adaptive Complex.»Vol.16, No.4, pp. 323-359.

Tadesse Berisso.(1994). "Warfare Among the Guji- Oromo of Southern Ethiopia." Proceeding of 11th International Conference of Ethiopian Studies. A.A. IES, Vol. II Page 309-323.

_____________.(2004).«The Pride of the Guji-Oromo: An Essay on Cultural Contact and Self-Esteem.» JOS.Vol.11, No-1 and 2,

_____________.(2013).«The Riddles of the Number Ninein Guji-Oromo Culture» George F. McLean(ed.).Cultural Heritage & Contemporary Change Series II. Africa, Volume 15, P.p. 53-68. The Council for Research in Values & Philosophy.U.S.A.

Tedecha Gololcha. (1988). "The politico-Legal system of the Guji Oromo." BA Thesis in Law.School of Law A.A.U.

Tita Mekonin.(2003). "Erecha፡ Its Meaning and Significance in the Traditional Oromo Religion." (Unpublished). A.A.U. BA Thesis in Sociology and Social administration.

## 2. በአማርኛ የተጻፉ

### 2.1 መጻሕፍትና መጣጥፎች

ታቦር ዋሚ። 2006። *የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች*። አ.አ.፣ አርቲስትክ ማተሚያ ድርጅት።

ቴዎድሮስ ገብሬ። 2001። *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ-ጽሑፍ ንባብ።* አዲስ አበባ፣ አ.አ.ዩ. ፕሬስ።

አለማየሁ ኃይሌና ሌሎች።1998። *የኦሮሞ ታሪክ እስከ አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን*። ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤ አ.አ.፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

------------------። (2000)። **በገዳ ስርዓት፡ የቱለማ ኦሮሞ ፖለቲካ**። ኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ፈቃደ አዘዘ። (1991)። **የሥነቃል መምሪያ**፤አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።

### *2.2 የመመረቂያ ጽሑፎች*

ጥላሁን ኢቢዶ። (1982)። "የጌደኦ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ ዲማጽ፣ አ.አ.ዩ. (ያልታተመ)።

ጥላሁን ተሊላ። (2007)። "የቱለማ ኦሮሞ "መርሣ" ወቅቶች ፎክሎር አውዳዊ ጥናት" ለአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አ.አ.ዩ.

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ። *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ*። ነሐሰ 15/ 1987 ዓ.ም. አንደኛ ዓመት፣ ቁጥር-1፣ አዲስ አበባ።

## 3.በአፋን ኦሮሞ የተጻፉ

### 3.1. መጻሕፍትና መጣጥፎች

Alamaayyoo fi Kan biroo. (1999). **Sirna Gadaa: Siyaasaa Oromoo Tuulamaa.** Biiroo Aadaafi Tuuriizimii Oromiyaa, Mana Maxxansa Biraaninna.

Addunyaa Barkeessaa. (2011). **Akkamtaa: Yaadrimee Qorannoo Hujoo.** Finfinnee, Oromiyaa.

Danbalaa Elemaa. (2000). **Odeeffanoo Bu'uuraa kan Naannowwan oromoo Gujii.** Chamber Printing House.

Dirribii Damusee. (2009).**Ilaalcha Oromoo; Barroo Amantaa,Sirna Bulciisaa fi Seenaa Oromo.** D.G. Printing & Publishing Enterprise. Finfinnee.

Waajjira Aadaafi Turizimii Godina Gujii፡ **Baallii 74[ffaa]**. Maxxansa addaa, Gurr./ 2008.

WAWA, (2006). **Waaqeffannaa Barsiisa: Amantii Durjireessaa.** Jildii I,lakk.1.

### 3.2. የመመረቂያ ጽሑፎች

Imaanaa Bayyanaa. (2007). "Qaaccessa Qabiyyee Faaruu Amantii Duudhaa Oromoo Naannoo Shawaa." Afaan Oromoofi Ogbarruun. Waraqaa Eebbaa MA. (kan hin maxxanfamne). Yuniversiitii Addisaabaa.

Zlaaalam Abbabaa. (2000). "Sirna Gaa'laafi Moggaasa Qaalluu Oromoo Gujii." Afaan Oromoofi Ogbarruun.Waraqaa Eebbaa MA., (kan hin maxxanfamne). Yuniversiitii Addisaabaa.

# አባሪዎች

## አባሪ-አንድ

### ዋና ዋና የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | አድራሻ | ሥራና የት/ደረጃ | በጥናቱ ውስጥ ያላቸው ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሄሌሎ ሞኮና | ሴ | 54 | አባያ ወረዳ፣ ካላልቱ ቀበሌ | የቤት እመቤት፣ አልተማሩም | በቃሉ ተቋም የሴቶችን ድርሻ በመግለጽና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 2 | ሀጂ መሀመድ ጅብሪል | ወ | 80 | ም/ሀረርጌ (ድሬዳዋ) | የሃይማኖት አባት፣ 10ኛ ክፍል | ስለባህላዊ ዳኝነትና ገዳ ስርዓት ከታዘቡት ተነስተው መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ አንድ ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 3 | መሀመድ አማን | ወ | 52 | ም/ሀረርጌ (ድሬዳዋ) | 8ኛ ክፍል | ስለገዳ ስርዓት ከታዘቡት ተነስተው በማነጻጸር መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ አንድ ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 4 | መሀመድ አሊማያ | ወ | 75 | ም/ሀረርጌ (ድሬዳዋ) | 6ኛ ክፍል | ስለባህላዊ ዳኝነትና ገዳ ስርዓት ከታዘቡት ተነስተው መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ አንድ ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 5 | ሚጁ ባካሩ | ሴ | 59 | ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | የቀድሞ ሀዳ አምባ፣ አልተማሩም | ስለቃሉ ሚስት ተግባራት መረጃ የሰጡ |
| 6 | ሞና ጎዳና | ወ | 66 | ዋደራ ወረዳ ነዋሪ | በአሁን ደረጃ በዩባ እርከን ላይ የሚገኙ | ስለገዳ ስልጣን ሽግግር፣ ስለ አዋጅ ነገራ፣ ስለኮንቶማና ዳሪሙ አከፋፈል በበቂ ሁኔታ መረጃ የሰጡ |
| 7 | ሞኮና ናጋአ | ወ | 75 | ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | ገበሬ፣ መሰረተ ትምህርት | የቃሉ አጎትና የቅርብ አማካሪ ሲሆኑ፣ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ነበሩ፡፡ ባጠቃላይ ስለቃሉና |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የተከታተሉ | በተቋሙ የሚከወኑ ከበራዎችንና ሂደታቸውን በዝርዝር ያሰረዱና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው። |
| 8 | ሳንባቱ በዳዳ | ሴ | 30 | ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | 8ኛ ክፍል፣ የቤት እመቤት | ቃሉ በተራራዎች ላይ በመውጣት መስዋት እንደሚያቀርቡና የተሳታፊዎቹን መጠን በተመለከተ ከምታውቀው የገለጸች። |
| 9 | ረጋቱ በሪሶ | ሴ | 45 | ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | የቃሉ እናት (ሀዳ ኦዳ)፣ አልተማሩም | ስለሀዳ አንባ የስራ ድርሻ፣ስለቃሉ ተግባርና በሂሮ ስለሚደረገው መስዋዕትና የክዋኔውን ሂደት በተመለከተ መረጃ የሰጡ። |
| 10 | ሮባ ኤሌማ | ወ | 70 | አባያ ወረዳ፣ ሚኤሳ ቀ/ገ/ማ | ገበሬ፣ መሰረተ ትምህርት የተከታተሉ | የጉጂ ኦሮሞ ባህላዊ ምግብ ውስጥ ስለ ቡና ቃላ ጥቅም ያሰረዱ። |
| 11 | ቃባሌ ጃልዴሳ | ሴ | 32 | የዱግዳ ዳዋ ወረዳ ነዋሪ | ሀዳ ቦላ የነበሩና አልተማሩም | ስለ ጉጂ ኦሮሞ ቁሳዊ ባህል በከፊል መረጃ የሰጡ። |
| 12 | በሪሶ ጃልዴሳ | ወ | 54 | የዱግዳ ዳዋ ወረዳ ነዋሪ | በዶሪ የእርከን ደረጃ ያሉ፣ አልተማሩም | ስለ ጉቱ ጉዞ፣ ስለቁንቢ አወሳሰድ ስርዓትና ሂደቱ መረጃ የሰጡ። |
| 13 | ባሊ ጃርሶ | ወ | 74 | የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | በሉባ ደረጃ የሚገኙ፣ አልተማሩም | በግል ከሰጡት መረጃዎች በተጨማሪ በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ ተሳትፏል፣ ስለሞራ አንባቢ፣ ስለሁሉቃ፣ ስለቁንቢና የገዳ ስልጣን ሽግግር ከበራ መረጃ የሰጡ። |
| 14 | ባሾ ሮባ | ሴ | 35 | በአባያ ወረዳ፣ የሀሴ ጎላ ነዋሪ | የቤት እመቤት፣ አልተማሩም | ሴቶች በቃሉ ከበራዎች ላይ ያላቸውን ሚና የገለጸች። |
| 15 | ብርሃኑ ንጉሴ | ወ | 45 | ቦሬ ወረዳ ቦሬ ከተማ ነዋሪ | የቦሬ ወረዳ የቀድሞ ባህልና | ስለጎንዶሮ ዓይነቶች፣ ፋይዳዎቻቸው፣ ስለሞራ አንባቢና ስለሁሉቃ መረጃ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ቱሪዝም ጽ/ቤት ሃላፊ የነበሩ | የሰጡ |
| 15 | ቦሩ ሚጣ | ወ | 80 | የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | ባሱራ፣አልተ ማሩም | ስለባሱራ እርከንና የስራ ድርሻ ገለጻ ያደረገና በቡድን ውይይት ላይ የተሳተፈ፡፡ |
| 16 | ታከለ አብዲሳ | ወ | 62 | ም/ሀረርጌ (ድሬዳዋ) | የመንግስት ሰራተኛ | ስለገዳ ማንሰራራትና የስልጣን ሽግግር መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ አንድ ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 17 | ታደሰ ደንቦባ | ወ | 30 | አባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | ተማሪ፣ የገዳ ደንቦባ ጉሚ ልጅ | ስለገዳ ተግባራት በቡድን ውይይት ላይ መረጃ በመስጠት የተሳተፈና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፈ ነው፡፡ |
| 18 | አለማየሁ አድማሱ | ወ | 40 | አባያ ወረዳ፣ ጓንጓ ከተማ ነዋሪ | 12+2፣የመን ግስት ሰራተኛ | ስለፋጭ ከበራ ሂደትና ፋይዳው መረጃ የሰጡ፡፡ |
| 19 | አባ ሚኤ | ወ | 76 | ዱግዳ ዳዋ ወረዳ ነዋሪ | በዩባ ደረጃ ላይ ያሉ፣ አልተማሩም | ስለዩባና ባሱራ፣ ስለሙዳ ጉዞ መረጃ የሰጡ፡፡ |
| 20 | አባባ ቃሉ ቶቴ | ወ | 50 | ቆቲ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | የቃሉ ቶቴ ልጅ | ስለቃሉና የቁንቢ አወሳሰድ ሂደት፣ስለቃሉ መስፈርቶች፣ ስለተቋሙ ለውጥና ቀጣይነት ላይ ያለውንና የነበረውን ሁኔታ የገለጹና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው፡፡ |
| 21 | አዱላ ሀላከ | ወ | 80 | ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | አልተማሩም፣ ገበሬ | ስለቃሉ ጋብቻ፣ ለቃሉ የሚሰጡ ስጦታዎች፣ |
| 22 | አዱላ ዋታ | ወ | 57 | ቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | አልተማሩም፣ ገበሬ | ስለገዳና የተለያዩ ሃይማኖቶች ያለውን ግንኙነት በተመለከተ መረጃ የሰጡ፡፡ |
| 23 | ኡዴሳ ዲራሞ | ወ | 36 | የአባያ ወረዳ፣ ቡናታ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | አልተማሩም፣ ገበሬ | ስለፋጭ፣ ስለሁሉቃ፣ስለ መስዋዕት ማቅረብና ጎንዶሮ ከበራዎች መረጃ የሰጡ፡፡ |
| 24 | ወርቁ ካባባ | ወ | 54 | የአባያ | 8ኛ ክፍል፣ | ስለቀጣይነትና ለውጥ ላይ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወረዳ፣ካላል ቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | ገበሬ | በቡድን ውይይት ላይ የተሳተፉ:: |
| 25 | ዘላለም በቀለ | ወ | 32 | አባያ ወረዳ፣ ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | 10ኛ ክፍል የቀበሌው ማናጀር | በቀበሌያቸው ዙሪያ ስላሉ መንፈሳዊ ስፍራዎች አስመልክቶ መረጃ በመስጠትና ለወደፊት ጥበቃውን እንደሚያጠናክሩ ያሰረዱ ናቸው:: |
| 26 | ደሳለኝ ሆርዶፋ | ወ | 40 | በአባያ ወረዳ፣የጓንጓ ከተማ ነዋሪ | የአባያ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኛ፣12+2 | ስለቃሉ ተቋምና መስዋዕት ማቅረቢያ መንፈሳዊ ስፍራዎች አስመልክቶ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝና በጽ/ቤታቸው ያሉ መረጃዎች በመሳየት የተባበሩኝ፣ |
| 27 | ዲኮ ሚጁ | ሴ | 55 | አባያ ወረዳ፣ የካላልቱ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ | የቤት እመቤት | ስለቃሉ ተቋም ፋይዳና በአሁን ወቅት በቃሉ በኩል ያሉ ተግዳሮቶችን፣በቃሉ ተቋም የነበረውንና አሁን ያለውን ተግባራት በንጽጽር ማብራሪያ በመስጠት |
| 28 | ዳራሮ ሆርዶፋ | ወ | 77 | አባያ ወረዳ፣ የካላልቱ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ | ገበሬ፣ አልተማሩም | ስለጉዲ ማህበረሰብ የጋብቻ ሁኔታ መረጃ የሰጡና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው:: |
| 29 | ገላኖ ቦሩ | ሴ | 45 | የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | ሀዳ ቦላ | ስለቁሳዊ ባህል እና በመንፈሳዊ ጉዞው ውስጥ የሴቶችን ሚና በተመለከተ መረጃ የሰጡ |
| 30 | ገዳ ዋቆ ዱቤ | ወ | 70 | የቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ | የኡራጋ አባገዳ የነበሩ | ስለጉቱ መንፈሳዊ ጉዞና ቁንቢ አወሳሰድ ሂደት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ፣ |
| 31 | ገዳ ሀልቻዬ ዳራ | ወ | 65 | አባያ ወረዳ፣ የደበቃ ደቦቤሳ ቀ/ገ/ማ/ ነዋሪ | የዌስቱ ጎሳ አባገዳ | ስለቁሳዊ ባህል፣ስለሂሮ ከበራ ሂደትና ስለቃሉ ተቋም ጥቅም መረጃ በመስጠትና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው:: |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 37 | ጎባና ቶቴ | ወ | 59 | የአባያ ወረዳ ካላልቱ ቀ/ገ/ማ ነዋሪ | ገበሬ፣ አልተማሩም | ስለጉቱ መንፈሳዊ ጉዞ በተመለከተ እነማን እንደሚሄዱና ሂደቱም ምን እንደሚመስል በመግለጽ የተባበሩና በቡድን ውይይት ላይ ሦስት ጊዜ የተሳተፉ ናቸው። |
| 38 | ፍቅሩ ወ/ሰንበት | ወ | 36 | የጓንጓ ከተማ ነዋሪ | 12+4፣ የአባያ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኛ | ስለቃሉ ጋብቻ ክብራ በተመለከተ የማህበረሰቡን ተሳትፎ አስመልክቶ መረጃ በመስጠት የተባበሩ፣ ስለቃሉ ተግባራት የቀድሞውና የአሁኑን በማነፃፀር የገለጹልኝ። |

## አባሪ-ሁለት

ከቃለመጠይቁ በፊት ለቃለመጠይቁ የሚሆኑ ሰዎች ተመርጠዋል። በመቀጠል የሚመቻቸውን ሰዓት አብሮ በመወያየት ቀጠሮ ለመያዝ ተሞክሯል። ስለስራው ባጭሩ ለማስረዳት ዝግጅት ተደርጓል።

**ለጥናቱ መረጃ ማሰበሰቢያነት የቀረበ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች**

**_ቃለመጠይቁን የሰጠው አካል ሙሉ መረጃ፡-_**

1. ሙሉ ስም ________________________
2. ዕድሜ ___________________________
3. ቀበሌ ___________________________
4. የስራ ድርሻ________________________
5. ቀን ____________________________

በቅድሚያ ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለዚህ ቃለ-መጠይቅ ፍቃደኛ ሆነው በመገኘትዎ ከልብ አመሠግናለሁ። በመቀጠል እነዚህ ጥያቄዎች ለዶክትሬት ዲግሪ የማሟያ ጥናት አገልግሎት ብቻ የሚወሉ በመሆናቸው የሚሰጡኝ መረጃ በእውነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ።

1. ላንተ/ላንቺ/ለእርሶ ቃሉ ምንድነው?
2. የቃሉ መማክርት አባላት እነማናቸው? ተግባራቸውስ ምን ምንድነው?
3. የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ምን ምንድናቸው? ለምን ይከበራሉ?
4. እነዚህ የቃሉ ከበራዎች ከሰሙትና ካዩት ላይ በመነሳት ምን ምን ለውጦችን አስተውለዋል?
5. የጉቱ ጉዞ ማለት ምን ማለት ነው? ፋይዳውስ ምንድነው?
6. በቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ውስጥ መስዋዕት ለምን ይቀርባል? የክዋኔው ተምሳሌት ምን ያመለክታል?

7. ቃሉ ለእግዚኣብሔር መስዋዕት የሚያቀርበው መቼ ነው?፣ የት ነው?፣ ለምን ያቀርባል?፣ ከማን ጋር ያቀርባል? የሚሉትን በማቅረብ የተገኘውን መረጃ በመቅረጸ ድምጽ፣ በማስታወሻ ይያዛል፡፡
8. በመጨረሻም ከሚሰጡት መልስ ላይ በመንተራስ ማስታወሻ በመያዝ ማብራሪያ የሚፈልጉ ምላሾችን መልሶ በመጠየቅ ማስታወሻ ይያዛል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** በተራ ቁጥር 5 እና 6 ላይ የሚገኙ ጥያቄዎች ባህሉን በደንብ ለሚያውቁ የሀገር ሽማግሌዎች እና የባህል ኤክስፐርት (ባለሙያዎች) የቀረቡ ሲሆኑ የተቀሩት ሁሉንም ተሳታፊዎች የሚመለከቱ ናቸው።

Af-gaaffiin dura namoota af-gaaffiin isaaniif taasifamu filatamaneeru. Itti aansuun, Yeroo isaaniif mijatu mari'achuun walii beellamuuf yaalameera. Dhimma af-gaaffichaa gabaaban ibsuuf qophi'ii taasifamee jira.

Gaaffilee af-gaaffii odeeffannoo qorannichaaf ittiin funaanuuf dhiyaate

<u>Odeeffannoo ragaa kenitootaa፡-</u>

1. Maqaa guutuu ____________________
2. Umrii ___________________________
3. Ganda __________________________
4. Gahee hojii ____________________
5. Guyyaa__________________________

Hundaan dura af-gaaffii kanaaf yeroo hojii keessan wereeguudhan asitti naaf argamuu kessaniif guddoo isin galateeffadha. Af-gaaffiin kun qo'annoo Doktarummaa gutachuuf qofa kan oolu ta'uu isaa ibsaa, ragaan naaf kennamu dhugaarratti akka hundaa'u kabajaan isin gaafadha.

1. Qaalluu jechuun si'iif/ isiniif maal jechuudha?
2. Miseensonni gumii Qaalluu eenyufaadha? Gaheen isaan maal maalfaadha?
3. Jilli Qaalluu maal maalfaadha? Maaliif jilata?
4. Argaafi dhageetti keessanirran kaatanee Jila kanneen irratti jijjiirama hubatane jiraa?
5. Godaansa gutuu jechuun maal? Faayidaan isaa maal?
6. Qaalluun jila isaarratti maaliif falata? Fakkeenyummaan isaa maal agarsiisa?
7. Qaalluun yoom yoom fala? Eessatti fala? maaliif fala? eenyufaan wal fala? ragaalee jedhanu Teep-rikerderiini woraabuufi yaadannoo qabachuun walitti qabama.

8. Dhumarrati deebii af-gaafficharratti hunda'uun wantoota ibsa barbaadanu yaadannoo qabachuun kan ibsa dabalata barbaadanu gaafachuun deebii isaa yaadannoo ni qabama.

**Hubachiisa:-** Gaffileen lakkoofsa 5 fi 6 irraatti jiran jaarsoolee aadaa beekanii fi ogeessoota aadaatiif kan dhiyaatan yoo ta'an kan hafan hirmaattoota hunduma kan ilaallataniidha.

## አባሪ-ሦስት

<u>የቡድን ተኮር ውይይት ጥያቄዎች</u>

1. የጉጂ ኦሮሞ ቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ቀደም ካሉ ስርዓቶች አንስቶ እስካሁን ባለው ውስጥ ያሉት ለውጦች ምን ምንድናቸው? አሁንስ ምን ደረጃ ላይ ይገናሉ?
2. የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎች እየተዳከመ ነው ወይስ እየዳበረ እየሄደ ነው ትላላችሁ? ምክንያታችሁ ምን ምንድናቸው?
3. የቃሉና የገዳ ስርዓት የዋቄፋታ ሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞዎች ብቻ ነው ትላላችሁ? ለምን?

ከሁሉም በፊት ለዚህ ቡድን ተኮር ውይይት እዚህ ስለተገኛችሁልኝ ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። እዚህ ቡድን ተኮር ውይይት ላይ የቀረቡ ጥያቄዎችም ሆኑ የሚሰጡ መልሶችና አስተያየቶች ለዶክትሬት ዲግሪ የማሟያ ጥናት አገልግሎት ብቻ የሚውሉ በመሆናቸው፤ ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ በመስጠትም ሆነ አስተያየት በማቅረብ ንቁ ተሳትፎ እንዲታደርጉ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ።

አባሪ-አራት

**Jaarsummaa**

Jaarsummaa jechuun maali?yaada jedhurratti Obboo Mokkonnaa, Obboo Roobaa Elemaafi gadaa Halchaayyee wal marii taasifame

Guyyaa 10/12/2007,Obbo Mokkonnaa Naga'oo, umriin woggaa 75, Qootii (Galma)fiGadaa Halchaayyee Daarraa, umrii 65, Ganda Dabaqqaa Daboobeessa yoo ta'anu, lachuu Galma abbaa Qaalluu keessatti yeroo baay'ee waliin hojjatu. Kanaafuu,waa'ee jaarsummaa ilaalchisee muuxannoo guddaa akka qabanu isaan irraan hubaachuuf danda'eera. Kanaafuu, Jaarsummaa jechuun maali?gaaffii jedhu isaaniifi dhiyeese.Isaanisi: dursanii,

Obboo Mokkonnaa:- Jaarsummaa jechuun akka aadaa keenyaatti adeemsa rakkoo hawaasa keessatti uumameef manguddoota naannoo sanitti jiranuu karaa ittiin hiikaniidha. Amma akka fkn, name mana tokko keessatti jiraatu, ykn immoo,olla wal sababa adda addaatiin walitti bu'uu danda'a. Dhimma kana mana murtiitti hingahin dura ykn immoo, erga gaheen booda kan balleessa abbaa dhiibban itti gaheef gama aadaatiin waan isaaf ni madaala kan jedhame akka muru taasifamee araarri bu'a.

Obboo Halchaayyee:-dhimmi Jaarsummaa kun gama aadaa Gujiitti nami tokko cadhi jedhee hin himatu. Haalli ittiin himatu jira.Innisi, dursee abbuma isa yakke san "abboo ani si himadhaara?" jedhee gaafata. Deebin isaa:-

1. Ana hin himatin balleessa kiyya anuu beekera si kiisa. Kan jedhu ta'uu danda'a,
2. Lafti yoo dhiyeeru taanaan lafti olii gadi jedha.sababi isaas, halkan hayyuu hin gaafatanu name bishaan wayii fudhate waan jaarsi jedhu fudhachuu dhiisuu danda'a,
3. Erga gaaffin eegalameen booda, himadhu; maal balleessan kiyya jedhee dhimmi ka'u sun jabaa yoo ta'ee isa rakkistu taanaan, ani abbaa qaba. Jedha.Yeroosan, Jaarsummaa abbaa kee fidi; meerre abbaan kee?jedhu. Karaa deemeera jedha. Jaarsoliin akka tole jedhee dhimmichi ilaalamu yoo dhiibba itti uumanille nama abba qabu; abbaattu gaafatama jechuun mormee dubbiin akka bultu taasisu.Yeroo ammaa namu dubbii baratee xinnoo rakkisaara malee, dhimmi jaarsi dadhbu hinjiru.Tasa dimma ulfaate yoo ta'e galma abbaa Qaalluutti dhuma jedhane.

## አባሪ-አምስት

ከ1424-2015 ስልጣን ላይ የነበሩ የገዳ አባቶች ስም ዝርዝር

| የገዳ ስልጣን ዙር | የገዳው ስም | የስልጣን ዘመኑ | የገዳው መደብ ስም |
|---|---|---|---|
| 1 | አባ ገዳ ጇጄ ጎባ | 1424-1431 | ሙዳና |
| 2 | // // ጇሎ ወላጎ | 1432-1439 | ሀልቺሳ |
| 3 | // // ጇሩ ኡታ | 1440-1447 | ዳላና(dhallana) |
| 4 | // // ጉሉ ጋራሮ | 1448-1455 | ሀርሙፋ |
| 5 | // // ሄባኑ ጃልዶ | 1456-1463 | ሮባሌ |
| 6 | // // ቢላ ማናኮ | 1464-1471 | ሙዳና |
| 7 | // // ባሪሶ ጉሚ | 1472-1479 | ሀልቺሳ |
| 8 | // // አዶላ አኖሌ | 1480-1487 | ዳላና |
| 9 | // // ጎቡ ሻሮ | 1488-1495 | ሀርሙፋ |
| 10 | // // ጎሉ ሱባ | 1496-1503 | ሮባሌ |
| 11 | // // ጭሪ ጋሎ | 1504-1511 | ሙዳና |
| 12 | // // ቡርጭሳ ሻኩ | 1512-1519 | ሀልቺሳ |
| 13 | // // አጋ ካላቻ | 1520-1527 | ዳላና |
| 14 | // // ጇሎ ቢዶ | 1528-1535 | ሀርሙፋ |
| 15 | // // ጋናሌ ሮቤ | 1536-1543 | ሮባሌ |
| 16 | // // ዱባ አዲ | 1544-1551 | ሙዳና |
| 17 | // // አቦ ራሶ | 1552-1559 | ሀልቺሳ |
| 18 | // // ሀላኬ ሉሌ | 1560-1567 | ዳላና |
| 19 | // // ጎቡ ዳዬ | 1568-1575 | ሀርሙፋ |
| 20 | // // ጋናሌ ሎሌ | 1576-1583 | ሮባሌ |
| 21 | // // ቃናሾ አኖሌ | 1584-1591 | ሙዳና |
| 22 | // // ጃቦ ስቡ | 1592-1599 | ሀልቺሳ |
| 23 | // // ቃልቃልቻ ቱካሾ | 1600-1607 | ዳላና |
| 24 | // // ጎሎልቻ ሻሩ | 1608-1615 | ሀርሙፋ |
| 25 | // // አባ ዶላ | 1616-1623 | ሮባሌ |
| 26 | // // አጋ ሳቆ | 1624-1631 | ሙዳና |
| 27 | // // ጇሎ ባንሳ | 1632-1639 | ሀልቺሳ |
| 28 | // // ሀሮ ሾቴ | 1640-1647 | ዳላና |
| 29 | // // ጃርሶ ዱጎ | 1648-1655 | ሀርሙፋ |
| 30 | // // ኡሾ ዋሬ | 1656-1663 | ሮባሌ |
| 31 | // // ጋናሌ ዳናባላ | 1664-1671 | ሙዳና |
| 32 | // // ጎዳና አጋ | 1672-1679 | ሀልቺሳ |
| 33 | // // ጎዳሬ ቦኮ | 1680-1687 | ዳላና |
| 34 | // // ጃርሶ ሶሬ | 1688-1695 | ሀርሙፋ |
| 35 | // // አጋ ቡዴ | 1696-1703 | ሮባሌ |
| 36 | // // ቱኬ ሽፋ | 1704-1711 | ሙዳና |
| 37 | // // ጇሎ ባዳ (Badhaa) | 1712-1719 | ሀልቺሳ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 38 | // // አጋ ዋሬ | 1720-1727 | ዳላና |
| 39 | // // ብራ ሱኬ | 1728-1735 | ሀርሙፋ |
| 40 | // // ጂሎ ጡሎ | 1736-1743 | ሮባሌ |
| 41 | // // ባላኮ ጂሎ | 1744-1751 | ሙዳና |
| 42 | // // ቡዱሾ ሀላኬ | 1752-1759 | ሀልቺሳ |
| 43 | // // ሶራ ቡሉልታ | 1760-1767 | ዳላና |
| 44 | // // እጁ ጋላቤ | 1768-1775 | ሀርሙፋ |
| 45 | // // ሱሮ ጨኮ | 1776-1783 | ሮባሌ |
| 46 | // // ጂሎ ዋሬ | 1784-1791 | ሙዳና |
| 47 | // // ጋልቹ ኬማ | 1792-1799 | ሀልቺሳ |
| 48 | // // ሚደ ኒቲ (Miidhee) | 1800-1807 | ዳላና |
| 49 | // // ዳዳ ኩራ | 1808-1815 | ሀርሙፋ |
| 50 | // // ጥሎ ሾሌ | 1816-1823 | ሮባሌ |
| 51 | // // ቡኖ ዳኤ (Dhaa'ee) | 1824-1831 | ሙዳና |
| 52 | // // ዳሼ ሀላኬ | 1832-1839 | ሀልቺሳ |
| 53 | // // ቡኜ ቦሩ | 1840-1847 | ዳላና |
| 54 | // // አጋ ካላቻ | 1848-1855 | ሀርሙፋ |
| 55 | // // አዱላ ካራ | 1856-1863 | ሮባሌ |
| 56 | // // ዋቆ ጋራሮ | 1864-1871 | ሙዳና |
| 57 | // // ብራ ጩቂ | 1872-1879 | ሀልቺሳ |
| 58 | // // አኖሌ ባዳ (Badhaa) | 1880-1887 | ዳላና |
| 59 | // // ሮባ ቦሩ | 1888-1895 | ሀርሙፋ |
| 60 | // // ጂሎ ከንዶ (Kendhoo) | 1896-1903 | ሮባሌ |
| 61 | // // ጋልቹ ጩሩቆ | 1904-1911 | ሙዳና |
| 62 | // // ጂሎ ቦኮ | 1912-1919 | ሀልቺሳ |
| 63 | // // ጂሎ ሳዬ | 1920-1927 | ዳላና |
| 64 | // // አጋ አዲ | 1928-1935 | ሀርሙፋ |
| 65 | // // ኡሾ ጂሎ | 1936-1943 | ሮባሌ |
| 66 | // // ቱኬ ጉዬ | 1944-1951 | ሙዳና |
| 67 | // // ጂሎ ሚጠ | 1952-1959 | ሀልቺሳ |
| 68 | // // አዶላ ጂሎ | 1960-1967 | ዳላና |
| 69 | // // ጊርጃ ጂሎ | 1968-1975 | ሀርሙፋ |
| 70 | // // አዶላ አጋ | 1976-1983 | ሮባሌ |
| 71 | // // ጎዳና ካታ | 1984-1991 | ሙዳና |
| 72 | // // አጋ ጤንጣኖ | 1992-1999 | ሀልቺሳ |
| 73 | // // ዋቆ ዱቤ | 2000-2007 | ዳላና |
| 74 | // // ጂሎ ማንዶ (Maandhoo) | 2008-2015 | ሀርሙፋ |

**ምንጭ**፡-Waajjira Aadaafi Turizimii Godina Gujii፡Baallii 74[ffaa]. Maxxansa addaa,Gurr./2008.

አባሪ-ስድስት

Dhuftee Qaalluu

Yoona akka dhage'aa guddannetti Qaalluun Gujii Waaqarraan gadi bu'e.Yemmuu gadi bu'u waan akka sabbata waaqaa jiruun maramee irraangadee hiikamaa isa erga lafa geessiseen booda gara waaqatti maramee deebi'e. Iddoon itti gadi bu'e godina Gujiitti, aanaa Adoola keessatti lafa Obbaa(obbittii) jedhama. Yeroo sana Qaalluun ruufaan maramee, qumbiifi kallacha waliin bu'e. Akkaataa kanaan akkuma bu'een, dursanii nama gosa waajjituu ta'anettuu isa argane. Maalummaa isaa baruuf itti siiqane; Sodaachatuma irra maraa erga turaneen booda hawaasa olla sani jirutti himane jedhama. Namoota sana keessan name lamaan itti siqee yoo ilaalanu ruufa keessa namni akka jiru hubatane. Nami kuni kallacha ofirratti qaba ture. Ruufa sana keessatti Qaalluun cinaa qumbiin marsee jira ture. Gujiin olla sanii itti dhiyaatee; "Nami kuni woyyuudha."Jechuun dubbisuuf yaalani. Inni garuu nama tokkoofille deebii hin laanne ture. Nami adda addaa akka dubbisu yaalameeruun nami tokkolle isa dubbisuu hindandeenye.Dhumaratti, intalti durba gosa galalchaa taatu tokko yoo dhuftu Qaalluun itti seeqate.Intalti durba geese turte.Ishiinissi, "gara manaatti haagallu?" jettee isa gaafate. Yeroo sana innisi ishii wal dubbachuu eegale. "Ani mana namaa hin galu.Galma naaf ijaaraa." jedhe.Gujiin walitti dhufee galma ijaareef.Itillee afanii teesisane. Aannaan buchumaan(qodaan) yoo itti kennanu; fudhachuu dide. Boodarratti, Okoleen akka isaaf gumaachanu isaanitti hime.Isaanissi waanuma jedhame raawwatane. Gumaachi Qaalluuf taasifamu dhufteen isaa kanumarraan madde jedhama.Intalti durba gosa galalchaa sani isuma bira dhiisanee deemane. Achiin ijooleessi horatane. Dhugaani jirusi kanuma Jechuun naaf ibsan.

Qaalluun tokko umriin angoo isaa hagam?gaaffii jedhuuf Obboo Mokkonnaan yemmuu deebisanu "Qaalluun tokko umrii isaa guutuu hojjata. Hanaga waaqni si gaheera jedhutti; jechuun koo hanaga hanachufa liqiinfatutti ni tajaajila. Qaalluun Yoo hanachufa liqimse ayyaaan isarratti bule jiru garuu nijiraata; hin du'u.Kanaafuu, ijoollee isaa keessaan kan ulaagaa barbaachisan kan guutu yoo jiraate filuudhaan ni moggaafama. "Jechuun deebisane. Itti aansuun, ulaagalee qaalluu moggafamuuf barbaachisan aakkaata armaan gaditti ibsaniiru.(Obboo Mokkonnaa Naga'oo, umriin woggaa 75, Aanaa Wonagoo, Ganda Qootii, Guyyaa 1/12/2006 A.L.I)

durba gosa galalchaa sani isuma bira dhiisanee deemane. Achiin ijooleessi horatane. Dhugaani jirusi kanuma Jechuun naaf ibsan.

Qaalluun tokko umriin angoo isaa hagam?gaaffii jedhuuf Obboo Mokkonnaan yemmuu deebisanu "Qaalluun tokko umrii isaa guutuu hojjata. Hanaga waaqni si gaheera jedhutti; jechuun koo hanaga hanachufa liqiinfatutti ni tajaajila. Qaalluun Yoo hanachufa liqimse ayyaaan isarratti bule jiru garuu nijiraata; hin du'u.Kanaafuu, ijoollee isaa keessaan kan ulaagaa barbaachisan kan guutu yoo jiraate filuudhaan ni moggaafama. "Jechuun deebisane. Itti aansuun, ulaagalee qaalluu moggafamuuf barbaachisan aakkaata armaan gaditti ibsaniiru.(Obboo Mokkonnaa Naga'oo, umriin woggaa 75, Aanaa Wonagoo, Ganda Qootii, Guyyaa 1/12/2006 A.L.I)

Qaalluun tokko Moggaafama ulaagaan barbaachisan maalfaadha?
"Qaalluun tokko Moggaafama ulaagaa barbaachisan hedduudhaa. Akkuma seerri durumarraan jalqabee kan argaa dhageettiin dhalootarraan gara dhalootaatti darbaa kan dhufe jiran, Isaanissi:

1. Ilma Qaalluurraan dhalate ta'uu qaba,
2. Ilmi kuni kan dhalate haadha manaa Qaalluu keessaan ishee dubartii gosa galalcharraan (haadha ambaarraan) kan dhalate ta'uu qaba,
3. Mil'uu (mul'ii) isaa ilaalchise kan ija hindabsine,
4. Qaamni isaa guutuu kan ta'e,
5. Harka bitaacha'aa kan hin taane,
6. Biduu kan hinqabaanne,
7. Goddaannisa kan hin qabaanne,
8. Kan ruufaan dhalate (kan ruufaan maramee kan dhalate),

   Yoo ta'nu, gama biraatiin, kan dhugaa dubbatu, nama karaa waaqaa akeeku, hawaasa isa jala bulu hunda ija tokkoon kan ilaalu ta'uu qaba.

Gama moggaasa Qaalluu yoo ilaalle bifa lamaan raawwatamuu danda'a.
1[ffaan,] gaa'elaafi moggaasi Qaalluu isa yeroo jalqabaaf kan raawwatamuu yoo ta'u,inni biroo immoo, ijoollee Qaalluu keessaan name moggaafamu yoo dhabame kan duratti gaa'ela raawwatan keessan yeroo filamu jira. Kanaafuu, namni moggaafamu kun gaa'ela duraan raawwatu sun akaakuu gaa'ela adda addaa ta'uu danda'a. Gama biraatiin immoo, dubartiin inni fuudhe sunissi gosti ishii adda addaafi saba adda addaarran ta'uu ni danda'a.
Ega ulaagaalee amma ibsamane kana kan guutu yoo hin jiraanne hoo maaltu raawwatama?
Obboo Mokkonnaa

«Obboleessi Qaalluu keessan kan ulaagaa guutu yoo jiraate isaan keessaan ni filama.»

Ega ulaagaalee amma ibsamane kana kan guutu yoo argame hoo maaltu raawwatama?

Obboo Mokkonnaa

«Ulaagaalee amma ibsamane kana ijoollichi jira taanaan woggaa kudhanittille moggaasuu ni danda'ma. Garuu bakka ijoollichi hinjiraanneetti nama guddaa jiranu keessaan nifilatama.

Sanaan booda moggaasa Qaalluuf ulaagaa guddoon gaa'ela raawwachuudha.»

Gaa'glli (fuudhi) Qaalluu Gujii Oromoo gaa'ela hawaasa Gujii biroorraan wanta adda taasisan jiru?

Obboo Mokkonnaa

«Garaagarummaa wanta hedduu qaba.Akkuma beektu fuudhi gosa adda addaattuu jira. Fkn, butin, addibaanaa, hawwadii dhaalaa/ sigabaafi kadhaadha. Kanneen keessan Qaalluun gaa'ela kan raawwatamuuf isa sirna Kadhaan kan raawwatamu saniidha.

Haalli adeemsi sirni kadhaa kuni hanga guyyaa fuudhaa jiru yoo ilaale iddoo hedduuti garaagarummaa jiru ilaaluu dandeenya. Isaanisi:

Inni jalqabaa durba Qaalluuf taatu Kaadhimachuu barbaachisa. Kaadhimachuuf immoo, durba filachuun, kadhaa (gaaffii), marii, gaa'ela (fuudha) ni raawwatama.

Akka fakkeenyaatti fudhannee gaa'ela abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo haa ilaallu. Abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo dura kan ture obboleessa keenya kan ture Qaalluu Saqoo Naga'oo jedhama. Abbaa Qaalluu Naga'oo Totteerraan dhalate.Guyyaa dhalate, ruufaan dhalate. Ulaagaalee hafanessi ni guuta ture. Garuu, Abbaa Qaalluu Naga'oo Totteen osoo tajaajilarra jiruu umriin isaa gaa'elaaf gahe.Akkuma aadaa keenyaatti fuusisane.Innissi, jiruu isaa eegale. Dubartii Gujii adda addaafi kan saba biraarran dabalee fuudheera. Dhumarratti,yoo abbaan Qaalluu 14ffaa'n yoo hancufa liqiimsu nama bulii hinqabne keessan ijoolleen ulaagaa guuttu keessan tokko ana ture. Abbaan keenya ,ana yaamee harka na qabee eebbise. Uummata akka bulchu bakka nabuuse. Ani garuu,imaanan kun ibidda; nama guba. Dhugaa dubbachuu qaba. Dubartii name biraa tarkaafate hin tarkaanfatu. Ardaa bulchuu sababoota kanaaf kan birootiin waan sodaadhuuf didadhe. Kanaafuu, akkuma aadaa kanaaan dura itti bulame namuma guddaa jiranu keessan kan ulaagaa guuttatu filama. Sababi isaasi waaqni ganamumaan waan isassi filatee; qopheeffateef ta'e.

Sanaan booda, name qaalloomu akka eenyummaa isaa beekameen,sirna moggaasaaf qaphiin eegale.Akkuma dura sitti hime abbaa baallii guutuu ta'uuf

wanti lama isa hafa ture. Inni tokko, gama amantaa duudhaafi aadaa Gujiitti durba gasa galalchaa keessaan gaa'ela raawwachuu isarraan eegama ture. Sababi isaasi, boru haadha ambaa kan taatu ishii waan ta'eef;cinaa isaatti kan faltu waan ishii taateef.Inni lammeessoon immoo, sirna moggaasa isaa raawwatamuu qaba ture. Kanaafuu,seera guuttachuuf durba gosa galalchaa erga fuusisneen booda akkuma aadaa ganamaatti guyyaa lammeessootti sirni moggaasi isaa raawwatame. Erga baallii guuttateen booda abbaan Qaalluu 15^ffaa ta'uun hanga guyyaa hancufa liqiimseen tajaajilaa turaniiru.

Asirratti wanta kaasuu barbaadee durba abbaa qaalluuf taatu filachuurraan kaasee hanga guyyaa fuudhaa inni galmaan gadi hinba'in dhimma jiru hunda fixanii kan fidadun abuyyaa (bakka abbaa) gadoota, kallootaafi manguddoota, obboleetti isaa taniiti.Baasiin fuudhaaf ba'ulle uummata Gujiitiin guuttama. Gumaachaa guyyaa fuudhaa jabillee dhibbaatamaan lakkawaman uummataaraan galaaf.

Itti aansuun kan iddoo fudhate immoo, isa Qaalluu 16^ffaa dha; abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo jedhama. Haadhotii manaa abbaa Qaalluu Saqoo keessan haadha ambaarraan kan dhalatee, ulaagaa barbaadamu sana kan guute isa waan ta'eef filatame.»(Obboo Mokkonnaa Naga'oo, umriin woggaa 75, Aanaa Wonagoo, Ganda Qootii, Guyyaa 12/11/2007 A.L.I)
Guyyaa darbe abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo Qaalluu 16^ffaa ta'anii akka filatamane ibsatanii dhaabbachiisne turre.Mee haala akkamiin moggaafamaneree?
Obboo Mokkonnaa
«Akkuma duratti dubadhetti abbaa Qaalluu Aagaa Saqoo waan akka qaalloomu kan filatameef inni guddaan waan ulaagaa gama aadaafi amantaa keenyaan taa'e sana waan guutuuf dargaggeesa yoo ta'elle waaqni waan isa qopheesseef isattuu filatame. Sababni isaasi,inni tokkoffaan inni kan dhalate hadhootii mana abbaan Qaalluu 15^ffaa hadha ambaarraan waan ta'eef.Gama biraatiin name qaalloomu gosa Gujii keessaan gosa obbituu keessan ta'a. sababini isaa Qaalluun Gujii inni jalqabaa yemmuu waaqarraan bu'u iddoon inni lafa bu'e sun "Obbaa" ykn "Obbitti" jedhama.Kanaafuu, gosti qaccee mana isarraan ba'ane Obbituu jedhamu. Sababa kanarran kan ka'e nami qaalloomu tokko gosaan Obbituu ta'uu qaba.Obbituun hundi gosa Qaalluu jedhamti; kabajasi qabdu.
Gama biraatiin dubartiin haadha ambaa taatu immoo,durba gosa galalchaarran waan taateef qabdi. Akkuma dhuftee Qaalluu Gujii keessatti akka kaaseetti; durbi Qaalluu isa yeroo jalqabaa haasofsitefi isaa wal galte waan gosa galalchaa taateef.Intalti sun durba geese turte.Achumaan waliin jiraachuu eegalane; ijoolleessi horatane.Baalliin isaasi gara ilmasaatti darbe. Haaluma kanaan ergasi,

baalliin abbaarran gara ilmaatti darbaa dadarbaa akka asiin gahe himteen waa'ee dhuftee Qaalluu keessatti ni himama.

-Faaydaani Dhaabbati (galmi) Qaalluu Gujii hawaasaaf qabu maalfaa jettu? Mee amma immoo, obboo Halchaayyerraan eegala.

-Obboo Halchaayyee "miti erga Obboo Mokkonnaan ibseen booda inninuu hin hafu malee yeroo sana itti dabala; Itti fuufaa isin."

Obboo Mokkonnaan «Tole kaa, dursinee waaqa haa kadhannu.

Ee waaqa nagaan nu bulchiteetta nagaan nu oolchi. Nu oolchi !

Faroo hamaa falafaltuu hamaa nurraa qabi. Nurraa qabi!

Ee muchaan kunillee waa'ee aadaa keenyaa qo'adha jedhuutti jira nu'uufi afaan ittin haasofnu, isaafi immoo, hojii isaa haa qajeelchu. Haa qajeelchu.

Waa'ee faaydaani galmi Qaalluu Gujii uummataaf qabu maalfaadha jedhee mitii? Abbaa gadaa Halchaayyee «Eeyyee! akkasuma jedhe.»

Obboo Mokkonnaan "Maalree, akkuma qaalluu kanniisaa kan oolmaa keenya, bulii keenya, horii keenya, maatiifi qa'ee keenanya akka naagaa argatu, kandhalate akka guddatu, kaguddate akka le'u iddaa falatufi jilatuudha. Waaqarraan iddoo araara kadhatuu dha. Galmi kan rakkate dhufee iddoo himatuu dha. Kan himatame immoo, dhufee iddoo dhaagaa baafatuudha.Galmi Qaalluu malee; Qaalluunisi galma malee hin ta'u.Halchaayye waan itti dabaltu yoo jiraate itti jedhi."

Abbaa gadaa Halchaayyee «waanti hedduun jedheemeera. Galmi gama tokkoon mallattoo eenyummaa Gujiitii. Gujiin Qaalluun bula.Qaalluun immoo galma isaatiin bula.Qaalluun abbootii gadaa wal, jaarsolee wal waa'ee biyyaa, waa'ee sabaa iddoo ittiin mari'atuudha.Iddoo murtii ittiin dabarfatuudha.Nami rakkate iddoo itti dheessuudha. Nami nama akka tasaa ajjeese maatii isaa wal iddoo dheessee baafatuudha.» (Obboo Mokkonnaan Naga'oo, umrii woggaa 75, Aanaa Wonagoo, Ganda Qootii, fi Abbaa gadaa Halchaayyee Dharraa, umrii woggaa 65, Aanaa Abbaayyaa, Ganda Dabaqqaa Daboobessa,Guyyaa, 16/12/2007 A.L.I.

## አባሪ-ሰባት

### Bokuu

Gaheen abbaa gadaa ardaafi looniif waaqa kadhata. Gama biraatiin yoo nami sababa adda addaatiin lolamee dhufe jaarsaaf akka dubbii ilaalan isaaniif dabarsa.Haalli lola isaa yoo afaan taree jiraate, ykn balleessa biraa yoo raawwate horiin ykn ganzabaan qaxxa'a. Saniin booda araarsee lakkisa. Yeroo himannaa san nami himatame sun yoo waakkate name himate, dhugaa qabu fidee raggaasifata.dhugaan sun himteetuun; ammale dide kan jedhu yoo ta'e gara galma qaalluutti dabarsan.

Ishi amma dhugaan kan abbaa gadaa, abbaa qaalluuti. Dhuguma akka dubbii ammaa dubartiin bada akkasi, bada akkana jedhanii hin arrabsanu. Yoo dubartii maqaa badaan yoo takaalane seera qabdi.Maal qabdi?Yoo abbaa gadaa ykn abbaa qaalluu bira yoo deemte Korma qalsiisan.

Adabbii abba qaalluun dabre sana yoo dide jedhe, ni bokama. Bokuu jechuun name kun olla isaatti yoo iyye reebuu akka hindeemnef, yoo du'e akka hin awwaallef, ibidda akka hinkennamneef...ergaan qaalluurran gara abbaa gadaatti; abbaan gadaa immoo, gama jaarsoleen ollaaf dabarsu. Yoosuu ollaan boka san hojiirra oolcha.Yeroo san name bokame sun ariitiidhaan galma qaalluu deemuun boka san hiikisiisee dhufa. Sanii booda, adabbiin kun akka ka'een haaluma akka yeroo bokaa; ergaan adabameera, sirro'e jira; bokni haa ka'uuf jedhamee gara gadiitti ergaan dabaree niraawwatama.

Inni guddaan qaalluufi gadaan kabaja qaban.Kanaafuu, namootiin himatamane ragaa akka dhiyeesan yeroo hintaasifamne jira.Maaliif yoo jedhame, namni dhufee isaan kaadu hin jiru. (FKN, dhihoo kanatti nami tokko lowwan hatee, gama seeratiin wal himanii fala dhabe, anattuu hateera jedhee amanee horii san deebisiisanii araarri bu'eera.

Balbalti kunuu dhugaadha, gadaanu dhugaadha, qaalluun dhugaadha.Nami isaan sobee hinba'u; ija isaanii dhaabbatee sobuu waan hindandeenyeef dhugaa kee fidi hin jedhanu.Qaalluun waaqa, gadaan waaqa, nami waaqa kaadu jiraa?Hin jiru, kanaafuu hin kaadanu.Garuu tasa yoo hammaate akka ragaa isaa fidatu taasifama. (Obboo Taddasaa Danboobaa, aanaa Abbaayyaa,Ganda Bunnaata, 23/4/2007 A.L.I.)

# አባሪ-ስምንት

## የተለያዩ መረጃዎችን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች




ሀዳ ቦላ ቃባሌ ጃልዴሳ (የቀድሞው የኡራጋ ገዳ ባለቤት) በመንፈሳዊ ጉዞ ወቅት የዋንዛን እንጨት ጨምሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ቁሶችን እንዴት እንደሚያዝ የሚያሳይ ፎቶ በሚኤ ቦኮ




ከመረጃ አቀባዮች ውስጥ የወ/ሮ ዲኮ እና  የአቶ ሞኮና ናጋኦ ፎቶ




በሚኤ ቦኮ አርዳ ጂላ ላይ የገዳ ስልጣን ለመረከብ በዝግጅት ላይ እያሉ



ስለፋጭና ጉጆማ ከበራ የተዘጋጀ አርቴፊሻል [illegible] በከፊል የሚያሳይ




ከጃልዳባዎች መረጃ በመሰብሰብ ላይ እያለሁ የሚያሳይ ፎቶ



ከላልቱ ቀበሌ የሚገኙ መረጃ አቀባዮቼ በከፊ የሚያሳይ ፎቶ




ከምስራቅ ሐረርጌ በሚኤ ቦኮ በዓሉ ላይ ለመታደም የመጡና መረጃ አቀባዮቼ የነበሩ



በሚኤ ቦኮ የአዋጅ ነገራው ላይ ሴቶች ታድመው ሲከታተሉ የሚያሳይ ፎቶ



የሰው ሁሉቃ መቼት የሚያሳይ ፎቶ፡-



አዲሶቹ አባገዳዎች የመሀሉ የኡራጋ አባገዳ ጂሎ ማንዶ፣ በስተግራ ያሉቱ የሆኩ አባገዳ ሲሆኑ በስተቀኝ ያሉት ደግሞ የማቲ አባገዳ ሚዳጋ ይባላሉ።



በሚኤ ቦኮ የበዓሉ እድምተኞች በከፊል የሚያሳይ ፎቶ



ከአማካሪዬ ዶ/ር ታደሰ በሪሶ ጋር በሚኤ ቦኮ አረዳ ጂላ ላይ የተነሳነው ፎቶ

ዚህ ሥራ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ በአግባቡ ጠቅሼ መጠቀሜን
የረጋገጥኩ ይህ ሥራም የራሴ ስለመሆኑ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡
ም፡- ዘላለም አበበ
ርማ፡- ____________________
ን፡- ____________________